ኩፋ.8፣20 ወኩሉ ሕሊና ወፈቃዱ ለሰብእ ይሄሊ ከንቶ ወእኩየ በኩሉ መዋእል። ኩፋ.9፣1 ወከፈልዋ ለምድር ሠለስተ መክፈልተ ለሴም ወለያፌት ወለካም በበርስቶሙ። ወባሕቱ ቆራር ይእቲ ምድረ ያፌት ወምድረ ካም መርቁ ይእቲ ወምድረ ሴምሰ ኢመርቁ ወኢደደክ። ኩፋ.10፣10 እስመ በመዋእሊሁ ለራግው ሐነጽዋ እንዘ ይብሉ ቦቱ ነዓርግ ውስተ ሰማይ ወአኀዙ ይሕንጹ። ፶፫ ወአርባዕቱ ምእት ወሠላስ በእመት ዓርገ ኑኁ ወክልኤቱ ስዝር። ወኢሰምዐ እንከ አሐዱ ቃለ ካልዑ ወአንተጉ እንከ ሐኒጸ ሀገር ወማህፈድ ወፈነወ እግዚአብሔር ነፋሰ ዓቢየ ውስተ ማኅፈዶሙ ወገፍትዐ ውስተ ምድር። ኩፋ.10፣18 ወኀደረ ካም ውስተ ምድር እንተ ኢኮነት እንቲአሁ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየት ይእቲ ምድረ ከነዓን ስለዚህ ነገር የሴም እጣ የከነዓን ሀገር ተባለች። ኩፋ.11፣13 ወአኀዝኩ እትናገር ምስሌሁ እብራይስጠ በልሳነ ፍጥረቱ ወነስአ መጻሕፍተ አበዊሁ ወጽሑፋት እማንቱ ዕብራይስጠ።

ኃጢዓት፣ ቅንዐት፣ መጣላት

ኩፋ.10፣23 ወወጠኑ ውሉደ ኖኅ ይትቃተሉ ለጼውዎ ወለሐኒጸ አህጉር ዕኑዓት ወለተልዕሎ ብእሲ ላእለ ሕዝብ ወለሠይመ መንግሥት መቅድመ። ወአኀዙ ይጼወው ሀገረ ለሀገር ወለተሣይጦ ለገብርና ወለአመትና። ኩፋ.18፣14 ወዐብየ ይሥሐቅ ፈድፋደ ወቀንዐ ላእሌሁ ፍልስጥኤም። ኩፋ.18፣18 ወተገለዙ ኖሎተ ጌራሮን ምስለ ኖሎተ ይስሐቅ እንዘ ይብሉ ዘዚአነ ዝንቱ ማይ ወተንሥአ ይስሐቅ እም ህየ ወከረዩ ዓዘቃተ ካልዐነ ወኢተበአሱ በእንቲአሁ።

ጸሎት፣ ሕልም

ኩፋ.10፣33 ወአኀዘ ይጸሊ አብራም ኀበ ፈጣሬ ኩሉ ከመ ያድኅኖ እምስህተተ ውሉደ ሰብእ። ኩፋ.11፣8 አድኅነኒ እም እደ መናፍስት እኩያን እለ ይሄለጡ ውስተ ሕሊና ልበ ሰብእ። ኩፋ.12፣1 ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም በሕልም እንዘ ይብል ኢትፍራህ አብራም አነ ውእቱ ቃውምከ ይቤሎ።

እግዚአብሔር፣ ረድኤተ እግዚአብሔር

ኩፋ.10፣43 አምልኩ አምላከ ሰማይ ዘያወርድ ዝናመ ወጠለ ዲበ ምድር ወይገብር ኩሎ ላእለ ምድር ወኩሎ ፈጠረ በቃሉ ወኩሉ ሕይወት እም ቅድመ ገጹ። ኩፋ.11፣7 ኩሉ ተአምረ ከዋክብት ወተአምሪሃ ለወርኀ ወለፀሐይ ኩሉ በእደ እግዚአብሔር ለምንት አነ እትኃሠሥ ለእመ ፈቀደ ያዝንም ነግሀ ወሠርከ ወእመ ፈቀደ ኢያውርድ ኩሉ ውስተ እዴሁ። (ይህም ማለት ለምሳሌ ጤፍን ስንፈጨው ይደቃል። አትክልት ዝናብ ሲዘንብ ይለመልማሉ። ስለዚህ የፍጥረታትን ግንኙነት እስከ ፈለግነው ድረስ የማወቅ አእምሮ ተሰጥቶናል ብዙዎች ይህንን ተጠቅመው ብዙ ግኝት ሰርተዋል። ከዚህ የወጣ ግኝት ወይም innovation የለም ማለት ነው)። ኩፋ.11፣9 በእደ ገብርከ ግበር ወኢይሑር በስሕተተ ልብየ አምላኪየ።

ሰማእተ ሐሰት

ኩፋ.11፣1 ተንስአ አብራም በሌሊት ወአውዳየ ቤተ ጣዖታት ወሰብእሰ አልቦ ዘአእመረ ወተንሥኡ ሌሊተ ወፈቀዱ ከመ ያድኅኑ አማልክቲሆሙ እማዕከለ እሳት ወሠረረ አራን ከመ ያድኅኖሙ ወውእየ በእሳት ወሞተ በቅድመ አቡሁ ታራ።

አሥራት፣ በዓል፣ መሥዋዕት፣ ብኩርና

ኩፋ.11፣35 ወእግዚአብሔር ሠርዐ ሥርዓተ ለዓለም ከመ የሀብሙ አሥራተ ለካህናት ለእለ ይትቀነዩ በቅድሜሁ ወአልቦ ለዝ ሕግ ወሰነ መዋዕል እስከ ትውልድ ዘለዓለም ሠርፆ። ኩፋ.14፣19 ወሰመያ በዓለ እግዚአብሔር። ኩፋ.15፣13 ወሕጽብ እደዊከ ወእገሪከ ዘእንበለ ትቅረብ ውስተ ምሥዋዕ ወሶበ ፈጸምከ አዕርጎ መሥዋዕት ግባዕ ወተሐጸብ እደዊከ ወእገሪከ ወኢያስተርኢ በዲቤክሙ ኩሉ ደም ወውስተ አልባሲክሙ። ኩፋ.18፣6 ወመነነ ኤሳው ቀዲመ ተወልዶ በእንተ ተብሲል ወሥርናይ ዘወሀቦ ያዕቆብ ወልህቀ ያዕቆብ ወኤሳውሰ ተትሕተ እም ዕበዩ። ኩፋ.34፣7 ወኢይክሉ ገቢረ ጳሲካ በአህጉሪሆሙ ወበኩሉ በሐውርት ዘእንበለ በቅድመ ደብተራ እግዚአብሔር።

ግዝረት

ኩፋ.12፣30 ወዘኢተገዝረ ሥጋ ቁልፈቱ በዕለት ሳምንት ትሴሮ ይእቲ ነፍስ እም ዘመዳ እስመ ኪዳንየ ነሠተ። ወገብረ አብርሃም በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር። ወነስአ እስማኤልሀ ወልዶ ወኩሎ ልደ ቤቱ ወዘሂ ተሣየጠ በወርቁ ኩሎ ሮሰ ዘውስተ ቤቱ ወገዘረ ሥጋ ክስበቶሙ።

ትእግስት፣ ቅንነት፣ ተዐቅቦ

ኩፋ.14፣22 ወሞተት ሣራ በኬብሮን ወሖረ አብርሃም ከመ ይብክያ ወይቅብራ።ወናሜክሮ እመ ይትዔገሥ መንፈሱ። ወተረክበ በዝኒ ዕጉሥ ወኢተሀውከ አልተበሳጨም እስመ በትእግስተ መንፈሱ ተናገረ ምስለ ደቂቀ ኬጢ ከመ የሀብዎ መካነ ከመ ይቅብር በድኖ ውስቴቱ። ወእግዚአብሔር ሞገሠ ወሀበ ሎቱ በቅድመ ኩሎሙ እለ ይሬእይዎ ወተረክበ ቡቱ ምዕመነ ወዕጉሠ። ወተጽሕፈ አርከ እግዚአብሔር ውስተ ጽላተ ሰማይ። ኩፋ.14፣31 ወያዕቆብሰ ፍጹም

ወራትዕ። ያዕቆብ ግን ፍጹም ቅን ነበር። ኩፋ.15፣18 ወኢትስሐት ስሕተተ እስከ ለሞት ቅድመ አምላክ ልዑል። ወተዐቀብ ዑቃቤ ዘአምላክ ልዑል። ወግበር ፈቃዳቲሁ ወይባርከከ በኩሉ ምግባሪከ ወያነስእ እምኔከ ተክለጽድቅ።

አባት፣ እናት፣ ቡራኬ

ኩፋ.14፣45 ወአዘዞሙ አብርሃም ለውሉዱ ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ እግዚአብሔር ወከመ ይግበሩ ጽድቀ። ወያፍቅር አሐዱ አሐዱ ቢጾ። ወአፍቅርዎ ለአምላከ ሰማይ ወተጸመዱ ኩሎ ትእዛዞ ወኢትሑሩ ድኅረ ጣዖቶሙ ወድኅረ ርኩሶሙ ወአማልክተ ስብኮ ኢትግበሩ ለክሙ። እስመ ከንቱ ውእቱ። እስመ ግብረ እደው እሙንቱ ኢታምልክዎሙ ወኢትስግዱ ሎሙ። አላ አንትሙሰ አምልኩ አምላከ ልዑለ። ኩፋ.16፣9 ወጸውዖ አብርሃም ለያዕቆብ ወይቤሎ ወልድየ ያዕቆብ ይባርከ አምላከ ኩሉ። ወየሀብከ እግዚአብሔር ዘርዓ ጽድቅ እም ውሉድከ ይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ወኩን ኃያለ። ወየሀብከ አምላክ ልዑል ኩሎን በረከታተ። ወያንጽሕከ እም ኩሉ ርስሐት ወርኩስ ከመ ታስተሥሪ እም ኩሉ አበሳ ዘበኢያእምሮ ጌገይከ ወየጎይልከ ወይባርከ። ወአንተኒ ወልድየ ያዕቆብ አምላክ ልዑል ይርዳዕከ። ኩፋ.19፣13 ብዛኅ ወለሀቅ ወተከዐው ውስተ ምድር ወይትሐሠይ ዘርዕከ። ወሰዐመቶ ለወልዳ ወትቤሎ ያፍቅር ብከ እግዚእ ለዓለም በከመ ልበ እምከ። ወጸውዐት ርብቃ ያዕቆብሃ ወልዳ ወትቤሎ ናሁ ሰማዕክዎ ለይስሐቅ አቡከ እንዘ ይትናገር ምስለ ኤሳው እኁከ። ወሰምዐ ያዕቆብ ቃለ ርብቃ እሙ። ወይቤሎ አቡሁ መጽአ እኁከ በሕብል ወነስአ በረከታቲከ ወአብልአኒ ወአስተየኒ ወነስአ በረከታቲከ። ኩፋ.19፣57 ወኮነ እም ድህረ ተንስአ ያዕቆብ ለሐዊር መስጴጦምያ ኀዘነ መንፈሳ ለርብቃ ድኅረ ሖረ ወልደ ወትበኪ። ወይቤላ ይስሐቅ ለርብቃ እኅትየ ኢትብክዩ በእንተ ያዕቆብ ወልድየ እስመ በሰላም የሐውር ወበሰላም ይትመየጥ ወይናዝዛ ይስሐቅ ለርብቃ በእንተ ያዕቆብ ወልዳ። ኩፋ.20፣59 ወይፈኑ ያዕቆብ ለአቡሁ ለይስሐቅ እም ኩሉ ጥሪቱ ልብሰ ወሲሲተ ሥጋ ወስቴ ወሐሊበ ወቅብዓ ወኀብስተ። ወይባርክዎ ይስሐቅ ወርብቃ ለያዕቆብ በኩሉ ልቦሙ። ኩፋ.22፣4 ወሖረ ያዕቆብ ኀበ አቡሁ ይስሐቅ ወኀበ እሙ ርብቃ ወወጽአት ርብቃ እማኅፈድ ውስተ አንቀጸ ማኅፈድ ከመ ትስዓሞ ለያዕቆብ ወትሕቅፎ ወሐቀፈቶሙ ወሰዐመቶሙ ለውሉዱ። ኩፋ.25፣47 ወከፈለ ይስሐቅ ኩሎ ዘቦ ጥሪቶ ለክልኤሆሙ ውሉዱ በይእቲ ዕለት።

ተዘክሮ እግዚአብሔር

ኩፋ.15፣2 ወበኩሉ መዋእለ ሕይወትየ ሀሎኩ እንዘ እዜክሮ ለእግዚአብሔር ወእንዘ አኀሥሥ በኩሉ ልብየ ከመ እግበር ፈቃዳቲሁ ለአምላኪየ ወበኩሉ ጊዜ ኩን ንጹሐ በሥጋከ።

ትዳር

ኩፋ.16፣9 ወተዐቀብ ወልድየ ያዕቆብ ከመ ኢትንሳእ ብእሲተ እም ኩሉ ዘርዐ አዋልደ ከነዓን ኢትፍራህ ወልድየ ያዕቆብ አምላክ ልዑል ይዕቀብከ እምነ ሙስና። ወእም ኩሉ ፍኖተ ስሕተት ውእቱ ይባልሕከ። ወሰከቡ ክልኤሆሙ ኀቡረ ውስተ አራት አሐቲ ወኖመ ያዕቆብ ውስተ ሕጽነ አብርሃም አበ አቡሁ ወባረኮ በኩሉ ልቡ።

ልቅሶ

ኩፋ.17፣3 ወወድቀ ይሥሐቅ ውስተ ገጸ አብርሃም ወበከየ ወቃል ተሰምዐ በቤተ አብርሃም ወተንስአ እስማኤል ወልዱ ወሖረ ኀበ አብርሃም አቡሁ ወበከዮ ለአብርሃም አቡሁ። ወውሉዱ ይስሐቅ ወእስማኤል በከዩ ፴ መዋዕለ ወኩሉ ሰብአ ቤቱ። ወተፈጸመ ላህ ብካየ አብርሃም የአብርሃም ልቅሶ ኀዘን ተፈጸመ። ወሠለስተ ኢዮቤልዮ ሐይወ ወአርባዕተ ሱባኤ ዓመት። ፫ተ ወ፷ ወኃምስተ ዓመተ ኮነ ወተፈጸመ መዋዕለ ሕይወቱ።

እስራኤል፣ ቅዱስ ቅንዐት

ኩፋ.21፣8 ወኢይትረከብ ዘማ ወርኩስ በውስተ እስራኤል ኩሎ መዋዕለ ትውልደ ምድር እስመ ቅዱስ እስራኤል ለእግዚአብሔር። ኩፋ.21፣18 ወቀተልዎሙ በጻእር ሌዊ እና ስምዖን እህታቸው ዲናን የደፈሯትን ገደሏቸው። ወኮነቶሙ ጽድቀ ወተኀርየ ዘርዐ ሌዊ ለክህነት እስመ ቀንዐ ከመ ይግበር ጽድቀ። ወኩነኔ ወበቀለ እም ኩሎሙ እለ ይትነስኡ ላእለ እስራኤል። ኩፋ.23፣52 እስመ ሕዝብ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር እስራኤል።

የአክብሮት ስግደት

ኩፋ.23፣58 ወሐዊሮሙ ውሉደ ያዕቆብ ሰገዱ ለይስሐቅ ወለርብቃ ወሶበ ርእይዎሙ ይስሐቅ ወርብቃ ለእሙንቱ ውሉድ ባረክዎሙ።

መወደድ

ኩፋ.28፣12 ወአፍቀርዎ ኩሎሙ መኳንንቲሁ ለፈርዖን እስመ በርትዕ የሐውር ወአልቦ ትዕቢት ወአዕብዮ ልብ ወነሢአ ገጽ እስመ በርትዕ ይኬንኖሙ። ወረትዐት መንግሥቱ ለፈርዖን በእንተ ዮሴፍ።

መጽሐፈ ሄኖክ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተክርስቲያን እንደመሆኗ ሁሉ በዓለም ከምትታወቅባቸው ዓበይት መገለጫዎች ውስጥ በዋቢነት የሚጠቀሱት በጥንታውያን ብሔራውያን ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ ተጠብቀው ከቆዩት የብሉያት አንድምታ ትርጓሜ በዓለም እስካሁን የሌለው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ብቻ ተጠብቆ የቆየው ሄኖክ ነው። ሄኖክ ማለት ተሐድሶ ማለት ነው። ይሁዳ.14-16 በከመ ተነበየ ሄኖክ ዘውእቱ ሳብእ እምአዳም ብሏል። ይኸውም አዳም፣ ሴት፣ ሄኒስ፣ ቃይናን፣ መላልኤል፣ ያሬድ እና ሄኖክ ነው።

አንድምታ

ሄኖ.42፣1 ካልዕ መጽሐፍ ዘጸሐፈ ሄኖክ ወልዱ ለማቱሳላ ወልዱ። ይህንን ወደ ገነት ሳይወጣ ጽፎታል ይላሉ። ወደ ገነትም ከወጣ በኋላ ጽፎታል ይላሉ። (አንድምታ የሚነገሩ ታሪኮችን

ሁሉ ስለሚያቀርብ እንዲህም ይላሉ እንዲህም ይላሉ እያለ ሲባል የነበረውን ያስቀምጣል። ይህ አይነቀፍም በዚያ ጉዳይ ከጥንት ጀምሮ የሚባሉ አስተያየቶችን ያስቀምጥና ማስረጃ ሲያጣ ሳይፈርድ ይሄዳል። ይህ ከሌሎች በተሻለ ምን ይባል እንደነበረ እንድናውቅ ያደርገናል መኖሩ አያስነቅፍም ያስደንቃል እንጂ)።

ቅዱሳን፣ ሄኖክ

ሄኖ.1፣6 ወይከውን ፍትሐ ላዕለ ኩሉ ወላዕለ ጻድቃን ኩሎሙ። ለጻድቃንሰ ሰላመ ይገብር ሎሙ። ወየዐቅቦሙ ለኀሩያን ወይከውኑ ኩሎሙ ዘአምላክ። ሄኖ.1፣24 ወለኀሩያንሰ ይከውን ብርሃን ወፍቅር ወፍሥሓ ወሰላም። ወእሙንቱሰ ይወርስዋ ለምድር። ምድር አላት ምድር አልፋ በምድር ተተክታ ትኖራለችና አንድም በምድር በሰሩት ስራ ትወረሳለችና አንድም ምድራውያን ጻድቃን ይወርሷታልና። ሄኖ.4፣1 ወእም ቅድመ ኩሉ ነገር ተከብተ ሄኖክ ወአልቦ እም ውሉደ ሰብእ ዘየአምር በኀበ ተከብተ ወኩሉ ግብሩ ምስለ ቅዱሳን። ወይመውኡ ጻድቃን በስሙ ለእግዚአ መናፍስት። ሄኖ.28፣5 ብውዓን ጻድቃን ኩሎሙ። ወብውዓን ኩሎሙ እለ የሐውሩ በፍኖተ ጽድቅ። ሄኖ.40፣22 እምሕል ለክሙ ጻድቃን እስመ በሰማይ ይዜክሩ መላእክት በእንቲአክሙ ለሰናይ በቅድመ ስብሐቲሁ ለዓቢይ ወአስማቲክሙ ይጸሐፍ በቅድመ ስብሐቲሁ ለዓቢይ። ወይእዜኒ ኢትፍርሁ ጻድቃን ሶበ ትሬእይዎሙ ለኃጥዓን ይጸንዑ ወይዴለው በፍትወቶሙ ወኢትኩኑ ሱቱፋነ ምስሌሆሙ አላ ረሐቁ እም ግፍዓ ዚአሆሙ። እስመ ለሐራ ሰማይ ሀለወክሙ ትኩኑ ሱቱፋነ።

ምጽአት፣ ትእግስት

ሄኖ.1፣9 ወናሁ መጽአ በትእልፊት ቅዱሳን ከመ ይግበር ፍትሐ ላዕሌሆሙ ወያኅጕሎሙ ለረሲዓን ወይትዋቀስ ኩሎ ዘሥጋ።በእንተ ኩሉ ዘገብሩ ወረሰዩ ላዕሌሁ ኃጥዓን ወረሲዓን። ሄኖ.42፣3 ወአንትሙሰ ጽንሑ እስከ ተሐልፍ ኃጢአት።

ሥነ ፍጥረት፣ ዘመናት

ሄኖ.1፣10 ሥሩዕ ኩሉ በበዘመኑ ወኢይትዐደው እም ትእዛዞሙ። ወለብው በእንተ ኩሉ ወአእምሩ በከመ ገብረ ለክሙ ወኩሉ ምግባሩ ይትቀነዩ ሎቱ ወኢይትመየጡ። አላ በከመ ሠርዐ አምላክ ከመዝ ይትገበር ኩሉ። ወርእዩ እፎ አብሕርት ወአፍላግ ኀቡረ ይፈጽሙ ኩሎ ግብሮሙ። ሄኖ.14፣33 ማይሰ ዘመልእልተ ሰማያት ተባእታይ ውእቱ ወማይሰ ዘመትሕተ ምድር አንስታይ ይእቲ። ሄኖ.21፣6 ወርኢኩ ስሱ ኀዋኅው እለ እም ኀበ ይወጽእ ፀሐይ ወስሱ ኀዋኅው እለ ኀበ የዐርብ ፀሐይ ወወርኅ። በሄኖክ አቆጣጠር አንድ ቀን 12 ክፍል ነው። ከምሥራቅ እስከ ምእራብ በአንድ ኖኅት 60 ኬክሮስ አለ። ከንትሮስ የሚባለው ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እንደዘሀ የተዘረጋው ነው። ኬክሮስ የሚባለው እንደ ማግ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው ነው። ፀሐይ በሠረገላ ሆኖ በርጉዕ ነፋስ ይሄዳል። ወብርሃነ ዚአሁ ሰብዓተ እደ ያበርህ እምዘወርኅ። የጨረቃና የፀሐይ ሰሌዳቸው እኩል ነው። ሄኖ.22፣1 ወክበቡ ከመ ክበበ ፀሐይ እንዲል።ወበመስፈርት ይትወሀብ ሎቱ ብርሃን። እስከ 15 ቀን እየተጨመረለት እስከ 14 ቀን

እየተነሳው 29 ቀን አብርቶ በ30ኛው ቀን ጠፍ አድሮ በ31ኛው ቀን ሠርቅ ያደርጋል።በሄኖክ አቆጣጠር ዓመቱ 364 ቀን ነው። ሄኖ.24፣6 ወለመዋዕል አርአየኒ ዑርኤል መልአክ ዘአንበሮ ለእግዚአ ስብሐት ዘለዓለም። ሄኖ.25፣1 ወበአጽናፈ ምድር ርኢኩ አሠርተ ወክልኤተ ኀዋኅዋ ርኅዋተ ለኩሎሙ ነፋሳት ወበአርባዕቱ እምኔሆሙ ይወጽኡ ነፋሳተ በረከት ወሰላም ወእም እልኩ ሰመንቱ ይወጽኡ ነፋሳተ መቅሰፍት። ወሶበ ይትፈነው ይደመስስዋ ለኩላ ምድር። ነፋሳት ለውሃ ሕይወት ናቸው። ለዕፅዋት ለፍጥረታት ሁሉ ሕይወት ናቸው። ሄኖ.26፣1 አስማቱ ለፀሐይ ከመዝ አሐዱ ኦርያሬስ ወካልዑ ቶማስስ ወለወርኅ አርባዕቱ አስማት ቦቱ አሐዱ ስሙ አሶንያ ወካልዑ እብላ ወሣልሱ ብናሴ ወራብዑ ኤራዕ። ሄኖ.27፣2 ወኩሉ ግብር ዘዲበ ምድር ይትመያየጥ በዚህ ዓለም ያለው ሥራ ሁሉ ይለዋወጣል። ሄኖ.28፣7 ወእለ ይሌልዩ ማዕከለ አርባዕቱ ክፍለ ዓመት። ወእሉ አስማቲሆሙ ለመራሕያኒሆሙ እለ ይፈልጡ አርባዕተ መክፈልተ ዓመት እለ ሥሩዓን ምልክኤል ወሕልመልሜሌክ ወሚልኤል ወናርኤል።

ደቂቀ ሴት

ሄኖ.2፣1 ወኮነ እምዘበዝኑ ውሉደ ሰብእ በእማንቱ መዋዕል ተወልዳ ሎሙ አዋልድ ሰናያት ወላህያት ወርእዩ ኪያሆን መላእክት ውሉደ ሰማያት። ወፈተውዎን ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ንዑ ንኅረይ ለነ አንስተ እም ውሉደ ሰብእ ወንለድ ለነ ወልደ ወይቤሎሙ ስማዝያ ዘውእቱ መልአኮሙ እፈርህ አንሰ ዮጊ ኢትፈቅዱ ይትገበር ዝንቱ ግብር። ወአውስእዎ ሎቱ ኩሎሙ ወይቤሉ መሐላ ንምሐል ኩልነ። ወንትዋገዝ በበይናቲነ ከመ ኢንሚጣ ለዛቲ ምክር። ወንግበራ ለዛቲ ምክር። ወነስኡ ሎሙ አንስትያ ወወጠኑ ይባኡ ኀቤሆን ወተደመሩ ምስሌሆን ወመሀርዎን ሥራያተ ስር መማስን ቅጠል መበጠስን ወስብዓታተ ጋኔን መሳብን ወመቲረ ስርው ወዕፀው አመርዎን። ወእማንቱሰ ጸንሳ ወወለዳ ረዓያተ ዐበይተ ወቆሞሙ በበ፴፪ በእመት። እሉ በልዑ ኩሎ ጻማ ሰብእ።ወተመይጡ ረዓይት ይብልዕዎሙ ለሰብእ።ወሥጋሆሙ በበይናቲሆሙ ተባልዑ። ወአዛዝኤል መሀሮሙ ለሰብእ ገቢረ አስይፍት ወመጥባሕት ወወልታ ወድርዓ እንግድዓ ወአውቃፋተ ወሠርገሙ ወተሰሀሎተ ወአሰንዮ ቀራንብት ወዕብነ እምኩሉ ዕብን ክቡር ወኅሩይ። ወአሚዛራክ መሀረ ኩሎ መሳብዕያነ ወመታርያነ ስርዋት። ወበራቅኤል ራእያነ ከዋክብት ወኮከብኤል ትእምርታተ ወአስራድኤል መሀረ ሩጸተ ወርኅ። ወበኅጉለተ ሰብእ ጸርሑ ሰብእ ወበጽሐ ቃሎሙ ሰማየ። ሄኖ.19፣19 ወሣልስ ስሙ ጋርድኤል ዝ ውእቱ ዘአርአየ ዝብጠታተ ሞት ለውሉደ ሰብእ። ሰው ሰውን መትቶ ለሞት የሚያበቃውን አመታት ያስተማረ ነው። ወውእቱ አስሐታ ለሔዋን ወውእቱ አርአየ ንዋየ ሞት ለደቂቀ ሰብእ። ወልታ ወድርዓ ወሰይፈ ለቀትል። ወራብዕ ስሙ ፔንሙዕ ወውእቱ አለበዎሙ ለሰብእ መጽሐፈ በማየ ሕመት ወክርታስ ወነምስ ስሙ ካዕድያዕ ዝንቱ ውእቱ ዘአርዓየ ለውሉደ ሰብእ ኩሎ ዝብጠታተ እኩየ ዘነፍሳት ወዘአጋንንት። ጽንስ ማስወረድን ያሳየ እባብ ሰውን ነድፎ እንዲገድለው ያሳየ ነው።

እግዚአብሔር፣ አስማተ እግዚአብሔር

ሄኖ.2፣33 ወአንተ ትሬኢ ኩሎ ወአልቦ ዘይትከሀል ይትነባዕ እምኔከ። ወአንተ ተአምር ኩሎ ዘእንበለ ይኩን ወአንተ ተአምር ዘንተ። ሄኖ.9፣37 ውእቱ የአምር ዘእንበለ ይትፈጠር ዓለም ምንት ውእቱ ዓለም ወለትውልደ ትውልድ ዘይከውን። ሄኖ.20፣2 ይቤሎ እግዚእ ለቅዱስ

ሚካኤል ያርእዮ ስሞ ኀቡዐ ከመ ይርዐይዎ ለውእቱ ስም ኀቡዕ ወከመ ይዝክርዎ በመሐላ ከመ ይርዓዱ እም ውእቱ ስም አጋንንት። እስመ ኃያል ውእቱ ወጽኑዕ። ሄኖ.20፣38 ወምስሌሆሙ ርእሰ መዋዕል ወርእሱ ከመ ጸምር ጸዐዳ ወንጹሕ ልብሱ ዘኢይተረኅም። ሄኖ.29፣19 ንጉሠ ነገሥት ወአምላከ ኩሉ ዓለም። ወመለኮትከ ወመንግሥትከ ወዕበይከ ይነብር ለዓለም ወለኩሉ ትውልደ ትውልድ ሥልጣንከ። እስመ አንተ ገበርከ ኩሎ ወኩሎ አንተ ትመልክ ወአንተ ኩሎ ተአምር ወትሬኢ ወትሰምዕ። ወአልቦ ዘይትነሳዕ እምኔከ እስመ ኩሎ ትሬኢ።

መላእክት

ሄኖ.6፣1 ወዘንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለእለ ይተግሁ ቅዱሳን መላእክት ዑራኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን በመብረቅ በነጎድጓድ የተሾመ ነው። ሩፋኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን በሰው ነፍሳት ወይም በሰው ቁስል የተሾመ ነው። ራጉኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን። ሚካኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን። ሠረቃኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን አእምሮ ባጡ ሰዎች ላይ የተሾመ ነው። ገብርኤል አሐዱ እመላእክት ቅዱሳን በምንጭ ላይ የተሾመ ነው። ሄኖ.10፣15 ወራብዕ ዘዲበ ንሥሓ ለተስፋ እለ ይወርሱ ሕይወተ ዘለዓለም ውእቱ ፋኑኤል። ንሥሓ በሚገቡ ሰዎች የተሾመ ፋኑኤል ነው። ሄኖ.20፣38 ወየዓውድዎ ለውእቱ ቤት በአውዱ ኪሩቤል ወሱራፌል ወአፍኒን እሉ እሙንቱ እለ ኢይነውሙ። ወየዐቅቡ መንበረ ስብሀቲሁ።

ምስጋና፣ ቅንነት

ሄኖ.27፣2 ወእምዝ ሶቤሃ ባረክዎ ለእግዚእ ዓቢይ ወንጉሠ ስብሐት ዘለዓለም በከመ ገብረ ኩሎ ግብረ ዓለም። ወሰባሕክዎ ለእግዚእ በእንተ ትእግስቱ ኃጥዓንን ስለታገሠ ጌታን አመሰገንኩት። ሄኖ.34፣40 ፍቁራንየ አፍቅርዎ ለርትዕ ወባቲ ሑሩ ወኢትቅረቡ ኀበ ርትዕ በክልኤ ልብ። አላ ሑሩ በጽድቅ ደቂቅየ። ወይእቲ ትመርሐክሙ በፍንዋት ኄራት። ሄኖ.37፣23 አሌ ለክሙ አብዳን እስመ ትትነሳሉ በእበድክሙ።

ሞት፣ ኃጢአት፣ ስንፍና

ሄኖ.27፣14 ወይእተ ጊዜ እቤ ብፁዕ ብእሲ ዘይመውት እንዘ ጻድቅ ወኄር። ወኩሉ መጽሐፈ ዓመፃ ዘኢተጽሕፈ ዲቤሁ ወኢተረክበ ጌጋይ በላእሌሁ በዕለተ ኩነኔ። ሄኖ.37፣18 ከመዝ ኃጢአትኒ ኢተፈነወት ዲበ ምድር አላ ሰብእ እም ርእሶሙ ፈጠርዋ ወምክነት ለብእሲት ኢተውህባ አላ በግብረ እደሃ ትመውት ዘእንበለ ውሉድ። ሄኖ.40፣22 ኃጥዓን ይጸሐፉ ሀለው ኩሎ ኃጢአተክሙ በኩሉ ዕለት።

መጻሕፍት

ሄኖ.28፣2 ወዕቀብ ወልድየ ማቱሳላ መጻሕፍተ እደሁ ለአቡክ። ወከመ ተሀብ ለትውልደ ዓለም። ሄኖ.35፣21 ወአንዘ እንከ ይትናገር ኄኖክ እመጻሕፍት። ሄኖክ ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ያስተምር ነበር። ሄኖ.37፣31 አሌ ለክሙ እለ ትጽሕፉ ነገረ ሐሰት ወነገረ ረሲዓን። ሄኖ.40፣36 እስመ ለጻድቃን ወለጠቢባን ይትወሀባ መጻሕፍት ለፍሥሓ ወለርትዕ ወለጥበብ ብዙኅ።ወሎሙ

ይትወሀባ መጻሕፍት ወእሙንቱ የአምኑ ቦሙ ወይትፈሥሑ ወቦሙ ይትሐሠዩ ኩሎሙ ጻድቃን እለ እምኔሆሙ አእመሩ ኩሎ ፍንዋተ ርትዕ። ሄኖ.42፣10 ወኩሎ በረከቶሙ ነገርኩ በመጻሕፍት።

ጦቢት፣ ዮዲት፣ አስቴር፣ ኢዮብ

ጦቢት አሥሩ ነገድ በ720 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በተማረኩ ጊዜ የተማረከ ጻድቅ ሰው ነው። በመጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ታሪክም በስደት ሀገር የተፈጸመ ነው። አስቴር ከ486 እስከ 465 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በፋርስ ሀገር የተፈጸመውን የአይሁድ ታሪክ የያዘ ነው።ኢዮብ የአብርሃም አምስተኛ ትውልድ ነው።

መጽሐፈ ጦቢት

ጦቢት ነገዱ ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው።

ቅዱሳን፣ ምጽዋት፣ እንበለ

ጦቢ.1፣3 አነ ጦቢት በፍኖተ ጽድቅ ሖርኩ ወበርትዕ ሐየውኩ በኩሉ መዋእለ ሕይወትየ ወምጽዋትየኒ ብዙኃ ገበርኩ ለአኃውየ። ጦቢ.1፣20 ወአልቦ ዘአትረፉ ሊተ ዘእንበለ ሐና ብእሲትየ። ጦቢ.2፣1 ወሶበ አተውኩ ቤትየ አግብዑ ሊተ ሐናሃ ብእሲትየ። ጦቢ.4፣10 እስመ ምጽዋት ታድኅን እሞት በእለተ ምንዳቤ። ጦቢ.4፣14 ወእምነ እክልከ ሀብ ለርኁብ ወእምነ አልባሲከ ሀብ ለዕሩቅ ወእም ኩሉ ዘይተርፈከ ግበር ምጽዋተ። ጦቢ.12፣9 እስመ ምጽዋት ታድኅን እሞት ወታነጽሕ እም ኩሉ ኃጢአት ወእለሰ ይገብሩ ጽድቀ ወምጽዋተ ይመልዑ ላእሌሆሙ ሕይወተ።

መጽሐፍ፣ መልአክ

ጦቢ.2፣6 ወተዘከርኩ ዘይቤ አሞጽ። ጦቢ.3፣16 ወተሰምዐ ጸሎቶሙ ለክልኤሆሙ በቅድመ ስብሐተ ዕበዩ ለእግዚአብሔር ወፈነዎ ለፋኑኤል ከመ ይፈውሶሙ ለክልኤሆሙ። ወለጦቢትኒ ከመ ያስስል ጢሰ ዓይኑ ወለሣራሂ ወለተ ራጉኤል ከመ የሀባ ለጦብያ ወልደ ጦቢት ትኩኖ ብእሲቶ። ወከመ ይስአሮ ለአስማንድዮስ ጋኔን እኩይ (አስተውል በሽታ ሁሉ ከሰይጣን የተነሳ ይሆናል። መድኃኒቱ ግን እጽ ሊሆን ይችላል የዓሣ ጉበት ሊሆን ይችላል ብቻ ከፍጥረታት በአንዱ ነው። ስለዚህ በእጽዋት እና በሌሎችም ፍጥረታት የሚለዉ አጋንንት አሉ ማለት ነው)። ጦቢ.12፣12 ወይእዜኒ አመ ጸለይክሙ አንተ ወሣራ መርዓትከ አነ አባዕኩ ተዝካረ ስእለትክሙ ቅድሜሁ ለቅዱሰ ቅዱሳን። አነ ውእቱ ሩፋኤል መልአክ አሐዱ እምነ ሰብዓቱ ሊቃነ መላእክት ቅዱሳን እለ የዐርጉ ጸሎቶሙ ለቅዱሳን።

ትዕቢት፣ መገዛት

ጦቢ.4፣13 እስመ ኀበ ሀለወት ትእቢት ህየ ሀሎ ኃሣር ወብዙኅ ሐኬት ወኀበ ሀለወ ሐኬት ህየ ሀሎ ተጽናስ ወንደሉት። ጦቢ.4፣14 ወእም ከመ ተቀነይከ ለእግዚአብሔር ይፈደፍድ አስብከ ወዘትጸልዕ ለርእስከ ኢትግበር ለመኑሂ።

መጽሐፈ ዮዲት

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ ማሸነፍ

ዮዲ.6፣21 ወጸውዕዎ ለአምላከ እስራኤል ኩላ ይእተ ሌሊተ ከመ ይርድኦሙ። ዮዲ.15፣12 ዮዲት ሆሎፎርኒስን አሸንፋ ስትመለስ ወሮጻ ኩሎን አንስተ እስራኤል ይርአያሃ ወይባርካሃ ወገብራ ላቲ ዓቢየ በዓለ ወነስአት ጸበርተ ውስተ እዴሃ በእጇ ዘንባባውን ያዘች መዋዒት ነኝ ስትል። ወወሀበት ለአንስት እለ ምስሌሃ።

ጸም፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር

ዮዲ.8፣6 ወነበረት ዮዲት መበለተ ወቀነተት ሠቀ ውስተ ሐቄሃ ወትጸውም ወትረ ኩሎ መዋዕለ ወሰናይት ይእቲ ራዕያ ወላህይ ገጻ ጥቀ ፈድፋደ። ወትፈርሆ ለእግዚአብሔር ፈድፋደ። ዮዲ.12፣9 ወሠርከ ሠርክ ትበልዕ። ዮዲ.16፣19 ዘሰ ይፈርሆ ለእግዚአብሔር ዓቢይ ውእቱ በኩሉ ጊዜ።

መጽሐፈ አስቴር

ረድኤተ አበው፣ እግዚአብሔር

አስቴ.5፣14 ጹሙ ሊተ ኢትብልዑ ወኢትስተዩ እስከ ሠሉስ ዕለት መዓልተ ወሌሊተ አነኒ ወአዋልድየ ንጸውም። አስቴ.5፣20 ወአንተ ተአምር ኩሎ እግዚኦ።

የክፉት ውጤት

አስቴ.8፣10 ወሰቀልዎ ለሐማ ዲበ ውእቱ ዕፅ ዘአስተዳለወ ለመርዶክዮስ።

መጽሐፈ ኢዮብ

ቅዱሳን፣ መላእክት

ኢዮ.1፣1 ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በብሔረ አውስጢድ ዘስሙ ኢዮብ ወውእቱ ብእሲ ራትዕ ወንጹሕ ወጻድቅ ወፈራሄ እግዚአብሔር ወይትገኀሥ ምስለ ልቡ እም ኩሉ ምግባር እኩይ። ኢዮ.38፣8 አመ ተፈጥሩ ከዋክብት ሰብሑኒ ኩሎሙ መላእክትየ በዓቢይ ቃል።

አባትነት

ኢዮ.1፣6 ወያበውእ ኢዮብ መሥዋእተ በእንተ ደቂቁ በጕልቆሙ ወአሐደ ላሕመ በእንተ ነፍሱ ወይብል ኢዮብ ለእመቦ ዘይሄልዩ ደቂቅየ እኩየ ላእለ እግዚአብሔር ወከመዝ ይገብር ኢዮብ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ።

ትእግስት፣ ተግሣጽ

ኢዮ.1፣23 ወይቤ ኢዮብ ዕራቅየ ወጻእኩ እም ከርሰ እምየ ወዕራቅየ እገብእ ውስተ ምድር። እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብሔር ነስአ። ወኮነ ከመ እግዚአብሔር ፈቀደ። ወባሕቱ ይኩን ቡሩከ ስሙ ለእግዚአብሔር። ወበዝ ኩሉ ዘረከቦ አልቦ ዘአበሰ ኢዮብ ቅድመ እግዚአብሔር ወኢወሀበ ዕበደ ለእግዚአብሔር ወይቤላ ለብእሲቱ ሶበ ትቤሎ ባርኮ ለእግዚአብሔር ወሙት። ኢዮ.2፣12 ሠናይቶሰ ነሣዕነ እም ኀበ እግዚአብሔር ወእኪቶሰ ሶበ በጽሐተነ ኢንትኤገሥኑ። ወበኵሉ ዝ ዘረከቦ አልቦ ዘአበሰ ኢዮብ ቅድመ እግዚአብሔር። ኢዮ.5፣16 ብፁዕ ብእሲ ዘእግዚአብሔር ገሠጾ።

ሞት፣ ማስረዳት፣ ዘለፋ

ኢዮ.3፣20 ዕረፍቱ ለሰብእ ሞት። ኢዮ.6፣21 ወእመቦ ዘስሕትኩ አጠይቁኒ የበደልሁት ያለ እንደሆነ አስረዱኝ። ኢዮ.7፣1 ቀዳሚሁ አኮኑ ጽላሎት ውእቱ ሕይወቱ ለሰብእ ዲበ ምድር። ተዘከር ከመ ነፍስ ይእቲ ሕይወትየ። ኢዮ.8፣9 ሣሬረት ንሕነ ወኢነአምር። መዋቲ ዘይትወለድ እም አንስት ከመ አድግ ይመስለኒ። ኢዮ.13፣21 ዘለፋክሙኒ ኃላፊ ከመ ሐመድ ወሥጋክሙኒ መሬት። ኢዮ.14፣9 ሰብእሰ እም ከመ ሞተ ይጸይዕ ወእም ከመ ሞተ መዋቲ ኢይሄሉ እንከ ሰብእሰ እምከመ ኖመ ኢይነቅሕ እስከ አመ የሐልፍ ሰማይ። ኢዮ.31፣3 አሌ ሎ ለሞተ ዓማጺ።

አንድምታ፣ መቀባጠር

ኢዮ.9፣8 ዘይብላ ለወርኅ ኢትሥርቂ ጨረቃን በጠፍ ጊዜ እንዳታበራ የሚያደርጋት አንድም የሚያሳልፋት እርሱ ነው። ኢዮ.11፣2 በብዝኀ ነቢብኑ ዘትጸድቅ ይመስለከ። ኢታብዝኅ ነቢበ እስመ አልቦ ዘይትዋቀሰከ። ሰብእሰ ኀሣሤ ንባብ ውእቱ። ኢዮ.16፣3 ወኩልክሙ ኩሎ ዘመጽአክሙ ትነብቡ ዘእንበለ አቅም። ኢዮ.28፣1 ቦ ብሔር እም ኀበ ይወጽእ ብሩር። ብር የሚገኝበት ሀገር አለ እንደ ሸዋ አንድም ምእመናን የሚበዙበት ሀገር አለ እንደ እስክንድርያ። ሐጺንሂ እም ውስተ ምድር ይትገበር ለወርቅኒ ቦ ብሔር እምኀበ የዐርርዎ ለብርትኒ ከመ ዕብን ይፈጽሕዎ ለጽልመትኒ አዘዘ እድሜሁ ለምድርኒ ይወጽእ እምኔሃ እክል እህል የሚሆንበት ሀገር አለ ደንቢያ በረንታ ነው። ኢዮ.39፣4 ይህ ዋሊያ ምጥ ይጸናበታል እኩሌታ አካሉ ወጥቶ ሳር እየበላ መንፈቅ ይቀመጣል የመብረቅ የነጎድጓድ ድምጽ በሰማ ጊዜ ፈትለክ ብሎ ወጥቶ ይሄዳል። ወአልባቲ ፍርሀት ለሰገኖ እስመ ወሀባ እግዚአብሔር ጥበበ ወከፈላ ምክረ።

እግዚአብሔር

ኢዮ.12፣9 መኑ የአምር ዘንተ ኩሎ ከመ እደ እግዚአብሔር ገብረ። ዕዝን ነገረ ይፈልጥ

ወጉርኤ እክለ ይጥዕም ወባሕቱ ኩሉ እም ኀበ እግዚአብሔር። እስመ እም ኀቤሁ ኃይል ወጽንዕ ወእንቲአሁ ጥበብ ወምክር። ኢዮ.34፣27 ወያነግሥ ብእሴ መደልወ በእንተ እከየ ሕዝቡ ወያነግሥ ብእሴ ራትዐ በእንተ ሠናየ ሕዝቡ።

ኃጥዓን

ኢዮ.15፣16 መዋዕሊሁኒ ወዓመታቲሁኒ ለኃጥዕ በጕልቍ ይትወሀቦ። ለኃያል ትግርምቱ ያወድቆ ወኢየአምር ለሊሁ ከመ ድቀት ትጸንሖ ዕለተ መቅሰፍት ወጽልመት ማኅተቶሙ ለኃጥዓን ሞት። ይጸንሱ ጻእረ በከርሶሙ ወትመልዕ ከርሶሙ ጕሕሉተ። ኢዮ.19፣29 እስመ መቅሠፍት ትመጽኦሙ ለኃጥዓን አሜሃ የአምሩ ኩሎ እከዮሙ እም አይቴ ዘበጽሖሙ። ኢዮ.20፣5 ፍሥሓሆሙ ለረሲዓን ቀትል ዓቢይ ወሐሴቶሙ ለኃጥዓን ኀጕል።

መጽሐፈ ነገሥት

መጽሐፈ ነገሥት የሚባሉት አንደኛውና ሁለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል ሦስተኛውና አራተኛው መጽሐፈ ነገሥት ናቸው። በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ቁጥራቸው ሁለት ነው። አራት አድረገው የተገረጎሟቸው ሰባው መተርጉማን ሊቃውንት ናቸው። መጻሕፍተ ነገሥት የሚለውም የሰባው ሊቃናት ስያሜ እንደሆነ ተረጋግጧል። አርባዕቱ ብሔረ ነገሥት አንቀጸ ነገሥት የሚል ስያሜም አለው። አንደኛና ሁለተኛ መጻሕፍተ ነገሥት በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን በነቢዩ ሳሙኤል ስም ተሰይሟል። ምክንያቱም አንደኛ በእነዚህ ውስጥ ዋና የታሪክ ባለቤቶች የሆኑትን ሳኦልንና ዳዊትን ቀብቶ ያነገሠ ሳሙኤል በመሆኑ ነው። ሁለተኛ አንደኛ ሳሙኤል 31፣13 ለመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ወጠኖ ሳሙኤል ወፈጸምዎ ናታን ወጋድ ይላል። አንደኛ ሳሙኤል ከምእራፍ አንድ እስከ 25 ያለውን ታሪክ የጻፈ እርሱ ስለሆነ ነው። ነቢዩ ሳሙኤል የዘመነ መሳፍንት ፈጻሚ የዘመነ ነገሥት ጀማሪ የነቢያትን ትምህርት ቤት ያቋቋመና የእስራኤልን መንግሥት ያጸና ነው። አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፈ ነገሥት ከሊቀ ካህናት ኤሊ ዘመነ ምስፍና እስከ ንጉሥ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (1171-1056) ያለውን ታሪክ አካተው ይዘዋል። ሦስተኛና አራተኛ መጻሕፍተ ነገሥት ደግሞ ከ (1015-586) ቅድመ ልደተ ክርስቶስና መንግሥተ ሰሎሞንን (1055-1015) ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ያለውን አካቶ የያዘ ነው። የሦስተኛውና የአራተኛው መጻሕፍተ ነገሥት ጸሐፊ ኤርምያስ እንደሆነ የቤተ እስራኤል ትውፊት ያስረዳል (መጽሐፈ ተልሙድ.14)። የቤተ ክርስቲያን ትውፊትም ያስረዳል። ለኦሪት ለነገሥት ለግብረ ሐዋርያት ታሪክ የላቸውም እነርሱ ለሌላው ታሪክ ይሆናሉ እንጂ።

መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ

አንድምታ

ምክንያት፡- ሁለተኛ ሦስተኛ አራተኛ ይጽፋልና ቀዳማዊ አለ። አንድም ዘንጉሥ ቀዳማዊ ይላል። የቀደመ ንጉሥ የሳኦልን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው። ሳኦል ከዳዊት ከሰሎሞን

ይቀድማል እና ቀዳማዊ አለ። አንድም ዘነገሥት ቀዳማውያን ይላል። የቀደሙ ነገሥታት የለሳኦልን የለዳዊትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው። መጽሐፈ ነገሥትን በአራት ብሔር ከፍሎ ጽፎታል ስለምን ቢሉ በአራቱ ማዕዝን ያለ አንድም ከአራቱ ባሕርይ የተፈጠረ ሰው እንዲጠበቅበት እንዲያመሰግንበት እርሱ ባወቀ ገንዘብ። አንድም በአራቱ መዓዝነ ዓለም ምሉዕ የሆነ ጌታ እንዲመሰገንበት እርሱ ባወቀ ገንዘብ። ይህም መጽሐፈ ነገሥት ምግባር ትሩፋት ሃይማኖት የለበት ስለምን ተጻፈ ቢሉ። ፍትሐ እግዚአብሔር ስለተገለጸበት ነው። አንድም እኩያን ነገሥታት አሉ አብነት አታድርጉ ለማለት ሠናያን ነገሥታት አሉ አብነት አድርጉ ለማለት። አንድም ሦስተኛው ብሔር የቤተ መቅደስን ስራ ይናገራል። ቤተ መቅደስ የመንግሥተ ሰማያት ሕዝቡ የመላእክት ንጉሡ የሰማያዊ ንጉሥ የጌታችን አምሳል ነውና። ኤሊ ግን ዙፋኑን ከደብተራ ኦሪት ደጃፍ አዘርግቶ ተቀምጦ ነበር። ስለምን ቢሉ ኦሪት ኢይባዕ ሞዓባዊ ወአሞናዊ ትላለችና አህዛብን ለመጠበቅ አንድም መባዓ ለመቀበል። 1ኛ ሳሙ.3፣4 ወይቤሎ ሳሙኤል ሳሙኤል ስለምን ደጋግሞ ጠራው ቢሉ በሀገራቸው ደጊመ ቃል ልማድ ነውና። አብርሃም አብርሃም አልአዛር አልአዛር ማርታ ማርታ እንዲል። አንድም የሰይጣን የሆነ እንደሆነ አንድ ጊዜ ብቻ ተናግሮ ይተዋል።የእግዚአብሔር እንደሆነ ለማጠየቅ ደጋገመው።

ጥቅስ፡- ይህም ለከንቱ አልተጻፈም እኛ ልንመከርበት እና ልንገሰጽበት ተጽፎልናል። ወኩሉ ዘተጽሕፈ ለተግሳጸ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትእግስትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ እንዲል። ሮሜ 15፣4። 1ኛ ሳሙ.1፣1 ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘእም አርማቴም ዘመሴፋ የመሴፋ እጻ ከምትሆን ከአርማቴም የተወለደ አንድ ሰው ነበር። ስለምን በዋቄ ጀመረ ቢሉ ብዙ መጻሕፍት ይቀድሙታልና ሄኖክ ኢዮብ ኦሪት ለዚያ ዋቄ ሊሆን በዋቄ ጀመረ። አንዱስ መጽሐፍ ለአንዱ ዋቄ አይሆነውም ብሎ መጽሐፍ ምስጢር ይጠነቅቃል እንጂ አንድና ብዙ ሩቅና ቅርብ ሴትና ወንድ አይጠነቅቅምና በዋቄ ጀመረው። አንድም መጽሐፍ በዋቄም ያለዋቄም ይጀምራል። ያለ ዋቄ ሲጀምር ሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ብሏል። በዋቄ ሲጀምር ኢዮብ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በሀገረ አውስጢድ ዘስሙ ኢዮብ ብሏል።

ቁንቋ፡- አንድም ቀዳሚሆሙ ለአህዛብ አማሌቅ እንዲል የታላላቆችን የደጋጎችን ነገሥታት ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው። አንድም የለ ዳዊትም የለ ሰሎሞንን የለሕዝቅያስን የለ ኢዮስያስን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው። 1ኛ ሳሙ.9፣1 ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምደቂቀ ብንያም ወስሙ ቂስ ብእሲ ኃያል። ኃያል የጉልበት አንድም የእውቀት ወጽኑዕ የነገር።

ታሪክ፡- ይህስ ጥንተ ነገሩ እንደምን ነው ቢሉ ጌታ ይህንን ዓለም ፈጥሮ እንዲያው አልተወውም ያለ ምግብ ያለመጋቢ አልተወውም ብትልም ይሆናል። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ሄኖክ በሕገ ልቡና ሲመገቡ ኖሩ መጽሐፈ ሄኖክ ተጻፈላቸው በሄኖክ ሲመገቡ ኖሩ። ቀጥሎ መጽሐፈ ኢዮብ ተጻፈላቸው በኢዮብ ሲመገቡ ኖሩ ቀጥሎ ኦሪት ተጻፈችላቸው በኦሪት ሲመገቡ ኖሩ። ቀጥሎ ነገሥት ተጻፈላቸው በነገሥት ሲመገቡ ኖሩ። ሐና ልጅ ስላልነበራት ታዝን ነበረ። ዕጹተ ማኅጸን እያሉ ይሰድቧት ነበረ።

ገለጻ ወይም ምርምር፡- ይህም መጽሐፈ ነገሥት እገሌ ተወለደ እገሌ ሞተ እገሌ ነገሠ እገሌ ተሻረ ነው የሚል። ሕልቃና ማለት ጥሪት ተጋብዖ ማለት ነው። ሐና ማለት ርስይ ክብራ

ማለት ነው። አንድም ትፍስሕት ማለት ነው። ሰቢረ ክሳድ ትእምርተ ኀዘን ነው። ሳሙኤል ማለት ሰምአኒ ማለት ነው። ወጸለየት ሐና ጸንዐ ልብየ በእግዚአብሔር። በዚህ ሦስት ነገር አለበት ሃይማኖት፣ ትሕትና፣ ትንቢት። ሃይማኖት እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር ያለው ነው። ትሕትና ወኢይጸእ ዓቢይ ነገር እም አፉክሙ ያለው ነው። ትንቢት እግዚአብሔር አስተዳለወ መንበሮ ያለው ነው። እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር ብሎ አብን ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ ያለችው ወልድ ነው። ወአልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚኦ ያለችው መንፈስ ቅዱስ ነው። አድከመ ቀስተ ኃያላን የነፍናናን ስልጣን አጠፋ ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን ለነ ሐና ኃይል እንደ ዝናር አስታጠቃቸው። እስመ መካን ወለደት ሰብዓተ መካን ሐና ፍጹም ልጅ ሳሙኤልን አስገኝታለችና። እስመ ጉልቆ ሳብእ ፍጹም ውእቱ በነበ ዕብራውያን እንዲል። አንድም ወወለደት ዓዲ ሠለስተ ደቂቀ ወክልኤ አዋልደ ይላል። እርሱን ከወለደች በኋላ ሦስት ወንዶች እና ሁለት ሴቶች ወልዳለችና ሳሙኤልን ስለ ሁለት ቆጥሮ የሙሴን ምስፍና የአሮንን ክህነት አንድ አድርጎ ይሏልና። ወእንተሰ ብዙኅ ባቲ ስእነት ወሊደ። ወላድ ፍናና ግን መውለድ ተሳናት ማኅጸኗ በቅናት ተዘግቷል አንድም እንደ ሳሙኤል ያለ ፍጹም ልጅ ስላላስገኘች። አንድም እግዚአብሔር ያስተዳሉ መንበሮ ብለህ መልስ አስተዳለወ ሲል ነው። በግብጻውያን ሊፈርድባቸው ለእስራኤል ሊፈርድላቸው መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ። ወአድከመ ቀስተ ኃያላን የግብጻውያንን ስልጣን አጠፋ ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን። ለእስራኤል ኃይልን እንደዝናር አስታጠቃቸው። ጽጉባነ እክል ኃጥኡ ርኅቡም ይላል። ጠግበው ይኖሩ የነበሩ ግብጻውያን ተራቡ በረድ መትቶባቸው አንበጣ በልቶባቸው ወርኁባን ጸግቡ ተርበው የነበሩ እስራኤል ጠገቡ መና ከደመና ውሃ ከደንገያ አፍልቆ መግቧቸው እስመ መካን ወለደት ሰብዓተ መካን ቤተ እስራኤል ፍጹማን ልጆችን ሙሴ አሮንን አስገኝታለች። ወእንተሰ ብዙኅ ባቲ ስእነት ወሊደ። ብዙ ልጆች የነበራት ግብጽ ግን መውለድ ተሳናት ልጆቿን ኤርትራ አስጥማባት የወላድ መካን ሆናለችና። አንድም እንደ ሙሴ እንደ አሮን ያለ ልጅ ስላላስገኘች። አንድም እግዚአብሔር ያስተዳሉ መንበሮ በባቢሎናውያን ሊፈርድባቸው ለትሩፋን ሊፈርድላቸው መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ። አድከመ ቀስተ ኃያላን የባቢሎናውያንን ስልጣን አጠፋ። ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን ለትሩፋን ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው ጽጉባነ እክል ኃጥኡ። ጠግበው የነበሩ ባቢሎናውያን ተራቡ ወርኁባን ጸግቡ ተርበው ይኖሩ የነበሩ ትሩፋን ጠገቡ ሲወጡ ብእለ አሕዛብን ዘርፈው ወጥተዋልና። እስመ መካን ወለደት ሰብዓተ መካን ቤተ እስራኤል ፍጹማን ልጆች ዮሴእን ዘሩባቤልን አስገኝታለችና። ብዙ ልጆች የነበራት ወላድ ባቢሎን ግን መውለድ ተሳናት ልጆቿን የቂሮስ የዳርዮስ ጦር አጥፍቶባት የወላድ መካን ሆናለችና።አንድም እግዚአብሔር ያስተዳሉ መንበሮ በአይሁድ በአጋንንት በመናፍቃን ሊፈርድባቸው ለሐዋርያት ለነፍሳት ሊፈርድላቸው መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ። አድከመ ቀስተ ኃያላን የአይሁድን የመናፍቃንን የአጋንንትን ስልጣን አጠፋ። ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሰጣቸው ለነፍሳት ልጅነትን ሰጣቸው። ጽጉባነ እክል ኃጥኡ አስራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን ተቀብለው ጠግበው ይኖሩ የነበሩ ካህናተ ኦሪት ተራቡ አጋንንት ከእክለ ስልጣን ተራቡ ወርኁባን ጸግቡ ልብደ ሠሪ ዓሣ ወጋሪ የነበሩ ሐዋርት ጠገቡ ነፍሳት ልጅነትን ጠገቡ። እስመ መካን ወለደት ሰብዓተ መካን ወንጌል ፍጹም ልጅ ወልደ እግዚአብሔርን አስገኝታለች። መካን አላት ወንጌልን በመልከጼዴቅ ጊዜ ታይታ ጠፍታ ነበርና። ወእንተሰ ብዙኅ ባቲ ስእነት

ወሊደ ብዙ ልጆች የነበሯት ወላድ ኦሪት ግን መውለድ ተሳናት ልጆቿን የጥጦስ ጦር አጥፍቶባት የወላድ መካን ሆናለችና። አንድም እንደ ወልደ እግዚአብሔር ያለ ልጅ ስላላስገኘች ወላድ አላት ኦሪትን ከአሮን ጀምሮ ሊቀካህናት ጠፍቶባት አያውቅምና። እግዚአብሔር ይቀትል ወየሐዩ እግዚአብሔር ያነዲ ወያብእል። ያቴሕት ወያሌዕል። ያቴሕት ጠላቱን ወያከብር ወዳጁን ያቴሕት በሥጋ ወያከብር በነፍስ። 1ኛ ሳሙ.9፣16 ከተበላበት ከተጠጣበት ደስክ አይታጣምና።

ተቃርኖ፡- ሕልቃና ሁለት ሚስቶች ነበሩት እንደዛሬው ሥርዓት አልጸናምና። አንድም ብዛታቸውን ነው እንጂ ማነሳቸውን አይወድም ነበርና። ወተንስአት ሐና ወቆመት ቅድመ እግዚአብሔር። ለእግዚአብሔር ሁሉ ቅድመ ሲሆን መሥዋእት የሚሰዋበትን ጸሎት የሚጸለይበትን ቦታ ሁሉ ቅድመ እግዚአብሔር ይለዋል። ወርኅበ አፉየ ላዕለ ጸላእትየ አፈም በጠላቶቼ ላይ ሰፋ። አሁን በአፍ ላይ አፍ ተጨምሮላት አይደለም ዕፁተ ማኅጸን ርግምተ ከርስ ይብስተ አጥባእት ኃጥእተ በረከት ይሏት ነበርና ርኁተ ማኅጸን ልምልምተ አጥባዕት በዓልተ በረከት ሆንኩ ስትል ነው። 1ኛ ሳሙ.3፣1 ወሳሙኤልሰ ይነውም ውስተ ቤተ መቅደስ ኀበ ታቦተ እግዚአብሔር ከደብተራ ኦሪት ውስጥ ተኝቶ ነበር ማለት አይደለም ከቅጽሩ ውስጥ ሲል ነው።

አብነት፡- ወተፈሣሕኩ በፍርቃንከ በአድኅኖትከ የሚል አብነት ይገኛል።

ምሳሌ፡- 1ኛ ሳሙ.17፣37 ወነስአ ዳዊት ቀስታሞ ውስተ እዴሁ ወነረየ ሎቱ ኀምስተ አእባነ እም ውስተ ፈለግ ወሞጸፈ በእዴሁ አሐተ እብነ እም ህየ ወወጸፋ ወሐጸ ለዝንቱ ኢሎፍላዊ ውስተ ፍጽሙ። ወቦአት ይእቲ እብን ውስተ ፍጽሙ ውስተ ናላሁ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር። ወነስአ ሰይፎ ወቀተሎ ቦቱ። ለጊዜው እንዲህ ተደርጓል ለኋላው ምሳሌ ነው ዳዊት የጌታ ኀልያድ የዲያብሎስ ምሳሌ ነው።

እግዚአብሔር

አዶናይ ማለት ገዢ ፈጣሪ ማለት ነው። ኤሎሄ ማለት አምላክ ማለት ነው። ጸባያት ማለት ዘመዋዕያን ዘኃይላት ማለት ነው። አንድም መዋኢ እግዚአ ኃይላት ማለት ነው። 1ኛሳሙ2፣3 እስመ እግዚአብሔር ማዕምር ውእቱ። እግዚአብሔር ይቀትል ወየሐዩ እግዚአብሔር ያነዲ ወያብእል። ያቴሕት ወያሌዕል። እግዚአብሔር ባሕቲቱ ቅዱስ። 1ኛ ሳሙ.2፣10 ወውእቱ ይኴንን እስከ አጽናፈ ምድር ወይሁቦሙ ኃይለ ለነገሥትነ። 1ኛ ሳሙ.3፣10 ወመጽአ እግዚአብሔር ወቆመ በሰው ልማድ መጽአ ቆመ ብሏል እንጂ በእግዚአብሔር መውጣት መውረድ ኑሮበት አይደለም። 1ኛ ሳሙ.15፣30 ወኢሂ ይኔሥሕ እግዚአብሔር እስመ ኢኮነ ከመ ሰብእ ዘይኔሥሕ። ጌታ ተጸጸተ ለሚለው ሀተታ ምንጩ ይህ ነው።

ጸሎት

1ኛ ሳሙ.2 ወይሁቦ ጸሎቶ ለዘጸለየ። ወባረከ ዓመተ ጻድቃኑ። 1ኛ ሳሙ.7፣8 ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል ለሳሙኤል ኢታርምም በእንቲአነ ወጽራሕ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ወያድኅነነ እም እዴሆሙ ለኢሎፍሊ። 1ኛ ሳሙ.12፣19 ወይቤልዎ ኩሉ ሕዝብ ለሳሙኤል ጸሊ ኀበ

እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ኢንሙት እስመ ወሰክነ ላእለ ኩሉ ኃጣውኢነ እኪተ። ወሊተኒ ኢይግበር ሊተ እግዚአብሔር በዘእኤብስ ሎቱ ከመ እጎድግ ጸልዮ በእንቲአክሙ መምህር ነቢይ ሆኖ አለመጸለይ እግዚአብሔርን መበደል ነውና።

ትምክህት

1ኛ ሳሙ.2፣10 ኢይትመካህ ጠቢብ በጥበቡ ብልህ ሰው በጥበቡ አይመካ አየረ አየራትን ፈለክ ፈለካትን ዕመቀ ዕመቃትን ምሕዋረ ደመናትን አውቃለሁ ብሎ። ኢይትመካህ ኃያል በኃይሉ ብሮጥ እቀድማለሁ ባስር አጠብቃለሁ ብወረውር አርቃለሁ ብሎ። ኢይትመካህ ባዕል በብዕሉ ወርቅ ብር በሳጥኔ እህል በጎተራዬ ከብት በበረቴ አለ ብሎ።

ዕርገት

1ኛ ሳሙ.2፣10 እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጎድጎደ

ሕጻናት

1ኛ ሳሙ.2፣10 ወሕጻንሰ ነበረ ይትለአክ ቅድመ እግዚአብሔር ወቅድመ ኤሊ ካህን።

መሥዋእት

1ኛ ሳሙ.2፣10 ወኮነት ዛቲ ኃጢአቶሙ ለእሙንቱ ደቂቀ ኤሊ ቅድመ እግዚአብሔር ዓባየ ጥቀ እስመ አበሱ ላእለ መሥዋእተ እግዚአብሔር።ወዐበዩ ሰሚያተ ቃለ እግዚአብሔር ወቃለ አቡሆሙ። 1ኛ ሳሙ.2፣32 ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኤሊ ለምንት በእኪት ዓይን ነጸርከ ላእለ መሥዋእትየ ወላዕለ ዕጣንየ ወአብደርከ ደቂቅከ እምኔየ። ክልኤሆሙ ይመውቱ በአሐቲ እለት በኵናት ወአቀውም ሊተ ካህነ ምእመነ። 1ኛ ሳሙ.7፣9 ወነሥአ ሳሙኤል መሐስዓ በግዕ አሐደ ወገብረ መሥዋእተ ለእግዚአብሔር። እስራኤልም ኢሎፍላውያንን አሸነፉ። 1ኛ ሳሙ.15 ወይቤሎ ሳሙኤል ለሳኦል እምነ መሥዋእት ወቁርባን ይፈቅድ እግዚአብሔር ትስማእ ቃሎ።

ፍቅር፣ መገዛት

1ኛ ሳሙ.2፣10 ወገዘክቱሰ ሳሙኤል የሐውር በሰናይ ቅድመ እግዚአብሔር ወቅድመ ሰብእ። 1ኛ ሳሙ 12፣20 ወተቀነዩ ለእግዚአብሔር በኩሉ ልብክሙ። ወኢትትልውዎሙ ለእለ ኢይበቁዑ። ወኢይክሉ አድኅኖተ ነፍስክሙ ወኢምንትኒ። 1ኛ ሳሙ.15፣33 ፊንሐስ ዘንበሪን ሳሙኤል አጋግን መግደላቸው ጽድቅ እንጂ ኃጢአት አይደለም። ኃጢአት የሚሆንባቸው ግደሉ ተብለው እንደ ሳኦል ባይገድሉ ነበር። ወገብረ ሳሙኤል ኩሎ ዘከመ ይቤሎ እግዚአብሔር። 1ኛ ሳሙ.18.1 ነፍሰ ዮናታን ተአስረ በነፍሰ ዳዊት ወአፍቀሮ ዮናታን ከመ ነፍሱ። ወአፍቀረቶ ሜልኮል ወለተ ሳኦል ለዳዊት።

አገልግሎት

1ኛ ሳሙ.3፣1 ወገዘክቱሰ ወልድ ሳሙኤል ሀለወ ይትለአክ ለእግዚአብሔር ቅድመ ኤሊ ካህን።

ተግሣጽ

1ኛ ሳሙ.3፣10 ወይቤ እግዚአብሔር አይዳእክሥ ለኤሊ ከመ እትቤቀሎ አነ ለቤቱ ለዓለም በኃጢአተ ደቂቁ እስመ አኀሠመ ላእለ እግዚአብሔር ደቂቁ ወኢገሠጾመ፡

ፍኖት እኪት፣ የክፉት ውጤት

1ኛ ሳሙ.3፣22 ወደቂቁስ ሐዊረ ሖሩ በፍኖት እኪት ቅድመ እግዚአብሔር፡፡ 1ኛ ሳሙ.4፣1 ወእምዝ ተጋብኡ በእማንቱ መዋእል ኢሎፍሊ ላእለ እስራኤል፡፡ ኢሎፍላውያን ትውልዳቸው ከወደኤት ነው ቢሉ ካም መስሮምን ይወልዳል የመስሮም ልጆች ናቸው፡፡ እስራኤልም በኢሎፍላውያን ፊት ድል ተነሡ፡፡

መሸነፍ

1ኛ ሳሙ.4፣3 ወይቤሉ ሊቃውንተ እስራኤል በበይነ ምንት አውደቀነ እግዚአብሔር ቅድሜሆሙ ለኢሎፍሊ፡፡ ወንንሣእ ታቦተ አምላክነ እም ሴሎም ወትሑር ቅድሜነ ወታድኅነነ እም እደሆሙ ለጸርነ፡፡ ወነስእዋ ኢሎፍሊ ለታቦተ እግዚአብሔር ወሞተ ኤሊ፡፡

ታቦተ እግዚአብሔር

1ኛ ሳሙ.5፣1 ወነሥእዋ ኢሎፍሊ ለታቦተ እግዚአብሔር ወወሰድዋ ወአብእዋ ውስተ ቤተ ዳጎን፡፡ ዳጎን የሰው ምስል ነው፡፡ ወረከብዎ ለዳጎን ውዱቀ በገጹ ቅድመ ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ምድር፡፡ ወርእሱ ለዳጎን ምቱር ወክልኤሆን እደዊሁ ምቱራት ወአልቦ ዘተርፈ እምኔሁ ለዳጎን እንበለ ማእከሉ፡፡ ወከብደት እደሁ ለእግዚአብሔር ላእለ ሰብአ አዛጦን፡፡ወአንበረዋ ለታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ሠረገላ፡፡ 1ኛ ሳሙ.6፣19 ወኢተቀበልዋ ደቂቀ ኢያኮንዩ ምስለ ሰብአ ቤተ ሳሚስ እንዘ ይሬእይዋ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወቀተለት እምኔሆሙ ኃምሳ ምዕተ ወሰብአ ብእሴ፡፡

ንሥሓ፣ ጸም

1ኛ ሳሙ.7፣3 ወይቤሎሙ ሳሙኤል ለኩሉ ቤተ እስራኤል እንዘ ይብል ለእመ በኩሉ ልብክሙ ገባእክሙ ኀበ እግዚአብሔር አሰስሉ እማእከሌክሙ አማልክተ ነኪር ወአምሳሊሆሙ ለበዓሊም ወአስተዳልው ልበክሙ ለእግዚአብሔር ወተቀነዩ ሎቱ ለባሕቲቱ፡፡ ወያድኅነክሙ እም እደሆሙ ለኢሎፍሊ፡፡ ወጸሙ ይእተ አሚረ ያን ጊዜ ጸመ ንሥሓ ጸሙ፡፡ ወይቤሉ አበስነ ቅድመ እግዚአብሔር፡፡

ሐውልት

1ኛ ሳሙ.7፣12 ወነሥአ ሳሙኤል እብነ አሐተ ዓባየ ወሰመያ አቤኔዜር፡፡ አቤኔዜር አላት እብነ ረድኤት ማለት ነው፡፡ ወይቤ እስከ ዝየ ረድአነ እግዚአብሔር (ስለዚህ ይች ድንጋይ የረድኤተ እግዚአብሔር ማስታወሻ ናት ማለት ነው)፡፡

ንጉሥ፣ ቀርነ ቅብዕ

1ኛ ሳሙ.8፣4 ወተጋብኡ ሰብአ እስራኤል ወሖሩ አርማቴም ኀበ ሳሙኤል ኀቡረ ወይቤልዎ ናሁ አንተ ረሳእከ ወደቂቅከኒ ኢሖሩ በፍኖትከ ወይእዜኒ ሢም ለነ ንጉሠ ዘይኴንነነ ከመ ኩሉ አሕዛብ። ወይቤሎሙ ሳሙኤል ዝንቱ ውእቱ ኮነኔሁ ለውእቱ ንጉሥ ዘይነግሥ ለክሙ ይነሥእ ደቂቀክሙ ወይሠይሞሙ በሠረገላቲሁ ወበአፍራሲሁ ወይሬስዮሙ እለ ይረውጹ ቅድመ ሠረገላቲሁ ወይሬስዮሙ ሐራሁ ወወዓልያኒሁ ወይሠይም ላዕሌሁ መኳንንተ አሠርቱ ምእት ወምእት ወኃምሳ ወያስተጌብሮሙ ገራውሂሁ። ወኢይሰምአክሙ እግዚአብሔር እስመ ለሊክሙ ኃረይክሙ ለክሙ ንጉሠ። 1ኛ ሳሙ.9፣16 ወቅብዖ ወአንግሦ ላእለ እስራኤል ወያድኅኖሙ ለሕዝብየ እም እደ ሖሙ ለኢሎፍሊ እስመ ርኢኩ ሕማሞሙ ለሕዝብየ። እስመ በጽሐ ገዓሮሙ ኀቤየ። 1ኛ ሳሙ.10፣1 ወነሥአ ሳሙኤል ቀርነቅብዕ ወሦጠ ላእለ ርእሱ ለሳኦል ወሰአሞ። አፉን መሳሙ ትእምርተ ፍቅር ነው። ወይቤሎ ቀብዐከ እግዚአብሔር ትንግሥ ላእለ ሕዝበ እስራኤል። 1ኛ ሳሙ10፣24 ወየበቡ ኩሉ ሕዝብ ወይቤሉ ሕየው አበ ነጋሢ ሺህ ዓመት ያንግሥህ ብለው መረቁት። 1ኛ ሳሙ.16፣16 ወነሥአ ሳሙኤል ቀርነ ቅብዕ ወቀብዖ ለዳዊት በማዕከለ አኃዊሁ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕለ ዳዊት እም ይእቲ እለት። ዳዊት በተቀባ ጊዜ ሰባት ሀብታት አድረውበታል። ሀብተ ኃይል፣ ሀብተ መዊእ፣ ሀብተ ክህነት፣ ሀብተ መንግሥት፣ ሀብተ ትንቢት፣ በገና መደርደር፣ ሀብተ ፈውስ ናቸው። ሀብተ ኃይል የሚለው ታግሎ መጣል ሩጦ መቅደም ነው። አንበሳ በቡጢ መግደል ነው። ሀብተ መዊዕ የሚለው በጦር መካከል ገብቶ ድል መንሳት ነው። ሀብተ ክህነት መሥዋእት ይሠዋ ነበርና። ሀብተ መንግሥት ነግሷልና። ሀብተ ትንቢት ጴዋዌን ሚጠትን ሥጋዌን ተናግሯልና። ሀብተ በገና በገና ይደረድር ነበርና። ድውይ መፈወስም በዚያው ሳኦልን ይፈውሰው ነበር። 1ኛ ሳሙ.24፣7 ወይቤሎሙ ዳዊት ለሰብኡ ሐሰ ኢይረሲ ሊተ እግዚአብሔር እስመ መሢሁ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወከልያሙ ዳዊት ለሰብኡ ወኢያብሖሙ ከመ ያንስኡ እደዊሆሙ ወይቅትልዎ ለሳኦል።

ነቢይ

1ኛ ሳሙ.9፣6 ወይቤሎ ውእቱ ወልድ ናሁ ብእሴ እግዚአብሔር ሀሎ ውስተ ዛቲ ሀገር። ወይእዜኒ ንሑር ህየ ከመ ያይድዐነ በአይ ፍኖት ነሐውር። እስመ ረአዩ ይቤልዎ ሕዝብ ለነቢይ ትካት።

ተርእዮ

በፊት በፊት የሚሄድ ሰው የራሱ ምስጢር ይታይበታል እንጂ የሌላውን ምስጢር አያይምና።

ዝማሬ፣ መዝሙር፣ ቅኔ

1ኛ ሳሙ.10፣5 ወእምዝ ሶበ ቦእከ ህየ ውስተ ሀገር ትረክብ መዝሙረ ነቢያት እንዘ ይወርዱ እምነ ባማ ወቅድሜሆሙ ማኅሌት ወከበሮ ወእንዚራ ወመሰንቆ ወናሁ ይትኔበዩ ወእንዘ ከመዝ እሙንቱ እነርሱ ሲያመሰግኑ ይመጽእ ላእሌከ መንፈሰ እግዚአብሔር ወትትኔበይ ምስሌሆሙ

ወትትመየጥ ወትከውን ካልአ ብእሴ። በአእምሮ በእውቀት ሌላ ሰው ትሆናለህ። 1ኛ ሳሙ.11፣7 ወመጽአ ኃይለ እግዚአብሔር ላእለ እስራኤል ወወዉኡ ከመ ዘአሐዱ ብእሲ። 1ኛ ሳሙ.16፣25 ወእምዝ ሶበ ይመጽእ ዝክቱ መንፈስ እኩይ ላእለ ሳኦል ይነስእ ዳዊት መሰንቆ ወይዜምር በቅድሜሁ ወየአርፍ ወይኤድሞ ወየኀድጎ መንፈስ እኩይ።

በመልክ በእይታ አለመፍረድ፣ ፍርድ

1ኛ ሳሙ.16፣9 ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሳሙኤል ኢትነጽር ገጸ ወኢትርዓይ ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ እስመ መነንክዎ እስመ ሰብእ ይሬኢ ገጸ ወእግዚአብሔርሰ ልበ ይሬኢ። 1ኛ ሳሙ.24፣16 ወይፍታሕ ፍትሕየ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ይፍረድልኝ።

ኅልያድ

1ኛ ሳሙ.17፣4 ወኑኑ ስድስ በእመት ወስዝር ወጌራ ዘብርት ላእለ ርእሱ ወይለብስ ልብሰ ኀጺን።

ስንቅ መላክ

1ኛ ሳሙ.17፣16 ወይቤሎ እሴይ ለዳዊት ንሣእ ለአኃዊከ ዘንተ መሥፈርተ ጥሀን ወአሠርተ ኅብስተ።ወአኃዊከ ሐውጽ በሰላም ወዜናሆሙ ንሣእ። (በአገልግል እንጀራ ይዘህ ጤፍ እያረመ መኮላ እየመኮሉ ስትወስድ ወዘተ ተረዳው)

ጦርነት

1ኛ ሳሙ.17፣18 ወሳኦልሰ ወኩሉ ቤተ እስራኤል ይትቃተሉ በቆላተ ኤላ ምስለ ኢሎፍሊ።

ተአምኖ

1ኛ ሳሙ.17፣37 ወውእቱ እግዚአብሔር ዘአድኃነኒ እም እደ አንበሳ ወእም እደ ድብ ወውእቱ

ያድኅነኒ እም እዴሁ ለዝንቱ ኢሎፍላዊ። ወነስአ ዳዊት ቀስታሞ ውስተ እዴሁ ወጎረየ ሎቱ ኀምስተ አእባነ እም ውስተ ፈለግ ወሞጸፈ በእዴሁ አሐተ እብነ እም ህየ ወወጸፋ ወሐጸ ለዝንቱ ኢሎፍላዊ ውስተ ፍጽሙ። ወቦአት ይእቲ እብን ውስተ ፍጽሙ ውስተ ናላሁ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር። ወነስአ ሰይፎ ወቀተሎ ቦቱ።

ቅንዐት

1ኛ ሳሙ.19፣9 ወኮነ መንፈስ እኩይ ላእለ ሳኦል ወሀሎ ውስተ ቤቱ ይነብር ወኩናት ውስተ እዴሁ ወዳዊትሰ ይዜምር ቅድሜሁ ወፈቀደ ይርግዞ ለዳዊት በይእቲ ኩናት ወተግኅሠ ዳዊት ወአምሰጠ ወፈነወ ሳኦል ወዐልያኒሁ ይዕግቱ ቤተ ዳዊት ከመ ይቅትልዎ ለዳዊት በጽባሕ ወአይድአቶ ሜልኮል ብእሲቱ ወአውረደቶ ለዳዊት እንተ መስኮት። ወአምሰጠ ወሖረ ዳዊት ኀበ ሳሙኤል ውስተ አርማቴም።

ማኅበረ ነቢያት

1ኛ ሳሙ.19፣20 ወለአከ ሳኦል ሰብአ የአኀዝዎ ለዳዊት ወረከቡ ማኅበሮሙ ለነቢያት ወሳሙኤል ይቀውም ማዕከሌሙ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላእለ ሰብአ ሳኦል ወተነበዩ።

ሞት

1ኛ ሳሙ.25፣1 ወሞተ ሳሙኤል ወተጋብኡ ኩሉ እስራኤል ወበከይዎ ወቀበርዎ ውስተ ቤቱ አርማቴም።

ጠንቋይ፣ ሟርተኛ

1ኛ ሳሙ.28፣3 ወሳኦልሰ ሰአሮን ለእለ ያነቅሓ ምውተ። እንተ ታነቅሕ ማለቱ ግን ሙት አስነስታ አይደለም። ከመቃብሩ ሄዳ ስታሟርት ከመቃብሩ ግዙፋን አጋንንት አይታጡምና አስነሽልኝ ያላትን ሰው መስለው ስለታዩ እንዲህ አለ። ወሶበ ርእየቶ ይእቲ ብእሲት ለሳሙኤል ጸርሐት በዓቢይ ቃል። ልታስነሳው ሄዳለች ተነስቶ ቆይቶ ሳኦልን ጥሪው ብሏታል። ሳኦልን ባየችው ጊዜ ጮኸች። ወትቤሎ ይእቲ ብእሲት ለሳኦል ለምንት አስተሐቀርከኒ እንዘ አንተ ውእቱ ሳኦል። እንዶር የእስራኤል እጣ ናት።

ጽናት

1ኛ ሳሙ.30፣6 ወጸንዐ ዳዊት በእግዚአብሔር ወነሥአ ሳኦል ሰይፎ ወተረግዘ ለሊሁ ቦቱ ወሞተ።

መጽሐፈ ነገሥት ካልእ

ነገርን ማጥራት

2ኛ ሳሙ.1፣2 መጽአ ብእሲ እም ትእይንተ ሕዝቡ ለሳኦል ወይቤሎ ዳዊት እም አይቱ መጻእከ። ወይቤሎ እም ትእይንተ እስራኤል አነ ዘድኅንኩ ወሞቱ ሳኦል ወዮናታን ወልዱ ወይቤሎ ዳዊት ለውእቱ ብእሲ ዘዜነዎ እፎ አእመርከ ከመ ሞተ ሳኦል። ወበከዮሙ ዳዊት ለሳኦል ወለዮናታን ወልዱ።

ንጉሥ

2ኛ ሳሙ.5፣4 ወመጽኡ ኩሎሙ ሊቃናተ እስራኤል ኀበ ንጉሥ ውስተ ኬብሮን ወተመሐለ ምስሌሆሙ ዳዊት መሐላ በኬብሮን በቅድመ እግዚአብሔር ወቀብዕዎ ለዳዊት ይንግሥ ላዕለ ኩሉ እስራኤል። ወልደ ሠላሳ ዓም ውእቱ ዳዊት አመ ያነግሥዎ ወአርብዓ ዓመተ ነግሠ።

ጽዮን

2ኛ ሳሙ.5፣8 ወአስተጋብዐ ዳዊት ቅጽራ ለጽዮን እንተ ይእቲ ሀገረ ዳዊት።

እግዚአብሔር

2ኛ ሳሙ.5፣8 ወእግዚአብሔር ዘኩሉ ይመልክ ሀሎ ምስሌሁ። 2ኛ ሳሙ.22፣32 መኑ ጽኑዕ ውእቱ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር ወመኑ ፈጣሪ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ ኃያል።

የውጭ ግንኙነት

2ኛ ሳሙ.5፣12 ወፈነወ ኪራም ንጉሠ ጢሮስ ሐዋርያተ ኀበ ዳዊት ወእፀወ አርዝ ወጸረብተ እጽ ወወቀርተ እብን ወሐነጹ ቤተ ለዳዊት

መዝሙር

2ኛ ሳሙ.6፣4 ወዳዊትሰ ወኩሉ ደቂቀ እስራኤል ይትዋነዩ ቅድመ እግዚአብሔር በእንዚራ ወየኀልዩ በጸናጽል ወበናብሊስ ወበመሰንቆ። 2ኛ ሳሙ.6፣13 ወዳዊትሰ የአነገር በእንዚራ ቅድመ ታቦት።

ታቦተ እግዚአብሔር

2ኛ ሳሙ.6፣5 ወአልዓለ እዴሁ ዖዛ ላዕለ ታቦተ እግዚአብሔር ከመ የአኃዝ ወያጽንዓ እስመ ተግኅሠት ዘንበል ብላለችና። ወወግዖ ላሕም እንዘ ይእኅዝ እይዛታለሁ ሲል ዖዛን ላመ በቀንዱ ወጋው። አንድም ዖዛ አልተቀባም ነበርና። ወተምዐ እግዚአብሔር ላዕለ ዖዛ ወአውደቆ በህየ ወሞተ ወተሰምየ ውእቱ መካን ምምዋቲሁ ለዖዛ እስከ ዛቲ ዕለት። ወነበረት ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ አቢዳራ ጌትያዊ ሠለስተ አውርኃ ወባረከ እግዚአብሔር ኩሎ ቤቶ ለአቢዳራ በእንተ ታቦተ እግዚአብሔር። ወዳዊት ወኩሉ ሕዝበ እስራኤል ወሰድዎ ለታቦተ እግዚአብሔር በውውዓ ወበቃለ ቀርን።

ርእይ፣ ሐልዮ፣ ነቢብ፣ ገቢር

2ኛ ሳሙ.11፣2 ወሶበ ኮነ ፍና ሠርክ ተንስአ ዳዊት እምስካቡ ወርእየ ብእሲተ እም ላእለ ናሕስ እንዘ ትትሐጸብ ወለአከ ዳዊት ኀቤሃ ወነሥኣ ወሰከበ ምስሌሃ ወጸንሰት ይእቲ ብእሲት። ወጸሐፈ ዳዊት እንዘ ይብል አብዕዎ ለኦርዮ ውስተ ጽኑዕ ቀትል ወኀድግዎ ወተመየጡአ ይቀኍስልአ ወይሙትአ። ኦርዮ የጌታ ምሳሌ ጌታም መስቀለ ሞቱን ተሸክሞ ሄዷልና ኦርዮም ጦማረ ሞቱን ይዞ ሄዷልና። ወሞተ ኦርዮኒ ኬጥያዊ ወኮነ እኩየ ዝንቱ ነገር ዘገብረ ዳዊት በቅድመ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር።

አንድምታ

ኦርዮ የጌታ ምሳሌ ጌታም መስቀለ ሞቱን ተሸክሞ ሄዷልና ኦርዮም ጦማረሞቱን ይዞ ሄዷልና። **እርቅ፡-** 2ኛ ሳሙ.24፣14 ይኄይሰኒ እደቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር እስመ ብዙኅ ውእቱ ምሕረቱ ፈድፋደ እምእደቅ ውስተ እደ እጓለ እመሕያው። ሲራክ እምእደቅ ውስተ እግዚአብሔር ይኄይሰኒ እደቅ ውስተ እደ እጓለ እመሕያው አለ አይጣላም ቢሉ አይጣላም።

ሲራክ አይገኝም እንጂ በነፍስ በሰው እጅ መውደቅ ይሻላልና። ዳዊት በሥጋ በፍጡር እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላልና ሲል ነው።

በምሳሌ መናገር

2ኛ ሳሙ.12፣1 ወፈነዎ እግዚአብሔር ለናታን ነቢይ ኀበ ዳዊት። (በምሳሌ መናገር ጉዳዩን በሕሊና ለማስቀመጥ ነገሩን ለማጉላት ወሳኝ ነገር ነው)። ወቦአ ኀቤሁ ወይቤሎ ሀለው ክልኤቱ እደው ውስተ አሐቲ ሀገር አሐዱ ባዕል ወአሐዱ ነዳይ ወቦ ለዝክቱ ባዕል ብዙኀ እንስሳ ወመራዕይ አባግዕ ወለዝክቱሰ ነዳይ አልቦቱ ዘእንበለ አሐቲ በግእት ወእምዘበልአ ትበልእ ወመጽአ ነግድ ኀበ ዝክቱ ብእሲ ባዕል ወነሥኣ ለበግእቱ ለዝንቱ ነግድ ወተምዐ ዳዊት ፈድፋደ ላእለ ውእቱ ብእሲ ወይቤሎ ናታን ነቢይ ለዳዊት አንተ ውእቱ ብእሲ ዘገበርኮ ለዝንቱ።

ንሥሓ

2ኛ ሳሙ.12፣12 ውይቤሎ ዳዊት ለናታን አበስኩ ለእግዚአብሔር። በዚህ ጊዜ እግዚኦ በመዓትከን ደርሷል። ቤርሳቤህ ከዳዊት የጸነሰችው ልጅም ሞቷል። ዳዊትም ቤርሳቤህን አገባና ሰሎሞንን ወለደ። ሰሎሞን ማለት መስተሳልም መስተፋቅር ማለት ነው። ዳዊትና ጌታ በታረቁበት ወራት ተወልዷልና። አንድም ዘመኑ ዘመነ ሰላም ሆኗልና።

ምክር

2ኛ ሳሙ.17፣18 ትኄይስ ምክረ ኩሲ እምክረ አኪጦፌል።

ትእዛዛተ እግዚአብሔር

ለአንድ ቤት አስር ደጃፍ ይኖረዋል። ዘጠኙን ዘግቶ አንዱን ይተወዋል ሌባ በዚያ ገብቶ ከእውቀት እስከ ሽበት የሰበሰበውን እንዲወስድበት ከትእዛዛት አንዱን ማፍረስም እንዲሁ ነው። 2ኛ ሳሙ.22፣37 ወትምህርትከ ዘያጸንዐኒ ለዝሉፉ ወተግሣጽከ ውእቱ ዘይሜህረኒ።

ስግደት

2ኛ ሳሙ.18፣28 ወጸርሐ አኪማሆስ ወይቤሎ ለንጉሥ ሰላም ለከ ወሰገደ ሎቱ ለንጉሥ በገጹ ውስተ ምድር።

ጸሎት

2ኛ ሳሙ.22፣7 ወሶበ ተመንደብኩ ጸዋእክዎ ለእግዚአብሔር ወለአምላኪየ ከመ ይርድአኒ ወሰምዐኒ በጽርሐ መቅደሱ ቃልየ።

አንድነት

2ኛ ሳሙ.22፣26 ምስለ ጻድቅ ትጸድቅ ወምስለ ብእሲ ንጹሕ ትነጽሕ ወምስለ ኅሩይ ኅሩ ትከውን ወምስለ ጠዋይ ትጠዊ።

ትንሣኤ

ሐተታ ፀሐይ መውጣቱ የመወለዳችን በዚህ ዓለም ሲበራ መኖሩ በዚህ ዓለም የመኖራችን መግባቱ የመሞታችን ተመልሶ በምሥራቅ መውጣቱ የመነሳታችን አምሳል ነው።

መጽሐፈ ነገሥት ሣልስ

ጸሎት

1ኛ.ነገ.8፣52 ወእደዊሁ ያሌዕል ውስተ ሰማይ።

ሽምግልና

1ኛ.ነገ.1፣1 ወዳዊትሰ ንጉሥ ልህቀ ውኀለፈ መዋእሊሁ ዳዊት ፈጥኖ አረጀ።

ንግሥና፣ ንግሥተ አዜብ

1ኛ.ነገ.1፣5 ወአዶንያስ ወልደ አጊት ተንስአ ወይቤ አነ እነግሥ። የዳዊትን ማርጀት የሰሎሞንን ሕጻንነት አይቶ እነግሣለሁ አለ። የወንድሜ የአቤሴሎም መንግሥቱ ያልጸናለት ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት ሰው ባይይዝ አይደለምን ብሎ ከቤተ መንግሥት ኢዮአብን ከቤተ ክህነት አብያታርን ይዞ እነግሣለሁ ብሎ ተነሳ። በኋላ ግን በንጉሥ ዳዊት ትእዛዝ ካህኑ ሳዶቅ ሰሎሞንን በግዮን አነገሠው ወይቤሉ ኩሉ ሕዝብ ሕየው አበ ነጋሢ ሰሎሞን። ወሰሎሞን ነበረ ዲበ መንበረ ዳዊት። 1ኛ.ነገ.9፣4 ወአንተኒ ለእመ ሖርከ ቅድሜየ በከመ ሖረ ዳዊት አቡከ በጽድቅ ወበንጹሕ ልብ ወበርትዕ ወበኩሉ መዋዕል ከመ ትግበር ኩሎ ዘአዘዝኩከ ወትእቀብ ሕግየ ወትእዛዝየ አቀውም መንበረ መንግሥትከ ላዕለ እስራኤል ለዓለም። ወእመሰ ተመየጥክሙ ወኃደግሙኒ ወኢዐቀብክሙ ትእዛዝየ ወሕግየ ወሖርክሙ ወተቀነይክሙ ለባዕዳን አማልክት እደመስሶሙ ለእስራኤል። ወለዝንቱኒ ቤት ዘቀደስክዎ (ቤተመቅደስ) እገድፎ እም ቅድመ ገጽየ። 1ኛ.ነገ.10፣6-9 ወትብሎ ንግሥት ወይኩን ቡሩክ እግዚአብሔር አምላክከ ዘሠምረ ያንብርከ ላእለ አትሮንሰ እስራኤል። 1ኛ.ነገ.11፣1 ወሰሎሞንሰ ንጉሥ መፍቀሬ አንስት ውእቱ ወነሥአ አንስተ እም ነኪር ሕዝብ ወለተ ፈርዖንሂ ወሞዓባውያተ ወአሞናውያተሂ ወእም ኩሎሙ አህዛብ ዘይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ኢትባኡ ኀቤሆሙ ሰብዓቱ ምእት አንስቲያሁ ወሠለስቱ ምእት ዕቁባቲሁ ወእምዝ አመ መዋዕለ ልህቀ ሰሎሞን ኢኮነ ልቡ ምስለ እግዚአብሔር አምላኩ ወሜጣሁ ልቦ አንስቲሁ እለ አውሰቦን እም ነኪር።ወአትለዋሁ ኀበ አማልክቲሆን ወሐነጸ ሰሎሞን ቤተ ለኮሞስ አምላከ ሞዐብ ወሠዐ ወዐጠነ ለአማልክቲሆን ወገብረ ሰሎሞን እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር። ሰሎሞን ንጉሥ ሞተ ወነግሠ ሮብዓም ወልዱ።

ክህነት መሻር፣ ነቢይነት

1ኛ.ነገ.2፣27 ወሠአሮ ሰሎሞን ለአብያታር ከመ ኢይኩን ካህነ ለእግዚአብሔር ወለሳዶቅ ካህን ሜሞ ሊቀ ካህናት ህየንተ አብያታር። 1ኛ.ነገ.19፣16 ወለኤልሳእ ወልደ ሳፋጥ ቅብዖ ይኩን

ነቢየ ህየንቱክ። ወነሥአ ጽምደ አልእምቲሁ ወጠብሐ ወአቅረበ ለሕዝብ ወበልዑ ወተለዎ ለኤልያስ።

መሐላ

መሐላ እግዚአብሔር ሁልጊዜም መጠበቅ አለበት። 1ኛ.ነገ.2፣44 ወለምንት ኢዐቀብከ መሐላ እግዚአብሔር።

ጸጋ

1ኛ.ነገ.3፣4 ወሦዐ ሰሎሞን በገባያን ወጸለየ ወይቤ ሀቦ ለገብርከ ልበ በዘይሰምእ ወያገብእ ፍትሐ በጽድቅ ለሕዝብከ። ወይቤሎ እግዚአብሔር ወሀብኩከ ልበ ጠቢበ ወለባዌ ወዘኒ ኢሰአልከኒ እሁበከ ብዕለ ወክብረ ወእመ ሖርከ በፍኖትየ። ወዐቀብከ ትእዛዝየ ወሥርዓትየ።

መሥዋእት

1ኛ.ነገ.3፣16 ወቆመ ቅድመ ምሥዋእ በቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በጽዮን ወአብዓ መሥዋእተ ሰላም። ሕዝቡን ከእርሱ እርሱን ከእግዚአብሔር አንድ የሚያደርግ መሥዋእት ሠዋ

ስለፍጥርታት ምርምር

1ኛ.ነገ.4፣33 ወነበበ ሰሎሞን በእንተ እጸው እም እጸወ አርዝ ዘውስተ ሊባኖስ እስከ ሐምለ ሁሱጵ ዘይወጽእ ዲበ አረፍት ይህ ለዚህ ይበጃል እያለ። አንድም በዚህ ጊዜ ቢቆርጡት ጽንዕ ይሆናል እያለ ተናገረ። ወነበበ በእንተ እንስሳሂ የዚህ ባሕርይ ልዝብ ነው የዚህ ባሕርይ ቁጡ ነው እያለ ተናገረ። ወአእዋፍ ወበእንተ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር። ወበእንተ ዓሣት ወይመጽዑ እምኩለኩ አህዛብ ይስምዑ ጥበቢሁ ለሰሎሞን።

የውጭ ግንኙነት

1ኛ.ነገ.5፣9 ወወሀቦ ኪራም ለሰሎሞን ዕጸወ ቈድሮስ ወጳውቄና ወሰሎሞንኒ ወሀቦ ለኪራም ንጉሠ ጢሮስ ክልኤተ እልፈ በመስፈርተ ቆሮስ ሥርናየ ወኮነ ሰላም በማእከለ ሰሎሞን ወማእከለ ኪራም ወተመሐሉ ወገብሩ ኪዳነ ማእከሎሙ።

ቤተ መቅደስ፣ ምስል

1ኛ.ነገ.6፣19 ወለኩሉ ቤቱ ቀፈሎ በወርቅ ፍጹም ወገብረ በውሳጤ ዳቤር ክልኤተ ኪሩቤለ እም እጸ ዘይት ዘአሥር በእመት ቆሙ። ወአሥዐለ ሥዕለ ኪሩብ። ሥዕለ ኪሩብን ቀረጸ። ወሰበከ ክልኤተ አእማደ እምነ ብርት ከብርት ሁለቱን አዕማድ በለዝንና ያቁምን ሠራ ወገብረ ሰሎሞን ኩሎ ንዋያተ ለቤተ እግዚአብሔር ምሥዋዓ ዘወርቅ። ቆመ ብእሲ ማለት በሰው ቁመት ልክ ሦስት ክንድ ከስንዝር ነው። ሁለቱ ቆመ ብእሲ ሰባት ክንድ ነው። ስድስቱ ቆመ ብእሲ 21 ክንድ ነው። 1ኛ.ነገ.8፣16 ወይቤሎ እግዚአብሔር ለዳዊት አቡየ እስመ ፈቀድከ በልብከ ከመ

ትሕንጽ ቤተ ለስምየ ሠናየ ገበርከ እስመ ፈቀድከ በልብከ ወባሕቱ አኮ አንተ ዘተሐንጽ ቤተ ለስምየ አላ ወልድከ ዘወጽአ እም ሐቄከ ውእቱ የሐንጽ ቤተ ለስምየ። ወአልዓለ ሰሎሞን እደዊሁ ወይቤ ይኩና ክሡታተ አዕይንቲከ ውስተ ዝንቱ መካን መዓልተ ወሌሊተ ወስማዕ ስእለቶ ለገብርከ ወለሕዝብከ እስራኤል ዘጸለዩ በዝንቱ መካን። 1ኛ.ነገ.9፣3 ወይቤሎ እግዚአብሔር ሰማእኩ ጸሎተከ ወስእለተከ ዘሰአልከ ቅድሜየ ወቀደስክዎ ለዝንቱ ቤት ዘሐነጽከ ከመ የሀሉ ስምየ ለዓለም ወይሄልዋ አዕይንትየ ወልብየ ህየ በኩሉ መዋዕል።

ጽዮን፣ ታቦት

1ኛ.ነገ.8፣1 ይእተ አሚረ አስተጋብዖሙ ለኩሎሙ ሊቃናተ እስራኤል በጽዮን ከመ ያምጽኣ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እም ሀገረ ዳዊት እንተ ይእቲ ጽዮን። ወአልቦ ህየ ውስተ ታቦት ዘእንበለ ክልኤቱ ጽላት ዘእብን።

ረድኤተ እግዚአብሔር

1ኛ.ነገ.8፣52 ወይሄሉ እግዚአብሔር አምላክነ ምስሌነ በከመ ሀሎ ምስለ አበዊነ ወኢየኃድገነ ወኢይገድፈነ ወንሑር በኩሉ ፍናዊሁ ወንእቀብ ኩሎ ትእዛዛቲሁ ወሥርዓቶ ዘአዘዞሙ ለአበዊነ።

የምረቃ በዓል

1ኛ.ነገ.8፣62 ወገብረ ሰሎሞን በዓለ ይእተ አሚረ ወኩሉ እስራኤል ምስሌሁ በዓቢይ ማህበር።

ምክር

1ኛ ነገ.12፣4 ወነገሮሙ ንጉሥ (ሮብዓም) ለሊቃናት ወይቤሎሙ ምንተ ትሜክሩኒ ቃለ ዘአወስኦሙ ለዝንቱ ሕዝብ ወይቤልዎ ዮምሰ ገብሮሙ አንተ ለዝንቱ ሕዝብ ወተቀነይ ሎሙ ወይከውኑከ አግብርተ በኩሉ መዋእል። ወነደገ ምክሮሙ ለሊቃናት ዘአምከርዎ ወተማከረ ምስለ ደቂቅ ወአበየ ሰሚዖቶሙ ለሕዝብ ንጉሥ። ወአለውዎ እስራኤል ለቤተ ዳዊት (ሮብዓም) ወአንገሥዎ ለኢዮርብዓም ላእለ ኩሉ እስራኤል። ወአልቦ ዘተለዎ ለቤተ ዳዊት ዘእንበለ በትረ ይሁዳ ወብንያም ባሕቲቶሙ።

ባዕድ አምልኮ

1ኛ.ነገ.11፣25 ወመከረ ንጉሥ ኢዮርብዓም ምክረ ወገብረ ክልኤተ አልህምተ ዘወርቅ ወይቤሎሙ ለሕዝብ አክለክሙ ዐሪግ ውስተ ኢየሩሳሌም ናሁ አማልክቲክሙ እስራኤል እለ አውጽኡክሙ እም ግብጽ። ወኮነ ዝንቱ ነገር ጌጋይ። ወገብረ ውስተ አውግር አብያተ አማልክት ወገብረ ገነውተ አማልክት።

መጻሕፍት

1ኛ.ነገ.16፣20 ወተረፈ ነገሩ ለዘምሪ ወኩሉ ግብሩ ዘገብረ ናሁ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ

ኖብያቲሆሙ ለነገሥተ እስራኤል።

ኤልያስ፣ አብድዩ

1ኛ.ነገ.17፣1 ወይቤሎ ለአክአብ ሕያው እግዚአብሔር አምላከ ኃይል ከመ ኢይወርድ ዝናም ዘእንበለ በቃለ አፉየ። ወገብረ ኤልያስ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር። ወቋዓት ያመጽኡ ሎቱ በአፈ ጽባሕ ኅብስተ ወፍና ሠርክ ሥጋ ወኅብስተ። የሰራፕትዋን ሴት ልጅ ጸልዮ ከሞት አስነሳው። 1ኛ.ነገ.18፣3 ወጸውዖ አክአብ ለአብድዩ መጋቢሁ ወአብድዩሰ ፈራሄ እግዚአብሔር ውእቱ ፈድፋደ። ወአመ ቀተለቶሙ ኤልዛቤል ለነቢያተ እግዚአብሔር ነሥአ አብድዩ ምእተ ብእሴ እም ነቢያት ወኅብዖሙ በበኃምሳ ውስተ በዓት ወሴሴሙ እክለ ወማየ። ወሶበ ርእዮ አክአብ ለኤልያስ ይቤሎ አንተኑ ውእቱ ኤልያስ ዘትገፈትዖሙ ለእስራኤል። ወይቤሎ ኤልያስ አንሰ ኢይገፈትዖሙ ለእስራኤል አላ አንተ ወቤተ አቡከ።

መወላወል እንደማይገባ

1ኛ.ነገ.18፣21 ወቀርበ ኤልያስ ኀበ ኩሎሙ እስራኤል ወይቤሎሙ ኤልያስ እስከ ማእዜኑ ተሐነክሱ በክልኤሆን ጌጋያቲክሙ ለእመ እግዚአብሔር ውእቱ አምላክ ኪያሁ ትልው ወለእመ በአል ውእቱ አምላክ ኪያሁ ትልው።

መልአክ

1ኛ ነገ.19፣4 ወእምዝ ሰከበ ወኖመ ኤልያስ ህየ ታሕተ እጽ ወሶቤሃ መጽአ መልአከ እግዚአብሔር ወገሠሶ ወይቤሎ ተንስእ ወብላዕ። 1ኛ.ነገ.22፣18 ርኢክዎ ለአምላከ እስራኤል እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ወኩሎሙ መላእክተ ሰማይ ይቀውሙ እም የማኑ ወእም ጸጋሙ።

ቅዱስ ቅንዓት

1ኛ.ነገ.19፣10 ወይቤ ቀኒዐ ቀናዕኩ ለእግዚአብሔር ዘኩሉ ይመልክ እስመ ኀደጉከ ደቂቀ እስራኤል።

ርስት

1ኛ.ነገ.20፣3 ወይቤሎ ናቡቴ ለአክአብ ኢያምጽእ ሊተ እግዚአብሔር ከመ አሀብከ ርስተ አበውየ። ኤልዛቤልም በሐሰት ምስክር አስገደለችው።

ነቢያተ ሐሰት

1ኛ.ነገ.22፣20 ወእምዝ ወጽአ መንፈስ ወቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ወይቤ አነ አስሕቶ ለአክአብ ወይቤሎ እግዚአብሔር በምንት ታስሕቶ ወይቤ አነ አሐውር መንፈሰ ሐሰት ውስተ አፉሆሙ በነቢያቲሁ።

መጽሐፈ ነገሥት ራብዕ

ዕርገተ ኤልያስ፣ አጽመ ኤልሳዕ

2ኛ ነገ.2፣1 ወእምዝ አመ ያዐርጎ እግዚአብሔር ለኤልያስ ውስተ ሰማይ ሖሩ ኤልያስ ወኤልሳእ እም ገልገላ። ወእንዘ የሐውሩ ክልኤሆሙ መጽአ ሠረገላ ዘእሳት ወአፍራስ ዘእሳት ወዐርገ ኤልያስ ውስተ ሰማይ። 2ኛ ነገ.2፣20 ወይቤሎሙ ኤልሳዕ አምጽኡ ሊተ መስብክተ ሐዳስ ወደዩ ውስቴቱ ጼው ወአምጽኡ ሎቱ ወሦጠ ውስቴቱ ኀበ ነቅዐ ማይ ዝኩ ጼው ወይቤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈወስክዎ ለዝኢ ማይኢ ከመኢ አልቦኢ ዘይመውትኢ እምኔሁኢ። ለጊዜው እንዲህ ተደርጓል ለኋላው ግን ምሳሌ ነው አዲስ ሽክላ የእመቤታችን ልጓኩት ዘኤልሳእ እንዲል። ጼው የጌታ ጼው ዘአጥዐሞ ለልሡኅ እንዲል። ምረቱ የመርገም የፍዳ ምሳሌ ነው። 2ኛ ነገ.13፣21 ወወረደ ውእቱ በድን ላዕለ አዕጽምተ ኤልሳእ ወለከፎ ውእቱ በድን ለበድነ ኤልሳእ ወሐይወ ውእቱ ብእሲ ወተንሥአ።

ተሣልቆ

2ኛ ነገ.2፣23 ወአኀዙ ይሣለቁ ላእሌሁ ወይቤልዎ ዕርግ በራህ። ወሶበ ተመይጠ ድኅሬሁ ወርእዮሙ ረገሞሙ በስመ እግዚአብሔር። ወመጽኡ በጊዜሃ ክልኤቱ ድባት እም ገዳም ወቀተሉ እምኔሆሙ አርብዓ ወክልኤተ ደቂቀ።

መዝሙር

2ኛ ነገ.3፣15 ወይእዜኒ አምጽኡ ሊተ ዘይዜምር ወእምዝ ሶበ ዘመረ ዘይዜምር መጽአ እደ እግዚአብሔር ላዕሌሁ።

ጠበል፣ ጸበል

2ኛ ነገ.5፣13 ወሖረ ንእማን ወወረደ ወተጠምቀ በዮርዳኖስ ሰብዓተ ጊዜያተ በከመ ይቤሎ ኤልሳእ ወሐይወ። ወይቤሎ ንእማን እመ አኮ ለገብርከ የሐብዎ ጸረ ክልኤቱ አብቅልት መሬተ። የሁለት በቅሎዎች ጭነት አፈር ለባርያህ ይሰጡት ዘንድ እዘዝ አለው።

ረድኤተ እግዚአብሔር

2ኛ ነገ.6፣16 ወይቤሎ ኤልሳዕ ኢትፍራህ እስመ ይበዝኑ እለ ሀለው ምስሌነ እምኔሆሙ ወጸለየ ኤልሳዕ ወይቤ እግዚኦ ክስት አዕይንቲሁ ለዝ ወልድ ወይርአይ ወከሠቶ እግዚአብሔር አዕይንቲሁ ለዝክቱ ወልድ ወርእየ ኩለንታሁ ደብረ አፍራስ ወሠረገላተ እሳት የዐውዶ ለኤልሳዕ።

ረኀብ

2ኛ ነገ.6፣25 ወኮነ ዓቢይ ረኀብ ውስተ ሰማርያ እስከ ኮነ ርእሰ አድግ በኃምሳ ሰቅለ ብሩር ኩስሓ ርግብ በሐምስቱ ሰቅለ ብሩር። ልጇን አብስላ የበላች አለች።

ጸሎት

2ኛ ነገ.19፣1 ወሶበ ሰምዐ ሕዝቅያስ ንጉሥ ትእይርቶ ለሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ሠጠጠ አልባሲሁ ወለብሰ ሰቀ ወቦአ ቤተ እግዚአብሔር ወለአከ ኀበ ኢሳይያስ ነቢይ ወልደ አሞጽ። ከመ ይጸሊ ሎቱ። 2ኛ ነገ.20፣2 ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይሴብሖ ወይቤሎ እግዚአብሔር ወእቄስክከአ ላእለ ክራማቲከአ ዐሠርተ ወኃምስተ ዓመተአ።

ተርእዮ

ሕዝቅያስ ሲፈወስ ሠርክ የነበረው ተመልሦ ሠለስት ሆኗል። የባቢሎን ንጉሥ መሮዳህ ሠርክ የነበረው ተመልሦ ሠለስት የሆነበት ነገሩ ምንድን ነው?ብሎ ጠየቀ ሕዝቅያስ የተፈወሰበት ቀን ነው አሉት። ለዚህስ ባይገብሩ እግዚአብሔር እዳ ይላል ብሎ የበልዓን ልጅ በልዳድን እጅ መንሻ አሲዞ ሰድዶታል። ወተፈሥሐ ሕዝቅያስ በእንቲአሁ ወአርአዮሙ ኩሎ ቤተ ኒቆታሁ ወርቀ ወብሩረ። ወአፈዋተኒ ወቅብዓኒ ሠናየ ወቤተ ንዋይኒ ወአልቦ ኀበ ኢያርአዮሙ ሕዝቅያስ ዘውስተ ቤቱ ወዘኩሉ ምኩናኑ። ወይቤሎ ኢሳይያስ ይመጽእ መዋእል ወይነሥዑ ኩሎ ዘውስተ ቤትከ ወኩሎ ዘዘገቡ አበዊከ እስከ ዮም ወይወስዱ ባቡሎን ወአልቦ ዘያተርፉ ይቤ እግዚአብሔር (ሰው የእግዚአብሔር ሲሆን የዓለሙ ሁኔታ አያስደስተውም አያሳዝነውም ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል። የዓለሚቱ ድርጊት ሁኔታ አያሳዝነውም አያስደስተውም።ማንም ይንገሥ አይመለከተውም ጉዳዩ በማንኛውም ሁኔታና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው። ማንም ቢያወድሰው ማንም ቢያንቋሽሸው አይመለከተውም። በማንኛውም የዓለሚቱ ሁኔታና ጊዜ የሰው ነፍሳዊ ድኅነት ብቻ ነው የሚያሳስበው እንጂ)።

መልአክ

2ኛ ነገ.19፣31 ወእምዝ መጽአ መልአከ እግዚአብሔር በይእቲ ሌሊት ወቀተለ እምተዐይኪሆሙ ለፋርስ አሠርተ ወሰመንተ እልፈ ወኃምሳ ምእተ።

ንጉሡ			የነገሠበት ዘመን		
ኤሊ			40 ዓመት		
ሳሙኤል			20 ዓመት		
ሳኦል			40 ዓመት		
ዳዊት			40 ዓመት		
ሰሎሞን			40 ዓመት		
ሀገር		ከተማ	ሀገር		ከተማ
እስራኤል		ሰማርያ (10ሩ ነገድ)	ይሁዳ		ኢየሩሳሌም (2ቱ ነገድ)
ንጉሡ	የነገሠበት ዘመን	ምርመራ	ንጉሡ	የነገሠበት ዘመን	ምርመራ

ኢዮርብዓም	24 ዓመት		ሮብዓም	17 ዓመት	
ናባጥ	2 ዓመት		አብያ	7 ዓመት	ወአሰሰለ ዓሣ ኩሎ አማልክት እም ብሔር ወሠዐረ ኩሎ አማልክተ ዘገብሩ አበዊሁ
ባዖስ	24 ዓመት		አሣ	41 ዓመት	
ኤላ	2 ዓመት		ኢዮሳፍጥ	25 ዓመት	በዓሣ ግብር ጸና ያን ጊዜ ነቢዩ ሚኪያስ ነበረ።
ዘምሪ	7 ቀን	ዘንበሪና ታምኒ 2 ዓመት ተዋጉ ዘንበሪ አሸንፎ 12 ዓመት ነገሠ።	አካዝያስ	1 ዓመት	
ዘንበሪ	12 ዓመት		ጎቶልያ	6 ዓመት	
አክአብ	12 ዓመት	ነቢዩ ኤልያስ በዚህ ዘመን ነበረ።ኤልዛቤል ሚስቱ ናት።	ኢዮአስ	40 ዓመት	ዮዳሔ ካህን በዚህ ዘመን ነበረ።
አካዝያስ	2 ዓመት		አሜሴያስ	29 ዓመት	
ኢዮራም	12 ዓመት	ነቢዩ ኤልሳእ ነበረ	አዛርያስ	52 ዓመት	ያዝያን ሌላ ስሙ ነው።በዘመኑ አዛርያስ የሚባል ሊቀ ካህናት ነበር።
ኢዩ	28 ዓመት	ደግ ነበረ	ኢዮአታም	17 ዓመት	
ዮአክስ	17 ዓመት		አካዝ	16 ዓመት	
ዮአስ	16 ዓመት		ሕዝቅያስ	29 ዓመት	ነቢዩ ኢሳይያስ ነበረ
ኢዮርብአም	41 ዓመት		ምናሴ	55 ዓመት	ሐነጸ አብያተ አማልክት ዘነሰተ አቡሁ ሕዝቅያስ ወሠዐ ወልዶ በእሳት
ዘካርያ	6 ወር	ወበመዋዕሊሁ ለፋቁ ሐ መጽአ ቴልጌል ቴልፌልሶር ንጉሠ ፋርስ ሰባት አህጉር ወግቶ ማርኮ ወደ ፋርስ ወስዷቸዋል።	አሞጽ	2 ዓመት	
ሴሎም	30 ቀን		ኢዮስያስ	31 ዓመት	ፈርያን ኒካዑ ንጉሠ ግብጽ ገደለው።
ምናሔም	10 ዓመት		ዮአክስ	3 ወር	
ፋቁስያስ	2 ዓመት		ኤልያቄም	11 ዓመት	ያነገሠው ፈርያን ኒካዑ ነው ስሙንም ዮዐቄም አለው።ለግብጽ እየገበረ ሳለ ወበመዋእሊሁ ዐርገ ንጉሠ ናቡከደነጾር ንጉሠ ባቢሎን ውስተ ውእቱ ብሔር እንዲል
ፋቁሔ	20 ዓመት				
ሆሴዕ	9 ዓመ	የፋርሱ ንጉሥ ስልምናሶር በእርሱ ላይ ዘመተ ሆሴዕም ተገዢ ሆነ በኋላ ሆሴዕ አልገብርም አለ እንደገና ወተቃተሉ			

	ት	ንጉሠ ፋርስ ወአመ ታስዕ ዓመተ መንግሥቱ ለሆሴዕ ነሥኣ ንጉሠ ፋርስ ለሰማርያ ወአፍለሶሙ ለእስራኤል ብሔረ ፋርስ፡፡ወኢተርፉ እንበለ ነገደ ይሁዳ ባሕቲቶሙ፡፡ንጉሠ ፋርስም በምትኩ አህዛብን በሰማርያ አሰፈረባት አንበሳ ተነስቶ ይበላቸው ጀመር፡፡ንጉሡም ከአይሁድ አንድ ካህን ልኮ እንዲያስተምራቸው አደረገ፡፡ጣዖታቸውንም ተው አንበሳውም መብላቱን አቆመ፡፡ሕዝቅያስ በነገሠ በ6 ዓመቱ 10ሩ ነገድ ተማረኩ			ለግብጽ ይገብሩ የነበረውን ለባቢሎን ገበሩ በኋላ ግን አልገብርም ስላለ ኤልያቄም ተገደለ፡፡
			ኢዮአቄም	3 ወር	ሌላ ስሙ ኢኮንያን ነው ወአፍለሳ ናቡከደነጾር ለኢየሩሳሌም ወለኩሎሙ መላእክቲሆሙ ወለዓበይቶሙ ወአውጽአ ኩሎ መዛግብተ ቤተ ንጉሥ ወሰበረ ኩሎ ንዋየ ወርቅ ናቡከደነጾር፡፡
			ሴዴቅያስ	11 ዓመት	ኢኮንያንን ማርኮ ሴዴቅያስን ያነገሠው ናቡከደነጾር ነው፡፡በኋላ ግን ሴዴቅያስ ስለከዳ ናቡከደነጾር ሠራዊቱን አስከትሎ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ወነሠቱ ዓረፍተ ጥቅማ ለኢየሩሳሌም ወለዘተርፈ ሕዝብ ውስተ ሀገር አፍለሶሙ ናቡዛርዳን ሊቀመበስላኒሁ ለናቡከደነጾር ወለእለተርፉ ሕዝብ ሢሞ ላዕሌሆሙ ለጎዶልያ፡፡

መጽሐፈ ዜና መዋዕል

የሳባ ዘር ሀረግ

1ኛ ዜና.1፣1 አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ፣ ቃይናን፣ መላልኤል፣ ያሬድ፣ ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜህ፣ ኖኅ፣ ሴም፣ አይላም፣ አሡር፣ አርፋክስድ፣ ሳላን፣ ቃይናን፣ ዔቦር፣ ዮቅጣን፣ ኤልሞዳድ፣ ሣሌፍ፣ አራሞት፣ ያራሕ፣ ቂዱራም፣ ኤዜል፣ ዲቅላም፣ ጌማሄል፣ ኤልሜሄል፣ ሳባ ይላል፡፡ ይህ የሴሙ ሳባ ሲቆጠር ነው፡፡ የካሙ ግን ኖኅ ካምን ወለደ ካም ሳባን ወለደ፡፡

የሰው ዘር

ሲዶን፣ ኬጤዎን፣ ኢያቡሴዎን፣ አሞሬዎን፣ ጌርጌሴዎን፣ ኤዊዎን የከነዓን ልጆች ናቸው፡፡ የአብርሃም ዕቅብት ኬጡራ ምድያምን ወለደች፡፡ አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ ሕዝቅያስ፣ ምናሴ፣ አሞጽ፣ ኢዮስያስ፣ ኢዮአቄም፣ ኢኮንያን፣ ፈዳያ፣ ዘሩባቤል፡፡ ፈዳያ ዘሩባቤልን ወለደ፡፡ የዕሴይ ልጆች ኤልያብ፣ አሚናዳብ፣ ሳማን፣ ናትናኤል፣ ራዳይ፣ አሶን፣ ዳዊት ናቸው፡፡ ሴት ልጆቹ ደግሞ ሶርህያ እና አቢግያ ናቸው፡፡ የሶርህያ ልጆች አቢሳ፣ ኢዮአብ፣ አሣሄል ነበሩ፡፡ አቢግያ አሜሳይን ወለደች፡፡

ካህናት፣ አገልግሎት

1ኛ ዜና.6፣32 ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤት በኢየሩሳሌም እስኪሠራ ድረስ በምስክሩ ድንኳን ማደሪያ ፊት በበገና እያዜሙ ያገለግሉ ነበር፡፡ በየተራቸውም ለአገልግሎታቸው ይቆሙ

ነበር። አገልጋዮችም እኒህ ነበሩ ከቀዓት ልጆች ዘማሪው ኤማን ነበር። በቀኙም የሚቆም ወንድሙ አሳፍ ነበር። በግራቸው የሚቆሙት የሜራሪ ልጆች ነበሩ። 2ኛ ዜና.8፣14 የእግዚአብሔርም ሰው ዳዊት እንዲህ አዝዞ ነበርና ካህናቱን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት ሥርዓት በየአገልግሎታቸው ሰሞን ከፈላቸው። ሌዋውያንንም እንደ ሥርዓታቸው ያመሰግኑ ዘንድ በካህናቱም ፊት ያገለግሉ ዘንድ በየሰሞናቸው ከፈላቸው። 2ኛ ዜና.23፣6 ወደ እግዚአብሔር ቤት ግን ከካህናትና ከሌዋውያን አገልጋዮች በቀር ማንም አይግባ እነርሱ ቅዱሳን ናቸውና ይግቡ።

መጽሐፍ

1ኛ ዜና.9፣1 እስራኤልም ሁሉ ስለኃጢአታቸው ወደ ባቢሎን ከተማረኩ በኋላ በየትውልዳቸው ተቆጠሩ። እነሆም በእስራኤልና በይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል። 2ኛ ዜና.20፣34 የቀረውም የፊተኞቹና የኋለኞቹ የኢዮሳፍጥ ነገሮች እነሆ የእስራኤልን ነገሥታት ታሪክ በጻፈው በአናኒ ልጅ በነቢዩ በኢዩ ታሪክ ተጽፏል።

ደብተራ፣ ቤተ መቅደስ

1ኛ ዜና.15፣1 ዳዊትም በከተማው ለራሱ ቤቶችን ሠራ ለእግዚአብሔርም ታቦት ስፍራ አዘጋጀ ድንኳንም ተከለላት። 1ኛ ዜና.15፣23 በራክያና ሕልቃናም ለታቦቷ በረኞች ነበሩ። ዘካርያስ አልዓዛርም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት መለከት ይነፉ ነበር። ያመሰግኑትና ያከብሩትም ዘንድ ከሌዋውያን ወገን አቆመ አለቃውም አሳፍ ነበር። 2ኛ ዜና.3፣1 ሰሎሞንም በዓውደ ኦርና የእግዚአብሔርን ቤት መስራት ጀመረ። 2ኛ ዜና.6፣40 አሁንም አምላኬ ሆይ በዚህ ስፍራ ወደሚሆነው ጸሎት ዓይኖችህ የተገለጡ ጆሮዎችህም የሚያደምጡ ይሁን። 2ኛ ዜና.7፣5 በዚያችም ዕለት ንጉሥ ሰሎሞን 22000 በሬዎችንና 120000 በጎችን ሰዋ። እንዲሁም ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤተ ቅዳሴ አከበሩ። 2ኛ ዜና.7 አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ ጆሮዎቼም ያዳመረጣሉ። አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ። እናንተ ግን ብትመለሱ የሰጠኋችሁን ሥርዓቴንና ትእዛዜን ብትተው ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ብታመልኩ ብትሰግዱላቸውም እኔም ለአባቶቻችሁ ከሰጠኋቸው ምድር እነቅላችኋለሁ። ለስሜም የቀደስሁትን ይህን ቤት ከፊቴ እጥለዋለሁ በአሕዛብም ሁሉ መካከል ምሳሌና ተረት አደርገዋለሁ።

መዝሙር፣ መዘምራን፣ ቅኔ፣ ግጥም

1ኛ ዜና.15፣19 መዘምራንም ኤማንና አሳፍ ኤታንም በናስ ጸናጽል ከፍ አድርገው ያሰሙ ነበር። በመሰንቆ በልዑል ቃል ያዜሙ ነበር።ስምንት አውታር ባለው በገና ይዘምሩ ነበር። የሌዋውያንንም አለቃ ኮንንያስ በዜማ ላይ ተሾሞ ነበር ብልሃተኛ ነበርና። 2ኛ ዜና.5፣12 መዘምራንም የነበሩት ሌዋውያን ሁሉ ጥሩ በፍታ ለብሰው ጸናጽልና ከበሮ መሰንቆም እየመቱ በመሠዊያው አጠገብ ቆመው ነበር። ከእነርሱም ጋር 120 ካህናት መለከት ይነፉ ነበር።

መለከቱንም የሚነፉ መዘምራኑ በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ‹‹እግዚአብሔር ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግነው›› እያሉ በአንድ ቃል ድምጻቸውን ወደላይ ከፍ አድርገው በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ የእግዚአብሔር የክብሩ ደመና የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው። 2ኛ ዜና.7፣5 ካህናቱም በየሥርዓታቸው ሌዋውያኑም ደግሞ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚለውን የዳዊትን መዝሙር እየዘመሩ ቆመው ነበር።እስራኤልም ሁሉ ቆመው ነበር። 2ኛ ዜና.20፣22 ዝማሬውንና ምስጋናውንም በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞዓብ ልጆች በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ኃይልን ሰጣቸው። 2ኛ ዜና.23፣13 መዘምራንም በዜማ ዕቃ እያዜሙ የምስጋና መዝሙር ይዘምሩ ነበር። 2ኛ ዜና.35፣25 ኤርምያስም ለንጉሡ ለኢዮስያስ የልቅሶ ግጥም ገጠመለት።ይህም በእስራኤል ሁሉ ዘንድ ወግ ሆኖ በልቅሶ ግጥም ተጽፏል።

መሥዋዕት፣ ቁርባን፣ በዓል

1ኛ ዜና.21፣15 የእግዚአብሔርም መልአክ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር። ዳዊትም ዓይኖቹን አነሳ። የእግዚአብሔርም መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ አየ። ዳዊትም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱንም መሥዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርንም ጠራ። እግዚአብሔርም መልአኩን አዘዘው ሰይፉንም በአፎቱ ከተተው። 2ኛ ዜና.8፣13 ሙሴም እንዳዘዘ እንደ ሥርዓታቸው በየቀኑ ሁሉ በየሰንበታቱም በየመባቻዎቹም በየበዓላቱም በየዓመቱ ሦስት ጊዜ በየቂጣው በዓልና በየሰባቱ ሱባኤ በዓል በየዳሱም በዓል ቁርባን ያቀርቡ ነበር። 2ኛ ዜና.35፣1 ኢዮስያስም ለአምላኩ ለእግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ፋሲካ አደረገ።

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር

2ኛ ዜና.1፣1 የዳዊት ልጅ ሰሎሞንም በመንግሥቱ በረታ።አምላኩም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር። እጅግም አከበረው አገነነውም። 2ኛ ዜና.20፣6 አቤቱ የአባቶቻችን አምላክ ሆይ ኃይልና ችሎታ በእጅህ ነው። 2ኛ ዜና.20፣15 ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና ከዚህ ታላቅ ወገን የተነሳ አትፍሩ አትደንግጡም እናንተ የምትዋጉ አይደላችሁም ተሰለፉ ዝም ብላችሁ ቁሙ። የሚሆነውንም የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ። እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ነውና አትፍሩ አትደንግጡም።

ጸጋ፣ ቸርነት

2ኛ ዜና.1፣7 እግዚአብሔር ሰሎሞንን የምሰጥህን ከእኔ ለምን አለው።ሰሎሞንም እግዚአብሔርን አለው። አሁንም በዚህ ፊት እወጣና እገባ ዘንድ ጥበብንና ማስተዋልን ስጠኝ እግዚአብሔርም ጥበብና ማስተዋልን እሠጥሀለሁ አለው። 2ኛ ዜና.7፣10 እግዚአብሔር ለዳዊትና ለሰሎሞን ለሕዝቡም ለእስራኤል ስላደረገው ቸርነት በልባቸው ደስ ብሏቸው ሄዱ። እግዚአብሔርም ለሰሎሞን በሌሊት ተገልጦ እንዲህ አለው ጸሎትህን ሰምቻለሁ ይህንንም

ስፍራ ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ። ዝናም እንዳይወርድ ሰማያቱን ብዘጋ ወይም የሚያፈራውን እንጨት ሁሉ ይበላ ዘንድ አንበጣን ባዝዘው ወይም በሕዝቤ ላይ ቸነፈር ብሰድ በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ በፊቴም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ። ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።

አንድምታ

ይህ በግሪኩ የለም ይህ በዕብራይስጡ የለም የሚለው በአውድ ሲተረጎም የሚጨምርና የሚቀንስ ስላለ ነው። ሌላው ከአንዱ ቅጅ ወደ ሌላ ቅጅ ሲል ብዙ ልዩነቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ለምሳሌ አንዱ ቅጅ 5 ያለውን አንዱ 50 አንዱ 13 ሊለው ይችላል። ሲገለባበጥ ብዙ ልዩነቶች ይፈጠራሉ። ይኸውም ከገልባጩ ችግር ሊፈጠር ይችላል። የአብነት ልዩነቶች መፈጠራቸውም በዚህ በቅጂ ልዩነት ይመስላል። 2ኛ ዜና.22፣2 አካዝያስም መንገሥ በጀመረ ጊዜ እድሜው 22 ዓመት ነበረ (ዕብራይስጡ 42 ዓመት ይላል)። ይህ ዓይነት የቁጥር ልዩነት ሲገለባበጥ የሚፈጠር ስህተት ይሆናል ወይንም የአቆጣጠር ልዩነትም ሊሆን ይችላል። የቃላትም ልዩነት በዚህ መልኩ ሊፈጠር ይችላል። አንዱ ነው ያለውን አንዱ አይደለም ሊለው ይችላል። ስለዚህ ጠቅላላ ዓውዱን ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ያለውን እውነት እያስተያዩ ማመሳከር ይገባል። ቢቻል እናት መዝገቡን ወይም ቀደም ብለው የታተሙ ቅጅዎችን ማግኘት ጥሩ ነው።

ንሥሓ፣ ጸም

2ኛ ዜና.6፣37 በተማረኩበትም ሀገር ሆነው በልባቸው ንሥሓ ቢገቡ በምርኳቸውም ሀገር ሳሉ ተመልሰው ኃጢአት ሠርተናል በድለንማል ክፉም አድርገናል ብለው ቢለምኑህ ጸሎታቸውን ስማ ፍርድንም አድርግላቸው አንተም የበደሉህን ሕዝብ ይቅር በል። 2ኛ ዜና.20፣3 ኢዮሳፍጥም ፈራ እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና በይሁዳም ሁሉ ጾም አወጀ። 2ኛ ዜና.33፣12 ምናሴም ተማርኮ በተጨነቀ ጊዜ አምላኩን እግዚአብሔርን ፈለገ።በአባቶችም አምላክ ፊት ሰውነቱን እጅግ አዋረደ ከንቱውን ስመለከት የማይጠቅመኝንም ነገር ሳበዛ በፊትህ ክፉ ስራ ሠርቻለሁና። አሁንም ቸርነትህን እየለመንሁ በልቤ ጉልበት እሰግዳለሁ አቤቱ ጌታየ ፈጽሜ በደልሁ ኃጢአቴንም አምናለሁ ይቅር በለኝ አቤቱ ይቅር በለኝ ለኃጢአቴም አሳልፈህ አትስጠኝ ብሎ ጸለየ። መዳን የማይገባኝ ሲሆን በይቅርታህ ብዛት አዳንከኝ በየጊዜውና በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አመሰግንሀለሁ እግዚአብሔርም ልመናውን ተቀበለው። ምናሴም የጣዖት መሠዊያዎችን ሁሉ ከከተማይቱ በስተውጭ ጣላቸው የእግዚአብሔርንም መሠዊያ ደግሞ አደሰ።

ንግሥና፣ ንግሥት ሳባ

2ኛ ዜና.8፣10 የንጉሡ የሰሎሞን ዓይነተኞች አለቆች 250 ነበሩ። 2ኛ ዜና.9፣1 የሳባም ንግሥት የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በግመሎች ላይ ሽቱና ብዙ ወርቅ የከበረም ዕንቁ

አስጭና ከታላቅ ኀዘ ጋር ሰሎሞንን በኢየሩሳሌም በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። የዓረብ ነገሥታት ሁሉ ወርቅና ብር ያመጡ ነበር።

ምቀኝነት፣ ባዕድ አምልኮ

2ኛ ዜና.21፣13 ከአንተም የሚሻሉትን የአባትህን ቤት ወንድም ገድለሀልና እነሆ እግዚአብሔር ሕዝብህንና ልጆችህን ሚስቶችህንም ያለህንም ንብረት ሁሉ በታላቅ መቅሰፍት ይቀስፋል። ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር መድኃኒት በማይገኝለት ደዌ አንጀቱን ቀሰፈው። 2ኛ ዜና.33፣4 እግዚአብሔርም ስሜ በኢየሩሳሌም ለዘላለም ይኖራል ባለው በእግዚአብሔር ቤት የጣዖት መሠዊያዎችን ሠራ።

መጽሐፈ ዕዝራ

ጾም፣ ጸሎት

ዕዝ.8፣23 ስለዝህም ነገር ጾምን ወደ እግዚአብሔርም ለመንን እርሱም ሰማን። ነህ.1፣3 የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሷል በሮቿም በእሳት ተቃጥለዋል አሉኝ። ይህንንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ። አያሌ ቀንም አዝን ነበር። በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር። ዕዝ.ሱቱ.3፣13 ዛሬ እንደጾምህ ዳግመኛ ሰባት ቀን ብትጸልይና ብታለቅስ ከዚህ የሚበልጥ ትሰማለህ። ዕዝ.ሱቱ.3፣20 እኔም መልአኩ ዑርኤል እንዳዘዘኝ አዝኜ እያለቀስሁ ሰባት ቀን ጾምሁ። ከሰባት ቀን በኋላም የልቡናዬ ሀሳብ እጅግ አደከመኝ የጥበብም መንፈስ ሰውነቴን አነሳሳቻት። ዕዝ.ሱቱ.4፣31 ዳግመኛ ሰባት ቀን ብትጾምና ብትጸልይ ከዚህ የሚበልጥ ዳግማኛ እነግርሀለሁ። ዕዝ.ሱቱ.8፣24 ግንብ ወደ አልተሰራበት ምድረ በዳ ብትሄድና ከእንጨት ፍሬ ብቻ ብትበላ ሥጋም ባትበላ ከእንጨት ፍሬ ብቻ በቀርም ወይን ባትጠጣ ወደ ልዑል ሁልጊዜ ብትጸልይ መጥቼ እነግርሀለሁ።

ረድኤተ እግዚአብሔር

ዕዝ.8፣31 የአምላካችንም እጅ በላያችን ነበረ። በመንገድም ከጠላትና ከሚሸምቅ ሰው እጅ አዳነን ወደ ኢየሩሳሌምም ደረስን። ዕዝ.9፣9 አምላካችን ግን በባርነታችን አልተወንም። ነህ.2.18 ተነሱ እንስራ የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ንጹሓን ባርያዎቹ ተነስተን እንሰራለን። ዕዝ.ካል.4፣59 ድል መንሳት ከአንተ ዘንድ ነው።ጥበብም ከአንተ ዘንድ ነው። ክብርም ከአንተ ዘንድ ነው።

ቃል ኪዳን

ነህ.1፣5 አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትዕዛዝህን ለሚያደርጉ ቃልኪዳንና ምሕረትን የምትጠብቅ አምላክ ሆይ። ነህ.2፣5 ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ።

መጽሐፍ፣ ትምህርት

ነህ.8፣8 የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ፡፡ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፡፡ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር፡፡ ዕዝ.ሱቱ.4፣20 በሰማይ መጻሕፍት ይገለጣሉ፡፡ ዕዝ.ሱቱ.13፣24 አንተ ግን ብዙ ብራና አዘጋጅ ነገ በዚህ ሰዓት ትጽፍ ዘንድ ትጀምራለህ፡፡ ዕዝ.ካል.8፣3 ይህም ዕዝራ ከባቢሎን መጣ፡፡እርሱም የእስራኤል አምላክ የሰጠውን የሙሴን ኦሪት ሁሉ ያውቅ ነበር፡፡ እርሱም ጸሐፊ ነበር፡፡ ዕዝራም ብዙ ትምህርት የሚያውቅ ነበረ፡፡ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ከእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዝ የሚጎድለው አልነበረም፡፡ ዕዝ.ካል.8፣23 የእግዚአብሔርን ሕግ የማያውቁትንም አስተምሯቸው፡፡

ንሥሐ፣ ሞት፣ ምናኔ

ነህ.9፣2 ቆመውም ኃጢአታቸውን የአባቶቻቸውንም ኃጢአት ተናዘዙ፡፡ ዕዝ.ሱቱ.6፣9 የሞትስ ነገር እንዲህ ነው፡፡ ከልዑል ዘንድ የትዕዛዝ ቃል ከወጣ በኋላ እገሌ ይሙት ባለጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች፡፡ ለልዑል ጌትነትም አስቀድማ ትሰግዳለች፡፡ ዕዝ.ሱቱ.6፣48 ሁላችንም የምንኖረው ሕይወት ምን ይጠቅመናል? በጎዘን እንኖራለንና ከሞትንም በኋላ ዳግመኛ ፍርድ ይቆየናልና፡፡ አዳም ሆይ ምን አደረግንህ አንተ ባትበድል ይህች መከራ በእኛ ላይ ባልመጣችብን ነበር፡፡

እግዚአብሔር፣ ዕውቀት፣ በእንተ ክርስቶስ

ነህ.9፣6 አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ፡፡ ዕዝ.ሱቱ.1፣8 አሕዛብም ሁሉ በየሥራቸው ኖሩ፡፡ በፊትህም በደሉ አንተንም ካዱ አንተ ግን አልከለከልሃቸውም፡፡ ዕዝ.ሱቱ.2፣11 የምትፈርስና የምትበሰብስ አንተ የማይበሰብስ የልዑልን መንገድ ማወቅ አትችልም፡፡ በምድር የሚኖሩ ሰዎች በምድር ያለውን ማወቅ ይችላሉ እንጂ በሰማያትና ከሰማያት በላይ ያለውን አይደለም፡፡ (ፍጡር ፈጣሪን በእምነት ካልሆነ በቀር እንደፈጠረው በምንም ሊያውቅ አይችልም፡፡ ሳይፈጠር ሲፈጠር ምን ይመስል ነበር የሚለውን የሚያውቅ የለምና፡፡ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው)፡፡ ዕዝ.ሱቱ.2፣52 ኢይሩማኤል ‹‹ስለጠየቅኸኝ ምልክትስ ከብዙ በጥቂቱ መንገር ይቻለኛል፡፡ ስለ ሕይወትህ ግን እነግርህ ዘንድ አልተላክሁም እኔም አላውቀውም፡፡ ዕዝ.ሱቱ.3፣33 ከፈጣሪው ይልቅ እስራኤልን አንተ እጅግ ትወደዋለህን? እኔም አቤቱ አይደለም አልኩት፡፡ ዕዝ.ሱቱ.3፣48 እኔም ለፈጠርሁት ዓለም በየጊዜው ሥርዓት ሠራሁለት፡፡ ዕዝ.ሱቱ.4፣55 አቤቱ ይህንን ዓለም ስለ እናንተ ፈጠርሁት ብለሀልና፡፡ ዕዝ.ሱቱ.5፣19 አንተ በፍርድ ከአንዱ ከእግዚአብሔር የምትሻል አይደለህም፡፡ ከልዑልም አንተ የምትራቀቅ አይደለኽም፡፡ እግዚአብሔር ሕጉን ሰርተው በሕይወት እንዲኖሩ አዝሏቸዋልና ሕጉን ቢጠብቁ ግን ባልተፈረደባቸውም ነበር፡፡ ዕዝ.ሱቱ.10፣37 እነሆ አንበሳ እያገሣ ከዱር ተነሳ፡፡

ምረቃ፣ በዓል፣ ካህናት፣ ምስጋና

ነህ.12፣27 የኢየሩሳሌምም ቅጥር በተመረቀ ጊዜ ምረቃውን በደስታና በምስጋና በመዝሙርምበጸናጽልም በበገናም በመሰንቆም ለማድረግ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጧቸው ዘንድ

ሌዋውያኑን በየሰፈራቸው ሁሉ ፈለጉ። የመዘምራኑም ልጆች ከኢየሩሳሌም ዙሪያና ከሌሎችም መንደሮች ተሰበሰቡ። እስራኤልም ሁሉ በዘሩባቤልና በነህምያ ዘመን ለመዘምራኑና ለበረኞቹ ፈንታቸውን በየዕለቱ ይሰጡ ነበር። የተቀደሰውንም ነገር ለሌዋውያን ሰጡ። ዕዝ.ሱቱ.9፣8 እኛ ስለብዙዎች እናዝናለን አንቺ ግን ስለ አንዱ ልጅሽ ታዝኛለሽ። አሁንም ይህንን ኀዘንሽን ከአንቺ አርቂ። ዕዝ.ሱቱ.9፣16 እግዚአብሔርን ብታመሰግኚው ይረዳሻልና። ልጅሽንም በጊዜው ታገኝዋለሽ። ዕዝ.ካል.1፣15 መዘምራኑ የአሳፍ ልጆችም ዳዊት በሰራው ሥርዓት በሹመታቸው ነበሩ። ከሰሞኑም የሚያጓድል አልነበረም።

ክፉ ልብ፣ ሀሳብ

ዕዝ.ሱቱ.1፣19 ቀዳማዊ አዳም ክፉ ልብን ገንዘብ አድርጎ ነበርና ድል ተነሳ። እርሱ ብቻ አይደለም። ከእርሱ የተወለዱ ልጆችም ሁሉ እንጂ። ዕዝ.ሱቱ.13፣14 መዋቲ አሳብን እንግዲህ ተወው የማይሞተውንም ልበስ።

ጻድቃን፣ መልአክ

ዕዝ.ሱቱ. 2፣27 ዓለም የጻድቃንን ተስፋ ማስቀረት አይችልምና ይህ ዓለም ጭንቀትን የተመላ ነው ደዌንም የተሞላ ነውና። ዕዝ.ሱቱ.3፣15 ወደ እኔ የመጣውና የተናገረኝ መልአኩም እጄን ያዘኝ በእግርም አቁሞ አጸናኝ። ዕዝ.ሱቱ.5፣18 ጻድቃን ሰፊውን ተስፋ እያደረጉ ጠባቡን ይታገሡታልና። ጠባቡን የሚታመኑ ኃጥዓን ግን ሰፊውን አያገኙትም።ዕዝ.ሱቱ.5፣45 አቤቱ ትዕዛዝህን ጠብቀው የኖሩ ብጹዓን ናቸው። አሁንም በሚመጣው ዓለም ደስ ታሰኛቸው ዘንድ ጻድቃን ጥቂት እንደሆኑ አያለሁ። ዕዝ.ካል.1፣23 የኢዮስያስም ስራው እግዚአብሔርን መፍራት በተመላበት ልቡና በፈጣሪው ፊት የቀና ነበር።

ፍጥረት

ዕዝ.ሱቱ.2፣36 መልአኩ ኢይሩማኤልም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው እንደ እናንተ ያሉ ጻድቃን ቁጥራቸው በተፈጸመ ጊዜ ነው።ይህ ዓለም በሚዛን ተመዝኗልና። ባሕሩንም በመስፈሪያ ሰፍሮታልና የተሰጠውም መስፈርት እስኪፈጸም ድረስ ዝም ይላል አይነቃምም። ዕዝ.ሱቱ.4፣49 ያንጊዜም የፈጠርሀቸውን ሁለቱን እንስሳት ጠበቅህ የአንዱን ስሙን ብሔሞት አልከው። የሁለተኛውንም ስሙን ሌዋታን አልከው።

የዓለም ፍጻሜ ምልክት፣ ምጽአት

ዕዝ.ሱቱ.3፣1 ምልክቱም እነሆ ወራት ይመጣል። የጽድቅ መንገድም ትሰወራለች። ሃይማኖትም ከሀገር ትጠፋለች። በደልም አንተ ካየኸውና ከሰማኸው ይልቅ ይበዛል። ፀሐይም ድንገት በሌሊት ያበራል። ጨረቃም በድንገት በቀን ያበራል። ከእንጨቶች ደም ይፈስሳል። ድንጋይም ትጮሀለች ሕዝቡም ይታወካሉ። ከዋክብትም ይረግፋሉ ብዙዎች ያልጠረጠሩት ይነግሣል። ሁሉም ቃሉን ይሰማል። በብዙ ሀገሮች ሽብር ይሆናል። ጥቅል እሳትም ይላካል። የምድረ በዳ አውሬዎች ከቦታቸው ይፈልሳሉ ወዳጆችም እንደጠላት በድንገት እርስ በእርሳቸው

ይጋደላሉ። ዕዝ.ሱቱ.4፣26 ያንጊዜም ያረጉና ከተወለዱ ጀምሮ ሞትን ያልቀመሱ እነዚያን ሰዎች ያዩዋቸዋል። ዕዝ.ሱቱ.5፣31 የመዋቲ ሰው ዓለምም ያልፋል። ምድርም የተቀበሩባትን ሰዎች ትመልሳለች መሬትም በውስጡ ያረፉትን ሰዎች ይመልሳል። ሰውን ስራው ይከተለዋል። የቁርጥ ፍርድ ይከፈታል። በወዲህ ደስታና ዕረፍት በወዲያም ፍርድና እሳት አለ። የፍርድ ቀንስ እንዲህ ናት። ፀሐይ ጨረቃም ከዋክብትም የሏትም። ደመናም መብረቅም ነጎድጓድም ነፋስም ውሃም ሰማይም ጨላምም ሌሊትም መዓልትም የሏትም። ክረምት በጋም መከርም ብርድም ሐሩርም ጥቅል ነፋስም። በረድ፣ ውርጭ፣ ጉም፣ ዝናም፣ ጠል የለባትም። ማታና ጠዋት ብርሃንና ብልጭልጭታ ፋናና መብራት የለም። ከእግዚአብሔር ከጌትነቱ ብርሃን ብቻ በቀር ይህ ሁሉ የለም። ዕዝ.ሱቱ.6፣44 የፍርድ ቀንስ የዚህ ዓለም መጨረሻ ናት። ለሚመጣውም መጀመሪያ ናት። ዕዝ.ሱቱ. 13፣35 ከሞት በኋላ ፍርድ ይመጣልና ያን ጊዜም የጻድቃን ስማቸው ይገለጣል የኃጥዓንም ስራቸው ይገለጣል።

ምሳሌ፣ ምርምር

ዕዝ.ሱቱ.4፣8 ያዕቆብ የኤሳውን ተረከዝ ይዞ ተወለደ። ኤሳው የዚህ ዘመን ፍጻሜ ምሳሌ ነው። ያዕቆብ የአዲሱ ዘመን መጀመሪያ ነው። ነገር ግን ዕዝራ አትመራመር። ዕዝ.ሱቱ.9፣45 ሠላሳ ዘመን መካን ሆንኩ ያለችህም ይህ ነው። የሚያቆርቡት መሥዋዕት ሳይኖር ዓለም ሦስት ሺ ዘመን ኖሯልና።

ትዕግስት፣ ማሸነፍ፣ ይቅርታ

ዕዝ.ሱቱ.6፣56 ትዕግስትን ያጸኗት ፊታቸው ያበራል። ዕዝ.ሱቱ.6፣59 ድል ያደረገ እኔ ያልሁትን ያገኛል። ድል የተነሳ ግን አንተ ያልከውን ያገኛል። ዕዝ.ሱቱ.7፣32 በጎ ስራ የሌለን እኛን ይቅር ብትለን ያን ጊዜ ይቅር ባይ ትባላለህ። በአንተ የተዘጋጀ በጎ ሥራ ያላቸው ጻድቃንን ግን በሥራቸው ይቅር ትላቸዋለህ። ዕዝ.ሱቱ.9፣8 ስለአገኘሽ ቅጣትና መከራም ትዕግስተኛ ሁኚ። ዕዝ.ካል.3፣10 ሦስቱ የፋርስ ሹሞች ለዳርዮስ አንደኛው ወይን ያሸንፋል ብሎ ጻፈ። ሁለተኛው ንጉሥ ያሸንፋል ብሎ ጻፈ።ሦስተኛው ሴቶች ያሸንፋሉ ከሁሉም ይልቅ እውነት ታሸንፋለች ብሎ ጻፈ። ዕዝ.ካል.8፣53 ዳግመኛም ስለዚህ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ለመንን እርሱም ይቅር አለን።

ጽዋዓ ልቡና

ዕዝ.ሱቱ.13፣38 ዕዝራ ዕዝራ ብሎ ጠርቶ እንዲህ አለኝ። አፍህን ክፈት እኔም የማጠጣህን ጠጣ አፌንም በከፈትሁ ጊዜ ውሃ የተመላ መልኩ እሳት የሚመስል መጠጥን አጠጣኝ። ተቀብየም ጠጣሁት። ልቡናየም ፈጽሞ ዕውቀትን ተናገረ። 24 መጻሕፍትም ተጻፉ።

ጽድቅ

ዕዝ.ካል.4፣36 ከእውነት ጋር ዓመፃ አይገኝም። እውነት ግን ሁልጊዜ ታሸንፋለች ሕይወትም ናት። ለዘላለሙም ፈጽማ ጸንታ ትኖራለች። በእርሷ ዘንድ ልዩነትና ለፊት ማዳላት የሉም።

በፍርዲም ዓመፅ የለባትም። እርሷም ታሸንፋለች።

መጽሐፈ መቃብያን

1ኛ መቃ.2፣1 ከነገደ ብንያም ስሙ መቃቢስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ።መልከ መልካምና እጅግ ብርቱዎች የሆኑ ሦስት ልጆች ነበሩት።

ትምክህት፣ ትዕቢት

1ኛ መቃ.1፣1 ስሙ ጲሩጻይዳን የሚባል ክፋትንም የሚወዳት አንድ ሰው ነበር። በፈረሶቹ ብዛትና ከሥልጣኑ በታች ባሉ በጭፍራዎቹ ጽናት ይመካ ነበር። ያ ጲሩጻይዳን ግን ትዕቢተኛ ነበረ። 1ኛ መቃ.12፣18 እኔም ጌታዋ እንደሆንሁ በእኔ ትመካለች እንጂ ጌታዋ እንደመሆኔ የምትፈራኝ ፈቃዴንም የምታደርግ አይደለችም። 1ኛ መቃ.13፣12 በጠዋት የሚወጣ የአጥቢያ ኮከብ ከሰማይ ለምን ወደቀ? በትዕቢቱና በትምክህቱ ዙፋኔን በሰማያትና በከዋክብት ላይ እዘረጋለሁ እንደልዑልም እሆናለሁ ብሏልና እንደ አንተም ካሉ መላእክት ሁሉ በትዕቢትህ ተዋረድህ። 2ኛ መቃ.9፣1 እግዚአብሔር ያይደለህ አንተ ደካማ ሰው ሆይ ለምን ትኮራለህ ዛሬ ሰው ነህ ነገም መሬትና አመድ ነህ በመቃብርህም ትልና ብስባሽ ትሆናለህ።

ባዕድ አምልኮ፣ ጥንቆላ፣ ሟርት

1ኛ መቃ.1፣2 በመዓልትና በሌሊት መሥዋዕት የሚሠዋላቸው ብዙ ጣዖታት ነበሩት። እርሱ ግን በልቡናው ድንቁርና እነርሱ ኃይልንና ብርታትን የሚሰጡት ይመስለው ነበር። በልቡም በግዛቱ ሁሉ እነርሱ ሥልጣንን የሚሰጡት ይመስለው ነበር። ጣዖታትን የሚያገለግሉ ካህናትን ሾመ። ከዚያች ከረከሰች መሥዋዕት እነርሱ እየበሉ ቀንና ሌሊት ጣዖቶቹ የሚበሉ አስመስለው ይነግሩት ነበር። በልቡ ድንቁርናና በእውቀቱ ማነስ እነርሱ የፈጠሩት እነርሱም የሚመግቡትና የሚያነግሡት ይመስለው ነበር። የሚያስታቸው የሰይጣን መንፈስ በዚያ በጣዖቱ ምስል ያድራልና።የልቡናቸውንም ፈቃድ ይነግራቸዋልና እንደወደዱም ይገለጥላቸዋልና። 1ኛ መቃ.4፣22 እነርሱ ግን አይገድሉም አያድኑምም መልካም አያደርጉም ክፉም አያደርጉም አያዋርዱም አያከብሩምም አያደኸዩም ባለጸጋም አያደርጉም አይነቅሉምም አይተክሉምም ነገር ግን ዕውራነ ልብን እንዳይድን በአጋንንት መንፈስ ያስታሉ። 1ኛ መቃ.24፣5 ከጣዖትና ከጥንቆላ ከሟርትም ራሳችሁን አድኑ። በእነዚህ ይህን በሚያደርጉና በሚሰሟቸውም ላይ ፈቃዳቸውን በሚያደርጉና ወዳጅም በሚሆኗቸው ላይ በትዕዛዛቸውም በሚሄዱ ላይ የእግዚአብሔር መቅሰፍት ይመጣባቸዋል።

ሰማእትነት

1ኛ መቃ.2፣24 እኛ ግን ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለንም። ስለቅዱስ ስምህ ሰውነታችንን ለሞት እንሰጥ ዘንድ ብርታትና መጠጊያም ሁነን። 1ኛ መቃ.3፣1 የልዑል እግዚአብሔር ባሮች አብያ፣ ሲላ፣ ፈንቶስ ሞተው የተነሱ እነዚህን በፊታችሁ እንዳያችሁ ከሞታችሁ በኋላ እንደዚሁ ትነሡ ዘንድ አላችሁ። ፊታችሁም በመንግሥተ ሰማይ ይበራል። ከእነዚያ ሰዎችም

ጋራ ሂዱ በዚያም ሰማዕትነትን ተቀበሉ። 1ኛ መቃ.2፣27 መልካቸው ፈጽሞ ያማረ ሁለትም ሰዎች በፊታቸው ቆመው በታዩአቸው ጊዜ እንደመብረቅ የሚያስፈሩ የእሳት ሰይፎች ወርደው ያን ጊዜ አንገታቸውን ቆርጠው ገደሏቸው። ያን ጊዜም እንደቀደመው ሕያዋን ሆነው ተነሱ። የመልካቸው ደም ግባት ፈጽሞ ያማረ ሆነ። ከፀሐይም ይልቅ አበሩ። ከቀደመውም ይልቅ ያማሩ ሆኑ።1ኛ መቃ.3፣21 ቅጣታችንን በምታበዛብን መጠን ዋጋችን ይበዛል። 1ኛ መቃ.3፣29 ለሰማእትነት ከቆምን በኋላ እንሸሽ ዘንድ አግባብ አይደለም። እነዚያም ቅዱሳን ወደ እሳቱ በገቡ ጊዜ ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ። መላእክትም ነፍሳቸውን አብርሃምና ይስሐቅ ያዕቆብም ወደ አሉበት ደስታ ወደሚገኝበት ወደገነት ወሰዷቸው።

ፍርድ

1ኛ መቃ.4፣15 ክፉ ነገርን ስላደረግህብን ፈንታ ክፉ ነገርን አንከፍልህም። ፍዳን የሚከፍል እግዚአብሔር ነውና። 1ኛ መቃ.7፣6 እግዚአብሔር እንደሾመህ በሚገባና በእውነት ፍረድ እንጂ ለታላቅና ለታናሽ ፊት አታድላ ያለእርሱ ማንን ትፈራለህ? መንገዱንና ትዕዛዙን ጠብቅ። 1ኛ መቃ.18፣1 ወደ እግዚአብሔር እንደምትሄድ አስብ። ሁሉም በእጁ አለ። አንተ በሰራኸው ስራ ይፈርድብህ ዘንድ በፊቱ ትቆማለህ።

እግዚአብሔር፣ ፈሪህ እግዚአብሔር

1ኛ መቃ.5፣17 እግዚአብሔር ሳያውቀው የሚደረግ ነገር የለም። 1ኛ መቃ.5፣33 እርሱን የሚገዛው የለም እርሱ ግን ሁሉን ይገዛል። እርሱን የሚሾመው የለም እርሱ ግን ሁሉን ይሾማል። እርሱን የሚሽረው የለም እርሱ ግን ሁሉን ይሽራል። የሰማይና የምድር ስልጣን የእርሱ ነውና ከእጁ የሚያመልጥ የለም። በእርሱ ዘንድ ሁሉ የተገለጠ ነው እንጂ ከዓይኑ የተሠወረ የለም። ሁሉንም ያያል እርሱን ግን የሚያየው የለም። ወደእርሱ የሚጸልየውን ጸሎቱን ይሰማዋል ከማይጎድል መዝገቡም ሁሉን ይመግባል ለዘላለም የሚኖር ንጉሥ ነውና። 1ኛ መቃ.6፣17 የሁሉ ነፍስ በእጁ ነው። የሁሉም ሕይወት በአፉ ነው። ለሚያከብሩት ሰዎች ክብርን የሚሰጣቸው እርሱ ነው። ሁሉን የሚችል ነው። ወደእርሱም በንጹሕ ልቡ የጸለየውን የጸሎቱን ዋጋ ይሰጠዋል። በባልቴቶችና በሙት ልጅ ክፉ የሚሰሩ የጎይለኞችን ትዕቢት ያጠፋል። 1ኛ መቃ.6፣32 ሳሙኤልም ቃሉን ለመለወጥ እንቢ አለ። የፈጣሪውን እግዚአብሔርን ቃል ፈርቷልና። የሚሞት ንጉሥን ግን አልፈራውምና። 1ኛ መቃ.6፣34 እርሱ ሁሉን የሚያዝዝ ንጉሠ ነገሥት ስለሆነ። የነገሥታቱን የመኳንንቱን ስልጣን ሁሉ የሚሽር እርሱ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ ነውና እርሱን የሚያዘዘው የለም። 1ኛ መቃ.7፣25 የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጥሮታል። የእግዚአብሔር ቃል ሰውን ሁሉ ከመቃብር ያስነሳዋል። 1ኛ መቃ.7፣29 ዳግመኛ የእግዚአብሔርን ፍርድ የማያውቁ ሰዎችን እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው። እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ እወቁ እኔ እገድላለሁ አድናለሁም እቀስፋለሁም ይቅርም እላለሁ ወደሲኦል አወርዳለሁ ከእጄም የሚያመልጥ የለም።ዳግመኛም ወደ ሰማይ አወጣለሁ። ምድራዊ መንግሥት ኃላፊ ነው።ወደዘላለማዊው መንግሥቴ ትገቡ ዘንድ ሕጌንና ሥርዓቴን ጠብቁ። 1ኛ መቃ.13፣8 ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር እኔ እበቀላለሁ ብሏልና። 1ኛ መቃ.26፣3 እግዚአብሔርም እውነትንና ቅንነትን

በሚሰራ ሰው ደስ ይለዋል። 1ኛ መቃ.29፣10 እናንተ አግድም አግድም አትሒዱ እናንተ ቅረቡን እኔም እቀርባችኋለሁ ቀና መንገዶችን እወዳለሁና ይላል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር። 1ኛ መቃ.30፣12 ለባለጠጋውና ለድሃው ምግብ የምመግብ እኔ ነኝ። ሰውን ብቻ አይደለም ነገር ግን ወፎችንና እንስሶችን በባሕር ያሉ ዓሣዎችንና አውሬዎችን እባቦችንም እመግባለሁ። በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ሁሉ በአየር ላይ የሚበረውም ሁሉ የእኔ ነው። 1ኛ መቃ.31፣1 ነገሥታት ያለእኔ ፈቃድ አይነግሡም ጦም አዳሪዎችም ያለ ትዕዛዜ አይደኸዩም ኃይለኞችም ያለትዕዛዜ አይበረቱም። ትዕዛዜን የሚጠብቁ ነገሥታትና መኳንንትንም እወዳቸዋለሁ። እነርሱም ደስ አሰኝተውኛልና በጠላቶቻቸው ላይ ኃይልንና ድልን እሰጣቸዋለሁ። ምድረ ርስትንም እሰጣቸዋለሁ። 1ኛ መቃ.32፣1 እናንተም ነገሥታትና መኳንንት ቃሌን ስሙ ትዕዛዜንም ጠብቁ ይላል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር። 1ኛ መቃ.34፣15 ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰወር የለም። የተገለጠውንም የተሰወረውንም ሁሉ ያውቃል እንጂ። 2ኛ መቃ.13፣5 የእኛ የሰዎች ዘመናችን ምንድን ነው? እንደ ጥላ የሚያልፍ በእሳት ዳርም እንዳለ ሰም አይደለምን አቤቱ አንተ ግን ለዘላለም ትኖራለህ። ዘመንህም የማይፈጸም ነው። ስም አጠራርህም ለልጅ ልጅ ነው። 3ኛ መቃ.8፣6 እመኑት እርሱም መጠጊያ ይሆናችኋል። ጥሩት እርሱም ይቅር ይላችኋል።ለምኑት እርሱም አባት ይሆናችኋል።

መላእክት፣ ጻድቃን

1ኛ መቃ.5፣18 እርሱም ያገለግሉት ዘንድ የከበረ ስሙንም ያመሰግኑት ዘንድ የሰማይ መላእክትን አዘዘ። መላእክትም ሕይወትን ወደሚወርሱ ሰዎች ሁሉ ይላካሉ። መልአኩ ሩፋኤል ወደ ጦቢት ተላከ። ጦብያንም በራጉኤል ሀገር አዳነው። 1ኛ መቃ.13፣15 መላእክት በልብ ትሕትና ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑታል። ከትዕዛዙም አይወጡም የፈጠራቸውና የሠራቸውም እርሱ እንደሆነ አውቀዋልና ከትዕዛዙም እንዳይወጡና እንዳይተላለፉ ሕሊናቸውን ጠበቁ። 2ኛ መቃ9፣25 ጻድቃን እግዚአብሔር ከማይወደው መንገድ ሁሉ ይርቃሉ እርሱም ይወዳቸዋል።

መንግሥተ ሰማያት

1ኛ መቃ.6፣3 በምድር እንዳለ አዳራሽም አይደለም ነገር ግን ፈጽሞ ብሩህ የሆነ በሰማይ ያለ አዳራሽ ነው። የወርቅ የብርና የዕንቍ የሆነ ወለሉም ንጹሕ ነው። ፈጽሞ የሚያበራ መልኩም ከሰው ልቡና የራቀ ነው ንጹሕና ብሩህ ነው። ከእርሱም የሚፈስ የሕይወት ውሃ አለ። የብርሃን ድንኳን አለ። በኤርሞን ሽቱም የተከበበ ነው። በቤቱም ዙሪያ መልኩና መዓዛው ልዩ የሆነ ጣፋጭ የገነት ፍሬ ተተክሏል በዚያም የወይንና የዘይት ቦታ አለ። ፈጽሞም ያማረ ነው። የፍሬውም መዓዛ የጣፈጠ ነው። በዚያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደረጉ ደጋግ ነገሥታት ደስ ይላቸዋል። ሥራቸውም ቦታቸውም በመንግሥተ ሰማያት በዘላለም ሕይወት ቦታ የታወቀ ነው።

መጽሐፍ

1ኛ መቃ.6፣15 ዳዊት በመዝሙሩ አቤቱ በቁጣህ አትቅሰፈኝ በመቅሠፍትህም አትገስጸኝ ብሎ

እንደተናገረው። 1ኛ መቃ.7፣10 መጽሐፉንም ካልሰማኸው አምላክህ እግዚአብሔርን አልሰማኸውም።

ንጉሥ

1ኛ መቃ.7፣5 አምላክህን ለምን አትፈራውም? ሕዝቡንና መንጋውን በእውነት ትጠብቅ ዘንድ የፈጠረህና በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ያነገሠህ እግዚአብሔር ነው። 2ኛ መቃ.10፣1 እናንተም ነገሥታቱና መኳንንቱ በሰይጣን ጎዳና አትሂዱ ነገር ግን የፈጠራችሁን እስከዛሬም ድረስ የጠበቃችሁን እግዚአብሔርን ፍሩት።ሁሉንም በሚገዛ በእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዝ ጸንታችሁ ኑሩ።

ፍቅር፣ አንድነት፣ ምግባር፣ ትዕግስት

1ኛ መቃ.7፣10 ቃሉንም ካልጠበቅህ እርሱን (እግዚአብሔርን) አልወደድኸውም። 1ኛ መቃ.8፣4 ሥር ለቅጠል ውሃ ታጠጣለች መሬትም ለእንጨቶች ጽናትን ትሰጣለች። 1ኛ መቃ.12፣5 በሥራቸው እግዚአብሔርን አያውቁትም። 1ኛ መቃ.15፣10 ሄደን ስለ እነዚህ ሰዎች ሰውነታችንን ለሞት እንስጥ ብለው ወንድማማቾች መብክዩስ፣ መቃቢስና ይሁዳ ተማከሩ። በእጃቸውም ጦራቸውን ይዘው ሄዱ አክራንድዮስ ንጉሥ ምድያምንም ገደሉት። እግዚአብሔርም በመክብዩስና በወንድሞቹ እጅ የእስራኤልን ልጆች እንዲህ አዳናቸው። 3ኛ መቃ.8፣5 ታገሡ እግዚአብሔር ከሚጠላችሁ ሰዎች ለእናንተና ከእናንተም በኋላ ለልጆቻችሁና ለልጅ ልጆቻችሁ መጠጊያ ይሆናችሁ ዘንድ ከመከራ የተነሳ ልቡናችሁን አታሳዝኑ።

ትንሣኤ

1ኛ መቃ.7፣16 ከሞት እንደምትነሳ በጎም ቢሆን ክፉም ቢሆን በሰራኸው ሥራ ሁሉ በፊቱ ቁመህ እንደምትመረመር አስብ። 1ኛ መቃ.7፣27 እነሆ የሞቱ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ሕያዋን እንደሚሆኑ ታወቀ። 1ኛ መቃ.8፣1 ስለሙታን ትንሳኤ ስማኝ ልንገርህ ዛፎች ይተከላሉ ቅርንጫፎችንም ያወጣሉ ወይንም ሀረግ ያወጣል። እግዚአብሔር ፍሬውን ካለመኖር ያመጣዋልና ከእርሱ የወይን ጠጅ ይጥላሉ። 1ኛ መቃ.8፣10 የጻድቃንን ነፍሳት በብርሃን ቤት ያኖራቸዋል የኃጥዓንን ነፍሳት ግን በጨለማ ቤት ያኖራቸዋል። 1ኛ መቃ.8፣16 ቀኑ ይመሻል ትተኛለህም ሌሊቱ ይነጋል ከመኝታህም ትነሣለህ። አንተ ግን በተኛህ ጊዜ የሞትህ ነህ በነቃህም ጊዜ የትንሳኤ ምሳሌ ነው። ሌሊት የዚህ ዓለም ጠዋት የትንሳኤ ምሳሌ ነው። የስንዴም ቅንጣት ካልፈረሰ አይበቅልም። ስንዴ ብትዘራ ገብስ ትሰበስባለህን ጣፋጭ ፍሬስ ብትተክል የመረረ ሆኖ ይበቅልልሀልን እንደዚሁስ ሁሉ ኃጢአተኛ ቢሞት በትንሳኤ ጊዜ ጻድቅ መሆን ይችላልን ሁሉም እንደስራው ይከፈለዋል እንጂ በሌላ ኃጢአት የሚፈረድበት የለም። ዛፍ ጠል ካልዘነመበት ቅጠሉ አይለመልምም ዝግባውም የክረምት ዝናም በእርሱ ካልወረደ ከሥሩ ይነቀላል። እንደዚሁም ሁሉ ከእግዚአብሔር የሕይወት ጠል ካልወረደላቸው ሙታን አይነሡም። 1ኛ መቃ.9፣1 ተራሮች ከእግዚአብሔር ዘንድ የምሕረት ዝናም ካልዘነመላቸው ለእንስሳዎችና ለአውሬዎች ሣርን አያበቅሉም። በሙታን ትንሳኤ በመላእክት አለቃ በቅዱስ

ሚካኤል አፍ መለከት በሚነፋ ጊዜ በዚያ እንዳንቀላፋህ አትቀርም። ተራሮች ኮረብቶች ዝቅ ይላሉ ወንዞችና ጥልቆች ይስተካከላሉ ጥርጊያ ጎዳናም ይሆናሉ። ለሥጋ ለባሽም ሁሉ ትንሳኤ ይሆናል። 1ኛ መቃ.10፣1 እንዲህ ካልሆነ ግን የቀደሙ አባቶች ከአዳም ጀምሮ ከአቤልና ከሴት ከኖኅና ከሴም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብና ከዮሴፍ ከሙሴና ከአሮን ጀምሮ ከአባቶቻቸው መቃብር ውጭ ይቀብሩ ዘንድ ያልወደዱ ለምንድን ነው?በትንሳኤ ጊዜ ከዘመዶቻቸው ጋር በአንድነት እንዲነሡ አይደለምን። 1ኛ መቃ.10፣8 እግዚአብሔር ሕይወት መስጠትና ማስነሳት ይችላል። 1ኛ መቃ.11፣1 በዛብሎንና በኤዶምያስ ጣዖቶች የሚያመልኩ ያን ጊዜ ይዋረዳሉ መዳራትንና ርኩሰትን ዝሙትንም ስለሠሩ ጣዖትንም ስለ አመለኩ እግዚአብሔር ይበቀላቸዋል። 1ኛ መቃ.12፣14 ዳግመኛ በትንሳኤ ጊዜ እበቀላታለሁ ወደ ሕጌ አልተመለሰችምና በትዕዛዜም ጸንታ አልኖረችምና በቤቴና በንዋየ ቅድሳቴ ላይ ስድብን ውርደትን እንደአደረገች ሁሉ በሁሉ ዘንድ ጎስቋላ አደረግኋት። 1ኛ መቃ.13፣17 አንተና (ዲብሎስን ነው) በተንኮልህ ያሳትካቸው በአንድነት ወደ ገሀነም ትወርዳላችሁና ወዮልህ። 1ኛ መቃ.36፣44 ሙታን እንደሚነሱ በጎ ስራም የሰሩት ወደ ዘላለም ሕይወት ክፉ የሠሩትም በሙታን ትንሳኤ ጊዜ ወደ ዘላለም ቅጣት እንደሚሄዱ አምኗልና። በጎ ስራ የሠሩ ጻድቃን ግን ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይነግሣሉ። ክፉ የሰሩም ለዘላለም ይፈረድባቸዋል። 2ኛ መቃ.14፣2 ሳምራውያን ግን ሥጋችን ትቢያ ይሆናልና አይነሳም ይላሉ። ትንሳኤም በተደረገ ጊዜ የነፍሳችንን መነሳት እናምናለን። ነፍስ እንደ ነፋስ የማትታይና እንደ ነጎድጓድ ድምጽ ስለሆነች እነሆ እዚህ አለች የማይሏትና የማትታይ ስለሆነች ሥጋ ቢሞት አትሞትምና። ሥጋችን ግን በሁሉ ትታያለች አመድና ትቢያም ትሆናለች ይላሉ። ፈሪሳውያን ደግሞ የሙታንን መነሳት እናምናለን ነገር ግን ነፍሳትን በምድር ያይደለ በሰማያት ሌላ ሥጋ ያለብሳቸዋል ይላሉ። ሰዱቃውያንም ነፍሳችን ከሥጋችን ከወጣች በኋላ ከሞት አንነሳም ይላሉ። 2ኛ መቃ.16፣1 በሥጋህ በእጅህና በእግርህ ጥፍር በራስህም ጠጉር ያለውን እስኪ አንተ ራስህ አስበው በቆረጥሀቸውም ጊዜ ፈጥነው ይወጣሉና። ለማመን ልብና አእምሮ ካለህ በዚህ እወቅ በጎ ሥራ የሠሩ ሰዎች የሕይወት ትንሳኤ ይነሳሉ ዋጋቸውም እግዚአብሔር ለደጋጎች ያዘጋጀው መከራና ደዌ የሌለበት ከዚህም በኋላ ዳግመኛ የማይሞቱበት የንጹሓን ማደሪያ የደስታ ገነት ነው። ክፉ ሥራ የሰሩ ግን የደይን ትንሳኤ ተነስተው ከአሳታቸው ከዲያብሎስ ጋራ ከሰው ልጆች ሁሉ አንድ ሰውስ ስንኳ ይድን ዘንድ ከማይወዱ ከሠራዊቶቹ ከአጋንንትም ጋራ ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ። የጨለማ ዳርቻ ወደሆነ ጥርስ ማፋጨትና ልቅሶ ወዳለበት ይቅርታና ምሕረት ወደሌለበት እስከ ዘላለም ድረስ መውጫ ወደሌለበት ወደገሀነም ይወርዳሉ። በሥጋቸው ሳሉ በምድር ላይ በሕይወታቸው በጎ ሥራ አልሠሩምና የነፍስና የሥጋን በአንድነት መነሳት ለማያምኑ ሰዎች ወዮላቸው። 3ኛ መቃ.6፣5 ይህንን ዓለም ስለናቁት እጅግ ደስ ያሰኛቸዋልና የጻድቃን ሰዎች ነፍሳት በመላእክት ይባቤ ደስ ይላቸዋል። የኃጥዓን ነፍሳትን ግን ክፉዎች መላእክት ይቀበሏቸዋል። በኃጥዓን ነፍሳት ይዘባበቱባቸው ዘንድ ከዲያብሎስ ይላካሉ።

ሞት፣ ኃጢአት፣ ቸልተኝነት

1ኛ መቃ.8፣7 የመሬት ባሕርይ ግን በራሷ ጸናች አመድም ሆነች። የውሃ ባሕርይም በራሷ ጸናች ጠልም ሆነች። የነፋስ ባሕርይም በራሷ ጸናች ነፋስም ሆነች። የእሳት ባሕርይም በራሷ

ጸናች የሚሞቅ እሳትም ሆነች። እግዚአብሔር የፈጠራት ነፍስ ግን ወደ ፈጣሪዋ እጅ ተመለሰች። 1ኛ መቃ.17፣3 ሃይማኖትና ምግባር የላቸውም በጎ ሥራን የጠሉ ናቸውና እግዚአብሔርንም አያውቁትም ከክፋትና ከመቀማት ከረከሰ ሥራና ከሁከት ሁሉ በቀር አባታቸው ሰብልያኖስ እንዳስተማራቸው ከዘፈንና ከጨዋታ በቀር የሰላምን መንገድ አያውቁትም። 1ኛ መቃ.36፣15 ከሞት ወደ ሕይወት ትሻገሩ ዘንድ መልካም ማድረግንና የድኅነት መንገድን ችል አትበሉ። 2ኛ መቃ.18፣9 ስለዚህም በአዳም መተላለፍ ፍዳን እንቀበላለን ሥጋችንም በመቃብር ውስጥ ቀለጠች አጥንቶቻችንም ደቀቁ። ምድርም ቅልጥማችንን ጠጣች ጠፋንም ደም ግባታችንም በትቢያ ጠፋ። ሥጋችንም በመቃብር ተቀበረ ከሚያበሩ ዓይኖቻችንም ትሉ ወጣ መልካችንም በመቃብር ጠፋ ትቢያም ሆንን መልከ መልካም የነበሩ ቁመታቸውም ያማረ የቃላቸውም ንግግር የተቀላጠፈ የጎልማሶች የመልካቸው ደም ግባት ወዴት አለ? የነገሥታቱ ኃይላቸው የመኳንንቱስ ክብራቸው ወዴት አለ? በፈረስ መጠረር በወርቅና በብርም ማጌጥ በሚያንጸባርቅ የጦር መሳርያም መጠረር ወዴት አለ? የመባልዕት ጣዕም የወይን መጠጥ የት አለ? 2ኛ መቃ.19፣7 አንቺ ምድር ፍሬሽን በላን አንቺም ሥጋችንን በላሽ።

ክብር፣ ጽድቅ

1ኛ መቃ.12፣34 እኔ ለክብር አድርጌሽ ነበረ። አንቺ ግን ራስሽን ለውርደት አደረግሽ። እኔ ለእኔ ብየሽ ነበር። አንቺ ግን ለሌላ ሆንሽ። እኔ ለቅድስና አጭቼሽ ነበር። አንቺ ግን ለዲያብሎስ ሆንሽ እኔም እንደስራሽ ክፋት እበቀልሻለሁ። 1ኛ መቃ.17፣6 የእግዚአብሔር መንገድ ግን ትሕትናና የውሀነት ባልንጀራንም መውደድና ወንድምን አለማበሳጨት ከሰው ሁሉ ጋርም መፋቀርና ሰላም ነው። 3ኛ መቃ.5፣4 በዚህም ዓለም የሠራኸውን በጎውንና ክፉውን አስብ ክፉው ይበዛ እንደሆን መዝን ምከርም። በጎ ነገርንም ብታበዛ ሙታን በሚነሱበት ቀን ደስ ይልህና ሐሴት ታደርግ ዘንድ ለአንተ መልካም ይሆንልሀል።

ተአምኖ፣ ረድኤተ እግዚአብሔር

1ኛ መቃ.21፣7 በብዙ ሠራዊትና በፈረሶች በቀስትና በጋሻም ከመታመን በእግዚአብሔር መታመን ይሻላልና። በእርሱም የታመነ ሰው በሕይወት ይኖራል ይከብራል ፈጽሞም ከፍ ከፍ ይላል። ያመኑበትን ይጠብቃቸዋል። 1ኛ መቃ.24፣3 ከእናታችሁ ማኅጸን ያወጣኋችሁ ያሳደግኋችሁም የመገብኋችሁም ያለበስኋችሁም እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነኝና ለምን ታመካኛላችሁ ይህን ሁሉ አደረግሁላችሁ ምንስ ሰጣችሁኝ? እኔስ ከእናንተ ምን እሻለሁ? የነፍሳችሁን መዳን ነው እንጂ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር እንዲህ አለ። 2ኛ መቃ.4፣28 እምነቱን በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ አድርጓልና ድል የሚነሳው አልነበረም።

ክፉ ሰዎች፣ ኃጥዓን

1ኛ መቃ.25፣14 የበደለኞችም ጉባኤያቸው እንደ ጉም ሽንት ነውና ደስታቸውም እንደምትበር ወፍ ነውና። የብርና የወርቅ የሚሆን የመልካቸውም ደም ግባት በምድር ጠፊ ነው። ሁሉም

ትናንትና እንዳለፈችው ቀን ያልፋል። የአማረ አኗኗራቸውም እንደሚያልፍ ጥላ ነው። 2ኛ መቃ.15፣18 ያን ጊዜም መጨረሻ የሌላት ድኅነትና መረጋጋት የሌለባት የምታገኛቸውን መከራ ያያሉ። በልቡናቸውም መረጋጋት እና ዕረፍት የሌለው ኀዘን ይሆናል። የማያንቀላፋ ትል የማይጠፋም እሳት ያገኛቸዋል።

ጠላት፣ በሽታ፣ መከራ፣ ፍርሀት

2ኛ መቃ.1፣3 የእስራኤልም ልጆች ቢበድሉ ሞዓባዊውን መቃቢስን አስነሳባቸው። እርሱም ሁሉን በሰይፍ ገደላቸው። 2ኛ መቃ.2፣5 ቁጣዬን አነሳስተሀልና የልብ በሽታን አመጣብሃለሁ ይላል እግዚአብሔር። 3ኛ መቃ.6፣4 የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚፈጽሙ ሰዎች ግን ፍርሀት የለባቸውም።

ንሥሓ

2ኛ መቃ.2፣8 አሁንም ከሠራኸው ክፋት ሁሉ ተመለስ ብትመለስ በእግዚአብሔር ፊት ፈጽመህ በለቅሶና በኀዘን ብትናዘዝ በንጹሕ ልቡናም ወደ እርሱ ብትለምን በፊቱ የሠራኸውን ኃጢአትህን ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር ይልሀል። የዚያን ጊዜ መቃቢስ ትቢያ ለብሶ ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ። በልቅሶና በኀዘን በብዙ ልመናና በስግደትም ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የሚጨክኑም ብጹዓን ናቸው። ነቢዩም ወደ መቃቢስ ዘሞዓብ ሄደ ከእንግዲህ ወዲያ ግን ጣዖት ማምለክን ተው አለው። መቃቢስም እሺ አለ። 3ኛ መቃ.6፣8 ወደ እግዚአብሔር ፊት በደረሳችሁ ጊዜ ያለመከራ ያለደዌ በደስታ ትኖሩ ዘንድ ዘመናችሁ ሳያልፍ በአላችሁበት ንሥሓ ግቡ። ከእግዚአብሔር ወደሚያርቅ ከንቱ ፈቃድ እንዳይስባችሁ በእናንተ ጽኑ ነቀፋና መቀማጠል መብልንና ደስታንም መውደድ አይገኝባችሁ። ያለ ልክ የጠገበች ሰውነት የእግዚአብሔርን ስም አታስብምና። የዲያብሎስ መንፈስ ያድርባታል እንጂ። በልክ የሚበላ ግን በእግዚአብሔር መሰረት የጸና ይሆናል። እንደ አድማስም ድንጋይ አጥርም እንዳለው ግንብ ይጸናል።

ዲያብሎስ

3ኛ መቃ.1፣12 ዲያብሎስ እንዲህ ይላል "ማደሪያየም ላደረግኋቸው ሰዎች ምልክትን አሳያቸዋለሁ በከዋክብት አካሄድም ቢሆን ወይም በደመና መውጣት ወይም በእሳት ማናፋት ወይም በአውሬዎችና በወፎች ጩኸት እነርሱ ማደሪያዎቼ ናቸውና በዚህ ሁሉ በልቡናቸው ምልክቶችን አሳድርባቸዋለሁ" ይላል። እንደቃላቸውም የማደርግላቸው እንደ እገሊትና እንደእገሌ አዋቆች የሉም ብለው ለባልንጀሮቻቸው ይነግሯቸው ዘንድ የቃላቸውን ምልክት አደርግላቸዋለሁ ይላል። 3ኛ መቃ.1፣16 ያሳትኋቸው ሰዎች ከእኔ ጋራ በእሳት ውስጥ ይጨመሩ ዘንድ ከፈጠረኝ ከእግዚአብሔር ቃልኪዳን አለኝ። ጌታም ትእዛዜንና የመጽሐፎቼን ቃል ትተው ወደ አንተ ከመጡ ጥፋታቸው አያሳዝነኝም አለው ዲያብሎስን። ነገር ግን ለዘላለም በእሳት ውስጥ ትሰቃያላችሁ አለው። አንተ ማሳት ለተሳነህ ሰዎች መንግሥተ ሰማያትን እሰጣቸዋለሁ አለው። የአዳምን ልጆች ሁሉ እተነኮልባቸዋለሁና የዓለምን ምኞት

አጣፍጥላቸዋለሁና መብልን በመውደድ መጠጥንም በመውደድ ልብስን በመውደድም ቢሆን ነገርንም በመውደድ በመስጠትም በመንሳትም ቢሆን መስማትንና ማየትንም በመውደድ ቢሆን መዳሰስንና መሄድንም በመውደድ ቢሆን ትዕቢትንና ነገርንም በማብዛት ቢሆን እንቅልፍንና ሕልምንም በመውደድ ቢሆን መጠጥንና ስካርን በማብዛት ቢሆን ቧልትንና ቀልድን በመናገርም ቢሆን ባልንጀራቸውንም በማማት በጠብ ቢሆን መልከ መልካሞች የሆኑ የዚህን ዓለም ሴቶችን በማየትም ቢሆን የሚያስቷቸውን የሽቱዎችን መዓዛ በማሽተትም ቢሆን መዳንን እንዳይችሉ በዚህ ሁሉ እኔ እጣላቸዋለሁ።

ምስጋና

3ኛ መቃ.2፣12 አዳምና ልጆቹም እግዚአብሔር ስለ ትዕቢትህ (ዲያብሎስን ነው) በናቃችሁ በአንተና በሠራዊትህ ምሥጋና ፋንታ የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑ ዘንድ ተፈጠሩ። ስለዚህም በትሑታን ይመሰገን ዘንድ አዳምን ከምድር አፈር ፈጠረው። እንደ የዋህ ርግብ ሆና የተፈጠረች ተንኮልህን የማታውቅ ሔዋንም ባሳትሃት ጊዜ በተከናወነ ነገርህና በጠማማ ቃልህ አስካድሃት በምክንያትህም ከደስታ ገነት አወጣሀት።

ጸጋ፣ተዘክሮ

3ኛ መቃ.3፣2 ለአዳም ግን ክፉ የሆኑ አምስት አሳቦችና በጎ የሆኑ አምስት አሳቦች አሥር አሳቦች ተሰጡት። ለዲያብሎስ ግን ሥጋዊ አይደለምና አንዲት አሳብ ብቻ ኖራው ግን ሳተ። 3ኛ መቃ.6፣1 የምትሞቱበትን ቀን አስቡ።

በእንተ ክርስቶስ፣ሕገ ተፈጥሮ

3ኛ መቃ.4፣1 ጌታውም አዳምን ይቤገርው ዘንድ አለው። በጉንም ከተኩላ አፍ ያድነዋል። 3ኛ መቃ.9፣1 በሰማይም ያለ ቢሆን በምድርም ያለ ቢሆን ረቂቅም ቢሆን ግዙፍም ቢሆን ሁሉም የእርሱ ነው። ሁሉም በሥርዓቱ ጸንቶ ይኖራል። ከዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ ሕግና ትዕዛዝ የሚተላለፍ የለም።

መዝሙረ ዳዊት

አንድምታ

እነ ዮሐንስ አፈወርቅን እነ አትናቴዎስ ሐዋርያውን የመሰሉ ታላላቆቹ የቤተክርስቲያን አባቶች የተረጎሟቸውን የብሉያትና የሐዲሳት ትርጓሜ የሀገራችን ሊቃውንት እያቀኑ ለሰው እንደሚገባው እንደ ሀገሩ አነጋገርና ባህል እያደረጉ በምስጢር በታሪክ በሐተታና በምሳሌ እየገላለጡ ተርጉመዋቸዋል። የትርጓሜውም ዋና ጥቅሙ ምእመናን ምስጢሩን አውቀው እንዲጸልዩ ማድረግ ነው። የሚጠቅምና የሚያድን ሃይማኖት ቢሆንም ምስጢሩን ሳያውቀው የሚጸልየውን ሰው አበው በዓይነ ስውር መስለው ዓይነ ስውር በሚሄድበት ጎዳና ግራና ቀኝ በበትሩ እየዳበሰ ሲሄድ በቅርብ የሚገኙ አራዊት በትር መያዙን እንጂ ዓይነ ስውርነቱን

ባለማወቅ እንደሚሸሹና እንደሚርቁ አጋንንትና የክፉ ወገን የሆነ ሁሉ ቃለ እግዚአብሔር በቃሉ መናገሩን እንጂ የእርሱን አለማወቅ ስለማይፈልጉ ይርቃሉ ብለዋል ሐዊ። ቢሆንም ምስጢሩን ሳያውቁ ከመጸለይና ከማንበብ አውቆ መጸለይና ማንበብ እንደሚበልጥ የታወቀ ነው። ከተበላበት ከተጠጣበት ደስቅ የሚባል የእንቅልፍ ጋኔን አለና። መዝ.49፣3 እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ ወአምላክነሂ ኢያረምም። አንድም እግዚአብሔርሰ በሥጋ ማርያም ይመጣል። ወአምላክነሂ መጥቶ ዝም አይልም። አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እያለ ይዘልፋል። አንድም እግዚአብሔርሰ በክበበ ትስብእት ይመጣል። ወአምላክነሂ መጥቶም ዝም አይልም። ጻድቃንን ንዑ ኀቤየ ብሎ ይጠራል። ኃጥዓንን ሑሩ እምኔየ ብሎ ያሰናብታል። (ለአንድምታ መሰረቱ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በአንዱ ቦታ የተነገረው ለሌላው ቦታ እየሆነ ማለት ነው። ለምሳሌ ሰማያት ያመሰግናሉ ለሚለው ሰው እነርሱን አይቶ እኒህን የፈጠረ ብሎ ያመሰግነዋል። ከሌላ ቦታ ግዴታ በግብር የሚያስተረጉሙ ስላሉ እነዚያን ምሳሌ አድርጎ ተናገረ። ለምሳሌ ሰው እንደ እንስሳ ሆነ ይላል ቀንድ አበቀለ ማለት ሳይሆን ግብሩን መሰለ ማለት ነው። ምሳሌም የሚመሳሰልልህ ጉዳይ ካገኘህ መተርጎም ትችላለህ። ለምሳሌ መዝ.45.4 ፈለግ ዘይውኅዝ ያስተፈሥሕ ሀገረ እግዚአብሔር የሚለውን ይህ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ታዝዞ የመጣ ዝናም ኢየሩሳሌምን ደስ ያሰኛታል። ማለት የዘሩባትን እንድታበቅል የተከሉባትን እንድታጸድቅ ያደርጋታል። አንድም ከሰማይ የወረደ ቅዱስ ሚካኤል ሀገረ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ጠላቷ ሰናክሬምን አጥፍቶ ደስ ያሰኛታል። ብሎ ተርጉሞታል። ሌላ ሰው ደግሞ ፈለግ ገብርኤል ሀገረ እግዚአብሔር ማርያምን እያለ ቢተረጉመው ብቻ ከምስጢሩ ጋር ይሂድ እንጂ ነውርነት የለውም። የሲዲ ጳውሎስ ትርጓሜ የኤስድሮስ የወልደ አብ እየተባለ መለየቱም በዚህ አመስጥሮ የመጣ ነው። ትርጓሜ የተጻፈው ብቻ ነው ብሎ የሚያስብ ሊኖር አይገባም። ሌላው ለምሳሌ ቅዱስ ያሬድ በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ ሌሎችም አንቲ ውእቱ ዕፅ ሲሉ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም የሚለውን ወዘተ ሲተረጉሙ ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳቱ ነው።

ምክንያት፡- ሳሙኤል ሳኦልን በሎ ለወልድከ ይሑር ቅድሜነ። አዝዞ ሲል ነው። ምነው እርሱ አያዘውምን ቢሉ ቆርሶ ያላነረሱትን ቀዶ ያላለበሱትን ብላቴና ማዘዝ አይገባምና።

ምርምር፡- የዳዊት አርእስቱ 10 ነው። ይኸውም መዝ.1፣1 ተግሣጽ ለኩሉ፣ መዝ.2፣1 ትንቢት በእንተ ክርስቶስ፣ መዝ.3፣1 ትንቢት በእንተ ርእሱ፣ መዝ.4፣1 ትንቢት በእንተ መነናውያን፣ መዝ.5፣1 ትንቢት በእንተ ትሩፋን፣ መዝ.13፣1 ትንቢት በእንተ ሕዝቅያስ፣ መዝ.34፣1 ትንቢት በእንተ ኤርምያስ፣ መዝ.43፣1 በእንተ መቃብያን የመቃብያን መነሳት ከሚጠት በኋላ ነው። መዝ.49፣1 ትንቢት በእንተ ዘለፋ ካህናት፣ መዝ.71፣1 በእንተ ሰሎሞን ወልዱ ናቸው። በዚህም በአሥሩ አርእስት አምስት ነገር አለበት። እኒህም መዝ.1 ተግሣጽ ለኩሉ፣ ምዕዳን እንደነ ኢትቅናዕ መዝ.37 ያለው ነው። ጸሎት እንደ ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ መዝ.101። ትንቢት እንደ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ። አኩቴት እንደ አአኩተከ እግዚኦ እስመ ተወከፍከኒ ዓይነት ያለው ነው። እስመ መዝሙረ ዳዊትሰ ትመስል ገነተ ዘትጸገ ጽጌያተ ወትፈሪ ፍሬያተ በገነት አትክልት ሰባት ነገር እንዳለበት በዳዊትም ሰባት ነገር አለበት። 1ኛ አፍቅሮ ጸላእት መዝ.16፣4 አነ ዐቀብኩ ፍናወ ዕፁባተ። 2ኛ ትሕትና መዝ.21፣6 አንሰ እጼ ወአኮ ሰብእ። 3ኛ ሃይማኖት መዝ.21፣10 እም ከርሰ እምየ አንተ አምላኪየ። 4ኛ ተስፋ

መንግሥተ ሰማያት መዝ.26፣13 እትአመን ከመ እርአይ ሠናይቶ ለእግዚአብሔር በብሔረ ሕያዋን። 5ኛ ተአምኖ ኃጣውዕ መዝ.37፣4 እስመ ኖኀ እም ስእርተ ርእስየ ጌጋይየ። 6ኛ ስርየት መዝ.50፣2 ሕጽበኒ ወአንጽሐኒ እም ኃጢአትየ። 7ኛ ምጽዋት መዝ.116፣29 ዘረወ ወወሀበ ለነዳይ። መዝ.2፣1 ለምንት አንገለጉ አህዛብ። እንደዚህ ያለው ደረቅ ሐዲስ ይባላል። እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ። ሰአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ። ሰአል ማለቱ ከተዋሕዶ በኋላ ልመና ኖሮበት አይደለም ልመና ይስማማው የነበረ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ። መዝ.3 ሀተታ ሰይጣን ያስጀመረውን ነገር አያስፈጽምምና አምኖን ከወደዳት ይልቅ ኋላ የጠላት መጥላት ፀና። አቤሴሎም ወንድሟ ከሁለት ዓመት በኋላ በዚህ ምክንያት ገደለው። መዝ.67፣31 ይመጽኡ ተናብልት እም ግብጽ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር። (ይህንን ጳጳሳት ከግብጽ እየተሾሙ ይመጣሉ ብለው የተረጎሙ ነበሩ። ይህ ግን የግል አስተያየት እንጂ ጥሬው ንባብ እንዲህ ለማለት አያበቃም። እነ አድማሱ ጀንበሬን የነቀፏቸው ሰዎች የትርጓሜን አካሄድ የማያውቁ ሰዎች ናቸው)። መዝ.73፣12 ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ሁሉን መናገር ነው። ለከ ውእቱ መዓልት ወዚአከ ይእቲ ሌሊት ማለት መዓልትና ሌሊትን የፈጠርካቸው አንተ ነህ። ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ። መዝ.86፣5 እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ ሰዎቹም ቤተመቅደስ እናታችን ይላሉ። ወብእሲ ተወልደ ዘሩባቤል ተወልዷል። መዝ.88፣5 ይገንያ ሰማያት ለስብሐቲከ እግዚኦ። አሁን ለእነርሱ ግእዛን ኖሯቸው አይደለም ተዘርግተው እየታዩ የሚያስመሰግኑት ስለሆነ ነው። (እንጨቶች እሾህን እናንግስሽ አሏት እንዳለው ያለ ነው)። መዝ.88፣11 ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ። በሀገራቱ ሰዎችን መናገር ነው። ባርቅ ሲሳራን ድል አድርጎበታልና።

ቋንቋ፡- መዝ.1፣1 ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን። ረሲዓን የሚላቸው እንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዝበው የሚያመልኩ ናቸው። ወዘኢቆመ ውስተ ፍኖተ ኃጥዓን። ምነው ነቢይ ጎዳናን ከለከለ እንስሳት በሄዱበት አራዊት ጻድቃን በሄዱበት ኃጥዓን ይሄዱ የለምን ቢሉ በግብር ያልመሰለ ሲል ነው። ኃጥዓን የሚላቸው ሰርቀው ቀምተው አስረው ፈትተው ቋንጃ ቆርጠው ነፍስ ገድለው የሚኖሩ ናቸው። ወዘኢነበረ ውስተ መንበረ መስተሳልቃን። መስተሳልቃን የሚላቸው ዓይኑ በፈረጠ እጅ እግሩ በተቆረጠ የሚዘብቱ ናቸው። መዝ.6 አንተ በስውር ያደረግሁት ይመስልሀል እኔ ግን በጣይ በጉባይ እንዲሉ በፀሐይ በጉባኤ እገልጽብሀለሁ ብሏል። መዝ.28፣1 አምጽኡ ለእግዚአብሔር ክብረ ወስብሐተ። አሁን ክብር ስብሐት እንደ ላም ተነድቶ እንደ በግ ተጎትቶ የሚመጣ ሆኖ አይደለም። ስሙን እየጠራችሁ አመስግኑት ሲል ነው። ቁርባን የሚለው የስንዴ የወይን መሥዋእት የላም የበግ። መዝ.53፣4 ናሁ እግዚአብሔር ይረድአኒ ወእግዚእየ ያድኅና ለነፍስየ። ይልና ናሁ እግዚአብሔር እግዚእየ ይረድአኒ ወያድኅና ለነፍስየ ብለህ ግጠም። እነሆ ጌታየ እግዚአብሔር ሰውነቴን ረድቶ ያድናታል። እንዲህ ብለህ ግጠም እንዲህ ብለህ ግጠም የሚለው የቀድሞው ቃልም በሰዋስው ደረጃ የሚያስኬድ ሆኖ ግን ደግሞ ያንኑ ቃል በማገላበጥ ከሀሳቡ ጋራ ተያያዥ የሆነ ምርጥ ዓረፍተ ነገር መፍጠር ነው። መዝ.77፣25 ወኅብስተ መላእክቲሁ በልዐ እንለ እመሕያው በመላእክት እጅ የወረደውን እንጀራ አንድም የአለቆቹ የሙሴ የአሮንን ምግብ መላው እስራኤል በሉ። አንድም የመላእክትን ምስጋና

አመሰገኑ። መዝ.77፣65 ወተንስአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እም ንዋም የተኛ ሰው ፈጥኖ እንዲነሳ እግዚአብሔርም ከሰባ ዘመን በኋላ በረድኤት ተነሳ። ወከመ ኃያል ወጎዳገ ወይን አንድም ወተንስአ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ተነሳ። የወይን ስካር እንዳለፈለት ሰው ፈጥኖ እንዲነሳ ጌታም በሦስት ቀን ፈጥኖ ተነሥቷል።

ታሪክ፡- መዝ.6፣6 ወበአንብዕየ አርኀሥኩ ምስካብየ። የዳዊትን የእንባውን መጠን ከዚህ ይናገሩታል። በእንባው የበቀለ ሰርዶ ሰውነቱን ተብትቦ ይዞት ብላቴኖቹ በመቀስ እያረፉ አውጥተውታል ይላሉ። ይኸውም በዜና እስክንድር ታውቋል። መዝ.71፣1 እግዚኦ ኩነኔከ ሀቦ ለንጉሥ። ዳዊት ፈጥኖ አረጀ በምን ምክንያት ቢሉ ከዚያ በፊት ዘጠኝ መቶ ስምንት መቶ ዘመን ይኖሩ ነበር። ከኖኅ ወዲህ ግን ዘመን እየተከፈለ ሄዷል። 500፣ 400፣ 300፣ 200፣ 120 ሆኗል። ወይከውን መዋእሊሁ ለእንለ እመሕያው ምዕተ ወእስራ እንዲል። እርሱ ባለቤቱ ዳዊትም ወመዋዕለ ዓመቲነኒ ሰብዓ ክራማት ወእመሰ በዝኀ ሰማንያ ዓም ብሎ ጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ እውነተኛውንም ፍርድህን ለሰሎሞን ግለጽለት። አንድም እግዚኦ አቤቱ የባህርይህን ግዛት ለክርስቶስ በሥጋ ይገዛ ዘንድ ስጠው ማለት ስለሥጋ እንግድነት። ከመ ይኵንኖሙ ለሕዝብከ በጽድቅ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ ይላታል ለሰሎሞን ገብራለታለችና። አንድም ለጌታ ፍጥረት ሁሉ ይገዙለታል። ጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ። የሰሎሞን ጠላቶቹ አመድ ይመገባሉ ማለት ተዋርዷቸውን መናገር ነው። አንድም ግዳይ ብለው ሲጥሏቸው በግንባራቸው በከንፈራቸው ይዘውት ይነሳሉና። አንድም አጋንንት እንደ ትቢያ በንነው እንደጢስ ተንነው ይጠፋሉ። ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውዑ። የተርሴስ የደሴያት ነገሥታት እጅ መንሻ ግብር ለሰሎሞን ያቀርቡለታል። አንድም ሰብአ ሰገል ለጌታ ሦስቱን ንዋይ ይገብሩለታል። መዝ.102፣5 ዘይሔድሳ ከመ ንስር ለውርዙትከ። ታሪክ ያፈ ፊንክስ ይልና ከዚያ እባብ ብልየት ሲያገኘው 40 ቀን ጹሞ ይታደሳል ነገር ግን ንስርን እባብ የሚል አልተገኘም።

ደረቅ ሐዲስ፡- መዝ.109፣1 ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ። እንዲህ ያለው ደረቅ ሐዲስ ይባላል። ጌታየ አብ ጌታየ ወልድን በቀኝ ተቀመጥ አለው። አሁን በሥላሴ ቀኝ ግራ ኖሮባቸው አይደለም። ዕሪናቸውን መናገር ነው። ንበር ማለቱ ስለሥጋ እንግድነት ነው። መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔሥሕ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ።

መዝሙር፣ ምስጋና፣ እልልታ

መቶ አምሳውን መዝሙር ከአራት አድርገው ተካፍለው በ24ቱ ጊዜ አሥራ ሁለት አሥራ ሁለት እየሆኑ ያደርሱት ነበር። አለቆቻቸውም ማን፣ ቆሬ፣ አሳፍ እና ኤዶትም ይባላሉ። (በሰዓት 12 ሲሆን በ24 ሰዓት 288 ይሆናል)። መዝ.9፣1 እገኒ ለከ እግዚኦ በኩሉ ልብየ ወእነግር ኩሎ ስብሐቲከ እትፌሣሕ ወእትሐሠይ ብከ በአንተ በማመኔ ደስ ይለኛል። ወእዜምር ለስምከ ልዑል። መዝ.12፣5 እሴብሖ ለእግዚአብሔር ዘረድአኒ ወእዜምር ለስመ እግዚአብሔር ልዑል። መዝ.32፣2 ግነዩ ለእግዚአብሔር በመሰንቆ ወበመዝሙር ዘአሠርቱ አውታሪሁ (በገና) ዘምሩ ሎቱ ወሰብሕዎ ስብሀተ ሐዲስ። ሠናየ ዘምሩ ወየብቡ ሎቱ። መዝ.46፣6 ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ። መዝ.49፣13 ኢይበልዕ ሥጋ ላህም ወኢይስቲ ደመ

ጠሊ። ሡዕ ለእግዚአብሔር መሥዋእተ ስብሐት ወሀቦ ለልዑል ጸሎተከ። መዝ.65፣1 የብቡ ለእግዚአብሔር በኩሉ ምድር። ወዘምሩ ለስመ በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ። መዝ.68፣30 እሴብሕ ለስመ አምላኪየ በማኅሌት ወአዐብዮ በስብሐት። መዝ.70፣8 ምላዕ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኮቴተ። መዝ.95፣2 ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወባርኩ ለስመ ወተዝያነው እም ዕለት ዕለተ አድኅኖቶ ወንግርዎመ ለአሕዛብ ስብሐቲሁ ወለኩሎመ አሕዛብ ተአምሪሁ። መዝ.11፣4 ሠረቀ ብርሃን ለራትዓን በውስተ ጽልመት ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ። ወኢይፈርህ እም ነገር እኩይ። ጥቡዕ ልቡ ለተወክሎ በእግዚአብሔር ጽኑዕ ልቡ ወኢይትሐወክ ለዓለም ዘረወ ወወህበ ለነዳይ ወጽድቁኒ ይነብር ለዓለም። ወተነልቅ ፍትወቶመ ለኃጥዓን። መዝ.115፣7 ወሰበርከ መዋቅሕትየ ለከ እሠውዕ መሥዋእተ ስብሐት። መዝ.136፣4 እፎ ነሐሊ ማሕሌተ እግዚአብሔር በምድር ነኪር። መዝ.150፣1 ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ። ሰብሕዎ በቃለ ቀርን ሰብሕዎ በመዝሙር ወበመሰንቆ ሰብሕዎ በከበሮ ወበትፍሥሕት ሰብሕዎ በአውታር ወበእንዚራ ሰብሕዎ በጸናጽል ዘሠናይ ቃሉ።

መልካም ሰው

መዝ.1፣1 ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን። ወዘኢቆመ ውስተ ፍኖተ ኃጥዓን። ወዘኢነበረ ውስተ መንበረ መስተሳልቃን። ዘዳዕመ ሕገ እግዚአብሔር ሥምረቱ። ፈቃዱ ሕገ እግዚአብሔር የሆነለት ሰው ነው እንጂ። መዝ.14፣2 ዘየሐውር በንጹሕ ወይገብር ጽድቀ ወዘይነብብ ጽድቀ በልቡ ወዘኢንሕለወ በልሳኑ ወዘኢገብረ እኩየ ዲበ ቢጹ። ወዘኢያጽአለ አዝማዲሁ ወዘምኑን በቅድሜሁ እኩይ። ዘያከብሮመ ለፈራህያነ እግዚአብሔር ወዘኢለቅሐ ወርቆ በርዴ ወዘኢነስአ ሕልያነ በላዕለ ንጹሕ ዘይገብር ከመዝ ኢይትሐወክ ለዓለም። መዝ.36፣25 ወርዘውኩሂ ወረሳእኩ ወጻድቅሰ ዘይትገደፍ ኢርኢኩ ወዘርዑሂ ኢይጼነስ እክለ። ወዘርዑሂ ውስተ በረከት ይሄሉ። እስመ ጻድቀ ያፈቅር እግዚአብሔር ወኢይገድፎመ ለጻድቃን ወለዓለም የዓቅቦሙ። ወይትቤቀል ሎመ ለንጹሓን ወይሜሩ ዘርያመ ለኃጥዓን። ወጻድቃንሰ ይወርስዋ ለዓለም። አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሀር ጥበበ። ወሕገ አምላኩ ውስተ ልቡ። መድኃኒቶመ ለጻድቃን እምኀበ እግዚአብሔር። ወቀዋሚሆመ ውእቱ በጊዜ ምንዳቤሆመ ይረድኦመ እግዚአብሔር ወያድኅኖመ ወያነግፎመ እምእደ ኃጥዓን።

መጻሕፍት፣ ስግደት

መዝ.1፣2 ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ ወይከውን ከመ ዕጽ እንተ ትክልት ኀበ ሙኃዝ ማይ።እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ወቈጽላኒ ኢይትነገፍ። ይህችም ዕጽ በሀገራቸው ለውዝ ገውዝ በሀገራችን ሎሚ ትርንጎ ናት። መዝ.5፣5 ወእሰግድ ውስተ ጽርሐ መቅደስከ በፈሪሆትከ። መዝ.86፣6 እግዚአብሔር ይነግሮመ ለሕዝቡ በመጽሐፍ ወለመላእክቲሁኒ እለ ተወልዱ በውስቴታ። መዝ.95፣9 ስግዱ ለእግዚአብሔር በዓፀደ መቅደሱ። መዝ.101፣18 ወተጽሕፈት ዛቲ ለካልዕ ትውልድ። መዝ.131፣7 ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ።

ሃይማኖት፣ ምግባር፣ ፍርድ

ሃይማኖት በቅጠል ምግባር በፍሬ ይመሰላሉ። ከሃይማኖት ምግባር ይበልጣል ማለት አይደለም። በቅጠል መሠረትነት ፍሬ እንዲገኝ በሃይማኖትም መሰረት ምግባር ይሠራልና ሃይማኖትን በቅጠል ምግባርን በፍሬ መስሎ ተናገረ። መዝ.105፣3 ብጹዓን እለ የዐቅቡ ፍትሐ ወይገብሩ ጽድቀ በኩሉ ጊዜ።

ዕፅ ከንቱ፣ ፍቅረ ከንቱ

በነግህ ትበቅላለች በሠለስት ታብባለች በቀትር ታፈራለች በተስዓት ትደርቃለች በሠርክ ኪኮርኪ ብላ ትወድቃለች ከዚህ ደረሰች አትባልም። መዝ.4፣2 ለምንት ታፈቅሩ ከንቶ ወተኃሡ ሐሰተ።

በእንተ ክርስቶስ

መዝ.2፣1 ለምንት አንገለጉ አህዛብ። እንደዚህ ያለው ደረቅ ሐዲስ ይባላል። እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ።ሰአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ። ሰአል ማለቱ ከተዋሕዶ በኋላ ልመና ኖሮበት አይደለም ልመና ይስማማው የነበረ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ። መዝ.8፣1 እግዚኦ እግዚእነ ጥቀ ተሰብሐ ስምከ በኩሉ ምድር።እስመ ተለዐለ ዕበየ ስብሐቲከ መልዕልተ ሰማያት። እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐተ። በእንተ ጸላዒ ዲያብሎስን ደስ አይበለው ብለህ። መዝ.21፣16 ወአኃዙኒ ማህበሮሙ ለእኩያን ቀነውኒ እደውየ ወእገርየ ውኖለቁ ኩሎ አዕጽምትየ ወተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ ወተዐጸው ዲበ አራዝየ። መዝ.44፣2 ይሜኒ ላሕዩ እም ውሉደ እንለ እመሕያው። አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ ቅብዐ ትፍሥሕት እም እለ ከማከ። መዝ.46፣4 ሥኖ ለያእቆብ ዘአፍቀረ። የያዕቆብን ሃይማኖት የወደደ እርሱ ነው። አንድም የያዕቆብን ሥጋ ለመዋሐድ የወደደ እርሱ ነው። ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን። መዝ.109፣1 ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ። እንዲህ ያለው ደረቅ ሐዲስ ይባላል። ጌታየ አብ ጌታየ ወልድን በቀኝ ተቀመጥ አለው። አሁን በሥላሴ ቀኝ ግራ ኖሮባቸው አይደለም። ዕሪናቸውን መናገር ነው። ንበር ማለቱ ስለሥጋ እንግድነት ነው። መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔሥሕ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሚመቱ ለመልከጼዴቅ። መልከጼዴቅ ጌታን በምን ይመስለዋል ቢሉ መልከ ጼዴቅን ዘአልቦቱ አብ ወእም ይለዋል። ምነው በስንክሳር ተጽፎ የለምን ቢሉ በሌዋውያን ክታብ ስለሌለ ጌታም ለቀዳማዊ ልደቱ እናት ለደኃራዊ ልደቱ አባት የለውምና። አንድም መልከጼዴቅ በስንዴ በወይን ያስታኩት ነበር። ጌታም ስጋውን በስንዴ ደሙን በወይን አድርጎ ሰጥቶናል። አንድም መልከጼዴቅ በዚህ ጊዜ ተገኘ በዚህ ጊዜ ያልፋል አይባልም። ጌታም በዚህ ጊዜ ተገኘ በዚህ ጊዜ ያልፋል አይባልም። አንድም መልከጼዴቅን ዘእምነገዱ ለካም ይለዋል ከቤተ ሌዊ ሳይወለድ ክህነትን ገንዘብ አድርጓል ጌታም ከቤተ ይሁዳ ተወልዶ ክህነትን ገንዘብ አድርጓል።

ነገሥታት፣ ሰዱቃውያን

መዝ.2፣10 ወይእዜኒ ነገሥት ለብው ወተገሠፁ ኩልክሙ እለ ትኴንንዋ ለምድር። ተቀነዩ

ለእግዚአብሔር በፍርሀት። መዝ.4 ሳዶቅ የሚባል ሰው ነበረ።ሰው ሞቶ ከመቃብር ከገባ በኋላ ፈርሶ በስብሶ ይቀራል። ነፍሱም እንደ ጉም ሽንት በንና ትቀራለች የሚል ነው። የእርሱን ባህል የያዙት ሁሉ ሰዱቃውያን ተብለዋል። መዝ.32፣16 ኢይድኅን ንጉሥ በብዝኀ ሠራዊቱ። ወያርብህኒ ኢድኅነ በብዝኀ ኃይሉ። ወኢያመስጥ በብዝኀ ጽንዑ።

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ ጸሎት፣ ተስፋ

መዝ.3፣4 ቃልየ ኀበ እግዚአብሔር ጸራሕኩ ወሰምዐኒ እም ደብረ መቅደሱ አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ ወተንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንስአኒ። ኢይፈርህ እም አእላፍ አሕዛብ እለ ዐገቱኒ ወቆሙ ላእሌየ። ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወአድኅነኒ። መዝ.9፣7 ወኮኖሙ እግዚአብሔር ምስካዮሙ ለነዳያን ወረዳኢሆሙ ውእቱ በጊዜ ምንዳቤሆሙ። እስመ ኢተኀድጎሙ ለእለ የኀሡክ እግዚኦ። መዝ.17፣3 እንተ ሶበ ጸዋእክዎ ለእግዚአብሔር እድኅን እምጸርየ። ሶበ ተመንደብኩ ጸዋእክዎ ለእግዚአብሔር ወሰምአኒ በጽርሐ መቅደሱ ቃልየ። መዝ.33፣5 ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ወኢይትኀፈር ገጽክሙ። መዝ.34፣1 ግፍያሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ከዚህ የማይመለሱ አሉና ግፍያሙ አለ። ከዚያ የሚመለሱ አሉና ሥረይ ሎሙ አለ።አንድም አውቀው የሄዱ አለና ከዚህ ግፍያሙ አለ። ሳያውቁ የሔዱ አሉና ከዚያ በዘኢየአምሩ ይገብሩ አለ። አንድም በኢተነሳሒ ኃጥእ ሊጸልዩበት ይገባልና ግፍያሙ አለ። ለተነሳሒ ኃጥዕ ሊጸልዩለት ይገባልና ከዚያ አባ ሥረይ ሎሙ አለ። መዝ.38፣7 ወይእዜኒ መኑ ተስፋየ አኮኑ እግዚአብሔር። መዝ.43፣5 ብከ ንወግያሙ ለኵሎሙ ጸርነ። ወበስምከ ናኀሥሮሙ ለእለ ቆሙ ላዕሌነ በእግዚአብሔር ንከብር ኩሎ አሚረ። መዝ.59፣12 በእግዚአብሔር ንገብር ኃይለ ወውእቱ የኀሥሮሙ ለእለ ይሣቅዩነ። መዝ.69፣5 አንሰ ነዳይ ወምስኪን አነ። ወእግዚአብሔር ይድኅኒ። መዝ.78፣9 ርድአነ አምላክነ ወመድኃኒነ በእንተ ስብሐተ ስምከ እግዚኦ ባልሐነ። ወሥረይ ለነ ኃጢአተነ በእንተ ስምከ ከመ ኢይበሉነ አሕዛብ አይቴ ውእቱ አምላኮሙ። መዝ.83፣11 እግዚአብሔር ይሁብ ክብረ ወሞገሠ እግዚአብሔር ኢያስተጸንዖሙ እም በረከቱ ለእለ የሐውሩ በሕይወት። መዝ.117፣8 ይሄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እም ተአምኖ በእጓከ እመሕያው ይኄይስ ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እም ተሰፍዎ በመላእክት። ኩሎሙ አህዛብ ዐገቱኒ ወበስመ እግዚአብሔር ሞዕክዎሙ። ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንስዓኒ። መዝ.118 አሌፋትን አዳም በገነት ሳለ ሰባት ዓመት ሲጸልየው ኖሯል። ዕፀ በለስን ከበላ በኋላ ተሰውሮታል። መዝ.120፣1 እም አይቴ ይምጻእ ረድኤትየ ረድኤትየሰ እምኀበ እግዚአብሔር ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ናሁ ኢይዴቅስ ወኢይነውም ዘየአቅቦ ለእስራኤል። መዝ.126፣1 እመ እግዚአብሔር ኢሐነጸ ቤተ ክንቶ ይጸምው እለ የሐንጹ እመ እግዚአብሔር ኢዐቀበ ሀገረ ክንቶ ይተግሁ እለ ይኄልው። ወከንቱ ገይሦትክሙ።

ቅዱሳን፣ ትሩፋን፣ ሰማዕት፣ ቃልኪዳን፣ ጽድቅ

መዝ.4፣3 አእምሩ ከመ ተሰብሐ እግዚአብሔር በጻዲቁ። መዝ.5፣1 ትሩፋን የሚላቸው አሥሩ ነገድ ተማርከው በኢየሩሳሌም የቀሩ ሁለቱ ነገድ ናቸው። አንድም ሁሉም ተማርከው አበው አልቀው የቀሩ ውሉድ ናቸው። መዝ.32፣5 ብፁዕ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር አምላኩ። ሕዝብ ዘነረየ ሎቱ ለርስቱ። መዝ.33፣17 ጸርሑ ጻድቃን ወእግዚአብሔር ሰምዖሙ ወእም ኩሉ

ምንዳቤሆሙ አድኃኖሙ። ቅሩብ እግዚአብሔር ለየዋሀነ ልብ። ወያድኅኖሙ ለትሑታነ መንፈስ። ብዙኅ ሕማሞሙ ለጻድቃን ወእምኵሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር። መዝ.43፣22 እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ። መዝ.67.35 መንክር እግዚአብሔር በላእለ ቅዱሳኒሁ። አምላከ እስራኤል ውእቱ ይሁብ ኃይለ ወጽንዐ ለሕዝቡ። መዝ.88፣3 ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ ወመሐልኩ ለዳዊት ገብርየ ለዓለም። አስተዳሉ ዘርዐከ ወአሐንጽ ለትውልደ ትውልድ መንበረከ። መዝ.115፣3 ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር። መዝ.117፣18 አርኅው ሊተ አናቅጸ ጽድቅ እባዕ ውስቴቶን ወእግነይ ለእግዚአብሔር። ዛ አንቀጽ እንተ እግዚአብሔር ጻድቃን ይበውዑ ውስቴቱ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር። መዝ.118፣86 ኵሉ ትእዛዝከ ጽድቅ። መዝ.138፣17 ወበኀቤየሰ ፈድፋደ ክቡራን አዕርክቲከ እግዚኦ። አኮኑ ጸላእተከ ጸላእኩ እግዚኦ። መዝ.145፣8 እግዚአብሔር ያፈቅሮሙ ለጻድቃን። መዝ.150፣1 ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ።

ቁጣ፣ ዓማፂ፣ ዓመፃ፣ ሽንገላ

መዝ.4፣4 ተምዑ ወኢተዐብሱ። የሚገባ ቁጣ አለ ሕጻናት የተማሩትን እንዳይገድፉ ያልተማሩትን እንዲማሩ መናፍቃን ሃይማኖት እንዳይነቅፉ ክህደት እንዳያሰፉ ተቆጡ። መዝ.7፣14 ናሁ ሐመ ዓማፂ በዓመፃሁ ጸንሰ በጻዕር ወወለደ ኃጢኣተ። ግበ ከረየ ወደሐየ ወይወድቅ ውስተ ግብ ዘገብረ። ወይገብዕ ፃማሁ ዲበ ርእሱ። ወትወርድ ዓመፃሁ ዲበ ዲማኁ። መዝ.10፣5 ዘሰ አፍቀራ ለዓመፃ ጸልኣ ነፍሶ። መዝ.36፣1 ኢትቅናዕ ላእለ እኩያን ወኢትቅናዕ ላእለ ገበርተ ዓመፃ እስመ ከመ ሣእር ፍጡነ ይየብሱ ወከመ ሐመልማለ ሐምል ፍጡነ ይወድቁ። መዝ.36፣25 ርኢክዎ ለኃጥእ ዐብየ ወተለአለ ከመ አርዘ ሊባኖስ ወሶበ እገብእ ኃጣዕክዎ። ኀሠሥኩ ወኢረከብኩ መካኖ። መዝ.61፣4 በአፉሆሙ ይድኅሩ ወበልቦሙ ይረግሙ። መዝ.77፣36 ወአፍቀርዎ በአፉሆሙ ወሐሰውዎ በልሳኖሙ ወኢኮነ ርቱዐ ልቦሙ። ወኢተአመንዎ በኪዳኑ።

መሥዋዕት፣ ተአምኖ፣ ማዳን

መዝ.4፣5 ሡዑ መሥዋእተ ጽድቅ ወተወከሉ በእግዚአብሔር። መዝ.12፣5 ወአንሰ በምሕረትከ ተወከልኩ ይትፌሥሐኒ ልብየ በአድኅኖትከ። መዝ.19፣7 እሙንቱሰ በአፍራስ ወበሠረገላት ወንሕነሰ ነዓቢ በስመ እግዚአብሔር አምላክነ። እሙንቱ ተአቅጹ ወወድቁ ወንሕነሰ ተንሣእነ ወረታእነ። መዝ.25፣1 ወተወከልኩ በእግዚአብሔር ከመ ኢይድክም። መዝ.26፣1 እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ ወያድኅነኒ ምንትኑ ያፈርሀኒ። መዝ.41፣5 ለምንት ትቴክዚ ነፍስየ ወለምንት ተሐውክኒ እመኒ በእግዚአብሔር ከመ እገኒ ሎቱ።

እግዚአብሔር፣ ሕገ እግዚአብሔር

መዝ.5፣5 ጸላዕከ እግዚኦ ኵሎሙ ገበርተ ዓመፃ። ወትገድፎሙ ለኵሎሙ እለ ይነቡ ሐሰተ። ብእሴ ደም ወጉህላዌ ያስቆርር እግዚአብሔር። መዝ.7፣9 ይፈትን ልበ ወኵልያተ እግዚአብሔር። እግዚአብሔር መኮንነ ጽድቅ ኃያል ወመስተዓግሥ። መዝ.9፣7 እግዚአብሔርሰ

ይነብር ለዓለም። ወውእቱ ይኴንና ለዓለም በጽድቅ። ወይኴንኖሙ ለአሕዛብ በርትዕ። የአምር እግዚአብሔር ገቢረ ፍትሕ። ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም። መዝ.10፣6 እስመ ጻድቅ እግዚአብሔር ወጽድቀ አፍቀረ። መዝ.11፣6 ቃለ እግዚአብሔር ቃል ንጹሕ። መዝ.17፣35 ወትምህርትከ ዘያጸንአኒ ለዝሉፉ ወተግሣጽከ ውእቱ ዘይሜህረኒ። መዝ.18፣7 ሕጉ ለእግዚአብሔር ንጹሕ ወይመይጣ ለነፍስ። ስምዑ ለእግዚአብሔር እሙን ወያጠብብ ሕጻናተ። ኵነኔሁ ለእግዚአብሔር ርቱዕ ወያስተፌሥሕ ልበ። ትዕዛዙ ለእግዚአብሔር ብሩህ ወያበርህ አዕይንተ። መዝ.23፣1 ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ። ዓለምኒ ወኵሎሙ እለይነብሩ ውስቴቱ። መዝ.24፣14 ኃይሎሙ ውእቱ እግዚአብሔር ለእለ ይፈርህዎ። መዝ.32፣5 ያፈቅር እግዚአብሔር ጽድቀ ወምጽዋተ። መዝ.46፣6 እስመ ንጉሥ እግዚአብሔር ለኩሉ ምድር እግዚአብሔርሰ ይነብር ዲበ መንበሩ ቅዱስ። መዝ.50፣17 ልበ ትሑተ ወየውሃ ኢይሜንን እግዚአብሔር። መዝ.71፣18 ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ። መዝ.73፣12 እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እም ቅድመ ዓለም። ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር። በማዕከለ ምድር በኢየሩሳሌም አዳምን ፈጥሮ መድኃኒት አደረገ። መዝ.80፣9 ወኢትስግድ ለአምላክ ነኪር እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ። መዝ.85፣15 አንተሰ እግዚኦ መሐሪ ወመስተሣሕል ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጻድቅ። መዝ.89፣2 ዘእንበለ ይቁም አድባር ወይትፈጠር ዓለም ወምድር እም ቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም አንተ ክመ። መዝ.93፣1 እግዚአብሔር እግዚእ መስተበቅል። መዝ.101፣25 አንተ እግዚኦ አቅደምከ ሣርሮታ ለምድር ወግብረ እደዊከ እማንቱ ሰማያት። እማንቱሰ ይትኃጕላ ወአንተሰ ትሄሉ።ወኩሉ ከመ ልብስ ይበሊ። ወከመ ሞጣሕት ትዌልጦሙ ወይትዌለጡ። ማለት በሕጻንነት በእርጅና በሕይወት በሞት ትለውጣቸዋለህ ይለዋወጣሉም። አንተሰ አንተ ክመ ወዓመቲከኒ ዘኢየኀልቅ። መዝ.102፣6 ገባሬ ሣሕል እግዚአብሔር ወይፈትሕ ለኩሉ ግፉዓን መሐሪ ወመስተሣሕል እግዚአብሔር ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጻድቅ ኢይቀስፍ ወትረ ወኢይትመዓዕ ዘልፈ። አኮ በከመ ኃጢአትነ ዘገብረ ለነ ወኢፈደየነ በከመ አበሳነ። ወበከመ ይምሕር አብ ውሉዶ ከማሁ ይምሕሮሙ እግዚአብሔር ለእለ ይፈርህዎ እስመ ውእቱ የአምር ፍጥረተነ። መዝ.102፣19 እግዚአብሔር አስተዳለወ መንበሮ በሰማያት ወኩሉ ይኴንን በመንግሥቱ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ኃይሉ ላዕኩ እለ ይገብሩ ፈቃዶ። ውስተ ኩሉ በሐውርት መለኩቱ። መዝ.103፣1 አሚነ ወዕበየ ስብሐት ለበስከ ወለበስከ ብርሐነ ከመ ልብስ ወረበብኮ ለሰማይ ከመ ሠቅ ዘይጠፍር በማይ ጽርሑ ወረሰየ ደመና መከየዶ ዘየሐውር በክነፈ ነፋስ። መዝ.103፣10 ዘይፈኑ አንቅዕተ ውስተ ቆላት ወያሰትዩ ለኩሉ አርዌ ገዳም። ወይትቄከፉ ሐልስትዮታት ለጽምዖሙ። ዘይሰቅዮሙ ለአድባር እም ውሳጥያቲሆሙ ዘያበቍል ሳእረ ለእንስሳ ወሐመልማለ ለቅኔ እንለ እመሕያው።ይትፌሣሕ እግዚአብሔር በተግባሩ። መዝ.110.7 ግብረ እደዊሁ ጽድቅ ወርትዕ ወእሙን ኩሉ ትእዛዙ ወጽኑዕ ለዓለመ ዓለም። መዝ.112.5 መኑ ከመ እግዚአብሔር አምላክነ ዘይነብር ውስተ አርያም ወይሬኢ ዘበታሕቱ። በሰማይኒ ወበምድርኒ ዘያነስኦ እምድር ለነዳይ። መዝ.113፣4 አምላክነሰ ውስተ ሰማይ ላዕለ በሰማይኒ ወበምድርኒ ኩሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር። መዝ.115፣3 ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኩሉ ዘገብረ ሊተ። መዝ.116፣2 ወጽድቁሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም። መዝ.118፣1 ብጹዓን እለ ንጹሓን በፍኖቶሙ ወእለ የሐውሩ በሕገ እግዚአብሔር እለሰ ይገብሩ ዓመፃ ፍኖተ ዚአሁ ኢሖሩ።

መዝ.118፣126 ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር። እግዚአብሔር ስራ የሚሰራበት ጊዜ አለው። ነገረ ቃልከ ያበርህ ወያጠብብ ሕጻናተ። መዝ.120፣1 ናሁ ኢይደቅስ ወኢይነውም ዘየአቅቦ ለእስራኤል። መዝ.134፣13 ስምከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም። መዝ.135፣4 ዘገብረ ዓቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ ዘገብረ ሰማያተ በጥበቡ ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ። ዘይሁብ ሲሳየ ለኩሉ ዘሥጋ። መዝ.138፣7 አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ እጎይይ እም ቅድመ ገጽከ። እመኒ ዐረገ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ። ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ። እስመ ጽልመትኒ ኢይጸልም በኀቤከ። መዝ.144፣13 መንግሥትከሰ መንግሥት ዘለኩሉ ዓለም። ወምኵናንከኒ ለትውልደ ትውልድ። ምዕመን እግዚአብሔር በኩሉ ቃሉ።

ይቅርታ፣ አንብዕ፣ አርምሞ

መዝ.6፣2 ተሣሀለኒ እግዚኦ እስመ ድውይ አነ። ካንተማ ጋራ ተጣልቼ እስከ መቼ ድረስ ነዋ ሰው የሆነ እንደሆነ ሲሞት ሲሻር አርፈዋለሁ ይባላል። ሲሞት አርፈዋለሁ እንዳልልህ በባህርይህ ሞት የለብህ ሲሻር አርፈዋለሁ እንዳልልህ በመንግሥትህ ጎልፈት ሽረት የለብህ። ተመየጥ እግዚኦ ወባልሓ ለነፍስየ ወአድኅነኒ በእንተ ምሕረትከ። መዝ.6፣6 ወበአንብዕየ አርኀሥኩ ምስካብየ። መዝ.38፣2 ተጸመምኩ ወአትሐትኩ ርእስየ ወአርመምኩ ለሰናይ።ለክፉ ነገር ዝምታ አለና ለበጎ ነገር ዝም አልኩ።

ጓደኝነት፣ ዘመን፣ ምክር

መዝ.17፣25 ምስለ ጻድቅ ትጸድቅ ወምስለ ብእሲ ንጹሕ ንጹሐ ትከውን ወምስለ ኅሩይ ኅሩየ ትከውን ወምስለ ጠዋይ ትጠዊ። መዝ.102፣15 ሰብእሰ ከመ ሣእር ውእቱ መዋዕሊሁ ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ። መዝ.110.7 ምክር ሰናይት ለኩሉ ዘይገብራ። መዝ.132፣1 ናሁ ሰናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልው አኃው ኅቡረ።

ጠላት፣ ማሸነፍ

መዝ.17፣37 እደግኖሙ ለጸርየ ወእኅዞሙ ወኢይትመየጥ እስከ አጠፍያሙ።አመነድቦሙ ወኢይክሉ ቀዊመ። ወይወድቁ ታሕተ እገርየ። መዝ.118፣133 አርትዕ ፍኖትየ ወሐረትየ በከመ ነቢብከ ወኢይማእኒ ኩሉ ኃጢአት።

መላእክት፣ ጸጋ፣ ካህናት

መዝ.33፣7 ይትዐየን መልአከ እግዚአብሔር ዓውዶሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ። መዝ.73፣18 ሀተታ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ እንደ ሃይማኖቱ ጽናት እንደ ምግባሩ ቅናት ነው። መዝ.81፣6 አንሰ እቤ አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኩልክሙ። አንትሙሰ ከመ ሰብእ ትመውቱ። መዝ.131፣7 ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ።ወጻድቃኒከ ትፍሥሕተ ይትፌሥሑ።

ነቢብ፣ ምክንያት

መዝ.33፣12 መኑ ውእቱ ዘይፈቅድ ሐይወ ወያፈቅር ይርአይ መዋዕለ ሰናያተ ክላዕ ልሳነከ

እም እኩይ ወከናፍሪከኒ ከመ ኢይንብባ ጉሕሉተ። ተገሐሥ እም እኩይ ወግበር ሰናየ። ኅሥሣ ለሰላም ወደሜና። መዝ.77፣2 እከሥት በምሳሌ አፋየ ወእነግር አምሳለ ዘእም ትካት። ኩሎ ዘሰማእነ ወዘርዒነ ወዘነገሩነ አበዊነ። ወኢንብዑ እም ደቂቆሙ ለካልእ ትውልድ። ወከመ ያእምር ካልዕ ትውልድ። ደቂቅ እለ ይትወለዱ ወይትነሥኡ። ከመ ይረስዩ ትውክልቶሙ ላዕለ እግዚአብሔር ወከመ ኢይርስኡ ግብረ እግዚአብሔር። ከመ ኢይኩኑ ከመ አበዊሆሙ ትውልድ እንተ ኢያርትዐት ልባ። መዝ.140፣4 ኢትሚጦ ለልብየ ውስተ ነገር እኩይ ለአመክንዮ ምክንያት ለኃጢአት።

ጸም፣ ምጽዋት፣ መከራ

መዝ.34፣14 ወአሕመምክዋ በጾም ለነፍስየ። መዝ.40፣1 ብጹዕ ዘይሌቡ ላዕለ ነዳይ ወምስኪን እም ዕለት እኪት ያድኅኖ እግዚአብሔር ወኢያገብያ ውስተ እደጸላዒሁ። እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ አራተ ሕማሙ። መዝ.48፣9 ዘጸመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ እስመ ኢይሬኢ ሙስና።

ፍቅር፣ ትሕትና

መዝ.41፣1 ከመ ያፈቅር ኀየል ኀበ አንቅዕተ ማያት ከማሁ ታፈቅር ነፍስየ ኀበ እግዚአብሔር። ጸምዐት ነፍስየ ኀበ አምላኪያ ሕያው። መዝ.69፣5 አንሰ ነዳይ ወምስኪን አነ። ወእግዚአብሔር ይድአኒ።

ሰው፣ ደስታ፣ በዓል

መዝ.48፣12 ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ። ዕዝራ ግን እንስሳት ይኄይሱነ ብሂል። ላም ከአፋፍ ላይ ሲመገብ ከገደል ስር ለምለም ሣር ጥሩ ውሃ ያየ እንደሆነ የረገጠው መሬት ካልከዳው በቀር ወርጄ ልመገበው አይልም። ሰው ግን ጽድቅ እንዲጠቅም ኃጢአት እንዲጎዳ ሲያውቅ ጨለማ ለብሶ ሊሰርቅ ሊቀማ የኅልማሳ ሚስት ሊነሳ ይሄዳልና። መዝ.76፣3 ተዘከርክዎ ለእግዚአብሔር ወተፈሣሕኩ። መዝ.103፣15 ወይን ያስተፈሥሕ ልበ ሰብእ ወቅብዕ ለአብርሆ ገጽ። እክል ያጸንዕ ኃይለ ሰብእ። መዝ.117፣27 ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት። መዝ.118፣52 ተዘከርኩ ፍትሐከ ዘእም ዓለም ወተፈሣሕኩ እግዚኦ። ይኄይሰኒ ሕገ አፉከ እም አእላፍ ወርቅ ወብሩር። መዝ.121፣1 ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ ቤተ እግዚአብሔር ነሐውር። መዝ.125፣5 እለ ይዘርዑ በአንብዕ ወበሐሴት የአርሩ። መዝ.143፣15 ብጹእ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር አምላኩ።

አለመፍራት፣ ተግባረ እድ

መዝ.48፣16 ኢትፍርሆ ለሰብእ ሶበ ይብእል ወሶበ ይበዝኅ ክብረ ቤቱ እስመ ኢይነስእ ምስሌሁ ኩሎ አመ ይመውት ወኢይወርድ ምስሌሁ ኩሉ ክብረ ቤቱ እስመ ፈግዐት ነፍሱ በሕይወቱ። መዝ.127፣2 ፍሬ ጻማከ ተሴሰይ።

ደብር፣ ኢትዮጵያ፣ ሥነ ፍጥረት

መዝ.67፣15 ደብረ እግዚአብሔር ደብር ጥሉል ደብር ርጉዕ ወደብር ጥሉል ደብር ዘሠምሮ እግዚአብሔር የኀድር ውስቴቱ። መዝ.67፣31 ይመጽኡ ተናብልት እም ግብጽ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር። መዝ.73፣12 ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ሁሉን መናገር ነው። መዝ.148፣5 እስመ ውእቱ ይቤ ወኮነ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ። ትእዛዘ ወሀቦሙ ወኢኀለፉ።

በቅጣት መመለስ፣ መርሳት፣ ተግሣጽ

መዝ.77፣34 አመ ይቀትሎሙ ውእተ አሚረ የኀሥሥዎ ይትመየጡ ወይገይሡ ኀበ እግዚአብሔር። ወተዘከሩ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ ረዳኢሆሙ። መዝ.77፣41 ተመይጡ ወአመከርዎ ለእግዚአብሔር ወኢተዘከሩ እዴሁ ዘአድኃኖሙ እምእደ ጸሮሙ ዘገብረ ተአምረ በግብጽ። መዝ.117፣18 ገሥጾሰ ገሠጸኒ እግዚአብሔር ወለሞትሰ ባሕቱ ኢመጠወኒ።

መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ

መጻሕፍት አምላካውያት

ጌታ በወንጌል እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ ዘትትናገሩ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ሰማያዊ ውእቱ ይትናገር በላእሌክሙ ሲል በማቴ.10፣20 እንደተናገረው ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተጻፉ በመሆናቸው መጻሕፍት አምላካውያት ይባላሉ። በግእዝ የተጻፉ የሀገራችን መጻሕፍተ ብሉያት ጥንታቸው መሰረታቸው ዕብራይስጥ ነው። በተለያየ ዘመንና ምክንያት ተተርጉመዋል።

ምሳሌያተ ሰሎሞን

ሰሎሞን ማለት መስተሳልም ማለት ነው ዘመኑ ዘመነ ሰላም ስለሆነ። ዳዊት ከእግዚአብሔር በታረቀበት ወራት ስለተወለደ መስተሳልም ተብሏል።

አንድምታ

ምክንያት፡- የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ እንደፀነሰች አውቃ ወደ ዳዊት ላከች። በምን አውቃ ቢሉ ፊቷ ይቀላል ጡቷ ይጠቁራልና። አንድም ከግዳጇ እንደነጻች ነበረችና። ዳዊት ለኦርዮ ጦማረ ሞቱን ጽፎ ሰደደው። ኦርዮ ይህንን አይቶ ወደሌላ ያልሄደ ስለምን ነው ቢሉ ያልተማረ ጨዋ ነበረና። አንድም ዳዊትና ኢዮአብ በሚያውቁት ቋንቋ ተጽፎ ነበርና። አንድም የንጉሥ ብላቴና ራስ ራሱን እያየ ይከተለው ነበርና። አንድም የንጉሥ ማኅተም በቀይ ቀለም ይጻፋልና በአንበሳ ማኅተም ይታተማል ከደረሰበት ሊያዩት ብቻ እንጂ ቀዶ ማየት ያስፈራልና። አንድም ይህ ሁሉ አይደለም ሲመጣ በፍቅር ተቀበለው ሲሄድ በፍቅር ሸኘው ባይጠረጥር ሳያየው ቀርቷል። ዳዊት ግን በተወለደ በ70 ዘመን አረጀ ስለምን ፈጥኖ አረጀ ቢሉ የሌሊት ግሥገሣ የቀን ዘለሳ ያማታው ነበርና። አንድም ከኖኅ ወዲህ ዘመን እየተከፈለ መጥቶ ነበርና ወይኩን መዋዕሊሁ

ለወልደ እጓለ እመሕያው ምእተ ወእሥራ ዓመተ እንዲል። (ለምክንያትህ አስረጅ ጥቅስ ማቅረብ ነው)። አንድም በዓውደ ኦርና መልአከ እግዚአብሔር ሲቀስፍ ታየው ደነገጠ ኃይሉ ተከፈለ። ስለዝህ ፈጥኖ አረጀ (በዘመኑ ያደረጋቸውን ድርጊቶች ለሌላው ድርጊት ምክንያት አድርጎ መበየን ነው)። ምሳ.18፣8 ሐካይያን ያበዝኑ ፍርሀተ። የማያርሱ የማይቆፍሩ የማይጽፉ የማይደኑሡ ሀኬተኞች ሰዎች ፍርሀትን ያበዛሉ እንራብን እያሉ። ምሳ.24፣29 ነገረ እግዚአብሔር ርሱን። የእግዚአብሔር ነገሩ የጋመ የጋለ ነው። ጻድቃንን አናዶ ወደ ገዳም ሰማእታትን አናዶ ወደ ደም ይወስዳቸዋል። ምሳ.24፣45 በእንተ ሠለስቱ ነገር ታድለቀልቅ ምድር ወራብዖሙሰ ኢትክል ጸዊረ። ገብር እመ ነግሠ ወአብድ እመ ጸግበ እክለ።

ምሳሌ፡- ይኸውም ምሳሌ ነው። ኦርዮ የጌታ አምሳል። ኦርዮ ጦማረ ሞቱን ከኢየሩሳሌም ወደ አራቦት ይዞ እንደሄደ ጌታችንም ከሊቶስጥራ ወደ ቀራንዮ መስቀለ ሞቱን ተሸክሞ ሄዷል። ምሳ.16፣14 መዓተ ንጉሥ ከመ መልአከ ሞት። የንጉሥ ቁጣ እንደ መልአከ ሞት ነው። መልአከ ሞት እንዲያስደነግጥ ያስደነግጣልና። ከመ ብርሃነ ፀሐይ ገጸ ንጉሥ። የንጉሥ ፊት እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው ያ ደስ እንዲያሰኝ ደስ ያሰኛልና። (ግብሩንና በሌላው ያለውን የግብሩን ተጽእኖ የሚፈጥረውን ስሜት አይቶ እንደተረጎመ አስተውል)። ምሳ.19፣17 ለድሃ የሚሰጥ የሚመጸውት እግዚአብሔርን ያበድረዋል። ያበደረ ሰው ያን ገንዘቡን እንዳያጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋውን አያጣም። ምሳ.24፣38 ውስተ ገራሕተ ብእሲ አብድ ሐለፍኩ ናሁ በቁለ ሦክ ወየዐብር ሣእሩ ፍጹመ። ወይክውን በድወ ድኅረ አነ ነሳሕኩ ከዚህ በኋላ አዘንኩ።

ገለጻ፡- ምሳ.21፣19 ይኄይስ ነቢር ውስተ ገዳም እም ነቢር ምስለ ብእሲት መዓትምት ወመግዝዕት ወነባቢት። አራዊት ቢጣሉት ሥጋውን ነው እንጂ ነፍሱን አይጎዱትም። ይህች ግን በሥጋም በነፍስም ትጎዳለች።

አብነት፡- ምሳ.22፣12 ይሜንን ቃለ ጥበብ ኃጥዕ። ኃጥዕ ሰው የጥበብን ነገር ይንቃል። አንድም ቃለ ጠቢብ ይላል። የብልህን ነገር ይንቃል።

ተቃርኖ፡- ምሳ.24፣38 ወኢትኩን ስምዐ በሐሰት ላዕለ ሰብአ ብሔርከ ምነው በሌላው መስክርበት ማለት ነውን ቢሉ በጸናው መናገር ነው እንጂ ይመስክርበት ማለትስ አይደለም። አንድም በተፈጥሮ ሁሉም ሀገሩ ነውና ላእለ ሰብአ ብሔርከ አለ።

መምህር፣ ረድኤተ እግዚአብሔር

ምሳ.1፣6 ዘሰ አጥረየ ሐዳፈ የአምር ምሳሌ ወሥውረ ነገረ። ምስጢረ መጻሕፍትንም ያውቃል። ምሳ.21፣31 ፈረሰ ያስተዳልው ለዕለተ ጸብእ። ፈረስን ለጸብዕ ቀን ያዘጋጃሉ ገፈራ ያበሉታል። ወእም ኀበ እግዚአብሔር ረድኤት። ድል መንሳት ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ምሳ.22፣17 ኀበ ቃለ ጠቢባን አቅርብ ዕዝነከ ለአጽምዖ ወስማዕ ቃለ ዚአየ። ወልብከ አቅርብ ከመ ሰናየ ታእምር።

ጥበብ፣ እግዚአብሔር

ምሳ.1፣7 ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር ወአእምሮ ሠናይት ለኩሉ ዘይገብራ ጥበበ ወተግሣጸ ይሜንኑ ረሢዓን። ምሳ.3፣19 እግዚአብሔር በጥበብ ሣረራ ለምድር ወአስተዳለወ ሰማያተ በአእምሮ። ምሳ.9፣8 ወልድየ እመ ጠቢበ ኮንከ ለርእስከ ጠቢበ ትከውን ለቢጽከ። ምሳ.15፣2 ውስተ ኩሉ መካን አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ወያስተሐይጽ እኩያነ ወኄራነ። ምሳ.24፣12 አእምሮ አእምር ከመ እግዚአብሔር የአምር ልበ ኩሉ። ወዘገብረ እስትንፋሰ ለኩሉ ውእቱ የአምር ኩሎ ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ። ምሳ.24፣53 ወለእመ አጸርከ አንፈከ ይወጽእ ደም አፍንጫህን ብትጠምቀው ደም ይወጣል። ወእመ ሰሀብከ ነገረ ይመጽእ ጋእዝ ወኩነኔ።

እናት አባትን ማክበር

ምሳ.1፣8 ስማዕ ወልድየ ሕገገ አቡከ ወኢትትሐየይ ትእዛዘ እምከ። አክሊለ ክብር ትነሥእ ለርእስከ። ምሳ.10፣1 ወልድ ጠቢብ ያስተፌሥሕ አባሁ ወወልድ አብድ የኀዝና ለእሙ። ምሳ.23፣24 ሰናየ ያልሕቅ አብ ጻድቅ። ደግ አባት ሰርቶ ቀጥቶ ያሳድጋል። ወበወልድ ጠቢብ ይትፌሣሕ ነፍሱ። በተማረ ልጅም ልቡናው ደስ ይለዋል። ወይትፌሥሑ ብከ አቡከ ወእምከ ወትትሐሠይ እንተ ወለደተከ። ምሳ.24፣35 ትውልድ እኩይ አባሁ ይረግም ወእሞ ይባርክ ክፉ ልጅ አባት እናቱን ይረግማል።

ትእዛዘ እግዚአብሔር፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር

ምሳ.3፣1 ወልድየ ሕገገ ዚእየ ኢትርሳእ ወቃላትየ ይዕቀብ ልበከ ኑኃ መዋእል ወዓመታተ ሕይወት ወሰላም ይዌስክከ። ምሳ.4፣18 ፍኖተ ጻድቃንሰ ከመ ብርሃን ይበርህ ወፍኖተ ኃጥዓንሰ ጽልመት። ምሳ.7፣2 ወልድየ አክብሮ ለእግዚአብሔር ወዘእንበሌሁሰ ኢትፍራህ ባዕደ። ዕቀብ ትእዛዘ ዚአየ ወተሐዩ ወጸሐፎ ውስተ ልብከ። ምሳ.8፣13 ፈራኄ እግዚአብሔር ይጸልእ ዓመፃ ወጽልዓ ወትእቢተ። ምሳ.10.8 ፈሪሀ እግዚአብሔር ያነውኅ መዋእለ። ምሳ.15፣27 ወበፈሪሃ እግዚአብሔር ይትገኀሥ ኩሉ እኩይ። ምሳ.23፣13 ኢትቅናዕ ልብከ ላዕለ ኃጥዓን አላ በፍርሀተ እግዚአብሔር ሀሉ በኩሉ ሰዓት። ምሳ.24፣29 ወኢትወስክ ውስተ ነገሩ ከመ ኢይዝልፍከ ወሐሳዌ ኢትኩን። በአሠርቱ ቃላት አነሠ ብለህ አትጨምር።

ሐልዮ፣ ርእይ፣ ነቢብ

ምሳ.3፣5 ሐሊ ሰናየ ቅድመ እግዚአብሔር ወሰብእ። ምሳ.4፣24 አርኅቅ እምኔከ አፈ እኩየ ወከናፍረ ዓመፃ አንኅ አርኅቆ እምኔከ። አዕይንቲከኒ ርቱዐ ይርአያ ወቀራንብቲከኒ ይቅጽባ ጽድቀ። አግኅሥ እገሪከ እም ፍኖት እኪት። ምሳ.5፣3 ኢትነጽር ብእሲተ እኪተ እስመ መዓር ይውኅዝ እም ከናፍረ ብእሲት ዘማ እንተ ለጊዜሁ ያመርዕሮ ለጉርኤከ። ወእም ድኅሬሁሰ ዘይመርር እም ሐሞት ትረክብ። ምሳ.15፣26 ምኑን በኀበ እግዚአብሔር ሐልዮ ዓመፃ። ወለንጹሓን ነገሮሙ አዳም። ምሳ.16፣1 ልበ ብእሲ ኄር ይሐሊ ጽድቀ። ዓይነ ዘይኔጽር ሰናየ ያስተፌሥሕ ልበ። ወዜና ኄራት ያጠልል አዕጽምተ። ምሳ.16፣20 ፀቃውዐ መዓር ነገር

ሠናይ። ነቅዐ ሕይወት ሕሊና ሰናይት ለእለ አጥረይዋ። ምሳ.18፣21 ሞት ወሕይወት ውስተ እደ ልሳን። ምሳ.21፣24 ወዘይዜክርሰ እከየ ኃጥዕ ውእቱ። ክፉ ነገርን የሚያስብ ሰው ኃጥእ ነው ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል።

ተአምኖ፣ ጽድቅ፣ ምጽዋት

ምሳ.3፣5 ሀሉ በእግዚአብሔር ተወኪለከ በኩሉ ልብከ ወበጥበብከ ኢትትዐበይ። ምሳ.11፣2 ወጽድቅሰ ታድኅን እሞት። ጽድቁ ለንጹሕ ያረትዕ ፍኖቶ። ምሳ.15፣9 ወእለሰ ይዴግንዋ ለጽድቅ ያፈቅሮሙ እግዚአብሔር። ምሳ.15፣27 በምጽዋት ወበሃይማኖት ይሠረይ ኃጢአት። ይኄይስ ኅዳጥ ኅብስት ምስለ ጽድቅ እም ብዙኅ ፍሬ ዘምስለ ዓመፃ። ምሳ.16፣7 ገቢረ ጽድቅ ሥሙር በኀበ እግዚአብሔር።ምኑን በኀበ እግዚአብሔር መዳልወ ዓመፃ። ምሳ.16፣20 ወዘይትዌከልሰ በእግዚአብሔር ብፁዕ። ምሳ.19፣17 ይሌቅሖ ለእግዚአብሔር ዘይምሕር ነዳየ። ለድሃ የሚሰጥ የሚመጸውት እግዚአብሔርን ያበድረዋል። ምሳ.19፣18 ይኄይስ ነዳይ ጻድቅ እም ባዕል ሐሳዊ። ምሳ.20፣6 ዓቢይ ወክቡር ብእሲ መሐሪ። ምሳ.21፣21 ዘይዴግን ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ይረክብ ክብረ ወሕይወተ። ምሳ.22፣9 ብእሴ ፍሡሐ ወሀቤ ያፈቅር እግዚአብሔር። ደስ ብሎት የሚሰጥን ሰው እግዚአብሔር ይወደዋል።

ተግሣጽ

ምሳ.3፣11 ወልድየ ኢትአንተል ተግሣጸ እግዚአብሔር። እስመ ዘአፍቀረ እግዚአብሔር ይገሥጾ ከመ አብ ወልዶ ዘይሠምር። ምሳ.4፣1 ስምዑ ውሉድየ ተግሣጸ አብ ከመ ይኩን ብዙኅ መዋእለ ሕይወትክሙ። ምሳ.9፣8 ኢትዝልፎሙ ለእኩያን ከመ ኢይጽልኡከ ዝልፎ ለጠቢብ ወያፈቅረከ። ምሳ.19፣18 ዝብጥ ወልደከ ወይከውነከ ለተስፋ። ምሳ.23፣13 ወኢትትሐየይ ገስጾ ደቂቅከ። እስመ እመ ዘበጥኮሙ በበትር ኢይመውቱ። አንተ ትዘብጦሙ በበትር ወነፍሶሙ ትባልህ እሞት።

ቸልተኝነት፣ ቁጣ፣ መናቅ

ምሳ.3፣21 ወልድየ ኢትትሐየይ። ምሳ.14፣35 መዓት ተንጉል ጠቢባነ። ምሳ.22፣12 ይሜንን ቃለ ጥበብ ኃጥዕ። ኃጥዕ ሰው የጥበብን ነገር ይንቃል። አንድም ቃለ ጠቢብ ይላል። የብልህን ነገር ይንቃል።

ከፍጥረታት መማር፣ ስንፍና

ምሳ.6፣6 ተመየጥ ኀበ ቃሕም (ጉንዳን) ሐካይ ወኢትኩን ሐካየ ወቅናዕ ርእየከ ፍናዊሁ። ወኩን ጠቢበ እምኔሁ። ያስተጋብእ በሐጋይ ሲሳዮ ብዙኃ ከመ ማዕረር። አው ሑር ኀበ ንህብ ወአእምር ከመ መስተገብርት ይእቲ ወበኃይልሰ ጽብስት ወበምግባራሰ ጽንዕት። ምሳ.6፣9 እስከ ማዕዜኑ ሐካይ ትሰክብ ወማእዜ እም ንዋምከ ትነቅሕ ሕቀ ትነውም ወሕቀ ትነብር ወሕቀ ትነብር ሕቀ ትዴቅስ ወሕቀ ታስተጋብእ እዴከ ዲበ እንግድዓከ ወእምዝ ይመጽአከ ከመ እኩይ ሐዋርያ ንዴት። ብእሲ አብድ ወዓማሚ የሐውር ፍናወ ዘኢኮና ኄራተ። ምሳ.22፣12 ያመክኒ

ሀካይ ሶበ ይልእክዎ። ወይብል አንበሳ ሀሎ ውስተ ፍኖት ወውስተ መራሕብት ቀትል። ምሳ.23፣9 ውስተ እዝነ አብድ አልቦ ዘትነግር ከመ ኢይመንን ነገረከ ሰናየ። ምሳ.24፣13 ብላዕ ወልድየ መዓረ እስመ ሰናይ ጸቃውዕ ከመ ያመዓርዕሮን ለጉርኤከ። ምሳ.24፣53 ሠለስቱ ዘአዳመ የሐውሩ ወራብዕሰ ዘሰናይ ፍናዊሁ ዕጓለ አንበሳ ዘይጸንእ እም እንስሳ ኢይትመየጥ ወኢይደነግጽ እም እንስሳ።

ቅዱሳን፣ መሥዋእት

ምሳ.10፣6 በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርእሰ ጻድቃን። ገክረ ጻድቃን ምስለ ውዳሴ። የጻድቃን ስም አጠራር ከምስጋና ጋራ ሲጠራ ይኖራል። ወስመ ረሲዓን ይጠፍዕ። ምሳ.10፣8 ጠቢብ ይትዌከፍ ትእዛዘ ነቅዐ ሕይወት ውስተ አፈ ጻድቃን። ምሳ.11፣2 በኂሩተ ጻድቃን ትረትዕ ሀገር። በበረከቶሙ ለራትዓን ትትሌአል ሀገር። ወበአፉሆሙ ለረሲዓን ትትገፈታዕ። ምሳ.12፣21 ኢያሠምሮ ለጻድቅ ምንትኒ እኩይ። ምሳ.15፣8 መሥዋእተ ረሲዓን ርኩስ በጎበ እግዚአብሔር። ወጸሎተ ኄራንሰ ጎሩይ ሎቱ። ምሳ.18፣10 ዓቢይ ኃይል ስመ እግዚአብሔር ወኪያሁ በደግኖ ጻድቃን ተለዓሉ። ምሳ.24፣16 ስብዐ ይወድቅ ጻድቅ ወይትነሣእ። ወረሲዓንሰ የአክዩ በእኩይ።

ስድብ፣ ጉቦ፣ ስካር

ምሳ.11፣2 ጎበ ቦ ጽእለት ህየ ሀሎ ኃሣር። ምሳ.14፣3 እም አፈ አብዳን ይወጽእ በትረ ጽእለት። ምሳ.15፣27 የጎጉል ርእሶ ዘጎልያነ ይነሥእ። ወዘይጸልእሰ ነሲአ ጎልያን ይድኅን። ምሳ.20፣1 እኩይ ወይን ለጸዐሊ ወለሰካሪ። ምሳ.20፣3 ክብሩ ለብእሲ ተከልዖ እም ጽእለት። ምሳ.24፣61 ባሕቱ መኳንንት መዐትማን እሙንቱ ወይነ ኢይስተዩ ከመ በስታይ ኢይርስእዋ ለጥበብ ወኢይክሉ አርትዖ ፍትሕ ለድኩማን።

ደስታ፣ ደግ ሴት፣ ክፉ ሴት

ምሳ.12፣25 መደንግጽ ቃል የሐውክ ልበ ብእሲ ጻድቅ። ወዜና ሠናይሰ ያስተፌሥሕ ልበ። ምሳ.15፣19 ልብ እም ከመ ትትፌሣሕ ትበርህ ገጽ ወእመሰ ተነዝን ትዴምን። ምሳ.18፣22 ዘረከበ ብእሲተ ኄርተ ረከበ ሞገሠ። ምሳ.21፣19 ይኄይስ ነቢር ውስተ ገዳም እም ነቢር ምስለ ብእሲት መዓትምት ወመግዝዕት ወነባቢት። ምሳ.24፣17 እመ ወድቀ ጸላኢከ ኢትትፈሣሕ ቦቱ ወበተአቅፎቱ ኢትትዐበይ። በመሰነካከሉም አትታበይ። እስመ ይራኢ እግዚአብሔር ወኢይኤድሞ።

ሽንገላ፣ ዕጣ

ምሳ.16፣20 ቦ ፍናው ዘይመስላሁ ለብእሲ ርቱዓተ ወጽንፎኒ ይኔጽራ ማዕምቅተ ሲኦል። ምሳ.18፣18 ጋእዘ የጎድግ ዕጻ። ዕጣ ጠብ ክርክር ያስተዋል። ወማእከለ ጽኑዓን ይፈልጥ።

መከራ፣ ትዕግስት

ምሳ.17፣13 በክመ ይትፈተን ወርቅ ወብሩር በክውር ከማሁ ጎሩያነ ልብ በጎበ እግዚአብሔር። ምሳ.17፣27 መስተዐግሥ ብእሲ ጠቢብ።

ክባቴ አበሳ፣ ስም

ምሳ.17፣3 ዘየጎብዕ አበሳ ይፈቅድ ዕርቀ። ምሳ.22፣1 ይኄይስ ስም ሰናይ እም ብዕል ብዙኅ ወእም ብሩር ወወርቅ ሞገሥ አዳም።

ጓደኛ፣ ጸጋ፣ ሀብት (ኢኮኖሚ)

ምሳ.17፣17 በኩሉ ጊዜ አፍሪ አርከ ወአኃው በምንዳቤ ይከውኑ በቋዕያነ። ምሳ.18፣10 ሀብት ብእሴ ያሌዕል። ምሳ.24፣4 ኩሉ ክብር ወብዕል ሰናይ። ምሳ.24፣32 ኢተሀበኒ ብዕለ ወንዴተ አላ ሥራዕ ሊተ ዘይትፈቀድ ወዘየአክለኒ። ከመ አዕቢልየ ሐሳዌ ኢይኩን ወኢይበል መኑ እግዚአብሔር ወእመ አኮ ነዲይየ ኢይስርቅ ወኢይምሐል በስመ እግዚአብሔር በሐሰት።

ፍርሀት፣ፍርድ

ምሳ.18፣8 ሐካይያን ያበዝኑ ፍርሀተ። የማያርሱ የማይቆፍሩ የማይጽፉ የማይደጉሡ ሀኬተኞች ሰዎች ፍርሀትን ያበዛሉ እንራብን እያሉ። ምሳ.24፣38 ኃፊረ ገጽ በፍትሕ አኮ ሠናይ በፍርድ ጊዜ የሰው ፊት ማፈር በጎ አይደለም።

መረዳዳት፣ ሥርዓት

ምሳ.18፣19 እኁ ምስለ እኁ ዘይትራዳእ ከመ ሀገር ጽንእት ወልእልት። ምሳ.22፣28 ወኢትንሥት ሥርዓተ ዘለዓለም ዘአንበሩ አበዊከ።

ተግሣጸ ሰሎሞን

መከራ፣ ንጽሕና፣ ትእግሥት፣ መቅሰፍት

ተግ.1፣4 አጽርዮ ለብሩር ዘኢኮነ ፍቱነ። ያልጠራ ብርን መላልሰህ በክውር አጥራው ወይነጽሕ ለከ ንጹሐ ፍጹመ። ተግ.1፣15 በትእግሥት ስነ ሕይወት ትነግሥ። ተግ.3፣21 መከራሆሙ ለወርቅ ወለብሩር ርስነት። ወብእሲ ይትመከር በጎበ እለ ይቄድስዎ። ተግ.4፣2 በኃጢአተ ረሲዓን መቅሰፍት ይትነሣእ።

ተዐቅቦ፣ መመጠን

ተግ.1፣10 ተአቀብ ርእስከ ከመ ዝንጉገ ኢትኩን።ወዕቀብ ፍናዊከ በስነ ምግባሪከ በበጎ ሥራህ ስራህን ጠብቅ። ተግ.1፣15 ወልድየ መዓረ እምከመ ረከብከ ብላዕ በአቅም ከመ ኢትጽገበ ወኢትቂዕ።

መምህራን፣ ኖላዊነት

ተግ.1፣10 ውጽቦ ወርቅ ውስተ እንቄ ሰርድዮን ዘብዙኅ ሜጡ ውዱድ ከማሁ ቃለ ጠቢብ ውስተ ዕዝነ ዘይሰምእ ሰናይ ውእቱ። ተግ.3፣23 አእምሮ አእምር መንፈሰ መራእይከ። የመንጋህን ባሕርያቸውን ፈጽመህ እወቅ እንዲያሻቸው አውቀህ ከለመለመ ሳር ከጠራ ውሃ አድርሳቸው። ተግ.5፣17 መሀር ወልደከ ወየዐርፈከ።ልጅህን አስተምር ከድካም ከኀዘን ያሳርፍሀል። ወይሁብ ሠርጐ ለነፍስከ። በኃጢአ መምህር ይበዝኑ ኃጥዓን። ኢይሄልዎ መምህር ለሕዝብ ኃጥዕ ለኃጥዕ ወገን መምህር የለውም።

ኀዘን፣ እርግማን፣ ማሸሚጠጥ

ተግ.1፣20 ከመ ነቀዝ ለዕዕ ወቁንቁኔ ለልብስ ነቀዝ እንጨትን ውስጥ ውስጡን እንዲበላው ብል ልብስን እንዲያጠፋው ከማሁ ኀዘን ለብእሲ ታማስን ልቦ። ተግ.2፣2 መርገም ዘበከንቱ ኢይበጽሕ ኀበ መኑሂ። በከንቱ የሚራገሙት መርገም የገዘቱት ግዝት ከማንም ከማን አይደርስም። ተግ.3፣11 አርኅቅ እምኔከ ቃለ ዝንጉጌ የሸሙጥን ነገር ከአንተ አርቅ።

ፍቅር፣ ለክፉ አለመመለስ

ተግ.1፣20 እመ ርኅበ ጸላዒከ አብልዖ ወእመ ጸምዐ አስትዮ።ወእግዚአብሔር የአስየከ ሰናያተ። ተግ.2፣4 ወልድ ኢታውስኦ ለአብድ በከመ ዕበደ ዚአሁ ከመ ኢትኩን ከማሁ።

ኀፍረት (ማፈር)፣ አንድምታ

ተግ.2፣11 ቦ ኃፍረት እንተ ታመጽእ ኃጢአተ። ኃጢአትን የምታመጣ ኃፍረት አለች። ሰውን አፍሮ ፈርቶ ጾም መግደፍ ሐሰት መፍረድ ሐሰት መመስከር ነው። ወቦ ኃፍረት ለክብር ወለስብሐት ክብር ሊሆን የሚያፍሩት ኃፍረት አለ። እግዚአብሔርን አፍሮ ፈርቶ ጾም መጾም እውነት መፍረድ እውነት መመስከር ነው። (ሰሎሞን በዓለም ላይ የሚደረገውን ድርጊት የፍጥረታት ጸባይ ሁኔታ ሁሉ በጣም እያብራራ ጽፏል። ስለዚህ ማንኛውንም ፍጥረት ከነድርጊቱ ማወቅ መልካም ነው ማለት ነው።ማስተማሪያም ይሆናል)። ተግ.4፣21 ዘኢየኃፍር ገጸ ጻድቃን አኮ ኄር። የጻድቃንን ፊት አይቶ የማያፍር ሰው ግን በጎ አይደለም።

በሰው ነገር ጥልቅ አለማለት፣ ቁጣ፣ ምቀኝነት

ተግ.2፣17 ከመ ዘይእኅዝ ዘነበ ከልብ ከማሁ ዘይቀውም በነገረ ባዕድ። በኃጢአ ዕጸው ይጠፍእ እሳት ወበብዝኀ እጸው ይነድድ እሳት ወበኀበ ኢሀሎ መዓትም የሐስዕ ኃእዝ። ዘይክሪ ግበ ለቢጹ ይወድቅ ውስቴቱ። ተግ.5፣22 ብእሲ መዓትም ይክሪ ኃእዘ ወብእሲ ቁጡዕ ከረየ ኃጢአተ።

ፍቅር፣ ምጽዋት፣ ተአምኖ

ተግ.3፣5 ይኄይስ ዘለፋ ክሡት እምኀ ቡዕ ፍቅር ከተሰወረ ፍቅር የኀላ ጠብ ይሻላል። ይኄይስ

ፍቅዐት ዘአርክ እም ሠናይ ስእመተ ጸላሚ። ይኄይስ አርክ ቅሩብ እም እጉ ዘርጉቅ የኀድር። ተግ.3፣11 ሐጺን ለሐጺን ያበልሖ። ብረት ብረትን ይስለዋል። ወብእሲ ያበልሖ ገጸ ካልዐ። ከመ ኢይትማሰል ገጽ ገጸ ከማሁ ልበ ሰብእኒ ኢይትማሰል። ተግ.4፣27 ዘይሁብ ለነዳይ ጽኑሰ ኢይጸነስ ወዘሰ ይመይጥ ዓይኖ ውስተ ዓቢይ ተጽናስ ይሄሉ። ተግ.5፣22 ወዘሰ ተአመነ በእግዚአብሔር ይድኅን።

ቅዱሳን፣ ንጉሥ

ተግ.4፣12 በረድኤተ ጻድቃን ይከውን ብዙኅ ስብሀት። ወበፍናወ ረሲዓን ይትኀሳሉ ሰብእ። ተግ.5፣4 ንጉሥ ጻድቅ ያነሥእ ሀገረ። ጻድቅ ንጉሥ ሀገርን ያቀናል። ወብእሲ ዓማፂ ይነሥት። በደለኛ ሰው ግን ሀገርን ያጠፋል። ሰብእ ጸዋጋን አንደዱ ሀገረ። ወጠበብትሰ ሜጡ መዓተ። ተግ.5፣22 ምኑን ብእሲ ጻድቅ በኀበ ብእሲ ገፋኢ ወርኩስ ለኃጥዕ ፍኖት ርትዕት።

ንሥሓ

ተግ.4፣13 ዘይከድን አበሳሁ ኢይረትእ ፍናዊሁ ወዘሰ ይነግር ወይዘልፍ ገሀደ ይትፈቀር። ወዘሰ ይጸልእ ዓመፃ ነዋኃ መዋእለ የሐዩ።

ትእቢት፣ ስድብ፣ ትሕትና

ተግ.5፣22 ትእቢት ወጽእለት ያቴሕት። ወለትሑተ ሕሊናሰ ያቀርቦ እግዚአብሔር ለክብር።

ደግ ሴት

ተግ.5፣27 ብእሲተ ጽንእተ እመቦ ዘረከበ ክብርት ይእቲ እም እንቁ ክቡር ዘብዙኅ ሜጡ። ለእንተ ከመዝ ብእሲት ይትአመን ልበ ምታ። ትትራድኦ ለምታ ሠናየ በሠናይ ወአኮ እኩየ በእኩይ በኩሉ መዋእለ ሕይወታ። እንዘ ትባዝት ጸምረ ወአጌ ገብረት ሠናየ በእደዊሃ። ወትትነሣእ በሌሊት ወትሁብ ሲሳየ ለሰብአ ቤታ። ወእመታ ታጸንእ ለፈቲል። ወእራኃ ሰፍሐት ለነዳያን። ሕግ ወምጽዋት ውስተ አፉሃ። ወአፉሃ ፈትሐት በጥበብ ወበሥርዐተ ሕግ እስመ ብእሲት ጠባብ ትትባረክ ወፈራሂተ እግዚአብሔር ይእቲ ትሴባሕ።

ጥበበ ሰሎሞን

አንድምታ

ቋንቋ፡- ጥበበ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ዘነግሠ በኢየሩሳሌም። ዘነግሠን ለዳዊት ለሰሎሞንም ቢቀጽሉ የተመቸ።

ጥቅስ፡- እንዲል እንዲል የሚሉት ከሌላ መጽሐፍ ጥቅስ ያሉ ናቸው። የአንዳንዶችን በቅርበት ስናገኘው የአንዳንዱ ግን ከየት እንደሆነ አይታወቅም እንግዲህ አባቶቻችን ብዙ መጻሕፍት አንብበው ስለጻፉት መፈለግ ነው።

መኳንንት፣ ሐልዮ፣ መምህራን

ጥበ.1፣1 አፍቅርዋ ለጽድቅ ኦ መኳንንተ ምድር ወሐልዩ ኃይለ እግዚአብሔር። እስመ ጠዋይ ሕሊና ያርኅቅ እም እግዚአብሔር። ጥበ.4፣25 እስመ ብዝኀ ጠበብት መድኃኒተ ዓለም።

እግዚአብሔር

ጥበ.1፣8 እስመ መንፈሰ እግዚአብሔር መልዐ ዓለመ። ወዘይእኅዝ ኩሎ ዓለመ ያገምር አእምሮ ቃሎሙ። ወበእንተ ዝንቱ ኢይትኃባዕ እምኔሁ ወኢምንትኒ እምዘይትናገሩ ቃለ ዓመፃ። ጥበ.7፣41 እስመ ኢይስዐኖ ለእዴከ እንተ ኩሎ ይክል። ወየማንከ እንተ ፈጠረት ዓለመ እምነ ከንቱ ዘአልቦቱ ገጽ። (ዓለምን እምኀበ አልቦ ለመፍጠሩ ማስረጃችን ይህ ነው)። ወባሕቱ ኩሎ በአቅም ወበኀልቀ ወበመዳልው ሠራዕከ። እስመ ዕበየ ክህሎትከ ህልው ኀቤከ ዘልፈ። ትምሕር ኩሎ እስመ ከሀሊ አንተ ላዕለ ኩሉ። ወትትሐየይ ኃጣውዕ ሰብእ እንዘ ትጸንሖ ለንሥሓ። ወአልቦ ዘትሜንን ምንተኒ እምዘገበርከ ትምህክ ወትሣሃል ላዕለ ኩሉ ፍጥረት። ጥበ.8፣1 ኦ እግዚኦ መፍቀሬ ሰብእ እንቲአከ ይእቲ ጥበብ። እስመ ቅንየትከ ወምልክናከ ኩሎ ይሬስየከ ትሣሀል ላዕለ ኩሉ። ጥበ.12፣18 ተበቀላ ለይእቲ ሌሊት ቃልከ መዋኢ ወጸባዒ ወመስተቃትል ዘይክል ኩሎ። ጥበ.13፣34 ወበኩሉ መካን አንተ ትሄሉ ህየ።

ነጎርጓር፣ ሐሜት፣ ሞት፣ ዝሙት

ጥበ.1፣13 ተዐቀቡኬ እም ነጎርጓር ዘኢይበቁዕ እም ሐሜት ባልሑ ልሳነክሙ። ጥበ.1፣18 እስመ እግዚአብሔር ኢገብረ ሞተ ወኢያስተኤድሞ ኃጉሎሙ ለሕያዋን ወረሲዓንሰ በእደዊሆሙ ወበቃሎሙ ጸውዕዎ ወአርከ አምሰልዎ። ጥበ.9፣10 እስመ ቀዳሚሃ ለዝሙት ሐልዮ ውስተ ፈጠራሁ ለጣዖት።

ሰዱቃውያን፣ ትእቢት፣ ክፋት

ጥበ.1፣25 እስመ ጎዳጥ ውእቱ ንብረትነ ወማኅዘን ወአልቦ ፈውስ ለሞተ ብእሲ ወአልቦ ዘተአምረ ዘገብአ እም ሲኦል እስመ በከ ለሊነ ተፈጠርነ። ወእም ድኅረዝ ንከውን ከመ ዘኢተፈጠርነ። እስመ ከመ ጢስ እስትንፋስ ውስተ አንፍነ። ወእም ከመ ጠፍአ ሥጋነ ሐመደ ይከውን። ወመንፈስነሂ ይትከአው ከመ ሳሕወ ደመና። ንዑኬ ንትፈጋዕ በዘሀሎ ሰናያት ይላሉ። ጥበ.3፣11 ምንት በቁዐነ ትዕቢት ወምንተ አምጽአ ላዕሌነ ብዕል ምስለ ትዕቢት ኃላፊ ውእቱ ዝንቱ ከመ ጽላሎት። ጥበ.3፣28 ወገቢረ እከይ ይገፈትዕ መናብርተ ኃያላን።

ቅዱሳን፣ ክፉ ትውልድ

ጥበ.1፣60 ነፍሶሙሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ስቃይ። ጥበ.1፣80 እስመ ለትውልድ ዓማፂት እኩይ ደኃሪታ። ጥበ.2፣20 ወብእሲሰ ጻድቅ መዊቶ ይኬንን ረሲዓነ እንዘ ሀለው ሕያዋኒሆሙ። ጥበ.3፣20 ወጻድቃንሰ ርቱዓን ለዓለም የሐይው ቀና የሚሆኑ ጻድቃን ግን ለዘላለሙ በደስታ ይኖራሉ። ወጽኑሕ አስቦሙ በኀበ እግዚአብሔር። በእንተዝ ይነሥኡ መንግሥተ ክብር ወቀጸላ ስን እም እደ እግዚአብሔር።

መጽሐፈ ሰሎሞን መክብብ

ይህንንም በሕጻንነቱ የሠራው ስራ እንዳልረባው እንዳልጠቀመው አይቶ ከአረጀ በኋላ ንሥሓ ገብቶ ተናግሮታል። ይኸውም ከንቱ ከንቱ ይቤ መክብብ በማለቱ ይታወቃል።

የዓለም ከንቱነት፣ ውዳሴ ከንቱ

መክ.1፣2 ከንቱ ከንቱ ይቤ መክብብ ኩሉ ከንቱ። ምንት ፍድፋዴሁ ለሰብእ በኩሉ ጻማሁ ዘይጻሙ እም ታሕተ ፀሐይ። ትውልድ የኀልፍ ወትውልድ ይመጽእ። ይሠርቅ ፀሐይ ወየዐርብ ፀሐይ። ወኩሎሙ ውኂዛት የሐውሩ ውስተ ባሕር ወባሕርኒ ኢኮነት እንተ ትመልእ ውስተ መካና። ወኢይጸግብ ዓይን በርእይ ወኢይመልዕ እዝን በአጽምዖ ርኢኩ ኩሎ ፍጥረተ ዘተገብረ በመትሕተ ፀሐይ ወናሁ ኩሉ ከንቱ። መክ.2፣8 አስተጋባዕኩ ብዙኀ ብሩረ ወወርቀ ወጥሪተ መንግሥት ወበሐውርተ ኃይላት ወኃላይያነ ወፍግዐ ምስለ ውሉደ ሰብእ። ወናሁ ኩሉ ከንቱ። መክ.10፣16 ሐተታ በሕጻንነት በሚሰራው ሥራ ውዳሴ ከንቱ አለበት። በእርግና በሚሰራው ስራ ውዳሴ ከንቱ የለበትም። ትምክህትን ከልቡናህ አርቅ።

አንድምታ፣ ሰው፣ ንጽሕና

መክ.2፣8 እስመ ለጠቢብ አዕይንቲሁ ዲበ ርእሱ። የብልሁ ዓይኖቹ በራሱ ላይ ናቸው አለ ሰማያዊ ነገር ያስባልና። (በግብር እንደተረጎመው አስተውል)። መክ.3፣19 ምንት ፍድፋዴሁ ለሰብእ እም እንስሳ። መክ.9፣8 በኩሉ ጊዜ ይኩን አልባሲከ ንጹሐ። መክ.12፣1 ከንቱ ከንቱ ይቤ መክብብ ኩሉ ከንቱ። ደግ መጽሐፍ ከሆነ በጀመረበት ይጨርሳልና እርሱም በጀመረበት ጨረሰ።

ሞት

መክ.2፣16 እስመ ናሁ መዋዕል ይመጽእ እነሆ መዋእለ ሞት ይመጣልና። ወኩሉ ይትረሣእ ሁሉ በሞት ይዘነጋልና። እስመ ኩሉ ከንቱ። ጸላእኩ አነ ኩሎ ሥራህየ ዘአነ እሠርህ እም ታሕተ ፀሐይ እስመ አኀድጎ ለሰብእ ዘይትወለድ እም ድኅሬየ ወመኑ የአምር እመ ጠቢበ ይከውን ወእመ አኮ አብድ። ወእመ ይሜለጥ በኩሉ ሥራኅየ ዘሠራኅኩ።

ዘመን

መክ.3፣1 ቦ ለኩሉ ዘመን ወቦ ጊዜ ለኩሉ ምግባር እም ታሕተ ፀሐይ። ጊዜ ለጸኒስ ወጊዜ ለወሊድ ጊዜ ለሕይወት ወጊዜ ለመዊት። ጊዜ ለሐኒጽ ወጊዜ ለነሚት ጊዜ ለብካይ ወጊዜ ለሰሐቅ ለሰሐቅ ምን ጊዜ አለው ቢሉ ወንድም በለእንጀራ ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ ፊት ያጠቆሩበት እንደሆንነ ወንድሜ የእኔን መምጣት ጠልቶ ነው እንዳይል ስቆ መቀበል ይገባልና ጊዜ ለሰሐቅ አለ። ጊዜ ለአርምሞ ወጊዜ ለተናግሮ።

አንድነት፣ ጥበብ

መክ.4፣9 ይኄይስ ክልኤቱ እም አሐዱ እለ ቦሙ አስብ ሰናይ በጸማሆሙ እስመ እመ ወድቀ አሐዱ ያነሥዖ ካልዑ። አሌ ሎቱ ለአሐዱ እመ ወድቀ አልቦ ካልእ ዘያነሥኦ። ወፈትል ሥሉስ ኢይትበተክ። መክ.9፣18 ትኄይስ ጥበብ እምንዋየ ሐቅል።

ተዐቅቦ፣ መምህራን፣ ንጉሥ

መክ.5፣1 ዕቀብ እገሪከ ሶበ ተሐውር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ወቅረብ ለሰሚአ ትምህርቶሙ ለጠቢባን። ዓዲ ተዐቀብ ከመ ኢትኅጕዕ በአፉከ። በእንተዝ ይኩን ነገርከ ጎዳጠ (ከመናገርህ በፊት የምትናገረውን በቃለ እግዚአብሔር መዝነው። ተመዝኖ ካለፈ ተናገረው ካላለፈ ዝም በል)። መክ.10፣16 አሌ ለኪ ኦ ሀገር እንተ ንጉሥኪ ወሬዛ። ወመኳንንትኪ ይበልዑ በነግህ።

ፍቅረ ንዋይ፣ተዘክሮ፣ሐልዮ

መክ.5፣10 ዘያፈቅር ብሩረ ኢይጸግብ ብሩረ። መክ.7፣13 ርኢ ተግባሮ ለእግዚአብሔር። መክ.10፣3 ወዘይኄሊ ኩሎ አብድ ውእቱ። መክ.12፣1 ተዘከሮ ለፈጣሪከ በመዋዕለ ውርዙትከ ዘእንበለ ይምጻእከ መዋዕል እኩይ።

መኃልየ ሰሎሞን

እግዚአብሔርን በመርአዊ ቤተ እስራኤልን በመርዐት መስሎ የሚናገር ነው። ይህንንም ጦር ያልጠፋለት ምስጢሩን የማያውቅ ሰው ሊጸልየው አይገባም።

ውበት፣ ቆናጽል፣ መቅጫ

መኃ.1፣5 ጸላም አነ ወሠናይት እም አዋልደ ኢየሩሳሌም። መኃ.2፣15 አስግሩ ለነ ቆናጽለ ንዑሳነ እለ ያማስኑ ዓፀደ ወይንነ ዓፀደ ወይንነ ይጽጊ። መኃ.5፣1 ሀተታ የአይሁድ ውግረት የባቢሎን ግበ አናብስት የፋርስ እቶነ እሳት የሮም ስቅለት ነው።

መጽሐፈ ሲራክ

አንድምታ

ታሪክ፦ ዘኢያሱ ሲራክ። ሲራክ የግብር ስሙ ነው። ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። ይህ ሌላ ኢያሱ ነው። በዘመኑ የነበረ ድምትርያስ ድምጥርያስ ይባላል። የጽርእ ንጉሥ ነው። አለቃም ነው ይሉታል። ጠጅ አሳላፊው ተጣልቶ ወደ ኢያሱ ሲራክ ሄዶ ተሰወረ። ከብዙ ዘመን በኋላ ታርቆ ገባ። የት ነበርህ አለው። በኢያሱ ሲራክ ዘንድ ነበርሁ አለው። ወዳጄ ስለው እንዲህ አደረገኝ ብሎ አምጥቶ አሥሮ አጋዘው በዚያው በተጋዘበት ሳለ መከራውን ታግሦ ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መንፈሳዊ ግለጽልኝ ብሎ ለመነ። ተገልጾለት ይህንን ተናግሯል። (ይህንን ታሪኩን ካልጠየቅህ አታውቀውም ቅዱሳን ሊቃውንት ስለዚህ ከሌላ መጻሕፍት ያገኙትን ወይም ሲወርድ ሲዋረድ የተነገረውን ስለጻፉልን ምስጋና ይገባቸዋል)።

ጥበብ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር

ሲራ.1፣1 ቀዳሚሃ ለኩላ ጥበብ እም ኀበ እግዚአብሔር ይእቲ። ሲራ.1፣26 ጥበብኒ ወአእምሮኒ ፈሪሀ እግዚአብሔር ውእቱ ወፈቃዱኒ ሃይማኖት ወየውሃት። ሲራ.2፣15 እለ ይፈርህዎ ለእግዚአብሔር ያስተዳልው ልቦሙ። እለ ይፈርሁ ለእግዚአብሔር ኢይረስዑ ቃሎ። ወእለ ያፈቅርዎ የአቅቡ ትእዛዞ ወፍናዊሁ። ሰውን ፈርተን በገሀነም ከምንወድቅ እግዚአብሔርን ፈርተን በዓላውያን እጅ ብንወድቅ ይሻለናል። ሲራ.36፣15 ወምስለዝ ኩሉ ርኢ ግብሮ ለልዑል። ወጉርኤ ይፈልጦ ለኩሉ ጣዕመ እክል። ሲራ.41፣15 ይኄይስ ብእሲ ዘየኀብእ እበዲሁ እምነ ብእሲ ዘይከብት ጥበቢሁ።

ደስታ፣ ፍቅር

ሲራ.1፣11 ፈሪሀ እግዚአብሔር ትፍሥሕተ ልብ ውእቱ ወይሁብ ሐሴተ ወያስተፌሥሕ ወያነውኅ መዋዕለ ሕይወት። ሲራ.6፣1 ኩን ዐርከ እም ትኩን ጸላኤ። ሲራ.7፣11 ወኢትሥሐቅ ላእለ ብእሲ ኀዙን ባዘነ ሰው አትዘብትበት። አንተን አሳዝኖ እርሱን ደስ የሚያሰኝ እግዚአብሔር አለና። ሲራ.7፣20 ወኢታሕሥም ላዕለ ነባሪከ ዘበጽድቅ ይትቀነይ ለከ። ሲራ.8፣6 ኢትትፈሣህ ላእለ ዘሞተ። ተዘከር ከመ ኩልነ ንመውት። ሲራ.12፣9 ትፍሥሕትከ ያቆስሎሙ ለጸላእትከ።

ትዕግሥት፣ ረድኤተ እግዚአብሔር፣ ተአምኖ

ሲራ.1፣22 እስከ ተኀልፍ ጊዜሃ ተዐገሣ ለመዓት ወድኅረ ታስተፌሥሐከ። ሲራ.2፣4 ወተወከፍ ኩሎ እንተ በጽሐተከ ወተዐገሥ በመዋዕለ ተጽናስከ። እስመ በእሳት ያሜክርዎ ለወርቅ ወለብእሲኒ ጻድቅ በሕማመ ተጽናስ ያሜክርዎ። ተአመኖ ዳዕሙ ለእግዚአብሔር ወይረድኦከ። ወአርትእ ፍናዊከ ወተወከል ቦቱ። እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር ጽንሕዋ ለምሕረቱ። እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር ተአመንዎ። እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር ተሰፈውዋ ለሰናይቱ። ርእዩ ቀደምተ ዓለም ወአእምሩ መኑ ዘተአመነ በእግዚአብሔር ወተኀፍረ። እስመ መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር ወመስተሣህል የኀድግ ኃጢአተ ወያድኅን በዕለተ ምንዳቤ። ሲራ.28፣1 ዘይትኤገሥ ለእግዚአብሔር ይትቤቀል ሎቱ ወኃጢአቶኒ የኀድግ ሎቱ። መከራ ቢመጣበት ሳይቆጣና ሳይበሳጭ ለሚታገሥ እግዚአብሔር በቀሉን ይመልስለታል። ኃጢአቱንም ያስተሰርይለታል።

ኑፋቄ፣ ኃጢአት፣ ሐሜት፣ ኃጥዓን

ሲራ.2፣12 አሌ ሎቱ ለልብ ዘይናፍቅ።እስመ ኢተአመነ ወእንበይነዝ ኢያመስጥ። ሲራ.5፣5 ኢትወስክ ኃጢአተ በዲበ ኃጢአትከ እንዘ ትብል ብዙኅ ምሕረቱ ለእግዚአብሔር። ምሕረትኒ መቅሰፍትኒ እም ኀቤሁ። ላዕለ ኃጥእ ይወርድ መቅሰፍቱ። ሲራ.5፣13 ኢትኩን ሐማዬ ወኢትዝለፍ በልሳንከ። ሲራ.7፣17 እስመ ፍዳሆሙ ለኃጥዓን ዕጹ ወእሳት። ሲራ.8፣5 ኢትትሀበቦ ለዘይትጋነይ በእንተ ጌጋዩ ተዘከር ከመ ኩልነ ኃጥዓን ንሕነ።

እናትና አባትን ማክበር

ሲራ.3፣3 ዘያከብር አባሁ ይትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ። ዘያከብር አባሁ ይትፌሣሕ በውሉዱ ወበእለተ ጸሎቱ ይሰምዖ ፈጣሪሁ። ዘያከብር አባሁ ይነውኅ መዋእሊሁ። በቃልከኒ ወበምግባሪከኒ አክብሮ ለአባከ ከመ ትብጻሕከ በረከቱ።መድኅረ አብ ያጸንዕ አብያተ ውሉድ ወመርገመ እም ይሜሩ መሠረተ። የአባት ምርቃት የልጆችን ቤት ያጸናል። የእናትም መርገም ሥር መሰረትን ያጠፋል። ወልድየ ጹር ርስዓኒሁ ለአቡከ ወኢታኅዝኖ በሕይወቱ። ወእመኒ ልኅቀ ወነጥአ ልቦ ኦሆ በሎ ለግእዙ። ወአክብሮ በአምጣነ ትክል። ወኢታስተአክዮ በርስዓኑ። ጽሩፍ ውእቱ ዘይገድፎ ለአቡሁ ወርጉም ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ዘያምዕዓ ለእሙ።

ትሕትና፣ ትእቢት

ሲራ.3፣18 በአምጣነ ዕበይከ ከማሁ አትሕት ርእሰከ። ወትረክብ ዕሤተከ በኀበ እግዚአብሔር። ወለብዙኃን አስሐቶሙ ትዝሕርቶሙ ወለብዙኃን አውደቆሙ ትዕቢተ ልቦሙ። መንሱቶሙ ለዕቡያን አልባቲ ፈውስ እስመ እኩይ ተክል ገብረ ላዕሌሆሙ ሥርወ። ሲራ.4፣27 ወኢታትሕት ርእሰከ ለብእሲ አብድ ወኢታድሉ ለገጸ ዓቢይ። ሲራ.5፣13 በኀበ ዓቢይኒ ወኀበ ንዑስኒ አስተርኢ ኄረ። ሲራ.10፣11 ወእም ከመ ሞተ ሰብእ ይከውን ክፍለ ዕጹ። ቀዳሚሃ ለትእቢት ታወጽኦ እም እግዚአብሔር ወታክህዶ ልቦ እምነ ፈጣሪሁ። ሲራ.11፣4 ኢትዘኃር በስነ አልባሲከ። በመዋእለ ክብርከኒ ኢታዕቢ ርእሰከ።

ምጽዋት፣ ያዘነ ሰው፣ ፍትሐት፣ መባዕ፣ መሥዋእት

ሲራ.3፣30 ለእሳት እንተ ትነድድ ያጠፍዓ ማይ ወምጽዋት ታኅድግ ኃጢአተ። ሲራ.4፣1 ወልድየ ኢትክልዖ ለነዳይ ሕይወቶ ወኢትሚጥ አዕይንቲከ እምዘይስእለከ። ሲራ.4፣2 ወኢታሕምም ነፍሰ ኅዝንተ ወኢታምዕዕ ብእሴ ኅዙነ። ወኢታደንግጽ ልበ ትኩዘ። ወለነዳይ አጽምዖ በእዝንከ ወአውስእ ሠናየ ቃለ በየውሃት። ወአድኅኖ ለግፉዕ እም እደ ገፋኢሁ። ኩኖ ለእኃለ ማውታ ከመ አቡሁ። ሲራ.7፣33 ወለዘሞተሂ ኢትኅድግ ጸግዎ። ለሞተም ሰው መስጠትን አትተው። በዘመናቸው ሽቱ መቀባት ነበረ በዘመናችን ፍትሐት ማስፈታት ተዝካርንም ማውጣት ነው። ሲራ.14፣11 ወአብእ መባዓ ለእግዚአብሔር በዘይደልወከ። ሲራ.29፣2 ለቅሑ ለቢጽከ አመ ተጽናሁ። ሲራ.31፣21 ርኩስ መሥዋእቱ ለመባዓ ዓመፃ። ወግሙን ቁርባኖሙ ለኃጥዓን ወኢይትዌከፎሙ መባዖሙ ለረሲዓን። ሲራ.32፣1 ዘየዐቅብ ሕጎ ያበውዕ መባዓ። ወዘያጸምዕ ትእዛዞ ይሠውእ ለመድኃኒቱ። እሴቶ ያገብእ ዘያበውእ ስንዳሌ። ሲራ38፣16 ብኪ ወልድየ ላዕለ ዘሞተ ወበከመ ግዕዙ ግበር ሎቱ ተዝካሮ። ዘሞተሰ አዕረፈ ወባሕቱ ግበር ሎቱ ተዝካሮ ወእምዝ ንግፍ ላሐከ።

ፍርድ፣ ኀፍረት፣ ንጉሥነት፣ ሊቃውንት

ሲራ.4፣27 ኢታድሉ በሐሰት በእንተ ነፍስከ። እስመቦ ዘበኀፍረት ይገብር ኃጢአተ ወቦ ዘበኀፍረት ይገብር ጽድቀ። ሲራ.7፣6 ወኢትፍቅድ ከዊነ መኮንን። ሲራ.10፣1 ንጉሥ ጠቢብ ይጌሥጽ አሕዛቢሁ ወመኮንን ለባዊ ይገብር ሥርዓተ። ንጉሥ አብድ ያኃጉል አሕዛቢሁ ሀገርኒ

ትጸንዕ በጥበቢሆሙ ለሊቃውንቲሃ። ሲራ.10፣23 አኮ ርቱዕ ያስተአክይዎ ለነዳይ እንበይነ ንዴቱ ወአኮ ርቱዕ ያክብርዎ ለብእሲ ኃጥዕ እንበይነ ብዕሉ። ሲራ11፣2 ኢታድሉ ለሰብእ እንበይነ ላሕዩ ወኢታስተአክዮ ለሰብእ እንበይነ ሕሠሚሁ። ሲራ.11፣6 ኢትሐስ ዘእንበለ ትሕትት ጠይቅ ቅድመ ወድኅረ ትጌሥጽ ዘእንበለ ትስማእ ኢታውስእ። ወውስተ ነገረ ባዕድ ኢትባዕ። ሲራ.27፣7 እንበለ ትጠይቆ ለሰብእ ኢትንዐዶ ስራውን መርምረህ ሳትረዳው ሰውን አታመስግነው።

ስማዕትነት፣ ነቢብ

ሲራ.4፣28 እስከ ትበጽሕ ለሞት ተበዐስ በእንተ ጽድቅ። እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ይትበዐስ በእንቲአከ። ሲራ.5፣10 አስምክ ላዕለ ጥበብከ ወአሐደ ይኩን ቃልከ ወኩን ፍጡነ ለሰሚዕ ወመስተዐግሥ ለአውስዖ ቃል። ኃሣርከኒ ወክብርከኒ እምቃልከ ወእምልሳኑ ለሰብእ ድቀቱ።

መጻሕፍት፣ ጸጋ

ሲራ.6፣35 ወኩሎ ነገረ መጽሐፍ አፍጥን ለሰሚዕ። ሐሊ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ወአንብብ መጻሕፍቲሁ በኩሉ ጊዜ ወውእቱ ያጸንዐከ ልበከ ወይሁበከ ታፍቅራ ለጥበብ። ሲራ.11፣16 ነድይኒ ወብዒልኒ እም ኀበ እግዚአብሔር። ሲራ.36፣2 ብእሲሰ ጠቢብ ያፈቅር መጻሕፍተ ወዘሰ ይናፍቅ ወኢይትአመን በመጽሐፉ ይከውን ከመ ሐመር እንተ ታንኮልል ማዕከለ ዓውሎ።

ትዳር፣ ካህናት፣ ጓደኛ

ሲራ.7፣25 አብጽሓ ለወለትከ በአቅማ ወዕቀባ ወለብእሲ ጠቢብ አስተዋስባ። ሲራ.7፣29 በኩሉ ነፍስከ ፍርሆ ለእግዚአብሔር ወአክብሮሙ ለካህናቲሁ ወበኩሉ ኃይልከ አክብሮ ለፈጣሪከ ወኢትኅድጎሙ ለእለ ይጸመድዎ ወሀቦ ክፍሎ ዘእዙዝ ለከ ቀዳምያተ። ሲራ.31፣26 ከመ ዘቀተለ ቢጾ ዘፈለጠ ብእሴ እም ብእሲቱ። ባልና ሚስትን የለየ ሰው ባልንጀራውን እንደገደለ ያለ ነው። ሲራ.36፣29 ዘአውሰበ ብእሲተ ኄርተ ረከበ ተድላሁ እስመ ረድኤቱ ወዓምደ ምስማኩ ይእቲ። ሲራ.37፣1 ቦ አርክ ለስም በከ ዘይትዓረክ። ወቦ ዓርክ ዘይከውነከ ጸላኤ ወቦ አርክ ዘይቀርበከ አመ ትፍሥሕትከ ወእም ከመ ተመንደብከ ውእቱ ይከውነከ ጸረከ። ወቦ አርክ ዘእንበይነ ከርሠ።

በሽተኛን መጠየቅ፣ ዘፈን፣ ማመንዘር

ሲራ.7፣35 ወኢትትሐከይ ሐውጾ ድውይ። ሲራ.9፣4 ወኢትዛዋእ ምስለ መሰንቃዊት ከመ ኢታሥግርከ በማኅሌታ። ሲራ.9፣8 ሚጥ ዓይነከ እምነ ብእሲት ሠናይት ወኢያፍቱከ ስና ለብእሲተ ባዕድ። ብዙኃን እለ ስህቱ በስነ ብእሲት። ኢትንበር ምስለ ብእሲተ ብእሲ። ሲራ.25፣21 ኢያሥሕትከ ላህያ ለብእሲት እስመ መቅሰፍት ወመንሱት ወዓባይ ኀሣር ይእቲ።

እግዚአብሔር፣ ነጻ ፈቃድ

ሲራ.12፣6 እስመ እግዚአብሔር ይጸልያሙ ለኃጥዓን ወይትቤቀሎሙ ለእኩያን። ሲራ.15፣12 ወኢትበል ውእቱ አስሐተኒ ውእቱሰ ኢይፈቅድ ብእሴ ኃጥአ። እስመ ኩሎ ርኩሰ ጸልዐ እግዚአብሔር። ወውእቱሰ ገብሮ ለእጓለ እመሕያው ቀዳሚሁ ወነደጎ በግእዙ ዘፈቀደ። ጥንቱንም እግዚብሔር ሰውን ክፉና በጎ በሚያውቅ ግዕዛን ፈጥሮ በወደደው ሊኖር ተወው። ናሁ አንበረ ለከ እሳተ ወማየ ከመ ትደይ እደከ ኀበ ዘፈቀድከ። ሕይወትኒ ወሞትኒ ቅድሜሁ ለእጓለ እመሕያው። ወዘኀረየ እም ውስቴቶሙ ይሁብዎ። እስመ ብዙኅ ጥበቢሁ ለእግዚአብሔር ወጽኑዕ ኃይሉ ወየአምር ኩሎ ወይሬኢ ወውእቱሰ አልቦ ዘአዘዘ ይግበር ኃጢአተ ወኢያብሖ ወኢለመኑሂ ከመ የአብስ። ሲራ.32፣5 ፈቃዱ ለእግዚአብሔር ከመ ኢትግበር እኩየ ወሥምረቱ ከመ ትትገኀሥ እም ዓመፃ። ኢትባዕ ቅድመ እግዚአብሔር ዕራቀከ። በፍሥሕ ዓይን አእኩቶ ለእግዚአብሔር ወኢትኅድግ አብያ እምውስተ ቀዳሚ ተግባርከ። ወእንዘ ትትሐሠይ አብዕ አሥራቲሁ ለተግባርከ እስመ እግዚአብሔር ያገብእ ዕሤተከ ወየዐሥየከ ምስብዒተ። ሲራ.39፣16 ዓቢይ ግብሩ ለእግዚአብሔር ወፈድፋደ ሠናይ። ወኩሉ ሥርዓቱ በበዕድሜሁ ወቅድሜሁ ውእቱ ግብረ ኩሉ ዘነፍስ ወአልቦ ዘይክል ተነብየ እም ቅድመ አዕይንቲሁ። እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወእስከ ለዓለም ኩሎ አእመረ ወአልቦ ምንትኒ ነኪር በቅድሜሁ።

ሞት፣ ምስጢር፣ ተዘክሮ

ሲራ.14፣11 ወተዘከር ከመ ኢይኅነዲ ዕለተ ሞት። ዘእንበለ ትመጥ አሠኒ ለቢጽከ ወለቤትከ ወበአምጣነ ትክል ስፋሕ እደከ ወሀብ። ኩሉ ግብር ይበሊ ወየኀልቅ ወገባሪሁኒ የኃልፍ ምስሌሁ። ወባሕቱ ብፁዕ ውእቱ እንዘ ጠቢብ ውእቱ ዘሞተ። ሲራ.19፣10 እስከ አመ ትመውት ኢታውጽእ ቃለ ዘሰማእከ ወተአመን። የዐነብዝ አብድ እስከ ይነግር ቃለ ዘሰምዐ። ሲራ.28፣5 ተዘከር ኃጢአትከ ወኅድጋ ለጽልዕ። ተዘከሮ ለሞት ወለመስና ወዕቀብ ትእዛዞ ተዘከር ሕጎ ወኢትትቀየም ቢጸከ። ሲራ.41፣3 ኢትፍራህ ኩነኔሁ ለሞት ተዘከሮሙ ለእለ እምቅድሜከ ወለእለ እምድኅሬከ እስመ ኩነኔ እግዚአብሔር ውእቱ ላዕለ ኩሉ ዘነፍስ።

ተፈጽሞበታልና። **ሰሙነ ሕርቃል** ዘትከውን እምቅድመ ጾም ዓቢይ። መገለጫውን ሲያይ ነው እንጂ የጾሙትስ ሐዋርያት ናቸው። ሕልሙን ያየ ናቡከደነጾር ሲሆን ራእይ ዘርእየ ዳንኤል እንዲል። ሐዋርያት እሑድ እሑዱን አውጥተው ቢቆጥሩት ጎደለባቸው አስቀድመው አምስት ቀን ጹመው ለስብከተ ወንጌል ይፋጠኑ ነበርና ሳያዘጋጁት ቀርተዋል። በኢየሩሳሌም ፎቃ በሮም ሕርቃል ነገሠ። ፎቃ በኢየሩሳሌም ባሉ ምእመናን መከራ አጸናባቸው። ሕርቃል መጥቶ ድል አድርጎታል። ምእመናን ደግሞ ቀድሞም ሐዋርያት ጹመውታል ብለው ጹመውታል። **ወጾመ ሰብእ ነነዌ** ሠለስቱ እለታት። ሀተታ ሐዋርያት የነነዌ ሰዎች የተነሣሕያን አብነት ናቸውና ሥርዓቱም ጾሙም አይቅር ብለው ሰርተውታል። **ወጾመ ድራረ ልደት ወጾመ ድራረ ጥምቀት**፡- ይህንንም ገሀድ ይለዋል። ወሀሎ ጾም ዘይቀድም እምልደት ወጥንተ ዚአሁ መንፈቀ ህዳር ወፋሲካሁ በዓለ ልደት። ለአዳም የተነገረው ትንቢት ስለተፈጸመበት ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ስለተፈጸመበት **ጾመ ነቢያት** ይለዋል። ወእምዝ **ጾመ ሐዋርያት** ወውእቱ ይተሉ እምበዓለ ኃምሳ ወፋሲካሁ አመ ሐሙሱ ለሐምሌ በዓለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ። ለእሉ አጽዋም ይደሉ ዐቂቦቶሙ ዘእንበለ ሕጸጽ። **ጾም በእንተ በዓለ እግዝእትነ**፡- ወጥንቱ ቀዳሜ ነሐሴ ወበዓለ እግዝእትነ ፋሲካሁ። ወበእሉ አጽዋም እለተሠርዐ ይጹሙ እስከ ተሰዓቱ እምዕለት ወኢይብልዐ ቦሙ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ። ወዘሰ አፈድፈደ ጾመ እምዝንቱ ዘተሠርአ ይፈደፍድ እሴቱ ወኢይጹሙ በእለተ እሑድ ወበሰንበት ዘእንበለ ጥሉላት። እስመ እግዚአብሔር አእረፈ ቦቱ እምኩሉ ግብር። በሰሙነ ሕማማት ቅዳሜ ይጾም። ወበእሉ እለታት ኢይብልዐ ቦሙ ዘእንበለ ጎበስት ወጼው ወማይ ባሕቲቱ። **አክፍሎት**፡- ለዕለታተ ዓርብሰ ወሰንበት ጹምዖሙ ለክልኤሆሙ ጎቡረ። ወዘይክል ኢይጥዓም ምንተኒ ቦቶን እስከ ንቅወተ ዶርሆ ዘሌሊት። ወለእመ ኢክህለ ብእሲ ከመይጹም ክልኤሆን ዕለታተ ጎቡረ ይዕቀብ ጾመ እለተ ሰንበት። ከጸራቅሊጦስ በኋላ ያለውን አንድ ሳምንት በዓል አድርጉ ይላል። ይህን ሲል ግን ብሉበት ስላላለ እየጾምን እናከብረዋለን። ቢበላበት ኑሮ በጥምቀት ረቡዕ ሲውል ብሉበት እንዳለን ይህንንም ብሉበት ባለን ነበረ። ወናሁ ይቤሉ ባስልዮስ ወአፈወርቅ እስመ ገቢረ በዓልሰ አኮ በመብልዕ ውእቱ። ወለእመሰ መጽአ በእንቲአሁ ተጋእዞ ጸዊሞቱ ድልው። ወይሄይስ ፈድፋደ እመብልዕ። ወለእመ ኮነ አሐዱ ውስተ ቀላይ ወኢያእመረ ዕለተ ሕማማት ይጹም እምድህረ በዓለ ሃምሳ። ወዘኢይጸውም ጾመ አርብዓ ወረቡዕ ወዓርብ እመ ኮነ ካህን ይትመተር ወለእመ ኮነ ሕዝባዊ ይትፈለጥ ዘእንበለ ዘሀሎ ቦቱ ደዌ ክሱት። ዶቅ፡- ወኢይደሉ በጾመ አርብዓ ከመ ናብዕል ዕለተ ሰማእታት አላ ይኩን ተገዝረ ሰማእታት በእሑድ ወሰንበት። ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ ቢውል ባለፈው እሑድ ቅዳሜ። እሑድ ቅዳሜ ሐሙስ አርብ ቢውል በሚመጣው እሁድ ቅዳሜ ይውላል። ወኢይደሉ ይስተይ መኑሂ እምካህናት ወይነ በጾመ ፶ ወኢበጾመ ረቡዕ ወዓርብ ወኢይባእ ውስተ ቤተ ምኅጻብ። ይኩን ቁርባን በሌሊት በጥምቀት ወበልደት። ወከማሁ በበዓለ ሃምሳኒ። ወበጾመ ፶ ቅድስት በሱባኤ ቀዳማዊ ይጹሙ እስከ ዕርበተ ፀሐይ ወሶበ ጎለፈ ይጹሙ እስከ አሠርቱ ወአሐዱ ሰዓት ወበመዋእለ ሕማማትሰ እስከ ጸአተ ኮከብ ወኢይሠርገው በእሎን መዋእላት ወአንስትኒ ይግድፋ ሥርጋዌሆን። ወኢይኩን በሰሙነ ሕማማት ጥምቀተ ክርስትና። ወኢሚመተ ክህነት። ወጸሎተ አስተብቁዖ ላዕለ ምውታን። ወዳዕሙ በበዓለ ሆሣዕና ይትነበብ ግንዘተ መታን በእንተ እለይመውቱ በሰሙነ ሕማማት። ወኢይትበሀል በዕለተ

ሐመስ ጸሎተ ተአምኖ (የይሁዳ ሰላምታ ይሆናልና) ወኢ እግዚአ ሕያዋን ወጸሎተ ቡራኬ። ወኢይደሉ ግንዘት በእለተ እሑድ ወኢብካይ በእለተ ፋሲካ። ኢይደሉ አውስቦ በጾም።

አንቀጽ 16 በእንተ ምጽዋታት

ወምጽዋትሰ ፆታ ውእቱ እም ጸዋትወ ምሕረት። ወውእቱ ተሣሕሎቱ ለሰብእ በንዋዩ ላእለ እለ ይፈቅድዎ እንዘ ኢየኀሥሥ ነሲአ ፍዳ እምኀቤሆሙ። ምጽዋትሰ ልቃህ አምላካዊት ይእቲ። ምጽዋት እንደ ጸሪቀ መበለት ለድኃውም ታሂል። ወዘአልቦቱ ምንትኒ ይጹም ወይረሲ መንፈቀ ኅብስቱ ለቅዱሳን። ምጽዋት እንተ ተሠርዓት ኀበ ክልኤቱ ትትከፈል በኅቡዕ ወበገሀድ። ወዘገሀድሰ ዘይመጸውት ኀበ ካህን ስዩም ወይእቲ አስራት ወበኩር ወብጽዓት በከመ ቃለ ሐዋርያት። ዘኅቡዕሰ ለጽኑሳን ወለርኁባን ወለጽሙዓን ወዕሩቃን ወለአናግድ ወለድውያን ወለመቁሐን ወለእለሂ ተሰዱ። ምጽዋት ይደልዎ ቅድመ ለዘቦቱ ዕጸበ ፈቃድ ዘከመ ሰማእታት ወእምዝ ለካህናት ወእምዝ ለአዝማድ ምእመናን ወእምዝ ለኢምእመናን ወፈድፋደሰ ለሰብአ ሃይማኖት። በመማር በማስተማር ለሚደክሙ መምህራን አብዝተው ይስጧቸው። ወይእዜኒ አምጣነ ብነ መዋእል ንግበር ሠናያተ ለኩሉ ሰብእ ወፈድፋደሰ ለሰብአ ሃይማኖት። ይልቁንም በእሑድና በበዓላት ምጽዋት ይገባል። ኢታጽርኡ ውሂበ እንዘ ብክሙ ዘትሁቡ። በስካር በስንፍና ገንዘቡን ለሚያጠፋ በምጽዋት ሊረዱት አይገባም። ተመጽዋች ለሚመጸውተው ሰው ሊጸልይ ይገባል። እያለው ወይም መስራት እየቻለ ምጽዋት የሚለምን በምጽአት ጊዜ ይፈረድበታል። ምጽዋት ታነጽሕ እምኃጣውእ ወትሰሪ አበሳ ወታድኅን እምእኩይ። ወዳዊትኒ ይቤ ብጹዕ ዘይሌቡ ላእለ ምስኪን ወነዳይ። እም ዕለት እኪት ያድኅኖ እግዚአብሔር። ወኢትኅዝን ሶበ መጽወትከ ለእጉከ። እስመ እግዚአብሔር ያፈቅሮ ለወሀቢ ዘይሁብ በፍሥሓ። ብር የቀማ ሰው ቢጸጸት ብሩን ይመልስ። ኃጥእ ንሥሓ ከገባ ምጽዋቱን ይቀበሉት።

አንቀጽ 17 በእንተ ዘይሰየም ላዕለ ንዋየ ምጽዋት ወንዋየ ቤተክርስቲያን

የአዝዝ ኤጲስ ቆጶስ በኩሉ ንዋየ ቤተክርስቲያን። ወያስተዋጽእ እምኔሁ ዘይፈቅድ ለሊሁ ለርእሱ ወለጽኑሳን እምቀሳውስት ወለዲያቆናት። ወይኩን ንዋየ ቤተክርስቲያን ዕቁበ በኀበ ዕውቃን ቀሳውስት ወዲያቆናት። ወኩሉ ንዋየ ቤተክርስቲያን ዘከመ ልብስ አው ገራውህ አው አጸደ ወይን ወእንስሳ ወዘይመስሎ ይኩን ዕቁበ በእደ ሕዝብ ፈራሕያነ እግዚአብሔር። ከቤክርስቲያን አጸድ ገብተው ሊጸለይባቸው የሚገቡ ፍሬዎች ወይን፣ በለስ፣ ሮማን፣ ዘይት፣ ተፋሕ፣ እንኮይ፣ ኮክ፣ ሽቱ ናቸው። ወያብኡ ካእበ ጽጌረዳ። ሽንኩርት፣ ዱባ፣ ሾላ አይግቡ ማለት አይጸለይባቸው።

አንቀጽ 18 በእንተ አስራት ወበኩራት ወብጽአታት ወጉልታት

ወንጌልኒ ይቤ ሀቡ ዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር። ወበኩረ ፍሬያተ ምድር እምዘሀለዎ ሎቱ ለይሰድ ኀበ ቤተክርስቲያን ወቀዳምያተ ምክያዳቲሆሙ። የእንስሳት በኩር ወቀዳምያተ ዘይት ወመዓር ወሐሊብ ወጸምር ወቀዳምያተ ዓስበ ግብረ እደዊሆሙ። ዘንተ ኩሎ ያምጽኡ ኀበ ኤጲስ ቆጶስ ወቀዳምያተ ፍሬ ዘእጽዋቲሆሙ። ወካህንሂ ዘይትዌከፍ ኪያሃ ያእኩቶ

ለእግዚአብሔር። **ስለት ወይም ብጽአት** በጎ ነገርን ለማግኘት ወይም ክፉ ለመዳን የሚደረግ ነው። በራስ ላይ የሚደረግ ለምሳሌ እንደ ድንግልና እንደ ጾም ያለ ሊሆን ይችላል። ወይም በልጁ ወይም በገንዘቡ ሊሆን ይችላል። ልጁን ለእግዚአብሔር የተሳለ ሰው ወይኩን ሜጠ ተባእት እም ፭ እስከ ፮ ዓመት ፱ ሰቅል እምነ ብሩር። ወሜጠ አንስት ፴ ሰቅል።ወለእመ ኮነ እመጠነ ኀምስቱ ዓመት እስከ ወልደ ፳ ዓመት ለይኩን ሜጠ ተባእት ፳ ሰቅል ወሜጠ አንስት አሠርቱ ወክልኤቱ ሰቅል። ወለእመኮነ ታሕተ ኃምስቱ ዓመት ሜጠ ተባእት ኀምስቱ ሰቅለ ብሩር ወሜጠ አንስት ሠለስቱ ሰቅለ ብሩር። ወለእመ ኮነ ወልደ ፮ ዓመት ወዘይትሌዓል እምኔሁ ይኩን ሜጠ ተባዕት አሠርቱ ወኀምስቱ ሰቅለ ብሩር። ወሜጠ አንስት አሠርቱ ሰቅል። ወሰቅልሰ አሐዱ ፳ አቦሊ ውእቱ መክራ ባገኘው ጊዜ ተሳለ እንጂ የተሳለውን ስለት መፈጸም የማይቻለው ድኃ ቢሆን ለይሑር ኀበ ኤጲስ ቆጶስ አው ኀበ ቀሲስ ዋጋውን ይወስኑለት ዘንድ። ለእግዚአብሔር ስለት ከተሳላችሁ ለመፈጸም አትስነፉ ቸል ቸልም አትበሉ ኃጢአት ይሆንባችኋልና። ባትሳሉ ኃጢአት የለባችሁም። ወዘወጽአ እምአፉክሙ ግበሩ ወፈጽሙ። አባት እምቢ ብሎ የልጁን ሥለት ባይፈጽም ልጁ ነጻ ነው። አባቱም በልጁ ላይ ሥልጣን ስላለው ነጻ ነው። ሴት ልጅ ባል ካገባች በስለቷ ባሏ ሊያዝዝ ይገባል። ቢፈቅድም ባይፈቅድም ይችላል። ሰምቶ ዝም ካለ በኋላ ቆይቶ ቢያፈርስ ግን በደል ይሆንበታል። ጉልት፡- ጉልትሰ ይትከፈል ኀበ ክልኤቱ ሀብት ወምጽዋት። ዲናር መሳለት አይገባም። ይኸውም ረብሕ ጥቅም ለማግኘት ዘወትር የማይኖር ሊሆን አይገባም። ከብት ንብ መሳለት አይገባም እነዚህ ሁሉ ዘወትር አይኖርምና። በሰረቋቸው ጊዜ በኮበለሉ ጊዜ በሞቱ ጊዜ ይታጣሉና። ከእኒህ ማናቸውንም ሊጎልት ቢወድ ሸጦ ለውጦ በዋጋቸው ነዋሪ ነገር ገዝቶ ሊጎልት ይገባል። የሚጎለት እንደ ሕንጻ እንደ እርሻ ያለ ነው። የሚጎልተው ሰው ከገንዘቡ የሚያገበትን እንጂ የማያገበትን መሳለት አይገባውም። የሚጎለትለት ሰውም የሚጎልተው ሰውም አካለ መጠን ያደረሰ አዋቂ ራሱን የቻለ ሊሆን ይገባል በሃይማኖት በምግባር የተመሰገነ ሊሆን ይገባል። ጉልትን ሊመጸውቱት አይገባም። የተጎለተለት ሰው ቢጠፋ ለቤተክርስቲያን ወይም ለተቸገሩ ሰዎች ይሰጥ። ረብሕ ጥቅም የሚገኝበት ሥርዓት ቢፈርስ መልሶ ሊያጸኑት ይገባል። የሚጎልት ሰው ሲጎልት ከ2 እስከ 7 የሚደርሱ ሰዎች ሊኖሩ ይገባል።

አንቀጽ 19 በእንተ እለተ እሑድ

ኢትትዐቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ። እሑድ አይሰገድም ወዝንቱ አንቀጽ ዘእንበለ ግዘት ይህም ማለት ለምሳሌ ባሕታዊ ጾር ተነስቶበት ቢሰግድ ዕዳ የለበትም። ዳኞች ምእመናንን እሑድ አይቅጠሩዋቸው። ወኢይግበሩ ቅስተ ወተኳንኖ ወኢይጎሥሥ መኑሂ በይእቲ እለት ንዋየ እምኳልኡ። ወይሑሩ ቦቱ ኩሎሙ ሰብእ ኀበ ቤተክርስቲያን። ድስቅ፡- ተጋብኡ ኩሎ እለተ ኀበ ቤተክርስቲያን ወፈድፋደሰ በዕለተ ሰንበት ወበዓላት ወበእለተ ትንሣኤ ዘውእቱ ሰንበት። ባርያዎችንኳ እሑድ ቤተክርስቲያን መጥተው ሊማሩ ይገባል። **ንዑሳን በዓላት** የሚባሉት ቃና ዘገሊላ፣ መጋቢት 10 መስቀል፣ ስብከት፣ ብርሃን፣ ኖላዊ፣ ጌና፣ ግዝረት፣ ልደተ ስምዖን፣ ደብረ ዘይት። ዓበይት በዓላት የሚባሉት ልደት፣ ጥምቀት፣ ሆሣእና፣ ዕርገት፣ ጰራቅሊጦስ፣ ደብረታቦር፣ ትንሳኤ፣ ትስብእት፣ ስመ ኃ ሕማማት ናቸው። ጥንተ በዓለ እግዚእ በዓለ ብስራት መጋቢት 29 ነው። ልደት ታህሳስ 29 ነው። ጥምቀት ጥር 11 ነው። ወይኩን ገቢረ ቁርባን

በልደት ወጥምቀት መንፈቀ ሌሊት። ወኢትግበሩ በዓለ ትንሳኤ ክልኤተ ጊዜ በአሐቲ ዓመት። ወኢትግበሩ በዓለ ትንሳኤሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘእንበለ በእለተ እሁድ ባሕቲቱ ወብልዐ ጊዜ ንቅወተ ዶርሆ ወእመ አኮ በነግህ። ሀተታ የትንሳኤ ቁርባን በ10 ሰዓት የልደት የጥምቀት 6 ሰዓት ነው። በዓለ ኃምሳና ቅዳሜ በሠለስት። በሰባቱ አጽዋማት በዘጠኝ ሰዓት። የጸሎተ ሐሙስ በሠርክ። እምድኅረ አርብዓ ዕለት ግበሩ በዓለ ዕርገት። እምድኅረ ኃምሳ ዕለት ግበሩ በዓለ ጰራቅሊጦስ። ወኢትግበሩ በዕለተ በዓለ ሐዋርያት።

አንቀጽ 20 በእንተ ሰማእታት ወተአማንያን ወከሀድያን

ሰማእታት ይኩኑ በጎቤክሙ ክቡራነ። ሰማእት ውእቱ እጉሀ ለክርስቶስ። ወሰማእታትሰ እሉ እሙንቱ ዘይቤ ክርስቶስ በእንቲአሆሙ ዘሰ አምነኒ በቅድመ ሰብእ አነኒ አአምኖ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። አምኖ ያልተጠመቀ ሰው አይዘን እስመ ሕማሙ ዘጾሮ በእንተ ክርስቶስ ውእቱ ይከውኖ **ጥምቀተ** ኀሩየ። እስመ ተጠምቀ በደሙ በባሕቲቱ። አንድ ሰው በክፉ ነገሥታት ምክንያት ከሃይማኖቱ በግድ ቢወጣ ከዚህ በኋላ ንሥሓ ቢገባ ይቀበሉት። እስመ ኢገብረ ዘንተ በፈቃዱ። ወይባእ ቅዳሴ ለእመ ኮነ ካህን። እስመ ሕግነ ሕገ ሣሕል ወምሕረት። **ረስጠጅ**፦ ወለኩሎሙ ዘከዓው ደሞሙ በእንተ ሃይማኖተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይግበሩ ሎሙ ተዝካረ በዕለተ ስምዐ ኮኑ ባቲ። ወያንብሩ አእጽምቲሆሙ ለሰማእታት በቤተ ክርስቲያናት ወምኔታት ከመ ይኩን እመካነ ሥጋቲሆሙ ፈውስ ወበቁኤት ዓቢይ ለድውያን ወለሕመማን። ወዘይሜንኖሙ ለእለ ይትጋብኡ በበዓለ ሰማእታት ምሉዓ ትእቢት ውእቱ ዉጉዘ ለይኩን። ዜናሆሙ ለሰማእታት ይትነበብ በበዓሎሙ።

አንቀጽ 21 በእንተ ድውያን

ጸሎት በሃይማኖት ያሐይዎ ለድውይ። ወእመኒ ቦቱ ኃጢአት ይትኀደግ ሎቱ። ሶበ ፈነዎሙ እግዚእነ ለሐዋርያት በበክልኤቱ ኮኑ ይቀብእዎሙ ለድውያን።

አንቀጽ 22 በእንተ ሙታን

ተጋብኡ ዘእንበለ ሐኬት ኀበ ቤተክርስቲያን ወአንብቡ መጻሕፍተ ቅዱሳተ። ወዘምሩ በእንተ እለ ኖሙ። ወአእርጉ ሎሙ አኮቴተ ቁርባን ዘውእቱ ሥጋሁ ቅዱስ ወደሙ ክቡር ለንጉሥ ሰማያዊ። ወተጋነዩ በእንተ እለ ኖሙ እንዘ ተሐውሩ ቅድሜሆሙ ወእንዘ ትዜምሩ። ወእመ ኮነ ምእመነ በክርስቶስ ይቤ ዳዊት ክቡር ሞቶሙ ለጻድቃኒሁ ወካዕበ ይቤ ግብኢ ነፍስየ ውስተ እረፍትኪ። ሶበ ሞተት ብእሲት በወሊድ አው በመዋእለ ሕርሳ ይሕጽብዋ ወይግንዝዋ ወይጸልዩ ላእሌሃ በቤተክርስቲያን እስመ ሞት አንጽሓ። ወሐጺበ ምውት ድልው ውእቱ እምቅድመ ይግንዙ እስመ ለጣቢታ እምድህረ ሞተት ሐጸብዋ። እስመ አእጽምቲሆሙ ለሕያዋን በእግዚአብሔር ኢኮነ ምኑነ ወኢርኩሰ። ወለእመ ኮነ መዋቲ ካህነ ይቀም ቅድመ ምሥዋእ ወእምድህሬሁ ያንብቡ ላእካን ላዕሌሁ እምቃላተ መዝሙር። ወእምድህረ ዝንቱ ይቅድም ሊቀ ካህናት ወይጸሊ ላእሌሁ ወእምድህረ ፍጻሜ ጸሎት ይስዓም ወእምድህሬሁ ይስዓምዎ ጉባኤ እለ ሀለው ህየ። ወእምድህሬሁ ይክዓው ላዕሌሁ ሊቀካህናት ቅብዓ ዘይት ወይጸሊ ላእሌሁ።

ሀተታ ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ሕጻን ከሕጻን ሊቀብሯቸው ይገባል። ረስጣ፡- ወግበሩ በግልስት ዕለት ተገኳረ በእንተ እለኖሙ በመዝሙራት ወበጸሎታት በእንተ ዘተንስአ በግልስት እለት እግዚእነ። ወግበሩ በሳብእት እለት ተገኳሮሙ ለሕያዋን ወግበሩ ካዕበ በፍጻሜ ወርኀ። ወሀቡ ለነዳያን እምጥሪቱ ለዘሞተ ከመ ይኩን ተገኳረ ሎቱ። ይደሉ ከመ ያእርጉ ቁርባነ በአሠርቱ ወአርባእቱ ዕለት። ወበታስእት ዕለት ወዐሠርቱ ወክልኤቱ ወከማሁ በአርብዓ እለት ወበተፍጻሜተ ክልዔቱ አውራኅ። ወዘወሰከ ላእለ ዝንቱ ሎቱሂ ወለዘሞተሂ ይፈደፍድ አስቦሙ። ሀተታ ባሕታውያንን እጃቸውን ከዓይናቸው ላይ ጥለው ይገንሏቸዋል። ቀሳውስትን እጃቸውን አመሳቅለው ይገንሏቸዋል። ዲያቆናትን እጃቸውን ከአንገታቸው ላይ ጭነው ይገንሏቸዋል። ሕጋውያንን እጃቸውን ከብልታቸው ላይ ጭነው ይገንሏቸዋል። ረስጠብ፡- ወኢይትዓንተል አሐዲሂ በእንተ መቃብሩ ለሰብእ አላ የሀቦሙ አስቦሙ ለእለ ይከርዩ ወየአቅቡ ውእተ መካነ ወይሴስዮሙ ኤጲስ ቆጶስ።

ፍትሐ ሥጋዊ

ይህ ክፍል ዳኞች በዚህ ዓለም ተሸመው የሚሰሩትን ሥራ ሰልጥነው የሚኖሩበትን ነገር ይናገራል። የአስተዳደርን ነገር ይናገራል።

አንቀጽ 23 በእንተ መብልእ ወአልባስ ወማህደር ወተግባረ እድ

ዘይደሉ ለመሚሐውያን። ወመብልዕሰ በውስተ ሕግ መሲሐዊት አልቦ ውስቴቱ ሕርመት ዘእንበለ ዘከልኡ ሐዋርያት እምኄሁ። ወውእቱ በሊዓ ደም ወኅኑቅ ወብልዓ አርዌ ወማውታ። እየተጠራጠሩ መብላት ኃጢአት ነው። ወኩሉ ዘይትአመን ከመ ኩሉ ግብር ብዉሕ ለበሊዕ ይብላዕ ኩሎ። ወኢይመንኖ ዘይበልዕ ኩሎ ለዘኢይበልዕ ወኢይኮንኖ ዘኢይበልዕ ለዘይበልዕ። ወኩሎ ዘይሠይጡ በምስያጥ ብልዑ እስመ ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ። ወእመቦ ዘጸውዐክሙ አሐዱሂ እምእለ ኢየአምኑ ወፈቀድክሙ ከመትሑሩ ብልዑ እምኩሉ ዘአቅረቡ ለክሙ ዘእንበለ ትሕትቱ። **አልባስ**፡- ይኩን ለመልእክተ ቤተመቅደስ ልብስ ፀዐዳ ድልው። የሚያስመካ ልብስ አትልበሱ። ኢይልበሱ ካህናት ልብሰ ሐራ ወልብሰ ሐናጺ ወልብሰ ጠቢባን (ፈላስፎች)። ከሐዋርያት አንዱ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የወደቀውን ጨርቅ አንስቶ ሰፍቶ ወስዶ ከነዳያን ደጅ ይጥለዋል። ያን አንስተው የለበሱት እንደሆነ ይህን ለብሼ ፈጣሪየን ላሳዝነው ኑሯልን ብሎ እንደገና ለዓይን የሚከፋውን ለአፍንጫ የሚከረፋውን አንስቶ ሰፍቶ ወስዶ ይለብሰዋል። ባስልዮስኒ ይቤ ይደሉ ለነ ከመ ንስራዕ ልብሰነ በዘንከድን ዕርቃነነ። ወለመነኮሳትሰ ይኩን ልብሶሙ አልባሰ ጸምር ገዚፍ። **ማህደር**፡- ወይቤለነ ሎቱሰ አልቦቱ ማህደር ወኢነበ ዘያሰምክ ርእሶ። ወሐዋርያሁኒ ወደሶሙ ለእለ የኀድሩ ውስተ ጾላእት ወግበበ ምድር ወይቤ እስመ ኢይደልዎሙ ዓለም። ወቅዱሳንኒ ጠቢባን ኮኑ ይኄልቁ ርእሶሙ ከመ ነጋድያን ወፈላስያን። ስለሚያልፈው ዓለም ማዘን የለብንም። **ተግባረ እድ**፡- ሁሉን መስራት ይገባል ዘእንበለ ዳእሙ ዘይትቃረና ለሕግ ዘከመ ሥራይ ወጠንቁሎ አው ግብር ከመ ገቢረ ጣዖት ወንዋያቲሁ ለጣዖት ወጸዋዕያን ወጠንቋልያን ወዘፋንያን ወአጽሕሶ በእግር። ወዘይደሉሰ ለመሲሐውያን እምግብራት ለሕይወተ ሥጋ ዘሪእ፣ አሥግሮት፣ ወአኒም፣ ወሰፍየ አልባስ፣

ወንድቀት፣ ወዓጺድ ወገቢረ ፈውስ ለረኪበ ጥዒና፣ ጸራቢ፣ ነሀቢ፣ ጸሐፊ፣ መምህር፣ ወነጋዲ።

አንቀጽ 24 በእንተ ፍኅረት ወሕጼ ወአውስቦ

ሕጼ እጅ መንሻ መስጠት ነው። ፍኅረት ቃል ኪዳን መጋባት መተጫጨት ነው። አውስቦ ማግባት ነው። ቦቱ ክልኤቱ ግብራት አሐዱ እምኔሆሙ ወሊደ ውሉድ ለአትርፎ ዘርእ እስመ ይቤ ብዝኁ ወተባዝኁ ወኢይከውን ዝንቱ ዘእንበለ በተራክቦ። ወዓዲ ለአቅልሎ ዋዕየ ፍትወት። ወዳግማዊኒ ረድኤት ዘይከውን ማእከለ ውሱባን በእንተ አቅልሎ ድካም በዝንቱ ሕይወት በከመ ይቤ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ። ወንድ ከሴት ሂዶ ማጨት ይገባል። ይቤ ጳውሎስ ሠናይ አውስቦ እም ዋዕይ በፍትወት። ባዕል መለኮት ነዳይ ሥጋን ተዋሕዲል። ባዕለ ጸጋ ድኃን ማግባት ይችላል ማለት ነው። ወኩሉ ዘበጽአ ከመ ይእቀብ ድንግልናሁ ይፈጽም ፈቃዳቲሁ ወእመ አኮ ይከውን ፍትሑ ከመ ዘአውሰበ ክልኤተ ብእሲተ። ወለአውስቦሰ ዳግሚት ኢትኩን ላቲ በረከተ ተክሊል አላ ይግበሩ ጸሎተ አስተሥርዮ። ከሣስተኛ ግቢ በኋላ መጽሐፍ ያዘዘው ግቢ የለም። ኢረከብነ አሐደ እምእሉ ዘይፈቅድ ለሕገ አውስቦ ዘእንበለ ከዊነ ዘርእ ባሕቲቱ። ልጅ ለመውለድ ብቻ ነው እንጂ ከአበው የግቢን ሥርዓት ለዝሙት የሚሻት አላገኘንም። ጽንሷ ከታወቀ በኋላ ሩካቤ የሚያደርግ ወንድ የተጸነሰው ወንድ ቢሆን ግብረ ሰዶም እንደ መስራት ሴት ብትሆን ከልጁ እንደ መድረስ ያለ ነው። ከሥርዓት የወጡ ከአሕዛብ ግን ዝሙቷን ብቻ ሽቶ የሚያገባ አለ ዳግመኛም ችግር ፈርቶ ሚስቱ ትከሳብኛለች ትጠቁርብኛለች ብሎ እንዳይጸነስ የሚያደርግ አለ። የገንዘቧን ብዛት አይቶ የሚያገባ አለ። ክብሯን ጌትነቷን አይቶ የሚገባ አለ። ወበእንተ ዝንቱ ቦ ዘይትዔገሥ ሕሰመ ራእየ ብእሲቱ በእንተ ፍቅረ ንዋይ። እስመ ፍትወት ይእቲ እሞን ለነሠራት ወለድካማት ወጻማት ወበአማን ወላዲተ ሕማም ይእቲ። በሐጻኒ በመጋቢ እጅ ያለ ከሆነ ኢይከውኖ ከመ ይሕጸ ለርእሱ። ማጫ መስጠት ግን ራሱ ሂዶ መስጠት ይገባዋል ደብዳቤ ሰዶ ቢሆን ሽማግሌም ሰዶ ቢሆን ማጫ መስጠት ለእርሱ ይገባዋል። ወደድሁ ጠላሁ የሚል እርሱ ነውና። **የተከለከሉ ጋብቻዎች፡- ቀዳማዊ** አውስቦ አዝማድ ዘበሥጋ ወእሉ እሙንቱ ኀበ ሠለስቱ ጾታ እለ ዘመልእልት ወውእቶሙ ወላድያን ወእምሒዋን ወዘይትሌዓሉ (ቅድመ አያት) ወዘይቁሐቱ ወውእቶሙ ውሉድ ወውሉዶሙ ወዘይወርዱ። በሀገራችን በአንድ ወገን ሰባት በአንድ ወገን ሰባት ተከልክሎ በስምንተኛው መጋባት ነው። የአበ ልጅም እንደዚሁ ነው። ባል የሚስቱን የክርስትና ልጅ ሚስት የባሏን የክርስትና ልጅ አያግቡ። የአንሺ እናት አባት ከተነሺ እናትና አባት አይጋቡ። የአንሺ ወንድም እህት ከተነሺ ወንድም እህት አይጋቡ። የአንሺ የልጅ ልጅ ከተነሺ የልጅ ልጅ አይጋቡ። ሴት ከሌላ የወለደችው ልጇን ባሏ ክርስትና ካነሳው ልጅ ማጋባት አይገባትም። ይህ መንፈሳዊ ተዛምዶ ነውና ይህን ያፈረሰ ንሥሐው ምንኩስና ነው መንፈስ ቅዱስን በድሏልና። የሥጋዊ ተዘምዶን ያፈረሰ ተፋቶ ቀኖናውን ፈጽሞ ሌላ ያግባ ታግባ። አብሮ ያደጉ ሰዎች ምንም እንኳ ከአሳዳጊዎቻቸው እጅ ቢወጡ መጋባት አይገባቸውም። የማደጎ ልጅ፣ አባት፣ እናት ከማደጎ ልጅ፣ አባት፣ እናት አይገባቸውም። የአዳጊ አባት አጎት አክስት ከአሳዳጊ አባት አጎት አክስት መጋባት አይገባቸውም። ልጅ የአባቱን ሚስት ማግባት አይገባውም። አባት ያሳደጋትን ልጅ ማግባት አይገባውም። አባት ለወለደው ልጅ ድኃይቱን ፈልጎ ያጋባው ቢያጋባው ከትሕትና

ከርኅራኄ ይቆጠርለታል። ልጅ የአባቱን ሚስት የልጅ ልጅ የአያቱን ሚስት ማግባት አይገባውም። ልጅ የአባቱን ሚስት እኅት የልጅ ልጅ የአያቱን ሚስት እኅት ልጅ የአባቱን ሚስት አያት የልጅ ልጅ የአባቱን ሚስት አያት ማግባት አይገባውም። አባት የልጁን ሚስት አያት የልጅ ልጁን ሚስት ማግባት አይገባውም። አባት የልጁን ሚስት እኅት አያት የልጅ ልጁን ሚስት እኅት አባት የልጁን ሚስት እናት አያት የልጅ ልጁን ሚስት እናት አባት የልጁን ሚስት አያት አያት የልጅ ልጁን ሚስት አያት ማግባት አይገባውም። ወንድም የወንድሙን ሚስት አኅት የወንድሙን ልጅ ሚስት ማግባት አይገባውም። ወንድም የወንድሙን ሚስት እኅት አኅት የወንድሙን ልጅ ሚስት እኅት ወንድም የወንድሙን ሚስት እናት አኅት የወንድሙን ልጅ ሚስት እናት ወንድም የወንድሙን ሚስት አያት አኅት የወንድሙን ልጅ ሚስት አያት ማግባት አይገባውም። ባል የሚስቱን ዘመዶች ማግባት አይገባውም። በሴት የተከለከለ ሁሉ በወንድም የተከለከለ ነው። የወንድምን እጮኛ ወንድም ማግባት አይገባውም። ልጅ የአባቱን ሚስት ዘመዶች ማግባት አይገባውም። ልጅ የአባቱን ሚስት ዘመዶች ማግባት አይገባውም። አባትም የልጁን ሚስት ዘመዶች ማግባት አይገባውም። የዘመዶቿን ሚስቶችም ማግባት አይገባውም። ኢይደልዎ ለምእመን አውስቦ ለዘኢኮነት አማኒተ። **ፈናፍንታም፡-** ወውእቱሂ ዘቦቱ ፍጥረተ ተባእት ወአንስት ኅቡረ በአሐዱ መካን። ሲጠመቅ ስሙ በማን ይጠራል ቢሉ ሙጻአ ስንት ታይቶ በወንድ አካል የሸና እንደሆነ ገብረ እገሌ ወልደ እገሌ። በሴት አካል የሸና እንደሆነ ዓመተ እገሌ ወለተ እገሌ ይባላል። ስድሳ ዓመት የሆናትን ሴት ማግባት አይገባም። የባሏን ሙት ዓመት ያልፈጸመችን ሴት ማግባት አይገባም። ከመተጫጨት በኋላ ወንዱ ምንኩስና እፈልጋለሁ ቢል ማጫውን ሳይመልስ (ከእርሷ) ይችላል። ፍሂርሰ ኪዳን ውእቱ። ወተስፋ ዘይቀድም እም አውስቦ።በደብዳቤም ያለ ደብዳቤም ይሆናል። **መጅ፡-** ያስተጻንኡ ፍኅርተ በቅድመ ክልኤቱ ካህናት በአንብሮተ እድ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወበመስቀል ኃታሚ መስቀል አስጨብጠው ቀለበት አድርገው የሕጼን አኳኋን ይወስኑ። ሰባት ዓመት ላልሆነው ሕጻን ማጨት አይገባም። አጭቶ ለማግባት ቀን ያልወሰነ ሰው በ2 ዓመት ውስጥ ያድርገው በጣም ብዙ ጊዜ ከሄደ 3 ዓመት ያድርገው ከዚህ የበለጠ ከሄደ ግን ለሌላ ትታጭ። የታወቀ ምክንያት ካለ 4 ዓመት ይሁን። ነፍስ ገድሎ ቢሆን እስኪታረቅ መጠበቅ ይገባል። ወፍጻሜ መጠነ አካልሰ ዘእደው ፰ ዓመት ወእመ አኮ ፰ ወነምስቱ ዓመት ወለአንስትኒ አሠርቱ ወክልኤቱ ዓመት ወእመ አኮ አሠርቱ ወነመስቱ ዓመት። ኢይኩን ሥርዓተ ተዋስቦ ዘያስተዋስብዎሙ ዘእንበለ በተሣምሮቶሙ ለክልኤሆሙ። የሚጋቡ ሰዎች የወንድና የሴት አካለ መጠን ያደረሱ ሊሆን ይገባል። **ተክሊል፡-** ወኢይግበሩ ሎሙ ተክሊለ ምንተኒ በኅቡዕ ዘእንበለ ይትጋብኡ ብዙኃን አላ ይግበሩ በቅድመ ብዙኃን። ወማዕሰረ ተዋስቦሰ ኢይከውን ወኢይትፈጸም ዘእንበለ በሀልዎተ ካህናት ወጸሎት ዘላእሌሆሙ ወይመጥውዖሙ ቁርባነ ቅዱሰ። ወዘእንበለ ዝንቱሰ ኢይትኆለቅ ሎሙ አውስቦ። የወንድ ወገኖች ወንዱን ይዘው በሰሜን የሴት ወገኖች ሴቲቱን ይዘው በደቡብ ይገባሉ። አንድ ልብስ አልብሰው ያቆርቧቸዋል። እርሱ ከአባቱ ቤት እርሷ ከእናቷ ጋራ ሲተኙ ይሰነብታሉ ቁርባኑን በሚሹበት ጊዜ እየሄዱ ይቆርባሉ። አርባው ቀን ሲፈጸም ሰርጉን ያደርጉላቸዋል። ከዚህ የወጣ ግቢ ግን እንደ ባዘራ እንደ አለሌ መሆን ነው። ካህናት ሁለተኛ ካገቡ ከክህነታቸው ይሻሩ። ወለእመ ኮኑ ዘይትዋሰቡ መዓስባነ ኢይግበሩ ሎሙ በረከተ ተክሊል እስመ ዝንቱ በረከት ይደሉ ለብእሲ ድንግል ወለብእሲት ድንግል።

ወለእመ ኮነ አሐዱ እም ተዋሳብያን ድንግለ ለይትባረክ ባሕቲቱ፡፡ በአራተኛ ግቢ የተወለዱ ልጆች ካህን ሊሆኑ አይገባም፡፡ ርስት መውረስም አይገባቸውም፡፡ ወብእሲት ማእምንት ለእመ ተወስበት ለብእሲ ኢአማኒ ትሰደድ እምጎባኤ ወለእመ ነሥሐት ወተከልአት እምኔሁ ይትወከፍዋ፡፡ ወለእመቦ እጉ ዘቦቱ ብእሲት ዘኢተአምን ወፈቀደት ትንበር ምስሌሁ ኢይህድጋ ወብእሲትኒ ማእምንት እመ ባቲ ምት ዘኢየአምን ወይፈቅድ ውእቱ ከመ ይንበር ምስሌሃ ኢትትፈለጦ ለምታ፡፡ እስመ ብእሲት ዘኢትአምን ትትቄደስ በብእሲ ምእመን፡፡ በጾም ወቅት በመዋእለ ትክቶ ሩካቤ አይገባም፡፡ አሌ ሎቱ ለዘይገብራ ለዛቲ ኃጢአት በሰሙነ ሕማማት ቅድስት፡፡ በቀሩት አጽዋም ግን እመቦ ዘተመውዖ እም ፍትወት ነዳዲት ወዘኢይትከሀሎ ላዕለ ተጋድሎ የፈቲውን ጾር ማራቅ ይገባዋል፡፡ **ክዓቄ ዘርዕ፡-** እመቦ ብእሲ ዘሰከበ ምስለ ብእሲት ወአግነሠ ዘርዓ እምኔሃ ኢይሕየው እም ቀቲል ከመ አውናን፡፡ ወኢትባእ ትክት ውስተ ቤተክርስቲያን ወኢትቅረብ እስከ ይትፈጸም መዋእለ ትክቶሃ ወእመኒ ኮነት ብእሲተ ንጉሥ፡፡ ወመወልድትኒ ኢይትመጠዋ እምሥጢራት እስከ ይከውን ፰ ዕለት በተባዕት ወ ፵ ዕለት በአንስት፡፡ ወብእሲትኒ እንተ ወለደት ትንበር በአፍኣ እመካን ቅዱስ ፵ ዕለት ለእመ ኮነ ተባዕተ፡፡ ወእመሰ ወለደት አንስተ ፹ ዕለተ፡፡ ወለእመ ተወስበት ብእሲተ ቀሲስ ለካልእ እምድህረ ሞቱ እስመ ገብረት ጽእለተ ወወሀበት ሕጸጸ ለመዓርግ ቀዳማዊ ይደልዋ ንሥሓ፡፡ ሩካቤ ማድረግ የማይቻለው ቢሆን ትዳር ይፈርሳል፡፡ ሁለተኛ በስምምነት ከመነኮሱ ትዳር ይፈርሳል፡፡ በተጣሉ ጊዜ አንዱ የአንዱን ሰውነት የሚያጠፋ ከሆነ ትዳር ይፈርሳል፡፡ ከ5 ዓመት በላይ በእስራት ከቆየ ሌላ ታግባ፡፡ አንድ ወቄት 12 ብር ነው፡፡ ሴት ከሥራ በማናቸውም ሥራ የባልዋን ሰውነት ለማጥፋት ብትሞክር ሌሎችም ሊያጠፉት እንደመከሩበት እያወቀች ባትነግረው ግቢ (ትዳር) ይፈርሳል፡፡

አንቀጽ 25 በእንተ አኀርሞተ ዕቁባት

ዕቁባት ማኖር እንደማይገባ ይናገራል፡፡ ነሢአ ዕቅብትሰ በውስተ ሕግነ ቅድስት ኀሩም ውእቱ፡፡

አንቀጽ 26 በእንተ ሀብት

ገንዘብ ተቀባይ ቢሞት ሰጪ የተቀባይን ልጆች ገንዘቤን አምጡ ማለት አይገባም፡፡

አንቀጽ 27 በእንተ ልቃሕ

ልቃህሰ ሀብት ይእቲ እም አዝማዲሃ ለምጽዋት ዘአዘዘ ባቲ እግዚአብሔር ይደሉ ተአግሦ ላዕለ ተለቃሒ እስከ ይረክብ ዘይፈድዮ፡፡ አራጣ ከመቀበል መራቅ ይገባናል፡፡ አበዳሪ ከ ፴ ዘመን በኋላ ገንዘቤን መልስልኝ አይበል፡፡

አንቀጽ 28 በእንተ ሕሰት

የመዋስን ነገር ይናገራል፡፡ የተዋስከው ነገር ምሳሌ ላም ብትሆን ከገደል አፋፍ ሁና ዝም ብትልና ወድቃ ብትሞት ዋጋዋን ላዋሰህ ሰው ትከፍላለህ፡፡

አንቀጽ 29 በእንተ ማኅጸንት

የአደራን ነገር ይናገራል። ማኅጸንትሰ ንዋይ ይእቲ ዘይሁባ አማኅጻኒ ለዘያማኅጽኖ ከመ ይእቀባ ሎቱ ዘእንበለ ካእበት። የመጽሐፍ አደራ ለተማረ ሰው ነው እንጂ ላልተማረ መስጠት አይገባም የጎታ መክደኛ ያደርገዋልና።

አንቀጽ 31 በእንተ ግእዛን ወግብርናት

ሰው ሁሉ ከአንድ አዳም በመገኘት ባለመገዛት አንድ ነው። ወዳዕሙ ጸብእ ወኃይለ ፈረስ ታመጽእ ቦሙ ከመ ይትቀነዩ በበይናቲሆሙ። እሰመ ሕገ ጸብእ ወመዊእ ትሬስዮሙ ለምውዓን አግብርተ ለመዋእያን። አማኒ ባርያን ላላመነ ሰው መሸጥ አይገባም። የባርያ ልጆች ለአባታቸው ጌታ ይገዙ። ወአግዕዚሰ እምተግባረ ትሩፋት ይእቲ።ባርያን ዋጋውን ከፍሎ ነጻ ማውጣት ይገባል።

አንቀጽ 33 በእንተ ተግይጦ ወሠይጥ

ተግይጦሰ ኢትከውን አማነ ዘእንበለ ለእመ ኮነ ሠያጤ ወተግያጤ ብውሃነ ላእለ ንዋዮሙ። ጽልእ ውእቱ ተግይጦ በመዋእለ እሑዳት ወበበዓላተ እግዚአብሔር ወበበዓላተ እግዝእትነ ማርያም።

አንቀጽ 37 በእንተ ፍናዋት

የታች ቤት ወደ ላይኛው ቤት ጭስ አያጭስበት። የላይኛውም ወደ ታችኛው ቆሻሻ አይላክበት። ዳኞች ስለሚፈርዱበት ጉዳይ ወጉን ታሪኩን ማጥናት መመርመር ይገባቸዋል።

አንቀጽ 40 በእንተ ዘይትረከብ እምዘ ተኃጥአ

አግብእ ዘተገድፈ ለእጉከ ለወንድምህ የጠፋውን ገንዘብ መልስለት። የጠፋውን ሁሉ ቸል ብለህ ልትሄድ አይገባህም።

አንቀጽ 41 በእንተ ዘይኤዝዝ በንዋዩ

ወአዝዞሰ ይከውን በጽሒፍ ወዘእንበለ ጽሒፍ። ባርያ በጌታው ትእዛዝ ቢሆን ነው እንጂ ማዘዝ አይገባውም። በተፈጥሮ ወንድ ግማሽ ነፋስ ግማሽ እሳት ሙሉ ውሃ ሙሉ መሬት ነው። ሴት ግማሽ ውሃ ግማሽ መሬት ሙሉ ነፋስ ሙሉ እሳት ናቸው። በእናት በኩል ካለ ዘመድ በአባት በኩል ያለ ዘመድ ይቀድማል።ምግባሩ ብልሹ ለሆነ ልጅ ሊያወርሱት አይገባም።

አንቀጽ 43 በእንተ ፈታሒ

ህልያን የዓውር አዕይንተ ጠቢባን ከመ ኢይርዓዩ ጽድቀ ወይቄልጥ ቃለ ርቱዓ። ፈታሒ ይፈትሕ ማእከለ ተጋእዝያን። ይኩን ፈታሒ ብእሴ። ሠላሳ ዘመን የሞላው ይሾም። ዳኛም ያለ ካህን አይኑር። ፈታሒ ይኩን ምእመነ ኦርቶዶክሳዌ ወካህነ በጥዩቅ። የተሾመበትን ሀገር

የሚያውቅ ታጋሽ ይሁን። ጆሮው የማያከራክረው አንደበቱ የበረታ ይሁን። ወይኩን ማእምረ ሕግ ወነገረ መጻሕፍት አምላካውያት። በፍርድ ጊዜ ማዘን መራራት የለም። ዳኞች ሆይ “ወለእመ ኮነ ርቱዓ ፍትሕክሙ ትረክቡ ዕሤተ ሠናየ በርትዕ እምኔሁ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእኒ”። ዳኛ ደስ ብሎት ሳለ አዝኖ ሳለ ሊፈርድ አይገባውም። ተርቦ ተጠምቶ ሰክሮ ተጨንቆ ተበሳጭቶ ሳለ ታሞ ሳለ አይፍረድ። ዳኛ ሳይፈርድባችሁ ባላጋራ ሳያወርድላችሁ አትማሉ። ወከዊነ መሐላሰ በጊዜ ጋእዝ ናሁ ይትፈቀድ በበይነ ግብር። ወባሕቱ ይደሉ ለሰብእ ከመ ኢይምሐል በዘይትከሀሎ ይቤዙ መሐላሁ በንዋዩ በእንተ ዕበየ እግዚአብሔር። በፈራሽ በተርታ ነገር ስመ እግዚአብሔር ጠርተህ አትማል። ይልቁንም በሐሰት አትማል። ሰው በእውነትንኳ ቢምል ንሥሓ ሊገባ ይገባዋል። ካህን በሐሰት ከማለ 3 ዓመት ይሰደድ። ኢትጎበር ምስለ ብዙኃን ለገቢረ እከይ። ዳኝነት ለመስጠት በቤተክርስቲያን መሰብሰብ አይገባም። ኢይሑር ክርስቲያናዊ ጎበ መስፍነ አሕዛብ ወኢጎበ ሊቃናት ዓላውያን ከመይፍትሑ ሎቱ። ዘመድ ለዘመድ አይመስክር። ሰካራም አይመስክር። መስካሪዎችን ዳኛው ድርስ ነገሩን ቦታውን ይጠይቃቸው። ምጽዋት የሚለምን ሰው አይመስክር። አበዳሪ በተበዳሪ መመስከር አይገባውም። በሐሰት የመሰከረ ሰው በሐሠት የመሰከረበት ሰው ይቀጣበት በነበረው ቅጣት ይቀጣ። የሚመሰክር ሰው የሚመሰክረውን ማስተዋል ይገባዋል።

አንቀጽ 44 በእንተ ነገሥት

ወኢይደሉ ከመ ትሚም ላእሌከ ብእሴ ነኪረ ዘኢማእምን። ወይኩን አሚኖቱ ፍጹመ በእግዚአብሔር። በተአምኖ ጌዴዎን ወባርቅ ወሶምሶን ወዮፍታሔ ወዳዊት ሞዐ ነገሥት። ወገብሩ ጽድቀ ወኮነ መዋዕያነ በውስተ ጸብዕ። መናፍቅ ንጉሥ ንጉሥ አይባልም አመጸኛ ነው እንጂ። ለዘይደልዎ ክብር አክብሩ። ኩሉ ሰብእ እምኔክሙ ለይግነይ ለሥልጣነ መኮንን ዓቢይ እስመ ኢይሠየም መኮንን ዘእንበለ እምነበ እግዚአብሔር። ወእምከመ ወጽኡ መሐይምናን ለጸቢዐ ጸሮሙ ያቅሙ በቅድሜሆሙ መስቀለ ክርስቶስ ወይሰግዱ ሎቱ። ወለእመ ወጻእከ ለጸብእ ላእለ ጸርከ ወርኢከ አፍራሰ ወሠረገላተ ወሕዝበ ዘይበዝኑ እምኔከ ኢትፍራህ እምኔሆሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ምስሌከ። ሕጻናቶችን ባልቴቶችን ሽማግሌዎችን አታጥፉ ዛፎችን አታቃጥሉ።

አንቀጽ 45 በእንተ ዘይደሉ ተናግሮቱ በዝንቱ መጽሐፍ እምብሉይ ወሐዲስ

ወለመኳንንት ኢትሕምይሙ ወኢትጽርፍ ላእለ መኮንነ ሕዝብከ። ኢትሳተፍ በቀቲለ ጻድቅ። እህላችሁን በምታጭዱበት ጊዜ አጥርታችሁ አትጨዱ። የወደቀውን አትልቀም ለድኃው ለመጻተኛው ተውለት እንጂ። አይሰማም ብለህ በደንቆረው ክፉ አትናገርበት። ወኢትደይ ዕቅፍተ ቅድመ ዕውር። ኢትላጺ መንፈቀ ሥእርተ ርእስከ። የሞተ ሰው ቢኖር ፊታችሁን አትንጩ። ሰውነታችሁን አትጠቀሩ አትበጡ ወደሚርተኛ ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ። ካላመነች ሴት የደረሰ ከከብት የደረሰ ሰው ይሙት። የካህን ልጅ ብትሰስን በእሳት ያቃጥሏት። ቢያከብሩን ቢመርቁን ደስ አይበለን ቢያዋርዱን ቢረግሙን አይክፋን። በጎ መስራት ሲቻለው የማይሰራ ዕዳ ይሆንበታል። ስለጌታችን ብላችሁ ለሰው ሁሉ ራሳችሁን አዋርዱ።

አንቀጽ 46 በእንተ ኩነኔሆሙ ለከሐድያን

ለአማልክት የሚሰዋ ይገደል። ሳይወዱ በግድ ለጣዖት የሰው ሰዎች በሰባት ዓመት ንሥሓ ይቀበሏቸው።

አንቀጽ 47 በእንተ ቀቲል

ከሰባት ዓመት በታች ያለ ሕጻን እብድ ሰካራም ቢገድል ሞት አይገባውም። ኢይቅትልዎሙ ለአበው ህየንተ ውሉዶሙ። ወእለ ይጼውኡ አጋንንተ ለቀቲለ ሰብእ ይትኮነኑ በሰይፍ። ንሥሓ መንፈሳዊ ቅጣት ነው። የንጉሥን ሕይወት ለማጥፋት የሚሞክር ይገደል። ሳያውቅ የገደለ 7 ዓመት ንሥሓ ይሠጠው። ሴት የገደለ ንሥሓው 20 ዓመት ነው። አንዲትን ሴት በሥራይ ጽንሷን ቢያስወርዳት መላ ዘመኑን ንሥሓ ይግባ።

አንቀጽ 48 በእንተ ኩነኔ ዝሙት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

አንድ ሰው ከዘመዱ ከደረሰ በሰይፍ ይቀጣ አፍንጫው ይፎነን። አንድ ሰው ከሁለት እህትማማቾች ከደረሰ ይገረፍ። ሁለት ወንድማማች ከሁለት እህትማማች ቢደርሱ ይቀጡ። እለ ያወስቡ መነኮሳይያተ ወዲያቆናውያተ ወገዳማውያተ ይምትሩ አዕናፊሆሙ። ሴትን ልጅ የሚነጥቁ በሰይፍ ይገደሉ። እመቤቱን ለመንጠቅ የሞከረ ባርያ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት። ግብረሰዶም የሚሰሩ በሰይፍ ይገደሉ። ሴት ልጅ ብታስወርድ ይደብድቧት። ከእንስሳ የሚደርሱ አባለ ዘራቸው ይቆረጥ። በእንስሳ የሚሰስን 20 ዓመት ቀኖና ይቀበል።

አንቀጽ 49 በእንተ ኩነኔ ሰረቅት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

እለ ይሠርቁ ሕጻናተ ይቅትልዎሙ አው ይስድድዎሙ ይትቀተሉ።

አንቀጽ 51 በእንተ ሥእርት ወግዝረት ወተአምኖ ኃጣውእ

ኢይደልዎሙ ለእደው ከመ ያንኑ ሥእርቶሙ። ባልተማረ ግብረገብ ካህን ከመናዘዝ መናዘዙን መተው ይሻላል። የተጻፈ ንባቡን የሚቃወም ትርጓሜ መተርጎም ለማንም ለማን አይገባም።

መጽሐፈ ቅዳሴ

ጌታ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያስተማረው **ወንጌል** ይባላል ወንጌል ማለት ብስራት ማለት ነው። ከትንሳኤ በኋላ ያስተማረው **ኪዳን** ያባላል። ጌታ ከትንሳኤ በኋላ በጉባኤ ያስተማራቸው የትንሳኤ፣ የአግብዖ ግብር፣ የጥብርያዶስ ነው። አራተኛ የዕርገት ነው።

ትምህርተ ጎቡዓት፣ ኪዳን፣ መስተብቁእ

ጎቡዓት ያላቸው አምስቱ አዕማደ ምስጢር ናቸው። ምሥጢረ ሥላሴን አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ መሆን እንደምን ይሆናል ብለው ለሰው ይነግሩታል ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው አይችልምና ጎቡዕ ብለውታል። አንዱን አካል መዋቲ ነው ኢመዋቲ ነው ማለት ጎቡዕ

ነውና። ባስልዮስ ዐሥሩን መስተብቁእ ከሲኖዶስ ዘጠኙን ኪዳን ከመጽሐፈ ኪዳን አምጥቶ ተናግሯል።

ዲያብሎስ፣ ሽንገላ

ያፍ ሥሩር አለው ለማሳት ይፋጠናልና። ነድ ውኡይ አለው ደዌ ትኩሳት እየሆነ ያማልና ፈታዊ አለው አምላክነትን ሲሻ ተገኝቷልና። ጋኔን ማለት ዕሩቅ ዉዱቅ ማለት ነው። ሰይጣን ማለት መስተጻርር መስተቃርን ባላጋራ ማለት ነው። ወገጹ ዘፍጹም በጽልመት ፈርሀ ወደንገጸ ዲያብሎስ። ጌታ ቀድሞ ሲፈጥረው ሊቀመላእክት አጋዜ መንጦላእት ቅሩበ እግዚአብሔር አድርጎ ፈጥሮት ነበር። ሲክድ ብርሃኑን ገፎ በብርሃኑ ቦታ ጨለማ አኅናጽፎ እንጦርጦስ አውርዶታል። ሰይጣን አስቀድሞ ያልሆነ ሥራ ማሰራት ኋላ ማጸጸት ልማዱ ነው። አጋንንትን በቦታቸው ሲኦል ይላቸዋል። ሰይጣን በምንስዋን አኃው አድሮ የኛ ቆራቢ እያለ ይሳደባል። ሰው በሞተ ጊዜ ሰይጣናት በአየር ተጋብዖ ያደርጋሉ። ሥጋውን ደሙን የተቀበለች ነፍስ ያዩ እንደሆነ ደሙ ማኅተሟ ነውና አይቀርቧትም ጥለዋት ይበተናሉ። አጋንንት መጥቁልን "ለእመ ትብለነ ጠብልልዎ ለሰማይ ንጠበልል ለከ" አሉት። እመቤታችን **ህርም ስድክኤል** የሚባል ኅቡዕ ስም ተገልጾላት ትጸልይ ነበረ። ገብርኤል አጋንንቱን አጥፍቷቸዋል። ሄሮድስ ዓመት ዓመት ከመንፈቅ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ሕጻናት ልብስ ቀለብ እሰጣለሁ ብሎ ሰበሰበ ከዚህ በኋላ ልጆቻቸውን የሌላቸው ልብስ ቀለብ እንቀበልበታለን እያሉ እየተዋሱ ሂደዋል። እንደዚህ አድርጎ 14 እልፍ ከ4 ሺ ሕጻናትን አስገደለ።

ልደት

ጌታ ሊወልድ 24 ቀን ሲቀረው መካነ ልደቱን አስጠበቀው።

እግዚአብሔር

ለሊከ ኪያከ አንጦላእከ ወለሊከ ብከ ተከደንከ ሥውር ብከ ዕበይከ በኃይልከ እንዲል። ዘበነቢያት አቅደመ ተአውቆ ወእመላእክት ተአኩተ። ተሰቅለ በእንቲአነ። እንደ ሁለቱ ወንበዴዎች ስቶ እንደ ሰማእታት ዕሴት ሽቶ አይደለምና በእንቲአነ አለ። ኦ አእዳው እለ ለሐኪሁ ለአዳም እፎ ተቀነዋ እንዲል። ቅዱሳን በእርሱ ሌላውን ያዩበታል እርሱን ግን አያዩትም። የእርሱን ባሕርይውን መርምረው አያውቁትም። ወኩሎ በዘይደሉ አቅደምከ ሀልዮ። **ሊጠን**፡- ስምከ ሕያው ዘኢይመውት። እግዚአብሔር ንዋዮሙ ለነዳያን ተስፋሆሙ ለቅቡጻን መንስኢሆሙ ለሙታን። እግዚአብሔር ዘህልው ውስተ ኩሉ ወይሄሉ ውስተ ኩሉ። በዮናኒ **ጳራቅሊጦስ** ማለት ናዛዚ ከሣቲ መንጽሒ መጽንኢ መስተፍሥሒ መስተሥርዩ ማለት ነው። ሰውን ኃያል ቢሉት ድካም ንጹሕ ቢሉት ኃጢአት ይስማማዋል። እግዚአብሔር ግን ኃያል ዘአልቦ ድካም ንጹሕ ዘአልቦ ኃጢአት ነው። ጸባዖት ማለት መዋዒ እግዚአ ኃይላት ማለት ነው። ዘለዓለም ሥላሴ። ከሦስትነት ወጥቶ ወደ አራትነት አይለወጥምና። ከአንድነት ወጥቶ ወደ ሁለትነት አይለወጥምና። እግዚአብሔር ስለ ልእልናው በሰማይ አለ ይባላል። ዘበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመና እንዲል። እግዚአብሔር፡- አኮ እምካልዕ መካን ዘይመጽእ ለአስተርእዮ ኀቤሆሙ አላ

ሀሎ ኀቡዓ ወምሉዓ ማዕከሌሆሙ ወውሣጤሆሙ ለጻድቃን እንዲል። **ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፦** አልብከ ጽንፍ ወአልብከ ማኅለቅት አልቦ ዘይረክበከ ወአልቦ ዘየአምረከ አልቦ ዘይክል ርእዮተከ ለሊከ ተአምር ርእሰከ። ስውር አንተ እምነ ኩሉ ወክሡት ለከ ኩሉ።አልብከ ጥንት ወአንተ ትሁብ ለኩሉ ማኅለቅተ። ኩሉ እምኔከ ወኩሉ ብከ። ወአንተ ውስተ ኩሉ ሀሎከ። ልዑል አንተ እምልዑላን በእበይከ። አንተ ውእቱ ዘእንተ ውስጡ ለኩሉ ወአንተ ውእቱ ዘእንተ አፍአሁ ለኩሉ። ክዱን ብከ ዕበይከ ወስውር ብከ ኃይልከ ለሊከ ብከ አንጦላእከ ኪያከ ወአንተ ብከ ለሊከ ተከደንከ። ፈጣሪ ዘኢይኤዝዝዎ ንጉሥ ዘኢይሠይምዎ ባዕል ዘኢይሁብዎ። ጌታ ወዶ ተራበ መራቡ ግን ለአጽድቆተ ትስብእት ለአቅርቦተ ሰይጣን ነው። ለካሳ ነው። ተኖለቆ ምስለ ጊጉያን ከመ ይደምረነ ምስለ ጻድቃን። ለጌታ ሁሉ ቅድሙ ሲሆን ሥጋው ደሙ የሚሰዎበት ቤተመቅደስን ቅድሜከ ይለዋል። **ቅዳሴ ማርያም፦** ወመለኮትሰ ኢይትከሀል ይትበሀል ዘንተ የአክል ወዘንተ ይመስል። አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ዘበላዕሉ ጠፈር ወዘበታሕቱ መሠረት አላ ጠፈር ውእቱ ወመሠረት ውእቱ። አኮ ዘንብል ሠለስተ ከመ አብርሃም ይሥሐቅ ወያእቆብ አላ አሐዱ ውእቱ እንዘ ሠለስቱ ግጻዌ። አኮ ዘንብል አሐዱ ከመ አዳም ቀዳሜ ኩሉ ፍጥረት አላ ሠለስቱ ውእቱ እንዘ አሐዱ ህላዌ። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት። ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፦ አልቦ ዘይክል ርእዮቶ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ። ጌታን ስለክብረ አዳም ጭቃ ይዞ ታየ ይለዋል። ከሁሉ ይልቅ ነፋስ ይረቃል ከዚያ ነፍሳት ከዚያ መላእክት ከመላእክት ከአካላቸው ሕሊናቸው ይረቃል። የሕሊናቸው ርቀት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አምባ እንደ ተራራ ነው። ጌታ ሰውን መውደዱ በሕጉ በሥርዓቱ ቢጸና ነው። ሰው ጌታን መጥላቱ በሕጉ በሥርዓቱ አለመጽናቱ ነው። መላእክት ጌታን አይተው የሚሰግዱለት አይደለም ለሥልጣኑ ይሰግዳሉ እንጂ ለጌትነቱ ይገዛሉ እንጂ። የዕርገት የታቦር የምጽአት ደመና የባሕርይ ክብሩ ነው። ሰው ሲፈጠር ከግንባሩ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ተብሎ ይቀረጽበታል። ኂላ ሲበድል ያ ቀርቶ መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት ተብሎ ይቀረጽበታል። ንሥሓ ሲገባ ስመ በግኡ ስመ ሥላሴ ይቀረጽበታል። አንተ ለሊከ ተአምር ህላዌከ ወአንተ ለሊከ ትጤይቅ መለኮተከ። ኦ ዘታወጽኦ ለሕጻን እምሐቁ ብእሲ ወትፌንዎ ውስተ ከርሰ ብእሲት ወትጠበልሎ በሰፋድል ረቂቅ። ወእንዘ ማይ ውእቱ ታረግኦ በጥበብከ። ሕጻኑ በተወለደ ጊዜ መልአክ የሚቀበርበትን መቃብር ከፍቶ በሕሊና ያሳየዋል በሕሊና መቃብሩን አይቶ ምር ብሎ ያለቅሳል። አንድም ከዚያ ከሚቀበርበት ምድር አፈር አምጥቶ ያቀምሰዋል ያን ጊዜ ምር ብሎ ያለቅሳል። ይቤ ዳዊት በመዝሙር እግዚኦ መኑ የኀድር ውስተ ጽላሎትከ ተሰጥዎ መንፈስ ቅዱስ ወይቤ ዘየሐውር በንጹሕ ወይገብር ጽድቀ። አዳም በገነት ሳለ አንድነት ከሦስትነት ተገልጸለት እንደ መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያለ ያመሰግን ነበረ።

ቁርባን

እምቅድመ ይቁድሶ ካህን ኅብስት ወወይን ወሶበ ይቁድሶ ካህን ይወርድ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ ወይትመየጥ ኅብስት እም ከዊነ ኅብስት ኀበ ከዊነ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወከማሁ ጽዋእኒ ይትመየጥ ወይትቄለጥ እም ከዊነ ወይን ኀበ ከዊነ ደም አምላካዊ። ሁለት አነው ከበርሃ የሚኖሩ አንዱ የበቃ አንዱ ያልበቃ የበቃው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ ጠየቀው ያልበቃውም

አንተን ብፈራህ ነው እንጂ ይህስ ለእኔም ይረቅብኛል አለው። የበቃውም እስኪ ቤተክርስቲያን እንሂድ ብሎ ተያይዘው ሄዱ ቆመው ሲያስቀድሱ ቁሱ ሀበነ ሲል በአምሳለ በግዕ ሲያርደው ሲያወራርደው አሥሩ ጣቶቹ ሁሉ በደም ተነክረው አይቶ ያልበቃው ደንግጦ ወድቋል ለሁሉ በሚቻል መታየቱ ነው እንጂ ዘወትር እንዲህ እሆናለሁ ብሎ ድምጽ አሰምቶታል። ወያብዑ አርባእተ ጽርስፎራ በእለተ እሑድ ወሠለስተ በካልዓት። ከአርባእቱ ሦስቱ የጴጥሮስ የዮሐንስ የያእቆብ ምሳሌ አንዱ የጌታ ምሳሌ ነው። ከሦስቱ ሁለቱ ወንበዴዎች አንደኛው ጌታ ነው። ወኢይኩን ኅብስት ዘነቅዐ አላ ይኩን ድኑነ እምኩሉ ነውር። ወኢያቅርቡ ኅብስተ ዘተርፈ እምትማልም። ወዘይሠርዕ ጽዋዓ ኢይደይ ወይነ ብሉየ ወኢይቶሥሕ ማየ ብዙኀ። ደሙ እንደ "ለ" ፊደል ግራ ቀኝ ውሃው በመካከል ወርዷልና ሁለት እጅ ወይን አንድ እጅ ዉሃ ይሁን አለ። ሌላው 9 እጅ ወይን አንድ እጅ ውሃ አለ። ከ4ቱ ቅንዋት ከአፉ ከአፍንጫው ከራሱ በገረፉት ጊዜ ከመላ ሕዋሳቱ ሐራዊ ኅዙን በወጋው ጊዜ ደም ፈሶታል ዘጠኝ ይሆናል። አሥረኛ ማየ ገቦ ነው። ወእምቅድመ ኩሉ ይትሐጸብ እደሁ ካህን ወኢያይብስ ዳእሙ ይመዝምዝ ቦቱ ኅብስተ እንበለ ቡራኬ ነሚኦ በእደሁ። መቀት ሳለው ሥጋውን ደሙን ያቀብል መቀት ከተለየው መለኮት ተለየው ያሰኛልና። መሢሐዊ ዘኢይነሥእ እምቁርባን እንዘ ይትከሀሎ ይከውን ከመ ዘኢተጠምቀ እምድህረ ተጠምቀ። ጌታን በዕለተ ሐሙስ ጥዒሞ አጥዓሞመ ይለዋል ስለምን ቢሉ ለእርሱ የሚረባው የሚጠቅመው ሁኖ አይደለም እንዳያስፈራቸው ለማስደፈር ነው እንጂ። እንደ ባለመድኃኒት ቀምሶ ይሠጣቸዋል አንድም ለአብነት ነው። ሳይቀበል ቢያቀብላቸው የላሬ ቁስ ሳልቀበል አቀብየ ልሂድ ባለ ነበርና። ወኢይደልዎ ለካህን ከመ ይልክፍ በእደሁ ዘጸጋም ከናፍረ ጽዋዕ ቁሱ ጽዋውን ተጠንቅቆ በቀኝ እጁ ከንፈሩን ይዞ በ4 ማዕዘን ይወዝውዘው። መሥዋእቱ ካለ ዘንድ ሕማሙ ሞቱ የግድ ይታሰባልና ሶበ ትገብርዎ ለዝንቱ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ አለ። ቁርባንን ቅዱስ ምሥጢር ይለዋል።ለእለ ይትሜጠው ንሥዐተ ቅዱስ ምሥጢር እንዲል። አንድ ባሕታዊ 40 ዓመት በገዳም ኑሮ በመልአክ አሳሳቢነት ቁርባን ሊቀበል ቅዳሴ ገብቶ ቅድሳት ለቅዱሳን ሲል ሰምቶ ሳይቀበል ተመለሠ። እንደገና 40 ዘመን ኑሮ ሊያስቀድስ ሊቆርብ መጣ ልክ ይኸው ቃል ሲባል ሊወጣ ሲል መልአኩ አሁንስ በቅተሀል ተቀበል ብሎት አጽናንቶት ተቀብሏል። ይህም ከኃጢአት መንጻት ብቻ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል አያበቃም ምግባር ትሩፋት ሰርቶ መቀበል ይገባል። ወካህናትሰ ይትመጠው እማእከላይ ኅብስት/ቁርባን። አስቀድመው ካህናት ይቀበሉ ከዚያ ሕዝቡ ከዚያ የተጠመቁ ሕጻናት። ከዚያ ንፍቅ ዲያቆናት ከዚያ አናጉንስጢሳውያን ከዚያ መዘምራን ከዚያ ዐጸውተ ጥኅት ይቀበሉ። ከእነዚህ በፊት ግን ደናግል ይቀበላሉ በፊት የመነኮሱት ከዚያ ያልመነኮሱ ደናግላን። ከዚያ በንሥሓ ተመልሰው የመነኮሱ መነኮሳት ይቀበላሉ። በሴቶችም እንዲሁ በየመዓርጋቸው ይቀበሉ። ደናግላን የካህናት ሚስቶች ከዚያ የዲያቆናት እያለ ማለት ነው። ከታመመ ሰው ውጭ ከቤተክርስቲያን ውጭ ማቁረብ አይገባም። ወይኩን ተመጣዌ ቁርባን ዕሩቀ ርእስ ወምስቁለ እድ። ካህን ቢሆን መጠምጠሚያውን ያውርድ ሴት ብትሆን ሰርመዴዋን ክንንቧን አውርዳ ይቀበሉ። የሚፈትተው ካህን ትላልቅ አድርጎ አይፈትት። በመጠን በመጠን አድርጎ ይፈትት። ሥጋውን ሲቀበል አንድ ጊዜ አሜን ደሙን ሲቀበል አሜን ወአሜን ይበል። በደሙ ሁለት ጊዜ አሜን ማለታችን ሁለት ጊዜ ከጎኑ ደም ፈሷልና ከሞት አስቀድሞ ከመላ ሕዋሳቱና ከሞት በኋላ ከጎኑ። የታመመ ሰው ቢኖር በቤተክርስቲያን ያሉ

ምእመናን ከተቀበሉ በኋላ ከቤቱ ሂደው ካህናት ያቀብሉት፡፡ ወለእመ ተርፈ ሥጋ ወደም ይመጥዎሙ ካህን ለካህናት ወለዲያቆናት እምቅድመ አቁርሮ ማይ ለለአሐዱ ክልኤተ ጊዜ ከመ ይኩን ሥሉሰ ምስለ እንተ ነስኡ ቀዲመ፡፡ የሦስትነት ምሳሌ ነው፡፡ ወእም ደምኒ ከማሁ ክመ ወለእመ በዝነ ይንሥኡ ሠለስተ ጊዜ፡፡ እስመ ኢይትዋለጥ ኀበ ከዊነ ኅብስት ወወይን፡፡ ከሥጋው ከደሙ ነጥቦ ቢገኝ እንደምን ይሁን ቢሉ ከማየ መቁረር አስቀድሞ ቢሆን አንስተው ይላኩታል ማየ መቁረርን ካደረጉ በኋላ የተገኘ እንደሆነ ግን በጽዋእ አድርገው በማኅፈድ ሸፍነው አሳድረው በነጋው መሥዋእት ሰርተው እንደገና ቀድሰው በደም ጠምተው ይቀበሉታል፡፡ ደሙ ግን ቡራኬው ጸሎተ ቅዳሴው ሳይፈጸም ፈሶ የተገኘ እንደሆነ እንደገና ሌላ አምጥቶ ቡራኬውን ጸሎተ ቅዳሴውን አድርሶ እንደገና መቀበል ነው፡፡ ኢይደሉ እምድህረ ተመጥዎ ቁርባን ተሐጽቦ አእዳው ወአእጋር ወተዓርቆ አልባስ ወሰጊድ ወአስተብርኮ፡፡ ሥጋው ደሙ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፡፡ መንግሥተ ሰማያት ከገቡ በኋላ ድካም አለ ያሰኛልና፡፡መራቆትም መለኮት የተለየው ያሰኛልና፡፡ **ወወሪቀ ምራቅ፡-** ለወጣኒ ከተቀበለበት ሰዓት እስከ ተቀበለበት ሰዓት መጠበቅ ይገባዋል፡፡ ፍጹማን ግን እስከተቻላቸው ይጠብቃሉ፡፡ እንደ አባ መቃርስ 60 ዓመት ምራቁን አልተፋም፡፡ ወአውጽአ ደም፣ ቀሪጸ አጽፋር፣ ወተላጽዮ ጸጉር፣ ሐዊረ ፍኖት ሩቅ ጎዳና መሄድ አይገባም ሀተታ እንደሰጊድ ነው፡፡ ወተፋትሖ ምስለ ሰብእ፣ወበዊእ ውሰተ ቤተ ብለኔ፣ በሊዕ ወሰትይ ዘእንበለ ዓቅም፡፡ ከመጠን የወጣን መብል መጽሐፍ ደዌ ይለዋል፡፡ ወተራክቦ ምስለ ብእሲት፡፡ አስቀድሞ 3 ቀን ከተቀበሉ በኋላም 3 ቀን ሊጠበቁ ይገባል፡፡ ወዘይመስሎ ለዝንቱ ኢይደሉ እምድህረ ነሲአ ቁርባን፡፡ የተረፉትን ሁለቱን ኅብስቶች አውሎጊያ ይላቸዋል፡፡ እኒህ ሁለቱ እንደ ሰአልናከ ምግብ ናቸው፡፡ ቁርባን አይደሉም፡፡ ቂም፣ በቀል፣ ቅናት፣ ተንኮል የያዘ ሰው ቢኖር አይግባ አይቅረብ፡፡ የሐልዮ ኃጢአት ያለበት ሰው ቢኖር አይቁረብ፡፡ ምእመናን በጥምቀተ ማይ እንደተጠረገ ቤት ይሆናሉ ከኃጢአት ይነጻሉ ዘይት ዘኢጽሉይን (ቅብዓ ዘይት) ሲቀቡ ከቁራኝነት ይላቀቃሉ እንደተነጠፈ እንደተጎዘጎዘ እንደተለሰነ ቤት ይሆናሉ፡፡ በቅብዓተ ኔሮን ንጉሥ ከነሠራዊቱ ገብቶ ዙፋኑን ዘርግቶ እንደተቀመጠበት ቤት ይሆናሉ፡፡ ከሥላሴ ይወለዳሉ በዚህ ጊዜ 2 **መላእክተ ዑቃቢ** ይሰጠዋል፡፡ አንዱ በመዓልት አንዱ በሌሊት ይጠብቀዋል፡፡ ሰው በሞተ ጊዜ ሰይጣናት በአየር ተጋብዖ ያደርጋሉ፡፡ ሥጋውን ደሙን የተቀበለች ነፍስ ያዩ እንደሆነ ደሙ ማኅተሚ ነውና አይቀርቧትም ጥለዋት ይበተናሉ፡፡ ሕዝቡ ያልበቁ ልዑካኑ የበቁ እንደሆነ የሕዝቡን (ሕዝቡ የተቀበለውን ቁርባን) ለልዑካኑ ይደርብላቸዋል፡፡ ሕዝቡም ልዑካኑም ያልበቁ እንደሆነ መልአክ ወስዶ በበረሃ ለወደቁ ባሕታውያን ያቀብላቸዋል፡፡ ያም አያውቅም ይህም አያውቅም ያ እንዳይታበይ ይህ ከቀቢጸ ተስፋ እንዳይደርስ ነው፡፡ ቁርባን አንድነቱን ሦስትነቱን አውቀው ሕማሙን ሞቱን አምነው ኃጢአታቸውን ለመምህረ ንሥሓ ነግረው መምህረ ንስሓ ያዘዘውን ሰርተው በሚገባ ለሚቀበሉ ሰዎች የሚያድን እሳት ነው፡፡ ሐተታ እሳት በመጠን የሞቁት እንደሆነ የበሉትን የጠጡትን ያስማማል፡፡ እሳት በላዒ ለአማጽያን ለእለ ይክህዱ ስሞ፡፡ይህም እንደ ማየ ግብጽ ነው በግብጻውያን ሲለወጥባቸው በእስራኤል አልተለወጠባቸውም፡፡

አሜን

ሃይማኖት ቢሉ አምን ታሪክ ቢሉ እውነት በረከት ቢሉ ይደረግልን ማለት ነው፡፡ መሰንቆሰ

ይእቲ ሃይማኖት እንተ ለብስዋ ሰማእት።

የደም ስር

ለሰው 666 አሥራው አሉት። ነፋስ ለስድስቱ ያቀብላል። ስድስቱ ለስድሳው ስሳው ለ600ው ያቀብላሉ በዚህ ሰው አዋቂ ሕያው ሁኖ ይኖራል።

ትሕትና

አባ መቃርስ አርድእቱን አስከትሎ ሲሄድ ሕጻናት አደባባይ ተሰብስበው እኩሉ አንድ ወገን እኩሉ አንድ ወገን ሁነው አንድ ባዕለ ጸጋ አለ እርሱ ይወደናል እኛ እንጠላዋለን አንድ ድኃ አለ እርሱ ይጠላናል እኛ እንወደዋለን ሲሉ ቁሞ ያዳምጣቸዋል። አባታችን ከእነዚህ ሕጻናት ምን ቁም ነገር ይገኛል ብለህ ነው አሉት። መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ሕጻናት አድሮ ሲዘልፈን አትሰሙምን ባለጸጋ የተባለ ክርስቶስ ድኃ የተባለ ዲያብሎስ ነው አላቸው። ይ.ዲ. እለ ውስተ ንሥሓ ሀሎክሙ አትሕቱ ርእሰክሙ። አባ ሕርያቆስን ግብረገብ ነውና ሥርዓት ቢያጸናባቸው ይጣሉታል ያልተማረ ነውና ይንቁታል ከመሾም መማር አይቀድምምን እያሉ። እርሱ ግን ወእቀውም ዮም በትሕትና ወፍቅር ብሎ እንዲያመጣው እንደጠሉኝ ልጥላቸው እንደናቁኝ ልናቃቸው ሳይል በፍቅር በትሕትና ጸንቶ ያስተምራቸው ነበረ። ኢንሰርገው እንከ ትዕቢተ ወትዝህርተ። ትዝህርት የአስተያየት የአነጋገገር የአለባበስ የአካሄድ ነው። ትዕቢት የልቡና። ናጥሪ እንከ ትሕትና ምስለ ንጽሕና ናጥሪ እንከ አፍቅሮ ወየዋሐተ ከመ ሐዋርያት። የውሃት ያዩትን ዓለም ባላዩት መለወጥ ነው።

መላእክት

ወኢይመስሎሙ ለመላእክት ከመ ዘቀደስዎ መጠነ መንፈቀ መንፈቃ ለአሐቲ ሰዓት እምአመ ተፈጥረ ዓለም እስከኔሁ። ሠራዊተ ዲያብሎስ የነበሩ ከሠራዊተ ሚካኤል ተደርበዋል። መላእክት ከቤተክርስቲያን አይለዩምና በቅድመ መላእክትከ እዜምር ለከ። ቅዱስ ገብርኤል መጋቤ ሐዲስ ነው። ቅዱስ ሚካኤል መጋቤ ብሉይ ነው። ሥጋው ደሙ ከሚፈተትበት ስሙ ከሚነገርበት መላእክት አይለዩም። በመዓልት 600 በሌሊት 600 መላእክት ይጠብቁታል። 300ም የሚሉ አሉ። በቅዳሴ ጊዜ ግን እንደሻሸ ይነጠፋሉ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ እንደ ግንድ ይረበረባሉ። ሰውና መላእክትን እግዚአብሔር መፍጠሩ ለምስጋና ነው። መላእክት ጌታን አይተው የሚሰግዱለት አይደለም ለሥልጣኑ ይሰግዳሉ እንጂ ለጌትነቱ ይገዛሉ እንጂ። ናሁ ሀለው መላእክት እለ ይሔውጹ ቤተክርስቲያን።

ሰው፣ ዕፀዋት፣ እንስሳት

ከዕጸው ከአዕባን ለይቶ እንስሳትን አራዊትን በደማዊት ነፍስ አክብሯል። ከእንስሳት ከአራዊት ለይቶ ሰውን በነባቢት ነፍስ አክብሯል።

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ እውቀት

እግዚአብሔር የትሑታንን ሰውነት በረድኤት ይጎበኛል። የተቸገረውን ሰውነት ቸል አይልም። ለሊሁ ዓለሞሙ ወለሊሁ ተድላሆሙ ወለዓለም ውእቱ ርስቶሙ ወባላሂ ለእጓለ ማውታ። ዕቤራት የሚላቸው ጎመን ዘሪ ቤት ሰሪ ባል ልጅ የሌላቸው ናቸው። **ሰላም፡-** ንጉሠ ሰላም ሰላመ ሀበነ። ጸልዩ በእንተ እለኖሙ መሐራ እግዚኦ ወተሠሀላ ለነፍሰ አቡነ እገሌ። ሀበነ እግዚኦ አዕይንተ አዕምሮ ወትረ ኪያከ ይርአያ ወአእዛኒነኒ ቃለ ዘባሕቲትከ ይስምዓ። **ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፡-** ኦ እግዚኦ ትጸውር ለኩሉ እንዘ ኢትደክም። ትሜሲ ለኩሉ እንዘ ኢታሐጽጽ። ሐተታ ሙሴ ጌታን ትበላለህን አለው አዎን አለው ምንተ ትበልዕ ወምንተ ትሰቲ ብሎ ቢጠይቀው ኃጥዕ እመ ይኬሥሕ መብልዕየ ውእቱ ወእመ ይግእር ስቴየ ውእቱ። ትሔሊ ለኩሉ እንዘ ኢታረምም ትዜክር ኩሎ እንዘ ኢትረስእ ተአቅብ ኩሎ እንዘ ኢትነውም። ሙሴ ጌታን ኢትነውምኑ ብሎ ቢጠይቀው እወ ኢይነውም ብሎታል። ጴጥሮስም እንደ ሙሴ ቢጠይቀው የዕንቁ ዕዋ ውሃ ሞልቶ ሰጠው ሳይጠጣ ወዲያው አንጎላቸ ጽዋው ከእጁ ወድቆ ተሰበረ። ቢነቃ ውሃው ፈሶ ጽዋው ተደፍቶ አገኘው ደነገጠ። እኔ ይሕን ዓለም የያዝኩት በመካከል እጀ ነው።ንዋም ቢኖርብኝ እንዲህ አንድ ጊዜ ያልፍ የለምን ብሎታል። ዳግመኛም ይህን ዓለም እንደምን አድርገህ ይዘኸዋል ቢለው ዓለሙን በመሀል እጁ ይዞ እርሱን በመካከል አድርጎ አይቴ ሀሎከ አለው ኢየአምር ብሎታል። ደመናን እግዚአብሔር ካላዘዘው አያዘንምም። ኦ ዛቲ ዕለት ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ሰአሊ ለነ አስተምሕሪ በእንቲአነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ፡- ሐተታ ምን ግእዛን አላትና ሰአሊ ለነ ለነ አለ ቢሉ በእንተ ጽንሰቱ በእንተ ትንሳኤሁ ብለው በዚች ቀን በሰሩት ስራ የሚከብሩ ስለሆነ ነው።

ንዑሰ ክርስቲያን

ንዑሰ ክርስቲያን የሚላቸው የሃይማኖት የምግባር ነው። የሃይማኖት ወንዱ ካደገ ከጎለመሰ የመጣ እንደሆነ ሴቲቱም ካደገች ከቆነጀች በኋላ የመጣች እንደሆነ ፈጥነው አያጠምቋቸውም አምስቱን አዕማደ ምስጢር እያስተማሩ 3 ዓመት ያኖሯቸዋል። ምግባር ሲፈጸምላቸው ሃይማኖት ሲረዳቸው ያጠምቋቸዋል። የምግባር የተጠመቁት ኃጢአታቸውን ለመምህረ ንሥሓቸው ነግረው እስከዚህ ድረስ በበረሃ ሁናችሁ እስከዚህ ድረስ በአጸደ ቤተክርስቲያን ቁማችሁ እስከዚህ ድረስ ከቤተክርስቲያን እየገባችሁ ምዕዳን እየሰማችሁ ፃኡ ሲባል እየወጣችሁ እስከዚህ ድረስ ቁማችሁ እያስቀደሳችሁ ቅዳሴው ሲፈጸም እየወጣችሁ በዚህ ጊዜ ሥጋውን ደሙን ተቀበሉ ብሎ የሚወስንባቸው ናቸው። ጸልዩ በእንተ ንዑሰ ክርስቲያን። ፃኡ ከተባለ በኋላ ንዑሰ ክርስቲያን ወጥተው ከአጸደ ቤተክርስቲያን ሁነው ይስሙ።

መጽሐፈ ቄደር

ወንዱ ከአረማዊነት የደረሰ እንደሆነ ሴቲቱም ከአረማዊ የደረሰች እንደሆነ ቀኖናቸውን ሲፈትሙ ይህን መጽሐፍ ደግመው ያጠምቋቸዋል ከኃጢአት ይነጻሉ።

ሰው የታመመ እንደሆነ ይህን ደግመው ያጠምቁታል ከደዌ ሥጋ ይድናል።

የቅዳሴ ታሪክ፣ ቅዳሴ፣ ሥርዓተ ቅዳሴ

አዳም በገነት ሲኖር መካነ ጸሎት ለይቶ ይኖር ነበር። ከገነት ሲባረር በደብር ቅዱስ መካነ ጸሎት ለይቶ ይኖር ነበር። አዳም ከሞተ በኋላ አጽሙን እንደታቦት አድርገው መሥዋእት ጸሎት ሲያቀርቡ ነበር። ይህ ሲያያዝ ከኖኅ ደረሰ። ኖኅም ከመርከብ ሲገባ አጽመ አዳምን ይዞ ገባ። ከመርከቡ ከወጣ በኋላም አጽመ አዳምን እንደ ታቦት አድርጎ መሥዋእት ሠዋ። ከዚያ ሴም ለመልከጼዴቅ አስጠብቆታል። ከዚህ በኋላ እነ አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ያእቆብ ወዘተ ቦታ አለዩም። እስከ ሙሴ በፈለጉት ቦታ ይጸልዩ ነበር። ሙሴ ደብተራ ኦሪትን ከሰራ በኋላ በደብተራ ኦሪት ሲያያዝ ሰሎሞን ላይ ደረሰ በመቅደስም ሆነ። ይህ እስከ ሥጋዌ ደረሰ። ሐዋርያት እንደ ጌታችን በየደረሱበት እየቀደሱ ያቆርቡ ነበር። በኋላ በፊልጵስዩስ የመጀመሪያዋ ህንጻ ቤተክርስቲያን ተሰራች። ጌታም እምይእዜሰ አንትሙኒ ከመዝ ግበሩ ብሎ አሏቸዋል። በ12ቱ መገብተ አውራኅ አምሳል 12 ሁኖ በ7ቱ መገብተ እለታት አምሳል 7 ሁኖ ይቀደሳል። ቅዳሴ ሲገባ መጀመሪያ ካህኑ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ 3 ጊዜ የአስተብርኮ ሰጊድ ሰግዶ አቡነ ዘበሰማያት ይድገም። ልብሱን በእጁ ይዞ አጭርነቱን ረዥምነቱን ልዑካኑ መምላታቸውን ሕዝቡ መሰብሰባቸውን አይቶ አቡነ ዘበሰማያት አሳርጎ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ አንድ ጊዜ እጅ ነሥቶ ቀሳውስትን ዲያቆናትን ሕዝቡ ሳይቀሩ ማሩኝ ይላቸዋል። ልዑካን መሟላታቸው ሳይታወቅ ልብሰ ተክህኖ አይለበስም። ከዚህ በኋላ የቤተመቅደሱ መድረክ 3 ነው። ከሚመቸው ላይ ሁኖ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ጸሎቱን ይጀምራል። መቅድመ ኩሉ ይጸሊ ቀሲስ ጸሎተ ንሥሓ ጊዜ በዊያቱ ኀበ ቤተክርስቲያን ወይበል እመዝሙረ ዳዊት 24፣ 60፣ 101፣ 102፣ 129፣ 130። ቁሱ ጸሎተ ንሥሓውን ሲደግም ወድቆ መስማት ይገባል። መቅደስ ከመግባቱ በፊት ጸሎተ ጎርጎርዮስን ይጸልይ። ወእምዝ ይባዕ ካህን ውስተ ቤተመቅደስ ወይስግድ ቅድመ መንጦላእት ወይበል ጸሎተ ባስልዮስ ላእለ ሣዱናት እንዘ ያርኑ። ሊቀጳጳስ ሳለ ጳጳስ ጳጳስ ሳለ ቄስ ልብሰ ተክህኖውን መባረክ አይገባውም። ወእምዝ ይባዕ ውስጠ ወይስግድ ቅድመ ታቦት።ወእምዝ ጸሎት ላእለ ኩሎሙ ንዋየ ቤተክርስቲያን። ከዚያ ታቦቱን ያልብስ ወይክድን መንበረ ጻሕሉን ያልብስ ወጽዋዓ በልብስ ቅዱስ በንጹሕ ማኅፈድ። ወኢይኅድግ ምንተኒ ዘኢኮነ ክዱነ። ወይኅረይ **ዕጣነ** ወያንብር ውስተ ሙዳየ ዕጣን። 5 ቆቀር እጣን መርጦ በሙዳይ ያኑር። አስቀድሞ ታቦቱን አልብሶ በዚያ ላይ ማኅፈዱን አድርጎ 5 ቆቀር ዕጣን መርጦ በሙዳይ አድርጎ ጻሕሉን ጽዋውን እርፈ መስቀሉን አድርጎ በዚያ ላይ መላውን አልብሶ ጸሎቱን ይጀምራል። እመቦ ጳጳስ አው ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ አው ዲያቆን ዘኢተምህረ ወኢያእመረ መጽሐፈ ኪዳን ወሲኖዶስ ወዲድስቅልያ ወሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እስከ ፍጻሜሁ ወኩሎ ሕገጋቲሁ ኢይግባዕ ለግብረ ተልእኮ ውስተ ቤተ ክርስቲያን። ወለእመ ቦአ በተሐብሎ ወድፍረት ይትመተር እማእርጊሁ ወይሰደድ እም ቤተክርስቲያን። ወለእመ ተጠየቀ ዲበ ካህን ከመ ይገድፍ አንብቦ ይትከላእ እስከ ያጸሪ አንብቦ ወለእመ አበየ ይትከላእ እም ቁርባን። ወዘይቀድስ ካህን ይቁም በፍርሀት። ቅዳሴ ከገባ በኋላ ጎሊናውን አፍዓዊ/ዓለማዊ ነገር ጥቂትስ እንኳ ያስብ

ዘንድ አይተወው አያሰናብተው። በታቦቱ በግራና በቀኝ ያብሩ እንጂ በአንድ መብራት ሊቀድሱ አይገባም። ዛሬስ ጌታው እገሌ ወይዘሮ እገሊት መጥተዋል ድምጤን ይስሙልኝ ቃሌን ይዩልኝ ብሎ በማቀማጠል በማደላደል አይቀድስ። በቅዳሴ ጊዜ ችግር ካለም ጠቅሶ ማሳየት እንጂ የሚናገር አይኑር። ከእመቦ ቀጥሎ ቁሱ ከጎብስቱ ላይ እጁን ረቦ እየዞረ ይጸልይ።ከዚያ አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ። ወእምዝ በርጡብ እደሁ ይንሣእ ካህን ጎብስተ ወይመዝምዞ ላዕለ ወታሕተ። ዳግመኛም አመሳቅሎ በመሐል እጁ ያትም። ከዚህ በኋላ በሰሜን ደጅ መንበር ውስጥ ለውስጥ ንፍቅ ቁስ በማጎፈድ ይቀበለው። በደቡብ ደጅ በመንበሩ ውስጥ ለውስጥ ለሰራዒው ቁስ ይሥጠው። ወእምዝ ይዑድ አሐደ ጊዜ ጎበ ታቦት ማህቶት ቅድሜሁ መብራት የያዘ ዲያቆን ከፊቱ ወዲያቆን ድህሬሁ። መብራት የያዘው የዮሐንስ መጥምቅ ቁሱ የጌታ ኂለኛው የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌ ጎብስቱ ከቤተልሔም ተነስቶ ወደ ቤተመቅደስ መግባቱ ጌታ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄዱ ምሳሌ ነው። ከገባም በኋላ ጎብስቱን የያዙት በፊት በፊት ቁሱ እጁን ረቦ በኋላ ሁኖ አንድ ጊዜ ይዞራሉ። ሁለተኛ ቁሱ ቁሞበት ከነበረው ሲደርስ ዲያቆኑ ዙሮ ይቆማል። ንፍቁ ቁስ ማጎፈዱን ይገልጥለታል። ቁሱ አውርዶ ጎሠሥኩ ገጸከ እያለ ክርስቶስ አምላክነ እያለ አትሞ ይዞራል። ሦስተኛ ቁሱ ከተቀበለበት ሲደርስ በሰሜን ደጅ መንበር ንፍቅ በማጎፈድ ውስጥ ለውስጥ ይቀበለዋል። ሠራኢ ቁስም በንፍቅ በኋላ አልፎ በደቡብ ደጅ መንበር ውስጥ ለውስጥ ተቀብሎ ቅዳሴ ውኩፍን ደግሞ አዙሮ ከመንበር ከጻሕሉ ላይ ያኖረዋል። ሁለተኛ ቁሱ ይዞት መዞሩ በር ተዘግቶባቸው ዳር ከዳር እስከ ሐና ቤት ዙረዋልና የዚያ ምሳሌ። መጀመሪያ ቁሱ የሚቀበልበት ቦታ የጌቴሴማኒ ቁስ ለንፍቅ የሚሰጥበት የሐና ቤት ንፍቅ የሚቀበልበት የቀያፋ ቤት ሠራኢ ቁስ አልፎ የሚቀበልበት የጲላጦስ ቤት ጻሕል የመስቀል ምሳሌ ነው። ወይዑድ ዲያቆን እንዘ ይእጎዝ ጽዋዓ ሠለስተ ጊዜ ወይበል እግዚአብሔር ይሬእየኒ እስከ ተፍጻሜቱ። ጌታ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዙሮ ለማስተማሩ አስተምሮ ወደ መስቀል የመሄዱ ምሳሌ ነው። ተራዳኢው ቁስ ከዲያቆን ተቀብሎ በሰሜን ደጅ መንበር ከጽዋ ይገልብጥ። ከዚህ በኋላ በጎብስቱ ላይ እጁን አመሳቅሎ ይጸልይ ከዚያ በወይኑ ይጸልይ። ከዚህ በኋላ ዋናው ቁስ በሃይማኖት በምግባር አንድ እንደሆኑ ለማጠየቅ እጁን ከንፍቁ ቁስ ጋር አገናኝቶ ይበል ተዘከረኒ ኦ አቡየ ቀሲስ በጸሎትከ ቅድስት ይበል። ንፍቁም ከቀሳፊ መልአክ ይሰውርህ መሥዋእትህን ጸሎትህን ይቀበልልህ ብሎ ይመልስለት። ወእምዝ ይቁም ካህን ርቱዓ ሰፊሆ እደሁ ወገጹ መንገለ ምሥራቅ ወይበል በዓቢይ ቃል። ዲያቆኑ ወደ ምእራብ መዞሩ ሕዝቡን ተንስኡ ጸልዩ እያለ ለማንቃት ነው። ቁሱና ዲያቆኑም ከጌታ መቃብር ለታዩት ለሁለቱ መላእክት አምሳል ናቸው። ሰላም ለኩልክሙን ቁስ በጌታ ተገብቶ ተናግሮታል። ከዚህ በኋላ መብራቱን የያዘው ዲያቆን በፊት ለፊቱ ሰራኢው ዲያቆን ጳውሎስ መጽሐፍ ይዞ በኋላ ቁሱ በመሐል ሁነው ታቦቱን ሦስት ጊዜ ይዙረው። ወእምዝ ይረድ ውስተ አንቀጸ ምእራብ ወይእጥን ሠለስተ ጊዜ በአድንኖ ርእስ። ጳጳስ ቢኖር ሦስት ጊዜ በዐደት አንድም በንዝኅት ይጠነው። ወእምዝ ይእጥን ካህናተ ኩሎሙ። ወእንዘ ይወጽእ ያንብር እደሁ ዲበ ርእሰ ዲያቆን ወይበል በረከተ ጳውሎስ ይኅድር በላእሌከ። የሚያነብ ነውና በረከተ ጳውሎስ አለ። ጳውሎስን ወደምእራብ መልእክታተ ሐዋርያትን ወደሰሜን ግብረ ሐዋርያትን ወደ ደቡብ ወንጌልን ወደ ምሥራቅ ዙረው ያንብቡ። **ምስባክ**፦ ዲያቆኑ ሁለት ጊዜ ሕዝቡ ሦስት ጊዜ ነው። አምስት ጊዜ መባሉ 5500 ዘመን ትንቢት ለመነገሩ አምሳል ነው። በስድስተኛው ቁሱ ወንጌል

ማለቱ በስድስተኛው ሺ ጌታ ሰው ሆኖ ወንጌልን ለማስተማሩ አምሳል ነው። የማዕዘን ቡራኬ የጸሎተ ዕጣን ቡራኬ ከቁጥር አይገባም። ወይሣለሙ ኩሎሙ ካህናት ወኩሉ ሕዝብ ወንጌለ። ወንጌልን ሲሳለሙ ሴት ብትሆን ሰርመዲዋን ክንብንቧን ታውርድ ካህን ቢሆን ቀጸላውን ጥምጥሙን ንጉሥ ቢሆን ዘውዱን ያውርድ ትእምርተ ትሕትና ነውና ወንጌል ሲነበብም እንደዚሁ ያድርጉ። በቅዳሴ ጊዜ ከተሠጥዎ በቀር አርምሞ ተደሞ ሊሆን ይገባል። **ደወል፡-** ፯ኡ ሲባል ደወል ይደወላል። ደወል በኖኅ ተጀምሯል። በነግህ በቀትር በሠርክ ይደውል ነበር። በነግህ ለጸሎት ለተግባር በቀትር ለምግብ በሰርክ ለማሰናበት ይደውል ነበር። ዛሬም የተጋብኦ ደወል የትንቢተ ነቢያት የግብር ደወል የብስራተ ገብርኤል የወንጌል ደወል የስብከተ ዮሐንስ የእግዚኦታ ደወል የጌታ ትምህርት። የድርገት ደወል የሐዋርያት የፅ አርድእት ትምህርት ምሳሌ ነው። ፯ኡ የሑሩ እምኔየ የዚህን ጉዞ ደወል የግርማ መዓቱ ምሳሌ። ወንጌል ከተነበበ በኋላ መቅደሱ ይዘጋል ምሕረት ለመከልከሉ ምሳሌ ነው። ወተሐጽቦተ እዴሁ ለቀሲስ አምሳለ ሕጽበተ እዴሁ ለጴላጦስ። ወኢይደሉ ለቀሳውስት ወለዲያቆናት እለ ኢበጽሑ ለጸሎት ሌሊተ ከመ ይባዑ ውስተ ምሥዋዕ። ያደሩ እያሉ ያላደሩት አይግቡ ሲል ነው። የሚታጎል ቢሆን የሚቻለው ገብቶ ይቀድስ። **ቅዳሴ ሐዋርያት፡-** ሐዋርያት ቅዳሴ የጻፉበት ምክንያት መናፍቃን ሐሳውያን ሐዋርያት ነን እያሉ እየጻፉ ዙረው አስተማሩ የዋሃን ሰዎችንም አሳቱ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለወጡ በዚህ ምክንያት ሐዋርያት በሮም ጉባኤ አደረጉ። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሠሩ። ይህን ቅዳሴ ሐዋርያት ብቻቸውን ተናግረውታል። አስተጋባኢው ባስልዮስ ነው። ባራኪው ሠራኢው ቂስ ነው ንፍቅ አይባርክም። **ይ.ዲ** እለ ትነብሩ ተንሥኡ ሀተታ አሁን በቅዳሴ ጊዜ ከሕመም ከአረጋዊ በቀር የሚቀመጥ ኑሮ አይደለም። ከዓራተ ዝንጋኤ በተዘከሮ ከዓራተ ሐኬት በአንክሮ ተነሡ ሲል ነው። ውስተ ጽባሕ ነጽሩ፡- ሀተታ ምሥራቅ ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ምእራብ ማኅደረ ዲያብሎስ መሆኑን መናገር ነው። አንድም የጌታን ነገረ ምጽአቱን አስቡ ሲል ነው። አንድም ምሥራቃውያን ሰብአ ሰገል ባመኑባት በወንጌል እመኑ። ዲያቆናትን እስመ እሙንቱ ከመ ሕዝብ ይላቸዋል። ዕርገተ ዕጣን 13 ጊዜ ነው። ዓውዶ ሲገባ፣ ኦ ተወካፌ ንሥሃ ሲል፣ ጸዋትው ሲያልቅ ሦስት ጊዜ፣ በዕርገተ ሕጻን ጊዜ እፍን አድርጎ ሦስት ጊዜ ከሥጋው ሦስት ጊዜ ከደሙ 12 ይሆናል። ድርገት ሲወርድ ሁለት ቀሳውስት አንዱ ሥጋውን አንዱ ደሙን እያጠኑ ይወርዳሉ 13 ይሆናል። የ13ቱ ሕማማተ መስቀል ምሳሌ ነው። ይ.ዲ አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት፡- እስከዚህ ሥጋው ደሙ በማኅፈድ እንደተሸፈነ ይቆያል። በዚህ ጊዜ ሠራኢው ቂስ ኅብስቱን አንስቶ ይይዛል። ንፍቁ ቂስ ማኅፈዱን ይገልጽለታል። ማንሳቱ የትንሳኤ አምሳል ነው። አንስኦተ ማኅፈድ መልአክ ወአንኮርኮራ ያላት የድንጋይቱ አምሳል። ወእምዝ ያንቅዖ ለኅብስት ኅበ ኃምስቱ ገጽ ንስቲተ እንዘ ኢይሌልዮ። ከላይ ከታች ከግራ ከቀኝ ከጎኑ አራቱ የአራቱ ቅንዋት ምሳሌ አንዱ የኩናተ ሐራዊ ምሳሌ። ሕዝቡ ሦስት ጊዜ አሜን አሜን አሜን ይበሉ ሀተታ ለአጠይቆ አካላት ቃሉ ያለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ። አንድም በነባቢት ነፍስ በደማዊት ነፍስ በሥጋ እንቀበለዋለንና ነው። ወኢይደልዎ ለካህን ከመ ይልክፍ በእዴሁ ዘጸጋም ከናፍረ ጽዋዕ ቂሱ ጽዋውን ተጠንቅቆ በቀኝ እጁ ከንፈሩን ይዞ በ4 ማዕዘን ይወዝውዘው። አንድ ሐራዊ አለን የለን ብሎ ጎኑን ቢወጋው ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደቀኝ ተናውጧልና የዚያ ምሳሌ ነው። በቀኝ እጁ እንጂ በግራ እጁ ሥራ መስራት አይገባውም። ሥጋውን ከታች ወደላይ እየፈተተ መውረዱ የርደቱ ከቀኝ

ወደግራ ከግራ ወደ ቀኝ መፈተቱ ከናዝሬት ወደገሊላ ከገሊላ ወደ ናዝሬት እያለ ለማደጉ ምሳሌ ነው። ዙሪያውን ይፈትተዋል 3 ዓመት ከ3 ወር ዙሮ ወንጌልን ለማስተማሩ ምሳሌ ነው።ከታች እየፈተተ ወደ ላይ መውጣቱ የትንሳኤ የዕርገት ምሳሌ ነው። ዬ ዬ ዬ ወዮ ወዮ ወዮ ማለት ነው። **ሠራዊተ መላእክቲሁን** ከመንጦላእት በአፍዓ እና በውስጥ ሁነው ይጸልዩታል። በአፍአ ያሉት የነቢያት በውስጥ ያሉት የሐዋርያት ምሳሌ። ንፍቅ ቂስ ንፍቅ ዲያቆን በአፍኣ ሠራኢው ቂስ ሠራኢው ዲያቆን በውስጥ ሁነው ነው። ጻድቃን ተጋደሉ ሰማዕታት ከዓው ደሞሙ በእንቲአሁ በአሚነ ዚአሃ ለማርያም ንገኒ ዬ ዬ ዬ ሐዋርያት ተለው ብሎ የጨመረ ቅዱስ ያሬድ ነው። ንፍቅ ዲያቆን ሲገባ አርጎው ኖኃተ መኳንንት ይበል። መንጦላእቱ መከፈቱ ጌታን ሁሉ እንዲያየው ብለው በገበያ ቀን ሰቅለውታልና የዚያ ምሳሌ ነው። ፍትሐት ዘወልድን ጸሎተ ንሥሓን ወድቀው ያስደግሙ። ካህኑ መላውን ኅብስት አንስቶ መያዙ የዕርገቱ ምሳሌ ነው። **እግዚኦታ** የገባ በግርፋት ነው። አንድ ተረፈሳ ቢሉ የአዳም ቀኖና ምሳሌ ነው። አዳምና ሔዋን በፈታሒነቱ መሐሪነቱን ተመራምረው ንሥሓ ገቡ። 35 ቀን በባሕር፣ ሰይጣን ራሱን በገለጸላቸው ጊዜ ደንግጠው 3 ቀን አድረዋል። ቅዱስ ገብርኤል አፋፍሶ ደብር ቅዱስ ወስዶ አኑሮታል፣ አዳምን ሰይጣን በድንጋይ መታው ደንጋይቱ እንደ ደብተራ ሁናው 3 ቀን ተቀመጠ። በሦስተኛው ቀን መልአኩ መጥቶ አንስቶታል። አእዋፍ ከገነት ካመጡት ፍሬ ፈርፍሮ ከደሙ ጨምሮ መሥዋዕት አቀረበ። 41 እግዚኦታ ይህ ነው። አአምን አአምን አአምን ሲል የሦስትነት ምሳሌ ወእትአመን ሲል የአንድነት ምሳሌ ነው። ዘሎቱ ይደሉ ክብር ወስብሀት ወስግደት ሲል በዝየ ይሥግዱ ካህናት ወዲያቆናት። ሕጽበተ እድ ካህናት እጃቸውን ይታጠቡ ለጊዜው ጻሕል ጽዋ የሚይዙ ናቸውና ፍጻሜው ግን እኛ ካወቅነው ኃጢአት ነጽተናል እኛ ካላወቅነው ኃጢአት አንጻን ለማለት ነው። ድርገት ሲወርድ መውደቅ እጅ መንሳት ይገባል። ቅዱሳት አንስት በትንሳኤው ለክርስቶስ እንደሰገዱ የዚያ ምሳሌ። ድርገት ወደ ምእራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምእራብ አድርጎ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው። ወደምስራቅ መመለሱ የትንሳኤ አምሳል። ከወጡም በኋላ ዲያቆን አንድ ጊዜ ዙሮ ይገባል። መዞሩ ሐዋርያት ከዕርገት በኋላ የጌታን ነገረ ሕማሙን ዙረው ለማስተማራቸው ምሳሌ ነው። አንድም በእለተ ዓርብ **መላእክት** ደሙን ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ረጭተውታልና የዚያ ምሳሌ። ድርገት ሲመለስ እጅ መንሳት ሐዋርያት በዕርገት እጅ ነስተው ለመቅረታቸው ምሳሌ ነው። ዲያቆኑም የጌታ ምሳሌ ነው። ነአኩቶ የንዑ ኀቤየ ምሳሌ ነው ሥጋሁ ወደሙ የምስሓ ደብረ ጽዮን ምሳሌ ነው። ሐዳፌ ነፍሱ ጸልዩ ያለው እንደሆነ ጸልዩ እስኪል ወደ ምእራብ ዙሮ። ጸልዩ ካለ በኋላ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ይጸልያል። ወደምዕራብ መዞሩ 5500 ዓመት አዳም በዓረበ ገሀነም ለመኖሩ ምሳሌ። ጸልዩ ካለ በኋላ ፊቱን ወደምሥራቅ መመለሱ ከ5500 ዘመን በኋላ ጌታ መከራቸውን አይቶ ልመናቸውን ሰምቶ ሰው ሆኖ ወደቀደመ ቦታቸው ለመመለሱ ምሳሌ ነው።ዝማሬ ጌታ በተነሳ ጊዜ ያመሰገኑት የዝማሬ መላእክት አምሳል ነው። ቁሱ እጁን በታቦቱ ላይ አመሳቅሎ መጸለዩ ጌታ በዕርገት ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ባርኮ ለማረጉ ምሳሌ ነው። ቡራኬ፦ 42 ጊዜ ነው። 21 የአፍኣ 21 የውስጥ ነው። የውስጥ ቡራኬ በእጅ የአፍአ ቡራኬ በመስቀል ነው። የንዋየ ቅዱሳት ቡራኬ ከቁጥር አይገባም። ለምን 21 ሆነ ስንል ጌታ ሦስት ቀን በመቃብር የማደሩና 18 ሰዓት መከራ የመቀበሉ ምሳሌ ነው። በመጨረሻ ካህኑ ሕዝቡን ካህናቱን በእጁ ይባርካል። ጌታ በዕርገት ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ለመባረኩ ምሳሌ ነው።

ወቀሳውስት ይትባረኩ በተእኅዞ እድ ይትባረኩ በበይናቲሆሙ። ሠራዒው ለንፍቁ ለካህናቱ ሁለቱን እጆን አነባብሮ ዘርግቶ ይስጣቸው። ወሶበ ይባርክ ለቀሳውስት ሚመተ እደሁ ለአቡነ ጴጥሮስ ይበል። ቅዳሴ እግዚእ፡- ከኪዳን የተከፈለ ነው የከፈሉትም ሐዋርያት ናቸው። አንድም የኂላ ሊቃውንት ናቸው። አንድም ባስልዮስ ነው። **ቅዳሴ እግዚእ** በቁስቋም ህዳር 6 በሕንጸታ ሰኔ 21 በፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት ነሐሴ 16 ቀን ይቀደሳል። **ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፡-** ይህን ቅዳሴ ዮሐንስ ቀዳሚሁ ቃል ባለውና ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ባለው መካከል ደርሶታል። አስተጋባኢው ባስልዮስ ነው። አንድም መልአኩ ከውቅያኖስ አስኪሉ በወጣለት እንቁላል እየቀዳ ሲያፈስ አየው። ምሥጢረ መለኮትን መመርመር ከባድ መሆኑን ለማሳየት ማለት ነው። በዘመነ ስብኸት በበዓለ ሐዋርያት በበዓለ ሰማእታት በጽጌ በፍሬ በቅዳሴ ቤተክርስቲያን በአቤል በነቢያት በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ይቀደሳል። **ቅዳሴ ማርያምን** የደረሰው አባ ሕርያቆስ ነው። ሐዋርያት የተማረ ግብረ ገብ ይሾም ብለዋል። ብህንሳ ቅድመ ትሰመይ አርጋድያ ወድህረ መኑፍ። ብዙ ጊዜ ስመ ተፋልሶ አግኝቷታል እንደ ዘጌ ሴትና ወንድ ያልተለየባት ገዳም ናት። በእመቤታችን በዓል በታኅሣስ 28 ቀን የጌና በመጋቢት 29 የትስብእት በጥቅምት 2 ቀን ቀድስ። ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፡- ይህን ቅዳሴ 318ቱ ሊቃውንት አርዮስን ረትተው ጽፈውታል። **ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፡-** በአማኑኤል በታኅሣስ 28 ቀን በቃና ዘገሊላ በጻድቃን በብዙኃን ማርያም በማህበረ በኩር በሠለስቱ ምእት በአርባዕቱ እንሳሳ በካህናተ ሰማይ ቀድስ። **ቅዳሴ አትናቴዎስ፡-** አትናቴዎስ ጽፎታል አስተጋባኢው ባስልዮስ ነው። ስለክብረ ሰንበት ተናግሮታል ስለዚህ እሑድ እሑድ ይህን ሊቀድሱት ይገባል። በግንቦት 7 እና እሑድ እሁድ ቀድስ። ይረስዮ ያላቸው ቅዳሴያት 7 ናቸው፡- ቅዳሴ ሐዋርያት፣ እግዚእ፣ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ባስልዮስ፣ ኤጲፋንዮስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ ናቸው። የንፍቅ ዑደት ሦስት ነው ግብረ ሐዋርያት አንቦ ሲገባ፣ ወንጌል አንቦ ሲገባ፣ ሠራዊተ ብሎ ሲገባ ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የኢየሩሳሌም መቅደስ የቤተልሔም ታቦት፣ መንበር፣ መንጦላእት አንድ ወገን የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ሁለቱ አእማድ የኢያቄምና የሐና ምሳሌ። ኩስኩስት የእመቤታችን ማይ የክርስቶስ አምሣል ነው። መሠረቱ ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉት የአስሩ አበው ሦስቱ ደጅ የሦስቱ አበው ሁለቱ አእማድ የሙሴና የአሮን ዓቢያን መሳክው የዓቢያን ነቢያት ንዑሳን መሳክው የደቂቀ ነቢያት መንጦላእት የዓረፍተ ዘመን የውስጥ አእማድ የሐዋርያት የአፍአ አእማድ የፅ አርድእት ንዑሳን አእማድ የቅዱሳት አንስት 4ቱ ማእዘን የ4ቱ ወንጌላውያን አናቅጽ የቅዱሳን አበው መኃተው የሊቃውንት ምሳሌ ናቸው። ጠርብ የሰማእታት አምሳል። ማገር የረድኤተ እግዚአብሐየር ሣሩ ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕጻናት አምሳል። አንድም መሠረቱ የጴጥሮስ ሕንጻው የምእመናን ምሳሌ ነው። ሁለቱ አእማድ የጴጥሮስና የጳውሎስ ዓቢያን አእማድ የቀሳውስት ንዑሳን አእማድ የዲያቆናት። መጋረጃ ቅጽር የመላእክት የረድኤተ እግዚአብሐር ምሳሌ ናቸው። ሦስቱ ደጅ የሥላሴ ምሳሌ ከመስቀሉ ላይ የሚሆነው የሰኃን እንቁላል የተዘክሮተ እግዚአብሐር ምሳሌ። አጸደ ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ቤተክርስቲያን የመላእክት ምሳሌ። ደጀ ሰላም የገነት ቤተክርስቲያን የመንግሥተ ሰማያት ማኅረጽ መቀጫ እናቱ የሐዋን ልጁ የአዳም ሥርናይ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ሥርናይ በመቀጫ እንዲፈተግ

ጌታም ስለእኛ ብዙ መከራ ተቀብሎ አድኖናል። ሕጻኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ሂድ ያለው መልአክ የሊቀዲያቆን ዮሴፍ የዓቃቢ ሰሎሜ የዲያቆናት ቤተልሔም የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ሦስት ጉልቻ የሦስቱ ማደሪያ ሁናለችና። **ሰገኖ** እንቁላሏን ቀፍቅፋ እስክታወጣ ድረስ ስትመለከት ትኖራለች ምግቧን በምትፈልግበት ጊዜ ተባዕቱን ተክታ ነው። አንድ ጊዜስ እንኳ ጥላው ዘወር ያለች እንደሆነ ይለውጥባታል ደርቆ አይፈለፈላትም። 40 ቀን ሲሆናት ድምጽ ታሰማቸዋለች እነርሱም በውስጥ ሁነው ድምጽ ያሰሟታል ፈልፍላ ታወጣቸዋለች። ሰገኖ የመንፈስ ቅዱስ ቅርፍቱ የፍዳ የመርገም ድምጽ ሲያሰሟት ቀፍቅፋ እንድታወጣቸው እኛም አቡነ ብለን በጠራነው ጊዜ ከግብረ ዓለም ይለየናል። አንድም ሰገኖ የምእመናን ዕንቁላሉ የተዘከሮተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

ንዋያተ ቅድሳት

ጻሕል፡- ሥጋው የሚቀመጥበት ነው። ወይንሣእ ካህን ሜሮነ ወይቅብዖ ለጻሕል ኀበ አርባዕቱ ገጽ በትእምርተ መስቀል እንተ ውስጡ ወዓውዱ። በጽዋእኒ ወበእርፈ መስቀል ወበአልባስ ከመዝ ግበር። ልብሱን ግን ሜሮን አይቀባውም። ክህነት የሌለው ሰው ሊይዛቸው ሊዳስሳቸው አይገባም። **ጽዋዕ** ፡-ደሙ የሚቀመጥበት ነው። **ዕርፈ መስቀል**፡- ደሙን የሚያቀብሉባት እንደ ማንኪያ ዓይነት ናት። ወረስዮን ለዛቲ ቤተክርስቲያን ወለዛቲ ታቦት ንዋያተ ኅሩያተ። ጌታ የተገነዘበት መግነዝ ጨርቅ **ማኅፈድ** ይባላል። እሊህም 5 ናቸው።አንዱ በአውዱ ላይ ይነጠፋል። አንዱ ከጻሕሉ ላይ ይነጠፋል። ሦስቱ ሦስት ጸታ ያለው አኀበር አለ በዚያ ይነጠፋል። እርፈ መስቀል የኩናተ ሐራዊ ማኅፈድ የከለሜዳ አኀበር የአክሊለ ሦክ ዓውድ የኅልኅታ ታችኛው ማኅፈድ የመግነዝ ላይኛው የሰበን አምሳል ነው። ወይኅረይ **ዕጣነ** ወያንብር ውስተ መዳየ ዕጣን። 5 ቆቀር እጣን መርጦ በመዳይ ያኑር። መዳይ የእመቤታችን ዕጠን የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ዘጠኙ ዕፀው ዕጣን ሚዓ፣ ዶሪራ፣ ኡድ፣ ሰሊክ፣ መስተክ፣ ስኒን፣ ሰንድሮስ፣ አበሜ፣ ቀናንሞ ናቸው። ወ**አልባሰ ቅዳሴ** እለ ይቁድሱ ቦቶን ይኩና ጸአድወ ወአኮ ሕብራተ በእለተ ልደት በትንሳኤ በዕርገት መላእክት ወርኃ ትፍሥሕት ወርኃ ተድላ ነው ሲሉ ብሩህ ብሩህ ልብስ ለብሰው ታይተዋል።

ማዕድናት

ብረቱን ሰባት ጊዜ ከከውር ወደ ከውር ቢያመላልሱት ከብርት ማዕርግ ብርቱ ከብር ብሩ ከወርቅ ወርቁ ከዕንቁ ማዕርግ ይደርሳል።

ፊደላት

ግእዝ የአብ ካእብ የወልድ ሣልስ የመንፈስ ቅዱስ ከራብእ እስከ ሳብዕ ያሉት ከምሥጢረ ሥላሴ ውጭ ያሉት 4ቱ ምስጢራት ናቸው። አንድም ግእዝ ካዕብ የአብ ሣልስ ራብእ የወልድ ኃምስ ሳድስ የመንፈስ ቅዱስ ሳብእ የአንድነት ምሳሌ ነው።

ትንሣኤ

ጌታ በተነሳ ጊዜ ዓለመ ሁሉ ብርሃን ሁኗል። ብርሃኑን ከአይሁድ በቀር ያላየው የለም። የእነ አልአዛር ትንሳኤ አስነሽ ይሻል የጌታ ግን በገዛ ሥልጣኑ ነው። ጌታ የተነሳ ከኀቱም መቃብር ነው። ኂላ ግን እንደተነሣ ለማጠየቅ መልአክ ድንጋይቱን አንስቷታል። ወኢደምሰሰ እግዚእ አሠረ ቅንዋት እምድህረ ትንሳኤ ወዘውስተ እገሪሁ።

ስቅለት

ከመቃብረ አዳም ዕጽ በቅሎ ነበር ያንን ቆርጠው እንደመቀጫ ፈልፍለው መስቀሉን ከዚያ ላይ ተክለውታል። ሀተታ ጌታ የተሰቀለባት ቀራንዮን ሕንብርታ ለምድር ይላታል ድማሃ ለምድር ይላታል። **ጲላጦስ፡-** ጌታን ቢያስገርፈውም ለአስተምህሮተ አይሁድ ነው።የገረፍሁት እንደሆነ ራርተው ይተውታል አይሰቅሉትም ብሎ ነው። **500 ቢጽ**፡- ከ500 ከፍ ከ600 ዝቅ የሚሉ በዕለተ ዓርብ ከእግረ መስቀል የተነሡ ሙታን ናቸው። ከእነዚህ እስከ ዕርገት እስከ ጰራቅሊጦስ ያስተማረ አለ። ወዲያው እስከ ትንሳኤ ቆይቶ የሞተ አለ። ጌታን 39 ገርፈው ተሳስተን እያሉ 6666 ጊዜ ገርፈውታል ቦ ዘይቤ 50000። ድርገት ወደ ምእራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምእራብ አድርጎ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው። ወደምስራቅ መመለሱ የትንሳኤ አምሳል። ብረቱን 50 እንደ መርፌ ጥቃቅን አድርገው ከሾህ ጋራ ታተው ለጌታ አክሊል ደፍተውለታል። **ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፡-** ኦ አእዳው እለ ለሐኂሁ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል።

እማሬ

እስመ ዝንቱን የመሰለ ሲመጣ ማመልከት ነው። ንሥዑ ብልዑ ዝ ጎብስት ሲልና ንስዑ ስትዩ ዝ ጽዋዓ ሲል እማሬ አለ።

ቅድስት ማርያም፣ መሶበ ወርቅ

በመሶበ ወርቅ የነበረው መና እስከ ሥጋዌ በደብተራ ኦሪት ነበር። አማናዊ መና ወልደ እግዚአብሔር በማኅጸነ ማርያም ባደረ ጊዜ እንደ ሰም ቀልጦ ጠፍቷል።መሶብ የእመቤታችን ምሳሌ ነው። እመቤታችን ለአንድ ባሕታዊ ከ33ቱ በዓላት ፍልሰታን አስተርእዮን ኪዳነ ምሕረትን ልደትን የበለጠ እወዳቸዋለሁ ከእነዚህ ደግሞ ልደትን የበለጠ እወደዋለሁ አባት እናቴን መባችሁን አንቀበልም ብለዋቸው አዝነው ነበር እኔን ከወለዱ በኂላ መባቸውን ተቀብለዋቸዋል ደስ ብሏቸዋል የእነርሱ ደስታ ደስታየ ነው ብለዋለች። የእመቤታችን ቅድመ አያቶቿ ቴክታ በጥሪቃ ይባላሉ። ከዚያ ሄኤሜንን ወለዱ ሄኤሜን ማለት ረከብኩ ስእለትየ ረከብኩ ተምኔትየ ማለት ነው። ሄኤሜን፣ ዮርዮ፣ ቶና፣ ሲካር፣ ሄርሜላ፣ ሐና፣ እመቤታችን። ሐና እመቤታችን ጸንሳ ሳለ የሞተው አጎቷ ሳምናስን ሽንኩሩን ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ አርፎበት ድኗል።

ሃሌ ሉያ፣ ምስጋና

ሃሌ ሉያ ማት ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ማለት ነው። አንድም ስብሐት

ለእግዚአብሔር ማለት ነው። 14ቱንም ቅዳሴ በዜማ የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው። አንድ ባሕታዊ እመቤታችንን ከምስጋናሽ ሁሉ ማንን ትወጃለሽ ቢላት ልጇ ዳዊትና አቡነ ዘበሰማያትን ቢደግሙለት እንዲወድ እኔም ውዳሴየን ቅዳሴየን ቢደግሙልኝ እወዳለሁ አለች። ሳሙኤል ትውልደ ጌድዮን ዘገበዘ አክሱም ይህን እየደገመ ሲሄድ ክንድ ከስንዝር መጥቆ ይሄድ ነበረ። ለቅዱስ ያሬድ ሕርያቆስን ከብህንሳ ኤፍሬምን ከሶርያ በደመና ጠቅሳ አምጥታለት እየነገሩት በዜማ ደርሶታል። እግዚአብሔር በስራው ሁሉ ምስጉን ነው። ለዳዊት 288 የእለት መዘምራን ነበሩት የእሊህ አለቆቻቸው ቆሬ፣ የማን፣ ኤዶትም፣ አሳፍ ናቸው። ዳዊትን ለአራት ተካፍለው ሲጸልዩት ዛቲ እለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር የሚለው ለአሳፍ ደርሶታል።

ጸሎት

በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለሁሉ መጸለይ ይገባል። ጸልዩ በእንተ ሕይወተ ናቡከደነጾር ወብልጣሶር ወልዱ እንዲል። ከሞተ በኋላ ግን በሃይማት ለመሰለ እንጂ ላልመሰለ መጸለይ አይገባም። ኦ እግዚኦ ሚጥ ልበ ነገሥት ለአሠንዮ ላእሌነ በኩሉ ጊዜ። ጸጉ ሰላመ ለሊቃውንተ ቤተክርስቲያን። የጸሎቱ ሁሉ ፍጻሜ ስብሀት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ነው። በአቡነ ዘበሰማያት አምስት ነገር አለበት፡- ሃይማኖት (ያላዩትን አባት አቡነ ማለት)፣ ተስፋ (ትምጻእ መንግሥትከ ማለት)፣ ፍቅር (አንዱ ለአንዱ ኢታብአነ ብሎ መጸለይ)፣ ትሕትና (ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ከወጣንያን ጋር ጎድግ ለነ አበሳነ ማለት ነው)፣ ጸሎት (ሁለንተናው ጸሎት ነው)።

ዓለምን ስለመጥላት

ኦ አኃውየ ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም። በዓለሙ ያለውን መብል መጠጥ አትውደዱ ኃላፊ ነውና። አንድም ከተማ አትውደዱ በከተማ ያለውን ሹመት ሽልማቱን አትውደዱ ኃላፊ ነው። አንድም ሥጋችሁን አትውደዱ። ከሳ እናወፍረው ጠቆረ እናቅላው ማለትን አትውደዱ ሥጋችሁ መዋቲ ነው ፈቃዱም ኃላፊ ነውና። (መዋቲን ስላከበረው እግዚአብሔር ይመስገንና በመዋቲ ተልእኮ በመዋቲ ክብር በመዋቲ ሹመት በመዋቲ ደመወዝ በመዋቲ ጥሩ አኗኗር በመዋቲ ልጆች በመዋቲ ጉዳይ አትቅና። ከዚያስ ከቅናት ይልቅ ፈጣሪ በሰማይ የሚጠይቅህ ፍቅርን ነውና ሰውን ሁሉ ውደድ እርዳው ራራለት ታገሠው አትማው አትዋሸው አትስደበው አታናደው የመሳሰሉትን ጌታ ያዘዘንን እናድርግ ያላዘዘንን አናድርግ። በዚህ ምድር ምንም የሚያጓጓ ነገር ስለሌለ ሥርዓታትን ሕገጋትን ለመጠበቅ ጣር እንጂ እነርሱን ላለመፈጸም የሚያበቃ ምንም ምድራዊ ምክንያት አይኑርህ። ክብር ኩራት መሞገሥን መውደድ ትችትን መጥላት የሚወድህን ለአንተ ጥሩ አመለካከት ያለውን መውደድ የሚጠላህን የሚንቅህን መጥላት እና የመሳሰሉት እነዚህ መዋቲ ስለሆኑ ተዋቸው። እግዚአብሔር እንዳዘዘው መኖር ነው ታላቅ ነገር ማለት ነው)።

ፍቅረ ንዋይ

ሁለት አኃው በአንድነት ይኖራሉ ይዋደዳሉ። ከእለታት አንድ ቀን ድስት ሙሉ ወርቅ አገኙ።

አንደኛው በሽተኛ ነው። አንደኛው ወንድሜ መ·ቶልኝ ኮሶዬን ጠጥቼ ጠላቴን አውጥቼ ይህን ወርቅ ይገፍ ከተማ ገብቼ ከብሬበት ኑሬ እያለ ይመኝ ጀመር። ያኛውም ብቻውን ይህን ይመኝ ጀመር። መድኃኒቱን ደቁሶ መርዝ ጨምሮ በጠበጠው ያም ሰይፉን ሲስል ቆየ ባለሰይፉ ገድሎ ሲጠጣ እርሱም ሞተ።

ጸጋ

ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ እንደ ሃይማኖቱ ጽናት እንደ አእምሮው ስፋት ነው። እምቅድመ ትጽንን ሕሊናሁ ለብእሲ ኀበ ኄርት ወኀበ እኪት ኢተሀድር ጸጋ መንፈስቅዱስ ላዕሌሁ ወኢትርኅቅ እምኔሁ እንዲል።

ጥበብ

ጥበብ ሥጋዊና ጥበብ መንፈሳዊ ተብሎ ይከፈላል። ጥበብ ሥጋዊ ነቢዩ ሰሎሞን ሀብ መንፈቆ ለዛቲ ብሎ ሕጻኑን ለእናቱ ያስመለሰበት ነው። ጥበብ መንፈሳዊ ቃል ወልድ እጐየ ናሁ ውእቱ መጽአ ብሎ የተናገረው ትንቢት ነው።

ቅዱሳን፣ ሰማእት፣ መምህራን

ሙሴ፡- የቀደመ ስሙ ምልክአም ነው። መልአከ እግዚአብሔር ማለት ነው። **አባ አክሎግ፡-** ራሱን ታማሚ ነው ውሃ ሽግ አድርጎ ማን በሰጠኝ ሲል አንበሳ ሰማው። ከነጋድያን ነጥቆ አምጥቶ ከፊቱ አቀረበለት እግዚአብሔር ካመጣህ ወርደህ ብርቱን አውርደህ ውኃ ሽግ አድርገህ ስጠኝ አለው አድርጎ ሰጠው ከነበረበት ወስደህ ስጥ አለው። **እስጢፋኖስን ቀዳሜ ሰማእት** ይለዋል ከጌታ ቀጥሎ ከሐዋርያት አስቀድሞ መከራ የተቀበለ እርሱ ነውና። **ያእቆብ እጉሁ** ለእግዚእነን እናቱ በሕጻንነቱ መታበት ከአባቱ ቤት አግኝታው ከጌታ ጋራ እያጠባች አሳድገዋለችና እጉሁ አለ። ሐሊበ ድንግልናዊንስ ዕሩቅ ብእሲ መጥባት አይቻለውም ብሎ እንደ እናት ሁና አሳድገዋለችና። ከገድል ጽናት የተነሳ እግሩ እንደ መቀጫ ተድበልብሎ ነበር። ለስብከተ ወንጌል አይፋጠንም ብለው በኢየሩሳሌም ሹመውት ሂደዋል። አንድም የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ እንዲሉ። **ሉቃስ** ማለት መበስር ማለት ነው ብሥራተ መልአክን ይጽፋልና። አንድም ዓቃቤ ሥራይ ማለት ነው ቀድሞ ዓቃቤ ሥራይ ዘሥጋ ነበር ኋላ ግን ዓቃቤ ሥራይ ዘነፍስ ሁኗልና። **ጴጥሮስ** ማለት መሠረት ማለት ነው። መሰረትነቱ ለሃይማኖት ለልጅነት ነው። **ማቴዎስ** ማለት ኅሩይ እመጸብሐን ማለት ነው ግብር ከሚያስገብርበት መርጦታልና። **ታዴዎስ** ማለት ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው ኦሪትን እንደ ዘርእ ወንጌልን እንደ ማዕረር አድርጎ አስተምሯልና አንድም እለቱን ዘርቶ ዕለቱን ለመሥዋእት አድርሷልና። **ማትያን** ማለት ምትክ ማለት ነው። **ጳውሎስ** ማለት ንዋይ ኅሩይ ብርሃን ማለት ነው። ዘሰ አጥረየ ሐዳፈ የአምር ምሳሌ ወስውረ ነገረ። እለሰ አልቦሙ ሐዳፍ ይወድቁ ከመ ቆጽል። በዘመነ ዳኬዎስ የተሰወሩ በዘየዓቢ ቴዎዶስዮስ ጊዜ የወጡ ሰብዓቱ ደቂቅ ሰማእታት ናቸው። ሃይማኖታችንን አንለውጥም ብለው በዋሻ ተቀምጠው የነበሩ ናቸው። ከእነዚያ አንዱ እየወጣ ምግባቸውን እየገዛ ይመለሳል። ኋላ መጣ ሲሉ ሰምተው ዋሻቸውን ዘግተው እንደዘጉ ከዚያው አርፈዋል። እየመጣ

የሚጠይቃቸው አንድ ምእመን ነበረ፡፡ ሊያያቸው ቢሄድ ድምጽ አጣ እኒህ ሰዎች አርፈዋል መሰለኝ ብሎ የገቡበትን ቀን በብረት ሰሌዳ ቀርጾ በመስኮት አግብቶ ተወው፡፡ 362 ዘመን ዳኬዎስ ሙቶ ብዙ ነገሥታት ነግሠው ዘየዐቢ ቴዎዶስዮስ ነገሠ፡፡ በእርሱ ጊዜ አልቦ ትንሳኤ ሙታን የሚሉ መናፍቃን ተነሡ ለእነርሱ መርቻ አድርጎ አንቅቷቸዋል፡፡ ምግባቸውን በተራ በተራ እየወጡ ይገዛሉ፡፡ ከእነርሱ አንዱ ምግባቸውን ሊገዛ ከተማ ወጥቶ ነገሩ ሁሉ ተለውጦ አገኘ፡፡ ስመ ጣዖት ይጠራበት በነበረው ስመ እግዚአብሔር ሲጠራ ጣዖት ቁሞበት ከነበረው መስቀል ቁሞበት አየ፡፡ ይህች ሀገር ኤፌሶን አይደለችምን አለ ናት አሉት ከገበያ ገብቶ ምግቡን ሲገዛ የያዘው ወርቅ የዳኬዎስ ስም የተጻፈበት ነውና የመምለኬ ጣዖት ወርቅ ይዘሀል ብለው ያዙት፡፡ ከየት መጣህ አሉት ሀገሬ ከዚህው ነው አላቸው እስኪ እነማንን ታውቃለህ አሉት፡፡እነ እገሌን እነ እገሌን አላቸው የጠራቸውን ሰዎች ስንኳንስ ሰዎችን ስማቸውን የሚያውቅ ጠፋ፡፡ ከዚያ ዋሻቸው ሲታይ 372 ዘመን ሁኖ ተገኘ፡፡ የእኒህም ስማቸው መክሲሞስ፣ መርዲሞስ፣ ታሙኪሮስ፣ ቴዎዶስዮስ፣ ቀስጠንጢኖስ፣ ዮሐንስ፣ እንጦንዮስ፣ ዲዮናስዮስ ይላል፡፡ **ዮሐንስ** ማለት ፍሥሓ ወሐሴት ማለት ነው፡፡ ፍሥሓ ወሐሴት አለ ቅብዓ ትፍሥሕት መንፈስ ቅዱስን አሠጥቶ ደስ ያሰኛልና፡፡ ርኅራኄ ወሣሕል አለ በጸጋ ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ በከንቱ ዘነሳእክሙ በከንቱ ሀቡ ባለው ጸንቶ ያስተምራልና፡፡ አንድም ውሉደ መንግሥት ወክህነት ማለት ነው፡፡ አንድም ደቂቀ ምሥጢር ማለት ነው፡፡ ነባቤ መለኮት ወልደ ነጎድጓድ ማለት ነው፡፡ ሰማእታት መዋዕያን መሐይምናን ንጹሐን ናቸው፡፡ ፍትወታት እኩያት ኃጣውእን ፈቃደ ሥጋን ድል ነስተው መከራ የተቀበሉ ናቸው፡፡ **ሕርያቆስ** ማለት ኅሩይ ማለት ነው ለሹመት መርጠውታልና፡፡ አንድም ረቂቅ ማለት ነው ምስጢረ ሥላሴን ይናገራልና፡፡ አንድም ፀሐይ ማለት ነው አብ ፀሐይ ወልድ ፀሐይ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ እያለ ይጽፋልና፡፡ አንድም ብርሃን ማለት ነው የምእመናንን ልቡና በትምህርቱ ብሩህ ያደርጋልና፡፡ አንድም ንህብ ማለት ነው ንህብ የማይቀምሰው አበባ የለም እርሱም የማይጠቅሰው ሊቅ የለምና፡፡ **ሙሴ** ማለት እንለ ማይ ማለት ነው፡፡ **አሮን** ማለት ደብር ማለት ነው ደብረ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ **ጌዴዎን** ማለት ጽንዕ ማለት ነው፡፡ **ኤልያስ** ደክሞት ያረፈ በደደሆ እንጨት (ዕፀ ከርሚን) ሥር ነው፡፡ **የቶማስ ዘመርዓስን** አጽቁን እየቆረጡ ለጣዖት አጠኑት፡፡ ደቀመዛሙርቱ በቅርጫት አድርገው በአህያ ጭነውት ሲሄዱ የአህዮችን አንገትም ቆረጡበት፡፡ ጌታ 317 ናቸው ቢሉ 318ኛ ሁኖ 318 ናቸው ቢሉ 319ኛ ሁኖ የጠመመውን ሲያቀናላቸው የጎደለውን ሲሞላላቸው ይውል ነበር፡፡ እደ ቶማስ እስከ እለተ ምጽአት ስትሾም ስትሸር ትኖራለች፡፡ ጌታ ሰውን መውደዱ በሕጉ በሥርዓቱ ቢጸና ነው፡፡ ሰው ጌታን መጥላቱ በሕጉ በሥርዓቱ አለመጽናቱ ነው፡፡ ቅዱሳን የራሳቸው ክብር ከሚገለጥ የወንድማቸው ክብር ቢገለጥ ይወዳሉ፡፡ ቅዱሳን ከሞቱም በኋላ ኃጢአት እንደሚያስተሰርዩ በባስልዮስ ማወቅ እንችላለን፡፡ ነቢያት ወሰማእት ሠናያነ መዊእ፡፡ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእን ድንግል አለው ከዕለታት አንድ ቀን ጌታ ዝናሩን ፈትቶ አኑሮት ሳለ ጌታየ ልታጠቀው አለው፡፡ ታጠቀው አለው ከታጠቀው በኋላ ፍትወት እንስሳዊት ጠፍታለታለችና፡፡ **ዮሐንስ አፈወርቅን**፡- ንጉሱ አርቃድዮስ ኢያእመራ እስከ አመ ወለደት ያለው እንዴት ነው ብሎ ጠየቀው፡፡ ዮሐንስም እንደ ጸነሰች ለማጠየቅ መልኳ እየተለወጠ ይታየው ነበርና ጌታን ከወለደች በኋላ ግን በአንድ ጎብረ መልክእ አወቃት ማለት ነው ብሎ ተረጎመለት፡፡ በመስኮት

ያለች ሥዕለ ማርያም ወርዳ ሦስት ጊዜ ራሱን ዙራ ሠናየ ተናገርከ ዮሐንስ አፈወርቅ ዮሐንስ ልሣነወርቅ ዮሐንስ እንቆጳዝዮን ብላ መልሳ ከቦታዋ ተቀምጣለች።

ሐልዮ

ይ.ካ አልእሉ አልባቢክሙ፡- በልቡናችሁ ሰማያዊ ነገር አስቡ። ይ.ሕ ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ፡- ሰማያዊ ነገር ብናስብ በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አለን።

13ቱ ሕማማተ መስቀል

አክሊለ ሦክ፣ ተኮርኦተ ርእስ፣ ተጸፍዖ መልታሕት፣ ወሪቀ ምራቅ፣ ተቀስፎ ዘባን፣ ተአሥሮ ድኅሪት፣ ኩትፈተ እድ፣ ጸዊረ መስቀል፣ አራቱ ቅንዋት፣ ርግዘተ ገቦ (ይህስ ከሞተ በኋላ ነው ብሎ ሰትየ ሐሞት) ናቸው። አንድም አክሊለ ሦክና ተኮርዖተ ርእስ አንድ ወገን። ተጸፍዖ መልታሕትና ወሪቀ ምራቅ አንድ ወገን፣ ተቀስፎ ዘባን፣ ተአስሮ ድኅሪትና ኩትፈተ እድ፣ 4ቱ ቅንዋት፣ መስቀል፣ ጸዊረ መስቀል፣ ርግዘተ ገቦ፣ ሰትየ ሐሞት፣ ወሪደ መቃብር። **4ቱ ቅንዋት** የሚባሉት ሁለቱ ከግራ ቀኝ እጁ። ሁለቱን እግሩን ደርበው በአንድ ቀኖት ቸንክረውታል። አንድ ከደረቱ ይህስ ኢትስብሩ አጽሞ ለበግዕ ያለው ይፈርሳል ብሎ እግሩን እየራሱ ቸንክረውታል ቢሉ የተመቸ አንድ ነው ቢሉ ስቁረቱን ቆጥሮ ነው።

ሰባቱ ተአምራት፣ ሰባቱ አጽርሓ መስቀል

ሰባቱ ተአምራት የሚባሉት፡- ፀሐይ ጨለሚል፣ ጨረቃ ደም መስሏል፣ ከዋክብት ረግፈዋል፣ ሙታን ተነስተዋል፣ መቃብራት ተከፍተዋል፣ አዕባን ተፈትተዋል፣ መንጦላእተ ምኩራብ ከ2 ከ3 ተቀዲል። ሰባቱ አጽርሓ መስቀል የሚባሉት፡- ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ፣ አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ፣ አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ፣ ጸማዕኩ፣ ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት፣ ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ፣ ተፈጸመ ናቸው።

ምሕረት

በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ። ይህ ሦስት ጊዜ መባሉ የሦስትነት ምሳሌ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው። ዬ ዬ ዬ ወዮ ወዮ ወዮ ማለት ነው። እመቤታችን ለውሻው የእግዚአብሔር ፍጡር ነው ብላ ውሃ ስትሰጠው የእስራኤል ሴቶች አለባበስሽም የስራ ፈት ይመስላል ብለው ሰደቧት።

ጌታን መከተል

ሐዋርያት ተለው አሠሮ። ሐዋርያት በእርሱ አምነው ቤታቸውን ንብረታቸውን ጥለው ተከተሉት። (በዚህ ምድር ትልቁ ቁም ነገር እና ለብዙ ችግሮች መፍትሔ ወንጌልን መስበክ እና ሰው በወንጌል እንዲመራ ማድረግ ነው)።

ትሩፋት

የተበደለው በዳዩን ማረኝ ሲለው ይህ ትሩፋት ነው።

ይቅርታ

እንደበደሉን እንበድል አትበሉ። አንድም በዚህ ቀን ይህን በደሉን ብላችሁ አታስቡ። አዳም ሔዋንን እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ በአንቺ ምክንያት አጣሁ ብሎ ፊት ነሣት ሴቶች ድንጉጦች ናቸውና ሸሽታ ሄዳለች። ሂዶ ሔዋንን አመጣት። እርሷም ከጫማው ወድቃ ማረኝ ብለዋለች። ዮሐንስ አፈወርቅ ከሞተ በኋላ በንግሥቲቱ ደዌ አደረባት ከመቃብሩ እየሄደች በድየሀለሁና ይቅር በለኝ እያለች ትወድቅ ትነሣ ጀመር በኋላ ተፈወሰች።

ምጣኔ ሀብት

ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፡- ሀተታ 12 ወቂት አንድ ልጥር ነው። 12ቱ ልጥር አንድ ምናን ነው። 12ቱ ምናን አንድ መክሊት ነው። አንድ መክሊት 1728 ብር ነው።

ክህነት

ከሊቀጳጳስ ጀምሮ እስከ ቂስ ያሉት በአንብሮተ እድ ይሾማሉ ቅብዓት ያለበት ነው። ዲያቆን በአንብሮተ እድ ይሾማል ቅብዓት የለውም። ከዚያ በታች ያሉት በቃል ይሾማሉ።አ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር።

ታቦት

በአቀራረጽ ከላይ ሥላሴን ዝቅ ብሎ እመቤታችንን አንገቷን አቅንቶ ዝቅ ብሎ ሰማእትም ጻድቅም ቢሆን አንገቱን ወደእመቤታችን አቅንቶ ይቀረጻል። በታቦት ከላይ አልፋ ወዖ ከዚያ የዮሐንስ ስም ሦስተኛ ምስለ ፍቁር ወልዳ ነው። ይህ ታቦቱ ታቦተ ማርያም ታቦተ ኢየሱስ ታቦተ ዮሐንስ ቢሆን ነው።

ስመ እግዚአብሔር

ለሰሎሞን ሐፍራኤል ጭርዋቅ የሚባል ስመ አምላክ የተቀረጸበት ሐቲም ቀለበት ነበረው። ትእምርተ መንግሥቱ ግርማ ሞገሡ እርሱ ነው። ከሴት ሲደርስ አንበሳ መደብ ሲወጣ ከዙፋኑ አኑሮ ነው። በዘመኑ ሳቤላ የምትባል ነቢይ ነበረች። እመቤታችን ሀርም ስድክኤል የሚባል ጎቡዕ ስም ተገልጾላት ትጸልይ ነበረ። ገብርኤል አጋንንቱን አጥፍቷቸዋል።

ገነት

የጻድቃን ነፍሳት በገነት ይኖራሉ። ሀየ ሀለው ጻድቃን በትእግስቶሙ የትእግስታቸውን ዋጋ አግኝተው አሉ። ሀየ ሀለው ነቢያት ምስለ ትንቢቶሙ የትንቢታቸውን ዋጋ አግኝተው ከዚያ አሉ። ሀየ ሀለው አበው ቀደምት።ሀየ ይነብሩ በትፍሥሕት ወበሐሴት። ሀየ ይነብሩ ጻድቃን

በክብር፡፡ አኮ ብነ ዝየ ሀገር አጽዳፍ ወጎጻጉጽ ወመብእስ ዘኢኮነ ርቱዓ አላ ዘበላዕሉ ኀበ ዘቀደሙ በጺሐ ነቢያት ወሐዋርያት፡፡ አኮ ብነ ዝየ አብያት ዘሕኑጽ በኖጻ ዘይነፍሕዎ ነፋሳት ወይገፍእዎ ወኃይዘት አላ ዘበላዕሉ ኢየሩሳሌም አግዓዚት ኀበ ቀደሙ በዊአ ካህናት ንጹሐን፡፡

ቅጣት

የጽርዓውያን ሰይፍ የፋርስ እቶነ እሳት የባቢሎን ግበ አናብስት የአይሁድ ውግረተ አዕባን የሮም ስቅለት ነው፡፡

መቃብር

እስራኤል የሚቀበሩት በየእርስታቸው ነበር፡፡

ምጽአት

ጌታ ይህን ዓለም ለማሳለፍ የሚመጣ እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ነው፡፡ በምጽአት ኢተአክል ኩላ ምድር ዘእንበለ ምክያደ እግር፡፡ ምድር ሁሉ ከአንድ ጫማ የተረፈ መቆሚያ አይገኝም፡፡ አልቦ አሜሃ ሐጺር ወነዊኅ ጸሊም ወቀይሕ አላ አሐዱ አካል፡፡ ሐተታ ወንዱ በአቅመ አዳም በ30 ዓመት ሴቷ በአቅመ ሔዋን በ15 ዓመት ሁነው ይነሣሉ፡፡ አሜሃ ጻድቃን ይትፌስሑ እስመ ለሀው በሕይወቶሙ ወኃጥአን ይበክዩ እስመ አፍቀሩ ሰሐቀ ወሥላቀ፡፡ አሜሀ ይፈትሕ ንጉሥ በኩነኔ ርትዕ ዘአልቦ አድልዎ፡፡ ጌታም ያለቅስላቸዋል፡፡ ከሚያለቅስማ አይምራቸውምን ቢሉ ፈታሂ በርትዕ ስለሆነ ይፈርድባቸዋል መሐሪ ስለሆነ ያለቅስላቸዋል፡፡ አሜሃ ኃጥአን ይበክዩ በእንተ ርእሶሙ ወጻድቃን ይበክዩ በእንተ ዘመዶሙ ወመላእክተ ሰማይ የጎዝኑ በእንተ ፍጥረተ ሰብእ፡፡ አሜሃ ይትፈጸም ኩሉ ዘይነብብ ዐመፃ፡፡ ሐተታ ወንጌል ምላሽ አለ አለ ከዚህ ምላሽ የለም አለ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፡፡ ነገር እንደዚህ ነው ምላሽ የለም ወንጌል ምለሽ አለ ማለቱ የሚያሰኝ ስለሆነ ለሰው በሚያውቀው በሚረዳው ለመናገር ነው፡፡

አምስቱ ከለባት

ዘማዊ፣ ቀታሊ፣ ዘያጣዕ፣ ሠራቂ፣ ሐሳዊ ናቸው፡፡

ፍርድ

አንትሙሰ ሕቱ እንተ አፍአሁ ወአኮ እንተ ውስጥ፡፡ የውስጥ ያይደለ የአፍአውን ኃጢአት መርምሩ ወእንተ ውስጥሰ እግዚአብሔር የአምን ወይፈትን በማህቶተ ዚአሁ፡፡ መቅድመ ናግርሮ ለሥጋነ፡፡

ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያምን ኤፍሬም ደርሶታል፡፡ ኤፍሬም እና ስምዖን ዘዓምድ የያእቆብ ዘንጽቢን ደቀመዝሙር ናቸው፡፡ ያእቆብ ዘንጽቢን ቁጥሩ ከ318ቱ ሊቃውንት ነው፡፡ ለአውግዙተ አርዮስ ሲሄድ አስከትሎት ሂዶ ነበር፡፡ ባስልዮስም ቁጥሩ ከ318ቱ ሊቃውንት ነው፡፡ ባስልዮስ ጥሩ

ልብስ መልበሱ ስለክብረ ወንጌል ነው። ኤፍሬም ለብሐዊ የተባለበት ምክንያት ብርሌ ብርጭቆ እየሰራ የዓመት ልብሱን የእለት ምግቡን እያስቀረ ይመጸውት ነበር። ውዳሴ ዘሠኑይ የሚለው ቃለጸሐፊ ነው። ኤፍሬም የሚጀምር ፈቀደ እግዚእ ብሎ ነው። ሰአሊ ለነ ቅድስትን ማን ተናግሮታል ቢሉ ቅዱስ ኤፍሬም ተናግሮታል። ይህማ እንዳይሆን በግብጻውያን በመጽሐፋቸውም በቃላቸውም አይገኝምሳ ብሎ ቅዱስ ያሬድ ለዜማ መክፈያ ተናግሮታል። አንድም የኂላ ሊቃውንት ተናግሮታል ይላሉ። የብሉዩን ለአብ የሐዲሴን ለወልድ ሰጥቶ አድሎ መናገር ልማድ ነው እንጂ ሁሉም በሁሉ አሉ። ዓቢይ ነጌ ውርዝው ነጌ የሚባሉ አሉ ይህ ዓቢይ ነጌ ወርቹ የጠነከረ ነው አይታጠፍለትም። እረፍት ሲሻ ከገደል ከዛፍ ስር እየተጠጋ ያርፋል። አዳኞች የተጠጋበትን ዛፍ አይተው ከርክረው እንዳይጠረጥር ጭቃ ቀብተው ይሄዳሉ እንደ ልማዱ ሊያርፍ ይመጣል ይጠጋል ይዞት ይወድቃል። ወርቹ የጠነከረ ነውና መነሳት ይሣነዋል ይጮሀል ጩኸቱን ሰምተው ዐበይት ነጌያት ይመጣሉ። እንደነ እርሱ ወርቻቸው የጠነከረ ነውና ማስነሳት ቢሳናቸው አንድ ሁነው ይጮሀሉ። ጩኸታቸውን ሰምቶ ውርዝው ነጌ ይመጣል ወርቹ ያልጠነከረ ነውና ከኩንቢው ገብቶ ያስነሳዋል። ዓቢይ ነጌ የተባለ አዳም። አዳኞች የተባሉ አጋንንት እንደ መጮሁ ንሥሓ መግባት ዐበይት ነጌያት ነቢያት ካህናት ናቸው። ውርዝው ነጌ ጌታን ያመለክታል። ማርያም ማለት ፍጽምት ማለት ነው። አንድም ጸጋ ወሀብት ማለት ነው አንድም መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው። አንድም ልእልት ማለት ነው። መትሕተ ፈጣሪ መልእልተ ፍጡራን ይላታል። አንድም እግዝእተ ብዙኃን ይላታል። ዘውእቱ ዕብንን መምህር ኤስድሮስ ሲተረጉሙት። ወርቅ ብር ብርት በሦስቱ ሰማያት ያሉ መላእክት፣ ጭንና ጭኙ የብረት በአየር ያሉ አጋንንት፣ እግርና እግሩ የብረትና የሸክላ ቅልቅል ምስል ደቂቀ አዳምና ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት። እጅ ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ ድንጋያ ወርዶ አድቆት ተመልሶ ተራራ ሲያህል ማየቱ ሥጋ አምላክ ሁኖ እነዚህን ሁሉ ለመግዛቱ ምሳሌ ነፋስ የሥልጣነ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው ብለው ተርጉመውታል። ሐዋርያት እመቤታችንን እንደምን ጸነስሽው እንደምን ወለድሽው ንገሪን አሏት እንግዲያስ ሳስበው ጭንቅ ጭንቅ ይለኛል እጀን እግሬን ያዙኝ አለቻቸቸው። ወትሮ የማውቀው መልአክ ቀርቶ ወትሮ የማላውቀው መልአክ መጣ። ጊዜው ካፊያ ነበረ ቀኝ አጽፉን ቢባርከው ጎብስተ ሕይወት ሆነ በልቶ አበላኝ። ግራ አጽፉን ቢባርከው ጽዋዓ ሕይወት ሆነ ጠጥቶ አጠጣኝ ብላ ነገር ጀምራላቸው ሳለች ግሩም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ድምጽ አሰማቸው እንደ ቅጠል ረገፉ እርሷ ለበቃችው ምስጢር አልበቃችሁም ሲል ነው። ጌታ የእመቤታችንን ተድላ ሥጋዋን አይወድላትምና በደመና ነጥቆ ከጢባርዮስ ቄሳር ደብቋታል ጢባርዮስ ሊንከባከባት ፈልጎ ነበርና። ጌታን ከለሜዳ አስታጥቆ የሳለው ዮሐንስ ነው። ድንግል ማርያም መጽሐፈ ኢሳይያስን ስትመለከት ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ከሚል አንቀጽ ብትደርስ ከዘመኗ ደርሼ ወጥቼ ወርጄ አገልገፍያት ብላለች እንጂ እኔ ሁኜ አላለችም። ከዘመኗ መድረስ ደስ ያሰኛልና። አማን መነኑ ሰማእት ጣዕማ ለዛ ዓለም ወከዓው ደሞሙ በእንተ እግዚአብሔር ወተአገሡ ሞተ መሪረ በእንተ መንግሥተ ሰማያት። ኃጥዕ መዋቲ ሰው ሁለቱን ቀን ማለትም ቅዳሜንና እሑድን ያከብር ከነበረ ዓርብ በሠርክ ከሲኦል ይወጣል። እሑድ በሰርክ ወደ ሲኦል ይወርዳል። እንዲህ እያለ ሲኖር ጌታ የሚመጣ በዕለተ እሑድ ነውና እንደወጣ ይቀራል። ቅድስት ማርያም

ጥር 21 ቀን እሑድ ቀን አርፋለች። ነሐሴ 14 እሑድ ተነስታለች ከመ ትንሣኤ ወልዳ ያሰኘው ይህ ነው።

አንቀጸ ብርሃን

አምኃ አባዕነ ለከ ዕጣነ አቅረብነ ለከ እምዚአከ ለክቡር ስምከ። ይቄድስዋ መላእክት... ማርያም ፍሥሕት ሰላም ለኪ ማርያም ንጽሕት ሰላም ለኪ።

ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ኢትዮጵያ በሃይማኖት አመሠራረት በመንግሥት አወቃቀር በስነጽሑፍ አቀራረጽና በባሕላዊ ስልጣኔ ረገድ ከቀደምት የእውቅና አቻዎቿ ጋር እውቅና ያላት ሉዓላዊት ሀገር ለመሆኗ ታሪክ ይመሰክርላታል። ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን ገፍተው ለመጣል የተነሳሱ ምንም እንኳ ብዙ ቢሆኑ በኃይል የገፏት አርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስና ሰባልዮስ ናቸው። ዳሩ ግን አዕማዶቿ ሐዋርያትና ተከታዮቻቸቸው በክርስቶስ መሠረትነት ላይ ጸንተው የቆሙ ስለሆነ ስንኳን ገፍተው ሊጥሏት ከስፍራዋም ሊያናውጧት አልቻሉም። ይህን መጽሐፍ ብፁእ ጳውሎስ ተናግሮታል ዮሐንስ አፈወርቅ ተርጉሞታል። **ዮሐንስ አፈወርቅ** የተወለደው በ340 ዓ.ም ነው። እናቱ አትናስያ ርኅርኅት ሴት ነበረችና ልጇን ዮሐንስን በመልካም አስተዳደግ አሳደገችው። አቴና ወርዶ በጥበብ ሥጋዊ ከሁሉ በላይ ሆነ። መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብቶ ብሉይና ሐዲስን ተማረ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አጠና። ከለያልይ በአንዲቱ ሌሊት በትጋት በጸሎት አድሮ ሳለ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ መልአክ ብሩህ ልብስ ለብሶ በፊቱ ቁሞ ታየው። ራእየ ዮሐንስን ከጠፋ በኋላ ንባቡ ከትርጓሜው ተገልጸለት ተናግሯል። ሊቀጳጳስነት በተሾመ ጊዜ የላመ የጣመ ልቅመስ የሞቀ የደመቀ ልልበስ አላለም። ጳጳስም ሁኖ ያረጀ ጠጉሩ የተመለጠ ጸምር ከጉልበቱ በላይ ለብሶ ይኖር ነበር። ምግቡም ጥቂት ገብስ ከነሐሰሩ ነበር። ስለምን ቢሉ ፍትወት እንስሳዊት እንዳታሸንፈው ነው። መምህር ወመገስጽ ዘኢያደሉ ለገጽ ነበር። ክፉ ስራ ሰርተው የሻራቸው ብዙ ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ግንቦት 12 በ400 ዓ.ም አረፈ። ጳውሎስ ለዕብራውያን የሰደደውን ክታብ ዮሐንስ አፈወርቅ 34 አድርጎ ተናግሮታል። ቅዱስ ጳውሎስ አሐደ ጊዜ ኮነ የዐርጎሙ ለሰማእያን ላእለ አሐደ ጊዜ ያወርዶሙ ታሕተ። (ዮሐንስ አፈወርቅ እስከመጨረሻው ለምን እንዴት የት መቼ ምን ማን እያለ ነው የሚያብራራው። ለምን እንዴት የት መቼ... ወዘተ ብሎ ላገኘው መልስ እንደገና በእነዚሁ ቃለመጠይቅ የሰው አእምሮ እስከቻለ ድረስ ያስረዳል ለማስረዳት ምሳሌንም አባባልንም ይጠቀማል። የዘመኑን ፍልስፍናም ያውቃል ስህተቱን ይተቻል። እያንዳንዷን የዓረፍተ ነገር ቃል ይተረጉማል እንጂ አልፎ አልፎ አይደለም። እኛም ቅዱሳት መጻሕፍትን መደዳውን እያስተዋልን ያልገባንን እየጠየቅን መሄድ አለብን)።

ተወስኮ ዘነሣእያን

አይቆምም አይገታም አያቋርጥምና ዘኢይትኄለቅ አለ።

መከራ፣ ተግሳጽ

የክርስቲያን መከራ እንደ ሌላ እንደ ቀማኛ መከራ አይደለም ኋላ መንግሥተ ሰማያትን የምትወርሱበት ነው እንጂ። **ድርሳን 4** ይቤ እግዚእነ ናሁ በጽሐ ከመ ይሰባሕ ወልደ እጓለ እመሕያው። ርኢክኑ ኦ ፍቁር ከመ ሰመዮ ስብሀተ ለሕማማተ መስቀል ዘተወክፈ በእንተ አግብርቲሁ። ሚ መጠነ ፈድፋደ ይደልወከ አንተሂ ትሕምም በእንቲአሁ ርኢክኑ በቁሌቶ ለሕማማተ መስቀል። ብዙኅ ፍሬ ሠናይት ይትወለድ እምነ ሕማም። ነጽርኬ ከመ መከራ ወሕማም ኢኮነ ለምኑናን ወለርጉማን እስመ እግዚአብሔር ይትባረክ ስሙ ሰመየ ሕማማተ ወልዱ ክብረ ወስብሀተ። ወሐመ በእንቲአነ ወሕማማቲሁ ኮነ በእንተ አዳም ወአኮ በእንተ በቁሌተ ርእሱ። ወኢይምሰልከ ብሂሎትየ ተሰብሐ እምነቤሁ ከመ ተወሰከ ስነ ስብሀት አላ ስብሀቲሁ እምነቤሁ ውእቱ። **ድርሳን 5** መከራ ትወስድ ኀበ አእምሮ ወታጠብብ ፈድፋደ። **ድርሳን 6** መከራ ባያመጣብን አይችሉም ብሎ አዝኖልን ነው እንበል። መከራ ቢያመጣብን መከራ ተቀብለው ጸጋ ክብር ያግኙ እንጂ ብሎ ነው እንበል። **ድርሳን 22** በአምጣነ ይትመነደብ ሰብእ ከማሁ ይፈደፍድ ክብሩ። **ድርሳን 26** ጠየቀኑ ኦ እጉ ከመ እኩያን ይትፈሥሑ በዓለም ወጻድቃን ይትመነደቡ። ወአኮ ኩሎሙ ወዘያሌቡሰ እንበይነ ዝንቱ እስመ አብርሃም ኮነ ጻድቀ ወተደለወ ዓዲ በዝየ ወተፈግዐ ወባሕቱ ኮነ ምስለ ኀዘን ወመከራ ተረፈ ግብሩሰ ኮነ በኀዘን ወበገዓር። እስመ ኢይትከሀሎ ለጻድቅ የሀሉ ዘእንበለ ትካዝ ሶበኒ ኮነ ባዕለ። እንከሰኬ ኢተፈግዐ በብዕሉ እንበለ ኀዘን ወትካዝ። ዛሬ እናንተ የምትቀበሉት መከራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው መከራ ነው። ግፍዕሰ ተቀንዮ ለሥጋ። ከመከራ ሥጋ ተድላ ነፍስ ይገኛል። ደመና ለራሱ ዋዕየ ፀሐይን እየተቀበለ ለሌላው ጥላ ይሆናል። **ድርሳን 29** ወእመሰ ኢረከበክሙ ምንዳቤ ውእተ ጊዜ ይደልወክሙ ተሐልዩ ዘንተ ግብረ ከመ ልዑል ኀደገክሙ። በዮሐንስ አፈወርቅ ዘመን በተድላ በደስታ የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች አንድ ቀን አዝና አይታት ምነው አዝነሻል አላት ምን ልበል በተድላ በደስታ እኖራለሁ መከራ አግኝቶኝ አላውቅ እግዚአብሔር በመከራ ባይጎበኘኝ ተለይቶኝ እንደሆነ ብየ ነዋ አለችው። ከዚህ በኋላ ይጸልይላት ጀመር ወዲያው ከብት አለቀባት። ሂዶ ቢጠይቃት ከብት ያልቅብኝ ጀመር ሊታረቀኝ ነው መሰለኝ አለችው ዳግመኛም ውሎ አድሮ ቢጠይቃት ልጆቼ ሞቱብኝ የእርቅ ምልክት አገኘሁ አለችው። ከዚህም በኋላ ባሏ ሞተባት ዳግመኛም ሂዶ ቢጠይቃት ባሌ ሞተብኝ ፈጽሞ እንደታረቀኝ አወቅሁ አለችው። ኢትበል ይትረከብ ጽድቅ እንበለ ትካዝ። እግዚአብሔር ይጌስጽ ዘአፍቀረ ያለው ይህ ነው። ወዝንቱ ግብር ይመስል ከመ አበው። አባት የሌላ ልጅ ሲያጠፋ ዝም ብሎ ልጁ ሲያጠፋ ይጋረፋል። በዚህ አምሳል እግዚአብሐየርም የሚወደውን ይገስጻል። እስመ እግዚአብሔር ከሐሊ አኮ ዘይጌስጾክሙ ለፈጽሞ መፍቅድ እምፈቃዱሁ አላ ፈቂዶ በቁሌተክሙ። ሥላሴ የሚገሥጹን እኛን ለመጥቀም ነው እንጂ ራሳቸውን ለመጥቀም አይደለም። ከእኛ ምንም ሳይሻ ይወደናል እኛን ለመጥቀም ወዶ ይገስጸናል። **ድርሳን 30** እስመ ኩሉ ተግሳጽ በጊዜሁ ወእድሜሁ ኢይከውን ትፍሥሕተ አላ ኀዘን ወትካዝ ውእቱ ወባህቱ ድህረሰ ለእለ ይትኤገሡ ወይሠምሩ ይወልድ ፍሬያተ ጽድቅ ወሰላም። **ድርሳን 6** ነጽርኬ ከመይቤ ገሠጸቶሙ ለዝሉፋን። ኃጢአት አዘውታሮችን ገሥጽዋቸው እንዳለ አስተውል። ወበእንተ ኀዙናንሰ ኢይቤ ገሥጾሙ አላ ይቤ ናዝዝዎሙ። እስመ ለትኩዝ ለእመ ኢናዘዝዎ

ይትዌሰኮ ግዘፈ ልብ ወጽንዓተ ሕሊና። **ድርሳን 30** ሀተታ በመከራ ጊዜ ትሩፋት መስራት ያጸናል። **ድርሳን 33** ጳውሎስ ትማልም ዘይቤ በእንተ ኩሉ መዋእል ዘነለፈ ወዮምኒ በእንተ ዓለም ዘሀለወ ወዘይመጽእኒ ዘአልቦቱ ማኅለቅት። መከራ የክብር መገኛ ነውና እርሱ ጌታ መከራ እንደመቀበሉ እኛም በመከራ እንመስለዋለን።

ገሀነመ እሳት

ገሀነመ እሳት አንድ ጊዜ ከገቡ መውጣት የለም።

ሥጋዌ

ድርሳን 1 ወይቤ ኀየሰ እመላእክት በእንተ ዘወረሰ ስመ ዘየዐቢ እምኔሆሙ። ዘንተ ይቤ በእንተ ትስብእቱ። እስመ ብጹዕ ጳውሎስ አሐደ ጊዜ ኮነ ይትናገር በእንተ ልእልናሁ ወአሐደ ጊዜ በእንተ ርደቱ ወትሕትናሁ። **ድርሳን 2** ወፍካሬ ቃሉሰ ለሐዋርያ ዘይቤ ጸዳለ ስብሐቲሂ ይኤምር ከመ ውእቱ ብርሃን ዘእምብርሃን። ኩሎ ዘተብህለ በእንተ አብ ርቱዕ ያምጽኡ ኀበ ወልድ። ሶበ ይቤ ነበረ በየማነ ዕበይ አያቀ ዕሪናሁ ምስለ አብ በክብር።በሰውነቱ እንጂ በአምላክነቱ ከበረ አይባልም። **ድርሳን 3** ወአኮ ዘፈለሰ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት እስመ ይትኃጥኡ እመካኖሙ ሶበ ይትፈነው። አላ ነሥአ ሥጋ እንዘ ምሉዕ ውስተ ኩለሄ ወኢይትኃጣእ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት። **ድርሳን 4** ክርስቶስ ሞተ ቤዛ ኩሉ። ወአግዐዘነ እምአርዑተ ቅኔ መሪር ለዲያብሎስ ከመገዛት ነጻ አወጣን። **ድርሳን 5** ሶበ ይነግር ጳውሎስ በእንተ ትስብእቱ ያስተኤርዮ ምስለ ሙሴ። ወሶበ ይነግር በእንተ መለኮቱ ይቤ የአቢ ክብሩ እምዘሙሴ። ለሊሁ ኮነ **ሊቀካህናት**። እስመ ሊቀ ካህናት ውእቱ ይደልዎ ይሥረይ ኃጢአተ ሕዝብ። ኢተናገረ በዝንቱ በእንተ ባሕርየ መለኮቱ አላ ባሕቱ በእንተ ትስብእቱ። ወተሠምየ ክርስቶስ መጋቤ ላእለ ሕዝቡ እለ ፈጠሮሙ ወሙሴሰ መገቦሙ ለሕዝብ ዘኢኮኑ ዚአሁ። **ድርሳን 13** እመሰኬ ካህን ውእቱ አሜሃ ይተነብል። ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ቢሆን ያንጊዜ ተንበለ ተባለ። ወዘይቤሂ ጳውሎስ ይተነብል በእንቲአነ ዝኒ እስመ ሊቀካህናት ይተነብል። ርኢክኑ ዘንተ ትሕትና። ወእመቦ ዘይብል ቦቱኒ ፈቃድ ኀበ ስኢል ዘዘልፍ እፎኑ ይበውእ ዝንቱ ምጣኔ ውስተልብ ጻድቃንኒ ይረክቡ ኩሎ ተምኔቶሙ በአሐቲ ስእለት። ወእመኒ እቤለክ በእንተ ትስብእት አኮ ዘእፈልጥ መለኮቶ እምኔሁ። ወሶበ ትሰምዖ እንዘ ይብል ሊቀካህናት ኢይምሰልክ ከመ ዘልፈ ይትከሀን አላ ምእረ ሦአ ርእሶ ወእምዝ ነበረ።ወከመ ኢያምስልዎ ወትረ ዘይቀውም ወይትለአክ። **ድርሳን 17** እስመ ለሊሁ ምሥዋዕ ወለሊሁ ካህን ወለሊሁ ተሠዋኢ። እመቦ ዘይብል ለመኑ ውእቱ ዘአብአ መሥዋእተ ንብሎ ለአቡሁ ውእቱ።

ጥብዓት፣ አለመፍራት

ድርሳን 2 ይደልወነ ኦ አኃው ናጥሪ በኩሉ ጊዜ ልበ ጥቡዐ። በጊዜው ሁሉ አማኒ ትጉህ ጨካኝ ልቡናን ገንዘብ ማድረግ ይገባናል። **ድርሳን 4** ኢትፍርሐዎ ለዘተስእረ ሥልጣኑ ሰይጣን ወበጠለ ኃይሉ። ወተአተተ ዕበዩ። ጻድቃንን ምንም አያስፈራቸውም።

ሃይማኖት፣ እግዚአብሔር፣ ተስፋ

ድርሳን 2 ርቱዕ ለነ ንትወከፍ ኩሎ ዘተብህለ በአሚን ወበየውሃት እስመ ጎሊና ልብ ኢይትከሀሎ ይጠይቅ ምንተኒ እምኔሁ። ነአምር ከመ ውእቱ ምሉዕ ውስተ ኩሉ መካን። ወዘከመሰኬ እፎ ውእቱ ኢንክል አእምሮ። ንቤ ህልው ውስተ ኩሉ መካን ወባሕቱ ኢንክል ረኪቦቶ። ወዓዲ ንቤ ወለደ ወልደ እምአካለ ዚአሁ ወኢነአምር ዘከመ እፎ ውእቱ። ወኢንክል ነጊረ ምሳሌ በዘይደሉ። ኢትጎሥሥ ዘኢይትከሀለከ። **ድርሳን 3** እግዚአብሔር ልዑል የአምር ጎሊና ሰብእ እምቅድመ ኩነታ። **ድርሳን 7** ሃይማኖትሰ ታድጎን ፍጹመ ወትባልህ ብዙኅ ወዘእንበሌሃሰ አልቦ ዘይክል ድኂነ ወባሕቱ ኢትበቁዕ ባሕቲታ አላ ትፈቅድ ላቲ ረድኤተ ዘውእቱ ፍኖተ ርትዕ ወገቢረ ሰናይ። **ድርሳን 9** አሚንሰ መሰረት ውእቱ ወካልዓኒሃ ሕንጻ ወንድቅ እሙንቱ። **ድርሳን 19** ሐጺበ ጎሊና ወአንጽሖቱ እምነበ እግዚአብሔር ወቀሪብሰ በሃይማኖት ፍጽምት እምነቤነ ውእቱ። **ድርሳን 21** ተሰፍዎቱ ለዘኢያስተርኢ እምጽንዓ አሚን ውእቱ። ወለዘሰ ያስተርኢ አልቦ ዘይክል የሐስዎ። ምሳሌ ዝንቱ ናሁ ትንሳኤ ምውታን እስከ ዓዲሁ ኢመጽአ። ወባሕቱ በሃይማኖት ወበጽንዓ ተስፋ ንሬእዮ ከመ ዘሀለወ። ሕገ ሃይማኖት ያሴፉ ዘኢያስተርኢ። **ድርሳን 22** ወጠቢባንሰ ፈላስፋት ይቤሉ ኩሉ ዘያስተርኢ ዘተፈጥረ ኮነ እምግብር ዘያስተርኢ እስመ ኢተቶስሐ ልቦሙ በሃይማኖት ወኢበርሁ በብርሃነ ዚአሃ አላ ተአመኑ በጉሥዓተ ልቦሙ። ልባቸው ባፈላው ባነቃው ባስገኘው ነገር ያምናሉ እንጂ። ወለግቡራንሰ ቦሙ ጥንት። አቤልሰ አብአ መሥዋእተ በጽድቅ ናሁ አቤል ረከበ ምግባረ ትሩፋት ዘእንበለ ይርአይ መነሂ ዘይትሜሰል ቦቱ። እመሰ ከመዝ ውእቱ ተአውቀኬ ከመ እምነበ ነፍሱ አስረጸ ገቢረ ሰናይ። ናሁ አቤል ኮነ ያከብሮ ለእግዚአብሔር ወኢረድኦ ወኢያንገፎ እምእደ እጉሁ። እመሰ ትፈቅዱ አስበ ፍዳ በዝየ ኢይረትዕ ተአምኖትክሙ። **ድርሳን 23** ጥዩቅ ውእቱ ከመ አሚን ይወልድ ጽድቀ። **ድርሳን 25** ወእመቦ ዘይቤ ለምንት አመከሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም ንብል ከመ ያርእዮሙ ለሰብእ አሚኖቶ ወጥብዓተ ልቡ።

ሥርዓት

ኢትትአደው እምወሰን መምህራን መጻሕፍት ከወሰኑልህ ሥርዓት አትለፍ።

መላእክት

ድርሳን 3 ይትፌነው መላእክት ውስተ ኩሉ መካን በእንቲአነ ወይትለአኩ ለአድኅኖትነ። መላእክት ሰውን ስለሚወዱ ሰውን ለማገልገል ይላካሉ።

ኦሪትና ወንጌል

ድርሳን 3 ወንጌልም ሐዲስም ኦሪትም ብሉይም ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው። ወባሕቱ ኢኮነ ዕሩያነ በክብር እስመ ሐዳስ አብለየታ ለቀዳሚት። ወንጌልሰ አኮ ከመ ሕገ ኦሪት ዘታድጎን እም ፀብእ ወቀትል ምድራዊ ወታወርስ ርስተ ሥጋዊተ። **ድርሳን 8** አልቦ ውስተ ሐዲስ ሕግ ምንተኒ ሥርዓተ ሥጋ። ወኢትእዛዘ ኦሪት ዘይትአቀብ በከርሠ ታቦት። **ድርሳን 13** ወእመ ትቤለኒ ለምንትኬ ተብህለ ኦሪት ሕገ ሥጋ ዕብለከ በእንተ ዘይቤ ተገዘር ወቅባዕ ሥጋከ ወይኩን

ንጹሓ አልባሲከ ወተሠርገው ወሚሲ ሥጋከ ወአሥምሮ። ኦሪት ማዳን ሥርየት ማሰጠት ስላልተቻላት ተናቀች። ኢተክህላ ኦሪት ታብጽሕ ኀበ ሥርዓተ ነፍስ። ወበእንተዝ ተስእረት ውኀለፈት። **ድርሳን 14** ናሁ ተአውቀ ከመ ኢይቤ ጳውሎስ ኦሪትሰ እኪት ይእቲ ወባሕቱ ኢኮነት ፍጽምተ። ከኦሪት ያሳለፈው አለ ምሳሌ መሥዋእቱን። ያጸናውም አለ ምሳሌ አሠርቱ ቃላትን።

ቸል ቸል ማለት፣ ተአቅቦ

ድርሳን 3 ግብረ ድቀት ይትወለድ ፍጡነ እምኀበ ተሀይዮት። ወዓሊወ ትእዛዝ ቅሩብ ውእቱ ለሙስና። አላዋቂዎች የሺ ሞት ሰርግ ነው ይላሉ። **ድርሳን 7** መፍትው ለነ ንትአቀብ ፈድፋደ እስከ ንበጽሕ እስከ ሉዓሌ ሰማይ።

ተአምር

ድርሳን 3 ወእመቦ ዘይቤ መሰርያንሂ ይገብሩ ተአምራተ ንብሎ መሰርያንሰ ኢይትከሀሎሙ ይግበሩ ተአምራተ በጽድቅ አላ ይገብሩ ምትሐተ ወአርአያ ወጽላሎተ። አማናዊ ተአምራት ማድረግ አይቻላቸውም።

ጸጋ

መንፈስ ቅዱስ ይሁብ ጸጋሁ ለዘፈቀደ በዘይበቁየ ለርእሱ። ቦ እለ ኢይትወሀቦሙ ሀብተጸጋ ወገቢረ ኃይል በእንተ ሐረቶሙ እኪት ወሀኬቶሙ ወቦ እለ ኢይትወሀቦሙ እንዘ ሀለው በፍኖተ ጽድቅ። ወእመ ትብለኒ **በእንተ ምንት** ዕብለከ አነሂ ከመ ኢይትአበዩ ወኢይትመክሑ ከመ ኢይምጽዖሙ ሐኬት። ጸጋሰ ኢትትወሀብ ዘእንበለ ለትሐኑታን ወፈድፋደሰ ለምኑናን ወለየውሃን እለ በንጽሕ ሀለው። እስመ የዋህ ወትሑተ ልብ ዚይትሜካህ በሀብተ ጸጋ ወይብል ተውህበ ሊተ በኢድልወትየ ይፈደፍድ ብዕለ ጸጋሁ። ወዘሰ ይትሜካሕ በገድሉ ወይመስሎ ከመ በድልወቱ ተውህበ ሎቱ ይወድቅ ውስተ ትምክህት ወትዕቢተ ልብ።

ሞት

ድርሳን 4 እግዚአብሔር ሞት እንዳለ ተናግሯል። ወነብዓ እለተ ፍጻሜነ ከመ ንጽናሕ እንዘ ንብል ማእዜ እመውት ዮምኑ አው ጌሠመ ወእምድህረ ዓመትኑ አው እምድህረ ክልኤ ወዘንተ ገብረ በእንቲአነ ከመ ኢንህድግ ተጸምዶ ውስተ ምግባረ ትሩፋት ወከመ ኢንትመየጥ ውስተ ዕበድ። **ድርሳን 17** ወእመሰ የሐዩ ሰብእ ሕይወተ ዘለዓለም እምድህረ መዊት ኢኮነኬ ዘሞተ አላ አእረፈ ወኖመ።

ስብከት፣ መምህር

ድርሳን 4 አኮ ዘእፈቅድ ትዕቀቡ ቃልየ ቃለ ምህሮ ኪያየ ከመ ትገብክሩ አላ ከመ ይኩን በቁኤተ ዘነፍስክሙ ወገዘ ውእቱ ፍጻሜ ጻሕቅየ ዘበእንቲአሁ እትጋደል። **ድርሳን 6** ለእስራኤልሰ ኢበቀየሙ ቃል ዘሰምኡ እስመ እሙንቱ ሰምኡ በከመ ንሕነ ሰማእነ። ወባሕቱ ኢበቀየሙ

ሰሚአ ቃል እስመ እልክቱ ሰምኡ ወኢረከቡ በቁኤተ በእንተ ዘኢአምኑ፡፡ ወካሌብሰ ወኢያሱ ወልደ ነዌ ሶበ ኢጎብሩ ምስለ አላውያን ድኅኑ እመቅሰፍት ዘመጽአ እስመ ኢጎብሩ ምስሌሆሙ፡፡ አላ ተፈልጡ እምኔሆሙ ዘእንበለ ተሐውኮ፡፡ **ድርሳን 9** ለእመ አብዛኅነ ሰሚዓ ቃለ እግዚአብሔር ይፈደፍድ ውስቴትነ ፈቂደ ውእቱ፡፡ ዘይመጽእ ኀበ ትምህርተ መጽሐፍ ይደልዎ ከመ ይስማእ ቅድመ ፍካሬ ኖህያት፡፡ **ድርሳን 33** ኢትሑሩ መንገለ ትምህርት ነኪር፡፡ ወብሂለ ነኪርኒ ካልእ እምዘሰማእክሙ እምኔነ ወአልቦቱ ጽንዕ፡፡ **ድርሳን 34** እስመ ተኃጥኦ ሊቅሰ ግብር እኩይ ውእቱ፡፡ ወሕዝብሰ እመ ኢተጋነየ ለትእዛዘ ሊቁ ኮነ ከመ ዘአልቦቱ ሊቅ፡፡ወሐመርኒ እንተ አልባቲ ሐዳፊ ትሠጠም፡፡ የመምህር ኃጥዕነቱ የሃይማኖት ሳይሆን የምግባር ከሆነ ልንታዘዘው ይገባል፡፡ ጌታ ስለ ፈሪሳውያን ኩሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ ወዘከመ ምግባሮሙሰ ኢትግበሩ እንዲል፡፡ ወኖሎትኒ ዓዲ ይትአዘዙ ለመርዔቶሙ በከመ ይደሉ ተአዝዞ ለመርኤት፡፡ ለኖሎትኒ ይደልዎሙ ይኩኑ ንቁሐነ ወትጉሐነ፡፡ ለሊቅሰ ሶበ መነንዎ ወገደፍዎ ኢመፍትው ሎቱ ይትበቀል፡፡ባሕቱ ይብኪ ወይግዐር እስመ አቃቤ ሥራይኒ ለእመ ጸአሎ ድውይ ኢየኀዝኖ ወኢይትቤቀሎ፡፡ ያዝንለታል ያለቅስለታል እንጂ፡፡ የመምሕራን የበላያቸው እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ ሲያዝን ከበላዩ ወዳለ ወደ እግዚአብሔር ያመለክታል፡፡መምህራን ለእግዚአብሔር ያመለክታሉ እንጂ አይበቀሉም አይቀጡም፡፡ መምህር ባያስተምር አፍኃመ ገሀነምን በራሱ ላይ ይሰበስባል፡፡ ሹመትን ከመሻት ልንሸሽ ይገባናል፡፡ በግድ ተሸሙ ቢሉን ልንሸሽ አይገባም፡፡ በእኒህ አድሮ የመረጠንን እግዚአብሔርን አላዋቂ ማድረግ ነውና አንድም ትእቢት ነውና፡፡

ፍጥረት

ድርሳን 4 ፍጥረተ ዓለም ይኤምር ኀበ አፍቅሮቱ ሰብአ፡፡

ሰይጣን

ሰይጣን ነፍስን ከፍቅረ ንዋይ ተለይታ ያያት እንደሆነ ድል አይነሳትም፡፡ እስመ አልባቲ ንዋይ ዘየኃጉላ ወኢክብር ወኢብሔር ወኢዘመድ ዘይፈልጣ እምኔሆሙ፡፡ እመ ወረወ ብእሲ ርእሶ ውስተ ኃጉል በከንቱ አይብል ያድኅነኒ እግዚአብሔር ምግባር ዘሰይጣን ውእቱ፡፡

ትርጓሜ

ዮሐንስ አፈወርቅ ልማድን፣ ወግን፣ ምርምርን፣ እይታን፣ ታሪክን ለማስተማርያነት እንደተጠቀመው አስተውል፡፡ በተጨማሪም ለምሳሌ ይህን ዕብራውያንን ሲተረጉም ከሌሎች ከብሉይ ከሐዲስ ጋር አዋሕዶ ነው፡፡ ኃይለ ቃሉን ከኃይለ ቃል አዋሕዶ ነው የተረጎመው፡፡ ሌላው ተቃርኖንም ተጠቅሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ እንዲህ ይሆንባችኋል ይህ ደግሞ ከሰው ልማድ ውጭና ከቅዱሳት ትምህርት ውጭ ነው እያለ በማስረጃ እያስደገፈ ይናገራል፡፡

ምእመን፣ ቤተ ክርስቲያን

ድርሳን 5 እስመ ምእመን ብሂል ሰናየ ሕሊና፡፡ **ድርሳን 6** ለምእመናን እግዚአብሔር

ያደረገላቸውን በጎ በጎ ነገር ማሰብ በተገባቸው ነበር። ከሠራዊተ አጋንንት እንዳዳናቸው ለሰይጣን ለኃጢአት ከመገዛት ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ እንዳዳናቸው ማሰብ ይገባቸዋል። አጋንንትንም ድል እንዲነሡ ማድረጉን ማሰብ በተገባቸው ነበር። ሥጋውን ደሙን እንደሰጣቸው ማሰብ በተገባቸው ነበር። እስራኤላውያን ግን ያን ሁሉ አድርጎላቸው እግዚአብሔርን አሳዘኑት። እስመ ቤተክርስቲያንሰ ሰማያዊት ይእቲ። **ድርሳን 22** ኢይትከሀሎ ለሰብእ ይኩን ተአማኔ ለእመ ኢያግነሠ ርእሶ እምግእዘ ልማድ። **ድርሳን 32** ማኅበረ በኵር ዘይቤ መሐይምናን እሙንቱ።

ኃጢአት፣ ክሕደት

ድርሳን 6 ክሒድ ይወልድ ጽንዓተ ልብ። ክህደት አይምረኝም ማለትን ያመጣል። አይምረኝም የምትል ነፍስም ቃለ እግዚአብሔር ሰምታ አትመለስም አትደነግጥም። ኃጢአት ታበጽሕ ኀበ ክህደት ወክህደትኒ ትወልድ ሐረተ እኩየ። ቁጥዓ ወመዓት ይወልዱ ክሂደ። **ድርሳን 30** እስመ ኃጢአትሰ ጥዕምት ወድህረ ትመርር። ወጽድቅኒ ታቴክዝ ቅድመ ወድህረ ትወልድ ጣዕመ ወፍሥሓ ወክብረ። ኢይትወለድ እምኃጢአት ትፍሥሕት። በኃጢአት ተድላ ደስታ ከሚያደርጉበት በጽድቅ ተድላ ደስታ የሚያደርጉበት ዘመን ይበዛል። በኃጢአት ተድላ ደስታ የሚያደርጉበት ዘመን ጥቂት ነው። የሚያዝኑበት ዘመን ብዙ ነው በጽድቅ የሚያዝኑበት ዘመን ጥቂት ነው ተድላ ደስታ የሚያደርጉበት ዘመን ግን ብዙ ነው። (የሐዘንና ደስታን ስሜት ወይም ጣዕም በዚህ ምድር ያሳወቀን የወደፊቱን የገሀነምንና የመንግስተ ሰማያትን በጥቂቱ እንድንረዳው ስለሆነ በዚህ ምድር ደስታና ሐዘን መኖሩ መልካም ነው። የኋላውን እንድንረዳበት እንድናስተውልበት ይጠቅማልና)

መመርመር፣ ንሥሓ

ድርሳን 6 ሕቱ ርእሰክሙ ኩሎ እለተ። ወለእመቦ ብእሲ ኃጥእ ኢይቅብጽ ተስፋሁ እንዘ ሕያው ውእቱ። መጠነ ሀሎ እለት ይነሥሕ ወይትመየጥ። **ድርሳን 8** ጉርኤሰ ይፈልጥ ጣዕመ እክል። ወነፍስኒ ትፈልጥ ብሂለ ቃል። ልቡናም የነገርን ጣዕም ለይቶ ያውቃል። መሥሐቲ ሰይጣን እንዲሰለጥንብህ አትፍቀድለት። **ድርሳን 20** ክርስቶስ ይፈቅድ ያክብርከ። ወአንተሰ ትከይዶ ለክርስቶስ በስካርከ። ናሁ ረሰየከ ወልደ ወአንተሰ ትፈቅድ ከዊነ ገብር ለኃጢአት። ውእቱሰ መጽአ ይረሲከ ማኅደሮ ወአንተሰ ታስተጋብእ ኀበ ርእስከ ኅሊና እኩይ። እገሌ በእንደዚህ ያለ ጎዳና ሂዶ አንበሳ ሰበረው ወንበዴ ተጣላው ብሎ በዚያ ጎዳና ከመሄድ እንዲከለከል እንዲሁም ሁሉ እገሌ እንደዚህ ያለ ኃጢአት ቢሰራ ተጎዳ ብሎ ሰው ኃጢአት ከመስራት ይከልከል።

ፍርድ

ድርሳን 6 ወኩሉ ዘንገብር በዝየ አኮ ዘንትፈድዮ ይእዜ በእንቲአሁ። **ድርሳን 22** ናሁ አቤል ኮነ ያክብሮ ለእግዚአብሔር ወኢረድኦ ወኢያንገፎ እምእደ እኁሁ። እመሰ ትፈቅዱ አስበ ፍዳ በዝየ

ኢይረትዕ ተአምኖትክሙ። **ድርሳን 34** ሀተታ ኢትኮንኑ ከመኢትትኮነኑ ያለው ለምግባር ነው እንጂ ለሃይማኖት አይደለም። የሃይማኖት ችግር ካለበት ንቀፉት።

መንግሥተ ሰማያት

ድርሳን 7 ይኩን ሕሊናነ ወተስፋነ ህየ። **ድርሳን 23** ኢጸገወነ እግዚአብሔር በዝየ እረፍተ ፍጹመ አላ ጎዳጠ። የዚህን ዓለም ክብር ስትፈልግ በዚያችኛዋ ዓለም ያለው ክብር እንዳያመልጥህ። **ድርሳን 24** ወበከመ ጻድቃን ኮኑ ነግዳነ ወምውታነ እምዓለም ከማሁ ንሕነኒ ሞትነ ወነግዳነ ኮነ እመንግስተ ሰማያት። እሙንቱሰ ሐይው እንዘ የሐሥሡ ኪያሃ ወንሕነኒ ሐየውነ እንዘ ነሐሥሦ ለዝንቱ ዓለም። ተብህለ በእንቲአሆሙ ከመ ዔሉ በሐሜለት ወበዘብድወ ጠሊ እንዘ ይጼነሱ ወይትመነደቡ። ይቤ ዳዊት ፈላሲ አነ ውስተ ምድር። ይህ ስለ ምድረ ፍልስጥኤም እንዳልሆነ ለመንግሥተ ሰማያት ይጓጉ እንደነበረ ያስረዳል። ከመ ኩሉ አበውየ ብሎ አባቶቹ እነ አብርሃም ዕረፍት ያሏት መንግሥተ ሰማያት እንደሆነች ፈላሲ የሆኑት ደግሞ ከምድረ ግብጽ ሳይሆን አጠቃላይ ከምድር እንደሆነ ያስረዳል። ከነአንን እረፍት እንዳንላት ከነአን ገብተው ብዙ ጊዜ ተማርከዋል ብዙ መከራም አግኝቷቸዋል ስለዚህ አማናዊት እረፍት አባቶቻችን እነ አብርሃምም ተስፋ ያደረጓት ፍልስጥኤምን ሳይሆን መንግሥተ ሰማያትን እንደሆነ ያስረዳል። ዮሴፍና ያዕቆብ ከግብጽ አጽማችንን ውሰዱት ያሉት መቃብር መርጠው ነውን ብለን ብንጠይቅ አይደለም ነፍሳት ከሲኦል መውጣታቸውን ለማስረዳት ነው እንጂ ጻድቃን መቃብር ቢመርጡ ኑሮማ ሙሴ በምድረ በዳ። ዳንኤል በባቢሎን ኤርምያስ በእስክንድርያ ባልቀረ ነበር። **ድርሳን 33** ወአልብነ በዝየ ሀገር ጽንእት ዘትሄሉ ወትነብር አላ ባሕቱ ንኅሥሥ ሀገረ እንተ ሀለዋ ትምጻእ ከመ ናእርግ መሥዋእተ ስብሐት።

ትእግስት፣ መልካም ስራ

ድርሳን 7 ወእመቦ ዘየሐውር በፍኖተ ጽድቅ ይትዐገሥ እስከ ፍጻሜ ከመኢይደቅ። እስመ ብዙኀን እለ ወጠኑ ፍኖተ ጽድቅ። ወሶበ ስእኑ ላእለ ንስቲት ትእግስት ወወስኮ ጎዳጥ ዲበ ብዙኅ አኅጎሉ ኩሎ። **ድርሳን 10** አኮ ኀዲገ ኃጢአት ባሕቲቱ ዘይበቁዕ። አላ ይትፈቀድ ሎቱ ፈውስ ለመካነ ቁስል። አልቦ ዘይትመዘገን ከመ ምግባረ ትሩፋት። ኃጢአትን መጀመሪያ ላለመስራት መታገል ነው እንጂ ከሰራናት በኋላ ንሥሓ ብንገባባትም ይተርፍ ቁስላ ቁስሏ ይቀራል። **ድርሳን 10** ይደልወነ ከመ ንትአገሥ በአንኖ መንፈስ እንዘ ንጸውር ኩሎ ዘይበጽሐነ። እስመ ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ አሚን። **ድርሳን 21** እስመ ለዘወጠነ ገቢረ ይደልዎ ያፈድፍድ በበንስቲት በኩሉ መዋእሊሁ። ትእግሥተ ኢትግድፉ እስከ ትበጽሑ ኀበ ፍጻሜ ወትረክቡ ተስፋክሙ ወትረክቡ አክሊለ። **ድርሳን 22** አቤል ተገፍአ እምኀበ እኁሁ ወቀንአ ላዕሌሁ በእንተ ዘአምነ በእግዚአብሔር። ወከማሁ አንትሙኒ ይቀንኡ ላዕሌክሙ። በኖኅ ሰብአ ትካት ሲያፈዙበት ይህ ስራቸው አላሳዘነውም። ዮሴፍ በግብጽ ስደተኛ ሁኖ ሲኖር አላዘነም። **ድርሳን 28** ይቤ ወንሩጽ በትእግስት ወተጋድሎ ኀበ ዘጽኑሕ ለነ ተስፋነ ወኢይቤ ንትጋፋእ ወንትቃተል። እንደበደሉን እንበድል እንደተጣሉን እንጣላ አላለም። ወመነና ለኃፍረት እግዚእነ። ጌታችን ከአይሁድ ብዙ ስድብን እየተሰደበ ሲሰድቡት እየሰማ ኀብስት አበርክቶ በማብላት ሙት በማንሳት በኅ በኅ ነገር ያደርግላቸው ነበር። ወውእቱ ይመርሖሙ ኀበ ፍኖተ

ርትዕ። ይቤልዎ ጋኔን ቦቱ እንዘ ለሊሁ ይፈውስ አብዳኒሆሙ። ናግርር ርእሰነ በኩሉ ግብር በብዙኅ ትእግስት። **ድርሳን 30** አልቦ ምንትኒ ዘየሐምሞ ለሰይጣን ከመ ትእግስትነ። ኢንትቃወም በቃል ወበምግባር ወዘንቱ ግብር ይዌስክነ ጥበበ ወአስበ።

ረድኤተ እግዚአብሔር

ድርሳን 10 አእዳውሰ እለ የሐርሳ አኮ ዘይኤዝዛሃ ለምድር ታብቁል ወታፍሪ ወበእንተዝ ይቤ ትነሥእ በረከተ እም ኀበ እግዚአብሔር። እንድታብብ እንድታፈራ የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው። መምህራን ያልተመሰለውን መስለው ያልተተረጎመውን ተርጉመው ያስተምራሉ እንጂ ትምህርቱን እንዲያጸኑ ምሥጢሩን እንዲረዱ የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው። **ድርሳን 25** ያላሰብከው የማታውቀው መከራ ሊመጣብህ ይችላል። እግዚአብሔርሰ የአምር ኩሎ እምቅድመ ይኩን።

መልከ ጼዴቅ፣ ክርስቶስ

ድርሳን 12 ወእመ ትቤ እፎኑ ኮነ መልከ ጼዴቅ ዘእንበለ አብ ወእም ወአልቦ ጥንተ መዋእል ወማኅለቅተ ሕይወት እብለከ አነሂ ዘንተ ይቤ በእንተ ዘኢተጽሕፈ በመጻሕፍት። ለመልከጼዴቅሰ ኢይትአወቅ ጥንተ መዋእሊሁ ወማኅለቅተ ሕይወቱ በእንተ ዘኢተጽሕፈ ወለክርስቶስሰ በእንተ ዘአልቦ ዘይክል ረኪበ ህላዌሁ። ወዝ ውእቱ ተማስሎቶሙ። **ወሕገ ምሳሌሰ** ይቱሐት እምነ ራዕይ እሙን።

ቃለ እግዚአብሔር

ድርሳን 14 ሀተታ አሠርቱ ቃላትን በልብሳቸው ጽፈው ከአባር ከቸነፈር ይድኑበት ነበር።

ቁርባን

ሥጋው ደሙ ነፍስን የሚያነጻት ብቻ አይደለም። ቋንቋ እንድትናገር ምሥጢር እንድትተረጉም ያደርጋታል እንጂ። **ድርሳን 32** ውእቱሰ ሶበ ቦአ ውስተ ልበ ንጹሕ ያነሥኦ ወያነቅሆ ለተናግሮ።

መስቀል

ድርሳን 19 ሀተታ ጌታ በስድስት ክንድ መስቀል ነው የተሰቀለ።

ማኅበር፣ አንድነት

ድርሳን 19 ንትቀሐው ምስለ ቢጽነ በተፋቅሮ ወበምግባረ ሠናይ ወኢንኅድግ ተጋብኦ በበይናቲነ። እስመ ተጋብኦ ያፈደፍዶ ለፍቅር ወለአሥምሮ እግዚአብሔር። ፍቅር ይትወለድ እምተጋብኦ። ምግባር ሠናይት ይትወለድ እምፍቅር። እኅው ዘይትራድኦ ለእኅው ከመ ሀገር ዘጽኑዕ ጥቅማ።

ሥላቅ

ድርሳን 21 እስመ ሥላቅ ያመነስዋ ለነፍስ ወያጸልሞ ለኅሊና። መዘበት ነፍስን ያሳዝናታል አእምሮን ይለውጣል።

ውዳሴ ከንቱ

ድርሳን 21 እስመ ዘመደ እንለ እመሕያው ኮነ ያፈቅር ውዳሴ ከንቶ።

ጸሊአ ንዋይ፣ መንኖ ዓለም

እመሰ አእመርክሙ ከመብክሙ ንዋይ በሰማያት ዘይኄይስ ኢትኅሥሡ ምንተኒ ዘበዝየ። ዓለማዊ የሚባል የዚህን ዓለም ግብር የሚወድ ነው። **ድርሳን 31** ኤሳውሰ ኢለበወ መጠነ ብኩርናሁ ግሙራ ወአስተሐመመ ለዕረፍት ዘመናዊት ወኃላፊት። ፈጥና ለምታልፍ በዘመን በተወሰነች ለዚህች ዓለም ክብር ተጋ እንጂ። አኮ መፍትው ለነ ንትገበራ ለዓለም ባሕቲታ አላ ናእኩቶ ለእግዚአብሔር አኮቴተ ፍጽምተ በእንተ ዓለምኒ ዘትመጽእ። **ድርሳን 33** ወንመንን ኩሎ ግብረ ሰብአዊ አምጣነ ብነ እግዚአብሔር ክቡር። ወእመሰ ኮነ ለሊሁ ሎቱ ስብሐት ጸረ ወኩሉ ፍጥረት ኮኑነ አእርክተ አልብነ ረባሕ ወበቁኤት። ወከመዝ ዓዲ ሶበ አፍቀረነ ለሊሁ ኢይረክበነ እኩይ ግሙራ። ወሶበኒ ተጻብኡነ ኩሎሙ አልቦ ዘይክለነ። ሹመትን ከመሻት ልንሸሽ ይገባናል። በግድ ተሸሙ ቢሉን ልንሸሽ አይገባም። በእኒህ አድሮ የመረጠንን እግዚአብሔርን አላዋቂ ማድረግ ነውና አንድም ትእቢት ነውና።

ማሸነፍ

ድርሳን 25 አበዊነ ሞኡ ፍትወተ ሥጋ። እነ አብርሃም ፍትወተ ሥጋን ድል ነሱ። **ድርሳን 27** በተአምኖ ነቢያት ተጋደሉ ወሞኡ ነገሥተ ኃያላነ። **ድርሳን 33** ወእመሰ ኮነ ለሊሁ ሎቱ ስብሀት ጸረ ወኩሉ ፍጥረት ኮኑነ አእርክተ አልብነ ረባሕ ወበቁኤት። ወከመዝ ዓዲ ሶበ አፍቀረነ ለሊሁ ኢይረክበነ እኩይ ግሙራ። ወሶበኒ ተጻብኡነ ኩሎሙ አልቦ ዘይክለነ።

ፍቅር

ድርሳን 31 ኀሱ ሰላመ ምስለ ኩሉ እግዚእነኒ ይቤ የአምረክሙ ኩሉ ከመ አርዳእየ አንትሙ ለእመ ተፋቀርክሙ በበይናቲክሙ።

ተግሣጽ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ተግሣጽ ማለት ስሕተትን ማረሚያ አቋምን ማስተካከያ መናፍቃንን መቃወሚያ መሐንዲስ ነው።

ገሀነመ እሳት፣ ተአምራት

ተግሣጽ 1 ጥቀ ታውኢ ገሀነመ እሳት። የወዲያኛውን ዓለም መከራ መናገር የሚቻለው የለም።

ሀሎ ህየ እሳት ወጽልመት ወመዋቅሕት ወዕጹ ዘኢይነውም ወይመስለኒ ከመ ይእቲ እሳት ተአኪ እምነ ዛቲ እሳት። እስመ ሀሎ ህየ እሳት ዘይነድድ በእፎኬ ይትረከብ ጽልመት። ጠየቀኑ ከመ ይእቲ እሳት ተአኪ እምነ ዛቲ እሳት እስመ አልባቲ ብርሃን እመኒ እሳት ይእቲ ርኢከኑ ከመ ታውኢ ፈድፋደ እምነ ዛቲ እስመ ኢትጠፍእ ወበእንተዝ ተብህለ እሳቱ ዘኢይጠፍዕ። መፍትው ለነ ኦ አኃው ንጠይቅ መጠነ ዝንቱ ሥቃይ ዘውእቱ ገዐር ዘእንበለ ጽርዐት ወሐቅየ ስነን ኀበ አልቦ ረዳኢ። ንከውን ሥጡማነ ውስተ ነደ እሳት ማዕከለ እኩያን ወከዓውያነ ደም ኢይሬእዩነ ወኢንሬእዮሙ። አላ ይመስለነ ለባሕቲትነ ዘሀሎነ ህየ እንዘ ምስሌነ ብዙኅ ጉባኤ እስመ ጽልመት ኢየኅድገነ ንትረአይ በበይናቲነ አላ ለለአሐዱ ይጸውር ሥቃዮ በባሕቲቱ ወበእንተዝ አስተበቁአክሙ ኦ አኀየ ከመተሐልዩ ዘንተ ወትረ በአልባቢክሙ። **ተግሣጽ** 24 ወገቢረ ተአምራት ወመንክራት ኢይክል ያድኅን እምሥቃየ ኩነኔ። ምክንያቱም በስሙ አምነው ይድኑ ዘንድ ስለመጡ ሰዎች ተአምራት ሊደረግ ይችላል። እነ በለዓምም በክፋት ሳሉ ተአምራት ትደረግላቸው ነበረችና።

ንጽሕና

ተግሣጽ 1 ናሁኬ አንጽሐነ እግዚአብሔር ልዑል በደሙ ክቡር እምኃጣውኢነ ይደልወነ ኦ ፍቁራንየ ንእቀብ ንጽሕናነ። ወኢንቅረብ ግሙራ ኀበ ምንትኒ እም ርኩስ። በኩሉ ጊዜ ይደልወነ ናጥሪ ልበ ንጹሐ ወሕሊና ርቱዓ ወአፍቅሮ እግዚአብሔር ልዑል። ርቱዕ ለነ ንጽሐቅ ወንትጋደል ከመ ንኩን ንጹሐነ። እስመ አኮ ክቡድ ውእቱ ዘአዘዘነ ንግበር። **ተግሣጽ** 21 ንንግፍ እምኔነ እንከ ጽልአ። **ተግሣጽ** 28 ተጸምዶ ለተድላ ዝ ዓለም ያማስን ነፍሰ።

ቁርባን

ተግሣጽ 1 ኃጢአት ዘእምቅድመ ቁርባን ይሠረይ በጥምቀት ወእምድህረ ጥምቀትሰ ይሠረይ በሥጋሁ ወበደሙ።

ንዑሳት ኃጣውኢ፣ አቂበ ልሣን

ተግሣጽ 1 እስመ ንዑሳት ኃጣውኢ ይሰመያ ርስሐተ ዘውእቶን ጽርፈት፣ ጋእዝ ወሐሰት ወባሕቱ እላሰ ኢኮና ንዕሳተ አላ ዓቢያት ጥቀ አላ እማንቱ ያርኅቃ እመንግሥተ ሰማያት። የንጉሥን አዋጅን ማፍረስ ንጉሡን ማዋረድ እንደሆነ አንድም ሕንጻውን መንቀፍ ሐናጺውን መንቀፍ እንደ እንደሆነ ፍጡርን መንቀፍ ፈጣሪውን መንቀፍ ነው። እስመ ፈጣሪ ሎቱ ስብሐት ኢወሀበነ ልሣነ ከመ ንጽርፍ ቦቱ ወንንብብ ሐሰተ ወንትገዐዝ በበይናቲነ አላ ከመ ንሰብሆ ቦቱ ለእግዚአብሔር ልዑል ወናሥተፍስሖሙ በንባብ ለእለ ይሰምዑነ ከመ ይኩኖሙ በቁኤተ ወንስሐቦሙ ኀበ ሰናይ ፍቅር። ንግረኒ እስኩ ኦ ብእሲ ምንት ብከ በቁኤት ለእመ ትቤ እገሌ እኩይ ውእቱ። ደግ ሥራም መልካም ስራም ቢሰሩት ቢሰሩት አያልቅም። **ተግሣጽ** 3 ኩን ሰናየ በቃልከሂ ወበራእይከሂ ወኩን ልብወ በሥርዓተ ምክር ወተግሣጽ። **ተግሣጽ** 25 ኢትደቅ እም ልእልናከ ውስተ ግበ ጽርፈት።

ፍቅረ ቢጽ

ተግሣጽ 1 ወዘያከብር ቢጾ ያከብሮ ለእግዚአብሔር። **ተግሣጽ** 3 እስመ ዛቲ ሀብት/ፍቅር ታበጽሐነ ኀበ ኩሉ ምግባራተ ሰናይ ዘእንበለ ጻማ ወሐፍ። ወእመቦ ዘይብል ናሁ ይእዜ ንሕነሂ ሀሎነ በተፋቅሮ ቦ እምኔነ ዘቦ ክልኤቱ አዕርክት ወካልእሂ ዘቦ ሠለስቱ ንብሎ ተፋቅሮትክሙ ኢኮነ በእንተ እግዚአብሔር አላ በእንተ ተአርኮ። ወፍቅርሰ ዘበእንተ እግዚአብሔር ዛቲ ይእቲ አፍቅር ኩሎ ከመ አኃዊከ። ወለዓላውያንሰ አይሁድ ወአረሚ አፍቅሮመ ከመ አኃዊከ ዘሥጋ ወተራኅራኂ ላዕሌሆመ ወተክዝ በእንቲአሆመ ወከዓው ላእሌሆመ አንብአ መሪረ በእንተ ስሕተቶመ ወጠዋይ ፍኖቶመ ወበዝንቱ ግብር ትትሜሰሎ ለእግዚአብሔር ልዑል። **ተግሣጽ** 19 ፍቅርሰ ኢታገብር እኩየ ወኢታሒሊ ኀሙመ በላዕለ ቢጽ። አኮኑ ኢንፈቅድ እኩየ ለርእስነ አላ ኩሎ ሰናያተ ወኩሎ ክብረ። ከማሁኬ ይደሉ ንጽሐቅ ከመዝ በእንተ ቢጽነ። መኑ እምሰብእ ዘይትቁየማ ለነፍሱ ወይትመዓዕ ላዕሌሃ አኮኑ ይሠሀላ በኩሉ ግብር ንግበርኬ ከመዝ ምስለ ቢጽነ ከመ ኢይርከብ **ቂም** መካነ በውስቴትነ አላ ይዒል ውስተ መካነ በድው። ሳኦልኒ ሶበ ገብአ ውስተ እደሁ ለዳዊት ኢፈቀደ ይቅትሎ አላ አድኃኖ እም እደ ካልዓን። **ተግሣጽ** 28 ቅብዕሰ ፍቅረ ደቂቀ እጓለ እመሕያው።

መንግሥተ ሰማያት

ተግሣጽ 1 ሰናይት ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ወትትአደው እምነ አእምሮ ወልቡና ወአኮ እምነ ቃል ባሕቲቱ። **ተግሣጽ** 6 አማን ከመ ለእንታክቲ እረፍት ዘበአማን ኢይረክባ ኀዘን ወምንዳቤ ኢብክይ ወኀዘነ ልብ ኢኀርትምና ወኢ ፍርሀት ዘያቴክዛ ለነፍስ ወያደነግጻ አላ የኀድር ላዕሌሃ ፈሪሀ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ዘምሉዕ ጣዕመ ፍሥሓ። በህየሰ ፍሥሓ ወሰላም ዕረፍት ወተድላ ኂሩት ወየውሃት ርትዕ ወተፋቅሮ አልቦ ህየ ቅንአት ወተቃሕዎ ኢጽልመት ወኢሌሊት አላ ብርሃን ወመዓልት ሥን ወጸዳል አልቦ ህየ ጻማ ወጽጋብ አላ ወትረ ረኪበ ሰናያት ዘለዓለም።

ምጽዋት

ተግሣጽ 1 ወገቢረ ምጽዋትሰ አኮ ዘተሰርአ ላዕለ ብዑላን ባሕቲቶሙ አላ ላዕለ ነዳያንሂ። አብአት ክልኤተ ጸራይቀ እንዲል። እስመ ዘይሁብ ኀዳጠ እምውስተ ኀዳጥ ይፈደፍድ እምእለ ይሁቡ ብዙኀ እምውስተ ብዙኀ ከመ እንታክቲ መበለት። እስመ ነዳይኒ እመኒ ተጸነሰ ጥቀ ኢየኃጥእ ክልኤተ ጸራይቀ። እስመ ሕገ ምጽዋት ኢኮነ በብዝኀ ውሂብ አላ በከመ ስምረተ ልቡ ወኃይለ ሃይማኖቱ።

ሀብትና ድህነት፣ ጸጋ

ተግሣጽ 2 ብዕል የኃጢአት አጋዥር እንደሆነች ወተጽናስኒ ይረድእ ለገቢረ ጽድቅ። ንዴቱን ወደው የሚታገሱ ሰዎች አኗኗራቸው ከባለጸጎች አኗኗር ይልቅ ደስ ያሰኛል። ኢትትፈሣሕ ኦ ብእሲ በብዕለ ዝንቱ ዓለም ዘይወርስዎ ፈያት ወሰረቅት ወከዓውያነ ደም ወዘማውያን ኀሡራን ወምኑናን ወኩሎመ እኩያን። እመሰኬ ከመዝ ውእቱ ለምንት ትትኤበይ። ወእመቦ ዘይብል ተጽናስሰ ኃሣር ውእቱ ንንሥት እንከ ዓረፍተ ምክንያቱ ወንብሎ አኮ ኃሣር ውእቱ አላ እለ

ያስተሐቅርዎ ጎሡራን እሙንቱ። ወበእንተዝ ንሕነኒ መናንያን ኢንጎዝን ላዕለ እለ ያስተሐቅሩነ በእንተ ተጽናስነ። እብል እንከ ከመ ኢብዕል ወኢተጽናስ እኩያን በግእዞሙ። እስመ ተጽናስ ያሴስል እምኔሁ ትእቢተ ወትዝህርተ ወያፈደፍድ ንጽሐ ወጽንአ ነፍስ ወንጽሐ ልብ ምስለ ትሕትና። ወለባዕልሰ ሚ ይበዝኑ እለ ይክልእዎ ወያርጎቅዎ እምዛቲ ምግባራት። ወእመኒ ኃጣዕነ ኢንጎዝን አላ ናእኩቶ ለእግዚአብሔር ልዑል በእንተ ኩሉ። ንደኅት ይሄይሥ ፈድፋደ እምነ ብዕል። **ተግሣጽ 3** ኢመፍትው ለነ ንበል እምፈተውኩ እርከብ ሚመተ ለተልእኮ ውስተ ቤተክርስቲያን ወዓዲ ንዋየ ብዙኀ ከመ እመጸውት ላዕለ ነዳያን እስመ እግዚአብሔር ልዑል የአምር ፈድፋደ እምኔነ ዘይከውነነ ለበቁኤት። ወኢተአምር እመ ይፈደፍድ ስስዕትከ ጊዜ ትረክቦ ለብዙኀ ንዋይ። ወባሕቱ አንተ ይእዜ ትሐሊ ዘንተ ወሶበ ፈተነከ እምተወለጠ ልብከ። ታሪክ እንደ አውሎጊስ ወፍጮ እየነጠለ እያለዘበ ያን እየሸጠ ለልብስ ለቀለብ እያስቀረ ይመጸውት ነበረ። ዳንኤል የሚባል ባሕታዊ ወዳጅ ነበረው። ከቤቱ ሄደ እንዲህ ሲያደርግ አይታል በዚህ በጥቂት ገንዘብ እንዲህ ያደረገ ብዙ ገንዘብስ ቢያገኝ ነዳያንን እንዴት በጠቀመ ነበር ብሎ ወደጌታ አመለከተ ጌታም አብዝቶ ቢሰጠው ገፊ ጽርሐ ነዳያንን የማይሰማ ሆነ። ወዓዲ ኢትበል ለምንት ኢተውህበኒ ጸጋ ምህሮ ወሶበ ተውህበኒ እምበቋዕክዎሙ ለብዙኃን ወኢተአምር ከመ እመቦ ሶበ ረከብከ ሀብተ ምህሮ እምኮነከ ምክንያተ ኩነኔ ለነፍስከ በፍኖተ ቅንዓት ወአሜሃ ትሰመይ ዘደፈነ መክሊተ እግዚኡ። ወይእዜሰ ድኑን አንተ እምዝንቱ ኩሉ። መፍተው ለነ ንዕቀብ ዘጸገወነ እመኒ ጎዳጥ ወእመኒ ብዙኀ ሶቤሃኬ ንከውን ብዑላነ ፈድፋደ። **ተግሣጽ 18** መፍትው ንኅረይ ንደኅተ። ባዕልሰ ገብር ውእቱ ወነዳይሰ ኢይፈርህ እመሣጢ ወኮናኒ።ለነዳይሰ አልቦ ዘያፈርሆ ወኢዘያኅዝኖ ምንትኒ። ገንዘብ ክብር አያሰጥም።

ትሕትና፣ በሰው መመካት እንደማይገባ

ተግሣጽ 2 ኦ ፍቁራን ኢርቱዕ ንትአበይ ወንትጋየጽ በምንትኒ እምግብር እስመ እግዚእነ እንዘ አምላክ ውእቱ ኢአበየ ተወልዶ በአምሳለ ገብር። ሰውን ጌጥ እንዳናደርግ እንጠንቀቅ።ከስራ በማናቸውም ስራ እንታበይ ዘንድ አይገባም። ውሳጣዊ በመሆን እስክታገኛት ድረስ የአፍአዊ ትሕትናን ሥራ ልትሠራ ይገባል። እመሰ ይደሉ ተመክሖ መመካት አይገባም እንጂ የሚገባ ከሆነ ለንትመካሕ በንዴት ወበተጽናስ ወአኮ በብእል። **ተግሣጽ 27** ትሕትናሰ ዘበአማን አኮ ውእቱ ከመ ይጽእል ብእሲ ርእሶ አላ ይትዐገሥ ሶበ ይጼዕልዎ ካልዓን።

ክብር ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

ተግሣጽ 2 ንግረኒ ኦ ብእሲ እም አይቴ ትረክብ ክብረ በምግባራተ ዓለምኑ። አኮኑ ተነድገከ ወተሐውር። ወእመኒ ኢነደገተከ ለሊከ ተነድጋ እንበለ ፈቃድከ ወተሐውር እምኔሃ ነበ ኢትገብእ። ወአንተሰ ለምንት ትትሜካሕ ለእመ ከመዝ ውእቱ አጥሪ እንከ ምግባረ መንፈሳዊ ወመዓርገ ሉዓላዊ። ኢኮነሁ ዕራቀነ ዘቦእነ ውስተ ዓለም ወከማሁ ዕራቃቲነ ንወጽእ እምኔሃ። **ተግሣጽ 7** እመሰኬ ወድቀ አረጋዊ እመንበሩ ወሞፆ ፍቅረ ንዋይ ወክብረ ከንቱ ወሥርጋዌ ወተድላ ወስካር ወመዓት ወተራክቦ ወተቀብፆ ዕፍረት ይወድቅ እምክብረ አእሩግ በፈቃዱ። **ተግሣጽ 9** ኮንከኑ ንጉሠ በመዓልት ከማሁ ሊተኒ ሜሙኒ በሌሊት። እሬእየከ ከመ ኢትፈደፍድ እምኔየ በምንትኒ። አይቴ ሀለው እለ ነበሩ በዛቲ መዓርግ እምዘነግሡ በአሠርቱ ዓመት ናሁ

ኀለፉ። ወኮኑ ዘኢነበሩ ግሙራ ወባሕቱ ብጹዕሰ ጳውሎስ ኢኮነ በዝንቱ አርአያ ወትእምርተ ዝንቱ እስመ ውእቱ ነበረ ኩሎ መዋእለ ሕይወቱ እንዘ ያበርህ ወያንጸበርቅ አላ ናሁ ኀለፈ አርባዕቱ ምእት ዓመት እምዘ አዕረፈ ወሀለወ እስከ ይእዜ እንዘ ይትዌሰኮ ስን በዲበ ስን። ወፈድፋደ ክብሩ እምዘቀዳሚ አመሀሎ ሕያው ውስተ ምድር። ወሥኖሙሰ ለቅዱሳን ዘበሰማያት መኑ ይክል ፈጽሞ ነጊሮቱ። ወበእንተዝ አስተበቁዐክሙ ኦ ፍቁራን ከመ ትኅሥሡ ዘንተ ክብረ ወታድምዑ ኪያሃ። እስመ ውእቱ ክብር ዘበአማን ወሥን ዘኢየኀልፍ ወጸዳል ዘኢይጸምን። ወይእዜኒ ኦ ፍቁራን ኢናፍቅር ክብረ ወአስተጋብኦ ንዋይ።

ቁጣ፣ ተግሣጽ

ተግሣጽ 2 ቦ መዓት ዘበርትዕ። ሀተታ ሕግ ቢፈርስ ሕጻናት ከመማር ቢሰንፉ የተማሩትን ቢገድፉ መናፍቃን በጥባኤ ቢሰለጥኑ የሚገባ ቁጣ ነው። **ተግሣጽ 5** እስመ መዓት እምግእዘ አራዊት ውእቱ። ቁጣ የአራዊት ስራ ነው። **ተግሣጽ ፴** ኢንትመዓዕ ወኢንተክዝ ሶበ ይጌሥጹነ እስመ ሰብእ ንሕነ ወብነ አበሳ ወጌጋይ። እብል እንከ ለእለ ይሜህሩ ወይጌሥጹ ያጥርዩ ግእዘ ሠናየ ወውዱሰ። ወመገሥጽሂ ኢይኩን ከመ መዐትም።

ቅንአት

ቅንአት ምስለ ፍትወት እኪት ይእቲ። ወቅንአትኒ ሰናይት ይእቲ ለእመ ኮነት በእንተ ጽድቅ ከመ ቃለ ጳውሎስ ዘይቤ ቅንኡ ለእንተ ተአቢ ጸጋ።

እግዚአብሔር

ተግሣጽ 3 ወአንተሰ ኦ ብእሲ ኢትክል ጠይቆ ርእሰከ ከመ እግዚአብሔር እስመ ውእቱ የአምር ኩለንታከ። **ተግሣጽ 13** ይደልወነ ንትመሰል በክርስቶሰ ኦ ፍቁራን ወንትሉ አሠረ ዚአሁ ወንሐር በፍናዊሁ። ህልው ውእቱ እግዚአብሔር ውስተ ኩሉ መካን ወይሰምዕ ኩሎ። **ተግሣጽ 24** አልቦ ምንትኒ ዘይኤድሞ ለእግዚአብሔር ከመ ምግባረ ትሩፋት። አብዝኖ ሰሚዕ ወኢገቢሮቱ ያምዕያ ለእግዚአብሔር ሎቱ ስብሀት።

ሞት

ተግሣጽ 4 በእንተ ገሥጾ ላእለ ምውታን፡- ወኢርቱዕ ይትጋብኡ በላህ ወበንዘን።ኦ አኃውየ ንሳለቆ ለሞት ወንትቃጸቦ። አይቴ ቀኖትከ ሞት እያልን እንዘብትበት። ንግረኒ እስኩ ለምንት ንጻመ በገቢረ መኃትው ብሩሃት ወስምዓት ንጹሓት አኮኑ እንዘ ንፈንዎመ በክብር ለመታን። ወናሄኒ ግንዘቶመ በዓቢይ ጻሕቅ። ወንገብር ጸሎተ ወስብሐታተ እንዘ ንሴብሆ ወነአኩቶ ለእግዚአብሔር ልዑል። ወዝንቱ ስብሀት ወዝማሬ ዘንገብር በእንቲአሁ አኮኑ ንኤምር ከመ ሖረ ውስተ ፍሥሓ ወሐሴት። ለምንትኬ ይነጽዩ ሥዕርተ ርእሶመ ወብእሲትኒ ታዕቢ ቃላ ወትኬልሕ አይኑ ኃሣር ዘየዐኪ እምዝንቱ። እመኑኒ ኦ አኃው እምደለዎመ ለእሉ ከመ ይክልእዎመ በዊአ ውስተ ቤተክርስቲያን እስከ ነዋኅ መዋእል። እስመ ለዘከመ እሉ መፍትው ይብክይዎመ እንዘ ሀለው በሕይወቶመ። እስመ ይፈርሕዎ ለሞት ወይደነግጹ እምኔሁ

ወኢየአምኑ ትንሳኤ። ወእመቦ ዘይብል ንሕነሰኬ አኮ ዘንክሕድ ትንሳኤ አላ ንገብር ዘንተ በከመ ሕገ ልማድ። ወአንሰ አወስኣ ለዛቲ ነባቢት ወእብላ እስኩ ንግርኒ ዘእሴአለኪ ሶበ የሀውር ምትኪ ርኑቀ ብሔረ ትገብሪኑ ከመዝ በእንቲአሁ። ወእመ ትቤልኒ እወ እበኪ እብለኪ አነሂ ዘንተሰ ትገብሪ እንዘ ትሴፈዊ ግብአቶ። ወባሕቱ ላእለ ዘሞተሰ ትበክዩ በቀቢጸ ተስፋ እንዘ ኢትሴፈዊ ግብአቶ።

ትእዛዘ ቤተ ክርስቲያን

ተግሣጽ 4 ኦ አኃው ኢታስተሐቅሩ ትእዛዘ ቤተክርስቲያን እንተ ኢተሠርዐት በንበ ሰብእ። እግዚአብሔር ውእቱ ዘአዘዘ ሥርዓተ ምእመናን።

ትእግስት

ተግሣጽ 4 ንትአገሥ እንከ ሶበ ይዘልፉነ ወንትዐቀብ ከመ ኢነአብስ። ትእግስት ክፉውን ግብር ሁሉ ያጠፋዋል። መከራን መታገሥ አያስነቅፍም መልሶ መምታት መልሶ መስደብ ያስነቅፋል እንጂ። **ተግሣጽ ፭** ወንትዓገሥ ኩሎ ዘይመጽእ ላዕሌነ ከመ ናጽምእ ዓስበ ዘድልው ለተዐጋሥያን። እስመ ለሊሁ ይቤ ፁሩ ክበደ ቢጽክሙ በበይናቲክሙ።

ንሥሓ

ተግሣጽ 4 ሰናይኬ ሶበ ኢንቆስል እሾህ ባይወጋን ባንቆስል መልካም ነበረ። ወእመሰቦ ዘአቁሰለነ ንደይ ፈውሰ ውስተ ቁስላቲነ። ኃጢአት ባንሰራ መልካም ነበረ ኃጢአት ከሠራንም ንሥሓ እንግባ። **ተግሣጽ 14** ኢመፍትው ለነ ንቅብጽ ተስፋ ሶበ ገበርነ ኃጢአተ።

ፍዳ ጻድቃን ወኃጥአን፣ ፍርድ

ተግሣጽ 5 ኢመፍትው ለነ ናንክር ጥዒና ሕይወቶሙ ለእኩያን በዝ ዓለም ወተጽናሰ ንደቶሙ ለኄራን ወኢያንቀልቅል ሕሊናነ። እስመ ፍዳ አኮ በዝየ ኢ ዘሠናይ ወኢ ዘእኩይ።ወለእመ ርኢከ ብእሴ እኩየ ወቦ ንስቲት ምግባረ ሰናይ ወዓዲ እንዘቦ ብዕል ወተድላ ኢታንክር እስመ ረከበ አስቦ በዝየ። ወበህየሰ ይትመከአብ ሎቱ እከየ ዚአሁ ወይትኬነን ፍጹመ። ወብጹዕሰ ዘበአማን ዘተኮነነ በዝየ ከመ ያሰስል እምላእሌሁ ልብሰ ርስሐት ወየሐውር ህየ እንዘ ንጹሕ ውእቱ ዘአልቦ ነውር። ዕውቅ ውእቱ ከመ እኩያን ይትፈሥሑ በዝየ ወይትኬነኑ ፍጹመ በህየ። ነጽርኬ ዘከመ ይቤሎ አብርሃም ለውእቱ ባዕል አንተሰ ሠለጥከ ዓስበከ እስመ ፈጋዕከ በሕይወትከ ወአልአኅርሰ በተጽናስ ወይትፈሣሕ በዝየ ወአንተሰ ተሐምም። ርኢከኑ ከመ ክልኤሆሙ ረከቡ ዘይደልዎሙ። ኢንኅዝንኬ ኦ አኃው ሶበ ንሬእዮሙ ለኃጥዐን እንዘ ይዴለው በዝየ ወንሕነ ሶበ ንጼነስ። አላ ንትፈሣሕ በጊዜ ይረክበነ ምንዳቤ እስመ ይከውነነ ለስርየተ ኃጢአት ወለድምሳሴ አበሳ።

ትጋህ፣ጸሎት

ተግሣጽ 5 ኢንኅሥሥ ዕረፍተ ከመ ንርከብ አክሊለ ዘኢየኅልፍ። ናብዝኅ እንከ ጸልዮ። ጸሎትሰ

መድኃኒት ውእቱ ወአሰሳሌ ኩሉ ኃጣውዕ ወአበሳ ወዓቃቤ ሥራይ ለኩሎን ኃጣውኣ።

መከራ፣ ማሸነፍ፣ መላእክት፣ ተጋድሎ

ተግሣጽ 5 ይደልወነ ንሥአሎ ለእግዚአብሔር ልዑል ከመ ኢያብዐነ ውሰተ መንሱት ወእመኒ ቦእነ ንትዐገሥ በብዙኅ ገድል። ወባሕቱ ኢንባዕ በፈቃድነ ውስተ መናስው። ወእም ከመሰ በጽሐነ ምንዳቤ ኢንፍራሕ ወኢንደንግጽ። ወአንተሰ ኩን ድልወ ከመ ሐራዊ መስተቃትል ወሀሉ ወትረ በንቅሐት ወበተአቅቦ እንዘ ምጽአተ ቀትል ወተጻብኦ ትጸንሕ። ወተጋደል እስከ ፍጻሜ ወማዕ ሐራሁ ለጸላኢ መስተቃርን ወዝሩ ማኅበሮ ለጸር። ከመ ንማያሙ ለጸላእትነ እለ ይጸብኡነ ወንልበስ አክሊለ ዘመዊእ። **ተግሣጽ** 12 ትመውዕ በእንተ ዘተጋደልከ። **ተግሣጽ** 14 ኦ ፍቁራንየ ይደልወነ ከመ ንትጋህ ወንጸሊ ኩላ ሌሊተ እስመ ብነ እለ ይትራድኡነ ወንክል መዊአ ለእመ ፈቀድነ እስመ መላእክት ይነብሩ ምስሌነ። መፍትውኬ ንትጋደል በኩሉ ኃይልነ።ሰው ከኃጢአት ብቻ ስለተለየ ቅዱስ አይባልም ትሩፋት ምግባርም ሰርቶ ነው እንጂ። ይደልወነ ንትጋደል በዝንቱ ዘመን ሐጺር። **ተግሣጽ** 21 ይቤ እግዚእነ በዓለምሰ ሕማመ ትረክቡ ወባሕቱ ጽንዑ እስመ አነ ሞእክዎ ለዓለም። **ተግሣጽ** 23 ኦ ፍቁራን መኑኬ ዘይከውን ብጹዐ ከመ መዋዕያን። **ተግሣጽ** 25 ወአንተሰ እምከመ ኀደገ ተበቅሎ ጸላእትከ ይእተ ጊዜ ትመውዖሙ። **ተግሣጽ** 28 እስመ ኀዘን ያሴስል ኃጢአተ ወያመጽእ ኃይለ ወረድኤተ። ናብዝኅ በእንተ ዜንዎ እሙነ ከመ ንርከብ መዊዐ በላዕለ ኩሉ ግብር። ወእመሰ ለሊሁ ክርስቶስ ሖረ በትካዝ ወበጻማ ወአንተሰ በዕረፍት ናሁኬ ኢሖርከ በፍኖት ዘሖረ ባቲ ውእቱ አላ በካልእ።ወእፎኑ ትከውን ተላዊሁ እንዘ ኢትተልዎ አንተ።

ስንፍና/ሀኬት፣ ትሩፋት

ተግሣጽ 7 ኢመፍትው ለነ ንትሐከይ ተጸምዶ በጊዜ ርስዓን ወኢንበል የአክለነ ዘገበርነ በውርዝውና አላ ንወስክ በዲበ ገድልነ በከመ ይደሉ። ለትሩፋት የሚፋጠን ባሕታዊ ተክል ልትከል ዘር ልዝራ አይልም። ዕጸበ ገዳምን ግርማ ሌሊትን ድምጸ አራዊትን አያስብም። የምግባሩን ዋጋ መንግሥተ ሰማይን ያስባል እንጂ። ውዳሴ አያስደስተውም ሐሜት አያሳዝነውም። ይደልወነ ኦ አኃው ንዕቀብ ወትረ ነፍሳቲነ ከመ ኢይምጽአነ ሀኬት ወተሀይዮት።

መጻሕፍት አምላካውያትን ማንበብ፣ መማር

ተግሣጽ 8 ወለእመ ትብለኒ በምንትኬ ይትረየጻ ሕሊናቲነ ልቡናችን በምን ይለዝባል ትለኝ እንደሆነ እወ ይትረየጻ በአስተሐይጾ መጻሕፍት ወተጸምዶ ለሰሚያቶን። መጽሐፍ በመመልከት በመማር ይለዝባል ብየ እመልስልሀለሁ። ይደልወነ ናጽምእ ቃላተ መለኮት ከመ ኢይባእ ውስተ አልባቢነ ቃል ነኪር። አውአዩ እልዋን ኩሎ መጻሕፍተ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሀት ለአሐዱ ብእሲ ትሩፈ ምግባር ወአዘዞ ከመ ይጽሐፍ ወአስተጋብኦን እምዝርወት ዘውእቱ ዕዝራ። ወእምድህሬሁኒ ረሰየቶሙ ኪነጥበቡ ለ፵ ሊቃናት ከመ ይተርጕምዎን። ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ይምሀር።ስማዕ ዘይቤ ዳዊት

ንዑ ደቂቅየ ወስምዑኒ ፈሪሀ እግዚአብሔር እምህርክሙ። ናሁኬ አየቀ ከመ ፈሪሀ እግዚአብሔር ይከውን እምነ ትምህርታት።

ምጽዋት

ተግሣጽ 10 መፍትው ለነ ንመጽውት ላዕለ ኩሉ በዕሩይ እንዘ ኢንሌሊ አረማዊ አው መሢሐዊ። ወፈድፋደሰ ለምእመናን። እስመ ምጽዋት ምሕረት ይእቲ። አኃዊነ ኢናሕጽጽ ገቢረ ሰናይ ላዕለ ምእመናን ወካልአንሂ። ወእመ ርኢከ ብእሴ ኃጥአ እንዘ ይጼነስ ርድኦ ወኢትኅሥሥ ምግባራቲሁ እስመ ዘእግዚአብሔር ውእቱ። ለገንዘብህ አትዘንለት ለተቸገሩት አሳልፈህ ስጠው እንጂ። **ተግሣጽ** 11 ሰዎች ሁሉ የሚቸገሩት በስንፍናቸው አይደለም።በ እምኔሆሙ ዘበተሰጥሞ ውስተ ባሕር ንብረቶሙ ወቦ ዘተገፍአ በዓውደ ምኩናን ወቦ ዘተሰርቀ ንዋዮ ቦ ዘበደዌ ወቦ ዘበመከራ ወዘይመስሎ ለዝንቱ። ድኃ የሚያሳዝን ጨቹት ቢጮህ ሰው እንዲያዝንለትና እንዲሰጠው ነው። አካሉን አሳይቶ የሚለምንህ ቢቸገር ነውና እርዳው ከልመና የሚጨንቅ የለምና። ይሄይስ መዊት እምኔሁ። በየቀኑ ምጽዋት ስጥ ምክንያቱም አንተም በየቀኑ እንደምትበላ ሁሉ እነርሱም በየቀኑ መብላት አለባቸውና ብዙ ቀን ሰጥቻለሁ ብለህ አታቋርጥ ካቋረጥክ ይራባሉና። እግዚአብሔር ግን የሰጠህ እንድትረዳቸው ጭምር ነው።

ፍቅረ ንዋይ

ተግሣጽ 11 ኢያንድድከ ፍቅረ ንዋይ ወኢይማዕከ ስስዕት ዘጥሪት አላ ኩን ንዱደ በእሳተ መንፈስ ከመ ታውእያ ለፍትወት እኪት ወትምትራ በሰይፈ መንፈስ። ወዘሰ ያፈቅር ንዋየ ወአሠንዮ ሥጋ የአኪ እምኩሉ ደዌ። አሌ ለኪ ኦ ንዋይ። **ተግሣጽ** 20 ንዋይሰ ወጥሪት ይተርፉ በዝየ። ነፍስሰ ተነድኅሙ ወተሐውር ከሐ። **ተግሣጽ** 24 ኦ አኃውየ ንኩን ነግደ ወፈላሴ።

ትርጓሜ

ተግሣጽ 12 ዓዲ ቦ ኀበ ንሬሲ ብሂለ ኩሉ ውስተ ዘይበዝኅ ወውስተ ውኑድኒ ንብል አልቦ።

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ነጻ ፈቃድ

ተግሣጽ 12 ቅዱስ ጳውሎስ ኢለዘርጸ ወኢለዘበደረ ዳዕሙ ለዘእግዚአብሔር ምሕሮ ያለው። አንደኛ በሩጫችን በድካማችን እንዳንታበይ እና አኮ በጽድቅነ ዘእንበለ ዳዕሙ በረድኤተ ልዑል ሉዓላዊት እንድንል ነው። ማለትም ያለረድኤተ እግዚአብሔር ስራችን ከንቱ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው። ትመውእ በእንተ ዘተጋደልከ አንተሰ ተጋደል ወሐሊ ገቢረ ጽድቅ እንዘ ትብል እረክብ አስብየ ወብየ መባሕት እግበር ዘፈቀድኩ እስመ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሀት ኢይፈቅድ ከመ ንበል ኩሉ ዘንሔሊ እምነቤሁ ውእቱ። ከመ ኢንበል በከንቱ ይሁብ አክሊላተ። ምን ትሩፋት ብንሰራ ለመንግሥተ ሰማያት ዋጋ አይሆንምና ኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነቱ እርሷን መንግሥተ ሰማያትን ያድለን።

ሽንገላ፣ ከንቱ ውዳሴ፣ አለባበስ

ተግሣጽ 12 ቦ እምሰብእ እለ ይትሜሰሉ የዋሃነ እንዘ እኩይ ውስተ ልቦሙ። **ተግሣጽ** 27 ንጉየይ እምነ ውዳሴ። **ተግሣጽ** 28 ሴቶች ተውበው የሚወጡት ለመታየት ለከንቱ ውዳሴ አቦ አቦ ለመባል ከሆነ ኃጢአት ነው። ብዙኃት እማንቱ እለከመዝ መፍቅዶን ተሠርግዎ ወዘፈን ከመ ይሥሐባ ኩሎ ዘርእዮን። ወባሕቱ እስመ ብእሲትሰ ንጽሕት ወሠናይት ወመሐይምንት ኢትሠረገው በዘከመዝ አርአያ አላ በካልእ እምዝንቱ። ልብስ ለከዲነ ዕርቃን ብቻ ነው መዋል ያለበት። ወእመሰ ትፈቅዲ ታስምሪዮ ፍጹመ ለምትኪ ይኩን ሑረትኪ በስነ ግእዝ ወይዋሄ ወቃለ ርኅራኄ። ጌጠኛ ልብስ ብትለብሺ የዝሙት ነገርን ብትናገሪ እግዚአብሔር ይጠላሻል። ወይፈትውኪ ዕደው ርኩሳን ወዘማውያን። ሥርጋዌሃሰ ለብእሲት እምአፍኣ ይስሕብ ዕደወ ርኩሳነ ወዘማውያነ።

ቅድስት ድንግል ማርያም

ተግሣጽ 14 እመቤታችንን ርስኢ ሕዝበኪ ያላት የሕዝቦችሽን ኃጢአት አትስሪ ሲላት ነው።

ሐልዮ

ተግሣጽ 14 ነቅዐ ሐልዮ ከሌለ ቁርጽ ሐልዮ የለም ቁርጽ ሐልዮም ከሌለ ነቢብ የለም ነቢብ ከሌለ ገቢር የለም። ከሐልዮ ኃጢአት መዳን እንደምን ይቻላል የሚል ሰው ቢኖር ንብሎ ይትከሀል በተዘክሮ ሰናያት ወተዛውዖ በነገረ እግዚአብሔር ልዑል እስመ ለእመ አዘለፍነ ወትረ ዝክረ ፈጣሪ ይትባረክ ስሙ ንረስዓ ለእንታክቲ እከይ።

ተዘክሮ እግዚአብሔር

ተግሣጽ 14 ናጥሪ ኦ አኃው ተዘክሮ ልዑል በጊዜ ጽባሕ ወዘንተ ለእመ ገበርነ ኢንረክብ ዘይጸብዐነ ወለእመኒ ብነ ጸላዕት ንመውዖሙ እስመ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሀት ይከውን ረዳኢነ። ናጥሪ ለነ ፀሐየ ጽድቅ ዘኢየአርብ። ወእምከመ ነበርነ ውስተ አርያም ንሬኢ ኩሎ ከመ ጽንጽንያ። አልቦ ዘይክል ይፍልጠነ እምክርስቶስ። መፍትው ለነ ዘልፉ ንልሐኩ ውስተ አልባቢነ ተዘክሮ እግዚአብሔር ልዑል።

ነቢብ

ተግሣጽ 14 ወኢንትናገርኬ ምንተኒ ኅሡመ ዘእንበለ ሠናይት። እስመ ውእቱ አኮ ዘይኬንን በእንተ ገቢር ባሕቲቱ አላ በእንተ ቃልሂ።

ሳቅ

ተግሣጽ 15 አልቦ ረባሕ በውስተ ሰሐቅ በአይቱ ሰማዕከ በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ከመ ሰሐቀ ዘእንበለ ዳዕሙ ዘንዘነ ወተከዘ። ሰሐቅሰ ሰናይ ውእቱ ሶበ ንሬእዮሙ ለአዕርክቲነ እምድኅረ ጉንዱይ ዘመን። በቤተ ክርስቲያን ግን ሳቅ አይገባም።

ቁርባን

ተግሣጽ 17 መፍትው ንቅረብ በንጽሕ ኅበ ምሥጢር ግሩም ዘዲበ ማዕድ ቅድስት። ቁርባን ከተቀበልክ በኋላ ወደ ክፉ ሥራህ አትመለስ። እስኩ ንግረኒ ሶበ ትጥዒ እምሕማምከ መሪረ በ፴ ዕለት ወእምዝ ትገብዕ ወትሜሠይ መባልዕተ ምኑናተ ዘያመጽኡ ደዌ አኮኑ አንተ አኅጎልከ ኩሎ ፃማከ ወተዐቅቦትከ። መፍትውኬ ንትጋደል በኩሉ ኃይልነ። ሰው ከኃጢአት ብቻ ስለተለየ ቅዱስ አይባልም ትሩፋት ምግባርም ሰርቶ ነው እንጂ። ይደልወነ ንትጋደል በዝንቱ ዘመን ሐጺር።

ሰይጣን

ተግሣጽ 18 አኮ ከሐድያን ባሕቲቶሙ ዘይከውኑ ጸላዕቶ አላ ኩሎሙ እለ የሐውሩ በፍኖተ ርኩስ።

ነጻነት

ተግሣጽ 20 ሰው ገንዘብ ካልወደደ ሹመት ሽልማት ካልፈለገ ሰው ሁሉ ሲገዛ እርሱ አይገዛም። ገዥም ሁሉን ሲገዛ እርሱን አይገዛውም። **ተግሣጽ** 25 ቅድመ አግዕዝ ርእሰከ እምቅኔግብርናት።

መመርመር

ተግሣጽ 20 መፍትው ለነ ለመሢሐውያን ናእምር ዘይበቁዐነ ወዘኢይበቁዐነ ወንመንን አልባሰ ወርቅ።

ምስጋና

ተግሣጽ 20 እመሰኬ አእኮትነ በእንተ ኩሉ ዘይረክበነ ብነ ዐስብ አቢይ።የሰይጣን ፍላጎት የኢዮብን ገንዘቡን ማጥፋት አይደለም። ኢዮብ ነዳይ እንዲሆን ፈልጎም አይደለም። እግዚአብሔርን በዚህ ምክንያት እንዲሰድበው ነው እንጂ። ኢዮብን ተስፋ መቁረጥ አላገኘውም።

ከባቴ አበሳ

ተግሣጽ 21 ይደልወነ ኦ ፍቁራን ንፍራህ ወንትዐቀብ። ይደልወነ ንክድን አበሳ ቢጽነ።

ጽናት

ተግሣጽ 24 መርከበኛ መርከቡን ባሕሩን ሁሉ አዙሮ ከወደቡ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው መቅዘፉን ቸል ቢል ከዚህ በኋላ መርከቡ ቢሰጥም የድካሙን ዋጋ ያገኛል። የቀደመ ትጋቱ ከንቱ ይሆናል። ከማሁኬ ሥርዓተ ምግባር ዘጽድቅ። ለእመ ኢፈጸሙ ውጥነቶሙ በሰናይ ይጠፍዑ ወይማስኑ በሀኬቶሙ ወየኀጉሉ አስቦሙ።

ተድላ

ተግሣጽ 29 ወትፍግዕትሰ ያማስን ነፍሰ ወሥጋ ኅቡረ። አሰስል ነዘህላለ ወፍትወተ እኪተ ወአፍቅሮ ግብር ዓለማዊ። ወፈቲወ ዕቤ ወንዒድ/አቦ አቦ መባል። አብዝኖ መባልዕት ወአልባሰ ቀጠንት ያመነስዋ ለነፍስ። መንኑ ትፍግዕታተ። ኅድግ አብዝኖ መባልእት ወስቴ ወይን እስመ እምዝንቱ ይትወለድ ፍትወት እኪት። አብዝቶ ከመመገብ የተለየች ሰውነት ግን ክፉ ፈቃድን አታስገኝም።

መምህር

ተግሣጽ ፴ የሚያስተምር ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ዋጋ ያገኛል። ለቡ ኦ እኅው እስመ በዓለ መክሊት ኀምስቱ መምሕር ውእቱ ወበዓለ አሐዱ መክሊት ረድእ ውእቱ። በአቅምህ አስተምር።

መጽሐፈ መነኮሳት

ማር ይሥሐቅ

የማር ይሥሐቅ ሀገረ ሙላዱ ብሔረ ነገዱ ሶርያ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ የማር ይሥሐቅ አኅት ነው። በአባ ብሶይ ገዳም የቆስጠንጢኖስን ስሙን በጸሎተ ማኅበር በቅዳሴ ይጠሩታል። ከእለታት አንድ ቀን ቆስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ አባ ብሶይን ሰላም ለክሙ ብጹዓን መነኮሳት አለው። አንተም እንጂ ብጹዕ ነህ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቁሞልሀልና አለው። ይህንስ አውቁ ቢሆን መንግሥቱን ለቅቁ ከበረሃ ወድቁ ጤዛ ልሼ ደንገያ ተንተርሼ በኖርሁ ነበር አለው። **አንቀጽ** 4፣12 አበው ከየውሃት ሲደርሱ እንደ ሕጻን ይሆናሉ በላሁ አልበላሁም ይላሉ።

መጻሕፍት፣ ዕውቀት

መጻሕፍት የአትታ ጽልመተ እም ኅሊናት። **አንቀጽ** 1፣3 ወየሐበርታ ጽልመተ ላህላት እምነ አልባብ። ከመ ትርከብ ኑላዜ ፍጹመ በውስተ ነፍስከ አዝልፍ ወትረ ኀበ አንብቦ መጻሕፍት በጽማዌ ከመ ይመርሓሁ ለልብከ ወትረ ኀበ አንክሮተ እግዚአብሔር ልዑል። **አንቀጽ** 1፣7 ኢትንብቦ ለመኑሂ በዘኢለበውከ ወኢያእመርከ። ያልተረዳህውን ያላወቅኸውን አታስተምር። ከመ ኢትኅፈር በርእስከ። **አንቀጽ** 1፣9 የመናፍቃንን መጽሐፍ ከመመልከት ተከልከል። ቅረብ ኀበ አንብቦ ትእዛዛት አምላካውያት። ወአንብብ ዘልፈ ውስተ መጻሕፍቲሆሙ ለማእምራን እንዘ ኢትጸግብ።እስመ ይእቲ ትመርሖ ለልብ። ተጸመድ ላእለ አንብቦ መጻሕፍት እንተ ትከሥት ለከ ፍናተ ዘረቂቅ ንጻሬሁ ወለብሖተ ገድሎሙ ለቅዱሳን። አፈድፍድ ለመጻሕፍት ለብሖቶን። **አንቀጽ** 3፣9 ጸማ ሥጋዊት ወአንብቦ መጻሕፍት አምላካውያት የዐቅብዋ ለንጽሕና። ይትሐደስ ሰብእ በአንብቦ መጻሕፍት ዘወትር እለ ይወስዳ መንገለ ሰናያት። **አንቀጽ** 10፣1 እስመ ነጽሮ ዘዘልፍ ውስተ መጻሕፍት ቅዱሳት ይመልዓ ለነፍስ አንክሮተ ዘኢይትነገር ወትፍሥሕተ አምላካዌ።

ትሩፋት፣አርምሞ

አንቀጽ 1፣1 ትሩፋተ ሥጋ ከትሩፋተ ነፍስ ይቀድማል። ከትሩፋት አንዱ ሞትን ማሰብ ነው። **አንቀጽ 1፣4** አፍቅራ ለአርምሞ ፈድፋደ። **አንቀጽ 1፣11** ሁለት አኃው ወደ አባ እንጦንስ ሲሄዱ በመርከብ ተጭኖ አንድ ፍጹም ወደ እርሱ የሚሄድ አገኙ። በመርከብ ሆነው ዜና አበውን ነገረ መጻሕፍትን የሰሩትን ስራ እየተጫወቱ ሲሄዱ እየሰማ ዝም ብሎ ይሄዳል። ከአባ እንጦንስ በደረሱ ጊዜ መልካም ሽማግሌ አግኝታችኋል አላቸው። እርሱንም እኒህ አብረውህ ያሉት ደጋግ ናቸው ብሎ ጠየቀው። ደጋግስ ነበሩ ነገር ግን ለአንደበታቸው መዝጊያ የለውም ብሎታል። **አንቀጽ 4፣6** አርምሞ ይእቲ ጥንተ ንጽሕናሃ ለነፍስ። **አንቀጽ 19፣1** ወጽሙና እሙ ለቅድስና ይእቲ። የነፍስ ክብር ሰይጣን ከሚያመጣው መከራ ይገኛል። **አንቀጽ 21፣1** አርምሞ ከበዓት ተከቶ ከሰው ተለይቶ ዝም ማለት ነው። **አንቀጽ 34፣1** አርምሞ የአእምሮ መንፈሳዊ መገኛ ናት። አእምሮ መንፈሳዊም በትእግስት ይበዛል።

ትእግስት

አንቀጽ 1፣1 ተዐገሥ ሶበ ይሣለቁከ ወይዘነጉጉከ በፈቃድ ኄርት በእንተ ኂሩት። ከመ ትርከብ ሞገሠ በጎበ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት። ኩሎ ቃለ ክቡደ ዘይትኤገሥ ሰብእ በአእምሮ ዘእንበለ ይጸእ እምኔሁ ቃለ ትእቢት ወተዋሥኦ በውእቱ ጊዜ ይትወደይ ዲበ ርእሱ አክሊለ ሦክ ወብዑዕ ውእቱ። ጌታ ደስ ብሎን መታገሥ እንዲገባን ነግሮናል። **አንቀጽ 1፣11** ዘአልቦቱ ትእግስት ይመስል ሀገረ ዘአልባቲ ቅጽር።

መከበርን መጥላት፣ ትሕትናን መያዝ

አንቀጽ 1፣1 ዘይጎይይ እም ተከብሮ በአእምሮቱ ዝንቱሰ ናሁ አሠነያ ለነፍሱ ለተድላ ዓለም ዘሀለዋ ትምጻእ። **አንቀጽ 1፣4** ዘያፈቅር አልባሰ ጽዕድዋተ ኢይትከሀሎ ከመ ያጥሪ ሕሊናተ ትሑታተ። አቦ አቦ መባልን ቀልብ ማግኘትን የሚወድ ትሑት ሕሊናን ገንዘብ ማድረግ አይችልም። ለትሕትናሰ ይተልዎ ተጸምዶ ወትእግሥት። ለውዳሴ ከንቱሰ ይትለዐካ ዝሙት። **አንቀጽ 1፣6** ተጸነስ ከመ ትተሐት። ጉየይ እም ውዳሴ ከንቱ ከመ ትክበር። **አንቀጽ 3፣8** ውዳሴ ከንቱ የዝሙት ምክንያት ነው።

ፍቅረ ንዋይ

አንቀጽ 1፣1 ኢይምሰልከ ኦ ፍቁር ከመ አጥርዮ ወርቅ ወብሩር ባሕቲቱ ፍቅረ ጥሪት አላ ኩሉ ዘይሰቀል ቦቱ ፍትወታቲከ።

ተዐቅቦ፣ ትጋት፣ ተግባረ እድ፣ ፈሊጥ/እውቀት

አንቀጽ 1፣4 ተዐቀብ እም ንዑሳት ከመ ኢትደቅ ውስተ ዓቢያት። ኢትኩን ልህለሀ በግብርከ ከመ ኢትጎፈር ሶበ ትነብር ማዕከለ አዕርክቲከ። ኢተሀሉ ዘእንበለ ስንቅ ከመ ኢይጎድጉከ አዕርክቲከ ባሕቲተከ ውስተ ፍኖት። ወኩሎ ዘትገብር ግበር በአእምሮ። **አንቀጽ 3፣14** ጎድግ ተስፋሃ ለዛቲ ሕይወት ዘይእዜ ከመ ዘበጽሐ ጊዜሁ። ወኢይማዕከ ግሙራ ሀሌት። ርጉም

ውእቱ ኩሉ ዘይገብር ግብረ እግዚአብሔር በሀኬት። **አንቀጽ 6፣1** እስመ ሰይጣን ኢይትከሀሎ ይቅረብ ኀበ ብእሲ ለእመ ኢተሀከየ።

መንፈሰ ዝሙት

አንቀጽ 1፣6 አባ መርትያኖስ ከዋለበት ወደ በዓቱ ሲመለስ ዘማት ተሰብስበው አይተው ይህ መነኩሴ ኃያል ነው የሚያስተው የለም አሉ። አንዲቱ እኔ ባስተውስ ባታስችውስ ተወራርደው ሲመሽ ከደጅ ቁማ ደጅ ጸፋች። ምንድን ነሽ አላት ከሩቅ ሀገር የመጣሁ የእግዚአብሔር እንግዳ የምጠጋበት አጥቼ አውሬ ያጣላኛል ወንበዴ ይቀጠቅጠኛል ብየ ቁሜያለሁ አለችው። ያወጣ ያወርድ ጀመር ብትገባም ጾር ይነሳብኛል አይሆንም ብላት ነግደ ኮንኩ ብሎ ይፈርድብኛል ከሚፈርድብኝ እታገሠዋለሁ ብሎ አስገባት። እሳቱን አነደደላት ተቀመጠች እርሱ ጸሎቱን ያዘ። ሰውራ ይዛለችና የምትቀባውን ትቀባ የምታጤሰውን ታጤስ ጀመረች። እግሩን ከእሳት ጨመረው። የእርሷን መዓዛ እስኪያጠፋው።ከዚህ ሁሉ ያደረስኩት እኔ ነኝ አባቴ አላበጀሁም ማረኝ ብላ ንሥሓ ገብታለች። አመንኩሳት እርሱ በዓቱን ለቆላት ሄዷል። አንድም ገልጣ እንተኛ አለችው ከእሳቱ አንጥፊ አላት ይህማ እሳቱ ይፈጅን የለምን አለችው። የዚህን ዓለም እሳት ካልቻልነው የወዲያኛውን እንደምን እንችለዋለን አላት። ነገሩን አይታ አላበጀሁም ማረኝ ብላ ንሥሓ ገብታለች። **አንቀጽ 4፣5** ወአብዝኖ ንዋም ያፈደፍዶ ለዝሙት። **አንቀጽ 21፣2** የዝሙት መፍትሔ ብዙ አለመብላት አለመጠጣት የሴት መልክ አለማየት ነው።

ተጋድሎ፣ ትሕትና፣ ስግደት

አንቀጽ 1፣8 ወይኩን ንዋየ ሐቅልከ አንብዕ ወጾም ወትረ። **አንቀጽ 1፣11** እስመ ምሥጢራት ይትከሠታ ለትሑታን። **አንቀጽ 1፣13** አውትር ሰጊደ ወአስተብርኮ በአብራኪከ። **አንቀጽ 2፣1** ይቅርታን ታገኝ ዘንድ መጽውት። **አንቀጽ 2፣11** ግድፍ ክብረከ ወትሬኢ ክብረ እግዚአብሔር። ኢትጎሥሥ ከመ ያክብሩከ ጽልኣ ለክብር ከመ ትክበር ወኢታፍቅራ ከመ ኢትጎሥር። **አንቀጽ 3፣6** እውነተኛ ትሑት በበደሉት ጊዜ የማያዝን ነው። ቢሰድቡት አሁን ሆኜ ነው ብሎ ስድቡን ለማስቀረት ምክንያት የማይሰጥ ትሑት ነው። ቦ እም ሰብእ እለ ሰመዩ ርእሶሙ በፈቃዶሙ ዘማውያነ እንዘ ርኁቃን እሙንቱ እምገቢረ ዝሙት። እንደ አባ መቃርስ ከመንደር በአጠገብ ተባሕትዎ ይዞ ይኖራል። አንድ ድንግል ነበረች ሰይጣን አሳታት በዝሙት ጸነሰች ከማን ፀነሰሽው አሏት ከአባ መቃርስ አለቻቸው መጥተው ደበደቡት እየሰራህ ስጥ አሉት። እርሱም መቃሪ ልጅ ወለድሽ ምን ያሳርፍሻል እያለ ሌሊትም ቀንም ሰሌን እየሰራ ዕንቅብ እየሰፋ ሲሰጥ የምትወልድበት ቀን ደረሰ ምጥ ተያዘች ተጨነቀች። ያን መነኩሴ ባልሰራው ስራ ነው የተናገርኩት የጸነስኩት ከሌላ ነው አለቻቸው። ይቅር በለን እንላለን ብለው ቢሄዱ በዓቱን ለቆ ሄዶ አግኝተውታል። ወቦ እለ ይትሜሰሉ አብዳን ከመ ኢያክብርዎሙ ሰብእ በእንተ ስነ ሐረቶሙ ክብርት። **አንቀጽ 3፣12** አኮቴት ወትሕትና ትሬስዮ ለሰብእ መልአከ ዘበምድር። **አንቀጽ 28፣1** ክፉ ሕሊና ሆኖ የማይጎዳ የለም በጎ ሕሊና ሆኖም ክብርን የማያሰጥ የለም። **አንቀጽ 32፣3** እስመ ትውልድ ትሑታን ፍቁራን በኀበ እግዚአብሔር ከመ ማህበረ ሱራፌል። ማንንም አትንቀፍ ይልቁንም ክፉ ሰዎችን ስለክፉ ስራቸው አትንቀፋቸው። ሐሜትን አንውደዳት። **አንቀጽ 33፣2** ኃጥዐን የምትንቀው እንደኔ ጻድቅ ካልሆነ ብለህ ነውን?

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ ፍርሀት

አንቀጽ 2፣1 ለዘያፈቅር ሥምረቶ ለእግዚአብሔር ቦቱ መላእክት ሰማያውያን እለ ይመርሕዎ። ኢትትአመን ከመ ጽኑዕ አንተ። ወኢትትአመን በኃይልከ ወበአእምሮትከ ከመ ኢይንዓውከ ጸላኢ። ኢተሐሊ ከመ ምንትኒ ዘውስተ ዝንቱ ዓለም ዘኢይትዌለጥ። **አንቀጽ 2፣3** አልእል ንጻሬከ ኀበ እግዚአብሔር። **አንቀጽ 2፣4** ምእመናን በጌታ አምነው ከአጋንንት ጋራ ቢዋጉ መላእክት ይረዷቸዋል። ወመላእክትኒ ይሜህርሙ ዘመፍትው ሎሙ ይግበርዎ። ወአሐደ ጊዜ ይመርሕዎሙ ፍኖተ ሶበ የዐይሉ። ወአሐደ ጊዜ ያድኅንዎሙ እመከራት ዘይወድቁ ባቲ። ወይሁብዎሙ ጥበዐተ ወመዊዐ ወኑሃዜ። ቦ አመ ያመጽኡ ሎሙ ኅብስተ። **አንቀጽ 2፣5** ለእመ ኮንከ ተአምን ከመ እግዚአብሔር ልዑል ይሔሊ በእንቲአከ ወይርዕያ ለሕይወትከ ለምንትኬ ትገድፍ ሕሊናከ ላእለ ምግባር ሥጋዊ ዘየኀልፍ። ግድፍ ላእለ እግዚአብሔር ሕሊናከ። **አንቀጽ 20፣5** ፈሪ ሰው በሁለት ደዌ እንደተያዘ ይታወቃል አንዱ የሃይማኖት ሕጸጽ ነው እግዚአብሔር ያድነኛል አለማለት ነው። አንዱ ሥጋን መውደድ ነው።

ነቢብ፣ መከራ፣ ንጽሐ ነፍስ ወሥጋ

አንቀጽ 2፣3 አጥሪ ከናፍረ ጥዑማተ። የለዘበ የለዘበ ነገር ተናገር። **አንቀጽ 2፣7** እግዚአብሔር ያመጽእ ደዌ በእንተ ጥዒናሃ ለነፍስ። መከራን እግዚአብሔር ለአንተ ረብሕ ጥቅም ልትሆን አዘዛት። **አንቀጽ 2፣8** አእኩቶ ወትሕትና ይትወለድ እመከራ። ማኒ ፋርሳዊ የሚባል መናፍቅ ጸራቅሊጦስ ነኝ ብሎ ተነስቶ ነበር። **አንቀጽ 2፣9** መከራት ካልመጡብህ አምላክ ነኝ ወደ ማለት ትደርሳለህ። ከምጥ በኋላ እናቱን ደስ የሚያሰኝ ልጅ እንዲገኝ ከመከራ በኋላም ጸጋ ይገኛል። አባት ለልጁ እንዲያዝን ክርስቶስም በትሩፋት ለደከመ ሰውነት ያዝናል። **አንቀጽ 22፣1** መከራ ሳይቀበል ጸጋ ለአንዱስ እንኳ አይሰጥም። **አንቀጽ 24፣1** ንጽሐ ነፍስ ከሐልዮ ኃጢአት መለየት ነው። ንጽሐ ሥጋ የሚባለው በሥጋ ከሚሰራ ኃጢአት መንጻት ነው።

ለሰው ማዘን እንጂ በሰው አለመፍረድ

አንቀጽ 2፣13 አንዱ ጸዋሚ ተሐራሚ ዝኑሐዊ ነው አንዱ ሕጻን መናኝ ነው ጾር ተነሳበት ይሆንልኛል ብየ ነበር የማይሆንልኝ ሆነ አለው። አንተ ኀርቱም የእንጦንስን የመቃርስን ቆብ ተሸክመህ እንዲህ ትላለህ አለው። ብዙ ጊዜ ተመላልሶ እንዲህ አለው። አንድ ቀን ግን ከአባ እገሌም ዘንድ ከቁጣ በቀር ያገኘሁት የለ ብሎ ሲሄድ የዋህ ጳውሊ በጸጋ ተገልጦለት ከመንገድ ቆየው የት ትሄዳለህ አለው። የሆነውን ሁሉ ነገረው። ከዚያ የዚያን ጦር ወደ ባሕታዊው አሳደረበት። መቋሚያውን ነጥቆ ደጁን ከፍቶ እየሮጠ ደረሰ እጁን ያዘውና ከሁላችንም ጦሩን ያጥፋልን ብሎ አቡነ ዘበሰማያት ደግሞላቸዋል።

ጸሎት፣ ጾም

አንቀጽ 3፣9 ጸሎት ዘወትር ያጸንዕ በውስተ ልብ ፍርሀተ እግዚአብሔር ወተስፋ። **አንቀጽ 4፣1** ጸሎት ወአስተብቁዖት ወጾም ይእቲ ፍኖት ቀዳሚት ከመ ታቅርበነ ኀበ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት። **አንቀጽ 4፣6** የሥራ ሁሉ መጀመሪያ በጾም መድከም ነው። ጾም የወንጌል ስራ

መጀመሪያ ናት። እማ ለጸሎት ወነቅዓ ለአንብዕ ወመምህራ ለአርምሞ። **አንቀጽ 6፣1** የረድኤት ምክንያት የምትሆን ጸሎት ናት። አንድም በትሩፋት መድከም ትሕትና ናቸው። **አንቀጽ 10፣1** አገብራ ለነፍስከ ላእለ አውትሮ ጸሎት ወትመጽአከ ረድኤት እንዘ ኢተአምር አንተ። **አንቀጽ 11፣1** አስተብቁዖ ለእግዚአብሔር በጸሎት ዘባቲ ጻማ። **አንቀጽ 28፣3** ወዳጄ ከጸሎት ተለይተህ ክቡር እግዚአብሔርን እርዳኝ ሳትል መጻሕፍትን እተረጉማለሁ አትበል። እመን ከመ ጸሎት መራኑተ ፍካሬያት አማናውያት እለ ልኩዓት ውስተ መጻሕፍት አምላካውያት።

ዓለም

አንቀጽ 4፣3 ምንት ይእቲ ዓለም። ዓለምሰ ዘማ ይእቲ ዘወትር ወሰሐበቶሙ በፍትወተ ስና ለእለ ይኔጽሩ ኀቤሃ። በሚሞቱበት ቀን ግን አሜሃ የአምሩ ከመ መስሐቲት ይእቲ። **አንቀጽ 9፣1** አእምር ከመ ዛቲ ሕይወት ንስቲት ይእቲ ወፍጡን ኀልፊተ ዚአሃ። **አንቀጽ 13፣2** ዝልፋ ወትረ ለነፍስከ ኦ እጉ ወበላ ናሁ በጽሐ ተኃልፎትኪ እም ሥጋ ለምንት ትትፈሥሒ በዘአንቲ ሀለውኪ ዮም ቦቱ ወተነድጊዮ ዘትዴለዊ ለርእየቱ ኅዳጠ ዘመነ ወተኃጥዒዮ እስከ ለዓለም። አጽምዒ ነበ ዘቅድሜኪ ወሐልዩ ዘገበርኪ ምንት ውእቱ ወምስለ መኑ አኀለፍኪ መዋእለ ሕይወትኪ። ወለመኑ ዘአስተፍሣሕኪዮ በተጋድሎትኪ ከመ ይጸእእ ለቀበላኪ በጊዜ ጸአትኪ። ወበእንተ ምንት ጻመውኪ ወተመንደብኪ ኦ ነፍስ። የኀልፊት ምክንያት ካለበት ደስታ ተጠበቅ። **አንቀጽ 20፣3** አብዳንሰ ያከብርዋ ለንስቲት ዕረፍት ወኃላፊት እምነ መንግሥት ክብርት።

ሰይጣን፣ ልማድ

አንቀጽ 6፣1 እስመ ጸላዒነ መስተቃርን በእንተ ቅንዐቱ የሐውር በቅጥነት። እግዚአብሔር ይኤዝዝ ከመንዳደቆ ለጸላዒ ዘእንበለ ፍርሀት ወቁረተ ሕሊና። እግዚአብሔር ሳንፈራ ሳንባረድ ጠላታችንን እንገጥመው ዘንድ ያዛል። **አንቀጽ 6፣1** ሰይጣን ሰውን ድል ለመንሳት ጦሩን ይለዋውጣል። **አንቀጽ 32፣3** ፍራህ እምልማድ ፈድፋደ እምነ ጸላእት ከሰይጣን ይልቅ ልማድን ፍራ።

ንሥሓ

አንቀጽ 8፣1 እጠገናለሁ ብሎ መሰበር እንዳይመች ንሥሓ እገባለሁ ብሎ ኃጢአትን መስራት አይገባም።ኢናምዕዖ ለእግዚአብሔር በኀሡም ምግባራቲነ። ወኢናርኩስ አባላቲነ።

ዕውቀት

አንቀጽ 27፣1 አእምሮሰ ነበ ክልኤ ፍና። ቦ ዘይቀድማ ለሃይማኖት ከሃይማኖት የሚቀድም እውቀት አለ። ወቦ ዘይትወለድ እምኔሃ ከሃይማኖት የሚገኝ አእምሮ አለ። ባሕርያችን ሳይማር ክፉውን ከበጎ ለይቶ በአእምሮ ጠባይእ ያውቃል። በትምህርት የሚሰፋ አእምሮ መንፈሳዊ ነው። አእምሮ መንፈሳዊ የተባለችው ረቂቅ ምስጢርን ማወቅ ነው። **አንቀጽ 29፣1** አእምሮ መንፈሳዊን ሰይጣን አብዝቶ ይጠላዋል። አእምሮ መንፈሳዊ በሰው ልቡና ጸንቶ ቢኖር ሰው ይህን ዓለም በማሰብ እንዳይኖር ያውቃልና። የሰይጣንም ተንኮል ወደ ልቡና አይቀርብምና።

አእምሮ መንፈሳዊ ያለው ሰው ይህን ዓለም አያስብም። **አንቀጽ 30፣1** አእምሮ መንፈሳዊ የሚሰጥ ሰው ትሩፋት ቢሰራ ነው። በጎ መጋደልን ቢጋደል ነው። ንሥሓ ቢገባ ነው። የመንፈሳዊ ተመስጦ መጀመሪያ አእምሮ መንፈሳዊ ነው። የፍጹም ምስጢርም መገኛ ተመስጦ ነው። ሀብታት ምስጢራት በተመስጦ ይሰጣሉ።

ፍቅር

አንቀጽ 28፣1 አርክ ዘይጌሥጽ በጎቡዕ ዐቃቤ ሥራይ ጠቢብ ውእቱ። ወንድሙን በአደባባይ የነቀፈ ግን ጎዘን ያጸናበታል። ወዘያስተኃፍሮ በገጸ አዕርክቲሁ ናሁ አመረ ጎበ ኃይለ ቅንዓቱ። **አንቀጽ 32፣3** የተድላ የደስታ ወደብ ፍቅር ሆይ አንችን ያገኘ ሰው ንዑድ ክቡር ነው።

ፊልክስዩስ

ይሩማሊስ ጳላድዮስ የሚባሉ ሁለት ሊቃውንት መነኮሳት አገር ለአገር እየዞሩ የአበውን ዜና ያሉትን ከቃላቸው የሞቱትን ከአርድእቶቻቸው እየጠየቁ ጽፈዋል። መጽሐፉም መጽሐፈ ገነት ይባላል። ፊልክስዩስ በአጼ ድልነዓድ ጊዜ መጥቷል ሰይፈ አርእድም ይላሉ። ንዑስ ሰላማ ብርሃነ አዜብ ከግብረ ሕማማት ጋር መልሶታል። አረጋዊ በአጼ ልብነ ድንግል ጊዜ ተመልሷል። የማር ይሥሐቅ ጊዜው አልታወቀም። አንድም ታሪክ አገኘን ብለው በአጼ ገላውዴዎስ የሚሉ አሉ። ሰሊክ ዘደብረ ሊባኖስ ከአቡሻክር ጋር ተርጉሞታል። ማር ይሥሐቅ ጦራቸውን ግብራቸውን ይናገራል ፊልክስዩስ ዜናቸውን ታሪካቸውን ይናገራል። ፊልክስዩስ ገብረ ክርስቶስ ማለት ነው። ቅኔ ማለት የተስእሎና የተሰጥዖ ማቅኛ ነው። የተዛባውን ንባብና ምስጢር ለማቅናት መምህራን ከመጽሐፈ ገነት እያመጡ እንደ ጥቅስ በቃል ይናገሩታል። ሥርዋጽ ማቅኛ ቀድሞ ያልነበረ ኋላ የተጨመረ እንደ ቅኔ ያለ ነው። ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ከአባ ኤልያስ እየሄደ ምክር ይቀበል ነበር። ሥጋ አይበላም የሚሉ ሰዎች ስለነበሩ እንደሚበላ ለማስረዳት በግብጽ ያሉ ገዳማት ሁሉ ከዓመት አንድ ጊዜ ሥጋ ይበሉ ዘንድ ታዘዋል።

ብሕትውና፣ ምንኩስና

ሥርዓተ ብሕትውና በጳውሊ ሥርዓተ ምንኩስና በእንጦኒ ተጀምሯል። የጳውሊ አባቱ ባዕለ ጸጋ ነበረ። ሲሞት ገንዘቡን በታላቅ ወንድሙ እጅ አድርጎ ኋላ አካለ መጠን ሲደርስ ከፍለህ ስጠው ብሎት ተናዞ አረፈ። አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ የአባቱን ገንዘብ ከፍለህ ስጠኝ አለው። ግድማ ካልከኝ ብሎ ብዙውን አስቀርቶ ጥቂቱን መልካሙን አስቀርቶ ተራ ተራውን ሰጠው። እርሱም በዚህ ተናዶ ዳኛ አወጣለሁ ብሎ ሲሄድ እንደ አባቱ ያለ ባለጸጋ ሞቶ እኩሉ ሲያለቅሱ እኩሉ ሲፈቱ አገኘ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀ ባለጸጋ ሞቶ ይለቀሳል ብለው ነገሩት ከእነዚያ አንዱን እስኪ ምከረኝ ከወንድሜ ጋራ በገንዘብ ተጣልቼ ዳኛ አወጣለሁ ብየ መጥቼ ነበረ ቢለው። አባትህ ባለጸጋ ነበረ ጥሎት ሞተ አንተስ ብታመጣው ነግ ጥለኸው ትሞት የለምን ተወው ይቅርብህ አለው። እውነትህን እንጂ ነው ብሎ ትቶት ተመልሷል። የአባቱን ወንጌል ዮሐንስ ብቻ ይዞ ሄደ። ጌታም ለፈተና ሦስት ቀን ምግብ ነሳው በሦስተኛው መንፈቀ ጎብስት ወርዶለት አናብስት አናምርት አክይስት አቃርብት ካሉበት ነቅዐ ማይ ልምላሜ ዕፅ ከሌለበት

ተክል ከማይገኝበት ከጽኑ በረሀ ሄደ። **እንጦንስ** ደግሞ ቅዳሴ ለመስማት ከቤተክርስቲያን ገብቶ ቆመ ቂሱ ወንጌል ብሎ ወጥቶ ሲያነብ እመሰ ፈቀድከ ትኩን ፍጹመ ሚጥ ኩሎ ንዋየከ ወሀብ ለነዳያን ወነዓ ትልወኒ ያለውን ቃል ሰማ። ይህ አዋጅ የተነገረ ለእኔ ነው ብሎ እጎት ነበረችው ከደብረ ደናግል አስጠግቶ ሄዶ ፊት ከነበረባት ዋሻ ገብቶ ተቀመጠ። ከአለታት አንድ ቀን ወለተ አረሚ ሰናይተ ላሕይ ይላታል ከደንገጥሮቿ ጋር በቀትር ጊዜ መጥታ ከዛፉ እግር ከውሃው ዳር አረፈች። ፊት እርሷን አጠቧት ኋላ እርስ በእርሳቸው ይተጣጠቡ ጀመር። እርሱም እርቃናቸውን እንዳያይ ዓይነ ሥጋውን ወደ ምድር ዓይነ ነፍሱን ወደ ሰማይ አድርጎ ሲጸልይ ቆየ ያበቃሉ ሲል የማያበቁለት ሆነ ኋላ ደግሞ ቆይተው ነገረ ኃፊር እያነሱ ይጨዋወቱ ጀመር ምነው እንግዲህማ አይበቃችሁም አትሄዱምን አላቸው። ኦ እንጦኒ ኦ እንጦኒ ለእመ ኮንከ መነኮሰ ሐር ኀበ ደብር አለችው። ጌታ ለአበው ትምህርት የሚሆነውን ነገር በማናቸውም ባልበቃ ሰው አድሮ መናገር ልማዱ ነው። እንጦንስም ወደ በረሃ ሄደ። ሰይጣናትም ፈተና አበዙበት እርሱም በትሕትና ይዋጋቸዋል። መልአኩ የሰሌን ቆብ ደፍቶ የሰሌን መቋረፊያ ለብሶ የሰሌን መታጠቂያ ታጥቆ ብትን ሰሌን ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ቆመ። ወዲያው ጸልዮ ሦስት ጊዜ ሰገደ። ከዚያ ይህን ብትን ሰሌን ይታታ ጀመር። ሠለስት ሲሆን እንደገና ተነስቶ እንዲህ አደረገ የቀሩትንም የሰዓቱንም የሠርኩንም እንደዚሁ አድርጎ አሳየው በሠርክ ኦ እንጦኒ ከመ ከመዝ ግበር ወለእመ ገበርከ ዘንተ ትድኅን እም ጸብአ አጋንንት አለው። የመነኩሴ ቆቡ የአክሊለ ሦክ ቀሚሱ የከለሜዳ ቅናቱ የሐብል ሥጋ ማርያም የሥጋ ማርያም ምሳሌ ነው። አስኬማ የሰውነት ምሳሌ ነው። አብርሃም ይሥሐቅን በወለደ ጊዜ ኮሎዶጎሞርን ድል በነሳ ጊዜ ሰሌን ይዞ አመስግኗል። ዮዲት ሖለሆርኒስን በገደለች ጊዜ ይህን ይዘው አመስግነዋል። ኢሳይያስም ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ባለ ጊዜ ይህን ይዞ አመስግኗል። አውሎግዮን ማለት ስለ እግዚአብሔር ብለህ ክፈትልኝ ማለት ነው። እንጦንስ ወደ እርሱ ሲመጣ ለጳውሊ ሙሉ ኅብስት ወረደለት። ጳውሊ አራቱን ወንጌል ሲጸልይ አሥር ጣቶቹ ይበሩ ነበር። ለጳውሊ ነጭና ጥቁር የተቀላቀለባቸው አርጋብ ታዩት እኒህም ጽድቅና ኃጢአት እየቀላቀሉ የሚሰሩ ናቸው። በኋላም ሙሉ በሙሉ ጥቁር አርጋቦችን አየ እንጦንስም ምንድን ናቸው ቢለው በኋላ የሚነሱ ኀሣሥያነ ሚመት መፍቀርያነ ንዋይ እለ ይሠርዑ በነግህ ማዕደ ምስለ መኳንንት ይላቸዋል። **ተስእሎ** 1 ሥርዓተ ኤልያስ ወማቴዎስ ይኄይስ እም ሥርዓተ አብርሃም ወዘኬዎስ። አኮ በኅሊና አላ በሥርዓት። እስመ **ሥርዓተ ምንኩስና** በኀበ አበው ለኀበ ሠለስቱ ክፍል። ኀድዓት ምስለ ተጋድሎ ወደዌ ምስለ አኮቴት ወተልእኮ ምስለ ፍሥሓ ወጥብዓት። **ደዌ ዘበአኮቴት** እንደ ኢዮብ ነው። **ረድእ ዘበጥብዓት** ይምትር ፈቃዶ ወይግበር ሥምረቶ ለዘይትለአኮ። የራሱን ፈቃድ ትቶ የሚረዳውን ሰው ፈቃድ የሚፈጽም ነው። በአፍቅሮ ወፍሥሓ ወአኮ በመንኖ ወአንሳርጉሮ አላ ይትለአክ በእንተ ክርስቶስ ወአኮ በእንተ ሰብእ። መነኮሳት ስለ እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያስቡት አካላቸውን ሳይቀር ለእግዚአብሔር ሰጥተዋልና። እስመ ተቃወሙ ፈቃዳቲሆሙ ከመ ይፈጽሙ ሥምረቶ ለእግዚአብሔር።ወገደፉ ነፍሳቲሆሙ። ወተዐገሡ መናስወ ሰይጣናዊተ በእንተ ቃሉ ዘይቤ ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽልዓ ለነፍሱ ወይጹር መስቀሉ ኩሎ ዕለተ። ለብጹዓዊኒ አርሳንዮስ አበ ነገሥት ጸውዖ እግዚአብሔር እም ሰማይ እንዘ ይብል ኦ አርሳንዮስ ጉየይ እም ሰብእ ወአንተ ተሐየ። **ተስእሎ** 40 ይቤሉ አኃው እስፍንተ ይደልዎ ለእጎ ከመ ይንበር ውስተ ማኅበር ወይባእ በዓተ ብሕትውና ይቤ

መተርጉም የአክሎሙ ሠለስቱ ዓመት፡፡ ለእመሰ ኢኮኑ ምሁራነ ሰናይ ሎሙ ይትዐደው ሰመንተ ወአሠርተ ዓመታተ፡፡ **ተስእሎ 54** ይቤ እንጦንዮስ በከመ ዓሣ ሶበ ወጽአ እማይ ይመውት ከማሁ መነኮስኒ እም ከመ ኅንደያ እምኔቱ ወበዓቱ ኀበ ካልእ ይጠፍዕ፡፡ ወእመሰ ኅንደያ መነኮስ ውስተ ዓለም ይትመተር ተዘክሮ እግዚአብሔር እምኔሁ በእንተ ርእየቱ ወተናግሮቱ ምስለ ሰብእ ወያፈቅር ዕረፍተ ወይትሐወክ ልቡ በፍትወት፡፡ **ተስእሎ 55** በአምጣነ ሀሎ መነኮስ ዘልፈ ውስተ በዓቱ ይመውዕ ውእቱ ለለአሐዱ እም ሕማማት በጸጋ ረድኤቱ ለእግዚእነ፡፡

ተግባረ እድ

ተስእሎ 1 ሀለው ክልኤቱ አኃው ውሉደ ብእሲ ነጋዲ ወሶበ አእረፈ አቡሆሙ ተካፈሉ ርስቶ ወዘረወ አሐዱ እምኔሆሙ መክፈልቶ ላእለ አብያተ ክርስቲያናት ወምኔታት ወምስኪናን ወመፍቅዳውያን ወተምህረ ኪነ ዕድ ለሲሳየ ዕለቱ፡፡ ወአዝለፈ ኅድአተ ወጸሎተ ወጾመ፡፡ ኅድአት የሚለው ባሕታውያን ከዘጉ በኋላ በመስኮተ ቤት ዘልቆ ብርሃነ ፀሐይ አለማየት ቆብ ቅናት ቀሚስ አለማውለቅ ገላ አለመዳሰስ ነው፡፡ ተባሕትዎ ያዝኩ ብሎ ከዋሻ ቢከተቱ ሥራ ካልሰሩ እንደሸኾኩ መወተፍ ነው፡፡

ጸሎት

ጸሎተ ሥጋ በአንሣሕስሑ ከናፍር ነው፡፡ ጸሎተ ነፍስ ያለ አንሣሕሥሑ ከናፍር የሚጸለይ ነው፡፡ ጸሎተ ልቡና ካልደረሱበት አይታወቅም፡፡ **ተስእሎ 39** አባ አርሳንዮስ ፀሐይ ጫንቃውን ስትመታው የቆመ ዙራ ተመልሳ ግንባሩን እስክትመታው ድረስ ቁሞ አድሮ ንሣእ መክፈልተከ ኦ ሀካይ ብሎ ከድካሙ ያርፍ ነበር፡፡ **ተስእሎ 83** አርሳንዮስ በጸሎት ጊዜ ረቂቅ ምሥጢር በማየት ልቡናው ይራቀቅ ነበር፡፡ **ተስእሎ 156** ወዘኒ ይጼሊ በኩሉ ጊዜ ያስተፈሥሑ ለእግዚአብሔር፡፡

ጾም

ጾም የሚለው ውሎ ውሎ መብላት ሲርብ መተው ምግብ አለማሻሻል ጊዜ አለማለዋወጥ ነው፡፡ **ተስእሎ 62** እስመ በጾም ዘበበዓመት ይሁብ እግዚአብሔር ጸጋ ረድኤት፡፡

ከተርእዮ/ ከንቱ ውዳሴ መራቅ

ተስእሎ 2 ባሕታዊ የሚያደርገው ነገርን በሙሉ ሰው ያመስግነኝ ብሎ አይደለም፡፡ **ተስእሎ 49** ስብሐት የሐስሞሙ ለትሩፋን ፈድፋደ እምዘተርፉ ሕማማት፡፡ ወውእቱ ይወልድ ሎሙ ትዝህርተ፡፡ ወይትወለድ እምከንቱ ውዳሴ ቅንዓት ወተቃሕዖ፡፡ አንድ አሸክር የጌታውን እቃ ጥሎ አስታርቀኝ ብሎ መጣበት ሂድ ይታረቅሀል ብሎ ሰደደው ታረቀ፡፡ ለጌታው ደግሞ ጌታ አለው ያ ተጣልቶት እኔ ስታረቅ የነገረኝ ሰው ነበረ እስኪ ከእርሱ እንሂድ ብሎ ይዞት ሄደ፡፡ አባ ታድራም እንደመጡበት አውቆ በዓቱን ለቆ ከዛፍ ላይ ወጥቶ ቆቡን ከትክሻው ላይ ጥሎ ዕራቁቱን ሆኖ ቼ ቼ ሲል ቆያቸው እብድ ነው ብለው ጥለውት ሄዱ ይህን ያደረገው ከንቱ

ውዳሴ እንዳያጠቃው ነው። ርእሰ ሕማማተ ሥጋ አፍቅሮተ ክርስ ውእቱ ወርእሰ ሕማማተ ነፍስኒ አፍቅሮተ ስብሐት ብጡል። ወሶበ ሞዐ ብእሲ እሎንተ አርእስተ ሕማማት ይረክብ ዕረፍታተ።

ጸድቃን

ተስእሎ 3 ሰመዮሙ እግዚእ ለቅዱሳን ውሉደ ብርሃን ወሰመዮሙ ካእበ ለዓለማውያን ውሉደ ዓለም እስመ ይቤ እስመ ውሉደ ዝንቱ ዓለም ይጠበቡ እም ውሉደ ብርሃን። ተስእሎ 149 የጻድቃን ልቡናቸው ከሐልዮ ኃጢአት በተለየ ጊዜ ሕሊናቸው በጸጋ ብርሃን ብሩህ ይሆናል ይሬእዩ መላእክተ ቅዱሳነ ወሰይጣናተ መናፍስተ።

ትዕግስት

ተስእሎ 3 ወተዐገሡ መናስወ ሰይጣናዊተ። ተስእሎ 4 ቀድሞ ፍጹም የነበረ አንድ መነኩሴ ነበረ ወእም ድህረ ውእቱ ተሐየየ በእንተ መድኃኒቱ እስከ ኮነ ውእቱ ይበውእ ኀበ ቤተ ብእሲ ዘስሙ ኢዮብ ወይሰርቅ ዘይረክቦ እም ሲሳዩ ወአእመሮ ቅዱስ ወተዐገሠ በፍሥሓ ወበጊዜ ዕረፍቱ ጸውዖ ወበጊዜሃ ረሰየ የአኀዝ እደዊሁ ወየአምኖን ወያነብሮን ዲበ አዕይንቲሁ ወይቤሎ ኦ እኁየ አንሰ እስእሞን ለእሎን ክልኤ አእዳው ወእሁቦን ጸግዖቶን ላእሌየ እንተ በእንቲአሆን ዘእበውዕ መንግሥተ ሰማያት። ወተናሥሐ እንከ ዝኩ እኁ። ለአባ ኢዮብም 3 አክሊል ወረደለት አንዱ የደዌው አንዱ የትእግስቱ። ተስእሎ 9 ጳውሊ ባለ ሕግ ነበር የመጀመሪያ ሚስቱ በድላው ሳለ ሞተች ደግሞ አገባ ያችም በደለችው እንደምን ቢሉ በላዩ ላይ ባሪያውንም ቢሉ ሎሌውንም ቢሉ ይዛለች ከእለታት በአንዱ ከደጅ ኑሮ ቢገባ ተኝተው አገኛቸው ገልጦ አይቶ አንተ ኩን ላቲ ቡሩክ አንቲኒ ኩኒ ሎቱ ቡርክተ ብሎ መነነ። ተስእሎ 27 ሶበ ፈቀደ ሰይጣን ከመ ይንፍቅ ማዕከለ ክልኤቱ አኃው ዘበሥጋ ወሶበ አኀተወ ማኀቶተ እኁ ዘይንእስ አጥፍዐ ወአውደቆ ሰይጣን ሎቱኒ ወማኀቶተሂ ወዘበጦ እንከ እኁሁ ላዕለ መልታሕቱ ወገብረ ሎቱ ስግደተ ወይቤ እኁየ አንኀ መንፈሰከ ላዕሌየ ወአንሰ አኀትዎ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ትእግስቶ ለደቂቅ ወትሕትናሁ አዘዞ እግዚአብሔር ለመልአከ ውእቱ ደቂቅ ወአሠሮ እንከ ለዝኩ ሰይጣን በውስተ በዓት ወሣቀዮ እስከ ሳኒታሁ። ተስእሎ 56 አባ ታድራ ወአባ ሉቃ አዝለፉ ኀምሳ ዓመተ እንዘ ይጸፍዑ ሕሊናቲሆሙ እስመ ኮኑ ይፈቅዱ ፈሊሰ እመካኖሙ ወኮኑ ይብሉ እስከ ክረምት ነሐውር ሶበኒ ይበጽሕ ክረምት ይብሉ እስከ ሐጋይ ነሐውር እስመ አበው ይትዋነይዎሙ ለሕሊናተ ሰይጣናት። ተስእሎ 58 ቅኔ፡- አሐዱ እኁ ተናገሮ ለአድልፍዮስ ቃለ ጽርፈት ወኢያውስአ ወሶበ ፈጸመ ይቤሎ ሞገሠ ቃል ይትከዐው እም ከናፍሪከ። ለእመ ተዐገሥነ ከመ ክርስቶስ ንሕነሂ ንነግሥ ምስሌሁ። ተስእሎ 59 ሶበ ዘርከይዎ አኃው ለአባ መሴ ተብህለ ሎቱ ኢተሀከከኑ ልብከ ወይቤ ተሀከከ ወባሕቱ ኢተናገርኩ።

ፍቅር

ተስእሎ 3 አፍቅሮ እግዚአብሔር ይኄይስ እም አፍቅሮ ፍጡራን። የዓለማውያን ፍቅራቸው

ሁለት ወገን ናት አንድም የተከፈለች ናት በእንተ አንስቲያሆሙ ወውሉዶሙ። ለባሕታዊሰ ሎቱ አሐቲ አፍቅሮት ወውእቱኬ ክርስቶስ። ዓለማውያን ግን የልጅ ወዳጅ ፍቅር ይፈርስብናል ብለው በብዙ ወገን ይፈራሉ። ባሕታዊ ግን የአንድ ጌታ ፍቅር ብቻ ይፈርስብኛል ብሎ ይፈራል። **ተስእሎ 74** ሁሉን መውደድ ማለት ጻድቃንን በበጎ ስራቸው መውደድ ነው። ለኃጥዓን ከፍዳ ይድኑ ዘንድ እግዚአብሔርን መለመን ነው። **ተስእሎ 105** ይቤሉ አኃው እፎ ይክል ሰብእ ኢያንውር እጎዋሁ በውስተ ልቡ ወአውስአ አረጋዊ ወይቤ ለእመ ኢየሐስብ በልቡ ከመ ሎቱ ሠለስቱ ዓመት ውስተ መቃብር ኢይክል።

ትሕትና

ተስእሎ 3 ጌታ ለበብኑዳ ታየው ወይቤሎ ሑር ኀበ እገሊት ሀገር ወባእ ኀበ ቤቱ ለሊቅ ወሖረ ወአዘዞ ለሊቀ ሀገር ከመ ይክሥት ሎቱ ሥርዓቶ። ወከሠተ ሎቱ ወይቤሎ እስመ ሊተ ፴ ዓመት እም አመ ተመተርኩ እምነ መጻምርትየ። ወሥልሰ ጊዜያተ አእመርክዋ ወኮኑ ሊተ እምኔሃ ሠለስቱ ውሉድ ወኢገበርኩ ኀሙመ። ወሰብሐ እንከ በብኑዳ ሥርዓቶ ለመኮንን። **ተስእሎ 31** ለእመ ኮንከ ሐዋርያኒ ወታወጽእ ሰይጣናተ ወትገብር ተአምራተ ተዘከር እፎ ወድቀ ይሁዳ ውስተ አፍቅሮ ብሩር። ወለእመ ርኢከ ፈያታዌ አው ቀታሌ በል በአይቱ አአምር ለእመ ኮነ ይበድረኒ በዊአ ኀበ ገነት ከመ ፈያታዊ ዘየማን። ወለእመ ርኢከ ዘማዌ ወኃጥአ በል በአይቱ አአምር ለእመ ኮነ ለዝንቱ ሀለዎ ያፍቅሮ ለክርስቶስ ወይብኪ በእንተ ኃጣውኢሁ ፈድፋደ እምኔየ ወዘይሔሊኬ ከመዝ ለዓለም ኢይወድቅ እም ፍቅረ እግዚእነ። እመሰ ጸነ ኀበ ትዝህርት ይወድቅ እመልእልት። **ተስእሎ 37** ጌታ እንጦንስን ከአስካፍ ሂድ አለው።ይህ አስካፍ የንጉሥ ባለሟል ነበረ ራስ ቢትወደድ ነው ውስጡን ግን ሰቅ ታጥቆ በተባሕትዎ ይኖራል። ከዚያ ቢሄድ ከንጉሥ ቤት ውሎ ሲወጣ ደረሰ ሰራዊቱ ሲጋፋ ሰቁን ቢነኩት ወገቡን ቆርጦት ወደቀ አፍሰው ወስደው ከቤቱ አገቡት ተከትሎ ሄዶ ንገሩልኝ አለ። ነገሩለት ገባ አናወርህ እንደምን ነው ግብርህን ግለጽልኝ አለው። የእኔ ግብር ምን ይጠየቃል እንደምታየኝ የቤተመንግሥት ሰው ነኝ አለ። አይደለም ታዝገፍ መጥቻለሁና ግለጽልኝ አለው። ከዚያ ሰቁን ገለጸለት። አባ እንጦንስም ትሕትና ተምሯል። **ተስእሎ 84** ትሑት ሰው አጋንንትን አይፈራም። በከመ ይቤ ወቅሪስ እስመ ትሑት ይከውን ዘእንበለ ፍርሀት። ወእግዚአብሔር ያገርር ሎቱ ኩሎ። **ተስእሎ 117** እስመ ቅዱስ እንጦንዮስ ይቤ አንሰ ርኢኩ ኩሎ መሣግረ ሰይጣናት ትኩላነ ዲበ ምድር ወገዐረ ወይቤ ወይ ለነ መኑ ዘይድኅን እም ዝንቱ ኩሉ ወተብህለ ሎቱ ትሕትና ያድኅን እምኔሁ ለኩሉ። ይደልወነ ከመ ንትሐት በኩሉ ጊዜ። **ተስእሎ 126** አበው ሰመዩ ትሕትና በአስማት ሰናያን ወእንጦንዮስ ይቤ መርሕቅ ወመድኅን እመሥገርተ ሰይጣን። ወአባ አሞንኒ ሰመዮ ዕበዩ ለሰብእ። ወአባ ታድራኒ ሰመዮ መፍርሔ ሰይጣናት። ወቁልዝማዊኒ ሰመዮ ሰዋስወ ወአንቀጸ መንግሥተ ሰማያት። ወዮሐንስኒ ሰመዮ መርሶ ነፍሳት። **ተስእሎ 170** ኀሥሥ እም ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይጸንከ ትሕትና።

መንፈሰ ዝሙት

ተስእሎ 4 የዝሙት ጾር የተነሳበት አንድ መነኩሴ ነበረ። ወፈተዋ ለወለተ ካህነ ጣዖት ወነሠሠ አውስቦታ እም አቡሃ። ወአውስአ ሰይጣን ለአቡሃ እንዘ ይብል ለእመ ኮነ ዘይክህድ

አስኬማ ዘምንኩስና ወይክህድ ጥምቀቱ ሀቦ ሎቱ። ተስእሎ 7 በጊዜ ይትቃተሎ ዝሙት ለአሞንዮስ ያረስን ሐጺነ በእሳት ወያነብሮ ዲበ አባሉ። ተስእሎ 11 እም ድኅረ ዓመታት ብዙኅ ጸንዐ ላእለ አባ ኤልያስ ተቃተሎ ዝሙት ወወጽአ ገዳመ ወለአከ እግዚአብሔር ኀቤሁ ሠለስተ መላእክተ ወመተሩ እምኔሁ ሕማመ። ተስእሎ 13 ተዘክሮ እግዚአብሔር የተለየውን ልቡና ሰይጣነ ዝሙት ሰይጣነ ቁጣ እጅ ያደርገዋል። ተስእሎ 23 ሰጠቁ መላእክት እስኪቶ ለማር ኤልያስ ሊቀ ምኔት መነኮሳይያት ሶበ ኮነ ምስሌሁ በህየ ፍትወት። አባ ጢሞቴዎስ ከከተማው አጠገብ ገዳም አቅንቶ በዓት አበጅቶ ይኖራል ልብስ ምግብ እየሰጠ የሚረዳው ዓለማዊ ወዳጅ ነበረው። እኅት አለቸው ዘማ ናትና ምነው ተይ አትላትምን አለው አንተ ትመክራት እንደሆነ እንጂ እኔንስ በጅም አትለኝ አለው ይዘኃት ና አለው ይሟት ሄደ ምነው ይህን ነገር አትተይምን አላት። አባቴ ግብሩን ወድጀው መስሎሃልን የማድርበት እንጂ ባጣ ነው አለችው። ይህስ እውነቷን ነው አንተም እርዳት እኔም ሰሌን ሰርቼ እረዳታለሁ ብሎ ሲረዳት ኖረ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ያ ሰው መንገድ ሊሄድ ተነስቶ እኔ እስክመለስ ምግብህን ብታመጣልህስ አለው አይሆንም አለ። እንኪያ ትሞት የለም ባይሆን እያመጣች በአፍኣ እያኖረችልህ ትሂድ አለው። ከዚህ በኋላ እያመጣች በአፍኣ እያኖረችለት ስትሄድ ከዕለታት በአንዱ ድካሙ ካልቀረልኝ ገብቼ በረከት ተቀብየ ብሄድ ምነው አለችው ግቢያ አላት ገባች ተላመዱ መንፈቅ አብረው ኖሩ ኋላ የቀድሞ ክብሩን የኋላ ኃሣሩን አስቦ ሄዶ ከበረሀ ወድቆ ብዙ ዘመን ተጋደለ። ያ ዝሙት ሆኖ የተዋጋው ሰይጣን እንደ እንዝዝ ሆኖ ደቄ አሳደረበት መልአኩ አካሉን ሰንጥቆ አውጥቶ አሳይቶታል። ተስእሎ 91 አንድ አረጋዊ ለብቻው ተባሕትዎ ይዞ ሲኖር አረጀ ማኅበሩ እንግዲህማ ወደኛ መጥተህ እንርዳህ እንጂ አሉት ከሆነስ ትኩስ ምግብ ወደማገኝበት ወደመንደር አስጠጉኝ አላቸው። ከዓለማውያን ወገን አንዱን ምዕመን በነፍስህ ትጠቀማለህ አባታችንን እርዳልን አሉት እሺ ብሎ ከቤቱ ወስደው ሴት ልጅ አለችው እርጂው ብሏት ስትረዳው በእርሷ ተሰነካክሎ ልጅ ወለደ። ተስእሎ 100 መንፈሰ ዝሙት የሚቃወመው ሰው ሴቶችን አይይ አይስማ ወኢይትናገር ምስሌሆን ወኢይዘክሮን። ወአባ ጳኩሚስኒ ሶበ ጸንዐ ላእሌሁ ዝንቱ ተቃትሎት ኮነ ይዌሩ መንፈሶ ዕራቆ ቅድመ በዓተ ዝዕብ። ከጅብ ዋሻ ሄዶ ታዘሽ ከሆነ ወጥተሽ ንከሽው እያለ ዕራቁቱን ይቆም ነበረ። ወነስአ እም አዘቅት ከይሴ ወወደዮ ዲበ አባሉ ታዘሽ እንደሆነ ንደፊው እያለ እባብ ይጠመጥምበት ነበር። ተስእሎ 117 አባ መቃርስ ሰይጣንን አሮጌ ልብስ ለብሶ ቢረሌዎችን ይዞ ሲሄድ ወደ*ት ትሄዳለህ ቢለው ከአባ ማሚጦስ አለ። አባ መቃርስም ወደ ማሚጦስ ሄደ አባ መቃርስ መምጣቱን ከሩቅ ሲያይ ቅርጫት ደፋባት አባ መቃርስም እንደ*ት ነህ ሲለው። ማሚጦስ በአንተ ጸሎት በእግዚአብሔር ቸርነት ጾር ጠፍቶልኛል አለው። ኦ ወልድየ ማሚጦስ ፍታሕ በርእስከ እም ቅድመ ይፍታሕ ብከ እግዚአብሔር ብሎት ሲሄድ ዕፀው አዕባን መቃርዮስ ኮነ አምላከ በዲበ ምድር አሉት። ተስእሎ 141 ወሬዛ እስክንድራዊ ይለዋል ከገዳሙ ሊወጣ ሲነሳ አንተ ተው አትውጣ ጾር ይነሳብሀል አሉት እኔ አባ ብሎ ተመክቶ ወጣ ወዲያው ከመሸተኛ ቤት ገብቶ በልቶ ጠጥቶ ሲያበቃ ወዲያው ተስቧል መጋረጃ ገልጦ ሲገባ እባብ ነደፈው ሙቷል።

ዝና፣ በሰው መታወቅ

ተስእሎ 5 ወሀሎ እጉ ዘሎቱ ሰናይ ዝክር ማዕከለ ሰብእ ወኮነ ያምዕያ ለእግዚአብሔር ብዙኃ

ወነስኣ ነፍሶ ዘበስቃይ ወወደያ ውስተ ገሀነም ማኅደረ ሰይጣናት ወቦ ባሕታዊ ክመ ሰናየ ዝክር ወኮነ ያምዕያ ለእግዚአብሔር ዘልፈ ወእጉ ዘኮነ ሎቱ መቅጹት ዘምሉዕ ወርቀ ወበደዌሁ ኮኑ አኃው ይትለአክዎ ወያስተዋጽኡ በእንቲአሁ እም ንዋዮሙ ወተደፍነት ምስሌሁ መቅጹት ውስተ መቃብር ወኮነት ታስተርኢ እሳት ዲበ መቃብር ትእምርተ ገሀነም ዘድሉት ሎቱ። ተስእሎ 194 በሰው ዘንድ ስመጥር መሆንን አትውደድ ስሜ ይጠራ ብለህ በስመጥር ገዳም መሆንን አትውደድ። ስሜ ይጠራ ብለህ ለስመጥር መነኩሴ ረድእ መሆንን አትውደድ።

ሹመትን መጥላት

ተስእሎ 7 ወሶበኒ ፈቀዱ ይንስእዎ ለአሞንዮስ በአገብሮ ለኤጲስ ቆጶስና ቀረጸ እዝኖ ዘጸጋም። ከሹመት እንዲተውኝ ብሎ ነው። አንድም መልከ መልካም መባልን ስለጠላ መልከ ክፉ ይበሉኝ ብሎ ነው። ተስእሎ 23 የመክሲሞስና ዱማቴዎስ አባታቸው የሮም ንጉሥ ሎንድዮስ ይባላል። ብሉይ ሐዲስ ተምረዋል ከዚያ አባታቸው ሕግ ግቡ አላቸው ጠፍተው አንጾኪያ ከአባ አጋቦስ ሄዱ። አመነኮሳቸው አባ አጋቦስ ሲሞት ጵጵስና ሊሾሟቸው ሲሉ ሌሊት ወደ ገዳም ለማምለጥ መንገድ ጀመሩ በገድል ተቀጥቅጠው ኑረዋልና መሄድ የማይቻላቸው ሆነ ዝቅጥቅጥ ቢሉ መልአክ በደመና ወሰዳቸው።

ገነት

ተስእሎ 8 በእንተ ልእልናሁ እምድር ገነትሰ ይሰመይ ሰማየ። ወነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን ይከውና ውስተ ገነት እስከ ይመጽእ እግዚእ ለፍዳ።

ቁርባን

ተስእሎ 10 ኢወረቀ አባ መቃራ እለ እስክንድርያዊ ስሳ ዓመተ እም ኑኃ ተጠምቀ እስከ ጊዜ አዕረፈ በእንተ ተመጥዎቱ እምሥጢራተ ቅድሳት። ሶበ መጽኡ ለአሐዱ ምራቅ እምድኅረ ቀርበ እም ቅድመ ይስተይ ማየ አው ይብላዕ ኅብስተ በረከት ለየኅጦ እንከ ወለእመ አበየቶ ነፍሱ ለይኅሥዮ እንከ በግማደ ልብሱ። ጨርቁንም በኋላ በእሳት አቃጥሎ አመዱንም ውሃውንም አድርጎ ከፈሳሽ ወንዝ ይጨምረው እርሱ ባወቀ ይቀበለዋል። ተስእሎ 90 ይቤሉ አኃው ኮነ በአስቁጥስ ሶበ ይቁድሱ ካህናት ቁርባናተ ይወርድ ንስር ላዕለ ቁርባናት። ተስእሎ 142 ወኃጣውእሰ እንተ እም ቅድመ ጥምቀት በጥምቀት ይሠረይ ወኃጣውእሰ እንተ እም ድህረ ጥምቀት ትሰረይ በምሥጢራተ ቅድሳት። ለእመ ፈጸመ ኃጥዕ ቀኖናሁ እንተ ይትቄበላ እመምህራኒሁ።

ትዕቢት

ተስእሎ 12 አንድ መነኩሴ ከገዳም ሲወጣ ተው ወንበዴ ይጣላሀል አሉት። እኔ አባ ይሰግድልኝ እንጂ ይጣላኝ አለ። ሲሄድ ወንበዶች አገኙት አመልጣለሁ መስሎት ሸሸ አሳደው ይዘው ቢፈልጉ ገንዘብ አጡበት በሩጫ ያደከመን ለባዶ እጁ ነውን ብለው ገለባ ሸፍነው በእሳት ለብልበውታል። ተስእሎ 31 ይቤሉ ምንትኑ ይእቲ ትዕቢት ይቤ ለእመ የሐስብ ሰብእ ነፍሶ

ንጹሐ ወለእመ ውእቱ ኀለየ ከመ ትሩፍ እም ኃጥዓን። ተስእሎ 34 ጌታ አባ ጽላን ሄደህ ምእመናንን አስተምርልኝ አለው። ጌታየ የኔን መማር የእነዚያን አለመማር የእኔን ብቃት የእነዚያን አለመብቃት አይቼ ብታበይ እጎዳ የለምን ሂድስ ካልከኝ ሰይጣነ ትእቢትን አርቅልኝ ብሎ አመለከተ። እጅህን ከጫንቃህ ላይ አውጣው አለው። እጁን ከጫንቃው ላይ ቢያወጣ ደቦል ባርያ ያህል አገኘ ወቀበሮ ውስተ ኖጻ ይላል። ተስእሎ 103 እስመ ኩሉ ባሕታዊ ዘይዜነር ይወድቅ ውስተ እደ ሰይጣን።

ፈሪሀ እግዚአብሔር

ተስእሎ 16 በከመ ያየብስ እሳት ርጥበተ ዕፅ ወያውዕዮ ከማሁ ፍርሀተ እግዚአብሔርኒ እም ከመ ኀደረት ውስተ ብእሲ ታየብስ ሥጋሁ ወታጸመሂ አዕጽምቲሁ።

መልከ ጼዴቅ

የነገደ ካም ትውልዳቸው ነገዳቸው በኦሪት ባይጻፍ ነው እንጂ የመልከ ጼዴቅ እናት አባት አሉት ሐሴል ሳሌምን ሳሌም ሜልኪን ሜልኪ መልከጼዴቅን ይወልዳል እናቱ ሰሊማ ትባላለች አባቱ ጣዖት ያመልክ ነበርና መልከጼዴቅን ጠርቶ ከበጎቹ መርጠህ ለጣዖት የምንሰዋው በግ አምጣልኝ አለው። አባቱ ይህ ጣዖት ምን ይረባናል አለው። ከዚያ አባቱ ለጣዖት ሊሰዋው ሲል እሳት ከሰማይ መጥታ አባቱን በላችው።

ጸጋ እግዚአብሔር

ተስእሎ 19 ሙሴ ጸሊም በፀሐይ ያመልክ ነበር። ከዚያ ወደገዳም ሄዶ የገዳሙን አበምኔት አባ ኤስድሮስን አገኘና ምከረኝ አለው። ከዚያ መከረው አስተማረውና አጥምቆ አመንኩሶታል። ትስሕብ ጸጋ ሰብአ ነበ ፍድፋዴ በእንተ ሠላስ ግብራት። በእንተ ሕሊና አንዱ እርሱ አስቦ ነው። ወበእንተ ትምህርት ሁለተኛው ተምሮ ነው። ወበእንተ አንብቦ ሦስተኛው መጽሐፍ ተመልክቶ ነው። በጎ ሥራም ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሳ ከሰውም በጎ ፈቃድ የተነሳ ይፈጸማል። ወእም ቅድመ ትጽንን ሕሊናሁ ለብእሲ ለኒሩት ወለእከይ ኢትረድኦ ጸጋ። ተስእሎ 71 ባሕታውያን አስቀድመው በተፈጥሮ በተሰጣቸው ኃይል ትሩፋት ለመስራት ይደክማሉ። ወበደኃሪ ያደምዑ ኃይለ እም ጸጋ ዲበ ፍጥረቶሙ። ኂላ በጸፈጥሮ በተሰጣቸው ኃይል ላይ የጸጋ ኃይል ይጨመርላቸዋል። ተስእሎ 98 ኢየኀሥሥ እግዚአብሔር እምነ አሐዱኒ ፈድፋደ እምኃይሉ።

ረድኤተ እግዚአብሔር

ተስእሎ 20 ሙሴ ጸሊም ኃይለኛ ወንበዴ ነበር ኃይሉም አንበሳ ያገኘ እንደሆነ እንዳያመልጠው በእጁ ይዞ የሚገል ነው። ውሃም የመላበት እንደሆነ ደረት ለደረት ተጋፍቶ ዋኝቶ የሚሻገር ነው። በግ እንደ ሽንኩርት ልጦ የሚበላ ነው። ከዚህ በኋላ እንደዚያ መስሎት አጋንንትን በስራየ በጉልበቴ ድል እነሳለሁ ብሎ በብዙ ትሩፋት ይጋደል ጀመር። አጋንንትም ይህን አውቀው ጾር አጽንተውበታል። ለአባ ኤስድሮስ ጾር ጸናብኝ እንዴት ላድርግ ብሎ ቢነግረው

ከሰገነት ላይ ወጥቶ መላእክትን በምሥራቅ አጋንንትን በምዕራብ ተሰልፈው የሚዋጉ አስመስሎ አሳይቶታል ምንድን ናቸው ብሎ ጠየቀው። በእግዚአብሔር ኃይል ያልክ እንደሆነ እሊህ ይረዱሀል። በጉልበቱ ያልክ እንደሆነ እሊያ ይዋጉሃል አለው። በእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ ብሎ ድል ነስቷቸዋል። አእምር ከመ ጻማ ባሕቲታ ኢትረድኦ ለብእሲ ዘእንበለ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንተ ትጠረይ በጥምቀት ወተመጥዎ ቁርባን ቅዱስ። ወባሕቱ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ይመውዖ ለሰይጣን ወይትፈወስ። **ተስእሎ 23 ቅኔ፦** ይቤሎ እጉ ለአረጋዊ እስመ እፈቅድ አሥምሮቶ ለአምላኪየ በተባሕትዎ ወባሕቱ እፈርሕ ሰሚዕየ ጽንዐ ጸብዐ ተቃትሎቶመ ለሰይጣናት ወይቤሎ አረጋዊ ኢትዜከርኑ ረድኤተ እግዚአብሔር። **ተስእሎ 51** አንድ መነኩሴ ጾር ተነስቶበት ዓለሙን መስየ እኖራለሁ ብሎ ሲመጣ መንፈስ ቅዱስ የተኳለች የተቀባች ሕጻን መስሎ ታየው እቴ ወዴት ትሄጃለሽ አላት። ይህ ዓለም እንደ ጥላ ያልፋል እንደ አበባ ይረግፋል ሲሉ ሰምቼ ለምናኔ መውጣቴ ነው አለችው። ይህች ስትመንን እኔ ምንኩስናዬን ላፈርስ ብሎ ወደ ገዳሙ ተመልሶ ሄዷል። **ተስእሎ 62 ቅኔ፦** ይቤሎ አረጋዊ ለእጉ ኢትትሀከይ ሶበ ተቃተለከ ሰይጣን በአዝልፎቱ ወዕጽበቱ ወእምዝ ትመውዕ በረድኤተ እግዚአብሔር። **ተስእሎ 95** ወንጸውዖ ለእግዚእነ ለረድኤትነ በአውያት ልቡናዊት ወሶቤሃ ይርሕቅ እምኔነ ሰይጣን ወስሒት ወኃጢአት ወንግዕዝ እም ግብርናት ወይነጽሕ ልብነ። **ተስእሎ 140** ፱ ዘመን ዘግቶ ትሩፋት የሠራ አንድ ባሕታዊ ነበር ጌታ ዋጋህን ልስጥህ እንደቸርነቱ ልስጥህ ወይስ እንደስራህ አለው። እንደ ስራዬ ስጠኝ እንጂ የቸርነትህንስ ለሰብአ ዓለም አድርገው አለው። እንዲህ ባለ ጊዜ ረድኤተ እግዚአብሔር ተለየው። ጾር ተነሳበት ተሰነካከለ ወደቀ። **ተስእሎ 162** ተስእልዎ አኃው ለእንጦንዮስ በእንተ ቃል ዘእመጽሐፈ ሌዋውያን ወከልሐ በቃል ልዑል እንዘ ይብል ኦ እግዚአብሔር ፈኑ ኀቤየ ሙሴሀ ከመ ያጠይቀኒ ዛተ ቃለ ወመጽአ ሙሴ በአካለ ነፍስ። ክፉ ሀሳብ ሲነሳብህ ረድኤተ እግዚአብሔርን ጠይቅ ያን ጊዜ ሰይጣናት አፍረው ይሄዳሉ። አዕምሮህም ብሩህ ይሆናል።

ተጋድሎ

ተስእሎ 20 ዘሰ ይጻባዕ ምስለ ሰይጣናት ያፍቅር እንከ ከመ ይግበር ትእዛዛተ እግዚእነ። **ተስእሎ 23** አባ መቃርስ አበውን ዙረህ ጠይቅ የሚል ሕሊና ታሰበው ከእግዚአብሔር የተገኘ ይሆንን ወይስ ከሰይጣን የተገኘ ይሆን ብሎ አምስት ዓመት ሲያወጣ ሲያወርድ ኖረ። ኋላ ከእግዚአብሔር እንደተገኘ አውቆ ተነስቶ ሄደ። በረሃ ለበረሃ ሲዞር ሁለት ሰዎች ከባሕር ቁመው አያቸው ቢፈራ ከሩቅ ሆኖ ይመለከታቸው ጀመር ሰው እንደሆንህ ና አሉት ቀረበ ከዚያ እንደምን ትኖራላችሁ አላቸው። እንደምታየን አሉት ምን ትመገባላችሁ አላቸው ከባሕሩ ላይ እንደቅጠል ያለ አለ ይህን እንመገባለን ሰውነታችን ብትወድ ትቀበለዋለች ባትወድ ትተወዋለች አሉት። ስንት ዘመን ሆናችሁ አላቸው። 40 ዘመናችን ነው አሉት። ዓለሙ እንደ ወትሮ አለን ንጉሥም ይነግሣልን ጳጳስም ይሾማልን አሉት አዎን አላቸው ያደንቁ ጀመር። **ተስእሎ 27** ሥጋ በሚቀበለው መከራ ሥጋ በደከመ ቁጥር አጋንንትም ከሥጋ ይልቅ ይደክማሉ። ጻማሆሙኬ ለቅዱሳን ዘለዓለም ያደክሞሙ ውእቱ ለሰይጣናት እስመ ይጣቅይዎሙ መላእክት በትዕዛዘ እግዚአብሔር። ባሕታውያን አስቀድመው የሕሊናን ጾር ለማጥፋት በትሩፋተ ሥጋ ይደክማሉ። ወእም ድህረ ውእቱ ያጠርዩ ንጹሐ ልብ። **ተስእሎ 32** እባብ ራሱን ከተመታ መላ

አካሉ ይሞታል። መነኩሴም ነቅዐ ሐልዮን ካጠፋ ችግር አይገጥመውም። ከእርሷ በኋላ የሚመጣው ጦር ይጠፋለታል። **ተስእሎ 92** ዓቂበልብ ያለው ኃልዮ ኃጢአትን ፈጥኖ ከልቡናው ማራቅ ነው።

ሰይጣናት

ተስእሎ 23 በቀዳሚ ያረኩሱ ሰይጣናት ሕሊናቲሁ ለብእሲ። ሰይጣናት ሰው ወደ ተዘክሮተ እግዚአብሔር እንዳይደርስ በየደረጃው ይዋጉታል። ሶበ ተወክፉ ባሕታውያን ስፍጠተ ሰይጣናት በሕሊናሆሙ ወተፈግዑ ቦቶን ትጸለምት ነፍሳቲሆሙ። ለእመሰ ኢተወክፉ ስፍጠታቲሆሙ ይስዐሩ እንከ ሰይጣናት ወየኀሥሩ ወይትመየጡ ፍጡነ። **ተስእሎ 30** ሠለስቱ ሰይጣናት ቦኡ ኀበ ማር ወቅሪስ በአምሳለ ሠለስቱ ቀሳውስት። ሰይጣናትሰ ኮኑ ይገብሩ ውእተ ዘበምትሐታቲሆሙ ሕስውት። እስመ አልቦሙ ሥልጣን ከመ ይግበሩ አምሳለ ዘበአማን ዘእም ጠባይዕ ዘከመ ይገብሩ መላእክት። **ተስእሎ 31** ይትቃተልዎሙ ሰይጣናት ለመንፈቀ ባሕታውያን ቀዳሚ በአፍርሆ ወካዕበ በዘቢጥ። **ተስእሎ 34** ወለዘይመልኮ ትቁጥዕት ይነብር ሰይጣነ ቁጥዓ ውስተ ልቡ ወለዘያንጎረጉር ወይትናገር ነገረ እኩየ ይነብር ዲበ ልሳኑ ወለዘይነውም በውስተ ጸሎት ይነብር ዲበ አዕይንቲሁ ወለሰራቂኒ ይነብር ዲበ የማኑ። **ተስእሎ 52** ሰይጣናት ድኩማን አኃውን ጋሻ መከታ ሠረገላ አድርገው ትሩፋት የሚሰሩ ፍጹማንን ይዋጓቸዋል። **ተስእሎ 85** ይቤ አባ ጴሜን ሠለስቱ ኃይላቲሁ ለሰይጣን ዕልወት ወተሐይዮት ወፍትወት። **ተስእሎ 95** ሰይጣንሰ ውእቱሰ መልአክ ዘውዱቅ ወውእቱ ጸላዒ መስተቃትል።ፍትወትኒ ውእቱኬ ተፈግዖቱ በኀሊና ስሒት ወተአዝዞቱ ላቲ። ሴት ዘርዓ ብእሲን እንድትቀበል ልብም ሐልዮ ኃጢአትን ከሰይጣን ከተቀበለች። ሴቲቱ ልጅ እንደምትወልድ ልብም በነቢብ በገቢር ክፉውን ሐሳብ ትፈጽማለች። **ተስእሎ 107** በበይነ ክልኤ ፍና ያሜክሩ ሰይጣናት ሰብአ አሐዱ በእንተ ኃጢአት ከመ ሳኦል ወካልእ በእንተ ጽድቅ ከመ ኢዮብ። ወኀደጎ ያመክሮ ከመ ያስተርኢ ጽድቁ።

ማሸነፍ

ተስእሎ 26 ወበመንኖ ጥሪት ሞዐ አፍቅሮ ጥሪት ወበጾም ሞዐ ስስዕተ ወበትጋህ ሞዐ ንዋመ። ወበአንብቦተ መጻሕፍት ቅዱሳት ሞዐ ነገራተ እኩያተ ወስብሐተ ብጡለ ወበተየውሆ ሞዐ ትቁጥዕተ ወመዓተ ወበትሕትና ሞዐ ስብሐተ ብጡለ ወትዝህርተ ወበአፍቅሮ ሰብእ ሞዐ ጽልዐ ወቅንዐተ ወተጻርሮተ ወብዙኃተ እከያተ። **ተስእሎ 28** ለእመ ፈቀድከ ይፍርሁ ሰይጣናት እምኔከ መንንኬ እንከ ፍትወታተ። በከመ ይቤ ብጹዓዊ ማርቆስ ከመ ዘይፈርህ ወይጎይይ ዘይፈቅድ ይዘሙ ምስለ መጻምርተ ካልዑ ሶበ ሰምዐ ድምጸ ምታ ከማሁ ይደነግጽ ሰይጣንኒ ሶበ ሰምዐነ እንዘ ንጼውዖ ለእግዚአብሔር። ዘኢያሐጽጽ እመብልዐ ወመብዝኅቶሰ እምስትየ ማይ ኢይመውዖ ለመንፈሰ ዝሙት። **ተስእሎ 97** አበው ኀደግዎ ዘይከውን ምክንያተ ለኃጢአት። **ተስእሎ 127** ሶበ ሞዐ ሕማማተ ሠረቀ ብርሃን ውስተ ልቡ። ወይቤሉ አበው እም ከመ ሞዐ ባሕታዊ ስብሐተ ዕሩቀ ወዐርገ ኀበ ሉዓሌ ትሕትና ይሠርቅ ላዕለ ልቡ ብርሃን አምላካዊ በጊዜ ጸሎት። **ተስእሎ 142** ሰው ወንድሙን በማናቸውም በደል ቢበድል ከዚያ

በትሕትና ልብ ሆኖ ከጫማው ወድቆ ማረኝ ቢለው በደልኩ ይቅር በለኝ ቢለው ኃጢአቱ ይሰረይለታል ሶቤሃ ይነስእ በእንቲአሁ መዊዐ።

መስቀል

ተስእሎ 28 ይፈርሁ ሰይጣናት መስቀለ አኮ እመስቀል ባሕቲቱ አላ እም ትእምርትኒ ዘከማሁ አምሳሊሁ። ተስእሎ 29 ሁለት ሰዎች ከሰው ተለይተው ከበዓት ተከተው ብቻቸውን ይኖራሉ ሰይጣን አረጋዊ መስሎ መጥቶ በዓቴን ላሳያችሁ ብሎ ይሂቸው ሄደ ከገደል አፋፍ ደረሱ። ከገደሉ ቀጥሎ ባሕር ነው በዓቴ ይህን አልፎ ከዚያ ውስጥ ነው ብሎ ይህን ሁሉ እስክንዞር ይመሸብናል በዚህ ተጭነን እንሂድ ብሎ በምትሐቱ ደመና ጠቅሶ ከዚያ ላይ ወጣ አንዱ ባሕታዊም ወጥቶ አብሮ ተቀመጠ አንደኛው ማማተብ ለምዶ ነበርና ሊወጣ ቢያማትብ ያን አብሮ የተጫነውን ጥሎት ሸሸ ተንቆጭቁጮም ወርዶ ከባሕሩ ወደቀ። በመዞሪያ ሐዲ አማትቦ ወንድሙን አንስቶ እድሜያቸውን ሙሉ እያማተቡ የሚኖሩ ሆነዋል። ይደሉ ለነ ከመ ኢናብጥል ንሕነሰ ትእምርተ መስቀል። ተስእሎ 95 ወግበር ስግደታተ ቅድመ መስቀለ እግዚእነ።

በገዳም መኖር፣ ምናኔ

ተስእሎ 57 ይቤ እንጦንዮስ እስመ ዘይነብር ውስተ ገዳም ወይጸሙ ይድኅን እምሠለስቱ አጽባእ እምኔሃ ነገር ወርእይ ወሰሚዕ። በሕዋሳተ አፍዓ የሚጨመር ብዙ የውስጥ ጸር አለና። ተስእሎ 97 አባ አጋቶን መልካም ቤት ሰርቶ ሲጨርስ ቀና ብሎ አይቶ እንግዲህ አንችን አንችን እያየሁ ስራ ፈትቼ ልኖር ነውን ብሎ ጥሏት ሄደ።

አርምሞ

ተስእሎ 61 አባ አጋቶን ወደየ ውስተ አፉሁ ኖጻ ዕብን ፴ ዓመታተ ከመ ኢይትናገር። ወለእመ ረከበ እንከ በዘይነግር ነገረ በቁኤት ይነስእ ኪያሃ ውስተ እዴሁ። ወሶበኒ ነበረ ላዕለ ማዕድ ወጸሎት ያወጽኣ እም አፉሁ። ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ተዐቅቦቶ ወሀቦ መዊዐ ላዕለ ልሣኑ።

አንብዕ

ተስእሎ 77 ደቂቀ እስራኤልኒ ኢቦኡ ምድረ ርስት ዘእንበለ እም ድኅረ ውስተ ገዳም ፵ ዓመተ ወአንብዕ ትመስላ ለይእቲ ምድረ ርስት። ልቡናው ስላዘነ የሚያለቅስ አለ። ሐዘን መከራ ስለጸናበት የሚያለቅስ አለ። ደስ ብሎት የሚያለቅስም አለ። የቅዱሳን ልቅሶ ግን ከዚህ የተለየ ነው ለኃጢአታቸው ነው የሚያለቅሱት።

ተዘክሮ እግዚአብሔር

ተስእሎ 80 ይደሉኬ ላእሌኪ ኦ እኅት ከመ ትጽሪዮ ለእግዚእ በልብኪ በከመ ጸረቶ እግዝእትነ ማርያም በከርሣ። ተስእሎ 97 ዮሐንስ ሐጺር እንቅብ ሊሸጥ ሄዶ ከገበያ ተቀምጦ ሳለ አንዱ

ባለ እንቅብ ዋጋ ንገር አለው።ዮሐንስም ሚካኤልኑ የዐቢ ወሚመ ገብርኤል አለ። **ተስእሎ 152** ይቤ አባ ኤልያስ አንሰ እፈርህ ሠለስተ ግብራተ ወይእቲ ጸዐተ ነፍስ እም ሥጋ ወተራክቦተ እግዚእ ወጸዐተ ፍትሕ ላእሌየ። እስመ ተዘክሮተ እሎን ግብራት ትባልሐነ እም ገቢረ ኃጢአት ወታጸንዐነ ውስተ ገቢረ ኂሩት ወጽድቅ። **ተስእሎ 192** ተዘክሮትሰ ውእቱኬ ተአስሮተ ሕሊና ምስለ እግዚአብሔር።

ንሥሓ

ተስእሎ 82 ይቤሉ አኃው በእንተ ምንትኑ መንፈቀ ሰብእ ይረክቡ አዝማነ ለንሥሓ። ወናሁ ወሀበ ንሥሓ ለኩሉ ሰብእ እስከ እለተ ሞቱ።

እውቀት

ተስእሎ 85 ይቤ ማር ወቅሪስ እስመ እም ዘክሮ እግዚአብሔር ዘዘልፍ ትትወለድ አእምሮ እግዚአብሔር ወእም ተዘክሮ ፍጥረታት ትትወለድ አእምሮ ፍጥረታት።

ፈቃደ ሥጋ

ተስእሎ 156 ፈቃደ ሥጋ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተጋረደ የብረት ግድግዳ ነው። ከሰው ተለይቶ ከበዓት ተከቶ የሚኖር በጾም በትጋህ ሆኖ ትሩፋት የሚሰራ ሰው ይመውዕ ፈቃደ ሥጋ።

አረጋዊ መንፈሳዊ

እንጦንስ መቃርስን መቃርስ ጳኩሚስን ጳኩሚስ ቴዎድሮስን ቴዎድሮስ አቡነ አረጋዊን አቡነ አረጋዊ አባ ዳንኤልን ይወልዳል። ከዚያ በኋላ መነኮሳት እንደ ሣር በዝተዋል። ከብዙዎች አንዱ የአረጋዊ መንፈሳዊ ወንድም ዮሐንስ ነው። አረጋዊም ከወንድሙ ዮሐንስ ጋራ ይኖራል። አናወሩ ግን በትሕትና ነው ጽሕፈት ያውቃልና ጻፍ ይሉታል እኔስ ብርዑን ቀርጬ ቀለሙን በጥብጬ ብራናውን ዳምጬ አቀርባለሁ እናንተ ጻፉ ይላቸዋል። ንባብ ያውቃልና አንብብ ይሉታል እኔስ አትሮንስ አቀርባለሁ መጽሐፍ አወጣለሁ መብራት አበራለሁ እናንተ አንብቡ ይላል። ቅዳሴ ያውቃል ቀድስ ይሉታል። እኔስ ጥላ እሰፍራለሁ ቃጭል እመታለሁ ማዩን ቀድቼ መሥዋእቱን ሰርቼ አቀርባለሁ እናንተ ቀድሱ ይላል። ከእለታት አንድ ቀን ቀድስ ብለው ሊቀድስ ገባ ጸዋትው ጨርሶ ከፍሬ ቅዳሴው ሲደርስ መሥዋእቱ በአምሳለ ብርሃን በአምሳለ በግዕ በአምሳለ ሕጻን ተለውጦ አየው። ወፈቀድኩ እሕቅፎ ይላል። ከዚህ በኋላ ከሰው ሳልለይ እንዲህ ያለ ምስጢር የተገለጸልኝ ከሰው ብለይማ እንደምን ያለ ምስጢር በተገለጸልኝ ኑሯል ብሎ ከገዳሙ ወጥቶ አክይስት አቃርብት አናብስት አናምርት ካሉበት ነቅዐ ማይ ልምላሜ ዕዕ ከሌለበት ከጽኑ በረሀ ሄዶ ተቀመጠ። አረጋዊም ወንድሙ ዮሐንስ የሚጠይቀውን በመልእክት እየጻፈ ይልክለት ነበር። ሲጽፍም መልእክት ዘፈነዋ ሐራውያ ገዳም እያለ ነበር። ዮሐንስ ግን አረጋዊ መንፈሳዊ ብሎታል። በእርድና ጊዜ ፊልክስዩስን በተባሕትዎ ጊዜ ማር ይሥሐቅን

ጣዕም ከቀመሱ በኋላ ግን አረጋዊን መመልከት ይገባል። **ተውላጣት** የሚለው ከአንዱ መዓርግ ወደ አንዱ መዓርግ ማደጉን ነው።

ማሸነፍ፣ ተጋድሎ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ መጀመር ኃይለ መዊዕን ይሰጣል። **ድርሳን 34** ተጋደለ ምስለ ሰይጣን ወሞያ እስመ መስተቃርን እኩይ ይትቃተለነ በገቢረ ትእቢት ወይፈቅድ ያስሕተነ በግፍዕ ከመ ይማዕ። ወናሁ ንጉሥነ መዋዒ አወልተወነ በንዋየ ሐቅል ዘትሕትና። ወዘእንበለ ኃይለ ትሕትናሰ አልቦ ዘይክል መዊዐ። **መልእክት 10** መስተጋድል ዘይሬኢ አክሊላቲሁ ኢይሜምዕ እም ጽንዐ ጸብእ። አክሊልሰ ዘይሁቦሙ ክርስቶስ ለፍቁራኒሁ አመ ተፍጻሜተ ገድሎሙ ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ውእቱ። ኢንኩን ነኪራነ እም ተጋድሎ።

አንብቦ መጻሕፍት፣ መንግሥተ ሰማያት

ኦ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ክሥት አዕይንተ አልባቢነ ከመ ንለቡ አንብቦ መጻሕፍቲከ ቅዱሳት። **መልእክት 34** ብጹዕ ዘአጥረየ ሀገረ ዘትነብር ለዓለም ወዘይትዐረክ ምስለ ኩሎሙ እለ ሀለው ውስቴታ። **መልእክት 35** ወእስከ ይእዜ ኢኮንኩ ኢየሩሳሌም ሀገረ ክርስቶስ ንጉሥ። አአምን አንሰ ከመ እስከ ዓዲሁ ሀገረ ባቢሎን። ወአሕዛብኒ ርኩሳን የኀድሩ ውስቴትየ ዘውእቶሙ ሕማመ ዝሙት ርኩስ። ሀገሬ ባይደለ በዚህ ዓለም ለምን እኖራለሁ። መኖርንስ ለምን እወዳለሁ። ለሊከ ተአምር ከመ ዝንቱ ዓለም ሐሳዊ ውእቱ። **መልእክት 43** እግዚአብሔር ይህን ዓለም መከራ ልንቀበልበት ልንፈተንበት ፈጥሮታል። ይህ ዓለም ስራ የሚሰሩበት ዓለም ነው።

መንፈሰ ዝሙት

ድርሳን 1 መፍትውኬ ለሰብእ ይትዐቀብ እም ተዐርኮ ደቂቅ ከመ ኢይርኮስ ልቡ በሕሊና ዝሙት። ሕጻናት መልክአ አንስትን መምሰል አለባቸውና። ዝሙት ሴትና ወንድ የሚሰሩት ብቻ አይደለም ያልሰጡትንም መሻት ዝሙት ነውና። ዘያዘልፍ ነገረ ተውኔት ወተፈርዝዞ ዘማዊ ውእቱ በነፍሱ ወሥጋሁ። **ድርሳን 7** ከአጋንንት ሁሉ ይልቅ የሰይጣነ ዝሙት ጸሩ ብዙ ነው። ቦ አመ ያደክም መለያልየ ወቦ አመ የሐምግ ልበ ወያጸልም ሕሊናሃ እም ኩሉ ኑዛዜ። ወይሬስያ ቆራረ በጊዜ ጸሎት ወዝማሬ ወአንብቦ ወይመልያ ለብእሲ ሐኬተ። ወቦ አመ ይዘብጦ ለርእስ በዓቢይ ሕማም ዘጽኑዕ ጥቀ። ሰጊድህን ቁመትህን ክቡድ አድርጎ ያሳይሀል። ትተሀት እንድትተኛ ያደርግሀል። ወቦ አመ እንዘ ትቀውም ታረመስስ ዲበ አባላቲከ ወታግደመድም እገሪከ እግርህን ታፋትላለህ። ነገር ግን የታገሥህ እንደሆነ መልአክ እንቅልፉን ያርቅልሀል። ተዐገሥ ኦ እጉየ በእንተ እሉ ወሰብሕ በውስተ ልብከ። ወኢታዕርፋ ለነፍስከ ግሙራ በፍሥሓ አፍኣዊ። ወፍጡነ ይጎይይ እምኔከ ሰይጣነ ዝሙት። ሶቤሃ ዑቅ ኢትትሀየይ ወኢትኑም ከመ ኢይጎድግ ዐቃቢከ። ወእመሰ ኢይትከሀለከ ትትዐገሥ በእንተ ድካም ኑም እንከ እንዘ ትነብር። ሶበ አጽዐቀከ ሰይጣነ ዝሙት ተንስእ ሶቤሃ ወአንሶሱ ንስቲተ ወየጎልፍ እምኔከ። ወእመ አኮ ሶበ ትሰይን ስንተከ ይቆርር ለከ። እንደ እፉኝት እንደ ውሻ ንብ ቢነድፍህ ያለመጠን እንድታክ

ቢያደርግህ ሰይጣነ ዝሙት እንደሰለጠነብህ እወቅ። ወሶበ ያዜክረከ ዝንቱ ሰይጣን ጽዩዕ ምግባራተ ዘርእይ አው ዘሰሚእ በዘያነቅሕ ኅሊና ፍትወት ገሥጾ በመዓት ወጽርፍ ላእሌሁ ወሶቤሃ ይኅይይ ኅፉረ። **መልእክት 48** የዝሙት ጸር መድኃኒት ጾም ጸሎት ውሃ አለማብዛት ናቸው። እየደገመ እያመሰገነ ወዲያ ወዲህ ማለት ነው። ምንጣፍ አንጥፎ አለመተኛት ነው።

ተዐቅቦ፣ ምናኔ፣ ነቢብ፣ ሐልዮ

ድርሳን 1 ዘይከልእ አፉሁ እም ተናግሮ የዐቅቦ ለልቡ እም ደዌ ኃጢአት። ዘይሜንን ኩሎ ትፍሥሕታተ ይኔጽሮ ለእግዚአብሔር። ዘየዐቅብ ልሳኖ አልቦ ዘየሐይድ መዝገቦ እምኔሁ እስከ ለዓለም። ለዘይጌንዕ ለነቢብ ይርኅቆ ፈጣሪሁ። ዘያረምም ልሳኖ ወኩሎ ግዕዞ ያጠሪ ሥርዓተ ትሑተ ወይዋሄ። ከመ ሶበ ያረምም ባሕር ወይዝህን ይትለሀዩ ዓሣት ከማሁ ሶበ ይዝኅን ባሕረ ልብ እመዓት ወቁጥዓ ይትሐወሱ ዘልፈ በውስቴቱ ምሥጢራት ኅቡዓት ወራእያት አምላካውያት። በአምጣነ ይትገንሥ ብእሲ እም ተደምሮ ወተራክቦ ምስለ ሰብእ ከማሁ ይከውን ድልወ በልቡናሁ ለተናግሮ ወተላጽቆ ምስለ እግዚአብሔር። ለሰው አፍዓዊ ክብርን ካልናቀ ውሣጣዊ ክብርን ማግኘት አይቻለውም። **ድርሳን 15** በዓቂበ ሕሊናት የሚገኝ ክብር አለ። ኦ እጉ ኢይትከሀሎ ለብእሲ ግሙራ ይብጻሕ ኀበ ሀገረ ሕይወት ዘእንበለ ተዐቅቦ ዘውስጥ ወአፍዓ። ክላእ ንጻሬከ እም ኩሉ ስን ኃላፊ እንዘ ትኔጽሮ ለእግዚአብሔር ወትሐልዮ በልብከ። ክላእ እዘኒከ እም ኩሉ ሰሚዕ ዘተላሕዮ ዋዛ ፈዛዛ ነገር ከመስማት ጉሮሀን ከልክል። ልጉም አፉከ በፍጹም ተዐቅቦ። ወለልሳንከኒ ልጉም እም ነገረ ዘርቅ። **ድርሳን 23** ይቤ አረጋዊ ለእመ አብዝኀ ልሳንከ ነቢበ ይከውን ልብከ ቆሪረ። **ድርሳን 33** አበው ጸልእዋ ለተድላ ወአፍቀሩ ንጹተ። መነንዋ ለዓለሞሙ ወለኩሉ ትፍሥሕታቲሃ ዘእንበለ ይርአይዋ ለደኃሪት ዓለም። **ድርሳን 35** ሥራዕ በመዳልው ንባበ ልሳንከ። ወዕፁ ምስምዓቲከ እምነገረ መሐድምት ዕሩዕ ዘአልቦ ጥበብ። **መልእክት 33** የዚህ ዓለም የተድላ የደስታው ፍጻሜ ኀዘን ነው።ዕቀብ አዕይንቲከ እም ርእየ ኩሉ ሕስው እስመ ያነቅሓ ለፍትወትከ።

ሐሜት፣ ቂም

ድርሳን 1 ኢትስማእ ቃለ ሐሜት ላዕለ ቢጽከ። አማህ ብለው ቢነግሩህም አንድም ቢያመጣብህ አትስማበት። ወጉየይ እም ህየ ከቦታው ከሰው ከነገሩ ሸሽተህ ርቀህ ኑር። ከመ ኢትትኃጎል ነፍስከ እምነ ሕይወት። **መልእክት 18** ተዐቀብ እምነ ቂም እስመ ውእቱ ሰይጣን ልቡሰ ሥጋ ቂመኛ ሰው ሥጋ የለበሰ ሰይጣን ነውና።

ሰይጣነ መዓት

ድርሳን 1 ልቡ ለቁጡዕ ዕሩቅ ውእቱ እምሥጢራተ እግዚአብሔር። **ድርሳን 6** ጥቂት ቁጣ ቢሰማህ አእምር ከመ ጋኔነ ቁጥዓ ቀርበ ለተቃትሎትከ። ዕቀብ ኅሊናከ ከመ ኢትትቆጣዕ ላዕለ አሐዱኒ እም ሰብእ በውእቱ ዕለት። **ድርሳን 9** ዝንቱሰ ሰይጣነ መዓት ገፋዒ ውእቱ ያዜክራ ለነፍስ ምግባረ ዘኀለፈ። ለነፍስ ያለፈውን ነገር ያሳስባታል እገሌ እንዲህ ይበለኝ እንድትል

ያደርጋታል። ወዘሀለዎ ይኩን የሚመጣውንም ያሳስባታል። እገሌ እንዲህ ይሉኝ ይሆንን እንድትል ያደርጋታል።

ተዘክሮ

ድርሳን 1 ኃጣውእን ቆራርጦ የሚጥላቸው ሰይፍ ተዘክሮ ነው። በከመ ይትመነደብ ዓሣ በጊዜ ፀዐቱ ውስተ የብስ ከማሁ ኀሊናኒ ሶበ ይወጽእ እም ተዘክሮ እግዚአብሔር ይዘነግዕ በተዘክሮ ዓለም ኃላፊ። **ድርሳን 15** ለእመ ቀተለ ብእሲ ፍትወታቲሁ እምነ ሕይወት ኃላፊት በተዘክሮ ፍቅረ እግዚአብሔር ይከውን ሕያወ እም ይእዜ በእንታክቲ ሕይወት እንተ ሀለዋ ትምጻእ። **ድርሳን 23** መላእክትኒ በኩሉ ጊዜ ይደመሙ። ሰውን ለመርዳት መውጣት መውረዳቸውም ተደሚቸውን ሳይፈቱ ነው። **ድርሳን 24** ለምንት ለከ ኀልዮ ወዘንጋኤ ውስተ ሀገር ዘኢኮነት ዚአከ። **ድርሳን 34** ጌታ ሲጠመቅ ዮሐንስን ሆነህ አስበው። ከጉድጓዱ አጠገብ ሳምራዊትን ሴት ሆነህ አስበው። ምስለ ኖሎትኒ ስብክ ልደቶ ወሰብሕ ምስለ መላእክት ስብሐቲሁ። ወጹም ምስሌሁ ሶበ ይጸውም። ወአመ ይዌልጦ ለማይ ወይራስዮ ወይነ ሀሉ ሶቤሃ እንዘ ትመልያመ ለመሳብክት ማየ። ወሶበ ይባርክ ዲበ ኅብስት ጹር አስፈሬዳተ በመዝራዕታቲከ ወሀብ ለጉዑን። ወአመ ይነውም ዲበ ሐመር አንቅሖ ለሊከ ወውስተ ጉባኤሂ ሀሉ ምስሌሁ ኀበ ደብረ ዘይት ሀሉ ምስሌሁ ውስተ ምኩራብ አጽምእ ትምህርታቲሁ ሀሉ ውስተ መቃብር ምስለ አልዓዛር ከመ ያንስእከ። አርህስ እገሪሁ በአናብጊከ ከመ ማርያም ወመዝምዝ በሥእርተ ርእስከ። ወሶበ ይፈትት ኅብስተ ተመጠው እም እደሁ። ወአመ የኀጽብ እግረ አርዳኢሁ ቅረብ ኀበ ምኅጻብ ከመ ይኅጽብከ እም ኃጣውኢከ። ወሕምም ምስሌሁ ወተወከፍ ጽእለተ ወኀሣረ ወሥላቀ። ወወሪቀ ምራቅ ወቅንዋተ ሐጺን ወተሰቀል ምስሌሁ በዲበ መስቀል። አድንን ርእሰከ ወሙት ምስሌሁ ከመ ትትነሳእ በትንሳኤሁ። መቃብራት ተከሥቱ ወልብነሰ ኢለምለመ። በዓውደ መቃብሩ በፍርሀት ወበረዐድ ትቁም ነፍስከ በአምሳለ ማርያም ከመ ይበልዋ መላእክት ምንት ያበክየኪ። ወሶበ የዐርግሂ አጽንን ርእሰከ ከመ ይባርከ። ኦ ለእበየ ትሕትናከ ኦ ልኡል። አሌ ሊተ ኦ እግዚኦ ሚ መጠነ አበስኩ ለከ። **ድርሳን 34** ይቤለኒ አሐዱ እም አኃው ሶበ ኀለየ ልብየ በተዘክሮ ገነተ ተድላ ወበሀልዮ ነፍሳት እለ ሀለው ውስቴታ ሶበ ተመሰጥኩ በህየ። ብጹዕ ውእቱ ዘኅዱር ውስተ ልቡ ዝክርከ እግዚኦ በኩሉ ጊዜ። እስመ በፍርሀት ይኅይዩ አጋንንት። **ድርሳን 35** የኀልዮ ኃጢአትን የሚያጠፋ አንክሮ ተደሞ በልቡናህ ይኑር። ተዘክሮ ልቡናን ያነጻል ኀሊናንም ያጠራል። **መልእክት 30** አንሰ አነክር ኪነ ጥበቡ ለእግዚአብሔር በእፎኬ አስተጻመራ ለነፍስ ምስለ ሥጋ ከመ ኢትትፈለጥ።

ቅዱሳን፣ ድንግል ማርያም

ድርሳን 1 ሕይወቶሙ ወተድላሆሙ ወፍሥሓሆሙ ወሐሴቶሙ ክርስቶስ ውእቱ ለቅዱሳን። **ድርሳን 23** ወካዕበ ይቤ ሶበ አሐውር ወእመኒ ሀሎ አረፍት በቅድሜየ ኢየአምሮ። ሀተታ ሳያውቀው ሰንጥቆት ይሄዳልና። ብጽእት አንቲ ኦ እግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ እስመ ብጽአንኪ ዘአልቦ ትርጓሜ። **ድርሳን 35** ነገረ ማእምራን አጽምዕ። **መልእክት 7** ዘያፈቅር ቅዱሳነ ፍቁሮሙ ውእቱ ለመላእክት። **መልእክት 17** ጳውሎስ ያለ ጫማ ይሄድ ነበረ። ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስም ቁራሽ ይለምን ነበር። ወይስእል ፍርፋራተ ለሲሳዩ።

ትሕትና

ድርሳን 1 ዘይሜንን ወያስተሐቅር ርእሶ ይረክብ ጥበበ እም ኀበ እግዚአብሔር ወዘይሬሲ ርእሶ ጠቢበ ይሴስል እም ላእሌሁ ጥበበ እግዚአብሔር። **ድርሳን 3** ኃጢአትን ማሰብ ትሕትና ነው። አቦ አቦ ከመባል ቀልብ ከማግኘት ተጠበቅ። **ድርሳን 35** ወእም ኩሉ የዐቢ ትሕትና ልብ ወይመጥቆ ለሕሊና ከመ ይነጽር ልዕልና እግዚአብሔር። ማኅደረ እግዚአብሔር ይእቲ ነፍስ ትሕት። በኩሉ ግብር አቅድም አትሕቶ ርእስከ። ወምኑነ ኩን በሥርዓተ ጸሎት ወአንብቦ ወዘይመስሎ ለዝንቱ። በምትሰራው ስራ ሁሉ የተናቀ ስራ ለመስራት ጽሙድ ሁን። ክቡራት ለሆኑ ግብራት ግን አልበቃም በል። መናቅ መሰደብ ይገባኛል በል። ሁል ጊዜ ለመታዘዝ ሰውነትህን አገብር። አንተ ግን አዛለሁ አትበል። በአምጣነ ያስተኃቅር ብእሲ ርእሶ ከማሁ ይከብር በኀበ እግዚአብሔር። ሶበ ኢያግረረ ዮሴፍ ቀዲሙ ለሕገ ግብርናት እም ኢኮነ እግዚአ ላእለ ምድረ ግብጽ።

አርምሞ፣ ማኅሌት

ድርሳን 1 በአምጣነ ያረምም ልሳን እም ተናግሮ ከማሁ ይበርህ ልብ ለፈሊጠ ጥበብ ወለፈክሮ። አብዝኖ ነገር ያዘነግፆ ለልበ ነባቢ። **ድርሳን 6** ኩሉ ግብር ዘየአምርዎ አኃንንት ኢይከውነከ ዕረፍተ። **ድርሳን 21** የምስጢራት ወሰናቸው አርምሞ ነው። **መልእክት 32** በማኅሌትየ ኀሥሩ አኃንንት። አኃንንት በእኔ ምስጋና ድል ተነሱ።

ዘፈን፣ መብል መጠጥ፣ ጨዋታ፣ እንቅልፍ

ድርሳን 1 ኢትፍቱ ተላሕዮ ወጽጋበ ከርስ እንተ ትወልድ ሕማመ። ኢትጼወው በሰይጣን በፍቅረ ዘፈን ወተፈሥሑ። አብዝቶ መመገብ እንቅልፍ ማብዛት ከሰይጣን ከግብሩ ጋራ ይስማማል። አብዝቶ ሲመገብ ጊዜ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለዋል ጾር ይነሳበታልና። **ድርሳን 23** ለእመ ኮነ ፈቃደ ፍትወትከ ዓለማዊ ውእቱ የምትሻው የልቡናህ ፈቃድ ሥጋዊ ከሆነ። ዝንቱሰ ግዕዘ ከለባት ወአሕርው። ይህስ የውሻ የእሪያ ግብር ነው። ዘውእቱ ግብረ ከርስ ይሕውም ሆድን መመላት ነው ወአውስቦ ዝሙትን መውደድ ነው። ወለእመ ኮነ ፍትወትከ በእግዚአብሔር ዝሰ ግዕዘ መላእክት ውእቱ። **ድርሳን 25** በነገረ ተውኔት ኢትቁርር ነፍስከ እሙቀተ ፍቅሩ ለክርስቶስ ዘበእንቲአከ ጥዕሞ ለሞት። **መልእክት 4** አብዝኖ ንዋም ያጸልም ልበ ለእመ ተጋህከ ትከውን ሱታፌሆሙ ለሱራፌል። **መልእክት 18** ኃጣውዕ አብዝቶ ከሚመገብ ሆድ ይገኛሉ። ኢትምላእ ከርስከ ብዙኀ ከመ ኢያጽዕቀ ደዌ ዝሙት። ለባሕርይህ ተስማሚ የሆነ የዝሙት ጾር ምግብ በመክፈል ይጠፋል። **መልእክት 36** ዘመኑን እንደ እንስሳ ሆኖ ያላሳለፈ ንዑድ ክቡር ነው። ብጹዕ ዘይሬኢ ነፍሶ ወዘኢያኅለፈ መዋእለ ሕይወቱ ከመ እንስሳ። **መልእክት 40** ወንዋምከኒ ይኩን በአቅም። መጥነህ ተመገብ። **መልእክት 48** የኃጢአት ሁሉ መገኛ አበጋዙ ሀኬት ነው።

ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና

ድርሳን 3 በንጽሐ ሥጋ ጊዜ ግዙፋን ፍጥረትን እለ ብሔሞትን እለ አድማስን ያያሉ። በንጽሐ ነፍስ ረቂቃን ፍጥረትን መላእክትን ነፍሳትን ያያሉ። በንጽሐ ልቡና ሥላሴን ያያሉ። ይህም ማለት የፀሐይ ብርሃን በዛፍ በቤት በምግብ ሆኖ እንደምናየው ያለ ነው። **ድርሳን 6** ንጽሐ ልቡና የመንግሥተ ሰማያት አረቦን ነው። በንጽሐ ነፍስ ጊዜ ልቡና ከሑከታት እኩያት ይለያል። በእንዲህ ብዙ ከቆየ በኋላ ንጽሐ ልቡናን ገንዘብ ያደርጋል። ይህ ንጽሐ ልቡና ደግሞ መካነ ፍሥሓ ወሐሴት መካነ ብርሃን ብሔረ ሕይወት ነው። ዓረቦነ መንግሥተ ሰማያት ነው። በዚህ ጊዜ ትካዝ ኀዘን ጾር ሑከታት የለም። ዝ ውእቱ ሀገረ ጥዒና ዘአልቦ ምሳሌ። ይህ ዕረፍት ያለበት ነው። በንጽሐ ልቡና ጊዜ የሰውን ነፍስን መላእክትን አጋንንትን ከነግብራቸው ማየትን ገንዘብ ታደርጋለህ። ወትራኢ ነፍስ ነፍሰ ርእሰ ዚአሃ። ነፍስ መብል መጠጥን ሰውነቷን አታስብም። የሥጋን ህልውና ትረሳለች። **ድርሳን 10** ንጽሐ ልብ ላይ ስትደርስ መልአከ ዐቃቢህ ይገለጽልሀል። **ድርሳን 11** እስከ ስምንቱ ማዕርግ ድረስ ጻድቃን በመላእክት እጅ ይመራሉ። ከስምንተኛው ማዕርግ በላይ ግን ለመነኩሴው ይሰጠው ዘንድ ከፍጡራን ለአንዱስ እንኳ ክሂል የለውም። **ድርሳን 14** መዓርግ የሚሰጥ እንደ ሥራ እንደ ትጋት መጠን ነው። ሀገሪታ ይእቲ ሥጋ ለነፍስ። ብጹዓን ንጹሓነ ልብ እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር የተባለ በንጽሐ ልቡና ነው። እስመ ይሠርቅ ብርሃነ ሥሉስ ቅዱስ በውስተ ነፍስ። **ድርሳን 15** በንጽሐ ልቡና ፈቃደ ሥጋ ለፈቃደ ነፍስ ይገዛል። ፈቃደ ሥጋ ከፈቃደ ነፍስ ጋር አንድ ይሆናል። **ድርሳን 18** ንጽሐ ልብ ደክመው ስራ የሚሰሩባት አይደለችም። ትሩፋትን ወደው ያለ ድካም ይሰሩታል እንጂ። **መልእክት 47** በንጽሐ ሥጋ ግዙፋን ፍጥረትን በንጽሐ ነፍስ ረቂቃን ፍጥረትን በንጽሐ ልቡና ብርሃነ ሥላሴ ይታያል።

ሰይጣን

ድርሳን 6 ወእምከመ ርኢከ በውስተ ሕልምከ አክይስተ አው አቃርብተ አው ሰረቅተ አእምር ከመ ቀርበ ሰይጣን ለተጻብኦ። **ድርሳን 7** ሰይጣናት በአምሳለ አቃርብ ወከይሲ ወጽንጽንያ ይነስክዎ ለሥጋ ወየሐምምዎ ለሥጋ። ጽርሐ አጋንንት ከልብ በአፍዓ ነው የሚሰማው። የመንፈስ ቅዱስ ግን የሚሰማው በውስጥ ነው። የሰይጣን ግን ነገሩም ምትሐቱም በዓይነ ሥጋ በእዝነ ሥጋ እንጂ በዓይነ ነፍስ በእዝነ ነፍስ አይታይም። ቃለ መንፈስ ቅዱስ ቃለ መልአክ ግን በእዝነ ነፍስ የሚሰማ በልብ የሚታወቅ ረቂቅ ነው። የምግብ መዓዛ የሸተተህ እንደሆነ ሰይጣነ ስስት ሊዋጋህ እንደቀረበ እወቅ። በዚያ ቀን ምግብ ክፈል። **ድርሳን 8** ዝንቱሰ ሰይጣነ ጸሪፍ ይትናበብ ምስለ ነፍስ እንዘ ይሔምዮ ለእግዚአብሔር ወያመጽእ ኑፋቄያተ ላዕለ ምስጢራተ መለኮት ወላእለ እመ ድንግል ንጽሕት ወላዲተ አምላክ ማርያም ወይመስሎ ለሰብእ ከመ ለሊሁ ዘይነብብ እም ውስተ ልቡ እልክተ ጽርፈታተ ዓቢያተ። ስድቡ የእኔ መስሎህ አትደንግጥ አትጨነቅ የአንተ አይደለምና። አላ ትሰምእ ባሕቱ እም ኀበ ሰይጣን ዘይትናገር ዘንተ ምስሌከ እንዘ ለሊከ ኢትፈቅድ። እንዲደነግጥ የአንተ ነው በለው። ወከመዝ በሎ ያስተጋፍርከ እግዚአብሔር ኦ ሰይጣን ወከማሁ ግበር ለኩሎሙ ሕሊናት እለ እም ኀበ ሰይጣናት። ሰይጣናት የሰውን ሀሳቡን አያውቁምና። ይህ ሰይጣነ ጸሪፍ በምትጸልይበት ጊዜ

ጊዜ እግዚአብሔር ይሰማኝ ይመስልሀልን እያለ በአእምሮህ ያመጣብሀል። ሥጋውን ደሙን በሚለውጥበትም ጊዜ ይለወጥ ይመስልሀልን ሲቀበልም ቢሆን ያድነኝ ይመስልሀልን እያለ ያጠራጥርሀል። ይህ ግን የአንተ ስላልሆነ አትደንግጥ። ለሥነ ፍጥረት ፈጣሪ የለውም እያለ ሊያጠራጥርህ ይጥራል። አኮ አንተ ዘትጸርፍ ላእለ ፈጣሪከ ዘትሰግድ ሎቱ። ሰብሒ ኦ ነፍስ ፍቅርት እንዘ ኢትትሐወኪ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ዘይፈልጥ ስብሐታተኪ ንጹሐተ እምነ ጽርፈታቲሁ ለውእቱ ጉሕላዊ። አኮ ዘዚአኪ እማንቱ ጽርፈታት። ቀቢጸ ተስፋ አይሰማሽ የአንቺ አይደለምና።

ረድኤተ እግዚአብሔር፣ ተስፋ፣ ተአምኖ

ድርሳን 7 ኦ አኃውየ ፍቁራን ኢይትረከብ አሐዱ እም ውስቴትክሙ ዘይጸርፍ ወያንጎረጉር በጊዜ ምንዳቤ ወበመዋዕለ መከራ። አላ ይግድፍ ጎሊናሁ ላእለ እግዚአብሔር። **ድርሳን 9** ወለእመ ወደሱከ ሰይጣናት በውስተ ጎሊናከ ወአንቀልቀለ በልብከ ሁከተ ትእቢት ጸውዕ እግዚአብሔርሀ ለረድኤትከ ወተዘከር ኃጣውኢከ ሶቤሃ ይሰደድ ጸላኢ። ወይቴሐቱ ጎሊናቲከ ወይነጽሕ ልብከ። **ድርሳን 17** ሰው ሲበቃ በእርሱ አድሮ ያለ መንፈስ ቅዱስ ከደዌ ከመከራ የሚለምኑትን ሰዎች ያድናቸዋል ኃጢአታቸውን ያስተሰርይላቸዋል። **ድርሳን 18** ሀብታት ምስጢራት በትሩፋት ያይደለ በእግዚአብሔር ቸርነት ይሰጣሉ። ሕያዋን መላእክት በእግዚአብሔር ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። **ድርሳን 35** ወኢትትወከል ላእለ ብእሲ። **መልእክት 10** ንጸውዖ እንከ ለዕበየ ኃይልነ ከመ ይርድዐነ ወየሀበነ መዊዐ። ንክስት ድካመነ በቅድሜሁ። **መልእክት 21** ሚ ዕፁብ ወመንክር ብዝኀ ርኅራኄከ ኦ አምላክነ። **ድርሳን 6** አልቦ ግብር ዘየዐቢ እም ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እስመ ውእቱ ይቀጠቅጥ ኩሎ ጸብዐ። **ድርሳን 23** ወዘሰ ይገድፍ ጎሊናሁ ላእለ እግዚአብሔር ወኪያሁ ይሬሲ መሰረተ ለኩሉ ምግባራቲሁ እስከ ይከውን ባዕለ ፍጹመ በኃይለ ዚአሁ ለዘከመዝሰ አልቦ ዘይክል በርብሮተ ንዋዮ ወእመኒ ኖመ ለሊሁ ዐቃቢሁሰ ኢይነውም።

መስቀል፣ ጥምቀት፣ ጸሎት

ድርሳን 7 ግበር ትእምርተ መስቀል በጎሊናከ ውስተ መካነ ደዌከ። ወይትኀፈር በኃይሉ ለኢየሱስ ወይኅይይ ሰይጣን እምኔከ። **ድርሳን 29** ወበከመ አዳም ሥጋዊ ወለደ ሎቱ እም ሔዋን ደቂቀ በከመ አምሳሉ በዓለመ ዚአሁ ሥጋዊ ከማሁ ክርስቶስኒ አበ ዓለም መንፈሳዊ ይወልድ ውሉደ ዘከመ አምሳሊሁ እከርሰ ንሥሓ ወጥምቀት ለዓለመ ዚአሁ መንፈሳዊ። **ድርሳን 10** ሰይጣናት በምትሐት እንዳያታልሉህ ጸልይ። **ድርሳን 14** ከትሩፋት ሁሉ ጸሎት ትበልጣለች ከእግዚአብሔር ጋራ ባለሟል ታደርጋለች። በጸሎት ልብ ከእግዚአብሔር ጋራ አንድ ይሆናል። በጸሎት ሀብታት ምስጢራት ይገለጹለታል። ወባቲ ትትዋሐድ ነፍስ ምስለ ክርስቶስ። **መልእክት 11** ጸሎት ልብን የምታነጻ ናት። ጸሎተ ልቡና የእግዚአብሔርን ጌትነቱን አይቶ ተደሞ ነው።

ሥርዓት

ድርሳን 13 በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ሥርዓት ይህ ነው። ያልታዘዝነውን አለመሥራት የታዘዝነውን መስራት። የሚገባውን ብቻ መናገር እንጂ ብዙ ነገር ባይናገር። ዕርቃኑን የሚሰውር ተርታ ልብስ ቢለብስ። ለቁመተ ሥጋ ያሕል የሚበቃውን ቢበላ። የሚናገረውን ሰው ነገሩን አትከልክለው ሳታስጨርስ ፈጥነህ አትናገር። ሌላው ሲናገር አድምጥ እንጂ። ወኢይትፋዕ ምራቆ በቅድመ ሰብእ። በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ሳል ቢነሳበት ፊቱን መልሶ ይሳል። ከስስት ንጹሕ ሆኖ አፉን ከመቀባት በልብስ ከመዝራት ንጹሕ ሆኖ ተከናውኖ ይብላ። እጁን አራምዶ ከባልንጀራው ፊት አይቁረስ አንድም ቀድሞ አይቁረስ። ወለእመ ረፈቀ ውስተ ማዕዱ ምስለ እንግዳ ለያገብሮ ክልኤ ጊዜ አው ሠለስተ ከመ ይብላእ። ጸጥ ብሎ ይጉረስ ጸጥ ብሎ ይቁረስ። አፉን በከፈተ ጊዜ ይሸፍን ከመ ኢይርዐዮ መኑሂ። ወደ መምህሩ ቤት በገባ ጊዜ ከወዳጁ ዘንድ በሄደ ጊዜ በማገር የተሰቀለውን በቆጥ የተንጠለጠለውን እንዳያይ ተጠንቅቆ ሰውነቱን ይጠብቅ። ወበጎድአት አርጉ ኖኅተ ቤትከ። ወዕፀ በጽማዌ። ወኢያርጉ አንቀጸ ካልዑ ዘእንበለ ያስምእ ቃሎ። ወበንጹሕ ለይነጽር ኀበ ኩሉ። ወእመኒ ሖረ ፍኖተ ኢይብድር እምነ ዘይልሕቆ። ወሶበ ይሥሕቅ ኢይክስት ስነኒሁ። ለመናዘዝ ለመባረክ ወደ ሴቶች ሲሄድ ለይሚጥ ገጾ እምነ ርእየቶን በጊዜ ተናግሮቱ ምስሌሆን። ወያጥሪ አሐደ ዘይከሥት ሎቱ ምሥጢሮ። ወኢይክስት ገድላቲሁ ወምግባራቲሁ ወኢይፍታሕ ቅናቶ ዘእንበለ በዕውብ ግብር። አንበሳ መደብ ሲቀመጥ ከሰው ወገን የሚያየው አይኑር። ወሶበ ይብሎ ልሒቅ በፍኖት ነዓ ንዘምር አሆ ይበሎ። ነፍስ ከምትጎዳ ሥጋ ቢጎዳ ይሻላል።

ፍቅር

ድርሳን 15 አባ ጳኩሚስ በአንዲት ሴት አጋንንት ሰፍረውባት አየ ወደእኔ መልሰው ብሎ ጸለየ። በእርሷ ሰፍረውባት የነበሩት አጋንንት ወደ እርሱ መጡ ማቅ ምንጣፍ ለብሶ ከአመድ ላይ ተኝቶ ያማስናቸው ጀመር ከዚህ በኋላ እንሂድ እንጂ ሲሉ ሰማቸው። ቆዩ እንጂ አላቸው ከዚያ እየሸሹ ሄዱ። ድርሳን 24 የፍቅር አካሏ አካለ እግዚአብሔር ነው። ድርሳን 25 ለሰው ሁሉ በጎ ሲደረግለት አይቶ ደስ ለሚለው ጸጋ ክብር ይሰጠዋል። ወዘሰ የኀዝን በእንተ አሠንዮ ካልኣን ኢየኃጥዕ እኩየ ወፍጡነ ይከውን ድቀቱ። ዘይፈዲ ሰናየ ህየንተ እኩይ ያስተፈሥሖሙ ለመላእክት ወይኤድሞ ለእግዚኦሙ። እስመ ተመሰለ በፈጣሪሁ። ወዘሰ ይፈዲ እኩየ በእኩይ ዘየዐቢ እኩይ ይመጽእ ላእሌሁ። ድርሳን 33 ዘይቀውም በብሔረ ፍቅር ይደልዎ ይእቀብ ትእዛዛቲሁ። ወበፈጽሞቶሙኒ ይሁቦ ሠራኤ ትእዛዛት ቅድስተ ፍቅረ ወለተ ትእዛዛት። ፍቅርሰ ታረምሞ ለሥጋ ወለጎሊና። ሰው ሲበቃ እንደፈጣሪው ለሁሉ ያዝናል ይራራል። እርሱንም ሁሉ ይወደዋል። አበው ፍቅርን ዓለም ሐዲስ ይሏታል። ድርሳን 35 ወለእመ ርኢከ ብእሴ እንዘ ይገብር እኩየ ወእመቦ ዘተስእለከ መኑ ዘገብረ ዘንተ በሎ ኢጠየቁ። ለኩሉ ዘተስእለከ አውስእ ወዘአዘዙከ ግበር ለበቁኤተ ነፍስከ።

ትዕግሥት፣ ንሥሓ

ድርሳን 15 ሰይጣናት ሰውን ለማሳት መናደዳቸው ወደ መባረድ ቶሎ ይለወጣልና ታገሥ።

ድርሳን 26 ንሥሓ ይወልድ ውሉደ ሐዲሳነ እምውስተ ብሉይ። ወንጹሐነ እምነ ርኩስ። ወብሩሃነ እም ጽልመት። ሰናያነ ወጥዑማነ ወምዑዛነ እም ጺአት። መኑ ዘኢያነክራ ለአፍቅሮትከ ኦ እግዚእነ ዘመጻእከ ለተወልዶ ከመ ትለድ ኪያነ እም ከርሰ ንሥሓ። ስብሐት ለከ ኦ አበ ኩሉ ዘወሀብከነ ዛተ እመ ሐዳስ። ድርሳን 28 ኦ ነፍስ ተዐገሢ ሕማመ ወመቅሰፍተ ኀዘነ ወምንዳቤ እም ኀበ አጋንንት እለ ይገብሩ ፍትወቶሙ ላዕሌኪ ተወኪለኪ በእግዚአብሔር። ወበኩሉ ምንዳቤኪ ፍትሒ በጽድቅ ወበርትዕ ዲበ ርእስኪ ከመ አንቲ ኮንኪ ምክንያተ ለኩሎሙ። እንከሰ በፍሥሓ ተወከፊ ምረራተ ለፈውሰ ዚአኪ ወኢትሕምዩ ካልዓነ በቃል ወበኀሊና። ድርሳን 29 ንሥሓሰ እመ ሕይወት ይእቲ ብዑዕ ዘይትወለድ እምኔሃ እስመ ኢይመውት። መድኃኒቶሙ ወግእዛኖሙ ይእቲ ለአግብርት። ወበከመ ይጼውዖሙ ክርስቶስ ለእሊአሁ ኀበ ንሥሓ ከማሁኬ ሰይጣንኒ ወእለ ይትኤዘዙ ሎቱ ይርሕቁ እምኔሃ። ኩሎ ግብረ ጻማሁ ለሰይጣን ይእቲ ታማስን ወኩሎ ቅቱላኒሁ ይእቲ ታነስእ ወኩሎ መሣግሪሁ ይእቲ ትሰብር። ወታስተዴሉ ፍኖተ ለእለ ያፈቅርዋ ከመ ያንሶስው ዘእንበለ እቅፍት። ይእቲ ትራስዮሙ ለዘማውያን ደናግለ። ወታነጽሖ ለምድርነ እስከ ትሁብ ፍሬ ዘርእ ለሐረሳዊ ክርስቶስ ህየንተ አሐዱ ፴ ወ፷ ወ፻። ይእቲ ትመይጦሙ ለከሐድያን ኀበ ከዊነ ሐዋርያ። ወሐዋርያትኒ እለ አሰሰልዋ እም ላእሌሆሙ ለብሱ ጽልመተ። ይእቲ ትመልሓ ለዕፅ እንተ ፍሬሃ ሕምዘ ሞት። ወትተክል ዕፀ ሕይወት ውስተ ገነታቲነ። ንሥሓን ሰይጣን በጣም ነው የሚጠላት። እስመ ይእቲ ትነስእ ኩሎ ብእሎ። ወታማስን ኩሎ ጥሪቶ። አባ ያዕቆብ ከዓለም ባጠገብ ተባሕትዎ ይዞ ይኖራል። የንጉሡ ልጅ ታመመች አድንልኝ ብሎ ላከበት። እርሱም አጥምቆ አድኖ ሰደደለት። ደዌዋ ይመለስባታልና ከዚያው ከአንተ ዘንድ ትቆይ ብሎ ታናሽ ወንድሟን ጨምሮ ላከለት። በእርሷ ተሰነካከለ። ሰይጣን ትነግርብሀለች አለውና አስገደለው ወንድሟንም ይነግርብኛል ብሎ ገደለው ከዚያ 40 ዓመት በረሀ ወደቀ። ከዚያ ዝናብ አልዘንብ አለ ሕዝቡም ሁሉ ምሕላ ያዘ አባ ያዕቆብ ካልጸለየላችሁ አይዘንምም አላቸው። ነሣሒ ይትፈቀር በኀበ መላእክት ወይጸልእዎ አጋንንት። ቡርክት አንቲ ኦ እመ አድኅኖ። አንቲ ውእቱ ዘአድኃንኪዮ ለዳዊት እም ኃጢአት። መኑ ዘነስአኪ ምስሌሁ በውስተ ጸብእ ወኢያግረርኪ ጸላእቶ ታሕተ መከየደ እገሪሁ ኦ ንሥሓ። ሰዶም ዘኢፈቀደት ተወክፎተኪ ውዕየት በእሳት። ጸባብ ይእቲ ፍኖተ ንሥሓ ወባሕቱ ትወስድ ኀበ መንግሥተ ሰማያት። መልእክት 23 ጽናሕ እስከ የኀልፍ ክረምት ወአንተ ትራእዮሙ ለዕፀ ወ ሕይወት እንዘ ይጸግዩ በውሳጤ ገነታቲከ።

ተርእዮ፣ ከንቱ ውዳሴ፣ ሹመት፣ ርቀት

ድርሳን 23 ጥልቅ ባሕር ላይ ያሉ ዓሣት መታየትን ስለሚያበዙ አጥማጅ ይይዛቸዋል። ከጥልቅ ባሕር ያሉት ግን አይያዙም። መልእክት 18 ዕፁ እዘኪከ እም ቃለ ዘይቄድሰከ ቅድመ ገጽከ ወጉየይ እምኔሁ። ውስተ መፍቀሬ ሲመት ኢየኀድር እግዚአብሔር። ድርሳን 23 የነፋስ ርቀት በነፍስ ርቀት ዘንድ እንደተራራ ነው። የነፍስ ርቀት በመላእክት ርቀት ዘንድ እንደተራራ ነው የመላእክት ርቀት በሥላሴ ርቀት ዘንድ እንደ ተራራ ነው።

መዓርጋት፣ አምስቱ ተውላጣት

ድርሳን 24 ጽማዌ፣ ልባዌ፣ ጣዕመ ዝማሬ የንጽሐ ሥጋ ናቸው። አንብዕ፣ ኩነኔ፣ ፍቅር፣

ሐሰት የንጽሐ ነፍስ ናቸው። ነጽሮ መላእክት፣ ተሰጥሞ፣ ከዊነ እሳት የንጽሐ ልቡና ናቸው። ከበዓት ስትገባ ጽማዌ ይኖርሀል። **መልእክት 48** ወሶበ የኀልፍ እምኔከ ዝንቱ ተውላጥ ይመጽእ ድህሬሁ ልባዌ። ልባዌ ምሳሌ ያስመስላል ምስጢር ያስመረምራል። ወአስተታሉ ዝማሬ ወአንብቦ ወሰጊድ ቅድመ መስቀል። ከልባዌ መዓርግ በኋላ ልቡና ከዝንጋኤ የተለየ እንደሆነ ይመጽእ እም ድህሬሁ ውላጤ ካልእ ፍቅረ ዝማሬ ወአንብቦ። ወዓዲ እምድህረ አንብቦ ወዝማሬ ለእመ ኮነ ልብ ዕሩቀ እም ውዳሴ ከንቱ ይመጽእ ነቅዐ አንብዕ ወይሰግድ ቅድመ መስቀል ኩሎ ጊዜ። ይህም እንብ በግድ የሚፈስ አይደለም ማለት ላልቅስ ብሎ የሚያለቅስ አይደለም። ለማስቀረት በአናብዕ ላይ ሥልጣን የለውም። ወእም ድህረ ዝንቱ ሙኃዘ አንብዕ ይሠየሙ ውስተ ልብ ክልኤቱ ራዕያት ዘውእቶሙ ኩነኔ ወዐቃቤ። ኩነኔ ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ነው። ዐቃቤ በዚያው መጽናት ነው። ኩነኔ መደበኛ ዐቃቤ ጥገኛ ነው። የልባዌ ጥገኛ አንብቦ፣ የአንብዕ ጥገኛ ሰጊድ ቅድመ መስቀል፣ የኩነኔ ጥገኛ ዐቃቤ፣ የሐሰት ጥገኛ ብርሃን/እሳት ነው። ሐሰት የሚለው እንደ እግረ ፀሐይ ካሰቡት ሁሉ መገኘት ነው። ከዚያ ነጽሮ መላእክት ይሰጣል ዝማሬያቸውንም ይሰማል። ከዚያ ተሰጥሞ ብርሃን ይሰጣል ከዚያ ከዊነ እሳት ይሰጣል። **አምስቱ ተውላጣት፦** ሙኃዘ አንብዕ ዘያስተፈስሕ፣ ሙኃዘ ንባብ መንፈሳዊ፣ ሞት መንፈሳዊ፣ ዘኢይጸሐፍ በመጽሐፍ፣ ምግባረ ኅሊና ቀዳማዊ ከመ ኃምሳዊ ናቸው። ሰው በከዊነ እሳት መዓርግ በደረሰ ጊዜ በወትሮ መልኩ አይታይም ከእግር እስከ ራሱ ድረስ እሳት ይመስላል። ይከውን ምግባረ ሕሊና ቀዳማዊ ከመ ኃምሳዊ። በዚህ መዓርግ ጊዜ የመጀመሪያው የጽማዌ ስራ እንደ አምስተኛው እንደ ኩነኔ ይሆናል። ከዚህ መዓርግ በኋላ ሙኃዘ አንብዕ ዘያስተፈሥሕ ይሰጣል። ከዚያ የውኂዘ ንባብ መዓርግ ይሰጣል።

ክርስቶስ

ድርሳን 24 ዮሴፍ ጌታን በሕጻንነቱ ሳለ እንደመጠኑ ወንበር አድርጎ ከፊቱ ያስቀምጠው ነበር። አዋልደ ዮሴፍም ጌታን እኔ ልያዝ እኔ ልያዝ ይነጣጠቁት ነበር። በእጁ የታቀፈውም ሰው በግድ ካልሆነ ወዶ ለአንዱ አይሰጠውም ነበር። በክንዱ ያቀፈው ሰው ሁሉ መዓዛው ከልብሱ ተዋሕዳ ትኖራለች።መኑ ዘርእዮ ወኢተፈሥሐ ወኢረስአ ኩሎ ትካዘ ልቡ።መኑ ዘእም አንስት ዘሞተ ፍቁራ ወኢረስዐት ምውተ ዚአሃ ሶበ ርእየቶ ጊዜ ናዕሱ። ርእየቱ ይሰድድ ምንዳቤያተ። ወድምጸ ቃሉ ይመልሕ ሕማማተ እም ውስተ ልብ። ሁል ጊዜ ጌታን ለማየት ያልሳሳ ያልናፈቀ የለም። ኩሎሙ እለ ርእይዎ ይትሐሰዩ በርእየቱ። **ድርሳን 34** ተወልደ በአምሳሊከ ከመ ይለድከ በአምሳሊሁ።ጾመ ከመ ይምህርከ ሥርዓተ ተጋድሎ ወመዊእ። ተሣለቁ ላእሌሁ ከመ ትትወደስ ለሊከ። **መልእክት 22** ኦ እግዚኦ ኩለንታከ ውስተ ኩሉ መካን። እሳት በዚህ ዓለም በምላት ሳለች ያለ እንጨት ያለ ኩበት አትገለጽም። እግዚአብሔርም በሁሉ ያለ ሲሆን የሚገለጸው በምግባር ነው። **መልእክት 47** ወኩሎ ዘፈጠረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተገብሮ ወኩሎ ፈጠረ ለነጽሮ ወለዘክሮ።

ዜና አይሁድ

ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እንደጻፈው። የአፍራቅያው ንጉሥ አእሳስም ለሚስቱ ለምሕያ ከነበረችበት

ቦታ እስከ ቤተ መንግሥቱ ቅርጣግና የውሃ መውረጃ ቦይን አስቆፍሮ ሰራ። ተርክዮሽ የሚባል ንጉሥ በሮም 35 ዓመት ነገሠ። ከሮማውያን ሴቶች መካከል የሌላ ወንድ ሚስት ስለወደደ አስገድዶና ከባሏ ነጥቆ ከወሰዳት በኋላ ከብስጭት የተነሳ የገዛ ሆዷን በጩቤ ተርትራ በገዛ ራሷ ሞተች። ይህንን የተረዱት አባቷ ባሏ እና ወንድሟ ተርክዮሽን በምኩራብ መግቢያ ተደብቀው ጠበቁትና ገደሉት። ከዚህ የተነሳ የሮም ሰዎች ሲነግሡ አመጸኞች ይሆናሉ ስለዚህ ንጉሥ አያስፈልገንም አሉ እና እንዳያነግሡ ተማማሉ። ከመካከላቸው አንድ ሰው መረጡና ንጉሥ ሳይሉት ሽማግሌ ብለው ሰየሙት። በእርሱ የሚመሩም በስነ ምግባር የተመሰከረላቸው 320 ሰዎች መረጡ በዚህም መንግሥትን ሠሩ። ሐማ እስራኤላውያንን ጨርሶ እስከ ማጥፋት ፈልጎ የነበረው ሐማ አማሌቃዊ ነው። በሳኦል ዘመን አማሌቃውያንን በእግዚአብሔር ትእዛዝ አጥፍተዋቸው ነበር። እና የጥላቻው ምንጭ ይህ ነው። ሐማ ንጉሡ አይሁድን የሚጠላበትን መንገድ ይፈላልግ ጀመር። የእስክንድርን አባት ንጉሡ ፊልጶስን የገደለው ከበታቹ ያለ የመንግሥት ባለስልጣን ነው የፊልጶስን ሚስቱን ወዲት ነበረና። የእስክንድርን እናት ሊያገባ ፈልጎ ነው። እስክንድርም የአባቱን ገዳይ ፋራስን ገደለው። እስክንድር ሲነግስ የ20 ዓመት ወጣት ነበረ። ጥበበኛና አስተዋይ ነበረ። ያስተማረውም እውቁ ፈላስፋ አርስጣጣሊስ ነው። እስክንድር ፈሪሀ እግዚአብሔር ነበረው። ድፍረቱም የሚገርም ነበር። የደራ ሰራዊት እስክንድርን ስለፈሩት ንጉሣቸውን ገድለው እስክንድርን ሊታረቁት ፈለጉ። እስክንድር ግን ደራን የገደሉ ወታደሮችን አስገደላቸው። ጠላቱን ግን አልቅሶ ቀበረው። በክብር እንዲቀበርም አደረገ። ለቤተእግዚአብሔር ሁል ጊዜ በየዓመቱ ብዙ ገንዘብ ይሰጥ ነበር። በቤተ መቅደስ ዙሪያ ለሰፈሩ ነዳያንና ምስኪናን ምግብ ይሰጥ ነበር። ለካህናትና ለሌሎች የቤተመቅደስ አገልጋዮችም ፍላጎታቸውን ያሟላ ነበር። እስክንድር በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በራሴ ፈቃድ የማደርገው የለኝም ይል ነበር። ዓለም በሥርዓት እንድትመራ እግዚአብሔር ፈቅዷል። እስክንድርን ወታደሩ በመርዝ ገደለው ቂም ነበረበትና። አባቱ ፊልጶስ የመቄዶንያ ንጉሥ ነበር። እስክንድር አይሁዶችን ይወድ ነበር እግዚአብሔርንም ይወድ ነበር። መቄዶንያ የዮናናውያን ይዞታ ነው። እኒህ ደግሞ የያፌት ወገኖች ናቸው። አንትያኮስ አምላክ እኔ ነኝ አለ። አይሁድ ግን አንሰግድልህም አሉት። በአይሁድ የቤተ መቅደስ ካህናት የነበሩ መባልስ ስምዖንና ኤልፊሞስ ግን ሹመትን ፈልገው አይሁድ ለአንተ አይሰግዱም አሉት። አንቲያኮስም ከአይሁድ ብዙ ሰው ገደለ። እነዚህ ከሀድያን አመጸኞች ካህናት ነገር እየሰሩ ወገኖቻቸውን ማስፈጀት ሥራችን ብለው ተያያዙት። አረጋዊው ካህን አልአዛርን አስገደሉት። አንቲያኮስ ካስገደላቸው ሰባት ወንድማማቾች አንዱ "ንጉሥ ስለሆንክ ለቤተ መንግሥትህ እንድንገዛ ብታዘን እንገዛለን እንታዘዛለን አንተን ግን አናመልክህም የሚመለከው እግዚአብሔር ብቻ ነው ለፍጡርም አንሰግድም ፍጡርም አናመልክም" አለው።አንቲያኮስም እጁንና እግሩን ቆረጠው። ሌላኛው ወንድም "እግዚአብሔር የተወን አይምሰልህ ለአንተ በሥጋችን ላይ ሥልጣን ሰጠህ ዘላለማዊውን ክብር እኛን ያጎናጽፈናል" አለው። ከሰባቱ ስድስቱ ተገለው ሰባተኛው ሕጻን ልጅ ሊገደል ሲል እናታቸው መጣች ግን አልደነገጠችም ሰባተኛው ሕጻኑን ልጅ እንዲያጸናው ትጸልይለት ነበር። እንዲህም አለች እግዚአብሔር ለእናንተ የሚበጀውን ያውቃል እኔ ስለ እናንተ የሚጠቅመውን አላውቅም አለች። በጣም በእናንተ የተደሰትኩት ዛሬ ነው አለች። አንጥያኮስ እናታቸውን ባየ ጊዜ ትንሹን ልጇን እንዳይገልባትና ብቻዋን እንዳትቀር

እግዚአብሔርን ክዶ ለአንጥያኮስ ሰግዶ እንዲተርፍላት ምክሪው አላት። እርሷም ልጄን ስጠኝና ለብቻየ ልምከረው አለችው። ከዚያ ልጇ ሲጠጋት ልጅ ሆይ ከሁሉ አብልጬ እወድሃለሁ ስማኝ ሕገ እግዚአብሔርን ያስተማርኩህ እኔ ነኝ። እግዚአብሔር ሰውን በዚች ዓለም የፈጠረው ትእዛዙን ያከብር ዘንድ ነው። ከዓለም በሞት ሲለይም ወደ እግዚአብሔር ይሄዳል። እግዚአብሔርም መልካም ለሰራ መልካምን ያድለዋል ክፉ ከሠራ ደግሞ ለመከራ ይዳርገዋል። ስለዚህ ይህን ጣዖተኛ ንጉሥ አትፍራው ከግርማው አትደንግጥ በትእዛዘ እግዚአብሔር ጸንተህ ሙት ወንድሞችህ የተቀበሉትን ሞት ሙት ከዚያ ወደ ዘላለም ደስታ ትሄዳለህ ለቅጽበተ ዓይን ጊዜ ያህል እንኳ ልቡናህ ከእግዚአብሔር አይራቅ አለችው። ሕጻኑም ንጉሡን አንተ በእኛ ላይ ብትከፋ ለነፍስህ ይተርፋል መልካም ብታደርግም እንዲሁ አለው። ንጉሡም ተናዶ እናትና ልጇን ገደላቸው። አይሁዳውያንን ያስፈጃቸው ይሁዲነቱን ክዶ ከዮናናውያን ጋር ያደረ አይሁዳዊ ነው። በኋላ ግን እርሱም ሞተ። አይሁድ ስለ ሃይማኖታቸው እየተዋጉ መሞትን ይፈልጉ ነበር። አይሁድና ዮናናውያን ጦርነት ሲገጥሙ ከሚዘረፈው ንብረት በርካሽ ለመግዛት አብረው ወደ ጦርነት የሄዱ ነጋዴዎችም ነበሩ። አንትያኮስም ከባድ ሕመም ታሞ ሞተ። የአይሁዱ ንጉሥ ይሁዳ አንትያኮስን ካሸነፈ በኋላ አንቲያኮስ የሰራቸውን ጣዖታት አፈረሰ የእሪያ ሥጋ የተሰዋበትን ምሥዋእም አጠበው መቅደሱንም አጸዳው። አዲስ መሠዊያንም ሰራ። መሥዋእትም ሰው ህዝቡም ለተከታታይ ሳምንት በዓል አደረገ ይህች በዓል በዓለ ሕንክ ትባላለች። ከስሉ በሚባል ወር በ25 ቀን የምትከበር በዓል ነበረች። በዓሉ ቋሚ ሆኖ ለብዙ ዘመናት ኖሯል። ነገደ ካይተም የሚባሉት በሮምና በአካባቢዋ ይኖሩ የነበሩ ናቸው። እስራኤል መጀመሪያ ችግር ሲደርስባቸው ይጾማሉ ይጸልያሉ ከዚያ ጦርነት ይገጥሙና ያሸንፋሉ። እግዚአብሔር ይረዳቸዋል። ከዚያ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር በሙሉ ምስጋናን ያቀርባሉ። 3ቱን ነገረ ሰሪዎች ነገር የሚሰሩለት ሰው አስገደላቸው። ንጉሡ ለበቀል እንዲነሳሳና እንዲወጋቸው የሚገፋፋ ሁኔታንና ብዙ የማስመሰል ተንኮልን ተናገሩ ብዙ ሴራ ሰርተው ሞቱ። አይሁድ በበዓለ መጸለት በቤተ መቅደስ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ይዘፍኑ ነበረ።በኋላ አይሁድ ለሦስት ተከፈሉ እኒህም የፈሪሳዊ ቡድን፣ የሰዱቃዊ ቡድን፣ እና የምትእዝላ ቡድኖች ናቸው። አንደፈር አይሁዳዊ ሲሆን ከካህኑ ዕዝራ ጋራ ከባቢሎን ከተመለሱ አይሁዶች አንዱ ነው። አንዲት እናት ልጇ በሆዷ እያለ ስለሞተች ሙታ እያለ ልጇ በሆዷ ይንቀሳቀስ ነበረ። ስለዚህ ብልሀተኞች የሞተችውን ሴት ሆድ ቀደው ሕጻኑን አወጡት ጤናማም ሆኖ ወጣ ስሙንም ቁሳር አሉት በእነርሱ ቋንቋ የሚቀድ የሚሰነጥቅ ማለት ነው። ሲያድግ እጅግ በረታ 320ውን መማክርትና ሸማግሌውን ገድሎ የመጀመሪያው ቁሳር ሆነ። ሄሮድስ የአንደፈር ልጅ ነው በመስፍንነት በገሊላ ላይ ሾመው። ሄሮድስ የገሊላ መስፍን ሆኖ ሲሾም የ15 ዓመት ልጅ ነበረ። በኋላ ቁሳርን ሁለት ታላላቅ ባለስልጣናት ገደሉት። ከቁሳር ቀጥሎ የወንድሙ ልጅ አውግስጦስ ነገሠ። በዚህ ዘመን ጌታችን ተወለደ። ሄሮድስ ሊቀ ካህናቱን አርስተቦሎስን በሠራዊቶቹ አስገደለው። ሠራዊቱ ዋና ሲጫወቱ እየዘፈኑ እየዋኙ ሳለ ሄሮድስ አርስቶቦሎስን ወደ ውሃው ውሰዱትና በማስጠም ግደሉት ብሎ በምስጢር ነገራቸው እንዳላቸውም አደረጉና የገዛ ራሱ ዋና ሳይችል ቀርቶ እንደሞተ አስመስለው ሬሳውን አወጡ። ሕዝበ አይሁድም በሱ መሞት እጅግ አለቀሱ አዘኑ። ሄሮድስም አለቀሰ። ሄሮድስ እስክንድራንና ልጇን ለመግደል አመቺ ጊዜ እየጠበቀ በአፉ ግን እጅግ የተለሳለሰ አኳኋን ያሳያቸው ነበር። የሄሮድስን ዲስኩር

ሲሰሙ የአይሁድ ወንዶች በስሜት ለጦርነት ተነሱ ለሄሮድስም ወደኋላ እንደማይሉ ቃል ገቡለት። የእስክንድራ ልጅ ማርያም አንደበተ ርቱዕ የማትዋሽና አድርባይነትን የማታውቅ ነበረች። ሕሊናዋ ንጹሕ ሃይማኖቷ የቀና ሰውን በስድብ የማታስቀይም ነበረች። ለትዕቢተኛ ግን ራስን ዝቅ ማድረግ አትወድም ነበር። ከዚህም የተነሳ ሄሮድስን በሚፈጽመው አረመኔያዊ ተግባር ትዘልፈው ነበር። የሄሮድስ እህት ትጠላት ነበርና የሌለ ውሸት እየነገረች ሄሮድስ እንዲገላት ትፈልግ ነበር። አንድ ቀን ባሌን አማገጠችብኝ አለችው ሄሮድስ ግን ማርያም የአመንዝራነት ጠባይ እንዳልነበራት ያውቅ ነበርና ከዚህም ሌላ በሰበቡ እንዲገድልላት ትፈቅድ እንደነበር ያውቅ ነበርና እህቱን አልሰማትም። የሄሮድስ እህትም ዓላማዋን ለማስፈጸም ሩጫዋን ቀጠለችበት። ለብዙ ሰዎችም እንዲዋሹላት ብዙ ገንዘብ ትሰጣቸው ነበር። ለነገር አቀባዩዋም መርዝ ሰጥታ ለሄሮድስ አሳየው በምግብ ጨምሬ እንዳበላህ ማርያም ሰጠችኝ በለው አለችው። እሱም ይህን አደረገ ሄሮድስ በዚህ እጅግ ተናደደና ማርያምን እስር ቤት አስገባት። እህቱ ግን ሴራዋ እንዳይታወቅባት ከሌሎች መስተዋድያን ጋር ሆና ተሳዳቢ ዘማዊት ሥነ ሥርዓት የሌላት ናት አሁኑኑ ትገደል በማለት አዋከቡት። በዚህ ጊዜ እርሷን ለእናንተ አሳልፌ ሰጥቻለሁና የፈለጋችሁትን ፈጽሙባት አላቸው እነርሱም ገደሏት። ከመግደላቸው በፊት ግን አንቺ አመንዝራ እያሉ ባላደረገችው ሰደቧት። እርሷ ግን ዝም አለቻቸው ለማንም መልስ አልሰጠችም ፊቷንም አልከፋትም ህሊናዋም አልታወከም ፍጹም ፍርሀት አልታየባትም እንደ ወገኖቿ በጥብዓት ታየች እንጂ ያለፍርሀት አንገቷን አመቻችታ ሰጠቻቸው። ኤዶማውያን በሄሮድስ ዘመን ይገረዙና የአሪትንም ሕግ ያከብሩ ነበር። ሀገረ ሳምርን ሄሮድስ አቅንቷታል ሳብስጥያ የሚል ስያሜም ሰጣት። ሄሮድስ በአይሁድ የተሾመ አይሁዳዊ ነው። አዛዡ የበላዩ ግን የሮሙ ንጉሥ ነበረ። ሄሮድስ ታላቅ ቤተ መቅደስንም ሰራ። የሄሮድስ ሚስቱ በእጎቱ ያስገደላት ማርያም ነበረች። የባሕርን ውሃ ነፋስ እንደሚያውከው የሰውን ልብ ነገር ያውከዋል። የጨዋታና የቀልድ ብዛት ምስጢርን ያባክናል። አንደፊር በአፉ መልካምን እየተናገረ በወንድሞቹ ላይ ነገርን ከመጠንጠን አላረፈም ነበር። ሲያገኛቸው ትህትናን የተላበሰ በመምሰል የክብርና የመንድማማችነት ቃል ያሰማቸው ነበር። በሐሰትና በስብቀት በመስተዋድይነትም የተካኑ ሰዎችን አዘጋጅቶ ሐሰቱን እውነት በማስመሰል ከሄሮድስ ጋር እንዲያጣሏቸው ወደ ሄሮድስ ላከባቸው። ሄሮድስ ግን የነገረ ሰሪዎችን ስብቀት ሰምቶ እነዚህን ልጆች ከማፍቀር አልቀነሰም። አንደፊር ፍሩዳ የተባለውን የአባታቸውን ወንድምና የአባታቸውን እጎት ሰሎሚትን በሽንገላ መንገድ እንዲጠመዱ አደረገ። እነዚህም ለሄሮድስ እስክንድርና አርስቶቦሎስ አንተን ለመግደል እየተዘጋጁ ነው። አንደፊርንም ሊገድሉት ተዘጋጅተዋል በማለት ነገሩት። ሄሮድስ ወንድሙ ፍሩዳ እውነተኛ ነው ብሎ ያምን ስለነበር ነገራቸውን አመናቸው። አንደፊር የሚባል የሄሮድስ ልጅ ነበረው። ተንኮለኛ ነበር ሊገደል በሰይፍ ፊት ቆሞ እንኳ ብዙ ውሸት ተናገረና ውሸቱ እውነት እንዲመስል እንደ እውነተኛ ሰው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ህዝቡም የተናገረው ውሸት እውነት መስሎት አለቀሰ። ሄሮድስ ከሞተ በኋላ አርከላኦስ ዳግማዊ ሄሮድስ ተብሎ ነገሠ። ቀዳማዊ ሄሮድስ እንደሞተ ታፍኖ የኖረው ሕዝብ በሚቹ ሄሮድስ ላይ የነበረውን ጥላቻ በመግለጽ ተነፈሰ በየአደባባዩ እየወጣም ገለጸ። አርከላኦስንም ልትነግሥ አይገባህም የአረመኔ ልጅ ነህና አሉት። አርከላኦስም ብዙ ተቃዋሚዎችን ገደለ። በዚህም ምክንያት አውግስጦስ ቄሳርን ከአይሁድ ወገን ያልሆነ እንዲያነግሥላቸው ለመኑት። አርከላኦስ

ግን ከከሳሾቹ ይልቅ ተቀባይነትን አግኝቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። 7 ዓመትም ገዝቶ ሞተ። በኋላም አውግስጦስ ቄሳር የዳግማዊ ሄሮድስን ወንድም የቀዳማዊ ሄሮድስን ልጅ አንጠሬስን ሄሮድስ ብሎ ሾመው። ይህም ሄሮድስ ክፉ ገዢ ሆነ አመንዝራም ሆነ ወንድሙ ፊልጶስ በሕይወት እያለ ሚስቱን ሄሮድያዳን ቀማው። የወንድሙን ሚስት በመቀማቱ የአይሁድ ታላላቅ ሰዎች ቢቃወሙት ገደላቸው። መጥምቁ ዮሐንስንም ገድሎታል። ከፊልጶስ ሚስት ሄሮድስ ሁለት ልጆችን ወልዷል። አይሁድ ዮሐንስን ይሕያ ይሉታል። ክርስቲያኖች ደግሞ ዮሐንስ ይሉታል። ይህ ሣልሳዊ ሄሮድስ ሞተ የወንድሙ ልጅ አግሪጳም ነገሠ። ቀዳማዊ ሄሮድስ ብዙ ክፉ ስራ እንደሰራ ሁሉ ጥቂት መልካም ስራም ነበረው ሀገሪቱን ከግብጽ እህል ገዝቶ ከረሀብ ታድጓል። እንጀራን እያስጋገረም ደካሞችን አብልቷል ማየት የተሳናቸው እጅ እግር የሌላቸው ሁሉ በሄሮድስ ዘመን ቀን ወጥቶላቸው ነበር። ወጣቶች ደግሞ በጉልበታቸው ዕለታዊ ቋሚ ስራን እየሰሩ በረሀብ ዘመኑ ምግባቸውን እንዲያገኙ አድርጓል። አይሁድና አሕዛብ በዚህ ተግባሩ ብዙ አመስግነውታል የአካባቢው ሀገሮች መንግሥታትም አድንቀውታል። አውግስጦስ ቄሳር ሲሞት ክፉው ጢባርዮስ ቄሳር በሮም ነገሠ። ጢባርዮስ ቄሳርም ሞተና ኔሮን ቄሳር ነገሠ። ይህ ኔሮንም ሰዎች ሁሉ አምላክ እንዲሉት አዘዘ። ሲምሉም በስሙ እንዲምሉ አዘዘ። መሥዋዕት በስሜ አቅርቡልኝ አለ። አህዛብ ሁሉ እሺ አሉ። አይሁድ ብቻ ተቃወሙ ኔሮን በአይሁድ ተቆጣ አይሁድም ጾመው ጸልየው ከበቡት ከዚያ አንገቱን ቆረጡት አካላቱን በሙሉ ቆራርጠው ጣሉት። ሥጋውንም ውሾች በሉት አልተቀበረም። ከእርሱ ቀጥሎ ቀላውዴዎስ ቄሳር ነገሠ እርሱም ጣዖታትን አፈራረሰ። ከእርሱ ቀጥሎ ሌላው ኔሮን ቄሳር ነገሠ። በዚሁ ዘመን በአይሁድ ሀገር ጠብ ትርምስ በዛ በሀገረ ሮማንያም እንዲሁ በዛ። ክፋት አመጽ ትእቢት መርገምና ዝሙት ከእርስ በእርስ መገዳደል ጋራ ሰፈነ። ሰዎች የሌላውን ንብረት እየሰረቁ መሸጥ የሌሎችን ሚስቶች በአመጽ መድፈርና ሌላም የመበጣበጥ ድርጊት በየቦታው በዛ። ማንም በነጻነት መንቀሳቀስ የማይችል ሆነ። የውንብድና ተግባር ብቻ ተጧጡፎ እውነት ጠፋ። ይህን ከሀገረ አይሁድ ለማስቀረት የቄሳሩ ሹም አስባስያኖስ መጣ እርሱንም ተከትሎ ጥጦስ መጣና ሀገረ አይሁድን ደመሰሰ። ቤተመቅደስንም አፈረሰ። አይሁዶች የእርስ በእርስ መገዳደል ሰፍኖባቸው ኖሩ ማንም ሰው በየኪሱ ጩቤን እየደበቀ መግደል ሆነ። ለውንብድና የተሰማሩትን በገንዘብ እየገዙ እገሌን ግደልልኝ የሚሉ የሚያስገድሉና ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ሰዎች በዙ። ሰላማዊ በመምሰል አንዱ ወደ አንዱ በመጠጋት በሹል ብረት መግደል እንደ ባሕል ሆነ። የገደለው ሰው ወዲያው በሰው መሐል ይገደላል። የቸገራቸው ሰዎች ይህን ሞት "እውር ሞት" በማለት ሰይመውታል። በየደረጃው የተለያየ ትምህርት ጥበብና ሙያ ያላቸው ሰዎች እገሌ ገደላቸው ባልተባለ ሁኔታ ደማቸው በከንቱ ፈሰሰ። ከህዝበ አይሁድ ብዙዎች የሕይወት ዋስትና አለመኖሩን ሲያዩ ሴቶችንና ሕጻናትን ከሀገር አስወጥተው ከሀገር ውጭ እንዲቀመጡ አደረጉ። ጴጥሮስና ጳውሎስን የገደላቸው ኔሮን ዳግማዊ ነው። በኔሮን በ13ኛ ዓመት ዮሐንስ ወንጌሉን ጻፈ። ልብ ብሎ ማድመጥ ወደ መልካም ቁም ነገር ይመራል። ሀገር ሲበጠበጥ ደስ የሚላቸው ሰዎች አሉ። ብዙ የሮም ነገሥታት ለአይሁድ ቤተ መቅደስ አምኃ መስጠትን አስለምደው ነበር። ጥጦስ የቄሳር ታማኝ የአስባንዮስ ልጅ ነው። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የአይሁድ ካህን ነበረ። ለእግዚአብሔር ትእዛዝ መሞት አያስፈራኝም ይል ነበር። ማንም ሰው ሕይወቱን በገዛ ራሱ እንዲያጠፋ የእግዚአብሔር

ፈቃድ አይደለም ይል ነበር። ሕይወቱን በእጁ የሚያሳልፍ የአእምሮ ድክመት ያለውና ማስተዋል የጎደለው ነው። ኔሮን ቄሳር ሲሞት አስብያኖስ ነገሠ። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የአስባንዮስ ልጅ የጥጦስ አማካሪ ሆነ። አይሁድ ለሦስት ተከፍለው ማለትም አልአዛር ስምዖን ሐናን በሚባሉ ቡድኖች ተከፋፍለው ይጨፋጨፉ ጀመር። ሀገሪቱ ሬሳ በሬሳ ሆነች። ሬሳው አልቀበር ስላለ ከበድኑ የሚወጣው ሽታ ከዚሁም በሚነሳ ወረርሽኝ ሕዝቡ አለቀ። ሰው በደም እየተንሸራተተ ይወድቅ ነበር። ጦር ቃጠሎ ረሀብ የሕዝቡ እድል ሆነ። ልቅሶ ዋይታ ሰቆቃ የሕዝቡ የዕለት ከዕለት እጣ ፈንታ ሆነ። አይሁድ የቂጣ በዓልን ለማክበር መሳሪያቸውን በየልብሳቸው ውስጥ ደብቀው ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ እርስ በእርስ ለመገዳደል ማለት ነው። አይሁድ በመካከላቸው ባለው ጠብ ደክመው የጥጦስን ተንኮል አልተከታተሉትም። ጥጦስም ገብቶ አሸነፋቸው። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንም "ክፋትን ሁሉ አድርጋችሁ ከእግዚአብሔር ረድኤትን ለምን ትጠብቃላችሁ አላቸው? የረከሰውን ስነ ምግባር ተይዞ ከእግዚአብሔር ረድኤትን መጠበቅ አይቻልም። በየጊዜው ብዙ ሽንፈቶች በሕዝበ እስራኤል ላይ ተከስተዋል ብዙ ድሎችም ተመዝግበዋል። ሶምሶን ሳይበድል ኃይለኛ ነበረ ሲበድል ግን በጠላት እጅ ወድቆ እንደ ሴት ባሪያ እህል እየፈጨ ኖረ። ሳኦል በእግዚአብሔር አጋዥነት ጠላትን አሸነፈ እግዚአብሔርን ካስቀየመ በኋላ ግን በጠላት እጅ ወደቀ። ዳዊትም እግዚአብሔርን በማስቆጣቱ ከልጁ አቤሴሎም ጋር ተጋጨ። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን "አባቶቻችን አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ሰላማውያን ሆነው በእግዚአብሔር ስለተመሩ ሁሉን አሸነፉ የእኛ መሰረቶች እነርሱ ነበሩ። በእነርሱም ምግባር ልንመራ ይገባናል። እነርሱ በአካባቢያቸው ከሚኖሩ አሕዛብ ጋር እየተስማሙ ይኖሩ ነበር። ለግብጻውያን የታዘዙበት ጊዜ አለ። ለሮም ነገሥታት የታዘዙበት ጊዜ አለ። ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ አላስወቀሳቸውም" እግዚአብሔር ያመጣውን በአኩቴት ተቀብሎ መኖር ይመረጣል አላቸው። በዚህ ዓለም አንዱ ክፍል ዓለምን ተቆጣጥሮ ለተወሰነ ጊዜ ሊቆይና ለጊዜው ደግሞ እርሱ ሲወድቅ ሌላው ይተካል። እናንተ በብዙ ነገሥታት ላይ እንድትሰለጥኑ የሆነበት ጊዜ ነበረ። የተገዛችሁበት ጊዜም ነበረ አላቸው። ሮማውያን ላለንበት ዘመን ዓለምን እንዲይዙ ፈቅዷል አላቸው። ከአቅም በላይ ለሆነው እየተገዙ መኖር ነውር አይደለም። የሕዝቅያስ ጸሎት የሰናክሬምን ሠራዊት አስወገደ። ሴዴቅያስ የነቢያትን ምክር አልቀበል ብሎ ለውድቀት ተጋለጠ። አሁን ግን የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ አይደለም ያላችሁት አላቸው። በእናንተ ጽናትና ኃይል ጠላት አይሸነፍም። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ካልሆነ ጥቅም የላችሁም። የእርስ በእርስ መላላታችን በእኛ ላይ መቅሰፍትን አመጣ አላቸው። እግዚአብሔርን አስቀይሞ ድልን የተቀናጀ የለም። ጥጦስ ለአይሁድ በጎ ነገርን ያስብ ነበር። አልዓዛር ስምዖንና ሐናን ግን ጥጦስን ለማበሳጨት ሐሳቡን ለውጦ እስከ መጨረሻው ድረስ አይሁድን እንዲጠላና እንዲጨፈጨፉ ለማድረግ የቻሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። ከጥጦስም ብዙ ሠራዊት ገደሉበት እርሱም ኢየሩሳሌምን አስከበባት። ረሀብ ጸና ያገኙትን ጥንብ ሁሉ መብላት ጀመሩ። ትንሽ ስንዴ ያለችው ሰው ከተገኘ ያችን ለመውሰድ ይገድሉታል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው እህል ቢኖረው ሲፈጭ ወይም ሲጋግር እንዳይታይና እንዳይሰማ በጥሬው ብቻ መብላቱን መረጠ ዱቄት ያለውም ቢሆን ዱቄቱን ይቅመው ነበር። አባት ከልጁ ልጅ ከእናቱ እናትም ከልጇ ቀምቶ መብላት የግድ ሆነ።ሕያዋን ሙታንን ለመቅበር እጅግ ተቸገሩ ቀብረውም ለመጨረስ አልቻሉም። አየሩ በጠቅላላ ተመረዘ በሕይወት

የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ደስም ያሉትን ሲሞቱ እንዳያስቸግሯቸው ከነ ሕይወታቸው ባገኙት ጥልቅ ጉድጓድና አዘቅት ይከቷቸው ነበር። ሌሎች ደግሞ ለታመሙት መቃብር ይቆፍራሉ ህይወታቸው እያለች ከመቃብሩ ላይ ተኝተው ህይወታቸው እስክታልፍ ይጠባበቁ ነበር። በከፍታማ ቦታ ከነሕይወቱ የተገኘ ሰው ከእርሱ በጉልበት የተሻለ ከመጣበት ገፍትሮ ወደ ገደል ይጥለዋል። የሚጠጣው ውሃ ሁሉ በሰው ሬሳ የተበከለ ሆነ። የእንስሳትን ፋንድያ እበት መብላት ጀመሩ። የሠረገላቸውን ቁርበት በልተው ጨረሱ። የሰይፋቸውን መያዣ ሁሉ በሉት። ቅጠል ወይም ሳር ተበልቶ አልቆ ሊገኝ አልቻለም። አንዲት እናት ልጇን ጠብሳ በላቸው። የእሳት ጢስ ያዩ ሰዎች ሁሉ ወደ እርሷ ሄደው ርጥብ ሥጋ አግኝተሽ ለምን ብቻሽን ትበያለሽ አሏት። ተቀመጡና ላቅርብላችሁ አለቻቸው። እነርሱም ተቀመጡ የልጇን ሥጋ አመጣችና አቀረበችላቸው። ይህ የምወደው ልጄ ሥጋ ነው አለቻቸው። ሊበሉ እየጓጉ የመጡት ሁሉ ደነገጡ እየተንቀጠቀጡም ወጡ። የዚችም ሴት ተግባር በሀገር ሁሉ ተሰማ። ይህ ሁሉ የሆነው በግል ሥልጣን ጥመኞች ነው። ይህች እናት ልጇን በጣም ነበር የምትወደው አይታ አትጠግበውም ነበር። አንተ ብትሞት ቀባሪ የለኽም ስለዚህ አንተን የተሸከመች ሆዴ መቃብር ትሁንህ ብላ ነው ተጨፍና ያረደችው። የእግዚአብሔር ፍርድ አይዛባም ዘለዓለም ትክክል ነው። ብዙዎች በግፍ እየተገደሉ እግዚአብሔርን ከማመስገን ጋር ሞትን ተቀብለውታል። ጥጦስ የሴትዮዋን ሁኔታ ተረድቶ ለአይሁድ ራራላቸው። ለተራበው ሕዝብም ምግብ አቀረበለት ሊበላ ሲል ጉረሮው ተዘግቶ የሞተ አለ። አንዳንዶቹ ደግሞ ሳስተው በትልቁ ይጎርሱና ሕቅታ እየያዛቸው አለቁ። አንዱ ወርቁን እንዳይዘርፉት ዋጠው ሆዱን ቀደው የዋጠውን ወርቅ አወጡት። ይህን ዜና የሰሙ ሰዎች ወርቅ ለማግኘት የብዙ አይሁዶችን ሆድ ቀደዱ። ቤተ መቅደስ በሬሳ ተሞላ። ሮማውያን አይሁድን ሊወጓቸው የመጡ መታዘዛቸውን ስላቋረጡ ነው። የጥጦስ ሠራዊቶች እምቢ ብለው ቤተ መቅደሱን አቃጠሉት ጥጦስ ግን እንዲቃጠል አይፈልግም ነበር። ከቤተመቅደሱ ግንብ እርሱ እግዚአብሔር ክርስቶስ እንደሆነ አላስተዋሉትም የሚል ጽሑፍ ተገኘ። የአይሁድ ቤተ መዛግብቶች ሁሉ ተቃጠሉ። የኋላው ደስታ አሁን በሚካሄደው መራራ ትግል ይመሰረታል። ይህ ያለንበት ዓለም የሥራ ዓለም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የደስታ ዓለም ነው። የዓለምን ጎዶሎነት የተረዳ ሁሉ ዳግማዊውን ዓለም ይማጸናል። በሕዝበ አይሁድ ያልደረሰ አሠቃቂ መከራ የለም። አይሁድም ከምርኮ ሞትን እንመርጣለን ብለው እየተዋጉ በጦርነት አለቁ።

መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

የቤተክርስቲያን አባት ለመባል የሚያበቁ ሦስት መስፈርቶች እንዳሉ በዓለም አቀፉ ትምህርተ ቤተክርስቲያን ተመዝግቧል። እነዚህም ክህነት፣ ኢአማንያንን ወደ አሚነ ክርስቶስ ማምጣት፣ ለአስተምህሮ የሚሆኑ መጻሕፍትን ጽፎ ለቤተክርስቲያን ማበርከት ናቸው። ቀሌምንጦስ ዘሮም ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር 20 ዓመት ያህል አብሮ ኖሯል። መጽሐፈ ቀሌምንጦስን ጴጥሮስ እየነገረው የጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው።

እግዚአብሔር

ለቡኬ ኦ ወልድየ ቀሌምንጦስ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ ቀዳሚ ወእም ቅድመ ቀዳሚ ሕልው ዘአልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት። ልዑል ውእቱ መልእልተ ልዑላን። ዘአልቦ ታሕት ወኢላዕል ኢውሳጤ ወኢአፍኣ። ኢይትሌለይ ወኢይዜነው።

መላእክት

እም ቅድመ ኩሉ ፈጠረ መላእክተ በአሠርቱ ትዝምድ ወረሰዮሙ ይሰብሕዎ በሰናይ ዜማ ወማሕሌት በበመዓርጊሆሙ ወዘየዐቢ እምኔሆሙ ይቀርብ ኀበ መንበሩ ለእግዚአብሔር ልዑል። ወለመንፈሳውያንሰ ከመ ሰብእ ኢኮነ ፍጥረቶሙ። ወአልቦ ላዕሌሆሙ ፍትወተ ሥጋ። ቀሌ.6፣39 ወኢይክሉ አዕይንተ መላእክት ይርአዩነ (ይላሉ ሥላሴ) አላ ባሕቱ ይሴብሑነ ወይቁድሱነ። ኦ ጴጥሮስ ኢፈጠርክዎሙ ለመላእክት ለጻሕቅየ ኀቤየ ዘእንበለ ዳዕሙ ፈቀድኩ እጸግዎሙ ብዕልየ ወክብርየ። ወለኩሎሙ እለ የአምኑ ብየ እፈኑ ለለአሐዱ አሐዱ ክልኤተ መላእክተ አሐዱ በየማኑ ወአሐዱ በጸጋሙ ወየአቅብዎሙ እም ኩሉ እኩይ። (እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር በሕሊናው የነበረ እንጂ በኋላ ያመነጨው አይደለም። አዳም ቢወድቅ እንደሚቀጣው እንደሚምረው ወዘተ ዲያብሎስ ቢወድቅ እንደሚፈርድበት። አዳም እጸ በለስን እንደሚበላ መፍጠሩ በሕሊናው የነበረ ስለሆነ የባሕርይው ስለሆነ ነው። እጸ በለስን አዳም እንደሚበላው እያወቀ ለምን ፈጠረው ለምንለው ነገር መልሱ። አዳም እጸበለስን እንደሚበላ ማወቁ አትብላ እንደሚለው መናገሩ የእግዚአብሔር የባሕርይው ስለሆነ ይህ እግዚአብሔር ሊለው ያሰበውን ደግሞ መናገሩ ስለማይቀር ነው የሚል ነው። ሕዝቅያስን ትሞታለህ እንደሚለው ያውቅ ነበር። ካለው በኋላ 15 ዓመት ጨምሬሀለሁ እንደሚለውም ያውቅ ነበር። የሚያውቀውን በባሕርይ እውቀቱ ተናገረ)።

ሰው

ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር እም ኩሉ ምድር ንስቲተ ሐመደ ወእም ኩሎሙ ማያት ነጠብጣበ ማይ ወእም ነፋሳት ንሥቲተ ወእም እሳት ንስቲተ ወኮነ ኩሎሙ ውስተ እራኁ ወፈጠሮ ለአቡነ አዳም። ቀሌ.2፣10 ወሶበ ርእየቶ ሐዋን ለሰይጣን እንዘ ስውር ውስተ አርዌ እም ኢተናገረቶ አላ እም ኀየት እምኔሁ። ባሕቱ አመክነየ ወተሠወረ ውስተ አርዌ። ይእቲሰ ፈተወት ትብላዕ እም ፍሬ እጽ እስመ ቀዲሙ ኢሰምዐት ትእዛዘ ፈጣሪሃ እግዚአብሔር ልዑል ዘአዘዞ ለአዳም። ቀሌ.2፣19 ወበተስዓቱ ሰዓት ኮነ ጸአቶሙ እም ውስተ ገነት ዘእንበለ ፈቃዶሙ በዓቢይ ኀዘን ወብካይ ወላህ። ወእም ድህረ ለብሱ ቆጽለ በለስ አልበሶሙ እግዚአብሔር አነዳ ማእስ ዝ ውእቱ አነዳ ሥጋነ ዘመልእልተ ሥጋነ። ወአውሰባ ሴት ለሉድ (ለአቤል ተሰጥታ የነበረችውን) አገባ። ወሶበ ሞተ አዳም ጸልሙ ፀሐይ ወወርኀ ሰቡዓ መዋዕለ ወሰቡዐ ለያልየ። ወኮነ ዕረፍቱ ለአዳም ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት በእለተ አርብ አመ ሰብዑ ለሚያዝያ። ቀሌ.2፣19 እም ድኅረ ኃሙስ መዋዕል ወመንፈቀ መዓልት እምሕረከ ወእሠሐለከ። ቀሌ.12፣41 ሥጋ ትፈቱ ፍግዓ ወዕረፍተ በዲበ ምድር መንፈስ ትፈቱ ጻማ ወጸሎተ ሥጋ ትፈቱ ስቱ ወንዋመ ወነፍስ

ትፈቱ ንሥሓ ወትጋህ ሥጋ ትፈቱ ጻማ ወጸሎተ። ሥጋ ትፈቱ ትዕቢተ ወትዝሕርተ በዲበ ምድር ወነፍስ ትፈቱ ትሕትና ወየዋህተ ፍቅረ ወጸጋ።

ፍጥረት፣ ማስተዋል

ቀሌ.2፣8 እስመ ቀዳሜ ፍጥረቱ (ለእባብ) በአምሳለ እጓለ ገመል። እስመ ፍጥረታ ለብእሲት ድኩም ውእቱ ወተአምን ኩሎ ነገረ ዘትሰምእ። ቀሌ.2፣56 ለቡ እንከ ወልድየ። ወበቀዳሚት ሰዓት ዘዕለተ እሑድ ፈጠርክዎ ለሰማይ ወለኩሎሙ መላእክት።

ጊዜያት

በቀዳሚ ሰዓተ ሌሊት የዓርግ ጸሎቶሙ ለመሐይምናን ኀበ እግዚአብሔር። ወበካልዕ ሰዓት ይከውን ጸሎቶሙ ለመላእክት ወአስተብቁዖቶሙ። ወበሣልስ ሰዓት ይሴብሕዎ አዕዋፈ ሰማይ። ወበራብዕ ሰዓት ያመልክዎ መንፈሳውያን። ወበኃምስ ሰዓት ይሴብሕዎ ኩሉ እንስሳ ወአራዊት። ወበሳድስ ሰዓት ይከውን ስእለቶሙ ለኪሩቤል። ወበሳብዕ ሰዓት የዓርጉ መላእክት ስእለቶሙ ኀበ እግዚአብሔር። ወበሳምን ሰዓት ይሴብሕዎ ሰማያውያን ብሩሃን። ወበታስዕ ሰዓት ይትቀነዩ መላእክት ኀበ እግዚአብሔር ወይቀውሙ ቅድመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ልዑል። ወበአሠርቱ ሰዓት ይጼልል መንፈስ ላዕለ ማያት ወይጎይዩ ኩሎሙ አጋንንት ወይሴስሉ እምነ ማያት ወሶበ ነስአ ካህን ማየ በዛቲ ሰዓት ወቶስሐ ምስሌሁ ዘይተ ቅዱሰ ወቀብዐ ቦቱ ድውያነ ወእለ ቦሙ መናፍስት ይትፈወሱ እም ደዌሆሙ። ወበአሰርቱ ወአሐዱ ሰዓት ይከውን ፍሥሓሆሙ ለጻድቃን። ወበአሠርቱ ወክልኤቱ ሰዓት ይትዌከፍ እግዚአብሔር ልዑል ጸሎቶሙ ወስእለቶሙ ለኩሎሙ ውሉደ ሰብእ። በቀዳሚት ሰዓተ ሌሊት የአኩትዎ አጋንንት ለእግዚአብሔር ልዑል ወአልቦሙ እከይ ላዕለ ሰብእ ወኢመኑሂ እኩየ እስከ ይፈጽሙ ቅኔሆሙ። በዳግም ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ዓሣት ወኩሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማይ አራዊት ወአናብርት ለእግዚአብሔር። ወበሣልስት ሰዓት ትሴብሖ እሳት ለእግዚአብሔር። ወበራብዕት ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ሱራፌል። ወበኃምስ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ማያት ዘመልእልተ ሰማያት። ወበሳድስ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ደመናት ወብርሃናት ወበረድ። ወበሳብዕ ሰዓተ ሌሊት የብዙ ሱባኤ ያርጋል ይፈጸማልም ወትትቀደስ ምድር ወየሐውር ዲቤሃ እግዚአ አጋእዝት። ቀሌ.3፣7 ወበሳምንት ሰዓት ታወጽእ ምድር ሣእረ ወሐመልማለ። ወበታስእ ሰዓት ይትቀነዩ መላእክት ለእግዚአብሔር ወትበውእ ጸሎቶሙ ለውሉደ ሰብእ ቅድመ እግዚአብሔር። ወበአሥር ሰዓት ይትረኃው አናቅጸ ሰማይ ወይሰምእ እግዚአብሔር ጸሎቶሙ ለውሉደ መሐይምናን ወይትወሀቦሙ ስእለቶሙ እም ኀበ እግዚአብሔር። ወበድምፀ ክነፊሆሙ ለሱራፌል ይነቁ ዶርሆ ውእተ ጊዜ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር። ወበአሠርቱ ወአሐዱ ሰዓት ይከውን ፍሥሓ ወሐሴት ዲበ ምድር።

ደመ አቤል፣ ቃየል

ቀሌ.3፣26 ወይቤሎሙ ሴት ለደቂቁ በደሙ ለአቤል ጻድቅ ኢይረድ እምኔክሙ መኑመ እም ዝንቱ ደብር ቅዱስ። ወኢይደመር ምስለ ደቂቀ ቃየል ቀታሊ። ወአምሐሎ ለሔኖስ በደመ አቤል

ከመ ያሰኒ ላዕለ ሕዝቡ በጽድቅ ወበንጽሕ ወኢያጽርእ ተቀንዮ ቅድመ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም። ቀተሎ ላሜህ እውር ለቃየል ቀታሊ በገዳም በውስተ ዕፀው። እስመ ላሜህ እንዘ የሐውር ውስተ ገዳም ሰምዐ ቃለ ወኢያእመረ ከመ ቃየል ውእቱ። ወመሰሎ ድምጸ አርዌ ወእምዝ ነስአ እብነ ወወገረ ቦቱ ወደደቆ ለቃየል ማዕከለ አዕይንቲሁ ወቀተሎ። ሙሴ የገደለው ግብጻዊ ናቦም ይባላል።

ዘፈን፣ ዝሙት፣ ምግብ፣ ስድብ፣ ስካር

ቀሌ.3፣40 ወሶበ ሰምዑ ደቂቀ ሴት በድምጸ ዝንቱ ተውኔት ወጥዑም ዜማሁ ወረዱ እም ላዕለ ደብር ቅዱስ ወተደመሩ ምስለ ደቂቀ ቃየል እኩያን። ወኮኑ ሥሩሓነ በተውኔት ወበመብልዕ ወበመስቴ ወበዝሙት። ወአንስት ይጎይያ ድጎረ ወራዙት ወራዙትኒ ይጎይዩ ድጎረ አንስት ዕራቆሙ ገሀደ ውስተ ምስያጣት ከመ አዕዱገ ገዳም። ወየሐውሩ ክልኤቱ እደው ወሠለስቱ ጎበ አሐቲ ብእሲት ወይሰክቡ ምስሌሃ ዘእንበለ ጎፍረት። ወአልቦ ዘየአምር ውሉዶ እም ውሉደ ካልዐ። ወቀነዮሙ ሰይጣን ፈድፋደ። ቀሌ.3፣55 ወመነኖሙ እግዚአብሔር ለእለ ተርፉ ደቂቀ ሴት በእንተ ዘአፍቀርዋ ለኃጢአት። ወኢትትናገሩ ጽርፈተ ላዕለ ቢጽክሙ እስመ በጽርፈት ወድቀ ሰይጣን እመንበሩ። እመቦ እም ክርስቲያን ዘየሐውር ጎበ ዘፈን ወተውኔት ወይበውዕ ቤተብለኔ ይትመተር እም ቤተ ክርስቲያን። ቀሌ.10፣55 እስመ እም ስካር ይመጽኡ ምርዓት፣ ዝሙት፣ ስስዕት፣ ጽርፈት፣ ትዕቢት፣ ወመሐላ በሐሰት ወዝንጋኤ።

ድንግልና፣ አርዓያ

ወአቀበ ኖኅ በድንግልና ርእሶ ጎመስተ ምእተ ዓመተ። ወእምዝ ተናገሮ እግዚአብሔር መሐሪ ወአዘዞ ያውስብ ብእሲተ እንተ ስማ ሐይከል። ቀሌ.8፣114 ወአንተኒ ኦ ወልድየ ቀሌምንጦስ ኩኖሙ አርዓያ ለብዙኃን።

ቋንቋ፣ ጋብቻ

ቀሌ.3፣136 የአዳም የንግግር ቋንቋ የዕብራውያን ቋንቋ ነበር የሚሉ ሁሉ ውሸታሞች ናቸው። እስመ እለ ይቀውሙ በየማነ እግዚአብሔር ይትናገሩ በነገረ ሱርስት። ወይንበር ብእሲ በአሐቲ ብእሲት።

ጎልጎታ

የአዳም አፈጣጠር ከተፈጸመ በኋላ አዳም በምድር ላይ ቆመ ወደ ጎልጎታም አቀና። ወስሙ ለውእቱ መካን ጎልጎታ እስመ ህየ አንበረ ርእሰ አቡሆሙ ለከሉ ፍጥረት ወህየ ነበረ ርእሰ ከይሲ ዘአስሐቶ ለአዳም። ቀሌ.5፣5 ወሶበ ኮኖ ለይስሐቅ አሠርቱ ወክልኤቱ ክረምት ፈቀደ አብርሃም ይሠዋ በደብረ ማኖስ መካን ዘተሰቅለ ቦቱ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወስሙ ለውእቱ መካን ጎልጎታ። ወበህየ ፈጠሮ እግዚአብሔር ለአዳም። ወበህየ ርእዮ ዳዊት ለመልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይጸውር መጥባሕተ ለአማስኖታ ለኢየሩሳሌም።

ቤተ ክርስቲያን፣ ሥርዓት

ቀሌ.5፣31 ኢርቱዕ ለሕዝብ ይባኡ ቤተክርስቲያን እንበለ ይጠመቁ። እስመ እም ድኅረ ተጠምቁ ይከውኑ አባግዒሁ ለክርስቶስ። ቀሌ.8፣54 እቀቡ ሕጋ ለቤተክርስቲያን ከመ እሰባሕ በላዕሌሃ እስመ በእንቲአሃ ተሰቀልኩ ወሞትኩ። ዕቀቡ ሥርዓተ በፍድፋዴ። ቀሌ.9፣11 ቤተክርስቲያን ብሂል ነፍሰ ክርስቲያን ብሂል። ቀሌ.9፣46 እስመ ለመሐይምናን እሞሙ ቅድስት ቤተክርስቲያን ወአቡሆሙ እግዚአብሔር። ቀሌ.9፣66 ወለሕዝባውያን አዕሩግ ወሕጻናት ወአንስት ቅዱሳት ወደናግል ወመዓስብ ዕቤራት ወእጓለ ማውታ ወዲያቆናዊት እለ የአቅቡ አብያተ መበለታት ፍሉጥ ምቅዋሞን በበይናቲሆን። ቀሌ.10፣3 ይትመተሩ ኩሎሙ ገበርተ ዓመፃ እለ ኢአቀቡ ሥርዓታ ለቅድስት ቤተክርስቲያን። ወግበር ሥርዓታ ለቤተክርስቲያን።

ዕርገት፣ ቁርባን

ቀሌ.6፣6 ወእምዝ ነስአኒ ወአዕረገኒ ውስተ ደብረ ዘይት። ውስተ መካን ዘዐርገ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ሰማይ። ቀሌ.11፣34 ሶበ ይብል ካህን ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ወጽዋዕ ዘቤተ ክርስቲያን ይወርድ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ መሥዋዕት።

ሥላሴ

ቀሌ.6፣16 አልቦ ሰማይ ዘያገምረነ ወኢምድር ዘይጸውረነ ወነበ ሀለውነ ኢንትዌለጥ እም ግብር ውስተ ግብር። ወኢንትመየጥ እመካን ውስተ መካን። ወኢይሬእየነ ዓይን ወጥበቢሁ ለሰብእ ኢይክል አእምሮተነ። አቡየ እሳት ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ ዘእንበሌነሰ አልቦ ፍጥረት። ከእኛ ውጭ ፍጥረት የለም። አነ በአብ ወመንፈስ ቅዱስ ወአልብነ ጥንት ወኢተፍጻሜት ወኢይትአወቅ መዋዕሊነ። እስመ እም ቅድመ መዋዕል ወአዝማን ንሕነ። ወኢይክል ሕሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ እስመ ንሕነ መልእልተ ኩሉ ሕሊናት። ወኮነ ስብሐቲነ እም ኀቤነ ንሕነ ውእቱ ቀደምት ወደኀርት። ቀሌ.6፣42 ወለእመ ዘፈቀድነ ንገብር አልቦ ዘይክልአነ እም ኩሉ ፍጥረት። ወኢየአምረነ ሕሊና ጥበቢሆሙ ለመላእክት። ንሕነ ንፈጥሮ ለኩሉ ዘእንበለ ጻማ ናቀርቦ ለርኁቅ ወናርሕቆ ለቅሩብ። ንሬእዮ ለኩሉ ወአልቦ ዘይሬእየነ ወውስተ ኩሉ ንሕነ። ይቤ እግዚአብሔር በኀቤየ ይከውን ክረምት ወሐጋይ። እስመ አነ ውእቱ አምላከ ክረምት ወሐጋይ። ወንሕነ ናወርድ ዝናማተ ወናረውያ ለምድር። ኦ ጴጥሮስ ሶበሰ ኢያፍቀርክዎሙ ለሰብእ እም ኢያስተርአይክዎሙ በዝንቱ ሥጋ። ሶበሰ ኢኮነት ዛቲ ቅድስት ድንግል እም ኢፈጠርክዋ ለሐዋን። አልቦ ዘየአምር ስነ መለኮትየ። እስመ ግብርየ ፍትሕ ወርትዕ ወምሕረት። ወአነ ቀደምኩ አዕምሮ ከመ የዓልወኒ አዳም ወባሕቱ ፈጠርክዎ በፍቅር ወበምሕረት። ቀሌ.7፣1 በእንተ ትስብእትየ ፈጠርክዎ ለአዳም።

አለማወቅ፣ መጻሕፍት

ቀሌ.6፣56 ወእምዝ አብጽሐኒ ውስተ ግሩም መካን ዘኢኮነ ውስተ ሰማይ ወምድር። ወይቤለኒ ኦ ጴጥሮስ አይቴ ሀለውከ። ወእቤሎ ኢየአምር እግዚኦ። ቀሌ.10፣50 ተመሀሩ እም ሊቃናት

ወአጽምዑ ቃለ መጻሕፍት፡፡ ደዩ ውስተ ልብክሙ ቃለ መለኮት ወኢትርስኡ ቃለ መምህርክሙ፡፡

ዲያብሎስ

ቀሌ.6፣77 ወይቤለኒ ኦ ጴጥሮስ ናሁ ቀደምኩ አእምሮ ከመ ዝንቱ ዕልው ያምዕዓኒ አላ ባሕቱ ፈጠርክዎ ከመ ይትገሠጽ በዘአነ አምጻእኩ ኩነኔ ላእሌሁ ከመ ኢይሄሊ ካልእ መልአክ ምክረ እኩየ ወዕልወተ ከመ ዲያብሎስ ለሊሁ በፈቃዱ አጥረየ ዕልወተ፡፡ አኮ ባዕድ ዘአገበሮ ዐሊወ፡፡

ገነት፣ መንግሥተ ሰማያት፣ ገሀነም

ገነትሰ መልእልት ይእቲ ወትትሌዓል መልእልተ አድባር ወአውግር ነዋኃት መጠነ አሠርቱ ወነመስቱ በእመት፡፡ ቀሌ.7፣14 ለገነትሰ አንበርናሃ ውስተ ኤዶም ኀበ ኢይረክባ ጽልመት አላ ትነብር ብርህተ ግርምተ ወልእልተ፡፡ ወአልቦ ውስቴታ ቁር ወዋዕይ፡፡ ወእጸዊሃ ለገነት ብሩሃን፡፡ ኦ ጴጥሮስ ኢይበውዕ ውስተ ገነት ጽልመት ወኢጸዳል፡፡ እስመ ኩለንታሃ ብርሃን ዘይፈደፍድ እም ብርሃነ ፀሐይ፡፡ ወኢይጸራዕ እም ውስቴታ ስብሐት መዓልተ ወሌሊተ፡፡ ኦ ጴጥሮስ አልቦ ውስተ ገነት ክረምት ወኢሐጋይ፡፡ ወአልቦ ውስቴታ ፍትወተ ዝንቱ ዓለም ኢበሊዕ ወኢሰትይ እስመ ጼና መዓዛሃ ያጸግብ ነፍሳተ፡፡ ኦ ጴጥሮስ ዛቲ ገነት ድሉት ይእቲ ለኀሩያንየ እለ አሥመሩኒ በሕይወቶሙ፡፡ ቀሌ.7፣28 መንግሥተ ሰማያት ተዐቢ ወትክብር ወትትሌኣል እምኔሃ ወኩሉ ዘድልው ለመንግሥተ ሰማያት ይቀድም ይባእ ውስተ ገነት፡፡ አልቦ ደዌ ወአልቦ ሕማም ወነዘን፡፡ ቀሌ.8፣22 ወለእለ ይገብሩ ምግባረ ዲያብሎስ ይትኴነኑ ምስሌሁ ውስተ ገሀነም፡፡ ወእለሰ ይገብሩ ምግባረ መንፈስ ቅዱስ ይትፌሥሑ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት፡፡ትሕትና ወፍቅር ወየውሃት ትዕግስት ወሰላም ምሐረ ነዳይ ወውሂበ ምጽዋት ይሰመያ መራሑተ መንግሥተ ሰማያት፡፡

ተግሣጽ፣ አንድምታ

ቀሌ.8፣40 ኦ ወልድየ ቀሌምንጦስ ኢትምሐክ ትትመዓዕ ወትገሥጾሙ ለእለ ተአደውዎ ለቤተ ክርስቲያን እስመ አኮ አንተ ዘትትቤቀል ላቲ፡፡ ዘአቀመ ላቲ መልአክ በነገረ ዚአከ ይትቤቀል ላቲ፡፡ ውእቱሰ ይገብር በከመ ፈቀደ ወአንተ ቀዲመከ ገሥጽ እንከ ወአሰኒ ምግባርከ፡፡ (ትርጓሜ ላይ የሚገባ ቁጣ አለ የማይገባ ቁጣ አለ የሚለው ምንጩ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው)፡፡ ቀሌ.9፣123 አንትሙ ሥዩማነ ቤተክርስቲያን ገሥጽዎሙ ለነገሥት ወለመኳንንት በእንተ እከየ ምግባሮሙ ወአርትዕዎሙ ወኢትፍርሕዎሙ፡፡ ወእመሰ አኮ ክልኤክሙ ትትኴነኑ፡፡ ኦ ካህናት ኢትፍርሑ ገሥጽዎሙ ለኃጥዓን በኩሉ ዘርኢክሙ ወሰማእክሙ ኃጢአቶሙ፡፡ ቀሌ.10፣24 ይእዜኒ መምህራነ ቤተክርስቲያን ኢታስትቱ ገሥጽዎሙ ለእለ ስህቱ ሕዝበ ክርስቲያን፡፡ ከመ ኢይትመዐዐክሙ እግዚአብሔር አመ ትበጽሑ ቅድሜሁ፡፡ ቀሌ.11፣62 ዝኬ ዘይቤ አምጻእኩ መጥባሕት ለብሔር በእንተ እለ ይትፈልጡ እምአዝማዲሆሙ በእንተ ስምየ፡፡

ንሥሓ፣ ጸሎት፣ ፍቅር

ቀሌ.9፣17 ከመዝ አዝዞሙ ለካህናት ከመ ይንግርዎ ለኃጥዕ ይነሥሕ እም ኃጢአቱ ወኢያድሉ ለገጽ። ወኢይፍርሕዎ ለባዕል በእንተ ብዕሉ ወኢለንጉሥ በእንተ ዕበየ ክብሩ። እስመ ንጉሠ ሰማያት ወምድር ዘላእሌሁ። ቀሌ.9፣33 እስመ ዘይጼሊ ለእግዚአብሔር በንጹሕ ልብ ውእቱኬ ይነስእ ሰናየ ዘአስተዳለወ ለእለ ያፈቅርዎ። ቀሌ.11፣115 ይቤይስ እምኩሉ ፍቅረ እግዚአብሔር። ቀሌ.12፣32 እም ድኅረ ሞት አልቦ ንሥሓ። አስተፋጥኑ ገቢረ ሰናይ ወንሥሓ እንዘ ሀሎክሙ በሕይወትክሙ ከመ ኢትበሉ እፎ ኢገበርነ ዘሰማዕነ፡ ፡በጉጉዓ ነሥሐ።

ፈሪሃ እግዚአብሔር

ቀሌ.9፣104 አጽንዑ ልበክሙ ወኢትትሀወኩ እም ውኂዛት ወእመሂ እም ነፋሳት ወእመሂ እም ኃይለ አጋንንት። እመሂ በዘያስተርኢ ወእመሂ በዘኢያስተርኢ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ዘቦቱ በቁኤት። እስመ ፈሪሀ እግዚአብሔር ተአቅብ እም ኩሉ መንሱት ዘይመጽእ ላእሌሁ እመሂ በቃል ወእመሂ በምግባር ወእመሂ በዘኮነ ግብረ ሕሊና ዝንቱ ዓለም።

መጽሐፈ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ

አዘጋጅ፡- ምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት

ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን ስትሸጋገር የካህናተ ደብተራ ባህልና ሥርዓት አለባበሳቸው ጥምጥሜ ከበሮው ጸናጽሉ የመሳሰሉ የምስጋና መሳሪያዎችም አብረው ቀጥለዋል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ጥልቅ የሆነ የምስጢር ይዘት ያለው የእግዚአብሔር ማመስገኛና ማምለኪያ ዜማ ያገኘችው በቅዱስ ያሬድ ነው። የቤተ ክርስቲያናችን የአምልኮ ቀመር በአጠቃላይ በድጓ ይትበሀል ላይ የተመሰረተ ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ በዮዲትና በግራኝ መሐመድ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ በደረሰው ስደትና ሞት ምክንያት መጠነኛ ለውጥ ቢከሰትበትም ቃናው ሳይለወጥ እስከዛሬ በአገልግሎት ላይ ይገኛል። የአጫብር የተጉለት የቤተልሔም የወንጨር የቆማ ዜማ በተከሰተው ሥልተ ድምጽ ለውጥ ምክንያት የመጣ ነው። ለአጫብር ድጓ የምስክር መምህር ሲሆኑ ማዕርጉ ሊቀ ማዕምራን ነው። የምስክሩ ቦታ ምስራቅ ጎጃም የጋግራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው። ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው 5ቱ ጸዋትወ ዜማ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሥእት፣ ምዕራፍ ናቸው። ድጓ ማለት ድግዱገ ጽሕፈት ጽሕፈቱ የረቀቀና የደቀቀ በጣም የቀጠነ ረቂቅ የሆነ ምልክት ያለው ስልተ ዜማ ነው። አንድም ድጓ ንባቡን አላልቶ ድጓ ለቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያን ትጥቋ መቀነቷ ማለት ነው። ዋናው ትርጓሜ ግን ድጓዕ ማለት ነው። ይኸውም በትግሪኛ ድጓዕ ማለት መዝሙረ ኀዘን ሰቆቃው መሾ ማለት ነው። ድጓዐ ኤርምያስ እንዲል ሰቆቃወ ኤርምያስ ሲል። ዜማ ከመላእክት ተፈጥሮ ጋር አብሮ የተገኘ ቀዳማዊ ሀብት ነው። ቀዳሚ ዜማ በማለት ቀዳማዊነቱን አርያም በተባለው ድርሰቱ አስረድቷል። ቀዳማዊነቱ ብቻ ሳይሆን ታላቅም እንደሆነ ዐቢይ ዜማ ተሰምዐ በሰማይ ዘመላእክት ግናይ ብሎ ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በማለት ቅዱስ ያሬድ አድናቆቱን ገልጹዋል። ያሬድ ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ

ወሪድ ርደት ወይም መውረድ ማለት ነው። የቅዱስ ያሬድ አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ትባላለች። አብጡድና ክርስቲና የሚባሉ ወንድምና እህቶች ነበሩት። ድጓ በ4 ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል ድጓ ዘዮሐንስ፣ ድጓ ዘአስተምሕሮ፣ ጾመ ድጓ፣ ድጓ ዘፋሲካ ናቸው። ቅዱስ ያሬድ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1567 ዓ.ም በኢትዮጵያ የዜማ ልዩነት አልነበረም። አጫብሮች መሰረታዊውን ረቺሙን ዜማ ይዘው ወንበር ዘርግተው አስተምረዋል። አጫብር ሲሶ እነሴ ትገኛለች።

ዘመናት

1ኛ ከመስከረም 1-7 ዘመነ ዮሐንስ ይባላል። የሚዘመረው ስለዮሐንስ ጥምቀት ርእሰ ዓውደ

ዓመት ነው።

2ኛ መስከረም 8 ዘካርያስ ይባላል

3ኛ ከመስከረም 9-15 ዘመነ ፍሬ ይባላል።የሚዘመረው ፍሬን ማዕረርን ሰብልን የሚያነሳ ነው።

4ኛ ከመስከረም 16-25 ዘመነ መስቀል ነው። የሚዘመረው መስቀልን ስቅለትን ቅንዋትን ሕንጸተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያነሳ ነው።

5ኛ **መስከረም 26-ታኅሣሥ 25 ዘመነ መጸው** ነው። ከመስከረም 26-ኅዳር 5 ዘመነ ጽጌ ነው የሚዘምሩት ጽጌን ፍሬን የክረምት ማለፍን የበረከት መምጣትን የሚያነሱ ናቸው።

6ኛ ኅዳር 6-ታኅሣሥ 6 ዘመነ አስተምሕሮ ነው። በእነዚህ ሳምንታት የሚዘመሩት ርኁቀ መዓት መሐሪ፣ ዘአልቦ መዓት፣ ሥርየተ ኃጢአት አስተምሕሮ ናቸው።

7ኛ ታኅሣሥ 7-13 ዘመነ ስብከት ነው።

8ኛ ታኅሣሥ 14-20 ብርሃን ይባላል።የሚዘመሩ ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ ብርሃን ዘመጽአ ውስተ ዓለም የሚሉና የመሳሰሉት ናቸው።

9ኛ ዘመነ ኖላዊ ከብርሃን ቀጥሎ ያለው ዘመን ነው።በዚህ ሳምንት የሚዘመሩት ኖላዊ ዘመጽአ ውስተ ዓለም ኖላዊነ ኄር ኖላዊሆሙ ለእስራኤል የሚሉና የመሳሰሉ ናቸው።

10ኛ ታኅሣሥ 27 ቀን መርዐዊ ይባላል።

11ኛ ታኅሣሥ 28 ቀን አማኑኤል ይባላል።

12ኛ **ታኅሣሥ 26-መጋቢት 25 ዘመነ ሐጋይ** ነው። አንዳንድ ጊዜም ከዘመነ ክረምት ውጭ ያሉትን ሐጋይ ይላቸዋል። ክረምተ ወሐጋየ ዘአንተ ፈጠርከ እንዲል። ታኅሣሥ 29-ጥር 9 ዘመነ ልደት። በመካከል ከጥር 7-9 ናዝሬት ሕጽነት ትባላለች።

13ኛ ጥር 10 ቀን ገሐድ ይባላል።

14ኛ ጥር 11 እስከ ጾመ ነነዌ ዘመነ ጥምቀት ወአስተርእዮ ይባላል። የሚዘመሩ መዝሙራት አንሶሰወ አስተርአየ ተወልደ ተጠምቀ ከብካብ ማይ አውይኖተ ማይ መርአዊ ናቸው።

15ኛ ከጾመ ነነዌ ቀጥሎ ካለው ሳምንት ጀምሮ እስከ ዘወረደ ያለው ዘመነ መርአዊ ይባላል።

16ኛ ከዘወረደ እስከ ትንሳኤ ዓቢይ ጾም ነው። የሚዘመሩ መዝሙራት ጾም ጸሎት ምጽዋት ንሥሓ የመሳሰሉት ናቸው። ጾመ ሕርቃል ሙሴኒ ይባላል። ከቅድስት እስከ ኒቆዲሞስ ጾመ ኢየሱስ ይባላል። ከዚያ ሰሙነ ሕማማት ነው።

17ኛ **መጋቢት 26-ሰኔ 25 ዘመነ ጸደይ** ነው። ዘመነ ትንሳኤ (ከትንሳኤ እስከ ዕርገት ያሉ 39 ቀናት ናቸው በዚህም የሚዘመሩ መዝሙሮች ሞትን ትንሳኤን ስቅለትን ቅንዋትን የመሳሰሉት ናቸው) ዘመነ ዕርገት (ከዕርገት ጀምሮ ያለው 10 ቀን ነው። የሚዘመረው ጴዋዌን ዕርገትን የመሳሰሉት ናቸው) ዘመነ ጰራቅሊጦስ (ከጰራቅሊጦስ እስከ ሰኔ 17 ያለው ነው የሚዘመረው ዕርገትን ትንሳኤን ርደተ መንፈስ ቅዱስን የሚያነሳ ነው)።

18ኛ ሰኔ 17-25 ዘመነ አስተምሕሮ ይባላል። በእነዚህ ሳምንታት የሚዘመሩት ርኑቀ መዓት መሐሪ አስተምሕሮ ናቸው።

19ኛ **ከሰኔ 26-መስከረም 25 ዘመነ ክረምት** ነው። ከሰኔ 26-ሐምሌ 18 ደመና ዘርዕ ዝናም። ከሐምሌ 19-ነሐሴ 9 መብረቅ ነጎድጓድ ጠል ባሕር አፍላግ። ከነሐሴ 1-16 ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሞት ትንሳኤና ዕርገት የመሳሰሉት መዝሙሮች ይዘመራሉ። ከነሐሴ 10-27 አብርሃም፣ዕጉለ ቋዓት፣ዓይነ ኩሉ ደስያት። ከነሐሴ 28-ጳጉሜን 5/6 ጎሕን ነግህን ጽባሕን ብርሃንን የመሳሰሉ ናቸው።

ዮሐንስ መጥምቅ

1ኛ ጸርሐት ቤተ ክርስቲያን ኀበ ዮሐንስ ወትብሎ አንተኑ ክርስቶስ ወይቤላ አንሰ ኢኮንኩ ኪያሁ። እምከርሰ እሙ አእመረ ሰገደ ወአንፈርአጸ። ጸርሐ ዮሐንስ ወይቤ ድኅረ እምነቢያት እምቅድመ ምጽአተ ወልድ ቤዛ ኃጢአቶሙ አጥምቅ በማይ አንሰ ተፈኖኩ። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ መጥምቅ ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ሊቅ።ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ሰማእት ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ሕይወት። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ኅሩይ ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ፀሐይ። ርእዩ ዕበዮ ለዮሐንስ ዘመላእክት ይሰግዱ ሎቱ። ውስተ ሐቂሁ ቅናቱ ዘአዲም ንብረቱ ገዳም ወኩሉ ነገሩ በሰላም። ዮሐንስ ጸሊ በእንቲአነ ጸሎትከ ወትረ ይብጽሐነ። ወወረደ ልዑል ኀበ ዮሐንስ ወይቤሎ አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ። ኢሳይያስ ነቢይ መልአከ ሰመዮ (ለዮሐንስ)። ፍሕመ መለኮት ገሠሠት የማኑ። ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ በሄኖን። ዮሐንስ ወንጌላዊ ተሰመይከ ነቢየ ልዑል። ዮሐንስ ካህን ዘአጥመቀ ረቢ አማን እመላእክት የዐቢ። እምከርሰ እሙ አእሚሮ ሰገደ። ኢይሰቲ ወይነ ወሜሰ። ዮሐንስ ክቡር ዘእም ነገደ ሌዊ በውስተ ከርሰ እምከ ለእግዚእከ ሰገድከ። እፎ አጥመቆ በማይ መሬታዊ ለሰማያዊ። ወዓዲ ወልደ ነጎድጓድ ተሰመይከ እስመ ኮንከ ሰባኬ ወንጌል። አብያተ ዘውቅሮ መኒነከ በተዘክሮ ማኅደር ዘበሰማያት ጸንረ ገመል ረሰይከ አራዘከ። ርእሶ አምተረ በዛቲ ዕለት። የዮርዳኖስን ውሃ ኖሎስ ይለዋል። ብፁዕ አንተ ዮሐንስ

እደዊከ ቅዱሳት እለ አጥመቃሁ ለመርአዊ። ኤልሳቤጥ ወለደቶ ለዮሐንስ ነቢየ ልዑል ሰመየቶ። 2ኛ ወዘካርያስ ሰአለ መጽሐፈ ወጸሐፈ እንዘ ይብል ዮሐንስሀ ይሰመይ ነቢየ ልዑል ይሰመይ ዓርኩ ለመርዓዊ ይሰመይ። ወአዝማዱ በሥጋ ይሰመይ። ዮሐንስ ብሂል ፍሡሕ ወልድ ብሂል። ብዙኃን ተፈሥሑ በልደቱ ለዮሐንስ። ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ዮሐንስ ወልደ ሶፎንያስ።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ጥምቀት፣ ትርጓሜ፣ ረድኤት

ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘሚሞ ለጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት። አማን እብለክሙ ከመ ሞተ በኀቤየ ወአነ ቀበርክዎ በእደየ። ወቴዎድሮስ በናድልዮስ ወቴዎድሮስ ሊቀ ሠራዊት ተባረኩ እምኔሁ ወገብኡ በውስተ ትእይንቶሙ ወአኀዙ ይትቃተሉ ምስለ ቁዝ ወነገሥተ አረማ ወጼወዎ ለኒኅሚዶስ። ወበከየ ቴዎድሮስ በናድልዮስ በእንተ ዘርእዮ ኩሉ ሠራዊት ለኒኅሚዶስ። ወስእኑ ከቢቶቶ ከመ ያእትውዎ በኀቡዕ ኀበ ሊቀ ጳጳሳት ወአእተውዎ ኀበ ዲዮቅልጥያኖስ ለኒኅሚዶስ ወይቤሎ አንተኑ ኒኅሚዶስ ወይቤሎ እወ። ወይቤሎ ንጉሥ ኢወሀብኩከኑ ኀበ ሊቀ ጳጳሳት ምዕቅብና ወሚመ ጠፋዕከኑ እምኔሁ ወሖርከ። ወነገሮ ኒኅሚዶስ ኩሎ ዘኮነ። ወእምዝ ለአከ ንጉሥ ኀበ አጋግዮስ ወይቤሎ አምጽኦ ሊተ ለኒኅሚዶስ ዘአዕቀብኩከ እስመ ገበርነ ሰላመ ምስለ አቡሁ ወአነ እፈቅድ እሚጦ። ወይቤ አባ አጋግዮስ ኒኅሚዶስ ሞተ በኀቤየ ወአነ ቀበርክዎ በእደየ ወይቤሎ ዲዮቅልጥያኖስ ሐር ሥራዕ ቁርባነ በእዴከ ወአቅርበነ ወንግበር በዓለ ለእግዚአብሔር እስመ ሞዕናሆሙ ለጸላእትነ። ወቦአ ንጉሥ ወቀደሰ አባ አጋግዮስ። ወይቤሎ ዲዮቅልጥያኖስ አማንኑ ሞተ ኒኅሚዶስ ወትምሕልኑ በእንተዝ ነገር በዝ መሥዋዕት ወመሐለ አባ አጋግዮስ ወውእተ ጊዜ አንቃዕደወ ሰማየ ዲዮቅልጥያኖስ ንጉሥ ወቆመ እስከ ክልኤቱ ሰዓት እስመ ይትሐዘብ እመ ይወርድ እሳት እምሰማይ ከመ ያውዕዮ። ወእምዝ ሰሐቦ ዲዮቅልጥያኖስ በእዴሁ እንዘ ይእኀዝ ፊቃሮ ለአባ አጋግዮስ ወአስተርአዮ ለኒኅሚዶስ። ወተናገረ ኒኅሚዶስ ኩሎ ዘኮነ ቅድመ አጋግዮስ ወሕዝብ። ወአስተዮ ዲዮቅልጥያኖስ ፍሉሐ ወርቀ እምዘተወክፎ እምንጉሠ ቁዝ ወሞተ ሶቤሃ። ወእምድህረዝ አዘዘ ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ይዕጽው ኩሎ አብያተ ክርስቲያናት ወያርኅው አብያተ ጣዖታት። ወገብረ አማልክተ ወአዘዘ እመቦ ዘኢይሰግድ ለአማልክት ይትመተር ክሳዶ። የሳሌምን ሕጻናት የሄሮድስ ሠራዊት ሲገድሏቸው ከሞቱት በፊት የቀሩት ሕጻናት ይስቁ ነበረ ሞትንና ሕይወትን አያውቁም ነበርና። ወመነኑ ሰማዕተ አንጾኪያ ክብረ ወእንዘ የሐውሩ ለሞት ይትፌሥሑ ከመ ዘየሐውር ውስተ ከብካብ። ወኢሖረ ቴዎድሮስ ኀበ ዲዮቅልጥያኖስ ንጉሥ። ወፈርህዎ ዲዮቅልጥያኖስ ወብእሲቱ። ወእምዝ አስተርአዮ ሰይጣን ተመሲሉ ከመ መልአከ ብርሃን እንዘ ዕሩቅ እም ብርሃን። ወይቤሎ አነ ውእቱ ሐዳስ አምላክከ አነ አጸንዓ ለመንግሥትከ አጥፍየ ለቴዎድሮስ። ቴዎድሮስ መዝሙረ ዳዊት ይደግም ነበረ። ነገሩ ምሳሌው ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አይወጣም ነበረ። ዘፋኞች ዓላማቸው ሰውን እንዲያመነዝር ማድረግ ነው። በ153 ችንካሮች ቴዎድሮስን አሰቀለው። ወውእቱሰ ቅዱስ ሰማእት ኢያውስአ እንዘ ይቀንውዎ ወበከየት ሬሰንድያ እህቱ ለቴዎድሮስ። ወይቤሎ እግዚእነ ለቴዎድሮስ አስተዳሎኩ ለከ ሠለስተ አክሊላተ አሐዱ በእንተ ድንግልናከ ወአሐዱ በእንተ ዘጻመውከ በእንተ ፍቅርየ ወአሐዱ በእንተ ዘሞትከ በእንተ ስምየ። ወኩሉ ዘይቤ ኦ አምላከ ቴዎድሮስ አነ እትዌከፎ ጸሎቶ ወእረድኦ አለው። ወእመኒ ሖረ ውስተ ቀትል ወጸብዕ ወጸውዐ ስመከ አነ እከውኖ ረዳኤ አለው። ወወረደ ብርሃን ወፈርሐ ዲዮቅልጥያኖስ። ወዲዮቅልጥያኖስ ነግሠ አርብዓ ወአሐዱ ዓመታተ። እስራ ወሠለስቱ ዓመት ነበረ በሕገ ክርስቲያን። ወእምዝ ገፍትዖ ሚካኤል ሊ ቀመላእክት እመንበሩ ወአየሮ አዕይንቲሁ።ወረሰዮ እግዚአብሔር ነዳየ ወግዱፈ ወነበረ ውስተ ፍናው እንዘ ይስእል ጎብስተ ወይመጽኡ ሕጻናት ዘሀገረ አንጾኪያ ከመ ይሣለቅዎ ወይስሕቅዎ ወይቤልዎ ንሕነ ነአመን በክርስቶስ። ወይቤሎ ሰይጣን ለድዮቅልጥያኖስ ሊተሂ አሌ ሊተ ወለከሂ አሌ ለከ። ወአኀዞ ዝልጋሴ ዓቢይ ወጼነወ ኩሉ ሥጋሁ ወአጸየ ወተመትረ ልሳኑ በዕጼያት ወሞተ እኩየ ሞተ። ወእም ድህረዝ አንገሥዎ

ለቆስጠንጢኖስ። ወርእየ ቆስጠንጢኖስ አርባዕተ ከዋክብተ በአርአያ ትእምርተ መስቀል ወጽሑፍ በማእከሎሙ በሮማይስጥ ዘይብል በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ፀረከ። ይህን በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ካህናተ ጣዖት 4ቱ ከዋክብት 4 አማልክት ናቸው። ጣዖት አምልክ ማለቱ ነው ብለው ተርጉመውለት ነበረ። ነገር ግን አውስግንዮስ በትክክል ተርጉሞለት እነዚያ እንዲገደሉ ሆኗል።

ገድለ ቅዱስ ፋሲለደስ

ፋሲለደስ የተወለደው ሮም ነው። መስከረም 11 አንገቱን ተሰይፎ አረፈ።ይህንን ገድል የተናገረው ቅዱስ ክልስቲኖስ ሊቀ ጳጳስ ዘሮሜ ነው። የዲዮቅልጥያኖስ ሚስት እናት ወንድም ነው ፋሲለደስ። ለፋሲለደስ አውሳብዮስ የሚባል ልጅ ነበረው። አባዲርና ቴዎድሮስ ምስራቃዊ የፋሲለደስ የእጎቱ ልጆች ናቸው። ይቤሎ ሚካኤል ለአውሳብዮስ አነ ውእቱ ዘሰማእኩ ስእለቶ ለፋሲለደስ እንዘ ይስእል በእንቲአከ ወበእንተ ዮስጦስ ወመጻእኩ ከመ አድኅንክሙ። የፋሲለደስ ሚስቱ የፊቅጦር እናት እኅት ናት። ኑማርያኖስ ሲሞት ፋሲለደስ ለጥቂት ጊዜ ሮምን አስተዳድሯል። ዲዮቅልጥያኖስ ፋሲለደስን ይፈራው ነበረ። አንሰ አልብየ ነገር ምስለ ንጉሥ ዘንደኅ ለእግዚአብሔር ፈጣሪሁ ወሰገደ ለጣዖታት ይለው ነበርና። ሱስንዮስ ሰማዕት የፋሲለደስ የአባቱ ወንድም ልጅ ነበረ። አቦሊ የዮስጦስ ልጅ ነው። የዮስጦስ ሚስቱ ታውክልያ ትባላለች ሰማዕት ናት። ጌታ ለፋሲለደስ ወኩሉ ዘያለብስ ዕሩቀ በእንተ ስምከ ወኩሉ ብእሲ ዘይሰሚ ስሞ በስምከ ኢይመጽእ ላዕሌሁ ሕማም ውስተ ሥጋሁ ወበነፍሱ እስከ ለዓለም። ወኩላ ብእሲት መካን እንተ ትስእለኒ በስምከ አነ እሁባ ፍሬ ከርሳ ወፍሬ ሕይወት። ሦስት ጊዜ ሞቶ ተነስቷል ፋሲለደስ በአራተኛው ሞቷል። መጽሩስን ፋሲለደስ ጸልዮ አዳነው መጽሩስም ፋሲለደስን አስገደለው። መላእክት ጥብዓት ያለው ክርስቲያን ሲያዩ ያደንቃሉ ይወዳሉም።

ገድለ ቅዱስ ፊቅጦር

ወኮነ ፊቅጦር ማዕምረ ኩሉ መጻሕፍት ወቃለ ነቢያት ወትርጓሜሁ ወኩሎ ዘበእንተ ክርስቶስ። ወይገብር ብዙኀ ሰናያተ ወኮነ መፍቀሬ ጾም ወጸሎት። ወስመ እሙ ማርታ ወለተ ፋሲለደስ። ፊቅጦር ብሂል አሰሰለ ኀዘንየ ብሂል። ፊቅጦር ድንግል ስለሆነ ክርስቶስ ይወደው ነበር። መዝሙረ ዳዊትን መላእክትም ይዘምሩታል። ሚያዝያ 27 ቀን በአርያኖስ መኮንነ እንዴናው ሰማዕት ሆነ። ወነበባ ፊቅጦር ለእሙ ማርታ በአካለ ነፍስ እንዘ ይብል ወመንግሥተ ተንባላት ኀዳጥ መዋዕል እሙንቱ ወእም ድህረ ኀዳጥ መዋዕል ያነግሥ እግዚአብሔር ላእለ አህጉረ ኢትዮጵያ ብእሴ ቅዱሰ መፍቀሬ ክርስቶስ ወበእደ ዚአሁ ይትነሰቱ አረማውያን ወእምዝ የሐውር ብሔረ ግብጽ ወያጠፍዖሙ ለኩሎሙ ተንባላት ወለመንግሥቶሙ ወንጉሠ ኢትዮጵያ የነድግ ሠራዊቶ መንገለ አዜብ ወንጉሠ ቁስጥንጥንያ የነድግ ሠራዊቶ መንገለ ሰሜን ወይትራከቡ ነገሥት ወክልኤቱ ሊቃነ ጳጳሳት በእስክንድርያ ወይብል ሊቀ ጳጳሳት ዘቁስጥንጥንያ ሃይማኖት ዘእንቲአነ ትሜይስ ወተባህሉ ጳጳሳት ንቀድስ ዲበ ታቦታት አሐዱ በአሐዱ ታቦት ወአሐዱ በአሐዱ። ወለእመ ወረደ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ትሬእይዎ ኩልክሙ ክሡተ ኀበ አሐዱ እምኔነ ወዘበውእቱኬ ሃይማኖት ንሑር ኩልነ። ወገብረ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ከመ ርግብ

ፀዐዳ ወብርሃን ኀበ ቀደሰ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ። ሶቤሃ ይትፌሣሕ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ እስመ ዘሊቀ ጳጳሳቲሁ ወዘዚአሁ ሕግ ወሃይማኖት ኮነ ሥሙረ በቅድመ እግዚአብሔር ወንጉሠ ሮምሰ የኀዝን ወያስተጋብኦን ለኩሎን መጻሕፍቲሁ ወይዌርዎን ውስተ ባሕር ወይረግምዎ ለልዮን ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ዘትካት በእንተ ዘአማሰነ ሃይማኖቶሙ። ወገብኡ ኩሎሙ ውስተ አሐቲ ሃይማኖት። ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግብጽ አባ ሲኖዳ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። ወይከውን ዓቢየ ፍሥሓ። የፊቅጦር እናቱ ገድለ ፊቅጦርን ስትሰማ ወደ እናቱ ሀገር አፉን ለጉመው ወሰዱት የሚለው ላይ ሲደርስ ታለቅስ ነበረ።

ገድለ አባ በግዑ

ይቤ ዳዊት መንክር እግዚአብሔር በላእለ ቅዱሳኒሁ እስመ መንክረ ይገብር እግዚአብሔር በላእሌሆሙ። ወሶበ ይትነበቡ መጻሕፍት ይሰምእ በለብዎ። ሁሉ ከንቱ የሚለው ሲነበብ አለቀሰ። የተበላሸ የተላ በጣም የሚሸት ቅጠል ይበላ ነበር። ይህን ለምን ታደርጋለህ ሲሉት የከረፋ ኃጢአቴን እያሰብኩ ይል ነበረ። ሰውነቱ አልቆ እየተሸከሙ እየወሰዱ ያቆርቡት ነበር። ኦ ፍቁርየ ኢትወድስ ርእሰከ ወኢትፍቅድ ካልዓንኒ ይወድሱከ ከመ ትትወደስ በጎበ እግዚአብሔር ወአጥሪ ትሕትና ከመ ትርከብ ልዕልና። ወለእመ ርኢከ ዘይኤብስ ሰብእ ኢትጽልኦ ወኢትመንኖ ሶበ ኢተአምር ተፍጻሜቶ ወአንተሰ ጸሊ በእንቲአሁ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይምሐሮ ወይሣሀሎ እግዚአብሔር በጸሎትከ። እስመ ለጳውሎስ ሰዳዴ ረሰዮ ሐዋርያ ወለመጸብሐዊ ረሰዮ ወንጌላዊ ወለአባ በግዑ ፈያታይ ረሰዮ ቅዱሰ። ነቢዩ ዕዝራ የዱር ዛፍ ፍሬ ነበር የሚበላ። ኢሳይያስም የሜዳ ጎመን ነበረ የሚበላ። መንግሥተ ሰማያት አሸናፊዎች ብቻ የሚኖሩባት ናት። ሲኦል ደግሞ የተሸናፊዎች ናት። አባ በግዑ ታኅሣሥ 27 አረፈ። ንሕነሰ ኃጥዐን ንነብር እንዘ ነሐሊ ወንብል ምንተ ንበልዕ ወምንተ ንሰቲ ወምንተ ንትከደን ወበዝንቱ ሕሊና ንነብር ውስተ ዝንቱ ኃላፊ ወበነግህ ዘበላዕነ ወዘሰተይነ የኀልቅ በጽባሕ። ወከመ ሲኦል ኢትጸግብ ነፍሰ ሰብእ ከማሁ ሰብእኒ ኢይጸግብ ፍቅረ ንዋይ። ሰብእሰ ዘይነብር ዲበ ምድር ይረዊ ወይጸምዕ ይጸግብ ወይርህብ። የኀዝን ወይትፌሣሕ። ወፍሥሐሁኒ ኢይነብር ለዓለም እስመ ኃላፊ ኩሉ ንብረተ ዓለም።

ገድለ አባ ኪሮስ

ወደ ገዳም እንዲሄድ እግዚአብሔር አዘዘው ከዚያም ሲሄድ አባ በብኑዳን አገኘው። አባ ኪሮስን ያመነኮሰው እርሱ ነው። አባ ኪሮስ ሮማዊ ነው። ወለአባ በብኑዳ ኩሎ አሚረ ያመጽእ ሎቱ ፍና ሠርክ ኀብስተ ሰማይ ወጽዋዓ ወይን ቅዱስ ሚካኤል። ለክፉ መነኩሴ ይህን ኀብስት ሰጥቶት በረከቱ ቀረበት። ወበከየ ብካየ መሪረ። አንበሳም በላው። አባ ኪሮስ ይህን አይቶ ታላቅ ልቅሶ አለቀሰ የመምህሬን ጉዳይ ሳላውቅ ከዚች ምድር አልነሳም አለና ሣር እስኪበቅልበት ቆየ። ጌታ ተገለጠለት ነገር ግን መንፈስ ከሆነ ብሎ እስኪ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በል አለው። ጌታም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አለ። ጌታም እስመ ለኩሉ ግብር ቦቱ ፍዳ አለ። ብፁዕ ውእቱ ዘአምላኩ ገሠጾ በዲበ ምድር አለውና አጽናናው። አባ በብኑዳ የተቀጣ

በሥጋ እንጂ በነፍሱስ ገነት ነበረ። መዝሙረ ዳዊትን ይደግም ነበረ። በዋሻ በአንድ ሰይጣን እስከ ዕለተ ምጽአት ዘግቶበታል። ሰገደ ኪሮስ ታሕተ ሥዕላ ለእግዘእትነ ማርያም። ይቤሉ ቅዱሳን ሶበ ይበጽሖሙ መከራ በኃጢአትነ ተፈደይነ። ዲያብሎስን ብርያል ይለዋል። መነኮሳት ዙረው የማያዩት የሚሰድቡት የሚያቃልሉት ግን ሚካኤል ገብርኤል ሩፋኤል ሰዳክያል አብረውት የሚውሉ ድውይ መነኩሴ ነበር። ከሞተ በኋላ ቅድስናውን አይተው ተረድተው ማረን አሉት እርሱም መንግሥተ ሰማያት የገባሁ በእናንተ ምክንያት ነው አላቸው እና እግዚአብሔር ይቅር ይበላችሁ አላቸው እነዚያ መነኮሳትም ወደዱት ዝክር ያደርጉለትም ጀመር በጣምም ወደዱት። ቅዱሳን ታመው እንኳ እስኪሞቱ ነበር የሚሰግዱት። አባ ኪሮስ ነፍሱን በመላእክት በቅዱሳን ፊት ለእግዚአብሔር ምን ልትመልሺ ነው እያለ ይገሥጻት ነበር። ይቤሎ እግዚእ ለኪሮስ አማንየ እብለከ ኩሉ ሰብእ በሕልምኒ ዘጸውዐከ ወይብለከ አባ ኪሮስ አኀድግ ኃጢአቶ። ዝማ ሆድ ሕማም አመመውና ሞተ። ገድሉን የጻፈው የቀበረው አባ ባውማ ነው። እግዚአብሔር ለቅዱሳን የፈለጉትን ያደርግላቸው ነበር እናትህን ድንግል ማርያምን አሳየን ሲሉት ያሳያቸዋል ዳዊትን ሲሉት ዳዊትን ያሳያቸዋል። አባ ኪሮስን ነፍሱን ከሥጋው አዋሕዶ ነው ገነት ያስገባው።

ገድለ ዘርዐ ቡሩክ

ትርጉም በሊቀ ሊቃውንት ሰሎሞን ዳዊት የዘርዓቡሩክ የክርስትና ስማቸው ጸጋ ኢየሱስ ነው። ግዮን በገነት በወተት መልክ ለሕጻናት ክፍለ ርስት ሆኖ የተሰጣቸው ነው። አባታቸው ደመ ክርስቶስ እናታቸው ማርያም ሞገሳ ይባላሉ። ዘርዓ ቡሩክ በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተወለዱ። ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጋር አብረው ቀድሰዋል። 12 ክንፍ ተሰጥቷቸዋል በግዮን ምንጭ ግሽ አባይ 30 ዓመታት ጸልየዋል። ጥር 13 ዕረፍታቸው ነው። ለግዮን ምንጭ መጽሐፎቻቸውን አደራ በመስጠት ሄደዋል። ከእስር ቤት ሲመለሱ ግዮን ሆይ የሰጠሁሽ መጽሐፎችን ግሺ ትፊ አሏት ያን ጊዜ ብራናቸው ሳይርስ ቀለማቸው ሳይደመሰስ አገኛቸው። ከዚያ ጀምሮ ግሺ ዓባይ ተባለች። በግዮን ጸበል የተጠመቀ ሁሉ እንደሚድን ጌታችን ቃልኪዳን ገባላቸው። ጽጽስና ከእግዚአብሔር ተቀብለዋል። ወበእንተ ገድሉ ተውህበ ሎቱ ሀብተ ትንቢት። እናቱ ጾም ጸሎትን የምታዘወትር ፈራሂተ እግዚአብሔር ነበረች። ወባረከቶ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ። ወሰአመቶ አፋሁ ወእገሪሁ ወኩሎ አባላቲሁ ወሰአሞ እግዚእነ። እግዚአብሔር ለአቡነ ዘርዓቡሩክ ጳውሎስ ያስተማረባቸውን ሀገራትና ኢትዮጵያን አስራት አድርጎ ሰጠው። በ7 ዓመቱ ዓርብ ረቡዕን መጾም ጀመረ በ12 ዓመቱ ሰባቱን አጽዋማት መጾም ጀመረ። ህዳር 21 አክሱም ጽዮን ሄዶ ቀድሷል። ብሔሞትና ሌዋታንን አይቶ አልፈራም። ወከሠተ አፋሆሙ ወቦአ ውስተ ከርሶሙ ወኖለቆ አስናኒሆሙ ወጎደረ ውስቴቶሙ በጸጋ። ወእምድህረዝ ተመይጠ በፈቃዱ። ይህ መጽሐፍ ትንባሆን ይከለክላል። አቡነ ዘርዓ ቡሩክ ከ24ቱ ካህናተ ሰማይ ጋር አጥኗል።

ገድለ አብርሃም ወገድለ ይሥሐቅ ወገድለ ያዕቆብ

እግዚአብሔር ሰውን በምሳሌው ፈጠረው ማለት በነባቢት በለባዊት በሕያዊት ነፍስ ስለሚመ

ስለው ነው እንጂ እግዚአብሔር አዳምን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት የሚመስለው ሆኖ አይደለም። አብርሃም አባቱን ታራን ጣዖታቱ ሕይወት የላቸውምና ለምን ታመልካቸዋለህ አለው አባቱ ታራም መስሎ ለመኖር ነው እንጂ ሰዎችም ይገድሉኛል ብየ ነው እንጂ አለው። አብርሃምም ሌሊት ተነስቶ የጣዖት ቤቱን ከነእቃው አቃጠለው። ወንድሙ አራምም ጣዖቱን ያድናቸው ዘንድ ወደ እሳቱ ተወረወረ በበላዩም እሳት ነደደበት። ከአባቱ ከታራ በፊትም ሞተ። ይህን ገድል የተረጎሙት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ናቸው። አብርሃም 175 ዓመት ኖሮ ነሐሴ 28 ቀን አረፈ። የአብርሃምን ነፍስ የወሰዳት መልአከ ብርሃን ነው። ይሥሐቅም 180 ዓመት ኖሮ የሞተ ነሐሴ 28 ቀን ነው።ተአቀብ ከመ ኢይጻእ እምአፉከ ቃለ እኪት። ያእቆብም ነሐሴ 28 ቀን አረፈ።

ድርሳነ ኤፍሬም በእንተ አበው ወሣራ

ከነአን ከአብርሃም በፊት ጣዖት ይመለክባት የነበረች ናት። ኩሉ መካን ዘእግዚአብሔር ውእቱ። ሣራ አብርሃምን አንተ እግዚእየ ወአነ አመት ትለው ነበር። ሣራ አብርሃም ሲያዝን ታዝን ነበር። ወትበኪ ሣራ ወእንዘ ይበኪ። አብርሃምም ምንም ምን አይደብቃትም ነበር። ለአብርሃምም ታማኝ ነበረች። ሣራ አብርሃምን ብርሃነ አዕይንቲየ ትለው ነበር። ፈርዖን አጋርን ባርያ ትሁንሽ ብሎ ነው የሰጣት።

ገድለ እስትንፋስ ክርስቶስ

በወሎ ክፍለ ሀገር ተወለዱ። ዓባይ ባሕር 9 ዓመት ተዘቅዝቀው ጸልየዋል። ብሉይ ሐዲስ ተምሯል። እመቤታችን ልጇ ለዘላለም ኑርልኝ ትለው ነበር አንድ ጊዜ ታቅፈዋለች አንድ ጊዜ ታጠባው ነበር። በየቀኑ 150 መዝሙረ ዳዊት ይደግም ነበር። ወሶበ ያነብብ ዳዊት ውእተ ጊዜ ይመጽእ ዳዊት ንጉሥ ወይዘብጥ ሎቱ አውታረ መሰንቆ ወያስተፌሥሖ ጥቀ። ወእምዝ ይዌጥን መኃልየ ነቢያት ወይመጽኡ ኃቤሁ አሠርቱ ወሠለስቱ ነቢያት ወይባርክዎ። ወይከሥቱ ሎቱ ምሥጢራተ ኅቡዓተ። ወእምድህረ ፈጸመ ይብል ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ወእምዝ ይዌጥን ውዳሴ ማርያም። ሶቤሃ ትመጽእ ማርያም ድንግል ኀቤሁ ምስለ ፍቁር ወልዳ ወምስለ መላእክት ወቅዱሳን አበው ወእምዝ ይቤ አቡነ ዘበሰማያት። ወጊዜ አንበበ መልክዓቲሆሙ ይመጽኡ ጻድቃን ወሰማእታት ወይሁብዎ ሰላመ። ጌታ ኦ እስትንፋሰ ክርስቶስ ለሊሁ ቅብዕ ወለሊሁ ቀባኢ ወለሊሁ ተቀባኢ በል አለው። በ14 ዓመቱ ነው ወደ ገዳም የሄደው። ወእመሰ ዘይብል ሠለስቱ ልደት ውጉዘ ለይኩን በሥልጣነ መለኮትየ አለው።ወትረ ይኄጽር መጻሕፍተ ለአንብቦ። ወበልሳኑሂ ኢተናገረ ጉሁሉተ ወኢሐሜተ። የጌታን ግርፋት እያሰበ ይገረፍ ነበር። ነቢያት ወሐዋርያት ዘመድነ ይብልዎ ወማርያም ፍቁርየ ትቤሎ። ወመላእክትኒ በአክናፊሆሙ ይጸውርዎ። ወተባረከ እም ኩሎሙ ቅዱሳት መካናት። ወሖረ ሀገረ አክሱም ወተሳለማ ለጽዮን። በ33 ዓመቱ መነኰሰ። ወከመዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለእስራ ወአርባዕቱ **ካህናተ ሰማይ**፦ ትርሞን፣ አኪያል፣ ቀርትያል፣ ጽርትያል፣ ኤልያል፣ ዘርትያል፣ ቱቲያል፣ ዮልያል፣ ከርትያል፣ ለብትያል፣ ሚታኦል፣ ራዋል፣ ሳውር፣ አናዋል፣ ፈላላኤል፣ አክርትያል፣ አፍልፋኤሌ፣ አውኑዋኤል፣ ናናንኤል፣ ቲታር፣ አርናስ፣ ዝርኬዕብጦ፣

ዋቲርናናሳኬብኡማስ ናቸው። እስትንፋሰ ክርስቶስ በአጼ ፋሲል ዘመን አካባቢ የነበሩ ናቸው። **ዮናኤል** የሚባል ቅዱስ መልአክ አለ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስን ረድቶታል። አድያም ሰገድ ኢያሱ የሦስት ልደት ተከታይ ነበረ። የመነኮሳትን ልብስ በሕዝብ ፊት አስወለቀ። በኋላ አጼ አድያም ሰገድ ኢያሱ የሁለት ልደት ተከታይ ሆኗል። ይህንን ገድል የጻፈው ልብሰ ክርስቶስ የተባለው የእስትንፋሰ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ነው። ሥውራን ቅዱሳንም ያለቅሳሉ። ጎቡዓን ገዳማውያን አሉ።

ገድለ ክርስቶስ ሠምራ

ረሀብኒ ወተጽናስ ወኩሉ መከራ ኢይትከሀል ዘእንበለ ትዕግስት። በሐብለ ትሕትና እሠር ጎሊና ልቦሙ ለጻድቃን። ሕማሙሰ ለዝ ዓለም ኢኮነ መጠና ለእንተ ትመጽእ ዓለም። እስመ ዜና ጻድቃን ያስተፈሥሕ ልበ። ቡልጋ ይእቲ ሀገረ ሙላዳ ለቅድስት ክርስቶስ ሠምራ። እናቷ እሌኒ አባቷ ደርሳኒ ይባላል። ወመሐርዋ ሕገ እግዚአብሔር ወኩሎንኬ ሥርዓታት። ባሏ ሠምረ ጊዮርጊስ ይባላል። 9 ወንድ 2 ሴት ልጆች ነበሯት። አገልጋይዋን ብትመታት ሞተች ከዚያ ብታድንልኝ እመንናለሁ ብላ ብጽአት ገባች እግዚአብሔርም ባርያዋን ከሞት አስነሳት። ልጇን እያለቀሰ ከገዳሙ አፍዓ ጥላው ገባች። ቅዱስ ሚካኤልም ሕጻኑን ሄሮድስ ካስገደላቸው ሕጻናት ጨመረው። እያለቀሰ ጥላው የገባች ለፈጣሪዋ የገባችው ቃል ኪዳን ስለነበር ለእግዚአብሔር አድልታ ነው። በሥጋዋ መካከል ዓሣዎች እስኪመላለሱባት ድረስ ጣና ባሕር 12 ዓመት ጸለየች። 6 ክንፍ በሰውነቷ ላይ በቀሉ። ወበአሐቲ ዕለት እንዘ ሀለወት እምነ ክርስቶስ ሠምራ ቀዊማ ውስተ ባሕረ ጻና ከመ ትበኪ በእንተ ኃጢአታ ተዘኪራ ዕለተ ሞታ ወሶቤሃ መጽአ ኀቤሃ ዲያብሎስ ተመሲሎ ከመ ሊቀ ጳጳሳት ዐቢይ ወግሩም። ወሶቤሃ ፈቀደት ትስግድ ሎቱ እስመ መሰላ አሐዱ እም ቅዱሳን ዘይናዝዛ እም ኀዘና ወባሕቱ መጽአ ኀቤሃ ቅዱስ ሚካኤል ወአግብኣ ውስተ ድህር ወይቤላ ኢትስግዲ ሎቱ እስመ ኢኮነ ጳጳሰ አላ ሰይጣን ውእቱ። ሰይጣንን የማያሸንፈው ምግባረ ጽድቅ የለም። ሁሉም ምግባራት ለእርሱ መሸነፊያዎቹ ናቸው። ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ሐዋርያትን ነቢያትን ሰማዕታትን በጣም ትወዳቸው ነበር። ሊባርኳት ሲመጡ ትሰግድላቸው ነበር። ወትቤሎ ክርስቶስ ሠምራ ለኢየሱስ መሐሮ ለዲያብሎስ አኮ ዘአፈቅሮ ኪያሁ አላ በእንተ ደቂቁ ለአዳም እም ከመ ውእቱ ሐይወ አልቦ ኩነኔ ወሥቃይ አለች። ይቤላ እግዚእ ማኅደርኪ ይኩን ምስለ ወላዲትየ ወነዋ ሰመይኩኪ በትረማርያም ብፁዓን ኩሎሙ እለ ያፈቅሩኪ። ዲያብሎስን ሲኦል ሂዳ ና ውጣ ስትለው እምቢ ብሎ ጎትቶ ወደሲኦል ሲወስዳት ቅዱስ ሚካኤል በሰይፉ ብሎ እርሷን አውጥቷታል። ጼዐ ወበጥበጥ ኩሉ አባለ ሥጋሃ በጽንዓ ገድል። ወኮነ መዋዕለ ሕይወታ ለእምነ ክርስቶስ ሠምራ 375።

ገድለ አቡነ አረጋዊ

ምስለ ገድለ አባ ጳንጠሌዎን ወአኃዊሁ። እንጦንስ ወለዶ ለመቃርስ ወመቃርስ ወለዶ ለጳኩሚስ ወጳኩሚስ ወለዶ ለዘሚካኤል ዘውእቱ አረጋዊ። ወዮሐኒ ወለዶ ለኢየሱስ ሞዐ ዘሐይቅ። አቡነ ዘሚካኤል ዘውእቱ አረጋዊ መክብበ ሰመንቱ ቅዱሳን። ራብዕ ትውልድ እም እንጦንዮስ

ወመቃርስ ወጳኩሚስ። አቡሁ እም ነገሥተ ሮም ዘስሙ ይሥሐቅ ወእሙ እድና። ወተራከቦ አረጋዊ ለአባ ጳኩሚስ ወተምህረ ኩሎ ሥርዓታተ ምንኩስና እምኔሁ። ወአልበሶ አባ ጳኩሚስ ልብሰ ምንኩስና ወሰመዮ ዘሚካኤል። በ14 ዓመቱ መነኮሰ። ወመጽኡ ኀቤሁ አባ **ሊቃኖስ** ዘቁስጥንጥንያ (ደብረ ቆናጽል) ወአባ **ይምአታ** ዘሀገረ ቁስያ (ገረአልታ) ወ**ጽሕማ** እም አንጾኪያ (ጴዴንያ) ወጉባ እም ኪልቂያ ወ**አፍጼ** እም እስያ (ይሐ) ወ**ጳንጠሌዎን** እም ሮምያ ወ**አሌፍ** እም ቂሳርያ (አኀድዐ) ቅዱሳነ ሮም። ወሰመይዎ **አረጋዌ** (ደብረ ዳሞ) እንዘ ሕጻን በእንተ ጥበቡ ወምክሩ። እኒህ ቅዱሳን ወደ ሮሜ ሄደው ሰበኩ። ወሜጥዋ ለሀገረ ሮሜ ኀበ ሃይማኖት። ወካዕበ ሰምዐ ወረከቡ እመጻሕፍት ቅዱሳት ዘከመ ወሀባ ኪዳነ እግዚእነ ለእሙ ማርያም ዓሥራተ ምድረ አዜብ ወበጊዜሃ ተነድፈ ልቡ በፍቅረ ይእቲ ሀገር ዘወሀባ እግዚእነ ወእምዝ ወጽአ በሌሊት ዘእንበለ ያእምሮ ሰብእ እንዘ ይመርሖ ቅዱስ ሚካኤል ወይጸውሮ በክነፊሁ ወአብጽሖ ፍጡነ ሀገረ አክሱም ኀበ ሀለው ንጉሥ ወጳጳስ። ወገብአ ፍጡነ ሮምያ ወነገሮሙ ለአኃዊሁ ወመጽኡ ምስለ መጻሕፍቲሆሙ ወበጽሑ ሀገረ አክሱም። ወሶበ ርእይዎሙ ንጉሥ ወጳጳስ ለእሙንቱ ቅዱሳን ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሓ ወአፍቀርዎሙ ፈድፋደ በእንተ ሃይማኖቶሙ ወስነ ጽድቆሙ። ከአብርሃ ወአጽብሀ ስድስተኛ በነበረው በንጉሥ አልአሜዳ ጊዜ መጥተዋል። ዘጠነኛው አባ **ይሥሐቅ** (መደራ) ነው 7 ዓመት በሮም ከነገሠ በኋላ አብሯቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ መነኮሰ። ወአርአዩ ብዙኀ ተአምራተ። 12 ዓመት አክሱም ከተማ ተቀመጡ ከዚያ ወደየገዳማቱ ተለያዩ። አረጋዊ ከተራራ ጫፍ ለመውጣት ቢፈልግ ዘንዶውን ላከለትና በዘንዶ ወጣ። ቅዱስ ሚካኤል እንደ እናት እንደ አባት ያረጋጋው ነበረ። የዘንዶው ርዝመት 60 ክንድ ነበረ። ሚካኤል ሰይፍ ይዞ ይጠብቀው ነበር። ወይቤ አባ አረጋዊ ሀሌ ሉያ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወበእንተዝ ተሰይመ ደብረ ሀሌ ሉያ። ኢበልዐ ምድራዊ ኅብስተ እስከ አመ ተከብቶቱ። ደቀ መዝሙሩ ማትያስ ይባላል። እምድህረ ኀመስቱ ምዕት ዕሥራ ወአርባእቱ ዓመት እም ልደተ ክርስቶስ ኮነ ዓቢይ ጸብእ ውስተ ሀገረ ናግራን። ሂሩት ንጉሣቸው ነበረ። ሕዝበ ናግራን ደጋግ ቅዱሳን ነበሩ። ፊንሐስ የሚባል አላዊ ንጉሥ ሂዶ አገራቱን አመዘበራት ቅዱሳኑን ክርስቶስን ካልካዳችሁ ብሎ ገደላቸው አስጨነቃቸው አጽመ ቅዱሳንን አቃጠለ። ከዚያ የእስክንድርያው ጳጳስ ጢሞቴዎስ እርዳን ተበቀልልን ብለው ወደ አጼ ካሌብ ላኩ። አጼ ካሌብም አቡነ አረጋዊን አማከራቸው። አቡነ አረጋዊም ሑርአ በሰላም ወያግርር ለከ ጸረከ ወጸላእተከ ወያግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እደዊሆሙ ለአግብርቲከ ለከሂ የሀብከ ግርማ ወሞገሰ ወያግብእከ በዳህና ወበሰላም አለው። ካሌብሰ ንጉሠ ኢትዮጵያ ጻድቅ ውእቱ። ሂዶም አጽራረ ናግራንን አሸነፋቸው። ወካሌብ ቀተሎ ለሊሁ ለዓላዊ ፊንሐስ። ወሐነጸ ካሌብ ቤተክርስቲያን በሀገረ ናግራን ወሜመ ላቲ መኮንነ ለዛቲ ሀገር ዘይሰመይ አብርሃ ወተመይጠ ኀበ አክሱም ወመንኮሰ እም አባ ጳንጠሌዎን። 12 ዓመት በጾም በጸሎት ሲጋደል ቆይቶም አረፈ። ወበሰመንቱ ዓመተ መንግሥቱ ለባዚን ተወልደ ክርስቶስ በሥጋ እምድንግል። (አንድን በቅዱሳት መጻሕፍት ወይም ገድላት ያለ እውነት በአሁኑ የምርምር ዘዴ ውሸት ነው ብለው በአሁኑ የአመክንዮ አሰጣጥ ቢነግሩህ አመክንዮአቸው ራሱ ደካማ እንደሆነ ተረዳ።ሕጸጽ እንዳለበት አስተውል። አንደኛ ለአቀረቡት ምክንያት በዚያን ጊዜ ኖረው የዓይንም የጽሑፍም ማስረጃ የላቸውም። ሁለተኛ ሃይማኖታዊ እይታዎችን በየትኛውም ዓይነት ምርምር Disprove ማድረግ አይቻልም። በስሜት ሕዋሳትህ ውድቅ የምታደርገው አይደለም። ሦስተኛ እነርሱ

ይህን ውድቅ ሲያደርጉ የተጠቀሙት መንገድ ሳይንሳዊ ከሆነ ሳይንስ ራሱ ሕጸጽን የተሞላ መሆኑን እነርሱም ሳይቀሩ የሚመሰክሩት ጉዳይ ስለሆነ ነው። አራተኛ በጽሑፍ ጥናት አረጋግጠነዋል እንዳይሉ ጽሑፉ ራሱ ምን ትርጓሜ እንዳለው በአሁኑ መመዘን አይቻልም። ምክንያቱም ይህንን ባለሙያዎችም የሚያምኑበት ጉዳይ ነው። ለምሳሌ የአሁኑ ባለጌና የቀድሞው ይለያያል እና በአሁኑ የድሮውን እተቻለሁ ማለት ችግር ነው። ስለዚህ ሃይማኖትን በሳይንሳዊ መንገድ ተከትሎ ውድቅ ማድረግ አይቻልም። ቢቻልም ሳይንስ ፍጹም ሲሆን እንጂ በብዙ ሺ የሚቆጠር የአመክንዮ መፋለስ እያለበትና በሕጹጽ ሳይንስ ፍጹም እምነትን ውድቅ ማድረግ አይቻልም)። ንጉሥ ገብረ መስቀል አቡነ አረጋዊ እያሳየው ቤተክርስቲያን ሰራ። አክሱምን እሞን ለአህጉር ይላታል። ወደ ደብረ ዳሞ መወጣጫ እንዲሆን የወሰነ አቡነ አረጋዊ ነው።ወበጽሐ ቅዱስ ያሬድ ኀበ ሀሎ አቡነ አረጋዊ ወተአምኑ ወተሐቀፉ። ወተሳለመ ወነጸረ ስነ ሕንጼሃ ወተፈሥሐ ወከልሐ በውስቴታ በመዝሙር ወይቤ ይሔውጽዋ መላእክት እስመ ማኅደረ መለኮት ይእቲ ያድክዋ ያድክዋ ወርኢኩ ስነ ሕንጼሃ ለቅድስት ቤተክርስቲያን አለ። ወተፈሥሐ አቡነ አረጋዊ በሰሚዐ ዜማሁ ለያሬድ። ቅዱስሰ አቡነ አረጋዊ ይሜህር ለኩሉ ቃለ ሃይማኖት። ይቤሎ እግዚእ ለአረጋዊ ትትከበት ከመ ኤልያስ ወሄኖክ ነቢያት። ወኮነ ተሰውሮቱ ለአቡነ ክቡር አረጋዊ አመ አሠሩ ወረቡዑ ለጥቅምት ለወርኃ ጥቅምት በመዋዕለ መንግሥቱ ለገብረ መስቀል። አባ ዮሐኒ የደብረ ዳሞ ሰባተኛው መምህር ነው። ከአቡነ ዮሐኒ ጋር አቡነ ተክለ ሃይማኖት 12 ዓመት ቆይቶ መንኩሶ ወደ ኢየሱስ ሞዐ ሄደ። አባ ይሥሐቅንም/ገሪማንም ተሰወረ ነው የሚለው። ጥበቡ ለእግዚአብሔር ስውር ውእቱ እምነ ፍጡራን። መሰረት ዘእንበለ ሕንጻ ከንቱ ውእቱ። ጽድቅን ወለተ መከራ ይላታል። ለአባ በብኑዳ ከርሰ አንበሳ ኮነቶ መቃብረ።

ገድለ ቂርቆስ ወኢየሉጣ

ኢየሉጣና ቂርቆስ በነበሩበት ዘመን እግዚአብሔርን ማመን ማምለክ እንደነውርና ክፉ መቅሰፍትንም እንደሚያስከትል ተደርጎ ይነገር ነበር። ዲያብሎስ የነገሠበት የጭንቅ ዘመን ነበር። ብዙ ክርስቲያኖችን አስገደለ ነገር ግን ሽንፈቱ የዲያብሎስ ነበር። ኢየሉጣ ጎየት እም ሀገረ ሮም ወበጽሐት ጠርሴስ ዘቂልቅያ በእንተ ፍርሀተ መኮንን። ለሕጻናት ዘቀተሎሙ ሄሮድስ መክብቦሙ ውእቱ ቂርቆስ ሕጻን። ወቂርቆስ ቆመ ውስተ ዓውድ ወሰበከ ሥመ ሥላሴ። በሰማእታት ገድል ብዙ ሰዎችንም ሰማእት እንደሆኑ እናገኛለን። ኢየሉጣን ያሰቃያት መኮንን እስክንድር ነው። የኢየሉጣ ሀገሯ አንጌቤን ነው። ኢየሉጣ መከራ የደረሰባት ለጣዖት አልሰግድም በማለቷ ነው። አፍቀሮ መኮንን ለቂርቆስ ነጺሮ ከመ ግሩም ወራእዩ ወሰናይ ላሕዩ ወይቤሎ በሓ ፍሥሕ ሕጻን ወአውስአ ሕጻን ወይቤሎ አማንከ ፍሥሕ አነ በፍሥሐሁ ለአምላኪየ። ለከሰ አልብከ ፍሥሓ እስመ ከመዝ ይቤ አልቦሙ ፍሥሓ ለረሲዓን።ቂርቆስን እየተሸከመ ከመሬት ጣሉት 50/50 ገረፉት። ወእንዘ ይቀስፍዎ ዓቢየ ቅስፈተ አንስአ አዕይንቲሁ ወአእኮቶ ለእግዚአብሔር ወጸለየ። ወአንከረ መኮንን ትእግስቶ ለፍቁር ሕጻን። ወአስተአጸበ እም ጣዕመ ነገሩ ወሣዕሣዓ አፉሁ። ወይቤላ መኮንን ለኢየሉጣ ናሁ ወልድኪ ሕጻን አምነ በአማልክትየ ወትቤ ኢየሉጣ አምጽኦ ዝየ ከመ እስማዕ አነ እም ቃሉ። ኢየሉጣ ለቂርቆስ ትጸልይለት ነበረ እግዚአብሔርንም ስለልጇ ታመሰግነው ነበር። የእነ ቂርቆስን

አፍንጫቸውን በጋለ ብረት ጨው ጨምሮ በሳቸው። ቂርቆስም ጥዑም ለጉርኤየ ነቢብከ እመሳር ወሥከር ጥዕመኒ ለአፉየ ያለውን መዝሙር ዘመረ። አሌ ሎሙ ለእለ ይሠይምዎ ለጥዑም መሪረ ወለመሪር ጥዑመ። ቦ ጊዜ ይትሜሰል ሰይጣን ከመ መልአከ ብርሃን ወቦ ጊዜ ያበውእ መንፈሰ ሐሰት ውስተ አፉሆሙ ለነቢያት ወያስሕት ሰብአ። መኮንን እስክንድርም ቂርቆስን አድነኝ አለው አዳነውም። ካዳነው በኋላ ግን የፈወሳችሁኝ አጽሎንና አቴና ሆይ ምስጋና ይገባችኋል ብሎ ካደ። (በነገራችን ላይ እግዚአብሔር ለሰውና ለመላእክት ክፉና በጎውን የሚለዩበትን አእምሮ ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ለዲያብሎስም ሲዋሽ ውሸቱ ስህተት መሆኑን በልቡ እያወቀ በሰጠው ነጻነት ካደ እንጂ በኋላ የተነሡ ጣዖት ያመለኩትም ስህተት መሆኑን እያወቁ ካዱ። ወይም እግዚአብሔር በሰጣቸው አእምሮ ባለመመራመራቸው ወደቁ እኒህም በአየር የቀሩት አጋንንት ምሳሌ ናቸው)። የቂርቆስን ምላሱን ቆረጡት። ቂርቆስሰ ኢፈርሀ ሞተ ሥጋዌ ወኢፈቀደ ከመ ይክሀዶ ለክርስቶስ። ወሶበ ርእየ ሕጻን ቂርቆስ ከመ ፈርሀት እሙ ይቤላ ኦ እምየ ኢትፍርሂ በነጽሮተ ዝንቱ ጽሕርት ብሎ ጸለየላት። ወጎየ እምኔሃ ዲያብሎስ ወትቤ ኢየሉጣ ኦ ወልድየ ዘኮንከኒ መርሐ ለመንግሥተ ሰማያት ንፈጽም ገድለነ ዘጽኑሕ ለነ። ወወረውዎሙ ሰገራት ውስተ ጽሕርት ወነደገ ጽሕርት ዋዕዮ ወፍልሐቶ እስመ ገብርኤል ረሰዮ ከመ ማይ ቆሪር። ሞፃ ኃያል ቂርቆስ በብዝኀ ትእግስቱ። ወበከየ ሰይጣን። ወተከለለ ቂርቆስ በሰይፍ ወፈጸመ ገድሎ ጥር 15 ወኢየሉጣ። ሰይጣን በሕልምም ይታያል። ገድለ ቂርቆስ ላይ ጎጃም በተደጋጋሚ ተጠርታለች። ገድለ እስትንፋሰ ክርስቶስ ላይም እንዲሁ።

ድርሳነ ኢያቄም ወሐና

ድርሳናትን ገድላትን አዋልድ የምንላቸው ከአሥራው መጻሕፍት/መጽሐፍ ቅዱስ ሳይወጡ ዐሥራው መጻሕፍትን አመስጥረው ስለሚያስረዱ ነው። የሐና እናቷ ከሌዊ ወገን ናት ፋስቱና ትባላለች። ይሄይስ ኢወሊድ እምነ ወሊድ ብዙኃን እለ አልቦሙ በቁኤት። የኖኅ እናት ሐይከል ትባላለች። የአብርሃም እናት አድና ትባላለች። ሕዳር 11 አርፋለች። የጌታ አያት ናት። እመቤታችንም እናቷ መሞቷን ሰምታ አለቀሰች። እስመ ለማጣት ኮና ሎቱ ሠላስ አዋልድ እላ እማንቱ ማርያም ወሶፍያ ወሐና። ማርያም ወለደታ ለሰሎሜ ወሶፍያ ወለደታ ለኤልሳቤጥ ወሐና ወለደታ ለእግዝእትነ ማርያም። ኤልሳቤጥ ይእቲ እሙ ለዮሐንስ። እመቤታችን ስትወለድ ቅዱሳን መላእክት አመሰገኑ። ሐና ጸንሳ ሳለ ብዙ ሕመማን ሆዷን እየነኩ ተፈውሰዋል። ዝንቱ ውእቱ መጽሐፈ ልደታ ለእግዝእትነ ማርያም ናታን ወለዶ ለሌዊ ወሌዊ ወለደ ማጣትሀ ወቅስራሃ ወቅስራ ወለደ ኢያቄምሀ ወኢያቄም ወለደ ማርያምሃ። ወሶበ ሞተ ናታን እኑሁ ለያዕቆብ አውሰበ ብእሲቶ ማጣት ከመ ያቅም ዘርዐ ለእኑሁ ወወለዶ ለኤሊ ኤልያስ ወያዕቆብ አኃው እሙንቱ። ወያዕቆብ ወለዶ ለዮሴፍ።

ገድለ ቅድስት አርሴማ

ይብልዋ ኩሎሙ ቅዱሳን ተፈሥሒ ኦ አርሴማ ቅድስት። ወተአቢ እም ኩሎን አንስት ዘእንበለ እግዝእትነ ማርያም። አባቷ ቴዎድሮስ እናቷ አትኖስያና ትባላለች። እናት አባቷ ሊያጋቧት ፈልገው ነበረ እምቢ አለቻቸው እንጂ በመልክ ከእመቤታችን ውጭ የሚበልጣት አልነበረም።

ዲዮቅልጥያኖስን እንዲያገባት ሰይጣን አሳሰበው። ወአዘዘ ሠዓልያነ ከመ ይሑሩ ውስተ ኩሉ በሐውርት ውኀረዩ ሎቱ አርሴማሃ። ወሶበ ርእየ ዲዮቅልጥያኖስ ሥዕላ ተፈሥሐ ፈድፋደ ወፈነወ ኀበ ነገሥት ወመኳንንት። ወሶበ አእመራ ደናግል ዘንተ ነገረ በከያ። ወቅድስትሰ አርሴማ እንዘ ትጼሊ ወእንዘ ታነብብ መጻሕፍቲሃ በከመ ልማዳ። ወተዐቅቦሙ በጥንቃቄ ለሕገገ መጻሕፍቲሃ። ምንም ፍርሀት የሚባል አታውቅም ነበረ። ሰላም ለክሙ አ ቅዱሳኒሁ ለእግዚአብሔር ወሊተኒ ተዘከሩኒ በጸሎትክሙ ከመ ይረስየኒ ከማክሙ ከመ እኩን ሰማእቶ ትል ነበረ። መዝሙረ ዳዊትን ትደግም ነበረ። ወመኮንን ድርጣድስ ለአከ ኀቤሃ ብዙኃተ አንስተ ወዕቤራተ ወውርዝዋተ ከመ ያሥሕታ በነገረ ዘርቅ ወከመ ኦሆ ትበሎ። ወትኩኖ ብእሲተ። ወነስኣ ምስሌሆን ፀቃውዐ መዓር ወፍሬያተ ሐመልማለ ጥዑማተ ፈድፋደ ከመ ይሰአላሃ ወያስሕታ። ወይእቲሰ ብጽእት አርሴማ ታውኅዝ አንብዓ በሰጊድ ወበስኢል በጾም ወበጸሎት ኀበ እግዚአብሔር ፈጣሪሃ ከመ ያድኅና እም እደ ጸራዊ ርጉም። ወሶበ ርእየቶን ቡርክት አርሴማ ለአንስት መስሕታት ከመ ቀርባ ኀቤሃ አተበት ገጻ በትእምርተ መስቀል ወጸለየት ወመሐረቶን ለእላ አንስት በቃለ ምዕዳን ዘቃለ መጻሕፍት። ወአምና በቃለ አርሴማ ወአውኃዛ አንብዖን ወተማኅጸና እላ አንስት ለአርሴማ በኃይለ ጸሎታ። ወመከርዋ ለአርሴማ እላ አንስት እንዘ ይብላ ዝንቱ ረሲዕ ኢያስፍጠኪ በነገረ ሐሰት ዘውእቱ ዝሙት እያሉ መከሯት። ሊያሳስቱ መጥተው አመኑ። ትቤ አርሴማ ኢይፈርህ ሞተ ሥጋ ዘበምድር አላ እፈርህ ዘበሰማያት ሞተ። ንድፍት ይእቲ በሐጸ ፍቅሩ ለክርስቶስ። ሶበ ርእያ ንጉሥ ድርጣድስ ለአርሴማ ቅድስት አብኣ ውስተ ጽርሐ መንግሥቱ። ወጸለየት ኀበ እግዚአብሔር ወረድእዋ ሚካኤል ወገብርኤል። ቅዱሳኑን ከግንድ ጋር የኂሊት አሥረው አራዊት ለቀቁባቸው። ወሰበሩ አቁያጺሆሙ ለቅዱሳን ወቀጥቀጡ አዕጽምቲሆሙ ወሠጠቁ ከርሶሙ ወሰሐቡ አማዑቲሆሙ ወዘርዘሩ መለያልይሆሙ ወፈጸሙ ገድሎሙ ከመዝ። አርሴማን ወደ እሳት ሲጥሏት ምንተ ይሬስዮ እሳት ለወርቅ ዘእንበለ ዘያጸርዮ። ንማየ ለእኩይ ሕሊና ትል ነበር። ንጉሥ ድርጣድስ የሚደረገውን ተአምራት በሙሉ አርሴማ መሰርይት ናት እያለ አይቀበለውም ነበር። ድርጣድስ የሚያመልካቸው 77 ጣዖታት ነበሩ አርሴማ ብታማትብባቸው ወደምድር ወደቁና ጠፉ በጣዖታቱ ላይ አድረው የነበሩ አጋንንትም ይህች ሴት ክፋትን የተመላች ናት ወዲያ በሏት ይሉ ነበር። ብርናኤልና አቅናኤል የሚባሉ ቅዱሳን መላእክት አርሴማን ረዷት። ስትጸልይ መላእክት መጡና ጣዖታትን አፈረሷቸው። ትሄሊ ወትረ አርሴማ በልባ ክብረ ኩሎሙ ጻድቃን ዘመንግሥተ ሰማያት። ዘይሔልዮ ለዝንቱ ዓለም ኢይሔልዮ ለእግዚአብሔር በኩሉ ልቡ ወበኩሉ ፍናዊሁ። መዐደቶሙ አርሴማ ለቅዱሳን በቃለ መጻሕፍት እስመ መዓርጊር ቃላ ወጥዑም ከናፍሪሃ። ኦ ኀሊናየ ለምንት ለኪ ትወርዲ ውስተ ምድር ባሕቱ ርእዩ ወነጽሪ ማኅበረ በኩር። ህየ ዳዊት ይዜምር ወይዌድሱ ኩሎሙ ቅዱሳን። ወሶበ ርእየ ድርጣድስ ስና ለቅድስት አርሴማ ፈቀደ ከመ ያርኩሳ ድንግልናሃ። ወኢተክህሎ ወገደፈቶ ወሰሐበቶ ውስተ ምድር። ወሶቤሃ ተሐፍረ ንጉሥ ድርጣድስ በቅድመ ሐራሁ በእንተ ዘተመውዐ ወአዘዘ ከመ ይምትሩ ርእሳ በሰይፍ። ወፈጸመት ስምኣ። ወይቤላ እግዚእነ እንከሰ የአክለኪ ጻማ ዘበምድር ወኩሉ ምንዳቤ ወነዘን በእንተ ስምየ። ወእም ክሳዳ ፈልፈለ ደም ወሐሊብ ወመዓር ወተፈሥሑ መላእክት። መስከረም 27 አረፈች። ጎርጎርዮስ ሊቀጳጳስ ዘአርማንያ እስኪያድነው ንጉሡ አውሬ ሆነ። ከዳነ በኂላም ጥሩ ክርስቲያን ሆነ። ጎርጎርዮስ 15 ዓመት በጉድጓድ ተጥሎ አንዲት መበለት ምግቡን እየላከችለት ቆይቷል።

ተአምሯ ላይ ቅድስት አርሴማ ገና ሳትወለድ ታቦት ተቀርጾላት እንደነበረና ያንንም መልአኩ ይጠብቀው እንደነበር ተገለጹዋል።

ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

አባ ጊዮርጊስ የተወለዱት አማራ ሳይንት ነው። አባቱ የሸግላ አስተዳዳሪ ሕዝበ ጽዮን እናቱ እምነ ጽዮን ናት። በ1357 ዓ.ም ሐምሌ 7 ቀን ተወለደ። በጊዜው ታላቅ የትምህርት ማዕከል የነበረችው ሐይቅ ደብረ ነጎድጓድ ናት። መነኮሳት አባ ጊዮርጊስን ትምህርት የማይገባው እያሉ ይነቅፉት ነበር። አባ ጊዮርጊስ ግን እንደሰደቡኝ ልስደባቸው እንደናቁኝ ልናቃቸው አላሉም። በእመቤታችን ሥዕል ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ያለቅሱ ነበረ። እርሷም ቅዱስ ዑራኤልን ይዛ ጽዋዓ ልቡና አጠጣቻቸው። ከዚያም የሰማይና የምድር ምስጢር ሁሉ ተገለጸላቸው። ድጓውን በዘመናት ከፋፍለው ያስተማሩ እርሳቸው ናቸው። ደብረ ባሕርይ እጅግ ታላላቅ ሊቃውንት የወጡበት ነው። ጎምስቱ ጉልቆ ሐዋሳት ዘውእቶሙ ሰሚዕ ወርእይ ወአጼንዎ ወጥዒም ወገሚሥ። ዕቀብ ድንግልናከ አለቸው እመቤታችን አባ ጊዮርጊስን። ወትብል እስመ ኩሉ ዘዐቀበ ድንግልናሁ ይክውን እጉየ አለችው። ወወሀበቶ ጥበበ ወአእምሮ በዘይድኅን እም ዓለም ወበዘይትቃወም ለእኩይ። ወአቀባ ለነፍሱ እም ሐልዮ ዘበምድር ወእደዊሁኒ እም ገሚሠ ኩሉ ርኩስ ዘይጸልእ እግዚአብሔር። ወእገሪሁ እም ነሶሳው ጎበ ዘኢይበቁዕ ወአዕይንቲሁ እም ነጽሮ ከንቱ ወእዘኒሁ እም ሰሚዐ ሐሜት ወዛውዕ። ወዓዲ አቀበ ልሳኖ እም ነቢብ ጽሩዕ ዘኢይደሉ ዘእንበለ ዳዕሙ ለአንብቦ ቃለ መጻሕፍት ወደጊመ ቃለ መለኮት። ሰቀላ ለሥጋሁ በፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዮሐንስ ወንጌላዊም ድንግልናህን ጠብቅ እያለ ያነጋግረው ነበር። ጴጥሮስ ጳውሎስም እየመጡ ያነጋግሩት ነበረ። ወእም ድህረዝ ኮነ አባ ጊዮርጊስ መምህረ ለነገሥት ወለካህናተ ደብተራ ወለኩሉ ዓበይተ መንግሥት ለንቡራነ እድ ወለመኳንንት ወይዬብብ በማኅሌተ ያሬድ ብርሃነ ኢትዮጵያ። ወያነክሩ ሕዝብ ጣዕመ ነገሩ ወስእሳኤ አፉሁ። ድርሳን ሊጽፍ ተዘጋጅቶ ሳለ እመቤታችን ተገልጻ ሳትጠይቀኝ መጽሐፌን ለመጻፍ ለምን ደፈርክ አለችው ይቅርታ ጠይቆ ጻፍ ብላው መጻፍ ጀመረ። ቢቱ የተባለ የንጉሡ ወዳጅ በምጽአት ወልድ ብቻ ይመጣል ብሎ ነበር። አባ ጊዮርጊስም ሲመልስለት ይቤ ወልድ ዘሰ አምነኒ በቅድመ ሰብእ አአምኖ አነኒ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት ብሎ ረትቶታል። ቢቱ ግን በአባ ጊዮርጊስ የሐሰት ወሬ በመፍጠር ከንጉሡ ጋር አጣላው። አባ ጊዮርጊስንም ንጉሡ አስገረፈው ወከዐወ ደሞ ከመ ማይ በዲበ ምድር። ወእም ድህረዝ ወደይዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወበይእቲ ሌሊት አስተርአይዎ ኩሎሙ ሐዋርያት ወብዙኃን እምነ ጻድቃን ናዘዝዎ። ጻድቃን ሲሞቱ መላእክት ቅዱሳን ይደሰታሉ። ከድካም ከኀዘን ወደ ገነት እንኳን መጣህ ይሉታል። ወእንዘ ሀሎ አባ ጊዮርጊስ ውስተ ቤተ ሞቅሕ አእረፈ ዳዊት ንጉሥ ጻድቅ ወየዋሕ ወለሐዎ አቡነ ጊዮርጊስ ዓቢየ ላሐ። በግፍ ላሳሰረው ንጉሥ በጣም አለቀሰለት ደቀመዛሙርቱ ለምንድን ነው መደሰት ሲገባህ ሲሉት እስመ ኮነ ያፈቅራ ለማርያም ነበር ያላቸው። ወተወክፈ አባ ጊዮርጊስ ምንኩስና ደብረ ሊባኖስ እም አባ ዮሐንስ ከማ። ፍካሬ ሃይማኖትን ከደረሰ በኋላ ሊቃውንትና ንጉሡ አይተውት አማንኬ ዮሐንስ አፈወርቅ ወቄርሎስ ዘእስክንድርያ ተንስኡ በመዋእሊነ። ኢትዮጵያ ተመሰለት በቁስጥንጥንያ ወተዐርየታ ለእስክንድርያ አሉ። ይቤሉ አበው አልቦሙ ፋሲካ ለመነኮሳት እስከ ዕለተ ሞቶሙ። ወሶበ ይጼሊ አባ ጊዮርጊስ እንዘ ይብል ንዒ ኀቤየ ኦ ድንግል

ትመጽእ ኀቤሁ ዘልፈ እግዘእትነ ማርያም ኦ አኃውየ እስመ ለኩሉ ጸሎት ቦቱ ረባሕ። ለዘሂ ይጼሊ በስመ ነቢያት ይሔውጽዎ ነቢያት ወለዘኒ ይጼሊ በስመ ሐዋርያት ይሔውጽዎ ሐዋርያት በስመ ርእየ አባ ሲኖዳ። አባ ጊዮርጊስ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል።

ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

አባቱ ማርቆስ እናቱ እግዚእ ክብራ ትባላለች። መነኩሴው ማርቆስንና እግዚእ ክብራን በማደሪያየ እደሩ በዚችም ሌሊት ሩካቤ ሥጋ ሳትፈጽሙ እንዳታድሩ በሚካኤል ስም አምላችኋለሁ አላቸው እንዳላቸውም አደረጉ። ተወለደ በጸሎተ ሚካኤል አሉት። ንዴት በፍትወተ ሥጋ ቁረት በኀበ እግዚአብሔር ልዑል። በሕጻንነቱ ሲጾም ቄስ አባቱ አሁኑኑ መጾም የለብህም ብሎ ገርፎታል። በግድ አፉ ላይ ምግብ ይጨምርበትና በቃ ጾም ሽረሀል ብላ ይለዋል እርሱም በግድ አፌ ላይ ስለጨመርክ አልሻርኩም ሻርኩ የምባለው ፈቅጀ ብበላ ነበር አለው። ሀገሮሙሰ ለቅዱሳን ኢየሩሳሌም ሰማያዊት። ሐምሌ 21 ቀን አረፈ። ከሁሉም ቅዱሳን ግብር ቀሰመ።

ገድለ ቅዱስ እስጢፋኖስ

እስጢፋኖስ ማለት በግሪክ ቋንቋ አክሊል ማለት ነው። ገማልያልና ሐቢብ ናቸው የቀበሩት። ሌላ ስሙ አስተፓኖስ ነው። ናያስ መሠርይ በበሬው ጆሮ ሹክ ቢልበት በሬው ለሁለት ተከፈለ። እስጢፋኖስ ናያስን መልሰህ አስነሳው ቢለው አቃተው እስጢፋኖስ ግን ከሞት አስነሳው ሕዝቡም በኢየሱስ አመነ። ናያስም ወንበር አሰርቶ ወደ ሰማይ በኃይለ አጋንንት ሲሄድ የሕዝቡ እምነት ጎደለች። ቅዱስ እስጢፋኖስም እምነታችሁ አይጉደል አላቸው እና ጸለየ ወአውደቆ በጸሎቱ ለውእቱ ሰይጣን ጸዋሬ ናያስ ወወድቀ ናያስ። የናያስ ጓደኛ ተአምሩን አይቶ አመነ። ናያስንም እንዲያስነሳለት እስጢፋኖስን ለመነው። ናያስም ከሞት ተነስቶ በእግዚአብሔር አመነ። የስራይ መጽሐፎቹን በሙሉ በሕዝቡ ፊት አቃጠላቸው። ወሶበ ተሐጽነ ሙሴ ሠለስተ አውርኃ ሰመዩ ስሞ ምልክዓም። ወሰመየቶ ወለተ ፈርያን ምልክዓምሀ ሙሴ። ወኮነ ሳውል እም እለ ይፈትው ቀቲለ እስጢፋኖስሀ ወውእቱኬ ጳውሎስ ወአንበሩ ኀቤሁ አልባሲሆሙ እለ ቀተልዎ። ወወገርዎ በአእባን እንዘ ይሴብሆ ወየአኩቶ ለእግዚአብሔር ዘረሰዮ ድልወ ለዝንቱ ክብር ወአእረፈ ሶቤሃ። ወተቀጸለ በሠለስቱ አክሊላት አሐዱ በእንተ ድንግልናሁ ወአሐዱ በእንተ ተራድኦቱ ወአሐዱ በእንተ ስምዐ። ከዚህ በኋላ አጽሙ ለቀሲስ ሉቅያኖስ ተገልጾለት ከብዙ ዘመን በኋላ ወጥቶ ቤተክርስቲያን ተሰርቶለታል። ጳውሎስን አሪት ያስተማረው ገማልያል ነው።

ገድለ ሐዋርያት

ይህ መጽሐፍ ከ12ቱ ሐዋርያት በተጨማሪ የቅዱስ ማርቆስን የቅዱስ ሉቃስን የአብሮኮሮስን የሌሎችንም አርድእት ገድል አካቶ የያዘ ነው። ጥበብ ትእግስት ፍቅርና የውሃት የሐዋርያት ሐዋርያዊ ጉዞ መሣሪያዎች ነበሩ። የትንሹዋ እስያና የምሥራቅ ሀገሮች የሐዋርያትን ለስብከት ወንጌል መሰማራት ዜና ስለደረሳቸው በየክልላቸው ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ጀመሩ። ጸጉረ

ልውጥ እንግዳ ካገኙ ይገድሉታል። ወይም አርደው ለጣዖት መሥወዕት ያቀርቡታል። ቅዱስ ጳውሎስም ማንንም እንደማያስገቡ ስለተረዳ የጣዖት ልብስ ለብሶ ገባ። ሕዝቦቹም በደስታ ተቀበሉት። እርሱም ወደ ሀገሩ ገብቶ የሀገሩን ሰዎች በሙሉ አሳመነ። ሁለተኛ ጴጥሮስና በርተሎሜዎስ እልዋሕ ወደተባለው ሀገር ለሐዋርያዊ ተልእኮ ሲጓዙ እንዴት ወደዚህች ሀገር ለመግባት እንደሚችሉ ተመካከሩ። በዚህ ጊዜ በርተሎሜዎስ ቅዱስ ጴጥሮስን አንተ የባርያ ነጋዴ ነኝ ብለህ እኔ ደግሞ ለባርነት እንደምሸጥ ተናገር አለውና በዚህ ተስማሙ አደረጉትም። ቅዱስ ማርቆስ ግብጽ በሥጋ ዘመዱ በኩል አድርጎ ገባና ሰበከ። የእስክንድርያ ሕዝቦች ከማርቆስ በፊት ሕጻናትን እያረዱ ለጣዖት ያቀርቡ ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስ ወደሮም ለመሄድ በዝግጅት ላይ እያለ በጉዞ ላይ እያሉ የተሳፈሩበት መርከብ በማዕበል በመመታቱ ምክንያት ብዙዎች ተሳፋሪዎች በእያሉበት ሞቱ ከፊሎቹ ደግሞ ተበታተኑ። ከተበታተኑት መካከል አንድ ወንድሞቹና እናቱ የደረሱበት ጠፍተውበት በማያውቀው ሀገር ወደብ ላይ ቁሞ የሚያለቅስ ሕጻን አየና ቅዱስ ጴጥሮስ ጠየቀው ሕጻኑም ነገረው። ከዚሁ ሰዓት ጀምሮ ይህ ሕጻን የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ ሆነ ይህም ቀሌምንጦስ ዘሮም ነው። ቁጥሩም ከሐዋርያውያን አበው ነው። በዘመነ ሐዋርያት የቅዱስ ቁርባን ጸሎት አልነበረም። አንድ መዝሙርን ይዘምሩና ጌታችን በምሴተ ሐሙስ የተናገራቸውን ዓረፍተ ነገሮች ብቻ በማውሳት ምእመናኑ ቅዱስ ቁርባንን ይቀበሉ ነበር። የቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ መጻሕፍት ከነፕላቶን የፍልስፍና መጻሕፍት ጋር የተሳሰሩ ናቸው።የቀሌምንጦስ ዘሮም መጻሕፍት ግን ምንም ወዲያና ወዲህ የማይሉ ምስጢረ ሥጋዌን በተጣራ መንገድ የሚያስረዱ ናቸው። ቀሌምንጦስ ዘሮም በአድራሻ ትርያዳን ለተባለው የሮም ንጉሥ አንድ መጽሐፍ ጽፏል። የቤተ ክርስቲያን መምህራን ከዚሁ መጽሐፍ አውጣትተው ለመጀመሪያ ጊዜ ቅዳሴን አዘጋጁ። ይህ ቅዳሴም ለብዙ ዓመታት የቤተክርስቲያን መመሪያ ሆኖ እንደኖረ ይነገራል። ቅዱስ ጳውሎስ በተሳፈረባቸው መርከቦች የማዕበል አደጋዎች እያጋጠሙ በጉዞ ላይ ብዙ ወራት አልፈዋል። በዚሁ ወቅት ተሳፋሪዎችን በሙሉ አሳምኗል። የግኖስቲኮችን አካሄድ ያመነጨው የፍልስፍና አስተሳሰብ መሆኑ አይካድም። ጴጥሮስን ዘቅዝቀው ሰቀሉት ምእመናን አሸሸውት ጌታ ነው ምእመናን እየሞቱ አንተ ፈርተህ ትሸሻለህ ብሎ ገስጾት ሄዶ የተሰቀለ። ቅዱስ ጳውሎስ ስማቸው በአሁኑ ጊዜ ተለይቶ የማይታወቅ ብዙ ሀገሮች እየተዘዋወረ አስተምሯል። አንድ መግቢያ ብቻ ባላት በባሕር በተከበበች ሀገር ሲሄድ ከሩቅ አዩትና ሊገድሉት ሲሸቀዳደሙ አይቷቸው ሮጦ ዋሻ ውስጥ ገብቶ አመለጣቸው። ሦስት ቀንም ከዚህ አራዊት ካሉበት ዋሻ ተቀመጠ ራበውና አለቀሰ እመቤታችን ተገልጻ ጌታ ለዚህ ተግባር የመደበህ ልትሸሸና ልታለቅስ አይደለም ውጣና አስተምር አለችው። በሕይወት ብዙ ከቆዩ ሐዋርያት አንዱ ስምኦን ወልደ ቀለዮጳ ነው። የ150 ዓመት ሽማግሌ ነበር። ሰማእት ሆኜ መሞት እፈልጋለሁ ይል ነበር።አይሁድ ወደ ገደል ወረወሩትና በዚያው አረፈ። ቅዱስ ማቴዎስ አርሚስ የተባለ የጣዖት ካህን አሳምኖ ረድኡ አድርጎታል።ሉቃስና ጳውሎስ የተለየ የማስተማር ዘዴ ነበራቸው የሰጡትን ትምህርት በጽሑፍ እያሰፈሩ ለምእመናን ይሰጡ ነበር። ወንጌላዊ ሉቃስ ለጴጥሮስም ለጳውሎስም ረድእ ሆኖ አገልግሏቸዋል።እየጻፈ ስላስተማረ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ቀኝ እጁን ቆርጠውታል። ታዴዎስና ጴጥሮስ በአፍራቅያ ሲያስተምሩ በአንድ ቀን ስንዴ አብቅለው አድርሰዋል አመንዝራ ሴትንም በአውታረ ነፋስ ወደላይ ሰቅለው አሳምነዋል። ዮሐንስና አብሮኮሮስ ለአንዲት እጅግ በክፋቷና በአመንዝራነቷ

የታወቀች ሴት ባሮች በመሆን ሴትየዋ ሃይማኖተኛ ከመሆን አልፋ ፍጹም እስክትሆን አብቅተዋታል። ኢትዮጵያውያን ለብዙ ምዕት ዓመታት ክርስትናን ጠብቆ በመኖርና ክርስቲያናዊ ስያሜን ባህላቸው አድርገው መገኘታቸው ባይካድም እምነቱ አፍአዊና ባህላዊ ከመሆን አላለፈም። ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝነው ካህናቱ ሕዝቡን ወደ እውነተኛ እምነት ከመሳብ ይልቅ የሕዝቡን ባህላዊና አፍአዊ ልምዱን ተከትለው አብረው መንጎዳቸው ነው። ጴጥሮስን አጥቦ የቀበረው ማርቆስ ነው። ጳውሎስን አይሁድ ሊገድሉት ሲፈልጉት በቅርጫት አድርገው አስመልጠውታል። ጢሞቴዎስ ከማመኑ በፊት ጳውሎስን አስሮታል ለጣዖትም ሊሰዋው አስቦ ነበር። እናቱ ሙታበት ቢያስነሳለት ነው አምኖ የተከተለው። ጳውሎስ እንዴት መስበክ እንዳለበት ያስብ ነበር። ሳይታመም አመመኝ ብሎ ከድውያን ጋር ገብቶ አሳመነ። ፈላስፋ ብሂል ዘውእቱ መፍቀሬ ጥበብ። ሐዋርያት ጭቅጭቅን ተንኮልን ትልቅ ጥልን አያገኙም ነበር የሕዝቡን ቁጣ ያበርዱት ነበረ። ሰይጣን በሚያደርስባቸው ፈተና ሁሉ አያጉረመርሙም ነበር። ለእግዚአብሔር ብቻ በጸሎት አቤት ይሉ ነበር እንጂ። ክስተቶችን በሙሉ አቅለው ነበር የሚመለከቷቸው። የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ስለሆኑ ጠባቸው ከሰይጣን ጋር ብቻ ነበር። በሥጋዊ ጉዳይ አዝነው አያውቁም። ጳውሎስ ተአምር ሲሰራ ካህናተ ጣዖት በክርስቶስ አመኑ። ቴዎዳስም አመነ። ጌታ ለጳውሎስ ኢትዮጵያ የስብከትህ ክፍል ናት ብሎ ነገረው። ቅዱስ ጳውሎስ ገባልያ ወደምትባለዋ ሀገር ለስብከት ሲሄድ መጀመሪያ ከዳርቻ ሰው አገኘና ስለሀገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ እምነት አኗኗር ጠይቆ ተረድቶ ገባ። ጴጥሮስን በጥፊ መትቶታል ጳውሎስ ገርፎታል ሲገርፈው ግን ግርፋቱ እንዳይሰማው ይጸልይ ነበር። መልአኩም እንዳያመው አድርጎታል። በኋላ አመንኩ ብሎ ከእግራቸው ሲደፋ ሕዝቡም አመነ። አንዲትን ሀገር ደግሞ ከማስተማሩ በፊት 15 ቀን ጎብኝቷታል። ቅዱስ ጳውሎስንም አንገቱን ቆረጡት ደምና ወተትም ወጣው ሰማእትነቱንም ጨረሰ። ናትናኤልንም ሰቅለው ነው የገደሉት። ሀገረ ስብከቱ ሰማርያ ነበረች። ለያእቆብ እጎአ እግዚእነ ደግሞ ኢየሩሳሌም ደረሰችው። ለጴጥሮስ ሮም ደረሰችው። ለዮሴፍ ሁለት ወንድ ሁለት ሴት ልጆች ነበሩት ያዕቆብ ትንሹ ልጅ ነበር። በእንተ ዘሞተት እመ እም ንእሱ ተርፈ እንለ ማውታ ባሕቱ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ተወክፈቶ ወሐጸነቶ ወበእንተዝ ተሰምየ እጎአ እግዚእነ። ወደ ሰው በሎች ደረሰው ለማትያስ አስረው ሳር ሊያበሉት ነበረ እምቢ አላቸው። ለእንድርያስም በሊቀ ሐመር ተመስሎ ጌታ ተገለጸለት ጌታ እንደሆነ ግን አላወቀም ነበር። የክርስቶስ ሐዋርያ ስለሆንክ በነጻ ወሰድኩህ ይለዋል ማዕበልም አልተነሳብንም አለው። እንድርያስም መረቀው በዓለ ሐመር መስሎት። ጌታም ጠየቀው በእንተ ምንት አይሁድ ክህዱ ክርስቶስሀ እያለ ጠየቀው እንድርያስም ጌታ መሆኑን ሳያውቀው ያስረዳው ጀመር። በኋላ እርሱ መሆኑን ተረድቶ ደነገጠ። በትእቢት ተናግሬያለሁና ይቅር በለኝ አለ። ጌታም ይቅር አለው። በኋላ ለማትያስ እንድርያስ ደርሶለት አሳምኖ አስጠምቋቸዋል። እልዋህ የበርተሎሜዎስ እጣ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ አድርሶታል። በርተሎሜዎስ ባሪያ ተደርጎ በጴጥሮስ ተሸጠና ዐቃቤ አጸደ ወይን ሆነ እመቤታችን ወይነ በርተሎሜዎስ የተባለች ለዚያ ነው። የበርተሎሜዎስ ወይን ጥሩ ፍሬን አፈራ። በርተሎሜዎስን በታላቅ ስልቻ አሸዋ ሞልተው ከዚያ ጋር አስረው ባህር ውስጥ ጣሉት በዚያም ሰማእትነቱን ፈጸመ። የቶማስ እጣ ሕንደኬ ናት። ቤት ስራልኝ ብሎ ንጉሡ ለቶማስ ብር ሰጠው ቶማስ ግን መጸወተው። የንጉሡ ወንድም ሞቶ ተነስቶ ቶማስ በሰማይ የሰራለትን ሕንጻ ነገራቸው ከዚያ ሁሉም አመኑ።

ንጉሡም ደስ አለው። ማቴዎስም የጣዖት ልብስ ለብሶ ገብቶ ብዙ አሳምኗል። ማቴዎስም አንገቱን ተቆርጦ ነው የሞተ። ሉቃስም እንዲሁ። ሀገረ አፍራቅያ የደረሰችው ለፊልጶስ ነው። ጴጥሮስ ሽኝቶት ተመልሷል። ፊልሞና የሚባል የእንድርያስ ተማሪ ነበር። ገጸ ከልብ ሰዎች ሐዋርያትን እንደረዷቸው በብዙ ቦታ ተጽፏል። እንድርያስን በድንጋይ ወግረው ሰቅለው ነው የገደሉት። ለዮሐንስ የደረሰው እጣ ሀገረ እስያ ነው። አብሮኮሮስ ከ72ቱ አርድእት ነው ቁጥሩ። ሮምና ዮሐንስን እሳት አንዳጅ አብሮኮሮስን አጣቢ አደረገቻቸው። ሐዋርያት ሲፈውሱ ኃይለ እግዚአብሔር እንጂ እኛ ማዳን አይቻለንም ይሉ ነበር። ዮሐንስ ከጌታ ዕርገት በኋላ 70 ዓመት ኖሯል ከዚያም አርጓል። ልብሱን ጫማውን በምድር ጥሎ ሄዷል። ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስም በድንጋይ ተወግሮ ነው የሞተ። ለማትያስ የደረሰችው እጣ ደማስቆ ናት። ሐዋርያት በየሀገሩ መሰርያን ናቸው ተብሎ ተወርቷል ስለተወራም ብዙዎች እንዳይገቡ ይከላከሉ ነበር። ይቤሉ ሐዋርያት ኢአዘዘነ እግዚአብሔር ከመ ንፍዲ እኪተ ሀየንተ እኪት አላ ሰናየ ሀየንተ እኪት። ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ የሰውን ሁሉ ቋንቋ ያውቅ ነበር። አኮ ልሣነ ሰብእ ባሕቲቱ አላ ልሣነ እንስሳ ወአራዊት ወአእዋፈ ሰማይ ሶበ ይትናገሩ በልሳናቲሆሙ። እርሱም በሰይፍ ተቆርጦ ነው የሞተ። ማርቆስ ቦአ ብሔረ ግብጽ ሶበ በጽሐ ሀገረ እስክንድርያ ተበትከ ቶታነ አሣእኒሁ ወነጸሮ ለፈሐቂ ወወሀቦ አሣዕኖ ከመ ያሠኒ ሎቱ ወአሠነየ ሎቱ ወጸውዐ ስመ እግዚአብሔር። ወይቤሎ ማርቆስ እመ ተአምሩ ከመ አሐዱ እግዚአብሔር ለምንት ታመልኩ አማልክተ ወይቤሎ ፈሐቂ ንሕነ ንብል ስመ እግዚአብሔር በአፉነ ዳዕሙ ኢነአምር መኑ ውእቱ። ማርቆስኒ አሕየዎ እዶ ለአርያኖስ። ማርቆስን በገመድ አስረው በመንገድ ሳቡት። ወሥጋሁ ኮነ ግሙደ ዲበ ምድር ወተክዕወ ኮኩሐ ደሙ። ሚያዝያ 30 አረፈ። በድኑን ሊያቃጥሉት ብለው በተአምራት ሳይቃጠል ቀረ። ለታዴዎስ የደረሰው እጣ ሶርያ ነው ጴጥሮስ አድርሶት መጥቷል። ስንዴ ዘርተው ለእለት አድርሰዋል። ገበሬውም ምሳ ይዞላቸው ሲመለስ የሰሩትን አይቶ ተከተላቸው። ዘማዊቱን ሴት በነፋስ ሰቅለው ሁሉን ካስተማሩ በኋላ እርሷንም አውርደው አሳምነው ዲያቆናዊት አድርገዋት ሄደዋል። ጸልዮ በመርፌ ቀዳዳ ግመል አሳልፏል። ለእንድርያስ በይነ ዘያፈቅሮ አቡሁ ኖለቆ በነገደ ሮቤል ለጴጥሮስ በይነ ታፈቅሮ እሙ ፈድፋደ ሰመየቶ ነበ ነገደ አቡሃ። ዮሐንስ በይሁዳ ያዕቆብ በሌዊ የተቆጠሩም ሐተታ እንደነ ጴጥሮስ ነው። ፊልጶስ እም ቤተ ዛብሎን ማቴዎስ እም ቤተ ይሣኮር በርተሎሜዎስ እም ቤተ ንፍታሌም ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ እም ቤተ ጋድ ታዴዎስ ቀናኢ እም ቤተ ዮሴፍ ወናትናኤል እም ቤተ ብንያም ይሁዳ አስቆሮታዊ እም ቤተ ዳን እስመ ዳን ሴጦ ለእጉሁ ዮሴፍ ለዕ ብሩር ከማሁ ይሁዳኒ ሤጦ ለእግዚእ ለዕ ብሩር። መስከረም 1 በርተሎሜዎስ ግንቦት 27 ቶማስ ጥቅምት 12 ማቴዎስ ሐምሌ 2 ታዴዎስ ሐምሌ 5 ጴጥሮስ ወጳውሎስ ጥቅምት 22 ሉቃስ ጎዳር 20/ጎዳር 17 ፊልጶስ ሐምሌ 10 ናትናኤል ታኅሣሥ 4 እንድርያስ ጥር 4 ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ሐምሌ 18 የጌታችን ወንድም ያዕቆብ የካቲት 10 ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ መጋቢት 10 ማትያስ ሚያዝያ 17 ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ሚያዝያ 30 ማርቆስ ያረፈበት ነው።

ገድለ ላሊበላ

አባቶች ሁሉን ነገር ስለ እግዚአብሔር ብለው ተውት። ጸዊረ መስቀሉኒ ዛቲ ይእቲ ጾም ምስለ አኩቴት ፍቅር ምስለ ትሕትና የውሃት ዘምስለ ንዴት አንብዕ ዘምስለ ትግሀት አልጉሞ ልሳን

እምነገረ ጽርፈት እምነቢበ አመጻ ወሐሰት አንጽሖ ሥጋ ዝሙት ዐዪል ውስተ ገዳም በዘብድወ ጠሊ ወበሐሜለት ወተዘግሖ ውስተ ጾማእት አንጽሖ ልብ እም ሐልዮ ኃጢአት። ወተዘክሮ ሞት በኩሉ ጊዜያት። ላሊበላ ዘተሰምየ ገብረ መስቀል እምቅብዓተ ንግሡ። ረሀብኒ መከራኒ ኢይትከሀል ዘእንበለ ትእግስት። መዝ.43፣5 ግሥሦሙ ለአድባር ወይጠይሱ አድባረሰ ይሰመይ ሰይጣን ወአጋንንቲሁ በእንተ ልእልና ትዕቢቶሙ። እሳተ ፍቅር ዘውስተ ልቦሙ ለሐዋርያት አንደደ መድኅን። በዛቲ እሳት ጻድቃን አጥፍዑ እሳተ ውርዙት ዘዕቁር ውስተ ሥጋሆሙ ወአጥረዩ ንጽሐ። ሉቃ 12፣49 በዛቲ እሳት ውዕዮሙ መከሳት ደናግል ጎደጉ አውስቦ ወመከሳት አይበሱ ሥጋሆሙ በትሕርምት ወዔሉ ገዳመ እንዘ ይፈርሑ እም አናብስት። ቅዱሳን ሁሉንም ጽድቅ ሰሩት እንጂ እየመረጡ የተውት የለም። ኢገብረ ላሊበላ ምንተኒ እም ግብራት በዘያቴክዞ ለመንፈስ ቅዱስ ዘየኅድር ውስቴቱ። ኢይትገሐስ መንፈስ ቅዱስ እም ብእሲ ንጹሕ። በመዋዕለ አንጽሐ ብእሲ ርእሶ ይሔውጾ መንፈስ ቅዱስ ወየኅድር ውስቴቱ ወይነብር ምስሌሁ እንዘ ይመርሖ ፍናዊሁ ወእንዘ ይሜህሮ ቀትለ ወጸብአ ምስለ እድው ሰይጣን ወውእቱ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይከውኖ ሰይፈ ረድኤት። ወካዕበ በመዋእለ አገመነ ብእሲ ርእሶ የኅድጎ መንፈስ ቅዱስ ወየሐንቆ መንፈሰ ጋኔን ወይከውን ዕሩቀ እመንፈሰ ጥበብ ወአእምሮ እመንፈሰ ኃይል ወጽንዕ እመንፈሰ ልቡና ወርትዕ ወይትወደይ ቤቱ ሕምዘ ክሂድ ወዝሙት ወያረውጾ ድህረ አንስት ዘማውያን ወይወዲ ሰይጣን ውስተ ልሳኑ ነገረ ሐሰት ወነገረ ሐሜት ነገረ ጽርፈት ወነገረ ላኪ ወጋእዝ ነገረ ውዴት ወነገረ ጽልሑት ወቅንዐት ወሰይፈ በቀል ከመ ይቅትሎ ለእጉሁ ወባእስ ወሕሰም ወይትፈሥሑ አጋንንት በሞቱ። ወይሣለቁ ቦቱ እንዘ ይብሉ ለምንት ኢገበርከ ጽድቀ። ኃጢአት ለምን ሰራህ እያሉ ይዘብቱበታል። እርሱም የማይጠቅም ጸጸት ይጸጸታል። ኢተግኅሰ ላሊበላ እምቃለ መጻሕፍት ዘውእቱ እስትንፋሰ መለኮት። እንዘ ይጼእልዎ ኢጸአለ ወእንዘ የሐምምዎ ኢተቀየመ አላ አግብአ ፍትሐ ለዘይኴንን ጽድቀ። ኢትጻኡ እምቃለ መጻሕፍት ከመ ኢተአብሱ። ላሊበላ እግዚአብሔር እንዳሳየው አድርጎ ቤተክርስቲያንን ሰራ። ሰኔ 12 ቀን አረፈ። ምርዓት ሥሥዕት አፍቅሮ መብልዕ ወመስቱ ወአፍቅሮ ፍግዐ ዘበምድር ዝንቱ ኩሉ ወዘይመስሎ ንዋየ ሐቅሉ ውእቱ ለሰይጣን ወምጉንጻሁኒ ሥጋ ውእቱ። ቅዱሳን መከራን በደስታ የተቀበሉት ክብር ስለሚያሰጥ ነው።መከራን በማንጎራጎር ካሳለፍነው ግን ክብር አያሰጥም። ነሚአ መንግሥትሰ ኢይትከሀል ዘእንበለ ፈቃደ እግዚአብሔር። ወሀለወት አሐቲ ብእሲት እኪተ ምግባር እጎቱ ለላሊበላ። ወይእቲኬ አምጽአት ሎቱ ለእጉሃ ገቢራ ሥራየ ወሕምዘ ቶሲሓ ወአዘዞ ላሊበላ ለአሐዱ ዲያቆን ዘይቀውም ቅድሜሁ ወይቤሎ ስተይ መቅድመ እንዘ ትባርክ ሊተ እስመ ከመዝ ልማዱ ለላሊበላ ወሞተ ዲያቆን ወከልብኒ ሞተ ወሰትየ ዘንተ ላሊበላ በእንተ ፍቅር። ነገር ግን በላሊበላ ሆድ ውስጥ አውሬ ነበረ ያን ገደለው። አውሬውም ወጣ። አውሬው ሲወጣ ላሊበላን አደከመው መልአክ ነፍሱን ወስዶ ምስጢረ ሰማያትን አሳየው። ቅዱስ ገብርኤል ይረዳው ነበር። ይትነሳእ እግዚአብሔር ወይዘረው ጸሩ የሚለውን መዝሙር ሰይጣናት በጣም ይፈሩታል። ለላሊበላ ሕንጻውን ለማየት የሚመጣውን እንደሚምርለት ቃል ገባለት። ላሊበላ 3 ቀን ሙሉ ምስጢረ ሰማያትን አየ ወአመ ሣልስት ዕለት ተመይጠ ኀበ ሥጋሁ ምውቅት። ሥጋው ስላልቀዘቀዘ አልቀበሩትም ነበርና። ይሄይስ ነቢር ምስለ አራዊት እም ነቢር ምስለ ሰብእ መሪረ ልሳን። ገዳም ሄዶ ላሊበላ አድኖ ነበር የሚበላ። መስቀል ክብራን አገባ። ላሊበላ ብሂል ንህብ አእመረ

ጸጋሁ ብሂል። መስቀል ክብራን ቅዱስ ሚካኤል ይጠብቃት ነበር እርሷ ግን አታየውም ነበር። የላሊበላ ክርስትና ስሙ አሠረ ክርስቶስ ነው። እናቱ ኪርወርና ትባላለች። አባቱ ዛን ስዩም ይባላል። ላሊበላ ኢየሩሳሌምንም ጎብኝቶ መጥቷል። ይቤ እግዚአብሔር ኢወሀብክዎ መንግሥተ ለላሊበላ በእንተ ክብረ ዓለም አላ በእንተ አብያተ ክርስቲያናት ዘሀለዎን ይትሐነጻ እንበለ እጽ ወመሬት። ንጉሥ ሐርበይ በኋላ ንሥሓ ገብቶ ንግሥናውን ለላሊበላ አስረክቧል። ላሊበላ ከአንድ ድንጋይ 10 አብያተ ክርስቲያናት ሠራ። እሉ እሙንቱ ቤተ ማርያም፣ ቤተ መድኃኔዓለም፣ ደብረ ሲና፣ ቤተ መስቀል፣ ቤተ ደናግል፣ ቤተ ሊባኖስ፣ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ መርቆሬዎስ፣ ቤተ አማኑኤል፣ ቤተ ጊዮርጊስ። ቅዱስ ላሊበላ ከሦስት ጉራሽ በላይ አይበላም ነበረ። መጠጡም አንድ ጽዋ ውሃ ነበር። መራ ተክለሃይማኖት የድልነዓድን ልጅ መሶበ ወርቅን አግብቶ ነገሠ። አዲስ ሥርወ መንግሥት በላስታ አቆመ። ከመሶበ ወርቅም ጃንሥዩምን ትርድአነ ገበዝን ግርማ ስዩምን ጠጠውድምን ወለደ። ጠጠውድም ገብረ መስቀልን ገብረ መስቀል አቡነ አሮንን ወለደ። ግርማ ስዩም ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስን ወለደ። ጃን ስዩም ቅዱስ ላሊበላን ወለደ።

ገድለ ይምርሐነ ክርስቶስ

አመ ተወልደ ከሠተ አዕይንቲሁ ወአንጸረ መንገለ ምሥራቅ ወሰብሖ ለአምላከ ሰማይ። አድኅ ዲቁናን ተቀበለ። ቅድስት ሕዝባ የምትባል ሚስት አገባ። ከዚያ ቅስና ተሾመ። ወነበረ ብዝኀ ዓመታተ በተጽናስ ወኢፈተወ በሥጋሁ ተድላ። ወአጥመቀ ብዙኃነ አረማውያነ ምሂሮ። ስመ መንግሥቱ ዳዊት ነው። ቅብዓ መንግሥት የቀባው እንደ ላሊበላ ራሱ ጌታ ነው። ሩፋኤል መልአክ ነው የረዳው። ቅንዓት ወትምክሕት ወትእቢት እሙንቱ ንዋየ ሐቅሉ ለሰይጣን። በማየ አይኅ ጊዜ ርግብ በእባብ አፍ እንቁላሏን ጥላ ፈጥፍጣለች። እባብም እንዳልበላው እግዚአብሔር ያወጣኛል እንዳልተፋው ተሰብሮ እግዚአብሔር ይፈርድብኛል ብሎ ዝም አለ። ጠቢብ ያሰኘው ይህ ነው። በሞት ይትፈጸም ኩሉ። ይምርሐነ ክርስቶስም በግዛቱ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ብሎ አወጀ። ወዓዲ ሠርዐ ከመ ኢያምልኩ ጣዖተ ኢተአምሩኑ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም ባሕቲቶ ፈጠሮ። ይመስለክሙኑ ዘነጥዐ ምእተ አዕጽምተ ከመ የሀቦ ለአዳም ረስዮ ምእተ አንስተ ከመ ይብዛኅ ሎቱ ፍጡነ። ወእግዚአብሔርሰ ኢገብረ ከመዝ አላ ወሀቦ አሐተ ከመ ለነ ያርኢ ሥርዓተ። እስመ ኅሊና ነቅዐ ውእቱ ለኩሉ ግብር። ክፉ ሕሊና ስታስብ ጸጋ እግዚአብሔር ይለየሃል። ወቂርቆስኒ ረድኦ ለይምርሓ። ይምርሓ በባሕር ላይ ቤተክርስቲያን ሰርቷል። ቅድስናውን አይተው ከሮም 50740 ሰዎች ጳጳሳት ካህናት መጥተው ኑረዋል። ክፍለ ድንግል ማርያም ይእቲ ዛቲ አድያም ኢትዮጵያ ወኢይነግሥ በውስቴታ አይሁዳዊ ወኢአረማዊ አላ ዘርቱዕ ሃይማኖቱ። እም ኩሉ አህጉር ትከብር ኢትዮጵያ። በመንግሥቱኒ ኢፈተወ ይምርሓ ትፍግዕተ ለሥጋሁ አላ ነበረ በጽሙና ወይጸውም ወትረ። ይምርሓ ጥቅምት 19 ቀን አረፈ።

ገድለ ቅዱስ ገብረ ማርያም

ገብረ ማርያም በይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት የነበረ መነኩሴ ነው። ማኅሌተ ጽጌን ከአባ

ጽጌ ብርሃን ጋር ሆነው ደርሰዋል። ገብረ ማርያም በወረኢሉ አውራጃ የደብረ ሐንታ ገዳም የሕግ መምህር ነበር። አባ ጽጌ ድንግልም ወሎ ነበሩ። በየሀገሩ እየዞሩ ያስተምሩ ነበር።በደብረ ሊባኖስ ተቀብረዋል። አባ ገብረማርያም መስከረም 15 ቀን አረፈ።

ገድለ ተክሥተ ብርሃን

የትውልድ ቦታቸው መንዝ ነው። መንዝ ደመ ክርስቶስን መልአኩ ዑራኤል ሲረጭ አስቀድሞ የነጠበባት ቦታ ናት። የተክስተ ብርሃን የመጀመሪያ ስማቸው አባ በኪሞስ ነው። በ12ኛው ክፍለ ዘመን በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር መጥተዋል። የተቀመጡበት ቦታም ዲማ ጊዮርጊስ ነው። የተክስተ ብርሃን መምህር አባ ፊልጶስ ዘደብረ ሊባኖስ ናቸው። ወአጥመቀ ኩሎ ሰብአ ጎጃም። ደብረ ድማኅ ተአቢ ወትትሌዓል በስባሔ ወበክብር እም ኩሎን አድባራት። ሥእርተ ርእሱ ወአጽሙ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ያለው ዲማ ነው። ሰው ለመታገሥ ጥብዓት የማይኖረው ፍቅረ እግዚአብሔር ስለሌለው ነው።

ገድለ ገብረ ናዝራዊ

ኢትዮጵያዊ ናቸው። ደብረ ጎረይክዋ የእርሳቸው ገዳም ነው። ቆመ ብእሲ ማለት ምሰሶ ማለት ነው። በሰሜን ሸዋ ይፋትና ጥሙጋ ደብረ ሲና በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተወለዱ። በትግራይ ብዙ አስተምረዋል። መከበርን አይወዱም ነበረ። ወአስቆረረ ፍጹመ ተወድሶ በጎበ ሰብእ። ሶበ ድኅነ ዳዊት እም እደ ሳኦል ንጉሥ ይቤ አድህነኒ እግዚኦ እም ብእሲ እኩይ እስከ ተፍጻሜቱ።

ገድለ ሊባኖስ

አባ ሊባኖስ በሮም ተወለዱ። በ530 ዓ.ም በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት የነበሩ ጻድቅ ናቸው። ከሮም እንደመጡ በአክሱም አካባቢ ባሉት ገዳማት ይኖሩ ነበረ። ከዚያም መጥተው በቀድሞ ስሙ ዜጋመል ግራርያ በዛሬው አጠራር ደብረ ሊባኖስ በጸሎት በተጋድሎ ብዙ ተአምራትን በማድረግ ኢአማንያንን አሳምነዋል። በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ደብረ ሊባኖስ የሚለውን ስያሜ አግኝቷል። አባ ሊባኖስ በዚች ምድር 500 ዓመት ነው የኖረው። ሐምሌ 3 ተወለዱ አባ ሊባኖስ መነነ ዓለመ ምስለ ተድላሃ። አባ ሊባኖስ ጥር 3 ቀን አረፈ። ከጫጉላ ቤት ነው የመነነ።

ገድለ ዜና ማርቆስ

ጎዳር 24 በሸዋ ተወለደ እናቱ ማርያም ዘመዳ ትባላለች። አቡነ ተክለ ሃይማኖት አመነኮሰው። ምሁር ኢየሱስ ገዳም 40 ዓመት ዘግተው አስተምረዋል። ምሁር ኢየሱስን የመሰረቱት እርሳቸው ናቸው። የዜና ማርቆስ አባት ጥንተ ሙላዱ ፍልስጥኤም ነው። ፍልስጥኤም ብሂል ፍልጥ ርስቶሙ ለደቂቀ ሌዊ ብሂል። ሳዶቅ ብሂል እግዚእ መሐር። የተክለ ሃይማኖት ዘመድ ነው። ዜና ማርቆስ በተወለዱ በሦስት ቀናቸው እሰግድ ለአብ እሰግድ ለወልድ እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሉ። በሦስት ዓመት ብሉይና ሐዲስ ተማረ። በጣዖት ላይ ሰይጣናት

ያድራሉ፡፡ አኖሬዎስ የዜና ማርቆስ የእህት ልጅ ነው፡፡ ይኩኖ አምላክ የዜና ማርቆስ የእናቱ ወንድም ነው፡፡ ነአኩቶ ለአብ የተሰወረባት ቦታ አሸተን ማርያም ትባላለች፡፡ ሰብአ ሸበል ወሰብአ ደጀን አምኑ በእደዊሆሙ ለአርድእተ አቡነ ዜና ማርቆስ ወአጥመቅዎሙ ወመሀርዎሙ ሃይማኖተ፡፡ ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት የሚለውን ዜና ማርቆስ ሲተረጉመው ዘመድ ብሂል ሰይጣን እስመ ሰይጣን ይደመሮ ለሰብእ በምክንያተ ኃጢአት ወአምልኮ ባዕድ እም ንዕሱ እስከ ርእስናሁ በእንተዝ ተሰምየ ዘመደ፡፡ ፀዐቲ ዘይከውን በአጽንዖ ጾም ወጸሎት፡፡ ኩኑ ከመ ሐዋርያት ትጉሃነ በስብከተ ወንጌል፡፡ ወኩኑ ከመ ሰማእታት መስተጋድላነ በሃይማኖት፡፡ ወኩኑ ከመ ጻድቃን ግሑሣነ እም ነገር እኩይ በአርምሞ ወበትእግስት በኩሉ ጊዜ፡፡ (ማንኛውም ቅዱስ ቢረዳህ ያው ነው ክብሩ ከአንዲት ቤተክርስቲያን መጥቶ ነውና የረዳህ፡፡ የሁሉም እርዳታ እንደሆነ አስተውል)፡፡ መጽሐፈ ገድሉሰ ተጽሕፈ በዘመነ መንግሥቱ ለዓምደ ጽዮን ወበዘመነ መንግሥቱ ለንጉሥነ ዘርዓ ያዕቆብ፡፡ አባ ዮሐንስ ጽሒፎ ደመረ ቦቱ ምስለ መጽሐፈ ገድሉ ዘቀዲሙ ወበደኃሪ መዋዕል አባ ቃለ ዓዋዲ ወሰከ ቦቱ በዘመነ መንግሥቱ ለልብነ ድንግል፡፡

ገድለ ሀብተ ማርያም

አባቱ ፍሬ ቡሩክ እናቱ ዮስቴና ይባላሉ፡፡ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ የምትለዋን ጸሎት ዛቲ ጸሎት ሰናይት ይእቲ ይል ነበረ፡፡ ይቤሎ እግዚእ ለሀብተ ማርያም አስተዳሎኩ ለከ ሰብዓተ አክሊላተ አሐዱ በእንተ ዘታነብብ ዘልፈ አርባዕተ ወንጌላተ ወካልዑ በእንተ ዘኢያኅጸርከ ቂመ ወበቀለ ወጽልሑተ ትዕቢተ ወትምክሕተ ውስተ ሕሊናከ ወሣልሱ በእንተ ንጹሕ ክህነትከ ወራብኡ በእንተ ዘተአገሥከ ጻማ በእንቲአየ፡፡

ገድለ ሳሙኤል ዘዋልድባ

አቡነ ሳሙኤል በአክሱም ጽዮን ተወለዱ፡፡ ደብረ በንኮል ሄደው ከአባ መድኃኒነ እግዚእ ምንኩስና ተቀበሉ የነበሩበትም ዘመን ከ1365 እስከ 1395 በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ መጠጡ ውሃ ምግቡ ገለባ ነበር፡፡ አንዱ ስጋ ወደሙን ተቀብሎ ቢያስታውክ አባ ሳሙኤል ትውኪያውን ከነመሬቱ በላው ላሰው፡፡ በዚህም እግዚአብሔር አከበረው፡፡ተመይኖ ቀሊል ውእቱ በጎበ ሰይጣን ወይትሜሰል በአርአያ ኩሉ፡፡ ወሶበ ይከብዶ ንዋም ለሳሙኤል ይገብር ግብረ እድ፡፡ አባ ሳሙኤል አንድ አንበሳ ታሞ በመርፌ በጥቶ አድኖታል፡፡ ዝንቱ ውእቱ አባ ሳሙኤል ዘቀደሳ ለሐቅለ ዋሊ በአንሶስዎቱ፡፡ ውርዝውና ኢሞያ ለአባ ሳሙኤል፡፡ አባ ሳሙኤል ለአራዊት ለእንስሳት ሳይቀር ያዝንላቸው ነበረ ጭንቀታቸውንም ያቀልላቸው ነበረ፡፡ ወሶበ ይዌድስዎ ለአባ ሳሙኤል በቅድሜሁ ኢይሁብ ፍሥሓ ለልቡ፡፡ በአንበሳ ተጭኖ ይሄድ ነበር፡፡ብጹዕ ውእቱ ዘያነብብ ውዳሴሃ ለእመ ፈጣሪ፡፡ ለእመ ተባረከ ምግብ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ይሠዐር ኩሉ ሕምዝ ወሥራይ፡፡ ዝናብ ሲመጣ ታላላቅ አንበሶች መደዳውን ይሆኑና ከዝናብ ያድኑት ነበር፡፡

ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን

የትውልድ ሀገሩ ኢየሩሳሌም ነው። አባቱ ምናጦስ እናቱ ማርያም ሰናይት ትባላለች። ከጌታችን ልደት በኋላ በ245 ዓ.ም ጎዳር 26 ቀን ተወለደ። ከእናቱም ማኅጸን እንደ ወጣ ዕለቱን ሥላሴን በአንድነት በሦስትነት አመስግኗል። በ257 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ከአቡነ አትናቴዎስ ጵጵስና ተቀብሎ የኢትዮጵያን ሰዎች ዙሮ በማስተማር የክርስትናን ጥምቀት አስፋፍቶና አጠናክሮ አጠመቀ። ጳጳስ በሆነ በሦስት ዓመቱ ጣና ዳጋ እስጢፋኖስ መጥቶ ነገሥታቱም መጥተው ሦስት ዓመት እያስተማረ ቆየ። የኢትዮጵያ ሰዎችም በመላ ክርስቲያኖች ሆኑ። አብርሃ ወአጽብሐም ደብረ ሣህል ጣና ቂርቆስን ሰሩ። ኢየሩሳሌም ይእቲ ማእከላ ለምድር። ከሣቴ ብርሃን ሐምሌ 26 ቀን ዐረገ። ወመጽአ ፍሬምናጦስ እምኢየሩሳሌም ኀበ ብሔረ ኢትዮጵያ ምስለ አሐዱ ነጋዲ ዘስሙ ሜርጵዮስ ወምስሌሆሙ አሐዱ ወልድ ዘይሰመይ አድስዮስ ወበጽሑ ኀበ ብሔረ አግዓዚት እንዘ ይመርሖሙ መልአከ እግዚአብሔር። ለሜርጵዮስ ቀተልዎ ፈያት ወማኅረክዎሙ ለእሙንቱ ሕጻናት ሰብአ ይእቲ ሀገር ወወሀብዎሙ ለንጉሠ አክሱም ዘስሙ አልዓሜዳ። ወእምዝ ነግሡ አብርሀ ወአጽብሐ ወአፍቀርዎ ፈድፋደ ለማር አቡነ ሰላማ ወበአሐቲ እለት ይቤ ፍሬምናጦስ ግዝረትሰ ወእምነት ሀሎ ኀቤክሙ ጥምቀት ወነሢዐ ቁርባን ኢሀሎ። ወይቤሎ ቅዱስ ሚናስ ግዝረተሰ አምጽኡ ሌዋውያን አበዊነ።ወእምነተ ክርስቶስ አምጽአ ሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ወበእንተ ጥምቀትሰ ወነሢአ ቁርባን ኢተፈነወ ሐዋርያ ኀቤነ። ወነሢኦ ፍሬምናጦስ መባሕተ እምነ ነገሥት ኄራን አብርሀ ወአጽብሐ ሖረ እስክንድርያ ወአስተፋነውዎ ነገሥት ኄራን ወወሀብዎ ወርቀ ወስንቀ ለፍኖቱ ወብዙኃን ሠራዊት ምስሌሁ። ወሐጸቦ እገሪሁ አቡነ አትናቴዎስ ወወለጠ ስሞ እንዘ ይብል ይኩን ስምከ ሰላማ ወሤሞ ጵጵስና ላዕለ ሀገረ ኢትዮጵያ። ወወሀቦ አልባሳተ ዘቤተክርስቲያን ወንዋያተ ቅድሳት ወመጻሕፍተ ብዙኃተ ወተግሣጻተ ዘአልቦ ኀልቁ ወመስፈርት ታቦተ ወቅብዓ ሜሮን ጽዋዓተ ወኮሳኩሳተ ወጽንሐሐተ ወመስቀላተ ወሠርጓተ ዘቤተ ክርስቲያን። ወይቤሎ አትናቴዎስ ለከ አወፊ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ጽዮንሃ ወይቤሎ ፍትሕ ወርትዕ ይብዛኅ በላዕሌከ ወበላዕለ ነገሥት ኄራን አብርሀ ወአጽብሐ ወበሀገረ ኢትዮጵያ ፍቅር ወሰላም ጠል ወልምላሜ ለምድር አንቅዕት ወቀላያት አትክልት ወአዝእርት ጽድቅ ወሰላም ይብዛኅ ላዕለ ሀገረ ኢትዮጵያ። ከዚያ ተሸሞ መጥቶ አብርሃን አጽብሐን ቅብዓ መንግሥት ቀባቸው። ወእም ድህረ እብነ ሐኪም ነበረት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ ሐይመት። ወገብሩ ላቲ አብርሃ ወአጽብሐ መቅደሰ ለታቦተ ጽዮን። ከዚያ ካህናትን ዲያቆናትን ሾመ። ወባረካ ሰላማ ለምድረ ተምቤን። ወነበሩ አጋንንት በሀገረ ትግራይ እለ ያስሕቱ ሕገ እግዚአብሔር ወይመክሩ ጠዋየ ነገረ። ወበእስኪቶሙ የኀድሩ ወያመጽኡ ዝሙተ ከመ ኢይግበሩ ትእግስተ ወንጽሕና። ወበከርሶሙ የኀድሩ ወበልብ የኀድሩ ወያጸምምዎሙ እዝኖሙ ከመ ኢይስምኡ ነገረ ሃይማኖት። ወበርእሶሙ የኀድሩ ከመ ኢይግበሩ ጸሎተ ወኢይትሜህሩ ሃይማኖተ።በሐቂሆሙ ወበእንግድዓሆሙ የኀድሩ ወያመጽኡ ዝሙተ። በአፉሆሙ ወበከናፍሪሆሙ የኀድሩ ወያመጽኡ ሐሰተ ወክህደተ። ወበአማዑቲሆሙ የኀድሩ ያመጽኡ ረሀበ ከመ ኢይፈጽሙ አጽዋማተ። ወበአስናኒሆሙ የኀድሩ ወያስሕቅዎሙ በነገረ ከንቱ። ወበመከየዲሆሙ የኀድሩ ወይወስድዎሙ ኀበ ስርቀት ወበንዋየ ውስጦሙ የኀድሩ ያመጽኡ ቂመ ወበቀለ ወጽልዓ ላእለ ቢጾሙ። አክብር

አባከ ወእመከ ዘይቤ እሙንቱ ሰብዓቱ አበዊሁ ለሰብእ አበ ሥጋ፣ አበ ክርስትና፣ አበ ነፍስ፣ አበ አስኬማ፣ አበ ሐሊብ፣ አበ ሃይማኖት፣ እግዚአብሔር። ተመክሐ በሃይማኖትክሙ ወአንከሩ ሰብአ ወልቃይት ኂሩቶ ወሣዕስዐ አፉሁ ወጣዕመ ነገሩ ለአባ ሰላማ ወእምዝ ሖረ ምድረ አገው። ወነበረ ብጹዕ ወቅዱስ ማር አቡነ ሰላማ በምድረ ሃይማኖት ጎጃም ወያፈቅሮሙ ለሰብአ ጎጃም ወአዕጻዳቲሃ ወአህጉራቲሃ ወኩሎሙ ሰብአ ዚአሃ ወለቃውንቲሃ መምህራኒሃ ወለካህናቲሃ ከመ ይወስኩ ጥበበ ላዕለ ጥበቦሙ ወባረካ ለምድረ ሞጣ ወደወለ ዋሸራ ዘብሔረ ጎጃም።

ገድለ አቡነ ሐራ ድንግል

በ1530 አካባቢ በበጌምድር ውስጥ በደራ ወረዳ በምትገኘው በላጉና ተወለዱ። ሐራ ድንግል የክርስትና ስማቸው ነው። የዘጌው የአቡነ በትረ ማርያም የዘመን ጓደኛ ናቸው። ንሕነ ሰብእ መሲሐውያን ደቂቀ አሐቲ ቤተክርስቲያን። ለሐራ ድንግል ሦስት ወንድም ሦስት እኅት ነበረው። ብሉይ ሐዲስ ተምሯል። እለሰ ይፈቅዱ ያእኩትሞሙ ሰብእ ነሥኡ እሴቶሙ እም ኀበ ሰብእ። ጠዋይ ኅሊና ያርሕቅ እም እግዚአብሔር። ሱስንዮስ የካቶሊክን እምነት ባወጀ ጊዜ ቦ ሰብእ እለ ተሰዱ ብሔረ ርጉቀ ለአድኅኖተ ሃይማኖቶሙ ወቦ እለ ተቀትሉ በእንተ ሃይማኖቶሙ። ወቦ እለ ሞቱ በካልዕ ሞት። ወቦ እለ ቦኡ በዛቲ ሃይማኖት ርኩስት/ካቶሊክ በእንተ ፍርሃት ወቦ እለ ቦኡ በእንተ ረኪበ ክብር ኃላፊ ወቦ እለ ቦኡ እስመ መሰሎሙ ዘይጸድቁ ቦቱ። የአዳም ቋንቋ እብራይስጥ ነበረ። ሐራ ድንግል ጥር 11 ቀን አረፈ። ሠዐልያን የቅዱሳኑን ሥዕል ሲስሉ ከቅዱሳኑ ትልቅ በረከት ያገኛሉ።

ገድለ አቡነ ተክለ ሐዋርያት

ስለሥጋ ወደሙ ክብር ታማሚው ሰው ወደላይ ያለውን ሐሞትና መግል የቀላቀለውን ትውከት በጠጡ ጊዜ በዚህም ምክንያት ጌታችን በግንባራቸው ፀሐይን አተመላቸው። የተወለዱ ኢትዮጵያ እናርት በምትባለው ቦታ ነው። ተጋድሏቸውን የፈጸሙት ደብረ ሊባኖስ አጠገብ ዐገታ ብርሃን ነው። አቡነ ተክለ ሐዋርያት የሸዋ ሰው ናቸው። አቡነ ተክለ ሐዋርያት ትፋቱን ሲበላው ኢተዘከረ ጼና ጸዐቱ አላ ክብረ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ። አባቶች ሲገናኙ ነገራተ እግዚአብሔርን ይጨዋወቱ ነበር። አቡነ ተክለ ሐዋርያት ጣዖት ቤትንና የጣዖት ተከታዮችን በእሳት አቃጠለ። ወወሀቦ እግዚእ ሰብዓተ አክሊላተ አሐዱ በእንተ ንግደቱ ለምህሮ ሃይማኖት እም ሀገር ለሀገር ወአሐዱ በእንተ የውሃቱ ወአሐዱ በእንተ ክህነቱ።

ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ

ሊቃውንት መማር በአእምሮ ጠባይዕ ውስጥ ተሰውሮ ያለውን የእውቀት ብርሃን የሚገለጽበት የአእምሮ መክፈቻ ነው ይላሉ። ይህ መጽሐፍ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዘመነ ተንባላት ያለውን ታሪክ ያካተተ ነው። የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ብዙ ማስረጃ ሰበሰብኩ ቢሆንም ይህም የተሟላ አይደለም ስለዚህ የራሴንም አስተያየት በመጨመር አስፋፋሁት ይላል። የዓለም አፈጣጠር ከጥበበኞች አስተሳሰብ እጅግ የራቀና የረቀቀ ነው። መጀመሪያና

መጨረሻ የለውም ፍጡርን ከፈጣሪ ለይቶ አያሳይም የሚሉ ነበሩ። በእነርሱ ዘንድ ስሩ ከግንዱ ሆኗል። ሌላም ሌላም የሚሉ ነበሩ። የቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሰሩ አባቶች ግን ዓለም መጀመሪያና መጨረሻ አለው አሉ ቅዱሳን ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ ከተናገሩት ቃልም ለማስረጃነት አቀረቡ። ይህ እውነተኛው ትምህርት ነው። ጥበበኞች ግን ከልባቸው ያመነጩትንና በመፈላሰፍ በመመራመር ያገኙትን ለመግለጽ ሞከሩ። እኛ ግን ከኦሪትና ከነቢያት መጻሕፍት ባገኘነው መንፈሳዊ እውቀት የዓለምን አፈጣጠር ምስጢር መረዳት እንችላለን። ሰዎች ስለዘመን ብዙ ተከራክረዋል መጀመሪያ የለውም የሚል ክህደት ያነሱ አሉ። ሌሎቹ ደግሞ ዘመን ቀዋሚ ነው የተገኘውም በራሱ ፈቃድ ነው አይለወጥም መጨረሻም የለውም ይላሉ። ጻድቃን ግን የመዓልት ትርጉሙ ፀሐይ ለተጀመረበት ጊዜ የተሰጠ ነው ይላሉ። የክርስቲያኖች አካሄድ ከፈላስፎችና ከሕግ አውጭዎች ይለያልና። ቃየል ሄኖህን ሄኖህ ጋይድን ጋይድ አሜኤልን አሜኤል ማቱሳላን ማቱሳላ ላሜህን ወለደ። ላሜህ ሴላና ሐዳን አገባ። ሐዳ ዮሴድን ወለደች እርሱ ማደሪያዎችን ሰራ። ሐዳ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘፈንና የመሰንቆ ጨዋታን አሳየ። ሴላ ቶቤልን ወለደችው። ብረትን መስራት የጀመረው ቶቤል ነው። አዳም ፴ ወንዶችንና ፴ ሴቶችን ወልዶ ነው የሞተው። አዳም ሲሞት ልጆቹ በመዛግብት ዋሻ ቀበሩት ዋሻው በደብር ቅዱስ ይገኝ ነበር። ሴትና ልጆቹ በደብር ቅዱስ ሆነው መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይሰሟቸው ነበረ። የሴት ልጆች ከደብር ቅዱስ ከሚገኘው የዕፅ ፍሬ ይመገቡ ነበር። ቃየልና ዘሮቹ ደግሞ የዘሩትን ይመገቡ ነበር። ቃየል የምድር አራሽ ነበረና። አቤል ስራው በጎችን ማርባትና መጠበቅ ነበር። አቤል የተገደለው በ300 ዓመቱ ነው። የመጀመሪያው ቋንቋ ዕብራይስጥ ነው የሚሉ አሉ ሦርያኛ ነው የሚሉ አሉ። የቃየል እድሜ አጠቃላይ 730 ነው። በቃየል ዘመን የቤቱል እህት ኑሄም ከቃየል ዘር የነበረች የተለያየ ጎብረ ቀለማት ያለውን ግምጃ ሰራች። ዮቤድ የተባለው ደግሞ ብዙ የቅኝት አውታሮች ያሉት መሰንቆን ሰርቶ መሰንቆውን እየመታ ይዘፍን ነበር። ይህን የጀመረ እርሱ ነው። አውሬዎችና ወፎች የመሰንቆውን ድምጽ ለመስማት ይሰበሰቡ ነበር። ዮቤድ መሰንቆን መስራት ከጀመረ ወዲህ የቃየል ልጆች ሌት ተቀን መዝፈኑን ተያያዙት እረፍት አልነበራቸውም። ዘፈናቸውም የጥጋብ ዘፈን ነበር። ደቂቀ ሴት ዘፈኑን ሲሰሙ ከደብር ቅዱስ ወደ ምድር ወረዱ ወደ ደቂቀ ቃየልም ተጨመሩ። ቃይናን ከነፍሰ ገዳዩ ከቃየል ልጆች ጋር ልጆቹ እንዳይጨመሩ ልጆቹን አዘዛቸው ታላቁ ልጁን መላልኤልንም እርሱን ተክቶ የሕዝቦቹ መሪ እንዲሆን አዘዘው። መላልኤልም ሕዝቦቹን በጽድቅ መራቸው። ሄኖክ ምስጢረ ከዋክብትን የማወቅ ዕውቀት ነበረው። ያፌት ሲወለድ ዓለም 2157 ዓመት ሆኖት ነበር። ማየ አይኅ በ2257 ጀመረ።የከነአን አባት ካም ነው። ቃይናን ከአዳም 13ኛ ትውልድ ነው። በ130 ዓመቱ ቃይናን ሰላትያልን ወለደ። ሰላትያል ዳግማዊ ቃይናንም ይባላል። አይሁድ ከልደተ አበው 1500 ዓመት ደምስሰዋል። ዳግማዊ ቃይናን የተባለውን ሰላትያልንም ከቁጥር ሰርዘዋል። ይህን ያደረጉት በፍጻሜ ዘመን ይመጣል ብሎ ነቢዩ ዳንኤል የተናገረለት ክርስቶስ እሱ አይደለም ብለው ሊገድሉት በተማከሩ ጊዜ ነው። ይህንንም ምክንያት በማድረግ የዳንኤል ሱባኤ አልተፈጸመም እያሉ ይተርካሉ። የቃይናን አባት አርፋክስድ ነው። ኤቦርና ልጆቹ የእብራውያን ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ። ከለዳውያን 5533 ክንድ ርዝመት ያለው ግንብ ገነቡ ይህን ለመስራት ፴ ዓመት ፈጀባቸው። ይህ የሆነው ዓለም ከተፈጠረ በ2827 ዓመት ነው። ግንቡን ለመስራት

የተሠለፉት 72 መሳፍንትና 25 የሴም ዘሮች ናቸው። ግሪክ የያፌት ዘሮች ሀገር ነው። ምድር እንደ ጽዋ/ጋን ክብ መሆኗን ልንገልጽ ይገባናል። በዚች ምድር አራት በገቡተኝነታቸው የሚታወቁ ክፍሎች አሉ። ከዚህም የተነሳ ፀሐይ ወደ አራቱ ገቡተኛ ብሔሮች ስትደርስ ስለሚጨልም ሌሊት ይከሠታል። በአንዳንድ ሀገሮች የፀሐይ ብርሃን እስከ 17 ሰዓት የሚቆይበት ጊዜ አለ። በሰንድና በሕንድ የሚገኙ ዕፅዋትና ድንጋዮች በአራዊት ለተነደፉ ሰዎች መድኃኒት ናቸው። ንጹሕ ነፋስ ለአእምሮ ጥሩ ነው። በብርዳማው አገር የእባብ ዘር ፈጽሞ የለም ብርዱ ያጠፋዋልና። (ፍጥረታትን የሚለውጥ እግዚአብሔር ነው። ለምሳሌ ብርድ ስለሆነ ፊትህ ጠወለገ ቢባል በብርድ ፊት እንዲጠወልግ ያደረገ ፈጣሪ ነው። በፍጥረታት መካከል ስላለው ውስጣዊና ውጫዊ ግንኙነት ውጤቱ እንዲህ እንዲሆን ያደረገው እርሱ ነው። የሳይንስ ሰዎች ለተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያትና ውጤት የሰጡት ይህን አይተው እንጂ ለግኙኝነቱ ስያሜና የግል አስተያየታቸውን ሰጡ እንጂ ምክንያቱን እነርሱ አልፈጠሩትም)። ፀሐይ ሳትጠልቅ 22 ሰዓት ሙሉ የምትቆይበት ሀገር አለ። ሌሊቱም 22 ሰዓት የሆነ ማለት ነው። የሕንድ ባሕር ከሕንድ ተነስቶ እስከ ኢትዮጵያ ይደርሳል። ጠቢቡ አርስጣጣሊስ እስክንድር በሚገዛው ሀገር መስታዎትን ሰርቶ ነበር ገንዘብ የጠፋበት ሰው በመስታዎት አማካኝነት ያገኝ ነበር። በሀገረ ኤፌሶን አንድ ከብረት የተሰራ ምስል ነበረ። ምስሉ በክብር በወንበር ተቀምጧል። በሀገሪቱ ላይ ክፉ የሚያስቡ ሁሉ በምስሉ አማካኝነት ከነመርከባቸው ይሠጥማሉ ተብሎ ይታሰብ ነበር። በኋላ ክርስቲያኖች አቃጠሉት። ጸሐፊዎች በዓለም የተፈጸሙትን ሁሉ ለመጻፍ ቢፈልጉ አይችሉም በዚህ ዓለም ብዙ ታሪክና ሊታመን የማይችል ነገር ተፈጽሟል። እስከ ዘመነ ኤቦር የሰው ልጆች መነጋገሪያ እብራይስጢ ነበረ። ከኤቦር ልጆች አንዱ ዮቅጣን ነው። ዮቅጣን የዓረቦች አባት በመሆኑ ይታወቃል። በኤቦር ዘመን ዓለም ከተፈጠረ 3117 ዓመት ነበረ። ናምሩድ በምስራቅ አቅጣጫ እሳትን ስላየ ለእሳት እየሰገደ ብዙ ቆየ። በራግው ዘመን ሰዎች ብዙ አማልክትን አመለኩ። የአባት የእናታቸውን ምስል እያሰሩም የሚሰግዱ ነበሩ። መልከ ጼዴቅ የኬቦር ልጅ የፋሌቅ ልጅ ነው። ናምሩድ የከለዳውያን አባት በመባል ይታወቃል። የፊርዖኖች መንግሥት የተመሰረተው በዘመነ ራግው ነው። ከራግው ዘመን በ200ኛው ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ከክምዮስ የሚባል ንጉሥ ነገሠና ከወርቅና ከብር ጌጣጌጥን መስራትና ከእነዚህ መአድኖች በተሠራ ድርሕም በሚባለው ገንዘብ መገበያየት የተጀመረው በእርሱ ዘመን ነው። በናኮር ዘመን ደግሞ ሚዛኖችና መለኪያዎች ተፈለሰፉ። ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥም በዘመኑ ታይቷል። መርቅልዮስ ዮናስ ዮናናዊ የከዋክብትን ጥናት ጀመረ ዮናናውያን ይህን ጥናት በፍልስፍናቸው አስገብተው ተጠቀሙበት። ናኮር በግብጽ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ደማስቆ ተቆረቆረች። አብርሃም በ3300 ዓመተ ዓለም ተወለደ። የአብርሃም እናት ዮታ ከሞተች በኋላ ታራ ንሕራብን አግብቶ ሣራን ወለደ። አብርሃም ለአህዛብ አማልክት አልተገዛም ጌታም ውጣ ብሎት በ75 ዓመቱ ወጣ። አብርሃምም ለእግዚአብሔር ሰዋ። አጋር ጸነሰች ሣራንም ማክበር ተወች። እስማኤል ከአረብ ነገሥታት የምትሆን ሚስትን አገባ በዓረብኛም ተናገረ ልጆቹም እስማኤላውያን ተባሉ። ይሥሐቅ ለመሥዋእትነት በቀረበ ጊዜ ዕድሜው 37 ዓመት ነበረ። ሣራ የአብርሃም ይሥሐቅን ለማረድ ሂዶ እንደነበር ሰምታ ታመመች በ127 ዓመቷም ሞተች። ሣራ ከሞተች በኋላ አብርሃም ኬጡራን አግብቶ ብዙ ልጅ ወልዷል። አብርሃም በ3503 ዓመተ ዓለም ሞተ። እስማኤልና ይሥሐቅ ቀበሩት የቀበሩትም አሁን ገሊላ በሚባለው ቦታ ነው።በዘመነ

አብርሃም ሄራቤት የምትባል ንግሥት ነገሠች እሷ የተራራው ካህን ልጅ ስትሆን በንጽቢንና በሮሐ ከተሞችን ቆረቆረች ጣዖታትንም አቆመች የእርሷ ጣዖት ለ50 ዓመት ተመለከ ቆይተው ግን ጣዖቶቿ ተቃጠሉ። ርብቃ ድንግል ነበረች። ይሥሐቅን ስታገባው የ40 ዓመት እድሜ ነበራት። የአብርሃም አገልጋይም ለይሥሐቅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ለርብቃ የወርቅ ቀለበት አገባላት። ኤሳው ብኩርናውን በምስር ንፍሮ ለያዕቆብ ሸጠ። ያዕቆብ ራሔልን ወደዳት መልከ መልካም ነበረችና። ሮቤል የአባቱ ዕቅብት ከነበረችው ከላባ ደረሰባት ያዕቆብም በዚህ ምክንያት የሮቤልን ብኩርና ለሌዊ ሰጠ። ዮሴፍ በፈርዖን ፊት ሲቀርብ 30 ዓመቱ ነበረ። ዮሴፍ የጲጥፋራን ልጅ አትኔስን አገባ። የዮሴፍ ወንድሞች ለዮሴፍ ያዕቆብ በዮሴፍ መሞት ምክንያት ዓይኑ እንደታወረ ነገሩት። (የውሸትን ውጤት አስተውል)። ፈርዖን ለያዕቆብ መኖሪያ ትሆነው ዘንድ ምድረ ራምሴን ሰጠው። ዮሴፍ ለውሃ ማጣሪያ የሚሆን ጥልቅ ጉድጓድ አዘጋጅቶ ነበር። በዮሴፍ ዘመን ጻድቁ ኢዮብ ተነሳ። እንበረም መጀመሪያ ማርያምን ቀጥሎ ከዚያ ሙሴን ወለደ። እስራኤላውያን እስከ ኢያሱ ዘመን መና ይወርድላቸው ነበር። ከኢያሪኮ ቅጽር መፍረስ በኋላ ቀርቷል። ፋሲካንም ከ40 ዓመት በኋላ እንደገና ባልቦላ ቂጣ አከበሩ። በኢያሱ መሪነት ሕዝበ እስራኤል 31 ነገሥታትን አሸነፈ። ኢያሱ ሲሞት ዓለም ከተፈጠረ 4904 ዓመት ሆኖት ነበረ። የፈርዖን ልጅ ብዙ ዕውቀት ያላቸውን መምህራን እየቀጠረች ስላስተማረችው ብዙ እውቀት አወቀ። ከማንም በበለጠ በእናትነት ደረጃ ትወደው ነበር። በግብጻውያን የታሪክ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ሰዎች ከግብጻውያን ጋር ስለተጣሉ የአባይን ውሃ ወደ ሌላ አቅጣጫ በማፍሰስ ግብጽን አመዘበሩ። ሙሴ በፈርዖን ታዞ ወታደሮችን ይዞ በግብጽና በኢትዮጵያ ምድር መካከል መርዛማ እባቦች ስለነበሩ እባቦቹን የሚበሉ አሞራዎች ይዞ ተነሳ ሙሴም ኢትዮጵያን ድል አድርጎ የኢትዮጵያን ንጉሥ ሴት ልጅ አግብቶ መጣ። የዓባይን ወንዝም ወደ ግብጽ እንዲፈስ አደረገው። ዓለም ከተፈጠረ እስራኤል ከግብጽ እስከ ወጡበት 3835 ዓመት ይሆናል። የእግዚአብሔር መልአክ ቀን በደመና ሌሊት በብርሃነ እሳት እየመራቸው ተጓዙ። እግዚአብሔር ለሙሴ ሁለት ጽላቶችን ሰጠው። ማርያም ሙሴን ስላማችው ለምጻም ሆነች እርሱ ግን ጸልዮ አዳናት። ካሌብና ኢያሱ ምድረ ርስትን ወረሱ። ሙሴ በ3873 ዓ.ዓ ሞተ። በአዳም 33ኛ ትውልድ በናያድ ጊዜ ሀገረ ቆሮንቶስ ተቆረቆረች። እንዲሁም በዘመኑ አርዮስፋጎስ በመባል የሚታወቁ የመሳፍንትና የፈላስፋዎች ማህበር በአቴና ተቋቋመ። ከዋክብት ፍጡራን ስለሆኑ ክፉም ሆነ ደግ ከእነርሱ አይገኝም የሚል ፈላስፋ ነበረ። ዲቦራ ነቢይት ከነገደ ኤፍሬም ናት። ጌዴዎን በምስፍናው ወራት ብዙ ሴት አገባ 70 ልጅም ወለደ። ከአዳም 44ኛ የሆነው ዮፍታሔ ለእስራኤል መስፍን ሆነ። እስከ ዘመነ ዮፍታሔ ድረስ የሰው ሬሳ በዋሻ ይቀመጥ ነበረ በዚህ ጊዜ ግን መሬት እየተቆፈረ መቀበር ተጀምሯል። (የሰው ልጅ የሚሰራው ስራ ሁሉ መነሻ አለው። አንዳንዱ በቅርብ ሌላው ከጥንት)። ሶምሶን በ4300 ዓመት አረፈ። ዙርነሐር በነገሠ በ2 ዓመት የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተ መብረቅና ነጎድጓድ ምድሩን አደባለቁት እሳተ ገሞራም ምድሩን አነደደው አንዱ ከተማ ከነሰው ከነእንስሳቱ ተደምስሰዋል። የኤሊ ልጆች ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሴቶች አዋረዱ። ለመባዓ እና ለመሥዋእት የመጣውን ለራሳቸው አደረጉ። በኤሊ ዘመን እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ራዕይን አስወግዶ ነበር። ሳሙኤል በቤተ መቅደስ ታቦተ ሕጉ ባለችበት ይተኛ ነበር። ሳኦል የነገሠ በ4407 ዓ.ዓ ነው። ሳኦልን እርኩስ መንፈስ ሲያሰቃየው ዳዊት እየዘመረ ያስታግሥለት ነበር። ጎልያድ ስድስት ክንድ

ርዝመት ነበረው። ሳኦል የተመረጠ በእጣ ነው። መጀመሪያ በነገድ ሲጣጣሉ ለነገደ ብንያም ደረሰው ከዚያ ከነገደ ብንያም ደግሞ ሲጣጣሉ ለሳኦል ደረሰው። የእስራኤል ልጃገረዶች ሳኦል ሺ ገዳይ ዳዊት እልፍ ገዳይ ብለው ስለዘፈኑ ሳኦል ዳዊትን ይጠላው ነበረ። ሜልኮል ዳዊትን በአርበኝነቱ በጣም ትወደው ነበረ። ሳኦል ዳዊትን በቤቱ አስከብቦ ሊገድለው በተነሳ ጊዜ ሜልኮል በመስኮት አዘልላ ከመገደል አተረፈችው። ዳዊትና ጓደኞቹ ተራቡና ካህኑ አቤሜሌክ ጎብስተ ቁርባን ሰጥቷቸው በሉ። ሳኦል በ4447 ዓመት ሞተ። ንጉሡ ኢዮአስ ካህኑ ዮዳሔን ሳያማክር ምንም አያደርግም ነበር። ካህኑ ዮዳሔ ከሞተ በኋላ ግን ጣዖት አመለከ። ነቢዩ ዘካርያስንም በድንጋይ አስደብድቦ ገደለው። በ4792 ዓ.ዓ አዛርያስ ነገሠ። ይህ በነገሠ በአምስተኛ ዓመቱ ጳጉሜን በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ስድስት ቀን እንዲሆን ተወሰነ። አዛርያስ ሌላ ስሙ ያዝያን ነው። አጥናለሁ ብሎ ቤተመቅደስ ገብቶ ለምጽ የወጣበት ንጉሥ ነው። የፋርስ ንጉሥ በመጋቢት 25 ቀን ለፀሐይ በዓል ያደርግ እንደነበር ይነገራል። ሙሴ እስራኤሎች በእባብ በተነደፉ ጊዜ ያቆመውን ዓርዌ ብርት ሕዝቅያስ ሰበረው። የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው ሲያመልኩት አይቷልና። የፋርሱ ንጉሥ የእስራኤልን ልጆች በሙሉ ማርኮ ወደ ኤዶም ወሰዳቸው በእስራኤል ልጆች ምትክ አህዛብን አሰፈረ። እኒህ አህዛብ ግን እግዚአብሔር ያጠፋናል ብለው ፈሩ። እግዚአብሔርም የአንበሳ መንጋ ላከባቸውና ብዙ ተበሉ በመበላታቸው ተጨነቁ። የእስራኤል አምላክ ሕግ ስለማናውቅ በአንበሶች ተበልተን ማለቃችን ነው ብለው ለፋርስ ንጉሥ ነገሩት። እርሱም ማርኮ ከወሰዳቸው እብራውያን መካከል አንዱን መጽሐፈ ኦሪት እንዲያስተምራቸው ላከላቸውና ተማሩ። በአንበሳ መበላቱም ቀረላቸው። እነዚህም ህዝቦች የቀሩት መጻሕፍትን ሳያውቁ በመጽሐፈ ኦሪት ብቻ ተወስነው ቀሩ። እስከ መጨረሻውም ሌሎችን መጻሕፍት የማይቀበሉ ሆኑ። ከሙሴ በቀርም ሌላ ነቢይን አይቀበሉም። ለእስራኤላውያን በፋርስ ንጉሥ የተማረኩት ምርኮ የመጀመሪያቸው ነው። እስራኤል የተማረኩት በሕዝቅያስ ዘመን ነው። በ4805 ዓ.ዓ ሕዝቅያስ ሞተ። በዘመነ ኢዮስያስ ነቢዩ ሶፎንያስ፣ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ነቢይት ኅልዳና ተነስተዋል። ኤርምያስ በራዕይ ቤተ መቅደስ እንደምትቃጠልና ህዝቦቿም ወደ ባቢሎን እንደሚማረኩ ስላወቀ የምስክር ድንኳንንና የእግዚአብሔርን ታቦት በዋሻ ውስጥ ደበቃቸው። እስከዛሬም ድረስ የተደበቁበትን ዋሻ ያወቀ የለም። ከግብጹ አንካሳው ፈርዖን ወይም ፈርዖን ኒካዑ ጋር ገጠመ። በዚሁ ጦርነት ተወግቶ ኢዮስያስ ሞተ። በ4893 ዓ.ም ይህ ሆነ። በሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ዘመን ነቢዩ ሆሴእ ኢሳይያስና ሚክያስ ነበሩ። በዘመነ አካዝም እኒሁ ነበሩ። ሮማኖስና ርናልዮስ የተባሉ ወንድማማች በሮም ላይ የነገሡት ከሕዝቅያስ በፊት በነበረው በአካዝ ዘመነ መንግሥት ነው። በ4760 ዓ.ዓ አካባቢ ማለት ነው። በአሜስያስ ወልደ ኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ኤልሳእ፣ ዮናስና ናሆም የተባሉ ነቢያት ነበሩ። በአዛርያስ/ዖዝያን ዘመን ደግሞ ዮናስ፣ አሞጽ፣ ሆሴእና ኢሳይያስ ነበሩ። በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት በ4763 ዓ.ዓ አካባቢ ኤልሳእ አብድዩ እና ዘካርያስ ነቢይ ነበሩ። ኤልያቄም ንጉሥ ለ3 ዓመት እንደተቀመጠ ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን በመውረር ሰዎቹንና ንብረታቸውን የቤተ መቅደስ ንዋያትንም ጭምር ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ። ሠለስቱ ደቂቅና ዳንኤልም አብረው ተማረኩ። ይህም በ4907 ዓ.ዓ ገደማ ነው። ሴዴቅያስ በነገሠ በዘጠኝ ዓመት በኢየሩሳሌም የቀሩትን ወደ ባቢሎን ወሰዷቸው። በሴዴቅያስ ዘመን ዕንባቆም ኤርምያስና ባሮክ የተባሉ ነቢያት ተነስተዋል። የናቡከደነጾር የጦር መሪ ናቡዛርዳን ይባል ነበር። የግብጽ

ሰዎች ኤርምያስን በድንጋይ ወግረው ገደሉት በግብጽም ተቀበረ። የትንቢት ዓመታቱም 38 ዓመት ናቸው። ነቢዩ ሕዝቅኤልን ደግሞ ተማርኮ በሚኖርበት አይሁድ ገደሉት። ናቡከደነጾር የሶርያ የግብጽ የሮም የባቢሎንና የፋርስ የበላይ ንጉሥ ሆነ። ናቡከደነጾር የእግዚአብሔር መንግሥቱ ዘለዓለም ነው እስኪል ሳር በል አውሬ ሆነ። በ4941 ዓ.ዓ ሞተ። በዳርዮስ ዘመነ መንግሥት የ70 ዓመቱ ስደት መጨረሻ ሆነ። ከብልጣሶር በኋላ ዳርዮስ ነገሠ። በዚህ ጊዜ ዕዝራና ዘሩባቤል ተነስተዋል። ቤተ መቅደስ መታደስ የጀመረው ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በ3 ዓመት ነው። በነዚህ ዓመታት ሐጌና የዩራክብ ልጅ ዘካርያስ ትንቢት ተናግረዋል። ዳርዮስ ተገደለ ቂሮስ ነገሠ። ነቢዩ ዳንኤል የእስራኤል ምርኮ ሳያልቅ ነው የሞተ። የአርጤክስስ መነሳት ከነዳርዮስ በኋላ ነው። መርዶኪዮስ ሊሰቀልበት የነበረው መስቀል 120 ክንድ ነበረ። አርጤክስስ አስቴርን ያገባት በ5060 ዓ.ዓ ነበረ። ነሕምያ ከዚህ በኋላ ነው የተነሳው ስሙን ዕዝራም ይለዋል። ሱቱኤልም ይለዋል ነቢይ ነው። በ5157 አካባቢ ሶቅራጥስ የነበረበት አካባቢ ነው። እስክንድር አርስጣጣሊስን ያማክረው ነበር። እስክንድር ቋፍ ወደተባለች ቦታ ወጥቶ ግንብ ሰራና ጎግ ማጎግን በዚሁ ውስጥ አሰራቸው። በብረት ሰንሰለት በማሰርም የኋሊት ዘጋባቸው። ግብጽ ውስጥም ከተማ ቆረቆረና እስክንድርያ ብሎ ሰየማት። እስክንድር በ5247 ዓ.ዓ አረፈ። በታሪክ ዙሪያ ሰዎች ሊለያዩ ይችላሉ እውነተኛውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በጥሊሞስ የእስክንድር ወንድም ነው። ወዳጅ እንጂ ወንድሙ አይደለም የሚሉም አሉ። ከዚያ ሌላ በጥሊሞስ ተነሳ። 72 የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትን ወደ እስክንድርያ አስመጥቶ 2ቱ በመንገድ ሞተዋል። 70 ብሉያቱን ከእብራይስጥ ወደ ዮናናውያን ቋንቋ ተረጎሙት። ይህም የሆነው በ5265 ዓ.ዓ ነው። ሲተረጉም አንዱን ለሁለት ሰጥቶ አስተያይቶ ነው ልክ መሆኑን ያረጋገጠው። ከአዳም እስከ ኖኅ 1757 ዓመት፣ ከኖኅ እስከ ሕንጻ ሰናዖር 501 ዓመት፣ ከአብርሃም እስከ ሙሴ 425 ዓመት፣ ከዳዊት እስከ እስክንድር 732 ዓመት፣ ከእስክንድር እስከ ክርስቶስ 319 ዓመት ነው። ጌታ ሁለት ዓመት ሲሆነው ወደ ግብጽ ተሰደደ። በግብጽ 4 ዓመት ተቀመጠ። አውግሥጦስ ቄሳር በ5515 ዓ.ዓ ሞተ። ሄሮድስ ሕጻናትን ከፈጀ በኋላ ጤና አላገኘም በተለያዩ በሽታዎች ተሰቃየ አበደ ሚስቱን ከተኛችበት ገደላት ቀጥሎ ትልቁን ልጁን ገደለው ቤተሰቦቹን በሙሉ ገደላቸው። በቢላዋ ራሱን ሊያጠፋ ሲልም ሰዎች ያዙት በ5513 ዓ.ዓ ሞተና ሌላ ሄሮድስ ነገሠ። ጌታ ሲጠመቅ ጢባርዮስ ቄሳር ከነገሠ 15 ዓመት ሆኖት ነበር። በዘመኑ ጲላጦስ ጢባርዮስ ቄሳርን ወክሎ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ይገዛ ነበር። ጌታ በ5534 ዓ.ዓ ተሰቀለ። ጢባርዮስ ቄሳር በ5538 ዓ.ዓ ሞተ። በምትኩ ጋብዮስ ቄሳር ለ4 ዓመት ነገሠ። በሐዋርያትና በምእመናን ላይም እጅግ ከፋ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ የሞተ በዚህ ጊዜ ነው። ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስም በሰይፍ የተገደለ በዚህ ወቅት ነው። በጋብዮስ ቄሳር ዘመነ መንግሥት ጴጥሮስ በሮማይስጥ/ላቲን ወንጌልን ጻፈ በሚወደው ደቀመዝሙሩ በማርቆስ ስምም ሰየመው። ከዚያ ቀላውዴዎስ ቄሳር ነገሠ 14 ዓመትም ገዛ። በዚህ ጊዜም ማቴዎስ ወንጌሉን በእብራይስጥ ጻፈው። ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ቆይቶ ይህንን የማቴዎስ ወንጌል ወደ ሮማይስጥ ተረጎመው። ከዚያ ኔሮን ቄሳር ለ13 ዓመት ነገሠ። ማርቆስ የተገደለ በዚህ ጊዜ ነው። ሊቀ ጳጳሳትን ለመሾም የጳጳሳት መሰብሰብ የተጀመረው ከ318ቱ ሊቃውንት ወዲህ ነው። ከዚያ በፊት አንዱ ራሱ ይሾም ነበር። ዕፀ መስቀልን አይሁድ የቀበሩት በኔሮን ዘመነ መንግሥት ነው። በያዕቆብ ምትክ ስምዖን ወልደ ቀለዮጳ ተሾመ። በኔሮን ዘመን ሠረጠሪኖስ


መስከረም 14 ወበመዋዕሊሁ ለአባ አጋቶን አስተርአየ ብእሲ ዘውስቴቱ ሰይጣን ወአስሐቶሙ ለህዝብ። ወከማሁ ኮነት ብእሲት ዘትቤ ሚናስ ሰማእት ይትናገረኒ ወአዘዘቶሙ ለሰብአ ሀገረ ዚኣሃ ይክርዩ አዘቅተ ማይ በስሙ ለቅዱስ ሚናስ ሰማዕት ከመ ይትፈወሱ እም ደዌሆሙ። ወለይእቲኒ አብጽሓ ኀቤሃ ወጸለየ ላዕሌሃ ወአውጽኦ ለመንፈስ ርኩስ እምኔሃ። ወአዘዞሙ ለሰብአ ይእቲ ሀገር ይድፍንዋ ለይእቲ ዐዘቅት። **መስከረም 21** ወዝንቱ ቅዱስ ቆጽርያኖስ ኮነ ቀዳሚ መሠርየ ወከሐዴ። ወውእቱ ሊቆሙ ለኩሎሙ መሠርያን። ወሖረ ኀቤሁ አሐዱ ወሬዛ ወነገሮ ዘከመ ፈተዋ ለዮስቴና ድንግል። ወኢተክህሎ ረኪቦታ ወይቤሎ ቆጽርያኖስ ኢትኅዝን አነ እፈጽም ለከ ፍትወተ ልብከ። ወእምዝ ሶቤሃ ፈነወ ኃይለ አጋንንት ላዕሌሃ በሥራዩ ከመ ያምጽእዋ ኀቤሁ። ወእሙንቱ አጋንንት ሶበ ይበጽሑ ኀቤሃ ኢክህሉ ነሢኦተ ኪያሃ እስመ ይውዕዩ እምነ ጸሎታ። ወብዙኀ ጊዜያተ ከመዝ ፈነዎሙ ኢክህሉ ያምጽእዋ ኀቤሁ ወእምዝ ጸውዖሙ ቆጽርያኖስ ለኩሎሙ አጋንንት ወይቤሎሙ ለእመ ኢያምጻእክምዋ ሊተ ለዮስቴና ድንግል አነ እትፈለጥ እምኔክሙ ወእከውን ክርስቲያናዌ። ወእምዝ ሐለየ ሊቀ ሰይጣን ከመ ይኒጦ። ውእቱኬ ረሰየ አሐደ እም ሰይጣናት ከመ ይትመሰል በአምሳሊሃ ወያስተርኡ ለቆጽርያኖስ በአርዓያሃ ለዮስቴና ወገብረ ከመዝ። ወተፈሥሐ ቆጽርያኖስ ወተንስአ ይትቀበላ ወይቤ ሠናይ ምጽአትኪ ኦ ዮስቴና። ወሶበ ዘከረ ዘንተ ስማ ወጽአ ከመ ጢስ ዝንቱ ሰይጣን ዘተመሰለ በአምሳሊሀ ወተዘርወ። ወአውዐየ ቆጽርያኖስ ኩሎ መጻሕፍቲሁ ዘሥራይ በጊዜሃ

ወተጠምቀ ጥምቀተ ክርስትና ወመንኮሰ ወኮነ ኤጲስ ቆጶስ ዘቅርጣግና። ወሶበ ኮነ ማኅበረ ጉባኤ ቅዱሳን በሀገረ ቅርጣግና ኮነ ዝንቱ ቅዱስ አሐደ እም እለ ተጋብኡ በህየ።

መስቀል

መስከረም 16 ትቤሎ እመ ዕሌኒ ቅድስት ኦ ወልድየ ኮንኩ ዘበጻዕኩ አንሰ ለእግዚአብሔር ከመ እሑር ሀገረ ኢየሩሳሌም ቅድስት እኅሥሥ ወእክሥት እፀ መስቀሉ ለክርስቶስ ንጉሠ ስብሀት። ወሰሚያ ቆስጠንጢኖስ ተፈሥሐ በዝንቱ ነገር ወፈነዋ ምስለ ሠራዊት ብዙኃን። ወይእቲ ሶበ በጽሐት ሀገረ ኢየሩሳሌም ተባረከት እምነ መካናት ቅዱሳት። ወእምዝ ሐተተት በእንተ እፀ መስቀል። ወበዓቢይ ጻማ ወምንዳቤ ረከበቶ ወአክበረቶ ክብረ ዐቢየ ወሰብሐቶ በዐቢይ ስብሀት። ወእምዝ አዘዘት ከመ ይሕንፁ ምሥዋዐ ቤተ መቅደስ በጎልጎታ ወበቤተልሔም ዘውስተ በዓት ዘተወልደ ውስቴታ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወበጽርሐ ጽዮን ወበጌቴሴማኒ ዘተቀብረ ሥጋሃ ለእግዝእትነ ማርያም ወበደብረ ዘይት ወበኩሎን መካናት ቅዱሳት። ወአዘዘት ካዕበ ያሠርግውዎሙ በዕንቆ ባሕርይ በወርቅ ወበብሩር። **መስከረም** 17 በዛቲ ዕለት በዓሉ ለመስቀል ክቡር ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዝንቱኬ ዘከሠተቶ እሌኒ ንግሥት እመ ለቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ጻድቅ። ወሶበ ኮስተረት ወግረ ኅልጎታ ረከበቶ ለመስቀል ክቡር። ወምክንያተ ከዊኖቱ ወግረ ዐቢየ እስመ ተአምራት ወመንክራት ብዙኃት ኮና ያስተርእያ እምነ መቃብሩ ወእመስቀሉ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። እስመ ሙታን ይትነሥኡ ወመጻጉዓን ወድውያን ይትፌወሱ። ወበእንተዝ ተምዑ አይሁድ ወሠርዑ ውስተ ኩሉ ብሔረ ይሁዳ ወኢየሩሳሌም ከመ ኩሉ ዘይኮሰትር ቤቶ አው መሬተ አው እዳወ ይውግር ላዕለ መቃብሪሁ ለናዝራዊ ኢየሱስ ወነበሩ እንዘ ይገብሩ ከመዝ መጠነ ሠለስቱ ምእት ዓመት። ወሶበ መጽአት እሌኒ አኀዘቶሙ ለአይሁድ ወአመንደበቶሙ እስከ አጠየቅዋ መካነ መቃብሪሁ ለእግዚእነ። ወአገበረቶሙ ካእበ እስከ ኮስተሩ ውእተ ወግረ ወተከስተ መስቀል ክቡር። **መስከረም** 25 ሰላም ለዕፀ መስቀል ደመ መለኮት ዘተነገዘነ። በዛቲ ዕለት ብሔረ አግዓዚ ዘበጽሐ። **ጥቅምት** 5 ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ በከዊነ ስምዕ ምስለ ሐና እመ ቅዱስ ኪራኮስ ጳጳስ። ሰላም ለኪራኮስ መካነ መስቀል ዘአመረ። ለንግሥት እሌኒ ከመ እም አቡሁ ተምህረ። **ህዳር** 8 መስቀል በአምሳለ ከዋክብት ለቆስጠንጢኖስ የተገለጸበት ቀን ነው። **መጋቢት** 10 በዛቲ ዕለት ኮነ አስተርእዮቱ ወተረክቦቱ ለመስቀል ክቡር ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወነስአት ዕሌኒ ብእሴ አረጋዌ አይሁዳዌ ወአመንደበቶ በረኃብ ወጽምዕ ወሶበተመንደበ ነገራ ለእሌኒ። ወነበሩ አይሁድ እንዘ ይዌግሩ ጉድፎሙ መጠነ ክልኤቱ ምእት ዓመት ወዘይፈደፍድ እስከ በጽሐት እሌኒ ንግሥት። **መጋቢት** 28 ወሶበ ቀደመ ትእምርተ መስቀል ዘሠራዊተ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ይትመውኡ ሠራዊቱ ለመክስምያኖስ ዕልው።

ቃል ኪዳን፣ ቤተ ክርስቲያን

መስከረም 18 ወአስተርአዮ እግዚእነ ለኤዎስጣቴዎስ ወወሀቦ ኪዳነ ለዘይጼውዕ ስሞ ወይገብር ተዝካሮ ወለዘይጽሕፍ ገድሎ። ወሶበ አዕረፈ ገነዝዎ ጳጳሳት ወካህናት በዓቢይ ክብር ወቀበርዎ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ መርምህናም ሰማእት ወአስተርአያ እም ሥጋሁ ተአምራት ብዙኃት። **ጥቅምት** 14 ወአዲ ወሀብኩከ ኪዳነ ለዘጸውዐ ስመከ ወለዘገብረ ተዝካረከ ለዘአጽገበ

ርኁበ ወለዘአስተየ ጽሙዐ ወለዘአልበሰ ዕሩቀ ወይገብር ኩሎ ሠናየ በእንተ ስምከ ወለዘጸሐፈ ወአጽሐፈ መጽሐፈ ገድልከ አነ አዐስዮ እሴተ ሰናየ በመንግሥተ ሰማያት ወበዝኒ ዓለም አዐቅቦ ወኢያንጥዖ እምኩሉ ሰናያት ለእመ ኢኮነ ናፋቂ። **ጥር 12** ወይቤሎ እግዚእ ለቴዎድሮስ በናድሌዎስ ወአነ እሁበከ ኪዳነ ለዘይጼውዕ ስመከ ወይገብር ተዝካረከ ከመ አድኅኖ እምኩሉ ምንዳቤሁ በውስተ ኩሉ መካን ለዘሂ ወሀበ ምጽዋተ ለነዳያን ወለዘአብአ መባዓ ለቤተክርስቲን በእንቲአከ ወለዘጸሐፈ ወአጽሐፈ መጽሐፈ ገድልከ ወለዘሐነጸ መርጡለከ አነ እሰሪ ኃጢአቶሙ ለኩሎሙ ወአወርሶሙ መንግሥተ ሰማያት። **ጥር 15** ወይቤሎ ሕጻን ቂርቆስ ለእግዚእነ ኢይትቀበር ሥጋየ ዲበ ምድር። ወይቤሎ መድኃኒነ ኩሎ ዘሰአልከኒ እሁበከ።ወሥጋከኒ አነብር ዲበ ሠረገላ ኤልያስ። ወይቤ ወንበ ተጸውዓ ስምየ በዛቲ መካን ኢይምጻእ ሞተ ላሕም ወኢ ብድብድ በሰብእ ወኢአባረ እክል ወሕጸተ ማይ። **ጥር 21** እስመ ኩሉ ዘይስእል ኀቤከ በስምየ ተወከፍ ስእለቶ በሣህልከ ወለኩሉ ዘሀሎ ውስተ ምንዳቤ ወይስእል ኀቤከ በስምየ አድኅኖ እምኩሉ ምንዳቤሁ። እስመ አንተ ከሀሊ ላእለ ኩሉ ግብር። ወባርክ ላእለ ኩሉ መካን እለ ይገብሩ ውስቴታ ተዝካርየ ወተወከፍ ቁርባኖሙ ለኩሎሙ እለ ያቄርቡ በስምየ። ወአውስአ እግዚእነ ወይቤላ ናሁ እገብር ለኪ ኩሎ ዘሰአልክኒ። ተፈሥሒ እስመ ኩሉ ጸጋ ወክብር ወሞገስ ተውህበ ለኪ። **የካቲት 16** እለ ይገብሩ ተዝካርየ ወየሐንጹ አብያተ ክርስቲያን በስምየ አው ዘያለብስ ዕሩቀ ወዘያጸግብ ርኁበ ወዘያሰቲ ጽሙዐ ወዘይሐየውጽ ድውየ ወይናዝዝ ጎዙነ ወያስተፈሥሕ ትኩዘ አው ዘይጽሕፍ ውዳሴየ ወይሰሚ ውሉዶ በስምየ ወዘጎለየ ማኅሌተ በዕለተ በዓልየ ዕስዮ እግዚኦ ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሀለየ ወለኩሉ ዘይትአመን በአስተብቁዖትየ ረስዮ እግዚኦ ግዑዘ እምሲኦል። **ሰኔ 17** ወእምዝ አዘዞ እግዚእነ ለሚካኤል ያምጽእ ነፍሰ ውእቱ ኃጥዕ ወገሠጣ በእደዊሁ ቅዱሳት ወረሰያ ከመ ዘኢተፈጥረት። ወይቤ ዛቲ ነፍስ ኢትኩን ውስተ ኩነኔ ወኢውስተ ሕይወት አላ ትኩን መሬተ። ወአእኮቶ አባ ለትጹን ለመድኃኒነ። **ሰኔ 21** የእመቤታችን በዓል ነው። በተጨማሪም በዓለም ሁሉ የቤተክርስቲያን መታነጽ መታሰቢያ ነው። ወእም ይእቲ ዕለት ኮኑ አበዊነ ሐዋርያት ቅዱሳን ዘየሐንጹ ቤተ ክርስቲያን ውስተ ኩሉ ዓለም።

ሠርግ፣ ሥላቅ

መስከረም 18 ወበዊዖ ቤተ መርዓ ሐዋርያ ቶማስ ጸለየ በእንተ መርዓዊ ወመርዓት ወመዓደሙ ቃለ ሃይማኖት ወባረኮሙ። **ጥር 6** ወርእዮሙ እንዘ ይገብር ታቦተ በእንተ ድኅነት እማየ አይኅ ተሣለቅዎ ለኖኅ ደቂቀ ቃየል ወይቤልዎ ዝንቱ አረጋዊ አብደ እፎ ይብለነ የዐርጉ ማያት መልእልተ አድባር። ወእምዝ ነስአ ኖኅ ሥጋ አቡነ አዳም ወሄዎም ወልዱ ነስአ ወርቀ ወካም ከርቤ ወያፈሖት ስሂነ ወአብአ ውስተ ታቦት። ወኮነ ዝናም ላእለ ምድር ፵ዓ ዕለተ ወ፵ዓ ሌሊተ ወመልአ ማይ ወአልዓላ ለታቦት ወተለዓለት እምድር ወከደነ ኩሎ አድባረ ነዋኃተ ዘመትሕተ ሰማይ አሠርተ ወንምስተ እመተ ተለኣለ መልእልቶሙ ማይ። ወሞተ ኩሉ ዘሥጋ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር እምነ አዕዋፍ ወእም እንስሳ ወእምነ ኩሉ አራዊተ ምድር ወኩሉ እንለ እመሕያው።

ትንቢት

መስከረም 25 ኦ አኃው ይትከሀሎኑ ለፍጡር አምስጦ እም ገጸ እግዚአብሔር ፈጣሪ። ወለእመ ኮነ ዝንቱ ዮናስ ዘእምነቢያት ዘደቂቀ እስራኤል እም ኢያእመረኑ ዘንተ። ዳዕሙ ገብረ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ ከመ ይኩን ትእምርተ እምዮናስ በነቢሮቱ ውስተ ከርሰ አንበሪ ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ ለነቢሮቱ ለመድኃኒነ በከርሠ መቃብር ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ ወእምዝ ከመ ይትነሣእ እምነ ምውታን። ወበከመ ዮናስ ወጽአ እም ከርሰ አንበሪ ዘእንበለ መስና እስመ ተንሥአ መድኃኒነ ዘእንበለ ውላጤ።

ንሥሓ

መስከረም 25 ወተአመኑ ሰብአ ነነዌ በቃለ እግዚአብሔር ወሰበኩ ጾመ ወለብሱ ሠቀ ንዑሶሙ ወዐቢዮሙ። ወሰበከ ንጉሠ ነነዌ ለንዑሶሙ ወለዐቢዮሙ ለሰብእ ወለእንስሳ ይቤ ኢይብልዑ ወኢይስተዩ ምንተኒ ወእንስሳኒ ኢይትረዐዩ ሣዕረ ወኢይስተዩ ማየ። ወርእየ እግዚአብሔር ምግባሮሙ ከመ ነሥሑ እምፍኖቶሙ እኩይ። ወእግዚአብሔርኒ ነሥሐ እምዘነበበ እኩየ ከመ ይግበር ላእሌሆሙ ወኢገብረ እኩየ። **የካቲት** 5 ዝንቱ አባ እብሎይ ዘአቅነየ ርእሶ ቀዳሚ ለኃጢአት። ወዝንቱ ኖላዌ አባግዕ ወወሀበ ርእሶ ለሰይጣን ወኢተርፎ ምንትኒ እምኃጣውዕ እስመ ይዜሙ ወይሰርቅ ወየኀይድ ወይቀትል። ወነበረ በዝንቱ ግብር መጠነ ፴ ዓመት እንዘ ይፈጽም ምግባረ ሰይጣን። ወበአሐቲ ዕለት እንዘ ይነብር ውስተ ገዳም ምስለ አባግዒሁ በመንፈቀ መዓልት ወናሁ ርእየ ብእሲተ ጽንስተ ዘበጽሐ ጊዜ ወሊዶታ ወወደየ ሰይጣን ውስተ ልቡ ሕሊና ወይቤ ዘተርፈተኒ እምኃጢአት አሐቲ ወይእቲ ከመ እሥጥቅ ከርሠ ብእሲት ወእርአይ ኀበ ይሰክብ ሕጻን በውስተ ከርሰ እሙ። ወሶቤሃ ሠረረ ወአኀዘ በሥዕርተ ርእሳ ወነጽሓ ውስተ ምድር ወነስአ መጥባሕተ ወሠጠቀ ከርሳ ወርእዮ ለሕጻን ዘከመ ኮነ ሰኪቦቱ በውሰተ ማኅጸን። ወይእቲ ሞተት መቅድመ ተጽዒራ። ሕጻንሰ ብዙኀ ኀንደየ እንዘ ይጼዐር በብዙኀ ጻማ ወሞተ። ወርእዮ ኖላዌ አባግዕ ዘንተ ዘገብረ ዐባየ ኃጢአተ በከየ ብካየ መሪረ። ወጾመ ወይቤ ስረይ ሊተ ወየብሰ ሥጋሁ ወጸልመ እምቁረ ሌሊት ወእምሐሩረ ፀሐይ። ወእምዝ ሰምዐ ቃለ ዘይብሎ ሠረየ ለከ እግዚእ። መፍትው ይንግሩ ኩሎ ገድሎ ለአባ እብሎይ ኖላዌ አባግዕ ከመ ይኩን ተስፋ ለእለ ወድቁ በኃጢአት ከመ ኢይምትሩ ተስፋ እምሕረተ እግዚአብሔር። **ሐምሌ** 1 ወአንትሙኒ ተመየጡ ኀበ እግዚአብሔር ወኀድጉ ምግባረ ኃጢአት ወሕሊና እኩየ ወዕቀቡ ትሕትና ወየውሃተ ወፍቅረ ወንጽሕና ወትነሥኡ ጸጋ እምኀበ እግዚአብሔር። **ጳጉሜን** 6 እንከሰ ንንቃሕ እምሀኬትነ ወንትነሣእ እምድቀትነ ወይደልወነ ከመ ንብኪ ቅድሜሁ ወንግበር ኀቤሁ በእንተ ዘኀለፉ አበሳነ ወኃጣውኢነ ብዙኀ። ወንስአሎ ከመ ያጽንዐነ ውስተ ሃይማኖት ርትዕት ወይዕቀበነ እመሣግሪሁ ለሰይጣን ጸላኢነ። ወንስአሎ ዓዲ ከመ እግዚአብሔር ይትዐገሥ ላእሌነ ወይጸንሐነ እስከ ንትመየጥ እምአበሳነ ወእከየ ምግባሪነ ወኢያጥፍአነ ፍጡነ በእንተ እከየ ምግባሪነ በከመ አጥፍያሙ ለብዙኃን አሕዛብ እለ እምቅድሜነ።

ተርእዮ፣ ከንቱ ውዳሴ፣ ትእቢት፣ ፍትወት

መስከረም 27 ወእምዝ ሶበ ከሠቱ ግብሮ ዕደው እለ መጽኡ እምኀበ ነበረ ቀዲሙ ኀየ በኀቡዕ ወበጽሐ ኀበ አንቀጸ ሀገር ወወጽአ ገዳመ።ወበህየ ፈጺሞ ገድሎ አዕረፈ። **ህዳር** 16 ወእምድኅረ

ጉንዱይ መዋዕል መጽኡ ለአባ ዳንኤል ሕሊና ትምክህት ወይቤ በልቡ ቦኑ ዘከማየ እም እለ ይነብሩ ገዳመ ዘተዐገሠ ጾም ወቀዊመ ወርእዮ እግዚአብሔር መፍቀሬ ሰብእ ትምክህተ ልቡ ፈነወ ሎቱ መልአኮ ብርሃናዊ ወይቤሎ ኦ ዳንኤል ለምንት ትትሜካሕ ዘከመዝ ትምክህተ ዘእንበለ ትሕትና። **ጥር** 27 ወአሐተ ዕለተ ክልኤተ ጎለተ ነስአ አግሪጳዳ ወአሠሮ ጎቡረ ወአንዘረ ቦሙ። አሜሃ ቦአ ሰይጣን ውስተ አፍራስ ወከልሑ አፍራስ እንዘ ያንፈርዕፁ። ወወለቱሰ ለንጉሥ ዘሞተ ነጸረቶ በመስኮት ዘጽርሐ መንግሥቱ ወአደማ ፈድፋደ እንዘ የአነዝር አግሪጳዳ ወወደየ ሰይጣን ውስተ ልባ ፍትወተ ዝሙት ወጸውዐቶ ለአግሪጳዳ ጎቤሃ ወተወስበት ሎቱ ወሰመየቶ ዲዮቅልጢያኖስሀ ወአንገሠቶ። **መጋቢት** 20 ሀሎ አሐዱ ኤጲስ ቆጶስ እኩይ ዘኮነ ላእለ ሀገረ ጎሕ ወያፈቅር ውእቱ ክብረ ዝንቱ ዓለም ኃላፊ። **ሐምሌ** 25 ወርእዮሙ ለሰብእ እንዘ ያከብርዎ ወነየ እምህየ ወበጽሐ ጎበ ካልዕ ሀገር።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር

መስከረም 29 በዛቲ ዕለት ኮነ ተዝካረ በዓለ ልደቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሀት እማርያም እምቅድስት ድንግል እግዝእትነ። **ህዳር** 2 ኢይደሉ ይፍልጥዎ ለቃል እም ትስብእቱ እምድኅረ ተዋሕዶ ከመ ኢይሠዐር ረብሐ ተዋሕዶ። **ታኅሣሥ** 7 ወበዛቲ ዕለት ኮነ ተዝካረ ስብከቱ ለመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት በአፈ ነቢያት ዘከመ ይትወለድ እማርያም። **ታኅሣሥ** 23 ወነረዮ ሳሙኤል ለወልደ እሴይ ወርእየ ዘይልሕቅ እስመ ሰናይ አርዓያሁ ወጽኑዕ ሥጋሁ ወኢነረዮ እግዚአብሔር አላ ይቤሎ ኢትርኣይ ገጸ ወኢትነጽር ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ እስመ አኮ ዘከመ ይሬኢ ሰብእ ዘይሬኢ እግዚአብሔር። እስመ ሰብእ ገጸ ይሬኢ ወእግዚአብሔር ልበ ይሬኢ። **ታኅሣሥ** 14 ወበዛቲ ዕለት ከሠተ መድኃኒነ ብርሃነ ውስተ ዓለም። **ታኅሣሥ** 21 ወበዛቲ ዕለት ኮነ አስተርእዮተ መድኃኒነ በአምሳለ ኖላዊ። **ታኅሣሥ** 28 በዛቲ ዕለት ኮነ በዓለ ጌና ዘውእቱ በዓለ ልደት። ወኖሎት ሰገዱ ለሕጻን። ወተመይጡ እንዘ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ጎበ መካኖሙ። **ታኅሣሥ** 29 በዛቲ ዕለት ኮነ በዓለ ልደት ክቡር ዓቢይ ቅዱስ ወልዑል እምኩሎን በዓላት ዕለተ ልደቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምቅድስት ድንግል ማርያም። እስመ አበዊነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ተሰነዓው በምክሮሙ ከመ ይግበሩ በዓለ ልደት ቅድስት በክልኤቱ ዕለታት። እስመ ልደት በደኃሪት ሌሊት አመ፳ ወሰመንቱ ወበመዓልት ፳ ወተስዓቱ። ወሶበ ይከውን ጳጉሜን ስድስተ በይእቲ ዓመት ይከውን በዓለ ልደት አመ ፳ ወሰመንቱ በመዓልት። ወለእመ ኮነ ጳጉሜን ኀምስተ ይከውን በዓለ ልደት አመ ፳ ወተስዓቱ። **ታኅሣሥ** 29 እስመ እሉ ሰብአ ሰገል እምዘመዱ ለበለዓም። ወእሉ እለ የአቅቡ ከዋክብተ ወሀሎ ውስተ መጽሐፎሙ ወውስተ መጽሐፉ ለበለዓም ከመ ሀለዎ ይትወለድ ንጉሠ አይሁድ እስመ ውእቱ በለዓም ይቤ ኮከብ ይሠርቅ እም ያዕቆብ ወንጉሥ እም እስራኤል። ወእግዚአብሔር መሐሪ በኪነ ጥበቡ አለበዎሙ ወሰሐቦሙ በዘየአምኑ ቦቱ እስመ እሙንቱ ዐቃብያነ ከዋክብት ወከሠተ ሎሙ ዘንተ ኮከበ። ወሶበ ርእይዎ ተፈሥሑ እስመ አርዓያሁ ውሉጥ እምከዋክብት በብዙኅ መክፈልት። እስመ ውእቱ ተመሰለ በድንግል እንተ ተሐቅፍ ሕጻነ። ወውእቱ የሐውር በመዓልት ወይትነባእ በሌሊት። ወሶበ ይትራከቡ ምስለ ሰብእ ይትነባእ። ወሶበ ይቀውሙ ይትከሠት ሎሙ በካልዕ ገጽ። ወውእቶሙ ሶበ በጽሑ ኢየሩሳሌም ተንብአ እምኔሆሙ ውእቱ ኮከብ ወንዘኑ ፈድፋደ ወኢያእመሩ ዘይገብሩ ወእምዝ

ቦኡ ኢየሩሳሌም። ወተሰአሉ በእንተ ዘተወልደ ወኮለቄመ ለእመንቱ ሰብእ ሠለስቱ እልፍ ወነገሥታቲሆመ ሠለስቱ። ወለለአሐዱ ንጉሥ ቦ በበእልፍ ሠራዊት። ወሰሚያ ሄሮድስ ንጉሥ ደንገጸ ወተሀውከ ወኩላ ኢየሩሳሌም ምስሌሁ። ወሰሚያመ እምነበ ንጉሥ ሖሩ። ወናሁ ኮከብ ዘርእዩ እምሥራቅ ይመርሖሙ እስከ አብጽሖሙ ቤተልሔም። ወቆመ መልእልተ በዓት ነበሀሎ ሕጻን። ወርእዮሙ ኮከበ ተፈሥሑ ዐቢየ ፍሥሓ። ወበፈቃደ እግዚአብሔር መጽኡ ዮሴፍ ወእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወሕጻንሂ እግዚእ ኢየሱስ በይእቲ ዕለት። በእንተዝ ረከብዎሙ ሰብአ ሰገል። እስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዙቱ ስብሐት ኢተሐጽነ ዘእንበለ በናዝሬት። ወኮነ ለዙቱ መዋዕሊሁ እምዘተወልደ ክልኤቱ ዓመት። ወርቀ አብኡ በእንተ መንግሥቱ ወዕጣነ አብኡ ለዙቱ እስመ አምላክ ውእቱ ወለዙቱ ክህነትኒ ወከርቤ አብኡ ትእምርተ ሞቱ ማሕየዊ። ወነገሮሙ በሕልም ከመ ኢይግብኡ ኀበ ኄሮድስ ወእንተ ካልእ ፍኖት ገብኡ ወአተው ብሔሮመ። ወኮኑ ሰባክያነ ወዓዋድያነ በእንተ አስተርእዮቱ ለአምላክ በሥጋ። **ጥር 6** በዛቲ ዕለት ቦአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዙቱ ስብሐት ወፈጸመ ሕገ ዘውስተ ኦሪት በከመ ይቤ ሐዋርያ ጳውሎስ ልሳነ እፍረት እስመ እግዚእ ክርስቶስ ተወክፈ ግዝረተ በሥጋሁ ከመ ይፈጽም ኪዳነ አበው። ወአውስአ ሕጻን እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይቤሎ ኦ ጠቢብ ገዛሪ ትክልኑ ትግዝረኒ ዘእንበለ ይትከዓው ደምየ። ወይቤሎ ጠቢብ አንሰ ኢይክል። ወሶቤሃ አንስአ እግዚእነ ሕጻን አዕይንቲሁ ውስተ ሰማይ ወይቤ ኦ አባ ሀበኒ ዮም ግዝረተ። ወኮነ ግዝረቱ ለእግዚእነ ዘኢይትዐወቅ በከመ ምስጢረ ጸአቱ እምከርሠ ድንግል እንዘ ኢይማስን ድንግልናሃ። ወከመዝ ከሠተ ክሂሎቶ በዘፈቀደ እምኪነ ጥበቡ እንዘ ኢይትመተር ምንተኒ እምሥጋሁ በግዝረት። **ጥር 12** ወበዛቲ ዕለት ሠርዐ መምህራነ ቤተክርስቲያን ከመ ይትገበር በዛቲ ዕለት ተዝካረ ተአምር ዘገብረ እግዚእነ ወአምላክነ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ውስተ ቤተ ክብካብ። **የካቲት 8** በዛቲ ዕለት ኮነ በአቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ቤተ መቅደስ እምድኅረ ፴ መዋዕል እም ልደቱ ክቡር። ወኮነ ሶበ ነግሠ በጥሊሞስ ዘይሰመይ መዋዔ በዓመት ፶፻፹፯ እምፍጥረተ አቡነ አዳም ወኮኑ ሕዝበ አይሁድ ታሕተ ሥልጣኑ ወፈነወ ኀበ ሀገረ ኢየሩሳሌም ወኀረየ ዕደወ ፵ እማእምራኒሆመ ወአብጽሖመ ኀቤሁ ወአዘዞመ ከመ ይተርጕሙ መጻሕፍተ ሕግ እምልሳነ ዕብራይስጢ ኀበ ልሳነ ጽርዕ እስመ ኮነ ዝንቱ በፈቃደ እግዚአብሔር። እስመ ሀለዎ ይፍልስ እም አይሁድ ወይኩን ለሕዝበ ክርስቲያን ዘውስተ ኩሉ ዓለም። ወበጽሐ መጽሐፈ ኢሳይያስ ለስምዖን። ወበዛቲ ዕለት አዕረፈት ሐና ነቢይት ወለተ ሩፋኤል እምነገደ አሴር። **መጋቢት 27** ወመጠወ እግዚእ ኢየሱስ ነፍሶ ለባዊተ ወነባቢተ ዘነስኣ እምእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም። **መጋቢት 29** ወዛቲ ዕለት በኩረ ኩሎን በዓላት እስመ ባቲ ኮነ ጥንተ መድኃኒተ ዓለም። **ሰኔ 29** በዛቲ ዕለት ተዝካረ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዙቱ ስብሐት እም እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም። **ነሐሴ 13** ወኮነት ደብረ ታቦር አምሳለ ቤተክርስቲያን እስመ አስተጋብአት ውስቴታ እምነ ብሊት ወሐዲስ።

ቅዱሳት ሥዕላት

ጥቅምት 9 ወረከቡ በቤተ ሞቅሕ ሥዕሎ ለቅዱስ መርቆሬዎስ ወጸለዩ በቅድሜሁ እንዘ ይበክዩ ወይብሉ ኦ ሰማእቱ ለክርስቶስ ኢትሰምዖኑ ለዝንቱ አላዊ ተሣልቆቶ ላእለ እግዚእነ ኢየሱስ ንጉሠ ስብሀት። ወሖረ ሥዕል ኀበ ሀሎ ዑልያኖስ ወረገዞ በረምኅ ወቀተሎ ወተመይጠ ውስተ

መካኑ ወያንጸፈጽፍ ደም እምልሳነ ረምሑ ወሶበ ርእዩ ዘንተ ግብረ መንክረ እሉ ቅዱሳን ይቤሉ ኦ ሰማእቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቀተልኮኑ ለዐልያኖስ። ውእተ ጊዜ ደነነ ሥዕል ከመ እወ ዘይብል ወተፈሥሑ እሉ ቅዱሳን ሊዋርዮስ ወባስልዮስ። **ጥቅምት** 14 ወእምዝ ተንሥአ በሌሊት ብጹዕ ገብረ ክርስቶስ ወቆመ ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ወጸለየ። ወይቤላ ኦ እግዝእትየ። ወዘንተ ብሂሎ ተሳለመ ሥዕላ ለእግዝእትነ። **ታኅሣሥ** 29 ወነሥአ እግዚእነ ልብሰ ፀዐዳ ወመዝመዘ ቦቱ ገጾ ወገብአ መልክኡ ውስተ ልብስ ወፈነዎ ሎቱ ምስለ ታዴዎስ ረድኡ እንዘ ይብል ንሣዕ ዘንተ ሥዕለ መልክዕየ ወውእቱ ይፈጽም ለከ ኩሎ መፍቅደከ ወይፈውሰከ እምደዌከ ወይባርክ ሀገረከ ወያረትዕ መንግሥተከ። ወአምኑ ሰብአ ሀገረሮሃ ምስለ ንጉሦሙ በሥልጣነ መለኮቱ ለእግዚእነ። **ሰኔ** 12 አፎምያ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አሥላ ትኖር ነበር። እና ሰይጣን ሲመጣ የምታሯሩጠው በዚያ ነበር።

ፈተና ወይም አመክሮ

ጥቅምት 20 አረጋዊሰ አባ ባይሞይ ፈቀደ ያመክሮ ወአሐተ እለተ ዘበጦ ወሰደዶ እም በዓቱ ወይቤሎ ኢይፈቅድ እኅድር ምስሌከ። ወቅዱስኒ አባ ዮሐንስ ሐጺር ቆመ ነአፍኣ ማዕከለ መርሕብ ወለለጽባሑ ይወጽእ አባ ባይሞይ ወይዘብጦ ወይብሎ ኢይፈቅድ እርዓይከ ውእቱሰ ይቤሎ ስረይ ሊተ ኦ አቡየ ወይሰግድ ታሕተ እገሪሁ። **ጥር** 9 ወእሙኒ ለዝንቱ ቅዱስ ፈራሂተ እግዚአብሔር መሐይምንት ወቀንዐ ላእሌሃ ሰይጣን ወቦአ ውስተ ልበ አሐዱ ብእሲ እኩይ ወአስተዋደያ ኀበ ሰብአ ፋርስ። ወእሙንቱ ጼወውዋ ወወሰድዋ ኀበ ብሔሮሙ ወይእቲ እሙ ሐለየት ታስተዋስቦ ለወልዳ አብርሃም ብእሲተ ወኢፈቀደ ውእቱ ዘንተ ወተፈሥሐት ቦቱ እሙ ፈድፋደ።

ትሕትና፣ መታዘዝ

ጥቅምት 20 ወእምዝ በአሐቲ ዕለት ረከበ አባ ባይሞይ ዕፀ ይቡሰ። ነሥኦ ወወሀቦ ለአባ ዮሐንስ ሐጺር ወይቤሎ ትክሎ ለዝንቱ ዕፅ ወስቅዮ ማየ እስከ ይሠርጽ ወይፈሪ። ወተአዘዞ አባ ዮሐንስ ለአቡሁ ወነሲኦ ውእተ እፀ ተክሎ ወሰቀዮ ማየ ለለእለቱ ክልኤተ ጊዜ ወማይኒ ርኑቅ መጠነ አሠርቱ ወክልኤቱ ምዕራፍ። ወእምድኅረ ሠለስቱ ዓመት ሠረፀ ውእቱ እፅ ወኮነ እፀ ዐቢየ ወጸገየ ወፈረየ ፍሬ ጥዑመ። ወእምነ ፍሬሁ ነስአ አባ ባይሞይ ወይቤሎሙ ለመነኮሳት ንሥኡ ወብልዑ እምፍሬ ተአዝዞ ወትሕትና። ወእሙንቱ ርእዮሙ ዘንተ መንክረ አንከሩ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ዘይሁብ ዘከመዝ ጸጋ ለእለ ይትኤዘዙ ለመምህራኒሆሙ። **ጥር** 22 ወሶበ ልሕቀ ንስቲተ እንጦንዮስ ያደንን ርእሶ ወይትኤዘዝ ሎሙ ለአበዊሁ። ወይቤ በነፍሱ እፎ ኀደጉ ሐዋርያት አበዊነ ኩሎ ግብረ ዓለም ወተለውዎ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። **የካቲት** 8 አባ ኤልያስን ንጉሡ ቴዎዶስዮስ በትሩፋት ነቢዩ ኤልያስን ትመስላለህ ሲለው አባ ኤልያስ እንዲህ አለ ‹ለኤልያስ እንበይነ ጽድቁ ያመጽኡ ሎቱ ቋዓት ሲሳዮ። ወሊተሰ ለእመ አነብር ሲሳይየ ውስተ ፀሐይ ይመጽእ ቋዕ ወይነስኦ ወየሐውር›› ወሰሚያ ንጉሥ አንከረ እምጣዕመ ቃሉ። **የካቲት** 21 ወፍትወት እንስሳዊት ትትሀወክ በውስቴቱ። ውእቱሰ ያበዝኅ ጸመ ወትጋሀ ለጸሎት ወሰጊድ። ወሶበ ኢተክህሎ ያግርራ ተአመነ ሎቱ ለአሐዱ አረጋዊ። ውእቱኒ ይቤሎ ኢትጠፍዕ ዛቲ ፍትወት እንስሳዊት ዘእንበለ ግብረ ትሕትና እስመ ትሕትና መድኃኒተ ዚአሃ።

መጋቢት 15 ወፈቀደ ሰይጣን ያውድቃ በትእቢት ወይቤላ ተፈሥሒ ኦ ሣራ እስመ ናሁ ሞዕኪዮ ለሰይጣን። አውስአቶ ወትቤሎ አንሰ ብእሲት ድክምት ዘኢይክል እማየ ዘእንበለ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። መጋቢት 29 ሶበ ተዐርግ ነፍሱ ለአባ መቃርስ ከልሑ ሰይጣናት እንዘ ይብሉ ሞዕከነ ሞዕከነ ኦ መቃሪ። ወይቤሎሙ አባ መቃራ ዓዲየ እስከ ይእዜ። ወሶበ ቦአ ውስተ ገነት ከልሑ በቃል ልዑል እንዘ ይብሉ ሞዕከነ ኦ መቃሪ። ወይቤሎሙ ይትባረክ አምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአድኀነኒ እም እደክሙ። ሐምሌ 8 ወአሐተ ዕለተ ሐጸበ ብሶይ እገሪሁ ለመድኃኒነ ወሰትየ መንፈቆ ወመንፈቆ ኀደገ ሎቱ ለረድኡ ከመ ይስተይ ወሶበ መጽአ ረድኡ ይቤሎ ተንስእ ኦ ወልድየ ወስተይ እማይ ዘውስተ ንብቲራ። ወይቤ ረድኡ በነፍሱ ለምንት ኢይሁበኒ እምጽሩይ ማይ ዘውስተ ማህየብ ወዘንተ ብሂሎ ተሀየየ ወኢሰትየ በከመ አዘዞ መምህሩ። ወካዕበኒ ይቤሎ ኦ ወልድየ ተንስእ ወስተይ ውእተ ማየ ዘውስተ ንብቲራ። ወሶበአገበሮ ተንስአ ወሖረ ኀበ ንብቲራ ወኢረከበ ማየ። ወአጠየቆ ቅዱስ አባ ብሶይ ዘከመ ሐጸበ እገሪሁ ለእግዚእነ ወሰትየ መንፈቆ ወኀደገ ሎቱ መንፈቆ ከመ ይስተይ ወሶበ ነገሮ ኀዘነ ፈድፋደ ወደንገጸ ዐቢየ ድንጋጼ ወይቤሎ አሐዱ ጻድቅ ስማዕ ወተአዘዝ ለአቡከ ለእመ ኮንከ ተአዛዜ እም ኢበጽሐከ ዝንቱ ድንጋጼ።

የውሀት

ጥቅምት 23 ሊቀጳጳሱን በውሸት ሊያስገድሉ የነበሩት ሰዎች ለፍርድ በንጉሡ ፊት ቀረቡ። ወአስተብቁዖ ሊቀ ጳጳሳት ለንጉሥ ወይቤሎ ኦ ንጉሥ መሐሮሙ ወኢትቅትሎሙ ለእሉ በእንተ እግዚአብሔር እስመ ለነ አዘዘነ እግዚእነ ከመ ንግበር ሠናየ ህየን እኪት። ወአንከረ ንጉሥ እም የውሃቱ ወተወክፈ ስእለቶ ወመሐሮሙ ሎቱ።

ፍቅረ እግዚአብሔር

ጥቅምት 25 ወሶበ ይዘከር አባ ቡላ (አቢብ) ስቅለቶ ወሕማማቲሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የዐርግ ላዕለ እፅ ነዊኅ ወይቄሩ ርእሶ ታሕተ ኩሎ አሚረ። ወይጸፍዕ ገጾ ወይመትር ሥጋሁ በበግማድ ወይቀሥፍ ዘባኖ ወእግዚእነ ይፈውሶ። ወአሐተ እለተ ሶበ ሐለየ ሕማሞ ለእግዚእነ ተከለ ሰይፎ ወዐርገ ዲበ ዕፅ ወወድቀ ዲቤሁ ወሞተ ወአንሥአቶ በእደዊሃ እግዝእትነ ማርያም።

በጎ ሕሊና

ህዳር 13 ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ ቅዱስ አስከናፍር ባዕል። ወዝንቱ አስከናፍር አሐዱ ውእቱ እመኳንንተ ሮሜ ወይሁብ ምጽዋተ ለነዳያን ወለምስኪናን ወይትዌከፍ ነግደ ወፈላሴ። ወበውእቱ መዋእል ሀለው አሠርቱ ወሠለስቱ ፈያት ዘየኀጉሉ ወየሀይዱ ሰብአ ዘረከቡ ወሶበ ሰምዑ ዜናሁ ለአስከናፍር ከመ ይትወከፍ ነግደ ወፈድፋደሰ ያፈቅር መነኮሳተ ተማከሩ ከመ ይሑሩ ኀቤሁ በትምይንት ከመ ይቅትልዎ ወይንሥኡ ኩሎ ንዋዮ። ወእምዝ ለብሱ ልብሰ ምንኩስና ወቆመ ውስተ ደጌሁ። ወሶበ ርእዮሙ ሐለየ ውእቱ ከመ እመንቱ አሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት። ወአሐዱ እግዚእ ክርስቶስ ወሰገደ ሎሙ ወአብአሙ ውስተ ቤቱ

ወአቅረበ ሎሙ ማዕደ። ወሐጸበ እገሪሆሙ ወውእተ ማየ ምህባበ እገሪሆሙ ነገሥ ላእለ ወልዱ መጸጉዕ ዘሠላሳ ወነመስቱ ክረምት። ወበጊዜሃ ሐይወ ወልዱ። ወሶበ ርእዩ ዘኮነ እሙንቱ ፈያት ደንገጹ ጥቀ። ፈያትም መንነው መንኩሰው በሰማእትነት አርፈዋል።

ሀልዮ

ህዳር 21 ወእምዝ ተዘከረ ጎልፈቶ ለዝንቱ ዓለም ወንብረተ መንግሥተ ሰማያት እንተ ኢተነልፍ ወረሰየ ኩሎ ሕሊናሁ በእንተ መድኃኒተ ነፍሱ።

ክህደት

ህዳር 22 ክህደተ ዲዮቅልጢያኖስ ኮነ በምክንያተ ወልደ ንጉሠ ቁዝ ዘአማሕጸኖ ኀበ አባ አጋግዮስ መነኮስ መፍቀሬ ወርቅ ኮነ ምንዳቤ ላእለ መሐይምናን። እስመ አጋግዮስ ነሢኦ ወርቀ ብዙኃ ፈነዎ ለወልደ ንጉሠ ቁዝ ወማሕረኮ ዳግመ። ወነቢያ ኪያሁ ወልደ ንጉሥ ጸውያ ለአጋግዮስ ወአዘዞ ከመ ያምጽእ ወልደ ንጉሠ ቁዝ ዘአማሕጸኖ ወይቤ አጋግዮስ በሐሰት ሞተ ወተቀብረ ወሶቤሃ አምሐሉ በቅድመ ምሥዋዕ ወጸንሐ ከመ እሳት ትወርድ ወታውዕዮ። ወሶበ ኀንደየ ርደታ ለነድ አምሐወ ወርቀ በእሳት ወአስተዮ ለአጋግዮስ ወአውዓዮ ወበእንተ ዝንቱ አምለከ ጣዖታተ ዘወርቅ ወዘብሩር።

ገጸ ክለባት፣ ዓለም

ህዳር 25 ወሶቤሃ ወለጠ እግዚአብሔር ፍጥረቶሙ ኀበ የውሃት ከመ አባግዕ። ወኮኑ ዘይነብሩ በነቤሆሙ ብዙኀ መዋዕለ ወእምዝ ኮኑ ክርስቲያነ። ገጻተ ከለባትሰ ኮኑ ዘይትኤዘዙ ወይትለአኩ ለአበ ቅዱስ መርቆሬዎስ። **ሐምሌ** 21 ወተንስኡ ላእሌሁ እስላም። ወበአሐዱ እመዋዕል እንዘ ይገብር ጸብአ ኮነ ሎቱ ለንጉሥ መዊዕ። ወድኅረሰ ኮነ መዊዕ ለእሳላም እስመ ከመዝ ሥርዓታ ለዛቲ ዓለም።

ቅዱሳት በዓላት

ታኅሣሥ 20 ወበዛቲ ዕለት ካዕበ ገብረ በዓለ ደቅስዮስ በዘአብሠራ ገብርኤል ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም። እስመ ውእቱ ደቅስዮስ ኤጲስ ቆጶስ እምንደተ ፍቅሩ አስተሐመመ ላቲ ወአስተጋብአ መጽሐፈ ተአምሪሃ። ወአስተርአየቶ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ አክሊሎሙ ለመሐይምናን። ወነስአት በእደሃ መጽሐፈ ወትቤሎ ኦ ፍቁርየ ደቅስዮስ አንሰ ሠመርኩ ብክ ወንዕድኩከ በእንተ ዘገበርከ ሊተ ዘንተ ወእምዝ ተሠወረት እምኔሁ ወሶበ ርእየ ደቅስዮስ ዘንተ ግብረ እምራዕይ ወእምፍቅረ እግዝእትነ ቅድስት ቅድስት ድንግል ማርያም ተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሓ ወነደ ከመ እሳት በእንተ ፍቅራ። ወእምዝ ገብረ በዓለ በዘዜነዋ ገብርኤል ሊቀ መላእክት ዘኢተክህሎሙ ሰብእ ይግበርዎ ቀዳሚ በውእቱ ጊዜ በእንተ ጸም። ወረሰየ ውእቱ እምቅድመ በዓለ ልደት ስቡሕ በሰመንቱ መዋዕል ዘውእቱ አመጿ ወ ሠኑዩ ለታኅሣሥ። ወተሠርዐ በመዋዕለ ጽጽስናሁ እስከ ዛቲ ዕለት። ወወህበቶ እግዝእትነ ልብሰ ክቡረ ወመንበረ ክቡረ።

ሰይጣን

ታኅሣሥ 24 ወይቤሎ ሰይጣን አልብነ ሥልጣን ከመ ንባእ ውስተ ሰብእ እንዘ ሀሎ በፍኖተ እግዚአብሔር ወላእለ ዘይጼውዕ ስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወላእለ ዘይትመጦ ሥጋሁ ወደሞ ለክርስቶስ በንጽሕ። **መጋቢት** 5 ወናሁ መጽአ ሰይጣን ተመሲሎ ከመ ቋዕ። **ሰኔ** 11 ኦ ዘምሉእ እምኩሉ እከይ ወአቡሃ ለሐሰት ረሀቅ እምኔነ እስመ አንተ ትትቃረኖ ለፍኖተ እግዚአብሔር በኩሉ ጊዜ። **ሰኔ** 12 መጽአ ሰይጣን በአምሳለ መልአክ ብርሃናዊ ወይቤላ ለአፎምያ አነ ውእቱ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ ፈነወኒ እግዚእ ኀቤኪ ወውእቱ ይኤዝዘኪ ከመ ትኅድጊ ዘንተ ምጽዋታተ ወትትወሰቢ ለአሐዱ ብእሲ መሐይምን ወአእመረ ከመ ብእሲት ዘአልባ ብእሲ ትመስል ሐመረ ዘአልቦ መልሕቅ ወአኀዘ ያምጽእ ላቲ ትእምርታተ እመጻሕፍተ ብሊት ከመ አብርሃም ወያዕቆብ ወዳዊት ወእለ ከማሆሙ እለ አውሰቡ ብዙኃተ አንስተ ወእሉ ዘአስመርዎ ለእግዚአብሔር። ወአውስአቶ ቅድስት አፎምያ ወትቤሎ እመሰ አንተ መልአከ እግዚአብሔር አይቴ ትእምርተ መስቀል ዘምስሌከ እስመ ሐራሁ ለንጉሥ ኢየሐውር ኀበ ካልዕ መካን ዘእንበለ ትእምርቱ ለንጉሥ። ወሰሚዖ ዘንተ ሰይጣን ተወለጠ አርዓያሁ ወሐነቃ ወይእቲ ጸርሐት ወተንበለት ኀበ መልአክ ክቡር ሚካኤል ወበጊዜሃ በጽሐ ኀቤሃ ወአድኃና ወለውእቱ ሰይጣን አኀዘ ይኮንኖ ወአውየወ ሰይጣን ወሰአሎ እንዘ ይብል እስመ እግዚአብሔር ተዐገሠ ላዕሌነ እስከ ተፍጻሜተ ዓለም መሐረኒ ወኢታጥፍዓኒ ዘእንበለ ጊዜየ ወእምዝ ኀደጎ ወሰደዶ። **ሐምሌ** 15 ወአምነ ንጉሥ ጸራግሞስ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በስብከተ ሐዋርያት ወእምድኅረዝ ሖሩ ሐዋርያት። ወሰይጣንሰ ተመሰለ በአምሳለ ንጉሠ እንዶር ወመጽአ ኀበ ጸራግሞስ ንጉሥ እንዘ ያተሉ አጋንንተ በአምሳለ ሐራ ወይቤሎ ለምንት በእንተ እሉ ክልኤቱ ሐዋርያት መሰግላን ዘኢታጠፍዖሙ ፍጡነ ዘእንበለ ያማስኑ ሀገረ በሥራዮሙ። ወተመይጠ ልቡ ለጸራግሞስ ንጉሥ ኀበ ዕልወት ወሣቀዮሙ ለሐዋርያት። **ነሐሴ** 13 ወሶበ ርእዩ ሰይጣናት ተጋድሎቶ ለአባ ጋልዮን ተመሰሉ በአምሳለ መነኮሳት ወቦኡ ኀቤሁ ጊዜ መንፈቀ ሌሊት ወይቤልዎ ንሕነ ገዳማውያን ሥውራን ሶበ አሐዱ እምኔነ ፈለሰ ፈተውነ ንንሣእከ ምስሌነ መጻእነ ኀቤከ። ሎቱስ መሰሎ ከመ እሙን ቃሎሙ። ወሖረ ምስሌሆሙ እስከ አብጽሕዎ መልዕልተ ደብር ምዝብርት ኀበ አልቦ ልብስ ወሲሳይ። ወሶበ ርእየ እንዘ ይትቃጸብዎ አእመረ ከመ ሰይጣናት እሙንቱ አተበ ላእሌሆሙ በትእምርተ መስቀል ወተዘርወ። **ነሐሴ** 14 ወዓዲ ሀለው ክርስቲያን ክልኤቱ ነዳያን ዐሳባን። ወአምጽአ ሰይጣን ውስተ አሐዱ ሕሊና ጽርፈት ወይቤሎ ለቢጹ ኦ እኁየ ለምንት ናመልኮ ለክርስቶስ። ወአውስአ ቢጹ ወይቤሎ አእምር እስመ ንዋየ ዝንቱ ዓለም ኢኮነ እምእግዚአብሔር ወኢምንትኒ። ለእመ ቦቱ ባቁዕ እምኢወሀቦሙ ለእለ ያመልኩ ጣዖተ ወለዘማውያን ወለቀታልያን ወለኩሎሙ አማፅያን። ወለቡ ከመ ነቢያት ቅዱሳን ኮኑ ነዳያነ ወምንዱባነ ወሐዋርያትኒ ከማሆሙ ምንዱባን።

የዓለም ተለዋዋጭነት

ነሐሴ 20 ወበዛቲ ዕለት አዕረፉ ሰብዓቱ ደቂቅ እለ እምሀገረ ኤፌሶን እለነበሩ በመዋዕለ ዳኬዎስ ንጉሥ አላዊ። ወእሉ ሰብዓቱ ደቂቅ ኮኑ እም ሐራሁ ለንጉሥ ዳኬዎስ ወሚሞሙ ዲበ መዛግብቲሁ። ወሶበ አቀመ አምልኮ ጣዖታት ኢተሳተፉ በግብረ አምልኮ። ወአስተዋደይዎሙ

ለእሉ ቅዱሳን ኀበ ንጉሥ። ወአኀዞሙ ወሞቅሖሙ። ወእምዝ ሶበ ንጉሥ ፈቀደ ይሑር ኀበ ካልዕ መካን ፈትሖሙ ወነደኅሙ እስከ ይትመየጥ። ወእምዝ መነኑ እሉ ቅዱሳን ግብረ ሐራ ከመ ኢይስግዱ ለርኩሳን ጣዖታት ወሖሩ ኀበ በዓት ዘውስተ ደብር ወተኀብኡ በሀየ። ወፈጸሙ አፈ በዓት። ወሀለው ምስሌሆሙ ብሩር ዘጽሑፍ ዲቤሁ ስሙ ለዳኬዎስ ንጉሥ። ወበበዕብሬቶሙ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ ይወጽእ ወይሣየጥ ሲሳዮሙ ወይትመየጥ ኀቤሆሙ። ወሶበ ሰምዑ ከመ ዳኬዎስ ገብአ እምኀበ ሐረ ፈጸመ አፈ በዓቶሙ ወኖሙ። ወሀለው አሐዱ ብእሲ እምውስተ ሐራ ምእመን ዘየአምር መካኖሙ ለእሉ ወጸንሖሙ ከመ ይርከቦሙ። ወሶበ ኢመጽኡ ተንስአ ወሖረ ኀበ በዓቶሙ ወረከባ ለበዓት በዘፈጸምዋ እምውስጥ ወመሰሎ ከመ እሙንቱ ሞቱ በረኀብ ወነስአ ጽላተ ዘእብን ወጸሐፈ ገድሎሙ። ወእሙንቱ ቅዱሳን ኖሙ በትእዛዘ እግዚአብሔር ፲፱፻፹፪ አዝማነ። ወመዊቶ ዳኬዎስ ወነግሡ ብዙኃን ነገሥታት እስከ መዋዕሊሁ ለቴዎዶስዮስ ንጉሥ። ወበመዋዕሊሁ ለዝንቱ ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ምእመን ተንስኡ ሰብእ እለ ይብሉ አልቦ ትንሳኤ ሙታን ወተለውዎሙ ብዙኃን። ወውእተ አሚረ አንቅሖሙ እግዚአብሔር ለእሉ ሰብዓቱ ቅዱሳን ደቂቅ ያግህድ ከመቦ ትንሳኤ ሙታን። ወእምዝ ወጽአ አሐዱ እምኔሆሙ ነሢኦ ብሩረ ከመ ይሣየጥ ሲሳዮሙ ወይስማዕ ዜናሁ ለዳኬዎስ አላዊ። ወሶበ ቦአ ውስተ ሀገር ተወለጠ ላእሌሁ ግብራ ለሀገር ወርእየ መስቀላተ ውስተ አናቅጸ ሀገር ወዲበ አረፋቲሃ ወእንዘ ይጼውዑ ስሞ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንበለ ፍርሀት። ወተሰአሎ ለአሐዱ ወይቤሎ አኮኑ ዛቲ ሀገር ኤፌሶን ወይቤሎ እወ። ወይቤልዎ እም አይቴ አንተ ወይቤሎሙ እምዛቲ ሀገር ወይቤልዎ መነ ተአምር ወይቤሎሙ እገሌሃ ወእገሌ። ወዘጸውዖሙ ሰብእ አልቦ ዘየአምሮሙ እምብዝኀ መዋዕል ወአንከሩ ኩሉ ሕዝብ ኩሎ ዘኮነ አመ ነገሮሙ ኩሎ። ወእምድኅረዝ ተመይጡ እሉ ሰብዓቱ ደቂቅ ወሰከቡ ወመጠው ነፍሶሙ ውስተ እደ እግዚአብሔር።

አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ

አክሲማሮስ ማለት የስድስት ቀናት ስነ ፍጥረት ማለት ነው። ኤጲፋንዮስ ማለት ከሣቲ(ምስጢር ገላጭ)፣ አስተርእዮ ማለት ነው። ወላጆቹ በኦሪት ሕግ የጸኑ አይሁድ ነበሩ።የገዛ አህያቸው ኩላሊቱን ረግጦ ጣለው። አባ ፊላታዎስ በመስቀል ምልክት አማትቦ አዳነው። ከዚያ እህቱንም አምጥቶ እርሱም ተጠመቀ። ተምሮ መንኩሶ የቆጵሮስ ደሴት ኤጲስ ቆጶስ ሆነ።

ሥነ ፍጥረት

ሥላሴ ይህን ዓለም እንፍጠር ብለው አሰቡ ካለመኖርም ወደ መኖር ፈጠሩት። ፈጣሪያቸውን ቢያውቁት የሚጠቀሙት ሰውና መላእክት ናቸው። የቀረው ፍጥረት የተፈጠረው ልንበላው ልንጠጣው ልንሠራበት ልንማርበት ነው። ከተፈጠረው ሁሉ የሰውን ፈቃድ የማይፈጽም የለም እንዳለ አረጋዊ መንፈሳዊ። ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ ሰባት ፍጥረታትን ፈጠረ እኒህም፡- እሳት፣ መሬት፣ ውሃ፣ ነፋስ፣ ሰማያት፣ መላእክትና ጨለማ ናቸው። የእሳት ግብሩ ብሩህነት፣ ሞቃትነት፣ ደረቅነት ናቸው። የነፋስ ሞቃትነት፣ ቀዝቃዛነት ጥቁርነት ናቸው። የውሃ ብሩህነት፣ ርጥብነት፣ ቀዝቃዛነት ናቸው። የመሬት ደረቅነት፣ ጥቁርነት፣ ርጥብነት

ናቸው። እሑድ ጠዋት ከቀኑ በመጀመሪያው ሰዓት ብርሃን ተፈጠረ። የዕለተ ፍጥረት አንዲ ቀን በእኛ 1000 ዘመን ናት። ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጽልመት ዕርግ ወትረ በበሠርክ በመሳክወ ምዕራብ ከመትኩን ሌሊተ። ወሶበ ሠረቀ ጎሕ ግባዕ ኀበ እምከ በርባሮስ ወኮነ ከማሁ። ይህ የተፈጸመው መጋቢት ሠላሳ ነው። መንፈስ ቅዱስ የፈጠራቸውን ፍጥረታት በሙሉ ቀድሷቸዋል አክብሯዋል

ሰማያት

ከእሳት ብርሃንን ወስዶ በሁለተኛው ሰዓተ ሌሊት ሰማይ ውዱድን በሦስተኛው መንበረስብሀትን ሰራ። ሰማይ ውዱድ ኪሩቤል የሚሸከሙት ነው። ሰማይ ውዱድን እንደ መሠረት አድርጎ በላይዋ መንበረ ስብሀትን ሠራ። ወገብረ ላቲ ሰብዓተ መንጦላዕተ ዘነደ እሳት ወአያደ ዲቤሃ ሰብዓተ ቅጽራተ። በአራተኛው ጽርሐ አርያምን ሰራ።በመንበረ ስብሀት ላይ ጽርሐ አርያምን እንደጠፈር እንደ ጣራ ሰራ። አልቦ ሰማይ ዘይጼልል ላዕሌሃ እስመመልእልታዊት ወጽንፋዊት። በአምስተኛው ሰዓተ ሌሊት ኢዮርን ከሰማይ ውዱድ በታች ሠራት። በስድስተኛው ከኢዮር በታች ራማን ሰራት በሰባተኛው ኤረርን ከራማ በታች ሰራት። ሰባቱ ሰማያት እግዚአብሔር በሚያውቀው የተያያዙት በቅጽር ነው። ኤረር፣ ራማ፣ ኢዮር ርዝመታቸው ወርዳቸው እኩል ነው። ከዚያ በስምንተኛው ሰዓተ ሌሊት ያችን እሳት ከነውዕየቷ ከፍሎ አውጥቶ ከሦስቱ ሰማያት በላይ ከሰማይ ውዱድ በታች አሰፈራት። ይችም እሳት የእሳት ሀገር ሆነች።በዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት ከዚህች እሳት በላይ በመንበረ ስብሀት አንጻር ፊት ለፊት ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ሰራ። ወባቲ አሠርቱ ወክልኤቱ አናቅጽ ውሉጣነ ብርሃን። በከዋክብት አምሳል የብርሃን መርገፍ አዙሮባታል። ወጽሑፍ አስማቲሆሙ ለአሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት ወለአሠርቱ ወክልኤቱ ነገደ እስራኤል በአሠርቱ ወክልኤቱ አናቅጺሃ። ወውስቴታ ታቦት ዘዶር ዘያበርህ በጸዳለ ሥሉስ ቅዱስ። የእግዝእትነ ማርያም አምሳል ናት። ሰባቱ ሰማያት የሚባሉ ጠፈርና ሐኖስን ሳይጨምር ነው። ለሰባቱ ሰማያት ፲፱፱፱ አናቅጽ አውጥቶላቸዋል። የእሳት ጉበን እሳት መድረክ ሠርቶ የውሃ ሳንቃ ገጥሞላቸዋል። ከዚህ በኋላ በየአናቅጹ ትዕምርተ መስቀል ያልያዘ ከታች ወደላይ እንዳይወጣ ሁለት ሁለት መላእክት ሰይፍን እያስመዘዘ በእያንዳንዱ አንቀጽ አድርጓቸዋል። ሙሴ በውጭ አንድ ሆኖ ቅጽር ለቅጽር ገጥሞ ቢያየው አንድ ሰማይ ብሎ ቆጠረ። ኤጲፋንዮስ ግን በውስጥ በኩል በአየር ወይም በርዝመት መራራቃቸውን በከተማ መለያየታቸውን አይቶ ሰባት ብሎ ቆጥሯል። መላእክት ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን አይተው አመሰገኑ ይላል።

መላእክት፣ ሳጥናኤል

ከዚህ በኋላ በአስረኛው ሰዓተ ሌሊት አጋዕዝትን ፈጠረ አለቃቸው ሳጥናኤል ነበረ። ሳጥናኤል ማለት ቅሩበ እግዚአብሔር አጎዜ መንጦላእት ማለት ነው። ሁለተኛ አሥሩን ነገድ ኪሩቤል አላቸው። እምታሕተ ሐቂሆሙ አሐዱ ወእምላእለ ሐቂሆሙ አርባእቱ ገጻት። ከእግራቸው እስከ ራሳቸው ድረስ በዓይን የተሸለሙ ናቸው። አንድም እንደነብር ዝንጉርጉር አንድም እንደ መስታወት ብሩህ ናቸው። ወሊቆሙ ገጸሰብእ ወገጸ አንበሳ ዝ ውእቱ ኪሩብ። ሦስተኛ አስሩን ነገድ ሱራፌል አላቸው እለ ስድስቱ ክነፊሆሙ። የምስጋና ነቅዕ ከእነዚህ ይጀምራል። አምሳለ

ዲያቆናት ናቸው። ኪሩቤል የቀሳውስት አምሳል ናቸው። ወሊቆመ ለሱራፌል ገጸ ንስር ወገጸ አንበሳ ዝ ውእቱ ሱራፊ። ወለራብዕ ዖታ አሠርቱ ስሞመ ኃይላት ወሊቆመ ሚካኤል። ወጾታ አሠርቱ ስሞመ አርባብ ወሊቆመ ገብርኤል። ወካልዕ ጾታ ዐሠርቱ ስሞመ መናብርት ወሊቆመ ሩፋኤል እሉ እመንቱ እለ ይጸውሩ ወላትወ መብረቅ ወኵናተ እሳት። ወለሣልስ ጾታ አሠርቱ ስሞመ ሥልጣናት ወሊቆመ ሱርያል። እነዚህ የሥላሴ ነጋሪት መኾኖች ናቸው። ወጾታ አሠርቱ ነገድ ስሞመ መኳንንት ወሊቆመ ሰዳክያል። እሉ እመንቱ እለ ይነድፉ በሐጸ እሳት። ወውኩላን ለዐቂበ እጓለእመሕያው ወያስተጋብኡ አዕጽምተ ሰብእ አመ ትንሳኤ ሙታን በዳግም ምጽአት። የመላእክት አንዱ ነገድ ከውሉደ አዳም ትክክል ነው። ወለዳግም ጾታ አሠርቱ ስሞመ ሊቃናት ወሊቆመ ሰላትያል እለ ይጼዓኑ በአፍራሰ እሳት ወጽሩዓን በነደ እሳት ወውኩላን ለዓቂበ ኩሉ ዘሥጋ። በደመ ነፍስ ሕያዋን የሆኑትን ሁሉ ይጠብቃሉ። ወለሣልስ ጾታ አሠርቱ ስሞመ መላእክት ወሊቆመ አናንያል። እሉ እመንቱ እለይዌጽፉ በሞጸፍተ ነጎድጓድ አዕባነ እሳት ዘሐጺን ወውኩላን ለዓቂበ ኩሉ ፍጥረት ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት ዘእምታሕተ ሰማይ ወእምላዕለ ምድር። ዕዕዋትን ሁሉ ይጠብቃሉ። በመካናቲሆመ ለእሉ ኩሎመ ነገደ መላእክት አልቦ ደዌ ወኢሕማም ኢሞት ወኢኀዘን ዘእንበለ ሰብሑቱ ለአምላክ። ጌታም ፈጥሮ ተሰወራቸው ማን ፈጠረን በበርእስነኑ ተፈጠርነ አሉ። ሳጥናኤልም እኔ ፈጠርኳችሁ አለ። መላእክትም ፈጣሪ በፍጥረቱ ይታወቃል ፈጥረህ አሳየን አሉት። እፈጥራለሁ ሲል እሳት ፈጀው ሐሰቱ ታወቀ። ገብርኤል ንቁም በበህላዌነ እስከንረክቦ ለእግዚእነ አለ። ወአኀድኦመ መልአከ ሰላም በቃሉ ይላል። ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ወአስተርአዮመ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወረሰዮመ ለመላእክቲሁ ከመ አንቆቅሖ ውስተ ሕጽኑ። እሳት ወለደት ብርሃነ ወዝንቱ ብርሃን ኮኖመ ጥበበ ወይቤሉ ቅዱስ ቅዱሰ ቅዱሰ እግዚአብሔር ጸባኦት። ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መላእክትን ቀደሳቸው የብርሃን መጎናጸፊ የብርሃን ዝናር የብርሃን ዘንግ ማኅተመ መስቀል የሆነ የብርሃን ጫማ የብርሃን መነጽር የብርሃን ዘውድ ደፋላቸው። አእምሮ ፍቅር ትሕትና የዋህት ትዕግሥት የሚሆናቸው ቅብዐት መላእክትን መንፈስ ቅዱስ ቀባቸው። ከኪሩቤል ገጸ ሰብእ ወገጸ አንበሳ ከሱራፌል ገጸንስርና ገጸ እንስሳን ወስዶ ሰማይ ውዱድን አሸከማቸው። ከሩፋኤል ነገድ 24 ሊቃናትን መርጦ በመንበረ ስብሀት በመጋረጃዋ ውስጥ ዙሪያውን ክንፍ ለክንፍ ገጥሞ አቁሟቸዋል። ኪሩቤልን ጀርባቸውን ወደ ውስጥ ፊታቸውን ወደ ውጭ እያደረገ አቁሟቸዋል። ካህናተ ሰማይን የእሳት የወርቅ ጽና አስያዛቸው። የብርሃን ካባ ላንቃ ጎብሩ መብረቅ የመሰለ አለበሳቸው። ወይቤሎመ እግዚአብሔር ለካህናቲሁ ጸሎተ ኩሎመ ቅዱሳን ይኩን ውስተ ማዕጠንትክመ ከመይዕርግ ጎቤየ ወይገለብቦ ለሰማይ ወለአርያመ ጢሰ ዕጣኖመ ዘመዓዛሁ ሰናይ። ወሲሳዮመ ለመላእክት ቅዳሴ ወስብሀት ወስቴሆመ ፍቅረ መለኮት። ወአልቦመ ለመላእክት ትእምርተ ተባዕት ወአንስት እስመ እሳታውያን እመንቱ። ወቦ እመላእክት ዘዘዚአሁ አርአያሆመ። ቦ ዘይበጽሕ ቆሞመ እምድር እስከ ሰማያት። ወቦ እለ ያጸልሉ በአክናፊሆመ አለተ ሀገረ። ቦ እለ አርእስቲሆመ መጠነ አድባር ዐበይት። ወቦ እለ ግሉፋን ኩለንታሆመ በአዕይንት። ቦ እለ ስድስቱ ክነፊሆመ ወእሳት አልባሲሆመ። ወቦ እለ ይትዐጸፋ መባርቅተ። ቦ እለ ይትቁጸሉ ደመናተ። ወቦ እለ ይጸብጡ ነፋሳተ። ቦ እለ አእጋሪሆመ አምደ እሳት። ወአልቦ ዘየአምር ክዋኔሆመ ወፍጻሜሆመ ለመላእክቲሁ ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ። በአዳም በተሰጠው ነገር ሰይጣን ሲቀና መላእክት

ደግሞ ደስ አላቸው እግዚአብሔርንም አመሰገኑት አዳምንም ወደዱት፡፡ ረቡዕ ቀን ሳጥናኤል አሁንም እፈጥራለሁ ብሎ እጁን ሲሰድ ተቃጠለ ዋይ አለ፡፡ ያኔ መላእክት ደንግጠው ምን ሆንክ አሉት በየውሃት እጀን ወደ እሳት ብሰድ ተቃጠልኩ አላቸው፡፡ ጌታም በጎቡእ ፈወሰው፡፡ የልቤን ባያውቅ እንጂ ብሎ አሁንም ለመፍጠር አሰበ ያሰበበት ልቡ ተቃጠለ ዋይ አሉ፡፡ ጌታም አልመለስ ማለቱን አይቶ ኃጢአቱን ለመላእክት ነገረበት እና ፈወሰው፡፡ በኋላ መላእክት ሳጥናኤልን አመስግን አሉት፡፡ ወይቤ ሳጥናኤል አንሰ እድው እምዝንቱ ኅሊና አለ፡፡ ለአዳም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንደምትሰጠው ከሰማ ወዲህ ኃይለኛ ቅናት አደረበት፡፡ ሰይጣን መላእክትን በእርሱ ክፉ ሀሳብ ለማሳበር መከራቸው፡፡ የተወሰኑት ምክሩን ተቀበሉት፡፡ ሌሎች ግን አልተቀበሉትም የፈጠረንን ፈጣሪያችንን አንክደውም አሉት፡፡ ኃይላት ሠራዊተ ሚካኤል መልሑ አስይፍቲሆሙ፡፡ ኪሩቤል ወሱራፌል አንስኡ ጉጠታቲሆሙ ዘእሳት ከመይትቃተሉ ምስለ ሰይጣን ወዐርገ ገብርኤል ምስለ ሠራዊቱ እንዘ ይጸውሩ ጉድበ እሳት ከመ ይርድእዎሙ ለኃይላት፡፡ ወቀነጸ ሩፋኤል ምስለ ሠራዊቱ እኂዞሙ ወላትወ መብረቅ ወሲናተ እሳት ዘይነድድ ወአገትዎ ለሳጥናኤል፡፡ ወዐርጉ ሱርያል ወሰዳክያል ወሰላትያል ወአናንያል ምስለ ሠራዊቶሙ፡፡ ሳጥናኤል ግን ድል ነሳቸው፡፡ መላእክትም ፈቃድህ ባይሆን ነውን ብለው ወደጌታ አመለከቱ፡፡ ከዚያ የብርሃን ትእምርተ መስቀል ሰጣቸው፡፡ እርሱን ባየ ጊዜ ሳጥናኤል ድል ተነሳ፡፡ ከዚህ በኋላ ሳጥናኤል ስመ እግዚአብሔር በተጠራበት ሁሉ የሚርድ የሚንቀጠቀጥ ሆነ፡፡ ከሰማይም ወደምድር (መካ) ወረደ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል የ99ኙ ነገደ መላእክት አለቃ ሆነ፡፡ ልዑለ መንበርም ተባለ፡፡ ቅዳሜ ሠርክ ለእሑድ አጥቢያ በተፈጠረው ጨለማ ተጠቅልሎ ከመካ ወደ ገሀነመ እሳት አውርዶታል፡፡ ፈጣሪ ነህ ያሉት አብረውት ወርደዋል፡፡ አንተ ከፈጠርክ እኛም እንፈጥራለን ያሉት በዚህ ምድር ሰውን እያሳቱ ይኖራሉ፡፡ የተጠራጠሩት ነአየር ላይ ቀርተው ነፍስን ያስደነግጣሉ፡፡ ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ጠባቂ መልአክ አለው፡፡ጠባቂ መልአኩ ካልተለየው ሰይጣን አይቀርበውም፡፡ ዲያብሎስ ታስሯል፡፡ በዚህ ዓለም ሰውን የሚያስቱት አብረው ያልወረዱት የእርሱ የዲያብሎስ ሠራዊቶች ናቸው፡፡ የአዳም ልጆች ስመ ሥላሴን አጋዥ አድርገው ድል ይነሷቸዋል፡፡

እግዚአብሔር

ነፋስ ፍሬን ከገለባ እንደሚለይ እግዚአብሔርም ኃጥዕን ከጻድቅ የሚለይ ፈታሒ ነው፡፡ ውሃ መንጽሒ ነው እድፍን ከአካል ይለያል ጌታም ኃጢአትን ከነፍስ ይለያል፡፡ እኛ እግዚአብሔር ወጣ ወረደ ማለታችን በዘፈቀደ(እርሱ በፈቀደልን) መታየቱን መናገራችን ነው እንጂ እግዚአብሔርስ መውጣት መውረድ የለበትም፡፡ ወተፈሥሐ እግዚአብሔር በኩሉ ተግባሩ ዘገብረ፡፡

ነፋሳት

ወዓዲ ገብረ እግዚአብሔር አሠርተ ወአርባዕተ መሳክወ እንተ መትሕተ ምድር ስድስተ በምሥራቅ ወስድስተ በምዕራብ ስድስተ በሰሜን ወስድስተ በደቡብ ከመይጸዐ ቦቱን ነፋሳት ወያስተናፍስዋ ለምድር፡፡ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከእሳት በታች ያሉትን ነፋሳት አስራ ሁለት አለቃ አደረገላቸው፡፡ አራቱ አለቆች ነፋሳተ ምሕረት ስምንቱ አለቆች ነፋሳተ መዓት ናቸው፡፡

መዝ.134፣7 ዘያወጽዖሙ ለነፋሳት እመዛግብቲሆሙ እንዲል። በሁለቱ ነፋሳተ መዓት መካከል አንድ ነፋሰ ምሕረት እያደረገ ሰርታቸዋል። ምድር እርጥብ ነበረች። እነዚህ ነፋሳት በ12ቱ መስኮት ወጥተው አደረቋት። ስለዚህም ተራሮች ጸኑ። መሬት ውሃውን ምጥጥ አድርጋ ጠጥታ እንደግንቦት እንደ ሰኔ ማሳ አማረች ለሰለሰች። ወደመናሰ ተፈጥረት እምድር እምላህበ እሳት ወነፋስ። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እሳትና ነፋስን ከመስኮታችሁ ግቡ በየቦታችሁ ጽኑ አላቸው። በዚህ ዓለም ያሉ እሳትና ነፋስ ከወደዔት ተገኙ ቢባል ጥቂት እሳትና ጥቂት ነፋስ አዝርእቱን ለመቀስቀስ ውሃውን ለመቀደስ በደመ ነፍስ የተፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ለማናፈስ ሲል ከፍሎ ትቷቸዋል። ገነትን ለማናፈስ በስተምራብ በኩል የተሾመ ነፋስ አለ። በዘጠኝ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ምዕራብ አሻቅቦ በነፈሰ ጊዜ በብሔረ ብዑዓን ላሉ ሰዎች ከገነት ዕፅዋት ፍሬ እንደ ዝናብ ይዘንብላቸዋል ይረግፍላቸዋል። ያንን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ። እሉ እሙንቱ ክልኤቱ **መካናተ ነፋስ**፡- ሔኖስን ተሸክሞ የሚኖር ባቢል የሚባል ነፋስ አለ። ሁለተኛው ከበርባሮስ ጀምሮ ይህችን ዓለም ተሸክሞ የሚኖር ታላቁ ነፋስ ነው። ነፋሳት ደመናት ለሰው ውሃ ቀድተው ዝናምን የሚያዘንሙለት ናቸው።

ዕፀዋት

ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቁል ምድር ሐመልማለ ዘርእ ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ። በምሳር የሚቆረጡ በማጭድ የሚታጨዱ በጥፍር የሚለቀሙ አዝርእትን አትክልትን ዕፅዋትን ፈጠረ። ወሶበ ይነሥእ አሐደ እምፍሬሁ ለዕፀ ሕይወት ይፈሪ ካልአ ህየንቴሁ። ከዚህች ከዕፀ ሕይወት አንዲቷን ፍሬ በበላች ጊዜ ጣዕሙ ከአፍ መዓዛው ከአፍንጫው ሳይለይ እስከ ሰባት ቀን ይቀመጣል። ወጼና ቆጽላኒ ወፍሬሃ ወጽጌሃ ይፈልጥ ነፍሰ እምሥጋ ዘእንበለ ደዌ ወሕማም። ወተከለ እግዚአብሔር አርባእተ ዐበይተ ዕፅዋተ በአርባዕቱ መዓዝኒሃ ለዕፀ ሕይወት። ወአውጽአ እግዚአብሔር አርባዕተ አፍላጋተ እምታህተ ሥረዊሆሙ ለአርባዕቱ ዕፅዋት ዐበይት። ወተከላ እግዚአብሔር ለእፀ በለስ ዘፈረየት ለነ ሞተ እንተ ድኅሪሃ ለእፀ ልቡና እመንገለ ምዕራባ ለገነት። ወአመ አዘዛ እግዚአብሔር ለገነት ከመ ታብቁል ዕፅዋተ አብቆለት ዐበይተ ወንዑሳነ ዕፅዋተ። በገነት ያሉት እፅዋት ታናናሹ ቅጠላቸው 12/12 ክንድ ይሆናል ይኸውም እንደ ኮከብ ያበራል። ገነትን ለማናፈስ በስተምራብ በኩል የተሾመ ነፋስ አለ። በዘጠኝ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ምዕራብ አሻቅቦ በነፈሰ ጊዜ በብሔረ ብዑዓን ላሉ ሰዎች ከገነት ዕፅዋት ፍሬ እንደ ዝናብ ይዘንብላቸዋል ይረግፍላቸዋል። ያንን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ። በገነት ያሉ አዕዋፋትም ዕፀወ ገነትን ይመገቧቸዋል። በጎናቸው የሚያፈሩ ዕፅዋት አሉ። በራሳቸው የሚያፈሩ አሉ። በሥራቸው የሚያፈሩም አሉ። ነጎድጓድና መባርቅት አትክልቱ እንዲያብቡ እንዲያፈሩ የሚያደርጉ ናቸው።

ማያት (ውሃዎች)፣ መሬት

ዘሠኑይ፡- ያች ብገር ተባገር ያላት ውሃ በእለተ ሰኑይ ከምድር ጀምራ እስከ ብሩህ ሰማይ ድረስ መልታ ነበር። ለይኩን ጠፈር በማዕከለ ሰማይ ብሎ ቢያዝዝ ውሃው ለአራት ተከፈለ። ጠፈር፣ ከጠፈር በላይ ያለ ውሃ(ሐኖስ)፣ ለምድር ምንጣፍ የሆነው፣ ለምድር እንደ መቀነት ያለው ውቅያኖስ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ሐኖስን ቀደሳት። ብገር ተባገር ካላት ነፋስ ከፍሎ ሐኖስን

አሸከማት፡፡ ብገር ተባገር ካላት መሬት ብሩህ ብሩሁን ወደላይ ትቶ ጥቁር ጥቁሩን ወደታች አወረደው በርባሮስም አለው፡፡ እልፍ አእላፋት ፀሐይ ቢገባበት ጨለማው የማይገፋ ነው፡፡ ከበርባሮስ በላይ በአየር አራርቆ ጸሊም ነፋስን አደረገ ከዚያ ከነፋስ በላይ በአየር አራርቆ እሳትን አደረገ ከዚያ ከእሳት በላይ በአየር አራርቆ ውሃን አደረገ፡፡ ከዚያ ይችን ምድር አደረገ፡፡ በውሃና በዚህች ምድር መካከል ግን አየር የለም፡፡ የዚች መሬት ዕንብርቷ ጉልላቷ ዱዳሌም ናት፡፡ በዚችም ጌታ በመስቀሉ ተሰቅሎ ድኅነተ ዓለም ያደረገባት ናት፡፡ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ምድርን ዙሪያ ዙሪያዋን ሁለት እጅ አድርጎ ከፍሏታል፡፡ የወዲያኛውን አንዱን እጣ ከንፈሩን ቀንፎ ወዲያና ወዲህ ዙሪያውን መሐል መሐሉን ቆፍሮ በወዲያ የወጣውን አፈር እንደ ብረት አጽንቶ ወደ ላይ አቁሞታል፡፡ የወዲሁን አፈር ወደላይ አቁሞ ትቶታል፡፡ ወደሰማይ አይደርስም በመጠን ነው፡፡ የወዲያኛውን አድማስ የወዲህኛውን ናዜብ አለው፡፡ አድማስን ከጠፈር እርሱ ባወቀ ገጥሞታል፡፡ ከዚህ በኋላ በአድማስና በናዜብ መካከል ዙሪያ ዙሪያውን ተቆፍሮ በጎድጓዳው ስፍራ እንደመቀነት ተጠምጥሞ የነበረውን ውሃ ዙሪያውን ሹሞታል ስሙንም ውቅያኖስ አለው፡፡ በዚህ ዓለም ያሉት ውሆች ከወዴት ተገኙ ቢባል ዛሬ ጠላ ሲሾም ከዋንጫው ከጽዋው ጠብ ጠብ ብሎ እንዲቀር ሁሉ ሰባት ታላላቅ ወንዞች ቀርተዋል፡፡ የምንጮች ግን ስፍር ቁጥር የለውም፡፡ አንስትያዊት ባሕር ዘሀለወት ታሕተ ምድር ወተባዕታይ ባሕር ዘዐርገ ውስተ ሰማይ፡፡ ወአመ አዘዛ እግዚአብሔር ለምድር ከመ ትለድ አድባረ ወአውግረ ወኩሎ አዕባነ ዘየብስ ወዘባሕር...ወኩሉ ፈለግ ተከፍለ፡፡ **ዘሠሉስ**፡- ወተከለ እግዚአብሔር ገነተ እመንገለ ምሥራቅ ልእልተ ወታህተ እምሰማይ፡፡ ብሩህ ብሩሁን መሬት በምሥራቅ በኩል ከናዜብ ወዲህ አድርጎ ዔደን ገነትን ተከለ፡፡ ወተከለ እግዚአብሔር አርባእተ ዐበይተ ዕፅዋተ በአርባዕቱ መዓዝኒሃ ለዕፀ ሕይወት፡፡ ወአውጽአ እግዚአብሔር አርባዕተ አፍላጋተ እምታህተ ሥረዊሆሙ ለአርባዕቱ ዕፅዋት ዐበይት፡፡ ወእሉ አስማቲሆሙ ግዮን እንተያውጎዝ ሐሊበ ወየዐውድ በኢትዮጵያ፣ ጤግሮስ እንተ ያውጎዝ መዓረ ወየዐውድ በቁስጥንጥንያ፣ ኤፌሶን እንተ ያውጎዝ ወይነ ወየዐውድ በአንጾኪያ፣ ኤፍራጥስ እንተ ያውጎዝ ቅብዐ ወየዐውድ በሮምያ፡፡ ወሶበ መጽኡ ውስተ ዛቲ ዓለም ይከውኑ ማየ፡፡ እኒህ እንደመስቀል ተመሳቅለው ገነትን ያጠጣሉ፡፡ ቦ ዘይነቅዕ እምሥራቅ ወየሐውር ለምዕራብ ከመይሰቂ ዘህየ ቦ ዘይነቅዕ እምዕራብ ወየሐውር ለምሥራቅ ከመይሰቂ ዘህየ ቦ ዘይነቅዕ እምደቡብ ወየሐውር ለሰሜን ከመይሰቂ ዘህየ ቦ ዘይነቅዕ እምሰሜን ወየሐውር ለደቡብ ከመይሰቂ ዘህየ፡፡ ወእሉ እሙንቱ መካናተ ማያት አርባዕቱ፡-ሐኖስ፣ ጠፈር፣ ውቅያኖስ፣ ከታች የምድር ምንጣፍ የሆነችው ውሃ ናቸው፡፡ እሉ እሙንቱ መካናተ መሬት ኀምስቱ፡- በርባሮስ፣ ይህች ዓለም፣ ብሔረ ብዑዓን፣ ብሔረ ሕያዋን፣ ገነት ናቸው፡፡ ብሩህነታቸው በቅደም ተከተል በርባሮስ፣ ይህች ዓለም፣ ብሔረ ብዑዓን፣ ብሔረ ሕያዋን፣ ገነት ናቸው፡፡ ከሁሉም በታች በርባሮስ ናት፡፡ ከበርባሮስ በላይ ይህች ዓለም ናት፡፡ ከዚህች ዓለም በላይ በደቡብ ብሔረ ብዑዓን ናት፡፡ በሰሜን ብሔረ ሕያዋን ናት፡፡ በምሥራቅ ገነት ናት፡፡ በምዕራብ ሲኦል ናት፡፡

ከንቱ ውዳሴ

በራሳቸው አፍርተው ፍሬያቸውን ወፍ ጠርጥሮት ጠላት ለቅሞት የሚቀሩ ዕፅዋት አሉ እነዚህም በዚህ ዓለም ብዙ ትሩፋት ብዙ ምግባር ሰርተው ይዩልን ይስሙልን ይወቁልን ብለው

በከንቱ ውዳሴ ተጎድተው በወዲያኛው ዓለም ሳይጠቀሙ የሚቀሩት አምሳል ናቸው። በሥራቸው የሚያፈሩት ዕዕዋት ደግሞ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ብዙ ትሩፋት ብዙ ምግባር ሰርተው ክብራቸውን ሸሽገው በወዲያኛው ዓለም የሚጠቀሙት አምሳል ናቸው። እንደሬት እንደመርዝ ያሉት የኃጥዓን ምሳሌ እንደወይን እንደ ሙዝ ያሉት የጻድቃን ምሳሌ ናቸው። ማቴ.7፣16-18 ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ እስመ ሰናይ ዕፅ ሠናየ ፍሬ ይፈሪ ወእኩይሰ ዕፅ እኩየ ፍሬ ይፈሪ እንዲል። በክረምት ለምልመው በጋ የሚደርቁት የኀጥዓን ምሳሌ ናቸው። ክረምት ደርቀው በጋ የሚለመልሙት የጻድቃን ምሳሌ ናቸው። በክረምትም በበጋም ልምላሜ የማይለያቸው እንደነ አብርሃም ነው በዚህ ዓለምም ጥሩ የኖሩ በዚያኛውም ዓለም ጥሩ የሚኖሩ ናቸው።

20ው ዓለማት

እሉ እሙንቱ ተስዓቱ **መካናተ እሳት**፡- ኢዮር፣ ራማ፣ ኤረር፣ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ ሰማይ ውዱድ፣ መንበረ ስብሀት፣ ጽርሐ አርያም፣ ምጽንዐተ ሰማይ፣ ባሕረ እሳት ገሀነመ እሳት ናቸው። ወእሉ እሙንቱ ክልኤቱ **መካናተ ነፋስ**፡- ሐኖስን ተሸክሞ የሚኖር ባቢል የሚባል ነፋስ አለ። ሁለተኛው ከበርባሮስ ጀምሮ ይህችን ዓለም ተሸክሞ የሚኖር ታላቁ ነፋስ ነው። ወእሉ እሙንቱ **መካናተ ማያት** አርባዕቱ፡- ሐኖስ፣ ጠፈር፣ ውቅያኖስ፣ ከታች የምድር ምንጣፍ የሆነችው ውሃ ናቸው። እሉ እሙንቱ **መካናተ መሬት** ኀምስቱ፡- በርባሮስ፣ ይህች ዓለም፣ ብሐሬ ብዑዓን፣ ብሐሬ ሕያዋን፣ ገነት ናቸው።

ብርሃናት

ዘረቡዕ፡- የፀሐይን ሰሌዳ ከእሳትና ከነፋስ ፈጠረ ይህም ይታወቅ ዘንድ በእሳትነቷ ትተኩሳለች በነፋስነቷ ትሄዳለች። የጨረቃና ከዋክብትን ሰሌዳ ከነፋስና ከውሃ ፈጠረ ይህም ይታወቅ ዘንድ በነፋስነታቸው ይሄዳሉ በውሃነታቸው ይቀዛቀዛሉ። ፀሐይ በመዓልት ጨረቃ በሌሊት ይሠለጥኑ ዘንድ አደረጋቸው። ለይኩን ብርሃን ብሎ ከፈጠረው ብርሃን የስነዴ ቅንጣት ያህል አምጥቶ ለፀሐይ ቀባት ከዚህች ለፀሐይ ከቀባት ላይ ሁለቱን እጅ ለጨረቃ አድርጎ አምስቱ እጅ ለፀሐይ ቀረ። ከአምስቱ እጅ አንዱን እጅ ለከዋክብት እያበላለጠ ቀባቸው። ከቀረው ከአራት እጅ ፀሐይ አንዱን እጅ ማያትን ደመናትን ቀባቸው። ለፀሐይ አሀን ያላት ሦስት እጅ ነው። ከዋክብት ሲፈጠሩ መላእክት አመሰገኑ። አራት የከዋክብት አለቆች አሉ ዓመቱን ከአራት በዘመን ከፍለው 91/91 ቀን ይገዙታል። ፀሐይ ዓመቱን ሙሉ ይገዛል። ከመጋት 26 እስከ ሰኔ 25 ከጳጉሜን 1 ቀንን ምልክኤል ይመግበዋል። ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ከጳጉሜን 1 ቀንን ሕልመልመሌክ ይገዛዋል ይመግበዋል። ከመስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25 ከጳጉሜን አንድ ቀንን ብርክኤል ይገዛዋል። ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ከጳጉሜን 1 ቀንን ናርኤል ይገዛዋል። ይህ ዘመን ሐጋይ ይባላል ምግቡም እሳት ነው። ከጳጉሜን ተርፋ ቀረችው አንዲቱ ቀን ዕለተ ምርያ (መድኃኒት) ትባላለች።

አንድምታ

ፀሐይ ስለምን መዓልቱን ብቻ አብርታ ቀረች ሌሊቱን ጨምራ ያላበራች ቢሉ ፍጥረቱ ሁሉ እንዳይነድ መዓልቱን ብቻ አሰለጠናት፡፡ መዓልት የመንግሥተ ሰማያት ሌሊት የገሐነመ እሳት ምሳሌ፡፡ ፀሐይ የጻድቃን ምሳሌ ጨረቃ የኃጥዓን ምሳሌ፡፡ አንድም ጨረቃ የጻድቃን ምሳሌ ጨረቃ አንድ ጊዜ ስታጎድል አንድ ጊዜ ስትሞላ እንደምትኖር ጻድቃንም አንድ ጊዜ በኃጢዓት ሲወድቁ አንድ ጊዜ በንሥሓ ሲነሱ ይኖራሉ፡፡ ምሳ.24፣16-17 ጻድቅሰ ስብዐ ይወድቅ ወስብዐ ይትነሣእ እንዲል፡፡ አንድም ፀሐይ የኃጥዓን ምሳሌ ፀሐይ በብርሃን ምሉዕ ሆና እንደምትኖር ኃጥዓንም በኃጢአት በክህደት ምሉእ ሆነው ይኖራሉ፡፡ አንድም ጨረቃ የኃጥዓን ምሳሌ ጨረቃ በምሉእ ተፈጥራ ስትጎድል ስትጎድል ፈጽማ እንደምትጠፋ ሁሉ ኃጥዓንም ከኃጢዓት ላይ ኃጢኣት ሲጨምሩ ከፍጹም ገሐነመ እሳት ይደርሳሉ፡፡ ስለምን እግዚአብሔር እሳትን ፈጥሮ ነፋስን ያልተወው ነፋስን ፈጥሮ እሳትን ያልተወው ቢሉ እሳትን ፈጥሮ ነፋስን ቢተወው ከሐሩሩ ብዛት ከሙቀቱ ጽናት የተነሳ ፍጥረቱ ሁሉ በነደደ በተቃጠለ ነበር፡፡ ነፋስንም ፈጥሮ እሳትን ቢተወው ከውርጩ ብዛት ከብርዱ ጽናት ተነሳ ፍጥረቱ ሁሉ ባረረ በተኮማተረ ነበር፡፡ ስለምን እሳትና ነፋስን ወደታች ውሃና መሬትን ወደላይ አደረገ ቢሉ እሳትና ነፋስ ቀሊላን ናቸው፡፡ መሬት እና ውሃ ተጭነው ባይዟቸው ወጥተው ወጥተው ከጠፈር በደረሱ ነበር፡፡ ውሃና መሬትም ክቡዳን ናቸው ነፋስና እሳት ተሸክመው ባይዟቸው ኖሮ ወርደው ወርደው ከበርባሮስ በተጨመሩ ነበር፡፡ ስለዚህ እርሱ ባወቀ በጥበቡ እንዲህ አድርጎ አደጋግፎ ፈጥሯቸዋል፡፡ ሥላሴ ሰባት ፍጥረታትን የሚሰማ ፍጥረት አልተፈጠረም ነበርና በአርምሞ ፈጠሩ፡፡ ኂላ ግን ሰማዕያን መላእክት ተፈጥረው ነበርና ብርሃንን በተናግሮ ፈጠሩ፡፡ ሥላሴ ጨለማን በፊት ብርሃንን በኂላ ስለምን ፈጠሩ ቢሉ ጨለማ የኦሪት አምሳል ብርሃን የወንጌል አምሳል አንድም ጨለማ የገሀነመ እሳት አምሳል ብርሃን የመንግሥተ ሰማያት አምሳል ነው፡፡ ስለምን ሰማያትን ከፈጠረ በኂላ መላእክትን ፈጠረ ቢሉ በፊትስ ፈጥሯቸው ቢሆን አብረነው ፈጠርን ተራዳን ባሉ ነበር፡፡ ይህም ይታወቅ ዘንድ በኂላ እንኳን ተፈጥሮ ሳጥናኤል እኔ ፈጠርኳችሁ ብሏል፡፡ ውሃ መንጽሒ ነው እድፍን ከአካል ይለያል ጌታም ኃጢአትን ከነፍስ ይለያል፡፡ መሬት የእግዚአብሔርን ባዕልነት ነፋስ የእግዚአብሔርን ፈታሒነት እሳት የእግዚአብሔርን ኃያልነት ያስረዳል፡፡ ዕዕዋት መዘራታቸው የመጸነሳችን መብቀላቸው የመወለዳችን ማደጋቸው የማደጋችን ማፍራታቸው የመውለዳችን መድረቃቸው የማርጀታችን መታጨዳቸው የመሞታችን በጎተራ መግባታቸው የመቀበራችን ከጎተራ ወጥተው ተዘርተው መብቀላቸው የትንሳኤያችን ምሳሌ ነው፡፡ ወንድን በኃይልና በጉልበት ብርቱ አድርገው ሴትን በኃይልና በጉልበት ደካማ አድርገው ስለምን ፈጠሯቸው ቢሉ ወንድ ለመግዛት ሴት ለመገዛት ተፈጥረዋልና፡፡ ሴትንስ በኃይልና በጉልበት ብርቱ አድርገው ቢፈጥሯት ባልተቻለችም ነበር፡፡ ስለምን ከጎኑ ፈጠሯት ቢሉ ከፍ ብለው ከራሱ ቢፈጥሯት ሴት ኩሩ ናት የባሰውን በኮራች ነበር፡፡ ዝቅ ብለውም ከእግሩ ፈጥረዋት ቢሆን ሴት ወራዳ ናት የባሰውን በተናቀች ነበር፡፡ አንድም ጎን በልብስ ይሸፈናል ሴቶችም መሸፈን ይገባቸዋል ሲል፡፡ ወባሕቱ አንስትሰ ይትገልበባ ርእሶን እንዲል፡፡ ስለምን ሥላሴ ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥሩ እንስሳት አራዊት አንገታቸውን ወደታች እየደፉ አዳምን ግን ቀጥ አድርገው ፈጠሩት ቢሉ ጌታ ሎሌውን እመቤት ገረዷን

ለተልእኮ በጠሯቸው ጊዜ ተገዥዎች ነን ሲሉ ተጎንብሰው አንገታቸውን ደፍተው እንዲታዘዙ አዳምን ገዣቸው ነህ ሲሉ ቀና አድርገው ፈጠሩት። ስለምን ሥላሴ ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥሩ በሠርክ ፈጥረው አዳምን በነግህ ቢሉ እንስሳት አራዊት በሠርክ መፈጠራቸው ሠርክን ጨለማ ይከተላዋል እነርሱንም በምድር በስብሳችሁ ትቀራላችሁ ሲል። ነግህን ብርሃን ይከተለዋል። አዳምንም በበጎ ምግባር በበጎ ሃይማት ብትገኝ ብርህት መንግሥተ ሰማያት ትከተልሀለች ሲሉት በነግህ ፈጠሩት። ስለምን ሥላሴ ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥሩ ለይኩን እያሉ በአዳም ንግበር አሉ ቢሉ ይህስ የዲያብሎስ ዘለፋ ነው።

እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፋት

ዘሐሙስ፡- ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ታስገኝ ብሎ በእግራቸው የሚሽከረከሩ በክንፋቸው የሚበሩ በልባቸው የሚሳቡ ተፈጠሩ። ብሔሞትን በየብስ ሌዋታንን በባሕር አሰፈራቸው። በጸጉራቸው ሺህ ሺህ ፍጥረት እየገባላቸው ያንን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ።የእነዚህም አሰፋፈራቸው ምድርን ዙሪያ ዙሪያውን ከሰባት ከፍሎ የወዲያኛውን አንዱን እጣ ለብሔሞት ሰጥቶታል።ሁለተኛውን ዕጣ ለሌዋታን ሰጥቷታል። በሦስተኛው እጣ በድምጽ የሚገድሉ ግሩማን አራዊትን አስፍሮባታል። በአራተኛው እጣ እሳትን አስፍሮበታል። በአምስተኛው እጣ በረድን አስፍሮበታል። ስድስተኛው እጣ ለሰው ተሰጥቶታል።ይህችን ዓለም ብሔሞትና ሌዋታን እንደቀለበት ከበዋት ይኖራሉ። **ዘዓርብ**፡- ወአመ አዘዛ እግዚአብሔር ለይእቲ የብስ አውጽአት ኩሎ እንስሳተ ወአራዊተ ወአዕዋፈ ዐበይተ ወደቃይቀ ዘአልቦን ጉልቍ።ወሶበ ፈጠሮሙ ለእሉ ተባዕተ ወአንስተ ፈጠረ። ሐሙስ ከተፈጠሩት በምን ይለያሉ ቢሉ ከባሕር የተፈጠሩት ወደ የብስ ወጥተው ቢውሉ ቢያድሩ ዋዕየ ፀሐይ ሲጸያቃጥላቸው ይሞታሉ። ከየብስ የተፈጠሩትም ከባሕር ገብተው ቢውሉ ቢያድሩ ውርጭ ቅዝቃዜ ሲጸናባቸው ይሞታሉ።

ሰው

ዓርብ በነግህ አዳምን በአርኣያው ፈጠረው። እጓለመሕያው እጓል የተባለ አዳም እም የተባለች ምድር ሕያው የተባለ እግዚአብሔር ነው። እሳት ወነፋስ ነፍስ እሙንቱ መሬትኒ አምትንት ወአጽፋር ውእቱ ማይኒ ደም ወምራቅ ወአንብዕ ውእቱ። እሉ እሙንቱ አርባዕቱ ጠባይዓት ዘሀለው ውስተ ነፍስትነ። ለዕዕዋትም ደመ ነፍስ አላቸው። ወአልቦ አሐዱ ዘኢተፈጥሩ ምንትኒ እም አርባዕቱ ጠባይዓት ዘእንበለ መላእክት ባሕቲቶሙ። በአዳም በሥጋውና በነፍሱ መፈጠር መቀዳደም የለበትም። ሥላሴ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብለው ቢያዝዙ ዓራቱ ባሕርያተ ሥጋ እና ሦስቱ ግበራተ ነፍስ አንድ ሆነው ተዋሕደው የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ አንድ ጊዜ ተገኝቷል። ድካም ንዋም ዕረፍት ንቃሕ ትጋህ የሚስማማው አድርገው ፈጠሩት። ዕረፍትና ድካም ንዋም የሥጋ ግብር (ባሕርይ) ናቸው። ትጋህና ንቃህ የነፍስ ግብር (ባሕርይ) ናቸው። ሔዋንን ከጎኑ ፈጠራት። የወንዶች አስራው 666 ነው። የሴቶች አስራው 333 ነው። አስራው የምንበላውን የምንጠጣውን የሚያስማሙልን ናቸው። ከእግር ጥፍራችን እስከ ራስ ጸጉራችን የሚያዋሕዱልን እኒህ ናቸው። አዳም ከተፈጠረበት ቦታ 40 ቀን ተቀምጧል። ወነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈስ ሕይወት በንፍህት መንፈስ ቅዱስን አሳደረበት። ከሥላሴ የጸጋ ልጅነትን ተወልዶ የጸጋ መንግሥት ነገሠ። ሥላሴ በባሕርይ የሚገዙትን እርሱ በጸጋ

ገዛ። ወአልበስዎ መላእክት አልባሰ ብርሃን ወአግብዕዎ ውስተ ገነተ ተድላ። ወነበረት ሔዋን ባህቲታ እንዘ የዐቅብዋ መላእክት ሰማንያ መዓልተ በዘተፈጥረት ቦቱ። ወአልበስዋ ለሔዋንኒ ከማሁ እም አልባሰ ብርሃን ወአግብዕዋ ገነተ ትፍሥሕት። ወንድ በ40 ቀን ሴት በ80 ቀን መጠመቃችን ይህን አብነት ይዘን ነው። ቤተ ክርስቲያን የገነት አዳምና ሔዋን የሕጻናት ምሳሌ። አዳምና ሔዋን ቀድሞ የተቀበሉትን መንፈስ ዛሬም ሕጻናጽ በክርስትናቸው ይቀበሉታል። አዳምን በአርአያነ ወበአምሳሊነ ያሉት እነርሱ ሕያዋን እንደሆኑ አዳምም በነፍስ ሕያው ነውና። አንድም ለአዳም ቃል ልብ እስትንፋስ ሦስት ነገር አለው። ሥላሴም በአንድነት በሦስትነት አሉና። አንድም እነርሱ በባሕርይ የሚገዙትን እርሱ በጸጋ ይገዛልና በአርአያነ ወበአምሳሊነ አሉ። እግዚአብሔር አዳምን እፀ በለስን እንዳይበላ አዘዘው። ሊገዙለት ሊታዘዙለት አራዊት እንስሳት ወደ ገነት ወደ አዳም ሄዱ። በመንገድ ዲያብሎስ አገኛቸው። የአዳምን ክብሩን ሲነግሩት የበለጠ ቀና። እኔንም ውሰዱኝ አላቸው። አንዳንድ አራዊትም ጎሠር ጎስቋላ ነህ እያሉ እየተከተሉ ያባርሩት ነበር። ወሶበ ቀርበ ዲያብሎስ ኀበ እግረ ገነት ፈርሀ እስመ ድንጉፅ ወርዐድ። ሳጥናኤልም ተከትሏቸው እንዳይገባ ፈሪ ነውና ፈራ። ለመግባት ምክንያት ሲፈልግ እባብን አገኘ። የሚመለሱትን አዳም ምን አላችሁ ሲላቸው በየቦታችሁ ሂዳችሁ ተዋለዱ ብሎ መርቆ ሰደደን። ፈጣሪም ሁሉን ግዛ ብሎታል ከአንዲት እፅ በቀር የከለከለው የለም የለም ያችን ቢበሉ ትሞታላችሁ ተብለዋል አሉት። ይችን ይዞ ያችን እፅ ማን ባበላልኝና በሞተ አለ። እባብን በከንቱ ውዳሴ ጠልፎ ተዋሐዳት። በእባቢ አድሮ አዳምን አናገረው። መላእክት ጊዜያትን አይተው መጥቅእ ይደውላሉ አዳም ይህንን እየሰማ ጊዜያት ያደርስ ነበር። በገነት ያሉት አዕዋፍ አንስርት ጸሎተ ማኅበር ያደርጉ ነበር። ሰላም ለከ ኦ ንጉሠ ኩሉ ዓለም በሰማይ ወበምድር አለው። አዳምም ኢኮንኩ አምላከ አላ መሬታዊ አነ አለው። ሴቶች ከንቱ ውዳሴ ይወዳሉና ሰላም ለኪ ኦ ሔዋን ንግሥተ ኩሉ ዓለም ሲላት ደስ አላት አሳሳታትም። ወሶበ ዐለው ትእዛዘ እግዚአብሔር ኀደጎሙ ጸጋ እግዚአብሔር። በ40 በ80 ቀን የተቀበሉት ልጅነት ተነሳ። ዕርቃን ለዕርቃን ተያዩ። በአራት እግሯ ትሄድ የነበረችው እባብ እግሮችሽ ወደ ሆድሽ ይግቡ ብሎ ረገማት እግር አልባም አደረጋት። መሬት ለብሰሽ መሬት በልተሽ ኑሪ አላት። ሔዋንንም በየወሩ ደምሽ ይፍሰስ በሕማም በመከራ ውለጂ አላት። አዳምንም ብላዕ በሐፈ ገጽከ ኀብስተከ ምድር እሾህ ታብቅልብህ አለው። አዳም በገነት ሲኖር ይበላ ይጠጣ ነበር ነገር ግን ሽንት አሠር አልነበረበትም። የሚበላው በሰውነቱ እየቀለጠ ይኖር ነበር። እመቤታችንና ጌታም በዝህ ምድር ሲኖሩ እንደዚሁ ነበሩ። አዳምን እግዚአብሔር ከገነት አስወጣው አዕዋፍም እያለቀሱ ሸኙት። ፈጣሪም ገነትን የእሳት ሰይፍ በያዘ ሱራፊ አስጠበቃት። መልአኩ አዳምን በደብር ቅዱስ አኖረው። ዲያብሎስንም ገሀነም አወረደው። ሰይጣንም ጌታን ከአዳም ልጆች እኔን ያፈቀሩኝ አብረውኝ ይውረዱ አለው። ጌታም እንዳታስታቸው በስሜ እረዳቸዋለሁ እንጂ ከእኔስ አንተን ከወደዱ አብረውህ ይውረዱ አለው። አዳምም ሔዋንን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን 40 ቀን ሱባኤ እንግባ አላት። በ35ኛው ቀን ሰይጣን ጸሎታችሁ ተሰምቷል እግዚአብሔር ልኮኛል ወደገነት ላግባችሁ አላቸው። አዳም ግን እምቢ አለው። ሰይጣንም ለሔዋን ነገራት። ሔዋንም እሺ አለችው። ዲያብሎስም ሔዋንን አዳም ቀድሞ አትብላ ያለውን በልቶ ተዋረደ። አሁን ደግሞ ገነት ላስገባችሁ ብሎ ቢልከኝ እምቢ አለ ትቻችሁ መሄዴ ነው የሰይጣን መጫወቻ ሆናችሁ መቅረታችሁ ነው አላት። ሔዋንም አዳምን ሄዳ እግዚአብሔር

ይቅር ካለን እንውጣ አለችው፡፡ አዳምም ሔዋንን ሰምቶ ወጣ ከእግረ ገነት ሲደርሱ ዲያብሎስ ነኝ ሱባኤያችሁን አፍርሳችኋልና ተስፋ የላችሁም አላቸው፡፡ ድንጋይ አንስቶ በአዳም ሲወረውርበት ድንጋይቱ ድንኳን ሆናለት ሦስት ቀን ተቀመጠ፡፡ ከደሙም በፍሬ እፅ ለውሶ ወደ እግዚአብሔር መሥዋእት አቀረበ፡፡ እግዚአብሔርም ተገልጦ አዓርግ መሥዋእተ በደምየ ለአቡየ ወእትቤዘወከ በሞትየ ወበመስቀልየ አለው፡፡ በሐሙስ እለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ አለው፡፡ አዳምም በዋሻ ተቀመጠ፡፡ የገነት አዕዋፋትም የሚበላውን አመጡለት፡፡ አዳም በገነት ሳለ የአዕዋፍ የአንስርትን ቋንቋቸውን ያውቅ ነበር፡፡ አዳም እስከ ጊዜ ሞቱ ድረስ በዚያ ዋሻ ኖረ፡፡ አዳምም ሠርግ አድርጎ ሔዋንን አገባት፡፡ ወርቅ ከርቤ ስኒን ዕጣንም ለሔዋን ማጫ ሰጣት፡፡ ከዚያ ሔዋንን አወቃት ወለደችም፡፡ በመጀመሪያ ቃየልና ሉድን ከዚያ አቤልና አቅሌማን ወለደ፡፡ ቃየል የእኔን መልከ መልካም ለአቤል ለአቤል የአቤልን መልከ ጥፉ ለእኔ ሰጠብኝ ብሎ አዘነ፡፡ አቤልንም በድንጋይ ገድሎ ሁለቱንም አገባ፡፡ አዳምም አለቀሰ፡፡ ሰባት ዓመትም አዘነ በኋላ ሔዋን ሴትን ከነመንትያው ሴት ልጅ ወለደች፡፡ በአብርሃም ዘመን እያረሱ መብላት ተጀመረ፡፡ መልአኩ በሬዎችን ማረሻውን ወገሉን አስተካክሎ ለአብርሃም ሰጠው፡፡

መድሎተ አሚን

አዘጋጅ፡- መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ሰው ሆይ እዝነ ልቡና ዐይነ ልቡና አለህ፡፡ የእግዚአብሔርን የጌትነቱን ምሥጢር የማወቅ ብርሃን በልቡናህ ተፈንጥቆበታል፡፡ ሁሉም በበኩሉ እውነተኛው ሃይማኖት እኔ የያዝኩት ነው ብሎ ያንኑ ለማጽደቅ ከመጣጣር በቀር በሰላማዊው መንገድ ተጨዋውቶ ሀሳብ ከሀሳብ ካለመለዋወጡና ካለመግባባቱ የተነሳ አንዱ የሚለውን ሌላው ሳይረዳው በመፈራራትና በመኳረፍ ተለያይቶ ይኖራል፡፡ መግባባትና መስማማት የሚገኘው ሁሉም በየበኩሉ እውነተኛው ሃይማኖት እኔ የያዝኩት ብቻ ነው ማለቱን ትቶ የሌላውንም አስተያየትና አመራር በቅን ሕሊና በመመልከት ነው፡፡ ማናቸውንም ነገር ቢሆን ስሩ መነሻው ካልታወቀ ጫፉን ይዞ ተነስቶ መልስ ልስጥበት ቢሉ መልሱ የተበላሸ መሆኑ አይካድም፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ለሮማው ፖፕ “እናንተ ቁም ነገር አድርጋችሁ የያዛችሁት የጴጥሮስን ወንበር ነው፡፡ እኛ ግን ቁምነገር አድርገን የያዝነው የጴጥሮስን ትምህርት ነው፡፡ ሮማ የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ናት እያላችሁ ትኮራላችሁ ቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስን ገብተው ቢያስተምሩ የቁልቁሊት ሰቅላ በሰይፍ መትራ ገላቸዋለች እንጂ አክብራ ተቀብላቸዋለችን አልተቀበለቻቸውም፡፡ ይህም ቢሆን ዐጽማቸው ያረፈበት ቦታ ስለሆነ ልትከበር ይገባታል ትሉ ይሆናል፡፡ ይህ የሚያስከብር ከሆነ ጌታ የተቀበረበት ኢየሩሳሌም ከሁሉ በላይ ተከብራ ኤጲስ ቆጶሷ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት መባል በተገባው ነበር” አሉት፡፡ ኢትዮጲያ ከጉባኤ ኬልቄዶን በፊት የአንድ ባሕርይን ባህል በፍሬምናጦስ ተቀብላ እስከዛሬም በዚያው ጸንታ አለች፡፡ ሃይማኖት በቃል ተነግሮ በጆሮ ተሰምቶ በልብ የሚታመን ነው፡፡

መቅድም፣ መግቢያ፣ ምርመራ

መቅድም ማለት ለሚመጣው ነገር መሪ ፊታውራሪ በር ከፋች ማለት ነው። ዲዮስቆሮስ ኬልቂዶናውያንን “እስኪ ንገሩኝ ኢየሱስ ወደሰርግ ቤት የተጠራ እንደ ሰውነቱ ወይስ እንደ አምላክነቱ አላቸው። እንደ ሰውነቱ አሉት። ውሃውን ወይን ያደረገውስ አላቸው እንደ አምላክነቱ ሲሉት መለኮቱ ከትስብእቱ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነዋ” አላቸው። በፖርቱጊዝ እርዳታ ግራኝ ድል ሆኖ ኢትዮጵያ ሙሉ ነጻነቷን አግኝታ መንግሥቷን በትክክል ማቋቋሟ የታወቀ ነው። ፖርቱጊዞችን ለእርዳታ ያመጣው ቤርሙዲዝ ከእንግዲህ ወዲህ አቡን ከሮም ይምጣ እኔም ለኢትዮጵያ አንደኛ ሮማዊ ጳጳስ ልሁን ብሎ ለአጼ ገላውዴዎስ አመለከተ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም አንከራከርና ሮማውያን ቢረቱን እንልቀቅላቸው ብንረታቸው ይልቀቁልን አሏቸው። ንጉሡም ፈቅደው ጉባኤ ተደረገ። **መግቢያውን** ሳይመረምሩ ከውሥጠ ምሥጢሩ ልግባ ማለት ሳንቃ ሳይከፈት ከጓዳ ልገኝ ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን እንደ ጥንቱ አንድ እንድትሆን ማሰብ ለዚህም አሳቢ ሲገኝ ማደፋፈርና ማበረታታት የተቀደሰ ተግባር ነው። ከሕግ ውስጥ ትንሽ ነው ተብሎ የሚታለፍ የለም። ማቴ.5፣19። የምታቀርበው ምክንያት ሀሳብህን የማይደግፍ መሰረተ ቢስ እንዳይሆን መርምር። ለነገሩ ማስረጃ ሳይሰጡ ሳይሆን አይቀርም ይሆን ይሆናል እያሉ መላ እየጣሉ መናገር አይገባም። ሳይንቲስቶች ሥነፍጥረትን በመመራመር በምድር የሚሸከረከር በሰማይ የሚበር ሰርተዋል። እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት በተቻለ መጠን ተመርምሮ ይደረስበታል። ባሕርየ እግዚአብሔር ግን በምርመራ አይገኝም። ሀሳብህን ብቻ ደጋፊ አትሁን። ሰው የነገሩትን ሰምቶ ይፈርዳል እንጂ ልቡና ያመላለሰውን ሰምቶ መፍረድማ የእግዚአብሔር ብቻ ነው። ለምታስተባብለው ነገር ሁሉ እውነተኛው ነገር ይህ ነው ብለህ በማስረጃ ማስተባብያ ካልተኩበት በቀር ሐሰት ነው ማለት ብቻ ሐሰት ሊያደርገው አይችልም። ሸፍንፍን ያለ ያልተገለጠ ነገር ከተናገሩ እውነት ነው ወይም ሐሰት ነው ብሎ መልስ ለመስጠት አይቻልም። መረጃ ሳትሰጥ ይህን እንዲህ ይሉታል ብትል ልብ ወለድ ነው የሚሆንና ያለመረጃ አትናገር። እኛ አምላክ አብርሃም የሚለውን የአብርሃም ፈጣሪ ብለን እንተረጉመዋለን። ሙሴን አምላኮ ለፈርዖን የሚለውን ደግሞ በፈርዖን ላይ ተአምራት ማድረግ የሚቻለው ነቢይ ብለን እንተረጉመዋለን። ሌላውንም ሁሉ እንደዚሁ ይህን በመሰለ አኳኋን እንደጊዜውና እንደአመጣጡ መለወጡ አይቀርም። ጌታ አብ የዐብየኒ ብሏል (ይህን ሲል በምን እንዴት ለምን በምን...ወዘተ ብለን መጠየቅ አለብን። ለምሳሌ በእድሜ ከሆነ ዮሐንስ መጥምቅም 6 ወር ይበልጠዋል።ስለዚህ በምን ስለምን የሚል ጥያቄ መጠየቅ አለብን ዝም ብለን እንነዳ)። አንድ መረጃ ሳይኖር በቃል ብቻ ምኞትን ተናግሮ እውነት ነው ብላችሁ ተቀበሉኝ ማለት ተገቢ አይደለም። ለራስህ ሀሳብ የሚስማማውን ሀሳብ ብቻ ሳይሆን የአንተንም ሀሳብ ሊቃወም የሚችል ትክክለኛ ሀሳብን በማስረጃ ተቀበል። አንድን ሀሳብ ደንበኛ ሀሳቡን አስለቅቀህ የራስህን ሀሳብ ደጋፊ ለማድረግ መሞከር ጥሩ አይደለም። የባለቅኔው ሀሳብ መነሻውና መድረሻው ካልታወቀ የቅኔው ምሥጢር በእርግጥ ሊታወቅ አይችልም። ትምህርት የሌላቸው ያላስተዋሉ ሰዎች መጻሕፍትን ለምኞታቸው እንደሚስማማ አድርገው ይለውጡዋቸዋል።

ካቶሊክ፣ ክልኤ ባሕርይ፣ መናፍቃን

ካቶሊኮች ባሕርየ ትስብእት ለባሕርየ መለኮቱ ሲገዛ ይኖራል ባይ ናቸው። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስን ከአብም ከወልድም ሠረፀ ይላሉ። ጌታ ከማርያም ሥጋ እንጂ ነፍስ አልነሳም ይላሉ። ሌላው ለምእመናን ሥጋውን ብቻ ትሰጣለች ለካህናት ሥጋውንም ደሙንም ትሰጣለች። ደሙን ለምእመናን አትሰጥም። ክርስቶስ ግን ሥጋየን ብሉ ደሜን ጠጡ ብሎ ላመነበት ሁሉ አስተካክሎ ቢሰጥ ደሙን ካህናት ብቻ ይቀበሉ ምእመናን አይቀበሉ ማለት ታላቅ ስህተት ነው። ማርቲን ሉተር እንደጻፈው ወደገነት መግቢያ የይለፍ ወረቀት ካርኒ ትሸጥ ከነበረም ስህተት ነው። አጼ ካሌብን ሮማ ቅዱስ ብላ የምታከብረው አጼ ካሌብ ካቶሊክ ቢሆን ነው ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም። ካሌብ ካቶሊክ ነበረ የሚል ታሪክ የለም። ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ጉባኤ ኬልቄዶን ድረስ የተነሱ አባቶችን እነ አትናቴዎስን እነ ቄርሎስን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች። ከእነዚህ አበው ግን ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ ብሎ ያስተማረ ወይም የጻፈ አይገኝም። ሮማ ከመጻሕፍት ሳይሆን በይመስላልና በያሰኛል ብቻ በሀሳቧ ገምታ የወሰነችውን የክልኤ ባሕርይ ባህል ለመንዛት ሞክራለች። ሮም በኦርቶዶክስነቷ ጸንታ አንድ አካል አንድ ባህርይ ማለትን ታስተምር በነበረ ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሮሙን ሊቀ ጳጳስ ያከብሩት እንደነበረ እርግጥ ነው። ኋላ ግን ሁለት ባሕርይ ማለትን ባመጣ ጊዜ ጥለውት ስለተለያዩ ቀርቶበታል። በወንጌል ሕግ ያመነ ሁሉ ተካክሎ ለክርስቶስ ይገዛል እንጂ አንዷ ቤተ ክርስቲያን ለአንዷ ቤተ ክርስቲያን ልትገዛ አያዝዝም። የልዮን ባሕል ቀዳማዊ ቃል ሰው ቢሆን አካላዊ ተዋሕዶ ተዋሐደ እንጂ ባሕርየ ትስብእትን አልተዋሐደም ስለዚህ ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ ሁለት ፈቃድ ነው የሚል ነው። ካቶሊካውያን በምሥጢረ ሥላሴ በኩልም መንፈስ ቅዱስን ከወልድም ሰረጸ ስለሚሉ በዚህም እንለያያለን። ካቶሊክ በፈቃድ የማይገናኙ ስለሆነ መለኮትም እንደፈቃዱ የመለኮትን ሥራ ይሰራል ትስብእትም እንደፈቃዱ የትስብእትን ስራ ይሰራል ብላ ወስናለች (እንዲህ ከሆነኮ ሥጋ መራብ ሲፈልግ መለኮት ዝም ብሎ ያየዋል። መለኮት በሥጋ ፈቃድ ሥጋ በመለኮት ፈቃድ አይመለከተውም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ስህተት ነው)። ካቲሊክ የቃል ባሕርዩ በተዋሕዶ ሳይሆን በመቃረብ ነው አካሉ ግን በተዋሕዶ ነው አሉ። የትስብእቱ ባሕርይ ለመለኮቱ ባሕርይ ይገዛል አሉ። **አውጣኪ** መለኮት መለኮትነቱን ለቆ ትስብእትም ትስብእትነቱን ለቆ በመካከላቸው ሌላ ሕማም ሞት የማይስማማው ረቂቅ ሥጋ ሆነ ይላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ዕብ.4፣14 ኢኮነ ሊቀ ካህናቲነ ዘኢይክል ሐሚመ የሚለው ነገሩን ያፈርስበታል። (ኦሪት ዘያመልክ በፍጡር ርጉም ውእቱ ስለምትል የክርስቶስን አካልና ባሕርይ ከመለኮት አልተዋሐድም ካሉ ለሥጋው ለመለኮቱ ይሰግዳሉ። ይህ ደግሞ እመኑ ብየ ወእመኑ በአቡየ ካለው ተቃራኒ ስለሚሆን ስህተት ነው)። ካቶሊክ በክርስቶስ የባሕርይ ምንታዌ አልጠፋም ትላለች። ካቶሊኮች አንድ አካል ካሉ ይህ አካል የትስብእት ወይስ የመለኮት ስንል ተዋሐዱ ካሉን ባሕርይስ ለምን አልተዋሐደም ስንላቸው መልስ የላቸውም። ካቶሊኮች ወአሐቲ ሥምረት ወአሐቲ ፈቃድ የሚለውን ከሃይማኖተ አበው ሊፍቁት ይወዳሉ። ወይም የሃይማኖተ አበው ክፍል አይደለም ሰው ጨምሮት ነው ብለው ያለምንም ማስረጃ ይክዳሉ። አቡሊዲስ ዘሮም የጻፈውን ስናሳያቸው አቡሊዲስ የሚባል ሊቀጳጳስ በሮም አልነበረም ብለው ይክዳሉ። ካቶሊኮች ልጅ ነፍስ የሚነሳው

ከእናት ከአባቱ ነው። እንዲህ ከሆነ የወንድ ዘር ሲፈስ የሴትም በውጭ ሲፈስ ነፍስ ጠፋ ይላሉ። ግን አያሰኝም በእንጨት ምሳሌ ስናየው እሳት በእንጨት ባህርይ እያለ እርስ በእርስ ካልተፈተገ እንደማይነድ ከችቦ እሳት ቢወሰድ እሳቱ እንደማይጎድል ልጅም ከወላጆቹ ነፍስን ቢነሳ ነፍሳቸው አትቀንስም። ፍየል የነብርን ልጅ ከእናንተ ቤት የተመከረ ከእኛም ቤት ተመክሯል አለቻት ይባላል።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ ወልድ ዋሕድ፣ ኢትዮጵያ

ቅዱሳት መጻሕፍትን ብንመረምር በብዛት ለክርስቶስ አንድ የሚል አነገዘ ብቻ ሲቀጽሉለት እናገኛለን እንጂ ሁለት የሚል አኃገዘ ሲቀጸል አንድም አናገኝም። 318ቱ ሊቃውንት ኦርዮስን ሲረቱ ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ብለው አሐዱ አሉት እንጂ ክልኤቱ አላሉትም። 1ኛ ቆሮ.8፣6 ወአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኩሉ በእንቲአሁ። መቅዶንዮስን የረቱት 150 ሊቃውንት ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እም አብ ብለዋል። ዮሐ.15፣26 “መንፈሰ ጽድቅ ዘይወጽእ እምኀበ አብ ውእቱ ሰማእትየ” ይላል። ኢትዮጵያን ግብጻውያን በሐዋርያነት መጥተው አስተምረው ያሳመኗት ሀገር አይደለችም። ኢትዮጵያ በሃይማኖት ትምህርት ከጥንት ጀምራ ራሷን የቻለች ስለሆነች እስክንድርያን በርትዕት ሃይማኖት ጸንታ ብታገኛት ተከተለቻት እንጂ ይህስ ባይሆን አትመስላትም ነበረ። ከንግሥተ አዜብ አስቀድሞ እውነትም ይሁን ሐሰትም ይሁን እርግጠኛው አይታወቅም ኢትዮጵያ ዘንዶ ታመልክ ነበረ እየተባለ ይተረካል። ይሁን እንጂ ይህን ታሪክ ስንመለከተው እንደ ንጉሥ አድርገው ገበሩለት እንጂ እንደ አምላክ አድርገው ያመለኩት መሆናቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ አናገኝም። ይህንንም የሚያስረዳ ነገር አጋቦስ ከሐማሴን መጥቶ ለምንድን ነው አትገሉትም ቢላቸው ባንችለው እንጂ ወደን ነውን ከቻልክ ግደለውና እንገዛልህ አሉት አደረገውም ገገርም ሆነ ይላል እንጂ አምላክ ነኝ ብሎ ተመለከ አይልም። ንግሥተ አዜብም ማንም ያስተማራት ሳይኖር “ለይኩን እግዚአብሔር አምላክከ ቡሩክ” ብላ እግዚአብሔርን ጠርታለች። ይህም በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምራ እግዚአብሔርን ያወቀች ለመሆኗ በቂ ማስረጃ ነው። ቀዳማዊ ምኒልክ በ22 ዓመቱ ከአባቱ ከሰሎሞን ዘንድ ሂዶ ታቦተ ጽዮንን ሕገ ኦሪትን ይዞልን መጣ። ሕጌን ቢጠብቁ ልጆችህ እስከ ዘለዓለሙ በዙፋንህ ነግሥው ይኖራሉ ስላለ። እግዚአብሔር በዚህ ሂደት የዳዊት የሰሎሞን የልጅ ልጆች እስከ ዘመናችን ሲነግሡ ኖረዋል። ሙሴ ሰለጰአድን ሰንበትን ሻርክ ብሎ ኢያሱም አካን ወልደ ከርሚን ለቤተ እግዚአብሔር እንዲሆን የተወሰነውን መባዓ ደበቅህ ብሎ ቅጣት እንደፈረዱባቸው የኢትዮጵያ ነገሥታትም ሕገ እግዚአብሔርን የተማሩ እንደመሆናቸው መጠን ካህናቱን ሕግ መጠበቅ አለመጠበቃቸውን ይቆጣጠሯቸዋል። የክህነትን ሥራ ግን እንስራ አይሉም። ወበህየ አበቁል ቀርነ ለዳዊት (ህየ የተባለች ኢትዮጵያ ናት)። ግብጻዊ ጳጳስ ከሀገሩ ተመርጦና ተሹሞ የመጣበት ዋናው ተግባሩ ወልድ ዋሕድ የምትል ሃይማኖትን ጠብቆ ቄስ ዲያቆን ሊሾም ነው እንጂ በሥጋዊ አስተዳደር ሊገባ አይደለም። ተስዓቱ ቅዱሳን ኦርቶዶክሳውያን አንድ ባሕርይ ባዮች መሆናቸው በአቋቋሟቸው ገዳማት አያያዝ ይታወቃል። መቼም መች ቢሆን ኢትዮጵያ የሁለት ባሕርይን ባህል የተቀበለችበት ጊዜ የለም። ኢትዮጵያ ከሃይማኖታ ክብሯን አትወድም። ክርስቶስ ተአምራትን ሲያደርግ ይህን የመሰለውን ስራ ለመለኮት ብቻ ብለህ አታስብ። የሰውነትንም የአምላክነትንም ሥራ የሰራ አንዱ እርሱ ክርስቶስ

ነውና፡፡ ወኢፈለሰ ህላዌ መለኮቱ ኀበ ህላዌ ትስብእቱ ወኢህላዌ ትስብእቱ ኀበ ህላዌ መለኮቱ፡፡ አላ በአሐዱ አካል ወለደቶ ማርያም ድንግል ወበአሐዱ ህላዌ ሰገዱ ሎቱ ሰብአ ሰገል፡፡ ሰው ከነፍስና ከሥጋ ተገኝቶ አንድ ሰው ይባላል እንጂ ሁለት ሰው እንዳይባል ክርስቶስም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ይባላል እንጂ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አይባልም፡፡ ኢትዮጵያ የመንግሥቷን ነጻነት ሊያጠፋ የሚመጣውን ጠላት በአርበኞቿ ቀስት ግንባር ግንባሩን ብላ እንደምትመልሰው የሃይማኖቷንም ነጻነት የሚያጠፋ መናፍቅ ሲመጣ ከሊቃውንቶቿ አንደበት በሚወረወር ልብን እንደፍላጻ በሚሰነጥቅ ኃይለ ቃል ትመልሰዋለች እንጂ ነጻነቱን እነጠቃለሁ ብላ አትሰጋም፡፡ የኬልቄዶን ውሳኔ ከመጻሕፍት ቃል የወጣ ልብ ወለድ ውሳኔ ስለሆነ ኢትዮጵያ አትቀበለውም፡፡ 2ኛ ጴጥ.3፣16 እለሰ አልቦሙ ትምህርት ወእለ ኢለበው ይመይጥዎ ለቃለ መጽሐፍ ከመ ሜጥዎን ለብዙኃት መጻሕፍት በግእዞሙ ወያማስኑ እንዲል፡፡ ኢትዮጵያ በእውነት በአምልኮተ እግዚአብሔር በኩል ከቤተ እስራኤል በቀር ተቀዳሚ የሌላት ሮማም ግብጽም ሌሎችም ሀገሮች የማይተካከሏት ተመራምራ ያመነች ሀገር ናት፡፡ አስቀድማ መጻሕፍተ ብሉያትን የተቀበለች በመሆኗ ስለክርስቶስ ሰው መሆን የተነገረውን ትንቢት የተቆጠረውን ሱባኤ ታውቅ ስለነበር ሥጋዌ መቼ ይደርስ ይሆን እያለች ስታወጣ ስታወርድ ሕጽዋ ለህንደኬ ኃላም ፍሬምናጦስ ተስፋ ደረሰ ሥጋ ለበሰ ብለው ቢነግሯት የሚያጠምቅ የሚያቆርብ መምህር ላኩልን ብላ ስንቅ ጨምራ ፍሬምናጦስን ወደ እስክንድርያ ልካለች እንጂ መጥቶ ያስተማራት ሀገር የለም፡፡ከፍሬምናጦስም በኋላ አልቦ ዘይነስእ ክብረ ለርእሱ፡፡ ሥልጣነ ክህነትን ሀብተ ክህነትን በገዛ ሥልጣኑ ገንዘብ ማድረግ የሚቻለው የለም የሚለውን ኃይለ ቃል ስለምታውቅ ጳጳስ ሲሞት በገዛ ሥልጣኔ ሾሜ ልተካ ሳትል ጳጳስ ላኩልኝ እያለች ወደ እስክንድርያ ትልክ ነበረ፡፡ ኢትዮጵያውያን የአንድ ባሕርይን ባህል ደግፈው የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳትን መስለው ካቶሊካውያንን ተቃውመው ከኢትዮጵያ ጠራርገው እንዳስወጧቸው በነአጼ ዘድንግል በነአጼ ሱስንዮስ በነአጼ ፋሲል በነአጼ ዮሐንስ ታሪክ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ ከግብጽ ጳጳሳትም ጋር ተስማምታ ተባብራ መኖሯ በሃይማኖት በባህል ስለተስማሙ በፈቃዷ እንጂ በግዴታ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የሮማን ካቶሊክ የምትቃወማት ባህሏን ሁሉ አንድ በአንድ አውቃ ጠንቅቃ ነው እንጂ ባለማወቅ አይደለም፡፡ ዲዮስቆሮስን የምናከብረውና የምንወደው ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ሳይወጣ ብናገኘው ነው እንጂ የአድልዎ አይደለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ አንድ እንደሆነ ዮሐ.1፣18፡3፣16 ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕጽነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ እስከ ወልዶ ዋሕዶ ወሀበ ወመጠወ ቤዛ እንዲል፡፡ ይህን መሰረት አድርገው ሐዋርያት በጸሎተ አመክንዮ ወልድ ዋሕድ ዘዕሩይ ምስሌሁ ብለዋል፡፡ ወውእቱ ፍጹም በመለኮት ወውእቱ አምላክ ዘበአማን ላሉትም ቃል መሰረቱ “ወጻእኩ እምአብ ወመጻእኩ አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ፡፡ ዮሐ.8፣42 ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ማቴ.3፣17 ያለው ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት አምላክ ሰው ሆነ ይሉናል እንጂ አምላክ ሰው ነው አይሉንም፡፡ ዮሐንስም ያ ቃል ሥጋ ሆነ አለን እንጂ ያ ቃል ሥጋ ነው አላለንም፡፡ ቀድሞ አምላክ ነበረ ዛሬም አምላክ ነው፡፡ ቀድሞ ሰው ነበረ ዛሬም ሰው ነው ግን አይባልም፡፡ ክርስቶስ ፍጹም ሰው የሆነ ፍጹም አምላክ ነው፡፡ ሥጋን ለመንሳቱ ቃል ሥጋ ኮነ ብሏል፡፡ ነፍስንም ለመንሳቱ አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ ብሏል፡፡ ኅቡረ ህላዌ ምስለ አብ በመለኮቱ ለሚለውም ቃል መሰረቱ ዮሐ.14፣10-12 አነ በአብ ወአብ ብየ የሚለው ነው፡፡ ይህን መሰረት አድርገው ሊቃውንት

በየአንቀጹ ዘዕሩይ ምስለ አብ እያሉ ነግረውናል። መለኮት ሥጋን የፍጡር ልቡና መርምሮ በማይደርስበት በግብር አምላካዊ ሥጋን በከዊን ተዋሐደው። መለኮት በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ወርዶ ሙስና መቃብርን አጥፍቶልናል። ሙስና መቃብርም ማለት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረት ነው። በአካለ ነፍስም መለኮት ወደሲኦል ወርዶ ግዕዛንን ለነፍሳት ሰብኮ ከቁራኝነት አስለቅቆናል። **ተዐቅቦ** ማለት በጠቅላላው ትስብእትና መለኮትን ከቱሳሔ ከውላጤ የሚጠብቅ አነጋገር ነው። ምሥጢሩም ሙሴ በደብረ ሲና ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉም ነበልባሉን ሳያጠፋው እንዳየ መለኮትም ትስብእትን በተዋሐደ ጊዜ መለኮቱ ትስብእትን አላጠፋውም ትስብእትም መለኮቱን አልለወጠውም ማለት ነው። ትስብእትም ማለት አካልንም ባሕርይንም አንድ አድርጎ የሚያሳይ አነጋገር ነው እንጂ አካልን ወይም ባሕርይን ብቻ የሚያሳይ አነጋገር አይደለም። ይህም ተዐቅቦ የባሕርይንም የአካልንም ተአቅቦ ያሳያል። የአንጾኪያው ሊቀጳጳስ ኪራኮስ ኢይደሉ ይኩን ህላዌ ዘእንበለ አካል ይላል። ለምሳሌ ውሃ አካልም ባሕርይም አለው አካሉ በእጅ ባይጨበጥም በጥርስ ባይላመጥም ሲፈስ ይታያል። ባሕርይውም እርጥበት ነው።ይህ ባሕርዩ የሆነ እርጥበት አካሉ በደረሰበት ሁሉ ይገኛል። እንጂ አካሉ በሌለበት ቦታ ብቻውን ሊገኝ አይችልም።እሳትም እንደዚሁ አካል ባሕርይ አለው። ባሕርይውም ዋዕይ ነው። አካሉ በእንጨት ወይም በመብራት ላይ ይታያል። ዋዕዩ ከአካሉ ላይ ሲፋጅ ሲያቃጥል ይገለጣል። እንጂ አካሉ በሌለበት ብቻውን ሊገኝ አይችልም። ባሕርይን ከአካል ለይተን አንድ በራስ የቆመ ህልው ነው አንልም። አካል በእጅ የሚዳሰሰው በዓይን የሚታየው ነው። ባሕርይ ግን በአካል ህልው ሆኖ ከአካል ሳይለይ አካል የሚሰጠውን ስሜት የሚገልጽ ነው። ንስጥሮስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ብሎ አስተማረ እንጂ ሁለት አካል ብቻ ብሎ አልቀረም። ጉባኤ ኤፌሶን በቅዱስ ቄርሎስ አፈጉባኤነት አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብሎ ወሰነ እንጂ አንድ አካል ብቻ አልቀረም። ሰው ባልን ጊዜ ባሕርይ ያለው አካል ወይም አካል ያለው ባሕርይን አንድ አድርገን እንናገራለን እንጂ አካልን ከባሕርይ ባሕርይን ከአካል ለይተን አንናገርም። ስለዚህ ቃል ሰው ሆነ ስንል አካልንም ባሕርይንም እንደተዋሐደ እናምናለን። በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ተቀመጠ ስንልም ለሥላሴ አራተኛ ሆነ አንልም ምክንያቱም ምንታዌ በተዋሕዶ ስለጠፋ ነው። ወንጌላዊ ቃል ሥጋ ኮነ አለ እንጂ ቃል ኮነ ባሕርየ ብሎ አልለየም። አንድ አካል አንድ ባሕርይ ስንል ቅድመ ተዋሕዶ መለኮታዊ ባሕርይ ያለው አካለ መለኮት በቃልነት ከዊን ለብቻ ሰብአዊ ባሕርይ ያለው አካለ ትስብእት በአዳማዊነት ለብቻ እንደነበረ እናውቃለን። የመለኮት አካሉ ምሉዕ ስፉሕ ረቂቅ ነው። ባሕርዩ ባይመረመርም አቅማችን የፈቀደልንን ያህል ባሕርዩ ክሂል ከሀሊነት ነው እንላለን። የትስብእትም አካሉ ግዙፍ የሚታይ የሚጨበጥ የሚዳሰስ ነው። ባሕርይውም የውሃ መሬት እሳት ነፋስና የነፍስ ባሕርያት ናቸው። መለኮትና ትስብእት ሲዋሐዱ እንደነፍስና እንደ ሥጋ በተዐቅቦ ነው። በውሃ በመሬት በእሳት በነፋስ ያሉ ባሕርያት ርጥበት ይብሰት ውዕየት ቁረት ነው። የነፍስ አካሏ ረቂቅ ባሕርይዋ ለባዊነት ነባቢነት ሕያውነት ነው። ነፍስና ሥጋ ሲዋሐዱ ሥጋ ግዘፍን ለቆ ሳይረቅ ሳይለወጥ ነፍስ ርቀቷን ለቃ ሳትገዝፍ ሳትለወጥ ነው። የእኒህም የነፍስና የሥጋ አካላቸው ሲዋሐድ ባሕርያቸውም ተዋሕዷል እንጂ ተለይቶ የቀረ አይደለም። ነፍስና ሥጋ በተዐቅቦ ተዋሕደው የተገኘው አካል አንድ ሰው ቢባል እንጂ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አይባልም። የመለኮትና የትስብእትም ዝኒ ከማሁ ነው። ክርስቶስ ሁለቱን የሰውነትንና

የአምላክነትን ስራዎች በአንድ ፈቃድ በአንድ ሥምረት በአንድ ሥልጣን እንደሰራቸው እንምናለን። ለያይተን ግን የመለኮትን ሥራ መለኮት ሰራ የትስብእትን ስራ ትስብእት ሰራ አንልም። ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሚለውን አነጋገር ጠማማ ልቡና ሲይዘው ፍጹም አምላክ ባለጊዜ ዕሩቅ አምላክ ማለትን ፍጹም ሰው ባለጊዜ ዕሩቅ ብእሲ ማለትን አሰምቶ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ማለትን የሚያስከትል መስሎ ስለሚታይ ክርስቶስ ፍጹም ሰው የሆነ ፍጹም አምላክ ነው እንላለን። ሥጋ ሞተ መለኮት ሕያው ነው ማለት ምንታዌን ሲያስከትል በሥጋ ሞተ በመለኮት ሕያው ነው ማለት ግን ከአንድነት የማያወጣ ምንታዌን የማያስከትል የአንድነት አነጋገር ነው። የባሕርያትም ተዋሕዶ እንደ አካላት ከምንታዌ ከቱሳሔ ከበዐዴ ከፍልጠት በተዐቅቦ ተጠብቆ የሚኖር ነው። ምንታዌና ተዋሕዶ ተቃራኒ ቃላት ናቸው። መንተወ መንታ አደረገ ማለት ነው። ተዋሐደ አንድ አደረገ ማለት ነው። ኢትዮጵያ ኢመጻእኩ እሥዐሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ብሎ ካጸናቸው ትእዛዛት በቀር ሕግ አድርጋ የያዘችው የአይሁድ ልማድ የለም። የጥንቆላ ስራ ብዙ ማግባት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕግ የተነቀፈ የተጠላ ነው። ይህንን ተላልፈው የሚሰሩ ካህናት ምእመናንም በሕገ ወጥነት ነው እንጂ ቤተክርስቲያን ፈቅዳ አይደለም። ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ የምትሆን በከዊን የምትለይ ባሕርይ ያለችው አካለ ቃል ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን ተዋሐደ። በሥጋው በደሙ ዓለምን አዳነ ሲል በተዋሕዶ እንጂ ሥጋ ብቻ አያድንም ቃል ብቻም እንዳንል ለቃል ሥጋ ደም የለውም። ደም የፈሰሰ ሰብአዊ ባሕርይ ካለው አካል እንጂ ከሰብአዊ ባሕርይ አይደለም። ቁስል የሚገኝ ከአካል ላይ ነው እንጂ ከባሕርይ ላይ አይደለም። ለምሳሌ በጥይት ተመቶ የሞተ ሰው ሲሞት አራቱ ባሕርያት ይለያያሉ። በዚያ ጊዜ የተመታው ቁስል ሆኖ በወደቀው አካል ላይ ይታያል እንጂ በተለያዩት ባሕርያት ላይ የሚታይ አይደለም። አካል የሌለው ባሕርይ ፍጹም ሊባል አይችልም። አምላክ ሞተ ለማለት ጥንቱ መሰረቱ አምላክ ተጸነሰ አምላክ ተወለደ ማለት ነው። ተጸነሰ ተወለደ ስንልም በሥጋ ነው። ዮሐንስ ወንጌላዊ ቃልን አንቀጽ ተቀባይ አድርጎ ቃል ሥጋ ኮነ አለ። እመቤታችን ወላዲተ አምላክ እመ አምላክ ብለን የምናከብራት አምላክን በሥጋ ስለወለደችልን ነው እንጂ ዕሩቅ ብእሲ ወለደች ብለን አይደለም። 1ኛ ጴጥ.4፣1 ክርስቶስ ተሰቅለ በሥጋሁ ይላል። በሥጋሁ ያለ መለኮት የተዋሐደው መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። በቃልነቱ ከዊን ትስብእትን የተዋሐደ ፍጹም መለኮት በሥጋ ሞተ እንላለን እንጂ መለኮት በባሕርዩ ሞተ አንልም። 1ኛ ጴጥ.3፣19 ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ እንዲል።ነፍስ በለባዊነቷና በሕያዊትነቷ ከዊን ሳይሆን በተለየ በቃልነቷ ከዊን ከሥጋ ምላስ ጋር ተዋሕዳ ንባብን ትሰጣለች። በዚህ ጊዜ የልብና የእስትንፋስ ከዊኗ ከምላስ ጋራ ተዋሐዱ አይባልም። መለኮትም እንዲሁ በልብና በእስትንፋሱ ከዊን ሳይሆን በቃልነቱ ከዊን ሥጋን ተዋሐደ ቢባል አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ አያሰኝም። ፀሐይም በዋዕይነቱ ከዊን ሳይሆን በተለየ በብርሃንነቱ ከዊን ከብንተ ዓይን ጋር ተዋሕዶ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያያል በዚህ ዋዕይ (ምንም እንኳ ብርሃን ባለበት ሁሉ ቢኖርም) አልተዋሐደም። መለኮት በሥጋ ሞተ ሲባልም አብ መንፈስ ቅዱስ ሞቱ አያሰኝም። በቃልነቱ ከዊን ሰው የሆነ ሥጋን የለበሰ ወልድ በሥጋ ሞተ ቢባል በልብነትና በእስትንፋስነት ከዊን ያሉ ሥጋን ያልተዋሐዱ አብ መንፈስ ቅዱስ ሞቱ የማያሰኝ ነው ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ የምትሰሙት የላከኝ የአብ ቃል ነው ብሎ አብን ባለቤት አድርጎ ቢናገር። ይህን ነገርኳችሁ እኔን የሚወድ ቃሌን ይጠብቅ ብሎ ራሱን ባለቤት አድርጎ

ቢናገር ጳራቅሊጦስ በመጣ ጊዜ ያስተምራችኋል ብሎ መንፈስ ቅዱስን ባለቤት አድርጎ ቢናገር በዚህ ንባብ ወንጌል የሦስቱም ሕግ እንደሆነች እንረዳበታለን። ጌታ ፈቃድከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ቢል በሌላው አንቀጽ ደግሞ ነፍሴን እኔ በፈቃዴ እለያታለሁ እንጂ ሊቀማኝ የሚችል የለም ሲል እናገኘዋለን። ጌታ አብ የዐብየኒ ሲል በሕማሙ ምክንያት ነው። ሕቀ አሕጸጽኮ እመላእክቲከ የሚለው ትንቢትም ለጌታ የተነገረ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን ክታቡ ጽፎታል ይህም ስለሕማሙ ከመላእክትንኳ አነሰ ተባለ። ካቶሊካውያን እንደሚሉት የመለኮትን ሥራ መለኮት የትስብእትነ ስራ ትስብእት ተከፋፍለው የሚሰሩት ቢሆን ነፋሳትንና ማዕበላትን መገሰጽ በተለይ የመለኮት ስራ ስለሆነ ትስብእትን አድነን ብለው ሐዋርያት ባልቀሰቀሱትም ነበር። ሥጋ እንደማያድን ዮሐ.6፣63 መንፈስ ውእቱ ዘያሐዩ ወሥጋሰ አልቦ ዘይበቁዕ ይላል። ቅድመ ዓለም በየማነ አብ የነበረ እርሱ እንደገና በሥጋ ነበረ በየማነ አቡሁ ተባለ። ሁለቱ ባሕርያት በተዋሕዶ አንድ ሆኑ እንላለን እንጂ አንዱን ባሕርይ አጥፍተን አንድ ባሕርይ ብቻ የምንል አይደለንም። ሳይቀላቀል ከሁለት አንድ እንዴት ሊሆን ይቻላል ለሚለው መልሳችን በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል የሚል ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ ብሏል።በሥጋ ብሎ ትስብእቱን በመንፈስ ብሎ መለኮቱን በመናገሩ ተዐቅቦ መኖሩን ሞተ ሐይወ ብሎ በአንድ አንቀጽ በመናገሩ ተዋሕዶውን ያስረዳናል። ተዋሕዶ ምንታዌን የማያጠፋ ከሆነ ተላጽቆ ተቃርቦ ያሰኛል እንጂ ፍጹም ተዋሕዶ አያሳኝም። ግብረ መለኮትና ግብረ ትስብእት በሁለትነት ጸንተው መኖራቸው የማይካድ ነው። ሰሪያቸው ግን ለሁለቱም አንድ ክርስቶስ ነው ብለን እናምናለን እንጂ የመለኮትን ስራ መለኮት የትስብእትን ሥራ ትስብእት ሰራ ብለን በማካፈል የምንነጋገር አይደለንም። በተዋሕዶ ንዴትም ምንታዌም ጠፋ። ቃል የነሳው ሥጋ የባሕርይ ክብርን በተዋሕዶ አገኘ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ አልከበረም እንላለን። ቃል እስትንፋስ ከልብ ይመነጫሉ እንጂ ልብ ከቃል ከእስትንፋስ አይገኝም። ቃልም እስትንፋስን እስትንፋስም ቃልን አያስገኙም። መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይሰርጻል ማለት እስትንፋስ ከቃል ይመነጫል እንደማለት ስለሆነ ስህተት ነው። አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን እየላከ ህልውናውን ይገልጻል እንጂ ለማንም የታየና የተገለጸ አይደለም። አብ ፈናዊ ወልድ መንፈስቅዱስ ተፈናዊ መባላቸው ስለዚህ ነው። ዮሐ.14፣16 ይፈኑ ለክሙ ጳራቅሊጦስሃ ካልዐ ዘከማየ። ዮሐ.8፣42 እምኀበ አብ ወጻእኩ ወመጻእኩ። ጌታ በሐዋርያት እፍ ብሎ ንሥኡ መንፈስቅዱሰ ማለቱ መንፈስቅዱስ ከወልድ ሰረጸ የሚያሰኝ ከሆነ ካህናትም በንፍሐት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩብናልና መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ሰረጸ እንደማለት የሚቆጠር ስለሆነ ስህተት ነው። ዮሐ.15፣26 ወሶበ መጽአ ጳራቅሊጦስ ዘአነ እፈኑ ለክሙ መንፈሰ ጽድቅ ዘይወጽእ እምአብ ውእቱ ሰማእትየ የሚለውም መንፈስ ቅዱስ ከአብ መስረጹን ያስረዳል እንጂ ከወልድ እንደሰረጸ አያስረዳም። ዮሐ.16፣7 ወእመሰ ሖርኩ አነ እፈንዎ ለክሙ የሚለውም ከወልድ ሰረጸ አያሰኝም። ዮሐ.16፣14 እስመ እምዚአየ ይነስእ ወይነግረክሙ የሚለውን ከፍ ብሎ አርእስቱን ሲመለከቱት "ወብየ ብዙኅ ነገር ዘእነግረክሙ ወባሕቱ ኢትክሉ ጸዊሮቶ ይእዜ ወመጺኦ ውእቱ መንፈሰ ይመርሀክሙ ኀበ ኩሉ ጽድቅ እስመ ኢይነግር ዘእምኀቤሁ ይላል። ይህን ስንመረምረው ዛሬ ልትይዙት አትችሉም እንጂ የምነግራችሁ ብዙ ነበረኝ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ እርሱ ይነግራችኋል ያላቸው ትምህርቱን እንደሆነ በግልጥ ይረዳል። ለአብ ያለው ሁሉ ለእኔ አለኝ ስላለ ወላዲ ከሆነ እኔም ወላዲ ነኝ ማለቱ አይደለም። እምዚአየ ይነሥእ ያለ

መምህርነትን ትምህርትን እንደሆነ ያስረዳል። እንጂ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደሰረጸ አያስረዳም። ገላ.4፣6 ፈነወ መንፈሰ ወልዱ ውስተ ልብክሙ ያለውም መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ሠረጸ የሚያሰኝ አይደለም። ይህ ቃል በህልውና አንድ የሚያሰኛቸው ነው። ስለዚህ ህልውናቸውን ለመግለጽ መንፈሰ ወልዱ መንፈሱ ለኢየሱስ ይላል። አቡሊዲስ መንፈስ ቅዱስኒ መንፈሶሙ ለአብ ወለወልድ ይላልና። ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስቅዱስ ስላለ ከሁለቱም ተወለደ እንዳያሰኝ ማለት ነው። ነሥአ ተወክፈ መንፈስ ቅዱሰ ሲል ለአብነት ለበኩርነት ተቀበለ እንጂ በተዋሕዶ ከመክበሩ በቀር ለራሱ አልረባውም አልጠቀመውም። ዐርገ ነበረ መባሉ በሥጋ እንጂ በመለኮቱማ ጥንቱንም ንቡር ነው። ትምህርታችን ወልድ ቅብዕ በተዋሕዶ ከበረ ነው። ዮሴፍ በከነአን ሞተ ሲባል በግብጽ ሕያው ነበረ። ነፍስ ከእናት ከአባት ትነሳለች።

ምግባረ ጽድቅ

አለቃ ናሁዳ “ለጽድቅ ኢንዘከራ ወኢትዘከረነ ጽድቅ። እስመ ጊዜ ብእልነ ንትኤበይ ወጊዜ ንዴትነ ንሰርቅ” ብሏል በቅኔው። ለተንኮል ረዳት መሆን እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ስራ ነው። ጌታችን የተናገረው ቃል ሁሉ ሕግ ነው።

ቅዱሳን

ነቢያት ጻድቃን ተአምር ያደረጉት በአምላክ ረድኤት እንጂ ፍጡር ተአምር ማድረግ አይችልም።

ቱሳሔ፣ ተላጽቆ ኀድረት ተቃርቦ፣ ቡዐዴ፣ ፍልጠት

ቱሳሔ ማለት መቀላቀል መደባለቅ ማለት ነው። ለምሳሌ ቡንንና ወተትን በቀላቀሏቸው ጊዜ ቡን ጥቁረቱን ለቆ ወደ ነጭነት ይሳባል። ወተትም ነጭነቱን ለቆ ወደ ጥቁረት ይሳባል። በመካከላቸው ሌላ መልክ ይፈጠራል። ሌላ ጣዕም ይወለዳል። **ተላጽቆ ኀድረት ተቃርቦ** ማለትም እንጨትና ብረት በምስማር እንደማያያዝ ነው። ለጊዜው አንድ ይሆናሉ ምስማሩ ሲነቀል ይለያያሉ። እነዚህ ተዋሐዱ ሊባል አይችልም። የክርስቶስንም ተዋሕዶ እንደዚህ ነው ካልን ቃል ሥጋ ኮነ ያለው ታበለ ውሸት ሆነ ስለሚያሰኝ አያስኬድም። **ቡዐዴ** ማለት ተዋሕዶው ተላጽቆ ተቃርቦ ነው ማለት ነው። **ፍልጠት** ማለት ከተዋሕዶ በኋላ የሚመጣ መለየት ነው። ለምሳሌ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደዋል ነገር ግን በሞት ጊዜ ስለሚለያዩ ተፈልጦ አለባቸው። የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ግን ምንም በነፍስና በሥጋ ተዋሕዶ ቢመሰል እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተፈልጦ የለበትም።

አካል፣ ባሕርይ፣ ገጽ፣ መልክዕ፣ ስም፣ ከዊን

አካል የሚባለው ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው ሕዋስ ወይም ቅርጽ ነው። **ባሕርይም** በአካል ሕልው ሆኖ የአካልን ጠባይዕ የአካልን ስሜት የሚገልጽ ነው። ስለዚህ ቃል ባሕርየ ሰብእ ያለውን አካለ ሰብእ ተዋሕዶ በሕጻናት መጠን በየጥቂቱ አደገ። ለሰው መራብ መጠማት መታመም መሞት የባሕርይ ተስማሚ ግብር እንጂ ባሕርይ አይደለም። በእህል በውሃ

በመድኃኒት የሚርቅ ነውና። ባሕርይ ግን መቼም መች ከአካል አይርቅም። አለመራብ አለመጠማትም የሥላሴ ባሕርይ ሳይሆኑ ለሥላሴ ባሕርይ ተስማሚ ግብር ናቸው። **ገጽ** ሲል ልብስ የማይሸፍነውን ከአንገት በላይ ያለውን መገለጫን መታወቂያን ግንባርን ያመለክታል። **አቃኒም** ሲልም ፍጹም ገጽ ፍጹም አካል ማለትን ያሰማል። **መልክዕ** ባለ ጊዜ ቀይ ጥቁር ማለት ሲከተለው ጎብርን መልካም ክፉ ማለት ሲከተለው ቅርጽን ደም ግባትን ያመለክታል። ገጽ፣ አቃኒም፣ መልክዕ የአካልን ስልት ስልቱን የሚያሳዩ አነጋገሮች ናቸው እንጂ ሌላ አይደሉም **አካል** በመባል ይጠቃለላሉ። **ስም** የሚለው ግን ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው የአንድ ሰው አካል ከሌላው ሰው አካል ተለይቶ ማን እንደሆነ ታውቆ የሚጠራበት ነገር ነው እንጂ ራሱ አካል አይደለም። አዳም ሴት ኖኅ የተጸውዖ ስሞች ናቸው። ሰው ላም በግ የአካል ስም ነው። ሰአሊ ጸሐፊ ነጋዲ የግብር ስም ነው። በሥላሴ የአካል ስም የምንለው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው። ወላዲ ተወላዲ ሰራጺ የአካል ግብር ስም ነው። አካላት በህልውና የሚገናዘቡበት የባሕርይ ከዊን ስም አላቸው ይኸውም ልብ ቃል እስትንፋስ ነው። ይኸውም አንድነት ሳለበት ልዩነት ልዩነት ሳለበት አንድነት አለበት። ልዩነቱ በከዊን አንድነቱ በህልውና መገናዘብ ነው። ነፍስ በአካሏ አንድ ስትሆን ሦስት ከዊን አላት። የልብነቷ ከዊን ቃል እስትንፋስን አስገኝቶ ዕውቀት ይሆናል። የቃልነቷ ከዊን ከልብነቷ ከዊን ተገኝቶ ከሥጋ ምላስ ጋር ተዋሕዶ ንባብን ይሰጣል። የእስትንፋስነቷ ከዊን ከልብ መንጭቶ አየርን በማውጣት በማግባት ሕይወት ይሆናል። ቃል እስትንፋስ ከልብ ቢገኝም ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በልብ ህልዋን ሆነው ይኖራሉ። ሥላሴ በህልውና አንድ ናቸው የሚያሰኘው ምሥጢር ይህ ነው። ቃል ከአካለ አብና ከአካለ መንፈስቅዱስ በከዊን የምትለይ በህልውና የምትገናዘብ ናት። ነፍስ በልብነቷ በእስትንፋስነቷ ሳይሆን በቃልነቷ ከዊን ብቻ ከምላስ ጋራ መዋሐዷ ነፍስን ከሦስት የሚከፍላት አንድነቷን የሚያጠፋ አይደለም። ዝኒ ከማሁ ተዋሕዶተ ቃል።ባሕርይ አካላዊ ፍጹመ አካል ይባላል እንጂ አካል አይባልም። አካልም ባሕርያዊ ሕያው ባሕርይ ይባላል እንጂ ባሕርይ አይባልም። አካል ሰሪ ባሕርይ አሰሪ ነው። ባሕርይ ስራ ሲያሰራ እንጂ በዓይን አይታይም። ፍጹም አምላክ የሚባል ሕያው ባሕርይ የሆነ ምሉዕ ስፉሕ ረቂቅ አካል ነው። ፍጹም ሰውም የሚባል ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ግዙፍ አካል ነው። ህላዌ እንደየ አገባቡ አኗኗር ባሕርይ ተብሎ ይተረጎማል።

ኮኵሐ ሃይማኖት

አዘጋጅ፡- መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ከእኛ ከኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት ወጥቶ ፍጡር የሚያመልክ ለጣዖት የሚሰግድ የለም። አመጽን እየሰሩ የክርስቶስ መልእክተኞች ነን የሚሉ ሐሰተኞች ሰዎች አሉ። ይህም አያስደንቅም ሰይጣን ራሱ መልአከ ብርሃን ይመስላልና። ክርስቶስን መከተል በግብር ነው።በድንግልና እንደኖረ በድንግልና መኖር። እንደጾመ መጾም። ለዕጓለ እመሕያውሰ አልቦ ኀበ ያሰምክ ርእሶ እንዲል በረሃ ወድቆ ዳዋ ጥሶ ደንጊያ ተንተርሶ መኖር ነው። ማቴ.7፣21 “የሰማይ አባቴን ፈቃድ ከሚፈጽም ሰው በቀር እግዚኦ እግዚኦ የሚለኝ ሰው ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም”። 2ኛ ጢሞ.3፣19 “በኋላ ዘመን ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱበት ጊዜ

እንዲመጣ እወቅ ብር ወዳጆች ተመኮች ዕቡዮች ተሳዳቦች። መሐላ የሚያፈርሱ ሐሜተኞች እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ ተድላ ደስታን የሚወዱ" ይላል። አቶ ዘመንፈስ እኛን ዕሪያ ብለህ ሰድበህናል ዕሪያ እንደኛ ይመነኩሳልን ይጾማልን በዓል ያከብራልን ለጽላት ይሰግዳልን ቅዱሳንን ይወዳልን። በየትኛው ግብሩ ይሆን እኛን የሚመስለን። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር የማንንም ጻዲቅ ሥጋና ደም መሥዋዕት ብላ አቅርባ አታውቅም። ከክርስቶስ በቀር ሌላ ሕይወት አለ ብለን ለራሳችንም አናምንም ለሌላውም አናስተምርም። ቅዱሳንንም ብናከብራቸውና ብንወዳቸው እርሱ ራሱ ኢይብለክሙ አግብርትየ አላ አዕርክቲየ ብሎ የሰጣቸውን ክብርመሰረት አድርገን የጸጋ ክብር እናከብራቸዋለን እንጂ የባህርይ አማልክት ብለን አናከብራቸውም። (ሰይጣን በዓመፃ ዓለምን በተለያየ አምልኮና አስተሳሰብ እንዲገባ ያደረገው ርትዕት ሃይማኖትን ለማጥፋት ነው። በተጨማሪም ሰውን ለማጠራጠር ነው። እንዲህም እንደሚያደርግ ተጽፏል)። ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ስትቀበል ሌላው ዓለም ጣዖት በማምለክ ውስጥ ይገኝ ነበር።

ዕውቀት፣ ምርመራ፣ መጻሕፍት

ራስን ካለማወቅ በታች የሚገኝ ድንቁርና የለም። አላዋቂነትን አለማወቅ የድንቁርና ፍጻሜ ነው። 1ኛ ቀሮ.3፣11 ወካልዓሰ መሠረተ አልቦ ዘይክል ሣርሮ ዘእንበለ ዘተሣረረ ወመሠረቱሂ ኢየሱስ ክርስቶስ። ጥቅሶችን ከላይ መነሻቸውን ከታች መድረሻቸውን ሳትመለከት በምን ምክንያት እንደተጻፉ ምሥጢራቸውን ሳትረዳ ከሕሊናህ ለነቃው መጥፎ ሀሳብህ ደጋፊ እያደረግህ አላግባብ መጥቀስ ያሳዝናል። አንድን ጥቅስ መናፍቃን ለክፉ ሀሳባቸው ምክንያት አድርገው ቢያቀርቡትም ሲመረመር ግን ለሀሳባቸው ደጋፊ የሚሆን በቂ ምክንያት አይደለም። የመጻሕፍትን ምሥጢር ግብ ተረዳ። ከብሉያት ከሐዲሳት ግብ ሳይወጡ በብሉያት በሐዲሳት የተሰወረውን ገልጠው የረቀቀውን አጉልተው የሚያስረዱን የሊቃውንት መጻሕፍትም አምላክ ያጻፋቸው የአምላክን ነገር የሚናገሩ ስለሆኑ የሕይወት መጻሕፍት ናቸው። (ሰይጣን በዓመፃ ዓለምን በተለያየ አምልኮና አስተሳሰብ እንዲገባ ያደረገው ርትዕት ሃይማኖትን ለማጥፋት ነው። በተጨማሪም ሰውን ለማጠራጠር ነው። እንዲህም እንደሚያደርግ ተጽፏል)። ኢሳ.4፣20 አሌ ሎሙ እለ ይጽሕፉ መጽሐፈ እኩየ ይላል። መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "ቁርዓንን ስላልተማርኩና ስላልተመለከትኩ እውነት ወይም ሐሰት ብየ እርግጠኛውን ልጽፍልህ አልቻልኩም። የማያውቁትን አላውቅም ማለት በቂ መልስ ነው"። ዮሐንስ ወንጌላዊ በወንጌሉ መጨረሻ ወቦ ባዕዳትኒ ብዙኃት ግብራት ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ በቅድመ አርዳኢሁ ዘኢተጽሕፈ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ ብሏል። አዋልድ መጽሐፍ አሉ። አቶ ዘመንፈስ "ቤተክርስቲያን አርድእት በተባለው መጽሐፏ ሐዋርያት ሰዶምና ገሞራን አቃጠሏት" ይላል ስለዚህ አዋልድ ውሸት ነው ላለው መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ሲመልሱ "አርድእት የሚባል መጽሐፍ ቤተክርስቲያን በሕግ የምትጸልይበት መጽሐፍ አይደለም በጭራሽ አታውቀውም ስለዚህ ቤተክርስቲያን አትወቀስበትም" ይላሉ። ሕዝ.27፣8 ወኢትርኮሱ በጣዖቶሙ ለግብጽ የሚለው ትንቢት በጊዜው ጊዜ ሥራውን ሰርቶ አልፏል። አሁን ግብጽ በማርቆስ ስብከት ወንጌልን አምና ወልድ ዋሕድ የምትል አርቶዶክሳዊት ናት። እንጂ መምለኪተ ጣዖት አይደለችም።ክህነተ ሌዋውያንም አልፋለች ተሽራለች። መልካ መልኮችንና ቅኔዎችን መልካም ቢሆኑም

ለሃይማኖትና ለምግባር ምስክርነት አንጠቅሳቸውም። ጠቃሚነታቸውን ግን አይተን እናስተምርባቸዋለን። በላሞች መልካምነት ብቻ ወተት ሕይወት ሊሆን አይችልም ወተቱ የሚቀዳበትም ንጹሕ ሊሆን ይገባል። መናፍቃን የሚጠቅሱት መጽሐፍ ቅዱስም መልካም ነው። ግን ወተቱ (ቃለ እግዚአብሔሩ) ያረፈው ከቆሻሻ ዕቃ (ልበ መናፍቅ) ስለሆነ ይገድላል። ከሥራው ገብቶ ሳይገኙሌላ የሰራውን እየጠቀሱ ማፈቸል አይገባም። ደራሲ ለድርሰቱ አንቀጽ ለይቶ አርእስት ሰጥቶ መጻፉ ሀሳቦቹ ሁሉ በየፈርጃቸው በየመልካቸው እንዲሆኑ ነው። ሕዝ.36፣25 ወእነገዘሐክሙ በማይ ንጹሕ ከመ ትንጽሑ እም ርኩስክሙ ወዘተ የሚሉት ቃላት በብሉይ ለነበሩ ሰዎች ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ይኖር ነበር። በሐዲስ ዘኢተወልደ እማይ ብሎ አጉልቶታል። ቅዱሳት መጻሕፍትን እግዚአብሔር በመለኮታዊ ጥበቡ በቅዱሳን ሰዎች አድሮ አስጻፋቸው። የነቢያት ትንቢት የሐዋርያት ስብከት የሊቃውንት ትርጓሜ ናቸው። ኢሳይያስ ነስአ ደዌነ ወጸረ ሕማመነ መጽአ ከመ አባግዕ ይጠባሕ ብሎ ተነበየ። (የእኛ ትምህርት ትርጓሜ ያለው ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በየዘመኑ ባለው አረዳድ እንዳይለዋወጥ ተመሳሳይ አረዳድ እንዲኖር አንድምታ አስፈለገ። እንደ መናፍቃን አካሄድ ግን አንድን ቃል በየዘመኑ በደረስክበት አረዳድ ተርጉም ይላሉ። ይህ ግን አደገኛ ነገር ነው። ለምሳሌ አንትሙ ጼው ለምድር የሚለውን ለመረዳት። ድሮ ጨው ጥሩ ነበረ አሁን ግን መጥፎ እየተባለ ስለሆነ። በአሁኑ አረዳድ ተረዱት ካሉ አደጋ አለውና ይህ እንዳይኖር የተበጠረ ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ትርጓሜ አለን። ይህ ደግሞ ከሁሉም የበላይ ያደርገናል። ስለ አንድ ቃል አሁን ባለን በእኛ ግንዛቤ ሳይሆን እንደቃሉ አተረጓጎም እንዲተረጎም አድርገናል። ባለን አረዳድ እንተርጉመው ካልን ግን ከጊዜ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከቦታ ቦታም የተለያየ አረዳድ ይፈጠራል። ይህ ብቻ አይደለም ከሰው ሰውም በእውቀት ስለሚለያይ እንደየእውቀቱ ወይም እንደየተማረው ትምህርት ሊተረጉመው ስለሚችል ታላቅ ልዩነት ይፈጠራል። ከባህል ባህልም የተለያየ አረዳድ ያደርጋል። በአንዱ አገር ጨለማ የጥሩ ተምሳሌት ሊሆን በሌላው የክፉ ተምሳሌት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ የሚለው ትርጉም በአንዱ ክፉ በአንዱ ጥሩ እንዳይሆን ቃሉ የተነገረበትን ምክንያትና ሁኔታ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን አረዳድ ለመገንዘብ አንድምታ አስፈላጊ ነው። መናፍቃን ትላንት ያሉትን ዛሬ የማይደግሙት። ዛሬ ያሉትን ነገ የማይደግሙት እንደየዘመኑ እንደየ አረዳዱ ተረዳ ስለሚሉ ነው። ይህ ደግሞ ጌታ ከምን አንጻር እንደተናገረው የሚያስረዳ አንድምታ ስለሌላቸው በዘመኑ አረዳዳቸው በመሰለኝ ጌታ ያላለውን እንዲህ ሲል ነው እያሉ እነርሱም ተሳስተው ሌላውንም አሳስተው ይኖራሉ። ብዙ ሰውም ሊያሳስቱ የሚችሉት ሰው በዘመኑ አረዳድ ብትነግረው ይቀበልሀልና ከመጽሐፍ ይልቅ በዘመኑ አረዳድ ስላሳዩት እንጂ መጽሐፉን ተረድቶት አይደለም)። እውነት ራሷን ቢይዟት እግሯ እግሯን ቢይዟት ራሷ ብቅ ማለቱ አይቀርም። ቅኔ የድርሰት መልመጃ የሀሳብ መግለጫ በሐረግና በቤት የተወሰነ ጊዜያዊ አጭር ሀሳብን የሚደግፉ የነገር ቀጠፋዎች ተጠረቃቅመው የሚገኙበት ማህሌታዊ ግጥም ነው እንጂ የሃይማኖትንም የምግባርንም ምሥጢር በቋሚነት የሚያስረዳ አይደለም። ወንጌል እመቤታችን እንደተሰደደች ተናግሯል። ይሁን እንጂ በስደቷ ጊዜ የደረሱባት ጸዋትወ መከራ ዝርዝር በወንጌል ሳይጻፍ የስደቷን ነገር በሚናገረው ነገረ ማርያም በተባለ መጽሐፍ ተጽፏል። እኛም ይህን መጽሐፍ እውነተኛ አድርገን ተቀብለነዋል። እርሷን የበደሉ እነትእማር ዝንጀሮ ሆኑ ይላል። ይህ እንደ እንግዳ ነገር

የሚቆጠር አይደለም ናቡከደነጾር አውሬ እንደሆነ ተጽፏልና። ፈጣሪ ይህን ያደረገው ከናቡከደነጾር የተነሳ እንጂ እግዚአብሔር ገፋኢ ሆኖ አይደለም። በድቡሽት ላይ ተመሰረተ ሕንጻና በሐሰት የተመሰረተ ነገር ሌላ አፍራሽ ሳይኖረው እርሱው ራሱ ሲፈርስ ይገኛል። ሰውን ለማስደሰትና ወገን ለማብዛት ፈቃደ ሥጋን ደስ የሚያሰኘውን መርጦ መናገር አውቆ አበድነት ነው። **ምሳሌ** ስለምትመስልለት ጉዳይ ለሕሊና ስሜትን የሚሰጥ ከሚመሰለው ነገር ሕጸጽ ያለበት ነው። **ሊቅ** የሚባል ከብሉያት ከሐዲሳት ግብ ሳይወጣ የተገኘ ነው። መጻሕፍት የነቀፉ **ስካርንና ጥጋብን** ነው እንጂ ከሥነፍጥረት ማናቸውንም ነገር ርኩስ ብለው አልነቀፉም። አንድን ሰው በግብሩ ብትጠራው **ስድብ** አይባልም። ሌባን ሌባ አላዋቂን አላዋቂ ውሸታምን ውሸታም ብትለው ስድብ አይባልም። ብሉይን ሐዲስ ሐዲስን ሊቅ ያብራራል ያስረዳል።በብሉይ ግልጽ ያልሆነው በሐዲስ ይብራራል። ሕንጻዊው ማኅተማ ጋንዲ የሀገሩ ልማድ ፍቅር እንደ እሳት ያቃጥለው ነበር።

ቅዱሳንን ማሰብ ማክበር ማክበር እንዲገባ

ዕብ.13፣17 ተዘከሩ መኳንንቲክሙ ዘነገሩክሙ ቃለ እግዚአብሔር እንዘ ትሬእዩ ሠናየ ግእዞሙ ይላል። ተአዘዙ ለመኳንንቲክሙ ወተኰነኑ ሎሙ እስመ እሙንቱ ይተግሁ በእንተ ነፍስክሙ ያላል። መዝ.139 ወበነቤየሰ ፈድፋደ ክቡራን አዕርክቲከ እግዚኦ ይላል። ጌታም ሐዋርያትን እብለክሙ አዕርክቲየ አንትሙ ብሏቸዋል። ዮሐ.14፣12 በእኔ ያመነ ሰው እኔ የማደርገውን ተአምራት ያደርጋል ከዚያም የሚበልጥ ያደርጋል ተብሎ በጌታ ቃል ከተነገረ ቅዱሳን ተአምራት ሰሩ ሲባል መናፍቃን ለምን ይደነግጣሉ? የጌታን ቃል አይቀበሉምን። እንደገና በማቴ.17፣20 የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት ካለቻችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ወደዚያ ተነሳ ብትሉት ይነሳል ብሏል። ከክርስቶስ በቀር ሌላ ሕይወት አለ ብለን ለራሳችንም አናምንም ለሌላውም አናስተምርም። ቅዱሳንንም ብናከብራቸውና ብንወዳቸው እርሱ ራሱ ኢይብለክሙ አግብርትየ አላ አዕርክቲየ ብሎ የሰጣቸውን ክብር መሰረት አድርገን የጸጋ ክብር እናከብራቸዋለን እንጂ የባህርይ አማልክት ብለን አናከብራቸውም። በችግራችንም ጊዜ በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወበእንተ ይስሐቅ ቁልኤከ እያልን የእነርሱን ስም እየጠራን እርሱን እንለምነዋለን እንጂ ቅዱሳንን የክርስቶስ ተወዳዳሪዎች አድርገን ሕይወት መድኃኒት ናቸው ብለን አናመልካቸውም። የአምልኮት ስግደት አንሰግድላቸውም። ቅዱሳንን የምናከብራቸው ዘኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ ተወክፈ ወዘኪያየ ተወክፈ ተወክፎ ለዘፈነወኒ ብሎ ጌታ ስለተናገረ ነው። ደግሞም ዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዐስበ ጻድቅ ይነስእ ብሎናል። ለእኛስ አማላጆቻችን በራሳቸው መብትና ሥልጣን ለማንም ዋጋ ሊከፍሉ የማይቻላቸው ለማማለድ የሚያበቃ የባለሟልነት ሥልጣን ያላቸው ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማእታት ናቸው። 1ኛ ዮሐ.5፣14 በእርሱ ስም ወደ እርሱ ያቀረብነውን ልመና ይሰማናል ይላል ዮሐንስ። የቅዱሳን አማላጅነት ይህ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂነትና በቅዱሳን አማላጅነት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። በኦሪትም አብርሃም አቤሜሌክን አማልዶ አድኖታል። ዘፍ.20፣1-18።ኢዮብ ለጓደኞቹ ማልዶ አድኗቸዋል። ኢዮ.42፣7-11 ስለዚህ እግዚአብሔር መሐሪነትን ለራሱ አማላጅነትን ለቅዱሳን መስጠቱን በእነዚህ ጥቅሶች እንረዳለን። ራሱ ነውና አቤሜሌክንም አብርሃም ይጸልይልህ ያለው። ለኢዮብ ኢዮብ ይጸልይላችሁ ብሎ። በእነርሱ በኩል እንደሚምራቸው የነገራቸው። ነገር

ግን በኦሪት ጊዜ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በደመ ክሶ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋራ ገና ስላላስታረቀው እኒህ ሁሉ ቅዱሳን ነቢያት በጸሎታቸው የሚጸልዩላቸውን ሰዎች በሥጋ ከሚያገኛቸው መከራ አዳኗቸው እንጂ በዐጸደ ነፍስ ስንኳን ሌሎችን ሊያማልዱ ለራሳቸው ርደተ ገሀነም አልቀረላቸውም ነበር። ሐዋርያትን ለሥልጣኑ ተካፋዮች አድርጎ ሾማቸው። ዮሐ.14፣14 ወእመቦ ዘሰአልክሙ በስምየ እገብር ለክሙ ኪያሁ። ግብ.ሐዋ.7፣8 እግዚኦ ስረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ ወኢትረሲ ጌጋየ ብሎ እስጢፋኖስ አማልዷል። ጌታ በዐጸደ ሥጋ ሳለ በጸለየው ጸሎት ያስታረቀ በዐጸደ ሥጋ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በዐጸደ ነፍስ ያሉትንም እንዳስታረቀ የማይካድ ነው። ሐዋርያት ነፍስን ከዓለመ ነፍስ አምጥተው ከሥጋ ጋራ አዋሕደው ካስነሱ በዐጸደ ሥጋ ሆነው በዐጸደ ነፍስ ላሉት ማማለድ እንደተቻላቸው ዕወቅ። ከትንሳኤ አስቀድሞ ያለው ዘመን በዓለመ ሥጋም ቢሆን በዓለመ ነፍስም ቢሆን የስራ ዘመን ነው እንጂ የእረፍት ጊዜ አይደለም። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፣14 መላእክት ሁሉ ረቂቃን ሲሆኑ የዘላለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለተልእኮ ይላካሉ ብሎ ነግሮናል። ጌታ ስለ ቅዱሳን ሰዎች በማቴ.22፣29-30 በሰማይ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ መላእክት ይሆናሉ ብሎ ነግሮናል። ዳንኤል ደግሞ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ይላል። እስራኤልም ተማርከው ፋርስ ባቢሎን በነበሩበት ጊዜ መልአኩ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እስከመቼ የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች ይቅር አትላቸውም ብሎ ቢጸልይላቸው እግዚአብሔርም እኔ ወደ ኢየሩሳሌም በምሕረት እመለሳለሁ ብሎ መልሶለታል ዘካ.1፣12-17። (ይህ የሚያስረዳን ቅዱሳን መላእክት እንዳማለዱ ነው።ስለዚህ ሰዎችንም ጌታ በሰማይ እንደ ቅዱሳን መላእክት ይሆናሉ ስላለ በሰማይም እንዲህ እያሉ ያማልዳሉ ማለት ነው)። በራእየ ዮሐንስም ሕጻናተ ሳሌም እስከ ማዕዜኑ እግዚኦ ቅዱስ ወጻድቅ ኢትትቤቀሎሙኑ ወኢትኴንኖሙ በእንተ ደምነ እምእለ ይነብሩ ዲበምድር ራዕ.ዮሐ.5፣9-12 ብለዋል። ስለዚህ በማይመለሰው ላይ ደግሞ ይጸልዩበታል። ለሚመለሰው ደግሞ ይጸልዩለታል። በዐጸደ ነፍስ ጸልዩልኝ ብሎ መዳን እንደሌለ በአልአዛርና በነዌ ታውቋል። በፍርድ ቀን በትንሳኤ ዘጉባኤ ሁሉም እንደሥራ እንደሥራው ዋጋውን ከማግኘት በቀር ማማለድ እንደሌለ እኮኑ ኢያድኅን እኅዋሁ ወኢያድኅን ሰብአ ብሏል። ዕዝራም ይህን የመሰለ በዕዝ.ሱቱ.7፣66 ተናግሯል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምልጃ የሚገባቸው በምን ግብር ጸንተው የሚገኙ ሰዎች መሆናቸውን ለይታ ምልጃ የሚደረግበትን ቦታና ጊዜም አጣርታ ታስተምራለች። ክርስቶስ በገዛ ራሱ ታራቂና አስታራቂ አማላጅም ሆኖ ዕዳችንን በመስቀሉ ከፈለው። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ተጋርዶ የነበረው የጥል ግድግዳ በክርስቶስ መስቀል ከፈራረሰ ወዲህ ጻድቃን እያማለዱ ድኅነትን ያሰጣሉ። ከክርስቶስ በቀር ለቤዛ ዓለም የተሰቀለ በሞቱ ዓለምን ያዳነ ሌላ ጻድቅ ወይም ሰማዕት ወይም መልአክ የለም። ርኅራኄም ሆነ ጭካኔ የሰው የባሕርዩ ተስማሚ ግብር እንጂ ባሕርይ አይደለም። ጌታ በተማሪየ ስም ጽዋ ውሃ ያጠጣ ዋጋውን እንዲያገኝ በእውነት እነግራችኋለሁ ማቴ.10፣42 ስላለን በጻድቃን ስም እንዘክራለን።ስለዚህ ዝክር ጌታ ያዘዘው ነው። ዳግመኛም ተዘከሩ መኳንንቲክሙ ይላልና ቃሉን አዋሕደን እንዘክራለን። በእግዚአብሔር ስም ያደረገውን ተአምራት የተቀበለውን መከራ እናዘክራለን።ስለ እገሌ ጻድቅ እያልን እንዘክራለን። መናፍቃን እግዚአብሔር የባለሟሎቹን ምልጃ አይሰማም ለማለት የሚጠቅሱት ጥቅስ በቂ ማስረጃ አይደለም። እኛ ቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጠው ስለነገሩን ነው እንጂ ከልቡናችን አንቅተን ቅዱሳን ያማልዳሉ አላልንም። ነዌ አብርሃምን

ያለጊዜው ያለቦታው ስለለመነው አልዳነም። ለሰው ለራሱ ድኅነት የመለመኛ ጊዜና ቦታ በምድር ነውና። በሰማይ ንሥሓ የለምና ነው። ስለዚህ ጉድለቱ ከነዌ እንጂ ከአብርሃም አይደለም። ጻድቃን ስለሞቱ አይሰሙንምና አማልዱን አንበላቸው ይላሉ መናፍቃን። ሰው ከሞተ በኋላ በምድር የሚሰራውን እንደሚያውቅ በአብርሃምና በነዌ ማወቅ እንችላለን። ነዌ ስለወንድሞቹ አብርሃም ደግሞ ነዌና አልአዛር በሕይወተ ሥጋቸው ምን እንደሰሩ አውቋልና። ዘአኮ መታን ይሴብሑከ እግዚኦ ያለው ሬሳን ሲመለከት እንጂ ነፍስን አይደለም። ጌታም ከሞቱ በኋላ እኔ የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ ነኝ ብሏል። እኛ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ሕይወት አለ ብለን አናስተምርም። ለቅዱሳን ቃል ኪዳን ተሰጥቷቸዋል። ሚል.2፣8-11 የሌዊን ቃልኪዳን አፈረሳችሁ ይላል። ኢሳ.8፣11 ለሁሉ ቃልኪዳን አትበሉ ይላል። ጌታ ይህን ያለበት ምክንያት በእግዚአብሔር ኃይል ድል እናደርጋለን ብሎ በመታመን ፈንታ ከአህዛብ ነገሥታት ጋራ ርዱን ብለው ቃልኪዳን ስለተጋቡና ስለተማማሉ እርሱን ሲወቅስ ነው እንጂ የቅዱሳንን ቃልኪዳን ሲነቅፍ አይደለም። ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት የሚያስፈራራላችሁና የሚያስደነግጥላችሁ እርሱ ይሁን በማለቱ ይታወቃል። እግዚአብሔር ምድርን እንዳያጠፋት ለኖኅ ቃልኪዳን ገብቶለታል። እንደ በላኤ ሰብእ ያሉት ኃጥአን ስለዳኑ ገድላት የወንበዴ ተባባሪ ናቸው የሚሉ መናፍቃን ማቴ.9፣13 ኢመጻዕኩ እጸውእ ጻድቃነ አላ ኃጥአነ ለንሥሓ የሚለውን የማያውቁ ናቸው። ሉቃ. 15፣2 ወአንጎርጎሩ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እንዘ ይብሉ ዝንቱሰ ይትዌከፍ ኃጥአነ ወይበልዕ ምስሌሆሙ። ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከአባቱ ያስታረቀን ለእኛ ቤዛ የሞተ ሌላ አለ አንልም። **ስግደት** የአክባሪና የተከባሪ የገገርና የተገገር ምልክት መሆኑ እርግጥ ነው። ለቅዱሳን መላእክት ኢያሱ የጸጋ ስግደት ሰግዷል።

ሃይማኖት፣ ምግባር፣ ቅዱሳት ሥዕላት፣ ማሸነፍ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ብቻዋን እንዳትጠቅም አውቃ በሃይማኖታችሁ ላይ ምግባር ትሩፋት ስሩ እያለች ታስተምራለች። ያዕ.2፣14-26። ገላ.5፣16-23 በፈቃደ ነፍስ ጸንታችሁ ኑሩ ፈቃደ ሥጋችሁን አትስሩ ይላል። ሥጋ ነፍስ የማትወደውን ይወዳል ነፍስ ሥጋ የማይወደውን ትወዳለች። ቅዱሳት ሥዕላትን እንድናከብር በዘጸ.37፣7 ባስልኤል የኪሩቤልን በቤተ መቅደስ እንደሳለ እንመለከታለን። እነዚህ ሥዕሎች ለሕያዋን ኪሩቤል መታሰቢያ ሊሆኑ በሕያዋን ኪሩቤል አምሳል የተሰሩ ናቸው። 1ኛ ነገ›6፣23 ላይም ተብራርቶ ይገኛል። ኪሩቤል በእኒህ ቅርጾች ወይም ሥዕሎች ላይ በረድኤት ከማደር በቀር ሰማያዊ ቦታቸውን ለቀው መጥተው በአካል የሚታዩ አይደለም። አቶ ዘመንፈስ ቅዱሳት ሥዕላትን አፍ ቦሙ ወኢይነቡ ብሎ ዘልፏቸዋል። የጣዖታቱን ዘለፋ ለቅዱሳት ሥዕላት ሰጥቶ መናገር ያሳፍራል። ንባብ ግእዛን የሌላቸው ፍጥረቶች ሁሉ በተአምራት እንዲነጋገሩ ብዙ መጻሕፍት ተናግረዋል። በጴጴንያ የእመቤታችን ሥዕል ትናገር ነበር ከፊቷም ወዝ ይወጣ ነበር ቢባል ውሸት አይሆንም የበለጓም አህያ የቢታንያ ድንጋዮች ተናግረዋልና። ስለጾምና ጸሎትም ማቴ.17፣21 ወዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት ተብሎ የተነገረለት ደገኛ ስራ ነው። ጌታ ከብዕል ከእውቀት ነዳያን ነን የሚሉ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ብሎ ትሕትናን። ዛሬ የሚያለቅሱ ሰዎች ንዑዳን ናቸው ብሎ ውኒዘ አንብዕን ለጽድቅ ብለው የሚራቡ የሚጦሙ ሰዎች ንዑዳን ናቸው ብሎ ጾምን። ለሰው የሚያዝኑ የሚራሩ ሰዎች ንዑዳን ናቸው ብሎ

ምጽዋትን ስለጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ንዑዳን ናቸው ብሎ ምናኔን አስተምሮናል። አምነው የሚሄዱበት መንገድ በጎ ምግባር ነው። የስምንቱ ትእዛዛት አበጋዛቸው አፍቅር ቢጸአ ነው። ሃይማኖትና ምግባር እንደነፍስና እንደ ሥጋ ተዋሕደው በአንድ ሰው ላይ ካልተገኙ ለየራሳቸው ከሆኑ የማይጠቅሙ ምውታን ናቸው። ሃይማኖት በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ በጆሮ ብቻ ሰምቶ ይህ ሊደረግ እንደምን ይቻላል ማለትን ትቶ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል ብሎ በሕሊና የሚታመን ረቂቅ ምሥጢር ነው። ጾም ትህርምት ዲያብሎስ ድል የሆነበት ነው። **ከዊነ ሰማእት** ማለት ጌታ በጲላጦስ ፊት እንዳደረገው በእውነት መመስከር ነው። ሳይፈሩ ሳያፍሩ ስለ እግዚአብሔር መመስከር ነው። ዮሐ.16፣32 በዓለም ዘንድ ግን ልዩ ልዩ መከራ ያገኛችኋልና እኔ ድል እንደነሳሁት እናንተም ጠንክራችሁ ድል ንሡ ይላል። ጌታ አምላኪየ አምላኪየ ለምንት ኀደገኒ የሚለውን እንደጸለየ እኔን ምሰሉ ስላለ እኛም እንጸልየዋለን። ጌታ የተናገረው በወንጌል የተጻፈው ሁሉ እውነት ነው። ሰይጣን እኒህን ድንጋዮች ዳቦ አድርግና እንብላ ብሎ ወደጌታ የስስት ጦሩን ወረወረ። ጌታም ሰው የሚድን እግዚአብሔር በተናገረው ቃል ነው እንጂ በጎብስት ብቻ አይደለም የሚል ጋሻ መክቶ የወረወረውን የስስት ጦር ሰበረበት። የትእቢት ጦርም የፍቅረ ንዋይ ጦርም ወረወረበት ጌታ ግን ሁሉንም ሰበረበት። በስስት ቢመጣበት በትህርምት በትእቢት ቢመጣበት በትሕትና በፍቅረ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊዐ ንዋይ ድል አደረገው። ድል ካደረገ በኋላ የሚያገለግሉት መላእክት መጡ ይላል። እናንተም ድል ብትነሱ መላእክት ይመጡላችኋል ሲል ነው።ጌታ ሲመጣ አንደኛው የሚጠይቀው ምግባርን ነው። ብራብ አብልታችሁኛል ብጠማ አተጥታችሁኛል ወዘተ እያለ ማለት ነው። ስለዚህ ምግባር አያስፈልግም እምነት ንቻ የሚሉት ተሳስተዋል። ደማዊት ነፍስና ነባቢት ነፍስ በፈቃድ የማይገናኙ የሚለያዩ ናቸው። ስለዚህ እርስ በእርሳቸው ይዋጋሉ። ደማዊት ነፍስ ብታሸንፍ ሰው እንስሳትን መስሎ ይኖራል። ሕግ እንዳልተሰራላቸው እንደ እንስሳት ጊዜ ሳይወስኑ መብላት መጠጣት መተኛት መነሳት በልዩ ልዩ ዓይነት ሥጋን ደስ የሚያሰኛትን ስራ ብቻ ሲሰሩ መኖር ነው። ነባቢት ነፍስ ያሸነፈች እንደሆነ መላእክትን መስሎ ይኖራል።1ኛ ቆሮ.15፣56-58 ወአይቴ መዎዖትከ ሲኦል ወለእግዚአብሔር አኮቴት ዘወሀበነ ንማዕ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። **አንብዓ ንሥሓ** ማለት ፊታቸውን ሳይከፉ ዕንባ እንደሰን ውሃ ሳያቋርጥ መፍሰስ ነው። ብላዕ በሐፈ ገጽከ የሚለው እርግማን ነው እንጂ ትእዛዝ ሕግ አይደለም። **ስግደት** የአክባሪና የተከባሪ የገገርና የተገገር ምልክት መሆኑ እርግጥ ነው። ለቅዱሳን መላእክት ኢያሱ የጸጋ ስግደት ሰግዷል። ቅዱሳት ሥዕላትን ጻድቁን እናስታውስባቸዋለን እንጂ ራሳቸው ጻድቁ ናቸው አንልም። ዘጸ.25፣21-22 በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ሆኜ እነግርሀለሁ ባለው መሰረት በታቦቱ አድሮ እግዚአብሔር ይሰማናል ብለን በታቦት በሥዕል ፊት ልመናችንን እናቀርባለን። እንጂ ራሱ ሥዕሉ ወይም ታቦቱ ይሰማናል ብለን የምንጸልይ አይደለንም።

ምንኩስና፣ ሕገ ሰብእ፣ ደመዎዝ፣ መላእክት

ጌታ ሐር ወሚጥ ኩሎ ዘብከ ወሀብ ለነዳያን ወነዓ ትልወኒ ብሏል። ብጹዓን እለ ይርህቡ ወይጸምዑ በእንተ ጽድቅም ይላል። ሰው ወኮነ ከመ እንስሳ የተባለ ቅርጹ ተለውጦ እንደ ከብት ቀንድ ጅራት ጋማ አወጣ ማለቱ አይደለም ግእዘ መላእክትን ጾምን ጸሎትን ትምህርትን ንጽሕናን ትተው ግዕዘ እንስሳትን ያዙ ሲል ነው። ምንኩስና ከአምላክ የተፈቀደ እግዚአብሔርን

በበለጠ አኳኋን ለማገልገል የታቀደ ሕገ ፍጹማን ነው። ምንኩስናን የሚነቅፍ መጽሐፍ ቅዱስ የለም። ጌታም ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ መኖርስ ለሁሉ አይቻልም ብሎ አለመቻሉን ተናገረ እንጂ አይገባም አላለም። 1ኛ ቆሮ.7፣29 ሚስት ያላገባ ሰው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኘው ገንዘብ ደስ ያሰኘው ዘንድ ደስ የሚያሰኝበትን ሥራ ያስባል። ካገባው ያላገባው የበለጠ የተሻለ ስራ ይሠራል ይላል። መልከጼዴቅ፣ ኤልያስ፣ ዮሐንስ መጥምቅ ንጹሓን ደናግላን ነበሩ። ብዙ ጸጋና ክብር እንዳገኙም ተጽፏል። ቆቡም የአክሊለ ሦክ ምሳሌ ነው ሌላ ነገር የለውም። ሰው የሩካቤን ተግባር እንስሳትን በሚመስልበት በደማዊት ነፍስ ፈቃድ ተሸንፎ የሚሰራው ነው። እንስሳዊ ግብር እንስሳዊ እውቀት ባላት በደማዊት ነፍስ እንስሳትን እንደመሰለ መልአካዊ ግብር መልአካዊ እውቀት ባላት በነባቢት ነፍስም መላእክትን መምሰል አለበት። እንስሳትን ከመምሰል መላእክትን መምሰል የበለጠ ተግባር ነው። ሩካቤን ያለ መምህር በአእምሮ ጠባይዕ የምታውቀው ነው። መዝ.39፣12 ፈላሲ አነ ውስተ ምድር ወነግድ ከመኩሉ አበውየ። መነኮሳትም ይሁኑ ካህናት አስተምረው አጥምቀው አቁርበው ደመወዝ መቀበል ኃጢአት አይደለም። ጌታ ራሱ በሉቃ.10፣7 ወውእተ ቤተ ንበሩ ወብልዑ ወስትዩ ዘእምኀቤሆሙ እስመ ይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ ብሏል። ምንኩስና ማለት አንድ ሰው ማንም ሳያስገድደው በራሱ ፈቃድ ብቻ ራሱን እንደ ብጽአት ገንዘብ ወይም እንደተቀደሰ መሥዋእት አድርጎ ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። ወንድማችንን የማንነቅፍበትን ግብር እንያዝ። **ደቂቀ ሴትን** መላእክት ያላቸው አለቆች ሲል ነው። ራዕ.ዮሐ.2፣1 ወጸሐፍ ሎቱ ለመልአከ ቤተክርስቲያን ዘኤፌሶን እንዲል። አንድም ንጹሓን ሲላቸው ነው። ማቴ.22፣30 እመሰ የሐይው ምውታን ኢያወስቡ ወኢይትዋሰቡ አላ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር ይከውኑ በሰማያት እንዲል። ደቂቀ ሴት ደግሞ ደቂቀ ቃየልን ያገቡ ስለሆነ መላእክት አለመሆናቸውን ያስረዳል። ፍትወት እንስሳዊ ለመላእክት ባሕርይ ተስማሚ አይደለም።ስለደቂቀ ሴት ሄኖክ ብቻ አይደለም የጻፈ ሙሴም ዘፍ.6፣1-4 ላይ ጽፏል። ስለ አጭርነታቸውና ስለረኻርምነታቸውም በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጎልያድን 6 ክንድ ከስንዝር ስለሚለው አዲስ ነገር አይደለም። ጎልያድ ስለረዘመ የሰው ዘር አይደለም አንልም። 1ኛ ሳሙ.17፣4።

በዓል፣ ታቦት

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከሰንበት ጋራ የቅዱሳንን በዓል ምክንያት በማድረግ ከቤተ እግዚአብሔር ሂዳችሁ እጅ ንሱ ቤት ለቤት አትልከስከሱ እያለች ታስተምራለች። 2ኛ ቆሮ.6፣16 ወመኑ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ ጣዖት ስለሚል ቤተክርስቲያን በጣዖትና በታቦት መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቃ ታውቃለች። በዓላትን እንድናከብርም በኦሪት በብዙ ቦታ ተጽፏል።የእግዚአብሔር ስም በተጻፈበት ታቦት ፊት ለእግዚአብሔር እንሰግዳለን እንጂ በእጃችን የቀረጽነው እንጨት አምላክ ነው ብለን አናምንም። ጽላቶች ቢሰበሩ ራስህ ጽላት ስራና እኔ ስሜን እጽፍባአዋለሁ ብሎ ጌታ ጽፎለታል። ለእግዚአብሔር ስም መስገድ የሚገባ መሆኑንንም ቅዱስ ጳውሎስ ፊልጵ.2፣9-10 ፍጥረት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሰግድ ዘንድ ከስም ሁሉ የበለጠ ስም ሰጠው ይላል። በታቦቱ ላይ ለእግዚአብሔር እንሰግዳለን እንጂ ታቦቱን አምላክ ነው ብለን አናመልከውም። ዘጸ.25፣21-22 በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ሆኜ እነግርሀለሁ ባለው መሰረት በታቦቱ አድሮ እግዚአብሔር ይሰማናል ብለን በታቦት

በሥዕል ፊት ልመናችንን እናቀርባለን፡፡ እንጂ ራሱ ሥዕሉ ወይም ታቦቱ ይሰማናል ብለን የምንጸልይ አይደለንም፡፡ (ስለዚህ ታቦት ሊሰበር ሊዘረፍ ይችላል፡፡ ይህን ጊዜ በታቦቱ አድሮ የሚሰማን እግዚአብሔር ምን ብንበድለው ነው ይህን ያደረገብን ብሎ ንሥሓ መግባት ነው የሚያዋጣው፡፡ በታቦት የሚያድር እኛን ለመርዳት ነውና፡፡ የማንረዳ ሆነን ስንገኝ በታቦቱ አድሮ ረድኤት ላያደርግልን ይችላልና)፡፡ በሚካኤል በጊዮርጊስ ወዘተ ስም ታቦት የምንሰይመውም ኢሳ.56፣3-6 ለጃንደረቦች ሰንበቴን ለሚጠብቁ እኔ የመረጥሁትንም ለሚመርጡ ሥርዓቴንም ለሚይዙ በቤቴ በቅጽሬ ስፍራ ስም እሰጣቸዋለሁ ስላለ ነው፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት

ማር.16፣20 ወእመኒ አእመርናሁ ለክርስቶስ በሥጋ እምይእዜሰ አልቦ ዘነአምሮ እንከ ይላል፡፡ 2ኛ ቆሮ.5፣16 ወገብአ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ ዘቀዳሚ ከተባለ ወዲህ ሳይሆን ከጽንስ እስከ ዕርገት በሠራቸው ስራዎች ብቻ የተፈጸመ እንጂ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ከዕርገትም በኋላ ከመማለድ በቀር አማላጅነት የለበትም የባሕርይ አምላክ ነውና፡፡ (ከሞት በኋላስ ጻድቃንም በማማለድ ድካም የለባቸውም ግን ያሳስባሉ፡፡ እርሱ ግን ከዕርገት በኋላ ራሱ ፈራጅ ስለሆነ ለማንም አያሳስብም)፡፡ ራዕ.ዮሐ.22፣12 እነሆ ፈጥኜ እመጣለሁ ለሁሉ ለእያንዳንዱ እንደስራው እሰጠው ዘንድ ዋጋዬም ከእኔ ጋራ ነው በማለቱ ጌታ ፈራጅ እንጂ አማላጅ እንዳልሆነ አስረድቶናል፡፡ አማላጅማ ቢሆን አሰጠው ዘንድ ነበረ የሚል፡፡ ለእኛስ አማላጆቻችን በራሳቸው መብትና ሥልጣን ለማንም ዋጋ ሊከፍሉ የማይቻላቸው ለማማለድ የሚያበቃ የባለሟልነት ሥልጣን ያላቸው ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማእታት ናቸው፡፡ ክርስቶስ ግን የአስታራቂነት ተግባር በመልእልተ መስቀል ከፈጸመ በኋላ አማላጅ ስንለው አንኖርም፡፡ (በወንጌል አብ ፍርድን ሰጠው ከሁሉ በላይ አደረገው ከመላእክት በላይ ያለ ስም ሰጠው ወዘተ የመሳሰሉት የሚለው ለሥጋ እንግድነት ነው፡፡ ይህም ሰጠው የተባለ በሥልጣናዊ ግብር ነው ማለትም ለአብ አድሎ ተናገረ እንጂ ሰጠው የተባለ እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ የሦስቱም መጠሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ወራዳ የነበረው ሥጋን ከፍ ማድረጉን ተዋሕዶ አምላክ እንዳደረገው የሚያስረዳ ድንቅ ምሥጢር ነው፡፡ ሥጋ ከተዋሕዶ በፊት ደካማ ነበርና አምላክ ሲዋሐደው ግን ሁሉን የሚገዛ ስለሆነ ተሰጠው ከፍ ያለ ስምን አገኘ ወዘተ ቢባል አይገርምም ድንቅ ነው ይገባልም)፡፡ 1ኛ ዮሐ.5፣14 በእርሱ ስም ወደ እርሱ ያቀረብነውን ልመና ይሰማናል ይላል ዮሐንስ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂነትና በቅዱሳን አማላጅነት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ዮሐ.14፣14 ወእመቦ ዘሰአልክሙ በስምየ እገብር ለክሙ ኪያሁ፡፡ ግብ.ሐዋ.7፣8 እግዚኢ ስረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ ወኢትረሲ ጌጋየ ብሎ እስጢፋኖስ አማልዷል፡፡ ጌታ በዐጸደ ሥጋ ሳለ በጸለየው ጸሎት ያስታረቀ በዐጸደ ሥጋ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በዐጸደ ነፍስ ያሉትንም እንዳስታረቀ የማይካድ ነው፡፡ ሐዋርያት ነፍስን ከዓለመ ነፍስ አምጥተው ከሥጋ ጋራ አዋሕደው ካስነሱ በዐጸደ ሥጋ ሆነው በዐጸደ ነፍስ ላሉት ማማለድ እንደተቻላቸው ዕወቅ፡፡ ክርስቶስ በገዛ ራሱ ታራቂና አስታራቂ አማላጅም ሆኖ ዕዳችንን በመስቀሉ ከፈለው፡፡ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ተጋርዶ የነበረው የጥል ግድግዳ በክርስቶስ መስቀል ከፈራረሰ ወዲህ ጻድቃን እያማለዱ ድኅነትን ያሰጣሉ፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከአባቱ ያስታረቀን ለእኛ ቤዛ

የሞተ ሌላ አለ አንልም። ለቤዛ ዓለም የሞተ ኢየሱስ ብቻ ነው። ጌታ እንደሰውነቱ ሊቀካህናት ተባለ። አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሚመቱ ለመልከጼዴቅ ተባለ።

ምሥጢረ ሥላሴ

በምሥጢረ ሥላሴ የአካላት ሦስትነትና የኩነታት ሦስትነት አንድ አይደለም። አካላት መጠቅለልና መቀላቀል ሳይኖርባቸው በተከፍሎ በተፈልጦ በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክዕ በየራሳቸው የቆሙ ሲሆኑ ኩነታት ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ በተጋብኦ በአንድነት አካላትን በህልውና እያገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩ ያሉ የሚኖሩ ናቸው። የነፍስን የአካሏን አንድነት ለሥላሴ ባሕርይና የባሕርይዋን ከዊን ለሥላሴ አካል ሰጥቶ ቢመረምሩት በነፍስ በባሕርይዋ ያለ ሦስት ከዊን አካሏን ከሦስት እንዳይከፍለው በሥላሴ ባሕርይ ያለ ሦስት ከዊንም ባሕርየ ሥላሴን መለኮተ ሥላሴን ከሦስት አይከፍለውም።

ምሥጢረ ሥጋዌ

በምስጢረ ሥጋዌ መለኮት ሰው ሆነ ስንል አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው አልሆኑም በማለታችን መለኮት በተከፍሎ ሰው ሆነ የምንል አይደለንም። ፍጹም መለኮት ሰው ሆነ እንላለን እንጂ በከፊል ሰው ሆነ አንልም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት አንድ ናቸው ካላችሁ በኋላ ፍጹም መለኮት ሰው ሆነ ብላችሁ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው አልሆኑም ካላችሁ አብ መንፈስ ቅዱስ ከመለኮትነት በአፍኣ ናቸው ወይም መለኮት እንደ አካላት ከሦስት ይከፈላል የሚል ጥያቄ ቢመጣ መጀመሪያ ፍጹም መለኮት ሰው እንደሆነ የሚያስረዳ ቆላ.2፣9 ክርስቶስ ዘላዕሌሁ ኀደረ ኩሉ መለኮቱ በሥጋ ሰብእ የሚለው ነው።ነፍስ በአካሏ አንድ ስትሆን በከዊን ሦስት ስትሆን በተለየ በቃልነቷ ከዊን ብቻ ከሥጋ ምላስ ጋር ተዋሕዳ ንባብን በሰጠች ጊዜ አካሏ ከሦስት እንዳይከፈል መለኮትም ከሦስት የሚከፈል አይደለም። የልብነቷና የእስትንፋስነቷ ከዊን ነፍስ ከመባል ከነፍስነት በአፍኣ ናቸው አይባሉም። አብና መንፈስ ቅዱስም ከመለኮትነት በአፍአ አይደሉም። ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ብለን እናምናለን። ዓለም ሁሉ በሰዋው መሥዋእት በጸለየው ጸሎት መዳን እንደተሳነው በሁሉ ዘንድ ከተረዳ በኋላ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ተወለደ።

ምሥጢረ ጥምቀት፣ ድኅነት

አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ከሥላሴ የጸጋ ልደት ተወልዶ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ነበረ። ሲሳሳት ልጅነቱን አስወሰደ። ጌታ ሰው የሆነበት ምሥጢሩ ያንን የሄደብንን ልጅነት ሊያስመልስልን ነው። ስለዚህ ያንን ልደት ለማግኘት ምክንያት የሚሆነንን ማየ ዮርዳኖስን ለመቀደስና ለመባረክ በዮርዳኖስ ተጠመቀ። ለኒቆዲሞስ ዳግመኛ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም አለው። በጥምቀት የምናገኘው ረቂቅ ልደት ነው። ጌታ ከመንፈስና ከውሃ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያትን አያያትም ስላለ 30 ዓመት ሳይሞላው የሚሞተውም ብዙ ስለሆነ በዚህ አያያዝ እንደ መናፍቃን ጥምቀት በ30 ዘመን ከሆነ ያልተጠመቀም የማይድን ከሆነ ጌታ በሞቱ ያዳነ ከ30 ዘመን በላይ የሞቱትን ብቻ ነው ስለሚያሰኝ ስህተት ነው። ጌታ

ግን ለደቀመዛሙርቱ እንደዚህ ሕጻን ካልሆናችሁ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም ብሏቸዋል። ሕጻናትን አትከልክሏቸው ወደእኔ ይምጡ ብሏል። ሕዝ.36፣25 ወእነግዘሐክመ በማይ ንጹሕ ከመ ትንጽሑ እም ርኩስክመ ወዘተ የሚሉት ቃላት በብሉይ ለነበሩ ሰዎች ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ይኖር ነበር። በሐዲስ ዘኪተወልደ እማይ ብሎ አጉልቶታል። አዳም ፈጣሪው የሰጠው የጸጋ ገጠርነት አንሶት የባሕርይ አምላክ መሆንን ተመኝቶ ዕጸ በለስን በመብላቱ ልጅነትን አጣ። ከዚህ በኋላ አዳም ባደረገው ስህተት ተጸጽቶ ንሥሓ ገባ ከዚያ በኋላ እርሱም ልጆቹም መሥዋእት ቢያቀርቡም መሥዋእታቸው ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ ሊያወጣቸው አልቻለም። ዘመኑም **ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ** ተባለ። በዚያ ጊዜ አኮ በተንባል ወኢ በመልአክ አላ ለሊሁ እግዚእ ይመጽእ ወያድኅነነ አሉ። ዓለም ሁሉ በሰዋው መሥዋእት በጸለየው ጸሎት መዳን እንደተሳነው በሁሉ ዘንድ ከተረዳ በኋላ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ተወለደ። የአዳምን ሕይወት ለማዳን የቻለው መለኮታዊ ሕይወት ያለው በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ሌላ ተጨማሪ አለው ብለን አናምንም።

ምሥጢረ ትንሣኤ

እግዚአብሔር ሰውን እንደ መላእክት ሕያው ሆኖ እየኖረ ስሙን ሊቀድስ ክብሩን ሊወርስ ፈጥሮታል። ሞት ግን ሰው በፈቃዱ ያመጣው እዳ ነው። ከዚህ አስቀድሞ ከእመቤታችን በቀር የጌታን ትንሳኤ የመሰለ ፍጹም ትንሳኤ የተነሳ የለም። እነ አልአዛርን ቢያስነሳቸው ረኃብ ጽምዕ በሚስማማው ሕማም ሞት በሚከተለው በብሉይ በግዙፍ ሥጋ ነው። ስለዚህ ለጊዜው ቢነሱ ወዲያው ከጥቂት ጊዜ በኋላ እየተመለሱ ሞተዋል። መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን እንዲታመም እንዲሞት አልፈጠረውም። ጌታ በዳግም ምጽአቱ ሰውን በወርድ በቁመት ሳያበላልጥ አስተካክሎ ያስነሳዋል። በሐዲስ ሥጋ ይነሳል ማለት ያ ሥጋ እውነት ሐሰት ጽድቅ ኃጢአት የማይፈራረቁበት ረኃብ ጽምዕ የማይስማማው ነው ማለት ነው። ከዚያ ከመላእክት ጋራ አንድ ማኅበር ሆኖ እግዚአብሔርን እያዩ ሲደሰቱ መኖር ነው። ከትንሳኤ አስቀድሞ ያለው ዘመን በዓለመ ሥጋም ቢሆን በዓለመ ነፍስም ቢሆን የስራ ዘመን ነው እንጂ የእረፍት ጊዜ አይደለም። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፣14 መላእክት ሁሉ ረቂቃን ሲሆኑ የዘላለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለተልእኮ ይላካሉ ብሎ ነግሮናል።

መጽሐፈ ቅኔ-ዝክረ ሊቃውንት

አዘጋጅ፡- መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ዲማ ጊዮርጊስ በ1885 ዓ.ም ተወለዱ። ያለው ይሏቸው ነበር አባታቸው ግን አድማሱ ይሏቸው ነበር። ከፊደል እስከ መዝሙረ ዳዊት ከአባ ወንድሙ ተማሩ። ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥእት ቅኔ ከአጎታቸው ከሊቀጠበብት ክንፉ ተማሩ። ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስና ከመምህር እንግዳሸት ቅኔና መጻሕፍት ተማሩ። ከመምህር አካለ ወልድ ሐዲሳትና ሊቃውንትን ተማሩ። ትእግስተኛ ትሑትና ብቁ ባለሙያ ነበሩ። የበገና መዝሙር የሚል መጽሐፍ ጽፈው ለራስ ሀብተ ማርያም ሰጥተዋቸዋል። ዲማ የቅኔ አስተማሪም ሆኑ። ከዚያ ታዕካ ነገሥት መጥተው መጋቤ ምስጢር

ተባሉ፡፡ ይህን ጊዜ ከተሾዋሚው ይልቅ እርሳቸውን ያገኘ ሹመቱ እድለኛ ነው ተባለ፡፡ አስተዋይ ስራ ወዳድ ተመራማሪ ነበሩ፡፡ በ1927 ዓ.ም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ የቢቸና ጊዮርጊስ ሊቀጠበብት ሆኑ፡፡ በ1933 ራቅ ወርቅ አስረው ቢቸና ጊዮርጊስ መልአከ ብርሃን ተብለው ተሾሙ፡፡ በ1936 ዓ.ም ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መብት በተደረገው ክርክር ከጎጃም ከተመረጡት ሊቃውንት አንዱ ነበሩ፡፡ በመንፈሳዊ አስተዳደር ገዢና ተገዢ ወይም ለአንዱ የሚሰጥ ለሌላው የሚነፈግ መሆን የለበትም የሚል ሀሳብ አቅርበው ለጊዜው በዚህ ሀሳባቸው ምክንያት ተቃውሞ ቢገጥማቸውም የሐሳቡ ጠቃሚነት በብዙዎች ስለተደገፈ ኢትዮጵያ የራሷን ፓትርያርክ እንድትሾም ሆናለች፡፡ በቤተክርስቲያኒቱ የታሪክና ድርሰት ክፍል የሊቃውንት ጉባኤ ፕሬዜዳንት በመሆን አገልግለዋል፡፡ ማንኛውንም ዓይነት መጽሐፍ ማንበብ መመራመርና ተጠይቆ ማስረዳትን የሚወዱ ነበሩ፡፡ በ1949 ዓ.ም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ተሾሙ፡፡ በ1959 ከፍርድ ሚኒስቴር በጡረታ ወጡ፡፡ የታሪክና ልብ ወለድ መጽሐፎችን ሳይቀር ያነቡ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ሬድዮ በዓቢይ ጾም በተከታታይ “ሐዲስ ሰውነት” በሚል ርእስ አስተምረዋል፡፡ መጻሕፍትን ዝም ብሎ ከመቀበል ይልቅ አስቀድሞ መመራመርን ይወዱ ነበር፡፡ ከመጻሕፍት ውስጥ አልፎ አልፎ ያልተብራሩና ትርጉም ያልተሰጣቸው አነጋገሮች ሲያጋጥሙ የራሳቸውን ትርጉም ይሰጡ ስለነበር ታላቁ ሊቅ አለቃ ጎሩይ ፈንታ መልአከ ብርሃን እንደተረጎመው እያሉ ያስተምሩ ነበረ፡፡ ሐምሌ 24 በ1962 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ከአባቶቻችን የቆየ ከሆነ አንነካውም እያልን የምናውቀውን ስህተት ተሸክመን ልንኖር አይገባንም፡፡ ጸሐፍቱ በስህተት የጻፉትን ጠንቅቀው ያወቁ ሊቃውንት ሊያርሙት ይገባል፡፡ የ ሐመሩ “ሐ” የሀሌታው “ሀ” የብዙኃኑ “ኀ” የእሳቱ “ሰ” የንጉሡ “ሠ” የጸሎተ “ጸ” የፀሐዩ “ፀ” ጉዳይ ሲታይ መጻሕፍትም ሊቃውንትም ተለያይተውባቸዋል፡፡ ሆኖም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ሰፋ ያለ ጉባኤ አድርገው እንዲነጋገሩበት በዚህ ጽሑፍ አሳስባለሁ፡፡ እኔ ግን የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን መጽሐፍ ተጠቅሜአለሁ እርሱ ይጠነቅቃልና፡፡ የሊቃውንቱን ታሪክ ስለጻፉ ከሸዋ ክቡር ብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደ ሥላሴን ከጎጃም ክቡር መልአከ ፀሐይ ተገኘን ሳስታውስ ደስ ይለኛል፡፡ ብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን ምክር ይጠይቋቸው ነበር፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ዲማ ቅኔ ሲያስተምሩ ሊቀጠበብት ነበር የሚባሉት፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ጥሩ የሰራን ያመሰግናሉ ያደንቃሉ፡፡ ሰው ለፍቶ ከስኬት ባለመድረሱም ከልብ ያዝኑ ነበር፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ የዋሉትን ያደንቃሉ ይወዷቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ተወዳጅ ባህል አላት ይህን ባህል ከአዲሱ ሥልጣኔ ጋር ማዋሐድ መልካም ነው ይላሉ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፡፡

ቅኔ፣ ጉት

ቅኔ ማለት ቀነየ ገዛ ካለው ግሥ የተገኘ ጥሬ ዘር ነው፡፡ ወይም ቀነየ ገዛ የሚለውን አንቀጽ ያስገኘ ጥሬ ዘር ነው፡፡ ፍችውም መገዛት ማለት ነው፡፡ ፍጡር አዲስ ምስጋና እየደረሰ በማቅረብ ለፈጣሪው መገዛቱን የሚገልጥበት ስለሆነ ነው፡፡ ለፍጡራን የሚደረሰውም ቅኔ ቅኔው የሚደረስለት ፍጡር ከቅኔ ደራሲው በላይ ክብር ያለው መሆኑን የሚገልጽ ድርሰት ስለሆነ መገዛትን ከማመልከት የራቀ አይደለም፡፡ አንድም ሕዋሳተ አፍኣን ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና

አስገዝቶ በተወሰነ ቁርጥ ሀሳብ የሚታሰብ ስለሆነ ቅኔ ተብሏል። ይኸውም ሊታወቅ በቅኔ ምሥጢር ልቡ የተካ ሰው ቅኔ በሚያስብበት ጊዜ በፊቱ የሚደረገውን ነገር እያየ አያይም እየሰማ አይሰማም።አንድም ቅኔ ማለት ተቀንየ ምሾ አወጣ፣ ግጥም ገጠመ፣ አራቆ ተናገረ፣ አዜመ አንጎራጎረ፣ መራ ዘፈነ ካለው የወጣ ጥሬ ዘር ነው። ስለዚህ ቅኔ ማለት በአጭሩ ጠቅላላ ትርጉሙ ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ላቅርብ ባለ ጊዜ ምሳሌ መስሎ ምሥጢር አሻሽሎ ግጥም በመግጠም የሚቀርብ ነው። መጋቢ መርሻ የሚባሉ የዲማው ባለቅኔ የሰውን የእውቀቱን መጠን የማውቀው በቅኔው ነው ይሉ ነበር። ግብሩን ሳይሆን ስሙን ብቻ አስጠግቶ ቅኔን ያሬድ ጀመረው ማለት አጥጋቢ ታሪክ ሆኖ አይገኝም። ከዚህስ ይልቅ ዋዜማ ሚበዝኑ መወድስ ኩልክሙ መባልን ስሙን ከያሬድ ይትበሀል ወስዶታል ቢባል አጥጋቢ ሳይሆን አይቀርም። እንግዲያ ማን ጀምሮታል ቢሉ ዮሐንስ ዘገብሎን የተባለ የዋድላ ተወላጅ ነው የሚሉ አሉ። ተዋነይ ወይም ደቀ እስጢፋ የተባለ የጎጃም ተወላጅ ነው የሚሉም አሉ። ዋድሎች በ1460 ዓ.ም አካባቢ ሱባኤ ገብቶ ለዮሐንስ ተገለጸለት ይላሉ። ቅኔ በኢትዮጵያ እንጂ በሌሎች ሀገሮች አይገኝም። አቶ አለማየሁ ሞገስም ቅኔ የሕሊና ሐሴት የአእምሮ ትፍሥሕት የድካም መድኃኒት የጎዘን ማስረሻ የፍልስፍና ማጎልመሻ ሊሆን ከእግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሰጠ ሀብት ነው ይላሉ። ተዋነይ ጽርዕ ወርዶ ከግዕዝ አገባብ ጋር አስማምቶ የጎደለውን ሞልቶ ለአጼ እስክንድርና ለሌሎችም አስተማረ። ከነቢያት መጻሕፍትና በየጊዜው ከተጻፉ መጻሕፍት አገባቡን ዐቢይ ደቂቅ ንዑስ ብሎ መድቦታል። የቅኔውን መንገድም ድርቡን ፍላጻውን ሠረዙን ወዘተ መድቦታል። ከቅዱሳት መጻሕፍት ከብሉያት ከሐዲሳት አግኝቶ ተናግሮታል ይላሉ። ቅኔ ለድርሰት መልመጃ ለቅዱሳት መጻሕፍት መክፈቻ ለመንፈስ ማደሻ ለአእምሮ ማጎልመሻ ሊሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ሕግ ተዘጋጅቷል። ውስጡን ሳይነካ ላይ ላዩን ጋልቦ አልፎ ቅኔ አውቃለሁ ማለት አይቻልም። መጽሐፍ ሲማሩ በራሳቸው አስቀድመው ተርጉመው የሚሄዱ የቅኔ መምህራን ነበሩ። የድርሰት ያልነው ዐርኬ መልካ መልክ ገድል በቅኔ አዋቂዎች እንደተደረሱ የማይካድ ነው። ዘወትር እንግዳ ድርሰት የሚያመነጭ አእምሮም እየጎለመሰ እየታደሰ መሄዱ የማያጠራጥር ነው። በየቀኑ እንግዳ ድርሰት እየደረሱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ በብሉይ በሐዲስ የታዘዘ ነው እንጂ ልብ ወለድ ነገር አይደለም። በብሉይ ቅዱስ ዳዊት ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ ይላል። በሐዲስም 1ኛ ቆሮ.14፣26፤ኤፌ.5፣18 ወይእዜኒ ሶበ ትትጋብኡ ኩልክሙ ብክሙ መዝሙር ወብክሙ ትምህርት ዘከሠተ አበይኖ ዘነገረ በሐውርት ወዘምድራሳት ወኩሎ በዘትትገነዩ ግበሩ ለበቁኤት ብሏል። ቅዱስ ጳውሎስ በተሰበሰባችሁ ጊዜ በማለት ያስታወሰው ይህ ስብሰባ ለስብሀተ ነግህ ለማሕሌት ለዋዜማ ለመወድስ በየጊዜው ከቤተክርስቲያን የምንሰባሰበው ስብሰባ ነው። መዝሙር አለላችሁ ያለውም ምዕራፍ በተባለው ክፍል ቅዱስ ያሬድ በዜማ ያዘጋጃቸው መዝሙራተ ዳዊት ናቸው። በሀገር ቋንቋ ተለይቶ የተገለጸ ትምህርት አለላችሁ የሚለውም ለዘመኑ ተስማሚ የሆነው ኃይለ ቃል በይትበሀል ተለይቶ ተለይቶ በምእራፍ መዝሙሮች ጣልቃ እየገባ የሚዘመረው የድጓ ትምህርት ነው። ወዘምድራሳት የሚለውም ዕለት ዕለት አዲስ ድርሰት እየሆነ ከያሬድ ድጓ ጋር ተጣምሮ የሚዘመረውን ቅኔ ነው ብንል የሚያኮራን ነው እንጂ የሚያሳፍረን አይደለም። ወኩሎ በዘትትሐነጹ ግበሩ ይላልና በቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የቅኔ ድርሰት ሁሉ ጸሎትነትን ወይም ምዕዳንነትን ወይም ምክርነት

ያለው ሆኖ እግዚአብሔርንም ሰውንም ደስ የሚያሰኝ ሊሆን ይገባዋል እንጂ የማይረባ የማይጠቅም ዋዛ ፈዛዛ ወይም ሰውን የሚያሳዝን ሽሙጥ ስድብ ያለበት ሊሆን አይገባም። ከምድራዊ ንጉሥ ፊት የማይገባ ነገር የተናገረ ሰው ቅጣት የሚፈረድበት መሆኑን ስለምናውቅ በእግዚአብሔር ፊት የማይገባ ነገር ተናግረን እንዳይፈረድብን እንጠንቀቅ። ጉት ቤት የማይመታ ቅኔ ነው። በቅኔ ሊቃውንቱ በኃጢአት የተጎሳቆለ ሰውነታቸውን ሲወቅሱ ምረረ ገሀነምን ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ሲያስታውሱ ሃይማኖታቸውን ሲመሰክሩ ዕበያተ እግዚአብሔርን ሲናገሩ የኖሩ ናቸው። ቅኔ ወደ ማወቅ መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። (ቅኔ ላይ ከፈለግህ ዓይኖችህን እንደ ባለጸጎች ታደርጋቸዋለህ ስትፈልግ አንዱን ሰው ዓለም ትለዋለህ። ስትፈልግ ሕማማትን አእርክቲሁ አግብርቲሁ ነገሥታት ትላቸዋለህ። ከፈለግህ ሰዎችን ሕማማት ትላቸዋለህ። ቅኔ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ታሪኮች ሁሉ ለሰምነት ሊቃውንት አውለዋቸዋል። በቅኔ ግእዛን የሌላቸውን እንዳላቸው ያላቸውን እንደሌላቸው አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ነው። ሌላው ሁኔታዎችንም ግእዛን እንዳላቸው አስመስሎ ወይም ግእዛን ያላቸውን እንደ ሁኔታ አስመስሎ ይነገራል። ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስን ወይም የአዋልድ መጻሕፍትን ኃይለ ቃል ሰም አድርጎ ወርቁ ግዕዛን ያለውም ይሁን የሌለው ይደረጋል። ለምሳሌ አልአዛር ምሥጢረ ቅኔ ብሎ የሚጀምር ቅኔ አለ። ቅኔ በሁኔታዎች በድርጊቶች በአድራጊዎች በተደራጊዎች በአደራራጊዎች በተደራራጊዎች በአስደራጊዎች የሚከሰቱ ክስተቶች ስሜቶች ንግግሮች የአካል እንቅስቃሴ የተፈጥሮ ወይም የፍጥረታት የእርስ በእርስ ግኑኝነት ላይ አትኩረህ ወርቁን አስገብተህ የምታደርገው ነው። ስለዚህ ማንኛውንም ንግግር የአካል እንቅስቃሴ ስሜት ክስተት ንግግር የተንኮል ሀሳብ ሰው ሲደሰት ሲያዝን ሲያገኝ ሲያጣ የሚላቸውን የሚያስባቸውን ልማዳዊ ነገሮች ከሰዎች ከሌሎችም አጠቃላይ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች በግኑኝነቱ ጊዜ የሚሆኑ ክስተቶች ሀሳቦች በሙሉ ወርቅ አስገብተን ቅኔ ማድረግ እንችላለን። ዋናው ወርቁን ከእነዚህ ነገሮች ጋር እንዴት ማዋሐድ እንዳለብህ ማሰቡ ነው። አጠቃላይ የፈጣሪና የፍጥረታት ክንውን ሁኔታ ወዘተ ቅኔ ይሆናል። አንብዕ ወደም አሕዛበ ምድር ብሎ የሚጀምር ቅኔ አለ። ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስነ ቃሎች ወዘተ ምርጥ ቅኔ ይሆናሉ። ትችቶች ለሕጻናት የሚባሉት እነ ዳዴ ስንቆጣ የምንላቸው ነገሮች ሁሉ ቅኔ ይሆናሉ። ሌላው ቅኔ ላይ ምርምር ዋና ነው መጻሕፍትን መመርመር ሁነቶችን መመርመር ይገባል። ኀልቀ ፍሬሁ ለያዕቆብ ሰግላ የሚል ቅኔ አለ። በቅኔ ከፈለገ ሐዘንን ገበሬ ይለዋል ከፈለገ እርሻ ይለዋል። በቅኔ ግዙፉን ማርቀቅ ረቂቁን ማግዘፍ ይቻላል። ረቂቁን ከግዙፉ ግዙፉን ከረቂቁ መመሰልም ይቻላል ምሳሌ አብርሃም ደመና ማለት ትችላለህ ወይም አብርሃም ትህትና ማለት ትችላለህ። እግዚአብሔር ጾም አምላክ ባሕታዊ ባዕለ ጸጋ ያነዲ ወነዳየ ያብእል የሚል ቅኔ አለ። በእግረ መንፈስ ንባዕ ሀገረ ንሥሓ የሚል ቅኔም አለ። ሌላው መራቀቅ አለ ለምሳሌ እግርህን ቅቤ መቀባት ለዓይን ለጆሮ መድኃኒት አይሆንም ብለህ ሰም አድርገህ ወርቅ መፍጠር ትችላለህ። ረቂቅን ከረቂቅ ግዙፉን ከግዙፍ መስሎም ቅኔ ይደረጋል። ሕይወት ያለውን ካለው ከሌለው ጋር። ሕይወት የሌለውንም ከሌለው ካለው ጋር መስሎ ቅኔ ማድረግ ይቻላል። በቅኔ የሚገርመው ኃጥዐ ጻድቅ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ደዌ ካህን ሆኖ ኢዮብን አቆረብኩት ሊል ይችላል። ለቅኔ ገደብ የለውም። ማንኛውንም ወርቅ በማንኛውም ነገር መመሰል ይቻላል ምሳሌ ምትረትን በጊዜያት ማለትም ምሳሌ ምትረት እሑድ ብለህ ወይም በሁኔታ ምትረት አለመስማማት ብለህ ወይም በድርጊት

ምትረት መብላት ብለህ መመሰል ትችላለህ። አብርሃምን ከመታሰር ጋር የመሰለ ሊቅ አለ። ተመየጢ ተመየጢ መንግሥተ ምኒልክ ሱላማጢስ የሚል ቅኔም አለ። ዳዊት ልቡናየ ዘመረከ በመሰንቆ የሚል ቅኔም አለ። የሀገሩን የአለባበስ የአነጋገር የቋንቋ ባህልና ልማድ ንግግር ሰም ማድረግ ትችላለህ)። ጎንጅና ዋሽራ ዋና የቅኔ ማዕከሎች ናቸው።

የቅኔ መንገድ፣ ሰምና ወርቅ

ምንም ሰምና ወርቁ እንደ ቅኔው ተጣምሮ ባይገኝ በመጠኑ ለማስረዳት እንሞክራለን። **1ኛ ሰምና ወርቅ መንገድ**። መሳ.9፣7-21 እንጨቶች ተሰብስበው ሔደው ዘይትን እናንግስሽ አሏት ወዘተ የሚለው ነው። ይህ ሰሙ ነው ወርቁን ዝቅ ብሎ ገልጾታል። ጌታም እየመሰለ አስተምሯል ማቴ.13፣1-58፤2ኛ ዜና መዋ.25፣17 ይህ አነጋገር እንደ ቅኔው መንገድ ሰምና ወርቁ በንባብ ተጣምሮ ሰሙን በመሰለ በአንድ ማሰሪያ ታሥሮ ባይገኝም ንግግሩ ሰምና ወርቅ መሆኑን እንገንዘብ። ፍጹም ሰምና ወርቅ የሆነ ንባብም አለ። መዝ.79፣5 ወትሴስየነ እክለ አንብዕነ ይላል። መዝ.126፣2 ትሴሰዩ እክለ ሕማምየ ይላል። ተዋነይም ከኦሪት ከነገሥት የጠቀስነውን የምሳሌ መንገድ በዚህ ዓይነት አሻሽሎ የቅኔን ሰምና ወርቅ መንገድ ወስኗል ቢባል የማያሳፍር ትክክለኛ መልስ ሆኖ እናገኘዋለን። **2ኛ አንጻር መንገድ** ሮሜ 5፣21 ወበከመ አንገሠቶ ኃጢአት ለሞት ከማሁ ጸጋሰ ለእግዚአብሔር ይላል። **3ኛ ውስጠ ወይራ መንገድ** መዝ.49፣19 ወይወርድ ውስተ ዓለመ አበዊሁ ፍኖው ወደ አባቶቹ መቃብር ይወርዳል ይላል። **4ኛ ሠረዝ መንገድ** እብለክሙ በመንፈስ ሑሩ ወፍትወተ ሥጋክሙ ኢትግበሩ እስመ ሥጋኒ ይፈቱ ዘኢይፈቱ መንፈስ ወመንፈስ ይፈቱ ዘኢይፈቱ ሥጋ ይላል ሲፈታም ሥጋ መንፈስ የማይወደውን ይወዳልና ፈቃደ ሥጋችሁን አትስሩ። መንፈስም ሥጋ የማይወደውን ይወዳልና በመንፈስ ፈቃድ ኑሩ ተብሎ ይፈታል። **5ኛ አፍራሽ መንገድ** መዝ.44፣9 አድኃንከነ እምእለ ሮዱነ ወአስተነፈርኮሙ ለኩሎሙ ጸላእትነ ሲል መጥቶ ይእዜሰ ገደፍከነ ወአስተነፈርከነ ይላል። **6ኛ ምርምር መንገድ** መሳ.14፣14 እምአፈ በላኢ ወጽአ መብልእ ወእምነ ጽኑዕ ወጽአ ጥዑም። ይላል ለምልክት ያህል እኒህን ብቻ ጠቀስን እንጂ ሌላውን የቅኔ መንገድ ሁሉ በዚህ መንገድ ቢከታተሉት ከቅዱሳት መጻሕፍት የተለየ ሆኖ አይገኝም። (የቅኔ ንባቡ ግጥሙ የቃላቱ ስብጥር ከሚስጥር በላይ ስለሚያስደስት ይህንንም በአገባቡ በግሡ ወዘተ ማሳመር ይቻላል። ምሳሌ ቀተሉ ነጌያተ እንዘ ነጌያተ ይመስሉ ዓይነት ማለት ነው። ገቢር ተገብሮውን ሰዋሰውን የቅኔ መንገዶችን ማወቅም ለዚህ ይረዳል። ንባብ በደንብ ምረጥ የሚያስቁ የሚያሳዝኑ የሚያኮሩ የሚያዋርዱ ነገሮችን ሁሉ አድርጋቸው። አዲስ ፈጠራ ለሰሚዕ የሚያስደስት የቃላት አሰካክ ከምሥጢር ጋርም ማድረግ ይቻላል። ምሳሌ አልቦ ሰናይ እንበለ ዘበልዐ ብሎ የሚጀምር መወድስ አለ)። በቅኔ ሌላው ዋናው ነገር ታሪኩን ማወቅ አለብን። ቅኔ በዋዌ ይበዛል። የቅኔ መምህራን ግሥ ጠገብ ናቸው።

አርእስተ ቅኔ፣ የቅኔ ዜማ

አርእስተ ቅኔ 22 ናቸው። ግእዝ ጉባኤ ቃና፣ እዝል ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኑ፣ ዋዜማ፣ አጭር ዋዜማ፣ አጭር ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ ዘይእዜ፣ አጭር ዘይእዜ፣ ማህልከ፣ መወድስ፣ ኩልክሙ፣ አጭር ኩልክሙ፣ ሕንጼሃ፣ ግእዝ ክብር ይእቲ፣ እዝል ክብር ይእቲ፣

ግእዝ እጣነ ሞገር፣ እዝል እጣነ ሞገር፣ ግእዝ አሠረ ንጉሥ፣ እዝል አሠረ ንጉሥ፣ የሕንጼሃ ክብር ይእቲ ናቸው። የስብሐተ ነግህ አደራረስ በሚደረስበት ጊዜ ረቡዕና ዓርብ ሲሆን ዕዝል ጉባኤ ቃና። ሰኞ ማክሰኞ ሐሙስ ሲሆን ዘአምላኪየ ቅኔ ይደረጋል። ቀዳም ቀዳም ግን ምቅናይ ስላለ የለም። **የጉባኤ ቃና** መነሻ መመሪያው መዝ.91 ይሄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር፣ መዝ.5 ቃልየ አጽምዕ እግዚኦ ወለቡ ጽራሕየ፣ መዝ.64 ለከ ይደሉ እግዚኦ ስብሐት በጽዮን ናቸው። ጉባኤ ቃና የተባለበት ምክንያት ቃና ቃነየ መዝሙር ቃኘ በገና ደረደረ ካለው ግሥ የተገኘ ጥሬ ዘር ነው። ቃና ማለትም የዜማ ስልት የዜማ ጣዕም የሚታወቅበት ድምፅ ነው። ወደቅኔ ትምህርት የሚሰማራ ሰው መጀመሪያ የሚገጥመው ይህ ዓይነት ቅኔ ስለሆነ መላውን ቅኔ በዚህ ስም አጠቃሎ ጉባኤ ቃና እንደማለት ጉባኤ ቃና ብለውታል። በጠቅላላው የቅኔ ጉባኤ ማለት ነው። ለአርባዕቶች ሁሉ ምልጣን አላቸው በስብከት በሆሳእና በትንሳኤ አደራረስ ማለት ነው። በሌላው ቀን ለሚዘመሩት አርባዕቶች ግን ምልጣን ስለሌላቸው ግእዝ ጉባኤ ቃና ተተክቶበታል። ጎሥዐ አራራይ ስለሆነ **አጭር ዋዜማ** ተተክቶበታል። አጭር ዋዜማ የሚባለውም መንደርደሪያውና ሦስተኛው ቤት ከነሐረጉ ነው። አምላከ አማልክት በሚለው ምዕራፍ 2ኛ አጭር ዋዜማ የሚያገቡ አሉ። ይኽኛው **አጭር ዋዜማ** ደግሞ የመጀመሪያውን ቤት ይመታና ሁለቱን ቤት ዘሎ መጽፊያውንና መጨረስን ቤት አድርጎ ይጨርሳል። ሁለቱ አንድ ረዥም ዋዜማ እንዲሆኑ ነው። **የዘአምላኪየ መነሻ** መዝ.62 አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ የሚለው ነው። ዘአምላኪየም የተባለ በአምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ መዝሙር ስለተመራ ነው። **የሚበዝኑ መነሻ** እግዚኦ ሚበዝኑ እለ ይሳቅዩኒ የሚለው ነው። ስያሜውንም ያገኘው ከዚሁ ነው። በትንሳኤ አደራረስ እግዚኦ ሚበዝኑ እለ ይሳቅዩኒ በሚለው ምእራፍ አመ ሣልስት ዕለት የሚለው መዝሙር ይዘመራል። በሌላው ጊዜ ግን ይህን የመሰለ መዝሙር ስለሌለ ሚበዝኑ ቅኔ ተተክቶበታል። **ዘይሌቡ** የሚባለው ቅኔ ብጹዕ ዘይሌቡ ላዕለ ነዳይ ወምስኪን በሚለው መዝሙር በመመራቱ ስሙ ዘይሌቡ ከመባል በቀር ሚበዝኑን የመሰለ ነው። ከሚበዝኑ የሚለይበት ነገር የለም። ኀምስቱና እግዚአብሔር ነግሡ አራራይ ሆኖ ምልጣን የሌለው ከሆነ ዋዜማ ቅኔ ተተክቶበታል። **ዋዜማ** መባሉም በዋዜማ ጊዜ ስለሚደረስ ነው። በሆሣእና ዋዜማ ይትባረኩ ሆሣእና በአርያም ነው ምልጣኑ ይሁብ ዝናመ ተወን ነው በሌላው ጊዜ ለይትባረኩ ምልጣን ስለሌለው ቅኔ ተተክቶበታል። **ሥላሴ** መባሉም ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ በሚለው መዝሙር የሚመራ ስለሆነ ነው። አምላከ አበዊነ የሚለው ንባብ አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያእቆብ ብሎ አንድነቱን ሦስትነቱን የገለጸበት ምስጢራዊ ኃይለቃል ነውና። ይትባረኩ ግእዝ ቢሆን ግን ቅኔው ዘይእዜ ይሆናል። አራራይ ቢሆን ዋዜማ ይሆናል። የሥላሴ ቅኔ አደራረስ በዚህ ብቻ አይወሰንም በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ ስብሐተ ነግሁ እዝል ስለሆነ በሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እም ሰማያት በሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ በሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ በሠለስቱ በጎበ ባረኩ ይገባል። በአርያም አደራረስ ሠለስቱ ደቂቅ ጎበ ባረኩ ይእዜ ትስእሮ ሲቀሩ በ12ቱ መዝሙረ ነቢያት ሥላሴ ቅኔ ይገባል። በሠለስቱ ደቂቅ ሙሉ ዋዜማ በጎበ ባረኩ **ሐዋርያቲሁ ከበበን** የመሰለ ክብር ይእቲ ነው። አጭር ዋዜማ የሚቀኙ አሉ። በይእዜ ትስእሮ **ሕንጼሃ** ቅኔ ይገባል። ምልጣን በሌለው በዘይእዜ አደራረስ ጊዜ **ዘይእዜ ቅኔ** ይገባበታል። ቅኔውም ዘይእዜው ግእዝ ቢሆን ዘይእዜ ቅኔ ዘይእዜው እዝል ቢሆን

ሥላሴ ቅኔ ነው። ዘይእዜ መባሉም ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ በሚለው መዝሙር ስለሚገባ ነው። በስብከት በሆሣእና በትንሳኤ መወድስ አደራረስ በተሣሀለኒ የሚገባው አርባዕት ባለምልጣን ነው። በሌላ ጊዜ በዚህ መዝሙር ለሚገባው አርባዕት ምልጣን ስለሌለው ቅኔ ገብቶበታል። ለንጉሥ ብቻ የሚጸለይ ነው። ንጉሥ በጦርነት ሣለ ንግሪ ወልታ የሚለውን እንጸልያለን። በአደራረስ ጊዜ በፍታሕ ሊተ የሚገባ መዝሙር ከሌለ **መወድስ ቅኔ** ተተክቶበታል። የእሑድ አደራረስ በጠቅላላው መወድስ ይባላል። ኩልክሙ አህዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ በሚለው ምዕራፍ የሚገባ ድጓ ከሌለ **ኩልክሙ ቅኔ** ተተክቶበታል። ለኩልክሙ አጭር ኩልክሙ የሚባል ሁለት ቤት አለው። መወድሱ ድጓ በሆነ ቀን ረጅም ኩልክሙ መቀኘት ግድ ነው። በሌላ ጊዜ ግን ረዥምም ቢሆን አጭርም ቢሆን እንደ ባለቅኔው ችሎታ ይሁን። ቅዳሴው እዝል ቢሆን **እዝል ክብር ይእቲ** ግእዝ ቢሆን **ግእዝ ክብር ይእቲ** ይሆናል። ክብር ይእቲ የተባለበት ምክንያት ባለቅኔው አንድ ጊዜ ዜማውን ዘልቆት መዘምራኑም ተቀብለው አንድ ጊዜ ከዘለቁት በኋላ ክብር ይእቲ ዛቲ ለኩሉ ጻድቃኑ ብሎ አዚሞ የሚሰግድ ስለሆነ ነው። የክርስቶስ ሞት ለጻድቃን ሁሉ ክብር ነው። ከዚህም ሌላ በሰሙነ ኒቆዲሞስ ሰኞና ማክሰኞ ብቻ የሚደረስ **ሐዋርያቲሁ ከበበን** የመሰለ 3 ቤት የሆነ ክብር ይእቲ አለ። ይኸውም ልክ እንደ ክብር ይእቲው ኅብስትን ጽዋዓን መንፈስን የሚያነሳ መሆን አለበት። ክብር ይእቲው በተጨማሪም ነገረ መስቀልን የሚያነሳ መሆን አለበት። ቅዱስ ያሬድ በቅዳም ሥዑር እና በጸሎተ ሐሙስ ዕጣነ ሞገርና ክብር ይእቲ ሰርቷል በሌላው ቀን ግን ስላልሰራ ቅኔው ተተክቶበታል። **ዕጣነ ሞገር** ማለት የጸሎት ፍጻሜ የጸሎት ማሳረጊያ መደምደሚያ ማለት ነው። ወገረ ማለት ዕጣኑን በጽና ውስጥ ባለ ፍሕም ጨምሮ ጢሱን ወደ ሰማይ አሳረገ ማለት ነው። አሠረ ንጉሥ የሚደረገው የንጉሡ አመራር ያማረ የበጀ ቢሆን የሚገባውን ምስጋና ከአስተዳደሩ የተቃወሰ ነገር ቢኖር አመራሩ እንዲቃና በለሰለሰና በለዘበ አነጋገር ምክር ማቅረቢያም ነው እንጂ ማመስገኛ ብቻ አይደለም። ንጉሡም ይህን ተከትሎ እውነት ሆኖ ሲገኝ ሊያቃናበት የጎደለውን ሊሞላበት ይገባል። በሰሙነ ኒቆዲሞስ ሰኞና ማክሰኞ ዕጣነ ሞገሩ ሕንጼሃ ቅኔ ነው። ቤቱም ሁለት ቤት ነው። **ሕንጼሃ** መባሉም ቅዱስ ያሬድ ሕንጼሃ ወሰራሬሃ አዳም። እም አስካለ ወይን ጉርኤሃ ጥዑም ብሎ የዘመረውን መዝሙር መስሎ ስለተገኘ ነው። በዚሁ በሰሙነ ኒቆዲሞስ ረቡዕ ብርሃነ ሕይወት ቤት ዓርብ ዘዮም መስቀል ቤት ልዩ ንባብና ዜማ ያላቸው ቅኔዎች አሉ። እነዚህም ቅኔዎች በዲማ እስከዛሬ አሉ ይሰራባቸዋል። ቅኔዎችም በሐረግና በዜማ ይለያያሉ እንጂ በግእዙ ዕጣነ ሞገር ልክ 7 ቤት ናቸው። ብርሐነ ሕይወት ቤት መባሉም ብርሃነ ሕይወትን መስሎ የሚሄድ ስለሆነ ነው። ዘዮም መስቀል መባሉም ዘዮም መስቀልን መስሎ የሚሄድ ስለሆነ ነው። ክብር ይእቲያቸው ግን ያው የተለመደው ግእዝ ክብር ይእቲ ነው። የቅኔ ዜማ ግን በየጊዜው እየተሻሻለ ሄዷል እንጂ አንድ ጊዜ የተወሰነ አይደለም። መሪው የጌታ ተመሪው የሐዋርያት ምሳሌ ነው። ጌታችን እኔ በቀስታ በሹክሹክታ የነገርኳችሁን እናንተ በሰገነት በአደባባይ አሰምታችሁ ገልጻችሁ አስተምሩ ባለው መሰረት ባለቅኔው ቀስ እያለ ይነግረዋል ተመሪው ድምፁን ከፍ አድርጎ ይመራል። ዕጣነ ሞገርን ከዐሠረ ንጉሡ ጋር በአንድ ምሥጢር መዝለቅም ይቻላል።

የቅኔ ቤት እና ሥርዓት፣ ፊደል

ፊደል የተገኘ በ7ኛው መቶ ዘመን በሦስተኛው ትውልድ በሄኖስ ነው። ለሄኖስ 22ቱን አሌፋት በጸፍጸፈ ሰማይ ጽፎ አሳየው በልቡ ቀረጸበት እኒህም ከአሌፍ እስከታው ያሉት ናቸው። እነርሱም ሀልዎተ እግዚአብሔር የሚታወቅባቸው የእግዚአብሔር ስሞች ናቸው። ብዙኃኑ "ነ" ፀሐዩ "ፀ" ከ22ቱ ፊደላት ትርፍ መሆናቸው ቢታወቅም "ነ" ለ "ሐ" "ፀ" ለ "ጸ" ድርቦች ሆነው አንቲካ ፊደል በሚባለው በጥንታዊው ፊደል ሁሉ እየገቡ ሲሰራባቸው ኖረዋል።ድምፅ አሰጣጣቸውም ኂላ እያደረ እየተረሳ አንድ እየሆነ ሂዷል እንጂ ልዩ ነበረ ይባላል። በዓረብኛና በትግሪኛ ግን ዛሬም እንደተጠበቀ ነው ይላሉ። እኒህም 22 ፊደላት እስከ አብርሐ ወአጽብሐ ድረስ በግእዝነታቸው ብቻ እየተጻፉ ሲያገለግሉ ኖረዋል። በአብርሀ ወአጽብሐ ዘመን ግን ከሣቱ ብርሃን ሰላማ መጻሕፍትን ከጽርእ ወደ ግእዝ ሲመልሱ በግእዝነታቸው ብቻ የመጻሕፍቱን አነጋገር ማጠቃለልና ማከናወን የማይቻል ስለሆነ በሰባቱ ድምጽ መስጠት እንዲችል ምልክት ጨምረውበታል። ይልቁንም በአጼ በካፋ ዘመን ሀሌታውን "ሀ" ከሐመሩ "ሐ" ከብዙኃኑ "ነ" አልፋውን "አ" ከዓይኑ "ዐ" እሳቱ "ሰ"ን ከንጉሡ "ሠ" ጽፎ የተገኘ ጸሐፊ እጹን ይቆረጥ ነበረ ይባላል። በኂላ ግን የመጻሕፍትን ምሥጢራቸውን የፊደሎችን አገባብ ሳይጠነቅቁ የሚራቀቁ በመላ በድፍረት የሚጽፉ ጸሐፍት እየበዙ ስለሄዱ በዘፈቀደ ተዘበራርቀው የተጻፉ መጻሕፍት እየበዙ ሄዱ። እነ ሁሉ ቀኙ እነ ምን አለበት አበላሹት። በምሥጢርም በኩል ሠረቀ ወጣ ነው ሰረቀ ሰረቀ ነው። ወዳቂውን ንባብ አንስተን ካነበብነው የምሥጢር ለውጥ ያመጣል። ሌላው በግልስ ቅጽል ጸሓፊ ይላል እንጂ ጸሐፊ አይልም።በገቢር ተገብሮም ብዙኀ ንዋየ ይላል እንጂ ብዙኃ ንዋየ አይልም ሳድስን ግእዝ ይወርሰዋል እንጂ ራብዕ የማይወርሰው ስለሆነ ነው። ሠዓሊ ይላል እንጂ ሠዐሊ አይልም። አንድ አ አንድ ጸ አንድ ሰ ይበቃናል የሚሉ አሉ። ይህ ሀሳባቸው ግን የ22ቱን ፊደላት ሁሉ ጥቅማቸውን አውቆ ለሄኖስ የሰጠው እግዚአብሔር የማይረባ የማይጠቅም ፊደል ሰጠው ከማለት እንደሚያደርሳቸው አላወቁም። ወእንዘ ይፈቅዱ ይጥብቡ አብዱ ማለት እኒህ ናቸው። የቅኔዎችን ቤት ጉባኤ ቃና ሁለት ዘአምላኪየ ሦስት ቤት እያለ እስከመጨረሻው ያለውን የወሰነው ተዋነይ ደቀ እስጢፋ ሐዊራ መንክራ ብሑር እስክንድር የተባሉ ደቀመዛሙርቶችን ይዞ ወስኖታል። ላወሳሰኑም ሕግና ሥርዓት አለው። ሕጉና ሥርዓቱም በግእዝ ጀምሮ እንደሆነ በግእዝ በካእብ ጀምሮ እንደሆነ በካዕብ እያለ ፊደል ሳይለዋውጡ ግዕዝና ራብዕ ሳይቀላቅሉ አንዱን ቤት ሳይደጋግሙ መጨረሻውን ፊደል ጠብቆ መዝለቅ ነው። ለምሳሌ ፊደል መለዋወጥ በመጀመሪያው ቤት ነግሠ ብሎ በሁለተኛው ቤት ገብረ ወይም ሐረሰ ቢል። ሐወጸ ብሎ እንደ ሆነ በሁለተኛው ነገረ ወይም ድኅፀ ቢል የፊደል መለዋወጥ ጸያፍ ነው። ግእዝና ራብዕ መቀላቀል በጽሐ ብሎ ቤት መትቶ በሁለተኛው ንሥሓ ቢል የቤት ማፍረስ ጸያፍ ነው። መሰለ ብሎ ቤት መትቶ አምሳለ ቢል ቤት ገጠመ ያሰኛል። ነገር ግን ይህ ሕግና ሥርዓት በባለቅኔዎችና በደራስያኑ ዘንድ በሕግ ተጠብቆ አይገኝም። "ሀ" የወንድ ተጸውዖ ስም ገቢር ነው። ሙሴሀ ሲል ሙሴን ይላል። "ሃ" የሴት ተጸውዖ ስም ገቢር ነው ሔዋንሃ ሲል ሔዋንን ማለት ነው። (ቅኔ **በሳብዕ ቤት** ስታደርግ ጥሬዘር ምሳሌ ከበሮ፣ ቦዝ ምሳሌ አእሚሮ፣ የካዕብ ተሳቢ ምሳሌ ክፍሎ፣ የግስ ዝርዝር ምሳሌ ቀተሎ እና ነባር ይሆናል። **በሳድስ ቤት** ስታደርግ ደግሞ ዘመድ ዘር ምሳሌ ቀትል፣ ሳቢዘር

ምሳሌ ቅትለት፣ መድበል ምሳሌ ቀተልት፣ ውስጠዘ ምሳሌ ቅቱል፣ ንዑስ አንቀጽ፣ ካልዓይ ትእዛዝ ዘንድ አንቀጽ፣ ነባር ሌላም ሥጋክን ሥጋሆን ቀተልክን ውእቶን አንትን ይሆናል። **በ፭ምስ ቤት** ጥሬ ዘር ምሳሌ ቅዳሴ፣ የሣልስ ቅጽል ተሳቢ ምሳሌ ቀታሌ፣ ነባር ይሆናል። **በራብዕ ቤት** ጥሬ ዘር ምሳሌ ራማ፣ የግስ ዝርዝር ምሳሌ ቀተላ፣ ነባር ሌላም ሥጋ ብሎ ሥጋሃ ሠላሳ ይላል ይሆናል። **በሣልስ ቤት** ሣልስ ቅጽል ምሳሌ ቀታሊ። የሴት ትእዛዝ ምሳሌ ንበሪ፣ የ "የ" ዓለም ባለባቸው ግሦች ምሳሌ ጌገየ ብሎ ይጌጊ ሌላም ቀተልኪ መንበርኪ ይእቲ አንቲ ይላል። **በካዕብ ቤት** የውእቶሙ ዝርዝር ምሳሌ ቀተሉ። ሥጋ ብሎ ሥጋሁ ውእቶሙ እማንቱ ውእቱ እሙንቱ አንትሙ ወይም የ "ወ" ግሦች ሲዘረዘሩ ምሳሌ ክልኤቱ ይሄሉ ነባር ይሆናል። **በግእዝ ቤት** ራሱ ግሱ በሳድስ የሚጨርሱ ስሞች ተሳቢ የቁጥሮች ተሳቢ ወዘተ ይሆናሉ)። ቤቱን በ "ሰ፣ቀ፣መ፣ለ" ጀምሮ በ "ሶ፣ቆ፣ሎ፣ሞ" የሚጨርስ ግእዝ ዕጣነ ሞገር አለ። ይኸውም የሚደረገው የመጋቢት መስቀል ዕለት ብቻ ነው። ፊደሎቹም እኒህ የተጠቀሱት 4ቱ ፊደሎች ብቻ ናቸው። ምሥጢሩም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው በመልእልተ መስቀል ለመካሱ ምሳሌ ነው።

ሊቃውንት

አለቃ ተክሌ ዘዋሽራ በቅኔ የተመሰገኑ ስመጥሩ ነበሩ። እግዚአ ውላጤ ክረምት ዓመተ ሁከት ዘኮነት የሚለው የእርሳቸው ቅኔ ነው። ዲማን እመ አህጉር ይሏት ነበር። የዋሽራ መምህራን ስመ ጥሩዎች ነበሩ። በየሀገሩ የዋሽራው መምህር እንዲህ አሉ እየተባለ ይነገርላቸው ነበር። **ንቡረ እድ መኩሪያ** የሐዲስ የቅኔ መምህር ናቸው። የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ተሹመው በዳኝነት ሰርተዋል። **አለቃ መርጌታ ፈንቴ** ሀገራቸው ጎጃም ዋሽራ ነው። ዜማ ቅኔ ተምረዋል። የቅኔ መምህር ናቸው የተረፈውን ጊዜያቸውን ውዳሴ ማርያም ከመድገም ሳያቋርጡ ያሳልፉት ነበር። ከዚህም የተነሳ ጠላት የዋሽራን ካህናት በመትረየስ ከቦ ሲፈጃቸው ከዚያ መካከል ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም እያሉ እያነበቡ ሄደው ዳኑ ይባላል። **በመምህር ገብረ ሥላሴ** በቅኔያቸው ውስጥ በዘርፍም በቅጥልም ቢሆን ጥልቅ ምሥጢር ሳይዝ ለሐረግ ማካሄጃ ለቤት መሙያ ተብሎ የገባ ተራ ነገር አይገኝበትም። ሁሉም ሲፈቱት የሚያጠግብ ምሥጢርን የያዘ ብቻ ነው። ሀገራቸው ወለጋ ነው። **ሊቀጠበብት ወልደ ኢየሱስ** ሀገራቸው ጎጃም ነው በምድር እንጂ በአልጋ ተኝተው አያውቁም። **አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ** በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ሆነው አገልግለዋል። በዋዜማ በድንግል መርዐተ አብ የሚለው ቅኔ **የቄስ ገበዝ ጓሉ** ቅኔ ነው ይባላል። **መምህር ትርፌ ንባቡ** ሀገራቸው ጎጃም ደብረ ጽሙና ነው። ሙያቸው ዜማ ቅኔ ብሉይ ነው። በሚሞቱበት ጊዜ መቃብሬ ደብረ ጽሙና ፍታቱ ዲማ ይሁን ብለው ሞተዋል። በሞቱበት ቀን ዲሞች ደብረ ጽሙና ልቀበር ማለታቸውን ስላልሰሙ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን አክብረው እያጓደዱ ሲፈቱ ውለው ወደ መቃብር በሚወስዱበት ጊዜ የደብረ ጽሙና ሕዝብ ጦር ሰርቶ የመምህራችንን ሬሳ ከዚህ አናስቀብርም እንወስዳለን ሲል ጠብ አንስቷል። የዲማም ሰው የኛ ታቦት ጣያት መሆኑ ነዎይ አንሰድም ብሎ ተዋግቶ ከዚያም ከዚያም ብሎ 15 ሰው ሞቷል። ከዚህ በኋላ ሁሉም በየበኩሉ ሬሳውን ማንሳትና በየደጁ መላቀስ ሆኗል። በዚህ ጊዜ **ራቅ መሰራ ጎበዜ** የተባሉ ቀልደኛ ተጫዋች ነበሩና እንዲህ ሬሳ በየደጁ ሊተርፍ በአንድ ሬሳ ስንጣላ አሉ ይባላል። **አለቃ ንጉሤ ይመር** ከደጃዝማች በላይ ዘለቀ ጋር ሆነው የአርበኝነት ስራ

ሰርተዋል። **መምህር እንግዳሸት** ሀገራቸው ጎጃም ዲማ ነው። የሐዲስ የሊቅ የቅኔ መምህር ናቸው። ማንኛውም ዓይነት ቅኔ ቢታጎል ዘርፈው ይቀኛሉ እንጂ ቅኔ በማሰብ አይቸገሩም ነበር። **መምህር ሠረገላ** ብሉይና ቅኔ ተምረዋል። መምህር ተጠምቆ አብነት አድርገውላቸዋል ይባላልና።ሕሙም ሠረገላ ተፈወሰ በተጠምቆ የሚል ቅኔ ዘርፈዋል። **ራቅ መሰራ ካሳ** ስለድጓ አዋቂነታቸው ድጓ ልብሱ የተባሉ የዲማ ሰው ነበሩ። ቁመታቸው አጭር በመሆኑ ተማሪ ካሳ ጉዱ ይላቸዋል። **ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት** ሊቅ ወዳጅ ነበሩ። **አለቃ ሐዋዝ ታየ** የጎጃሞችን ትርጓሜ ወንጌል አጠኑ። **መምህር አካለ ወልድ** የ4ቱ ጉባኤያት መምህር ናቸው። በጣም ከፍ ያለ አርምሞና ትእግሥት ነበራቸው። ከሙያቸውም የተነሳ አጼ ቴዎድሮስ ይማሯል እንደ አካልየ ብለው አመስግነዋቸዋል። ከቴዎድሮስ እስከ ዘውዲቱ የነበሩ ሽማግሌ ሊቅ ናቸው። **መምህር ደስታ ሐሊቡ** እንግዳ ካልመጣ በሀገር ያለ ድሃ አስጠርተው እንጂ ብቻቸውን እህል አይቀምሱም ነበረ ይባላል። **ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ** ቅኔ ዜማ ተምረዋል የጽሕፈት ሚኒስቴር ነበሩ። ተዋናይ ከተወለደበት ጎንጅ ቴዎድሮስ የሚባል ቤተ ክርስቲያን አለ። የቁሰ ገበዝ ካሳ ቅኔ ንባቡ የከበደ ምሥጢሩ የረቀቀ ስለሆነ ማንም ሰው ንባቡን በቶሎ ሊያጠናው ምሥጢሩን ሊደርስበት አይችልም ስለዚህ ተማሪ **ዕቡይ ካሳ** የሚል ቅጽል ስም አውጥቶላቸዋል። **አለቃ ወልደ አብ** ሀገራቸው ሸዋ ነው። በሀገራቸው ለዲቁና የሚያበቃ ትምህርት ተምረው በዲቁና ሲያገለግሉ ከመሐራ ላይ አጋፋሪው ለአቃቢይቱ ቅዳላት ለወልደ አብም ስጠው ሲል ሰምተው ለዓቃቤ ዋዌ ሆኜ አልኖርም ብለው ጎንደር ሄደው ተምረው የመጻሕፍት ባለቤት ሆነዋል። አለቃ ጎሩይ ከመምህር ወልደ አብ ሐዲስ ተምረዋል። አቶ የሚባሉ ብዙ ስመጥር ሊቃውንት በኢትዮጵያ ነበሩ። ለምሳሌ **አቶ የተሻወርቅ** አቋቋም ድጓ ሊቃውንት ተምረዋል። በቤተ መንግሥቱ የመዘጋጃ ቤት ኃላፊ ነበሩ። ሊቃውንት ስለሀገራቸው ታላቅ ፍቅር ነበራቸው። **መልአከ ፀሐይ ሮብዓም** ሀገራቸው መርጡለ ማርያም ነው። መልአከ ፀሐይ የተባሉበት ጎንደር ቁስቋም ነው። ጎጃም **መምህር ሰዋገኘሁ** የሚባሉ ሊቅ ነበሩ። የጎጃም መሳፍንት ሊቃውንቱን ያከብሩ ይወዱ ነበር። **ሊቁ መርአዊ** ዘጎንደር ህዝቡ የነሐሴ ሚካኤልን አክብሮ ውሎ በማግሥቱ በ13 የደብረ ታቦር እለት በራውን ጠምዶ ያርስ ጀመረ። ከዚያ ከዛራማ ይልቅ ትላንትና አታርሱም ኖሯል ትላንት የሚካኤልን በዓል አክብራችሁ ዛሬ በጌታ በዓል ልታርሱ አይገባም ብለው አስፈትተዋቸዋል። በዚህ ጊዜ ህዝቡ የሚካኤል ይታረስ ብለዋልና መናፍቅ ናቸው ብሎ አሳሰራቸው። **መምህር ውብሸት** የሚባሉ የቢችና ሊቅ ነበሩ። ጎጃም ይእቲ ኢየሩሳሌም የሚል ቅኔ ነበራቸው።

ቅኔ ሃይማኖትን ማስተማርያ ሲሆን

ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ህላዌ ስለሰራው ስራ ስለመወለዱ ስለማረጉ ወዘተ ቅኔ ይደረጋል። ለክርስቶስ የተደረገ መወድስ አለ እንዘ ማይ ውስተ ገቦሁ ማየ ይስእል የሚል። ሥላሴ በአዊን ህልውና ከመገናዘብ በቀር አንዱ አካል በአንዱ አካል አያድርም። ሊቃውንት የእግዚአብሔርን ሥራ በማድነቅ ቅኔ አድርገዋል። ረቂቅ ፍትሕ ፍትሐ ሆሣእና እስመ ሆሣእና አዘዘ በወልጦ ፍትሑ ለሙሴ። ከመ በአእባን ትትወገር ድንግለ አይሁድ ቅዳሴ። የሚል መወድስ አለ።

ጉባኤ ቃና

1 ዘመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ባሕቲቶ ነቢረ እግዚአብሔር ፈርሀ፡፡

እምኢሀልዎ ንዋም እስመ ዓለመ አንቅሀ፡፡

2 ዘሊቀ ጠበብት አያሌው

ተነፍረ ሞት ሰራቂ ለበርብሮተ ቤት ዘተግሀ፡፡

ቅድመ ሕሊናሁ ይፈጽም ሰራቂ እስመ በዓለ ቤት ነቅሀ፡፡

3 ዘሊቀጠበብት መንግሥቱ መዝገብ

ካህነ ደብረ ዘይት እብን ለባዌ መጽሐፍ ኩሉ፡፡

አኮኑ ጸሐፈ ቅዳሴ እግዚእ በቃሉ፡፡

ዘአምላኪየ

1 ዓይነ ሐራዊ ዘኖመ እምንዋመ ዑረት ነቅሀ

እስመ ማይ መቁረፌ አበሳ ላዕሌሁ ተነገዘሀ

ወበቅድሜሁ መስቀል ማኅቶተ ዓለም አብርሀ፡፡

2 መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ኅቡረ ልሕቁ በገራህተ ወንጌል ሉዓሌ፡፡

ክርዳድ ይሁዳ ወጴጥሮስ ስንዳሌ፡፡

እስከ ይበጽሕ ማዕረር ዘዕለተ ዓርብ ወይሌ፡፡

ቅኔ ስለቅዱሳን ክብር መግለጫ ሲሆን

ስለቅዱሳን ታሪክ ተአምራት ወዘተ ቅኔ ይደረጋል፡፡ ሥእርተ ጊዮርጊስ ዲማ ይገኛል እየተባለ ይተረካል፡፡ እና ባለቅኔው ወሥእርቱ በዲማኅ በቆለ ብለዋል፡፡ አለቃ ይመር ዘዲማ ቅዱሳንን በመንቀፍ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ስለሚቃወሙ ሰዎች የደረሱት መወድስ ቅኔ አለ፡፡ አይቴኑ ለነውር ብሔረ መላዱ፡፡ በውስተ ኩሉ ብሔር እስመ ከመ ነግድ ይሄሉ፡፡ ጠይቆተ ዝኒ ነገር ከመ ይትገሀድ ለኩሉ፡፡ ኃጥእ ይሣለቅ ላዕለ ጻድቅ ከመ ዘንጹሕ ወሰናይ ባሕሉ የሚል ቅኔ አላቸው፡፡ ለሙሴ አኃዊሁ ቀላያት ቆሙ የሚል ቅኔ አለ፡፡ ስለ ሰራፕታዋ ሴት ቀዳሚተ ዘመን ብእሲት እንተ አልባቲ አእምሮ፡፡ ለኤልያስ ነገረቶ ኤልያስ እንተ ገብሮ፡፡ የሚል ቅኔ አለ፡፡

ጉባኤ ቃና

1 ዘአለቃ አበበ ሐመረ ኖኅ ኅንደር

አኮ ፍጡን ጊዮርጊስ እንተ ይጽሕፍ ወንጌለ፡፡

በዋሕድ ዓምድ እስመ ውእቱ ወዐለ፡፡

2 ዘቁሰ ገበዝ እንግዳ ዲማ

ጊዮርጊስ ካህን መፍቀሬ ማህሌት ተመትሮ፡፡

ርእሶ አጽነነ ለጸዊረ መጥባሕት ከበሮ፡፡

3 አርምሚ ባህር በስመ አጋእዝት ሥላሴ፡፡

እስመ ኢተውኅጠ ለኪ ነገረ ዚአኪ ሙሴ፡፡

ዘአምላኪየ

1 አልቦ ሥርዓት በዘሌዋውያን ምርፋቅ

ታሕተ ነቢሮ እስጢፋ ልሂቅ

አምጣነ ነበሩ ላእለ አእባነ አፍዓ ደቂቅ

አጭር ዋዜማ

1 ዘመምህር ገብረ ጊዮርጊስ

ነጺርየ ዓይኖ እመጽእ ብሂላ፡፡

ሖረት ንስር ኀበ ገብረ አብ እንላ፡፡

ዋዜማ

2 ዘመርጌታ ያሬድ ቂርቆስ

መነነቶ ወኀደገቶ

ለተክለሃይማኖት አብ ጽኑዐ ሃይማኖት መሐላ፡፡

ብእሲት እግሩ ዘዓቢይ ኃይላ፡፡

ወኢፈቀደት ነቢረ ውሳጤ ቀዊም መርጡላ፡፡

ስድስተ አክናፈ ደቂቀ ተድላ፡፡

በላእሌየ ወለደ ብሂላ፡፡

ሥላሴ

1 ዘመልአከ ብርሃን አድማሱ ጆንበሬ

አእዱገ ዘአጥረዩ በኃጢሠ መስነቅት ይጻምው

ወዘአጥረዩ መስነቅተ ለአጥርዮተ አድግ ተግሁ፡፡

እስመ ባዕድ እምረባሐ አድግ ለመስነቅት ረባሑ፡፡

በቁኤቱስ ለቶማስ በቋዒ ለእመ አኮ ከማሁ፡፡

እለ አጥረይዎ ይትፈስሑ፡፡

እስመ መስነቅተ ጽድቅ ይከውን ማዕሰ ሥጋሁ፡፡

ወመስነቅተ ይጼዓን ለሊሁ፡፡

ዘይእዜ

1 ዘአለቃ ተክሌ ዘዋሸራ

ለምንት ወልድ እንተ ጸውዖ

ለነቢይ ኤልያስ ኀበ ደብረ ታቦር ጽርሑ፡፡

እንዘ ወልድ የአምር ከመ በደመና ይመጽእ አቡሁ፡፡

አኮኑ ኤልያስ ለደመና ሰማይ ጸላኢሁ፡፡

አመ ደመናሰ መጽአ ምስለ ረዳኢሁ፡፡

ኤልያስ ኀየ እስመ የአምር ፍዳሁ፡፡

ቅኔ ሥነ ምግባርን ሥርዓትን ማስተማሪያ ሲሆን

ስነ ምግባርን ስለመጠበቅ ባንጠብቅ ምን እንደሚያገኘን ብንጠብቅ ምን እንደምናገኝ ቅኔ ይደረጋል፡፡ ወበሐልዮ ፈረስ ያረውጸነ መስቴማ፡፡ ምዕረ ኀበ ወርቅ ወምዕረ ኀበ ዘማ የሚል ቅኔ አለ፡፡ ራስ ወልደ ገብርኤል “ዓለም እስከ ጊዜሃ በሐብለ ዝንጋኤ ትስሕበነ ወታወርደነ ታሕተ ኀበ ዘቀዳሚ መርገም፡፡ ለዘተወለድነ በሥጋ ወደም” የሚል ሥላሴ ቅኔ አድርገዋል፡፡ መምህር ወልደ ማርያም ዘዲማ በመወድሳቸው “አልቦ ዘይመውዖ ለዓለም በዓለም” ብለዋል፡፡ ዓለምሰ

እውር መራሔ እውር ዓለም። ኃጥአ ይባርክ ወጸድቀ ይረግም። የሚልም አለ። ይቤሎሙሂ ለአርዳኢሁ እግዚአ ቅዱሳን ጸም። አይቴ ቀበርክምዎ ለአልአዛር ቅብአ ላሕም። የሚል ቅኔም አለ። እንዘ ተድላ ዓለም ነነሥሥ ወእንዘ ንትሜነይ ክብረ። ሞት ይወስደነ ወያወርደነ መቃብረ። የሚል ቅኔም አለ። የጎንደሩ ሊቅ ክፍለ ዮሐንስ በእስጢፋኖስ አዕባን እመ የጎልቁ። ወገረኒ ኢያሱ በወርቁ ብሏል።

ጉባኤ ቃና

1 ዘአቶ ላቀው

ኃያል ጸም ለእመ አንሥአ በትሮ

ኢያውስአ ቃለ ፈራሀ ልቡና ከበሮ

ዘአምላኪየ

1 ዘመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ኦ ጠቢብ ለፍቅረ ዓለም ፍርሆ።

ዓለም እመ ቀርበተከ ወትብለከ አሆ።

እስመ ትክህደከ ሥልሰ እስከነ ይነቁ ዶርሆ።

መወድስ

1 ዘመምህር ገብረ ሥላሴ

እምዘመደ ሰብእ ይሄይስ ዘመደ እንስሳ

ወፍቅረ እንስሳ የዐቢ እም ተፋቅሮ ሰብእ ለለጊዜሁ።

እንዘ ገፋኢሁ ለይስሐቅ እደ አብርሃም አቡሁ።

በግዕ አኮኑ ለይስሐቅ ቤዛሁ።

ወከመ ኢይትርፍ አምሳሊሁ

ኢየሱስሃ ሰቀሉ አይሁድ አዝማዲሁ።

ንሕነኒ ሶበ ሰማዕነ በመጽሐፈ ዕዳ ዜናሁ።

ምንት እም እንስሳ ለሰብእ ፍድፋዴሁ።

እንዘ አድግ የአምር ፍኖተ ምቅማሁ።

አምጣነ እስራኤል ኢጠየቁ ወኢያእመሩ ሥላሴሁ።

ቅኔ ሥነ ፍጥረትን ለማድነቅ ለምርምር

ይህ ደግሞ ስለፍጥረታት የእርስ በእርስ ግንኙነት እርስ በእርስ ስላላቸው ተጽእኖ ስለዓለም ሁኔታ በዓይን ያየውን በጆሮ የሰማውን በስሜት ሕዋሳቱ የተረዳውን ምክንያት አድርጎ ቅኔ ይደረጋል። ራስ ወልደ ገብርኤል ዘትግራይ ቅኔ አዋቂ ነበሩ። ተማሪው "ፈረሱ ለፍርያን ይብል ድህረ ድህረ"። ሲል አንተ "እስመ እግሩ ኢለመደ ባሕረ" በለው አሉት ይባላል። ቦ ኀዘን መርስኤ ኀዘን ብሎ የሚጀምር መወድስ አለ። ዓለምኒ ለዘለዓለም ኢትነብር የሚል ቅኔ አለ። ቶማስና ነገርን መስለው ቅኔ ያደረጉ ሊቃውንት ነበሩ። ውሃንና ነገርን መስለው ቅኔ ያደረጉም አሉ።

ዋዜማ

1 ዘአለቃ አፈወርቅ ዘውዴ

ትመስል ዘትጸልኦ

ብእሲት ዘርዕ ለዝናመ ሰማይ ብእሲሃ።

ሶበ መጽአ ዘምስለ በረድ እንግዳ ኀቤሃ።

እንዘ ትብል ደወይኩ እስመ ትነውም አሜሃ።

ሶበ ባሕቲቶሰ መጽአ በፍሥሓ።

ትትዌከፎ እምንዋም ነቂሃ።

ሥላሴ

2 ዘአለቃ ወልደ ማርያም ሀብቴ

ንዋይ የሚባል ልጃቸው ስለሞተባቸው የተቀኙት የኀዘን መግለጫ ቅኔ ነው።

ሚጡ ንዋየክሙ

ወምጽዋተ ሀቡ ለነዳያን

ዜናዌ ተስፋ አብ ይብለነ በቃሉ ለደቂቀ ኀዘን መራር

የሀብክሙ መንግሥተ ዚአሁ አቡክሙ ኄር

ወአመ ተነደፍኩ አንሰ በፍቅሩ ለንባበ ዝንቱ ምሥጢር

ንዋይየ ሚጥኩ ለመቃብር

ወእምዘጊቦቱ ምጽዋተ እመ አበድር

ወሀብክሥ ምጽዋተ ለምድር

የአማርኛ ቅኔ

በአማርኛ ቅኔ ደጃዝማች ተፈሪ እንደ አንድ ቃል ሊነበብ ይችላል። ይህን የመሰለ ሌላም ማድረግ ይቻላል።

1 መወድስ ዘአለቃ አፈወረቅ ዘውዴ

ገጣባ ዓለም የነጋዴ አህያ

እንዘ ዘክዘክ ትብሊ የምታጋድይ ተላላ።

እንዘ ጎድን ጎድን ይብሉኪ እየተጋፋሽ ከኂላ።

ሦከ አሜከላ ዘትጎምዲ

በሐመድ ዘትንከባለሊ ተራግፈሽ ዳውላ።

ከወደል ጋራ እያስካካሽ

ዘታጓምሲ ገለባ ወትገምጢ አተላ።....

የትንቢት ቅኔ

በ1883 ዓ.ም አለቃ ለማ በአሠረ ንጉሳቸው ስለ ዓድዋ ጦርነት ትንቢት ተናግረዋል

አሠረ ንጉስ

1 ዘአለቃ ለማ

ምኒልክ ግበር ላዕለ ሮምያ መጠነ እዴከ ትክል።

አምጣነ ለአጺድ በጽሐ ማዕረራ ወመዋዕሊሃ ለነጉል።

ዓዲ ተዘከር ውስተ ወንጌል።

ላዕለ ሮምያ በለስ ኢሀሎ አስካል።

ከመ ይቤ ወልደ ያሬድ ቃል።

ስለደር ሡልጣን

ደር ሡልጣን በኢየሩሳሌም ውስጥ በጌታ መቃብር በጎልጎታ የሚገኝ የኢትዮጵያ ገዳም ነው። ርስትነቱም ንግሥተ አዜብ ኢየሩሳሌም ሄዳ ከሰሎሞን ተገናኝታ ስትመለስ የጓዝ መስፈሪያ ይሁንሽ ብሎ ሰጥቷታል። ኋላም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ቤት ሳይሰራበት ክፍት ሆኖ ስለተገኘ ከዚሁ ከኢትዮጵያ ርስት ሰቅለውታል እየተባለ ይተረካል።

ምሥጢረ ተዋሕዶ

አዘጋጅ፡- መምህር ወልደ አብርሃም

ቅብዓትና ጸጋ

ቅብዓትና ጸጋ የሚሉ የእምነት ስያሜዎች የተሰጡትና የታወቁት ከአጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በኋላ ነው። ቅብዓትና ጸጋ በሮም ካቶሊክ ምንጭነት የተገኙ ናቸው ብለን የምንነሳውም ስለዚህ ነው። ቅባትና ጸጋ በንባብ እንጂ በምሥጢር አንድ ናቸው። በጎንደር ነገሥታት ዘመን አብዛኛዎቹ ነገሥታትና መሣፍንት የቅባት እምነትን ይደግፉ እንደነበር ተክለጻዲቅ መኩሪያ ጽፏል።

የካቶሊክና የተዋሕዶ ክርክር በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት

1ኛ ዝክሪና ጳውሊ፡- ካቶሊኮች ሁለት ባሕርይ አሉ። በዚያን ጊዜ በጣም የታወቁት ሊቃውንት **ዝክሪና ጳውሊ** ነበሩ። ካቶሊኮች ሁለት ባሕርይ ሲሉ። ዝክሪና ጳውሊ መጀመሪያ ሀገራችሁ ወዴት ነው? ሃይማኖታችሁስ ምንድን ነው? ብለው ጠየቋቸው። ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ የሚል ከቅዱሳት መጻሕፍት የት አለ? አሏቸው። ጌታ ያችን ዕለት አላውቃትም አለ የሚለው ነው አሉ። አባ ዝክሪ አብን ልብ ወልድን ቃል መንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ ብለን በአብ ልብነት ያስባሉ ያውቃሉ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያዋን ሁነው ይኖራሉ። ለየራሳቸው ልብ ቃል እስትንፋስ የላቸውም። ወልድ ያችን ዕለት በልቤ አብ ሰውሬ አቆያታለሁ አሁን በቃልነቴ አልናገራትም ሲል ያችን ዕለት ከአብ በቀር የሚያውቃት የለም አለ አሉት። ቀጥሎም ሮማዊው እኔ ክርስቶስን ፍጡር እለዋለሁ አለ። አባ ጳውሊ ሲመልስ ክርስቶስን ፍጡር የሚል ንባብ ከምን አገኘህ? አለው። ሮማዊውም ተጠምቶ ከሳምራዊት ውሃ ለምኗልና አምላክ ቢሆን ሁሉ በእጁ ስለሆነ ከውቅያኖስ ይጠጣ ነበር አለ። አባ ጳውሊም ፍጡር ከሆነ ይህ ውሃ አጠጭኝ ብሎ የሚለምንሽ ማን እንደሆነ ብታውቂ ኑሮ የሕይወት ውሃ አጠጣኝ ብለሽ በለመንሽው ነበር ለምን አላት አሉት። ሮማዊውም መልስ አጥቶ ዝም አለ። ከዚያ ሮማዊ አምላክ ከሆነ አልዓዛርን ወዴት ቀበራችሁት ብሎ ለምን ጠየቀ የተቀበረበትን አላወቀውም ነበርን? አለ። ጳውሊ ሲመልስ እግዚአብሔር አዳምን አይቴ ሀሎክ ብሎ ጠየቀው ይላል። ሙሴንም ምንት ውስተ እዴከ ብሎ ጠየቀው ይላል። ፍጡር ከሆነ አልአዛር አልአዛር ነዓ ጻዕ አፍኣ እመቃብር ብሎ እንዴት ሊያስነሳው ቻለ አሉት። ሮማዊውም ይህንስ ቅዱሳንም ያደርጉታል አለ። አባ ጳውሊ ሲመልስ ቅዱሳን ተአምራት ቢያደርጉ የእርሱን ሥም ጠርተው

ነው። ጌታ ግን እኤዝዘከ ጻዕ እምኔሁ እያለ በገዛ ሥልጣኑ ነው ሲለው። ሮማዊው መልስ አጥቶ ዝም አለ።

2ኛ እጨጌ በትረጊዮርጊስ፡- አልፎንሱ ሜንዴዝ "የአብ የባሕርይ ልጁ ሞተ የሚል ገጸንባብ ከምን ይገኛል አለ"። እጨጌ በትረጊዮርጊስም ሮሜ 5፣10 ጠላቶቹ ስንሆን እግዚአብሔር በልጁ ሞት አዳነን ይልብሀል አሉት። አልፎንሱ ሜንዴዝ "የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው አለ። እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መብራት አስበርተው የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው አሉት። መልስ አጣ። በዚህም ተባረረ። በኤርትራ ጠረፍ ኤምስጣቴዎስ ዘሳንካ ጊዮርጊስን እና ቆረንጭ ተክለ ሃይማኖትን አስተማረ። እነርሱም ተመልሰው አስተማሩ እና ቅባትና ጸጋን አስፋፉ። ኤምስጣቴዎስ በሀገሩ በጎጃም ቅባትን አስፋፋ። ቆረንጭ ተክለሃይማኖት የጸጋን ትምህርት በጎንደር በሸዋ በወሎ አስፋፉ።

የቅባቶች አስተምህሮ

"ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ" ይላልና ተዋሕዶ ሁለትነትን እንጂ ንዴትን ከሥጋ አላራቀም። ንዴት ከሥጋ የራቀው በመንፈስቅዱስ በማኅጸን በተቀባ ጊዜ ነው ይላሉ። እኒህ ቅባቶች በሦስት ይከፈላሉ። 1ኛ በአጼ ፋሲል ዘመን የነበሩት እነ እውር ዘኢየሱስ። መጽሐፍ አንደየ ርእሶ ይላልና። 1ኛ ቆሮ.8፣9 ቃል በተዋሕዶ ጊዜ ዜገ ከሥጋ ጋር ሲዋሐድ የባሕርይ ክብሩን አጣ ለቀቀ። ሲቀባ ወደጥንተ ክብሩ ተመልሶ በሰውነቱም በአምላክነቱም አንድ ወገን የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል። ተቀቢው ቃልም ሥጋም ነው። 2ኛ ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነት ክብር አላገኘም ሲቀባ ግን ክብር ተላልፎለት በቅብዓት የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ብለዋል። 3ኛ በተዋሕዶና በቅብዓት የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል። ቅባቶች አብ ቀባኢ ወልድ ተቀባኢ መንፈስቅዱስ ቅብዕ ይላሉ። ቅባቶች ተቀብዐን ሲተረጉሙ "መንፈስ ቅዱስ ቃል ለተዋሐደው ሥጋ ሕይወት ሆነው" ማለታችን ነው ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ አድርገው የሚጠቅሱት ዮሐ.5፣26 "ለአብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ ለወልድም ሕይወት ይኖረው ዘንድ ሰጠው" የሚለውን ነው። ግን ደግሞ ራሱ ጌታ እኔ ትንሳኤና ሕይወት ነኝ ይልባቸዋል። ዮሐ.1፣4 በእርሱ ሕይወት ነበረች የሚለው ያፈርስባቸዋል። ሰጠው ያለውን እኛ የምንተረጉመው ስለ ሥጋ እንግድነት እንላለን እንጂ ሥልጣንም ፈራጅነትም የራሱ የባሕርዩ ነው። ከአብ ለወልድ የሚሰጥ አይደለም። ቅባቶች ግን ቃል ለተዋሐደው ሥጋ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሆነው ሲባል መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ መሆኑ እርግጥ ነው። ታዲያ ለሥጋ ሕይወት የሆነው በአካሉ ነው? ወይስ በጸጋው?። በጸጋው ነው ከተባለ ቃል ሥጋ ሆነ ብለናልና በቃልና በሥጋ መካከል ልዩነት የለምና የቃል ሕይወት መሆኑ ነው። የጸጋ ሕይወት ያለው አምላክ ደግሞ የለንም። ሕይወት የሆነው በአካሉ ነው ከተባለ ደግሞ በተዋሕዶ ወይስ በጎድረት የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በጎድረት እንዳይባል ቃል ሥጋ ሆነ ስላልን ምንታዌ ስለሌለ አንዱን አካል በአንዱ ማሳደር ይሆንብናል። በሥላሴ ደግሞ ኃዳሪና ማኅደር የለም። በተዋሕዶ እንዳንል መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ ያሰኛልና በዚህ በዚህ ይረታሉ።

የጸጎችና የቅባቶች አስተምህሮ ልዩነት

ጸጋዎች የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበለው በዮርዳኖስ ነው። ሲሉ ቅባቶች ደግሞ አንቀጹ ተቀብዐ ለሥጋም ለቃልም ነው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበለው በማኅጸን ነው ይላሉ።

የተዋሕዶ አስተምህሮ

ቤተ ክርስቲያን ከአመሰራረቷ ጀምሮ ፈተና እንዳልተለያት ግልጽ ነው። ከውጭም ከውስጥም ያልተነሳባት ፈተና የለም። እኛ ግን የተዋሐደውን ሥጋ በባሕርይ ክብሩ በተዋሕዶ አከበረው እንጂ እንደኛ እንደ ፍጡራን ክብርን ከመንፈስ ቅዱስ አልሻም እንላለን። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ክቡራን ናቸው። አንዱ አክባሪ አንዱ ክብር አንዱ ተከባሪ አይደለም። ተዋሕዶ የኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የመሆን ምሥጢር ነው። የምሥጢሩ ቅድመ ነገር ዘፍ.3፣22 አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ የሚለው ነው። አካለ ቃል ያለውን ሳይለቅ እንደያዘ አካለ ሥጋ ያለውን ሳይለቅ እንደያዘ ያለመፋለስ ያለመለወጥ ያለመመለስ ያለመጨመር ያለ መጉደል ያለመደመር በተአቅቦ ተዋሐዱ ማለት ነው። በሥጋ የነበረ ንዴት ግን ወደ ቃል አላለፈበትም። የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ የባሕርይ ተዋሕዶ ነው ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት የለባቸውምና። ነድየ መባሉ ሰው መሆኑን መግለጹ ነው። በተዋሕዶ ቃል የሥጋን ርስት ገንዘብ አደረገ። ሥጋም የቃልን ርስት ገንዘብ አደረገ። ስለዚህ በተዋሕዶ የቃል የሆነው ሁሉ ለሥጋ ሆኗል። በመንፈስ ቅዱስ ከበረ አብ ቀባኢ ወልድ ተቀባኢ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ማለት ሥላሴን በክብር ማበላለጥ ስለሆነ ስህተት ነው። ሥላሴ በቅብዕ/ክብር አንድ ናቸው። ቃል ክቡር ነው በባሕርይ ክብሩ የከበረ ነው። የአብ ክብር የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ክብር ነው። የሥላሴ ክብርም እንደባሕርይ ከአካል አይለይም። ስለዚህ በተዋሕዶ የቃል የሆነው ሁሉ ለሥጋ ከተሰጠ በተዋሕዶ ሥጋ የቃልን ክብር ክብሩ አድርጓል። ዮሐ.1፣14 አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን። ሃይ.አበ.90፣7 “ዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ” እንዲል። ሃይ.አበ.69፣40 “ሶበ ትሰምእ ስመ ክርስቶስ ኢትሕሊ ከመ ውእቱ አምላክ ወሰብእ ባሕቲቱ አላ አምላክ ወሰብእ ኀቡረ እንዘ አሐዱ ውእቱ”። ቅዱስ ቄርሎስም በብዕለ ዚአሁ አብዓሎ እግዚአብሔር ቃል ለሥጋነ በትድምርት እንተ ኢትትነገር ወረሰ ቅዱሰ ወማኅየዊ ይላል። ከዚያውም መለኮቱ ቀብዖ ለትስብእቱ ይላል። እግዚአብሔር ቃል በራሱ ክብር/በመለኮቱ ሥጋን አከበረው ሲዋሐድ ሲቀባ አንድ ጊዜ ነው ልዩነት መቀዳደም የለም። ተዋሐደ አንድ ሆነ ነው። አንድ ሲሆን ምንታዌ ሲጠፋ አምላክ ተብሎ ሲጠራ በሥርዓተ ተዋሕዶ ሁሉም ተፈጽሟል። በመጽሐፍ “መንፈስቅዱስን ተቀበለ” ቢል ማለቱ ሥጋ ጥንተ ሕይወቱን በተዋሕዶ ሕይወት አደረገ ማለት ነው እንጂ እንደ እኛ በህድረት አከበረው ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ እንዳያከብረው ክብር ያጣበት ጊዜ የለም። በተዋሕዶ ሊቀካህናት ሆነ ነቢይ ሐዋርያ ሆነ።ስለዚህ መክበር በተዋሕዶ ነውና። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ እንላለን። አብ መንፈስ ቅዱስ ፈጠሩት ከቃል ጋር አዋሐዱት ይባላል እንጂ ተዋሐዱት ክብር ሆኑት አይባልም። ቃል በተለየ አካሉ ሥጋን ሲዋሐድ ለሥጋ ባሕርይ ክብሩ ክብር ሆነው ማለት ይገባል። ወርቁ ለብር ጌጥ ክብር ሁኖት ይኖራል። ሰሪው/ነሀቢው ለብሩ ጌጥ አይሆነውም። ሥጋ እንደብር ቃል በተለየ አካሉ እንደ ወርቅ ነው። የሠሪው እጅ ሰራው

አስጌጠው እንጂ ክብር ጌጥ ሆነው አይባልም። አብና መንፈስቅዱስ በሰሪው ይመሰላሉ። በአጠቃላይ በተዋሕዶ ቃል ከሥጋ አንድ በመሆኑ ለአብ ለመንፈስቅዱስ ሥጋ ቃላቸው ሆነ። የአብን ልቡናነት የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት ገንዘቡ አደረገ። ስለዚህ ሥጋ የቃልን ርስት ገንዘቡ ሲያደርግ ከበረ አምላክ ሆነ የባሕርይ ልጅ ሆነ የቃልን ርስት ገንዘብ ያደረገው ደግሞ በተዋሕዶ ነው። ውሱን ሲሆን ምሉዕ ግዙፍ ሲሆን ረቂቅ መዋቲ ሲሆን ሕያው ሆነ። የባሕርይ አምላክ በመሆን የባሕርይ ልጅ በመሆን በተዋሕዶ ከበረ ማለት ነው። ሥጋን ከበረ ቃልን አከበረ እንላለን። ይሁን እንጂ እንዲህ ብሎ በቋሚነት መግለጽ አይቻልም። ምክንያቱም ምንታዌ ጠፍቷልና ሊቃውንቱ "ክቡር ቃል ስለሰውነቱ በሰውነቱ ከበረ" ይላሉ። ሥጋ በቃል ርስት ወልደ አብ ተብሏል። ሥጋ በተዋሕዶተ መለኮት ለመክበሩ መዝ.45፣4 ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ ይላል። ዮሐ.17፣19 "ለልየ እቁድስ ርእስየ" እኔ ራሴን አከብራለሁ ይላል። ለሊሁ ቀባኢ ወለሊሁ ተቀባኢ ወለሊሁ ቅብዕ ይላል አዕማደ ምሥጢር። ወልድ ቅብዕ ለሚለው ማስረጃ ቁርሎስ መለኮቱ ቀብዖ ለትስብእቱ ያለውና ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ናቸው። ለሥላሴ ሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። ለሌላው ፍጥረት ግን "አብ ሕይወት ወልድ ሕይወት መንፈስቅዱስ ሕይወት ነው"። ወልድም ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ ብሏል። ይህ ለፍጥረታት ነው። ጌታ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ ካሉ ተቀብዐ አንቀጹ ለቃል ነው ካሉ መንፈስ ቅዱስ ለቃል ክብር ሆነው ሲሉ ቃልን እስከ ተዋሕዶ ክብር አልባ ማድረጋቸው ነው። ወይም ጥንትም የቃል ክብሩ መንፈስ ቅዱስ ነበረ ሊሉ ነው። ይህ ደግሞ ስህተት ነው ሥላሴን ማበላለጥ ነውና። ስምዓት 124፣34 "ወካዕበ ይቤ እስመ ክርስቶስ ኢተቀብዐ በእንተ መፍቅድ ዘቦቱ አላ ለሊሁ ቀባዒ ውእቱ ወዓርገ ኀበ ሥልጣነ መለኮቱ እንዘ ሰብእ ውእቱ ወለሊሁ እግዚአብሔር ይላል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ግን ዘይት ዘይትን ተቀባ እንዳይባል ሁሉ ወልድም እርሱው ራሱ ቅብዕ ሁኖ ወልድን ተቀባ አይባልም ይላሉ። ይህ ግን ስህተት ነው እኛስ ቃልን ለሁለት ከፍለን አንዱ አንዱን ያከብራል አንልም ከተዋሕዶ በኋላ እንዲያውም ምንታዌ ስለሌለ ቃልን ከሥጋ አንድ አድርገን በተዋሕዶ እንናገራለን። ይኸውም ስለ ሥጋ እንግዳነት ከበረ እንላለን እንጂ ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ ከባሪ ቃል አክባሪ አንልም። ስምዓት 124፣14 "ከመ ለሊሁ ተቀብዐ ከመ ሥርዓተ ትስብእት ወዳዕሙ ውእቱ ዘይቀብዕ ርእሶ በመንፈሱ ባሕቲቶ"። መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ ሲል በህልውና ነው። ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ልኮኛል ማለት ሰው ሆኜ ለድኅነት አስተምራቸው ዘንድ በህልውናየ ባለ በግብረ መንፈስ ቅዱስ አዋሐደኝ ማለት ነው። መዝ.44፣7 እግዚአብሔር የደስታ ዘይትን ቀባሕ ማለት ልዩ ተዋሕዶን አዋሐደህ ማለት ነው። ከዚያ በፊት ከባልንጀሮችህ ይልቅ ይላል። ባልንጀሮች የተባሉ ነቢያት ናቸው። የእነርሱ የጸጋ የእርሱ የባሕርይ ነውና። ስለዚህ እግዚአብሔርነትህ አምላክነትህ ልዩ ተዋሕዶን አዋሐደህ ማለት ነው። ምክንያቱም አምላክ፣ እግዚአብሔር የሦስቱም መጠሪያ ስም ነውና። ተቀባን ተዋሐደ ብለው አበው የተረጎሙት አለቃ ኪዳነወልድ እንደሚሉት አለፍችው አለ አገባቡ ተርጉሞ ለማደናገር ወይም ለመከራከር ሳይሆን መክበር ወይም ተከባሪ መሆን የተዋሕዶ ውጤት ስለሆነ ነው። ቅባቶች ተቀብዐን ሲተረጉሙ "መንፈስቅዱስ ቃል ለተዋሐደው ሥጋ ሕይወት ሆነው" ማለታችን ነው ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ አድርገው የሚጠቅሱት ዮሐ.5፣26 "ለአብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ ለወልድም ሕይወት ይኖረው ዘንድ ሰጠው" የሚለውን ነው። ግን ደግሞ ራሱ ጌታ እኔ ትንሳኤና ሕይወት ነኝ ይልባቸዋል። ዮሐ፣1፣4

በእርሱ ሕይወት ነበረች የሚለው ያፈርስባቸዋል። ሰጠው ያለውን እኛ የምንተረጉመው ስለ ሥጋ እንግድነት እንላለለን እንጂ ሥልጣንም ፈራጅነትም የራሱ የባሕርዩ ነው። ከአብ ለወልድ የሚሰጥ አይደለም። ቅባቶች ግን ቃል ለተዋሐደው ሥጋ መንፈስቅዱስ ሕይወት ሆነው ሲባል መንፈስቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ መሆኑ እርግጥ ነው። ታዲያ ለሥጋ ሕይወት የሆነው በአካሉ ነው? ወይስ በጸጋው?። በጸጋው ነው ከተባለ ቃል ሥጋ ሆነ ብለናልና በቃልና በሥጋ መካከል ልዩነት የለምና የቃል ሕይወት መሆኑ ነው። የጸጋ ሕይወት ያለው አምላክ ደግሞ የለንም። ሕይወት የሆነው በአካሉ ነው ከተባለ ደግሞ በተዋሕዶ ወይስ በኅድረት የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በኅድረት እንዳይባል ቃል ሥጋ ሆነ ስላልን ምንታዌ ስለሌለ አንዱን አካል በአንዱ ማሳደር ይሆንብናል። በሥላሴ ደግሞ ኃዳሪና ማኅደር የለም። በተዋሕዶ እንዳንል መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ ያሰኛልና በዚህ በዚህ ይረታሉ። የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት አንስተው ሕይወት ስለሆነው በመንፈስ ቅዱስ ከበረ ሲሉ የአብን ልቡናነትንን አንስተው በአብ ከበረ ማለትን እንዴት ተውት። የሥላሴ የኩነት ሦስትነት ተፈልጦ ተከፍሎ ሳይኖርበት በአንድነት አካላትን የሚያገናዝቡ ስለሆነ በዚህም መሰረት ቃል በቃልነቱ ከዊን ጸንቶ ሥጋን ሲዋሐድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በህልውና ሳይለይ ነው። ሥጋ በተዋሕዶ የቃልን ሀብት ገንዘብ በማድረጉ የአብን የልቡናነት ከዊን የመንፈስ ቅዱስን የሕይወትነት ከዊን በህልውና ገንዘቡ አደረገ። በተዋሕዶ ቃል ሥጋ ሆነ ሥጋም ቃልን ሆነ። ቃልን ከመሆን በላይ ሌላ መክበር ደግሞ ስለሌለ ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ እንላለን። ሥጋ ቃልን ሲዋሐድ አልከበረም በመንፈስ ቅዱስ ነው የከበረ ማለት ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ያንሳል ማለት ነው። ዮሐንስ አፈወርቅ 2፣15 “አብን በልብነት መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስነት ገንዘብ ለማድረግ ሥጋ ቃልን ተዋሐደ” ይላል።

ሥመ ሥላሴ

ስም አካል የሚጠራበት ነው እንጂ ራሱ አካል አይደለም።

የሥላሴ ግብር

ግብር ማለት ሥራ ማለት ነው። ሥላሴ ሁለት ዓይነት ግብር አላቸው። ኩነታዊ ግብርና ሥልጣናዊ ግብር ናቸው። **ኩነታዊ ግብር** የሚባለው የአብ ግብሩ መውለድ ማስረጽ የወልድ ግብሩ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ ናቸው። የሥላሴ የአካል ግብር ስም ወላዲ አስራጺ ተወላዲ ሰራጺ ናቸው። በዚህ የግብር ተፋልሦ በሥላሴ የለባቸውም። የአንዱ ግብር የሌላው አይሆንም። ***ሥልጣናዊ ግብር*** የሚባለው ሥላሴ አንድ የሚሆኑበት ግብር ነው። ሥልጣናዊ ግብር የምንላቸው መስጠት መፍጠር መግደል መንሳት ማንጻት ማጽናት ማክበር ናቸው። እግዚአብሔር በመፍጠር አንድ ሥለሆነ ስነፍጥረትን ሁሉ በሥልጣናዊ ግብሩ ፈጥሮታል። አብ ለአጽንዖ መንፈስቅዱስ ለአንጽሆ ሲል ይህ አነጋገር ማጽናትን ለአብ ማንጻትን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ የአካል ግብር ለይቶ መስጠቱ አይደለም። ማጽናት ማንጻት የሥላሴ የሥልጣን ግብር ናቸውና የሚሠሩት ሥላሴ በአንድነት ነው። አብ ያነጻል ያጸናል ወልድ ያነጻል ያጸናል መንፈስቅዱስ ያነጻል ያጸናል። መዋሐድ ግን የወልድ ግብር እንጂ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ግብር አይደለም። ነገር ግን መጻሕፍት አንዱን ለአንዱ እየሠጡ መናገር

ልማዳቸው ነው። ለምሳሌ አብን አዋሐደ ፈጠረ ሲለው ዘቀደሶ አብ ወፈነዎ ውስተ ዓለም ይላል። ወልድን ፈጠረ ተዋሐደ ሲለው ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ ደመረ መለኮቶ ይላል። መንፈስ ቅዱስን ፈጠረ አዋሐደ ሲለው ፈጠረ መቅደሰ ሕያው በመንፈስ ቅዱስ ይለዋል። አብ አጸና ማለታቸው በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ማለት በህልውና ተገናዝቦ ያጸናል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስም መንጸሂ ናዛዚ የሚባለው በአብ ልቡናነት በወልድ ቃልነት በራሱ ሕይወትነትና በህልውና ተገናዝቦ ከአብ ከወልድ አንድነት ሳይለይ በአንድነት ነውና ልዩ ግብር አይደለም። እንዲያውም አብዛኛው የረቂቅነት ምስጢር የሆነ ነገሮችን መጻሕፍት ለመንፈስቅዱስ ሰጥተው የሚተረጉሙት ለዚሁ ነው እንጂ የመንፈስ ቅዱስ የሆነ ሁሉ የአብም የወልድም ነው። ለምሳሌ ለሰው መንፈስ ቅዱስ አደረበት ቢባል በጸጋ ያደሩበት አብ ወልድ መንፈስቅዱስ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነው የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው ቢባልም እንደዚሁ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከበረ አብ ቀባኢ ወልድ ተቀባኢ መንፈስቅዱስ ቅብዕ ማለት ሥላሴን በክብር ማበላለጥ ስለሆነ ስህተት ነው። ሥላሴ በቅብዕ/ክብር አንድ ናቸው። ቃል ክቡር ነው በባሕርይ ክብሩ የከበረ ነው። የአብ ክብር የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ክብር ነው። የሥላሴ ክብርም እንደባሕርይ ከአካል አይለይም። ስለዚህ በተዋሕዶ የቃል የሆነው ሁሉ ለሥጋ ከተሰጠ በተዋሕዶ ሥጋ የቃልን ክብር ክብሩ አድርጓል።

አካለ ሥላሴ

ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው በአካላት መጠቅለል መቀላቀል የለባቸውም። በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክ በየራሳቸው የቆሙ ናቸው።

ኩነት

የኩነታት ሦስትነት ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ በተጋብኦ በአንድነት አካላትን በህልውና የሚያገናዝቡ ናቸው። የሥላሴ የኩነት ሦስትነት ተፈልጦ ተከፍሎ ሳይኖርበት በአንድነት አካላትን የሚያገናዝቡ ስለሆነ በዚህም መሰረት ቃል በቃልነቱ ከዊን ጸንቶ ሥጋን ሲዋሐድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በህልውና ሳይለይ ነው። ሥጋ በተዋሕዶ የቃልን ሀብት ገንዘብ በማድረጉ የአብን የልቡናነት ከዊን የመንፈስ ቅዱስን የሕይወትነት ከዊን በህልውና ገንዘቡ አደረገ። በተዋሕዶ ቃል ሥጋ ሆነ ሥጋም ቃልን ሆነ። ቃልን ከመሆን በላይ ሌላ መክበር ደግሞ ስለሌለ ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ እንላለን።

የልደት በዓል፣ ጾመ ነቢያት

የጌታ ልደት በዘመኑ በታኅሣሥ 29 ሲሆን አባቶች በሰሩልን ሥርዓት መሠረት በዘመነ ዮሐንስ በታኅሣሥ 28 ይከበራል። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ልደት የሚውለው ዕለተ ሞርያ በዋለበት ጳጉሜን 5 ቀን ነው። ጳጉሜን 5 ቀን ሰኞ ቢውል ልደትም መዋል ያለበት ሰኞ ነው። ዕለተ ሞርያ ማለት ዕለተ መድኃኒት ማለት ነው። ስንክሳር ታኅሣሥ 28 በዓለ ጌና ዘውእቱ ልደት ይለዋል። ስንክሳር ህዳር 15 ጾመ ነቢያት ይጀመር ይላል።

ፍኖተ እግዚአብሔር

አዘጋጅ፡- አለቃ ጎሩይ ፈንታ

አለቃ ጎሩይ ከ1855-1948 ዓ.ም በቤተልሔም በጌምድር ተወለዱ። አባታቸው ሊቀ ካህናት ፈንታ ይባላሉ። እናታቸው ወይዘሮ ብሪቱ ይባላሉ። ተድባበ ማርያም ሂደው ከአለቃ ወረደቃል ቅኔ ተምረዋል። እንደገና ጎጃም ተሸግረው ከሁለት ስመጥር የቅኔ መምህራን ተምረዋል። እንደገና ጎጃም ጽላሎ ከአለቃ እንግዳ ብሉያት ተምረዋል። ቤተልሔም ከመምህር ደርሶ ድጓ አስመስከሩ። ጎንደር ሂደው ከመምህር ወልደአብ ወልደ ሚካኤል በጥቂት ቀን የሐዲሳትን ትርጓሜ አጥንተዋል። አእምሮ ከሚባሉ የአቋቋም መምህር አቋቋም ተምረዋል። አዲስ አበባ መጥተው ከመዘመር ካሳ ሊቃውንትን አጠኑ። እንደገና ጎጃም ሂደው ብሉያትን ከብሉይ መምህራን ከነ መምህር ሰውአገኘሁ ከነመምህር ጸበሉ ከነአለቃ ገብረኤልያስ ሊቃውንትን ከነ አለቃ ተስፋ ከነሊቀጠበብት ወልደሥላሴ ከእነመልአከ ሰላም ገብረማርያም ከእነ መምህር እንግዳሸት ተጠያየቁ። ከዚያ ዲማ ክብራን ዘጌ ጣና ቂርቆስ ሂደው መጻሕፍትን ተመለከቱ። ሹመት ወዳጅ አልነበሩም። ደብረሊባኖስ ተቀበሩ። ከመላው ኢትዮጲያ የተሰበሰቡ ሊቃውንት በጎንደር ዘመነ መንግሥት አንድምታን ሠርተዋል። ትርጓሜው ዜማው ሥርዓተ ማህሌቱ መልክ የያዘው በጎንደር ዘመነ መንግሥት ነው።

ትርጓሜ ቃላት

ሁከት፡- ሁልጊዜ የሚከናወን የባሕር እንቅስቃሴ ነው። **አቃኒም**፡- አካላት ማለት ነው። **ሕልው**፡- ነዋሪ ቋሚ ማለት ነው። **መልክዕ**፡- መልክ ማለት ነው። **ለባውያን**፡- የሚያስቡ ማለት ነው። **ምዕዳን**፡-ምክር ማለት ነው። **ተፈልጦ**፡-መለየት ማለት ነው። **ክሂል**፡- ችሎታ ማለት ነው። **ሕላዌ**፡- አኗኗር ማለት ነው። **ስመ ኩነት**፡- የመሆን የአካኋን ስም ማለት ነው። **መለኮት**፡- የእግዚአብሔር የአንድነት መገለጫና የግዛትና የጌትነት መጠሪያ ስሙ ነው። **ቅጥነተ ሕሊና**፡- የረቀቀ አስተሳሰብ ረቂቅ አእምሮ ጥልቅ አስተሳሰብ ምርምር ርቃቂ ማለት ነው። **ተረክቦ**፡- መገኘት ማለት ነው። **ተድህሮ**፡- ወደኋላ መቅረት ማለት ነው። **ትንሳኤ ዘጉባኤ**፡- ጌታችን ሁለተኛ ሲመጣ ሁሉም ሰው ተነስቶ በአንድነት በፊቱ የሚቆምበት የትንሳኤ ጊዜ ነው። **አሠረ ፍኖት**፡- ፈለግ የመንገድ ፈለግ ወይም ኮቴ ነው። **ኃይለ ዘርዕ**፡- እንደሰው አራቱን ባሕርያት ነስቶ ተወልዶ በየደረጃው ማደግ ነው። **ኃይለ እንስሳ**፡- እንደሰው መብላት መጠጣት መተኛት መነሳት ነው። **ኃይለ ንባብ**፡- እንደሰው ደረጃ በደረጃ አፍ እየፈቱ አከናውኖ የመናገር ችሎታ ነው። **ከዊን**፡- መሆን ማለት ነው። ለምሳሌ ከዊነ ልብ ስንል ልብ መሆን የልብን ቦታ መያዝ ወይም የእውቀትን ቦታ መተካት ማለታችን ነው። **ገጽ**፡- አካል መልክ ማለት ነው። **ዕሪና**፡- እኩልነት መተካከል ማለት ነው። **ዋሕድና**፡- አንድነት ማለት ነው። **ፍኖት መብእስ**፡- ያልተስተካከለ ወጣ ገባ መንገድ ማለት ነው።

ምሥጢረ ሥላሴ፣ ሥጋዌ

ምሥጢረ ሥላሴ በቅጥነተ ሕሊና ነው የሚታይ። ይህ መጽሐፍ ወላዲ መለኮት ተወላዲ

መለኮት ሠራጺ መለኮት ማለት እንደማይገባ ይገልጻል። በአንድ መለኮት ሦስት ኩነት እንዳለ ይገልጻል። **ዮሐንስ ተአቃቢ** እግዚአብሔርን በአካልም በመለኮትም ሦስት ብሎ ያስተምር የነበረ ዘጠኝ መለኮት ይላል የሚባል መናፍቅ ስም ነው። ትምህርቱ በዋልድባ ተስፋፍቶ ነበር። ፍኖትሂ ሠናይት ሃይማኖት ይእቲ ብሂለ አሐዱ መለኮት ወሠለስቱ አካላት። ጸጋሰ ኢትትወሀብ ዘእንበለ ለትሑታን ወፈድፋደሰ ለምኑናን ወለየዉሃን። ካቶሊኮች ባሕርይ ተዋሐደ ከተባለ ባሕርየ ሥላሴ አንድ ነውና ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ ያሰኛል ይላሉ። ዝቅ ያለው ከፍ ይበል። ሰባልዮስ አንድ ገጽ ከሚል በሦስቱ ገጻት ይመን። ተራራው ዝቅ ይበል። ዮሐንስ ተአቃቢ ዘጠኝ መለኮት ወይም ሦስት አማልክት ዘጠኝ አካላት ማለትን ትቶ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ይበል። መለኮት በሦስቱ አካላት ህልው ሆኖ ሦስቱን አካላት ያገናዝባል። ወበሠለስቲሆሙ ሀሎ አሐዱ መለኮት እንዲል ሃይማኖተ አበው። ሥላሴ በጎብረ መልክዕ ይመሳሰላሉ። ተወሕዷቸው በመለኮት ይነገራል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መለኮት መለኮት መለኮት መባላቸው አንድ መለኮት በሦስቱ አካላት ሕልው ሆኖ ሦስቱን አካላት ስላገናዘበ እንጂ መለኮት በአካል የተለየ ሆኖ አይደለም። መለኮት በአካል የተለየ ቢሆን ኑሮማ ሦስቱ ሁሉ ባልተጠሩበትም ነበር። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መባል ግን በአካል የተለየ ቢሆን በየራሳቸው ተጠሩበት እንጂ ሦስቱ ሁሉ እንዳልተጠሩበት ተረዳ። የኩነታት ሦስትነት እንደ አካላት አይደለም። አካላት መጠቅለልና መቀላቀል ሳይኖርባቸው በተከፍሎ በተፈልጦ በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክ በየራሳቸው የሚቆሙ ናቸው። ኩነታት ግን ተፈልጦ ተከፍሎ/መለየት መከፈል ሳይኖርባቸው በተዋሕዶና በተጋብዖ በአንድነት አካላትን በሕልውና/አኗኗር እያገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩ ያሉ የሚኖሩ ናቸው። እኒህም ከዊነ ልብ ከዊነ ቃል ከዊነ እስትንፋስነት ናቸው። የእሊህም ኩነታት ምስጢር "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ያለውን ንባብ መሠረት አድርጎ የነፍስ የአካሏንና የባሕርይዋን ከዊን ቢመረምሩ ይታወቃል ይረዳል። ሲመረመርም የባሕርያቸው ከዊን በአካሏ ከዊን የአካላቸውም ከዊን በባሕርይዋ ከዊን ይመረመራል። ነፍስ በአካሏ ከሦስት የማትከፈል ከዊን አላት ይሄውም ከዊነ ቃል ከዊነ ልብ ከዊነ እስትንፋስ ነው። በባሕርይዋ ሦስት ከዊን ያላት መሆኗ አካሏን ከሦስት አይከፍለውም። እንዲህ ሳትከፈል የልብነቷ ከዊን/ልብ መሆኗ ከቃሏና ከእስትንፋሷ ከዊን ሳይለይ በራስዋ ከዊን ከሥጋዊ ልብ ጋር ይዋሐዳል። በቃልነቷም ከዊን ከልብነቷ ከዊንና ከእስትንፋስነቷ ከዊን ሳይለይ በራሱ ከዊን ከሥጋ አንደበት ጋራ ይዋሐዳል። የእስትንፋሷም ከዊን ከልብነቷ ከዊንና ከቃሏ ከዊን ሳይለይ በራሱ ከዊን ከሥጋ እስትንፋስ ጋር ይዋሐዳል። እንዲህ አድርጎ የሥላሴን ከዊን በነፍስ ከዊን ቢመረምሩ ሦስቱ ሰው ሆኑ ከማለት ይጠብቃል። መለኮትን በአካል ሦስት ማለት ግን ክህደት ነው። ሊቃውንትም ይሄለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት ነው ያሉት። እሳት አንድ ባሕርይ ሲሆን ሦስት ከዊን አለው። ይኸውም ነበልባል/አብ ብርሃን/ወልድ ዋዕይ/መንፈስ ቅዱስ ነው። ነበልባሉ ከእንጨት ወይም ከፈትልና ዘይት ጋራ ተዋሕዶ ብርሃኑንና ሙቀቱን ይሠጣል። ብርሃን ከነበልባልና ከዋዕይ ተከፍሎ ሳይኖርበት በራሱ ከዊን ከዓይን ብርሃን ጋራ ይዋሐዳል። እንደዚሁም ወልድ በቃልነቱ ከዊን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በተለየ አካሉ ሰው ሆነ። ብርሃነ እሳት ከዓይን ጋራ በተዋሐደ ጊዜ ነበልባልና ዋዕይ እንዳልተዋሐዱ ወልድም ሰው በሆነ ጊዜ መለኮት አንድ ስለሆነ አብና መንፈስ ቅዱስ ተዋሐዱ አያሰኝም። ባሕርይ አንድ ሲሆን ከዊን ይለየዋልና። ይህንንም የሚያስረዳ ሐዋርያው ቅዱስ

ጴጥሮስ ቢጠይቀው በቀሌምንጦስ “አቡየ እሳት ውእቱ ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስቅዱስ ዋዕዩ” ብሎታል። የፀሐይም ምሳሌው እንደ እሳት ነው። ቀሌምንጦስ አያይዞ አቡየ ፀሐይ ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስቅዱስ ዋዕዩ ይላል። በአንድ መለኮት ሦስት አካላትና ሦስት ኩነታት አሉ። በመለኮት ተከፍሎ የለበትም መለኮት በአንድነቱ ጸንቶ አካላትን በተከፍሎ ሳሉ በህልውና የሚያገናዝብ ነው። ከአካል ጋር ከሦስት አይከፈልም። መለኮት ከአካል ጋር ከሦስት የሚከፈልስ ከሆነ አንድ ልብ አንድ ቃል አንድ እስትንፋስ መሆን የለም። ይህም ከሌለ በአብ ለባውያን በወልድ ነባብያን በመንፈስቅዱስ ሕያዋን መባል አይገኝም። በየራሳቸው ቃል ልብ እስትንፋስ አላቸው ያሰኛል። ይህ ደግሞ የዮሐንስ ተአቃቢ ትምህርት ነው። ሥላሴን ሕልውና እንደሚያገናዝባቸው ራሱ ጌታ አነ በአብ ወአብ ብየ ብሏል። ከብዙ ስህተት የሚያደርስ የሥላሴ የስማቸውን ምሥጢር ለይቶ አለማወቅ ነው። በባሕርይ የሚጠሩበት ስም አለ። በአካል የሚጠሩበት ስም አለ። በግብር የሚጠሩበት ስም አለ። በባሕርይ የሚጠሩበትን ስም ለአካልና ለግብር በግብር የሚጠሩበትን ለባሕርይና ለአካል በአካል የሚጠሩበትን ስም ለባሕርይና ለግብር ሰጥተው ሲናገሩ የአንድነታቸው የሦስትነታቸው ምሥጢር ፈራሽ ይሆናል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መባል የአካል ስም ነው። አካል ግብርን ያስገኛል እንጂ ግብር አካልን አያስገኝም። የሥላሴ ስሞች አካላት ሲኖሩ የኖሩ ናቸው እንጂ በኋላ የወጡ አይደለም። ለምሳሌ ሰው ሰው መባሉ ቆይቶ ያገኘው አይደለም። ይሥሐቅ ያዕቆብ መባል ግን በኋላ የወጣ ነው።ሥመ ሥላሴ ግን ሰው እንደሚለው አብሮ የተገኘ ነው። አካል በመለኮት ከዊን ይገናዘባልና መለኮት ተብሎ ይጠራል ስለዚህ አብ መለኮት ወልድ መለኮት መንፈስቅዱስ መለኮት ቢል ይሆናል። የአካል ግብር ግን አይገናዘብምና ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት ሊባል አይገባም። ሥላሴ በባሕርይና በባሕርይ ግብር በአካልና በአካል ግብር የሚጠሩበት ስም አለ። በአካል ግብር የሚጠሩበትን በባሕርይ ግብር በባሕርይ ግብር የሚጠሩበትን በአካል ግብር ካደረግነው ችግር ስለሚፈጥር በቅጥነተ ሕሊና ሁነህ አስተውል። ወላዲ ተወላዲ ሰራጺ ማለት የግብር ስም ነው። አካል የሌለው ባሕርይ ባሕርይ የሌለው አካል የለም የሚለው ለፍጡራን እንጂ ለሥላሴ አይሠራም። ወልድ ከአብ ሲወለድ አካሉ በተከፍሎ ቢለይም ሕላዌ መለኮት በተከፍሎ መለየት የለበትም። ሰው ግን ከእናቱ ሲወለድ በባሕርይም በአካልም ተከፍሎ ነው። በመለኮት ግን ተከፍሎ የለበትም አወላለዱም ብርሃነ ፀሐይ ተከፍሎ መለየት ሳይኖርበት ከክበብ እንዲገኝ ቃል ከልብ በተከፍሎ መለየት ሳይኖርበት በአካል ከዊን ይወለዳል። በሰው ግን ልጅ ከአባቱ ባሕርይ በአካል ተለይቶ የሚከፈል ስለሆነ አባትና ልጅ አንድ ልብ አንድ ቃል አንድ እስትንፋስ በመሆን አይገኙም። ወልድ ግን ከአብ ሲወለድ ባሕርይ እንደአካሉ የማይከፈል አንድ ስለሆነ ሦስት አካላት በአንድ ልብ በአንድ ቃል በአንድ እስትንፋስ ተገናዝበው ይኖራሉ። ወልድ ማለት አካሉ በቃልነቱ ከዊን ተድህሮ ሳይኖርበት አብን አህሎ መስሎ ከአብ አካል በመገኘቱ የሚጠራበት የተረክቦ ስሙ ነው። ተረክቦውም ተፈልጦ ሳይኖርበት በሕልውና ነው። የነፍስ ቃሏ ከልብነቷ ተገኝቶ ሳይለይ በአካሏ ሕልው ሆኖ እንደሚኖር ማለት ነው። ተወላዲ ማለት ግን በተከፍሎ የሚጠራበት የግብር ስሙ ነው። ወልድ ማለትና ተወላዲ ማለት በግስ በአንቀጽ መልክ ፊደሉ አንድ ሲመስል የምስጢር ልዩነት እንዳለው የተረክቦንና የተከፍሎን ምሥጢር ጠንቅቆ ማስተዋል ነው። ተረክቦ ያልነውም የአካሉ ሕልውና ከአብ አካል የተለየ ሆኖ በፍጹም ገጽ መልክ መታወቅ ነው እንጂ እግዚአብሔር

የተገኘበት ጊዜ አይደለም። እግዚአብሔር ማለትና መለኮት ማለት አንድ ሲሆን ልዩነት አለበት። መለኮት ማለት እንዲህ ነው ተብሎ በማይነገርና በማይታወቅ ጠባይ የሚጠራበት ስም ነው። እግዚአብሔር ማለት ግን አካል በአካልነቱ ግብር ሳይሆን በባሕርይ ግብሩ የሚጠራበት የግብር ስም ነው። ሊቃውንትም እግዚአብሔር ማለትን አንቀጽ ተቀባይ ባለቤት። መለኮትን ማድረጊያ እያደረጉ "በ" የሚባል አገባብ እየጫኑ ይነግሩናል። እግዚአብሔር አሐዱ በመለኮት ይላል እንጂ መለኮት አሐዱ በእግዚአብሔር አይልም። ይትዋሐዱ በመለኮት ይላል እንጂ ይትዋሐዱ በእግዚአብሔር የሚል የለም። መጻሕፍት ማዋሐጃ አድርገው የተናገሩትን መለኮትን አንቀጽ ተቀባይ ባለቤት አድርጎ መለኮት በአካል ሦስት ማለት ስህተት ነው። የሥላሴ መንግሥትን በአካል ሦስት ማለት ስህተት ነው። ዲዮናስዮስ "ኢንበውእ ውስተ ከፊለ መንግሥት አላ ንብል አሐቲ መንግሥት" ብሏል። መንግሥት ሦስት ከሆነ ዙፋን የሌለው መንግሥት የለምና ሦስት መንበር አለ የማለት የግድ ነው። ለሕዝቅኤል ሦስቱ አካላት የአንድ ህላዌ መለኮት በምትሆን በአንዲት መንግሥት አንድ መሆናቸውን ሲያስረዳ በአንድ መንበር ታይተውታል። መዝ.47፣7 መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም ያለውን ዮሐንስ አፈወርቅ ሲተረጉም ድርሳን ሦስት "ወዝንቱ ያሌቡ እንበይነ መንግሥቱ" ብሎ ተርጉሞታል። መንግሥት በአካል የማይከፈል አንድ ነው ማለት ነው። ወላዲ ተወላዲ ሰራጺ ማለት በአካል የማይገናዘብ ልዩ ነው። አብ ወልድ መንፈስቅዱስ ማለት ግን በህላዌ መለኮት ባለች በባሕርይ ከዊንና በህልውና የሚገናዘብና የሚዋሐድ ነው። መገናዘቡንም የሚያስረዳ በሃይ.አበ.33፣30 ወዝንቱ ስም ዘውእቱ ወልድ ያጤይቅ ሕብረተ ህላዌሆሙ ይላል። ሃይ.አበ.53፣11 ንነግረከ ወናሌብወከ ዘንተ ስመ ዘውእቱ ወልድ ከመ ውእቱ ሕላዌ ምስለ አብ ይላል። ይህ በሁለቱ አካላት ያለ መለኮት ተከፍሎ የሌለበት አንድ መሆኑን ይገልጻል። ስለዚህ ወላዲ ማለትና አብ ማለት ልዩነት እንዳለው ተረዳ። ለሥላሴ በየራሳቸው ልብ ቃል እስትንፋስ አላቸው ካልተባለ አካለ ጎደሎ ያሰኛል እንጂ በአካል ፍጹማን ያሰኛልን ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ልብ ቃል እስትንፋስ በአካል ህልው ሆኖ ለአካል ህይወት የሚሆን የባሕርይ ከዊን ነው እንጂ እርሱ ራሱ እንደ ዓይንና እንደ ጆሮ እንደ አፍና እንደ አፍንጫ በቅርጽ የሚለይ አካል አይደለምና ጎደሎ አያሰኝም። ይህም ማለት ሰው በሞተ ጊዜ ልቡ ቃሉና እስትንፋሱ ይለዩታል። በአካል ያለው ሕይወት ስለተለየው እገሌ ሞተ ይባላል እንጂ አካሉ ጎደለ አይባልም። አካሉም ከፍጹምነቱ ሳይጎድል በአልጋ ላይ ተኝቶ ይታያል። ኂላም በመግነዝ ተይዞ ፍጹም አካሉ ወደ መቃብር ይወርዳል። ኂላም በትንሳኤ ዘጉባኤ ነፍሱ ካለችበት ወጥታ ስታድርበት ልብ ቃል እስትንፋስ ያለው ሕያው ሁኖ ይነሳል። ልብ ቃል እስትንፋስ በነፍስ አካል ያለ ለሥጋ ሕይወት የሚሆን የባሕርይ ከዊን ነው እንጂ እርሱ ራሱ አካል እንዳይደለ ይታወቃል። እግዚአብሔር ማለት የባሕርይ ስሙን አያስረዳም። እንኳን የእግዚአብሔር ነፍስ እንኳን የነፍስ የባሕርይ ስሟን አያመለክትም። የባሕርይ ስሙን ማወቅ ፍጹም አይቻልም። መለኮት ማለት ስሙ ለማይታወቅ ባሕርይ መጠሪያ ሊሆን የሚነገር ስሙ እንጂ የጠባይዕ ስሙ አይደለም። አብን ፈጣሪ ሲለው ዘዳ.12፣6 "አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ" ይላል። ወልድን ፈጣሪ ሲለው ዮሐ.1፣3 ወቦቱ ኩሉ ኮነ ይለዋል።ዙሮ ዙሮ ግን በወልድ ቃልነት ነው። ሁሉም በየቃሉ አንድነት መጮህ አይደለም ይህ ከመመርመር የራቀ ነው። ዱለተኞች አንድ ላይ ተመሳሳይ ቃል እንደሚጮሁት አይደለም። ይህማ ቢሆን በየራሳቸው ቃል አላቸው በተባለ ነበር። ኃይል ክሂል ሥልጣንም አንድ ነው አይከፈልም።

በወልድ አካል ያለች ክሂል ሥልጣን ኃይል በአብና በመንፈስቅዱስ አካል ያለች አንዲት ናት፡፡ አብ አንስኦ ወተንሳእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ ቢል አንድ ነው፡፡ በአብ አካል ብቻ ወይም በመንፈስ ቅዱስ አካል ብቻ ባለ ኃይል ክሂል ሥልጣን ተነሳ እንዳይሉ ንስትሥ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሠሉስ ዕለት አነስኦ አለ ለልየ እሜጥዋ በፈቃድየ ብሏል፡፡ አነ ውእቱ ትንሳኤ ወሕይወት አለ፡፡ በኃይል በክሂል በሥልጣን በሚሰራ በባሕርይ ሥራ በሦስቱ አካላት መለያየት እንደሌለ የሚያስረዳ ነገር ከሙታን ተለይቶ መነሳት የክርስቶስ አካል ብቻ ግብር ሲሆን ማስነሳት የሦስቱ አካላት የባሕርይ ግብር ነው፡፡ ዕሪና የሚነገር በአካል ላይ በሚወድቅ ምሥጢር ነው፡፡ ሕልውናውም የሚነገር በከዊን ላይ በሚነገር ምሥጢር ነው፡፡ ዋሕድናም የሚነገር ስለባሕርይ ነው፡፡

ጌራ መደኃኒት

አዘጋጅ ዲ/ን አባይነህ ካሤ

ቃለ አብ፣ ተዋሕዶ

ዕብ.11፣3 “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል ተዘጋጁ” ሲል የእግዚአብሔር ቃል የተባለው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ዘመን ከተቆጠረ ፍጥረት ከተፈጠረ ወዲህ አብ ወልድን አልወለደውም፡፡ ሃይ.አበ.19፣1-9 ኢወለዶ አብ እምድህረ ዘመን እንዲል፡፡ ቃል እምቅድመ ዓለም የተወለደውን ልደት ትስብእት ከመለኮት ሲዋሐድ ገንዘቡ አደረገው፡፡ ቀዳማዊ መለኮት የደኃራዊ ትስብእትን ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ፡፡ መዋሐድ አንድ መሆን ማለት ሲሆን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አካላት እርስ በእርስ ተስማምተው ተዋድደው የሚያስገኙትን ውጤት ያመለክታል፡፡ በቱሣሔ መጠፋፋት ሲኖር በተዋሕዶ ግን ተአቅቦ አለ መጠፋፋት የለም፡፡ ሃይ.አበ 96፣1-17 እስመ ለምንታዌ አእተታ ተዋሕዶ፡፡ ተአቅቦ ትስብእትና መለኮትን ከውላጤ ከቱሳሔ የሚጠብቅ ምሥጢር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ ብላ ስታስተምረን አካላዊ ቃል በማኅጸነ ማርያም በአደረ ጊዜ በህልውና ገንዘቦቹ የሆኑ የአብ ልብነትና የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ለሥጋም ገንዘብ ሁነውታል ብላ ነው፡፡ ተዋሕዶ የሚለውን ቃል መጠሪያዋ ያደረገች ብቸኛዋ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ሌሎች ኦርየንታል አኃት አብያተ ክርስቲያናትም ቢሆኑ ምሥጢረ ሥጋዌን ሲተረጉሙ እንጂ ተዋሕዶ የሚለውን ቃል እንደኛ መጠሪያቸው አላደረጉም፡፡ ነሥአ ተወክፈ ስንል እመንገለ ሥጋሁ እንላለን እንጂ እመንገለ መለኮቱ አንልም፡፡ ሥጋ ቅድመ ተዋሕዶ ነዳይ ድኃ ነበረ፡፡ ስለዚህም መንሳት መቀበል ይስማማዋል፡፡ በጊዜ ተዋሕዶ አምላክነትን ፈጣሪነትን ሁሉን ቻይነትን ምልዐትን ረቂቅነትን ሥጋ ከመለኮት ተቀብሏል፡፡ እኔና አብ አንድ ነን ሲል መንፈስቅዱስን ትቶ አይደለም፡፡ የአንድነትን ባሕርይ የሚገልጹ ስለሆኑ በአንድ ወይንም በሁለቱ መገለጣቸው የሌላውን ግብር የሚያገል የሚያስቀር አይደለም፡፡ ሃይ4.አበ.124፣2፣39 መንፈስቅዱስ ፈጠረ ሎቱ እምድንግል መቅደሰ ሲል መፍጠር የመንፈስቅዱስ ብቻ ነው ማለት አይደለም የአንድነት ግብር ነውና፡፡ ሃይ.አበ.34፣5፣10 ወነሥአ እምኔሃ ሥጋ ፍጹመ ዘፈጠሮ ለርእሱ ሲል መፍጠር የወልድ ብቻ ነው ማለት አይደለም የአንድነት ግብር ነውና፡፡ ኀደረ

ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር ሲል ኀደረ ገንዘቡ አደረገ ሲል ነው። በግብረ አብ ሰው ሆነ በግብረ ወልድ ሰው ሆነ በግብረ መንፈስቅዱስ ሰው ሆነ ብንል ሁሉም አንድ ነው። አላዋቂ ሥጋን ስለተዋሐደ መለኮት አላዋቂ ሆነ አንልም። አላዋቂ የነበረ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ እንላለን እንጂ። ከተዋሕዶ በኋላ ነጣጥሎ ማሰብ አይገባም። ዐርገ እግዚአብሔር ሲል ስለሥጋ እንግድነት ነው እንጂ እግዚአብሔር ወጣ ወረደ አይባልም። መጻሕፍት አብ ወልድን አከበረው ብለው አልቀሩም ወልድም አብን አከበረው ይሉናል። ይህ መከባበር ግን በፈጣሪና በፍጡር መካከል ባለመከባበር ሥርዓት አይተረጎምም በአንዲት ባሕርያዊ ሥልጣን በአንድነት በዕሪና ባሉ መካከል ባለ ግንኙነት ይነገራል እንጂ።

ትምህርት፣ ምርመራ፣ አንድምታ ትርጓሜ

ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትን በቅዱሳት ሥዕላት ታስተምራለች። (በዜማ በቅኔ ስልትም በተለያዩ ጥበባት ስታስተምር ቆይታለች ወደፊትም ታስተምራለች)። ወንጌል በቤተ ክርስቲያን ሲጠቀስና በሰይጣን ሲጠቀስ መልእክቱ አንድ ሆኖ አያውቅም። ቃለ እግዚአብሔርን ሰይጣንም ለማሳሳት ጠቅሶታል። ግን የጠቀሰበት አግባብ ልክ አይደለም። ስለዚህ መናፍቃንም ከብሉይ ከሐዲስ ከሊቃውንት ቢጠቅሱ አትደንግጥ እኛን ለማሳሳት ነው። መናፍቃን ክህደታቸውን ከእኛ ትምህርት ጋር ቀላቅለው ስለሚያቀርቡ በትኩረት ልንከታተላቸው ይገባል። አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ መሄድ አደጋው ትልቅ ነው። የቃልን አገባብ አይቶና ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም መስጠት በየትኛውም የቋንቋ ሰዋስው የተፈቀደ ነው። ለአንድ ቃል የዐውዱን ሀሳብ ተከትሎ ተገቢውን ትርጉም መስጠት በቤተክርስቲያን ነባር ሕገ ትርጓሜ ነው። (ቅዱሳት መጻሕፍትን ስታነብ እያንዳንዷን የዓረፍተ ነገር ቅንጣት ከአገባብ ጀምሮ ከዓረፍተ ነገሩ ሀሳብ ጋር ያላትን ግንኙነት መመርመር አለብህ እንጂ አድበስብሰህ ምንም ነገር ልታልፍ አይገባም)። ሊቅነት የሚያውቁትን መስጠት እንጂ ወደግል አስተሳሰብ መጠምዘዝ አይደለም።ምንም ማስረጃ ሳያቀርቡ መተቸት መፈረጅ አሉባልታ ነው። (ትርጓሜ አንድን ዓረፍተ ነገር እስከ ቅንጣቱ መጨረሻ ማሰብ ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ ጌታ ኤ ብሎ ስለዓይን አካላዊ ባሕርያትና ግብራት ሂደ ማብራራት ነው። አንድን ቃል እንዲሁ መተው ሳይሆን ከሌላው ጋር ያለውን ውህደትና አካላዊ ግብራዊ ጠባይ አብራርተው ይሄዳሉ። አካል፣ ባሕርይ፣ ህልውና፣ ኩነት ወዘተ የሚሉት ቃላት በዚህ መልኩ በምርምር ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኙ እንጂ በልብ ወለድነት ሃይማኖተ አበው ላይ የተቀመጡ አይደለም። መናፍቃን እነዚህን ቃላት የማያውቋቸው መጽሐፍ ቅዱሱን በጥልቀት ስለማያውቁት እና ዝም ብለው ከላይ ከላይ ብቻ ስለሚጨልፉ ነው። የቃሉን ትርጉም ባሕርይ ጠባይ ግብር ሳያውቁ ስለሚናገሩ ነው። በዚህ በዚህ ቤተክርስቲያናችን ምንኛ ጥልቅ ናት። ስለዚህ የብሉይን የሐዲስን ትርጓሜ እንደገና እንዴት እንደተረጎሙት ለምን እያንዳንዱን ቃል ለማስገባት እንደፈለጉ ከቃሉ ጋር ለማብራሪያ ያስቀመጡት ምን ግንኙነት ቢኖረው ነው የሚለውን መርምር። የሐዋርያት ቃል ትርጓሜንም ያስተባበረ ነው። የሆነ ቃል ሲናገሩ ስለዚያ ቃል ግብር አካላዊ ገጽታ ትርጉም በደንብ አውቀው ነው ሳያውቁ አይናገሩትምና። ከእነርሱ በኋላ የተነሡት ደግሞ ለሚማረው አካል እንግዳ እንዳይሆንበት ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጌታ የተናገሩትን ነገር ዓረፍተ ነገር ከዓረፍተ ነገሩ አወቃቀር ጀምሮ ስለእያንዳንዷ ዓረፍተ ነገር ቃላት ሰሚው እንዲረዳው ነው። ሐዋርያት ነቢያት

ያን ቃል ተረድተውት ነው የጻፉት መቼም ሳይረዱት አልተናገሩትም። ተረድተው ከተናገሩት ደግሞ ያንን ቃል ትርጓሜውን አካላዊ ባሕርይውን ዓውዳዊ ትርጉሙን ግብሩን ምንነቱን በሚገባ ያውቁታል። ለእኛ ግን እንዳይከብደን ያንን ቃል የኋላ ሊቃውንት በደንብ እየተረጎሙ አስረዱን። ሐዋርያትም የተናገሩት ነገር እነዚህን ነገሮችና ከእነዚህም በተጨማሪ ያሉትን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንጂ ሳያውቁ አልተናገሩትም። የኋላ ሊቃውንት ደግሞ እኒህን እያብራሩ የሐዋርያትን ጥልቅ እይታ አስረዱን። ይህም ማለት ለምሳሌ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ የሚለውን ለመረዳት። ሙሴ ተረድቶት ጻፈው።ሙሴ የተረዳበትን መንገድ ለማወቅ ግን እኛ በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር፣ ሰማይ፣ ምድር፣ ፈጠረ የሚሉትን ቃላት ፍቻቸውን ባሕርያቸውን ግብራቸውን ሁኔታቸውን ማወቅ አለብን። አንድምታ ያደረገው ይህንን ነው። ሰማይን ሥዕለ ማይ አለ ይለዋል ስለሰማይ ቀለም እየነገረን ነው። ከዚያ ከውሃ እንደተፈጠረ ይነግረናል። ከዚያ ስለምድር ለም መሆኗን በተጨማሪም ሥር ድንጋይ ውሃ ስላላት በሰው ጅማት ደም እየመሰለ እያብራራ ይነግረናል። አንድምታ ይህን ሁሉ ማብራራት ያስፈለገው ቃሉን በደንብ እንድንረዳው ነው። መናፍቃን ግን ቃሉን ሳይረዱ የተጻፈውን ብቻ ይናገሩታል ምን ማለት ነው ስትላቸው ቃሉን ለማብራራት የግድ ወደ አሁኑ ቋንቋ ይሔዳሉ። ይህ ደግሞ ያን ጊዜ የተጻፈበት ቋንቋ እና ያሁኑ ስለሚለያይ ተመሳሳይ አረዳድ እንዳይኖር ስለሚያደርገው ወደ ልብ ወለድ ይሄዳሉ)። መዝ.33፣5-6 “የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች ብሎ አብን፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ብሎ ወልድን ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ይገልጻል። (ቃል ወልድ እስትንፋሰ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነውና ድንቅ ትርጓሜ ማለት እንዲህ ነው። ሌሎችንም እንዲሁ በደንብ መርምራቸው ዝም ብሎ የገባ ትርጓሜ የለም። በኋላ በታወቁ እውቀቶች የፊቱን በደንብ መግለጽ ይቻላል። ይህም ማለት ስለሥላሴ በብሉይ ምንም ዓይነት ግንዛቤ ሳይኖር ግን ተነግሯል። ለማብራራት ግን ያን ጊዜ አይቻልም ነበር። በኋላ ጌታ መጥቶ ያስረዳንን መነሻ አድርገን በብሉይ የተጻፉትንም በሐዲስ መነጽርነት ያኔ ግልጽ ያልነበሩት አሁን ይተነተናሉ። ስለዚህ በኋላ በተገኙ ቃላትና እውቀቶች የኋላውን እናመሰጥረዋለን። በአንድምታ እንተረጉመዋለን። በእያንዳንዱ ቃላት ላይ ከተተረጎመው ውጭ በሚገባ በሌላ አመሰጣጠር ተጨማሪ ትርጉም መተርጎም ትችላለህ ትርጓሜ አላለቀምና ስትተረጉም ግን የተረጎምከው ነገር ከሚተረጎመው ቃል ጋር ያለው ግንኙነት በደንብ የተመሳከረ መሆን ይገባዋል። አለቃ ጎሩይ አድማሱ ጀንበሬ እንዲህ ይለዋል ይሉ የነበረ በዚህ አግባብ ነው። አባ ኤስድሮስ ግን እንዲህ ብለዋል የሚባለውም በዚህ መንገድ ነው። በሆነ ጥቅስ መነሻ አድርጎ አንድ መናፍቅ ኑፋቄውን ሊያስተላልፍ ይችላል። ስለዚህ አንተ ያ ጥቅስ ተጠቀሰልኝ ብለህ ኑፋቄው እውነት ነው ወደሚል ፋላሲ አትግባ። ጥቅሱን የጠቀሰልህ ኑፋቄውን እንድትቀበልለት ስለሆነ በጥቅሱ ምክንያት ኑፋቄው ልክ ነው ብለህ ከመደንገጥ ጥቅሱን ለብቻ ኑፋቄውን ለብቻ ከነተባሉበት አግባብ ተረድተህ እይታህን አስፋው። ጥቅሱን እስከ መጨረሻው ኑፋቄውንም እስከ መጨረስ በተለያየ መለኪያ ገምግመህ ያዝ እንጂ አትነዳ። ምሳሌ ማለት እንደ አማናዊው ያልሆነ ግን ስለ አማናዊው የሚያስረዳ የሚመስል ነው። ምሳሌ ዕጸጳጦስ የሥጋዌ ምሳሌ ሆናለች። ለጊዜው ሌላ ነገርን ለማስረዳት ለሙሴ የታየች ብትሆንም ለኋላው ሥጋዌ ግን ደንበኛ ምሳሌ ስለሆነች የኋላ ሊቃውንት በእመቤታችን በሥግው ቃል ወዘተ መስለዋታል

በተለዋጭ ዘይቤም ተጠቅመዋታል ማርያምን ዕፀ ጳጦስ ይእቲ ይሏታል። በምሥጢር እንጂ ከዕፀ ጳጦስ እመቤታችን ትበልጣለች። ስለዚህ ምሥጢሩን ምሳሌውን ብቻ በማየት ዕፀጳጦስ ይእቲ ብለዋታል እንዲህ እንዲህ እያለ ዕፀ ጳጦስ ወደፊትም እንደየጊዜ ግብሩ በሌላ ልትመሰል ትችላለች። ያልተመሰለውን መመሰል አንዱ የትርጓሜ ሥልት ነው። በእርግጥ መጀመሪያ እያነበብከው ያለው ትዕዛዝ ነው ጥያቄ ነው ወይስ ዓረፍተ ነገር ወይስ አድናቆት ብለህ መርምረህ ቀጥለህ ስላለፈ ነገር ነው የሚናገር ወይስ ስለአሁን ወይስ ስለወደፊቱ ትንቢት የሚለውንም መመርመር ይገባል)። (ትርጓሜ ምሥጢርንም ያካትታል ንባብ ብቻ አይደለም። ነበልባል ሐመልማሉን አላቃጠለውም የሚለው ንባብ ነው። በዚህ ንባብ ምን ሊያስተላልፍ ፈለገ ብለን የምናገኘው ሀሳብ ምሥጢር ነው። በትርጓሜ መካከል ሊቃውንት ይህን አይሻም ሲሉ ይገኛሉ ይህ የሚያመለክተው የሚመሰለው ምሳሌ ከአማናዊው የሚቃረን ወይም ግንኙነት አልኖረው ሲል ግማሹን መስለው ያልተመሰለውን አይሻም ይሉታል። ሌላው ሐተታ የሚለው ምርመራ ነው ስለዚያ ቃል ከሌላ ቅዱሳት መጻሕፍት የተገኙ ሀሳቦችን እያቀረበ ከቃሉ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚመረመርበት ነው። ይህስ አይደለም ከዚህ አንጻር ይህ ነው እያለ ሀሳቦችን ከቃሉ ጋራ ያላቸውን ግንኙነት የሚመረምርበት ነው። ሐተታ ቃሉን ከብዙ አቅጣጫ አስቀምጦ በዶግማዊ እይታ ብያኔ መስጠትንም ያጠቃልላል። ታሪክ ጉዳዩ ግልጽ እንዲሆን ከሀሳቡ ጋር የሚስማማ የሆነ ድርጊትን ማሳያ ነው)። በንባብ ብቻ የሚሆን አንዳች ነገር ስለሌለ መጻሕፍትን ምሥጢራቸውን በርብሮ መረዳት ያስፈልጋል እንጂ ላይ ላዩን መብረር ወደሞተ ነፍስ ያደርሳል። (በአገባብ ጥያቄን አስፍቶ ማየትም ይገባል። ለምሳሌ አንድ ሰው ወደጎጃም ሄደ ሲል። ለማን ለምን ከማን እስከማን ወደማን ስለማን ከማን ጋር በማን ከዚያ በምን ለምን እስከምን ወደምን ከዚያ ወደየት በየት እስከየት ከዚያ ለመቼ ከመቼ እስከመቼ እያልክ በሌሎችም ቃለመጠይቅ እያሰፋህ መጠየቅ አለብህ በእያንዳንዱ ጥያቄ ደግሞ ለምን የሚል እያስገባህ መርምረው)። መጻሕፍት ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቅቁም። ያለፈውን እንደሚመጣ የሚመጣውን እንዳለፈ የመናገር ልማድ አላቸው። ዘይቤ አለመጠንቀቅ ምሥጢርን አያፋልስም። ማስረጃ የሌለው ክስ ዳኝነት አያሰጥም።

ኑፋቄ፣ መናፍቅ

ጸጋዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የጸጋ ልጅ ሆነ ይላሉ። ቅባቶች መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የባሕርይ ልጅ ሆነ ይላሉ። የመጣበትን ቦታ መሠረት ያደረገ ፍረጃ በቀድሞ አባቶች ዘንድ አልነበረም። የምድር ዜግነት ሌላ የመንግሥተ ሰማያት ዜግነት ሌላ። ሁለቱ ሲደበላለቁ እንደዚህ ያለ መሠረታዊ ችግርን ይወልዳሉ። ቅባቶች ተዋሕዶ ሁለትነትን እንጂ ንዴትን አላጠፋም ይላሉ። ዲያብሎስ ጌታን ሊፈትን በገዳመ ቆሮንቶስ በሞከረ ጊዜ የጠቀሳቸው ቃላት ሁሉ ከመጻሕፍተ ብሉያት የሚገኙ ነበሩ። ያልተባለ አልጠቀሰም ጥቅሱ መኖሩ ብቻውን ወይም መባሉ ብቻውን የእርሱን ሐሳብ እውነት አያደርገውም። አጠቃቀሱና ትርጉሙ መታየት ስለነበረበት የጠቀሰው ሁሉ አለቦታው ስለነበር ውድቅ ተደርጎበታል። ስለዚህ መጥቀስ ብቻውን አይበቃም።ሊቁን ስለጠቀሱ ብቻ እውነተኛ አያሰኛቸውም። ሊቁ ከሚያስተላልፈው ምሥጢር ጋር ይሔዳል ወይስ አይሔድም የሚለው መመዘን ይኖርበታል እንጂ። (ምንም ዓይነት ኑፋቄ በአመክንዮ ጠንካራ መስሎ ቢመጣ የራስህን አስተምህሮ በጥሩ መሰረት ከመሰረትክ

አያስደነግጥህም አንተ የያዝከውን የያዝከው በመጽሐፍ በሊቃውንት የተደገፈ ነውና ያን ጠቅሰህ ትረታዋለህ። አንተ የያዝከው ያለ መሠረት ከሆነ ግን ትፈራለህ ትደነግጣለህ በቀላሉ ኑፋቄ ወደልብህ እንደይገባ ከፈለግህ አንተ የያዝከውን ነገር በጥራትና በጥሩ መሰረት ያዝ። ያኔ ኑፋቄ እልም ድርግም ይላል። እንኳን ልትደነግጥና ልትፈራ ኑፋቄውን ከነመናፍቁ ታስፈራዋለህ እንደነ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ)። ዘር ሃይማኖት ሁኖ አያውቅም።

ግብረ ሥላሴ፣ ሥላሴ

የሥላሴን አንድነት የሚያመለክተውን መለኮትን ለአካል ግብር ቅጽል አድርጎ ማቅረብ (ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሠራጺ መለኮት) ማለት ሦስቱም ወላድያን ሦስቱም ተወላድያን ሦስቱም ሠራጽያን ማለት ነውና ግብርንና ሥምን ያፋልሳል። አንድነት ሦስትነትን ያጠፋል ያደናግራል። ወደዮሐንስ ተአቃቢ ክህደት ያመራል። አብን መድኃኒት እንለዋለን መንፈስቅዱስን መድኃኒት እንለዋለን ወልድን መድኃኒት እንለዋለን አምላካዊ ግብር ነውና። ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ሲል መንፈስቅዱስ ብሎ አድሎ ተናገረ እንጂ የሦስቱም ባሕርያዊ ግብር ነው። መለኮት እንደ አካላት የማይከፋፈል አካላትን በህልውና የሚያገናዝብ ነው። አካላትን በህልውና የሚያገናዝብ በመሆኑ መለኮተ አብ መለኮተ ወልድ መለኮተ መንፈስቅዱስ እንላለን። ሥላሴን አካላት በሚለያዩበት በግብር ስም ጠርቶ መለኮት ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ አይባልም። የባሕርይ ገንዘብ ማለት የሚሄድ የሚመጣ ሳይሆን በህልውና የጸና የማይለይ የማይርቅ ማለት ነው። ለምሳሌ ሰው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ አንዱ በሆነው በመሬትነት ምክንያት የሚታይ የሚዳሰስ የሚጨበጥ ግዘፍ ያለው አካል ነው። ስለሆነም ግዙፍነት የሥጋ የባሕርይ ገንዘቡ ነው ማለት እንችላለን። ሰው መባል ካለ ይህ ባሕርይ ከሰው አይለይም። ምንጊዜም በሰውነት ውስጥ አለና። መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ የባሕርይ ሕይወትነት ገንዘባቸው ነው ስንል በህልውናቸው የጸና ነው ማለታችን ነው። በህልውና የጸና ከሆነ መቼም መች አይርቅም አይለይም። መጻሕፍት እጅግ አስገራሚና አስደናቂ የሆኑ የእግዚአብሔርን ረቂቅ ሥራ የሚናገሩ ድርጊቶችን በመንፈስቅዱስ አድራጊነት መግለጽ ልማዳቸው ነው። የተሰወረውን በመግለጥ ከሦስቱ አካላት በብዛት የሚጠራው መንፈስቅዱስ ነው። ይህም በተለየ ግብር ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን ከረቂቅ ድርጊቶች ጋር የማዛመዱ ልምድ ስላለ ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያን መንፈስ ቅዱስን ለምን አታለልክ ብሎታል። ይህ የባሕርይ ግብር ስለሆነ ወልድን ለምን አታለልክ መንፈስ ቅዱስን ለምን አታለልክ አብን ለምን አታለልክ ቢል የባሕርይ ግብር ስለሆነ እግዚአብሔርን ለምን አታለልክ ለማለት ነው። ማቴ.1፣18 ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች ቢልም የሦስቱም ስራ ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስ በተለየ ግብሩ ያደረገው ነው አያሰኝም። እንዲህ ዓይነት የተለየ ግብር የለውምና። ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ቢልም ያው ነው። በመንፈስ ቅዱስ እንደተነገረ በአብም በወልድም ሊነገር የሚችል ግብር አምላካዊ ይባላል። መሥረጽ ግን ለመንፈስ ቅዱስ እንደተነገረ ለአብ መነገር ስለማይችል አካላዊ ግብር ይባላል። ለሥላሴ ወላዲ አስራጺ ተወላዲ ሰራጺ ከማለት አልፎ ሌላ ተደራቢ ግብር መቀጸል አይቻልም (ስለዚህ በመጻሕፍት አንዱ ተጠቅሶ ሲመጣ ይህን የመሰለ ሌላ ነገርም ሲመጣ አካላዊ ነው ወይስ ባሕርያዊ ግብር የሚለውን መመርመር አለብን)። (ከሰው አሰራርና ልምድ ያፈነገጠውን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ማለት የተለመደ ነው)።

ዮሐ.16፣13-15 “ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል” ሲል ክርስቶስ ስለመንፈስ ቅዱስ እንዲህ ስለተባለ መንፈስ ቅዱስን ተቀባይ ወልድን ሰጪ አድርገን አንናገርም። ዮሐ.15፣36 እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ስላለ ወልድን ላኪ መንፈስቅዱስን ተላኪ አንልም። ጉዳዩ የሰጪና የተቀባይ ሳይሆን በፈቃድ ተገናዝበው በህልውና አንድ መሆናቸውን ያሳያል። ጌታችን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ማለቱ እየታወቀ ቅዱስ ጴጥሮስ “ኃጢአታችሁ ይሠረይላችሁ ዘንድ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ” ማለቱ የሐዋ.ሥራ 2፣38 በህልውና ይገናዘባሉና አንዱ ቢጠቀስም ያሥራ የሁሉም ነውና። ሃይ.አበው 25፣4፣4 አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በአምላካዊ ግብር እያንዳንዳቸው ቢጠሩበትም ቀጥሎ ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ ብሎ የአንድነት ግብራቸው መሆኑን ያስረዳናል። ክርስቶስ ስለመንፈስ ቅዱስ ሲያስተምር እም ዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ ብሎ ማስተማሩ ቃልነትን በህልውና ከወልድ ገንዘቡ አድርጎ ይናገራል ማለቱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ወልድ የባሕርይ ሕይወቱ እንጂ እንደ ፍጡርና እንደፈጣሪ በመስጠትና በመቀበል የተመሰረተ ግንኙነት የላቸውም። ለአብ ፈጣሪነት አምላክነት ሁሉን ቻይነት ዘለዓለማዊነት የመሳሰሉት ገንዘቦቹ ናቸው ስንል ሳይሸራረፉ ሳይቀናነሱ ሳይከፋፈሉ የወልድም የመንፈስቅዱስም ናቸው ማለት ነው። ማጣት መጉደል ማነስ በሌለበት ተቀባይነት ሊኖር አይችልም።መንፈስ ቅዱስን መቀበል ማለት ጸጋ እግዚአብሔርን መቀበል ማለት እንጂ መንፈስ ቅዱስ እየተቆነጠረ የሚሰጥ ሆኖ አይደለም። መንፈስቅዱስ ሞላበት ሞላባት ማለትም ጸጋ እግዚአብሔር አደረበት አደረባት ማለት ነው። ይህም ፈጣሪ እግዚአብሔር ለፍጡራን ሰዎች የሚሰጠው ስጦታ ነው።

ሰው፣ ልጅነት

ሰው እንደመላእክት መንፈስ ብቻ አይደለም። እንደ እንስሳትም ደመነፍስ ብቻ አይደለም። በአኗኗርም በዚህ ምድር ብቻ እንደ እንስሳት ሆኖ ሊኖር የተፈጠረ አይደለም። የሐዋርያት ልጅነት በጸሎተ ሐሙስ የአበው ልጅነት በዕለተ ዓርብ የምእመናን ልጅነት በጥምቀተ ክርስትና ይሠጣል።

ድንግል ማርያም፣ ቁርባን፣ ዮሐንስ መጥምቅ

መንፈስ ቅዱስ አነጻት ማለት ከሦስት ነገሮች ከለከላት ማለት ነው። እኒህም ሰስሎተ ድንግልና ዘርዓ በእሲ ሩካቤ ናቸው። አንድም በዘር ከሚተላለፍ መርገመሥጋ መርገመነፍስ (ጥንተ አብሶ) ጠበቃት ሲል ነው። የምንቀበለው ሥጋ ወደሙ ነፍስ የጠለየው መለኮት የተዋሐደው ነው። እመቤታችን የወለደችው ሥግው ቃልን ነውና እመ እግዚአብሔር ወላዲተ አምላክ እመ አምላክ የምንላት በተዋሕዶ ምክንያት ነው። መጥምቀ መለኮት ብለን ቅዱስ ዮሐንስንም የምንጠራው በተዋሕዶ ምክንያት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ያጠመቀው ትስብእትን ብቻ ሳይሆን በተዋሕዶ የከበረውን ሥግው ቃልን ነውና።

ደብረ አሚን

አዘጋጅ ዲ/ን መልካሙ በየነ

መመርመር፣ ትርጓሜ

ምእመናን የእኛ የሆነውን ለመለየት ከላይ ያሉ ማራኪ ነገሮችን ብቻ መመልከት ሳይሆን ውስጡ ምን እንደያዘ መመልከት ይገባል። ይህም ራሳቸውን ከኑፋቄ ለመከላከል ይረዳቸዋል። ምሥጢሩን ካልመረመርን ወደ ምሥጢሩ ካልገባን ነገራችን ሁሉ ፈራሽ ይሆንብናል። ድንግል ማርያምን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ባበሠራት ጊዜ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለች። ያለ ወንድ ዘር መውለድ ከዚያ በፊት በየትኛይቱም ሴት ላይ አልታየምና ቢደንቃት ነገሩ ቢገርማት ነው። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ሲላት ነገሩን ተቀበለችው። አንድን ነገር ስሕተት ነው ብሎ ለመናገር ማስረጃ ያስፈልጋል። ጥቅስ ስለተጠቀሰ ብቻ እውነት ነው ብሎ ከመቀበል በፊት የተጠቀሰውን ጥቅስ መመልከት ያስፈልጋል። መናፍቃን የተጣመመ ትምህርታቸውን በጥቅስ ሊያቃኑ ይሞክራሉ። መናፍቃን የተዋሕዶ ልጆችን ለመቀሰጥ ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በታዋቂ ሊቃውንት ስም መነሳት ነው። ታሪክን በመሰለኝ መጻፍ ጥፋቱ ያመዝናል። (ሊቃውንት ከመጨረሻው ለምን ብለው ያገኙት ምሥጢር ላይ ነው ትኩረታቸው። ለምሳሌ የአዳምን ከዕጸ በለስ መከልከል በጾም አመስጥረውታል። ተከለከለ ብቻ ብለው አልቆሙም ብዙ ርእሰ ጉዳዮችን ከገጸ ንባባቸው ጀርባ ያለውን ምሥጢር ሲያመሰጥሩ ሲያራቅቁ ኖረዋል። አዳም እንደእኛ ሆነ የሚለውን በሥጋዌ አራቀውታል። ስለሆነ ጉዳይ የምታቀርባቸው ምክንያቶች ማስረጃዎች ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መሆን አለባቸው። ምንም ግንኙነት የሌለው ነገር ወይም አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት አትጥቀስ አትናገር። ገጽ ያብዛልኝ ተብሎ መጽሐፍ ላይም ይህን የመሰለ ነገር አታድርግ። ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸውን የሊቃውንት የሳይንቲስቶች የቅዱሳንን ንግግር ብቻ አስገባ። አንድ ሰው በፋላሲ ንግግሩ ሊያናድድህ አይገባም ሊያዝናናህና የሰውየው ከንቱነት ሊያሳዝንህ ነው የሚገባው። የተናገረው ልክ ከሆነና ለነፍስህ የሚጠቅም ከሆነ ግን ተግሳጹ አያናድህ ተቀበል ማንም ይናገረው ሕጻንም ሊቅም ጓደኛም መናፍቅም ማንም ይናገረው ተቀበል። ጉዳይህ ከነገሩ እንጂ ነገሩን ከተናገረው ሰው ሊሆን አይገባም)። ማንኛውም ትርጓሜ ትምህርተ መለኮትን የማያፋልስ መሆን አለበት። መስማት ለተሳነው ሰው የመለከት ድምጽ በጆሮዎቹ አይገባም። ማየት የተሳነውም ሰው የፀሐይ ብርሃን አይታየውም።

ዶግማ

ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም እምነት መሠረተ እምነት ማለት ነው። ዶግማ አይጨመርበትም አይቀነስለትም አይሻሻልም አይለወጥም ከጊዜው ጋር ስላልሄደ ስላልተስማማ አስቸጋሪ ስለሆነ ወዘተ በሚል ማንኛውም ምክንያት ማሻሻል መለወጥ መጨመር መቀነስ የለበትም።

ቀኖና

ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ሥርዓት ሥርዓተ እምነት ማለት ነው። 1ኛ ቆሮ.14፣40 “ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን”። ሁሉም የመሰለውን የሚያደርግበት መሆን የለበትም። ሥርዓት እንደአስፈላጊነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ እየታየ ሊጨመርበት ይችላል። ሊሻሻል ሊቀነስ የሚችል ነው። ለምሳሌ ያህል ጥምቀትን በ40 በ80 ቀን የምንጠመቅበት ሥርዓት አለን። ነገር ግን ሕጻኑን ለሞት የሚያበቃ ነገር ካገኘው ከዚያም ቀድሞ በሞግዚት ገብቶ እንዲጠመቅ ሥርዓት አለን። ይህ እንግዲህ ቀኖና ስለሆነ ነው።

አብነት

አብነቶች መሠረታዊ የሆነው ነገር ላይ አንድ ዓይነት አገላለጽ ቢኖራቸውም በያዙት የታሪክ ፍሰት ማብራሪያና ገለጻ ወዘተ ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች ይኖራሉ። ነገር ግን የመሠረተ እምነት እና የቀኖና ወዘተ ልዩነቶችን አያሳዩም። መሰረታዊ ልዩነት የለባቸውም።

ሃይማኖት፣ ክሕደት፣ ኑፋቄ፣ ብራና

ክህደትና ኑፋቄ በብራና ስለተጻፈ ሃይማኖት አይሆንም። ሃይማኖትም በወረቀት ስለተጻፈ ክህደት ሊሆን አይችልም። ብራና ኑፋቄም ሆነ እምነት የጻፉበትን ዝም ብሎ ይቀበላል። ስለዚህ ቁምነገሩ ያለው ብራና መሆኑ ላይ ሳይሆን የተጻፈው ቃል ላይ ነው። እኛ ከእስራኤል እምነቱን ተቀበልነው እንጂ እንደ እስላሞች እምነቱን የተቀበሉበትን ቋንቋ (አረብኛ)፣ ባሕል፣ ጠባይ አልተቀበልንም። የራሳችን ቋንቋ ባሕል አለንና። በግእዝ የተነገረው በግእዝ የተጻፈው ሁሉ እውነት ነው ማለት አይደለም። ግእዝ በመናገሩ ግእዝ በመጻፉ ብቻ ሰውን እውነተኛ ነው ብለን የምናምን ከሆነማ የመላእክትን ቋንቋ የሚያውቀውን ሳጥናኤልን እንመነዋ¡ ስለዚህ ስህተት ስለሆነ እናስተውል። እምነታችንን በቤተ መከራ አናረጋግጠውም። ሃይማኖት የሚቀበሉት በተስፋ የሚረዱት ነው። መቅዶንዮስ “ለአብ መንበር እንዳለው እግዚአብሔርሰ ይነብር ዲበ መንበሩ ቅዱስ ተብሎ ተነግሯል። ለወልድ መንበር እንዳለው መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም ተብሎ ተነግሯል። ለመንፈስ ቅዱስ ግን መንበር እንዳለው የተነገረበት ቦታ የለምና ሕጹጽ ነው ብሎ” ተነሳ። አፈ ጉባኤው ጢሞቴዎስ “በአፈ ኢሳይያስ ነቢይ በዓመተ ሞተ ያዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዊኅ” ያለውን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ተርጉሞብሃል ብሎ ረትቶታል። መናፍቃን የራሳቸውን ፍላጎት በመጻሕፍት እና በሊቃውንት ስም ደብቀው ማስተላለፍ ይፈልጋሉ። መናፍቃን የሚሉትን ነገር ለማለት የሚያስችል ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። ይደግፍልናል ብለው የሚጠቅሱት የሚደግፍላቸው ይመስላቸዋል እንጂ ለኑፋቄያቸው የሚደግፍ ሳይሆን ኑፋቄያቸውን የሚያፈራርስ ነው። ሃይማኖት በመሰለኝ አይመራም።

ስመ ሥላሴ

ስመ አካል፦ ስንል ሥላሴ በአካል ሦስት በመሆናቸው አንዱ አካል ከሌላው ተለይቶ የሚጠራበት ነው።

ከዊን

አብ በልብነቱ ከዊን ለራሱ ብቻ አዋቂ ሆኖ አይቀርም። ወልድና መንፈስ ቅዱስም አዋቂዎች ይሆኑበታል እንጂ ገንዘባቸው ነውና። ወልድ በቃልነቱ ከዊን ለራሱ ብቻ ተናጋሪ ሆኖ አይቀርም አብና መንፈስ ቅዱስም ይናገሩበታል እንጂ ምክንያቱም ገንዘባቸው ነውና።መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋስነት ከዊኑ ለራሱ ብቻ ሕያው ሆኖ የሚኖር አይደለም። አብና ወልድም ሕያዋን ሆነው ይኖሩበታል እንጂ ምክንያቱም ገንዘባቸው ነውና።

ልደት

እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ የሚለው ቀዳማዊ ልደቱን ወአነ ዮም ወለድኩከ የሚለው ደኃራዊ ልደቱን ይገልጻል። ወለድኩህ ማለቱ ግን አብ ሁለተኛ በሥጋ የሚወልደው ሆኖ አይደለም። የቃል ገንዘብ ሁሉ ለሥጋ ገንዘቡ ነውና በሥጋው ወልደአብ ተባለ። አብም ልጁ ወልድ የተዋሐደውን ሥጋ ልጁ አለው ማለት ነው እንጂ። ምሳ.8፣24-25 ተራሮች ሳይመሠረቱ ከኮረብቶች በፊት እኔን ወለደኝ። ይህ የጌታ ቀዳማዊ ልደት ከፍጥረታት መፈጠር አስቀድሞ እንደሆነ ያስረዳናል።

ተዋሕዶ፣ ተአቅቦ

መጻሕፍት ከተዋሕዶ በኋላ የሥጋን ገንዘብ ለመለኮት የመለኮትን ገንዘብ ለሥጋ አድርገው መናገር ልማዳቸው ነው። ፍጹም ሰው ሆነ ብለን የማንቀር ፍጹም አምላክ ሆነም ብለን የምንናገር የሆንነው በምሥጢረ ተዋሕዶ ነው። ተአቅቦ ማለት መጠባበቅ አለመጠፋፋት ማለት ነው። ሥጋ ከመለኮት መለኮት ከሥጋ ጋር ሲዋሐድ አንዱ አንዱን ሳያጠፋው አንዱ አንዱን ሳይለውጠው ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ከሁለት አካል አንድ አካል ሆኖ መኖር ነው። የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ፍጹም ተዋሕዶ ነው። ፍጹም የምንለውም መከፈል መለወጥ መለየት መነጠል መቀላቀል መደባለቅ ማደር መጨመር የሌለበት ስለሆነ ነው። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ ሲል ከበረ ሥጋ አከበረ ቃል ነው። ሆኖም እነዚህን ቃላት የምንነጋገራቸው ቃልና ሥጋ በተዋሐዱበት ጊዜ (ቅጽበት) ብቻ ነው። ከዚህ ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ልንቀጽለው አይገባም። ቅድመ ተዋሕዶ ሥጋ በሥጋነቱ መለኮት በመለኮትነቱ አካልና ባሕርይ ያለበት ጊዜ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ለቃል የሚነገረው ለሥጋ ለሥጋ የሚነገረውም ለቃል ይሆናል። በአነጋገርም በአጻጻፍም "በ" የምትል ፊደል ጨምረን በሥጋው በመለኮቱ እያልን እንገልጻለን እንጂ "በ"ን አጥፍተን ሥጋው መለኮቱ አንልም። ሥጋው ተራበ ማለትና በሥጋው ተራበ ማለት በጣም ይለያያል። ሥጋው ተራበ ስንል መለኮትና ሥጋው መዋሐዳቸውን አያመለክትም። በሥጋው ተራበ ስንል መለኮት በሥጋው ተራበ ማለታችን ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ ብሏል። አልአዛርን ወዴት አኖራችሁት በማለት ጌታ የጠየቀኮ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ ካልሆነ በቀር ለአምላክ መቃብሩ ጠፍቶት አይደለም። እኔና አብ አንድ ነን ማለቱ ሥጋውን ፍጹም አምላክ ማድረጉን መናገሩ ነው። ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም ብሏል። ከሰማይ የወረደው ቃል ነው። የቃል ገንዘብ ለሥጋ ገንዘቡ መሆኑን መናገር ካልሆነ በቀር ሥጋውን ከሰማይ ይዞት መጣ

አንልም። ደቀመዛሙርቱን በተዘጋ ቤት ገብቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ይህ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ገንዘቡ እንደሆነ ሊያስረዳን ካልሆነ በቀር ግዙፍነት ባሕርዩ ለሆነ ሥጋ በተዘጋ ቤት መግባት እንዴት ይቻላል? ብረት ጥቁርነት ግዙፍነት ቁረት ባሕርዩ ነው።የእሳት ደግሞ የሙቀት የረቂቅነት ባሕርይ አለው። ብረት ከእሳት የገባ እንደሆነ ግዙፍነቱን ሳይለቅ የእሳትን ገንዘቦች በሙሉ ገንዘቡ ያደርጋል። እሳትም ረቂቅነቱን ሳይለቅ የብረትን ገንዘቦች በሙሉ ገንዘቡ ያደርጋል። ይኸውም ሊታወቅ ቁረት ገንዘቡ የነበረ ብረት የእሳቱን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ የሚያቃጥል ይሆናል። ረቂቅ የማይጨበጥ የማይዳሰስ የነበረው እሳትም የብርትን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ የሚጨበጥ የሚዳሰስ ይሆናል። በመዶሻ ይቀጠቀጣል። ልዩ መጠሪያው የጋለ ብረት ነው። ብረቱ ከእሳት ጋር በመዋሐዱ ወደ እሳትነት እሳቱም ወደብረትነት አይለወጥም። ብረቱ የትስብእቱ እሳቱ የመለኮቱ ምሳሌ ነው። ብረት ከእሳት ጋር ተዋሕዶ የጋለ ብረት ተዋሕዶ መለኮትም ከትስብእት ጋር ተዋሕዶ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል ሥግው ቃል ተብሏል። ብረት የእሳትን እሳትም የብረትን ባሕርይ ገንዘብ እንዳደደረጉ መለኮትም የሥጋን ግዘፍነት ጠባብነት ውስንነት ደካማነት መራብን መጠማትን መድከምን ገንዘቡ አድርጓል። ሥጋም የመለኮትን ገንዘቦች ረቂቅነትን አምላክነትን ፈጣሪነትን ምሉዕነትን ፈታሒነትን አንጻሒነትን አጽናዒነትን አክባሪነትን ገንዘቡ አድርጓል። የጋለ ብረት በመዶሻ መመታቱም በብረትነቱ ነው እንጂ በእሳትነቱ አይደለም። በክርስቶስም መራብ መጠማት መቸንከር መሰቀል መሞት መድከም ወደመለኮቱ አልደረሱበትም። እኒህ ሰው በመሆኑ የሚነገሩ ናቸው። በሥጋው ተራበ ብንልም ቅሉ በመለኮቱ ረኃብ ደረሰበት አንልም። ብርሃን ጨለማን ለማስወገድ ሌላ ብርሃን አይሻም እርሱ ራሱ ብርሃን በመሆን ጨለማን ያስወግዳል እንጂ። ቃልም ራሱ ክቡር ስለሆነ ሥጋን ሲዋሐደው አከበረው እንጂ ሌላ አክባሪ አልሻም። ዮሐ.17፣19 አነ እቀድስ ርእስየ ሲል በተዋሕዶ ማለቱ ነው። እኔ ሲልም በቃል ርስት ሆኖ ነው። እኔ ብሎ አምላክነቱን አክባሪነቱን ራሴን ብሎ ሰውነቱን ከባሪነቱን ይናገራል። እርሱ ራሱ አክባሪ ከባሪ ነው። ሃይ.አበው 2፣5 ዘአንገሥ ለሥጋ አዳም በመንፈስቅዱስ ወረሰዮ ቅዱሰ ወማኅየዊ ሲል በመንፈስቅዱስ አዋሐጅነት ማለት ነው። ማዋሐድ ደግሞ የሦስቱም ሥራ ነው። ቤተክርስቲያን ማክበርን ለአንዱ አካል ብቻ ለይታ አትሰጥም የሦስቱም ባሕረትያዊ ግብር ነውና። አብ አከበረ ወልድ አከበረ መንፈስ ቅዱስ አከበረ ቢባል አንድ ነው። ማክበር የሁላቸው ነውና። ኢሳ.61፣1 መንፈሰ እግዚአብሔር ዘላዕሌየ ዘበእንቲአሁ ቀብዐኒ በህልውናየ ያለ መንፈስ ቅዱስ ስለከዊነ ትስብእት ያዋሐደኝ ማለት ነው። ማዋሐድ የሦስቱም ግብር ነው። ባሕርያዊ ግብር ነው። አርጋኖን “ዘተቀባዕከ ሥጋሃ ለማርያም” ይላል። የማርያምን ሥጋ የተዋሐድክ ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ለወልድ ዓለማት ሳይፈጠሩ በፊትም ገንዘቡ ነው። ሞተ ዘኢይመውት ስንል የማይሞተው መለኮት በሥጋ በመወሐዱ በሥጋው ሞተ ማለት ነው። እኛ በተዋሕዶ ከበረ ስንል አካላዊ ቃል የተዋሐደውን ሥጋ አከበረው ማለታችን ሲሆን ይህ የማክበር ግብርም አምላካዊ እንጂ አካላዊ ግብር ስላልሆነ የሁሉም ግብራቸው ነው ማለታችን ነው። ቀባኢነት የባሕርይ ግብር እንጂ ለአካላት ተለይቶ የሚሰጥ ክብር አይደለም። ስለዚህ አብ ቀባኢ ወልድ ቀባኢ መንፈስ ቅዱስ ቀባኢ ቢል አንድ ነው። ሥጋ የለበሰውን ወልድ ተቀባኢ ብንለው ችግር የለውም ነገር ግን ቀባኢው ራሱ ነው። አብ ነው መንፈስቅዱስ ነው ብለን እንጨምርበታለን ለአብ ያለው ሁሉ ለወልድም አለውና። የባሕርይ ማለት በማንም የማይወሰድ

ማንም የማይለውጠው ማንም የማይቀማው ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለወልድ የባሕርይ ሕይወቱ አብ የባሕርይ አባቱ ነው ስንልም ከዓለም መፈጠር በፊት ሕይወቱ የሆነ መንፈስ ቅዱስ ከማንም አይቀበለውም ማንም አይወስድበትም አይለወጥበትም ማለት ነው። ሕይወትነት የመንፈስቅዱስ የተለየ ግብሩ አይደለም ይህ ግብር የሥላሴ አምላካዊ ግብር ነው። ሕይወትነት የመንፈስቅዱስ ከዊን ነው። ለመንፈስቅዱስ ከሠራጺነት ለወልድ ከተወላዲነት የወጣ አካላዊ ግብር የላቸውም። ስለዚህ ሕይወትነትን የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ግብር ማድረግ ስህተት ነው። ግብረ መንፈስ ቅዱስ ስንል በድንግልና መጽነስን በድንግልና መውለድን መናገራችን በረቀቀ አምላካዊ ወይም መለኮታዊ አሰራር ማለታችን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ከበረ ማለታችን አይደለም። ተዋሕዶ የሚለው የእምነታችን ስያሜ መሆን የጀመረው ከጉባኤ ኤፌሶን ጀምሮ ነው። ክርስቶስ ቅቡዕ መሢሕ የተቀባ ማለት ነው። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ ምስጢር "አንበሳ ይሰመይ በእንተ መዊኡቱ ወመሢሐ በእንተ መንግሥቱ" ይላል። እኛ ለሊሁ ቀባዒ ወለሊሁ ተቀባኢ ወለሊሁ ቅብዕ እንላለን። ሉቃ.9 ፣18-20 "ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ" ይላል። ከዚህ ላይ እግዚአብሔር ስንል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው። ስለዚህ የተቀባ ማለት እግዚአብሔርነትህ ያከበረህ ማለት ነው። ይኸውም በተዋሕዶ መክበሩን እንጂ በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ መክበሩን አያሳይም። መዝ.2፣2 ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ መሢሑ። መሢሑ ያለው እግዚአብሔር ወልድ ሰቅለውታልና። እግዚአብሔር ያለው እግዚአብሔር አብን ወልድ ቢነክ አብ ይነክ እንዲሉ ይላል።

ሚጠት

ሚጠት ማለት በትረመሴ እባብ ከሆነች በኋላ ተመልሳ በትር መሆን ነው። የጌታ ተዋሕዶ ግን እንበለ ሚጠት ነው።

የልጅነት ጥምቀት፣ የቁደር ጥምቀት

የቁደር ጥምቀት ልጅነትን ለማግኘት ሳይሆን የቀደመ ልጅነትን ለመመለስ የሚፈጸም ጥምቀት ነው። የልጅነት ጥምቀት ልጅነትን ለማግኘት ይፈጸማል። ክህነት በሌላቸው በመናፍቃን ዘንድ መጠመቅ እንደ እንቁራሪት እንደ ጉማሬ በውሃ ተዘፍቆ ከመኖር ውጭ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳድር የልጅነት ጥምቀት አይደለም። ጥምቀት አንዲት ናት ስንል የልጅነት ጥምቀትን የምናገኝባትን ጥምቀት ማለታችን ነው። የቁደር ጥምቀት እንደ አስፈላጊነቱ የሚደገም የሚሠለስ ነው። ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው ቢያጠምቅ ልጅነት ስለማያስገኝ እንደ ጥምቀት አይቆጠርም። ስለዚህ በቅብዐት ካህናት የተጠመቁ ሰዎች አማኒ ሊሆኑ አይችሉም። ፍትሐ ነገሥት 3፣24 ወለእመቦ ብእሲ ዘተወክፈ ጥምቀተ እምአላውያን ኢኮነ ምእመነ። ይህ ማለት ግን ጥምቀት ተደገመ ተሠለሰ ማለት አይደለም በመናፍቃን የተጠመቀው ጥምቀት አንድ ተብሎ አይቆጠርምና። በሐዋርያት ሥራ 19፣1-6 በቅዱስ ዮሐንስ የተጠመቁት መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ይላል ነገር ግን ከቅዱስ ዮሐንስ የንሥሓ ጥምቀት ተጠመቁ ይላል።

መድሎተ ጽድቅ ቅጽ ፩

አዘጋጅ፡- ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋራ ከመዋሐዳቸውና አንድ አካል ከመሆናቸው የተነሳ እርስ በእርሳቸው ፍጹም በሆነ ፍቅር ይዋሐዳሉ፡፡ የጊዜ የቦታ የዘር የቋንቋ ወዘተ ልዩነቶች ይጠፉና አንድ አካል እንሆናለን፡፡ (ትንቢት አያስገድድም፡፡ አስገዳጅ አይደለም ይሁዳ ትንቢት ተነገረበት እንጂ ጌታን እንዲሸጥ አስገዳጅ አልሆነም፡፡ የነነዌ ትንቢትም ትንቢቱ አስገዳጅ ስላልነበረ ንሥሓ ገብተው ድነዋል)፡፡

አምላክ፣ ክርስቶስ፣ ተዋሕዶ

የጌታን የዘር ሀረግ ሲጠቅስ ምንታዌን አጥፍቶ በሉቃ.3፣23-28 የአዳም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ብሏል፡፡ ከተዋህዶ በኋላ የአካልም የባሕርይም ምንታዌነት የለም፡፡ 1ኛ ቆሮ.1፣8 አውቀውስ ቢሆን የክብር ጌታን ባልሰቀሉትም ነበር ይላል፡፡ የክብር ጌታ መለኮት ብቻ ነው እንዳንል ሰቀሉት አለ፡፡ የተሰቀለው ትስብእት ብቻ ነው እንዳንል የክብር ጌታ አለው፡፡ ስለዚህ የተሰቀለው ያው አንዱ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ነው፡፡ አንጾኪያዎች ነገረ ተዋሕዶን የተመለከቱት ከሰብአዊ አቅጣጫው ነበር፡፡ የእስክንድርያዎቹ ደግሞ ምሥጢራዊና ረቂቅ ከሆነው ከአምላክነቱ ጀምረው ነበር፡፡ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች ታላላቅ አባቶችም መናፍቃንም ወጥተዋል፡፡ ዮሐንስ አፈወርቅ ከአንጾኪያ ነው፡፡ mono-physite ማለት አንድ ነጠላ ባሕርይ ማለት ሲሆን mia-physite ማለት ግን ከሁለት ነገሮች የተዋሐደ አንድ ማለት ነው፡፡ የተዋሕዶ ትምህርት ይዝኛው ነው፡፡የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለቁርሎስ በ1882 ዓ.ም የቅድስና ማዕርግ ሰጥተዋለች፡፡ ባስልዮስ ዘቂሳርያ እግዚአብሔርን በባሕርዩ መገለጫዎች እናውቀዋለን ብለን አስረግጠን መናገር የምንችል ሲሆን በባሕርይ ግን ሊታወቅና ሊደረስበት የማይቻል ነው ይላል፡፡

መናፍቃን፣ ምርመራ፣ ታሪክ፣ ዕውቀት

በዘመናችን መናፍቃን የማይተቹት የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ትችቱ ደግሞ በአብዛኛው እኛ የምናምነውን ሳይሆን እነርሱ እኛን ያምኑታል ብለው የገመቱትንና ሰዎችን ከቤተክርስቲያናችን በቀላሉ ለማስኮብለል ያመቻል ብለው ራሳቸው ፈጥረው ያቆሙትን ምስል መትተው በመጣልና ስለእኛ ራሳቸው በማፍረስ ጀግኖችና አዋቂዎች በመምሰል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ለመተቸት የሚነሳ ሰው የሚተቸውን ነገር በተጨባጭ መኖሩን ካላሳየ ነገሩ ትችት ከመሆን ይልቅ ሆነ ተብሎ በድንቁርና በተንኮል ወይም በጥላቻ ፍጹምነት ላይ ለመድረስ የሚደረግ ጉዞም ይመስላል፡፡ የሆነ ሆኖ ያልታያቸውን ነገር በንጹሕ መነጽር ማሳየት የተቹትንም ጉዳይ በእውነተኛ የእውቀት ሚዛን መዝኖ ትክክለኛነቱን እንዲያዩት መርዳት ከአንድ እውነተኛ አገልጋይ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ የመናፍቃንን ጽሑፍ በየዋህነት ብቻ ለተመለከተው ሰው ምናልባትም ቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔርን የማታውቅ በሰዎች ልማድ የተጀመረ ሰው ሰራሽ መስሎ እንዲታየው ለማድረግ ያልተጠቀሙበት ዘለፋና

ነቀፋም ሆነ ነውረኛ ቃላትና አገላለጽ አለ ለማለት ያስቸግራል። መናፍቃን ራሳቸውን የእውነት ጠበቃና አዳሽ አድርጎ ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት ቀድሞ ጀምሮ በነ መርቅያን ሳይቀር የነበረ ነው። ሐዋርያትን ትክክለኛውን ትምህርት የበረዙ አድርጎ ትክክለኛው የሙሴ ኦሪት ነው የሚሉ ነበሩ። አርዮስም ኦርቶዶክሳውያን አባቶችን አንድ ገጽ የሚለውን የሰባልዮስን ኑፋቄ የሚከተሉ ሰባልዮሳውያን ናቸው እያለ ራሱን የእውነተኛው ሃይማኖት ጠበቃና መምህር አድርጎ ለማቅረብ ይሞክር ነበር። እንኳን አማኝ ነኝ የሚል ሰው ቀርቶ ሰይጣንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ የመናፍቃን ጥንካሬያቸው በራሳቸው አስተምህሮ ላይ ሳይሆን እንደ ዝንቦች የእኛን ቁስሎች ደካማ ጎኖች በመፈለግና እነዚያ ላይ በመረባረብ ነው ይል ነበር። ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ጉዳይ ሊኖር ይገባል። ዋና ዋናዎቹ የመናፍቃን መነሻዎችና መሰረቶች በነገረ ሃይማኖትና በታሪክ ላይ ይመስለኛል እያሉ መናገርና ማመን በሐሰት መናገር ከእምነት ይልቅ በሚታየውና በሚሰማው መታመንና በመሳሰሉት የተመሰረቱ ናቸው። በዚህም ላይ ተገቢ ያልሆኑ አባባሎችንና አገላለጾችን መጠቀም ከመገለጫዎቻቸው መካከል አንዱ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከቀደምት አበው መጥቀስ ብቻውን የትክክለኛነት መለኪያ አለመሆኑ ግልጽ ነው። 2ኛ ጴጥ.1፣19-20 በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። 2ኛ ጴጥ.3፣16 ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። መሰለኝ በጎደለ መረጃና በስሜት የተመሰረተ ነው። ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃ ያልተገኘለትን ሳይሆን አይቀርም ሲነገር ተሰምቷል መገመት ይቻላል ልንገምት እንችላለን እያሉ መናፍቃን በመሰለኝ ይናገራሉ። ሃይማኖት ግን ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴ.5፣37 እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ ወፈድፋደሰ እምእሉ እምእኩይ ውእቱ ባለው መሰረት እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማለት እንጂ ከዚያ ወጥቶ ይመስላል ሊያስኬድ ይችላል ይሆን ይሆናል መገመት ይቻላል...ወዘተ እያሉ መቀባጠር ምናልባት ለሰብአዊ አስተሳሰቦችና ለምድራዊ ርእዮቶች ካልሆነ በስተቀር ለክርስትና ቦታ አግባብነት የለውም። መናፍቃን ቤተክርስቲያን የማታምነውና የማትቀበለውን እንደምታምን እያስመሰሉ በሐሰት መጻፍና መናገር ዋና ጠባያቸው ነው። የሆነ ሰው ገድል በሆኑ ሰዎች ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተረጎመ ማለት ቅድስናውን ቤተክርስቲያን ተቀበለችው ማለት አይደለም። አንድ ሰው ገድል ስለተጻፈለትና መልክ ስለተደረሰለት ብቻ ቤተክርስቲያኒቱ ዘንድ በቅዱስነት ተቀባይነት አግኝቷል ማለት አይደለም። እንደዚሁም ደግሞ በየቦታው ኖረው ብዙዎችን ማንም ሰው ሳያውቃቸው ያለፉ ገድልና መልክእ ሊጻፍላቸው ቀርቶ ከእነስማቸው እንኳ ሳይታወቁ ያለፉ ብዙ ቅዱሳን አሉ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም አባ እስጢፋኖስን ጻድቅ ብላ የተቀበለችበት ውሳኔ የለም። ለአጼ ዘርዓ ያእቆብም ታቦት አልቀረጸችም።በእርግጥ ልበ አምላክ የተባለው ዳዊትም ኦርዮን አስገድሏል ንሥሓ ገብቶ ዳነ እንጂ። የሆኑ ሰዎች ለኃይለ ሥላሴ መልክዕ ደርሰውላቸው ነበር ታዲያ መልክዕ የተደረሰለት ሁሉ ቅዱስ ተብሏል ማለት ነውን? በጭራሽ። መናፍቃን አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በቤተክርስቲያን ሥርዓት (ተክሊል) ሁለት ሚስቶች አግብተዋል ይላሉ። ንጉሡ በራሱ መንገድ ያደረጋቸው ነገሮች የራሱ ድርጊቶች እንጂ የግለሰቦችን ስህተት ከቤተክርስቲያን ለማስጠጋትና ለማሳበብ መሞከር ፍጹም ስህተት ነው። ቤተክርስቲያን የምትለውን ትምህርቷን መቃወም ሲያቅት የማትለውን ትላለች እያሉ መጻፍና የሐሰት ወሬ ማውራት የአቅመ ቢስነት መገለጫ ነው። መናፍቃን ዶክተር ዮራን ላርሰን

“የኒቅያ ጉባኤ አሳዛኝ ነው” ብሏል ብላችኋል። በእርግጥ ይህን ሰው አላውቀውም ነገር ግን አርዮሳዊ ወይም አይሁዳዊ ከሆነ ሊያገዝን ይችላል። ከእምነት ይልቅ በስሜት ሕዋሳት ላይ ላይ መመስረት አንዱ የመናፍቃን ጸባይ ነው። የስሜት ሕዋሳት አስተማማኝ የእውቀት ምንጭ አይደሉም። የእውነት መለኪያው ለማስረዳትና ለመረዳት ያለው ቅለትና ክብደት አይደለም። ለምሳሌ መናፍቃን አብርሃምሂ ርእየ ወተፈሥሐ የሚለውን የወንጌል ቃል አብርሃም በአጸደ ነፍስ ሆኖ ሊያይ አይችልም ሌላ ትርጓሜ ያሻዋል ይላሉ። ይህ በራሳቸው መረዳት ብቻ መወሰን ስለሆነ ስህተት ነው። በሃይማኖት የሚገኘው እውቀት ሰው ተመራምሮ የደረሰበት እውቀት ወይም ግኝት አይደለም። ሃይማኖት ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ወይም የተገለጠ ነው። በሃይማኖት የሚገኘው እውቀት ሰው ተመራምሮ የደረሰበት እውቀት ወይም ግኝት አይደለም። ጴጥሮስ ጥያቄውን በመለሰ ጊዜ ማቴ.16፣15-17 “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም ብጹዕ ነህ” ብሎታል። የሃይማኖት ምንጩ ጌታ ባይሆን ኖሮ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተመለከተ ጴጥሮስ የሚኖረው እውቀት በዘመኑ ከነበሩት ሌሎች ሰዎች የተለየና የተሻለ ሊሆን አይችልም ነበረ። ነገር ግን ከዚህ ዓለም ሥጋዊ ምርምርና ፍለጋ ውጭ የሆነው እግዚአብሔር እውነቱን ገለጠላቸው። 1ኛ ቆሮ.2፣4-5 እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ይላል። **ኑፋቄ** ማለት ጥቂቱን ተቀብሎ ሌላውን ደግሞ አለመቀበል ወይም መጠራጠር ነው። ቅዱስ ፖሊካርፕስ መርቅያንን የዲያብሎስ የበኩር ልጅ ይለው ነበር። ቅዱስ አግናጥዮስ ደግሞ መናፍቃን መርዝን የተመሉ ናቸው ይል ነበር። እንዲሁም በሰው መልክ ያሉ አራዊት ናቸው ይላቸው ነበር። በ2ኛውና በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያንን ሲያውኳትና ሲፈትኗት የነበሩ መናፍቃን ብዙ ናቸው። **ግኖስቲኮች** ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ትምህርት ርቃለች እንግዳ ትምህርት ታስተምራለች እያሉ ይቃወሟትና ያብጠለጥሏት ነበር። በተጨማሪም በተጠማቅያን ውሃ ውስጥ ገብተው ምንም ነገር ሳይዙ በባዶ የሚወጡ እያሉ ሊቀልዱባቸውና ሊያፌዙባቸው ይሞክሩ ነበር ጳጳሳትን ካህናትን ሙሰኞች ሥልጣን የጠማቸው ስስታሞች እያሉ መራራና ጠንካራ በሆኑ ቃላት ይሰድቧቸውና ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲጠላቸውና እንዲጸየፋቸው በማድረግ ከቤተክርስቲያን እየኮበለለ ወደ እነርሱ ጎራ እንዲገባ ለማድረግ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሂዱ ነበር። እያንዳንዱ ሰው ክርስቶስን እርሱ በተረዳው መንገድ በማመን ያለ ምሥጢራት አስፈላጊነት ይድናል ይሉ ነበረ። ቁስ አካላዊ የሆነ ነገር ሁሉ ክፉ ነው ይሉ ነበር። ከዚህ የተነሳም እግዚአብሔር ጸጋውን ለመስጠት ቁስ አካልን (በውሃ መጠመቅን፣ በሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ማሳደርን፣ በኅብስቱና በወይኑ ሥጋው ደሙን) ይጠቀማል ማለት በእነርሱ አስተሳሰብ ነውር ነው። ግኖስቲኮች ጌታን ከአምላክ እየወጡ ይመጣሉ እንደሚሏቸው Aeons (ብናኞች) አንዱ አድርገው ይመለከቱት ነበር። **መርቅያን** በየጊዜው ትዝ ባለ ቁጥር ከወንጌል እየቀነሰ እያወጣና እንደ አዲስ እየጻፈ እርሱ ትክክለኛ ወንጌል የሚለውን ጽፎ ሳይጨርስ ነበር የሞተው። ከፍተኛ ዋጋና ቅድሚያ ይሰጥ የነበረው ለመልእክተ ጳውሎስ ነበር። ከዚህም ከእርሱ ንድፈ ሀሳብ (ቲዎሪ) ጋር የማይሄዱትን ሀሳቦች እየቀነሰ ያወጣቸው ነበር። ከዚያም የራሱን ሀሳብ በምትካቸው ያገባ ነበር። እሳቤውንና ጽንሰ ሀሳቡን ሳይረዱ ሕገ ኦሪትን የሚነቅፍ የሚመስላቸውን በእጅጉ እያጎሉ ለማሳየት ይሞክሩ ነበር። **ሰባልዮስ** ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር በሆነ ዘመን የተገለጠበት የመገለጫ መንገድ ብቻ ነው የሚል ክህደት ይዞ ተነስቶ

ብዙ ሞኞችን አስከትሏል። **አርዮስ** ወልድን አብ ፈጠረው ከአብ ያነሰ ነው አለ። **ቴዎዶር እና ዲያድርስ** ኢየሱስን እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ካደረባቸው ከነቢያትና ከሌሎች ሰዎች ትንሽ ብቻ ከፍ ያለ እንጂ ሌላ የተለየ ነገር የለውም ይላሉ። **ጀሺኒያን** እመቤታችን ጌታን ስትጸንሰው ድንግል ነበረች ስትወልደው ግን አይደለችም ሁሉም ኃጢአት እኩል ነው ይል ነበር። ምንኩስናንና የድንግልና ሕይወትን የሚነቅፍ መጽሐፍ ጽፎ ነበር። **ቪጂላንቲየስ** ለአጽመ ቅዱሳን ክብር መስጠትን ይቃወም ነበር። በሌሊት በቤተክርስቲያን የሚደረጉ ጸሎታትን ይቃወም ነበር። **ማርቲን ሉተር** july 2,1505 በድንገት መብረቅ ከፊቱ ወደቀበት። ከመደንገጡና ከመፍራቱ የተነሳ ወደ ቅድስት ሐና ጮኸ። ከዚያ ቢተርፍ መነኩሴ እንደሚሆን ቃል ገባ። በኋላ ምንኩስናው ከበደው ተስፋ ቆረጠ። አውግስጢኖስ እግዚአብሔር በማይመረመር ውሳኔው የተወሰኑትን ሰዎች ይድኑ ዘንድ ለሕይወት አስቀድሞ መርጦአቸዋል (pre-destination) ይል ነበር። ሉተር ይህን ሲያይ ለመዳን ካልተመረጡት መካከል ብሆንስ የሚል ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ደረሰበት። ከዚያ ከጭንቀቱ ይገላግለኛል ብሎ ያሰበውን መዳን በእምነት ብቻ ብሎ ተነሳ። ሉተር ዮሐንስ አፈወርቅን ይነቅፈው ነበር። ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙንም ምንም ነገር ያልሆነ ባዶ ይላቸው ነበር። ሉተር ከእሾህ (ካቶሊክ) ሸሽቶ ከጋሬጣ (ኑፋቄ) ወደቀ። ማነጽ እንደማፍረስ መሥራት እንደመተቸትና እንደመቃወም ቀላል አይደለም። ተሐድሶዎች ለአለቃቸው ለዲያብሎስ የውስጥ አርበኞች ሆነው ይሰራሉ። ግኖስቲኮች የብሉይ ኪዳኑ አምላክ ጨካኝ ነው ይሉ ነበር። ነገሩን ሁሉ በየምንነቱ ከማየት ይልቅ ማደባለቅና ማምታታት የመናፍቃን መለያ ጠበያቸው ነው። ከመሰረቱ ያልጠራና ያልጀመረ ነገር ጥራዝ ነጠቅ የመሆንና ወደ ስህተት የማምራት እድሉ ሰፊ ነው። የንስጥሮስ እሳቤ መሰረቱ እምነት ሳይሆን ልምድና የስሜት ሕዋሳትን ማመኑ በዘመኑ ሥጋዊ ዕውቀት መንተራሱ ነው።ይህ ደግሞ ከእምነት ጋር ይጋጫል። ለምሳሌ በዘመኑ እውቀት ማንም ያለ ወንድ ዘር አይጸነስም ይህን የእመቤታችንን ጽንሰት በእምነት ካልሆነ በሳይንስ አታረጋግጠውም። በመጽሐፍ ቅዱስ **መንፈስ** የሚለው ቃል **1ኛ** መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል መዝ.138፣7 ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ እንዲል። **2ኛ** ጸጋን ያመለክታል ዘጸ.31፣3 በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት እንዲል። **3ኛ** ነፍስን ያመለክታል ኢዮ.12፣10 የሰውም ሁሉ መንፈስ በእጁ ናት እንዲል። **4ኛ** ቅዱሳን መላእክትን ዕብ.1፣14። **5ኛ** ርኩሳን መናፍስትን ያመለክታል። 1ኛ ዮሐ.4፣1-3 መንፈስን ሁሉ አትመኑ እንዲል። እኔ ያልደረስኩበትና ያልቻልኩት ነገር ሁሉ ስህተት ነው ማለት የመናፍቃን ስራ ነው። በተለያዩ ዘመናት መፈጸማቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግበው የምናገኛቸው ነገሮች በአህዛብ ዘንድ በተለያየ መልክና ሁኔታም ቢሆን ይታወቁ ወይም ይነገሩ የነበሩ መሆናቸው ምንጫቸው ከአረማውያን ፍልስፍና ነው አያሰኛቸውም። ለምሳሌ በኖኅ ዘመን ስለተፈጸመው የጥፋት ውሃ ታሪክ በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አይደለም የተጻፈው ምንም እንኳ ከጣዖታዊ ልማዳቸውና ተረቶቻቸው ጋር ቢያደባልቁትም ከመሰረታዊ ዓላማው አርቀው ቢሆንም እንኳ ታሪካዊ ጭብጡ ግን በተለያዩ ሕዝቦችና ባህሎቻቸው ስለጥፋት ውሃ ይታወቅና ይነገር ነበር። ስም በመቀየር አንዳንድ ተጨማሪ አስተሳሰቦችን በመጨመር ትንሽ ጭብጥ ብቻ ይዘው በልብ ወለድ በማስፋት ሊሆን ይችላል። ይህ የሆነው የኖህ ልጆች ሲበታተኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተመዘገበው ታሪካዊ ድርጊት በድንግዝግዝም ቢሆን ግንዛቤ ነበራቸው ማለት ነው። በተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ

ቁርጥራጭና ሽርፍራፊ እውነቶች ነበሩ። በምልዐት ያለው ግን በቤተ ክርስቲያናችን ብቻ ነው። ለሰዎች በተፈጥሮ የተሰጣቸው ንጽሕናንና ቅድስናን መውደድ በተለያዩ አህዛባዊ የጥንት ሰዎች ዘንድ ስለታየ ወይም ስለተነገረ በክርስትና ውስጥ እንዳናየው ሊባል አይገባም። ከዓለም ተለይቶ በገዳማት መኖር ቀድሞ በቡዲህስቶች በኤስያውያን ዘንድ ነበረ ብለን እኛ ገዳማዊ ሕይወትን ከእነርሱ ወረስነው አያሰኝም። **ቅዱሳት መጻሕፍትን** ስታነብ የነገሩ መነሻ ጭብጥ ያ ቃል ከመነገሩ በፊት የነበሩ ሁኔቶች ልምዶች ምን ነበሩ? በኂላስ የሚለውን መርምረው። ስለጉዳዩ አካላዊ ስነልቡናዊ ታሪካዊ እንዲሁም ማንኛውንም ማንነቶቹን ጠይቆ ተመራምሮ መረዳት ይገባል። ለምሳሌ ማቴ.6፣16-18 ስትጾሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ ይላል። ከዚህ ላይ ግብዝ መጠውለግ መጾም የሚሉትን ቃላት ማወቅ ይገባል ይህን ያለው ማን ነው? ጌታ ለምን (ሰራኤ ሕግ ስለሆነ) የሚለውንም ማወቅ ይገባል። ጉዳዩ ስለምን ነው ስትል ስለጾም አፈጻጸም የተቸው ጾሙን ነው ወይስ አፈጻጸሙን? አፈጻጸሙ እንዴት ነበረ ለማን ነበር መሆን የነበረበት ስንል ጾም ሰው ሊጠቀም ወደ እግዚአብሐየር የሚቀርብ ነው። ጸሐፍት ግን ለሰው ወደሰው ታይታ ስላደረጉት ተቻቸው። ጾምን ለውዳሴ ከንቱና ለታይታ የሚያደርጉት ሰዎች የሚጾሙት ከእግዚአብሔር ዘንድ በጾም የሚገኘውን ዋጋ ለማግኘት ሽተውና ተስፋ አድርገው ሳይሆን እንዲሁ ሰዎች እንዲያመሰግኗቸው ጾመኛ እንዲሏቸው ስለሆነ ያንኑ የፈለጉትን ዋጋ ከሰዎች ስለተቀበሉ ሌላ ዋጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የላቸውም ማለት ነው። ከዚህ አያይዘህ ስለግብዞች በብሉይ በሐዲስ ምን ተባለ ስለጾም በብሉይ በሐዲስ በሊቃውንት ምን ተባለ መቼ የት ተርእዮ እንደማይጠቅም የሚያስረዳ ሌላ ከየት ምን ምን አለ? መናፍቃን ከሐድያን ስለጉዳዩ ምን ይላሉ? ለምን መነሻ መድረሻ እያልክ ተመራመር።

ሰው፣ ጸጋ፣ ነጻ ፈቃድ፣ ሃይማኖቶች

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ድንቅና ልዩ በሆኑ በብዙ ጸጋዎች አክብሮ ፈጥሮታል። ከእነዚህ ጸጋዎች አንዱና ታላቁ የጸጋዎች ሁሉ አክሊል ሊባል የሚችለው ንግበር ሰብአ በአርዓያነ ወበአምሳሊነ የሚለው ነው። ማንኛውም ሰው በፈለገው ማመን ወይም አለማመን ሰው በመሆኑ የተሰጠው ተፈጥሮአዊ ጸጋ ነው። ይህን መብት የሰጠውም የነጻነት አምላክ የሆነው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሰውን እኔ የፈጠርኩትን አየርና ውሃ ፀሐይና መሬት ወዘተ እየተጠቀምህ እኔን አለማመን አትችልም ወይም እኔን ከማመን ውጭ ሌላ አማራጭ የለህም አይልም። በፍጹም ነጻነት ፈጥሮናል እንጂ። ስለዚህ ማንም ሰው የሚያምነውን ነገር መከተል ነጻነቱም መብቱም ነው። በዓለማችን ላይ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ እምነታዊ አስተሳሰቦችና ልማዶች የኖሩትና ያሉትም ከዚህ እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ፍፁም ነጻነት የተነሳ ነው። እግዚአብሔር አባትነቱንና አምላክነቱን ሽተውና ወደው እርሱን የሚፈልጉትና የሚያፈቅሩት ሰዎች ብቻ በእውነተኛ መንገድ እንዲያመልኩት እንጂ ማንም ሰው ያለ ውዴታው እንዲያመልከው አይፈልግም። ይህ ከእውነተኛ ፍቅርና ከነጻነት ጋር አብሮ አይሔድምና። እውነተኛ ፍቅርና ነጻነት ማለት ሌላውን አስገድዶ የራስን ፈቃድ ማስፈጸም ሳይሆን የሌላውንም ፍላጎትና ምርጫ ማክበር ነውና። ስለዚህ ፍጥረታትን አህዛብ ሲያመልኩ መናፍቃን ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለእነርሱ አስተሳሰብና አካሄድ የሚመቹ የመሰሏቸውን ጥቂት ጥቅሶች ወይም ሀሳቦች ብቻ ዘግነው ወይም አጠቃላይ ሀሳቡን አዛብተው ሲነጉዱ እርሱ

የነጻነት አምላክ ነውና ድርጊታቸው ስህተትና ኃጢአት ቢሆንም እርሱ ግን በትእግስት ይመለከታቸዋል። ይህም የዚህ ዓለም አኗኗር እስኪፈጸም ድረስ ይቀጥላል። እስከዚያ ድረስ ጌታ መልካሙን ዘር ይዘራል ጠላትም እንክርዳዱን ይዘራል። እስከ ጎልቀተ ዓለም ድረስ ልዩ ልዩ ዓይነት የክህደትና የስህተት ትምህርቶች ከምድራችን በተለያየ መልኩ ይኖራሉ።እስከ መከር አብረው ይደጉ ተብሏልና። ከዓቅሙ አንጻር መድከም የነበረበትን ያህል ያልደከመ ሰው ቅጣት ይገባዋል ብሏል ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ። ኃጢአት የባህርያችን ቢሆንማ ኖሮ ኃጢአትን መሥራት አያስፈርድብንም ነበር። ሰው ሆኖ አለመራብ አለመጠማት አለማዘንና አለመደሰት አይችልም ይህ የባሕርዩ ነውና። እግዚአብሔር ሰውን ነጻነት ያለው ክፉውንና በጎውን መለየትና መምረጥ የሚችል አዋቂና አስተዋይ አድርጎ ፈጠረው። ለዚህም ይረዳው ዘንድ ክፉ እውቀትን ወደማወቅ እንዳይሄድና የሚኖረው እውቀት ሁልጊዜም መልካም የሆነ ይሆንለት ዘንድ መልካምና ክፉ ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ በማለት ዘፍ.2፣16 አዘዘው። አዳም ሕጉን ቢጠብቅ ወደ ኢመዋቲነት ሊሸጋገር ባይጠብቅ ደግሞ ወደ መዋቲነት ሊወርድ በሙሉ ነጻነት ተፈጠረ። ሰው ክብሩን በማጣቱ ምክንያት ከእርሱ ላነሱ ሥነ ፍጥረቶች ተገዛ እነርሱን መፍራትና ማምለክ ጀመረ። ክርስቶስ በስሜት ሕዋሳት ሊመረመሩና ሊታወቁ የሚችሉ ነገሮችን ብቻ አይደለም የሰጠን። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሰራና ጸጋውን ሲያሳድር በሚታዩ ቁሳዊ ሀልዎት ባላቸው ነገሮች አማካኝነት መጠቀሙንና መስራቱን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየን እውነታ ነው። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሰራ ያለ ሥነፍጥረት አማካይነት እንዲሁ በቀጥታም ይሰራል። እንዲሁም ደግሞ በፈጠራቸው ሥነፍጥረታት አማካይነትም ይሰራል።ለምሳሌ ጌታ ሙሴን በበትርህ ውሃውን ምታው ብሎት ተከፍሏል። ዝም ብሎም በራሱ መክፈል ይችል ነበር። ማር.6፣13 ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው። ያዕ.5፣14 በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። በፊታችን መንግሥተ ሰማይ ቀርቦልናል ዘለዓለማዊ እሳትም እንዲሁ ታዲያ እሳቱን የምናመልጠው እንዴት አድርገን ነው? ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንገባውስ እንዴት ነው? የሚሉ ይኖራሉ። እርሱ ራሱ ነግሮናልና ስለዚህ ነገር ራሱ ባለቤቱ የተናገረውን ተማር። ዘለዓለማዊ ሕይወትን በተመለከተ ምስክሮቹና ማስረጃዎቹ ብዙዎች ናቸው። ይህን ዘለዓለማዊ ሕይወት ማግኘት ስንመኝ እርሱን የምናገኝባቸውን መንገዶች ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳዩናል። እግዚአብሔር አምላካችን ደስ ያለውን እንደሚያደርግ አምባገነን ባለሥልጣን አይደለም። ለዚህም ነው ዝም ብሎ ከእመቤታችን ያልተጸነሰው ይኩነኒ ስትል ነው እርሱ የተጸነሰው። በነገረ ሃይማኖት የምናውቀው የተነገረንንና የሆነውን ብቻ ስለሆነ ባልተፈጸመ (ባልሆነ) ነገር ላይ ተነስቶ ሀሳብ መስጠት አይቻልም። ለምሳሌ አብርሃም ይስሐቅን ቢሰዋው ኖሮ ብሎ መጠየቅ አልሰዋውምና ትርጉም የለውም።

ቅዱሳን፣ መምህራን፣ ንዋየ ቅድሳት ቅዱሳት መካናት ጊዜያት

ፖሊካርፕስና አግናጥዮስ የዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀመዛሙርት ነበሩ። ቅዱስ ሄሬኔዎስ የፖሊካርፕስ ደቀመዝሙር ነው። ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመለሱልን አባቶቻችን እውቀታቸውና ትምህርታቸው ምን ያህል ዓለም አቀፋዊና ሁለንተናዊ እንደነበር በግልጽ ያስረዳል። ስለ ቅዱሳን መማርና ማስተማር አስፈላጊ የሆነባቸው ምክንያቶች አንደኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገርና ስለሚያስተምረን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የብዙ አባቶች

ታሪክ ተጽፏል። የእነርሱ መጻፍ እግዚአብሔርን የበለጠ ይገልጠዋል እንጂ አይሸፍነውም። ዕብ.13፣7 የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ። የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው ይላል። እኛም ኑሯቸውን በገድል ጽፈን የምናነበው ለዚህ ነው። እግዚአብሔር በእነርሱ አድሮ የሰራውን ድንቅ ስራ ለማወቅና ለማመስገን ነው። መዝ.67፣35 መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ ይላል። ሌላው የቅዱሳን ሕይወት ሕያው ወንጌል ስለሆነ ነው። የክርስትና ዓላማው ሰዎችን ቅዱሳን ማድረግ ነው። ሮሜ 1፣7 ቅዱሳን ልትሆኑ የተጠራችሁ ይላል። ኢሳ.51፣2 ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም ወደ ወለደቻችሁም ወደሣራ ተመልከቱ ይላል። 1ኛ ቆሮ.11፣1 እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ። አንዱ ለአንዱ እንደሚጸልይ በ1ኛ ተሰ.5፣25 ስለ እኛ ጸልዩ የሚለው ያስረዳናል። ዘጸ.32፣12-14 ከመዓትህ ተመለስ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይሥሐቅን እስራኤልንም አስብ በማለት ሙሴ ተማጸነ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ሊያደርግ ስለነበረው ክፋት ራራ ይላል። ጌታ ፈያታዊውን አጽድቆታል እንደዚሁም ሁሉ በአንዳንድ ቅዱሳን ገድላትና ተአምራት ላይ ኃጢአተኞችን በቅዱሳኑ ምልጃ ማራቸው ቢባል ይህ ሊሆን አይችልም ብሎ መከራከር አይቻልም። የጴጥሮስ ጥላው ሕመማንን ይፈውስ ከነበረ የእመቤታችን ምልጃዋና ጥላዋ በላኤ ሰብእን የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲያገኝ ረዳው ቢባል ይህ ሊሆን አይችልም ሊያሰኝ የሚችል አንዳችም መሰረት የለም። እንደ ስምዖን ሰው እየበላችሁ ብትኖሩም ችግር የለውም የኋላ ኋላ እመቤታችን እያማለደች ታድናችኋለች ብላ ቤተክርስቲያን አታስተምርም። ይህ ተአምር ብቻ ነው ተአምር ደግሞ ለማን መቼ እና እንዴት እንደሚደረግ የሚያውቀው የተአምራት ባለቤት ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ዘጸ.32፣7-14 ላይ ሲታይ እግዚአብሔር ተወኝ ላጥፋቸው ባይ ሙሴ ደግሞ እባክህ ራራላቸው ባይ ሆነው ይታያሉ። ነገር ግን ሙሴ የተሾመ እስራኤልን ሊንከባከብ ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር እኔ የምሰጣችሁን ብቻ ወይም ከእኔ የሚወጣውን ፍትሕ ብቻ ዝም ብላችሁ ጠብቁ ከዚያ ውጭ የሚያገባችሁ ነገር የለም የሚል አምባገነን አይደለም። **አማላጅነት ለምን ስንል 1ኛ** የፍቅር መንገድና መገለጫ ነው። ሙሴ እነርሱን ከምታጠፋ እኔን አጥፋ እስከማለት የደረሰው ለወገኖቹ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው። የእውነተኛ ፍቅር መገለጫ ራስን አሳልፎ እስከመስጠት ነው። ዮሐ.15፣13 ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ የሚበልጥ ፍቅር የለም። በክርስቶስ አንድ አካል የሆንን ሁላችን ስለሌላው አካል ማሰብና መጸለይ ይገባናል። **2ኛ** እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያለውን ፍቅርና አክብሮት የሚገልጥበት ነው። ኢዮ.42፣7-8 ኢዮብ ይጸልይላችሁ እንዲል። ዘፍ.20፣7 ነቢይ ነውና ስለአንተም ይጸልያል ትድናለህም ይላል። **3ኛ** እግዚአብሔር ከኃጥአን ይልቅ የጻድቃንን ጸሎት የበለጠ ስለሚሰማ ነው። ምሳ.15፣8 የኃጥአን መሥዋእት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው ስለሚል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ቅዱስ ብርሃን ይለዋል። ቅዱሳንንም እንዲሁ ሲላቸው እናገኛለን። ይህ ስለሆነ ግን እኩል ናቸው አንልም። የእርሱ የባሕርይ የእነርሱ የጸጋ ብለን ለይተን እናስተምራለን እንጂ። አረዳዳችንም ለእግዚአብሔር ሲሆንና ለፍጡራን ሲሆን የተለያየ ነው። ለሰዶምና ለገሞራ ጥፋት ምክንያት የራሳቸው የሰዎቹ ኃጢአት ቢሆንም አስር ጻድቃን ቢገኙ ኖሮ እግዚአብሔር ስለእነዚያ አስር ጻድቃን ሲል ይምራቸው እንደነበር ራሱ ተናግሯል። በዚህም ስለጻድቃን ሲል ኃጥዓንን እንደሚምር በግልጽ ታወቀ። እስራኤላውያንም ኤርምያስን

ኤር.42፣2-3 ስለእኛ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ ብለውታል። የእግዚአብሔር ጸጋ በሰዎች አይገደብም። ሉቃ.5፣18-24 የጣራውንም ጡብ አሳልፈው በመካከል በኢየሱስ ፊት ከነ አልጋው አወረዱት። እምነታቸውንም አይቶ አንተ ሰው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው። የሰዎቹ እምነት የልጁ ኃጢአት እንዲሰረይለት ያደረጉትን አስተዋጽኦ ተመልከት። ማቴ.24፣21-22 ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።2ኛ ጴጥ.1፣4 ከመለኮት ተካፋዮች እንድትሆኑ ይላል። የኤልሳዕ አጽም ሙትን አስነስቷል። ቤተ ክርስቲያንን በቅዱሳን ስም መሰየም ከጥንት የነበረ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንጂ በኋላ ዘመን የመጣ አይደለም። ዕብ.11፣37 በድንጋይ ተወግረው ሞቱ ተፈተኑ በመጋዝ ተሰነጠቁ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ ሁሉን እያጡ መከራን ተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ። እንጦንስ ግንዱን የመነኩሴ ቆብና ልብስ አልብሶት ሰይጣናት መነኩሴ መስሏቸው ፍላጻቸውን ከሩቅ ሆነው ሲወረውሩበት አየ። ጌታ እኛ ማድረግ የማንችላቸው ስለእኛ መዳን ሲል የፈጸማቸው ነገሮች በድንግልና መወለድ ሕማማቱ ስቅለቱ ሞቱ ትንሳኤና ዕርገቱ ናቸው። ሌሎችን ግን ማድረግ የምንችላቸው ስላሉን ተመሰሉ ኪያየ አለን። ጌታችንን እስከተቻለን ድረስ በሁሉም ነገር ልንከተለው ይገባናል እንጂ ወሰንና ዳርቻ አበጅተን እኛ ራሳችን ባወጣነው መለኪያ መሰረት ሊሆን አይገባም። ማቴ.11፣27 ከእኔ ተማሩ ብሏል። ከእርሱ የምንማረው ደግሞ በቃል ያስተማረውንም በተግባር ሰርቶ ያሳየንንም ሁሉንም ነው። (ጌታ በእኔ ያመነ ከእኔ የበለጠ ተአምራትም እስከማድረግ ይደርሳል ያለው ለምንድን ነው? ስንል እርሱ 3 ሰው ከመታን ቢያስነሳ በእርሱ ቸርነት ደግሞ ከዚህ በላይ ያስነሱ ስለሚኖሩ እርሱ 40 ቀን ገዳም ቢቆይ 40 ዓመት የቆዩ ስለሚኖሩ እንጂ በችሎታ በእውቀት ይበልጡኛል ማለቱ አይደለም)። ማቴ.22፣30 በትንሳኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይሆናሉ አያገቡም አይጋቡም ስለሚል ሳያገቡ የመነኮሱ መነኮሳት ስላሉ ስለዚህ ምንኩስና ሥርዓተ መላእክት ተባለ። 1ኛ ቆሮ.7፣32-35 ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል። **ስለቦታ ቅድስና** ዘጸ.3፣1-5 አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ ይላል። 2ኛ ጴጥ.1፣17-18 እኛም ከቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋራ ሳለን ይህን ድምጽ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን ይላል። የጊዜን ቅድስና በተመለከተ ዘፍ.35፣2 ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የዕረፍት ሰንበት የተቀደሰ ቀን ይሆንላችኋል ይላል። በብሉይ ኪዳን የካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ንዋያትን ሁሉ የተቀደሰ እያለ ይገልጻቸዋል። ዘጸ.28፣2-4 ለወንድምህ ለአሮን ለልጆቹም የተቀደሰ ልብስ ያድርጉ ይላል። መሥዋእቱም የተቀደሰ ተብሏል ዘጸ.29፣33 ሌላ ሰው ግን አይብላው የተቀደሰ ነውና። ቦታዎቹም ሆኑ ጊዜያት ወይም ንዋያት የተቀደሱ ያሰኛቸው በተፈጥሯቸው ከሌላው ቦታም ሆነ ጊዜ ወይም የተለየ ነገር ኑሯቸው ሳይሆን እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ሥራውን በተለየ ሁኔታ የገለጠባቸው ስለሆነና ለእርሱው አገልግሎት የተለዩ በመሆናቸው ነው። በዓላት የሚከበሩባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች **1ኛ** የእግዚአብሔርን ሥራ ለማሰብ ለማዘከር ለማስታወስ ነው መዝ.110፣4 ተዝካረ ገብረ ለስብሐቲሁ እንዲል። **2ኛ** መንፈሳዊ ሐሴትን ለማግኘት መዝ.41፣4-5 በቃለ አሚን ወበትፍሥሕት ደምፀ እለይገብሩ በዓለ እንዲል። መዝ.117፣24 ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፈሣሕ ወንትሐሰይ ባቲ እንዲል። ዘጸ.13፣11-16 ልጅህ ይህ ምንድን ነው ብሎ በጠየቀህ ጊዜ እንዲህ ትለዋለህ እግዚአብሄር በብርቱ እጅ ከባርነት ቤት

ከግብጽ አወጣን እንዲል። በሆነ ገዳም ወይም የተቀደሰ ቦታ ወይም ጊዜ ወይም ሁኔታ የሚቀበር ሰው የሚያገኘው ጥቅም ምን እንደሆነ አዋቂው እግዚአብሔር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቅዱሳን አጽም ባረፈባቸው ቅዱሳት መካናት የተቀበሩ ሰዎች የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳገኙ ይታያል። 2ኛ ነገ.13፣20-21

ሃይማኖት

ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠና እኛ ደግሞ ተቀብለነው ኖረንበትና ሕይወትን አግኝተንበት ለሌሎችም የምናወርሰውና የምናስተላልፈው መሆኑን ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ.15፣3 እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ ይላል። 1ኛ ቆሮ.11፣23 ለእናንተ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለመሆኑ ደጋግሞ ይናገራል። ይሁዳ 3 ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ ይላል። ስለዚህ አንድ ጊዜ የተሰጠ እንጂ ሰዎች በመሰላቸው ወይም ባልመሰላቸው ጊዜ እንደሚወስኑት የስብሰባ አጀንዳ አይደለም። የሲኖዶስ እንኳ ድርሻውና ተግባሩ ያን አንድ ጊዜ የተሰጠውን ሃይማኖት መጠበቅ ሲያስፈልግም ያን ማብራራት ከእውነቱ የሚጣላ ነገር ይዘው ብቅ ያሉ መናፍቃን ካሉ አስተምሮ መመለስ ካልተቻለ ከነስህተቶቻቸው ማውገዝ ከዚያ ያለፈ በሃይማኖት ላይ የመጨመርም ሆነ የመቀነስ ሥልጣን የላቸውም። ገላ.1፣7-9 ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን ይላል። መሰለኝ በጎደለ መረጃና በስሜት የተመሰረተ ነው። ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃ ያልተገኘለትን ሳይሆን አይቀርም ሲነገር ተሰምቷል መገመት ይቻላል ልንገምት እንችላለን እያሉ መናፍቃን በመሰለኝ ይናገራሉ። ሃይማኖት ግን ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴ.5፣37 እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ ወፈድፋደሰ እምእሉ እምእኩይ ውእቱ ባለው መሰረት እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማለት እንጂ ከዚያ ወጥቶ ይመስላል ሊያስኬድ ይችላል ይሆን ይሆናል መገመት ይቻላል ወዘተ እያሉ መቀባጠር ምናልባት ለሰብአዊ አስተሳሰቦችና ለምድራዊ ርእዮቶች ካልሆነ በስተቀር ለክርስትና ቦታ አግባብነት የለውም። ሃይማኖት የሰው ልጅ ሊቀበለው በሚችለው መጠን እግዚአብሔር ስለራሱ ማንነት ለእኛ የገለጠው እውነታ ነው። ኤር.7፣23 መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ ብየ በዚህ ነገር አዘዝኋችሁ ይላል። ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የምታደርስ መንገድ ናት። ሃይማኖት ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ወይም የተገለጠ ነው። በሃይማኖት የሚገኘው እውቀት ሰው ተመራምሮ የደረሰበት እውቀት ወይም ግኝት አይደለም። ጴጥሮስ ጥያቄውን በመለሰ ጊዜ ማቴ.16፣15-17 “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም ብጹዕ ነህ” ብሎታል። የሃይማኖት ምንጩ ጌታ ባይሆን ኖሮ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተመለከተ ጴጥሮስ የሚኖረው እውቀት በዘመኑ ከነበሩት ሌሎች ሰዎች የተለየና የተሻለ ሊሆን አይችልም ነበረ። ነገር ግን ከዚህ ዓለም ሥጋዊ ምርምርና ፍለጋ ውጭ የሆነው እግዚአብሔር እውነቱን ገለጠላቸው። 1ኛ ቆሮ.2፣4-5 እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ይላል። የሰው ልጅ ሃይማኖትን ይቀበላል እንጂ ሃይማኖትን ሊሰራ ወይም ሊያሻሽል አይችልም። ጌታም በዮሐ.17፣8 የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁ እነርሱም ተቀበሉት ብሏል። ምግብናው እንደየዘመኑ ይለያያል። ይዘቱ ግን ያው አንድ ነው። ለምሳሌ ሕጻን ልጅ በሕጻንነቱ

ወተትና ፍትፍት ሲያድግ ደግሞ ጠንከር ያለ ምግብ ይሰጠዋል የሰውነት ባሕርዩ ግን ያው አንድ ነው አይለወጥም። ሃይማኖትም በዘመነ አበው በዘመነ ኦሪት በዘመነ ወንጌል የምግብናው ሁኔታ እንደየ ዘመኑ የሰዎች የመረዳት አቅምና ችሎታ ቢለያይም ይዘቱ ግን ያው አንድ ነው። ዕብ.1፣1-2 ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ የቅዱሳን መላእክት የአበው ቀደምት የእነ አዳም ኖኅ አብርሃም ሙሴ ዳዊት የነቢያት ኂላም የሐዋርያትና የሰማእታት የጻድቃንና የሊቃውንት ሃይማኖት አንድ ነው። ስለዚህ ሃይማኖት አንድ ጊዜ ስለተሰጠ ለውጥ ወይም ተሐድሶ አያስፈልገውም። ሃይማኖትን ይቀበሉታል ይጠብቁታል ያወርሱታል እንጂ ላድሰው ላሻሽለው አይባልም። ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተቀበልነው እንደመሆኑ መጠን የሰዎች ድርሻ አምኖ መቀበልና በዚያ በመጠቀም የዘለዓለም ሕይወትን መውረስ ብቻ ነው። ሲኖዶስም ቢሆን ቀኖና ይሰራል እንጂ በሃይማኖት ላይ የሚጨምረውም የሚቀንሰውም ነገር የለውም። ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖት ላይ የሚጨምር ደፋር የሚቀንስ ደግሞ ሌባ ነው ይላል። 2ኛ ጴጥ.2፣1 ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ ይላል። ማቴ.24፣23 ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ ቢቻላቸውስ የተመረጡትንስ እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ ይላል። ገላ.1፣8-9 ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን ይላል። ሰዎች ወደ ኑፋቄ የሚገቡባቸው ምክንያቶች አንደኛ እውነተኛውን የክርስትና ትምህርት አለማወቅና በተሳሳቱ ሰዎች ትምህርት መለከፋቸው ነው። ሌላው በራስ አስተሳሰብና ስሜት ብቻ መመራት እኔ አውቃለሁ ማለት ስህተትን አለመቀበል ጥቂት ጥቅሶች ላይ ብቻ መንጠልጠል እምነትን ለቁሳዊ ጥቅም ማግኛ መንገድ ማድረግ ናቸው። ኦሬንታል ኦርቶዶክስ የሚባሉት የኬልቄዶንን ጉባኤ የማይቀበሉት ናቸው። የምሥራቅ ኦርቶዶክስ የሚባሉት ደግሞ የኬልቄዶንን ጉባኤ የሚቀበሉ ከሮማ ካቶሊክ በ1054 ዓ.ም የተለያዩ ናቸው። የእምነት መለኪያው የሰው አእምሮ ወይም መምሰሉና አለመምሰሉ አይደለም። እምነት ነው እንጂ።

ድኅነት፣ ትእዛዛት፣ የእግዚአብሔር ቸርነት

የዕሩቅ ብእሲ ሕማም ደም እንደማያድን በአዳም አውቀናል። ደሙን መሥዋእት አቅርቦ ነበርና ያ አላዳነውም። አንዱን እምነት ከሌላው የሚለየው መሰረታዊ ጉዳይ ስለመዳን ያለው አስተምህሮ ነው። የቅጣት ምትክ ሀሳብ (penal substitution theory) መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ መሰረት ላይ ከመመስረት ይልቅ በፍልስፍናና logic የተመሰረተ ነው። መናፍቃን ጌታ ስለኛ ተቀጥቷል ከእንግዲህ እኛ አንቀጣም ይላሉ። ካመንን በኋላ በጥፋታችን አንጠየቅም ይላሉ።በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የጌታችን አዳኝነት ዕለተ ዓርብ ላይ ብቻ የተወሰነና የተገደበ ሳይሆን መላው ሥጋዌው ከጽንሰቱ እስከ ዕርገቱ ለመዳናችን አስፈላጊ ነበር። ጌታችን የመጣው ሥጋችንን ብቻ ለመቀደስ ሳይሆን መንፈሳችንንም ለመቀደስና የእርሱ ቤተመቅደስ ለማድረግ ነው። እግዚአብሔር ትዕዛዙን የሰጠን ለሰው ካለው ፍቅር የተነሳ እንጂ ሸክም ወይም እዳ እንዲሆኑብን አይደለም። ጌታ በኦሪት ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ ያለው በዚያ ዘመን ከነበሩት ሰዎች ሁኔታ አንጻር ነው። ማዳን ለክርስቶስ ብቻ ሳይሆን የአብና የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው። መዳን ከባርነት ነጻ መውጣትንም ይጨምራል። ነገረ ድኅነት የአስተምህሮዎችና

የአስተሳሰቦች ሁሉ ማንጠሪያና መለኪያ ነው። ሰው ለምን መዳን አስፈለገው ስንል ኃጢአት ሰርቶ ከክብር ስለተጎሳቆለ ነው። የሐዋርያት ተልእኮና ስብከት ዓላማው የሰው መዳን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም የተጻፉት ለሰዎች የመዳን እውቀትን ለመስጠት ነው። 1ኛ ቆሮ.15፣21 ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሳኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኗል። **የሰው ሕይወት ግቡ** ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹማዊ ሁኔታ መዋሐድ ነው ማለት ነው። ቅዱስ ሄሬኔዎስ ቃል የእኛን ባሕርይ የተዋሐደውና ሰው የሆነው ሰዎች የጸጋ አማልክት ይሆኑዘንድ ነው ይላል። እግዚአብሔር የሰጠን የመዳን ጸጋ የቸርነቱ ሥጦታ ነው። ሰው በስራው ብቻ የሚጸድቅ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ደጋግ አባቶች ለመዳን ክርስቶስ ባላስፈለጋቸው ነበር። በእግዚአብሔር በኩል ሰውን ለማዳን አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ድርሻ ተፈጽሟል። አሁን የሚቀረው የእያንዳንዳችን ድርሻ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ማቴ.22፣4 ሁሉም ተዘጋጅቷል ወደ ሰርጉ ኑ በሏቸው በማለት እየጠራ ነው። የእግዚአብሔርን ጥሪ እሽ ብሎ ተቀብሎ የሠርግ ልብስ ለብሶ ወደ ሰርጉ ቤት መግባት ደግሞ የእያንዳንዱ ድርሻ ነው። እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የራሱ ድርሻ አለው። ሰው በራሱ ፍላጎትና ጥረት ብቻ ሊድን እንደማይችል ሁሉ እግዚአብሔርም ያለ ሰው ፍላጎትና ከነጻ ፈቃዱ ውጭ በግድ እንዲድን አያደርገውም ማለት ነው። የእግዚአብሔር የማዳን ጥሪ ከሰው ፍላጎትና ለእግዚአብሔር ጥሪ በጎ መልስ ከመስጠት ጋር ሲዋሐዱ ለዚያ ሰው መዳን ይሆንለታል። ከዚህ ውጭ ድኅነት የለም። ፊልጵ.2፣12 በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ እንዲል። እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የሚከተሉትን መፈጸም ይኖርበታል። **1ኛ እምነት**፦ በአጠቃላይ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጸውን የእውነት ትምህርት ሳይቆነጻጽሉና ሳያጓድሉ በምልዐት መቀበልና ማመን ነው። የምናመልከውንና የምንሰግድለትን ማወቅ አለብን። ጌታ በዮሐ.4፣20-24 እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን ብሏል። ዕብ.11፣6 ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። **2ኛ ለድኅነት መሰረታዊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም**፦ እነዚህም ጥምቀት ሜሮን ቁርባን ንሥሓ ወዘተ ናቸው። **የጥምቀት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች አንደኛ** ሥርየተ ኃጢአት መዳን ነው። የሐዋ.2፣38 ንሥሓ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ማር.16፣16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል። 1ኛ ጴጥ.3፣20-21 ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድናል። ሕዝ.36፣25 ጥሩ ውሃንም እረጫችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ። **ሁለተኛው** የእግዚአብሔርን ልጅነት ለማግኘት ዳግም ልደት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው። ዮሐ.3፣3 ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። በመንፈሳዊ ልደት ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል። **ሦስተኛው** ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን በሞቱና በትንሳኤው ለመተባበር ነው። ሮሜ 6፣3 ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን ይላል። **አራተኛው** ክርስቶስን ለመልበስ ነው። ገላ.3፣27 የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል የሚለው ቃለ ወንጌል የሕጻናትን ጥምቀት የሚከለክል አይደለም። በመሰረቱ ይህ ቃል የተነገረው በተለያየ ምክንያት ሳይጠመቁ ላደጉና ማመን በሚችሉበት እድሜ ላይ ለደረሱ ሰዎች ነው እንጂ የሕጻናትን ጥምቀት በተመለከተ የተነገረ አይደለም።

ለምሳሌ ሊሰራ የማይወድ አይብላ ያለው መስራት እየቻሉ በስንፍና ምክንያት መስራት የማይወዱትን በተመለከተ እንጂ በእድሜ ሕጻናት የሆኑትንና በተለያየ ምክንያት መስራት የማይችሉትን የሚመለከት አለመሆኑ ግልጽ ነው። ሰማእትነትን ጌታችን ጥምቀት ብሎታል እንዲህ ሲል "እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን" ብሏል። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሰራና ጸጋውን ሲያሳድር በሚታዩ ቁሳዊ ሀልዎት ባላቸው ነገሮች አማካኝነት መጠቀሙንና መስራቱን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየን እውነታ ነው። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሰራ ያለ ሥነፍጥረት አማካይነት እንዲሁ በቀጥታም ይሰራል። እንዲሁም ደግሞ በፈጠራቸው ሥነፍጥረታት አማካይነትም ይሰራል። ለምሳሌ ጌታ ሙሴን በበትርህ ውሃውን ምታው ብሎት ተከፍሏል። ዝም ብሎም በራሱ መክፈል ይችል ነበር። ማር.6፣13 ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው። ያዕ.5፣14 በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። **ምሥጢረ ሜሮን** ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ባገኘችው ትውፊት መሰረት የምትጠቀምበት ምሥጢር ነው። **ምሥጢረ ቁርባንን** ጌታ በቃሉ ትምህርት የነገረን እንዲሁም በተግባር ሰርቶ ያሳየን ነው። ዮሐ.6፣41-60 ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኛ ኅብስቱ ወደ ሥጋ ሲቀየር ወይኑ ወደ ደም ሲቀየር በመዓዛውም በጣዕሙም በቀለሙም ይለወጣል የሚል ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የለም። ትምህርታችን ጥርት ያለ ነው እርሱም ውላጤ እንበለ ውላጤ የሚል ነው። 1ኛ ዮሐ.1፣7 ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያንጽሐነ እምኩሉ ኃጣውኢነ። ቁርባን ከምንም ከማንም በላይ ነው። የወርቅ አፈር ቢሰጥህ እንዳይነጥብብህ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካደረግህ ለሥጋውማ የበለጠ ልትጠነቀቅለት ይገባል። የክርስቶስ ሥጋና ደም በእያንዳንዱ ሰውነት ሲገባ በምልዐት እንጂ ሕጸት የለበትም። ገና በቀኖና ላይ ያለ ተነሣሒ ቀኖናውን ያልፈጸመ ክርስቲያን ቅዱስ ቁርባንን ሊቀበል አይገባውም። ገና ወደ ጥምቀተ ክርስትና ያልገቡ ንዑሰ ክርስቲያን ይባላሉ። ጌታችን ልዩ ሊቀካህናት የተባለበት ምክንያት በኦሪት መሥዋእት አቅራቢውና መሥዋእቱ እንዲሁም መሥዋእት ተቀባዩ የተለያዩ ነበሩ። ጌታ ግን ሦስቱንም ሆኗልና። ሁለተኛ የኦሪቱ ሊቀካህናት በየዓመቱ መሥዋእት ያቀርብ ነበር። ጌታ ግን በዕለተ ዓርብ ያቀረበው መሥዋእት ለዘላለም በቂ ስለነበር በየዓመቱ በቀራንዮ መሰቀልና መሞት አያስፈልገውም። የብሉዩ ሊቀካህናት ፍጡር በመሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስለሚሞት በሌላ ሰው ይተካ ነበር። ክርስቶስ ግን ዘላለማዊ ስለሆነ በሌላ ሊቀካህናት አይተካም። የብሉይ ኪዳኑ ሊቀካህናት መሥዋእት ከምድራዊ መከራ ማዳን ነው። የጌታ ግን ሰማያዊ ርስትን የሚያሰጥ ነው። በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ የሚቀርበው መሥዋእት ሌላ ሳይሆን ጌታችን አንድ ጊዜ የፈጸመውና በዕለተ ዓርብ የቆረሰው ሥጋውና የፈሰሰው ደሙ ነው። ዕብ.13፣10 ወብነ ምሥዋእ ይላል። መሰዊያ የሚኖረው መሥዋእት ሲኖር ነው። **3ኛ በተቀበሉት ጸጋ መጽናት መንፈሳዊ ተጋድሎና ክርስቲያናዊ መልካም ሥራ፡-** ሉተር የቅዱስ ያእቆብን መልእክት በሥራና በእምነት ስለመጽደቅ ስለሚናገር ገለባ መልእክት ይለው ነበር። የመናፍቃን አለመረዳትና ስህተት ያለው አንዱን ጥለው አንዱን አንጠልጥለው መሄዳቸው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪትን ሕግ ወንጌልን እምነት ሲል ይገኛል። ለምሳሌ ሮሜ 3፣28 ሰው ያለ ሕግ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለን ሲል በኦሪት የበግ የፍየል መሥዋእት ግዝረት ባይደለ በወንጌል እንጸድቃለን ሲል ነው። ገላ.3፣11 ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሏልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው ይላል። ሕግ ያለው ኦሪትን እምነት ያለው

ወንጌልን ነው። 1ኛ ዮሐ.2፣4 አውቄያለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው። የሐዋ.14፣22 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናልና። ሮሜ 2፣13 በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና። እግዚአብሔር የከለከለውን የሚሰራ ያዘዘውን የማያደርግ ከቅጣት አያመልጥም። ሉቃ.13፣24 በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ። ማቴ.24፣13 እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። በሕይወተ ሥጋ በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናን ገና በጉዞ ላይ ናቸው። ስለዚህም እስከመጨረሻው ይጸኑ ዘንድ መጋደል ይጠበቅባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ሲናገር ሌላውን ጥሎና ነጥሎ ሳይሆን ያን እንዳለ በመቀበል በዚያ ላይ ከዚያ ጋር መያዝና ማድረግ የሚገባንን ነገር የሚጨምር ነው። ያዕ.2፣14-16 ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው። እያንዳንዱ ጸሎትህ የምትዘምረው እያንዳንዱ ዝማሬህ ይመዘገባል። እያንዳንዱ ምጽዋትህ እያንዳንዱ ጾምህ ይመዘገባል። ስለ እግዚአብሔር ተብሎ የተኖረና የተጠበቀ ትዳር እንዲሁም ንጽሕና ይመዘገባል። እያንዳንዱ የሐሰት መሐላህ የአመንዝራነት ሥራህ እያንዳንዱ ነቀፋና ስም ማጥፋት መተት ይመዘገባል። ሐዘን በዚህ ዓለም እንዲኖር የተደረገበት ብቸኛ ምክንያት ለንሥሓ ብቻ ነበረ። አንድ ሰው ንብረት ስለተወሰደበት አዘነ እንበል። ነገር ግን ሐዘኑ የተወሰደበትን ንብረት አይመልስለትም።ሌላ ሰው ደግሞ ልጁ ስለሞተበት አዘነ እንበል። ሆኖም ሐዘኑ የሞተውን ማስነሳት አይችልም። የሆነ ሰው ቢገረፍ ቢመታና ቢሰደብ ያዝናል። ሆኖም ሐዘኑ የደረሰበትን ነገር አይመልስለትም። የሆነ ሰው በኃጢአት ወደቀና አዘነ እንበል የዚህ ሰው ሐዘን ግን ኃጢአቱን ያስወግድለታል በኀዘኑ ከበደሉ ነጻ ይሆናል። **ጾም** ለአዳም የተሰጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው። አዳም ማድረግ ይችል የነበረውን ነገር (ከዚያ ዛፍ መብላትን) ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብሎ እንዲተው ነበር የታዘዘው። ጾምም አንድ ሰው ለማድረግ መብት እያለው ነገር ግን ከዚያ በላይ ፈጣሪውን አስቦ ያን ነገር በመተው ከፈቃዱ መሥዋእት አድርጎ የሚያቀርብበት ነው። መዝ.53፣6 ዘእምፈቃድየ እሠውእ ለከ እንዲል። **የጾም አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፡- አንደኛ** እግዚአብሔርን የመፍራትና ወደ እርሱ የማዞር ምልክትና የእግዚአብሔርን ምሕረት መለመኛ መንገድ ነው። 2ኛ ዜና.20፣3 ኢዮሣፍጥም ፊራ እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና በይሁዳም ሁሉ ጾም አወጀ። ዕዝ.8፣23 ስለዚህም ነገር ጾምን ወደ እግዚአብሔርም ለመንን እርሱም ተለመነን። **ሁለተኛ** ጾም ሐዘንንና ችግርን ለእግዚአብሔር መንገሪያና ጭንቀታችንን ሁሉ በፊቱ ማፍሰሻ መንገድ ነው። ነህ.1፣4 አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር። **ሦስተኛ** ጾም የትውልድ ስብራት የሚጠገንበትና መልካም የሆነ ትውልድ የሚነጽበት መሣርያ ነው። ኢሳ.58፣6-14 እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን ከድሮ ዘመን የፈረሱት ስፍራዎች ይሰራሉ የብዙ ትውልድም መሰረት ይታነጻል። **አራተኛ** ጾም አጋንንትን የሚያወጣቸው ርኩሳን መናፍስትን የምንዋጋበት መሣሪያ ነው። ማር.9፣29 ይህ ወገን በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም። ኢዮ.1፣14 ጾምን ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ። የሐዋ.27፣9 ብዙ ጊዜም ካለፈ በኋላ የጾም ወራት አሁን አልፎ ስለነበር በማለት የታወቀ የጾም ጊዜ ያለ መሆኑን ተናግሯል። ጾም ሰውነትን በተወሰነ መጠን የሚያደክምና በልቶ ጠጥቶ የሚገኘውን እርካታ ለእግዚአብሔር መሥዋእት አድርጎ በመተው የሚቀርብ መሥዋእት ነው። መዝ.34፣13 ወአሕመምክዋ በጾም ለነፍስየ። መዝ.108፣24 ሥጋየም ቅቤ በማጣት ከሳ ያለው በጾም ጊዜ ቅቤ ስለማይበላ እንጂ ዳዊትን ያህል ገናና ንጉሥ

ቅቤ ችግሮት አልነበረም። ዳን.10፣1 ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም። ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ የተፈጠርነው በሐሴትና በደስታ እንድንኖር ነው ገነትን የተሰጠነው በሕይወት እየኖርን ሐሴትን እንድናደርግ ነበር ይላል። ቅዱስ ጀሮም "ቅዱስ ያዕቆብ እጉሁ ለእግዚእነ ከጸሎተ ሐሙስ ማታ አንስቶ ጌታችንን ከሞት ተነሥቶ እስኪያየው ድረስ ምንም ነገር እንደማይቀምስ ለራሱ ቃል ገባ"። ዮሐንስ አፈወርቅ "የጾም ግማሽ በማለቁ አትደሰቱ። ከዚህ ይልቅ በጾማቸው የኃጢአታቸው ግማሽ ተወግዶ ማሰብ ይገባቸዋል የክረምት ጠቀሜታው የበለጠ የሚታወቀው ወቅቱ ካለፈ በኋላ ነው ያን ጊዜ የአበባዎች ማበብ የአዝመራው ማፍራት የዛፎች መለምለም ከክረምቱ ያገኙትን ጠቀሜታ በግልጽ ይናገራሉ ጾሙ ካለፈ በኋላ በእኛ ላይ በሚያፈራው መልካም ፍሬ ጠቀሜታው ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ይሁን። **ምጽዋት፡-** አንድ ሰው ፍቅረ እግዚአብሔርን መሰረት በማድረግ ለሌሎች ሰዎች የሚያደርገውን መልካም ነገር የሚያጠቃልል ሰፊ ነገር ነው። አንድ ሰው ለተቸገረና በሐዘን ላይ ላለ ወገኑ መጀመሪያ የሚያደርገው ምጽዋት ችግሩንና ሐዘኑን በመንፈስ መጋራትና አብሮ መካፈል ነው። ዕብ.13፣3 ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስረኞችን አስቡ። ዳን.4፣27 በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር። ማቴ.19፣16-21 ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ። መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ። ዮሐንስ አፈወርቅ "እግዚአብሔር ሀብትህን ለሌላ እንድትሰጠው አንተን ያዘዘበት ምክንያት የአንተ ይሆን ዘንድ ነው የአንተ በሆነ መጠን የአንተ አይደለምና። **ንሥሓ፡-** በውስጡ በደለኛነትን አምኖ ማዘንና መጸጸትን ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝን ኃጢአትን ለካህን መናዘዝን ኃጢአትን ለበደሉት ሰው መናዘዝን። በንሥሓ አባት አማካይነት ቀኖና መቀበልን ያጠቃልላል። ኃጦአትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሔር የመናዘዙ አካል እንጂ ያን የሚተካ አይደለም። ሚል.2፣7 ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና። ዮሐ.20፣23 ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። ስለሚል ካህኑ እግዚአብሔር ይፍታህ ይላሉ። እኛ ተነሣሒ የሚቀበለው ቀኖና ስለ ኃጢአቱ የሚከፈለው ዋጋ ወይም የሚቀጣው ቅጣት ነው አንልም። ተግሣጻዊና ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ መዘጋጃ እንዲሆን ነው እንላለን እንጂ። ማቴ.8፣2-4 ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ። አዳም ከበደለ በኋላ እግዚአብሔር ለምን ከሕይወት ዛፍ እንዳይበላ ከለከለው? ለምንስ ከኤደን ገነት አስወጣው?ስንል ከቸርነቱ የተነሳ ነው እንጂ አዳምን ለመጉዳት ወይም ለመበቀል አልነበረም። አዳም ከነኃጢአቱ ሳለ ዕፀ ሕይወትን ቢበላ ኖሮ እንደ ዲያብሎስ የማይሞት ምውት ሆኖ እንዳይኖር ለማድረግ ነበር። አዳም ዘላለማዊ ምውት እንዳይሆን ቀኖናውን እስኪጨርስ ገነትን በሱራፊ አስጠበቃት። በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና የሚሰጥበት መሰረታዊ ምክንያትም ይህ ነው። ማንም በማይገባ ሕይወት ወደ ምሥጢራተ ቤተክርስትያን ቀርቦ እንዳይጎዳ ለመጠበቅ ነው። 1ኛ ቆሮ.11፣29 ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላል እንዲል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የማንም የቅድስና ደረጃ በራሱ ብቁ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ በቸርነቱ የሚሰጠው ነው እንጂ። ዮሐንስ አፈወርቅ "ከመጀመሪያ መልካም የሆነውን ነገር አለመምረጥ ክፉ ነገር ነው። መልካም ባልሆነው መንገድ መሄድ ከጀመሩ በኋላ አለመመለስ ደግሞ የበለጠ ክፉና የከበደ ዕዳ ነው። በሁሉም ነገር ጠንቃቆችና አስተዋዮች መሆን ይገባናል። ታላቂቷ ቅርጣግና አሁን ቱኒዚያ ናት። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አሁን ካለነው ሰዎች ምነው የጌታችንን ገጹን ባየሁት ልብሶቹን በዳሰስኳቸው ብለው የሚመኙ

ብዙዎች አሉ። እርሱን እያያችሁትኮ ነው እየዳሰሳችሁት ነው እየበላችሁት ነው። የተሐድሶዎች ስህተት መዳንን ከኃጢአት ቅጣት ማምለጥ ብቻ አድርጎ የሚወስድና በምዕራቡ ዓለም በመካከለኛው ዘመን ከነበረው የወንጀለኞች መቅጫ ሕግ አንጻር የተቃኘና በዚያ መሰረት የተመሰረተ መሆኑ ነው። በእኛ አስተምህሮ ግን መዳን ከዚያ ባለፈ "ከመለኮቱ ባሕርይ ተካፋይ እስከመሆን የሚደርስ እጅግ ሰፊና ጥልቅ ነው። እመቤታችንን ያወቅናት በሰው መዳን ሂደት ውስጥ ነው።ፈጣሪዋን ጡት ያጠባችው ያዘለችው እርሷ ብቻ ናት። 30 ዓመት ሙሉ አብራው የኖረችው የታደለችው እርሷ ብቻ ናት። 30 ዓመት ሙሉ የሚያስደንቁ ነገሮችን ስትሰማቸው ኑራለች ያን ሁሉ ምሥጢር ግን አውጥታ አልተናገረችም። እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር ይላል። እስከ መስቀሉ ድረስ አብራው ሄዳለች። **ወላዲተ አምላክ** ቃል ሥጋ ኮነ ካለውና የጌታየ እናት በማለት የገለጸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በአንድ ላይ ጠቅልሎ የሚይዝ ቃል ነው። ፍጡር ማዳንማ ቢችል ኖሮ አምላክ ሰው መሆን ባላስፈለገውም ነበር። ኢየሱስም በመስቀል ላይ ሆኖ እናቱን ይወደው ለነበረው ደቀመዝሙር አደራ ሰጠው (አስተውል ጌታ ለእመቤታችን የሚወደውን ደቀመዝሙር ነው የሰጣት። እንደ ጌታ የሚወዱትን ባይሰጡዋትንኳ መናፍቃን የሚሰድቧት ምን ሆነው ነው ስትል የሰይጣን ተማሪ ስለሆኑ ነው)። ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በቃላት የተዋበና የተቀመረ ምስጋና ለቅዱሳን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ተገቢም ትክክልም ነው አለ። 1ኛ ቆሮ.9፣24 እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ ሲል አንድ ሰው የሚድነው በራሱ ሩጫ ብቻ ነው ማለቱ አይደለም የክርስቶስን ቤዛነት ዘንግቶ አይደለም። ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች **1ኛ** እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለሆነ ነው። ዘዳ.33፣6 ይሕይወኒ ሮቤል ቁልኤየ ሞት በአቤል ፍትሐት በሮቤል ተጀመረ። ለመዳን የሚያስፈልጉ ነገሮች ሳይፈጸሙ በቅዱሳት መካናት መቀበር የመዳኛ መንገድ ነው ብላ ቤተክርስቲያን አታስተምርም።

ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ

አዘጋጅ፡-መሪጌታ ልሣነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ

ፊደል፣ምርምር

26ቱ የካም ፊደሎች ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሰ፣ ቀ፣ በ፣ ተ፣ ኀ፣ ነ፣ አ፣ ከ፣ ወ፣ ዐ፣ ዘ፣ የ፣ ደ፣ ገ፣ ጠ፣ ጰ፣ ጸ፣ ፀ፣ ፈ፣ ፐ ናቸው። የሴም ዘር የሆኑት የወረሱት አበገደ ብሎ ያለውን 22ቱን ፊደሎች ነው። መምህር ልሳነ ወርቅ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክና ቅርስ ኃላፊ ነበሩ። በ1973 ዓ.ም በያሬድ መዚቃ ትምህርት ቤት በያሬዳዊ ዜማ መምህርነት ተመደቡ። (ንብ ካለ ነገር ማር ትሰራለች ስለዚህ እኛም ባለ ነገር ተመራምረን ግኝት መስራት እንችላለን)። በቤተልሔም ያለው መጽሔተ ጥበብ በኋላ ዘመን የተጻፈ ነው። ዲድስቅልያ አንቀጽ 29 ወግበሩ በዓለ ልደት አመ እሥራ ወተሠዉ ለታኅሣሥ ይላል። ለአስተማሪና ለተማሪ በደገኞቹ ነገሥታት የተመደበውን ቀለብና ልብስ አጼ ሱስንዮስ ስለከለከለው በስደት የተበተኑ ተማሪዎች በድብቅ ትምህርታቸውን እየተማሩ የእለት እንጀራቸውን በመለመን እንቅፋትና ብርድ እየተመቱ መንደር ለመንደር እየዞሩ በሰው በር ቁመው በእንተ ቸሩ እግዚአብሔር እያሉ

መለመን ጀመሩ፡፡ ተማሪ እግዚአብሔርን የሚያገለግልበትን ትምህርት እየተማረ ቢለምን ሥራ ፈት አያሰኘውም፡፡

ከንቱ ውዳሴ/ተርእዮ፣ ደስታ፣ ኀዘን

(አንድን ሀሳብ ወይም ንግግር ወይም አለባበስ ሴት ወይም ጳጳስ ወይም ፕሮፌሰር እንዲወድልኝ ብለህ ከተናገርከው ካደረግከው እና ያሰብከው ቢሳካልህም ባይሳካልህም ዋጋህን በዚህ ምድር አግኝተሀል፡፡ እና በሰማይ ምንም ዋጋ የለህም፡፡ በማህበራዊ ሚዲያም ቢሆን ፎቶየን ሰው ይይልኝ ብሎ መፖስትክ ምናልባት ምንም ሌላ ትርጓሜ የለውም ተርእዮ ነው፡፡ አቦ አቦ መባል ደግሞ ፋይዳ የለውም በዚህ ምድር ተከፈለህ ማለት ስለሆነ እዘን፡፡ ቅዱሳን በዚህ ምድር ሰው ሲያመሰግናቸው አይወዱም የነበረ ዋጋቸው በምድር እንዳይቀርባቸው ነበር፡፡ ሀሳብንም ቢሆን ሰው ይይልኝ ሀሳቤን ምጥቀቱን ይረዳልኝ ብሎ መልቀቅ ማድረግ የተርእዮ አንዱ ክፍል ነው፡፡ ወይም ደግሞ የሆነ ነገር ተናግረህ ወይም አድርገህ ሌላ ሰው ስለዚያ ጉዳይ ምን ይለኝ ብለህ መጓጓት ከንቱ ውዳሴ ነው፡፡ የምታደርገው ነገር ሁሉ ሐዋርያዊ ከሆነ ከንቱ ውዳሴን ትጠላለህ፡፡ ሐዋርያት ሲያስተምሩ ተአምራት ሲያደርጉ ከትምህርቱ በኋላ ሰው ምን ብሎ ያደንቀን ይሆን ብለው አስበው አያውቁም፡፡ የሚያደርጉት ሁሉ ሰውን ለመጥቀም እንጂ ሰውን ጠቅመው ለመታወቅ አልነበረም፡፡ ይህንንም የሚያስረዳን ሰውን በተአምራት ፈውሰው ሰውየው መፈወሱን መጠቀሙን ካረጋገጡ በኋላ ይህን ያደረጉት እነርሱ መሆናቸውን እንዳይናገር ያደርጉ ነበር፡፡ ይህም የሚያሳየን ከንቱ ውዳሴን በጣም ይጠሉ እንደነበር ነው፡፡ ከንቱ ውዳሴና ተርእዮ እስኪለቀኝ አላስተምርም አልናገርም ያሉ አባቶች ነበሩ እንደነ አባ ጵላ ያለው ማለት ነው፡፡ ለመታወቅ ተብሎ ቀልብ ለማግኘት ተብሎ የሚደረግ ነገር ሁሉ ከንቱ ውዳሴን መፈለግ ተርእዮ ስለሆነ ዋጋህን በዚህ ምድር የሚያሰጥ ከንቱ ነገር ስለሆነ ናቀው፡፡ ጉዳይህ ሊሆን የሚገባው የጌታየን ቃል ለሰዎች ሰምተው እንዲጠቀሙበት መንፈሳዊ በቁኤት እንዲያገኙበት በምን መልኩ እንዴት ላስተላልፈው የሚለው ሐዋርያዊ አስተሳሰብ ነው፡፡እንጂ በምን መልኩ አስተላልፌ ልታወቅ ቀልብ ላግኝ በሰዎች ዘንድ ጥሩ ግምት ይሰጠኝ በሚል እሳቤ የጌታችንን ቃል ማስተላለፍ ያስቀስፋል፡፡ በጌታ ቃል አንተ ለመታወቅ መጣር አሳፋሪ ነው፡፡ የጌታየ ቃልኮ ዓላማው አንተንም ሌሎችንም ከዚህ ቆሻሻ አስተሳሰባችሁ አስወግዶ ዘለዓለማዊ ክብር እንድታገኝ ማድረግ ነው እንጂ በዓመድ እንድትመሰገን በአመድ ቀልብ እንድታገኝ በአመድ እንድትከበር አይደለም፡፡ በልብህ የተገለጸልህን ምሥጢር ያዝ፡፡ይህ ምስጢር ጥሩ ስለሆነ ለሰዎች ብናገረው ብጽፈው ያከብሩኛል ይወዱኛል ያደንቁኛል ብለህ ብትናገረው ክብር ታጣለህ፡፡ ማርያም ግን በልቧ ትጠብቀው ነበር ስለሚል ስለዚህ እርሷን አብነት አድርጋት እንጂ አትለፍልፍ፡፡ ምናልባት ለሰዎች ቢነገር በቁኤት የሚያገኙበት ከሆነ በሦስተኛ መደብ ተናገረው፡፡ ወይም በሌላ በማይታወቅ ስም ጻፈው፡፡ አንተ እንደጻፍከው ከታወቀና በዚህ ምክንያት ሰው ካከበረህ ግን በጣም እዘን ዋጋህን በዚህ ምድር እያገኘህ ነውና፡፡ ከተደሰትክ ግን ድሮም ከንቱ ውዳሴ ተርእዮ የምትወድ ከንቱ ነህና እፈር፡፡ ቅዱሳን ጌታ እንዳዘኑብህ እወቅ ሰይጣን ደግሞ በጣም እንደተደሰተብህ አስተውል፡፡ ወይም እንደ አባቶችህ ጽፈሕ አስቃምጠው ሰው ቢያይብህ እስክሞት አትናገርብኝ ብለህ አምለው፡፡ ሰው የሰራህውን ሥራ እንዳያውቅብህ ጣር ቅዱሳን አባቶች እንዳደረጉት ማለት ነው፡፡ ቅዱሳን ርቱዐ ሃይማኖት እያሉ በራሳቸው ስም

ያይደለ የጻፉ ስለምን ይመስለሀል። ሰው ካወቃቸው ከንቱ ውዳሴ ስለሚያቀርብላቸው ስማቸውን ሳይገልጹ ለሕዝቡ የሚጠቅም ነገር ነው ብለው ያሰቡትን ጻፉ እንጂ። ሐዋርያዊ ማለት ይህ ነው። ለሕዝብ ጥቅም የሚያስቡ እንጂ ራሳቸው ሊመሰገኑበት ሊወደዱበት ሊደነቁበት ያደረጉት ምንም ዓይነት ድርጊት አላደረጉም። ሰው በዚህ ምድር ብዙ ዘመን መቆየት የሚፈልግበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው? ለዚያስ እየኖረ ነወይ? መኖርን መመኘት ያለብህ ለሌሎችም መኖርን መመኘት ያለብህ ለነፍሳዊ ክብራቸው በማሰብ ለንሥሓ እንዲበቁ ትሩፋት እንዲሰሩ በማሰብ እንጂ ለሥጋዊ ክብርና ኑሮ ብለህ መሆን የለበትም። አንድ ሰው ክፉንኳ ቢያደርግ ሲኦል ቢገባ ስለማትጠቀም ለነፍሳዊ ክብር ፈጣሪ እንዲያበቃው ጸልይለት። ይህን ጊዜ አንተም ዋጋህ ይበዛል። ኀዘንህ ደስታህ በሥጋዊ ነገር ላይ ከሆነ ከንቱ ነው። ሥጋዊ ነገርን ለነፍሳዊ ክብርና ደስታ አውለው እንጂ ሥጋዊ ነገር ለነፍሳዊ ኀዘንና ውርደት አይዳርግህ። የማንኛውም ክፉ ሰው ሞት ያሳዝናል እንጂ አያስደስትም ውድቀቱም እንዲሁ። ምናልባት ይህ ክፉ ሰው የብዙ ምእመናንን ሕይወተ ሥጋ ቢያመሰቃቅልም ለእነርሱ እንዳይክዱ እንዲጸኑ ትእግስትን ለእርሱ ልቡናን እግዚአብሔር ሰጥቶት ነፍሳዊ ክብር ያገኝ ዘንድ ጸልይላቸው። ደስታህን ኀዘንህን እስከ መጨረሻው መርምረውና ሥጋዊ ከሆነ ጥላው። የቅዱሳኑን ደስታና ኀዘን ስትመለከተው በነፍሳዊ ጉዳይ እንጂ ሥጋዊ ነገር አይደለም። ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ያለብህ ለሌላውም ለአንተም ነፍሳዊ ጥቅም የሚያስገኝ ነገር ስለሚያደርግልህ ነው። ለምሳሌ ሰው በእጣ ቤት ቢደርሰው ደስ ሊልህ ይገባል። በቤት ምክንያት እግዚአብሔርን ከማሰብ እንዳይከለከል ሆኗልና ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ ለራበው ምግብ ሲያገኝ ተደሰት ምክንያቱም የራበው ሰው የሚያስበው ስለምግብ ነው። ስለ እግዚአብሔርና ስለነፍስ ጉዳይ እንዲያስብ ምግቡን እንዲሰጠው ትጸልያለህ። ለሆነ ሰው ሥጋዊ ነገርን ስጠው ለእገሌ ንሳው ስትልም ያኛውም አግኝቶ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ይህኛውም ሲያጣ ወደ ልቡናው ተመልሶ ነፍሳዊ ጥቅም እንዲያገኝ የሚለውን አስበህ መሆን አለበት። ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን ሥጋዊ ስለሆንክ ንሥሓ ግባ ደስታዎችህንና ኀዘኖችህን ሥጋዊና ነፍሳዊ ብለህ ለያቸው። ለስጋዊው ትኩረት አትስጠው በብዙኅ ሕማም ሀለወነ ንባኣ ያሉት በዚህ ምድር ትቸገራላችሁ ታዝናላችሁ እያለ ጌታም የተናገረው ይህን ዓይነቱን ሥጋዊውን ኀዘን ስለሆነ ይህ ኀዘን ግን ነፍሳዊ በቁኤት ስላለው ኀዘን ቢባልም ግን ጌታም ያደረገው በጌታም የደረሰ ስለሆነ ክብራችን ነው። ሕማሙን ክብር ይለዋልና። አብርሃም ነዌን አንተ በምድር ተደስተሀል ያለው ሥጋዊ ደስታን ስለሆነ ይህ ደስታ ደግሞ በነፍስ የሚያስቀጣ ወይም ለነፍስ ረብሕ የሌለው ስለሆነ ሥጋዊ ደስታን መርምረህ ተወው። ነፍሳዊ ኀዘን የሚባለው ሰው ከጌታ ትእዛዝ ወጥቶ ሲገኝ ነው በዚህ ኀዘን አይደለም ጌታ ሐዋርያትን ታዝናላችሁ ያላቸው ሰማያዊ ዋጋ በሚያሰጠው ምድራዊ ኀዘን ነው ታዝናላችሁ ያላቸው። ደስ ይበላችሁ የተባሉት ደግሞ በነፍሳዊ ጉዳይ እንጂ በሥጋ ጉዳይ አይደለም ለምሳሌ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ይላል እንጂ በሥጋዊ ጉዳይ ደስ ይበላችሁ አላለም። እመቤታችንን ከቁሳሩ የሰወራት ጌታ ተድላ ሥጋዋን ስለማይፈልግ ነው አይደል የሚል። አዎ ሥጋዊ ደስታ በጌታ ዘንድ በቅዱሳንም ዘንድ ቁም ነገር አይደልም። የምትናገረው ነገርም ለማንኛውም ነፍስ የማይሻክር ለምትናገረው ሰው ወደ ነፍሳዊ ጥቅም የሚመራ ሊሆን ይገባል እንጂ እግዚአብሔርን ወደ ማማረር ወደ መውቀስ የሚያደርስ ነፍሳዊ ጉዳት ቂም መጥላት ላይ የሚያደርስ መሆን የለበትም። ባጭሩ ትችቶችህ፣

ኀዘኖችህ፣ አድናቆቶችህ ደስታዎችህ ግባቸው ነፍሳዊ ሊሆን ይገባል። መቼም አንድን የእግር ኳስ ተጫዋች ደግፈህ የምታገኘው ደስታ ነፍሳዊ ሊሆን አይችልም። ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን የሚያደርገው ነገር ሲደረግለት ደስ ይበልህ። ያን ለከንቱ ውዳሴና ዝነኛ ስላደረግከኝ ካለ ነፍሳዊ ጉዳይ ሳይሆን ያመሰገነበት ሥጋዊ ጉዳይ ስለሆነ እዘንለት። ምስጋናው ሊሆን የሚገባው የነበረስ ለእግዚአብሔር ኃያልነት መጋቢነት እንጂ እርሱ ዝነኛ ስለሆነ አይደለም በሆነ ጉዳይ የበታችነት ወይም የበላይነት ከተሰማህ ጉዳዩ ሥጋዊ ነው ማለት ነው። ሥጋዊ ከሆነ ደግሞ ናቀው። ምክንያቱም በነፍሳዊ ዓለም ከቦታ ቦታ ከጊዜ ጊዜ ከሰው ሰው ከዘመድ ባዕድ የሚባል ነገር የለምና። በመልክዓ ምድር መቀናናትና መኩራራት የሥጋዊነት ጸባይ እንጂ ምንም ነፍሳዊ ፋይዳ የለውም። የአንተ ባልሆነ ንብረት መልክዓ ምድር የእኔ ብለህ መኩራራትህ ራሱ ከንቱነትህን ያስረዳል። አሁን አንተ ብትኖርበት አያት ቅድመ አያትህ ከሌላ የመጡ መጤዎች ናቸው። ዛሬ አንተ ብትኖርበት ነገ ሌላ ሰው ሌላ አካል ነው የሚኖርበት። እግዚአብሔርም ሲፈጥረው እንዲህ እንዲሆን አድርጎ ነው። እስኪ አያቶችህ ለአንተ ምኖችህ ናቸው አያውቁህምኮ በማያውቁህ ሰዎች መመካት ደንቆሮነት ነው። በነፍስ ያውቁኛል ካልክ በነፍስማ እንዲህ በሰፈር ሳይሆን ለሁላችንም እኩል በማማለድ ያውቁናል ለአንተ የበለጠ የሚደረግበት ዓለም አይደለም ዓለመ ነፍስ አይ በደመ ነፍሴም በሥጋየም በእነርሱ መደነቅ እፈልጋለሁ መኩራት እፈልጋለሁ ካልክ ደግሞ ይህ እንስሳዊነት ስለሆነ መብትህ ነው። ከሰው ግን እበልጣለሁ እያልክ የምታቅራራው የምትኮራው የበላይነት ስሜት ይሰማኛል ወዘተ የምትለው ግን በእንስሳዊነት ግብር እንደሆነ አስተውል። በነፍስ ግብርማ መወለድ ቦታ ጊዜ ሁኔታ አያበላልጥም የሚያበላልጠው ምግባር ሠናይ ብቻ ነው። ማንንም ቢሆን ስትገስጸው ተግሳጽህ የሚያስከፋው መሆን የለበትም የሚያስተምረው እንዲሆን አለዝበህ ተናገረው እንጂ። እነ አባ መቃርስኮ ያላደረጉትን ዝሙት አደረግን ያሉት ለሌላውም ነፍሳዊ ጥቅም ስለሚሰጥ ነው። ልባቸውም በዋሹባቸው ሰዎች አልተቀየመም ራሩላቸው እንጂ ዘፈን በየትኛውም መስፈርት ሲታይ ከንቱነት ነው። እንስሳትም በምግብ በአንዳንድ ድምጽ ስሜታዊ ይሆናሉ። ስለዚህ ዘፈንን መውደድ ከእንስሳዊነት ወገን ነው።ምናልባት እኛ በዚህ ረገድ ከእንስሳት የተለየነው ይህን ስሜታችንን በነባቢት ነፍስ መግለጻችን እና ለልጅ ልጅ ማስተላለፋችን እንጂ። ዘፈን መብል መጠጥ መውደድ ምኞት መውደድ ከእንስሳት ጋር አንድ የሚያደርገን ሥራ ስለሆነ አያኮራም። ምናልባት እንስሳት ምግብ መጠጥ ምኞት ሲሹ ምክንያታቸውን አላውቀው ብለው ይሆናል። እኛ ደግሞ ነባቢት ነፍስን ተጠቅመን ትርጉም ብንሰጠውም ያው ነው ከእንስሳዊነት አይወጣም። መዳራትም ከእንስሳት ጋር የሚያመሳስለን ስራ ነው። የእኛን ከእንስሳቱ ለየት ያደረገው ይህን ስሜት ለማጣጣም በነባቢት ነፍስ የተለያዩ ድርሰቶችን ደርሰን እጥፍ ማድረጋችን ብቻ ነው)።

ዜማ፣ ዘፈን

በቀድሞ ዘመን ምድራዊ ዜማ ማኅዘኒ የተጀመረው ከትካዜና ከኀዘን ጽናት የተነሳ ነው። ኢዮቤል የቃየልን በደል እያስታወሰ መሰንቆና በገና የመሳሰሉትን ከእንጨት አበጅቶ መሰንቆውን በቆዳ ሸፍኖ በጭራ ወጥሮ በገናውን በጅማት ገትሮ ድምፁን በድምፁ እያስማማ እንጉርጉሮውን ያሰማ ነበር ዘፍ.4፣21። መዝሙር ኃጢአት ለመፈጸም ቢቃኙት ጎጂ ነው። በኋላ የተነሱት

የቃየን ወገን ሴቶች ተኩለውና ተቀብተው ጌጥ አጊጠው ወቅረው ተቀባብተው በዝሙት ተነድፈው በመሰንቆና በበገና በክራር ሲዘፍኑ መላእክተ እግዚአብሔር ተብለው በንጽሕና ደብር ቅዱስ ይቀመጡ የነበሩት የሴት ልጆች በዘፈናቸው ጣዕም ተማርከው ከነበሩበት ደብር ቅዱስ ወርደው ከዘፋኞቹ ሴቶች ጋራ በዝሙት ወድቀው በረከሰ ስራቸው እግዚአብሔርን ስላስቀየሙት ኖኅን ብቻ አስቀርቶ አጠፋቸው። መንፈሳዊ መዝሙር የታመመውን በጣዕመ ቃናው እንደ ሳኦል ይፈውሰዋል። ሜልኮል ዳዊት የሚዘምረውን መዝሙር እንደ ዘፈን ቆጥራ መካን ሆና ቀርታለች። መንፈሳዊ መዝሙር ከኃጢአት ያነጻል። ዳዊት በኦርዮ ላይ በፈጸመው በደል መዝሙር እየዘመረ እያለቀሰ ቀኖና ይዞ እግዚአብሔርን ቢለምነው ይቅር ብሎታል መዝ.6፣1-13። ዕዝራ ሱቱኤልም በበረሀ ወድቆ ስለ ጽዮን ምርኮ እያስታወሰ መሰንቆውን እየቃኘ ሲያለቅስ ጽዮን እንደ ሴት ስታለቅስ ትታየው ነበረ። ቅዱስ ያሬድ የሚያዜመው ዜማ ምሥጢሩ የሚያጠግብ ቃሉ የሚያረካ አነጋገሩ የተሳካ ጣዕመ ቃሉና ኃይለ ቃሉ ደስ የሚያሰኝ ነው።ሀሌ ማለት ቅድመ ዓለም የነበረ አምላክ ማለት ነው። ሉያ ማለት ዓለምን አሳልፎ የሚኖር አምላክ ማለት ነው። ማኅሌትን በቅንነት ቢጸልዩት ከክፉ ጠላት ያድናል። እንደ ኢያሱ ጥቅመ ኢያሪኮን ለማፍረስ ይጠቅማል። (እኛ በየዘመኑ እንድንዘምራቸው በቅዱሳን ሊቃውንት የተዘጋጁ መዝሙራት አሉን። እኒህም ዘመኑን አስበህ ፈጣሪን የምታመሰግንባቸው ናቸው። የምስጋናው የመጨረሻ ግብ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። ለምሳሌ እገኒ ለከ እግዚኦ በውስተ ልብየ ይላል ዓውደ ዓመት ለባርኮ ንዒ ማርያም ይላል። በየዘመናቱ የሚባሉ ዜማዎችን በዚህ መልኩ ብትመረምራቸው የዜማዎች የመጨረሻ ግብ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ሃይማኖትን መግለጥ ጸሎት ወዘተ ሆነው ታገኛቸዋለህ። ዘፈኖች ግን በየሀገሩ በየዘመኑ የሚዘፈኑ ባህላዊ እና ዘመናዊ ዘፈኖች አሉ። ለምሳሌ በመስከረም ወር አበባየ ሆሽ ለምለም ጽንኤላዊው ዘመን ኢዮሃ አበባየ መስከረም ጠባየ ወዘተ እንዲሁ ስትመረምራቸው ከንቱዎችና መጨረሻ ግባቸው ምንም የሆኑ ዘፈኖች ናቸው። ምናልባት አእምሮን ያዝናናሉ ካልክ አእምሮህን ያዝናናው የዘፈኑ ጽንሰ ሀሳብ ነው ወይስ ዜማው። ዜማው ነው ካልከኝ ይህንንስ እንስሳትም የሚወዱት ዜማና የሚጠሉት ዜማ እንዳለ ይታወቃልና ያው በእንስሳነትህ የመጣ ተመስጦ ስለሆነ የዘላለሙን ሕይወት በማሰብ ለዚህ ትኩረት አትስጥ እልሀለሁ። በዘፈን ረገድ ከእንስሳት እኛ የተለየነው ምናልባት ሰውን የሚያሳዝነው የሚያዝናናው ምንድን ነው ብለን ያንኑ ዘፈን በነባቢት ነፍስ መርምረን ስላስቀመጥነው ነው። እኛ ሳይንስ ብለን ትኩረት ሰጥተን አጠናነው እንጂ አዲስ ነገር የለውም። ከእንስሳት የተለየ ያደረግነው ለምሳሌ እነርሱ ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ። አቅደው ይህ ቢሆን ምግባችንን በቀላሉ እናገኛለን እያሉ ለስሜታቸው ሳይንስ አልሰሩለትም እኛ ደግሞ ሰራንለት እንጂ ያው የእንስሳዊነት ጠባይ ነው። እኛን ከእንስሳት ሙሉ በሙሉ የሚለየን ሃይማኖት ብቻ ነው። እርሱ ደግሞ ደማዊት ነፍስን ለነባቢት ነፍስ ማስገዛትን ያስተምራል ወይም ደማዊት ነፍስን ተጠቅመን መልአካዊ ወይም ነፍሳዊ ስራ እንሰራበታለን። ከላይ ያየነው እንስሳዊ ሥራ ግን ግን ነባቢት ነፍስን ለሥጋ እና ለከርስ እንዲሁም ለመሳሰሉት እንስሳዊ ባህርያትን ለማጎልመስ መጠቀም እና በእንስሳዊነት ከእንስሳት በላይ ለመሆን መጣሪያ ነው። አሁን አሁን እየተፈጠሩ ያሉ ወረቦች ዜማዎች ቅኔዎች ሥጋዊ ይዘት ሊኖራቸው ስለሚችል መርምራቸው።ለምሳሌ ገነት ይእቲ ምድረ እገሌ ብትል። በግእዝ መሆኑ እንጂ ያው ዘፈን ነው። እግዚአብሔር አይደለም እየተመሰገነበት ያለው

ስለዚህ ይህ ሊስተካከል ይገባል። ቅኔም ዜማም ፈጣሪን ቅዱሳንን ቅዱሳት ቦታዎችን ጊዜዎችን ወዘተ ማድነቂያ እንጂ ሥጋዊ ነገር ማንጸባረቂያ አይደሉም። ለምሳሌ ቶማስ ሊቅ ስሒቆ ያስሕቅ ቢል በዚህ በጥበባዊ በቅኔያዊ አነጋገር የቶማስን ገድል በቶማስ የደረሰውን ለሰው ሲሰሙት ደስ በሚያሰኝ ጥበብ ገልጾታል)

ቤተ ክርስቲያን

ታቦት ዘዶር ሲል ታቦት እመቤታችን ዶር ቃል ወልደ አብ ማለት ነው። ሰሎሞን መቅደስ ሰርቶ የመጀመርያውን ዙሪያ ኤላም ሁለተኛውን ሃይክል ሦስተኛውን ዳቤር አለው። ሙሴም ደብተራ ኦሪትን ከሰራ በኋላ የመጀመርያውን ምስሀል አለው ሁለተኛውን ቅድስተ ቅዱሳን አለው ሦስተኛውን ምቅዋመ ሕዝብ አለው። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። ጻሕል በዘባነ ማርያም ጽዋዕ በሕጻን ኢየሱስ ይመሰላል። ዕጣኑ የትስብእት መዓዛው የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ሻኩራው 24 መሆኑ የካህናተ ሰማይ ምሳሌ። ቃጭሉ መጮሁ ዮሐንስ ክርስቶስ በተሰቀለበት አንጻር ቁሞ ያለቀሰው ልቅሶ ነው። (ቤተ ክርስቲያን የትም ትሁን የት የአንተ ናት። ለእገሌ ይቀርባል ስለተወለደበት አይባልም። በየትኛውም ሀገር በየትኛውም ጊዜ ያለች ቤተ ክርስቲያን ለማንኛውም ክርስቲያን እኩል ናት። ያደግኩባት ቤተ ክርስቲያን ብለህ ስለለመድካት ብቻ ከእርሷ ውጭ ሌላው ብዙም የማያሳስብህ ከሆነ ሃይማኖታዊ ሳይሆን የልማድ ጣዖት ስላለብህ ጣዖታዊ ነህ። በየትኛውም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ላለችው ቤተክርስቲያን ርስት ሲሰጥ ኮሌጅ ስትከፍትና የካህናትን ችግር ስትፈታ ስትሸለም ስትደነቅ ለወብላት ቤተ ክርስቲያን እንደተደረገ አድርገህ ደስታህ እኩል ካልሆነ ስትቃጠል ንብረቷ ሲዘረፍ ስትነቀፍ ካህናቶቿ ሲታረዱ ኀዘንህ እኩል ካልሆነ ሃይማኖትህ ምንድን ነው? ቤተ ክርስቲያን ለማሰራት ገንዘብ ስታዋጣ ከለያየህ ለአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን እኩል ስሜት ከሌለህ አንተ ማለት መናፍቅ ነህ። በአንዲቱ ቤተክርስቲያን የእኛና የእነርሱ የሚባል ክፍልፍል የለም ሁሉም የእኛ ነው። ስለሆነም በአንዲቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለአንዲቱ አገልጋይ ስታጣ መምህር ሲታጣባት ልታዝንና ያን ችግር ልትፈታ ይገባሀል። አገልጋይ መምህር ባላት እየተደሰትክ በሌላት እያዘንክ መፍትሄ ለማምጣት ነው መጣር ያለብህ። ቤተ ክርስቲያንን በጅምላ በክፍለ ሀገር በክልል በዞን በቀበሌ እያበላለጡ መናገር ምድራዊ ጣዖት ነው። የጎጃም ቤተክርስቲያን የትግራይ ቤተክርስቲያን እያሉ መለያየት። የእኛ ሊቃውንት ይበልጣሉ የእኛ ይበልጣሉ መባባል ቤተክርስቲያን አንዲት መሆኗን ከመዘንጋት የሚመጣ ደዌ ነው።ሁሉም የእኛ የአንዲቱ ቤተክርስቲያን የእኛ ሊቃውንት ናቸው እንጂ አንዷን ቤተ ክርስቲያን የእኛ የእኛ እያሉ መለያየት መናፍቅነት ነው። ለዚያ ነው የቀድሞ ሰዎች በአካባቢያቸው ላለው ሊቅና በሌላ ሀገር ላለ ሊቅ እኩል አድናቆት አክብሮት የነበራቸው። አረ እንዳውም ለሌላው ሀገር ሊቅ የበለጠ አክብሮት ስለነበራቸው ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ እስከማለት ተደርሷል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት መለያየትን የሚፈጥሩ ሰዎች ሲያጋጥሙህ ዝም ብለህ እለፋቸው አትናደድ ቢቻል ውደዳቸውና ከዚህ ክፉ አስተሳሰባቸውና ንግግራቸው አውጣቸው። አለበለዚያ ግን እንዳትነቅፋቸው እንዳትጠላቸው ተጠንቀቅ ጌታ ከሰይጣን ውጭ ማንንም እንድትተች ማንንም እንድትነቅፍ አላሰናበተህምና። ነገሩ ቢያሳዝንህም በአፍህ ላለመንቀፍ በሀሳብህ ላለመጥላት መጣር አለብህ። ቢቻል የሚነቀፍበትን ግብር እርሳውና ተወውና

የምትወድበትን ግብር ፈልገህ ውደደው ጌታችንም አባታችንም ያዘዘን ይህን ነውና። ማንኛውም መምህር ዲያቆን ተማሪ ለቤተክርስቲያን ስለሆነ ደስ ይበልህ ሁሉንም የአባትህን የጌታህን የኢየሱስ ክርቶስን ቤት የሚያገለግሉ ናቸውና የተመረጡትም በጌታ ነውና። በተቻላቸውም የጌታቸውን ቤት እያገለገሉ ያሉ ናቸውና ደስ ይበሉህ ሁሉንም ውደዳቸው ውዷን ቤትህን ሊያገለግሏት በችግር የተማሩ ልጆችን መውደድ ቢያንስህ ነውኮ። እስኪ በዓለም የሆነ ሰው በጣም ይጠላሀል ይሰድብሀል ያዋርድሀል እንበል። ነገር ግን ቤት ስትሰራ እየነቀፈህም ቢሆን ወንድሜን ልርዳው ብሎ አንተን በጥሩ ቤት ለማኖር ጭቃ ሲያቦካ ፍልጥ ሲፈልጥ ስታየው ደስ አይልህምን? ይሰድበኛል እንዳትል የሚዋደዱ ሰዎችም አንዳንድ ጊዜ ይሰዳደባሉ አረ ይደባደባሉም ነገር ግን ብዙውን ጊዜ በፍቅር ይኖራሉ። አገልጋዮች ቢሰድቡህ ክፉ ቢሆኑብህ እንኳ ግን ለጊዜው በዚች ዓለም ነው እንጂ ለዘለዓለሙ ዓለም አንተን ለማብቃት ግን ይሮጣሉ ይደክማሉ። ስለዚህ ውደዳቸው ሲታመሙ ይክፋህ ምክንያቱም አልፎ አልፎ የምትሰዳደቡ ምርጥ ጓደኞችህ እንኳ በሌላ ሰው ሲታመሙ ሲነቀፉ ሲዋረዱ ስታይ ይከፋሀልና ነው። ሲመሰገኑ ሲደነቁ ሰው ከፍ ከፍ ሲያደርጋቸው ደግሞ ደስ ይልሀልና ነው። ምክንያቱም የዘለዓለሙን ቤትህን እያሳመሩልህ ያሉት ድንቅ አባቶችህ ወንድሞችህ ናቸውና ነው። የቀድሞዎችንም አባቶቻችን የምንወዳቸውኮ ለዘለዓለማዊ ቤታችን የሚሆን ስራ ስለሰሩልን ነው። ዘረኝነት ቢሰሩብህ ክፉ ነህ ብለው በሰው ቢያስጠሉህ አይክፋህ የሆነ ሆኖ የተወሰኑ ምእመናንንም ቢሆን ምእመናንን በሚያስደስታቸው መንገድ አስደስተው ለዘለዓለሙ ኑሯቸው አብቅተዋቸዋልና በዚህ በኩል ደስ ይበሉህ መርቃቸው አድንቃቸው ውደዳቸው)።

ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ በአባቱ ከኩሽ ዘር የተወለደ ነው። በእናቱ ከሴም ዘር ነው። ቅዱስ ያሬድ በ439 ዓ.ም ዓርብ ዕለት ሚያዝያ 5 ቀን ተወለደ። ጽርሐ አርያም ወጥቶ ከቅዱሳን መላእክት አይቶ ከብሉይ ከሐዲስ ከሊቃውንት ከድርሳናት መጻሕፍት ሁሉ ጥሩ ቃላትን እየቀሰመ በዜማ አጣፍጦ ሰራ። ተስዓቱ ቅዱሳን ብሉይና ሐዲስን በግዕዝ ቋንቋ ከአባ ጌዴዎን ተማሩ። ያሬድ ከእጼ ተምሮ ወደ መምህሩ ተመለሰ (**ፍጥረታትን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ የሚላቸው እንዲህ ሲሆኑ ነው**)። በ13 ዓመቱ ብሉይ ሐዲስን ተገልጾለት አጠናቀቀ። በአክሱም ጻጻስ አቡነ ዮሐንስ ዲቁና ተሾመ። ቅዱስ ያሬድ አነጋገሩ የለዘበ ነበር። በጌዴዎን ምትክ ተተክቶ ብሉይ ሐዲስ ማስተማር ጀመረ። ሳዊራ፣ ብስድራ፣ እስክንድራ፣ መንክራ ከእርሱ የተማሩ ናቸው። ብዙ ሊቃውንትንም አስተምሯል። ያሬድ ድንግል ነው አላገባም። ሦስት የገነት ወፎች ወደ ጽርሐ አርያም ነጠቁት። በሰው ቋንቋ ተናገሩት። ወትቤሎ ኦፍ አሐቲ እነግረከ በዘትሌቡ ጸውዕ ስሞ ሐዲስ ለእግዚአብሐየር ወትነስእ ማኅሌተ እም እሥራ ወአርባእቱ ካህናተ ሰማይ በበዜማሁ። ቅዱስ ያሬድ የሚያዜመው ዜማ ምሥጢሩ የሚያጠግብ ቃሉ የሚያረካ አነጋገሩ የተሳካ ጣዕመ ቃሉና ኃይለ ቃሉ ደስ የሚያሰኝ ነው። ቅዱስ ያሬድ ድርሰቱን የጀመረበት ህዳር 6 በ534 ዓ.ም ከነግሁ 3 ሰዓት ነው። ግዕዝ የአብ እዝል የወልድ አራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ትምህርቴን ግለጽልኝ ብየ ብለምነው (አስተምሐረ-ለመነ) ጥዑም ዜማ ገለጸልኝ ሲል ዘመኑን (ህዳር 6) አስተምሕሮ አለው መሐሪ ዘአልቦ መዓትም አለ። ቅዱስ ያሬድ ሲያዜም ሕመምተኞች ይድኑ ኀዘንተኞች ኀዘናቸውን ረስተው ይደሰቱ ነበር። የሰማይ ወፎችም በጣዕመ

ዜማው ፈዘው ይውሉ ነበር። ቅዱስ ያሬድ ሰይጣንን በትእግስቱና በሚያዜመው ዜማ ድል ነስቶታል። ራዕ.12፣7-10 ወጸብእዎ ለውእቱ አርዌ ሚካኤል ወመላእክቲሁ ወተጸብኦሙ ውእቱ አርዌ ምስለ መላእክቲሁ ወስእኖሙ ወወድቀ ውስተ ምድር ምስለ መላእክቲሁ። ያሬድን ክህነት የሾመው እግዚአብሔር ነው። ለቅዱስ ያሬድ ዜማው ከነ ሥርዓቱ ነው የተገለጸለት። ዜማውን በሚያደርስበት ጊዜ ሁሉ ከመሬት 15 ክንድ መጥቆ ቆሞ ለተሰበሰቡት ሕዝብ ሲታያቸው ለራሱ ግን በተመስጦ አይታወቀውም ነበር። ከሊቃውንቱና ከካህናቱ መካከል ምሥጢሩ ስላልተረዳቸውና ጣዕመ ዜማው ስላልጣፈጣቸው ድርሰቱን አንቀበልም በማለታቸው ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል አዘው ከታህሳስ 1 ሰኞ ጠዋት ጀምሮ ምሕላ ተያዘ። ያሬድም ይህን ምሕላ ስብከት አለው። በኋላም ጌታ ከነ መላእክቱ ተገልጾ መላእክትም በያሬድ ዜማ ሲያመሰግኑ ሕዝቡ ስላየ ድርሰቱን ተቀበለው። አኮቴተ ቁርባን የሚለውን ከቅዳሴ ሕርያቆስ ውጭ ያለውን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው። አባ ሕርያቆስ ጥንት ትውልዱ አክሱም ነው። አባቱ ግብጽ ሂዶ ሳለ ከዚያ አግብቶ ሕርያቆስን ወለደ። መምህሬ ወደ አባቱ ሀገር አክሱም እንደመጣ ከቅዱስ ያሬድ ጋር ተገናኘ ይላሉ። አባ ኤስድሮስ ግን ውዳሴ ማርያም ትርጉማቸው ላይ በደመና ጠቅሳ አመጣችለት ብለዋል። መዋስእትን ለመንክራ ምዕራፍን ለሳዊራ ቅዳሴን ለብስድራ ዝማሬን ለእስክንድራ እየነገራቸው ጻፉት። ቅዱስ ያሬድ ማኅሌት በሚቆምበት ጊዜ በወርቅ ያስጌጠ እንደ በረዶ የነጣ ልብስ ለብሶ ነበር። ጌታም በደብረ ታቦር ነጭ ልብስ ለብሶ ታይቷል። ቅዱስ ያሬድ አክሊል የመሰለ ነጭ መጠምጠሚያ ጠምጥሞ ማኅሌት ያቀርብ ነበር። ንጹሕ ልብስ የእግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ምሳሌ ነው። በመዝሙረ ዳዊቱ ፍጻሜ መጨረሻ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለምን ያገባው ቅዱስ ያሬድ ነው። እግዚኦ ጸወነ ኮንከነ ጀምሮ እስከ ንዑ ንትፈሣሕ የሙሴ ጸሎት ናቸው ይባላል። ዳዊት የደረሰው ስለሚበዛ በዳዊት ስም ተጠራ እንጂ 150ው ሁሉ የእርሱ እንዳልሆነ በአርእስቱ ይታወቃል ይላሉ። መምህር ጌራና መምህር ራጉኤል አማራ ሄደው የዜማ ምልክት ያመለከቱ የአክሱም ተወላጆች ናቸው። ቅዱስ ያሬድ እሑድ ቀን አንዲት ሰራተኛ ሴት እህል ስትፈጭ ሰማት ወዲያው ሌላ ኃይለ ቃል ሳይናገራት በለዘበ በጣዕመ ዜማው ሃሌ ሉያ ሠርዐ ሰንበተ ለዕረፍት ለቅኑያን እያለ መከራት። ሃሌታውን በማኅረጽ ድምፅ ስላዜመው እስከ ቅርብ ጊዜ ድምፀ ማኅረጽ ተብሎ ነበር ይላሉ። ቅዱስ ገብርኤል ይባርክሎ ኩሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር እያለ ሲያመሰግን ሠለስቱ ደቂቅ እየተከተሉ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዐልኒ ውእቱ ለዓለም እያሉ እስከመጨረሻው አመስግነዋል። በሮማ ሄርማ የሚባል የግሪክ ተወላጅ ነቢይ ነበረ። እርሱም ለጳውሎስ ወዳጁና ቤተክርስቲያንንም በነቢይነቱና በደግነቱ በጥሩ ትምህርቱ በቀናች ሃይማኖቱ ታከብረው ነበር። በዚያ በሮሜ ሳለ አንድ ቀን ወይዘሮ ሴት በራእይ አይቶ በራእይ ተዋወቃት እንደ እኅቱ አድርጎም ወደዳት። መልካም ነገርንም አሰበላት። በሌላ ጊዜ በሌላ ቦታ ይች ሴት በፈለገ ጤግሮስ ውሃ ስትታጠብ ለሁለተኛ ጊዜ አያትና ተሰወረችበት። ከዚያ ወሪድየ ብሔረ ሮሜ ለብእሲት ርኢክዋ አእመርክዋ አፍቀርክዋ ከመ እኅትየ ሠናየ ሐለይኩ እምድህረ ጉንዱይ ዓመታት ወእምዝ እምድህረ ኀዳጥ መዋዕል ካዕበ ርኢክዋ ወትትኀጸብ በፈለገ ጤግሮስ እያለ ተቀኘላት። ቅዱስ ያሬድ ብእሲትን በቤተክርስቲያን ለውጦ አነበበው። ያሬድ ካህን ወንጉሥ ገብረ መስቀል ሠርዐ በፍቅር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ወቤተ መንግሥት። ወንጉሥ ገብረ መስቀል ይሰቀል በአጽምዖተ ዜማሁ። ውእቱሰ ያሬድ ካህን

ኢይፈቅድ ነቢረ በከተማ ንጉሥ። አላ ያፈቅር ከመ ይብጻሕ ወይዑድ ውስተ አብያተ ክርስቲያናት ዘኢትዮጵያ። ወባሕቱ ንጉሥ ኢያበውሆ ይትፈለጥ እምኔሁ እስመ ጥቀ ያፈቅሮ ከመ ርእሱ። ቅዱስ ያሬድ ዜማ ሲያስተምር "ዘወረደ መንፈስቅዱስ ጸራቅሊጦስ ላዕለ ሐዋርያት ወከሠተ ሎሙ ምሥጢረ ነገረ በሐውርት ይረድ ላዕሌክሙ ወይክስት ለክሙ ምሥጢረ ስብሐት" ብሎ መርቆ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልይ ነበር። ትምህርት ሲጨርስም "ዘተመሀርክሙ ኩሎ ስብሐተ እግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ያኅድር ውስተ ልብክሙ ወንበል አቡነ ዘበሰማያት" ብሎ ሲመርቃቸው አቡነ ዘበሰማያትን በዜማ አብረው ይጸልያሉ። ያሬድን ገብረ መስቀል በበትሩ ተመስጦ ቢወጋው ሕማሙን ታግሦ ዜማው እስኪያልቅ አመሰገነ። ስለ ማኅሌተ እግዚአብሔር ሰማእት ሆነ። ተከዚ ከአራቱ አፍላጋት አንዱ ኤፌሶን የተባለው ነው። ወሖረ ያሬድ ውስተ ገዳመ ስሜን ምድረ ጸለምት አዲዎ ተከዜ ወነበረ በህየ ደብረ ሐዊ ዘይትበሀል ሳኔር። ያሬድ አረፈ ማለት ሞተ ማለት አይደለም ተሰወረ ማለት ነው እንጂ። በ75 ዓመቱ ተሰወረ። ቅዱስ ያሬድ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያደራጀ በዜማ አቀረባቸው። አዕረፈ ያሬድ ካህን ፈጺሞ ገድሎ ወመዊየ ሰይጣነ በመኃልይሁ ጥዑም። ሳዊራ አባ ገሪማ ገዳም ደብረ መደራ ገብቶ። ዜማ እያስተማረ ብዙ ሊቃውንት አስተምሮ ዕድሜውን በዚያው ፈጸመ። መንክራ ደብረ ዳሞ ሂዶ ሲያስተምር ኑሮ በዚያው ተቀበረ። ብስድራ ሐማሴን ሄዶ ነው ያስተማረ። በማኅሌት ብዛት ልቡ ፈርጦ ነው የሞተው። የብስድራ ተማሪ ፀሐየ ቅዱሳን ወደ ሽዋ መጥቶ አጼ ገብረ መስቀል ባሰሩት ጎሐ ጽዮን ቤተክርስቲያን እያስተማረ ብዙ ደቀመዛሙርት ተክቶ በዚያው አረፈ። በስመ ኃዳሪ ይጼዋእ ማኅደር ወበስመ ማኅደር ይጼዋእ ኀዳሪ እንዲል ሊቃውንቱ በሚያገለግሉባት **ደብተራ** ተብለዋል። ወእስክንድራ መሐሮሙ ለካህናተ አክሱም። አባ በጸሎተ ሚካኤል ትውልዱ አክሱም ከተማ ነው። አባ በጸሎተ ሚካኤልን ከሴት ጋር አሰሩት ሴቲቱም ፈገግታ እያሳየች ትወደኛለህ ትለው ጀመረች። አባም ለይምሰል በአፉ አዎ እወድሻለሁ እያለ በልቡ ወአውጽአኒ እምዛቲ መስገርት እያለ ከጸለየ በኋላ ወንድና ሴት ታስረው ግብረ ሥጋ መፈጸም ውርደት ነውና ፍቺኝ ሲላት እውነት መስሏት ፈታችው ይህን ጊዜ ቀስ ብሎ አመለጣት። በጸሎተ ሚካኤልም መስገርትሰ ተቀጥቀጠ ወንሕነሰ ድኅነ እያለ ጸለየ። የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም አባቱም እናቱም የአክሱም ተወላጆች ናቸው። ጣና ቂርቆስ ያለው ድጓ ያሬድ የጻፈው ነው የሚለው አያስኬድም ምክንያቱ ከዚያው መጽሐፍ ውስጥ በ1523 ዓ.ም እኔ ዮሐንስ ከማ ጻፍኩት የሚል አለና። ገዳሙን ለማስከበር ተብሎ መዋሸት እና እውነትን አፍኖ መኖር አይገባም። ያሬድ ዜማውን አዜመ እንጂ ምልክት አላመለከተም። አስሩንም ምልክት የሰሩት አዛዥር ጌራና አዛዥር ራጉኤል ናቸው። 2ቱ የፊደል 8ቱ የምልክት ናቸው። **ሥረዮ** ማለት ራሱ ባለቤት ሆኖ መልሶ በሌላ ቀለም ላይ ተመልክቶ ዜማውን የሚመራ ዋና መሪ ነው። ወይ አይዋጋ ወይ አይሸሽ በህየንተ አበውኪ የገባ ነው። ቡበይ ላሜ በነዋ በግዑ የገባ ነው። በፋሲል ዘመነ መንግሥት ዙር አባ የመዋስእትና የዝማሬ ማስመስከሪያ ሆነ። በኋላ የነ ተዋነይ ቅኔ ሲመጣ የዜማ መምህራን በየዜማው መካከል እንዲደረግ ወሰኑ።

የዜማዎቹና የዘመናት ሥያሜዎች

የመዝሙረ ዳዊቱን መስመር በአራት በአራት ስለከፈለው **አርባዕት** ብሎታል። ቅዱስ ያሬድ ድርሰቱን የጀመረበት ህዳር 6 በ534 ዓ.ም ከነግሁ 3 ሰዓት ነው። ግዕዝ የአብ እዝል የወልድ

አራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ትምህርቱን ግለጽልኝ ብየ ብለምነው (አስተምሐረ-ለመነ) ጥዑም ዜማ ገለጸልኝ ሲል ዘመኑን (ህዳር 6) **አስተምሕሮ** አለው መሐሪ ዘአልቦ መዓትም አለ። ታኅሣሥ 7 የክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔርነቱ ስለተገለጸለት ነቢያትም አምለሰክ ሰው ይሆናል ብለው የተናገሩት ትንቢት የተፈጸመበት ቀን ስለሆነ **ስብከት** አለው። በሳምንቱ በታኅሣሥ 14 ጌታ በብርሃን አምሳያ ተገልጾ ሳምንት ሁሉ ሲታየው ስለሰነበተ **ብርሃን** አለው። ታኅሣሥ 20 ለሦስተኛ ጊዜ በአምሳለ ኖላዊ ኄር ተገልጾ ስለታየው ኖላዊነ ዘመጽአ ኀቤነ እያለ በሥርዓተ ዋዜማ አመሰገነው ስለዚህም **ኖላዊ** አለው። ከኖላዊ ሳምንት በኋላ ታኅሣሥ 25 ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን ጌታ በአምሳለ መርአዊ ሲታየው ስለሰነበተ **መርዓዊ** አለው። ምዕራፍ በጌታ ዕረፍት ጊዜ የተነገረውን ቃለ አምላክ (ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው) ጠቅሶ ዜማውን ስለጀመረው **ምዕራፍ** አለው። አንድም ቅዱስ ያሬድ የመዝሙሩን ድርሰት ፈጽሞ በዚሁ ጣዕመ ዜማ ሰይጣንን አሸንፎ ከፈተና ካረፈ በኋላ የደረሰው ስለሆነ **ምዕራፍ** አለው። **ዓቢይ ስብሐተ ነግህ** የተባለው በዓበይት በዓላት ስለሚዘመር ነው። **ንዑስ ስብሐተ ነግህ** ደግሞ ነጋ ነጋ ዓመት እስከ ዓመት የሚደረስ የዜማ ጸሎት ነው። ቅዱስ ያሬድ እግዚኦ መኑ የኀድር ውስተ ጽላሎትከ እያለ በአንክሮ ወደ ፈጣሪው ጥያቄውን በዜማ ሲያቀርብ መንፈስ ቅዱስ ዘየሐውር በንጹሕ ወይገብር ጽድቀ ብሎ ስለመለሰለት **መዋስእት** አለው። መዋስእት ማለት በጸሎት መጠየቅና ከእግዚአብሔር መልስ ማግኘት ማለት ነው። **የፍትሐት ሥርዓት** በቀዳም ስዑር ተጀመረ ጌታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳተ ሙታንን ከእስራት የፈታበት እለት ነው። ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ ሀሌ። ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዐርየ ሀሌ። ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ እንዲህ እንዲህ እያለ በሦስት መስመር እየተከፈለ ስለተጸለየ **ሠለስት** ተባለ። **ክሥተት** ማለት ከመዝሙረ ዳዊት ከመኃልየ ሰሎሞን ሁለት ሁለት መስመር እየተገለጸ (እየተከሠተ) ስለደረሰው ክስተት አለው። **ዘአምላኪየ** የተባለ በአምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ መካከል እየተዛነቀ ስለሚባል ነው። **ምልጣን** ማለት ከእናቱ ዜማው ለውጦ መሪ የሚያመለጥነው ነው። **መስተጋብኤ** ማለት የመዝሙረ ዳዊቱ ምርጫ ቃላት መሰብሰቢያ መከማቻ መደራጃ ማለት ነው። **ምቅናይ** ማለት የምዕራፉ መርገፍ ማለት ነው። **ምስጋድ** የተባለው እየሰገዱ የሚደርስ ጸሎት ነው። ስብሐተ ነግህ ከሌሊት ጨለማ አውጥተህ እንኳን ወደንጋቱ ብርሃን አደረስከን እያልን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና ነው። ንዋየ ቅድሳቱ ሁሉ እንዳለ በቤተክርስቲያ ውስጥ ሰንብቶ በ8ኛው ቀን ከቁርባን ፍጻሜ በኋላ ወደቤተ መዛግብቱ ስለተመለሰ **አግብኦተ ግብር** ተባለ።

22ቱ አርእስተ ዜማ፣ ሥርዓተ ማኅሌት

22ቱ አርእስተ ዜማ የ22ቱ ስነፍጥረት የ22 አሌፋት ምሳሌ ናቸው። እኒህም ዋዜማ፣ ኀምስቱ፣ እግዚአብሔር ነግሠ፣ ይትባረክ፣ **ሠለስት**፣ ሰላም፣ መዝሙር ዘሰንበት፣ **ዘአምላኪየ**፣ **እግዚኦ ሚበዝኁ** አመ ሣልስት ዕለት፣ አርባዕት፣ **ብጹዕ ዘይሌቡ** ሠርከ ሰንበት፣ **መወድስ (ፍታሕ ሊተ)** ክርስቶስ ተንስአ፣ **ኩልክሙ** ዮም በዛቲ ዕለት፣ እዝል፣ ዘይእዜ፣ ማኅሌት፣ ስብሐተ ነግህ፣ እስመ ለዓለም፣ **አርያም፣ ክብር ይእቲ፣ ዝማሬ፣ ዕጣነ ሞገር** ናቸው። ከ22ቱ አርእስተ መዝሙር ለ12ቱ ምልጣን አላቸው ለ10ሩ ግን የላቸውም። የሌላቸው በደማቅ ከዚህ በላይ የተጻፉት ናቸው። ምልጣን የሌላቸው የደናግላን ምሳሌ። ያላቸው ልጅ ያላቸው የሰብአ

ዓለም ምሳሌ ነው። የመዋስእት አደራረሱ 12 ጊዜ መድረሱ የ12ቱ ነገደ እስራኤል ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ምሳሌ። ጌታም ነፍሳትን ከባሕረ እሳት አሻግሮ ገነት አውርሷቸዋል። 9 ጊዜ መድረሱ የዓርብ 9 ሰዓት አምሳል ከጌታ ትኩስ ደም ጽሩይ ደም ፈሶ አዳምን እንዳነጻው ይህም መንጽሔ ኃጢአት ነውና። 7 ጊዜ መድረሱ የ7ቱ ዕለታት ምሳሌ በ7ኛው ቀን እንዳረፈ ይህም ምዕራፈ ነፍስ ነው ለማለት። 5 ጊዜ መድረሱ ስለ 5ቱ ቅንዋተ መስቀል ስለ 5ቱ አዕማደ ምሥጢር አምሳል ነው። እናቱ የእመቤታችን ምልጣኑ የጌታ ምሳሌ። በኒቆዲሞስ ሦስቱ መዝሙራት በአንድ ጊዜ መባላቸው አንዱ ህየንተ ዝማሬ አንዱ ህየንተ ጽዋዕ አንዱ ህየንተ መንፈስ ነው። ቅዱስ ያሬድ መዝሙሩን በ4 ክፍል (ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ ጾም፣ ክረምት) አድርጎ መስራቱ የ4ቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ነው። በዓርብ ስቅለት መሥዋዕት ሳይሰራ ቅዳሴ ሳይቀደስ ክብር ይእቲ ዝማሬ ዕጣነ ሞገር ለምን ሰራ ቢሉ ራሱ ኢየሱስ በመስቀል ተሰውቷልና ነው። 1 ሀሌታ የአንድ አምላክ 2 ሀሌታ የቃልና የትስብእት 3 ሀሌታ የሥላሴ 4 ሀሌታ የኪሩቤል 5 ሀሌታ ከ5500 ዘመን በኋላ የመወለዱ 6 ሀሌታ የ6ቱ ቃላተ ወንጌል 7 ሀሌታ የ7ቱ ሀብታት 8 ሀሌታ የ8ቱ ብሔረ ኦሪት 9 ሀሌታ በ9 ሰዓት ዓርብ ትኩስ ደምና ንጹሕ ውሃ የመፍሰሱ ምሳሌ ነው። ቁም ዜማ ዝማሜ መረግድ ጽፍዓት የኪሩቤል አምሳል ናቸው። ቁም ከመ ኪደተ ብእሲ ዝማሜ ከመ ኪደተ አንበሳ መረግድ ከመ ኪደተ ላሕም ጽፍዓት ከመ ኪደተ ንስር ነው። መራሒ ሰላም መምራቱ የጌታ ምሳሌ ተመሪ የአዳም ምሳሌ ነው። ምዕራፍ የማርያም ድንግል። በዘይብሉ ቅኔው የልጇ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። መሪ የዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ አንሺ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። በመሪ ገጽ ዕዝሉን የዘለቁ መዘምራን የአርድእተ ዮሐንስ ምሳሌ ናቸው። በአንሺ ገጽ የዘለቁት የአርድእተ ክርስቶስ ምሳሌ ናቸው። በመጨረሻ በጎብረት ማድረሳቸው መላእክትና ሰዎች በልደት በጎብረት የማመስገናቸው ምሳሌ ነው። መሪ ጎበ አንጸረ ቀዳማዊ ባለው ሲመሰል ተመሪው የሐውሩ በተባሉ በተከታዮቹ ይመሰላል። መስከረም 25 ቀን አጼ ገብረ መስቀል በአክሱም መናገሻ በተገኙ ጊዜ ቅዱስ ያሬድ ዘመኑንና በዓሉን (ክረምት የወጣበትን በዓል) አስተባብሮ የአጼ ገብረ መስቀልን ለሹመት እጩነታቸውን ጠቅሶ ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ሐጼጌ እያለ በዜማ አሳሰባቸው። መስከረም 25ም በየዓመቱ እንዲከበር ከዚያ ወዲህ ተወሰነ። ግሡ ሐጸየ አጨ ካለው የወጣ ጥሬ ዘር ነው። ጌተ ገገር ሆነ ይላል። ያሬድ ካህን ወንጉሥ ገብረ መስቀል ሠርዐ በፍቅር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ወቤተ መንግሥት። ወንጉሥ ገብረ መስቀል ይሰቀል በአጽምዖተ ዜማሁ። የማህሌቱን አደራረሱን የሰሩት በየጊዜው የተነሱ ሊቃውንት ናቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቅንዋተ መስቀል

ጌታ በ5500 ዓመት መስከረም ረቡዕ ገብቶ ታኅሣሥ 29 ቀን ማክሰኞ ሌሊት ተወለደ። በ5531 ዓመት ጥር 11 ማክሰኞ ሌሊት ተጠመቀ። ጌታ ከሱባኤው በወጣ በሦስተኛው ቀን ማክሰኞ ዕለት የካቲት 23 ቀን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ውሃውን ወደ ወይን ቀየረው። ውሃውን ከውሃ አነጻጽሮ ጥር 12 እንዲከበር ያሬድ ሰራው። ጌታን በአላዶር ቀኝ እጁን በዳናት ግራ እጁን በአዬራ ሁለቱን እግሮቹን ደርበው ቸነከሩት። ሳዶር የሚባለው ብረት እንደዝናር የሚታጠፍ ላይና ታቹ እንደ መጋዝ ጥርስ ያለው አምጥተው ሰውነቱ እንዳይንቀሳቀስ ከልቡ በታች በሽንጡ መካከል ከመስቀሉ ጋር አስታጠቁት። ሮዳስ የተጠላለፈው መስቀል የተያያዘበት ነው።

መላእክት

የቅዱሳን መላእክት ሥራ ያለድካም ያለ ዕረፍት ቀንና ሌሊት ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን በዜማ ማመስገን ብቻ ነው። መላእክት ሲያመሰግኑ አንዱ መልአክ ምስጋናውን ሲጀምር ሌሎች መላእክት አንዲት የሴኮንድ ደቂቃ ታህል ጸጥ ማለታቸውን ሲያስረዳን ያረመ ሕቀ ከመ ይወድስዎ እያለ በደረሰው ምዕራፍ ዘዘወትር አስተምሮናል።

ምሕላ

ዘጸ.30፣10-11 ይትመሐለል አሮን በዲበ አቅርንቲሁ ይላል። ኢዮ.10፣14 ቀድሱ ጾመ ወስብኩ

ምሕላ ይላል።

ስለዮዲት ጉዲት

ዮዲት ከአክሱም ጽዮን ደጀሰላም ተቀምጣ ወድቃ ታቦተ ጽዮንን ተማፀነች። የ22 ዓመት ጎልማሳ ዲያቆን በዝሙት ስለተነደፈ በልቡ ተመኛት በጣም ቆንጆ ነበረችና። ከቤተ ክርስቲያን ወርቅ ሰርቶ ጫማ አሰርቶ ሰጣት በስውር ወዲያውም አረከሳት። ካህናቱም የዲያቆኑ ችግር መሆኑን እያወቁ በዮዲት በሐሰት ፈርደው ለንጉሡ ሰጡት ንጉሡም እርሷ እንዳላጠፋች እያወቀ ልብሷን ገፎ ጡቶቿን በሰይፍ አስቆረጠው ወደቀች። ከዚያ ወዲህ ገበዘ አክሱም ሴት እንዳይገባ ተከለከለ። ዮዲትንም አውሬ እንዲበላት በረሃ ጥለዋት መጡ። እግዚአብሔር ግን አንድ ግብጻዊ እንዲጎበኛት አደረገ። ለግብጽ ንጉሥም ልኮ አሳከማት። ያም የአክሱም ንጉሥ ድግናገርን ሞቶ ልጁ አንበሳ ውድም ነገሠ። ከዚያ መጥታ ይህን ሁሉ ውድመት አደረሰች።

ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

አዘጋጅ፡-ሊቀሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ

ምንም ቢሆን ሊቃውንት ያሉት ሕዝብ ችግር አይፈጠርበትም ቁም ነገር አይጠፋበትም። ለሁሉም ነገር መልክ ይሰጡታል። ማንኛውንም ነገር ለመውደድም ሆነ ለመጥላት ነገሩን አስቀድሞ ከሥሩ ከመሰረቱ ማወቅ ያስፈልጋል። እንዲሁ መጥላትም እንዲሁ መውደድም ተገቢ አይደለም። (ዓለማቀፋዊ ወይም Universal እውቀት ይኑርህ። የሰው ልጅ መሬት ነው መሬት ደግሞ የዘሩባትን ታበቅላለች። ከመሬት ሰው የሚለየው ለነፍሱ የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውን እየመረጠ ማብቀል ይችላል። ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አሰራር የሚያመች አዲስ ድርሰት አዲስ ሥርዓት ማምጣት ይቻላል። ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚነታቸው ተመርምሮ እንደ ቅኔ እንደ አቋቋም አዲስ ግኝቶችንም ወደ ሥርዓታችን ማስገባት ይቻላል። ይህ የሚሆነው ግን በሲኖዶስ በኩል ነው። አዲስ የመጣው ነገር ደግሞ ምን ነፍሳዊ ፋይዳ አለው የሚለው ተገምግሞ ነው። ማንኛውም ሥርዓት ከነፍሳዊ ጥቅሙ አንጻር እየተገመገመ ሊሻሻል ይችላል። በብዙ ረገድ አሁን የያዝነው ሥርዓት በየዘመኑ እየተሻሻለ የመጣ አዲስ እየተጨመረበት ከድሮው እየተቀነሰለት የመጣ ነው። ስለዚህ ነፍሳዊ ጥቅሙ ከፍተኛ የሆነ አዲስ ሥርዓት ብትፈጥርም በሲኖዶስ ታይቶ ሊጸድቅ ይችላል። ከድሮው ውጭ አይሆንም

የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ። እኒህ ግን የያሬድንም ዜማ አዲስ ነው ከድሮው ውጭ አይሆንም ብለው የተቃወሙ በየዘመኑ የተነሱትን የሚቃወሙ። ነገር ግን እነርሱ ነባር ብለው የያዙትም እየተሻሻለ እንደመጣ የማያውቁ ድኩማን ናቸው። ስለዚህ የከዚህ ቀደሙን ባህልም አይተህ ነፍሳዊ ጥቅሙን አይተህ የሚስተካከለውን አስተካክለው። ነፍሳዊ ጥቅሙ የጎላ የውጭ አለባበስ ባህል የሥራ ባህል ወዘተ ካለ መዋስ ነው። አባቶቻችን ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተረጎሙ ያመጡልን ነፍሳዊ ጥቅማቸውን ገምግመው ነው። ለምሳሌ ሴቶች ሱሪ ቢለብሱ ያለው ነፍሳዊ ጉዳት ምንድን ነው ስትል ሰውነታቸውን ጥብቅ አድርጎ ውስጣዊ አካላቸውን ስለሚያሳይ በዚህ ምክንያት ደግሞ ወንዱ ፍትወት ስለሚነሳበት። ይህ ደግሞ ማመንዘርን ስለሚያስከትል ነፍሳዊ ጉዳት የሚያስከትል ስለሆነ ቢቀር ልትል ትችላለህ። የወንዱንም አለባበስ አነጋገር አበላል ወዘተ ከነፍሳዊ ጥቅሙ ጋር እያቆራኙ መተቸት ይቻል ይሆናል ማሻሻልም ይቻል ይሆናል። አዲስ የልብስ ዲዛይን መፍጠርም ይቻላል። አባቶችን ስታደንቅም ያስተላለፉልህን ነገር በነፍሳዊ ሚዛን ገምግመህ መልካም ሆኖ ስታገኘው ነው። ዝም ብለህ የአባቶቹ ባህል እያልክ ጊዜህን ከምታባክን ባህሉን መርምረህ ነፍሳዊ ጥቅሙን አይተህ ጥሩ ከሆነ ያስተላለፉልህን አባቶች ለማመስገን የአባቶችን ባህል ብትል መልካም ነው። አንተ የሌሎችን ባህል ለመጥላት የአንተን ለመውደድ መለኪያህ ነፍሳዊ ጥቅሙ እንጂ አንተ ስለለመድከውና ስላልለመድከው መሆን የለበትም። ስለዚህ የተሻለ ባህል አለባበስ ቋንቋ ካለ ውረሰው። እንኳን ባህል መንፈሳዊ ሥርዓትንኳ ሊሻሻል ይችላል። ክልማዳዊ አመክንዮ ውጣና ሃይማኖታዊ አመክንዮ ይኑርህ። በጥሩ አስተያየት ምሁራዊ በሚመስል ትንታኔ ተደብቀው የሚመጡ ጅል ሀሳቦች ሊኖሩ ስለሚችል በጥልቀት እያሰብክ ላለመሸወድ ሞክር። የሆነን ጉዳይ መልካምነቱን ካረጋገጥክ ለማድረግ ምንም ሊያግድህ አይገባም ባለህ ነገርና አቅም ያን ነገር ለማድረግ ሞክር። እግዚአብሔር በሰጠህ አቅም ትሰራለህ እንጂ ሌላ አትመኝም ጌታም የሚጠይቅህ በሰጠህ ነውና። ይህን ለማድረግ ጳጳስ ብሆን ንጉስ ብሆን ባዕለ ጸጋ ብሆን አትልም። ባለህ አቅም በፍቅር ትሰራዋለህ እንጂ። መልካም ነገር ለማድረግ የሌላቸውን ነገር የሚፈልጉ የሚጠብቁ ደካሞች ናቸው። እግዚአብሔርንም ማንኛውንም መልካም ነገር እንዳናደርግ ሙሉ ነገር አልሰጠኸንም እንደማለት ይቆጠራል። ከማንኛውም ሰው የሚጠበቀው በተሰጠው በትጋት ማገልገል እንጂ ንጉስ ብሆን ጳጳስ ብሆን ወዘተ የሚለው የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የሚለውን ሕግ መተላለፍ ይሆናል። ራስህን ከተሰጠህ ጸጋ ጋር እያወዳደርክ በተሰጠህ ጸጋ የሠራኸውንና ያልሰራኸውን ማወዳደር አለብህ እንጂ ራስህን ከሌላው ጋር የምታወዳድር ምን አገባህ? አንተም የምትጠየቅ በስራህ እርሱም የሚጠየቅ በስራው ነውና። አንዳንድ ጊዜ መንግሥት ራሱ እየሰደበ ይተናኮስህና መልሰህ ስትሰድበው ያሳስርሀል። ሰይጣንም በሰዎች አድሮ ይሰድብህ ያንቋሸሽህና መልሰህ ሰውየውን ስትሰድበው ስታቃልለው። ይችን ምክንያት አድርጎ ሲኦል ያስገባሀል። ስለዚህ ትዕግስት ይኑርህ ጌታ ትእግስት ይኑራችሁ ያለን ከዚህ ዓይነት ፈተናም ለመዳን ነው። አሁን የምትወደውንና የምትጠላውን በማስተዋቂያ ተጽዕኖ እንድትወደው እንድትጠላው የተደረገ ነው ወይስ እውነትም የሚጠላ የሚወደድ ሆኖ ነው የሚለውን በአእምሮ ጠባይዓዊና በቃለ እግዚአብሔር ሚዛንነት ፈትነው ፈትነህ ያዝ እንደ ከብት አትነዳ። ለምሳሌ ወንድምህና አውሮፓዊ ቦክስ ገጥመው ለወንድም የምታደላውኮ በእንስሳዊነት ባህርይህ ነው። እንስሳ የለመድውን ይወዳል ስለዚህም ያልለመደው በሬ ከለመደው ሲገጥም ሲያይ የለመደውን ሊያግዝ

ይችላል። እግዚአብሔራዊ እይታ ግን የለመድከውንም ያልለመድከውንም በእኩል ሚዛን አድርጎ በቃለ እግዚአብሔር ዳኝነት ነፍሳዊ ፍርድ መስጠት ነው)።

የፊደላት ትርጉም፣ ሥርዓተ ጽሑፍ

ሀ ብሂል ሀልዎቱ ለአብ እምቅድመ ዓለም፣ ቁጥሩ 1

ለ ብሂል ለብሰ ሥጋ እምድንግል፣ ቁጥሩ 2

ሐ ብሂል ሐመ ወሞተ፣ ቁጥሩ 3

መ ብሂል መንክር ግብሩ ለእግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 4

ሠ ብሂል ሠረቀ በሥጋ፣ ቁጥሩ 5

ረ ብሂል ረግዐት ምድር በቃሉ፣ ቁጥሩ 6

ሰ ብሂል ሰብአ ኮነ እግዚእነ፣ ቁጥሩ 7

ቀ ብሂል ቀዳሚሁ ቃል፣ ቁጥሩ 8

በ ብሂል በትህትናሁ ወረደ፣ ቁጥሩ 9

ተ ብሂል ተሰብአ ወተሠገወ፣ ቁጥሩ 10

ኀ ብሂል ኃያል እግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 20

ነ ብሂል ነሥአ ደቂነ ወጸረ ሕማመነ፣ ቁጥሩ 30

አ ብሂል አአኩቶ ወእሴብሆ ለእግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 40

ከ ብሂል ከሀሊ እግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 50

ወ ብሂል ወረደ እምሰማይ፣ ቁጥሩ 60

ዐ ብሂል ዐርገ ሰማያተ፣ ቁጥሩ 70

ዘ ብሂል ዘኩሎ ይእኀዝ እግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 80

የ ብሂል የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ፣ ቁጥሩ 90

ደ ብሂል ደመረ ሥጋነ ምስለ መለኮቱ፣ ቁጥሩ 100

ገ ብሂል ገብረ ሰማያተ በጥበቡ፣ ቁጥሩ 200

ጠ ብሂል ጠዐሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር፣ ቁጥሩ 300

፩ ብሂል ጸራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ፣ ቁጥሩ 400

፪ ብሂል ጸጋ ወክብር ተውህበ ለነ፣ ቁጥሩ 500

፬ ቁጥሩ 600

፭ ብሂል ፈጠረ ሰማየ ወምድረ፣ ቁጥሩ 700

፻ ብሂል ፓፓኤል ስሙ ለአምላክ፣ ቁጥሩ 800

የፊደል ተማሪ የቁጥር ተማሪ የተባለበት ምክንያት የየፊደሉን ስም ከመልክ በመለየት ሀ፣ ለ፣ ሐ እያለ እየቆጠረ ስለሚማር ነው። **ፊደለ ሐዋርያና ገበተ ሐዋርያ** የተባሉት የትምህርት ዓይነቶች ከአቡጊዳ ቀጥለው የሚገኙ ሲሆኑ የመጠሪያ ስማቸው እንዲህ የተባለበት ምክንያት ምን እንደሆነ አይታወቅም። በቤተ ክርስቲያን ግን የታወቀ ስማቸው መልእክተ ዮሐንስና ሌሎችም መልእክታት ናቸው። ፊደለ ሐዋርያ ቀ፣ ዳ፣ ሚ፣ ሁ፣ ቃ፣ ል...እያለ የሚሐደው ነው ገበተ ሐዋርያ የሚለው ግን እስካሁን ከነስሙ እንግዳ ነገር ነው። በጽሑፍ ጊዜ አርእስት የሚባለው የመጽሐፉ ራስ ያልተጻፈበት ቦታ ነው። **ጎዳግ** ማለት የተተወ ማለት ሲሆን በግርጌ ያልተጻፈበት ነው። **ግሌት** የተባለው ወደ መጨረሻ ያለው ቦታ ነው። **ሕላፍ** የተባለው ወደ ጫፉ ያለው ቦታ ነው። **ዓምድ** የተባለው በሁለቱ ጽሑፎች መካከል የማይጻፍበት ቦታ ነው። ወስፌው ያለፈበት ወይም መስመሩ **ሲራክ** ይባላል። **ምስማክ** የሚባለው ፊደሉ የሚጻፍበት በመስመሩና በመስመሩ መካከል ያለው ነው። **ማኅጸን** የተባለው በፊደሉና በፊደሉ መካከል የሚገኘው ቦታ ነው። ነጥብ (.) ንዑስ ሰረዝ (፣) ዓቢይ ሰረዝ (፤) ሙሉ ነጥብ (።) በግእዝ ሥርዓተ ጽሕፈት ያገለግሉ ነበር። ጥያቄ ምልክት ግን አልነበረም። በዚያ ምትክ "ኑ" ነበረ። ሕያውኑ አቡክሙ እንዲል። ከፊደላት ሀ፣ ሐ፣ ኀ፣ አ፣ ዐ በጉረሮ፡- ገ፣ የ፣ ከ፣ ቀ በትናጋ፡-ደ፣ ለ፣ ነ፣ ጠ፣ ተ በምላስ፡- በ፣ ወ፣ መ፣ ፈ፣ ጸ በከንፈር፡- ዘ፣ ሠ፣ ሰ፣ ጸ፣ ፀ፣ ረ በጥርስ የሚነገሩ ናቸው። ካህናት የሆኑ ሁሉ የጻፉ እንደሆነ ይጠነቀላሉ እየተባለ ጽሕፈት እንዳይማር አንዳንድ መምህራን ይከለክሉ ነበር። ከቁጥር ትምህርት ቀጥሎ ሁለተኛው **የንባብ ትምህርት** ነው። ድርሳናቱን ተአምሩን ብሉያቱን ሐዲሳቱን ወዘተ ማንበብ ነው።ግዕዝ ንባብ የተባለው ከቁጥር በተሻለ መንገድ ፊደላትን ማጋዝ ነው ዜማ የሚመስል ነገር ስላለው ከቁጥር ሻል ይላል። ውርድ ንባብ የሚባለው በስቅለት የሚባለው ነው። ከዚያ ቀጥሎ ከንባብ ቀጥሎ ያለው ትምህርት **ዳዊት መድገም** ነው። ዳዊት ቀን እየተማሩ ማታ ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃንን በቃል ስለሚማሯቸው **የቃል ትምህርት** ተብለው ይጠራሉ። **በስመአብ** ብሎ የሚጀምረውን የቃል ትምህርት ማን እንደደረሰው አይታወቅም። **ነአኩተከም** እንዲሁ (ከቅዳሴ ሐዋርያት የወጣ ነው የሚሉ አሉ) **በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል** ከወንጌል የተወጣጣ ነው። ቅዱስ ቅዱስ የሚለውም ከኢሳይያስ የተወጣጣ ይመስላል። ሌላው ግን በሀገር ሊቃውንት የተደረሰና የተቀነባበረ ነው። ግን መቼ ማን ደረሰው የሚለው ጥያቄ አሁንም መልስ አያገኝም። **ስብሐት** የሚለው በኢትዮጵያ ብቻ የሚባል የምስጋና ጸሎት ነው። ይህንም ማን እንደደረሰው መቼ እንደተደረሰ ግልጽ የሆነ ማስረጃ የለውም። **ሰላም ለኪም** በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብቻ የሚጸለይ ጸሎት ነው። የዜማም መጀመሪያ ነው። ደራሲውና የተደረሰበት ጊዜ አይታወቅም።

ውዳሴ ማርያም በቅዱስ ኤፍሬም በግጥም መልክ የተደረሰ ነበር፡፡ ወደ ግእዝ ሲተረጎም ግጥምነቱን አጥቷል፡፡ በጥንት ጊዜ ሶርያውያን በጸሎት ይጠቀሙበት ነበር ይባላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በቀር የሚጠቀምበት የለም፡፡ ሰአሊ ለነ ቅድስትን ቅዱስ ያሬድ እንደጨመረው ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ የኋላ ሊቃውንት ናቸው የሚሉም አሉ፡፡ **መልካ መልክ** የአንዱን ቅዱስ አካል በመዘርዘር ምስጋና ማቅረብ ነው፡፡ ድርሰቱም የኢትዮጵያውያን ነው፡፡ ከመልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ ውጭ ያለውን ተማሪው እንደ ቅዱሱ ፍቅር ተማሪው በግሉ ያጠናዋል እንጂ በትምህርት ቤት አይማረውም፡፡ **ዜማ** ማለት የምስጋና ድምጽ ማለት ነው፡፡ ድጓ የሚለው ስም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ የወጣ ይሁን በኋላ ጊዜ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም፡፡ **የዜማ ምልክቶች ምሳሌ** ድፋት ከሰማይ መውረዱ ዙሮ ማስተማሩ ነው፡፡ ቁርጥ አዳምን ለማዳን በሞት መቁረጡ ነው ይዘት በአይሁድ እጅ ተይዞ መገረፉ ነው፡፡ ቅናት ይሁዳ በቅናት ማሰቀሉ ነው፡፡ ጭረት ግርፋቱ ነው፡፡ ሂደት አንድ ጊዜ ወደ ሐና አንድ ጊዜ ወደ ጲላጦስ ጌታን መውሰዳቸው ነው፡፡ ርክርክ ሲገረፍ የደሙ አወራረድ ነው፡፡ ድርስ በነቢያት የተነገረው ትንቢት በዕለተ ዓርብ ደርሶ መፈጸሙ ነው፡፡ **ይትበሀል** ማለት በዚህ ጊዜ ይህ ይባላል እንደማለት ነው፡፡ ወለእመ ኮነ በዓለ ፋሲካ አመ ፴ሁ ለሚያዝያ ዘመነ ጸራቅሊጦስ ይትፈጸም አመ ፺ ወሰቡዐ ለሰኔ ወአሜሃ አልቦ ዘመነ አስተምህሮ፡፡

ስድስቱ ቃላተ ወንጌል

በወንድምህ በከንቱ አትቆጣ፣ ወደሴት አይተህ አትመኝ፣ ያለ አንድ ምክንያት ሚስትህን አትፍታ፣ ፈጽማችሁ አትማሉ፣ ክፉውን በክፉ አትቃወሙ፣ ጠላታችሁን ውደዱ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- ማን ፈጠረን?

መልስ፡- ሥላሴ

ጥያቄ፡- ሥላሴ ስንት ናቸው?

መልስ፡- አንድም ሦስትም

ጥያቄ፡- አንድነታቸው እንዴት ነው?

መልስ፡- በባሕርይ በመንግሥት በሥልጣን አንድ ናቸው

ጥያቄ፡- አብ ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፡- አባት ማለት ነው

ጥያቄ፡- ወልድ ማለትስ?

መልስ፡- ልጅ ማለት ነው

ጥያቄ፡- መንፈስ ቅዱስ ማለትስ ምን ማለት ነው?

መልስ፡- ሠራዒ ማለት ነው

ጥያቄ፡- የሥላሴ ሦስትነታቸው እንዴት ነው?

መልስ፡- በስም በአካል በግብር

ጥያቄ፡- የአብ ግብሩ ምንድን ነው?

መልስ፡-የአብ ግብሩ መውለድ

ጥያቄ፡- የወልድስ ምንድን ነው?

መልስ፡- የወልድ ግብሩ መወለድ

ጥያቄ፡- የመንፈስ ቅዱስስ ግብሩ ምንድን ነው?

መልስ፡- የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ ነው

ጥያቄ፡- አብ ወልድን ከወለደ መንፈስቅዱስን ካሠረጸ አይበልጣቸውም አይቀድማቸውም?

መልስ፡- አይበልጣቸውም አይቀድማቸውም ምክንያቱም ቅድምናቸው አንዲት ስለሆነች ነው፡፡

የቅዳሴ ሥርዓት፣ አቋቋም፣ ቅኔ፣ መጻሕፍት

ከሆሣእና እስከ አባ ገሪማ በዕዝል ይቀደሳል፡፡ ቅኔውም ቅዳሴውን ተከትሎ እዝል ሲሆን እዝል ግዕዝ ሲሆን ግእዝ ነው፡፡ ከገሪማ ሳኒታ እስከ መስከረም 25 ግእዝ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 እዝል፡፡ ከህዳር 6 ሳኒታ እስከ ስብከት ግእዝ ከስብከት ጀምሮ እስከ ጾመ ቅበላ እዝል ነው፡፡ ከዚህ በቀር በግእዝ ጊዜ ስቡሕ ከተባለ ምልጣንም ከተመለጠነ እዝል ይቀደሳል፡፡ **አቋቋም** ማለት የመቆም ሥነ ስርዓት ማለት ነው፡፡ ማኅሌቱ ተቁሞ በሚሰራበት ጊዜ የአገልግሎቱን ሥነ ሥርዓት የዜማውን ሥልት የሚገልጥ አቅድ ማለት ነው፡፡ የቆሜ የአጫብር የዋድሌ የተጉለቴ እስካሁን አቋቋም የላቸውም ጥሬውን ዜማ ተከትለው ይሔዳሉ፡፡ የታች ቤት የሚባለው ከጃን ተከል ዋርካ በታች ሲሆን የላይ ቤት ደግሞ ከጃን ተከል ዋርካ በላይ ያሉት ናቸው፡፡ ነግሥ በምን ምክንያት ነግሥ እንደተባለ አልታወቀም፡፡ ከመልክዐ የዓመት በዓሉን ነክ የሆነው መልክዕ ተመርጦ ይመረገዳል፡፡ ከድጓውም በዓሉን ወይም ዕለቱን የሚነካው ተፈልጎ ይዘመራል፡፡ **የዚቅ** ደራሲው አይታወቅም፡፡ መቋሚያ ሥርዓቱ እስኪፈጸም ድረስ መቆም ስላለባቸው በደከሙ ጊዜ የሚደገፉት ነው፡፡ አሁን ለማመስገኛም ነው፡፡ አለቃ ገብረ ሐና የሸንበቆውን ዝማሜ አይተው ተክሌ ዝማሜን ፈጠሩ፡፡ መቋሚያውን ከቀኝ ወደ ግራ ከወዘወዙ በኋላ ወደላይ አንስተው ወደታች ይወረውሩታል፡፡ ይህም ክርስቶስ ከሐና ወደ ቀያፋ ከአመላለሱት በኋላ በመስቀል ላይ እንደሰቀሉት ቀጥለውም ከመስቀል አውርደው እንደቀበሩት የሚገልጥ ትምህርት ነው፡፡ የቅዳሴው ምስክር ሰለልኩላ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ አይታወቅም በቅርቡ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ማስመስከሪያው ወደ ደብረ ዓባይ ተዛወረ፡፡ የጀመሩትም ከሰለልኩላ አስመስክረው የሄዱት መምህር ገብረ ኢየሱስ ናቸው፡፡ በጣም ድምጻዊ ስለነበሩ

ራሳቸው ወዝ እየሰጡ ዜማውን እያስረዘሙ በማዜማቸው ዜማቸው ተወዳጅ ሆነ። ዲያቆኑ አስቀድሞ የዲያቆኑን ስራ ጠንቅቆ ማወቅና መሥራት ስላለበት የመጀመሪያው ትምህርት **ግብረ ዲቁና** ተባለ። ሰዓታት በሀገራችን ተጀመረ የሚባለው በአባ ጊዮርጊስ ጊዜ ነው። በሌሎች ሀገሮች ግን በተለያየ አካሄድ ጥንታዊ ጸሎት ነው። ስብሐተ ፍቁርን አጼ ልብነ ድንግል እንደደረሱት ይነገራል። ለኖኅ ሐመሩን ተፈሥሒ ማርያምን ለአዳም ፋሲካሁን ኦ ርኅርኅተ ኅሊናን አጼ ልብነ ድንግል ደርሰዋል። የቅዱሳን መላእክት ስብሐተ ፍቁር ግን በየጊዜው እየተደረሰ የተጨመረ ነው። **ጉት ቅኔ** ሲል ጉት የሚለው ስም ከየት እንዴት እንደመጣ አይታወቅም። በሥራ ሲገለጥ ግን ከተራ ዓረፍተ ነገር የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ስውር ምስጢርን ያዘለ ነው። በግጥም ወይም በስድ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አዕዱግ ፍኖቶሙ የመሳሰሉ ናቸው። **የመጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ** መቼ የት ተጀመረ ለሚለው መልስ አልታወቀም። የሊቅነት ምስክር መማር ብቻ ሳይሆን መመራመርም ነው። የላይ ቤት ትርጓሜ የሚባለው የጎጃም ትርጓሜ ነው። የታች ቤት የሚባለው የጎንደር ትርጓሜ ነው። መጻሕፍተ ብሉያትን አጠናቆ ያወቀ መጋቤ ብሉይ ሐዲሳትን ያወቀ መጋቤ ሐዲስ ይባላል። የአንድም ትርጓሜ አገባብን በመጠበቅ ወይም እርሱን ሳይሻ ዘይቤን ብቻ በመጠበቅ ወይም ምሥጢሩን በመከተል ይተረጉሙታል። ዘይቤውን ሳይከተል ምስጢሩን ብቻ በመከተልም የሚተረጉሙ ይገኛሉ። ለምሳሌ በልዋ ለዛቲ ቁንጽል የሚለውን ሄሮድስን እንዲህ በሉት የሚል ዓይነት ማለት ነው። አንዳንዱ ኃይለቃል ለምን እንደተነገረም ምክንያቱን ይሰጣሉ ለዚያም አስረጅ ጥቅስ ይጠቅሳሉ። ነጠላ ትርጓሜ ከቋንቋ ቋንቋ መተርጎም ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት በዓለም ላይ አንድ ሆነው የተገኙት በቀጥተኛው ዘይቤ ብቻ በመተርጎማቸው ነው። መምህር ኤስድሮስ ብዙ መጻሕፍት አንብበው የቀድሞውን ትርጓሜ አድሰውታል። ብዙ ትርጓሜንም አቃንተዋል። ከእርሳቸው በኋላ መምህር አለቃ ወልደ አብ ዘሸዋ ለደቀመዛሙርት እንዲመች አድርገው መልክ ሰጥተው አሻሽለት። **ሕግ**- በዚህ ዓለም ለመኖር ለማኅበራዊ ኑሮም ሥርዓት ለሰው ልጅ በግድ ያስፈልጋል። ሁለት የቅኔ መምህራን እርስ በእርሳቸው እየተፎካከሩ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ሲጠያየቁ ሲፈታተኑ አንዱ እንዳኢ ምንድን ነው ሲለው። ያኛው እንጃ አለው። ዳኛው ጨዋ ስለነበር እንጃ ያለው መምህር ተሸነፈ ብሎ ወሰነ። የዜማ የአቋቋም የቅኔ መምህር **መርጌታ** ይባላል። **አቡነ ቀሲስ** የሚለው የአቡን ጸሐፊ ወይም ጉዳይ ፈጻሚ ነው።

ቅዱሳት ሥዕላት

የኢትዮጵያ ሥዕል ግብ ታሪክን መተረክ ትምህርትን መስጠት ነው። መንፈሳዊ ሥዕሎችም እየተደጋገሙ በብዛት ከመሳላቸው የተነሳ የተወሰነ የማይለወጥ ባህላዊ ደምቦችና ልምዶች ወጥተውላቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ክፉዎቹ በግማሽ ፊት በግማሽ መልክ ይሳላሉ። ቅዱሳን በሙሉ መልክ ከሁለት ዓይን ጋር ይሳላሉ። በሥዕለ ሥቅለት ላይ ጌታችን ራሱን ወደ ቀኝ አዘንብሎ ይሣላል። ምስለ ፍቁር ወልዳ ሁል ጊዜ ከግራ ወደ ቀኝ ሆኖ እመቤታችንም ራሷን ወደ ግራ አዘንብላ ነው። በቤተክርስቲያን **በምሥራቅ** ገጽ የጌታና ተአምራቶች የሐዋርያት ታሪኮችና ምስለ ፍቁር ወልዳ። **በምዕራብ** የስቅለት የልደት የጥምቀት ሕማማተ መስቀል ትንሳኤ ምስለ ፍቁር ወልዳና የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕሎች ይሣሉበታል። **በሰሜን** የሰማእታትና የእመቤታችን ሥዕሎች ይሳሉበታል። **በደቡብ** ገጽ ከልደቷ እስከ

ትንሳኤዋ የእመቤታችንን ታሪክና የምጽአት ታሪክ ይሳላሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው በመቅደሱ አራት ገጾች ላይ ነው፡፡ በመቅደስ በሮች **በምዕራብ** ቅዱስ ሚካኤል ፈርዖንን እንዳሰጠመ ሩፋኤል ዓሣ አንበሪውን እንደወጋ ይሳሉበታል፡፡ ከምሕዋሩ በላይ በምስራቅ ዕርገት በምዕራብ ቅድስት ሥላሴ በሰሜን ደብረ ታቦር በደቡብ ደብረ ምጥማቅ ይሳሉበታል፡፡ በአራቱም ገጾች ደግሞ ልዩ ልዩ የሆነ የመላእክት ቅድስናን የሚገልጡ ሥዕሎችና ሐረግ ይሳልበታል፡፡ የሠዓሊው የመዓርግ ስም አለቃ ነበር፡፡

ሕይወተ ማርያም ድንግል

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐኮነ መልዐክ

ምድራውያን ሁሉ የአንድ ነገር ጥገኞች ናቸው የምድር፡፡ የሥጋ ለባሹ ኑሮ በሁሉም መንገድ ከምድር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የተመሰለለት አካል ከምሳሌው ይበልጣል፡፡ ይህችን ዓለም በተባረከ ነገር እንጂ በብዙ ነገር ማሸነፍ እንደማይቻል ከነዳዊት ከነጌዴዎን የጦርነት ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ የሰው ትዕግስት የሚገለጠው በፈተና ውስጥ ማለፍ ሲችል ነው፡፡በገብርኤል ስብከት ዓለመ መላእክት ተረጋጋ፡፡ ለብዙ መላእክት በሕይወት መኖር ስብከቱ ምክንያት ሆነላቸው፡፡ በቀል የፍቅርን ያህል ጉልበት የለውም፡፡ ጥጦስና ዳክርስን ያስተባበራቸው ቃል ኪዳናቸው ውንብድና ነው፡፡ ጥላቻ ይጥላል ፍቅር ያነሳል፡፡

እግዚአብሔር

ከፍጥረታት መፈጠር በፊት ተገኝ ሳይሆን ገኚ ሆኖ እርሱ በመንግሥቱ ነበረ፡፡ ያነገሠው ሳይኖር ንጉሥ ሆኖ ከዘለዓለም እስከዘለዓለም ነበረ፡፡ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እንጂ የማይሆነውን አያስብም፡፡ ፈጣሪያችን ያለጊዜው የሚያደርገው ነገር ባለመኖሩ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ዘመን ይቀድማቸዋል እንጂ ሐሳቡን ዘመን ቀድሞት አያውቅም፡፡ ታማኝ ሆኖ ለዘላለም የሚኖረው ንጉሣችን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡መታመን የባሕርይ ገንዘቡ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረታትን አንድ አድርጎ የሚይዝ ነገር ግን በሰው እጅ ያልተሰራ ቤት ነው፡፡ በበረሀ ያሉ ወዳጆቹ በእርሱ ተጠልለው ይኖራሉ፡፡

ድንግል ማርያም

ለበሽተኛው ዓለም መድኃኒት ሆና የተዘጋጀች የአምላክ በጎ ጎሊና ናት፡፡ እግዚአብሔር ይህን ዓለም ለፍጥረታቱ ሲያዘጋጅ ለክብሩ መገለጫ ትሆን ዘንድ ያዘጋጃት ሌላኛይቱ ዓለም ደግሞ እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት፡፡ የሰው ዳግም ሕዳሴ በእመቤታችን ተከናወነ፡፡ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኩሉ ፍጥረት እንዲል አባ ሕርያቆስ፡፡ እመቤታችን አክሊለ ቅዱሳን የቅዱሳን ቁንጮ ናት፡፡ የእመቤታችን ክብር እግዚአብሔር ለገለጠላቸው ካልሆነ በስተቀር የተከደነ ነው፡፡ ሌሎች ሴቶችም ቅዱሳት ለመባል በቅተዋል፡፡ ግን ያለ ነውር የነበሩ አልነበሩም፡፡ እግዚአብሔር ነውራቸውን አስወግዶላቸው እንጂ፡፡ እግዚአብሔርን እመቤታች ያወቀችውን ያህል ማንም አላወቀውም፡፡ የድንግል ልዕልናዋ ሊነገር አይችልም፡፡ የእርሷን ነገር የተናገሩ ስለ እርሷ የጻፉም

እንኳን ቢኖሩ በማሳነስ እንጂ በማብዛት አይደለም። ለክብሯ እንደሚገባ መጠን አልተናገሩላትምና። ዕበያ ለድንግል ኢይትከሀል ለተነግሮ እንዲል። እመቤታችን የመለኮታዊው ባሕርይ ምስጢራዊት ቤተመዛግብት ናት። ጥላቻ ይጥላል ፍቅር ያነሳል።ወደ ሕይወት ዛፍ የምታደርስ መንገድ ማርያም ናት። እናቱን የፈጠረ ልጅ እርሱ የድንግል ማርያም ልጅ ክርስቶስ ብቻ ሲሆን ፈጣሪዋምንም የወለደች ብቸኛ እናት እርሷ እመቤታችን ድንግል ማርያም ብቻ ናት። ድንግል ማርያም የተፀነሰችው በ5485 ዓመተ ዓለም ነው። ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ገብቶ በምስጋና የተሞላ ሰላምታን ካቀረበ በኋላ የመጣበትን ዓላማ ሲገልጽ የጀመረው ትጸንሲ በማለት ነው። እመቤታችን ግን ይህን ስትሰማ ዝም አላለችም። ምድር ያለዘር ሴት ያለወንድ እንዴት ሆኖ ትጸንሻለሽ ትለኛለህ ብለዋለች ሉቃ 1፣34። ይህ ቃል ባል የታጨላት ቃል ይመስላልን? ለሚስትነት የታጨች ሴት እውነቱን ነው ባል ያገባሁ ለዚህ አይደል ትላለች እንጂ እኔ ወንድ ሳላውቅ መቼ ብላ ታውቃለች። ስለዚህ እጮኝነቷ በዮሴፍ ለመጠበቅ ነው። እርሷ ራሱ ወንድ ሰለማላውቅ ነው ያለች ይህ ደግሞ በኋላም በድንግልና እንደጸናች ያሳያል። የመልአኩም መልስ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ዮሴፍም ከሩቅ ምሥራቅ እስከ ምድረ አፍሪቃ ከእስክንድሪያ እስከ ኢትዮጵያ በመንገዷ ሁሉ አገለገላት። የመታጨቷ አንዱ ዓላማም ይህ ነበርና። በሄደችበት እየሄደ አገለገላት። ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትመለከት ያደገች በመሆኗ ለቀረበላት ምስጋና እፎኑ ከመዝኑ እንጋ አምኃ ይትአምኑ የሚል መልስ ሰጠች። የእመቤታችን ጎሊናዋ ለምንም ዓይነት ኃጢአት የተቆለፈ ነበረና ድንግል በጎሊናኪ ይላታል። ውሃ ቀጂዎች ሲሳለቁባት ክፉውን በዝምታ አሳለፈችው። የመልአኩን ውዳሴ ግን ተቃወመችው። ድንግል ማርያም በሰውነቱ የክርስቶስ እናቱ እንድትሆን የተመረጠች ቢሆንም በአምላክነቱ ደግሞ ጌታዋ ነውና ራሷን የጌታ ባርያ ብላ ትጠራለች። እስኪ ኤልሳቤጥን ተመልከቷት የጌታዬ እናት ወደእኔ ትመጪ ዘንድ አለች እንጂ ጌታየን ይዘሽ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆናል? ያለች አይደለም። ተአምር የሚደንቀው ፈጣሪ ሲያደርገው ሳይሆን ፍጡራን ሲያደርጉት ነው። ድንግል ማርያም ለዮሴፍ ልጆች እናት ሆነቻቸው። እናት አጥቶ በሞት መዳፍ ውስጥ ለወደቀው ዓለም እናት እስክትሆን እናትነቷን በቤተ ዮሴፍ ጀመረች። ጥር 21 ቀን በ49 ዓ.ም ድንግል ማርያም አረፈች። ከነሐሴ 1 እስከ 14 ሐዋርያት ከእነርሱ የተሰወረች ድንግል ማርያምን እንድትገለጽላቸው 2 ሱባኤ ጾሙ። እሑድ ነሐሴ 14 ቀን ጌታ እመቤታችንን ከዕፀ ሕይወት ስር አምጥቶ ሰጣቸው። ዕለቱን ቀብረዋታል። የተነሳችውም እነርሱ ቀብረዋት ከሄዱ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን በ49 ዓ.ም በዕለተ እሑድ ነው። አልዋለችም አላደረችም ከመትንሳኤ ወልዳ ያለው አንደኛ በዕለተ እሑድ መነሳቷን ሲያይ ነው። ሁለተኛ በሐዲስ ሥጋ (ዳግመኛ ሞት የማያገኘው ሥጋ) መነሳቷን ያጠይቃል። ከፍጡራን መካከል ዳግም ሞት የሌለበት አማናዊ ትንሳኤ የተነሳ ከእመቤታችን በቀር ሌላ ፍጡር የለም። አማናዊ ትንሳኤ የሚደረግ በዕለተ እሑድ ብቻ ነው። ምክንያቱም ትንሳኤ ዘጉባኤ የሚደረገው በዕለተ እሑድ ስለሆነ ነው። ነሐሴ 16 ፍልሰተ ሥጋዋን የምናከብርበት ምክንያት ግን ያንጊዜ ስታርግ ከቶማስ በቀር ያያት ስላልነበረ በዓመቱ በ50 ዓ.ም ሐዋርያት ነሐሴ 1 ጀምረው ሁሉም ትንሳኤዋን እንደገና ለማየት ሱባኤ ጀምረዋል። ጌታም በ16ኛው ቀን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር በክብር ተገልጾ አቁርቧቸዋል። ስለዚህም አባቶቻችን ሐዋርያት ትንሳኤዋን ያዩበትን ቀን

ፍልሠተ ሥጋሃ ብለን እናከብራለን። እና ነሐሴ 16 ትንሳኤዋ የተገለጠበት ቀን እንጂ የተነሳችበት ቀን አይደለም።

ነገረ ክርስቶስ

ተዋሕዶ የከዊንና የኅድረት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የኅድረት ተዋሕዶ የምንለው እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮባቸው መኖሩን ነው። የከዊን ተዋሕዶ የምንለው ደግሞ ጌታ ከእመቤታችን ነፍስና ሥጋ ነስቶ ማደሩን ነው። ለተጠማው ዓለም ዘለዓለማዊነት ጽምዐ ነፍስን ያስወገደለት የሕይወት ውሃችን ክርስቶስ የፈለቀው ከመንፈሳዊቷ ዓለት ከእመቤታችን ነው። መጠማታችንን አይቶ የተጠማ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣ ይጠጣም አለን ዮሐ.6። ጌታ ወደ መቃብር በወረደ ጊዜ ለመቃብሩ ክዳን ያደረጓት ዓለት ያች ለእስራኤል ውሃ ያፈለቀችዋ ናት። የቀደመው የሰው እና የእግዚአብሔር ተዋሕዶ በኅድረት ነበር። የአሁኑ የሰው እና የእግዚአብሔር ተዋሕዶ ግን በከዊን ነው። ያ ማለት ዛሬ በመላእክት አድሮባቸው ለቅዳሴ ሲያተጋቸው እንደሚኖር በሰውም ላይ እንዲህ አድሮ ይኖር ነበር። ዛሬ ግን ሰው እግዚአብሔር እግዚአብሔርም ሰው ሆኖ በመገለጡ ዝምድናችንን ከፍ አድርጎታል። መልአኩ ገብርኤል እንደተናገረው በማሕጸነ ማርያም የነገሠው ክርስቶስ እግዚአብሔር አምላክ የዳዊትን የአባቱን ዙፋን የሚሰጠው ለመንግሥቱም ፍጻሜ የሌለው ንጉሠ ነገሥት ነው። በዚህም የአዳም ባሕርይ ከቀደመው የጸጋ ጌትነት ይልቅ ወደተሻለ የባሕርይ ጌትነት እንደመጣ እናምናለን። እግዚአብሔር እንደተናገረ ዘፍ.3፣22 አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ እንዲል። አዳም ከሦስቱ አካላት እንደ አንዱ ሆኖ በማይቋረጠው ምስጋና የተመሰገነበት ዘመን ነው። የጸጋ የነበረው ምስጋና ለአዳም ባሕርይ የሚስማማ የባሕርዩ ሆነ። የክርስቶስ ባሕርይ የአዳም ባሕርይ ነውና።

ሥነ ፍጥረት

ሰማያውያኑም ሆኑ ምድራውያን በሰማይና በምድር የተወሰኑ ናቸው። አንዱ ወደሌላው ገብቶ ከተወሰነለት አልፎ እንዳይኖር እግዚአብሔር በልዩ ጥበቡ አትሞታል። ብዜሞትና ሌዋታን የራሳቸውን ዓለም ትተው ወደ እኛ ዓለም መጥተው ለመኖር ጥበበ እግዚአብሔር ማኅተም ባይሆንባቸው ኖሮ ማን በፊታቸው ይቆም ነበር። እኛም ይህን ዓይተን በኅብረት ድምጻችንን አንስተን ወኩሎ በጥበብ ገበርከ ብለን እንዘምርለታለን። አንዱ የሚኖርበት ዓለም ለአንዱ የማይመች ወይም የተከለከለ ዓለም ቢሆንም አንዱ ያለአንዱ ድጋፍ ግን መኖር በፍጹም አይችልም። እኛ በምናውቀውም ሆነ በማናውቀው ሕግ ሥነ ፍጥረታት እርስ በእርሳቸው ይደጋገፋሉ። አንዱ ለአንዱ የሕይወትን ስጦታ ይሰጣሉ። ሰው እነርሱን ይጠብቃል ይንከባከባል። እነርሱም ደግሞ ለሰው በምግብነት ዕውቀት በመሆን እንዲሁም ሕይወትን በመስጠት ያገለግሉታል። እነዚህ ሁሉ ዓለማት ማለትም በስም የምናውቃቸውም ሆነ የማናውቃቸው የተማርናቸውና ያልተማርናቸው ፍጥረት ሁሉ ያለባቸው ዓለማት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተዘጋጁ ናቸው። ዓለማችን ከተፈጠረች በሁለተኛው ቀን ይህ ግዙፍ ሆኖ የምንመለከተው ጠፈር ታየ። ይህች ምድር የሰው ዘር በጊዜያዊነት እንስሳትና አራዊት በባለቤትነት ይኖሩበታል። ኀዘን ይበዛባታል። ዓመፀኞች ይገዟታል። ግፈኞች ይነግሡባታል። ያም ሆኖ ግን ያለጊዜዋ እንዳትጠፋ አምላክ በመሐል እጁ ይዟታል። አዳም ከመሳቱ በፊት

ፍጥረታት አራዊት እርስ በእርስ አይበላሉም ነበር። አንዱ አንዱን አያሳድደውም ነበር። አሮጌውን አሮጌ ማለት የሚቻለው አዲስ ነገር ሲኖር ብቻ ነው። አዲሱን ኪዳን ከእግዚአብሔር ስንቀበል የቀደመውን ኪዳን አሮጌ ብለዋል። ሦስት ነገሮች ብቻ በእርጅና ሳይለወጡ ጸንተው ይኖራሉ። እኒህም አምላክ መላእክት እና ሰባቱ ሰማያት ናቸው። የእግዚአብሔር የዛሬ ታላቅነቱ በትናንት የተጀመረ አይደለምና ሁልጊዜ ቢይ እግዚአብሔር ተብሎ ሲመሰገን ይኖራል።

ታማኝነት

አምነው የሚልኩት ታማኝ መልእክተኛ ማግኘት የነገር ፍጻሜ መቅድም ነው። ቁራ ታማኝ ሆኖ ሊያገለግል በኖኅ ፊት ቃል ገብቶ የወጣ ቢሆንም ወድ ዓለም ሲመጣ የገጠመውን የሥጋ ፈተና አሸንፎ ለተመረጠለት ዓላማ ታማኝ ሆኖ ለተጨነቀው የመርከቧ ውስጥ ነዋሪ እግዚአብሔር ምድርን ይቅር እንዳላት ለመግለጽ አልተቻለውም። የምድር እናትነት ለአዳም የታመነች ናት።

መመረጥ

በመጀመሪያ በኖኅ ፊት ለመልእክተኛነት ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ተለይቶ ሞገስን ያገኘው ቁራ ነበር። ኖኅ መረጠው እንጂ እሱ ግን መመረጥ የማይገባው ፍጥረት ነበር። ምንም ከመርከብ ሲወጣ ንጹሕ ሆኖ የወጣ ቢሆንም ከመርከቧ ውጭ ባለው የዓለም ርኩሰት ላለመተዳደፍ የማይለወጥ ጎሊና የነበረው ፍጥረት ግን አልነበረም።

ስለ እጮኝነት

ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን አካሉ ከማድረጉ በፊት አጫት ለማጫዋ የሚሆን ለክብሯ የሚመጥን ሌላ ዋጋ ባያገኝ የገዛ ደሙን ማጫ አድርጎ ከፈለ። መታጨት አንዱ የመወደድ ምልክት ነው።

ከንቱ ውዳሴ

የእግዚአብሔር ሰዎች ስድብ የሚያስደስታቸውን ያህል መወደስ አያስደስታቸውም።ምክንያቱም በነቀፋ ከወደቁት በውዳሴ የወደቁት ይበዛሉና። (ሕጻናትን ትንሽ ሰርተው እሰይ ብለን ከንቱ ውዳሴ ብንሰጣቸው ክፉና መልካሙን እየለዩ እንዲሄዱ መልካሙን በማመስገን በማድነቅ ለማሳወቅ ክፍውንም በመንቀፍ ለማሳወቅ ነው። እና ለሕጻናትና ለአላዋቂቆች ይህንን ማድረግ ከንቱ ውዳሴ አይሆንም)። ሲጀምር ጀምሮ ሔዋን ኃጢአትን አሜን ብላ የተቀበለችው ከንቱ ውዳሴ በተባለ የሐር ግምጃ ስለተጠቀለለ ነው። ኃጢአት በዚህ የስጦታ ዕቃ መጠቅለያ ተጠቅልሎ ነው ለሰው ልጆች መታደል የጀመረው። ይህን የመሰለ ተንኮል የሚሰራ ጠላት እንዳላቸው ሳያውቁ የሚጓዙ አገልጋዮች ፈንጅ በተቀበረበት የጦር ቀጠና እንደልብ የሚንቀሳቀሱ ሞኞች ናቸው።

ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን

አሮጌው ኪዳን የሞትን መልእክት ማራቅ ያልቻለ ስለምድራዊ ርስት የተማለ ከአንድ ሕዝብ ጋር ብቻ የተደረገ መሐላ ነበር። አዲስ ኪዳን ግን አዲሲቷን ሰማይና አዲሲቷን ምድር መሰረት ያደረገ ነው።

ነጻነትና ባርነት

ኃጢአት በራሱ ባርነት ሲሆን ሲኦል ደግሞ የኃጢአተኞች እስር ቤት ነው። ነጻነት የሌለው ሰው ሁልጊዜም ተሰውሮ መኖርን ይመርጣል። አሁን የሰው ልጅ የባርነቱ ደብዳቤ ተቀዶ ታውጆ በሥልጣን እንዲኖር ተፈቅዶለታል።

ዓለም

ዓለማችን እንዲህ ናት ዓመፀኞች የሚገኑባት እውነት የሚሰደድባት ድንግል ማርያምን የምታሳድድ ሄሮድስን የምታነግሥ ናት። የእሪያ ዓይነት ልማድ ያላት ዓለም ናት።እሪያ አብሮ የሚኖረው መልኩን ላለማየት እውነተኛ መልኩን ያሳየውን እንቁ ረግጦ ይሰብረዋል። ችግሩኮ የመልኩ ክፉነት እንጂ እንቁውማ ያለውን መልኩን ነበር ያሳየው። ዓለማችን በኃጢአት የበለዘ ፊቷን የሚያሳዩዋት የእውነት መቅረዞችን እንደምንም ተሯሩጣ መርገጥ ትፈልጋለች።

በሞት የተገለጠ ፍቅር

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐኮነ መልአክ

የቀድሞው ጦርነት በአሕዛብና በእስራኤል መካከል ነበረ። ዛሬ ግን የጦርነቱ ስልት ተቀይሮ ነሰውና በአጋንንት መካከል ሆኗል። ቀራንዮ ሞት ራሱ የሞተባት የሰው ልጆች ደግሞ ከሞት ያመለጡባት ስፍራ ናት። ሁልጊዜ እግዚአብሔር ባዘዘን መንገድ በምንጓዝበት ጊዜ ሁሉ ሊቋቋመን ባይችልም ለጉዞው አለመሳካት ግን ጠላት የተቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ እሙን ነው። አባቶቻችን ከሞትም በኋላ ለጠላት ስጋት ለዲያብሎስ ፍርሀት ለእኛ ለልጆቻቸው ደግሞ ተስፋና ትምክህት ናቸው። ስለዚህም አሁን ያለው የሞት መንገድ አዲስ በመሆኑ የምንሞተው ሞት መዓዛ ያለው የአዲሱ ዓለም መንገደኞች ናፍቆት ነው።

እግዚአብሔር

ታናሽነት ያልቀደመው ታላቅነት ዘመን የሌለው ቀዳማዊነት ድህነት የማይስማማው ባለጠግነት ሞት የማያሰጋው ሕይወት ላለው እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። በጠላት ቤት ከተመከረው ክፉ ምክር ይልቅ የእግዚአብሔር ምክር ትጸናለች።

ዕለተ ዓርብ

ዓርብ የፍቅር ቀን ናት። ዕለተ ዓርብ የኀዘንና የደስታ ቀን ናት። የኀዘን ቀን የሆነችው ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተሰቀለባትና የሞተባት በመሆኗ ሲሆን የደስታ ቀን የሆነችው ደግሞ እለ

ውስተ ሲኦል ጻኡ ወእለ ውስተ መቃብር ተከሠቱ ወርእዩ ግዕዛነ ብሉ ያወጀባት ቀን ስለሆነች ነው። ረቂቁ የእግዚአብሔር ፍቅር በፍጥረቱ ላይ ገዝፎ ስለተገለጠባት ነው። ክብራችንም ሆነ ውርደታች የታወጀው በዚህ ቀን ነው። ዓርብ ለሰው ታላቅ ታሪክ ያላት ቀን ናት። ምዕራባውያን የሆኑ እንደሆነ ለዕለታትም ሆነ ለአውራኅ ስያሜን ሲሰጡ በሚወዷቸው በሚያከብሯቸው ግለሰቦችና አማልክቶቻቸው ስም ነው። የኢትዮጵያውያን ግን ሥነፍጥረትን መሰረት ያደረገ ነው። ከእሑድ እስከ ዓርብ ለተፈጠሩት ፍጥረታት ስም የማውጣቱ ጉዳይ ለአዳም የተተወ ነበር። እስካሁንም ድረስ እሱ ባወጣላቸው ስም ይጠራሉ። የቤተ ክርስቲያን ተድላ ደስታዋ ዓርብ ተጀምሮ ፍጹምነትን የሚያገኘው ግን በዕለተ እሑድ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ

ክርስቶስ ምእመናን ለ5500 ዘመን ለጮኹት ጩኽት መደምደሚያ የሚሆነውን የጩኽት ድምጽ በማሰማት የሞት ጽዋ ከዓለም እንዲወገድ የባሕርይ አባቱን ተማጸነ። በምእመናን ፈንታ ተገብቶ የግንባሩ ወዝ እንደደም ወይቦ እስኪወርድ ድረስ ሰገደ። ሰው የሚድነው መለኮት በተዋሐደው ሥጋና ደም እንጂ በዕሩቅ ብእሲ ሥጋና ደም ቢሆንማ ኑሮ እስካሁን የፈሰሰ ብዙ የነቢያት ጻድቃን ደም ነበር አይደል። የሰዎችን ነጻነት ግን መመለስ አልቻለም።ለሰው ነጻነት የሚያስፈልገው የአንዱ የእርሱ ደም ብቻ ነው። በዋጋ ተገዝታችኋል እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም ተብሎ እንደተጻፈው ክርስቲያን ሁሉ የራሴ ነኝ ብሎ የሚናገርበት አንደበት ሊኖረው አይችልም በከበረ ዋጋ ተገዝቷልና።

መቃብር፣ ሞት

የሰው ልጅ ተገንዞ ወደ መቃብር መውረድ የጀመረው አዳምና ሔዋን ከገነት በወጡ ከ15 ዓመት ከ23 ቀን ሲሆናቸው ነው። የኃያላኑ ኃይላቸው የጠቢባኑ ጥበባቸው የዐዋቂዎች ምክራቸው ሞትና መቃብርን ማሸነፍ አልቻለም። ክርስቶስ የሞተው ላለፈውም ለሚመጣውም ትውልድ ነው። መለያየት የኃጢአት ውጤት ነው።

ነጻነት

ሲኦል በሮቿን ሁሉ ለፈያታይ ዘየማን ክፍት አደረገችለት። በሰማያዊው ንጉሥ ክርስቶስ ደም የተረጋገጠ የነጻነት ደብዳቤ ስታይ ሁሉንም እስረኞቿን ሰጠች። አዳም ተንስኡ ለጸሎት ሲል ልጆቹ እግዚኦ ተሣሃለነ የሚል መፈክር ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ። ጌታም ደርሶ ሰላም ለኩልክሙ ሲል ያኔ አዳምና ልጆቹ በደስታ በዝማሬ ጎርፍ ተጥለቀለቁ። ገላ.5፣1 በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን።

ፍቅር

እውነተኛ ፍቅርን የትኛውም መዝገበ ቃላት አይተረጉመውም መፍቻ ቃሉ ደም ነውና። የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በሕይወቱ ተርጉሞ አስተማረው። የእውነተኛ ፍቅር መገለጫው ጥቅም ሳይሹ ማፍቀር ነውና ክርስቶስ ሰውን እንዲሁ ወደደው። ክርስትና

የፍቅር ሕግ ነው። ይቅርታን የማያውቁ በክርስትና ሊኖሩበት አይችሉም። ሕጉ በራሱ የይቅርታ ሕግ ነውና። የጥበበኛ ሰው ንግግር በዚህ የተገለጠ ነው በማንም ላይ ቢሆን ፈጥኖ አይፈርድም። ልብ ላለው ሰው ቀሪው ጊዜ ለትንሳኤ በቂ ነው።

የዶሮው ጪኸት

አይሁድ ጌታን ሲሰቅሉት አንድ ዶሮ ጮኂል የዶሮውን ጩኸት ግን ያስተዋለ አንድም ሰው አልነበረም። የዶሮው ጩኸት ምስጢር የገባው ለጴጥሮስ ብቻ ነበር። ገብቶትም ዞር ብሎ ምርር ብሎ አለቀሰ።

የተረጋጋ ሕይወት፣ ትእግስት

የተረጋጋ ሕይወት ልምድ ባለው ሰው ውስጥ ኃጢአትን ማሸነፍ ቀላል ነው። ችኮላ ትልቁ የኃጢአት መንገድ ጠራጊ ነውና። መረጋጋት ካለ ክፉንና በጎን መለየት ይቻላል። በችኮላ የተተከለች ኃጢአት የምትነቀለው በትእግስት ነው። አዳም በችኮላው ሞትን ፈጠረ። ክርስቶስ በትእግስቱ ሞትን ገደለ።

ትዕቢት፣ ሽንገላ

ትዕቢትን የተዘጋጁ ብቻ ያልፉታል። የመጀመርያ ኃጢአት በመሆኑ በኩረ ኃጢአት ይሉታል። በዕለተ ዓርብ የሞተው ማን ነው ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ሞት ነው የሚሆነው። ተንኮል በማር የተለወሰ መርዝን ይመስላል። መርዙ ከማሩ ጋር በሚያገኛቸው ሁለት ነገሮች በመልኩና በጥፍጥናው ራሱን ይደብቃል። ሰው በሚወዳቸው ሁለት ነገሮች ተሰውሮ ወደውስጥ የመግባቱን እድል ካገኘ እስከሞት የሚያደርስ ቀውስን ሊያስከትል ይችላል። የሰይጣንም ተንኮል በመልክአ ከይሲ በልሳነ ከይሲ ተሰውሮ በመምጣቱ ወደሰው ልጆች ገብቶ ሞትን እስኪመጣ ድረስ አልታወቀም ነበር።

ትያትር

መሆን አይችሉም እንጂ መስሎ የመስራት ልምድ ያካበቱ አንጋፋ ባለሙያዎች በዓለማችን ውስጥ ቆጥሮ መጨረስ አይቻል ይሆናል። የቴአትር አባት የተባለው ሰይጣን/እባብ ገነትን የቴአትር መድረክ አዳምና ሔዋንን ተመልካች አድርጋ የመጀመርያውን ቴአትር ይዛው ብቅ አለች። የሽንጣ መርዘም የቁመቷ ዘለግታ የመልኳ ማማረ የነበራት ደም ግባት እና በራስ የመተማመን መንፈስ በአንድ ላይ ተስማምተው በቴአትሩ ደራሲና አዘጋጅ ሰይጣን ዘንድ ተመራጭ አድርገዋታል። የአተዋወን ብቃቷና ቅልጥፍናዋ እጅግ ውብ ስለነበር በተመልካቾቿ ልቡና ውስጥ የመግባት እድሉን ያገኘችው ሳይውል ሳያድር ነበር። የሚሻለው ግን ከቴአትሩ (ማስመሰል) ወጥቶ ትክክለኛውን የክርስትና ኑሮ መለማመድ ብቻ ነው። ለገንዘብ ሲሉ የሚሰሩ የሚሰሩትን ግን የማያውቁ ብዙ ቴአትረኞች በዓለም መድረክ አሉ።

ዓለም

በቅዱሳት መጻሕፍት አነጋገር ይህ ዓለም ዓለመ ጻማ ሲባል ገንዘቡም ንዋየ ዓመፃ ተብሎ ይጠራል። ብዙዎችን በሃይማኖት እንዳይኖሩ አድርጓል። አንዳንዶቹን ራሳቸውን እንዲወጉ አድርጓቸዋል። አንዳንዶቹም ከክርስቶስ ጋር የጀመሩትን ጉዞ ገትቶባቸዋል። በአጠቃላይ ባለጠግነትን የሚሻ ልቡና ወደ መስቀሉ ለመውጣት ምንም ነገር እንደማያስፈልግ ሲያስረዳን ንጉሥ ክርስቶስ ንጹሕ ሰውነቱን ብቻ ይዞ ወደ መስቀል ወጣ። እጀ ጠባቡን ሳይቀር ረቂቁን ዓለም ሳይሆን ግዙፉን ዓለም ለሚሹ ግብዞች አከፋፈላቸው። ዓለም ለነዋሪዎቿ የሚመች አንድ አሳብ የላትምና የተነሳው ሁሉ ሲወቅሳት ይኖራል። የዚህ ዓለም ገረዶች የተባሉት ገንዘብን መውደድ፣ ሥልጣን፣ ክብርና ዝና፣ ሆዳምነት ወዘተ የታወቁ ብዙ ገረዶች አሉ። መስቀሉን ባልተሸከመ ክንድ ሊሸነፉ የሚችሉ ግን አይደሉም።

ጸጋ

በዚህ ዓለም ያሉ ጊዜያዊና አላቂ ስጦታዎች ለአሕዛብ (ለኃጥዓን) ፈቃዱን ለማይፈጽሙ ሁሉ አምልኮውን ለማያውቁ ሁሉ የሰጠ ሲሆን። ዘላለማዊና ውድ ስጦታ ራሱን ግን ለምእመናንና ለመረጣቸው ብቻ እንደሰጠ ታወቀ።

ሥርዓት

በስቅለት ጊዜ ዓርብ ከ6 ሰዓት እስከ 9 ሰኣት ሦስት ካህናት ጥቁር ለብሰው አምንስቲቲ ሙኪርያ አንቲ ፋሲልያሱ ይላሉ። በግእዝ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ማለት ነው። ሦስቱ ካህናት ጥቁር መልበሳቸው ሦስቱ ፍጡራን ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለመጨለማቸው ምሳሌ ነው። ሊቃውንት መቋሚያውን በትክሻቸው አድርገው መወረባቸው ጌታ መስቀሉን በትክሻው ለመሸከሙ ምሳሌ ነው። ዝቅ በማለታቸው መውደቁን በመነሳታቸው መነሳቱን ለማሳየት ነው። ወደቀኝ እና ወደግራ በመመለሳቸውም ከሐና ወደ ቀያፋ ከቀያፋ ወደ ሐና መመላለሱን ያሳያሉ።

ቅንዋት፣ መስቀል

ጌታችን የተቸነከረው በሦስት ቅንዋት ቢሆንም በመጻሕፍት በአምስት ቅንዋት እንደተቸነከረ ይነገርለታል። አምስቱም ቅንዋት3 በነገረ መስቀሉ ተሳትፎ አድርገዋል። ሳዶር መስቀሉ ተመሳቅሎ የተሰራበት ሲሆን አላዶር በሚባለው ቀኝ እጁን ተቸነከረ ዳናት የግራ እጁ የተቸነከረበት አደራ ሁለቱም እግሮቹ ተጋጥመው የተያያዙበት ነው። ሮዳስ ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ የሚለው ጽሑፍ የተያያዘበት ነው። ይህ መስቀል ሰባት ክንድ ከስንዝር እንደነበር ይነገርለታል። ሁለቱ ክንድ ወደ መሬት የገባ ሲሆን አንዱ ክንድ ከእግሩ በታች ከመሬት በላይ አንዱ ክንድ ከራስጌው ላይ የነበረው ሲሆን ጲላጦስ ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ ብሎ የጻፈበት ነው። ሦስት ክንድ ከስንዝር የጌታ አካሉ ያረፈበት ነው። ያለ መስቀል ምንም ዓይነት ጉዞ ማድረግ በቀላሉ በሰይጣን እጅ ለመውደቅ ይዳርጋል።

ፍርሀት

ኃጢአት በተዘራበት እርሻ ከሚበቅሉ ተክሎች መካከል አንዱ ፍርሀት ነው። ፍርሀት የብቸኝነት ምልክት የባዶነት ስሜት ነፀብራቅ ነው። ኃጢአት ከእግዚአብሔር የለያት ነፍስ የምታውቀው ብቸኝነቷን ነውና ፍርሀትና ድንጋጤ አይለዩዋትም። እግዚአብሔር የከበባት ነፍስ ግን ሁልጊዜም አርፋና ተዘልላ ትኖራለች እንጂ በአንዳች እንኳን አትጨነቅም። በጠላቶቿም ዘንድ እርሷ በዓላማ እንደተሰለፈ ሠራዊት ታስፈራለች እንጂ አትፈራም። እግዚአብሔርን መፍራት ግን የፍርሀትን መንፈስ የምናርቅበት ጥበብ ነው። ከኃጢአት በስተጀርባ ፍርሀት አይታጣም። በእኛ አእምሮ የነገሠው የሞት ፍርሀት ከእኛ እንዲወገድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ በፈቃዱ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ። በቁስሉ ቁስላችንን እንደፈወሰልን በፍርሀቱም ፍርሀታችንን አራቀልን። ጌዴዎን ምድያማውያንን እንዲያሸንፍ የረዳው በምድያውያን ውስጥ የነገሠው ፍርሀት ነው። በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን አሕዛብ ያሳደዳቸው አስቀድሞ የከበባቸው ፍርሀታቸው ነው። ፍርሀትን ምን አመጣው ካላችሁኝ ኃጢአት ባለበት ሁሉ ሞትና ፍርሀት የማይታጡ በመሆናቸው ነው። ሰይጣንና ሄሮድስ ከፍርሀታቸው የተነሳ ምንም የማያውቁ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚደርሱ የቤተልሔምና የአውራጃዎቿን ሕጻናት አስፈጃቸው። መቼም የፈሩት ነገር ስለፈሩት ከመሆን አይቀርም።

እናትህ ይች ናት

አዘጋጅ፡- ሊቀ ሊቃውንት ሰሎሞን ዳዊት፡- የአራቱ ጉባኤያት መምህርና የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ። በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ አብነት ትምህርት ቤት የተመሰረተው በአክሱም ጽዮን ነው።

እናት

የዚህ መጽሐፍ ማስታወሻነቱ ቁራሽ እየሰጡ ላስተማሩኝ ምእመናን እና ለመምህሮቼ ይሁንልኝ እናት ማለት ትውልድ የምትተካ መተኪያ ትክ መሰረት ማለት ነው። እናት ከራሷ በላይ አስበልጣ ልጇን የምትወድ 9 ወር ከ5 ቀን በማሕጸኗ ተሸክማ ከዚያም ተወልዶ ራሱን እስኪችል ድረስ አቅሟ በሚፈቅደው ነገር ሁሉ ተንከባክባ ታሳድጋለች። እናት በሚለው ስም የእናትነት ስራ የሚሰሩ ሁሉ ይጠሩበታል። ለምሳሌ እግዚአብሔር፣ ድንግል ማርያም፣ ወላጅ እናት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሀገር፣ የክርስትና እናት፣ ሞግዚት፣ የቀለም እናት ናቸው። ዘጸ.20 እናትን ማክበር ሀብትና ጤና ዕድሜና በረከት ነው። ጌታም ከድንግል ማርያም ተወልዶ ወንጌልን ሲያስተምር ማንኛውም ልጅ ለእናቱ መታዘዝ እናቱን መርዳትና ማክበር ተገቢ መሆኑን ከቃሉ ባሻገር በተግባር አሳይቶ አብነት ሆኖናል። ስለ እናት በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል በርካታ የግጥም መድበሎች ታትመዋል። በርካታ ድርሰቶች ተደርሰዋል። እናቶቻችን ለሀገራቸው ለትዳራቸው ለወገናቸው ለልጆቻቸው ለባህላቸው ለስርዓታቸው ለሃይማኖታቸው ታላቅ ፍቅር እና ክብር አላቸው። እናት ለልጇ ያላት ዓላማ በስነ ሥርዓት አድጎ በእውቀት በልጽጎ ለወግ ለመዓረግ በቅቶ ራሱን ችሎ ማየት ነው። እናት ለልጇ ሕይወቷን ትሰጣለች።

እናት ለልጇ እንድትራራ እግዚአብሔርም ለፍጥረቱ ቸርና ሩኅሩኅ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችን ከአባት በላይ አባት ከእናት በላይ እናት ስለሆነ ዘወትር አንተ አቡነ ወአንተ እምነ እያልን እናመሰግነዋለን። የመጨረሻዋ እናት ማን እንደሆነች ባይታወቅም የመጀሪያዋ እናት ግን ሔዋን ናት። ሔዋን እመ አሕዛብ ወሕዝብ እመ ነቢያት ወሐዋርያት እመ ጻድቃን ወሰማእት ለመላው የሰው ዘር የሁሉም ነገር መሰረት ናት። ሔዋን ማለት የእናቶች ሁሉ እናት የሰው ሁሉ ሕይወት ማለት ነው። በኦሪቱ ከያዕቆብ የተወለደ ሁሉ ቤተ እስራኤል እንደሚባል በመንፈሳዊና በምስጢራዊ ልደት ከክርስቶስ የተወለደ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

ሴቶች

ሚስት ማለት ሕይወት እረፍት ጠባቂ የምትመች ረዳት ማለት ነው። ሔዋን የተፈጠረች አዳም በተፈጠረ በሳምንቱ ነው። በዓለማችን ከተሰሩና ከሚሰሩ ታላላቅ ስራዎች በስተጀርባ ሴቶች አሉ ከትልቁ ሰው ከአብርሃም በስተጀርባ ሣራ ነበረች። በማንኛውም የሥራ ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑን ለማረጋገጥ የማህበራዊና የመንፈሳዊ ኑሮ መስራች የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ120ው የወንጌል ቤተሰቦች መካከል 36ቱ ሴቶች እንዲሆኑ አድርጓል። በእርግጥ መልካም ሴት እንዳለች ሁሉ ክፉ ሴትም እንደምትኖር መዘንጋት የለብንም። ከመልካም ስራ በስተጀርባ መልካም ሴት አለች። ከሩት ታሪክ የምንማረው ምንም የሌላት ድሀ ምስኪን አማቷን የቀን ስራ እየሰራች ስትረዳ የነበረች መሆኗን እንዲሁም ስራ የማትንቅ ትጉህና ታታሪ ሰራተኛ መሆኗን ነው።

መሥዋዕት

በአንድ ወቅት ቃየልና አቤል ለአምላካቸው መሥዋዕት አቀረቡ። የመሥዋዕት አቀራረባቸው ግን በዓይነቱም በጥራቱም የተለያየ ነበር። ቃየል በቸልተኝነት ዋግ የመታውን ወፍ የጠረጠረውን እንክርዳድ የተቀላቀለበትን እህል አቀረበ። አቤል ደግሞ ከሚጠብቃቸው በጎች በጣም ያማረውን ጠቦት አቀረበ። እግዚአብሔርም ሰዎች በቅንነት በንጽህና በቅድስና ሆነው የሚያቀርቡለትን ከጸሎት እስከ መሥዋዕት ድረስ የሚቀበል መሆኑን ለማስረዳት ምንም ባይመገበው የአቤልን የልቡን ቅንነትና ንጽሕና አይቶ የመሥዋዕቱን መበጀት ተመልክቶ መሥዋዕቱን ተቀበለለት። የቃየልን ግን የልቡን ጠማማነት የመሥዋዕቱን አለመበጀት ተመልክቶ ሳይቀበልለት ቀርቷል። ቃየልም በዚህ የተነሳ ፊቱን አጥቁሮ ልቡንም ለሰይጣን አስረክቧል።

መግደል

ቃየል በቅናትና በምቀኝነት በመነሳሳት ከጎኑ የሚቆም ታናሽ ወንድሙን አቤልን በድንጋይ ወግሮ ገደለው። በዚህም ድርጊቱ የመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ሆነ። አቤልም በወንድሙ የተገደለ በዓለም የመጀመሪያው ሟች ሆነ በቃኝን የማያውቅ መቃብርም በአቤል ተጀምሯል በማን እንደሚያቆም ባይታወቅም። ቃየልም በግፍ በማታለል የእናቱን ልጅ በመግደል እናት አባቱን ያሳዘነ የመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ነው። አሁንም ቢሆን ባለንበት ዘመን የቃየል የግብር ልጆች

የሰይጣን ታዛዦች ሰውን በድብቅ በግፍና በአሰቃቂ ሁኔታ በተለያየ መሳሪያ እየገደሉ የሚቀብሩ አሉ፡፡ የአባታቸው የቃየል መርገም አድሮባቸው እንደአባታቸው እንደ ቃየል በመፍራትና በመሸበር የሕሊና እረፍት በማጣት ሰውን ፈርተው በሰው እየተጠበቁ ይጠብቀናል ብለው አምነው በቀጠሩት ሰው እንደ ቃየል ዋጋቸውን ሲያገኙ ይስተዋላል፡፡ አንዳንዶችም ከአንዱ የኃጢአት ዋሻ ወደሌላው የኃጢአት ጫካ ሲሸሸጡ ይታያሉ፡፡ አጅሬ ሞት ግን ከገቡበት ገብቶ በበሽታ መሳሪያው አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ እንዳልነበሩ አድርጎ ለመቃብር ያስረክባቸዋል፡፡

ሰይጣን

ሰይጣን ስራ ፈትቶ የዋለበት ቀን ያደረበት ሌሊት የለም፡፡ በሰይጣን መሪነት በሰዎች ተባባሪነት ከአንዱ ወደ አንዱ ዓለምን በመዞር እንደደግ ነገር ክፉውን በማባዛት መልካሙን በማጥፋት ኃጢአትን በማለምለም ጽድቅን በማዳከም የትውልዱን ጊዜያዊና ሰይጣናዊ ፍላጎት በማነሳሳት የፈጣሪውን ትእዛዝ በማቃለል ከኃጢአት ወደ ኃጢአት በመዝለል ይኖራል፡፡ በማርያም መግደላዊት ያደሩ ሰባት አጋንንት በየራሳቸው ሰባት ዓይነት ስራ ያሰሯት ነበር፡፡

- መንፈሰ ሐሜት፡- ሁልጊዜ ሰውን ማማት ነው
- መንፈሰ ትዕቢት፡- ሁልጊዜ ትዕቢተኛ እና ኩራተኛ መሆን ነው
- መንፈሰ ቅንዐት፡- በሆነ ባልሆነው እንድትቀና ማድረግ ነው
- መንፈሰሐሰት፡- ሁልጊዜ እንደ ሐሰት አባት እንደ ዲያብሎስ ሐሰት እንድትናገር ያደርጋል
- መንፈሰ ትውዝፍት፡- ስራ ፈትታ ስትኳኳል ስትቀባ እንድትውል ማድረግ ነው
- መንፈሰ ዝሙት፡- የዝሙትን ስራ ማሰራት ነው
- መንፈሰ ጽርፈት፡- ሰውን እንድትዘልፍ እንድታዋርድ ማድረግ ናቸው፡፡

ጽንስ፣ መካንነት

አሁን አሁን በዓለም በጣም የረከሰ ነገር ሰው በየሜዳውና በየጫካው የሚጥለው የሰው ዘር መሆኑን ማንም ሰው ይመሰክራል፡፡ ምክንያቱም በየእለቱ የሚደመጠው ወሬ ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር እንደቀላል ነገር እንዳይጸነስ በመከልከል ከዚህ አምልጦ የተጸነሰው በመድኃኒት ሲገደል ከዚህ አምልጦ የተወለደው ደግሞ ወደቆሻሻ ባልባሌ ቦታ ሲጣል ማየት የተለመደ ጉዳይ ሆኗል የሚገርመው ወላጆች ምንም የማያውቁ ልጆቻቸውን ሲገድሉ ሲታገሉ አብረው መሞታቸው ነው፡፡ የእግዚአብሔር በረከት የሆነ ልጅ የትዳር መሰረት ነው፡፡ በዘመናችን ያሉ እናቶች ግን የቤተሰብ ምጣኔ በሚል ውስጡ ስስት ላዩ ዘመናዊነት በሆነ ፈሊጣዊ ዘዴ የእግዚአብሔር በረከት የሆነን ልጅ ላለመውለድ የመድኃኒት ጉድ ቢጸንሱ የሚያስወርድ የከፋ ዓይነት ሲጠቀሙ እናያለን፡፡

መልካም ሰው፣ ክፉ ሰዎችና ክፋት

ፈጣሪው ስለጽድቁ ስለመልካም ስራውና ስለደግነቱ የመሰከረለት የዋሁ አቤል እና መሰሎቹ ጻድቃን ያለምንም ስህተት ምንም ሳይበድሉ በዲያብሎስ ወዶ ዘማቾችና ወሮ በሎች ያለምንም

ፍርድ ተሰቃይተው የሚሞቱባትና የሞቱባት ዓለም ውስጥ እየኖርን ከዚች ዓለም በጎ ነገር አገኛለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው ካለ የዋህ ይመስለኛል። እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ቃል ሲተገብር ይኖራል። ዲያብሎስ ያደረበት ሰው ደግሞ በሐሰት ይቀባጥራል። ድህነትም ሆነ ብልጽግና የኃጢአት መመዘኛ አይደለም።

ፍርድ

እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ቢያስነሳ ሰው አሳሪና ታሳሪ ሳይሆን ሁሉም ሰው ከእስር ቤት አያመልጥም ነበር ብሏል ዮሐንስ አፈወርቅ። ኃጥዓን ጻድቃንን የገደሉባትና የሚገድሉባት ዓለም ናት ይህች ዓለም። መከራ ሲመጣ አስቀድሞ እግዚአብሔርን በጸም በጸሎት መጠየቅ ይገባል መፍትሔ የሚሰጥ የመጨረሻው ዳኛ እርሱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አስቱር አሳይታናለች።

ታላቅነት፣ ነቢይ

ሰው በስምንት ነገሮች ታላቅ ይባላል። በሃይማኖት በእውቀት በአመለካከት በዕድሜ በዘር ሀረግ በስልጣን በሀብት በስራ ወዘተ። የታላላቆች ታላቅ የሚባለው ሰው ግን ታላቁ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ በፍጹም ነፍሱ በፍጹም ሐሳቡ የሚያምን ሰው ብቻ ነው። ነቢይ ማለት በእግዚአብሔር ተመርጦ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ያለፈውን የሚመጣውን የጊዜውን የዘላለሙ ነገር ሁሉ ተገልጾለት የሚናገር የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ መምህር ወመገስጽ ዘኢያደሉ ለገጽ ነው። ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ዲያብሎስ ቢድን ሰው ሁሉ ይድናል የሚል እምነትን አሳድራ ጌታን ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው። ጌታም ለሰው ልጅ ያላትን ፍቅር አይቶ አደነቃት። ከራስ አልፎ ለትውልድ ማሰብ የትውልዱን የችግር ምንጭ ከነመፍትሔው ማስቀመጥ ትልቅነት ነው

ቃለ እግዚአብሔር

በዓለማችን ላይ ለሰው ልጅ የተለያዩ እድሎች ያጋጥሙታል። ነገር ግን በክርስቶስ አንደበት ሌቦች የማይሰርቁት ወንበዴዎች የማይዘርፉት ተብሎ የተነገረለት ታላቁ የሰው ልጅ እድል ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ማርያምሰ ኀርየት መክፈልተ ሰናየ ዘኢየሀይድዋ እንዲል።

ድንግል ማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተጸነሰች ጊዜ ሐና አጎቷ ሳምናስ ወልደ ጠሊቅ ሞቶ ሸንኮሩን ይዛ እያለቀሰች ሳለ ጥላዋ ቢያርፍበት ከሞት ተነስቶ ሰላም ለኪ እማ ለፀሐየ ጽድቅ ወላዲቱ ወእምሒውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ አላት። እመቤታችንን ቅዱስ ገብርኤል ያበሰራት በአምሳለ አረጋዊ ሆኖ ነው። ኪዳነ ምሕረት ማለት እመቤታችን ከፈታሪዋ የምሕረት ቃልኪዳን የተቀበለችበት ዕለት ነው። እመቤታችን ብሉይ ሐዲስ እየተማረች ዘመኗን በአግባቡ ተጠቅማ በ64 ዓመቷ አርፋለች። ስለ ድንግል ማርያም ሉቃስ እንዲህ ይላል፦

- ✓ ድንግል። ሉቃ.1፣27
- ✓ ጸጋ የመላባት። ሉቃ.1፣28

- ✓ እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር የሆነ። ሉቃ.1፣30
- ✓ ከሴቶች የተለየች። ሉቃ.1፣30
- ✓ ጸጋን ያገኘች። ሉቃ.1፣30
- ✓ መንፈስ ቅዱስ ያደረባት። ሉቃ.1፣34
- ✓ ወንድ የማታውቅ። ሉቃ.1፣34
- ✓ አምላክን የወለደች። ሉቃ.1፣38
- ✓ የጌታ ባለሟል። ሉቃ.1፣38
- ✓ አማኝ። ሉቃ.1፣38
- ✓ ቃሉን በልቧ የምትጠብቅ። ሉቃ.2፣51

ድንግል ማርያም እስከ 15 ዓመቷ በቤተ መቅደስ ብሉይ ኪዳንን በቃል ተምራለች በተግባር ተርጉማለች። ወንጌልን በኋ ከልጇ ተምራለች። ብሉያትን በለጋ እድሜዋ ወንጌልን ጌታ ከዋለበት እየዋለች ካደረበት እያደረች ተምረዋለች። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሌሎች ሴቶች የምትለይባቸው ሰባት ነገሮች ክፉ ነገር ከማሰብ፣ ክፉ ነገር ከመናገር፣ ክፉ ነገር ከማድረግ፣ ክፉ ነገር ከመስማት፣ ክፉ ነገር ከማየት፣ የማይገባ ነገር ከመንካት ወይም ከመዳሰስ፣ ክፉ ነገር ከመመርመር ከመመኘት ሁሉ ንጽሕት ናት።

ሀገር

አንድን ሀገር ትልቅ የሚያሰኘው በውስጡ ጠንካራ የስራ ባህል መልካም አስተዳደርና አስተማማኝ ሰላም ሲኖር ነው። ሀገር ማለት ሰው ሰው ማለት ሀገር ማለት ነው። ቅዱሳን ነቢያት በሙሉ ሌሎችም አባቶች ስለሀገራቸው ሉዓላዊነት እና ክብር ትንቢት ተናግረዋል አስተምረዋል ጽፈዋል መሥዋዕትም ሠውተዋል መሥዋዕትነትም ከፍለዋል። የሀገር ባለቤትና ጠባቂ እግዚአብሔርንም በጸሎት መላልሰው ጠይቀዋል።

ሕግ

ሕገ ልቡና ማለት የሕሊና ዳኛ ማለት ነው። ከአዳም እስከ ሙሴ የነበሩት አበው ምንም በጽሑፍ የሰፈረ ሕግ ባይኖራቸውም አምላክ የሰጣቸውን አእምሮ ተጠቅመው ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው ክፉውን ከበጎ ለይተው ስርዓተ ማኅበር መስርተው ተከባብረውና ተመካክረው ይተዳደሩበት ይዳኙበት ይመሩበት የነበረ ሕግ ሕገ ልቡና ይባላል።መላእክትም ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩ በሕገ ልቡና ነው። ዛሬም ቢሆን የሰው ልጅ ትልቁ ዳኛ ሕሊና ነው። ሕገ ኦሪት ከሙሴ እስከ ጌታ ያለው ዘመን ነው። በሌላ አገላለጽ ዘመነ ብሉይ ይባላል ሰዎቹም ኦሪታውያን ይባላሉ። ሰው በሕገ ልቡና ጸንቶ መኖር ስላልቻለ ሁልጊዜ ለፍጥረቱ የሚያስብ ቸሩ አምላክ ሙሴን በደብረ ሲና ጠርቶ ሕገ ኦሪትን ከነሙሉ ሥርዓቷ አስተማረው። ሕገ ወንጌል በሕገ ኦሪት መኖር ሲያቅተን የተሰጠን ሕግ ነው።ሕገ መላእክት ከምጽአት በኋላ ቅዱሳን የሚኖሩበት ሕግ ነው።

አምስቱ አዕማደ ምስጢር ምስለ ሥነ ፍጥረት አንድምታ

ትርጉም፡- አባ ቤተ ማርያምና ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ። ተግባረ ሥጋ መውጣት መውረድ እርሻ ቁፋሮ ውሃ ዋና በገና ፈረስ ግልቢያ ጽሕፈት ድጉሰት ናቸው። ተግባረ ነፍስ ጾም ጸሎት ፍቅር ትሕትና ስጊድ ምጽዋት ትዕግሥት ነው። ቅኔ ዜማ ማኅሌት የሚነቅፍ ሰው ትምህርት ያነሰው ያልተማረ ግበረ ገብ ያይደለ ያለ አዋቂ ነው። ኢትንብቡ ንባበ ጽሩአ ዘአልቦ በቁኤት ኢለነባቢሁ ወኢለሰማኢሁ። ምእመናን ሲጸልዩ እና ሲሰግዱ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አድርገው ነው። ሰው ሲሞት አስቀድማ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች መጋቤ ነፍስ መልአክ አለ ወስዶ ቦታ ሰጥቶ ያሰናብታታል።

ሃይማኖት

የኢትዮጵያ ሰው ሌላ ሃይማኖት መማር አይገባውም። ሁለት ልደት ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ሃይማኖት ይህ ነው። ከዚህ ሃይማኖት ወጥቶ በቅባት የባሕርይ ልጅ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ የሚል ግን ቀድሞ ሐዋርያት ኋላም በየጊዜው የተነሱ መምህራን ሊቃውንት አውግዘውታል። መጀመሪያ ኢትዮጵያ ያመነች በኦርቶዶክስ ሃይማኖት በአቡነ ሰላማ ስብከት ነው ከተግባረ ሥጋ ከተግባረ ነፍስ አስቀድሞ የቀናን ሃይማኖት ይማሩት ዘንድ ይገባል። መቅድመ ኩሉ ንትመሀር ሃይማኖተ እንዳሉ ሠለስቱ ምእት። ሃይማኖት መሰረት ምግባር ሕንጻ ነውና። የቀና ሃይማኖት የሌለው ምግባር ከጸብአ አጋንንት ከሥጋዊ ጠላት ከገሀነም እሳት አያድንም። ሕንጻው ጠፈሩ ያልጸና ቤት ከሌሊት ቁር ከመዓልት ሐሩር አያድንም በጎ ምግባርም የሌለው ሃይማኖት ከጸብአ አጋንንት ከሥጋዊ ጠላት ከገሀነመ እሳት አያድንም።የቀና ሃይማኖት ከበጎ ምግባር አንድ ሆኖ የጸና እንደሆነ ከጸብአ አጋንንት ከሥጋዊ ጠላት ከገሀነመ እሳት ያድናል። ኋላም ፍጹም መንግሥተ ሰማያት ያገባል። ሃይማኖትስ ለአጋንንትም አላቸው በጎ ምግባር የላቸውምና አይድኑም። አጋንንትኒ የአምኑ ቦቱ ወይደነግጹ እንዳለ ያዕ.2፣19። ለኢየሱስ አአምኖ ወለጳውሎስኒ አአምሮ እንዳለ ግብ.19፣15። ምግባርስ ለእስላሞችም አላቸው ነገር ግን የቀና ሃይማኖት የላቸውምና አይድኑም።

አዕማደ ምስጢር

ሃይማኖትስ ምንድን ነው ቢሉ አምስቱ አዕማደ ምስጢር ናቸው። አዕማድ ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። ምሰሶ የሌለው ቤት ይፈርሳል ይወድቃል ይደቃል። የቀና ሃይማኖት ያልተማረ በጎ ምግባር የሌለው ክርስቲያን መንጸፈ ደይን ይወድቃል በእግረ አጋንንት ይረገጣል።

ምሥጢረ ሥላሴ

ከሁሉ አስቀድሞ ምሥጢረ ሥላሴን ይማሩ ዘንድ ይገባል። መቅድመ ኩሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕሩየ እንዳለ ባስልዮስ በሃይማኖተ አበው። የምሥጢረ ሥላሴ ነግርስ እንደምን ነው ቢሉ አንድነታቸውን ሦስትነታቸውን ተግቶ ነቅቶ መማር ለይቶ ጠንቅቆ ማወቅ ነው። አንድነታቸውን ሶስትነታቸውን ያልተማረና ለይቶ ጠንቅቆ ያላወቀ ሰው መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም። የአባቱን ትውልድ የማያውቅ ሰው ርስት እንዳይወርስ የወልድ መወለድ የመንፈስ

ቅዱስ መሥረጽ እንደምን ነው ቢሉ ይህንማ ማን ያውቃል እንዲያው ዕፁብ ዕፁብ ድንቅ ተብሎ ይደነቅል በዕፁብ ይወሰናል እንጂ አይነገርም አይመረመርም። ወልድ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው አይደለም ሌላ ቃል አላቸው የሚል የተወገዘ ነው።

ምሥጢረ ሥጋዌ

ወልድ ያለ አብ ያለመንፈስ ቅዱስ አያጸናም አያነጻም አይከፍልም አያዋህድም በህልውና ነው እንጂ። እመቤታችን እንደ ኒቆዲሞስ ተከራክራ እንደ ዘካርያስ ተጠራጥራ አይደለም ነገር ግን ብልህ ደቀመዝሙር ከመምህሩ ቀለም ለመረዳት ነገር እንዲያበዛ እርሷም አውቅ እጠይቅ እጠነቅቅ እረዳ ብላ ነው እንጂ። ከዚህ በኋላ ነየ አመቱ ይኩነኒ አለች። ጸጋ ቅባት ካቶሊክ ማለት በንባብ መለያየት ነው እንጂ ነገራቸው አንድ ነው። ወልድ በተለየ አካሉ ለተዋሐደው ሥጋ ክብር ሆነው በተዋሕዶ ከበረ ብለን እናምናለን እናስተምራለን። አብ መንፈስ ቅዱስ ክብር ሆኑት ማለት አይገባም። አልተዋሐዱትምና ክብር ሆኑት ማለት አይገባም የክብርም መገኛው በተዋሕዶ ነውና። በመፍጠርና በማዋሐድ ግን ሦስቱ አካላት አንድ ናቸው። ክብር በመሆን በመዋሐድ ግን መንፈስ ቅዱስና አብ ከወልድ ጋራ አንድ አይሆኑም። ወሶበ ተራከበ እሳት ምስለ ሐጺን ያመውቆ እንዘ ቆሪር ፍጥረቱ ወይሬስዮ ከማሁ እፎ እንከ ፈድፋደ ኢያብዕል ቃል ሥጋ ዚአሁ እንዳለ ቄርሎስ። ለሥጋ ቃል በተለየ አካሉ ክብር ሆነው ማለት ይገባል። ጌታን ፈርሀ ሲል የጌታ ፍርሀት የፈቃድ ፍርሀት ነው። አንድም የእኛን ፍርሀት ያጠፋልን ዘንድ ፈራ። እያዘነ እየተከዘ የጸለየም ሕገ ተሰብኦን ለመፈጸም ነው። አንድም ለእኛ አብነት ለመሆን ነው። አንድም አዝኖ ሐዘናችንን ያጠፋልን ዘንድ ነው። ጌታ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ 36 ጊዜ ወድቋል። ጌታ በስቅለት ጊዜ ስለምን አምላኪየ አምላኪየ አለ ቢሉ የፈቃድ ነው። ለአጽድቆተ ትስብእት ቅድመ ተዋሕዶ አምላኪየ አምላኪየ ሲል የነበረ ሥጋን እንደተዋሐደ ሲያጠይቅ ነው። ለአቡየ እብሎ አምላኪየ በእንተ ሥርዓተ ትስብእት እንዲል። አንድም ለአቅርቦተ ሰይጣን ነው። ከዚያ ቀድሞ የነበሩ ሰዎች ነፍሳቸው በዲያብሎስ እጅ ትለይ ነበር።

ምሥጢረ ጥምቀት

ሕጻን ሜሮን የሚቀባው በዘር የተቆራኘው ጋኔን እንዲለቀው ነው ያለዚያ አይለቀውምና። ከአህዛብ የሚመለሱ ሕጻናትን በ40 በ80 ቀን ያጥምቋቸው ትልልቆችን ግን ሦስት ዓመት ተምረው ያጥምቋቸው። ሴቶችን ቁሱ ዓይኑን በሻሽ ተሸፍኖ የ60 ዓመት መበለት የቁሱን እጅ ይዛ ታስቀባቸው። አቅመ ሔዋን ያደረሱ ስለሆኑ ሕዋሳቸውን ያየ እንደሆነ የጎልዮ በደል ይሆንበታልና ፈቃደ ሥጋ ይነሳበታልና እንዳይነሳበት ነው።

ምሥጢረ ቁርባን

ቁርባን ለ15 ሰዓት ጹመን እንቀበለዋለን። የምንቀበለው ሥጋ ወደሙ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው። ሕያወ ባሕርይ ነው።

ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን

ጌታ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ መባሉ እንዴት ነው ቢሉ አርብ ከነግህ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ ብርሃን ሆኗል አንድ መዓልት ተብሎ ተቆጥሯል። ከቀትር አንስቶ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ጨለማ ሆኗል አንድ ሌሊት ተብሎ ተቆጥሯል። ከዘጠኝ ሰዓት እስከ ሠርክ ብርሃን ሆኗል ብርሃን ሆኗል አንድ መዓልት ተብሎ ይቆጠራል። ዕለተ ዓርብ ሌሊቱ አንድ መዓልቱ ሁለት ማለት ነው። አርብ ለቅዳሜ አጥቢያ አንድ ሌሊት። የቅዳሜ መዓልቱ አንድ መዓልት። ሦስት መዓልት ይሆናል። ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ አንድ ሌሊት ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት የተባለ ይህ ነው። አንድም ከርሰ ሐዋርያትን መቃብር ብሎ ነው። ምነው ጌታስ ከፍ ብሎ በአራት ቀን ዝቅ ብሎ በሁለት ቀን ሳይነሳ በሦስተኛው ቀን ስለምን የተነሳ ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው። የእኛስ ትንሳኤ እንደምን ነው ቢሉ ዛሬ በዚህ ዓለም ሰው ከእናት ከአባቱ ተወልዶ ሲወርድ ሲወጣ ሲመላለስ ሲበላ ሲጠጣ ይኖራል። ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት እንዲሉ ሞት አይቀርም ይሞታል። በሞተም ጊዜ አራቱ ባሕርያት በየመዛግባታቸው ይመለሳሉ አ አዳም መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት እንዳለች ኦሪት። ሐሳዊ መሲሕ የ፴ ዓመት ጎልማሳ ሲሆን በምትሐቱ በአብነቱ ፀሐይን በቀኝ እጁ ጨረቃን በግራ እጁ ሳይዝ የያዘ መስሎ አምላክ ነኝና እመኑልኝ እያለ ከወደ ምሥራቅ ይመጣል። ያን ጊዜ ያላወቁ ያልተማሩ ሰዎች ያምኑበታል። መሥዋዕቱም የውሻ ሥጋ ነው። ዛሬ የተሰወሩ እነ ሄኖክ እነ ዕዝራ እነ ኤልያስ እነ አቡነ አረጋዊ እነ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ከከተማ ገብተው የቀና ሃይማኖትን ይነግራሉ ያስተምራሉ። ፀሐይና ጨረቃን ከጥንት ቦታቸው እንዳሉ ያሳዩዋቸዋል። እሱንም ፍጹም ጋኔን የጋኔን ልጅ እንደሆነ ይነግሯቸዋል እሱም ያን ጊዜ ተናዶ በሰይፍ ያስፈጃቸዋል ይሞታሉ። ከዚህም በኋላ ጎግ ማንጎግ የሚባሉ በእስክንድርያ ሃይማኖት ተጠብቀው አሉ። እነርሱስ እንደምን ያሉ ናቸው ቢሉ ከወገባቸው በላይ ሰው ከወገባቸው በታች አንበሳ ጅራታቸው ሁለት ልሳን ያለው እባብ ነው። በሰውነታቸው ይዋጋሉ በአንበሳነታቸው ይሰብራሉ በእባብነታቸው ይነድፋሉ ሰበድዓት ማለት ነው። ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ነጋሪቱን አውልቆ አውልቆ ይጥለዋል እነሱም እስክንድር መስሏቸው እስክንድር ሸሸ እያሉ በኋላ በኋላ ይከተላሉ። እሱም እያሰበ የነጋሪት ድምጽ እያሰማ ወስዶ ከሐሳዊ መሲሕ ከተማ ይጥላቸዋል እስክንድርን ያገኘን መስሏቸው እርስ በእርሳቸው ተዋግተው ይተላለቃሉ ምድርም ብቻዋን ትቀራለች። ወታስተነፍስ ምድር ሰብዓተ ዕለተ እንዲል። ከዚያ ስምንቱ ነፋሳተ መዓት ምድርን እንደ አውድማ ይደለድሏታል። እኛ ስንነሳ ቀይ ጥቁር ጎባጣ መላጣ ዕውር አንካሳ ሳይኖር ወንዶች በአቅመ አዳም የ፴ ዓመት ጎልማሳ ሴቶችም በአቅመ ሔዋን የ15 ዓመት ቆንጆ ሆነው ይነሳሉ። ጻድቃን ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጎናጽፈው ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው ፍጹም ክርስቶስን መስለው ይነሳሉ። ኃጥዓን ጨለማ ለብሰው ጨለማ ተጎናጽፈው አረው ከስለው ከቁራ ሰባት እጅ ጠቁረው ፍጹም አለቃቸው ዲያብሎስን መስለው ይነሳሉ።

ሰይጣን

ከዕለታት በአንድ ቀን ዲያብሎስ እኔን የወደደ ባገኝ ስጠኝ ብሎ ጌታን ለመነው።ጌታም ሕይወተ

ሥጋ ሕይወተ ነፍስ የምሆናቸው እኔን ጠልተው ደዌ ሥጋ ደዌ ነፍስ የምትሆናቸውን አንተን ከወደዱ ሰጥቼሀለሁ ብሎታል።

ሥነ ፍጥረት

ይህ ስነፍጥረት የተባለ መጽሐፍ ዛሬ የተጻፈ ወይም የተፈለሰፈ አዲስ ነገር ሳይሆን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እግዚአብሔር በገለጠላቸው ነቢያት ሐዋርያት ቅዱሳን ጻድቃን ታውቆ ሲነገርና ሲያያዝ እስከ ዘመነ ሙሴ ደረሰ። ከዚያም ሊቀ ነቢያት ሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ በሚል አርእስት የሥነፍጥረትን ነገር አምልቶ አስፍቶ ጽፏል። ከእርሱም በኋላ ተራ በተራ የተነሱ ነቢያት የሱን መሰረትና መነሻ በማድረግ አጉልተው አስፍተው ጽፈዋል። እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ የሰው ልቡና መርምሮ ሕሊናው ተራቆ የማይደርስበት ስለሆነ ዕውቀ ድንቅ በማለት ይወሰናል እንጂ መርምሬ እደርስበታለሁ ማለት በከንቱ እንደመድከም ይሆናል። ይሁን እንጂ ከዓለም ፍጥረት ጀምረው የተነሱ ነቢያት ሐዋርያት ፈላስፎች ሁሉ እንደየተገለጠላቸው መጠን የስነፍጥረትን ነገር በከፊል የጻፉ ሲሆኑ የአሁኑ ጊዜ ትውልድ እነርሱ ከተናገሩትና ተመራምረው ከደረሱባቸው ሥነ ፍጥረቶች አንድ አንዱን ማብራራትና በሥራ ላይ ማዋልን እንደቀጠሉ ናቸው። ይኸውም በቀዳሚ ገብረ ሰማየ ወምድረ ካለው ውስጥ ተመራምረው የደረሱበትን ያህል መግለጥ ነው እንጂ ከአሁን ቀደም ያልተፈጠረና ያልታወቀ ፍጥረት ኖሮ አዳዲስ ነገር መግለጣቸውና መፈልሰፋቸው አይደለም። ፈላስፎችም ቢሆኑ ባለቤቱ ካልገለጠላቸው ማንኛውንም ነገር ማድረግ አይችሉም። ቢሆንም የአሁን ጊዜ ፈላስፎች ከአሁን ቀደም በዓይን ያልታዩ በእጅ ያልተጨበጡ አዳዲስ ጥበባዊ ብልሀቶችን ፈልስፈዋል። ይህንንም በስራ ላይ ያልዋለውን በሥራ ላይ አዋሉት ማለት ነው እንጂ ከስነ ፍጥረት ወጡ ማለት አይደለም። ራሳቸው ጥበበኞችም ጭምር በሞት የሚለዋወጡ የስነፍጥረቱ አካል ናቸው። የቀድሞ ቅዱሳኖች በብቃት በሰማይ ይበሩ ነበር የዛሬው ፈላስፎች ግን በጥበባዊ መርከቦቻቸው ተሳፍረው በአየር ላይ ይንሳፈፋሉ። ወደፊትም ይድረሱባቸው አይድረሱባቸው ወደፊት የሚታይ ሲሆን አሉ ወደሚባሉት ክፍለ ዓለሞች ለመድረስ በመዘጋጀት ላይ ናቸው። እንዲያውም የጨረቃን ዓለም ደርሰው ተመልሰዋል ይህም የሚያስመሰግናቸው እና የሚያስደንቃቸው ነው። አድናቆቱና ምስጋናው ግን የተወሰነላቸው 70/80ውን ዘመን የማያልፉ መዋቾች ሲሆኑ የቀድሞ ብጹዓን ፈላስፎች በቃል ተናግረውት በጽሑፍ አስፍረውት ካለፉ በኋላ ከዓይን ተሰውሮ በሥራ ላይ ለማዋሉ አስቸግሮ የነበረውን ስነፍጥረት በልዩ ልዩ ጉልህ ስራዎች ላይ በማዋላቸው ነው። ይህንንም ቅሉ እንዲደርሱበት ትንቢት ተነግሮላቸዋል ተነግሮባቸዋልም በሰማይ መብረር እንዲቻል ኢሳ.18፣1 አሌ ሎን ለአሕማር እለ ቦን ክንፍ ብሏል። ፈላስፋው ሰሎሞንም የስነፍጥረት ነገር በየጊዜው እንጂ በአንድ ትውልድ ውስጥ ተገልጾ እንደማይጨረስ ሲናገር ቦ ጊዜ ለኩሉ ብሏል። ስለልዩ ልዩ ክፍለ ዓለሞች መኖርም ምንም እንኳ ለበቁት ቢገለጽላቸው ካልበቁት ወገን በዓይነ ሥጋ አይቶ በእግረ ሥጋ ደርሶ የተመለሰ ፍጡር ባይኖርም ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ገነት ብሔረ ሕያዋን ብሔረ ብጹዓን የተባሉ ክፍለ ዓለሞች እንዳሉ በየመጻሕፍቱ ተነግረዋል። ጠቅላላው ፍጥረት ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ገንዘቡ ስለሆነ የፈጠረውን ስነፍጥረት ተመራምረን ከሀሊነቱንና መግቦቱን ገናናነቱን አውቀን እናመስግነው። እሑድ ቀን በመጀመሪያ ሰዓተ ሌሊት

አራቱን ባሕርያት 5ኛ ጨለማን ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጠረ። የእሳት ግብሩ ውዑይነት፣ ብሩህነት እና ይቡስነት ነው። የውሃ ግብሩ ብሩህነት፣ ርጡብነት እና ቀሪርነት ነው። የነፋስ ግብሩ ርጡብነት፣ ውዑይነት እና ጽሉምነት ነው። የመሬት ግብሩ ይቡስነት፣ ጽሉምነት እና ቀሪርነት ነው። እግዚአብሔር ባወቀ ይሰራል ሰው ባላወቀ ይፈርዳል እንዲሉ ምነዋ ሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ብሎ አንድ ሰማይ አለ። ከዚህ ሰባት ሰማያት አለ አይጣላምን ቢሉ አዎ አይጣላም እንደመናገሻ እንደግንብ ይሉታል። እርከን እርከኑን ሲያዩ ላይ ግንብ ታች ግንብ ሰገነት ይሉታል። እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ እንዲል። እንደዚሁም ሁሉ ሙሴ መያያዙን ሲያይ ሰማይ አለው።ከዚህ እርከን እርከኑን ሲያይ ሰባት ሰማያት አለ እንጂ አይለያይም አይጣላም። ሐዋርያትም 2ኛ ጴጥ.10፣13 ሐዳሳተ ሰማያተ ወሐዳሰ ምድረ ንሴፎ ብለው ሰማዮች እንዳሉ ገልጸዋል። የሰማልያል ወይም የሳጥናኤል ነገዱ አስር ነበርና አነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን ወአነ ገባሪሆሙ ለግቡራን ባለ ጊዜ ስድስቱ ከቅዱስ ሚካኤል ነገድ ተጨመሩ። አራቱ ከሦስት ወገን ተከፋፈሉ እኩሉ አምን ፈጠረን ብለው አመኑበት ሰገዱለት እኩሉ ማን ከማን ያንሳል እኛም ከበታቻችን ያሉትን ፈጠርናቸው እንበላ አሉ። ነገር ግን ከእርሱ በቀር ፈጠርሁ ያለስ የለም ብሎ ፈጥሮን ይሆን? አልፈጠረን ይሆን በማለት ተጠራጠሩ። እኩሉም ከዚያም ከዚህም ሳይሆኑ ፈዘው ቀሩ። በዕለተ ሠሉስ በአንደኛው ሰዓተ ሌሊት ሲሶው ውሃ ተከፍሎ በዚህ ዓለም ሞልቶ አድሮ ነበርና ይህንን ከሦስት ከፍሎታል። አንዱን እጅ ለይትጋባእ ማይ ውስተ ምእላዲሁ ብሎ ከምድር ወደታች ሰደደው አንዱን እጅ አስቀድሞ የሚያርፍበትን መሬት ጠርጎ ወደ ዳር አውጥቶ ውሃውን በውቅያኖስ ዙሪያ አስፍሮታል። አንዱን እጅ ከሁለት ከፍለው አንዱን ከምድር በታች አሰፈረው። አንዱን እጅ ዙሪያውን አጊድጉዶ በዚያው አስፍሮታል። ይኸውም ውቅያኖስ ይባላል። በዚህ ዓለም ያለው ውሃ ግን ዛሬ ወጭትን አጥበው ባፈሰሱ ጊዜ ጥቂት ልቅላቂ እንዳይታጣ እንደዚያ ሆኖ የቀረ ነው ይሉታል። ዳግመኛም ጥቁሩን መሬት ከታች አውርዶ መሰረት አድርጎ ደልድሎ ስሙን በርባሮስ ብሎታል። በርባሮስ ማለት መትሕተ ታሕቲት ማለት ነው። በሁለተኛው ሰዓት የመሬትን ቅጽር የመሬትን ጸፍጸፍ አበጅቶ ውሃን አሰፈረ። ዳግመኛም ውቅያኖስን ሲያሰፍር መሬቱን ጠርጎ ወደዳር አወጣው ብለን ነበርና ያ የጠረገው መሬት በዙሪያው የመሬት ቅጽር ቀጸረው ቅጽርነቱ ግን ከጠፈር የሚደርስ አይደለም። ከታች የሚቀር ነው ስሙንም ናጌብ አለው። በወዲያ አድማስን ወሰን አደረገለት። የገነት ከምድር ርቀቱ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለውን ያህል ነው። ረቡዕ ዕለት በነግህ ፀሐይ 4 ኬክሮስ ሲቀረው ተገኝቶ ያንን ጨርሶ በደቡብ በኩል ሲዞር አድሮ ረቡዕ ዕለት በነግህ በስተምሥራቅ ሲወጣ በምልአት ተገኝቶ ሲያበራ አድሮ በነግህ ከጨረቃ ጋር ተያዩ ይሏል። ለጨረቃ እስከ 15 ቀን ድረስ መጋቤ ወርኅ መልአክ አላት ብርሃን እያመጣ ይሥልባታል። ሥላሴ አዳምን የፀ ዓመት ጎልማሳ አድርገው በማእከለ ምድር በቀራንዮ ፈጠሩት። ዲያብሎስን ጌታ እሑድ ከኢሩሳሌም ሰማያዊት ወደ ኢዮር አውርዶታል። ረቡዕ ከኢዮር ወደዚህ ምድር አውርዶታል። ሐመስ ከመላእክት ጋር ገጥሞ ጌታ በልብሳቸው በአካላቸው ላይ የብርሃን መስቀል እየቀረጸ ሰደዳቸው ወርደው ቢገጥሙት ድል አደረጉትና በእግራቸው እየጠቀጠቁ እንጦርጦስ አወረዱት። አርብ አዳም በመፈጠሩ ድቀተ ጎሊና አግኝቶታል አርብ ወረደ ያሉት ድቀተ ጎሊናውን ቆጥረው ነው። ጌታ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ አለ ኋላ ከሦስቱ አካላት

አንዱ አካል ወልድ የአዳምን ሥጋ የሚለብስ ነውና የኋላውን ተናገረ። እባብ ደንቆሮ ነው ከመ አርቄ ምድር ጽምምት እዘኒሃ እንተ ኢትሰምእ ቃለ ዘይረቅያ እንዲል መዝ.57።

ጊዜያት

እሑድ ማለት አንድ መጀመሪያ ማለት ነው። መጀመሪያነቱ ለሰባቱ ዕለታት ነው። ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ዓለም የተፈጠረ መጋቢት 29 ቀን በዘመነ ዮሐንስ ነው። በዚያን ጊዜ ወንጌላውያን አልነበሩም ዘመነ ዮሐንስ መባሉ እንደምን ነው ቢሉ የኋላ ሊቃውንት የጌታን ቃል ለአራት ተካፍለው በዘመን በቦታ ሳይገናኙ ስለጻፉ ለክፈለ ዘመናት መታወቂያ እንዲሆኑ አድርገዋል። ይኸውም እንደአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ እንዲሆኑ ወስነዋል። ስለዚህ ዘመናቱን ለአራት እየመደቡ ወደኋላ ቢመለሱ ዓለም የተፈጠረበት ዘመን ለዮሐንስ ይደርሰዋል። ጌታ በ24 ሰዓቶች ስራ ስለሰራባቸው ፍጥረቱ ሁሉ እየወገኑ እየወገኑ ሆኖ ይጸልይባቸዋል። እግዚአብሔር ለአዳም እንደነገረው።

- በ፩ ሰዓተ መዓልት የዐርግ ጸሎቶሙ ለውሉደ መሐይምናን ኀበ እግዚአብሔር።
- በ፪ ሰዓተ መዓልት ይከውን ጸሎቶሙ ለመላእክት ወአስተብቁዖቶሙ ኀበ እግዚአብሔር።
- በ፫ ሰዓተ መዓልት ይሴብሕዎ አዕዋፈ ሰማይ ለእግዚአብሔር።
- በ፬ ሰዓተ መዓልት ያመልክዎ መንፈሳውያን ለእግዚአብሔር።
- በ፭ ሰዓተ መዓልት ይሴብሕዎ ኩሉ እንስሳ ወአራዊት ለእግዚአብሔር።
- በ፮ ሰዓተ መዓልት ይከውን ስእለቶሙ ለኪሩቤል ኀበ እግዚአብሔር።
- በ፯ ሰዓተ መዓልት ይበውኡ መላእክት ወይወጽኡ ኀበ እግዚአብሔር። እስመ በዛቲ ሰዓት ያዓርገ ስእለቶሙ ለኩሎሙ ሕያዋን።
- በ፰ ሰዓተ መዓልት ይሴብሕዎ ሰማያውያን ብሩሃን ለእግዚአብሔር
- በ፱ ሰዓተ መዓልት ይሴብሕዎ ወይትቀነዩ ሎቱ ኩሎሙ ሰማያውያን ወይቀውሙ ቅድመ መንበሩ ለልዑል።
- በ፲ ሰዓተ መዓልት ይጼልል መንፈስ ቅዱስ ላእለ ማያት ወይጎይዩ አጋንንት ወይሴስሉ እምነ ማያት። ወሶበ ኢጸለለ መንፈስ ቅዱስ ላእለ ማያት በዛቲ ሰዓት ኩሎ ዕለተ እም ኢክህለ መኑሂ ሰትዮቶ ለማይ ወእማሰነ ሥጋሁ እምኀበ አጋንንት እኩያን። ወሶበ ነስአ ካህን ማየ በዛቲ ሰዓት ወቶስሐ ምስሌሁ ዘይተ ቅዱሰ ወቀብዐ ቦቱ ድውያነ ወእለ ቦሙ መናፍስት ርኩሳን ይትፈወሱ እምደዌሆሙ።
- በ፲፩ ሰዓተ መዓልት ይከውን ፍሥሓሆሙ ለጻድቃን
- በ፲፪ ሰዓተ መዓልት ይትዌከፍ እግዚአብሔር ጸሎቶሙ ወስእለቶሙ ለውሉደ ሰብእ።
- በ፩ ሰዓተ ሌሊት የአኩትዎ አጋንንት ለእግዚአብሔር ልዑል ወአልቦሙ በዛቲ ሰዓት እከየ ላእለ ሰብእ ወኢላእለ መኑሂ እስከ ይፈጽሙ ቅኔሆሙ። አጋንንትኒ የአምኑ ቦቱ ወይደነግጹ እንዳለ።
- በ፪ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ዓሣት ወኩሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማያት አራዊትኒ ወአናምርት።
- በ፫ ሰዓተ ሌሊት ትሴብሑ እሳት እንተ መትሕተ ታሕቲት።

- ❖ በ፬ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ሱራፌል ለእግዚአብሔር።
- ❖ በ፭ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ማያት ዘመልእልተ ሰማያት ለእግዚአብሔር።
- ❖ በ፮ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ደመናት ለእግዚአብሔር በፍርሀት ወበረዓድ። ይባርክዎ መብረቅ ወደመና ለእግዚአብሔር።
- ❖ በ፯ ሰዓተ ሌሊት ትትቁደስ ምድር ወየሐውር ዲቤሃ እግዚአ መናፍስት። ወበዛቲ ሰዓት ሶበ ነስአ ካህን ማየ ወቶስሐ ዘይተ ቅዱሰ ምስሌሁ ወቀብዐ ቦቱ ዱያነ እም ተፈወሱ ወእም ሐይው እም ደዌሆሙ ወእምኖሙ እለ ኢይነውሙ።
- ❖ በ፰ ሰዓተ ሌሊት ታወጽእ ምድር ሣዕረ ወሐመልማለ ወታበቁል ዕፀወ። መዝ.148
- ❖ በ፱ ሰዓተ ሌሊት ይትቀነዩ መላእክት ለእግዚአብሔር ወትበጽሕ ጸሎቶሙ ለውሉደ ሰብእ ቅድመ እግዚአብሔር።
- ❖ ፲ ሰዓተ ሌሊት ይትረኀው አናቅጸ ሰማያት ወይሰምእ እግዚአብሔር ጸሎቶሙ ለውሉደ ሰብእ ወይትወሀቦሙ ስእለቶሙ ዘይስእሉ እም ኀቤሁ ወበዛቲ ሰዓት እም ድምጸ ክነፊሆሙ ለሱራፌል ይነቁ ዶርሆ ወይሴብሑ ለእግዚአብሔር።
- ❖ በ፲፩ ሰዓተ ሌሊት ይከውን ፍሥሓ ወሐሴት ዲበ ምድር እስመ ፀሐይ ይበውእ ውስተ ገነት ወይሠርቅ ብርሃኑ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወይበርህ ላዕለ ኩሉ ፍጥረት።
- ❖ በ፲፪ ሰዓተ ሌሊት መፍትው ለውሉድየ ይቁሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወይትቀነዩ።እስመ በዛቲ ሰዓት ይከውን ንስቲት አርምሞ በኀበ ኩሎሙ ሰማያውያን ወይወርድ ቃለ እግዚአብሔር ልዑል እም ሰማይ ዲበ ምድር።

5500 ዘመን ሲተነተን እንደሚከተለው ነው። ይህም ዘመን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባላል።

- ✓ ከአዳም እስከ ኖኅ ያለው ዘመን 2250 ዓመት ነው።
- ✓ ከኖኅ እስከ ሙሴ ያለው ዘመን 1588 ዓመት ነው።
- ✓ ከሙሴ እስከ ሰሎሞን ያለው ዘመን 599 ዓመት ነው።
- ✓ ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው 1063 ዓመት ነው።

ሥላሴ በተዋሕዶ

አዘጋጅ፡- መሠረት ስብሐት ለአብ። በአክሱም ከተማ በ1914 ተወለዱ። ቅኔን ጎጃም ተምረዋል።

መማር፣ ትርጓሜ

ብልድያኖስ የተባለ ሊቅ ዘይትቀነይ ለክርስቶስ በጽድቅ ይደልዎ ይትመሀር ዘኢየአምር ወይምህር ዘየአምር ዘእንበለ ቅንዐት። ወእመሰ ኢይፈቅድ ይትመህር ወይምህር እንዘ ይትከሀሎ ቦቱ ሕማመ ጋኔን። እስመ ርእሳ ለክህደት ጸጊበ ትምህርት ውእቱ ይላል መጽሐፈ ገነት። ምንጊዜም የሚማር ሰው ምን ጊዜም የሚያስተምረውን ትምህርት አያጣም። የኢትዮጵያ ሊቃውንት የምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት የትምህርተ መለኮት ውሳኔን ተቀብለው እንደ ማኅደር ተሸካሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ውሳኔያቸው የተመሰረተበት ቅዱስ መጽሐፍን በተመርሆ ልቡናዊ መርምረው ተመርሆውን በማዛመድ ሲያጣሩ የነበሩ ናቸው። ይህንን ብቻ ሳይሆን

የአሥራወ ቃላትን ሕግና ደንብ ጠንቅቀው አዛምደው የሚታረቀውን አስታርቀው የተገኙ ናቸው። እንዲሁም በየትውልዱ ያለፈውን ሕዝብ ከሚለዋወጠው የቋንቋው ዘይቤና ከተለዋዋጩ ባህሉ ጋር የሚስማሙ አሥራወ ቃላትን ከሁኔታው ጋር እያዛመዱ ያለፉ ናቸው። ወኢነንድኅ እንበለትርጓሜ ለኩሉ ዘነበብነ ይሉ ነበር። ይህም ያነበቡትን ሁሉ ሳይተረጎም ወይም ሳይመረመር እንዳይቀመጥ ማድረጋቸው ስለ ትምህርተ መለኮት ዕውቀት የነበራቸው አስተሳሰብ ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለሃይማኖት በምናብራበት ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታዊ ሀሳብ እንዳንወጣ እንጠንቀቅ። የትምህርተ መለኮት አሥራወ ቃላትና ምሥጢራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኝ ንባብ መመስረት ይኖርባቸዋል እንጂ ያለ ንባብ ትርጓሜ አይሆንምና የገዛ ራስን ሀሳብ ወይ ስሜት ብቻ ታቅፎ ለብቻ መጓዝ ምንም ያህል አያራምድም። ጥያቄዎች ጥያቄዎችን እየወለዱ ይገኛሉ። ይህም የቤተ ክርስቲያን ጥልቅ ትምህርት ከሚስፋፋበት መንገድ አንዱ በመሆኑ የሚነቀፍ ነገር አይደለም። ማንኛውም ጥያቄ በነጻ ሐሳብ ቢጠየቅ መረዳትን ስለሚያስከትል ቢጠየቅ የሚደገፍ ነው።

እውነት እና እምነት

የእግዚአብሔር መንግሥት መሰረቷ እውነት ስለሆነ ርትዕትና ቀጥ ያለች ናትና። እምነት ተብሎ የሚታመንበት ነገር ከእውነት ውጭ ስላልሆነ የመጣ ቢመጣ ተሸፋፍኖ የታሸገ እምነት ሊኖር ስለማይገባ ምንጊዜም እውነቱን ማመንና እውነቱም በግልጽ ያለስጋት መታወቅና መነገር ይኖርበታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ባዕድ ከሚሆን ሃይማኖት መራቅ ይገባናል። ክርስቲያናዊ እምነት የቆመው በቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት ላይ ነው። ሀሳቦች ወይም ፈሊጦች እውነት ወይም ስህተት የሆኑ እንደሆኑ የሚረጋገጠው ከቅዱሳት መጻሕፍትና ሐዋርያዊት ከምትሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ዘንድ የአምንታና የአሉታ መልስ ሲገኝለት መሆኑ የታወቀ ነው። የሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ትምህርት በጥልቀት እንጂ በመንሳፈፍ አልተመሰረተም።

እግዚአብሔር

ሰዎች እግዚአብሔርን እየፈለጉና እየመረመሩ እንዲያገኙት የሚወድና ፈቃዱ ያልተገደበ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች እንዲፈልጉት የሚገደዱበትን አእምሮ በልባቸው ውስጥ አሳድሯል። ይህም እርሱን እንዲፈልጉትና እንዲሹት የሚገደዱበትን የአእምሮ ፍላጎትና መሻት በልባቸው ውስጥ በማሳደሩ ይታወቃል። ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈልጉትና እንዲሹት የሚገደዱበትን የአእምሮ ፍላጎትና መሻት ራሱ እግዚአብሔር ከውስጣቸው ለማኖሩ፡-

- ✓ 1ኛ ሰው የስነ ፍጥረትን ውበት ሥርዓታቸውንና አቀማመጣቸውን ያያል። ስለዚህ እንዲህ አድርጎ የሰራቸው ማን እንደሆነ ሊያውቅ ይሻል። ሠሪያቸውንም ፈጣሪያቸውንም ለማወቅ እንዲፈልጉ የአእምሮ ሕግ ያስገድዳቸዋል።
- ✓ 2ኛ ሰው አካላዊ አቋሜን ካለመኖር ወደመኖር ያመጣሁ እኔ ራሴ ነኝ የገዛ ራሴን የፈጠርሁ እኔ ራሴ ነኝ አስቀድሜ ሰው እንድሆን የመረጥሁ እኔ ራሴ ነኝ ከልዩ ልዩ ዓለማት ይልቅ በዚህ ዓለም እንድኖር ወስኜ የመጣሁ የሰራ አካላቴን በሙሉ ሁለንተናየን የገነባሁ እኔ ነኝ ለማለት እስካልደረሰ ድረስ ሰው የገዛ ራሱን ከየት

እንደመጣ አካላዊ አቋሙን በሙሉ ማን እንደፈጠረለት ማን እንደሰራለት ማን እንዳመጣው ማንስ እንዳኖረው መመርመርና መፈለግ ፈልጎም ይህን ፈጣሪውንና ሰሪውን ማወቅና መረዳት የተፈጥሮ ግዳጁ ነው።

- ✓ 3ኛ ሰው ለአካላዊ አቋሙ አየር ጠየፍ ምግብ ልብስ ብርሃን መኖሪያ ማግኘት ያስፈልገዋል እንግዲህ ሰው እነዚህን የተጠቀሱትን ካለመኖር ወደመኖር ያመጣኋቸው የፈጠርኋቸውና በዚህ ምድር እንዲኖሩ ያደረኳቸው እኔ ራሴ በገዛ እጄ ነው ለማለት እስካልቻለ ድረስ እነዚህን ለሰብአዊ ሕይወቱ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አስቀድሞ ያዘጋጀለት ማን እንደሆነ በሥርዓትም አሰናድቶ ያቀረበለት ማን እንደሆነ ማወቅና መረዳት የተፈጥሮ ግዳጅ ሲሆን ያ መጀመሪያ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣውና የፈጠረው ባለበትም አካለዊ አቋም ሠርቶ ያኖረው ይህን ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ፈጥሮ አሰናድቶ እንዳቀረበለት በሕገ ተፈጥሮው ያውቃል እርሱን እንዲፈልገውና እንዲያገኘው ግዴታዊ የተፈጥሮ ሕግ ይሆንበታል።
- ✓ 4ኛ ሰው በሥጋው በነፍሱ በመንፈሱ በገዛ ራሱ ሊያስወግደው የማይችለው ችግር እንዳለበት ያያል። ይኸውም በሥጋው ያለበትን ችግር የጠቀስን እንደሆነ የጤና ጉድለት ሕማም በሽታ ልዩ ልዩ ደዌ ረኀብ ጥም እርዛት የዚህ ሁሉ ስቃይ ይደርስበታል። በኑሮው ደግሞ ምድር እሾህና አሜከላ አብቅላበት ወዙን እያንጠፈጠፈ እንዲኖር ተደረገ ሰርቶ እንጀራን ልብላ ላግኝ ሲል ደግሞ ከላይ የዝናብ እጦት ድርቅ በረዶ ውርጭ አመዳይ ሲሆንበትና ድካሙንና ልፋቱን መና ሲያደርግበት ሲያጠፋበት ያያል። ከዚህ በላይ ደግሞ እርሱን ያልፈጠሩት ሌሎች ፍጡራን አራዊት መናፍስት ጨካኞች በአጥቂነትና በሸማቂነት በአስጨናቂነት በአጥፊነትና በጎጅነት ሲያስፈራሩትና ሲያሰቃዩት ግፍም ሲፈጽሙበት ያያል። እንግዲህ ሰው በእንደዚህ ባለው ችግር ውስጥ በሚገኝበት ጊዜ የሚሸሸበትን የሚጠለልበትን የሚጠጋበትን ተገን ሲፈልግ ወደማን ነው የሚያየው ወደየት ነው የሚሸሸው ምንድን ነው የሚያስበው ማንን ነው የሚፈልገው። አግኝቶ ለማማረር ቢሆን ለመውቀስም ቢሆን ወይም ትድግናን ለመጠየቅ ቢሆን መጀመሪያ ፈጥሮ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣውን በዚህ አቋም እንዲኖር በዚህ ዓለምም እንዲቀመጥ ያደረገውን ፈጣሪውን ነው ለመፈለግ የሚገደደው። ሰው በነፍሱ በደመ ነፍስ ያለበት ችግር ኀዘን ጭንቀት መከራ ስቃይ ፍርሀት ኀፍረት ውርደት ጥቃት የመሳሰለውም በዚህ ዓለም አኗኗሩ ዘወትር ይደርስበታል ይህንም ሁሉ ከውስጡ ይሰማዋል። ከዚህም የተነሳ በብዙ ይጨነቃል። አዙሮም ሲያይ ወደዚህ አስጨናቂ ዓለም ለምን እንደመጣ ማሰብ ይጀምራል። በዚህም ጊዜ ያን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረውን እዲፈልገው ይገደዳል።

ሰው በመንፈሱ የደረሰበት ችግር እንዳለ ከውስጡ ይረዳል። ይኸውም ሰው የእግዚአብሐየርን ክብር በማጣቱ ካለበት ጉድለት የተነሳ የሚሰማው የሰውነቱ ቅሌት ነው። ደግሞ ኃጢአት ይሰራልና ለኃጢአቱ ዋጋ የሚከፈል ዕዳ እንዳለበት በመረዳቱ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ራሱን ያለምስክር እንዳልተወ አረጋግጧል። እግዚአብሔር ራሱን መደበቅ የሚወድ አፋራም አይደለም። ኢዮ.37፣12 በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስፈራ ግርማ አለ። ሁሉን

የሚችል አምላክን እናገኝ ዘንድ አንችልም። በመሠረቱ ማንም ወይም ማናቸውም ቢሆን የልዑል እግዚአብሔርን ህላዌ መለኮትና ህሉና ሥላሴን በጠቅላላው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለማወቅና ለመረዳት አውቆም እንዲህ ነው ብሎ ለማስረዳት እንደማይቻለው ከጥንት ጀምሮ ከነበሩት አበው ከነቢያትና ከሐዋርያት ከኋላም ከተነሡት ሊቃውንት አንድ ድምጽ ብቻ ተሰምቷል። ኢዮ.11፣7 የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን ይላል። ቅዱስ ጳውሎስም 1ኛ ጢሞ.6፣16 አልቦ ዘርእዮ ሰብእ ወአልቦ ዘይክል ርእዮቶ ብሏል። እንዲሁም ባስልዮስ ዘቂሳርያ ሃይ.አበ.ክፍል 4 ቁጥር 14 ለእመ ተጋብኡ ኀቡረ መላእክት ወሊቃነ መላእክት በበዘመዶሙ ወበበሥርዓቶሙ ዘምስለ ኩሎሙ ፍጡራን አሐተኔ ኢይክሉ ይርከቡ ኀዳጠ እምአእምሮተ ህላዌሁ ለእግዚአብሔር ይላል። ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራትም በሃይ.አበ ክፍል 2 ቁጥር 16 ላይ እፎኑመ ነአምር ምሥጢሮ ለፈጣሪ ዘኢተፈጥረ ዘይትሌዓል ኩሎ ሕሊናተ ይላል። ባስልዮስም ዳግመኛ እንዲህ ይላል ቦኑ ይትከሀለነ ንጠይቅ ስፍሐ ሰማይ ወዕመቀ ቀላይ እስመ ኢንክል ንጠይቅ ኀዳጠ እምፍጡራን። እፎመ ይትከሀለነ ንብጻሕ ኀበ አእምሮተ እግዚአብሔር ይላል። በመቀጠልም እመሰ ይርኅቀ ለሕሊናነ አእምሮተ ተግባራት ዘንኔጽሮሙ ወኢንክል ተናግሮ ዘከመ ድልወቶሙ እፎኑመ ንትሐበል ለተናግሮ ዘኢያእመርነ ይላል። ሃይ.አበ ባስልዮስ ክፍል 4 ቁጥር 3፤12፣4። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ እግዚአብሔር ጠቅላላ ህላዌና ስለባሕርዩ ግብር ሲናገር የእግዚአብሔርን ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው? ፍርዱም እንዴት የማይመረመር ነው? ለመንገዱ ፍለጋ የለውም የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና። ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን እያለ በመደነቅና በመገረም ምስጋናን ብቻ ያቀርብለታል ሮሜ.11፣33-36። ዮሐንስ አፈወርቅም በድርሳኑ ድርሳን 2 ላይ "እስመ ኢይትከሀሉ ለልሳን ይንብብ በእንቲአሁ ከመ ድልወቱ ወሕሊናሂ ኢይክል ሰሚኦቶ ኀድግሰ ልሳነ ሕሊና ልብኒ ዘይከብር እምኔሁ ኢይጤይቅ ምንተኒ እምኔሁ" ይላል። ቴዎዶጦስ ዘዕንቆራ በርቱዐ ሃይማኖት ምዕራፍ 3 ክፍል 2 ምዕ.22 ላይ "እስመ እግዚአብሔር ኢይትረከብ በሕሊና እንለ እመሕያው ወሕሊና እንለ እመሕያው ኢይረክብ መለኮተ ወህላዌ መለኮት ርኁቅ እምሕሊና እንለ እመሕያው ወይትሌዓል ኩሎ ሕሊናተ ፈድፋደ" ይላል። ርቱዓ ሃይማኖትም ኦ ብእሲ በመኑ ታስተማስሎ ለዘኢይትማሰልዎ ፍጥረታት ወዘከመ እፎ ትሄልዮ ለዘኢይትሄለይ። ኢይደሉ ያስተዐርይዎ በፍጡራን በመኑኒ ኢ በመብረቅ በእንተ ግርማሁ ወኢ በፀሐይ በእንተ ልዑል ብርሃኑ ኢ በሰማይ በእንተ ልእልናሁ ወኢበምድር በእንተ ራኅቡ ወኢ በባሕር በእንተ ዕመቁ ወኢ በእሳት በእንተዋዕዩ ኢ በነፋስ በእንተርቀቱ ወፍጥነቱ ወኢበምንትኒ ኢይትረከብ። በእንተጥያቄ መለኮቱ ለአምላክ ጽድቅ ኢተውህቦ ለፍጥረት ያእምር መነሂ ወመኑሂ ወበእንተዝኬ ኢይደሉ ንኅሥሥ ክዋኔሁ ለዘኢይትዐወቅ ኩነቱ። እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ የማይወሰን መሆኑን መገንዘብ በሌላ ወገን ደግሞ የፍጡራን ተፈጥሮ አቅምና ችሎታ የተወሰነ የተመጠነ መሆኑን መረዳት ይገባል። እንግድህ በግዘፍ ያለና በአቅምና በችሎታ የተወሰነ ሰው አቋም እንዲህ ሆኖ ከተገኘ ዘንድ የማይታይን የማይወሰንን መለኮታዊ ባሕርይ ለመጨበጥና ለመወሰን የማይቻለው ሆኖ በመቅረት ይወሰናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ህላዌና ምስጢር ለሰው የተሰወረ የተደበቀ ይሆንበታል። እንደዚሁም ደግሞ የማይለወጥ

የባሕርይ አምላክ ነውና እንደፍጡራን ግዙፍ ሊሆንና በግዘፍ ሊወሰን የማይቻል ሲሆን ሰው ግን ግዙፍና በማናቸውም ሁኔታ ራሱ ውሱን መሆኑን መርሳት የለበትም። የሐዋ.ስራ.14፣15-18 ራሱን ያለምስክር አልተወም ይላል። ፍጡራን እግዚአብሔርን ፈልገውና መርምረው የማያገኙት ከሆነ በህላዌው በምን ይታወቃል ቢሉ፡- የእግዚአብሔርን ህላዌ በምርምር ተመራምሮ ማግኘት እንደማይቻል ይታወቃል። ይህንን የመሰለ እንኳን እግዚአብሔርን ሰው የገዛ ራሱን ከየት እንደመጣ ሊረዳ አይችልም። ዕብ.3፣3 እስመ ለኩሉ ቤት ሰብእ ይገብሮ ወለኩሉሰ እግዚአብሔር ገብሮ። ሰው ስንኳንስ የእግዚአብሔርን ህላዌና ባሕርይ መርምሮ ሊደርስበት እግዚአብሔር የፈጠራቸውን የሰማይ ኀዋሕውንና ሰማያትን ወጥቶ መጥቆ ሊመረምር ያልቻለ ፍጡር ነው። ሰው በራሱ ምርምር የእግዚአብሔርን ህላዌ ፈልጎ ለማግኘት የማይችል ይሁን እንጂ ሰው እግዚአብሔርን ቢፈልግና ቢሻው ሊያገኘው የሚችልበት መንገድ ሊኖር እንደሚቻል ተስፋ አለ። ሰው እግዚአብሔርን ፈልጎ ለማግኘት የማይችልበት ሁኔታ፡-

- 1ኛ ምርመራው ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ መስመር ዘለል በሆነ መንገድ ከሆነ
- 2ኛ እግዚአብሔር በጸጋው ለሰው ራሱን ሳይገልጥለት ሰውም ክስተቱን ሳያገኝ በገዛ ራሱ ጥበብና ዕውቀት የእግዚአብሔርን ህላዌና እግዚአብሔራዊ ስራን መርምሮ ለመጨበጥና ለማግኘት ስለማይቻለው ነው።
- 3ኛ ሰው ፍለጋው በሥጋና በደም ፍለጋ ሆኖ በአእምሮ ግዘፍ ተውጦ የሚገኝ ስለሆነ
- 4ኛ ሰው ራሱ ግዙፍና በአእምሮና በአካል የተወሰነና የተፈጠረ ፍጡር ስለሆነ ዘላለማዊ ሕያው የማይታይ የማይወሰን ፍጹምና ምሉዕ የሆነውን አምላክ ሊያይና ሊጨብጥ ሊወስን የማይችልና የማይቻለው ከመሆኑ የተነሳ ነው።

ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚችልባቸው መንገዶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- 1ኛ ከእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት የተነሳ እግዚአብሔር ለሰው በሚሰጠው የራሱ መገለጥ። አምላካዊ መገለጥ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ለፍጡራን የሚሰጥ ነው። ሃይ.አበ ሱኑትዩ ክፍል 2 ቁጥር 13 “ወአልቦ ዘይመስሎ ለፈጣሪ በውስተ ኩሎሙ ፍጡራን ዘይትሌዐል እምንባብ ወኢይትከሀል ተሐትቶ በእንቲአሁ ወኢይክሉ አእምሮቶ ኩሉ ፍጥረት ዘመልዕልት ወዘመትሕት ይርከቡ ዘንተ ምስጢረ ዐቢየ ወዘንተ ግብረ መንክረ ወባሕቱ ጸጋ እግዚአብሔር ዘኀዱር ላእሌነ በምሕረቱ ኪያነ ወሠናይቱ ለነ አእመርነ ዘንተ ወእም አበው ንጹሓን ወለበውናሁ በነቢያት ኄራን ጸዋርያነ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን” ይላል። ይህም በወንጌል ማቴ.16፣16-18 ብጹዕ አንተ ስምኦን ወልደ ዮና እስመ ኢከሠተ ለከ ዘሥጋ ወደም አላ አቡየ ዘበሰማያት ከሠተ ለከ ይላል። ይህም በሰው ምርምር ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ክስተት በአዳምና በኖኅ በእነ አብርሃምና በእነ ሙሴ በሐዋርያት ተገልጧል። 2ኛ ሳሙ.23፣2-3 የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ ይላል። ሳሙኤል መገለጡን ባገኘ ጊዜ ባሪያህ ይሰማሀልና ተናገር አለ።ሙሴና ኤልያስ የእግዚአብሔርን መገለጥ ባዩ ጊዜ ከመገለጡ ግርማ የተነሳ ፈርተው ፊታቸውን ሸፈኑ። የነቢያት የሐዋርያት የጽሑፋቸው ይዘትም መገለጥ ሆኖ

መገለጡን ባሳያቸው በመንፈሰ እግዚአብሔር አመራር ቁጥጥር እንጂ ከገዛ ፈቃዳቸው እንዳልሆነ ዕብ.1፣1-2 ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን ነቢያት ከተናገረ በኋላ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ይላል። ጸሎት ክስተቱን እንድናውቅ የሚረዳን ታላቅ መሳሪያ ነው። መዝ. 49፣15 በከመራህ ቀን ጥራኝ እኔም እመልስልሀለሁ አንተም ታመሰግነኛለህ የሚል የተስፋ ቃል ፈጣሪ ስለሰጠን እንጸልያለን። ዮሐ.14፣13 ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ ብሎናል። ለምነውት ብዙዎች የፈለጉትን የለመኑትን አግኝተዋል።

- 2ኛ መሠረቱ የእግዚአብሔር ጸጋ ሆኖ የእግዚአብሔርን ህላዌና የህሉና ሥላሴ በተዋሕዶ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ስራ የሆነ ሁሉ ለመረዳት ከእግዚአብሔር ቃል ዝንፍ ሳይሉ በማጥናት። አባቶቻችን ጠቅላላ የትምህርተ መለኮትን ገለጻ በጽሑፋቸው ሆነ በንግግራቸው ሲያብራሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቃሉን መሰረት አድርገው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከልዩ ልዩ የሰው ፍልስፍናዎች ከልማደሀገር ውሳኔዎች ከአባቶችና ከምሁራን ሊቃውንት ውሳኔዎች በላይ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥግው ቃል ሆኖ በዚህ ምድር በተገለጠ ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት የሰፈረውን ቃል ቃሉ መሆኑን አረጋገጠ ሙሴ በጻፈው ብታምኑ ኖሮ በእኔ ባመናችሁብኝ ነበረ ሙሴ ስለ እኔ ጽፏልና ብላል ዮሐ.5፣46-47። በኤማሁስ መንገድም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ሲሄድ በመንገድ አግኝቷቸው በነቢያትና በሙሴ በኦሪት በመዝሙርም ያለውን ስለእርሱ የተጻፈውን እየጠቀሰ ባስረዳቸው ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ልባቸው ተቃጠለባቸው ይላል። ሉቃ.24፣32። ይህም ፍጹም መገለጥ ነው። መዝ.18፣7-11 የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ነው የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው ነፍስን ይመልሳል ሕጻናትን ጠቢባን ያደርጋል የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው ልብንም ደስ ያሰኛል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው ዓይንንም ያበራል ይላል። መዝ.12፣6 በምድር ላይ እንደተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደተጣራ ወርቅና ብር የእግዚአብሔር ቃላት ንጹሕ ናቸው ብሏል። ኢሳ.50፣42 እግዚአብሔር ወሀበኒ ልሳነ ጥበብ ከመ አእምር ዘእነብብ። ኤር.15፣16 ቃልህ ተገኝቷል እኔም በልቼዋለሁ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ።
- 3ኛ በተመርሆ ልቡናዊ (በመጽሐፍና በልቡና ስምምነት) መሰረት የሥጋና የደም ከሆነ ግብር ርቆ በጸሎትና መንፈሳዊ በሆነ ሕሊና በመመሰጥ የእግዚአብሔርን ህላዌ የሥሉስ ቅዱስ ህልውናን ማጥናት በሌላ አገላለጽ በአንጽሖመንፈስ ከትዕቢት ከትምክህት ከግብዝ ሕሊና ሸሽቶ በፍቅርና በየዋህነት በቅንነት ትምህርቱን በመከተል ነው። ቅዱስ ያሬድ በድጓው ወአንተሰ ለእመ ትፈቅድ ታእምር ጎድግ ሕሉና ዘበምድር ወዕድዎሙ ለከዋክብት ሥነ ሥርዓቶሙ ወኮላሬሆሙ እምዝንቱ ኩሉ ተልዒለከ በሕሊናከ ሐሊ አሐደ ሥሉስ ዘኢይሰደቅ ብሏል።

ሰው በፈጣሪው የተፈጠረ ፍጡር ነው። መነሻ እና መድረሻውም በፈጣሪው እቅድ ያለ እንጂ በራሱ እጅ እንደሌለ ያውቃል። ሰው በተፈጥሮው ድሀ ነው ስለዚህም ባለጸጋ ወደሆነው

አምላኩ ልመናና ጸሎት እንዲያደርግ ይገደዳል። 1ኛ ቆሮ.4፣7 ምንት ብከ ዘኢነሳእከ እምካልእከ ወምንት ውእቱ ዘኢኮነ ውሁበ ለከ። በዚህ ገለጻ መሰረት ሰው ከእግዚአብሔር ያልወሰደው ምንም የለም። ሰው በገዛ ራሱ ራሱን አላመጣም ወደዚህ ዓለም ከወጣና ከተወለደም በኋላ ለገዛ ራሱ ምግብ ስንቅና ልብስ ይዞ አልመጣም። ከእናቱ ጡቶች ወተት እንዲዘጋጅለት ያደረገም ያው ፈጣሪው ነው። እንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔር በወላጆቹ ላይ ለልጁ ኃይለኛ ፍቅር አሳድሮባቸዋል። ስለ ሰው ሕይወታዊ ኑሮ ያየን እንደሆነም ጤና ልብስ አየርና ምግብ የሚጠጣ ውሃ ብርሃንና መኖርያ ማረፊያ ለሰው እንደሚያስፈልገው አስቀድሞ አውቆ ያዘጋጀለት በሚኖርባት ምድር ያስቀመጠለት ከፈጣሪው በቀር ማን ነው? ሰው መቼም ይህንን ያደረገ እርሱ ራሱ እንዳልሆነ ያውቃል። በመሠረቱ እኛ ደካሞችና ከኢምንት የማንቆጠር መሆናችንን እያወቅን ሳለ ለሰው ልጆች በተሰጠ ጸጋና ምሕረት ስር ቆመን እርሱ ራሱ ከገለጸው ከቅዱስ ቃሉ እየተማርን በታላቅ ፍርሀትና ጥንቃቄ ስለ እርሱ እንናገራለን። ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ስለመለኮት እንዲህ ይላል ቀዳማዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እማዕዜ ወማእከላዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እስከ ይእዜ ደኃራዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እስከ ዝየ። አልቦ ጥንት ለህላዌሁ ወአልቦ ማኅለቅት ለክዋኔሁ ወአልቦ ጕልቍ ለመዋእሊሁ ወአልቦ ሐሳብ ለዓመታቲሁ ወአልቦ ጽልመት ለብርሃነ ገጹ። ዘጸ.3፣3-10 ልዑል እግዚአብሔር ለሙሴ በዕፀ ጳጦስ ሆኖ ተገልጦለት እኔ የአባቶቻችሁ የአብርሀም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ብሎ ካነጋገረው በኋላ አሁንም ናና ወደ ፈርዓን እልክሀለሁ አለው። እንግዲህ በእግዚአብሔር ለሙሴ ራሱን ሲያስተዋውቀው ስሙን ገልጾለት ነበር። ሙሴ ግን ዝቅ ብሎ ማን ነው ቢሉኝ ምን እላቸዋለሁ ብሎታል። በቅዳሴ አትናቴዎስ ወእምህየ ኢንክል ኀሊፈ እስመ ቦ ህየ ባሕረ እሳት ዘኢያበውሆ ለሕሊናነ ይዕዱ ይላል። ቅዱስ ኤፍሬም ናርምም እስመ ኢንክል ፈጽሞ ጥንቁቀ ነገረ በእንተ ዕበዩ። ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ አንተ ለሊከ ተአምር ህላዌከ ወአንተ ለሊከ ትጤይቅ መለኮተከ ብሎ ቀጥሎ ክዱን ብከ ዕበይከ ወሥውር ብከ ኃይልከ ለሊከ ብከ አንጦላእከ ኪያከ ወአንተ ብከ ለሊከ ተከደንከ። አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅም እስመ እንዘ ይትኀሳዕ በርእሱ ይትኀሳዕ ወእንዘይትከሠት በርእሱ ይትከሠት ሲሠወር በራሱ ይሰወራል ሲገለጥም በራሱ ይገለጣል ሲሉ ተናግረዋል። ነፍስ የረቀቀች የማትታይ በአምስት ሕዋሳት የማትዳሰስ የማትገሠሥ የማትጨበጥ ህላዌ ናት። ማንኛውም ነገር ባይታይንኳ ቅሉ መኖሩ ከታወቀ ስም ይሰጠዋል። ነፍስ ምንም ብትረቅ በሰው ውስጥ መገኘቷ እርግጠኛ ሆኖ ይታወቃል። ሊቁ አውሳብዮስ በመቅድመ ወንጌል ገጽ 25 ስለ ነፍስ ሲናገር ሥዕልት ዘእንበለ ገቢር ግብር እምግብር ሆና ያልተፈጠረች ወይም ከተለያዩ ንጥረ ባሕርያት ያልተፈጠረች ናት ብሏል። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም በመጽሐፈ አርጋኖን እስመ ክልኤቱ ነፍሳት ሀለዋ ውስተ ሰብእ ወአሐቲ መንፈሰ ሕይወት ዘወጽአት እም አፉሁ ለእግዚአብሔር ወኢትትኄለቍ ምስለ ጠባይዕ ወኢትመውት። ወአሐቲ ደመ ነፍስት ይእቲ እም ጠባይዕ ወይእቲሰ መዋቲት ይላል። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ማለት ሰው በዓለመ ግዘፍ በሚገኙት በአምስት ሕዋሳቱና በረዳት መሣሪያዎቹ ሊያስሰውና ሊዳስሰው ሊገሠው የማይችል ረቂቅ ህላዌ መሆኑን ያሳያል። ማቴ.5፣8 ልበ ንጹሖች እግዚአብሔርን ያዩታል። ሰው የራሱን መንፈስ ወይም ነፍስ በእውነት መመርመርና እንደምን እንዳለች አጥርቶ ማወቅ የግብሩ ተቀዳሚ አድርጎ እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮ እውስጡ ባኖረለት በመንፈሱ መነጸርነት የማይወሰንና የማይታይ ረቂቅ መንፈስ የሆነውን

እግዚአብሔርን ሊያይ መዘጋጀት አለበት፡፡ ሃይ.አበ. ዘጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት “ወንሕነሰ ነአምር ጥዩቀ ከመ ነፍስ ተንድር ውስቴትነ ከዊና አሐደ ምስለ ሥጋ ወመኑ ውእቱ ዘርእየ ነፍሶ ግሙራ ወመኑ ዘንሠሣ ወነጸራ በዓይነ ሥጋ ለነፍስ እንዘ ትትዋሐድ ምስለ ሥጋ፡፡ ወሶበ ንቤ ዘንተ ኢይምሰልክሙ ዘንክህድ ሀልወተ ነፍስ በሥጋ ይላል፡፡ ከ159-179 ዓ.ም የነበረ የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ቴዎፍሎስ አንዱን አረማዊ አምላኬን ላሳይህ ከፈለግህ ነፍስህን አሳየኝ ብሎታል፡፡ አምላክ በዓይን የሚታይ በዳሰሳም የሚታወቅ ሳይሆን በፈጠረው በፍጥረቱ ይታያል ይታወቃል፡፡ ነፍስ እንዳለችህ ታውቃለህ ታምናለህም፡፡ ይህን መቼም አትክድም ይሁን እንጂ በሥጋ ዓይንህ አታያትም በሥጋም እጅ አትዳብሳትም፡፡ ታዲያ በዓይነ ሥጋ ስላላየሀትና ስላልዳበስካት ነፍስ የለችኝም ብለህ አትክዳትም፡፡

እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርዓያነ ሲል ሰው እግዚአብሔርን በምን ይመስለዋል ቢሉ፡-

- በኩነት መመሳሰል፡፡ ይኸውም በለባዊነት በነባቢነት በሕያውነት መመሳሰል ነው፡፡ ይህ ኩነት ባልተፈጠረ ዘለዓለማዊ በሆነ በእግዚአብሔር እንዳለ ሁሉ በተፈጠረ በሰው መንፈስም እንዲገኝ ተደርጓል፡፡
- በጽድቅ በቅድስና መመሳሰል፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ የሰው መንፈስም በጽድቅና በቅድስና እንዲኖር በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ታስቦ ተፈጥሯል፡፡
- በእውቀት በክሂል በሥልጣን መመሳሰል፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ እውቀትና ክሂል ሥልጣንና ማመዛዘን ወዘተ እንዳለ ሁሉ በሰውም መንፈስ ውስጥ ክፉንና ደግን ጽድቅና ኃጢአትን እውነትንና ውሸትን ቅድስናንና ርኩሰትን ለይቶ ማወቅ ይህንም ለይቶ እንደማወቁ መጠን ተገቢውን የመምረጥና የመፈጸም ሥልጣንና ክሂል አመዛዝኖ የመፍረድም ክሂል እንዲኖርበት ተፈጥሮበታል፡፡በዚህም ምክንያት ይመስለዋል ተባለ፡፡

ምክንያት

ሰው ማንኛውም ነባቢ ፍጡር እንበል ከራሱ ጀምሮ የማንኛውም ፍጥረት መነሻና ምክንያት እየመረመረ በጥናትና በሐተታም እያጣራ ዘላለማዊና ያልተፈጠረ ህያው በህላዌ እስከ ማወቅ ድረስ ሊሄድ ይችላል፡፡ እስመ አልቦ ውስተ አመክንዮ ለእግዚአብሔር ለህላዌው ምክንያት የለበትም፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ለእግዚአብሔር ባሕርይ መነሻ ወይም ምክንያት የሌለው መሆኑን ሳይደብቁ ያረጋግጣሉ፡፡ ሮሜ.11፣33-36 ወአልቦ አሠር ለፍኖቱ ብሏል፡፡ ክብሩም ሆነ ግብሩ የባሕርይ ጌትነቱን ወይም ጌትነቱን ወይም በጎነቱን ሲገልጽ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ ጌትነቱ በጎነቱ በአጠቃላይ እግዚእናው ማለት መለኮቱ ምክንያታዊና አኂኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ፍጥረትን ለመፍጠርም ሆነ ፈጥሮ ለመግዛት ፈጥሮ ለመጠበቅ በፍትሕና በርትዕ ለማስተዳደር ለመስጠት ለመንሳት የተስፋ ቃልን ለመስጠት የሰጠውንም ተስፋ ሥራ ላይ ለማዋል የባሕርዩ ግብር ለፍጥረቱ ምክንያትና አኂኝ ነው፡፡ ምክንያታዊ ወይም አኂኝ ግብረ ባሕርይ ስንል ለማናቸውም ባሕርያትና ህላዌያት ለማናቸውም ሁናቴዎችና ግብራት በጠቅላላው የሚታዩም የማይታዩም ሆነው ረቂቅም ግዙፍም ሆነው በሕሉና አሉ ወይም ይኖራሉ ለሚባሉ ሁሉ ምክንያትና ጥንት መነሻ ይኸው ግብረ ባሕርይ መሆኑን በምንመለከትበት ጊዜ የምንናገርበት የተመርሆ ኀሠሣ ብሂላዊ ትምህርት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ

የጌታን ባሕርያዊ ግብር ምክንያታዊ መሆኑን ያስረዳል ይኸውም ሁሉ ከእርሱ ሁሉ በእርሱ ሁሉ የእርሱ መሆኑንና መፈጠሩን ያለእርሱ ግን የሆነ የተፈጠረ ነገር የሌለና የማይኖር መሆኑን ቅሬታ በማያስከትል ገለጻ ተናግሯል። ሮሜ.11፣36፤1ኛ ዮሐ.1፣1-3። ይህ አባባል ለማናቸውም ባሕርያትና ህላዌያት ለማናቸውም አካላትና ግብራት ለማናቸውም ሁኔታዎችና አቋሞች መገኘት ምክንያት መነሻ የእርሱ ግብረ ባሕርይ የግብረ ጠባይዕ ብቻ ሆኖ መገኘቱን የሚገልጽ ነው። ይህ የእርሱ ግብረ ባሕርይ (ጠባይዕ) ለተጠቀሱት ፍጥረታት ሁሉ ምክንያት ወይም መነሻ በመሆን ብቻ የተወሰነ እንዳይደለ ይታያል። አምላካዊ ክሂል የባሕርዩ ግብር ምክንያታዊነት ወይም አኂኝነት መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ከዚህ የግብረ ባሕርዩ ክሂል የተነሳ ከሀሌ ኩሉ አኃዜ ኩሉ ጸባጤ ኩሉ መዋኢ ጠቢብ መካር አዋቂ ኃያል ይባላል። አምላካዊ ሥልጣን የጌትነቱ ክብር የባሕርዩ ግብር ምክንያታዊነት ወይም አኂኝነት ነው። እንደምን ነው ቢሉ በሰማይና በምድር በማናቸውም ቦታ ሁሉ የሚገኙ ፍጥረታት በእርሱ እዘዝ ሠራዒነትና መጋቢነት አስተዳዳሪነት አገዛዝ እንደሚገኙ የታወቀ ነው። መዝ.118፣90-9 ሣረርካ ለምድር ወትነብር ወበትዕዛዝከ ይቀውም ዕለት እስመ ኩሎ ቀነይከ።

ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሳሌ

ምስጢረ ሥላሴ የዚያ የማይታይና የማይመረመር የማይወሰን ምሳሌ የሌለው የአእምሮ ሁሉ አእምሮ የሆነ የእግዚአብሔር ነገር የሚነገርበት ነው። **ምሳሌ** በአምላካዊ ቃሉ ራዕይ መሰረት ላይ ያለውን መንፈሳዊ መገለጥ ለመጨበጥ ያስችል ዘንድ ከላይ የተፈቀደ የመወጣጫ መሰላል ነው። እግዚአብሔር ሕያውና ዘላለማዊ የማይታይና ረቂቅ ህላዌ የማይወሰንና ምሉዕ ፍጹም ከፍጡራንም ልዩ ባሕርይ ያለው መሆኑን በአንድ ወገን ሲታይ በሌላ ወገን ደግሞ ሰው ፍጡርና ግዙፍ በአእምሮም ሆነ በአካል አቋሙ የተወሰነ ድሀና ደካማ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። እንግዲህ ሰው በዚህ አቋሙ የተወሰነ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ በመለኮታዊ ባሕርዩ የሚኖረውን ዘለዓለማዊና ሕያው የሆነውን አምላክ ለማወቅና መርምሮ ለማግኘት የማይገፋ የማይሞከር ኃይለኛ ማዕበል ጥልቀቱና ምጥቀቱ የማይደረስበት ጨለማ ይሆንበታል። ይህ ሁኔታ በሰው በኩል ያለ ሲሆን ለእግዚአብሔር ግን የሚሳነው ነገር ስለሌለ በጸጋው በፍቅሩ ለጋሥነቱ የገዛ ራሱን ለመግለጥ ፈልጎ በብዙ ዓይነትና በልዩ ልዩ ጎዳና ለሰው ልጆች ተገለጠ ዕብ.1፣1፣ ዘኍ.12፣6። በእግዚአብሔር ጸጋ ለተሰጠ ሕገ ምሳሌ መጠኑና መለኪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። ሳዊሮስ ዘእስሙናይን "ወእዌጥን እምቅድመ ኩሉ ግብር ወእቤ ከመ እግዚአብሔር አልቦቱ ምሳሌ ወኢምንትኒ ወኢያስተማስልዎ በኢምንትኒ አላ አልባቢነሰ ድኩማት ወያጽሕቃነ ለምሳሌ ወመክፈልት። ናስተማስሎ ቦሙ ከመ ናእምሮ በከመ ገብረ ውእቱ ዝክተ ለርእሱ ሶበ አስተማሰለ ርእሶ ለነ በአምሳል ብዙኃት ከመ ያጠይቀነ አእምሮቶ ውስተ አልባቢነ ድኩማት። ወአስተርአዮ ለሙሴ በጎበ እፀ ጳጦስ በአምሳለ እሳት። እላ አምሳላት ዘአስተማሰለ እግዚአብሔር ርእሶ ቦሙ ከመ ያጠይቀነ አእምሮቶ ውስተ አልባቢነ ድኩማት። አላ ውእቱ ይትሌዓል ላእለ ኩሉ ግብር ወአምሳል ወምሳሌ ወአእምሮ። ወለእመጠየቅነ ከመ ውእቱ ሰመየ ርእሶ ብርሃነ ወአስተርአየ በአምሳለ ብርሃን ይደልወነ ከመ ናስተማስሎ በብርሃን ከመ ይብጻሕ አእምሮቱ ውስተ አልባቢነ ድኩማት። ይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በከመ አምሳሊነ ወበአርአያነ። ወበዝ አጠየቀነ ከመሰብእ አምሳለ ሥሉስ ቅዱስ

እስመቦቱ ሠለስቱ ህላዌ እስመ መንፈሱ ለሰብእ ሠለስቱ ልብ ወነቢብ ወሕይወት፡፡ልብሰ ይወልድ ነቢበ፡፡ ለነቢብ ወለልብ ሕይወቶሙ መንፈስ፡፡ የትምህርተ መለኮት ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጊዜያቸውን ሁሉ መሠዋታቸው ማንበብን ብቻ ሳይሆን ጌታ ከመጻሕፍት ውስጥ ያለውን መርምሩ ብሎ በተናገረው መሰረት መጻሕፍትን ጠልቀው በመመርመር የቃሉን ውስጣዊ ጠባይና አባባል ለመረዳት መፈለጋቸው ነው፡፡ብሔራውያን ሊቃውንት በአምላክነቱ ምንታዌ በሦስትነቱ ርባኤ የለበትምና ብለዋል፡፡ የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት የገለጠው ራሱ እግዚአብሐየር ነው፡፡ ዘፍ.1፣ 27 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ሲል ተናግሯል፡፡ ዘፍ. 3፣22 እግዚአብሔር አምላክም እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ፡፡ ዘፍ.11፣1-7 እግዚአብሔርም ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን እንደባልቀው አለ፡፡ ኢሳ.6፣8 የጌታን ድምጽ ማንን እልካለሁ ማንስ ይሄድልናል ሲል ሰማሁ ብሎ ኢሳይያስ ጽፏል፡፡ እነሆ በእነዚህ ጥቅሶች አንድ ነጠላ ቁጥር በብዛት እንዲሁም የብዛት ቁጥር በነጠላ እየሆነ መነገሩን እናስተውላለን፡፡ ቅድስት ሥላሴ ማለት የተቀደሰች ሦስትነት ማለት ሲሆን ቅድስት ሲባል ጽንዕት ንጽሕት ክብርት ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ልዩ ሦስት ወይም ልዩ ሦስትነት ማለት ሦስት ሦስት እየሆኑ ከሚነገሩ ብዙ ነገሮች ይልቅ ፈጽሞ ልዩ የሆነ ሦስትነት ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልዩ ሦስት ሲባል በሦስትነትና በአንድነት የሚገኙ ልዩ ምሳሌዎች አሉና ከዚያ ለይቶ ለማስገንዘብ ነው፡፡ ከእነዚህም አንዳንዶቹ የአካል ሦስትነት ቢኖራቸው የባሕርይ የህልውና አንድነት የላቸውም ለምሳሌ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ብለን የምንጠራቸው ሦስት ስሞች ናቸው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በአንድ የአካል ስም ሲጠሩ በኩነታት ሦስትነት ያላቸው አሉ፡፡ እነርሱም ፀሐይ እሳት ቀላይ ባሕር ተክልና ነፋስ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለእሳት ለፀሐይ ለባሕር የግብር ሦስትነት ቢኖራቸው የአካል ሦስትነት የባሕርይ የህልውና አንድነት የላቸውም፡፡ ልዩ ሦስት የሚሆኑ ሥላሴ ግን በየአካላቸው ጸንተው ሳለ በአብ ልብነት በወልድ ቃልነት በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ተገናዝበው በህላዌ መለኮት ይዋሐዳሉ፡፡ በአንድ ህልውናም ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ፡፡ ሊቃውንት ለኩነታት ምሳሌ ለማድረግ ከመጽሐፍ ቅዱስ በፀሐይ ለመመሰል መዝ.18፣15፣ዕብ.10፣11 ላይ በውስተ ፀሐይ ሤመ ጽላሎቶ ይላልና ነው፡፡ በእሳት ለመመሰል ዕብ.12፣29፣ ዘዳ.4፣24 እስመ አምላክነ እሳት በላዒ ይላል፡፡ በውሃ ለመመሰል መዝ.76፣19 ወአሠርከኒ ውስተ ማይ ብዙኅ ይላል፡፡ መቼም ቢሆን ሄዶ ሄዶ የምሳሌ ጥቅሙ ለትምህርት ተፈላጊ የሆነውን ዓይነተኛውን ነገር ለመግለጽ ማስቻሉ ነው፡፡ ቅኔም በልዩ ልዩ ጎዳና መደንገጉ ለዚሁ ቁምነገር እንዲጠቅም ነው፡፡

አስማተ ሥላሴ

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማቴ.28፣19፣ ማቴ.3፣17፡፡ ልብ ቃል እስትንፋስ መዝ.32፣6-11፤ ዮሐ.1፣1-30፡፡ ወላዲ አሥራጺ ተወላዲ ሠራጺ መዝ.2፣7 መዝ.109፣3፡፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተባሉ የአካላት ስሞች በአካላት ስምነታቸው ጸንተው ይገኛሉ፡፡ ልብ ቃል እስትንፋስ የተባሉ የኩነታት ስሞችም በኩነት ስሞቻቸው ጸንተው ይገኛሉ፡፡ ወላዲ አሥራጺ ተወላዲ ሠራጺ በመባል የሚጠሩ የአካላት ግብራት ስሞችም በአካላት ግብራት ስሞቻቸው ጸንተው ይገኛሉ፡፡ ስሞች ወሳኝ የሆነ ትምህርታዊ ምስጢር ቋጥረዋል፡፡ ሃይ.አበ ዘጎርጎርዮስ ገባሬ

መንክራት ክፍል 1 ቁጥር 2-6 አእምር ኩሎ ግብረ እም ሠለስቱ ግብራት ዘውእቶሙ አስማት ወውእቱ ፍጥረት ወስም ወዘመድ ዘይትበሀል ሰብእ ወገብር ወመጋቢ። ሰብእሰ በእንተ ፍጥረተ ጠባይዕሁ ወገብርኒ በእንተ ግብርናቲሁ ወመጋቢኒ በእንተ ስም ዘተሰምየ። ወናሁ ንቤ በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወአኮ እሉ አስማት ዘቦኡ ላእሌሆሙ ድኅረ አላ እሙንቱ አካላት ወብሂለ ሰብእሂ አኮ ውእቱ ስም ዳዕሙ ውእቱ ፍጥረቱ እስመ ለኩሎሙ ሰብእ ቦሙ አሐዱ ስም ለለአሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ እሉ እሙንቱ አዳም አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ። ወአቃኒመ እግዚአብሔርሰ እሙንቱ አስማት ወአስማትኒ እሙንቱ አቃኒም እስመ ትርጓሜሁ ለአቃኒም አካላት ጽኑዓን ወቀዋምያን ፍጹማነ ገጽ ወመልክእ ብሂል ወሥሉስ ቅዱስ ይሰመዩ እሎንተ አስማተ ጽኑዓነ። አምላክ መዝ.17፣31። መለኮት ሮሜ.1፣20-22። እግዚአብሔር ኤልሻዳይ ዘፍ.17። እግዚአብሔር እግዚእ ይሆዋሕ ዘጸ.6፣3-8። አዶናይ ሕዝ.7፣2-5። እግዚእ ጸባኦት ኢሳ.6፣3። ኤሎሄ ኤሎሂም ማቴ.27፣46። መለኮት ጥንታዊና መሰረታዊ ስሙ ሊታወቅና ሊነገር ለማይችል ባሕርይ መጠሪያ ሊሆን የሚነገር የልዑል እግዚአብሔር ስም ነው። ሰለዚህ መለኮት የሚል ስም እንዲህ ነው ይህ ነው ይህን ይመስላል ተብሎ በማይነገርና በማይታወቅ ጠባይዑ የሚጠራበት የልዑል እግዚአብሔር ስም ነው። ከልዑል እግዚአብሔር ውጭ ማንም ሊጠራበት አይችልም። አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው ወመለኮትሰ ኢይትከሀል ይትበሀል ዘንተ የአክል ወዘንተ ይመስል። አላ ንቡር ዲበ አርያሙ ኀበ ኢይበጽሖ ሕሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ። ዳግም በግብረ ባሕርይ ስም ይጠራል።2ኛ ጴጥ.1፣3 ውስተ ኩሉ በሐውርት መለኮቱ ይላል። መለኮት በምሥጢረ ሥላሴ ሲነገር አንድነቱን ጠብቆ ሦስት አካላትን ያዋሕዳል ይሜለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት እንዲል። የእግዚአብሔር አብዛኛ ስሙ በግብሩ የሚጠራበት ነው። በባሕርይ ግብር ወይም በግብሩ መጠራቱ ስለፈጠረ ፈጣሪ ስለተመለከ አምላክ ሕያው ስለሚያደርግ ስለሚያድን ማኅየዊ ስለሚያስተዳድር ስለሚመግብ ሠራዒ መጋቢ ስለሚረዳ ረድኤት መጠጊያ ስለሚሆን ጸወን ምስካይ ስለሚታደግ ስለሚመክት ኃይል ጋሻ ይባላል። የባሕርየ እግዚአብሔር መጠሪያ የሚሆን ስም አይገኝም ይሁን እንጂ ሐዋርያው ዕብ.13 ላይ ባሕርየ እግዚአብሔርን የሚገልጥ ስምን ባላገኘ ጊዜ ባሕርየ እግዚአብሔርን ሊያወሳ በፈቀደበት ስፍራ በዝምታ አላለፈውም ክብርና ታላቅነት በሚባሉ ስሞች ገለጠው እንጂ። ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን 2 ወፍጹመ ኢይትከሀል ይርከቡ ስሞ ለዝኩ ባሕርይ። ኤልሻዳይ ማለት ሁሉን የሚይዝ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ማለት ነው ይህ ኤልሻዳይ የተባለበት ስም በስመ ህላዌያት ሲመጠን የገቢር አቋም የሚገለጽበት የባሕርይ ግብር ስም መሆኑን እንጂ የባሕርይን ስም የሚተረጉም አልሆነም። በሰዋስው ዘይቤ እግዚእ ማለት ጌታ ማለት ነው። ይህም መላኪ ተብሎ በግዕዝ ከሚነገር ቃል ጋር አንድ ዓይነት ተዘምዶ እንዳለው ይገልጻል። ስለዚህ እግዚእና ጌትነት ነው። አምላክ በሚለው ቃል ፍጡራንም ሲጠሩበት ተገኝተዋል መለኮት ግን ለፈጣሪ ብቻ መጠሪያ ነው። 1ኛ ቆሮ.8፡4፤12፣5 ወአልቦ አምላክ ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር ይላል ሙሴን ደግሞ ረሰይኩከ አምላኮ ለፈርዖን ብሎታል ከዚህ አልቦ ማለቱ በባሕርይ ነው የሙሴ የጸጋ ነውና። ሮሜ.1፣20 ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም ሲል በዚህ መለኮት የሚለውን ስም የግብረ ባሕርይ መጠሪያ እንዳደረገው እናያለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈው መልእክቱ ዘውእቱ ጸዳለ ስብሐቲሁ ወአምሳለ አርአያሁ ወነበረ በየማነ ዕበዩ በሰማያት ይላል። ይህንን ዮሐንስ አፈወርቅ ሲተረጉመው እስመ

ሶበ ኢረክበ ስመ ዘይኤምር ኀበ ባሕርይሁ ብህለ በዝንቱ አስማት እስመ ዕበይ ወስብሐት ኢይኤምሩ ኀበ ውእቱ ስም ዘፈቀደ ይዝክሮ ወባሕቱ ስእነ ረኪቦቶ። መለኮት የሚለው ስም ከመሠረቱ ለእግዚአብሐየር ግብረ ባሕርይ መጠሪያ ነው። በዚሁ እንዳለ ደግሞ መለኮት ስሙ ለማይታወቅ ለባሕርየ እግዚአብሐየር መጠሪያ ሆኖ ሲነገር እናገኛለን። መለኮት የእግዚአብሔር ሕይወተ ባሕርይ ተብሎ በሚነገርበት አቋም ይጠራበታል። ይህንንም የሚያስረዳ ሮሜ.1፣20፤21፣23 ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም ብሎ ካብራራ በኋላ አሕዛብ መለኮታዊውን ዕውቀት በሚጠፋ ነገር ስለለወጡ እስመ ወለጡ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ዘኢይመውት ብሎ ከላይ መለኮት ያለውን ከዚህ የማይሞት የማይጠፋ የእግዚአብሔር ክብር ብሎት ይገኛል። ዳዊትም መዝ.35፣9 እስመ ኀበኬከ ነቅዐ ሕይወት ብሏል። የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ ፊላታዎስም እስመ መለኮትሰ ዐቢይ ወክቡር ውእቱ ወኢይክል ላእሌሁ ሞት ብሏል። ባስልዮስ ዘአንጾኪያም ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 18 ወህላዌ መለኮትሰ ጽኑዕ ውእቱ ወኢይትገመር ወኢይረክቦ ውላጤ ወኢሚጠት ብላል። አግናጥዮስ ዘአንጾኪያም ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 13 ኢተአምርኑ ከመ ለእመ ትቤ መለኮት ሞተ አንተ ትከውን ቀታሊሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ እስመ ባሕርየ ሥላሴ አሐዱ ውእቱ ዘውእቱ ውእቱ አሐዱ መለኮት።መለኮት እግዚአብሔር ብርሃን ተብሎ ለሚጠራበት መጠሪያ ሆኖ ይነገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብርሃን ተብሎ ተነግሯል። አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ክፍል 1 ቁጥር 8 ላይ እጐዛን እሙንቱ በጽምረተ አሐዱ መለኮት ዘውእቱ አሐዱ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ብሏል።መለኮት ማለትና እግዚአብሔር ማለት አንድ ሲሆን ልዩነት አለበት መለኮት ማለት እንዲህ ነው ተብሎ በማይነገርና በማይታወቅ ጠባይዕ የሚጠራበት ስም ነው። እግዚአብሔር ማለት ግን በባሕርየ ግብሩ የሚጠራበት የግብር ስም ነው። እግዚአብሔር ማለት ትርጉሙ በአንድነት በሦስትነት ፈጥሮ የሚገዛ ቅድመ ዓለም የነበረ ድኅረ ዓለም ያለ ፍጻሜ የሚኖር ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ ማቴ.28፣19 በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ባለው መሰረት እነሆ የሥላሴ አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሚሉ አስማት የራሳቸው የአካል ጽንዕ እና አቋም ተለይቶ መታወቁ እርግጥ ሆኗል። አብ በዘለዓለምነት ሲኖር በነበረ በአካል ስሙ አብ ይባላል። ወልድም በዘለዓለምነት ሲኖር በነበረ በአካል ስሙ ወልድ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም በዘለዓለምነት ሲኖር በነበረ በአካል ስሙ መንፈስ ቅዱስ ይባላል።ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ሃይ.አበ.ክፍል 1 ቁጥር 2-6 ወናሁ ንቤ ካእበ በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወአኮ እሉ አስማት ዘቦኡ ላእሌሆሙ ድኅረ አላ እሙንቱ አካላት ወአቃኒመ እግዚአብሔር እሙንቱ አስማት ወአስማትኒ እሙንቱ አቃኒም እስመ ትርጓሜሁ ለአቃኒም አካላት ጽኑዓን ወቀዋምያን ፍጹማነ ገጽ ወመልክእ ብሂል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ 2ኛ ቆሮ.13፣14 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን ሲል አስተማረ። ይህም የሦስቱን አካላት ስሞች ያረጋግጣል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚሉ መጠሪያ ስሞች የአካላተ ሥላሴ መጠሪያ አስማት መሆናቸው ሲታወቅ ልቡና ወይም ከዊነ ልቡና ቃልነት ወይም ከዊነ ቃል እስትንፋስ ወይም ከዊነ እስትንፋስ ተብለው ሲነገሩ ግን ለየአካላቱ የኩነታት አስማት ሆነው መነገራቸውን ይገልጻል። ቅኑመ ስሙ ወልድ ለተባለ አካል ስመ ኩነቱ ቃል ነው።

ባሕርይ፣ ግብረ ባሕርይ፣ መለኮት

ባሕርይ ከርጥበት ከሁከት ከስፍሐት በመኖሩ ርጥበቱ ሁከቱ ስፍሐቱ ለመለያየትና ተለያይተው ለመኖር አይቻላቸውም። ግብረ ባሕርይ ማለት የባሕርይ ሥራ የባሕርይ ፍሬ የባሕርይ ውጤት የባሕርይ ነጸብራቅ ማለትን የሚያሳይ ስያሜ ነው። ግብረ ባሕርይ ስለ ልዑል እግዚአብሔር በሚመለከት ረገድ ሲነገር እግዚአብሔር አምላክ መለኮት በጎ ፈቃድ ጽድቅ ዳኝነት ፍትሕ እውነት ፍቅር ቸርነት ምሕረት ጸጋ ምክር ጥበብ እውቀት ተኬንዎ ክሂል ኃይል ጽንዕ ማዳን መቤዠት ጠባቂነት መጋቢነት በአጠቃላይ ስነ መለኮት የሆኑት ሁሉ የባሕርዩን ግብር ያሳያሉ። የፍጥረታት ግብረ ባሕርይ ስም ከልዑል እግዚአብሔር በጎ ፈቃድ የተነሳ በቃሉ ለፍጥረታት መፈጠር መንስኤ ከሆነላቸው ከሚታዩና ከማይታዩ ከልዩ ልዩ የተፈጥሮ ባሕርያት ውጤት ወይም ነጸብራቅ ሆነው ከሚገኙ የባሕርዮቻቸው ግብራት የሚታወቅ ነው። ለምሳሌ ርቀት ግዘፍ ጠባይ ልማድ ድምጽ ብርሃን ነጸብራቅ ወይም ልማድ አመል ሁኔታ ድርጊት ስራ አቋም የመሳሰሉትም ሁሉ ግብረ ባሕርይ የባሕርይ ውጤት እየሆነ የባሕርይ ዓይነትን መሰረት ይገልጻል። ባሕርይ ህላዌ መለኮት ያልተፈጠረ የማይመረመር የማይታወቅ ጎቡዕ ረቂቅ ቅድስት ሥላሴን አንድ የሚያደርግ የፈጣሪ ባሕርይ አምላክነት ሲሉ አለቃ ደስታ በአማርኛ መዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው ገልጸውታል። የባሕርዩ ግብር ለፍጥረት ህሉና ጥንተ ምክንያት የመሆንና አኋኝ የመሆን ጠባይዕነትን የሚያስገነዝብ ክብር ወይም ምስጋና በሚል ቃል የተገለጸው የባሕርየ ሥንና የባሕርየ ዕበዩ የባሕርይ ባለጸግነትና የባሕርዩ ቅድስና የባሕርዩ ግርማና የባሕርዩ ልእልና የባሕርይ ብርሃንና የባሕርይ ኃይል የመለኮት ክሂል የሚያንጸባርቅበት የሚያስተጋባበት መታወቂያ ነው። ኤፌ.2፣6 ከመ ያርኢ ብዕለ ስብሐቲሁ የክብሩ የባሕርዩን ባለጸግነት ያሳይ ዘንድ ይላል። ሌሎች ምሳሌዎችም ኤፌ.1፣19-20፣ ዘፀ.24፣16-17፣ ሕዝ.1፣27 2ኛ ጴጥ.1፣3፣ ኢሳ.2፣19-21፣ ሮሜ.9፣22-23፣ መዝ.112፣5፣ መዝ.144፣5፣ ቆላስ.1፣27፣ መዝ.49፣2፣ መዝ.8፣1። የመለኮት የብርሃን ነጸብራቅነቱ የብርሃኑን ባሕርያዊ ሕሉና ይገልጻል። የሕይወትም ሕያውነቱ የሕይወት ባሕርያዊ ሕሉናን ይገልጻል። አምላካዊ ፈቃድ ወይም ሥምረት በለባዊነት በነባቢነት በእስትንፋስነት ተገናዝቦ በአንድ ህልውና ለሚኖር ልኡልና ምጡቅ ለሆነ ለምልዐተ ሕይወት ባሕርይ ጨረሩ ወይም ጠባይዑ ሆኖ የተገኘ ነው። ፈቃድ ወይም ሥምረት ቢባል የመፈለግ የመሻት ፍች ቢኖርበትም ዋናው ዘይቤው በባሕርይ ቅድስና መስማማት ሆኖ ይገኛል። መዝ.113፣11 በሰማይኒ ወበምድርኒ ኩሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር አምላካዊ ፍቅር አምላካዊ የሕይወት ባሕርየ ግብር ወይም ጠባይዕ ፍቅር ሆኖ ይገኛል። ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳን 3 ተፈጥሮተ ዓለም ያኤምር ጎበ አፍቅሮቱ ሰብአ ይላል። ከሊቃውንት አንዱ እስመ ቅኔትከ ወምልክናከ ይሬስየከ ትሣሀል ላእለ ኩሉ ብሏል። እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም ይላል። በጠቅላላው ለባሕርይ ግብራት ሁሉ አበጋዝ አድርገን በማቅረብ የተመራንባቸው ፈቃድ ክሂል ሥልጣን ሥራ ላይ ከመዋላቸው አስቀድሞ ማለት ምንም ነገር ሳይሆንና ዓለም ሳይፈጠር የአምላክነት የባሕርይ ግብር ሆነው በእያንዳንዱ ሥላሴያዊ አካልም ምዕዛረ ሕይወት ሆነው በሚያንጸባርቅ ሥን መኖራቸው ጉልህ አድርጎ አስገንዝቦናል። የባሕርይ ጠባይዕ የሚሆን ፈቃድ ክሂል ሥልጣን በሦስቱ አካላት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የሕይወተ ባሕርይ ወይም የሕላዌ መለኮት ግብር ሆኖ ዓለም

ከመፈጠሩ አስቀድሞ ሲያንጸባርቅ መኖሩ በቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ ሆኖ የተብራራ ነው። ስለዚህ የባሕርይ ጠባይዕ የሆነ ፈቃድ በሦስቱ አካላት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የሕይወተ ባሕርይ ህላዌ መለኮት ጠባይዕ ሆኖ ለዘለዓለም ሲያንጸባርቅ ይኖራልና ሁሉ አንድ ፈቃድ ብቻ ሆኖ ከመገኘቱ በቀር ተከፍሎ ወይም መለየት የሌለበት መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት የሚያሻ ነው። ዮሐ.5፣30፣ ዮሐ.6፣39-40፣ ማቴ.11፣ 26-27፣ ሮሜ.8፣27። ሃይ.አበ ሱኑትዩ ቁጥር 11 ዘይፈቅድ አብ ይፈቅድዎ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወለዘኒ ይፈቅዶ ወልድ ይፈቅድዎ አብ ወወልድ። ፈቃድ ክሂል ሥልጣን ከዓለም ፍጥረት አስቀድሞ የአምላክነት ባሕርይ ግብር ሆነው በእያንዳንዱ ትሥልሥታዊ ምዕዛረ ሕይወት ወይም አንጸባራቂ ሥን ሆነው መኖራቸውን ደግመን እናስታውሳለን። ፍጥረታት መፈጠር ከጀመሩ በኋላም ቢሆን ፈቃድ ክሂል ሥልጣን ምንጊዜም ግብር ላይ ውለው ከመገኘት የተቋረጠበት ወቅት የለም። ዮሐ.5፣17-20 አቡየሂ እስከ ይእዜ ይገብር ወአነሂ ከማሁ እገብር እንዳለ። ባሕርይ ምንም እንኳ በፍጡራን ረገድ የቀዋሚነት ህሉናውን ለሚያሳውቅ ነገር ሁሉ ምክንያት ወይም መሰረት ተደርጎ ቢነገር ባሕርየ እግዚአብሔርን በሚመለከት ግን እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ። ባሕርዩን የሚያስገኝ ምክንያት የሌለ ነውና። የባሕርይ ሕሉና በግብር ይታያል እንጂ ራሱ ባሕርዩ ምንጊዜም አይታይም። የወፎች ድምጽ የድንጋይ መቆርቆር የጽጌረዳ መዓዛ የእሬት ምሬት የወርቅ መብረቅረቅ ይህ ሁሉ እያንዳንዱ አካላዊ ነገር ከባሕርዩ ያለውን በግብሩ ሲገልጽ የሚገኝበት ሁኔታ ነው።ፀሐይ ወጣ ተብሎ ሲነገር በዚህ ጊዜ ፀሐይ ስንል ስለ ባሕርይ ስሙ ወይም ስለግብር ስሙ ሳይሆን ስለፀሐይ አካል መናገራችን እንደሆነ ግልጽ ነው። ሌላው ፀሐይ ጨለመ ተብሎ ይነገራል በዚህም ጊዜ ፀሐይ የሚለው ስም ስለአካል ወይም ስለ ባሕርይ ሳይሆን ስለግብር ስሙ ተነግሯል። ፀሔ እሞቃለሁ ወይም ፀሐይ አቃጠለኝ ተብሎ ሲነገር ደግሞ በዚህ ጊዜ ፀሐይ የሚል ስም የአካል ህላዌን የግብር ህላዌን ሳይመለከት በግብር አማካይነት የባሕርይ ህላዌን የግብር ህላዌን ሲያሳይ ተነግሯል። የሥላሴን ባሕርይና አካል እንደ ሰው ባሕርይ እና አካል በመመጠን አካል የሌለው ባሕርይ ባሕርይም የሌለው አካል የለምና የሥላሴ ባሕርይም አካልን ተከትሎ ከሦስት ይከፈላል ማለት ስህተት ነው። በመሰረቱ ባሕርይ ተብሎ በሚነገር ቃል መናገር ስንሻ ከዚህ በፊት እንደገለጽን በልዑል እግዚአብሔር በጎ ፈቃድና ሥምረት ካለመኖር ወደመኖር ለተፈጠሩ በዓለመ መንፈስና በዓለመ ግዘፍ ለሚኖሩ ፍጥረታት ወይም ምክንያቶች መነሻቸውና መሰረታቸው ሆኖ በተለይም ለአካላትና ለግብራት ለዓይነቶች ሁሉ የአቋማቸው ምንጭና መሰረት መገኛ መሆኑን የሚገልጽ የህሉናቸው መታወቂያ ነው። የልዑል እግዚአብሔር ባሕርይ ስንል ግን ከመፈጠርና ከተፈጥሮ ውጭ ነጻ እንደመሆኑ መጠን ምክንያትና መነሻ የሌለው የማይመረመር ዘላለማዊ ሆኖ ስለሚኖር ባሕርዩ ከፍጡራን ባሕርይ ፈጽሞ የተለየ ነው።

ህሉና፣ ህልውና

ህሉና የባሕርይ ወይም የአካል የግብር ወይም የኩነት የአኳኋን የጠባይዕ ወይም የምክንያት ክዋኔው ወይም ኂኝነቱ በአጠቃላይ ማንኛውም ኑሮና አኗኗሩ መኖሩ በታወቀ መጠን በእነዚህ በተጠቀሱት ነገሮች በሚገኝበት ሁኔታ የሚጠቀመበት አቋም ወይም የአቋም መጠሪያ ነው። ስለዚህ አለ ይኖራል ተብሎ መኖሩና አኗኗሩ የሚታወቅ ሁሉ በሁለገብነቱ ይጠራበታል።

በትምህርተ መለኮት ይዞታ ፍጹማንና ምሉዓን የሆኑ የሚመሳሰሉና የተካከሉ አካላት አንድ በአንድ ተዋሕደው ሲኖሩ ወይም ሁለቱ በአንዱ አንዱም በሁለቱ እየተገናዘቡ የሚኖሩበት አኗኗር በሌላም አገላለጽ አንዱ ለአንዱ ዚአሁ (ገንዘቡ) ሆኖ መኖሩ የህልዋንን ትምህርታዊ ምስጢር ያስገነዝባል። እንግዲህ ህልውና ሲባል የተዋሕዶተ መለኮት በአካላት ወይም በኩነታት የአካላትን ተገናዝበው መኖር የሚገለጽበት ምስጢራዊ ይዘት የሚንጸባረቅበት ስም ነው ዮሐ.14 9-10። ምንጊዜም ቢሆን መለኮት ስለአንድ ጽናት ወይም የአንድን የእግዚአብሔራዊነት ይዞታን በማጥበቅ ቢነገር እንጂ የመለየትና የመከፋፈል ወደ ብዙም የመሰነጣጠቅ የመበታተን ይዞታ ሆነ ትርጉም የሚያመለክት ፍች የለበትም። በሥለሴ አካላት አብ መለኮት ወልድ መለኮት መንፈስ ቅዱስ መለኮት እያሰኘ ሲነገር ቢገኝም እንኳ አንድ መለኮት በሦስቱ አካላት ሁሉ ራሱ መለኮት እየተከፋፈለና እየተሰነጣጠቀ ወይም እየተበታተነ መገኘቱንና በዚህም ሁኔታ ታይቶ እንዲታወቅ መደረጉን ማሳየቱ አይደለም። ነገር ግን በየአካላቸው ፍጹማንና ምሉዓነ ገጽ የሆኑ አካላተ ሥላሴ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በኩነታቸው እርስ በእርሳቸው እየተገናዘቡ በህልውና እየተዋሐዱ ያለመነሻና ያለፍጻሜ የሚኖሩበት አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር የሚሰኙበት መሆናቸውን ስለሚያስረዳ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ጌታችን በወንጌሉ አነ በአብ ወአብ ብየ ሲል በአብና በወልድ ያለው የህልውና አንድነትን በግልጽ አስታውቋል። ስለመንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ ህልውና ሲገለጽ የአብ መንፈስ ብሎታል። መንፈስ ቅዱስ በራሱ ስላለው ህልውናን ሲገልጽ መንፈስ ቅዱስ ከእኔ ይወስዳል። ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው። ስለዚህም ከእኔ ይወስዳል እላችኋለሁ በማለት በአጠቃላይ የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስ በህልውና መገናዘብ እንዴት እንደሆነ ገልጾአል። ዮሐ.14፣10-11፣ 16፣14-15። ከዚህም የተነሳ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በህልውና የመገናዘባቸውንና በአንድ መለኮት። የመዋሐዳቸውን ምሥጢር የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እየተነተኑ ገልጸዋል። አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 5 ላይ ነአምን በአብ ከመህልው በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመ ህልው በአብ ወበወልድ። ሦስቱ አካላት እርስ በእርሳቸው ህልዋን የሚዋሐዱበትና የሚኖሩበት በልብ በቃል በእስትንፋስ ኩነታት መሆኑን መረዳት ይገባል። አብ በወልድ ወልድ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ናቸው ስንልም በኩነታት መሆኑን እንረዳለን። ዮሐ.14፣19 ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ ባለውና አነ በአብ ወአብ ብየ ባለው ተመርተው የቤተክርስቲያን መምህራን መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸላቸው መጠን አምልተው አስፍተው ተናግረዋል።

አካል

በመንፈሳዊ በዓይነ ሕሊና በዓለመ ግዘፍ በሥጋዊ ዓይን የሚታይ መልክና ገጽ እንዳሉት ይታሰባል። በሥሉስ ቅዱስ የሚገኙ ሦስት አካላት በዓለመ መንፈስ ያሉ ናቸው። በዓለመ ግዘፍ የሚኖር አካል ሁሉ ግን በባሕርይና በግብር በመልክ በዓይነት በመጠን ህላዌውን ወይም ህሉናውን ያሳውቃል። እኔ ወይም እኔ ራሴ የሚል በክሂል በሥልጣን በፈቃድ ለባዊነት ነባቢነት ሕያውነት ያለው ፍጹመ አካል ባለግዕዛን መሆን እንዳለበት በግዕዝ የምሥጢረ ቴዎሎጊያ ሊቃውንት ዘንድ እንደሚታወጅ ይታወቃል። በሕይወት ብሉተ ህሉና ልዩ ነዋሪ የሆነ ሕላዌ መለኮቱ እያንዳንዱን አካል ሕያወ ባሕርይ ስለማሰኘቱ ሥላሴያዊ የሆነ እያንዳንዱ

አካል ሕያወ ባሕርይ ወይም መለኮታዊ ወይም አምላካዊ አካል ይሰኛል፡፡ ሃይ.አበ. አትናቴዎስ ክፍል 5 ቁጥር 3 እስመ አካላት መለኮታውያን እሙንቱ፡፡ አንዱ ሕይወተ ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት ለእያንዳንዱ ሥላሴያዊ አካል ሕይወቱ ወይም ባሕርየ መለኮቱ በመሆን እያንዳንዱን ሥላሴያዊ አካል ሕያወ ባሕርይ ወይም መለኮታዊ አካል ስለማስገኘቱ የሚገልጽ አብነታዊ ትምህርት ነው፡፡ ጴጥሮስ ዘምስር “እስመ ረኪበ ቀጢናት በቀጢናት ወረኪበ ገዚፋት በገዚፋት ቀጢን ውእቱ ነገረ መለኮት ወየኀሥሥ ኅሊና ቀጢነ” ረቂቁን ማግኘት በረቂቅ ግዙፉንም ማግኘት በግዙፍ መሆኑን ተረድተን ይልቁንም ነገረ መለኮት ረቂቅ ስለሆነ የተራቀቀ ሕሊና ቅጥነተ ሕሊና እንደሚያሻው በመገንዘብ ወደምንፈልገው ምሥጢራዊ ግብ መድረስ ይቻላል፡፡ በግዕዛችን አካል የመባል ስያሜን የሚገልጹ ሁለት መሠረታውያን አቋሞች አሉ፡፡ እነርሱም ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ተብለው ሲመደቡ የተነገሩ ናቸው፡፡ አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 11 “ዘበውሳጤሁ ይትጋብኣ ዓለማት ክልኤቱ ዓለመ መንፈስ ወዓለመ ሥጋ”፡፡ የዓለመ ግዘፍ አካል ማናቸውም በዓለመ ግዘፍ ያለ ነገር ሁሉ በዚህ አኗኗር እንዳለ ታውቆ አካል ተብሎ የሚጠራበት ስም አካል ነው፡፡ የዓለመ መንፈስ አካል ደግሞ አካል ተብሎ የሚጠራበት ስመ አካል ነው፡፡ በዓለመ ግዘፍ አካል በግዕዙ ጥሬ ሰዋስው አካል አኪል ተብሎ ይነገራል፡፡ በአማርኛ መብቃት አቅም ማደግ ዕድገት ማለት ነው፡፡ በአማርኛ አከለ በቃ ለአካለ መጠን ደረሰ ተብሎ ይፈታል፡፡ በዓለመ መንፈስ ላሉት በምጣኔ አቅም መገኘታቸውን የሚገልጽ ነው፡፡አካል ስለ እግዚአብሔር ሲነገር ግን አካል መወሰን መመጠን ለማያሳይ ፍች ኢየአክሎ አይበቃውም ተብሎ እንደሚነገር መታወቅ አለበት ቅዱስ ያሬድ በድጓ ዘስብከት ዘሰማየ ሰማያት ኢገምሮ ምድርኒ ኢየአክሎ፡፡ ስለ ዓለመ ግዘፍ ግን በጣም ልም ከሆነ ብናኝና በጣም ረቂቅ ከሆነ ትናኝ እጅግ በጣም ረቂቅ ከሆነ አየር ጀምሮ የመጨረሻ ጥጥርነትና ጉልህነት እስካለው ውፍረት ደንዳናነትም ድረስ በዚያ በሚገኝበት አቅምና ብቃት እንደየመጠኑ እንደየመልኩ ተወስኖ መኖሩ እንደሚታወቅ ሁሉ በዓለመ ግዘፍ አካል ተብሎ ይሰየማል፡፡ በሌላም አገላለጽ በሰማይና በምድር ያለው የሚዳሰስና የሚገሠሥ የሚቋጠርና በአምስት ሕዋሳቶቻችን ተደርሶበት የሚጨበጥ ነገር ሁሉ በዓለመ ግዘፍ አካልነት እንዳለ ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አካል በሚል ስያሜ መጠራትም ገንዘቡ ነው፡፡ ሌላ ይቅርና ረቂቁ ነፋስ ወይም አየር ሊታገድ እንደሚችል ትነትም ሊቋጠር እንደሚችል ልም ብናኝም ሊያዝ እንደሚችል ይታወቃልና ተወሳኝ በሆነ አቅሙና ብቃቱ ከዓለመ ግዘፍ ወገን መሆኑ ግልጽ ነውና ያው አካል ይባላል፡፡ ምክንያቱም አቅምንና ብቃትን ከማሳየት አይዘልምና ነው፡፡ በዓለመ ግዘፍ የሚገኝ ማናቸውም አካል ህሉናውን ወይም አቋሙን በሦስት ነገሮች ይገልጣል እነዚህም ባሕርይ፣ ግብረ ባሕርይ እና መልክ ወይም ዓይነት ናቸው፡፡ መልክ ወይም ዓይነት የአካል ግብር ናቸው፡፡ እነሆ በዓለመ ግዘፍ የሚኖር አካል ሁሉ ቢረቅና ቢደቅ ቢጎላም በእነዚህ ሦስት ነገሮች ቀዋሚነቱን ይገልጻል፡፡ ኪራኮስ ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 28 ኢይትረከብ ህላዌ ዘእንበለ አካል ወአካልሂ ዘእንበለ ህላዌ ኢ በውስተ ሰማይ በላእሉ ወኢ በውስተ ምድር በታሕቱ፡፡ ይህ ህግ በዓለመ መንፈስ ህሉና ለሚኖሩትም ይሆናል፡፡ መልክ ወይም ዓይነት አካል የሚገለጽበት አቋም ወይም ግብር ነው፡፡ ግብር መባሉም የአካልን መልክ ወይም ዓይነት በትርኢቱ ሁናቴ ስለሚገልጥ ነው፡፡ መልክ ወይም ዓይነት ሲባል ቁመት፣ ስፍሐት፣ ርዝመት፣ ድንዳኔ እና ስነሕብር ይታዩበታል፡፡ ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ ምዕራፍ 1 ቁጥር 28 “ኢይደሉ ይኩን ህላዌ ዘእንበለ አካል

ወአካልኒ ኢይደሉ ይትረከብ ዘእንበለ አምሳሉ ለአካል ዘውእቱ አርዓያሁ” ብሏል።ማንኛውም ብቃትና አቅም እንዳለው የሚታወቅ ነገር ሁሉ ቁመትና ስፍሐት ርዝመትና ስነሕብር እንዲሁም ድንዳኔ አለው። አካል ተብሎ ሊጠራ የሚገባው በግዘፍ ብቻ ላለና በአምስት ሕዋሳት ለሚታወቅ ነገር ብቻ የተወሰነ ሆኖ አናገኘውም አካል የሚል ስያሜ የሚሰጠው በዓለመ ግዘፍ አቋም ላለ ብቻ ሳይሆን በረቂቅነት ለሚገኝ መንፈስ ለሆነውም ሁሉ አካል የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ይገኛል። በዓለመ መንፈስ የሚኖር አካል እኔ የሚል ነባቢ ለባዊ አለሁ ባይ ነው። ይህም ራሱን ለቻለ ለራሱ ብቁ የሆነ እውቀት ቀዋሚነት ላለው አለሁ ባይ ቁመና በመሆን ብቻ የተሰጠ ስያሜ ነው። አካል ማለት መኖርን የሚያስገነዝብ አቋም ማለት ነው። ሳዊሮስ ዘእስመ·ናይን “ወሶበ ዘከርከ ሠለስተ አካላተ ኢትበል ከመ ቦሙ ሠለስቱ ሕይወትነ ወሠለስቱ ቃላት አላ አሐቲ ሕይወት ወአሐቲ ነቢብ”። የሰው ባሕርይ በአካል ቢከፈል በየራሱ ልብ በየራሱ ቃል በየራሱ እስትንፋስ ያለው ሆኖ በየራሱ ልዩ ልዩ ሥራ ይሰራል። የሥላሴ ግን አካላቸው የተለየ ሲሆን ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ነው። አንድ መሆኑን የሚያስረዳ የሦስቱ ልብ አንድ ሆኖ አንድ እውቀትን ያውቃሉ። የሦስቱ ቃል አንድ ወልድ ሆኖ አንድ ነገርን ይናገራሉ። የሦስቱ እስትንፋስ አንድ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ አንድ ሕይወትን ይኖራሉ። ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 8-9 ወለለአሐዱ አሐዱ እምአካላት ፍጹም በገጹ ወበመልክኡ አብኒ አብ ውእቱ ወልድኒ ወልድ ውእቱ መንፈስቅዱስኒ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ወለለአሐዱ አሐዱ እምአካላት ኢይትዌለጡ እምህላዌሆሙ አብሂ ለከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወልድሂ ለከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ መንፈስቅዱስሂ ለከዊነ አብ ወወልድ ብሏል። ሚናስ ዘእስክንድርያ ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 8 ወአካላትሰ እስመ አካለ አብ ካልዕ እምአካለ ወልድ ወእም አካለ መንፈስ ቅዱስ። እያንዳንዱ የሥላሴ አካል በየአካሉ ጸንቶ አብ ምንጊዜም አብ እንደሆነ ወልድም ምንጊዜም ወልድ ነው። የሥላሴ አካላት እያንዳንዳቸው መፍለስና መቀያየር ሳይኖርባቸው በየአቋማቸው በየስሞቻቸው ተለይተውና ታውቀው መገኘታቸውን የቤተ ክርስቲያን መምህራን በትምህርተ መለኮት ያረጋግጣሉ። ሰባልዮስ ሦስቱን የሥላሴን አካላት በአንዲት ነፍስ አካልና ለአንዲት የነፍስ አካል ጠባይዓኒ እንጂ አካላኒ ባልሆኑ በለባዊነት በነባቢነት በእስትንፋስነት በመመሰሉ ትልቅ ስህተት ተሳሳተ። በእርሱ አንጻር ደግሞ ያሻሻሉ መስሏቸው ሦስት ኩነታት ነፍስ ባሏቸው በሦስት የነፍሳት አካላት የሥላሴን ትሥልስተ አካላት ሊመስሉ የተነሱ እነ ዮሐንስ ተዓቃቢ የሚባሉ ወገኖች ተገኝተዋል። እነዚህም በዚሁ ጉዟቸው በሦስት አካላውያን ኩነታት ወይም ጠባይዓት አንድ ባሕርየ መለኮት የሚገናዘበውን ወይም በመገናዘብ ዘለዓለማዊ ሆኖ የሚኖረውን አካላተ ሥላሴን ወደዘጠኝ ጠባይዓት ወይም ኩነታት በማባዛት የተበተኑና የማይገናዘቡ ሦስት ልዩ ልዩ አማልክትን እስከ መፍጠር የደረሱ ናቸው። እኒህም ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩልህ ባለው ቃል ይረታሉ። አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ባለው ይረታሉ። ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 6-7 ወኢንሰግድ ለሠለስቱ አማልክት አላ ለአሐዱ አምላክ። ኪራኮስ ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 11 አኮ ከመዝ ሃይማኖትነ አላ ለነሰ ለርቱዓን አሐደ አምላክ ንሰብክ ወአሐደ ህላዌ ወአሐደ መለኮተ ወአሐደ ኃይለ ወኢንብል ከመ በዝየ ሱታፌ ለለአሐዱ አሐዱ አካላት በከመ ይቤ ዮሐንስ ተዓቃቢ ዘይትሜካህ በእበዱ ምስለ እለ ይብሉ ሠለስቱ ህላዌ ዘመለኮት። ሦስቱ አካላት “አቃኒመ እግዚአብሔር ጸንተው የሚኖሩ የእግዚአብሔር ስሞች

እንደመሆናቸው መጠን በዘላለማዊ ጽንዕ የሚኖሩ እንጂ የሚቀላቀሉ ወይም የሚለዋወጡ አይደሉም። ሦስቱ አካላት በአስማተ ኩነታት እርስ በእርሳቸው እየተገናዘቡ በአንድ ህልውና መገኘታቸው ደግሞ መዘንጋት የለበትም።

ከዊን፣ ክዋኔ፣ ኩነት፣ ኩነታት

ሁኔታ መሆን አኳኋን ማለት ነው። ከዊነ አብ ከዊነ ወልድ ከዊነ መንፈስ ቅዱስ ሲል አብ መሆን ወይም መባል ወልድ መሆን ወይም መባል መንፈስ ቅዱስ መሆን ወይም መባል እያሰኘ ሊነገር ይችላል። ምስጢሩም የሦስቱን አካላት አቋምና ስም ያለማፋለስ ለመጠበቅ እንዲያስችል ነው። ኩነታት መለየትና መከፈል ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ በአንድነት አካላትን በህልውና በአኗኗር እያገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩና ያሉ የሚኖሩ ናቸው። ወልድኒ ቃሎሙ ውእቱ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስሂ መንፈሶሙ ውእቱ ለአብ ወለወልድ ብለዋል። በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ አንድነትና ተዋሕዶ አንድ ብሉተ ሕሉና ሕይወት ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት ሆኖ ሲታወቅ ሳይከፈልና ሳይለይ በትሥልስተ አካላት ኩነታት ህልውና ዘላለማዊ በሆነ ጽንዕ እየኖረ ስለመሆኑ እሙን ትምህርት ነው። ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ. ቁጥር 2 ወንትአመን ከመ አሐዱ መለኮት ዘሠለስቱ አካላት። የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ እናምናለን። አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ.ክፍል 1 ቁጥር 13 እስመ ባሕርየ ሥላሴ አሐዱ ውእቱ ዘውእቱ አሐዱ መለኮት። በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ ተገናዝቦ አንድ ልዑለ ባሕርይ ሕይወት ወይም አንድ ብሉተ ሕሉና የሆነ ህላዌ መለኮት ሆኖ መታወቅ ሳይወሰን ያለመለየትና ያለመከፈል በትሥልስተ አካላት ህልውና ዘለዓለማዊ በሆነ ጽንዕ የሚኖር ነው። በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ የተገናዘበው በዘለዓለምነት ያለና የሚኖር ልኡለ ባሕርይ ሕይወት ወይም ህላዌ መለኮት ያለመለየት ያለመከፈል በትሥልስተ አካላት ኩነታዊ ህልውና በዘለዓለማዊ ጽንዕ ነዋሪ ሆኖ መገኘቱ ነው። እያንዳንዱ ሥላሴያዊ አካል ሕያው ስለመባሉ አብ ሕያው ባሕርይ ስለመሆኑ በወንጌል ዮሐ.5፣26፤6፣57 ለአብ ቦቱ ሕይወት ወይም ሕያው አብ ብሎ ወልድ እንደተናገረለት ጽፏል። ወልድ ሕያው ባሕርይ ስለ መሆኑም ዮሐ.1፣4 ወሕይወት ቦቱ ውእቱ ብሏል። መንፈስ ቅዱስ ህያው ባሕርይ ስለመሆኑ ሮሜ.8፣2 መንፈሰ ሕይወት ሲል ተናግሯል። ሃይ.አበ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ክፍል 2 ቁጥር 5 ንብል አብ ሕይወት ወልድ ሕይወት ወመንፈሰ ቅዱስ ሕይወት እንዘ አሐዱ ሕይወት። እነሆም በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ ተገናዝቦ አንድ የባሕርየ ሕይወት ሆኖ በመገኘቱ ወይም አንድ ህላዌ መለኮት ሆኖ በመታወቅ ሳይወሰን ያለመለየትና ያለመከፈል በትሥልስተ አካላት ኩነታዊ በዘለዓለማዊ ጽንዕ እየኖረ እያንዳንዱን ሥላሴያዊ አካል ሕያው ባሕርይ ወይም መለኮታዊ አካል ማሰኘቱ ሊገነዘቡት የሚገባ መሰረታዊ ትምህርት ነው። በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ የተገናዘበ አንድ ሕይወተ ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት እያንዳንዱን ሥላሴያዊ አካል ሕያው ባሕርይ ወይም መለኮታዊ አካል ባያሰኝ ኖሮ ሦስቱ አካላት በአንድ ሕይወተ ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት አይያዙም በህልውናም አይገኝም ነበርና። ሦስት አማልክት በተገኙ ነበር። ነገር ግን በኩነታት የተገናዘበው አንድ ሕይወተ ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት ባለመለየትና ባለመከፈል ሦስቱን አካላት ሕያዋነ ባሕርይ አሰኝቶ ወይም መለኮታውያን አሰኝቶ ልዩ በምትሆን በሦስትነት ጽንዕ የሚኖሩ ሦስቱ አካላት የሚዋሐዱበትን ምስጢር

በማስጨበጡ ነው። ይህ አንዱ ሕይወተ ባሕርይ ወይም ህላዌ መለኮት ለእያንዳንዱ ሥላሴያዊ አካል ሕይወቱ ወይም ባሕርየ መለኮቱ ሆኖ መለኮታዊ ከማሰኘቱ በቀር ከዚያ ውጭ እንደትርፍ ሆኖ አይገኝምና። ሃይ.አበ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ክፍል 4 ቁጥር 4 አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ አላ አሐዱ አምላክ አለ። ሦስቱ አካላት በአንዱ በአብ አካላዊ ልቡና ለባውያን ሆነው ይኖራሉ። በአንዱም በወልድ አካላዊ ቃል ነባብያን ሆነው ይኖራሉ። በአንዱም በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅ "አብሰ ልቡና ወአእምሮ በርእሱ ወልቡ ውእቱ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ወአልቦሙ ካልዕ ልቡና ዘእንበሌሁ ወልድኒ ቃል በርእሱ ለርእሱ ወቃል ውእቱ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ ወአልቦሙ ቃል ዘእንበሌሁ ወመንፈስ ቅዱስኒ ሕይወት በርእሱ ለርእሱ ወሕይወት ውእቱ ለአብ ወለወልድ ወአልቦሙ ካልእ ሕይወት ዘእንበሌሁ" ብሏል። ሳዊሮስ ዘእስሙናይን "አብሰ ይቀውም በርእሱ ወነባቢ በወልድ ወሕያው በመንፈስ ቅዱስ ወወልድ ይቀውም በአብ ነባቢ በርእሱ ወሕያው በመንፈሱ ወመንፈስ ቅዱስ ይቀውም በአብ ነባቢ በወልድ ወሕያው በርእሱ። ከዊን በአስማተ አካላት ከዊነ አብ ከዊነ ወልድ ከዊነ መንፈስ ቅዱስ እያሰኘ በአካላት በአካላት የግብር ስሞችም ከዊነ ወላዲ ወአሥራጺ ከዊነ ተወላዲ ከዊነ ሠራጺ እያሰኘ እያንዳንዱ አካል በግላዊ መጠሪያ ስሙና አቋሙ ተረጋግጦና ተለይቶ እንዲታወቅ ያስገነዝባል። 1ኛ ቆሮ.2፣11-13 መኑ ብእሲ ዘየአምር ዘውስተ ልበ ሰብእ ዘእንበለ መንፈሱ ለሰብእ ዘላእሌሁ። ከማሁኬ ለእግዚአብሔርኒ አልቦ ዘየአምር ሕሊናሁ ዘእንበለ መንፈሱ ለእግዚአብሔር። ነፍስ በአቋሟ የምትታወቅበትና የምትገለጥበት ነገር ቢኖር በኩነታቷ ነው። ሦስቱ የባሕርይዋ ኩነታት ልብ ቃል እስትንፋስ ሕያዊት አካል መሆኗን ይገልጻሉ። ምዕላድ ዘዐቃቤ ሰዓት ከብቱ "ቃልና እስትንፋስ የሌለበትና ለባዊ ያልሆነ ሁሉ ምንም ዓይነት ሥራ ሊሠራ አይችልም ነገር ግን በእርሱ ሌላ ይሠራበታል"። የፍጡር ሰው ነፍስ በህሉናዋ የፈጣሪን ህሉና አሚልታ መግለጽ ትችላለች አንልም ይሁን እንጂ በምሳሌነቷ የመሰላል ያህል ወደ እምነት ለማሸጋገር የሚረዳ ትምህርት ትሰጣለች። ባስልዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 19 "ወአርዓያሰ ባሕቱ ኢኮነ ተውላጠ ህላዌ አላ ትእምርቱ ያበጽሕ ኀበመስፈርተ ጽድቅ" ብሏል። የነፍስ አስማተ ጠባይዓት ከሥላሴ አስማተ ኩነታት በስመ መኩሸ ይመሳሰላሉ። ሃይ.አበ ቴዎዶጦስ ዘእንቆራ ቁጥር 19 ወህየንተ ልብ ዘዝየ ነአምሮ ለአብ ህየ ወህየንተ ቃል ዘዝየ ነአምሮ ለቃለ እግዚአብሔር። የሥሉስ ቅዱስ ሦስት አካላት በየኩነታቸው እርስ በእርሳቸው ሲገናዘቡ ነፍስ ግን አንዲት አካል ከመሆኗ የተነሳ ከዚህ ከአንዱ አካልነቷ በቀር በልብ በቃል በእስትንፋስ የምትገናዘበው ሌላ አካልም ሆነ የአካል ስም የሌላት ናትና በዚሁ ረገድ አትመሰልም። የነፍስ ጠባይዓት ልብ ቃል እስትንፋስ አንዲት በመሆን ስለምትታወቅ ስለአካልነቷ ሕይወት አቋም ብቻ ሲገልጹ የሥሉስ ቅዱስ ኩነታት ልብ ቃል እስትንፋስ ግን እርስ በእርሳቸው ተገናዝበው አንድ ሕይወተ ባሕርይን "የህላዌ መለኮትን" አቋም ይገልጻሉ። የሥላሴ አካላት ሦስት ሲሆኑ የነፍስ አካል ግን አንዲት መሆኗ ይህ የማይመሳሰሉበት ነው። ሰው ሞተ ሲባል ሕያዊት አካል የሆነች ነፍስ ህሉናዋን መኖሯን የምታስታውቅባቸውን ሁሉ እንደያዘች ከነበረችበት ሥጋ ተገላለች ማለት ነው። ከዊነ ልቡና ያለ ቃልና ያለ እስትንፋስ ከዊነ ቃልም ያለልብና ያለእስትንፋስ ከዊነእስትንፋስም ያለልብና ያለቃል የኖረበት ወይም የሚኖሩበት ጊዜ የለም። አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 22 "ወአልቦ ጊዜ አመ ነበረ እንበለ አእምሮ

ወሕይወት” ይላል። ነፍስ ክሂል ያላት ፍጽምት ሕይወት መሆኗ ሊረጋገጥ የተቻለው የአካሏን ምልዐተ ሕይወት ሊያሳዩ የቻሉ ባሕርያተ ነፍስ ማለት ከዊነ ልብ ከዊነ ቃል ከዊነ እስትንፋስ አንድ ላይ በአንድ ተረክቦ ከመገኘታቸው የተነሳ ነው። በመሰረቱ እያንዳንዱ ሥላሴያዊ ኩነት ሁሉ አንድ ላይ በመገኘት በአንድ ህብረታዊ መገናዘብ ክሂል ያለው የልዑለ ባሕርይ ሕይወት ያለምንም ሕጸጽ በምልዐት መታየቱን ያስገነዝበናል።ተጋብኦ በተከፍሎ ተከፍሎ በተጋብኦ። እነሆ በነገረ ነፍስ ልብ ቃል እስትንፋስ የሰው ነፍስ አስማተ ኩነታት በመሆን ልዩ ክሂልና ሥልጣን ፈቃድ ያላት አንዲት አካል መሆኗን ከማሳየት በቀር ኩነታቱ የየራስ ህሉናዊ ጠባይዕነት(መነሻን) ሲገልጹ አይታዩም። ወይም በሌላ አገላለጽ ብንናገር ሦስቱ ሁሉ የአንዲቱ ነፍስ የአካሏ ጠባይዓት ሆነው ይገኛሉ እንጂ እያንዳንዳቸው የሚታወቁበት በየስሙ ተለይቶ የሚጠራ ልዩ አካል እንዳላቸው አይገልጹም። የሥሉስ ቅዱስ አስማተ ኩነታት ግን ግሩምና ገናና የሆነ የሕይወተ ባሕርይን ፈቃድና ክሂል ሥልጣንም ምጡቅ በሆነ አምላካዊ ልእልና በማሳየት ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ የሦስቱ አካላት ኩነታት መታወቃቸውን ይገልጻሉ። የሦስት አካላት ኩነታት በመሆንም አንድ ባሕርየ ሕይወትን ለማሳየት እርስ በእርስ ይገናዘባሉ። ነፍስ በአካሏ አንዲት ስትሆን ኩነታተ ነፍስ የሚባሉት ነባቢነት ሕያውነት ለባዊነት የአንድ አካልነቷ ጠባይዓት ሆነው መገኘታቸው ነው። የሥላሴ ኩነታት “ጠባይዓት” የተባሉ ለባዊነት ነባቢነት ሕያውነት ግን ከመሠረቱ ከአንዱ ባሕርየ መለኮት የነበሩና ያሉ ናቸውና የሦስት አካላት ኩነታት “ጠባይዓት” መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው።ስለዚህም የአንድ አካል ኩነታት “ጠባይዓት” በመሆን አይገኙም። የሦስት አካላት ኩነታት “ጠባይዓት” ሆነው አለመገኘታቸውም ደግሞ እርስ በእርሳቸው አካላትን አገናዝበው የሥላሴ አንድ ባሕርየ መለኮትን ይገልጻሉ። ሊቀሊውንት ኃይለ መስቀል ገብረ መድኅን “ነገር ግን ነፍስ ልብ ቃል ሕይወት በመሆን የከዊን ሦስትነት ቢኖራ ነፍስ በአካል አንዲት ናት እንጂ ሦስት አካል የላትም። ሥላሴ ግን እንዲህ ሳይሆኑ አብ አካላዊ ልብ ነው በአካሉ ይታያል ወልድ አካላዊ ቃል ነው በአካሉ ይታያል መንፈስ ቅዱስም አካላዊ ሕይወት ነው በአካሉ ይታያል ስለዚህ ሥላሴ ሦስት አካላት መሆናቸው ከነፍስ ይለያሉ በኩነታት በመገናዘብ ከነፍስ ይመሳሰላሉ” ብለዋል። ነፍስ በአካል ረገድ አንዲት ሆና የምትጠራው በአንድ አካል ስም ሆና ነው። ሦስትነቷ ግን ጠባይዕዋን ኩነታቷን ነው የሚገልጸው። የሥላሴ ህሉና “አኗኗር” ግን እንዲህ አይደለም። ሦስትነቱ የአካላቸውንና የየአካላቸውን ስም በጽናቱ እንደተጠበቀ ሦስቱን አካላታቸውን በሚያገናዝቡ ኩነታት በህልውና በመለኮት ወይም በባሕርይ አንድ ሆኖ መታወቅ ነው። ለእሉኒ ልብ ወቃል ወእስትንፋስ ቦሙ አካል ለለርእሶሙ ወይሠመዩ ሠለስተ በአካል እንዲል። መቼም የመፍጠር የማዳን የመቀደስ ክሂል በልብነት በቃልነት በእስትንፋስነት ካልተገለጸ ምልዓተ ሕይወት የሌለው መሆኑ ነው። ይህን በልእልና ባሕርይ ሕያው ያልሆነ አይሠራውምና። የነፍስ ጠባይዓት የአንዲት አካለ ነፍስ ጠባይዓት ሆነው የሚታዩ ናቸው ነፍስ በአካሏ አንዲት ናትና። የሥላሴ ግን የሦስት አካላት ኩነታት በመሆን ይገኛሉ። ምክንያቱም ኩነታት ሆነው የሚገልጹዋቸው አካላት ሦስት ናቸውና። ያዕቆብ ዘእልበረዲ “አአምን ከመ ውእቱ ዋሕድ በመለኮት ወሥሉስ በኩነታት። አልቦ ፍልጠት ማዕከለ ልቡናሁ ወንባቡ ወሕይወት። እብል ወእትአመን ከመአብ ልብ ወወልድ ንባብ ወመንፈስ ቅዱስ ሕይወት” መዝገበ ሃይማኖት ይላል። ኩነትን ግዕዘ ጠባይዕ ህላዌ መለኮት የሚልም ይገኛል። ኩነታትን አረጋዊ መንፈሳዊ ኃይላት ጠባይዓት ይላቸዋል። ሰይፈ ሥላሴ

በሚባለው መጽሐፍ ደግሞ ባሕርያት ይላቸዋል። ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 18 “ወክዋኔ ይትበሀል ከመውእቱ ህላዌ ዘያስተጋብዕ አካላተ። እስመ ህላዌ ይትበሀል ክዋኔ”። ጠባይዕ እንደ ህላዌ አንዳንድ ጊዜ ባሕርይ አንዳንድ ጊዜም አካል ወይም ኩነት እየተባለ ይተረጎማል። ጉንዳጉንዲ የሚገኝ ትምህርተ ሥላሴ በተከሥቶ መጻሕፍት ቅዱሳት “አብሰ ልቡና ወአእምሮ በርእሱ ለርእሱ ወልቡና ውእቱ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ወአልቦሙ ካልዕ ልቡና ዘእንበሌሁ ወልድኒ ቃል በርእሱ ለርእሱ ወቃል ውእቱ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ ወአልቦሙ ካልዕ ቃል ዘእንበሌሁ ወመንፈስ ቅዱስኒ ሕይወት በርእሱ ለርእሱ ወሕይወት ውእቱ ለአብ ወወልድ” ይላል። ነፍስ በአካል አንዲት ስትሆን በባሕርይዋ ሦስት ከዊን አላት። በባሕርይዋ ሦስት ከዊን ያላት መሆኗ አካሏን ከሦስት አይከፍለውም። ኩነታተ ሥላሴም ሦስት ቢሆኑም ግን በተዋሕዶ ናቸው። ለሦስቱ አካላት ሦስት ኩነታት አሏቸው። ኩነታት የተባሉትም ልብነት ቃልነት ሕይወትነት ናቸው። ኩነታት መለየት መከፈል ሳይኖርባቸው አካላትን በህልውና እያገናዘቡ በአንድ መለኮት ያሉ የነበሩ ናቸው። እነርሱም ልብ ቃል እስትንፋስ ናቸው። እነዚህም ለየራሳቸው አካላት አሏቸው። ዐቃቤ ሰዓት ከብቱ “ለእሉኒ ልብ ወቃል ወእስትንፋስ ቦሙ አካል ለለርእሶሙ” ይላሉ ምዕላድ ገጽ 3። በየአካላቱም ሲኖሩ ልብ በአብ ቃል በወልድ እስትንፋስ በመንፈስ ቅዱስ እንደሆኑ ይታወቃል። እነዚህም በየአካላቸው ጸንተው ሳይፋለሱ ይኖራሉ። ኢይፈልስ ልብ ለከዊነ ቃል ወእስትንፋስ ወእስትንፋስኒ ኢይፈልስ ለከዊነ ልብ ወቃል። ቅኑመ ስሙ አብ የተባለ አካል በስመ ኩነቱ በልቡና ቅኑመ ስሙ ወልድ ለተባለ አካልና ቅኑመ ስሙ መንፈስ ቅዱስ ለሆነ አካል ለባዊነት ወይም የእውቀት ማወቂያ ነው። ቅኑመ ስሙ ወልድ የተባለ አካል በስመ ኩነቱ በቃል ቅኑመ ስሙ አብ ለተባለ አካልና ቅኑመ ስሙ መንፈስ ቅዱስ ለሆነ አካል ቃል ወይም መናገሪያ ንባብ ነው። ቅኑመ ስሙ መንፈስ ቅዱስ የተባለ አካል በስመ ኩነቱ በእስትንፋስነት ቅኑመ ስሙ አብ ለተባለ አካል ቅኑመ ስሙ ወልድ ለተባለ አካል ስም እስትንፋስ ወይም ሕይወት ነው። በዚሁ መገነዛዘብ የትሥልስተ አካላት ህልውና ይታይበታል። ያዕቆብ ዘእልበረዲ “አብ እንዘ ሀሎ በአካሉ ወበግጻዌሁ ሀሎ በወልድ እስመ ቃሉ ውእቱ ወልድ ዘኢይትፈለጥ እምኔሁ። ወልድ እንዘ ሀሎ በአካሉ ወበግጻዌሁ ሀሎ በአብ ወመንፈስ ቅዱስ እስመ ቃሎሙ ውእቱ ወልድ ለአብ ወመንፈስ ቅዱስ ዘኢይትፈለጥ እምኔሆሙ። ወመንፈስ ቅዱስ ሀሎ በአብ ወወልድ እስመ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ መንፈሶሙ ዘኢይትፈለጥ እምኔሆሙ። ወልድ ቃለ አብ ስለመሆኑ ራዕ.19፣13 ስሙም እግዚአብሄር ቃል ይባላል። መዝ. 32፣6 በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ። መዝ.106፣20 ቃሉን ላከ አዳናቸውም። ዮሐ.1፣1-2 ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ወልድ ቃለ መንፈስ ቅዱስ ስለመሆኑ ዮሐ.15፣26 ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል። ዮሐ.16፣13፤14፣15 ነገር ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። ከእርሱ አይናገርምና የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ የሚመጣውንም ሁሉ ይነግራችኋል። ከራሴ (ከገንዘቤ) ወስዶ ይነግራችኋልና ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ ከእኔ ይወስዳል ይነግራችሁማል አልሁ። አስተውል መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሚወጣ ተናግሮ የመንፈስ ቅዱስ መስረጽ ከአብ መሆኑን ያስገነዘበ ሲሆን ለአብ ያለው ሁሉ ገንዘቤ ነው በማለቱ በህልውና ረገድ በአብ ህልው የሆነ መንፈስ ቅዱስ ለራሱም ለወልድ ገንዘቡ መሆኑን አስጠብቆት ይገኛል። ከእኔ ወስዶ

ማለት እኔን ወይም ቃልነቴን ገንዘብ አድርጎ ይነግራችኋል ማለትን ቃሉ እንደመሆኑ በእኔ ቃልነት ይነግራችኋል በራሱ አይናገርምና ማለት ከአካሉ ወይንም ከሠራጺነት ግብሩ አይነግራችሁም ቃሉ እኔ ብቻ ነኝና ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአብ እስትንፋስ ስለመሆኑ ኢሳ.48፣16 መንፈሱ ላከኝ። መዝ.32፣6 ወእም እስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎሙ። ማቴ.10፣20 ነገር ግን የአባታችሁ መንፈስ በእናንተ ሆኖ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ለወልድ እስትንፋስ ስለመሆኑ ምሳ.1፣23 እነግረክሙ እስትንፋሰ ቃልየ። ገላ.4፣5 የልጁን መንፈስ ወደ እናንተ ላከ። ኩነታት መለየት መከፈል ከሌለበት ህላዌ መለኮት ያሉና የሦስቱ አካላት ኩነታት ናቸው። ታዲያ አካላት ለኩነታት እርስ በእርሳቸው ይገናዘባሉ ሲባል ምን ማለት ነው ቢሉ አካላት በኩነታት አንዱ ያለ አንዱ ወይም አንዱ ያለሁለቱ ህልውና ስለማይኖራቸው እየተገናዘቡ በህልውና ይኖራሉ ማለት ነው። እያንዳንዱ የሥላሴ አካል በየራሱ ኩነት እንዳለ የገዛ ራሱ ለሌሎች መሆኑና ገንዘባቸው ሲሆን የሌሎችንም ለገዛ ራሱ ገንዘብ ማድረግ ነው። አብ በልብነቱ ለራሱ እንዳለ ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው መሆኑንና ወልድንና መንፈስ ቅዱስንም የራሱ ገንዘቡ ማድረጉ ነው። ወልድም በቃልነቱ ለራሱ እንዳለ ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው መሆኑንና አብንና መንፈስ ቅዱስንም ለራሱ ገንዘብ ማድረግ ነው። መንፈስ ቅዱስም ለራሱ እስትንፋስ ሆኖ እንዳለ ለአብና ለወልድ ሕይወት "እስትንፋስ" መሆኑና ለገዛ ራሱም አብንና ወልድን ገንዘብ ማድረግ ነው። ዐቃቤ ሰዓት ከብቱ "እመቦ ዘይብል ምንት ውእቱ ተዋሕዶ ንብሎ ለአሐዱ አካል ከዊኖቱ ዘካልእ ወረስዮቱ ካልአ ዘዚአሁ ዝንቱ ውእቱ ተዋሕዶ" ብለዋል። ልብ ልቡና ማለት እውቀት ማወቂያ አእምሮ የአእምሮ ሕግ የሀሳብና የፈቃድ ምንጭ ማለት ነው። በአብ ልብነት ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያስባሉ ያስባሉም ሲባል መቼም ማወቂያቸው ልቡናቸው እርሱ አብ መሆኑ ሳይዘነጋ የሚነገር አብነት ነው።ይህም ውሳጣዊ አንድነታቸውን ያስገነዝበናል። ኤጲፋንዮስ ሃይ.አበ ክፍል 3 ቁጥር 24-25 ቦኑ ትብሉኑ ቦቱ ለአብ ነፍስ በእንተ ዘይቤ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘሠምረት ነፍስየ ቦቱ። ዘሰ ይቤ አብ ለወልድ ዘቦቱ ሠምረት ነፍስየ በእንተ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ። ወአኮ ለነፍስ ሥጋዊት እስመ ኢኮነ አብ ሥግው ከመ ወልዱ። አረጋዊ መንፈሳዊ "በከመ ኢይትፈለጡ እምነፍስ ንባባ ወሕይወታ ከማሁ ኢይትፈለጡ እምአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ፀሐይ በክበቡ አካላዊነት ይታወቃል ከክበቡ የሚገኙ ጸዳልና ሙቀት ግን ኃይላቱ ወይም ግብራቱ ከመሆን በቀር በየራሳቸው አካል እንደሌላቸው እናያለን። ቃልና እስትንፋስ ግን እንደ አብ አካላውያን ናቸው። ከአብ አካላዊ ባሕርይ የሚወጡ ቃልና እስትንፋስ ከአካል ያልተራቀቁ ዝርዋን ያይደሉ ነገር ግን እንደ አብ አካል ያላቸው ፍጹማነ አካል ፍጹማነ መልክዕ ፍጹማነ ገጽ ናቸው። አተርጋዎን በርፎሪኮን አአትሪኮን የተባሉ ቃላት ምንም እንኳ በአወጣጣቸው በአገባባቸው ሁኔታ በተለያየ ስም ቢነገሩም የምሥጢራቸው መሰረታዊ አቋም የአካል ውጤቶች እንደሆኑ ይገልጻቸዋል እንጂ የገዛ ራሳቸው አካላውያን ቃላት መሆናቸውን አይገልጽም። አተርጋዎን የተባለው ድምጽ ፍሬ ነገር ያለበት የመላእክት ቃል ነው ኢሳ.6፣3 ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ያለው ነው። በርፎሪኮን ነቢያት የሰሙት ቃለ እግዚአብሔር ነው ዘጸ.19፣3 ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲል ይህ ቃል አካላዊ አይደለም። አአትሪኮን ደግሞ የሰው እና የእንስሳት የአእዋፋት ድንጋዮች ሲጋጩ ወዘተ የሚሰማው ድምጽ ነው። መንፈስ ቅዱስ በከዊነ እስትንፋስ ከአብ እንደወጣ ብቻ ቢያስቡና አካል እንደሌለው አድርገው ለሚያስቡት ወደ መሰረተ

ትምህርቱ ጠልቀን መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር እስትንፋስ አካላዊነት ጌታ በዮሐ.16፣13 እስመ ኢይነግር ዘእምነቤሁ ወዘሰምአ ዳዕሙ ይነግር የሚለው ያስረዳል፡፡ ዘሰምአ የሚለው እኔ ባይ አካል እንዳለ ያስረዳልና፡፡ መንፈስ ቅዱስ መንፈሰ አብ እንደተባለ ሁሉ መንፈሰ ወልድም ይባላል ገላ.4፣5 መንፈሰ ወልዱ እንዲል፡፡ እስትንፋሳቸው ነውና፡፡ 1ኛ ጴጥ.1፣11 ዘነገረ በእንቲአሁ ላእሌሆሙ መንፈሱ ለክርስቶስ፡፡ ነሲእ የህልውና መገናዘብ ነው፡፡እምዚአየ ይነስእ ወይነግረክሙ ሲል ከእኔ ቃልነትን ገንዘብ አድርጎ ማለት ነው፡፡ ምዕላድ ዘዐቃቤ ሰዓት “እመቦ ዘይብል በእንተ ምንት ይሰመይ አብ አሥራጼ ኀበ መንፈስ ቅዱስ ወኢይሰመይ አሥራጼ ኀበ ወልድ ንብሎ እስመ አውጽኦ ለመንፈስ ቅዱስ በከዊነ እስትንፋስ፡፡ ለወልድሰ እስመ ኢያውጽኦ በከዊነ እስትንፋስ በእንተዝ ኢይሰመይ አሥራጼ ኀበ ወልድ፡፡ ወተሰምዮ አስራጺ አኮ በእንተ አውጽኦ ባሕቲቶ አላ በእንተ አውጽኦ እስትንፋስ፡፡ እመሰ በእንተ አውጽኦ ባሕቲቱ ይሰመይ አሥራጼ እምተሰምየ አብ አሥራጼ ወልድ እስመ አውጽኦ፡፡ ዝሰ አልቦ ውስተ መጻሕፍት፡፡

ተዋሕዶ፣ ዕሪና፣ ተገናዝቦ

ዕሪና በዘመን ከፍና ዝቅ ትልቅነትና ትንሽነት ስፋትና ቀጭንነት በሌለበት ሁኔታ መተካከልን መመሳሰልን በአካልና በመልክ በገጽ አንድ ዓይነት አቋም እንዳለ የሚከሠትበት ይዘት ነው፡፡ ተዋሕዶ አንድ መሆን መገናዘብ ነው፡፡ ተዋሕዶ ዋሕድና መዋሐድ መገናዘብ የማለትን ትርጉም የያዘ ነው፡፡ ይህ ተዋሕዶ ወይም ዋሕድና “መገናዘብ” ባሕርይ ጠባይዕ በሚነገርበት ምሥጢር የሚገኝ ነው፡፡ መደባለቅንና መለወጥን ቡዓዴን መለያየትን እየተካከለ የመገናዘብ ምስጢር የሚጠበቅበት ነው፡፡ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርተ መለኮት በአንድ መለኮት በሚኖሩ ኩነታት ማለት በልብ ቃል እስትንፋስ አካላትን በህልውና የሚያገናዝብ ነው፡፡ ተዋሕዶ ዋሕድና በምሥጢረ ሥጋዌም የመገናዘብን ይዘት እየገለጸ የቃልና የሥጋን መዋሐድ ያስረዳል፡፡ ዕሪና ወይም መተካከል የሚነገር በአካላት ላይ በሚወድቅ ምሥጢር ነው፡፡ ዋሕድና ተዋሕዶ አንድነት የሚነገር ስለ ባሕርይ ወይም ስለጠባይዕ በሚነገር ምሥጢር ነው፡፡ ስለዚህ ስልት ስልታቸውን ሳያውቁ የሃይማኖትን ነገር ማስተማር መጽሐፍንም መጻፍ ምሥጢረ ሥላሴን ያፋልሳል፡፡ ዐቃቤ ሰዓት ከብቱ “አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ያለው ተዋሕዶ አካል በመሆን ወይም በአካል አይደለም የየራሳቸው አካል አላቸውና ነገር ግን በልብነቱ ነው፡፡ ወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የሚዋሐደው አካል በመሆን ወይም በአካልነቱ አይደለም የራሳቸው አካል አላቸውና ነገር ግን በቃልነቱ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ የሚዋሐደው አካል በመሆን ወይም በአካልነቱ አይደለም የየራሳቸው አካል አላቸውና ነገር ግን በሕይወትነቱ ነው” ብለዋል፡፡ በአንድ መለኮት ሦስት አካላት ሦስት ኩነታት እንዳሉ ማመን ነው፡፡ ኩነታት ግን ተፈልጦ ተከፍሎ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ በአኗኗር እያገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩ ያሉ የሚኖሩ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር አንድነቱ በባሕርይ በህልውና ነው፡፡ እነዮሐንስ ተዓቃቢ ሥላሴን ለእያንዳንዳቸው ሦስት ጠባይዓት “ኩነታት” ባሏቸው በሦስት ሰብአውያን አካላውያት ነፍሳት አምሳል መስለው ሦስት ባለጸጎች በሀብት ወይም በሽምግልና እንደሚተካከሉና እንደሚመሳሰሉ በተመሳሳይነታቸውም አንድነት እንደሚኖር አድርገው ሲያስተምሩ ሥላሴ እርስ በእርሳቸው በመገናዘብ የሚዋሐዱበትን ባሕርያዊ ተዋሕዶና መለኮታዊ አንድነት እንደሌለ አድርገው መናገራቸው ያሳዝናል፡፡ ሥላሴ አካላቸው የተለየ ሲሆን ባሕርያቸው ተከፍሎ

የሌለበት አንድ መሆኑን የሚያስረዳ የሦስቱ ልብ አንድ አብ ሆኖ አንድ እውቀትን ያውቃሉ፡፡ የሦስቱ ቃል አንድ ወልድ ሆኖ አንድ ቃልን ይናገራሉ የሦስቱም እስትንፋስ አንድ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ አንድ የሕይወት ስራን ይሰራሉ፡፡ አቡሊዲስ ሃይ.አበ ክፍል 2 ቁጥር 8-9 “ወልድ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው፡፡በዚህም ምክንያት የሥላሴ መለኮት አንድ እንደሆነ አወቅን”፡፡ መገናዘቡ በኩነታት አስማት እንጂ በአካልና በግብር አስማት እንዳልሆነ ጠንቅቆ መረዳት ያሻል፡፡ በማስተዋል የምንከታተል ከሆነ ሊቁ አቡሊዲስ ወልዶሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ ወይም መንፈስ ቅዱሶሙ ለአብ ወወልድ አይልም፡፡ በአካል ስማቸው ለማገናዘብ አይሞክርም፡፡ እንዲሁም ተወላዲሆሙ ለወላዲ ወለሠራጺ ወይም ሠራጺሆሙ ለወላዲ ወለተወላዲ ብሎ በግብር ስማቸው ለማገናዘብ ፈጽሞ አልቃጣም፡፡ በኩነት ስማቸው አገናዘባቸው እንጂ፡፡ ሊቃውንትም ስለ አካላት አስማት ሲጽፉ አቡሁ ለወልድ ወይም ወልዱ ለአብ ይላሉ እንጂ አቡሆሙ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ወልዶሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ አላሉም፡፡ ግብርንም እንዲሁ ወላዲሆሙ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ተወላዲሆሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ አላሉም፡፡ እንዲህ ቢል ኖሮ ወልድ የተወለደ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ነው ባሰኘ ነበር፡፡ ሊቃውንቱም ይህንን በመጠንቀቅ ዘበኀበ አብ ወልድ ዘበመንፈስ ቃል ይላሉ፡፡ በአብ ዘንድ ልጅ በመንፈስ ዘንድም ቃል የሚሆን ይሉታል፡፡ ዘበኀበ አብ ወልድ ዘበመንፈስ ወልድ ግን አላሉም፡፡ የሥላሴ ተዋሕዶ ወይም መገናዘብ አንድ ባሕርየ ሕይወት ወደመሆን እንጂ አንድ አካል ወደመሆን አይደለም፡፡ አካላትን ወደ አንድ አካል ለማዋሐድ መሞከር የአካላትን ጽንዕ እንደ ብረት ጨፍልቆ አንድ ድብልብል ነገር ስለማድረግ ያህል የሚቆጠር ነው፡፡ ታዲያ የሥላሴ ተዋሕዶ እንደምን ነው ተብሎ ቢጠየቅ ግን መልሱ እነሆ በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ የመገናዘብ ህልውና አንድ አምላካዊ ክሂልና ሥልጣን ፈቃድ የሚገለጽበት ልዑለ ባሕርይ “መለኮት” ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ “ተዋሕዶቱ ለአብ ምስለ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አኮ በከዊነ ሎሙ አካለ እስመ ቦሙ አካል ለለርእሶሙ አላ በከዊን ሎሙ ልበ ወተዋሕዶቱ ለወልድ ምስለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ አኮ በከዊን ሎሙ አካለ እስመ ቦሙ አካል ለለርእሶሙ አላ በከዊን ሎሙ ቃለ ወተዋሕዶቱ ለመንፈስ ቅዱስ ምስለ አብ ወወልድ አኮ በከዊን ሎሙ አካለ እስመ ቦሙ አካል ለለርእሶሙ አላ በከዊን ሎሙ እስትንፋሰ ወበእንተዝ ኢይሰመዩ አሐደ አካለ እስመ ተዋሕዶቶሙ አኮ በከዊን አካለ አላ ለከዊነ ሕይወት፡፡ ወብሂለ ሕይወትኒ ልብ ወቃል ወእስትንፋስ ውእቱ” ይላሉ፡፡ ዕሪና የሚነገር በአካላት ላይ በሚወድቅ ምስጢር ነው ዋሕድናም የሚነገር ስለ ባሕርይ ወይም ስለጠባይዕ በሚነገር ምስጢር ነው፡፡ ባሕርየ መለኮት ሦስቱን አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በኩነታቱ በልብነት በቃልነት በእስትንፋስነት እያገናዘበ አንድ የሚያደርጋቸው መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ሃይ. አበ. ክፍል 1 ቁጥር 6 ንትአመን በሠለስቱ አካላት ወሠለስቱ ገጻት እንተ አሐዱ ባሕርየ መለኮት፡፡ እስመ ባሕርየ ሥላሴ አሐዱ ውእቱ ዘውእቱ አሐዱ መለኮት፡፡ ዮሐንስ ዘእስክንድርያ ሃይ.አበ.ክፍል 1 ቁጥር 13 እስመ መለኮተ ሥላሴ አሐዱ ውእቱ ወበሠለስቲሆሙ ሀሎ መለኮት፡፡ተዋሕዶ እየተባለ የሚነገረው ህብረት እየተባለ የሚነገር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ኪራኮስ ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 5 “አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ”፡፡ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 6-7 ወአልቦ ውስተ ቅድስት ሥላሴ ግብርናት ወኢተጋንዮ ወኢይትሌዓል አሐዱ እምካልዑ በመዓርገ

መለኮት ወኢይኤገዞ አሐዱ ለካልዑ ዘከመ ተለአኪ በሥልጣኑ አላ እመንቱ ዕሩያን በአሐዱ ክብር ዘመለኮት ወምልክና ወሉዓሌ”። ዮሐንስ ዘአንጾኪያም ሃይ. አበ. ክፍል 1 ቁጥር 2 ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ካለ በኂላ ወከመዝ ዓዲ ዕሩያን ሥላሴ በህላዌ ወበመንግሥት ወስብሐት ወበፈጢረ ኩሉ ፍጥረት ይላል። ዐቃቤ ሰዓት ክብቱ “ወዓዲ ይሰመዩ ሥላሴ አሐደ በዘይትማሰሉ ቦቱ። ወእመ ትብለኒ ምንት ውእቱ ዘይትማሰሉ ቦቱ እብለከ ከዊነ ቀዳማዊ ወከዊነ ዘኢይትዋለጥ ከዊነረቂቅ ወከዊነ ምሉዕ። ወዝ ዘይትማሰሉ ቦቱ። በሌላውም ክፍል ከዊነ ፈጣሪ ከዊነ ዘኢይመውት ከዊነ ዘኢይትዋሰን ከዊነ ኢፍጡር ከዊነ ሕያው ይላል። አንዱን መለኮት ወይም ባሕርየ መለኮት በሦስት አካላት መጠን እየቀደዱ ለየአካላቱ ማዳረስ አይገባም። ባሕርይ ምንጊዜም አንድ ነውና። አንድ መለኮትን ወይም ባሕርይን እየቀደዱና እየከፋፈሉ ልዩ ልዩ መዓርጋትን (ደረጃዎችን) በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መካከል በማግባትበ ለአብ ታላቅነትን ለወልድ ታናሽነትን ለመንፈስ ቅዱስ የታናሽ ታናሽነትን መዓርጋት በመስጠት የተተናኮሉ እነ አቡሊናርዮስና መቅዶንዮስ ናቸው። ለባዊና ነባቢ ሕያው የሆነውን አንዱን እግዚአብሔር መለኮትን በመከፋፈል አብን ፈጣሪ ወልድን ፍጡር መንፈስቅዱስን አካላዊነት የሌለው ኃይል አድርጎ ሰጣጤ መለኮት በመሆን ራሱንና ተከታዮቹን ያሳተ አርዮስ ነው። ዐቃቤ ሰዓት ክብቱ “ሥላሴኒ ይትበሀሉ አሐደ በሕይወት እስመ ተዋሕዶቶሙ በከዊነ ልብ ወቃል ወእስትንፋስ”።

ተረክቦ

ስለ እግዚአብሔር ህላዌም ሆነ ባሕርይ ወይም ኩነትም ሆነ አካል ወይም ግብር ስንናገር ተገኘ አስገኘ እያልን የምንነጋገረው አነጋገር አኗኗሩን በሚገልጽ ይዞታ መናገራችን ነው እንጂ በኂላ ጊዜ እንደሚገኝና ከእርሱ በፊት ሌላ ቀዳሚ ነገር እንደነበረ አድርገን ስናሳይ አይደለም። ይህን በጥንቃቄ ማስተዋል ይገባል። የነፍስ ጠባይዓት በገላጭነት በተገላጭነት አቋም ሲታይ የተረክቦ ህልውናቸው ቅደም ተከተል የሌለበት ነው። ተረክቦ ወይም መገኘት ስንል የእኛን አእምሮ በሚመለከት ገለጻ መናገራችን ነው እንጂ የእግዚአብሔርን ሲመለከት የሚነገር አይደለም። እግዚአብሔር የተገኘበት ጊዜ የለም። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው። መቅደምና መቀዳደም የለም የሚለውን የሚያሰኘውን አንዱን ባሕርየ መለኮትን በመከፋፈልና በመቅደድ ወልድን ከአብ በኂላ እንደተገኘ እያደረገ ያስተማረ የአርዮስ ተከታይ አውናምዮስ ይባላል። ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ላስገኘ አብ ወጽአ የሚል አንድም ቃል ከቅዱሳት መጻሕፍት ስለማይገኝ ለአብ አስገኝ አለው ወይም ከዚህ ወጣ ሊባል የማይቻል ሆኗል። ይወልደዋል አይቀድመውም ያሰርጸዋል አይቀድመውም። ወልድና መንፈስ ቅዱስ አስገኝ ከማይኖርበት ከአብ ወጡ ሲባል ቅድምና ወይም ተድኅሮ አይኖርባቸውም። ምክንያቱም ጸአት መውጣቱ መኖሩ ሳይቀር በጸአትነት በአወጣጥ አቋሙ እያለ ነው። ተዋሕዶተ መለኮት ወይም የባሕርይ ህልውና በተከፍሎና በተመትሮ አይለያዩምና። የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የባሕርያቸው አኗኗር ከአብ ተለይቶ በየራሱ የሚቆምና ተመትሮ ወይም ተከፍሎ ቢኖርበት ኖሮ ቅድምና ወይም ተድኅሮ ሊኖርባቸው ይችላል ባሰኘ ነበር። ህልውናንና ጸአትን ጸአትን የሚያስተባብር ትምህርት ሥረ ነገር የተገኘው 1ኛ) እኔ ከአብ ዘንድ ነኝና ሲል ራሱ ተናግሯ ዮሐ.7፣19። እንዲሁም ወቃል እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ብሏል። 2ኛ) ስለመንፈስ ቅዱስና ስለአብ የህልውና አንድነት

ሐዋርያው ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ.2፣12 ነሳእነ መንፈሰ ዘእምነበ እግዚአብሔር ብሎ ተናግሯል። እግዚአብሔር አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን አስገኛቸው። አብ ልጁን ወልዶታል እንዴት እንደወለደው ግን ለማስተዋል ጭንቅ ነው። እጹብ ድንቅ ማለት ብቻ ነው። እንኳን የእግዚአብሔር የሰው እንኳ ነፍሳችን መኖሯን እናውቃለን ግን አይተናት አናውቅም ዳሩ ግን አላየናትምና እንዴት እንደምትኖር የአኗኗሯን ሁኔታ ስላላስተዋልን አይተናት አናውቅም። ስለዚህ እያወቅነው ሳለ እንዴት እንደሆነ ግን ለማስተዋል የማንችለው ነገር ነገር በመኖሩ ምክንያት ነው። የወልድ ባሕርይ ከሌላ የተገኘ እንግዳ ነገር ሳይሆን ለዚያ ማንም ለማያየውና ለማይቀርበው ጨለማ በሌለበት ለማይሞት ለአንዱ ልዑለ ባሕርይ አብ የብርሃኑ ነጸብራቁ ነው ማለታችን ነው። በምስጢር ረገድ ጸአት የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ከአንድ ከአብ ምንጭ መውጣትን ወይም ተረክቦን ወይም መገኘትን ያስገነዝባል። በሌላ በኩል ደግሞ አወጣጥን በሚመለከት ረገድ የተለያየ ይዞታ አላቸው የቃል ከልብ መውጣትና የእስትንፋስ ከልብ የመውጣት ሁኔታ እንደሚለያይ ማለት ነው። አኒኝ ማለት እንዲሆን የሚያደርግ ማለት ነው።

ግብር

ግብር ሲባል የባሕርይ ግብር የአካል ግብር የኩነት ግብር እየተባለ የሚነገር አብነት መሆኑ በቤተክርስቲን አብነት መምህራን አባባል እሙን ነው። መቼም ግብር ሲባል ገብረ ከሚል ግሥ በመውጣቱና ሠራ አደረገ ተብሎ በሥራ ሁሉ ላይ እየገባ እንደስራው ስልት እየፈታ እየተረጎመ የሚነገር መሆኑ በመተርጉማን ሰዋስዋዊ ደንብ የታወቀ ነው። በአንጻሩ ደግሞ በሕይወት ብሉተ ሕሉና (ብቸኛ ነዋሪ) የሚሆን ህላዌ መለኮትን ባሕርይ ስንል የዚህን የባሕርይ ግብር አገላለጽ እንደየሁኔታው ስልት እየፈቱ የሚተረጉሙ መተርጉማን ቃላት እንደሚኖሩ የሚዘነጋ ሊሆን አይገባም። ግብሩ የባሕርይ ገለጻ መሆኑን አጠቃሎ የሚያሳይ ሥነ መለኮት የሚለው ቃል ነው። ይኸውም ቅዱስ ያሬድ በድጓ ዘጥምቀት አስተርእዮ ኮነ ዘክርስቶስ ሥነ መለኮት የክርስቶስ የመለኮቱ ስን መገለጥ ሆነ ብሏል። ባስልዮስ ዘቂሳርያም ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 2 ላይ እስመ በሥነ መለኮቱ ወዕበየ ኂሩቱ ይትማሰሎ ለእግዚአብሔር አቡሁ ሲል ተናግሯል። ይህም አገላለጽ መዓዛ ዕጣን እንደማለት ነው። በዚሁ ብሉተ ሕሉና ብቸኛ ነዋሪ የሆነ የጌትነት የበጎነት ባሕርዩ በክብሩ በግብሩ ይገላጻል። ሊቃውንቱ አሐዱ ግብሮሙ ሲሉ ስለአንድ ግብር የሚያደርጉት ስለአካል ግብር ሳይሆን ስለባሕርዩ ግብር መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል።ስለ አካል ግብራት ሲናገሩ ሦስት ግባራትን በሚያመለክት የአብ ግብሩ መውለድ ማሥረጽ የወልድ ግብሩ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ ነውና። ግብር ሕይወተ ባሕርይን ወይም ህላዌ መለኮቱን እያንጸባረቀ የሚገኝ ነው። በዓለመ ግዘፍ የሚገኝ ማንኛውም አካል በባሕርይ እንደተመሰረተ ክዋኔውም ከባሕርይ እንደሆነ ሁሉ ባሕርይ ደግሞ በግብር ይገለጻል።ስለዚህ ግብር የባሕርይ ውጤት ነው። ዲዮናስዮስ ዘሀገረ አትናስ ሃይ.አበ. ክፍል 1 ቁጥር 11 ወበእንተ ተግህዶተ ሠለስቱ አካላት አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ አሐዱ መለኮት አብወቃሉኒ ወልድ ዘተወልደ እምአብ ብርሃን ዘእምብርሃን መንፈስ ቅዱስኒ ዘወጽአ እምአብ ብርሃን ዘእምብርሃን። ልደተ ወልድ ወጸአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትነገር ወይትሌዓል ላእለ ኩሉ ሕሊናት። ዮሐ.16፣27-28፤17፣18፤13፣3፤8፣4 ማቴ.13፣3። አባ ሚናስ ሃይ.አበ ክፍል 1 ቁጥር 9 "ወመንፈስ ቅዱስኒ ህልው እምአብ እንበለ ጥንት እምቅድመ ዓለም። አኮ

ውእቱ ተወላዲ አላ ወጽአ እም አብ”። **የኅድረት ጸአት** የሚባለው የሰው ከቤት እንደመውጣት የውሃ ከጉድጓድ እንደመውጣት የሸቱ ከብርሌ እንደመውጣት ያለው ነው።እነዚህ የኃዳሪና የማኅደርን ጸአት ወይም መውጣት የሚያሳዩ ናቸው እንጂ የባሕርይ ጸአትን ወይም መውጣትን የሚያሳይ ምሥጢር የላቸውም። **የባሕርይ ጸአት** የሚባለው የቃልና የእስትንፋስ ከልብ እንደመውጣት የጸዳልና የሙቀት ከብርሃን እንደመውጣት የነበልባል ዋዕይ ከፍህም እንደመገኘት የርጥበትና ሁከት ከውሃ ስፍሐት እንደመገኘት ያለ ሁሉ የባሕርይ ጸአትን የሚያሳይ ምስጢር ያላቸው ናቸው። መዝ.42፣5-6፣ ኢሳ.52፣8፣ ዮሐ.1፣1-2፣ ዕብ.1፣2-3፣ 1ኛ ዮሐ.1፣1፣ ራዕ.19፣13፣ ማቴ.12፣34-35፣ መዝ.40፣1፣ ኢዮ.34፣14። ርቱዓ ሃይማኖት “ከመ ልደተ ቃል ወጸአተ እስትንፋስ እም ልብ ከማሁ ልደቱ ለወልድ ወጸአቱ ለመንፈስ ቅዱስ እምአብ” ይላል። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሚወጣበት አወጣጥ ወልድ ከአብ ከሚወጣበት አወጣጥ ልዩ ነው። የግብር ስም የሥላሴ አካላት በየግብራቸው ተለይተው የሚታወቁበት ትምህርታዊ አቋም እና አብነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተተለመ መሰረታዊ ሀሳብ ነው። መዝ.109፣3 ወለድኩከ እምከርስ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ ተብሎ በተነገረ ንባብ አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ የሚሰኙበት ምስጢር ተገልጸበታል። ዳግመኛም ዮሐ.15፣26 መንፈስ ቅዱስ ዘይወጽእ እምኀበ አብ ተብሎ በተነገረ ንባብ አብ አሥራጺ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ የሚሰኙበት ምስጢር ተገልጸበታል። ሥርጸት በተለየ ለመንፈስ ቅዱስ ልደት በተለየ ለወልድ ይሰጣል ጸአት ግን ለሁለቱም ይሆናል። በጸአት ይነገር እንጂ የአወጣጣቸው ሁኔታ የተለያየ ነው። አትናቴዎስ ሃይ.አበ. ክፍል 4 ቁጥር 11-12 እስመ ኢኮነ አሐዱ ግብሩ ለዘተወልደ ወለዘኢተወልደ እስመ አሐዱ ሊሁይ እምካልዑ በግብረ ልደት። አብ አብ የተሰኘ ስለወለደና ስላሰረጸ ነው ወልድም ወልድ የተባለ የተሰኘ ስለተወለደ ነው መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ የተሰኘ ስለሰረጸ ነው የሚል ሰው ደፋር አላዋቂ ነው። የሥላሴ አስማተ አካላት ከግብራት የተገኙ ፍሬዎች ወይም ውጤቶች አይደሉም። መቃርዮስ ሃይ አበ ክፍል 1 ቁጥር 4 ንሰምዮ ለአብ አበ በእንተ ዘኮነ ወላዴ ወለወልድኒ ወልደ በእንተ ዘተወልደ እም አብ ወመንፈስ ቅዱስኒ መንፈስ ቅዱሰ በእንተ ዘወጽአ እምአብ ይላል። ይህ ቃል ከላይ የጻፉትን የሚሸር ነው።

ምሥጢረ ሥጋዌ

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል በማኅጸነ ቅድስት ድንግል ማርያም አደረ። በዚህ ክፍል አደረ ብለን የምንናገረው የመለኮት ተዋሕዶ በወልድ በቃልነቱ ስላለው ከዊን ነው እንጂ በአብና በመንፈስ ቅዱስ ስላለው ከዊን አይደለም። ስለዚህ የመካከለኛነት ስራ በወልድ የመሆን ምስጢር ማለት በአንድ ከሀሊ ሕይወት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በህልውና የሚገናዘበው ቃል በተለየ አካሉ ከድንግል ማኅጸን አድሮ ሥጋ መሆኑና የመወለዱ ምስጢር ነው። ወልድ ወደዚህ ምድር መጥቶ የማዳን ሥራውን ሲፈጽም በታየበት ጊዜ ራሱ የተለየ ፈቃድ እንዳልነበረውና የአባቱ ፈቃድ ግን የራሱ ፈቃድ እንደነበረ በቃሉ ያስተማረውን ብንመለከት እንረዳለን። የአብ ፈቃድ የወልድ ፈቃድ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አንድ ፈቃድ ይባላል እንጂ ሦስት ፈቃድ አይባልም። 1ኛ ዮሐ.4፣8-9 እግዚአብሔር ፍቅር ነው ይላል ይህ ፍቅር ደግሞ በምልአትና በፍጹምነት በቅድስት ሥላሴ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በርቶ ተንጸባርቆ ታይቶና ተገልጾ ታውቋል። ዮሐ.3፣16 እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን ለሰው ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ፍቅሩን ገለጸ።

ዮሐ.15፣13 እግዚአብሔር ወልድም የገዛ ራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ፍቅሩን ገልጹዋል። ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ሃይ.አበ. ክፍል1 ቁጥር 7 “ንሰብሖ ለአብ ዘመጠወ ወልዶ ዋሕደ ለሕይወተ ኩሉ ዓለም ንሰብሖ ለወልድ ዋሕድ ዘመጠወ ነፍሶ ባሕቲቱ በእንተ መድኃኒትነ ወዓዲ ንሰብሖ ለመንፈስ ቅዱስ ዘይበውእ ውስቴትነ ወያሐይወነ ወይሁበነ ሀብተ ተሳትፎ ምስለ እግዚአብሔር አሜን”። ባስልዮስ ዘቂሳርያ ሃይ.አበ ክፍል 4 ቁጥር 32 “ሠረቀ ክሡተ እመለኮተ አብ ዘእንበለ ጥንት ወዘእንበለ ፍልጠት እንዘ ይትዋሐድ ምስለ ሰብእ”። በሰው ታሪክ ውስጥ በግ ለሰው ቤዛ እና ጥቅም ይውላል እንጂ ሰው ለበግ ቤዛ ሆኖ ራሱን ሲሰጥ ታይቶ አይታወቅም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ነፍሱን ስለበጎቹ ቤዛ አድርጎ ሰጥቷል። በዓለማችን ቸር እረኛ የሚባለው በጉን ደህና አድርጎ እየተንከባከበ የሞኖር ነው። አውሬም እንዳይበላው የሚጠነቀቅለት ነው። ከተጠነቀቀለት በኋላ ግን በብዙ ገንዘብ ለበላተኛ ይሸጠዋል ወይም በገዛ ራሱ አርዶ ቀቅሎ ይበላዋል። በእውነት ከዚህ ዓይነት እረኝነት የሚታየው መልካም አጠባበቅ የንግድ ምስጢር እንጂ ቸር የሚያሰኝ አንዳችም ነገር የለበትም። ከእነዚህ የባሱ እረኞችም አሉ ምንም ለበጎቻቸው የማያስቡ በለመለመ ሳር የማያሰማሩ ጠማቸው የሚያሳድሩ አሉ እነዚህም ብዙ ጊዜ ከበጎች ሥጋና ቆዳ ብቻ የሚፈልጉ ከአውሬ የማያድኑ ክፉዎች አሉ። ጌታ ግን ቸር እረኛ ነው።

መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡- በሥራ ውለው ማታ ነፋስ በመቀበል ጊዜ አንድ ሀሳብ ቢያገኙ በማስተዋሻ ለመጻፍ ከውጭ ወደ ቤት ይመለሳሉ። በምሳ ወይም በራት ጊዜም አንድ ትርጓሜ ቢታሰባቸው ምግቡን ትተው ብድግ ይላሉ። ሌሊትም ተኝተው ሳሉ አንድ ምስጢር ቢገጥማቸው ከመኝታቸው ተነስተው መብራት አብርተው ይጽፋሉ። አብደሩ ጻድቃን መከራ ሥጋ እም ተድላ ሥጋ እስመ መጠነ አፈድፈዱ መከራ ይፈደፍድ ፍሥሓሆሙ። ለምንት ሰብእ ይጸልእ መከራ እመ ክብሩ አምጣነ ያበዝኅ መከራ። ዘላለማዊ ክብር የማያሰጥ ምድራዊ ክብር ብቻ ያለበት ስራ አትስራ። ንግግርህ ሀሳብህ ድርጊትህ ለአንተም ለሌሎችም ዘላለማዊና ሰማያዊ ክብር የሚያሰጥ ይሁን። ከዚህ ዓውድ የወጣ ነገር አታድርግ። አንድ ሰው በባህሉ መሰረት የፈለገውን ቢለብስ ቢናገር ያ ባህሉ ከእግዚአብሔር አንድነት የሚለየው እስካልሆነ ድረስ ደስ ያለውን ነገር ቢያደርግ አንተ ስላልወደድከው መጥላት የለብህም። ከእግዚአብሔር የሚለየው ከሆነ ግን በምክርም በተግሣጽም ምከረው። ስለ አንድ ጉዳይ ባለሙያ የተባለው አካልም ሊዋሽህ ይችላልና ለአእምሮህ ጥሩ አመክንዮ ሊኖርህ ይገባል እንጂ ባለሙያው ስላለ ብለህ ብቻ የምትይዘው ሊኖርህ አይገባም። ባህል ነው እነ እገሌም ያደርጉታል በታሪክም ተደርጓል የሚባል ነገር ሊገዛህ አይገባም ከዚያ ይልቅ ያ ነገር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛን ልክ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነው ማየት ያለብህ። በፍትሕ ላይ ሞራል፣ ቀልድ፣ ዝምድና ምንም አይሰራም የጉዳዩን እውነትነት ብቻ ማረጋገጥ እንጂ። ስለማንኛውም ሰው ጉዳይ ነገር ስታወራ አጠገብህ እንዳለ አድርገህ አውራ ይህን ብታደርግ ከሐሜት ከነቀፋ ይከላከልልሀል። ጌታ ሆይ ተሸናፊ ልብ ስጠኝ በል። ተሸናፊ ልብ ካለህ ትዕቢት፣ ትምክህት፣ ኩራት አይኖርብህም። አንድን ነገር ሰው አብዝቶ ስላወራው ስመ ጥር ሰዎች ስለተቀባበሉት እውነት

ነው አይባልም፡፡ የግድ አንተ ራስህ የምታውቀው ካልሆነ ዝም በል፡፡ ማንም ሰው ቢንቅህም ቢሰድብህም ቢቆጣህም በልብህም በአፍህም ልጁን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚስብ ነገር አድርግ፡፡

ፊደል

የሁለቱ ‹‹አ፣ ዐ›› የሦስቱ ‹‹ሀ፣ ሐ፣ ኀ›› ግዕዛቸው ከራብዓቸው በመልክ ብቻ ተለይቶ በድምጽ ስላልተለየና ልዩነቱ ስላልታወቀ በግዕዝ ቦታ ራብዕ ‹‹ጎሥዓ፣ ሞዓ፣ በልዓ፣ በዝኃ፣ በርሃ›› በራብዑ ፈንታ ግእዝ ‹‹ጸሐፈ፣ ከሀሊ፣ ወሀቢ›› እያለ ይገኛል፡፡ የራብዕ ጠባዩ አፍ ማስከፈትና ቃል ማገንታት ዝርዝር ማሳየት ነው፡፡ ለግዕዝ ግን ይህ ሁሉ የለውም፡፡ በ ‹‹ሀ›› ቦታ ‹‹ሃ›› እየተጻፈ ስህተት የሰለጠነበት ምክንያት ጽሕፈትና ትምህርት ተባብረው በአንድ ሰው እጅ ስላልተገኙ ነው፡፡ ስህተት ፊደል መለወጥ ነው፡፡ ግድፈት ግን ፊደልን መጣል ነው፡፡ሚካኤል ያለውን ሚኤል እንደማለት ያለ ነው፡፡ አፈወርቅ ድርሳን 9 ‹‹ወበከመ ዘይመጽእ ኀበ ትምህርተ መጽሐፍ ይደልዎ ከመ ይስማዕ ቅድመ ፍካሬ ሆህያት፡፡ ወለጸሐፊኒ ኢይትከሀሎ ጠንቅቆተ ጽሒፍ ለእመ ኢያእመረ ሥርዓተ ሆህያት፡፡ ወባሕቱ ለእመ አዝለፈ አስተሐይጾ ውስቴታ ወአብዝኀ ውስተ አእምሮ ፍካሬሃ ኢይረክቦ ዕቅፍት፡፡ የ ‹‹አ፣ዐ›› የ ‹‹ሀ፣ሐ፣ኀ›› የ ‹‹ጸ፣ፀ›› የ ‹‹ሠ፣ሰ›› ግሳቸውና ነባራቸው ልዩ ልዩ ሲሆን አብረው በአንድነት መገሰሳቸው እጅግ ታላቅ ግፍ ነው፡፡ ምንም እንደቀድሞው የድምጽ ልዩነት ባይኖራቸው የመልክ ልዩነት አላቸው፡፡ ምስጢራቸውና ስማቸውም እንደ መልካቸው እየቅል ነው፡፡ ፊደልና ጽሕፈት ለአዳም ልጆች የተገለጡና የተሰጡ በአዳም እድሜ ነው፡፡ በሄኖስ ዘመን ማለት ነው፡፡ የተሰጡበትም ምክንያትም ይህ ነው፡፡ ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ መፈጠሩ እንደ መላእክት ሕያው በሕገ ልቡና ሊኖር እንጂ በተፈጥሮ የተሰጠውን ሕግ ረስቶ ዘንግቶ እንደገና መጽሐፋዊ ሕግ ሊጥፍና ሊያስጥፍ በመጽሐፍ ሊደግፍ አልነበረም፡፡ ሄኖስን በራዕይ እንደ ሙሴ ስቦ በባለሟልነት አቅርቦ ረቂቁን ሕግና ትእዛዝ አግዝፈው አጉልተው የሚያሳዩ የዓይነ ልቡና መነጽሮች ፊደላትን ሰጠው፡፡ ወዲያው በልቡ እየሣለ ስነፍጥረትን ዐሠርቱ ቃላትን በቃል በፊደል ያስተምራቸው ዘንድ ያለፈውንም ታሪክና ዜና ተረስቶና ተዘንግቶ እንዳይቀር ለቅሞ ሰብስቦ ይጥፍላቸው ዘንድ ሥራውንና አሠራሩን ነድፎ አሳይቶ የሰው ሁሉ መገሥጽ መናዝዝ አድርጎታል፡፡ ዲያብሎስ ግን ቀንቶ ፔንሙ በሚባለው ጋኔን አማካኝነት በቅዱሱ ፊደል ሌላ ርኩስ ትምህርት ጥንቆላና ሟርት ስመ አጋንንት እንዲጥፉና እንዲያነቡ ያስተምራቸው ዘንድ ጌታ ለሄኖስ እንዳሳየው ሁሉ እርሱም በምትሀቱ ቀለምና ክርታስ በእጁ ይዞ ርኩስ ትምህርቱን እየጣፈና እየጠለሰመ መጽሐፍ አድርጎ አሳይቷቸዋል፡፡ በቃሉም ጨኸ እየሰበከ ሳይጮኽም ቀርቦ እንደባለቅኔ እያሾከሾከ ምስጢሩን ሁሉ በጆሯቸውና በዓይናቸው አጥግቧቸዋል፡፡ ይልቁንም ጽልሙታን ከዋክብት የተባሉ የደቂቀ ሴትን አለቆች እነ ስማዝያ ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ በመንገርና በማሳየት ማርኳቸዋል፡፡ ሄኖ.19፣22-25 እስመ ኢተወልደ ሰብእ ለዘከመዝ ግብር ከመ ያጽንዑ ሃይማኖቶሙ በቀለም ወበረቅ፡፡ እስመ ኢተፈጥረ ሰብእ ዘእንበለ ከመ መላእክት ከመ ይኩኑ ጻድቃነ ወንጹሓነ፡፡ ፊደል ፈደለ ጻፈ ቆጠረ ለየ መረጠ ይላልና ፊደል ከዚህ ይወጣል፡፡ ልዩ ምርጥ ማለት ነው፡፡ የግእዝ ቋንቋ ስር መሰረት የትግሬና የአማርኛም ጥንት እኒህ ናቸው፡፡ አ፣ በ፣ ገ(ጐ)፣ ደ፣ ሀ፣ ወ፣ ዘ፣ ሐ፣ ኀ(ኖ)፣ ጠ፣ የ፣ ከ(ኰ)፣ ለ፣ መ፣ ነ፣

ሠ፣ ዐ፣ ፈ፣ ጸ(ፀ)፣ ቀ(ቈ)፣ ረ፣ ሰ፣ ተ። ‹‹ሀ፣ ሐ፣ ኀ›› በአንድ ‹‹ጸ፣ ፀ›› በአንድ ‹‹ሰ፣ ሠ›› በአንድ ‹‹አ፣ ዐ›› በአንድ ሲቆጠሩ 22 ይሆናሉ። ‹‹ጳ፣ ፐ›› ሁለቱ ፊደላት ግን የተጨመሩ በኋላ ዘመን ነው። መጨመራቸውም መጻሕፍት ከተቀዱበት ምንጭ ከጽርእ ከዮናን ለማስማማት እንጂ በግእዝ ፊደላት ሕጸጽ ኖሮ አይደለም። ግእዝ የቋንቋና የፊደል ስም ሲሆን በአልፋ ‹‹አ›› እንጂ በዓይኑ ‹‹ዓ›› አይጣፍም። በዓይኑ ‹‹ዐ›› ሲጣፍ ትርጓሜው ሌላ ነው። የግእዝ ፊደሉ እንደሰው መልክ ብዙ ጊዜ በየዘመኑ ተለዋውጧል። ከፊተኞች ይልቅ የኋለኞች አሻሽለውታል። የግእዝ ፊደል ለብሉይና ለብሉይ ለሐዲስ የበቃና የተቀደሰ ብርሃን የለበሰ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ከካእብ እስከ ሳብዕ ያሉትን ካገባቸው በኋላ ነው። የአራቱ ዲቃሎች ጐ፣ ጘ፣ ኰ፣ ቈ አነባበብ እንደሚከተለው ነው። ጐ-ገወ፣ ጕ-ገወዉ (ጉኤ)፣ ጓ-ገውዋ፣ ጕ-ገወዬ፣ ጕ-ገወህ (ጉእ) እያለ ሁሉን ያሳያል። አበገደ ተለውጦ ሀለሐመ የሆነው በአባ ሰላማ ጊዜ ነው።

በጉረሮ የሚነገሩ 5 ናቸው አ፣ ዐ፣ ሀ፣ ሐ፣ ኀ

በትናጋ የሚነገሩ 4 ናቸው ገ፣ የ፣ ከ፣ ቀ

በምላስ የሚነገሩ 5 ናቸው ደ፣ ጠ፣ ለ፣ ነ፣ ተ

በከንፈር የሚነገሩ 6 ናቸው በ፣ ወ፣ መ፣ ፈ፣ ጸ፣ ፐ

በጥርስ የሚነገሩ 6 ናቸው ዘ፣ ሠ፣ ሰ፣ ጸ፣ ፀ፣ ረ ናቸው

ግእዝ ቋንቋ፣ መጻሕፍት

የዓለም ቋንቋ ሁሉ በየነገዱ ስም ሲጠራ ግእዝ ብቻ በማንም ነገድ ስም አልተጠራም በራሱ በገንዘቡ እንጂ። የብሉይ መምህራን ይልቁንም የጀርመን ሊቃውንት ወኮነ ኩሉ ምድር አሐደ ከንፈረ ወአሐደ ነገረ ያለውን ይዘው ተመርኩዘው ግእዝ የአዳም ቋንቋ ነው ይላሉ። ይህችንም ባህል ያነቃትና ያፈለቃት ከብሉይ መምህራን ያጣበቃት ሲዲ ጳውሎስ ነው። መዓልም ዮሐንስ የሚሉም አሉ። ሁለቱም ጀርመኖች ናቸው። ዳግመኛም የሐዲስ መምህራንም ወአንዘኑ ይንብቡ በልሳናት ካልዓት ያለውን ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ካለው አያይዘው ልሳናት ካልዓት ከተባሉት አንደኛው ግእዝ ነውና ከኢትዮጵያም ለፋሲካ በዓል የሄዱት የጳራቅሊጦስ ዕለት የጴጥሮስን ስብከት በግእዝ ቋንቋቸው ስለሰሙ አምነው ተጠምቀው ከ3000 አርድእት ተቆጥረዋል። አሰማማቸውም እንዲህ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ በራሱ ቋንቋ በዕብራስጥ እየጮኸ ሲሰብክ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ሁሉ በየሀገሩ ፊደል በቋንቋው በቋንቋው ያሰማል። ግእዝ በ3600 ዓመተ ዓለም ወደምድረ ካም የገቡ የነገደ ሴም ቋንቋ ነው። የግእዝም ብሉይ ከጽርእ ስለተቀዳ እንደ ጽርኡ ኢትዮጵያ ይላል እንጂ እንደ እብራይስጡ ኩሽ አይልም። ትርጓሜውም ጥቁር ጠቋራ ማለት ነው። መንግሥት ከአክሱም ወደ ዛጔ ሲያልፍ ዐማርኛም በላስቶች ዘመን የመንግሥት ቋንቋ ከመሆኑ በፊት ሴቱም ወንዱም ልጅ አዋቂው የሚናገርበት የኢትዮጵያ ጥሩ ቋንቋ ግእዝ ነበረ። ካዕብ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ ሆኖ ለብሉይ ለሐዲስ መብቃቱም ከሰላማ ወዲህ ነው። ብሉያችን የተቀዳበት ምንጩ ከሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ከጥንታዊ ጽርዕ እንደሆነ በውስጡ ያለው ጥሬ ንባብ የአህጉርና የሰው ስም ሁሉ

የጽርእ የዮናን ቃል ነውና። የአህጉር ስም ኩሽን ኢትዮጵያ፣ ባሕረ ቂሐት በማለት ፊንታ ባሕረ ኤርትራ ማለት፣ ፍሌሼትን ኢሎፍሊ፣ ዐዛን ጋዛ፣ ዐምራን ገሞራ፣ ልባኖንን ሊባኖስ፣ ሐዶቂልን ጤግሮስ ይህን የመሰለው ሁሉ የሰው ስም ያልነውም በመጨረሻው ያስ፣ያስ የሚለው ሁሉ የጽርእ ልማድ ነው። ዕብራይስጡ ሒዝቅያሁ፣ ይሻዕያህ፣ ይርምያህ ይላል እንጂ ያስ አይልም። ይልቁንም መጽሐፈ ዳንኤል ‹‹ውሊቢኖት ይሩሻለይም ዐድ ማሽያሕ ናጊድ›› ያለውን ወትትሐነጽ ኢየሩሳሌም እስከ ክርስቶስ ንጉሥ በማለቱ አለጥርጥር ያስረዳል። ክርስቶስ ማለት በጽርእ ነውና። ዳግመኛም በዚህ በእኛ ብሉይ ወደ ግእዝ ያልተመለሰ ብዙ የጽርእ ቃል እንዳለበት በጽርኡም ብሉይ ወደ ጽርእ ያልተመለሰ የዕብራይስጥ ቃል አለና። እንደዚሁም ደግሞ በእኛ ብሉይ ውስጥ ከዚያው ከጽርኡ የተቀዳ አዶናይ፣ ኤሎሄ፣ ጸባኦት ይህን የመሰለ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቃል ይገኛል። ብሉያትም ከጽርእ ወደ ግእዝ የተመለሰ ከሐዲሳት ጋራ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። የመለሳቸውም ጽርኣዊውና ጢሮሳዊው ፍሬምናጦስ ነው። የግእዙ ብሉያችን ከዕብራይስጥ ተተረጎመ የሚለው እም ጎበ አልቦ የተገኘ የሀሳብ ምኞት የሕልም እንጀራ ነው። በመኃልይም ውስጥ እንደ ዚቅና እንደ ስርዋጽ ከያሬድ በኋላ የገባ መዘምራን የሚያዜሙት መምህራን የሚተረጉሙት ጥሬነት የሌለው ትርፍ ንባብ አለ። ስሙንም ከጽርኡ ምላሽ ለይተው ዕብራይስጥ ይሉታል። እርሱ ግን ከግዕዝ በቀር እንደሌላው ጥሬ በዕብራይስጥ አይገኝምና ግእዝ እንጂ ዕብራይስጥ ሊሉት አይገባም። ዕብራይስጥ ብሎ ስም የሰጠው ከመሐል አግብቶ ያስቀመጠው ከቶ ማን እንደሆነ አልታወቀም። በጽርእ በዮናን የሌለውን ከዕብራይስጥ የማይገኘውን ዕብራይስጥ ብሎ አፍሶ ማግባት የድፍረት ድፍረት ነው። የግእዙ ብሉያት ከጽርእ ወደ አረብ ከአረብ ወደ ግእዝ የተተረጎመም አለ። ለምሳሌ የብሉይ መምህራን ስለጥበብና ስለመክብብ እንዲህ ያትታሉ። ከዕብራይስጥ ወደ ጽርእ ከጽርእ ወደ አረብ ከአረብ ወደ ግእዝ የተመለሰው ጥበብን አስቀድሞ መክብብን ያስከትላል። ከዕብራይስጥ ወደ ጽርእ ከጽርእ ወደ ግእዝ የተመለሰው ግን መክብብን አስቀድሞ ጥበብን ያስከትላል ብለው ይተርካሉ። ፍሬ ነገሩ ብሉያችን ከዕብራይስጥ አለመመለሱን ያስረዳል። የግእዝ መጻሕፍት እንደ እስራኤል ዘር ያልሄዱበትና የሌሉበት ሀገርና መንግሥት አይገኝም። ሐዲሳታችን ግን ሁለተኛ በካልእ ሰላማ ከአረብ ቋንቋ ተመልሷል። ከጽርእ በተመለሱት የጽርእ ጥሬ እንዲገኝባቸው ከአረብም በተመለሱት የአረብ ጥሬ ይገኝባቸዋል። ግእዝም ከላይ ከአዳም የነቃ ከታችም ከኖኅ የፈለቀ ሴማዊና አዳማዊ ቋንቋ ነው።

ኢትዮጵያ

ካም ኩሽን ወለደ። ኢትዮጲስ የኩሽ ሁለተኛ ስሙ ነው። ኩሽ ሳባንና አቢስን ይወልዳል። ሳባ የትግሮች አቢስ የአማሮች ሀገር ነው። ሴሞች ወደ አፍሪቃ የገቡት በኤርትራና በሕንድ ውቅያኖስ ጫፍ በሁለቱ ባሕሮች መካከል ወሰን ድንበር ሆኖ የቆመ እስያና አፍሪቃ የብስ ለየብስ ገጥመው ተያይዘው የነበሩበት ጠባብ መተላለፊያ ነበር። ኋላ ግን እስክንድር መቄዶናዊ የብሱን ቆርጦ መሬቱን ቆፍሮ ሁለቱን ባሕሮች ገጥሞና አገናኝቶ ባሕር ሆኗል። እሊህንም ነገደ ሴም ያልናቸውን ሕዝብ የነጮችና የዐረቦች ታሪክ ነገደ ዮቅጣን ሐበሻት ይላቸዋል። ዮቅጣንም የዔቦር ልጅ ነው። የሴም ዘሮች ነገደ ዮቅጣን ቀድሞ የሚኖሩት በየመን ነበር። ኢትዮጵያም ማለት ከኩሽ ሞት በኋላ በ2450 ዓመት በበጥሊሞስ ዘመን የወጣ ሐዲስ እንግዳ ጽርአዊና

ደኃራዊ ስም ነው። ፪ ሊቃናት ብሉያትን ከዕብራኒ ወደ ዮናኒ ሲመልሱ ዕብራስጡ ኩሽ የሚለውን የኩሽን ስም ሁሉ ኢትዮጵስ ስላሉት በዚህ ምክንያት ከግብጽ ወዲህ ያለው የኩሽ ሀገር ሁሉ ኢትዮጵያ ተብሏል። በላስቶች ዘመን ነብሪድ ይሥሐቅ ከዐረብ ወደ ግእዝ የመለሰው ክበረ ነገሥት ግን ኩሽን ኩግ፡ ኩሳ፡ አክናሁስ ብሎ ኢትዮጲስን የአክናሁስ ልጅ ይለዋል። የመላ የግምት የነሲብ አነጋገር ነው። ክብረ ነገሥት ከመጽሐፍ ቅዱስ አይቀድምምና። የአፍሪቃ ሰዎች መጥቆራቸው ኢትዮጵያም መባላቸው ያልተማሩ ሰዎች እንደሚሉት የካም ዘር በመሆን አይዶለም። ሄኖክ ያያቸው 12ቱ መሳክወ ፀሐይ ከመንፈቀ ሰማይ ወዲህ ወደ ደቡብና ወደ አዜብ በአፍሪቃ አንጻር ስለሆኑ የአፍሪቃ ሰዎች ለፀሐይ ይቀርባሉና። የራስ ቅማልና የልብስ ቅማል ከአንድ ሰው ተገኝተው ነጭና ጥቁር መሆናቸው በቦታ ምክንያት እንጂ ነው። ፍጥረት ሁሉ በፈጣሪው ትእዛዝ ያለበትን ዓለም የበቀለበትን መሬት ርስቱን መካነ ፍጥረቱን ይመስል ዘንድ ግድ እንዳለበት የታወቀ የተረዳ ነው። ካምም የሴም ባሪያ ሲባል ተገዥነትን እንጂ መልክንና የመልክን ጥቁረት አያመለክትም። ከአንድ አባት ከአንድ እናት ቀይና ጥቁር መወለዱም ከአንድ ራስ ማሽላ ነጭ ዓይነትና ጥቁር ዓይነት ፍሬ እንዲገኝ ነው። ሴቶችም ዓይናቸው የወደቀበትን ልባቸው የጎመገቦበትን በፎቶ ግራፍ ጽንስ እንዲያነሱትና ያን አስመስለው እንዲወልዱ እነሆ በላባና በያዕቆብ በጎች ይታወቃል። ቋንቋ እና ዘር ተደባልቋልና እኔ ንጹሕ የሴም ዘር ነኝ እኔ ንጹሕ የካም ዘር ነኝ ማለት አይቻልም። ስለዚህ ከሦስቱ በጸናው መናገር እንጂ ንጹሕ የዚህ ዘር ማለት አይቻልም። ነገደ እስራኤል በከነዓን ኋላ ገብተው እንደሰፈኑ ነገደ ዮቅጣንም በኩሽ ላይ ሰፍነዋል። አግዓዝያንም ተባሉ ራሳቸውን ለኩሽ ከመገዛት ነጻ ያወጡ ነጻነት ያላቸው ማለት ነው። ብሔረ ሳባን አግዓዚት ብሔረ አግዓዚ አሰኝተው የአቢስንም ክፍል ዐምሐራ አሰኝተውታል። ነጻ ሕዝብ ጨዋ የጨዋ ልጅ ማለት ነው። ያልጠራ ያልበራ እንቶ ፈንቶ ታሪክ በአዋቂዎችና በመርማሪዎች ዘንድ ያሳፍራል እንጂ አያኮራም። ኢትዮጵያን እንደ እርጎ የሚያረካትና የሚያስመካት ጃን ሆይና እቴጌም የሚያሰኛት ምንጨዋ ሲማስና ዱሯ ሲጣስ ከጥንት ጀምሮ የነበረው የነገደ ኩሽ ልብሰ መንግሥት አርድ አንቀጥቅጥ የዘውዳቸውም ፈርጥ የነጻነቷ ሽልማትና ጌጥ መንግሥተ ሳባዋ አሮጌው ካባዋ ነው እንጂ በኋላ ዘመን እንደ እጅ መንሻ ሆኖ የመጣላት የሰሎሞን ድርብ ምኒልክ የዘውዱ ቀጸላ የንግሥተ አዜብ ወርቅ ድባብ የየመን ጃንጥላ አይደለም። የአንድን ድርጊት ወይም ጉዳይ መጀመሪያ ምክንያቱንና ጊዜውን ሳይለዩ ተቀባዩን ሳያሳዩ ሸፍኖ ሸፋፍኖ ያልሆነውን የሆነ አስመስሎ መጻፍ ስህተት ነው።

የአዳም ተፈጥሮ

ጽነት፣ ኃጢአትና ሞት እነዚህ ሦስቱ የባሕርይ ሳይሆኑ ከባሕርይ ጋራ እንደፈትልና እንደሠም እንደጸምርና እንደቀለም ተስማሚነት ስላላቸው ከአፍኣ መጥተው ባሕርዩን እንደፈትል እንደጸምር ቀልመው አሳድፈው ንጣቱንና ጥራቱን አጠፉበት። እርሱም እንደ መላእክት ነጻነትና ልጅነት የልጅነት ስልጣን ስላለው ተስማሚነትን በርትዐት ጨቁኖ ከጽነትና ከኃጢአት ጋራ መዋጋት መታገል ተዋግቶና ታግሎም ማሸነፍ መጣል ምክረ ከይሲንም አለመስማት አለመቀበል ሲቻለው ወደቀ። የባሕርይም አለመሆናቸው ሊታወቅ 7 ዓመት ሙሉ በገነት ሲኖር የሐልዮና የነቢብ የገቢር ኃጢአት አልተገኘበትም። እስከ ሺህ ዓመት ያልመሉ ልጆቹ እያዩት

ከዓለመ ሥጋ ወደ ዓለመ ነፍስ ሊያርግ ነበር። ዳግማይ አዳም የተባለው ልጁ በትንሳኤ ረቆ ታድሶ ወንድሞቹ እያዩት እንዳረገ። የአዳም ኃጢአት ከአባት ወደልጅ መውረዱ አዳምን መስለው ተከትለው በሚሰሩት ብቻ ነው። ይኸውም ቡርክት አንቲ እም አንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ በተባሉት በእናትና ልጁ ይታወቃል። ጽድቁም እንደ ኃጢአት ነው። ከባሕርይ ተከፍሎ በመወለድ አይወረስም። አባትን መስሎ በመስራት ብቻ እንጂ።

ገቢር ተገብሮ

ግእዝና ሳድስ ካዕብና ሳብዕ ሣልስና ኃምስ ሱቱፋን ናቸው ይወራረሳሉ። ይኸውም በገቢር ተገብሮ ነው። በገቢር አንቀጽ ሞዐ ጸረ ወጸላኤ ሐነጸ ቤቶ ወጽርሑ ያለውን በተገብሮ ተሞዐ ጸር ወጸላኢ ተሐንጸ ቤቱ ወጽርሑ እያለ መሄዱን መናገር ነው። ራብዕ ኃምስና ሳብዕ ግን ተፈቃቃሪ ነው። መልኩንና ድምጹን ሳይለውጥ ሁሉን ይከታል። ይህም በልዐ ሥጋ ወመና ተበልዐ ሥጋ ወመና ማለቱን ያሳያል። ቀሠመ ጽጌ ወፍሬ ተቀሥመ ጽጌ ወፍሬ። አኀዘ ዶርሆ ወአንቆቅሑ። ተእኀዘ ዶርሆ ወአንቆቅሑ እያሰኙ በገቢር ተገብሮ ይከታሉ።

አኃዝ

ዕብራውያን እልፍ የሚሉት እንደ አረቦች አሥሩን መቶ ነው። የግእዙም እልፍ ጥንታዊው እንደዚህ ነበረ። ጥንታዊው የግእዝ አኃዝ እንደ ሱርስት እንደ ዕብራይስጥ እንደ ጽርእ እንደ ቅብጥ ያው ራሱ ፊደሉ እንጂ እንደአረብና እንደላቲን ሌላ ቁጥር ልዩ ዓይነት አኃዝ አልነበረውም። አኃዝ ከአንድ እስከ ምእልፊት ያለ የቁጥር ሁሉ ጠቅላይ ስም ነው።

አ- አሐድ	ለ- ሠላሳ
በ(ጸ)- ክልኤት	መ- አርብዓ
ገ(ጐ)- ሠለስት	ነ- ኀምሳ
ደ- አርባዕት	ሠ- ስሳ
ሀ- ኀምስት	ዐ- ሰብዓ
ወ- ስድስት	ፈ(ፐ)- ሰማንያ
ዘ- ሰብዓት	ጸ(ፀ)- ተስዓ
ሐ(ኀ፣ኍ)- ሰምንት	ቀ(ቈ)- ምእት
ጠ- ተስዓት	ረ-በ ምእት
የ- አሥርት	ሰ-ገ ምእት
ከ(ኰ)- ዕሥራ	ተ-ደ ምእት

በኋላ ዘመን ግን ከሰላማ ጋራ የነበሩ ቅብጣውያንና ጽርዓውያን አስቀድመን እንደተናገርነ የግእዝን ፊደል ተራውን አፋልሰው ሀለሐመ አድርገው አላኪያውና አላምሳያው አለፈርጹ አላጣማጹ እያቆራኙ ስለጣፉት እነሆ ከአሐዱ እስከ እልፍ ያለው አኃዝ ከፎ በስተቀር ሁሉም የጽርእና የቅብጥ ፊደል ነው። ፷ኤል ብሎ መጻፍ አይገባም። የንባቡና የትርጓሜው የምስጢሩ ጣዕም ይበላሻል። መዘርጋት ብዛትንና ስንትነትን እንደነዶና እንደ ችቦ አስሮ ሰብስቦ የሚያሳይ **የጅምላ ቁጥር** ነው። ምሳሌ 1፣2፣3። መተርተር ስንትነታቸው ከታወቀ ከብዙዎች ማኽል ስንተኛነትን ለይቶ የሚያሳይ **የተራ ቁጥር** ነው። ምሳሌ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ። መክፈል የክፍሎችን ስም እንደተራ ቁጥር እየለየ በየማዕርጉ የሚያሳይ **ክፍላዊ ቁጥር** ነው። ምሳሌ መንፈቅ፣ ሣልሲት ራብዒት። ማጠፍ ጅምላውን ቁጥር አጥፎ ደርቦ እያሳየ በመንታ መንገድ የሚወስድ **የአጸፋ ቁጥር** ነው። ምሳሌ አሐዳት አው ካዕበተ አሐዱ አንድ እጥፍ፣ ክልኤታት ወይም ካዕበተ ክልኤቱ ሁለት እጥፍ እያለ ይሄዳል። መጠቅለል እንደ አራቱ ክፍሎች አኃዝ ሳይኖረው በቅጽልነቱ ማነስና መብዛት ሕጸጽና ምልዓት የሚያሳይ የአኃዝ ቅጽሎች ሰብሳቢና ከታች የሚሆን **መድበል ቁጥር** ነው። ያውም ጎዳጥ፣ ብዙኅ እና ይህን የመሰለ ነው።

የወንዶች ጅምላና የሴቶች ጅምላ ቁጥር በአኃዝ አንድ በንባብ ልዩ ነው።

አኃዙ	የወንዶች	የሴቶች
፩	አሐዱ	አሐቲ
፪	ክልኤቱ	ክልኤቲ
፫	ሠለስቱ	ሠላስ
፬	አርባዕቱ	አርባዕ
፭	ኀምስቱ	ኀምስ
፮	ስድስቱ	ስሱ
፯	ሰብዓቱ	ሰብዑ
፰	ስምንቱ(ሰመንቱ አይባልም)	ሰማኒቱ
፱	ተስዓቱ	ተስዑ
፲	ዐሥርቱ(ዐሠርቱ አይባልም)	ዐሥሩ
፲፩	ዐሥርቱ ወአሐዱ	ዐሥር ወአሐቲ
፲፱	ዐሥርቱ ወተስዓቱ	ዐሥር ወተሰዑ
፳	ዕሥራ	ዕሥራ

፴	ሠላሳ	ሠላሳ
፵	ምእት	ምእት
፻	እልፍ	እልፍ
፲፻	ዐሥርቱ እልፍ (አእላፍ)	
፻፻	አእላፋት	
፲፻፻	ትእልፊት	
፻፻፻	ምእልፊት	

የወንዶችና የሴቶች ተራ ቁጥር እንደሚከተለው ነው፡፡

የወንዶች	የሴቶች
አሐዳይ፡ አሐድ፡ አሐዳዊ	ኣሐ(ድ)ት፡ አሐቲ
(ግእዝ፡ ጥንት፡ ቀዳሚ፡ በኵር)	(ቀዳሚት፡ ቀዳማዪት)
ካልእ፡ ካልኣይ፡ ዊ	ካልእት፡ ካልኣዪ(ዊ)ት
(ካዕብ፡ ዳግም፡ ዳግማይ፡ ዊ)	(ዳግምት፡ ሚት፡ ማዪት)
ሣልስ፡ ሣልሳይ፡ ዊ	ሣልስት፡ ሣልሳዊ(ዪ)ት
ራብዕ፡ ራብዓይ፡ ዊ	ራብዕት፡ ራብዓዊ(ዪ)ት
ኃምስ፡ ኃምሳይ፡ ዊ	ኃምስት፡ ኃምሳዊ(ዪ)ት
ሳድስ፡ ሳድሳይ፡ ዊ	ሳድስት፡ ሳድሳዊ(ዪ)ት
ሳብዕ፡ ሳብዓይ፡ ዊ	ሳብዕት፡ ሳብዓዊ(ዪ)ት
ሳምን፡ ሳምናይ፡ ዊ	ሳምንት፡ ሳምናዊ(ዪ)ት
ታስዕ፡ ታስዓይ፡ ዊ	ታስዕት፡ ታስዓዊ(ዪ)ት
ዓሥር፡ ዓሥራይ፡ ዊ	ዓሥርት፡ ዓሥራዊ(ዪ)ት

በወንዶች ዓሥር ወኣሐድ ወካልእ ወሣልስ እያለ እስከ ታስዕ በሴቶችም እንደዚሁ ነው፡፡ ከዚያ በላይ ዕሥራዊ፡ ት፣ ሠላሳዊ፣ ምእታዊ፣ እልፋዊ እያለ እስከ ምእልፊት ይሁዳል፡፡ ሲበዛም አበዛዙ እንደሚከተለው ነው፡፡

ቀደምት፡ ቀዳም(ማው)ያን፡ ያት

ደኅርት፡ ካልኣን፡ ኣት፡ ልኣው(ይ)ያን፡ ያት

(ዳግማን፡ ት፡ ዳግማው(ይ) ያን፡ ያት)

ሣልሳን፡ ት፡ ሣልሳው(ይ) ያን፡ ያት

ራብዓን፡ ት፡ ራብዓይ(ው)ያን፡ ያት

ኃምሳን፡ ት፡ ኃምሳው(ይ)ያን፡ ያት

ሳድሳን፡ ት፡ ሳድሳው(ይ)ያን፡ ያት

ሳብዓን፡ ት፡ ሳብዓይ(ው)ያን፡ ያት

ሳምናን፡ ት፡ ሳምናው(ይ)ያን፡ ያት

ታስዓን፡ ት፡ ታስዓይ(ው)ያን፡ ያት

ዓሥራን፡ ት፡ ዓሣራው(ይ)ያን፡ ያት

የክፍል ቁጥር የሚባለው ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መንፈቅ፡ ንፍቅ፡ ካልዒት= እኩል፡ እኩሌታ፡ ሁለተኛ እጅ

ሣልሲት= ሦስተኜት፡ ሦስትያ፡ ሚሦ

ራብዒት= ርቢት፡ አራትያ፡ ርቦ፡ ሩብ

ኃምሲት= አምስተኜት፡ አምስትያ፡ አምሾ

ሳድሲት= ስድስተኜት፡ስድስትያ

ሳብዒት= ሰባተኜት፡ ሰባትያ

ሳምኒት= ስምንተኜት፡ ስምንትያ

ታስዒት= ዘጠነኜት፡ ዘጠኒያ

ዓሥሪት= አሥረኜት፡ አሥርያ፡ ከአሥር አንድ

ሲበዛም ካልኢታት፡ ሣልሲታት፡ ዓሥሪታት ያሰኛል፡፡ ከአሥር በላይ ግን ክፍልነቱን ገልጦ ዐሠርቱ ወአሐዱ ክፍል፡ ዕሥራ ወክልኤቱ ክፍል እያለ በጅምላና በየዋህ ቁጥር ይዜዳል፡፡ በጅምላም አካሄድ ሲነገሩ ስማቸው እጅ፡ ክፍል እየተባለ ስንትነታቸውን ይገልጣል፡፡

ምእሕዲት= አንድ እጅ፡ አንድ ክፍል፡ እጅና ክፍል አንድ ወገን ነው

ምክልኢት፡ ምክብዒት= ሁለት እጅ፡ እጥፍ፡ድርብ

ምሥልሲት= ሦስት እጅ፡ ሦስት ክፍል

ምርብዒት= አራት እጅ

ምኀምሲት= አምስት እጅ

ምስድሲት= ስድስት እጅ

ምስብዒት= ሰባት እጅ

ምስምኒት= ስምንት እጅ

ምትስዒት= ዘጠኝ እጅ

ምዕሥሪት= ዐሥር እጅ

ሲበዙም እጅነታቸው እጥፍ ሆኖ ምእሕዲታት ምዕሥርታት ይላል፡፡

በጥሬነታቸው የክፍልን ሁኔታ የሚያሳዩ ጥሬዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ትእሕ(ድ)ዲት፡ እሕድና= አንድነት፡ አንደኛነት

ትክልእት፡ ክላኤ= ሁለትነት፡ ሁለተኛነት

ትሥልስት፡ ሥላሴ= ሦስትነት፡ ሦስተኛነት

ትርብዕት፡ ርባኤ= አራትነት፡ አራተኛነት

ትኀምስት፡ ኀማሴ= አምስትነት፡ አምስተኛነት

ትስድስት፡ ስዳሴ= ስድስትነት፡ ስድስተናነት

ትስብዕት፡ ስባኤ= ሰባትነት፡ ሰባተኛነት

ትስምንት፡ ስማኔ= ስምንትነት፡ ስምንተኛነት

ትስዒት፡ ትሳኤ= ዘጠኝነት፡ ዘጠነኛነት

ትዕሥርት፡ ዕሣሬ= አሥርነት፡ አሥረኛነት

የዕለታት አኃዝ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

እሑድ፡ አሐድ፡ አሚር= አንድ፡ አንደኛ፡ መባቻ፡ መጀመሪያ

ሰኑይ፣ ሠሉስ፣ ረቡዕ፣ ኀሙስ፣ ሰዱስ፣ ሰቡዕ፣ ሰሙን፣ ተሰዐ፣ ዐሡር ዐሥረኛ እያልክ ሁሉን እንዲህ እያልክ ፍታ። ‹‹አመ›› እና ‹‹በ›› ሲጨመሩባቸው መድረሻቸውን እየዘረዘሩ አመ ዐሡሩ ወአሚሩ አመ ዕሥራ ወሰኑዩ እያሰኙ እስከ ሠላሳ ይሄዳሉ።

የጊዜያት አኃዝ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርበዋል

እሕድ፡ ምእር= እሕደ፡ ምእረ =አንድ ጊዜ ፡በአንድ ጊዜ ይላል

ክልእ= ክልአ= ሁለት ጊዜ፡ በሁለት ጊዜ

ሥልስ= ሥልሰ= ሦስት ጊዜ፡ በሦስት ጊዜ

ርብዕ= ርብዐ= አራት ጊዜ፡ በአራት ጊዜ

ኀምስ= ኀምሰ= አምስት ጊዜ፡ በአምስት ጊዜ

ስድስ= ስድሰ= ስድስት ጊዜ፡ በስድስት ጊዜ

ስብዕ= ስብዐ= ሰባት ጊዜ፡ በሰባት ጊዜ

ስምን= ስምነ= ስምንት ጊዜ፡ በስምንት ጊዜ

ትስዕ= ትስዐ= ዘጠኝ ጊዜ፡ በዘጠኝ ጊዜ

ዕሥር= ዕሥረ= ዐሥር ጊዜ በአሥር ጊዜ እያልክ ሁሉንም መፍታት ነው። ዳግመኛም አሐደ ጊዜ፡ ክልኤተ ጊዜ፡ ሰብዓተ ጊዜያተ እያሰኘ በጅምላ ቁጥር ይነገራል። ከ11ም በላይ እንደዚሁ ነው።

የእጥፍ ቁጥር ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

አሐዳት፡ ካዕበተ አሐዱ= አንድ እጥፍ

ክልኤታት፡ ካዕበተ ክልኤቱ= ሁለት እጥፍ

ሠለስታት፡ ካዕበተ ሠለስቱ= ሦስት እጥፍ

አርባዕታት፡ ካዕበተ አርባዕቱ= አራት እጥፍ

ኀምስታት፡ ካዕበተ ኀምስቱ= አምስት እጥፍ

ሰድስታት፡ ካዕበተ ስድስቱ= ስድስት እጥፍ

ሰብዓታት፡ ካዕበተ ሰብዓቱ= ሰባት እጥፍ

ሰምንታት፡ ካዕበተ ሰምንቱ= ስምንት እጥፍ

ተስዓታት፡ ካዕበተ ተስዓቱ= ዘጠኝ እጥፍ

ዐሥርታት፡ ካዕበተ አሠርቱ= አሥር እጥፍ

ዐሥርታት ወአሐዳት ወይም ካዕበተ ዐሥርቱ ወአሐዱ አስራ አንድ እጥፍ፣ ዕሥራት ወይም ካዕበተ ዕሥራ፣ ሠላሳት ወይም ካዕበተ ሠላሳ እያለ እስከ ምእልፊት ይሄዳል። የጊዜም አሐዶች እሕዳት፣ ምዕራት ሲባሉ እንደ ምእሕዲታት ዕጥፍ ያሰኛሉ። ክልኣት፣ ሥልሳት፣ ርብዓት፣ ኀምሳት፣ ስድሳት፣ ስብዓት፣ ስምናት፣ ትስዓት፣ ዕሥራት እያሰኙ ሁሉም እጥፍ ይሆናሉ።

ሳድስ ውስጠ ዘ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።

እሑድ፡ ዋሕድ፡ (ዳን፡ ት፡ ሕድ)= አንድ የሆነ፡ አንዲዮ እያልክ ሁሉን እንዲህ ፍታ

ክሉእ፡ (ኣን፡ ኣት፡ ልእት)= ሁለቶ፡ ሁለቲዮ

ምንትው፡ (ዋን፡ ዋት፡ ቱት)= መንቶ፡ መንቲያ

ሥሉስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ልስት)= የተሠለሰ፡ ሦስቶ፡ ሦስቲዮ

ርቡዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ብዕት)= አራቶ፡ አራቲዮ

ኀሙስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ምስት)= አምስቶ፡ አምስቲዮ

ስዱስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ድስት)= ስድስቶ

ስቡዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ብዕት)= ሰባቶ፡ ሰባቲዮ

ስሙን፡ (ናን፡ ናት፡ ምንት)= ስምንቶ

ትሱዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ስዕት)= ዘጠኞ፡ ዘጠኝዮ

ዕሡር፡ (ራን፡ ራት፡ ሥርት)= ዐሥሮ፡ ዐሥሪዮ ብሎ በዚሁ ይቆማል። ከ10 አይወጣም።

የመስፈሪያና የሚዛን እጥፍ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።

መእሕድ= ሁለቱን አንድ የሚያደርግ

መክልእ= አራቱን አንድ የሚያደርግ

መሥልስ= ስድስቱን አንድ የሚያደርግ

መርብዕ= ስምንቱን አንድ የሚያደርግ

መኀምስ= ዐሥሩን አንድ የሚያደርግ

መስድስ= ዐሥራ ሁለቱን አንድ የሚያደርግ

መስብዕ= ዐሥራ አራቱን አንድ የሚያደርግ

መስምን= ዐሥራ ስድስቱን አንድ የሚያደርግ

መትስዕ= ዐሥራ ስምንቱን አንድ የሚያደርግ

መዕሥር= ሃያውን አንድ የሚያደርግ

ሁለተኛ መንገድ መእሕድ ብዙውን አንድ የሚያደርግ፣ መክልእ አንዱን ሁለት፣ መሥልስ አንዱን ሦስት፣ መዕሥር አንዱን አሥር የሚያደርግ እያሉ ተከፋይ አድርጎ ሲፈቱት ዕጥፍነቱ ቀርቶ ዝርዝርና ብትን ይሆናል።

ደምላይና ጠቅላይ መድበላዊ ቁጥር የሚባለው ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ኩሉ= ሁሉ፣ ምሉእ፣ ፍጹም፣ ብዙኅ፣ ንሕኑሕ፣ ዝሕዙሕ፣ ፍድፋድ፣ ንዑስ፣ ሕጹጽ፣ ጎዳጥ፣ ውጎድ፣ ንስቲት፣ ሕቅ፣ መጠን፣ አምጣን፣ ዐቅም ናቸው። ኩሉ ሲዘረዘር ኩሉ፡ ኩላ፡ ሎሙ፡ ሎን፡ ኩልከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ ኩልየ፡ ኩልነ እያሰኘ ጠብቆ ይነገራል። አንዳንድ ባለ አገባቦች ግን አንተ፣ አንቲ፣ አነ ባለው በእነዚህ በሦስቱ የለውም ብለው ያውጃሉ።

ሥነ ጽሑፍ

ያልተቀጻው ብራና ወረቀት አንዳንዱ ጥቅል ሰሌዳ ወይም ሉሕ ይባላል ዝርግ ማለት ነው። ከዚያ የሚቀዳው አንዳንዱ ክፍል ሳይታጠፍ ቅጽ ሲታጠፍ ቅጠል ይባላል። ቅጠል የሌለው እኩሌታ ቅጽ ሲሆን ጎላፍ ይባላል። 4ቱ ወይም 5ቱ እየታጠፈ በአንድነት ሲታሰር ጥራዝ ይባላል። ውግ ያለበት ክፍል ግራና ቀኙ ጠርዝ መግለጫውና መግለጫው ግልየት ላይኛው አርእስት ታችኛው ጎዳግ መካከለኛው ዓምድ ይባላል። እጥፋቱን እንደ ወንዝ አማክሎ ወደጥራዝ ያለው ማዶና ማዶው ምስማክ ይባላል መከዳ ማለት ነው። በመካከልም በእያንዳንዱ ውግ ፊት ውስፌውና እርሳሱ ያለፈበት ሰንበር ሰንበሩ ሲራክ በፊደልና በፊደል መካከል ያለው ክፍት ክፍት ኖኅት ይባላል። በየፊደሉ ውስጥ ያለው ከርስ ይባላል።

ሥርዓተ ነጥብ

. ነጥብ፣ ነቁጥ፣ ማጥበቂያ

፡ ንዑስ ነጥብ

፣ ወይም ÷ ንዑስ ሠረዝ

፤ ዓቢይ ሠረዝ

። ዓቢይ ነጥብ

... ነጠብጣብ ከእያንዳንዱ ምእራፍና አንቀጽ ፍሬው ተለቅሞ በቀሪው ቃል ፈንታ ይገባል።

ሥርዓተ ንባብ

ለንባብ ትምህርት ለስልቱና ለማዕርጉ እንደ5ቱ ጸዋትወ ዜማ 5 ክፍል አለው። እኒህም ቁጥር፣ ግእዝ፣ ውርድ፣ ዓቢይ፣ ድጋም ናቸው። ቁጥር እንደመንፈቀቅ ግእዝ እንደ መዳኽ ነው። እነዚህ ሁለቱ በሳር በስንጥር ይነገራሉ። ቁጥር በኖኅትና በኖኅት መካከል ያለውን የእያንዳንዱን ፊደል ራስ ራሱን በሳር እየነኩ 1፣ 2፣ 3 እንደማለት ሁሉ ስም ስሙን ለይቶ መጥራት ነው። ግእዝ ከነቁጥ እስከ ነቁጥ በእያንዳንዱ ስክ ያሉትን ፊደሎች እንደመሠረዝ ሳሩን በላያቸው እያሣለፉ በቅርብ በቅርቡ ማጋጠም ነው። ውርድ ዘርፍና ባለቤት ሳቢና ተሳቢ በማዛረፍና በማናበብ የሚወድቅና የሚነሳ የሚጠብቅና የሚላላ ቀለም ለይቶ በሐዘንዚን ቃል እየጮሁና እያለፉ እየተደገፉ ማንበብ ነው።ዓቢይ ንባብ ዋናው ንባብ ነው። ድጋም ከደጋሚው በቀር ሌላ የማይሰማው ስለሆነ በሩጫ አካሄድ ይመሰላል።

ሰዋስው

ሰዋስው ማለት ዘይቤው መሰላል ማለት ነው። እሙን ትርጓሜው ግን የግእዝ ቋንቋ አዋጅ የአሰካኩና የአጻጻፉ የአነጋገሩ ፈርጅ የንባቡ ሁሉ እጅና ፍንጅ አስተሳሰሩና አፈታቱ ተለይቶ የሚታወቅበት የትምህርት ደንብ ፍርድና አገባብ ማለት ነው።

አባት ዘር

ነጠላ ግስን ከነርባው የሚያስገኝ ጥሬ ዘርን ሁሉን የሚወልድ በሊዕ፣ ሰትይ፣ ጸጊብ፣ ሰኪር፣ መዊት ሐይው እያለ በሦስት ፊደል በቅሎ የሚሄድ ይህን የመሰለ ቃል አባት ዘር ይባላል። አባትነቱም አዳምን ይመስላል። አባት ዘር እርሱ ራሱ እንደ ሥር ሆኖ ሌላውን ፍሬቃል ቢያስገኝ እንጂ ለእርሱ አስገኝና አባት የለውም። ሁለተኛም ሥረ ነገር መሰረተ ቃል ስለሆነ አርእስት ይባላል። ሦስተኛም አጉል አንቀጽ ስለሆነ ንዑስ ይባላል። በአፈ ታሪክም የቀድሞ መምህራን ዘር ሳያስቀድሙ አይገሡም ነበር ይባላል። ቀቲል ቀቲሎት፣ ቀድሶ ቀድሶት እያለ ‹‹ት››ን እየጨመረ መሄዱ ለመዘርዘርና ለማዛረፍ ለማብዛት ነው። በዝርዝር ጊዜ ቀቲልሁ ቀቲሎቱ ቀድሶሁ ቀድሶቱ ቢል እንጂ ቀቲሉ ብሂሉ ብሎ በዘመድ አይዘረዝርም። ይህ በ ‹‹ለ›› ሲያዛርፍ ነው። በ ‹‹ዘ›› እና በግእዝ ሲያዛርፍ ግን እንዳለ ይገባል። ይህም ቀቲል ዘዳዊት፣ ዘዳዊት ቀቲሎት፣ ቀቲለ ዳዊት፣ ቀቲሎተ ዳዊት ጎልያድሀ እያለ ሌላውን ሁሉ ያሳያል። ብሂሉ ለዳዊት፣ ብሂሎት ዘዳዊት አለማለቱን ያሳያል። ሲያበዛና ሲዘረዝርም ሀልዎታት፣ ሀልዎታቱ፣ ሀልዎታቲሁ ያሰኛል። ቀቲል ቀቲልሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ የ፣ ነ ብሎ በአሥር ይረባል። ወይም ቀቲሎት ቀቲሎቱ ቀቲሎታ፣ ቶሙ፣ ቶን፣ ቀቲሎትከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ትየ፣ ትነ የገቢር ተሳቢም ሲሆን ቀቲለ ቀቲሎተ ቀቲሎቶ፣ ተከ፣ ተኪ፣ ተክሙ፣ ተክን፣ ተነ እያሰኘ እነዚህን ስድስቱን ብቻ ይለውጣል። የቀሩትም የአራቱ አዕማድ አርእስት አቅትሎሁ ቱ፣ ተቀትሎሁ ቱ፣ ተቃትሎሁ ቱ፣ አስተቃትሎሁ ቱ እያሰኘ በ10 በ10 መደብ ይረባል። አንደኛውን መንገድ ከጥቂት ሰዎች በቀር ሁሉ አያውቀውም።

መራኁት

ዘርና ግስ የሚነሱባቸው ፊደላት ወይም ቀለማት 5 ናቸው። መክፈቾች ማለት ነው። እሊህም ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ እና ሳብዕ ናቸው። ዘርና ግስ በእነዚህ ብቻ ቢነሱ እንጂ በካዕብ በሣልስ አይነሡም። የዘር መድረሻ ወይም መጨረሻ 2 ናቸው። ሳድስና ሳብዕ ይህም ነዊም ነቂህ፣ ሰብሖ ዘምሮ እያለ በእነዚህ ብቻ መድረሱን ያሳያል። ግስ ግን ምንም እንደዘር ባለ5 መነሻ ቢሆን ባለአንድ መድረሻ ነውና ቀደሰ፣ ባረከ፣ ሤመ፣ ጥሕረ፣ ሖረ እያለ በግእዝ ብቻ ይጨርሳል።

ነባር

ዘርነት የሌለው ከዘር ከአንቀጽ የማይገኝ የቋንቋ ቤተሰብ እየሆነ በውጥንቅጥነት የሚገኝ ጥሬ ቃል ሁሉ ነባር ይባላል። ትርጓሜውም የማይፈልስ የማይናወጥ የማይጠፋ የማይለወጥ ስም ማለት ነው። ነባር ስም ሁሉ እንደዘር ሆኖ ሊረባ ሊገሠሥ አንቀጽ ሊወጣለት ይችላል። ሰብእ ብሎ ተሰብአ፣ ወይን ብሎ አውየነ፣ እብን ብሎ አዕበነ፣ ክርስቲያን ብሎ ከረስተነ፣ ደብተራ ብሎ ደብተረ ተደብተረ እያለ ያሳያል። ከነባር ስም የሚወጣ አንቀጽ ነባር ግስ ይባላል። ከተጸውዖ ስም በቀር የማይበዛና የማይረባ የማይገሠሥ ስም የለም። ነባር መባሉም ስርና ምንጩ ስላልታወቀ እንጂ ዘር የሌለው ሆኖ አይደለም። ለጥሬ ለነባር እንደዘር እንደግሥ የፊደል ውሳኔ የለውም። ከግእዝ እስከሳብዕ ባሉት በ7ቱ ሁሉ ተነስቶ ከግእዝ በቀር በ6ቱ ሁሉ ይጨርሳል። አንቀጽ የሌላቸው አገባቦችና መጠሪያ ስሞች ፊደልና አኃዝም አንዳንድ ቅንጣት ዘሮች ስለሆኑ ቁጥራቸውና ክፍላቸው ከነባሮች ነው።

ግስ

ግስ ማለት የቋንቋ ጓዝ ማለት ነው። ሰማይ ከነግሱ ምድር ከነልብሱ እንዲሉ ከነጓዙ ሲሉ። ነጠላ ግስ ከ2 ፊደል አይወርድም ከ4 ፊደል አይወጣም። ልማድና ባዕድ ሲጨመር ግን 5ም 6ም 7ም ይሆናል። ከ7 በላይ ግን አይወጣም። በግስ ያሉ ዓመሎች 3 ናቸው። ‹‹አ›› እና ‹‹ሀ›› አንድ ወገን፣ ‹‹ወ›› እና ‹‹የ›› ሁለት፣ ደጊመ ቃል ሦስት ናቸው።

‹‹አ›› እና ‹‹ሀ››፦ በመካከል ያሉበት ግስ የቀተለ ሠርዌ በግእዝ ይነሳ የነበረውን ለውጦ ሳድስ ያደርጋል። ይህም ለአከ ብሎ ልኢክ ይላል ለሐከ ብሎ ልሐኩ ይላል። ጸዐለ ብሎ ጽዒል መሀረ ብሎ ምሂር እያለ ሌላውን ሁሉ ያሳያል። ጕሕቄ ብሎ ጕሕቍ ይላል። አ እና ሀ ማዕከል ሆነው እንዲህ ካላወጡት በቀር ዘርና አንቀጽ በሳድስ ፊደል አይነሳም። በክህለም ያለ ‹‹ሀ›› እስከ 80 ሠራዊት በካልዓይ ሁሉ ይታጣል። ይህም ክህለ ይክል፣ ክህልከ ትክል፣ ክህልኩ እክል እያለ ጭራሽ መታጣቱን ያሳያል። የብህለም አካሄድ እንደ ክህለ ነው። ይብል፣ እብል፣ ንብል እያለ ይሄዳል። አ እና ሀ መድረሻ ሲሆኑ በሰባቱም አርእስት ቅድመ መድረሻውን ሳድስ ያደርጉታል። ባልሐ፣ ጸውዐ፣ ፈርሀ፣ ገፍትዐ እያለ ሌላውን ሁሉ ያሳያል። ሌላው በሦስት ፊደል ግስ በቀተለ ቤት በሣልሳይ አንቀጽ ቅድመ መድረሻውን ራብዕ ያደርጉታል። ይግባዕ፣ ይብላዕ፣ ይባእ፣ ይጸዕ እንዲል።

‹‹ወ›› እና ‹‹የ››፦ ራሳቸውን እየጎረዱና እየዋጡ ወይም በጥፋት እየታጡ እየተዋጡ ለሌሎቹ መወልጣነ ድምጽ ይሆናሉ፡፡ የ‹‹ወ›› ካዕብና ሳብዕ ማድረግ የ‹‹የ›› ሣልስና ኃምስ ማድረግ ነው፡፡ ‹‹ወ›› መድረሻ ወይም መጨረሻ ሲሆን ካልአዩ ሳድስ ይሆን የነበረውን ጎርዶ ካዕብና ሳብዕ ያደርጋል፡፡ ይህም በገቢር ዘረወ ይዘሩ፣ ፈነወ ይፈኑ ማለቱን በተገብሮም ተዘርወ ይዘሮ፣ ተፈነወ ይትፈኖ ማለቱን ያሳያል፡፡ ደጊም ሲሆን በጭራሽ አይጎርድም ይህም ከወወ ይከውው፣ ጼወወ ይጼውው ይላል፡፡ ሳድስ ቅጽሉንም መካከሉ ካዕብ ይሆን የነበረውን ሳድስ ያደርጋል፡፡ ይህም ዝርው፣ ሥርው፣ ፍንው፣ ጺውው፣ ምጥው ማለቱን ያሳያል፡፡ ‹‹ወ›› ለሦስት ፊደል ግስ መነሻ ሲሆን ጥሬ ዘሩ አራት ፊደል ይሆን የነበረውን ጎርዶ ሦስት ፊደል ብቻ ያደርጋል፡፡ ይህም ወጥሐ ብሎ ሞጥሕ፣ ወደየ ብሎ ሙዳይ ማለቱን ያሳያል፡፡ ሳቢ ዘሩ ግን ልደት፣ ጸአት፣ ድቀት፣ ርደት እያለ ወይም ሳይጎርድ ውግረት፣ ውጎደት እያለ ይሄዳል፡፡ ሣልሳዩንም ከቀደሰና ከባረከ ቤት በቀር ሁሉን ይጎርዳል፡፡ ይህም ወሀበ ይውህብ የሀብ ይደቅ የሐዝ ማለቱን ያሳያል፡፡ ‹‹የ›› መድረሻ ወይም መጨረሻ ሲሆን ካልዓዩ ሳድስ ይሆን የነበረውን ጎርዶ ሣልስ ያደርጋል፡፡ የአርእስቱም ማዕከል ሣልስ ይሆን የነበረውን ለውጦ ሳድስ ያደርጋል፡፡ ይህም ሐቅይ፣ ሐቀየ የሐቂ፣ ሰቅይ ሰቂ ይሰቂ እያለ ሌላውን ሁሉ ያሳያል፡፡ በቦዝ አንቀጽም እንዲሁ ነው ሣልስ ይሆን የነበረውን ሳድስ ያደርጋል፡፡ ወርእያ ደንገጸት በሊያ ወሰትዮ አዕሚቆ ወነልዮ እንዲል፡፡

ደጊመ ቃል፦ ሁለተኛው ፊደል ሦስተኛውን ውጦ እየጠበቀ የፊደል ግሥ ይሆናል፡፡ ይህም ጠቢብ ጠበ፣ ነቢብ ነበ፣ ነዲድ ነደ፣ ቆሪር ቆረ እያለ መሄዱን ያሳያል፡፡

ልማድ

በኃላፊ አንቀጽ ላይ ተውሳክ እየሆኑ የግስን ጾታ የአንቀጽን ርባታ በየቤቱና በየሠራዊቱ ለይተው የሚመሩና የሚያስኬዱ የግስ ልማዶች እንደ አምስቱ አዕማድ 5 ናቸው፡፡ አ፣ ተ፣ አስተ፣ አን፣ አስ ናቸው፡፡ ‹‹አ›› እነ ፈለሰን በሚመስሉ በአንጉል ግሶች ላይ ሲገባ በአንድ ጊዜ የማድረግና የማስደረግ ልማድ ይሆናል፡፡ ይህም አምጽአ ብሎ አመጣ አስመጣ ማለቱን ያሳያል፡፡ እነ ቀተለን በሚመስል በገቢር ግስ ግን የማስደረግ ብቻ ይሆናል፡፡ ‹‹ተ›› የመደረግና የመደራረግ ልማድ ነው በ “ጸ፣ ዘ፣ ጠ፣ ሠ፣ ሰ፣ ፀ፣ ተ” ለሚነሱ ግሦች ብቻ ልማድ ነው፡፡ ተዘብጠ፣ ተጸምደ፣ ተድኅረ፣ ተሠይመ ‹‹አስተ›› መደቡ የማደራረግ ሲሆን ድርቡ የማድረግና የማስደረግ የመደረግም ነው፡፡ ሐመመ አስተሐመመ፣ ረሰየ አስተረሰየ ይላል፡፡ በጽአ አስተብጽአ፣ ረከበ አስተርከበ፣ ርእየ አርአየ አስተርአየ እያለ መሄዱን ያሳያል፡፡ ‹‹አን›› ደግሞ የማድረግና የመደረግ ልማድ ይሆናል፡፡ ሲገቡም ደጊመ ቃል ባለው ከደጊመ ቃልም በሚቀል ገለገን ጌገየን ጎድጎደን በሚመስል ይገባሉ፡፡ ይህም ጎገወ ብሎ አንጎገወ ቀልቀለ ብሎ አንቀልቀለ እያለ ሌላውን ሁሉ ያሳያል፡፡

አርእስተ ግስ

ለግስ ሁሉ ጠቅላዮችና መደበኞች ሆነው ነጠላ ግስን የሚመሩ የግስ አርእስቶች 7 ናቸው፡፡ ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ባረከ፣ ዴገነ፣ ኖለወ፣ ደንገጸ፣ ማህረከ ናቸው፡፡ ቀደሰ በሦስቱ ጾታ ይጠብቅና

በሌላው በሁለቱ ይላላል። ይኸውም ቀደሰ አቀደሰ ወይም አስተቀደሰ ያለው ይጠብቅና ተቃደሰ አስተቃደሰ ይላላል። ባረከም በራብዕ ስለተነሳ ተደራጊው መደራረግን አስደራጊው ማደራረግን ደርቦ በሁለት ይፈታል። ይህም ተባረከ ብሎ በቁመ ተባረከ ተበራረከ፣ አስተባረከ ብሎ አስባረከ አበራረከ ማለቱን ያሳያል። ቀተለ የግስ ሁሉ አባት መሪ ፊታውራሪ የአርእስት በኩር ታላቅ ወንድምና ግንባር ቀደም ጠቅላይ መስፍን ርእሰ ርኡሳን ነው።

የግስ ዓይነቶች

ገቢር ግስ፦ ተሳቢና ተቀባይ ያለው እና ሥራው ከአድራጊ ወደ ተደራጊ የሚያልፍ በተደራጊ ላይ የሚፈጸም ነው። ምሳሌ ቀተለ፣ ወደሰ፣ ደምሰሰ እንደዚህ ያለ ይህን የመሰለ ሁሉ ገቢር ይባላል።

ዐጉል ግስ፦ ተሳቢ የሌለው ሥራው ከዚያው ከአድራጊው የማይወጣ በአድራጊው ላይ ብቻ የሚፈጸም ነው። ምሳሌ ሠነየ፣ ቀደወ፣ ምዕዘ፣ ጼነወ፣ ልህቀ፣ ወርዘወ፣ ነቀወ፣ ሞተ፣ ሖረ፣ ደክመ ይህን የመሰለ ሁሉ ዐጉል ይባላል። ተገብሮ እንዳይባል ሌላ ገባሪ የለውም ገቢር እንዳይባል ሌላ ተሳቢ የለውም። አድራጊውም ተደራጊውም ርሱ ራሱ ስለሆነ ዐጓጉል ይባላል። ይህም ከገቢር ይልቅ ወደ ተገብሮ ያደላል ቁጥሩም ከተገብሮ ነው።

በአፅማድ ጊዜ ኮነ በአንድ ዘንመ አዝነመ በሁለት ሐነጸ ተሐንጸ አሕነጸ በሦስት ፈለሠ አፍለሠ ተፋለሠ አስተፋለሠ በአራት ቀተለ አቅተለ ተቀትለ ተቃተለ አስተቃተለ የመሰለው ሁሉ ነው። ቀተለ ገደለ ይቀትል ይገድላል ይቅትል እንዲገድል ሊገድል ይገድል ዘንድ ይቅትል ይግደል እያለ ይተረጎማል። ኮነ በትንቢት ብቻ ትርጋጽ እየሆነ በቀዳማይነት ይገባል። ይህም ኮነ ይፈርህ ኮነ ይጎይይ ይፈራ ነበር ይሸሽ ነበር ማለቱን ያሳያል። ቀተሎ ብሎ ገደለው ገደለበት ገደለለት ይላል። አሥሩ ሠራዊትና ሰማንያው መደብ እንደሚከተለው ነው።

ውእቱ ቀተሎ፣ ላ፣ ሎሙ፣ ሎን፣ ቀተለከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ኒ፣ ነ

አንተ ቀተልኮ፣ ካ፣ ኮሙ፣ ኮን፣ ከኒ፣ ነ

እሙንቱ ቀተልዎ፣ ዋ፣ ዎሙ፣ ዎን፣ ሉከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ኒ፣ ነ

አንትሙ ቀተልክምዎ፣ ዋ፣ ዎሙ፣ ዎን፣ ሙኒ፣ ነ

ይእቲ ቀተለቶ፣ ታ፣ ቶሙ፣ ቶን፣ ተከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ተኒ፣ ነ

አንቲ ቀተልኪዮ፣ ያ፣ ዮሙ፣ ዮን፣ ክኒ፣ ክነ

እማንቱ ቀተላሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ላከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ኒ፣ ነ

አንትን ቀተልክናሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ናኒ፣ ናነ

አነ ቀተልክዎ፣ ዋ፣ ዎሙ፣ ዎን፣ ኩ፣ ከ፣ ኪ፣ክሙ፣ክን

ንሕነ ቀተልናሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ናከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን

ቀተልኮ ባለው ቀተልካሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን ይላል ፍችው አንድ ነው። ሀሎ፣ ሀሎነ፣ በጎራጅ ሀለወ ሀለውነ ወዘተ በሥርው ነው። የወሀበ አካሄድ እንደ ቆመ ነው። ወሀበ ብሎ ይውህብ በማለት ፈንታ ይሁብ ይላል። ወሀብኩ እሁብ እያለ ይሄዳል። ዘንድ አንቀጽ፣ አርእስት፣ ቦዝ፣ ውስጠዘ፣ ሳቢ ዘር ንዑሳን አናቅጽ ይባላሉ። እነዚህ እንደ ሦስቱ ዓበይት አናቅጽ ነገር ሰብስበው የማያስሩ የማይጠቀልሉ ስለሆኑ ንዑሳን አናቅጽ ይባላሉ።

ቦዝ አንቀጽ

ከየአዕማዱ ሲወጣ ቀቲሎ አቅቲሎ ተቀቲሎ ተቃቲሎ አስተቃቲሎ እያለ ሌላ አንቀጽ በመሳብ ችልታ ሆኖ ይቀራል። አመ፣ ሶበ፣ ድኅረ፣ እንዘ በሚገቡባቸው በዓበይት አናቅጽ ፈንታ ወተወሊዶ ወተጠሚቆ ወጸቢሆ እያለ በ‹‹ወ›› ከፋይነት እየገባ እንደ ዐበይት አናቅጽ ይፈታል። ሲረባም ቀቲሎሁ፣ ሃ፣ ሎከ፣ ኪ፣ ልየ፣ ቀቲሎሆሙ፣ ሆን፣ ሎክሙ፣ ክን፣ ሎነ ብሎ ቅርቡንም ቀቲለከሁ፣ ሃ ከሆሙ፣ ሆን፣ ከኒ፣ ከነ እያሰኘ እስከ 80 ይዘምታል።

ውስጠዘ እና መስም

ሰራተኛ አካል በስራው የሚጠራባቸው ስሞች ሁሉ በውስጣቸው ዘ፣ እንተ፣ እለ ስላሉባቸው ሁሉም ውስጠዘ ተብለው ለተጸውዖና ለተቀብዖ ለባሕርይ ስም ሁሉ በቅጽልነት ወይም በበቂነት ይነገራሉ። ቅጽል ባለቤት አከል ነውና። ቀቲል ሥራ ቀታሊ ሠራተኛ ወይም የሰራተኛ ስም ቀትል የስራው ስም ምቅታል፣ ምስትቅታል የቦታና የመሳሪያ ስም ይሆናል። ሣልስ ውስጠዘ እና ሳድስ ውስጠ ዘ ሣልስና ሳድስ ያሰኛቸው መጨረሻቸው ነው።

ሣልስ ውስጠዘ፡- ቀታሊ፣ ሊት፣ ልያን፣ ያት ይላል። ቀታሊሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ሊከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ሊየ ለነ። ቀታልያኒሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ኒከ፣ ንኪ፣ ኒክሙ፣ ክን፣ ንየ፣ ኒነ። ቀታሊቱ፣ ታ፣ ቶሙ፣ ቶን፣ ትከ፣ ኪ ክሙ፣ ክን፣ ትየ፣ ትነ። ቀታልያቲሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ቲከ፣ ትከ፣ ቲክሙ፣ ክን፣ ትየ፣ ቲነ። እንዲሁም ምንጽሒ አቅታሊ መቅተሊ መስተፍሥሒ አስተፍሣሒ እያለ የሚገኝ ሁሉ እንደዚህ ይረባል።

ሳድስ ውስጠዘ፡- ቅቱል፣ ላን፣ ላት፣ ትልት ይላል። ቅቱሉ፣ ላ፣ ሎሙ፣ ሎን፣ ልከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ልየ፣ ልነ። ቅቱላኑ፣ ና፣ ኖሙ፣ ኖን፣ ንከ፣ ኪ፣ ኒክሙ፣ ክን፣ ንየ፣ ንነ ወይም ቅቱላኒሁ፣ ኒሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ኒከ ንኪ፣ ኒክሙ፣ ክን፣ ንየ፣ ኒነ። ቅትልቱ፣ ታ፣ ቶሙ፣ ቶን፣ ትከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ትየ፣ ትነ። ቅቱላቱ፣ ታ፣ ቶሙ፣ ቶን፣ ትከ፣ ኪ፣ ትክሙ፣ ትክን፣ ትየ፣ ትነ ወይም ቅቱላሁ፣ ሃ፣ ሆሙ፣ ሆን፣ ቲከ፣ ትኪ፣ ቲክሙ፣ ክን፣ ትየ፣ ቲነ ይላል። መስም ያልነውም በሣልስ ሲጨርስ እንደ ሣልሱ በሳድስ ሲጨርስ እንደሳድሱ ይረባል።

ሳቢዘር

‹‹ት››ን ምዕላድ አድርጎ ይወጣል። ወ እና የ ባሉበት ግስ ግን ቁመት ሚመት እያለ በካዕብ በሣልስ ይነሣል። ቅትለት ብሎ መግደል መገደል አገዳደል ገዳይነት ተገዳይነት ግድያ ትግል

እያለ ይተረጎማል። ስባሔ በአፈታቱ ከስብሐት ጋር ይገጥማል።

ነባር አንቀጽ

ውእቱ፣ ቦ፣ ሎ ነው። አሉታው አኮ፣ ሐሰ፣ ኢ ናቸው። ውእቱ ነው፣ ሆነ፣ አለ፣ ኖረ፣ ነበረ። ይእቲ ናት፣ ሆነች፣ አለች፣ ኖረች፣ ነበረች እያለ የተቀሩት መራሕያንም በዚህ መልኩ ይተረጎማሉ። ውእቶሙና እሙንቱ ውእቶንና እማንቱ እንዳንድ ወገን ናቸው።‹‹ነ›› በአሥሩ መራሕያን ሲረባ ናሁ ነዋ እነሆ ይልና ነያ፣ ሙ፣ ዮን፣ ነየከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን፣ ነየ፣ ነየነ እያለ ይረባል። ዝኩ ዝስኩ አነ እና ንሕነን ትተው በ8ቱ መደብ እንደሚከተለው ይረባሉ።

ዝኩ፡ ዝስኩ፡ ዝክቱ= ያው፡ ያውና፡ ያ ነው

እንትኩ፡ እንታክቲ= ያቻት፡ ያችው፡ ያችውና፡ ያች ናት

እልኩ፡ እልክቱ= እኒያው፡ እኒያውና፡ እኒያ፡ እነዚያ ናቸው

እልኮን፡ እልክቶን= እኒያው፡ እኒያውና፡ እኒያ፡ እነዚያ ናቸው

ዝ፡ ዝንቱ= ይኸው፡ ይኸውና፡ ይህ ነው

ዛ፡ ዛቲ= ይችው፡ ይችውና፡ ይህች፡ ይች፡ ይቺ ናት

እሉ፡ እሎንቱ= እኒሁ፡ እኒሁና፡ እኒህ፡ እነዚህ ናቸው

እላ፡ እሎን፡ እላንቱ= እኒሁ፡ እኒሁና፡ እኒህ፡ እነዚህ ናቸው

ቦ ውእቱ እርሱ አለ ኖረ ኮሯል ነበረ።

ቦ ይእቲ እርሷ አለች ኖረች ኮራለች ነበረች እያለ በአሥሩ መደብ ይረባል። አሉታውም አልቦ ብለህ አልኖረም አልነበረም የለም አልኖረችም አልነበረችም የለችም እያልክ መፍታት ነው። ዝርዝሩ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ቦ ቦቱ አለው አለበት ኖረው ኖረበት ኮሮታል ኮሮበታል ነበረበት በእርሱ ይላል

ባ ባቲ አላት አለባት ኖራት ኖረባት ኮራታል ኮሮባታል ነበረባት በእርሷ እያለ በአሥሩ መደብ ይሄዳል። አሉታውም አልቦ አልቦቱ ብለህ የለውም የለበትም አልኖረውም አልኖረበትም አልነበረበትም እያለ ይፈታል።

ሎ ሎቱ ለእርሱ አለው አለለት ኖረለት ነበረለት ይገባል ይገባዋል

ላ ላቲ ለእርሷ አላት አለላት ኖረላት ነበረላት ይገባል ይገባታል እያለ በአሥሩ መደብ ይፈታል።

አኮ በአሥሩ ሠራዊት እየገባ ይፈታል። አኮ ውእቱ አኮ ይእቲ እያለ ማለት ነው። ሐሰም በአሥሩ ይፈታል ሐሰ ላቲ ሐሰ ባቲ እያለ ይሁንላት አይሁንባት እያለ ይተረጎማል።

ዘመድ ዘር፣ ባዕድ ዘር ምዕላድ፣ ባዕድ ከምዕላድ፣ ስም

ዘመድ ዘር አንቀጹንና አርእስቱን መስሎ የሚወጣ ስም ነው። ይህም ነደ ነድ፣ ገብረ ግብር፣ ጠበ ጥበብ ይላል። ባዕድ ዘር የግሡን ልማድ መሰረት አድርጎ በባዕድ ፊደል የሚነሳ ስም ነው። መሰለ አምሳል፣ መስተብቁዕ፣ መስቀል ይላል። ምዕላድ ዘር ደግሞ በዘመድ ተነስቶ በባዕድ የሚጨርስ ወሳኬ ባዕድ ነው። አበው፣ ሐዳስዩ፣ ኪሩቤል፣ ብጽዓን፣ ሐሜት ይላል። ባዕድ ከምእላድ የተባለውም በባዕድ ተነስቶ በባዕድ ይጨርሳል። መስፈርት፣ ትድምርት፣ ትምህርት እያለ ይሄዳል። የተጸውዖ ስም የሚባለው የሰውና የአገር የባሕር የወንዝ የተራራ ወዘተ ስም ነው። ምሳሌ ሙሴ፣ ግብጽ፣ ዮርዳኖስ ይላል። የተቀብዖ ስም የሚባለው ደግሞ የሹመትና የማዕርግ ስም ነው። ምሳሌ ጳጳስ፣ ንጉሥ፣ ቀሲስ ይላል። የባሕርይ ስም የሚባለው ምሳሌ ዕጣን፣ ሰው፣ እንስሳ፣ አርዌ፣ ዖፍ፣ ፍጥረት፣ ዘመድ፣ መጽሐፍ፣ ንዋይ ይላል። ወንድነትና ሴትነት የሌላቸውን ነገሮች አንዳንድ ጊዜ በወንድ አንዳንድ ጊዜ በሴት ሲጠራቸው ይስተዋላል። ለምሳሌ ይትፈሣሕ ሰማይ ይልና በሌላ ቦታ ደግሞ ወሰማይኒ ተጠውመት ከመ ክርታስ ይላል።

አንድምታ

አንድምታ ትርጓሜን የሚማር ሰው ቅኔን በሚገባ ማወቅ ይጠበቅበታል። ምክንያቱም የሚተረጎመው ግእዙ ጥሬ ወደ አማረኛ ስለሆነና ሲተረጎም ደግሞ ሥርዓተ ሰዋስውን ተከትሎ ስለሚተረጎም ነው። ስለዚህ ቅኔ ሳይማር ግእዝ ሳያውቅ አንድምታ የሚማር ሰው የሚባለውን አብዛኛውን ባለመረዳት ያሳልፈዋልና ነው። መጽሐፍ ግን በመላእኮችና በጸሐፊዎች ስሕተት የሰዋስውን ሕግ ሳይጠብቅ ሩቁን በቅርብ ቅርቡን በሩቅ አንዱን በብዙ ብዙውን በአንድ ወንዱን በሴት ሴቱን በወንድ እያደባለቀ ይናገራል። አንባቢ ሆይ በመጻሕፍት ውስጥ ይህን የመሰለ ብዙ ዓይነት ጸያፍ አለና። አሕጻከ ስሑል፣ ዘእንበለ ይቁም አድባር፣ ተቆጣእክዎሙ ለይእቲ ትውልድ እያለ አላገባቡ ገብቶና ተጥፎ ብታገኝ እንደዚህ ያለው ጸያፍ ንባብ ሁሉ የመላኽና የጸሐፊ ስህተት እንደሆነ የግእዝ ሕግና የሰዋስው ሥርዓት እንዳይዶለ አስተውል። መተርጉማን ግን የተቀዳበትን ጽርኡንና ዐረቡን ዕብራይስጡንም ስላላዩት መጽሐፍ ምስጢር ብቻ እንጂ ሕገ ሰዋስው አይጠብቅም። አንድና ብዙ ወንድና ሴት ቅርብና ሩቅ አይጠነቅቅም ብለው ያውጁና ጸያፉን ሁሉ ልማደ መጻሕፍት ይሉታል። በገድል በተአምር በቅኔ በሰላምታ ድርሰት ብቻ ጸያፍ አለመገኘቱ ስለምን ነው ብትል ሥሩና ምንጩ ግእዝ ብቻ ስለሆነለት አበባውም ድርሰት ከግእዝ መምህራን ስለፈነዳና ከሌላ ቋንቋ ስላልተቀዳ ነው። አንድምታ አንድን ቃል ቅርብ በሆነ አገላለጽ በስእላዊ መልኩ ለማስቀመጥ በቅርጽ በመልክ በዓይነት ማብራራት ነው። በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ሊገለጹ የማይችሉ ነገሮችን ግን በምሳሌ ያሳያል። ለምሳሌ ነገረ ሥላሴን በእሳት፣ በፀሐይ ሥጋዌን በዕፀ ጳጦስ ወዘተ ማለት ነው። መጽሐፍ ከቋንቋ ቋንቋ ሲገለበጥም በዓውድ የተተረጎመም አለ። ቃል በቃልም የተተረጎመ አለ።

ሳቢና ተሳቢ

ሳቢና ተሳቢ ማለት ዘርፍና ባለቤት ወይም ቅጽልና ባለቤት እንደማለት ነው። ሳቢው አንቀጽ

ተሳቢው ባለቤት ነውና። በገቢር አንቀጽ አደረገ አላደረገም፣ በተገብሮ ተደረገ አልተደረገም፣ በአጉል አንቀጽ ሆነ አልሆነም፣ በነባር አንቀጽ ነው አይደለም ተብሎ የሚነገርለ(በ)ት አካል ወይም አንድ ሌላ ነገር በአንቀጽ የሚሳብ ስለሆነ ተሳቢ፣ ማሰሪያ ተቀባይ ስለሆነ ባለቤት ይባላል። በተሳቢነቱ አንቀጽ ቀድሞት ወይም ተከትሎት ሲነገር አገባብ አይወድቅበትም። ስሙም ነባር ካልሆነ በቀር ሳድስ፣ ሣልስ፣ ካዕብ ሆኖ በቁመ- ይነገራል እንጂ ተለውጦ ግእዝና ኃምስ፣ ሳብዕ አይሆንም። ምሳሌ ሰበኩ ሐዋርያት ወንጌለ እም ኢየሩሳሌም እስከ በሐውርተ አህዛብ ሲል ሁሉም እያንዳንዱ ሰበኩ ባለው ይሳባል።

የሳቢና የተሳቢ አርእስት 6 ናቸው።መሆን ወይም ኂኝነት፣መደረግ፣ማድረግ፣ማስደረግ መደራረግ፣ማደራረግ ናቸው።መሆን ኂኙን አካል ብቻ የሚያስብ የአጉል አንቀጽ ነው።ፈለሰ፣ ነገደ፣ዐርገ፣ወረደ፣ረትዐ፣ደክመ፣ጸንዐ ይህን የመሰለ ነው።በእነዚህም በስድስቱ አርእስት የሚገቡ ደቂቅ አገባቦች በ፡እም፡ለ፡ኀበ፡መንገለ፡ውእደ፡እንተ፡ውስተ እንደ አንቀጹ ስልት ልዩ ልዩ ስም አላቸው።ይህም በ እንደሚስበው አንቀጽ መሆኛ፣መደረጊያ፣ማድረጊያ፣ማስደረጊያ፣መደራረጊያ፣ ማደራረጊያ ነው።እም ሰጪ፣ለ ተቀባይ ይባላሉ።ሐረ፣ተመይጠ፣ወጽአ፣ወረደ በሚያሰኙ አናቅጽ ሲሳቡ ግን እም መነሻ፣ለ፣ኀበ፣መንገለ፣ውእደ፣ውስተ መገስገሻ፣እስከ መድረሻ ይባላል።መሆን ኂኝን መሆኛን መደረግ ተደራጊን መደረጊያን መነሻን መገስገሻን ወይም መድረሻን መነሻና መድረሻም ቢቀሩ ሰጪን ተቀባይን ማሰሪያ የሚያስለቅቅ ዓቢይ አገባብን ዘንድን ንዑስ አንቀጽን ይስባል።ማሰሪያ የሚያስለቅቅ አገባብ ግን መደረጊያ፣መነሻ፣መገስገሻ፣ተቀባይ ከተባሉት ጋራ ዐቢይ አገባብም ቢሆን አብሮ ይቆጠራል።መሆን ኂኝና መሆኛን፣መደረግም ተደራጊንና መደረጊያን ከዐቢይ አገባብ ጋራ ሲስብ ተወሰነት ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት በጉባኤ ኒቅያ በአፈ ሠለስቱ ምእት አመ ነግሠ ቆስጠንጢኖስ ይላል።መነሻ፣መገስገሻ ወይም መድረሻ ተደራጊ አገባብ ሲስብ ተፈነው ሐዋርያት እም ኢየሩሳሌም ውስተ ኩሉ ብሔረ አሕዛብ ሶበ ፈቀዱ ፈጽሞተ ቃሉ ለእግዚእነ ይላል።ተደራጊን ሰጪን ተቀባይን አገባብን ሲስብ ተሰብከ ሃይማኖት እም ቃለ ሐዋርያት ለአሕዛብ ድኅረ ዐርገ እግዚእነ ይላል።ስድስቱን ሁሉ ሲስብ ዐርገ ኤልያስ እምድር ውስተ ገነት በሠረገላ እሳት እም ድኅረ ተአምረ ዐቂቦቱ ሕገ እግዚአብሔር ይንበር ህየ ይላል። በዚህ ላይ በማድረግ ጊዜ አድራጊን በማስደረግ ጊዜ አስደራጊን ጨምር።አዕረጎ እግዚአብሔር ለኤልያስ አዕርጎተ ፍቅር።

መደረግ ተደራራጊን፣ መደራረጊያን፣ መነሻን፣ መገስገሻን ወይም መድረሻን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ አገባብን ይስባል። ሲገባም ተራወጹ ተቃሓውያን ሩጸተ እመካን እስከ መካን ዘወሰኑ ሎሙ ባዕዳን በመርህብ በዕለተ አዕረፉ እም ተግባረ ሥጋ ይክሥቱ ፍጥነተ እግሮሙ። ሁለተኛም መደራረግ ተደራራጊን፣መደራረጊያን፣አገባብን ሲስብ ተቃተለ ዳዊት ምስለ ጎልያድ በመካነ ዔላ ሶበ ዐርጉ ኢሎፍላውያን ኀበ ደቂቀ እስራኤል ይላል። ተደራጊንም ሲጨምር ተራወጹ አብያጽ ተቃሓውያን ሩጸተ በመርሕብ በዕለተ አዕረፉ እም ተግባረ ሥጋ ይላል። መነሻንና መገስገሻንም ሲጨምር ይትራወጹ ሩጸተ መንፈሳዌ ሐዋርያት ወአርድእት እም ኢየሩሳሌም ኀበ እስከ ብሔረ አሕዛብ ወእም ህየ ኀበ ሳሌም እንዘ ይሰብኩ ወንጌለ ይላል። በማደራረግም ጊዜ በዚህ ላይ አደራራጊን ጨምር። አስተራወጸ እግዚእነ ሐዋርያተ ወአርድእተ ይላል። ዳግመኛም መደረግ ተደራጊን፣ መደራረግ ተደራራጊን፣ ግእዝ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ አድርገው

ይስባሉ፡፡ ራብዕ ግን ለገቢርና ለተገብሮ ስለተመቸ ሁሉ ይስቡታል፡፡ ይህም በልዐ ሥጋ ወመና፣ ተበልዐ ሥጋ ወመና ማለቱን ያሳያል፡፡ ስመ ተጸውዖም በገቢር አንቀጽ ተደራጊ ተሳቢ ሆኖ ሲነገር የግእዝ ወራሽ ‹‹ሀ›› ይጨመርበታል፡፡ ጸውኡ ሊተ ናታንሀ ነቢየ ወሳዶቅሀ ካህነ ባለው ይታወቃል፡፡ መደረግ ሳድስን ካዕብን ሣልስን ሲስብ ተቀትለ ጸር አው ጸሩ ወሚመ ጸላኢ ይላል፡፡ ማድረግ ግእዝን ሳብዕን ኃምስን ሲስብ ቀተለ ጸረ አው ጸሮ ወሚመ ጸላኤ ይላል፡፡ በማስደረግ ጊዜ አቅተለ በማደራረግ ጊዜ አስተቃተለ በል፡፡

ሳቦች አናቅጽ 8 ናቸው፡፡ 3ቱ ዐበይት 5ቱ ንዑሳት ናቸው፡፡ ዐበይት አናቅጽ የሚባሉት ኃላፊና ትንቢት ትእዛዝ ከንዑሳትም ዘንድና ቦዝ እነዚህ 5ቱ በፊት ሆነው ወደኋላ በኋላም ሆነው ወደፊት ሲስቡ ዐርፈው እንጂ ተናበው አይስቡም፡፡ ይህም በፊት ሲሆኑ በልዐ ኀብስተ፣ ይበልዕ ኀብስተ፣ ይብላዕ ኀብስተ፣ ይብላዕ ኀብስተ ሖረ፣ በሊያ ኀብስተ፡፡ በኋላም ሲሆኑ ኀብስተ በልዐ፡ ይበልዕ፡ ይብላዕ፡ ይብላዕ ሖረ፣ ኀብስተ በሊያ ማለቱን ያሳያል፡፡ በቀሩትም በአራቱ አዕማድ አሳሳባቸው እንዲሁ ነው አይለወጥም፡፡ አርእስትና ሳቢ ዘር፣ ውስጠዘ እነዚህ 3ቱ አርፈው ተናበው በ‹‹ለ›› ተያይዘው በፊትም በኋላም ሆነው ይስባሉ፡፡ አርፈው በፊት ሆነው ሲስቡ በሊዕ፡ በሊያት፡ ብልዐት፡ በላዒ ኀብስተ ያሰኛሉ፡፡ በኋላም ሆነው ሲስቡ ኀብስተ በሊያት፡ ብልዐት፡ በላዒ ያሰኛሉ፡፡ ተናበው ሲስቡ በሊዐ ኀብስት፣ በሊያተ ኀብስት፣ ብልዐተ ኀብስት፣ በላኤ ኀብስት፡፡ በ‹‹ለ›› ተያይዘው ወደፊት ሲስቡ በሊዕሁ፡ በሊያቱ፡ ብልዐቱ፡ በላዒሁ ለኀብስት፡፡ ወደኋላም ሲስቡ ለኀብስት በላዒሁ፡ በሊያቱ፡ ብልዐቱ ያሰኛሉ፡፡ የቀረ ተሳቢ ሲጨምሩና አገባብ ሲጫናቸው ግን ወደፊት ብቻ እንጂ ወደኋላ አይስቡም፡፡ ይህም በሊዐ ኀብስት በማእድ ቢል እንጂ በማእድ በሊዐ ኀብስት፡ በላዔ ኀብስት አይልም፡፡ ሲያያዝም በሊያቱ ለኀብስት በማእድ ቢል እንጂ በማእድ በሊያቱ ለኀብስት አይልም፡፡ አገባብም ሲጫነው ለበሊዕ ኀብስተ፣ ለበላኤ ኀብስት ቢል እንጂ ኀብስተ ለበሊዕ ወይም ለበላዒ አይልም፡፡ በቀሩትም እንዲሁ ነው፡፡

በባለቤትና በዘርፍ በቅጽል መካከል ሌላ እንዳይገባ በሳቢና በተሳቢም መካከል ሌላ አይገባም፡፡ ይህም በማእድ ነዳይ በሊዐ ኀብስት አለማለቱን ያሳያል፡፡ ሳቢና ተሳቢ ማስተላለፍ ብርቱ ጸያፍ ነው፡፡ እም አርዐተ ኃጢአት ኢየሱስ ዘአግዐዘ ትዝምደ ሰብእ አያሰኝም፡፡ የዚህ ዓይነት ጸያፍ ግሥግሥ ይባላል፡፡ ኀብስት ለበሊዕ ያልነውም መከታ ይባላል፡፡ መከታውም ‹‹ለ›› ነው፡፡

ዘርፍና ባለቤት ተናባቢና ተያያዥ

ዘርፍ ማለት አጭር ቅጽል ማለት ነው፡፡ ምስጢሩ ግን ባለወገንና ባለገንዘብ የስም ተውሳክ የባለቤት ምስማክ ማለት ነው፡፡ ባለቤትም ማለት ባለዘርፍ የዘርፍና የቅጽል ጌታ ነው፡፡ አገናኝቶም ዘርፍና ባለቤት ሲሉት ነፍስና ሥጋ ወይም ባልና ሚስት እንደማለት ሆኖ ጽሙርነቱን ያሳያል፡፡ ዘርፍ ሁሉ የእርሱን ስምና ባለገንዘብነት መደብ አድርጎ የባለቤቱን ገንዘብነት ስሙና ግብሩን ወገኑን ዓይነቱን ገልጦ የሚያሳይ አጭር ቅጽል እንደመሆኑ በአስተሳሰሩና በአፈታቱ የዘ፣ እንተ፣ እለን አማርኛ ‹‹የ››ን አይለቅም፡፡ ዘርፍና ባለቤት የሚባሉ በ2 አገባብ በ ‹‹ለ›› እና ‹‹ዘ፣ እንተ፣ እለ›› ተያይዘው ወይም በአራት ፊደል በግእዝ በራብዕ

በኃምስ በሳብዕ ተናበው የሚጸፉና የሚጠሩ ተከታትለው የሚነገሩ ሁለት ስሞች ናቸው። ይኸውም አምላኩ ለሰማይ፣ አምላክ ዘሰማይ፣ አምላከ ሰማይ ይላል። ፍችውም የሰማይ አምላክ ማለት ነው። መንታ ዘርፍም ሲሆን አምላከ ሰማይ ወምድር እያሰኘ በ ‹‹ወ›› ያጫፍራል። ባለቤትም መንታ እየሆነ በዋዌ ተጫፍሮ በአንዳንድ ዘርፍ ላይ ይናበባል። ጎሩያነ ወሠናያነ ሊባኖስ፣ ጽጌያተ ወፍሬያተ ትሩፋት። ሦስት እየሆነም ሲጫፈር ድምጸ ወጣሕረ ወግርማ አራዊት ይላል። ይህም አካሄድ በመጽሐፍ እንጂ በቅኔ አልተለመደም።

‹‹ለ›› ለአንድና ለብዙ ለወንድና ለሴት አያያዥ ሲሆን ጥበቡ፡ጥበባቲሁ ለሰሎሞን፣ ምክሮሙ፡ ምክራቲሆሙ ለጠቢባን፣ ዕበያ፡ ዕበያቲሃ ለድንግል። ክብሮን፡ ክብራቲሆን ለአንስት ያሰኛል። የዘርፉንም ዘርፍ ቀስተ መሐላሁ ለኖኅ፡ ደቀ ጽርሑ ለዳዊት ያሰኛል። ደፍቶም ሲያያይዝ ለኖኅ ሐመሩ፡ ለጌዴዎን ጸምሩ ያሰኛል። የዘርፉንም ሲደፋ ለዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ ያሰኛል። አንዳንድ መምህራን ‹‹ለ›› ለዘርፍ ብቻ እንጂ ለዘርፍ ዘርፍ ደፊነት የለውም ይላሉ። ‹‹ዘ፣ እንተ፣ እለ››ም ሲያያይዙ መዝሙር ዘዳዊት፣ መዘምራን እለ ዳዊት፣ ብእሲት እንተ ዳዊት፣ ዕቁባት እለ ሰሎሞን ወይም ደፍተው ዘዳዊት መዝሙር፣ እለ ዳዊት መዘምራን፣ እንተ ዳዊት ብእሲት፣እለ ሰሎሞን እቁባት ያሰኛሉ።

ዘርፍና ባለቤት ተሳቢ ሆኖ በ2 አገባብ ሲያያዝ የባለቤቱ መድረሻ እንደ አንቀጹ ጠባይ በመወራረስ ይነገራል። ይህም ቀተለ ኢዮአብ ብሎ ጸረ ዳዊት፣ አጽራረ እለ ዳዊት፣ ዕቤረ እንተ ዳዊት፣ ጸሮ፡ አጽራሮ፡ ዕቤሮ ለዳዊት ወይም ደፍቶ ዘዳዊት ጸረ፣ እለ ዳዊት አጽራረ፣ እንተ ዳዊት ዕቤረ፣ ለዳዊት ጸሮ፣ አጽራሮ፣ ዕቤሮ ይላል።

የግብር ስም ከተጸውዖ ስም ሲናበብ ዘርፉ ለባለቤት ቅጽል እየሆነ ይፈታል። ይህም ነቢየ ሙሴ ብሎ ሙሴ የሚባል ነቢይ ወይም ነቢዩ ሙሴ ማለቱን ያሳያል። የተጸውዖ ስም ማናቸውም ስም ተናብቦት ዘርፍ አይሆንም። ይህም ዳዊተ መንግሥት፣ ናዝሬተ ኢየሱስ ወይም ኢየሱሰ ናዝሬት አያሰኝም። ናዝሬት እንተ ኢየሱስ፣ኢየሱስ ናዝራዊ ቢል እንጂ።

ቅጽልና ባለቤት

ቅጽል ማለት ከባለቤት ጋራ እንደዘርፍ ሳይያያዝና ሳይናበብ የባለቤትን ጠባይና አናዎር ለመግለጥ አብሮ የሚነገር ማለት ነው።ቅጽል ማለት የባለቤትን ስምና ግብር ጠባይና አኳኋን መልኩንና ዓይነቱን ወርዱን ቁመቱን ስፍሩን ቁጥሩን ሌላውንም ሁሉ የሚያሳይ የስምና የግብር ፍካሬ ነው። ጥሬ ዘር ቅጽል የሚሆነው ዘርፍ ሲይዝ ብቻ ነው። ብቻውን አይቀጸልም። ወገን ቅጽሎች የሚባሉት ‹‹ይ›› እና ‹‹ዊ›› ናቸው። ምድር ምድራዊ፣ ሰማይ ሰማያዊ፣ ኢትዮጵያዊ ይላል። ነባር ቅጽሎች የሚባሉት ‹‹ዘ፣ እለ፣ እንተ›› ናቸው። የቦታ ቅጽሎች ኀበ፣ መንገለ፣ ውእደ ናቸው። መካን ኀበ ይትገበር፣ መካን ውእደ ይትገበር ይላል። ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ ይላል። በምድር በድው ኀበ አልቦ መንገለ አልቦ ውእደ አልቦ እድ ይላል።

ቅጽል 2 ዓይነት ነው። ዘመድ ቅጽልና ባዕድ ቅጽል ሲዘረዘር ግን ስሙ 8 ነው። ውስጠዘ፣ ግልጠዘ፣ ወገን ቅጽል፣ መስም፣ ጥሬ፣ ንዑስ፣ ደቂቅ፣ አኃዝ ይባላል። ውስጠ ዘ የሚባለው እንደ ናዛዚ፣ መንፈስ፣ መልአክ ነው። ግልጠ ዘ እንደ ጳውሎስ ዘተጸውዐ፣ ፈቤን እንተ ትትለዐክ ነው። ወገን እንደ አብርሃም ከለዳዊ ነው። መስም እንደ ዳዊት መዘምር የሚለው ነው። ጥሬ የሚባለው ደግሞ እንደ ወንጌል ጽንዐ ሃይማኖት፣ ክርስቶስ አክሊለ ሰማእት ያለው ነው። ንዑስ እንደ አይ አፍ ወአይ ከናፍር አይ አኮቴት ያለው ነው። ደቂቅ ውእቱ ሚካኤል፣ ይእቲ ማርያም ዝኩ ብእሲ የሚለው ነው። አንዝ አሐዱ እግዚአብሔር እንዳለው ያለ ነው።

ቅጽል ከባለቤት ቀድሞ ወይም ተከትሎ ይነገራል። ይህም ክቡር አምላክ፣ አምላክ ክቡር እንደማለት ነው። ቅጽል ባለቤት ሲቀር በቂ ይሆናል። ይህም ድንግል ወለደት አምላክ ይላል። ቅጽል ከባለቤቱ አይርቅም ቢርቅ ግን ማሰሪያ አስፈላጊ ወይም መመርመሪያ ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር ክቡር በነበ እስራኤል ሲል ቅጽልነቱን እግዚአብሔር በነበ እስራኤል ክቡር ወይም ዘከብረ ሲል ማሰሪያ ማስፈለጉንና ተለዋጭነቱን ያሳያል።

ለአንድ ባለቤት 2 ውስጠ ዘ ወይም 2 ግልጠ ዘ በአንድ ወገን ሲቀጸል መንታ ይባላል። ይህም ማርያም ጎሪተ አምላክ ወፍቅርተ መላእክት ዐርገት ሰማየ ወይም ተዐውቀ እግዚአብሔር ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ወዘለብሰ ሥጋ በይሁዳ እንደ ማለት ነው። ሁለተኛም ለአንድ ባለቤት ውስጠዘ ግልጠዘ እንዲህ እንዳሁኑ ተጫፍረው በአንድ ወገን አይቀጸሉም። በግራ እና በቀኝ ሲቀጸሉ ግን ስማቸው መከዳ ይባላል። ይህም አስተርአየ ልዑል አምላክ ዘኢያስተርኢ በሥጋ እንደማለት ነው። ሦስተኛም የቅጽል ባለቤት ከአንቀጽ ባለቤት ቀድሞ የባለቤት አንቀጽ ሲወድቅበት አታላይ ቅጽል ይባላል። ይህም ተመትረ ሥላሴ ዘፈጠሩ ጊዮርጊስ በሰይፈ ጎጺን፣ ተሰቅለ ማርያም ዘወለደት አምላክ ዲበ እጽ ምኑን፣ ተንስአ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን ዘሰቀሉ ክርስቶስ እሙታን ይላል። በጥሬ ቅጽልም እሞሙ ለሰማእት ብዙኃን ማርያም እያለ አታላይነቱን ያሳያል። የዘርና የነባር ጥሬም ዘርፍ ሳይዝ አለመቀጸሉ ውስጠዘነት ስለሌለው ነው። ቤተልሔም ሀገረ ዳዊት፣ ማርያም እመ አምላክ እያለ ዘርፍ ሲይዝ ግን ውስጠዘነትና የውስጠዘ አፈታት ያገኛል። የግብርና የተቀብዖም ስም ዘርፍ ሳይዝ ለተጸውዖ ስም መቀጸሉ ውስጠዘ ስለሆነ ነው። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ (ቅቡዕ)፣ ስምዖን ጴጥሮስ (ኩሉሓዊ) ባለው ይታወቃል።

ንዑስ ቅጽል በጥያቄ ቃል የሚነገር የተጠያቂና የተመርማሪ ቅጽል ነው። አየ ገቦ ረገዙ፣ ምንት ውእቱ ሰብእ ማለቱን ያሳያል። ለሊሁ፣ ለሊሃ የሚሉትም ሲቀጸሉ ለሊሁ እግዚአብሔር ጸብዐ ሎሙ። ለሊሁ አምላክ ይመጽእ ወያድኅነነ። ኩሉ ከተጸውዖ ስም በቀር ኩሉ ብእሴ፣ ኩላ እከይ እያሰኘ ለብትኖች ሁሉ ይቀጸላል። አኃዝ ለጥሬ ሁሉ ይቀጸላል። ለለአሐዱ ለአንዱም ለአንዱም ለእያንዳንዱ ይላል። በበአሐዱ አንዱንም አንዱንም በእያንዳንዱ ይላል።

የጊዜ አገባቦች ቅጽሎች

ተዘርው ሐዋርያት በዕለት አመ ተእኅዘ እግዚእነ ይላል። ‹‹አመ›› የዕለት ቅጽል ነው። ይመጽእ መዋዕል አመ ይብሉ ብጹዓት መካናት። በባለቤትና በቅጽል መካከል ከባለቤቱ ዘርፍና ከዘርፉ ቅጽል በቀር ባዕድ ቃል አይገባም። ይህም አምላከ ሰማይ ምጡቅ ሕያው ማለቱን አምላክ ሕያው ዘሰማይ ወይም ተወሰነት ሃይማኖት በጉባኤ ርትዕት አለማለቱን ያሳያል። ከአንቀጽ ወዲያም ቅጽል እንደዚህ ይፈረቅቃል። ይኸውም ዮሐንስ ሰበከ ወንጌላዊ እንደማለት ነው።

ባዕድ ቅጽል

ባዕድ ቅጽል አንድና ብዙ ወንድና ሴት ቅርብና ሩቅ ሳያናግር ያናገረ ይመስላል። ባዕድ ቅጽልም የሚሆኑ 5 ናቸው። ግልጠዘ፣ ውስጠዘ፣ የቦታ፣ የጊዜ፣ የልክ ቅጽሎች ናቸው። ግልጠዘ በአምስቱ አዕማድ ሲፈታ አንቀጹን ቢዘረዝርም ባይዘረዝርም በዝርዝርነት ይፈታል።

በአድራጊ ሲገባ፡- ወይን እንተ ተከ(ሉ)ልዋ ገባእት ፈረየት አስካለ።

በተደራጊ፡- መስቀል ዘተሰቅ(ለ)ሎ ክርስቶስ ዕፀ ሎጥ ውእቱ።

በአስደራጊ፡- መቅደስ እንተ አሕነ(ጸ)ጻ ሰሎሞን ኪራምሀ ምንክርት ጥቀ።

በተደራራጊ፡- ዳዊት ዘተጻብ(አ)አ አቤሴሎም መፍቀሬ ወልድ ጥቀ።

በአደራራጊ፡- ሰሎሞን ዘአስተጻብ(አ)አ ዳዊት ምስለ ኢዮአብ ኢፈርሀ እምኔሁ።

ተሳቢውንም ሲዘረዝር እንደሚከተለው ነው።

በሐውልት ግሥ፡- ዐብየ ሰሎሞን ዘጸንዐት መንግሥቱ

በተግበሮ፡- ጸድቀ ኢዮብ ዘይትነከር ትእግስቱ

በማድረግ፡- ተሞቅሐ ጳውሎስ ዘሰበኩ አርዳኢሁ ወንጌለ

በአስደራጊ፡- ጽሙእ ጥቀ ዳዊት ዘአምጽ(እ)አ ሥዩማኒሁ ማየ ቤተልሔም ሐራ

በተደራራጊ፡- ሞተ ኤሊ ዘተቃተሉ ደቂቁ ምስለ ኢሎፍላውያን

በአደራራጊ፡- ሞያ ለዓለም ክርስቶስ ዘአስተቃተለት ወንጌሉ ሰማእተ ምስለ ዐላውያን።

ባዕድ ውስጠ ዘ ደግሞ እንደ ግልጠዘ ነው። በንባብ ባለቤቱን በአፈታት ተሳቢውን መስሎ ይነገራል። ምሳሌ ወይን ትክልተ ገባእት ፈረየት አስካለ። ገበራርት የተከሏት ወይን ዘለላን አፈራች። ትክልት በንባቡ ወይንን ይመስላል ሲፈታ ግን አገባቡና ዝርዝሩ የእርሷ አንቀጹ ገባእት ነው። ገባእት አድራጊ ወይን ተደራጊ ናቸውና።

ዳዊት ንጉሠ(ነ)ጋሜ እግዚአብሔር=እግዚአብሔር ያነገሠው ዳዊት።

ጎብስት በላኤ ነዳይ=ድሀ የሚበላው እንጀራ፡፡

ኪራም ሐናጼ ሰሎሞን መቅደሰ=ሰሎሞን መቅደስን ያሰራው ኪራም፡፡

መቅደስ ሕንጽተ ሰሎሞን ኪራምሀ=ሰሎሞን ኪራምን ያሰራት መቅደስ ያሰኛል፡፡

ዳዊት ተጻባኤ አቤሴሎም ወልዱ=ልጁ አቤሴሎም የተጣላው ዳዊት፡፡

አብ ተሰባሔ ወልድ በደብረታቦር=ልጁ በደብረታቦር የተገለጠ አብ፡፡

ሰሎሞን ጽኑዐ መንግሥት=መንግሥቱ የጠና ሰሎሞን፡፡

ጳውሎስ ሰባኬ አርድእት ወንጌለ=አርድእቱ ወንጌልን ያስተማሩ(ለት) ጳውሎስ፡፡

ዔሊ ተቀታሌ ደቂቅ ምስለ ኢሎፍላውያን=ልጆቹ ከኢሎፍላውያን ጋራ የተዋጉ ዔሊ፡፡

ክርስቶስ አስተቃታሌ ወንጌል ሰማእተ ምስለ ዓላውያን=ወንጌሉ ሰማእታትን ከዓላውያን ጋራ ያጋደለች(ለት) ክርስቶስ ይላል፡፡

ሐዋን ንግሥተ አምላክ=አምላክ የነገሠላት ሐዋን፡፡

አዳም ምውተ እግዚእ=ጌታ ስለ እርሱ የሞተ አዳም፡፡

መስቀል ስቁለ አምላክ=አምላክ በእርሱ የተሰቀለ ወይም የተሰቀለበት፡፡

አምላክ ምውተ (መዋቴ) ፈያት=ወንበዶች ከእርሱ ጋራ የሞቱ አምላክ፡፡

ማርያም ፍኑተ ገብርኤል እም ሰማይ=ገብርኤል ከሰማይ ወደ እርሷ (እስከ እርሷ) የተላከ ማርያም፡፡

አልቦ ሰራቂ ቅሡፈ ክርስቶስ=ክርስቶስ እንደ እርሱ የተገረፈ ሌባ የለም፡፡

በቂና አጸፋ

ቅጽል ሁሉ ባለቤት ሲቀር በባለቤት ፈንታ በቂ ተጠያቂ ወይም ወኪል ባለቤት አከል ነው፡፡ በበቂነቱም ተሳቢና ዘርፍ ይሆናል፡፡ ቅጽልም ይቀጽልለታል፡፡

ተሳቢ፡- ምንተ ይመስል ዘአጥመቀ በማይ፣ ዜንውዎ ለዮሐንስ ዘትራእዩ ወዘትሰምዑ

ዘርፍ፡- ወአንተኒ ሕጻን ነቢየ ልዑል ትሰመይ፣ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ ምድራዊ

ቅጽል፡- ቅዱስ ኃያል፣ናዝራዊ ቅዱስ፡፡

አጸፋ የሚሆኑ ግን 2 ብቻ ናቸው እነርሱም ደቂቅ ቅጽልና ዝርዝር ናቸው።

አገባብ

አገባብ ማለት የተገባ የሚገባ ሥርዓት የነገር አጣጣል የንባብ አሠካክ ወይም በይግባኝ መምህር የሚፈርደው ፍትሐ ሰዋስው ማለት ነው።

ዐቢይ አገባብ

በነባር በዘማች በዐበይት አናቅጽ እየገባ ማሰሪያነትን የሚያስለቅቅ ሁሉ ዐቢይ አገባብ ይባላል።

እስመ

ና፣ ስለ፣ እንደ ይሆናል። ‹‹ና›› ሲሆን በኃላፊና በትንቢት በዘንድና በትእዛዝ በነባር አንቀጽ በጽድቅ በአሉታ ይገባል። በኂላ ሆኖ የፊቱን በፊትም ሆኖ የኂላውን ያስረዳል።

በኃላፊ፡- ኢያምሰጠ አዳም እም ኩነኔሁ ለእግዚአብሔር እስመ በልአ እም እጽ ዘኢአዘዞ ይብልያ ወይም እስመ ኢዐቀበ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ተወክፈ አዳም በድልወት ፍትሐ ሞተ ሥጋ ወነፍስ እምእግዚኡ።

በትንቢት፡- ሰማእት ኢይፈርሁ ሞተ ሥጋ እስመ ይሬእይዋ ለመንግሥተ ሰማይ በዓይነ ተስፋ።

በነባር፡- ውሉደ እግዚአብሔር በእንተ ክርስቶስ ይትዔገሡ መከራ እስመ ውእቱ አርኣያሆሙ ወይም እስመ አኮ ዛቲ ዓለም ዘትነብር ለዓለም ይሬእይዋ ጻድቃን ከመ እዳው።

በዘንድ፡- በዘንድ ሲገባ በነባር ይፈታል። ይህም ጻድቃን ይብልዎ ለክርስቶስ እንዘ ያመጽእ ላእሌሆሙ መከራ ሥጋ ኄር ውእቱ እስመ ከመ ይኩን ዝ መከራ ሕይወተ ነፍሳቲሆሙ ሲል ይህ መከራ የነፍሳቸው ሕይወት ይሆን ዘንድ (እንዲሆን፡ሊሆን) ነውና ያሰኛል።

እስመ ና በተባለበት ሁሉ ስለ ይስማማዋል። በተለየ ግን ስለ እና እንደ ሲሆን በኃላፊና በነባር ይገባል። ይህም ተሠገወ ቃል እስመ ተዋረደ አዳም ብሎ አዳም ስለተዋረደ ይላል። እሙን ነገር እስመ ክርስቶስ መጽአ ውስተ ዓለም ብሎ እንደመጣ ማለቱን ያሳያል። አምጽኡ ሎቱ ወርቀ እስመ ንጉሥ ውእቱ ሲል ንጉሥ ነውና ንጉሥ ስለሆነ ንጉሥ እንደመሆኑ ተብሎ በሦስቱም ይፈታል። እስመ ንዑስ አገባብም ሲሆን በኃላፊና በትንቢት በነባር አንቀጽ እየገባ አኮ ቢያ ይሆናል። እስመ ሖረ ብሎ ሄደ እኮ ሄደ ቢያ ይላል።

አምጣኑ፡- እንዲሁ ና ተብሎ ይፈታል።

አኮኑ፡- በአገባብነቱ አስረጅ ነውና እንደ እስመ በኃላፊ በትንቢት በነባር አንቀጽ እየገባ ና ተብሎ ይፈታል።

በእንተ፣ በይነ፣ እንበይነ

እነዚህ ሦስቱ ዐበይት አገባቦች ‹‹ዘ››ን በር ከፋች አድርገው በኃላፊ አንቀጽ እየገቡ ‹‹ስለ›› ይሆናሉ፡፡ ንወድሳ ለማርያም በእንተ ዘተወልደ እምኄሃ እግዚእነ፡፡ ሞተ ክርስቶስ በይነ ዘሞተ እንበይነ ዘሞተ አዳም ይላል፡፡ ደቂቅ አገባብም ሲሆን በእንተ ስለ፣ በ ይሆናል፡፡ ስለ የበጎ በ የክፉ ነው፡፡ ይኸውም ነገር በእንተ ይሁዳ ወበእንተ ኢየሩሳሌም ባለው ይታወቃል፡፡ ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ማለት ነውና፡፡ ንዑስ አገባብ ሲሆን ደግሞ ደስ ይበለው ብሎ፣ ደስ ይበለው ሲል፣ ደስ አይበለው ብሎ፣ ደስ አይበለው ሲል ይሆናል፡፡ ቃል ሥጋ ኮነ በእንተ አዳም አዳምን ደስ ይበለው ብሎ ይላል፡፡ እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐተ በእንተ ጸላኢ ዲያብሎስን ደስ አይበለው ብሎ ይላል፡፡ በይነ በ እያጋነነው ሳያጋንነውም እንበይነ ብቻውን ሆኖ ሁለቱም ስለ ይሆናሉ፡፡ በበይነ ዝንቱ፣በይነ ምንት፣እንበይነ ምንት ይላል፡፡

ህየንተ፣ ተውላጠ፣ ፍዳ፣ በቀለ

ከበቀለ በቀር እነዚህ ህየንተ፣ ተውላጠ፣ ፍዳ ዘን በር ከፋች አድርገው ህየንተና ፍዳ በኃላፊ ተውላጠ በኃላፊና በትንቢት እየገቡ ስለ ይሆናሉ፡፡ ህየንቱ ዘገብሩ ግንፋለ፣ ተውላጠ ዘይሴሰይ፣ ተወክፈ አዳም ፍትሐ ሞት ፍዳ ዘአበሰ ይላል፡፡ በቀለ ደግሞ በቁም ቀሪነቱን ሳይለቅ ስለ፣እንደ ይሆናል፡፡ ብጹእ ዘይትቤቀለኪ በቀለ ተበቀልክነ ብሎ ስለተበቀልሽን እንደተበቀልሽን ይላል፡፡ ደቂቅ አገባብም ሲሆኑ ህየንተ ስለ፣ ፈንታ፣ እንደ ይሆናል፡፡ ስለ ሲሆን ይሙት ህየንተ ሕዝብ ይላል፡፡ ፈንታ ሲሆን ፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት፣ ተቀንየ ያዕቆብ ህየንተ ራሄል ይላል፡፡ እንደ ሲሆን ኦ እግዚኦ አሕመልምል ሊተ ነፍስየ ህየንተ ዕዕ ትክልት ማእከለ ገነት ይላል፡፡ ተውላጠም ለውጥነት ባለው በብትን እየገባ ስለ ይሆናል፡፡ ተውላጠ ዝ ሲል ስለዚህ ማለት ነው፡፡ ፍዳም በብትን ሲገባ ስለ ይሆናል፡፡ ፍዳ ወይን ይስተይ ማየ ዝናም ስለወይን በወይን ፈንታ ይላል፡፡

ኀበ፣ መንገለ፣ ውእደ

እኒህ አገባቦች ዘንድ፣ የ ይሆናሉ፡፡ ዘንድ ሲሆኑ በዘማች በነባር ያሳስራሉ፡፡ ይህም ተመዊኦቱ ለንጉሥ ይከውን ወይም ውእቱ ኀበ መንገለ ውእደ ኢፈድፈደ ሠራዊቱ ብሎ ካልበዛ ዘንድ ይሆናል ወይም ነው ማለቱን ያሳያል፡፡ ‹‹የ›› ሲሆኑ ግን የቦታ ቅጽሎች ናቸውና ነው፡፡ የቦታም ቅጽሎች ስለሆኑ 5 የቦታ አገባቦች ይስማሟቸዋል፡፡ 1ኛ ‹‹ኀበ፣ መንገለ፣ እንተ፣ ውስተ፣ ለ›› ወደ ሲሆኑ፡፡ 2ኛ ‹‹እንተ›› በ ሲሆን፡፡ 3ኛ ‹‹በ›› በቁም ቀሪ ሲሆን፡፡ 4ኛ ‹‹እም›› መነሻ ሲሆን፡፡ 5ኛ ‹‹እስከ›› መድረሻ ሲሆን ነው፡፡ ‹‹የ›› ለሚሆን አገባብ እነዚህ 6ቱ እየተስማሙት ሲነገር ፍችው ይበዘበዛል፡፡ ይህም የሐውሩ አግብርት እም ኀበ ሀለው መንገለ ኀበ ሀሎ ውእደ ኀበ ሀሎ እንተ ኀበ ሀሎ ውስተ ኀበ ሀሎ ለኀበ ሀሎ እስከ ኀበ ሀሎ እግዚኦሙ፡፡ ባሮች ካሉበት ጌታቸው ወዳለበት እስካለበት ይሄዳሉ፡፡ ይሄልው አግብርት እንተ ኀበ ሀሎ በኀበ ሀሎ እግዚኦሙ ባሮች ጌታቸው ባለበት ይኖራሉ ማለቱን ያሳያል፡፡

‹‹በ፣ እም፣ እንተ›› በየሚስጥራቸው ሲስማሙት አልቦ በጎበ ኢይክብር ነቢይ ብሎ የማይክብርበት ይላል። ቦ ብሔር እም ጎበ ይወጽእ ብሩር ብሎ የሚወጣበት ይላል። ኢየአምር እንተ ጎበ ይመጽእ ኃጢአት ብሎ የሚመጣበትን ያሰኛል።

ጎበ ተለይቶ በትንቢትና በደቂም ሲገባ ሲ፡ ሲ፣ ሳ፡ ሳ፣ እየ፡ እየ እያሰኘ በእንዘ አማርኛ ይፈታል። ሰሎሞን ጎበ ጎበ ይነውም ይከሥት ዓይኖ ብሎ ሲተኛ ሲተኛ ይላል ጎበ ጎበ ይነቅሕሰ ይከድኖ። ማየ አይጎ እስከነ አርብዓ መዋዕል ጎበ ጎበ ይምልእ ሖረ ብሎ እየሞላ እየሞላ ይላል። ወእም ድኅሬሁሰ ጎበ ጎበ ይነትግ።

ደቂቅ አገባብም ሲሆኑ ሦስቱ ሁሉ ወደ፣ አጠገብ ይሆናሉ። አሐውር ጎበ አብ፣ ነበረ ጎበ አዘቅት፣ ሖሩ መንገለ መስዕ፣ ኢታቅም መንገሌከ፣ እቱ ውእደ ሕዝብከ፣ በውእደ ማየ ባሕር ይላል። በተለየ ግን ጎበ በአካል ሲገባ ዘንድ፣ መንገለ ወገን ይሆናል። እንተ ሀለወት ጎበ አብ፣ ኢኮነ አምላከ እመንገለ እሙ አላ እመንገለ አቡሁ ይላል።

እንዘ

ሲ፣ ሳ፣ ስ፣ እየ፣ ቸልታ ይሆናል። ሲ፣ ሳ፣ ስ ሲሆን በነባር በዘማች ከዚያውም በትንቢት በጽድቅ በአሉታ ይገባል። ከሀሎና ከሀለወ በቀር በትንቢት ብቻ እንጂ በኃላፊ አይገባም። ይህም እንዘ ይበልዐ፣ ኢትበልዐ፣ ንበልዕ ብሎ ሲበሉ፣ ሳትበሉ፣ ሳንበላ ይላል። እንዘ ውእቱ ሲሆን ሲኖር፣ ሳለ እንዘ ሀሎ፣ ቦ፣ አልቦ፣ አኮ ብሎ ሳላ፣ ሳይኖር፣ ሳይሆን ይላል። ዖደ አድያመ ዮርዳኖስ እንዘ ይጸርሕ እየጮኸ ማለቱን ያሳያል። ቸልታም ሲሆን ሞተ እንዘ የሐምም ብሎ ታሞ፣ ተቀብረ እንዘ ይመውት ብሎ መፉቶ ያሰኛል።

መጠነ፣ አምጣነ፣ አቅመ

በኃላፊና በትንቢት ሲገቡ ያህል፣ ስለ፣ እንደ ይሆናሉ። በኃላፊ መጠነ ጸለይኩ በሕይወትየ ይላል። በትንቢት አምጣነ ትበልዕዎ ለዝንቱ ኅብስት ይህን ኅብስት የምትበሉት ያህል ወይም በምትበሉት ልክ፣ ስለምትበሉት፣ እንደምትበሉት መጠን እያሰኘ ሌላውን ሁሉ ያሳያል። አቅመ ውስተ ልቡ ኀደረ ፍቅረ ቃል ወሕይወቱ ብሎ ያደረበት ያህል፣ ባደረበት ልክ፣ ስላደረበት፣ እንዳደረበት መጠን ይላል። አምጣነ ተለይቶ በእንዘ ቦታ እየገባ ሳ ይሆናል። ይህም አምጣነ ሀሎ መርአዊ ምስሌሆሙ ብሎ ሳለ ማለቱን ያሳያል። ኢይክል ሰብእ ሐይወ አምጣነ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ ብሎ ሳይበላ ሳይጠጣ ማለቱን ያሳያል። መጠነ ተለይቶ ውጥን ይጨርሳል። ሰሎሞን ነገሥከ መጠነ አቡከ ላእለ እስራኤል፣ ሰበከ ጴጥሮስ ወንጌለ መጠነ ሙሴ ኦሪተ ይላል። ኢትሬኢኑ መጠነ ይበልእ ወይሰቲ እንዲበላና እንዲጠጣ እያሰኘ ከመ በገባበት ይገባል። ደቂቅ አገባብም ሲሆኑ ከመ በገባበት እየገቡ እንደ ይሆናሉ። በአፈታታቸውም ምስጢራቸውን አይለቁም።

ከመ

እንደ፡ ዳ፡ ዲ፡ ድ ይሆናል። ‹‹በ፣ዘ›› እያጋነኑት ሳያጋንኑትም ከማሁ አንጻር እየሆነው

ሳይሆነውም በኃላፊና በትንቢት ይገባል። በአንጻር በከመ ይምሕር አብ ውሉዶ ከማሁ ይምሕሮሙ ይላል። ውጥን ጨራሽም ሲሆን እንደ መጠነ ነው። እርሱ በገባበት ይገባል። ሁለተኛም ከመ ዘ፣ እንተ፣ እለ በገቡበት አንቀጽና ጥሬ ሲገባ መሰለ ይሆናል። ለምንት ትኄልዩ ከመ ዘኢመጻእኩ ያልመጣሁ ይመስል እንዳልመጣሁ ሁሉ። ከመ ዘሰራቂኑ ሌባ ይመስል እንደሌባ ሁሉ ይላል። ተፈሥሑ ነቢያት ከመ ይትወለድ ክርስቶስ ወከመ ይትቀተል ወይትነሣእ እንዲወለድ እንዲሞትና እንዲነሣ ይላል። ሲነባበርና ሲደረደር በኃላፊና በትንቢት ይገባል። ሲነባበር ከመ ከመ ቀርበ ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እያለ ፈጽሞ ያሰኛል። ሲደረድርም ነአምን ከመ ሐመ ወከመ መተ፣ ከመዝ ወከመዝ መከርኩ አነ እንዲህና እንዲህ ይላል። ከመ ከመዝ ግዒሮ ሞተ ሲል እንዲህ እንዲህ ብሎ ይላል። ከመ በዘንድ አንቀጽ ሲወድቅ አዳማቂ ሆኖ ይቀራል። ይህም ከመ ይብጻሕ ዘተብህለ ይህም ይደርስ ዘንድ እንዲደርስ ሊደርስ ይላል። ከመ ደቂቅ አገባብም ሲሆን በጥሬ በቅጽል በብትን ቃል ሁሉ እየገባ እንደ ይሆናል። ምስጢሩም አንጻርነት ነው። ተቀስፈ ከመ ገብር ወተሰቅለ ከመ እቡስ፣ ከመ በግዕ የዋህ ወከመ ላህም ንጹሕ እያለ በሁሉ ይገባል።

በዘ

በዘ ፍችው ገንዘብና፣ ስለ፣ እንደ ይሆናል። በኃላፊና በትንቢት ይገባል። በኃላፊ ስለጥኩ በዘአምጽአ ሊተ አፍሮዲጡ ብሎ ባመጣልኝ ገንዘብ ይላል። በዘወድአ ሞት ኩሎ ብሎ ሞት ሁሉን በጨረሰ ገንዘብ ይላል። ይትዋረድ ብእሲ እኩይ በዘአስተዋረደ ሰብአ ብሎ ባዋረደ ገንዘብ፣ ስላዋረደ እያሰኘ በኃላፊው ሁሉ ስለን ይደርባል። በትንቢትም ወትሜህር በዘታስህቶሙ ብሎ በምታስታቸው ገንዘብ ያሰኛል። በኃላፊ ገብቶም እንደ ሲሆን ስልቱ 2 ነው። አንደኛው የከመ ሁለተኛው የቦዝ ነው። የከመ ሲሆን ወኮነ በዘአንተ አዘገዘከ አንተ እንዳዘገዘከው ሆነ ይላል። የቦዝ ሲሆን እመ ኢረከብከ በዘበልአ ኩሎ ቤል ንመውት። ቤል ሁሉን እንደበላ ወይም በልቶ ባታገኝ እንሞታለን ይላል።

አርአያ፣ አምሳለ፣ ሕገ

ሦስቱ ሁሉ በኃላፊና በትንቢት አንቀጽ እየገቡ እንደ ይሆናሉ። አርአያ ጾመ ሙሴ ጾመ ኢየሱስኒ አምሳለ እሙንቱ ሦጥዎ ላዕሌነ፣ አምሳለ ይፈቅድ ንዒወ ብሎ ማደን እንዲሻ፣ ኢተአምሩኑ አኃዊነ ሕገ ንነግረክሙ ብሎ እንድንነግራችሁ ይላል። ደቂቅ አገባብም ሲሆኑ ይነቁ አምሳለ ዖፍ፣ ሕገ ሰብእ እነብብ፣ ሕገ ሰብእ አናሕሲ ለነ እያሰኘ እንደ ይሆናሉ።

እመ፣ ሶበ

በኃላፊና በትንቢት በነባር አንቀጽ እየገቡ ከ፣ ካ፣ ቢ፣ ብ፣ ባ ይሆናሉ። ከ በኃላፊ በጽድቅ በአሉታ በአሥሩ ሠራዊት ይገባል። እመ ለ እያጋነነው ሳያጋንነውም ሶበ ብቻውን ይነገራል። ይህም እመ ቀተለ፣ ሶበ ቀተሉ ብሎ ከገደለ ከገደሉ ይላል። በአሉታውም እመ ኢቀተለ ሶበ ኢቀተልከ ብሎ ካልገደለ ካልገደልክ ማለቱን ያሳያል። ቢ በሦስቱ ሩቆች ብ በአንዲቱ ሩቅና በ6ቱ ቅርቦች በትንቢት ይገባል። ይህም እመ ይቀትል ሶበ ትቀትል ቢገድል ብትገድል ይላል።

በአሉታውም ሶበ፡እመ ኢይቀትል ባይገድል እያሰኘ ሁሉን ያሳያል። በነባሮችም ሲገቡ እመሰ፡ ሶበሰ አምላክ ውእቱ ባሕቲቱ እፎመ እም አድኅነ ፍጡራነ አምላክ ብቻ ቢሆን ሰውም ብቻ ቢሆን ወይም ከሆነ እመ አኮ ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ከእኛ ጋራ ባይሆን ካልሆነ እመቦ፣ ሶበ አልቦ ቢኖር ባይኖር ካለ ከሌለ ያሰኛል።

ዳግመኛም ጥያቄና አንክሮ ባለበት በጥርጥር ቃል ሲገቡ አንቀጻቸው ቦዝ እየሆነ እንደሆን ተብለው ይፈታሉ። በዚህ ላይ ደግሞ የጥያቄ አገባብ ሁ ትራስ ሲሆናቸው ምናልባት ማለትን ይጨምራሉ። እመሰ፣ ሶበሰ እኩየ ነበብኩ ክፉ ተናግሬ እንደሆን ይላል። ያድኅኖ እመ ይፈቅዶ ብሎ ይወደው እንደሆን፣ ቢወደው ይላል። እመሁ፡ ሶበሁ የአምር በዓለ ቤት ምናልባት ቢያውቅ ያውቅ ቢሆን ይላል። እመ አኮ ሲጫፈር ሁለቱም ወይ ተብሎ ይፈታል። እመ አኮ አንተ ኤልያስ ወእመ አኮ አነ ኤልዛቤል ወይ አንተ ኤልያስ ተብለህ ወይም እኔ ኤልዛቤል ተብየ ይላል። ኢይክል ገብር ተቀንዮ ለክልኤ አጋዕዝት እመ አኮ አሐደ ይጸልእ ወካልኦ ያፈቅር ወእመ አኮ ለአሐዱ ይትኤዘዝ ወለካልኡ የአቢ።

አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ

ጊዜ፣ ሲ፣ ስ፣ ሳ፣ የ ይሆናሉ። ጊዜ ሲሆኑ በኃላፊ ብቻ ይገባሉ። ወአመ በጽሐ ወሶበ በጽሐ ወጊዜ በጽሐ እድሜሁ ፈነወ ወልዶ ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ ልጁን ላከ እያለ መሄዱን ያሳያል። በትንቢትም ገብተው እንደዚሁ ሲፈቱ ሲ፣ ስ፣ ሳ ተብለው ይፈታሉ። ምስጢራቸው ግን ከጊዜነት አይወጣም። ይህም ወአመ ይመጽእ ወልደ እጓለእመሕያው፣ አመ፡ ሶበ፡ ጊዜ ትመጽእ በመንግሥትከ ብሎ በሚመጣበት ጊዜ፣ በምትመጣበት ጊዜ፣ ሲመጣ ስትመጣ ይላል። ሳ ሲሆኑም በትንቢት አሉታ ይገባሉ። አመ፡ ሶበ፡ ጊዜ ኢይትሜህሩ ሰዋስወ ተምህሮ ትርጓሜ ከመ አመ፡ ሶበ፡ ጊዜ ኢይትበጥሑ ተሐግሞ ሰዋስውን ሳይማሩ ትርጓሜን መማር ሳይበጡ እንደ መታገም ነው።

ደቂቅ አገባብም ሲሆኑ በአርእስትና በሳቢዘር በጥሬ በብትን ይገባሉ። ይህም አመ ተሰቅሎቱ በሥጋ ይላል። ጊዜ፡ አመ፡ ሶበ ወርኀ ማዕረር በመከር ወራት ጊዜ ይላል። በአካልም ሲገቡ አመ፡ ሶበ፣ ጊዜ ኤልያስ ብሎ በኤልያስ ጊዜ ያሰኛሉ። አሜ፡ ሶቤ ሁነው ሲገኙ ጊዜ ተብለው ይፈታሉ ዘአሜ ልደቱ ሰገዱ ሰብአ ሰገል እንዲል። አሜሁ፡ ሃ፣ ሶቤሁ፡ ሃ፣ ጊዜሁ፡ ሃ እያሰኙ እስከ አስር ይዘረዘራሉ። ብቻቸውንም ሲፈቱ ያን ጊዜ፣ በዚያ ጊዜ፣ ወዲያው፣ ፈጥኖ፣ ቶሎ ያሰኛሉ።

እስከ

እስከ በቁሙ በትርፍ አማርኛ ድረስ ይሆናል። በኃላፊና በትንቢት ይገባል። በር ከፋቾቹም ነ፣ አመ ሶበ፣ ጊዜ ናቸው። በር ከፋችም ሳይዝ ብቻውን ይገባል። ኢወለደት ኤልሳቤጥ እስከ ልህቀት፣ ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት፣ ወኢይትመየጥ እስከ አጠፍያሙ፣ እሄሉ ምስሌክሙ በኩሉ መዋእል እስከ ኀልቀተ ዓለም፣ እስከ ሶበ ኩሉ ይትገበር ወይከውን ይላል። ደቂቅ አገባብም ሲሆን መድረሻና ፍጻሜ ይሆናል። ወምኩናኒከኒ እስከ አጽናፈ ምድር፣ መሐለ

ከመ የሀባ እስከ መንፈቀ መንግሥቱ ያሰኛል። ለ በገባበት በግብር በነገር ሲገባ በጽሐ ይበጽሕን ያመጣል። ይህም በፍቅር ተስሕበ እግዚእነ እስከ ለሞት ለሞት እስኪደርስ ይላል። እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ አረብ ይላል።

ድኅረ

በኃላፊ ብቻ በጊዜ በቦታ እየገባ ኂላ ይሆናል። እም እያዳመቀው ሳያደምቀውም ይነገራል። ድኅረ ተንስአ እም ድኅረ ተንስአ እመ-ታን አስተርአዮን ቀዲሙ ለአንስት ብሎ ከተነሳ በኂላ ይላል። ደቂቅ አገባብም ሲሆን ድኅረ ማዕጸ እም ድኅረ ማዕጸ ከመዝጊያ በኂላ ይላል። እንተም ሲስማማው መጽአት እንተ ድኅሬሁ እያለ በስተኂላው በስተጀርባው ያሰኛል፡

ዘ፣ እንተ፣ እለ

በዚአሁ ላይ ግን ዘዚአሁ እያለ ሁለተኛ ዘ ሲጨመር ውእቱን ያመጣልና ቅጽሎች ናቸው። ሲፈቱ የእርሱ የሆነ ወይም የሚሆን ያሰኛሉ። ‹‹ዘ›› ደቂቅ ሲሆን እንደ ‹‹በበ›› እና እንደ ‹‹ለለ›› ዘዘ እያሰኘ በዲገመ ቃል በዚአሁ ዝርዝሮች ላይ ሲገባ እየ ወይም እየ፡ እየ ይሆናል። ወአኀዙ ይንብቡ ዘዘዚአሆሙ እየራሳቸው፣ እያንዳንዳቸው በደጊመ ቃልም እየራስ እየራሳቸው ያሰኛል። ይፈልጦሙ ዘዘዚአሆሙ ብሎ እየብቻቸው ማለቱን ያሳያል። ‹‹እንተ›› ደቂቅ አገባብ ሲሆን እየ፣ በ፣ ወደ፣ ለ፣ ን ይሆናል። እየ ሲሆን የሀበነ ምሕረቶ ወትረ እንተ ጽብሐት እየጧቱ እየለቱ ወይም እንደ ዘዘ በደጊመ ቃል ጧት ጧት ዕለት ዕለት ያሰኛል። በ ወደ ሲሆን በቦታ ይገባል። በ ሲሆን ወእንተ ካልእ ፍኖት፣ ይሔውጹ እንተ መሳክው ይላል። ወደ ሲሆን ፈነወ እደሁ እንተ ስቁረት ይላል። ለ ን ሲሆን እንተ ባሕቲቱ እያለ በአካል ይገባል። እንተ ሶበ ጸዋእክዎ፣ እንተ ሶበ ጊዜ ተንስአ እያለ ሶበንና ጊዜን ያዳምቃል። እለም ደቂቅ ሲሆን በጥያቄና በተጸውዖ ስም እየገባ እነ ይሆናል። ስሙም አብዥር ይባላል። እለ መኑ አንትሙ፣ ወእምዝ ኀለፉ እለ ጳውሎስ እምነ ጳፉ እንዲል።

አላ፣ ዳእሙ፣ ባሕቱ፣ እንበለ

አራቱ ሁሉ እንጂ ይሆናሉ። ዳዕሙ፣ አላ፣ ባሕቱ በቀዳማይና በካልዓይ በሣልሳይ አንቀጽ ይገባሉ። ሥቃየ ገሀነም አኮ ዘቦቱ ፍጻሜ አላ፣ ዳእሙ፣ ባሕቱ ዘአልቦቱ ፍጻሜ ይላል። እንበለም ዘን አዳማቂና በር ከፋች አድርጎ በኃላፊና በትንቢት ይገባል። በኃላፊ እያንተጉ አይሁድ ዕረፍቶሙ እም ድኅረ ዐርብ ዘእንበለ ዘወሰኩ ይላል። በትንቢትም ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ ይላል። አላ በትንቢትና በነባር እንጂ፣ ግን ይሆናል። አላ ዘይንእሶ የዐብዮ፣ አኮ አነ አላ አንተ ወቤተ አቡከ እንዲል። ዳእሙም እንጂ፣ ብቻ፣ ግን ይሆናል። እሉኑ ዳእሙ ደቂቅከ ሲል ብቻ፣ ኩሎ ዘቦ መጠውኩከ ውስተ እደከ ዳዕሙ ኪያሁ ኢትግሥሥ ይላል። ባሕቱ ግን፣ ብቻ ይሆናል። መበለተ ባሕቱ ኢታውስብ ይላል። ወን እየደረበም ሲገባ ወባሕቱ እብለክሙ ይላል። እንበለም ዘ እያጋነነው በዘንድ አንቀጽ ገብቶ ሳ ይሆናል። ዘእንበለ ያእምር ሕጻን ሰምየ አቡሁ ወእሙ፣ ዘእንበለ ይቁም አድባር ይላል። ሦስተኛም እንበለ ደቂቅ አገባብ ሲሆን በቀር፣ አለ፣ ያለ፣ እንጂ ይሆናል። ዘ እያጋነነው ሳያጋንነውም በጥሬ ሁሉ ይገባል። በቀር ሲሆን

ወኢታገምር ፍኖታ ዘእንበለ አሐቲ ኪደተ እግረ ብእሲ ይላል። አለ፡ ያለ ሲሆን እንበለ ኃጢአት ተሰቅለ ይላል። እንጂ ሲሆን አዘዞሙ ኢይንግሩ ዘርእዩ በደብር ዘእንበለ አመ ተንስአ በተነሳ ጊዜ እንጂ ይላል።

ዓዲ

እንጂ፣ ም ይሆናል። ቀድሞ ተከትሎ ይነገራል። አላ፣ ዳእሙ፣ ባህቱ በገቡበት ሁሉ ይገባል። እንጂ ሲሆን ዋዌነቱ አይቀርም። አሉታውን በጽድቅ ሲያናግር አኮ በመቄዶንያ ወአካይያ ባሕቲቱ ዓዲ በኩሉ በሐውርት ብሎ በሀገሩም ሁሉ እንጂ ይላል። ንዑስ አገባብም ሲሆን ገና፣ አሁን፣ በዋዌነቱ ም ይሆናል። ገና ሲሆን በኃላፊና በትንቢት በትእዛዝና በነባር ይገባል። ይህም ዓዲ ሀሎኩ ምስሌከ ይቄስክ ዓዲሁ፣ ተዐገሡ ዓዲ ጎዳጠ፣ ዓዲ ብየ ነገር ዘትብሉ ከመ ዓዲ ሕያው ማለቱን ያሳያል። ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜሁ ይላል። ዓዲሁ፡ ሃ እያለም ሲዘረዘር ገና ይሆናል። እንዘ ዓዲሁ ጽልመት እንዲል።

ብሂል

ዘይቤው ማለት ይሆናል። ብሂል ሦስት ነገር ይሆናል። እነዚህም አንቀጽነትና አገባብነት ሰዋስውነት ናቸው። በአንቀጽነቱ አንቀጹን ሁሉ ይስባል። ሲነገርም ቀድሞ ተከትሎ አርፎ ተናቦ ይገባል። ይህም ብሂል ሠረቀ ብሂል ተወልደ ወይም ሠረቀ ብሂል ተወልደ ብሂል ወይም ብሂለ ሠረቀ ብሂለ ተወልደ ውእቱ ይላል። በካልዓይና በሣልሳይም ብሂለ ይሠርቅ ኮከብ እም ያዕቆብ፣ ብሂለ ንበር በየማንየ ይላል። በነባርም ኢይምሰልክሙ በብሂለ አብ ብነ ማለቱን ያሳያል።

ንዑሳን አገባቦች

ሰ

ና፣ ስ፣ ሳ፣ ማ፣ ግን፣ ትኅ ይሆናል። ምስጢሩ ግን የሁሉም አፍራሽ ነው። ሲገባም ትራስ እየሆነ በቃሉ መጨረሻ ይገባል። ጸንሐ፣ ተርፈ፣ ተጎድገ በሚሉ በእነዚህ በሦስቱ በሣልሳይ ብቻ እየገባ ና ይሆናል። አገባቡም ይህ ነው። ኢፈጸሙ አይሁድ ሕገ ወንጌል። ይጽናሕሰ፡ ይትርፍሰ፡ ይትጎደግሰ ዝንቱ ሕገ ኦሪትሂ፡ ኒ ጥቀ ኢፈጸሙ። ሲፈታም ይህስ ይቅርና የኦሪትን ሕግ ስንኳ አልፈጸሙም ያሰኛል። ስ ሲሆን በብትን በቅጽል ይገባል ወልድየሰ መዊቶ ሀለወ እንዲል። ሳ ሲሆን እንደዚሁ በቅጽል በብትን እየገባ ጥያቄ ይከተለዋል። አንተሰ መጻእከ እጕከሰ አንተስ መጣህ ወንድምህሳ ይላል። ማ ሲሆን ደግሞ በቅጽል በብትን በአገባብ ገብቶ በጥያቄ ምላሽ ይነገራል። ይቤሎ ለዘይቤሎ ሕያውኑ እጕከ ውእቱሰ ሞተ እርስማ ሞተ ያሰኛል። ትኅ ሲሆን ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ሰ ግን እየሆኑ ይከተሉታል። ይህም ሰብእሰ ገጸ ይሬኢ ወእግዚአብሔርሰ ልበ ይሬኢ።

እም

በ፣ ባ፣ ከ፣ ካ፣ ኪ፣ ክ ይሆናል። ኪ፣ ክ ሲሆን በትርፍ አማርኛ ይልቅ ያሰኛል። በ፣ ባ ሲሆን

እመ ይኄሥሕ ይሁዳ እም ጸድቀ ብሎ በጸደቀ ነበር፣ እም ኀየሶ ሶበ ኢተወልደ ብሎ ባልተወለደ ይሻለው ነበር ይላል። እመ ኢይበልዕ አዳም በለሰ እም ኢኀጥአ ጸጋሁ ዘተውህቦ፣ ሶበሰ ትሄሉ ዝየ እም ኢሞተ እጉየ ብሎ ባልሞተም ነበር፣ መኑ እም ወሀበኒ ማየ ይላል። ከ፣ ካ ሲሆን ከመንና ዘን በር ከፋች አድርጎ እንደዚሁ በኃላፊ አንቀጽ ይገባል። እም ከመ ለምለመ አጽቁ ይላል። ዘእም እያለም ሲገባ እምዘ ተብሎ ይፈታል ይህም ጸልኡ ዘእምአፍቀሩኒ ብሎ ከወደዱት ይልቅ ይላል። ኪ፣ ክ ሲሆን በዘንድ እየገባ ይልቅ ያሰናል። ይቀልል ጎልፈተ ሰማይ እም ትደቅ አሐቲ ቃል ይላል። ደቂቅ አገባብም ሲሆን ከ፣ ይልቅ፣ የተነሳ፣ ጀምሮ፣ ኂላ፣ ወዲያ፣ ወዲህ ይሆናል። አለግሱ የተነበበ እም ቦዝ አንቀጽ ይመረመርበታል። ይህም ዜነዋ ገብርኤል ለማርያም እም እግዚአብሔር ብሎ ታዞ ተልኮ ይላል። ተንስአ እመ-ታን ብሎ ከመ-ታን ተለይቶ ቀድሞ አስቀድሞ ይላል። እም ከርስ ስሕቱ ወነበቡ ሐሰተ ከማህጸን ጀምረው ማለትን ያሳያል። ይትበደር ሰብእ እም እንቄ ሰንጌር ብሎ ይልቅ እጅግ ይላል። ሰቀልዎ አይሁድ ለክርስቶስ እመንገለ ቅንዐቶሙ ብሎ የተነሳ ይላል። የተነሳ ሲሆን ነ፣ መንገለ በር ከፋቾች ሆነው ሳይሆኑም ብቻውን ምክንያት ባለው ቃል ይገባል። እም ኢየሩሳሌም እስከ ግብጽ ሲል ጀምሮ ይሆናል። ኂላ ሲሆን በአጸፋ ይገባል። ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ፣ ወእምዝ መጽኡ አርዳኢሁ ሲል ከዚህ በኂላ ይሆናል። ኢያበርህ ፀሐይ እም አድማስ አላ እም አድማስ ብሎ ወዲያ ወዲህ ይሆናል። እም ነን በር ከፋች ሳይዝ በ፣ ፈ፣ ሰ፣ ጸ፣ ፐ ብሎ በሚነሳ ቃል እም በረከት፣ እም ፈቃድ፣ እም ሰማይ፣ እም ጻፉ፣ እም ፓና እያለ በቅኔ ሲገባ ጸያፍ ነው። ሁለተኛም ከግእዝ እስከ ሳብዕ ባለው በመ ፊደል በሚነሱ ቃላት ሲገባ ደጊመ ቃልነት ስላለው እየጠበቀና እየዋጠ ቀለም ያስቀራል። ይህም እመብረቅ፣ እመላድ፣ እሚናስ እማርያም፣ እምሥራቅ፣ እሜሎስ ማለቱን ያሳያል።

አይ፣ ምንት፣ መኑ፣ ማእዜ፣ አይቴ፣ ስፍን

ባለቤት ሲኖር ቅጽል ባለቤት ሲቀር በቂ ይሆናሉ። ማእዜ ግን ብቻውን ይበቃል። ሁ፣ኑ ያጋንኗቸዋል። አላ፣ ባሕቱ፣ ዳእሙ ያጸድቋቸዋል። አይ፣ ምንት በበቂነትም በቅጽልነትም የግብር የነገድ የተቀብዖ ስም ይፈልጋሉ። ይህም አይ፡ ምንት ተሰቅለ ወይም አይ ብእሲ፡ ምንት ሰብእ ተሰቅለ በቀራንዮ ነቢይሁ፡ ኑ ወሚመ ሐዋርያ ኢረድእ ወኢጸድቅ ዳእሙ አምላክ ሥግው ይላል። ሂ፣ ኒ ትራስ ሲሆኗቸው ማንም ይሆናሉ። አይኒ ዘተምዐ ዘይዘብጥ መነሂ ብሎ ማንንም ማን ይላል። ኢአይኒ ወኢመኑሂ አንድስ እንኳ ያሰኛሉ። ኢተገብረ ዘከማሁ ወኢበአይኒ መንግሥት አልቦ ዘርእየ ወኢመኑሂ ይላል። ምንት ደግሞ ሂ፣ ኒ ትራስ ሲሆኑት ምን ምን አንዳች ይሆናል። አሌፅል እደውየ ኀበ ሰማይ ከመ ኢይነስእ ምንተኒ እም ንዋይከ ይላል። አይ፣ ማእዜ መቼ ይሆናሉ። አየ ዘመነ፣ በአይ ዘመን፣ ማእዜ ተወልደ ክርስቶስ። አይ ለሁሉ ይሆናል። ማእዜ ግን ለጊዜ ብቻ ነው። አይቴ ሐት፣ ወዴት ይሆናሉ። በአይቴ፣ ኀበ አይቴ፣ እንተ አይቴ፣ እም አይቴ፣ እስከ አይቴ እያሰኙ የቦታ አገባቦች ይስማሙታል። ለ ሲስማማው ኀበን በር ከፋች አድርጎ ለኀበ አይቴ ያሰኛል። ስፍን፣ እስፍንቱ ስንት፣ ምን ያህል ይሆናሉ። ስፍን የአንድ እስፍንት የብዙ።

መ፣ ሚ

መ ነገር ያበረታል ቃል ያገነታል አዳማቂ ሆኖ ይቀራል እንጂ ንዑስ አገባብ እንደመሆኑ የተለየ ፍች የለውም። ከአይ እስከ እፎ ባሉት በንዑሳንና በደቂቅ ቅጽሎች በአንቀጽም ሳይቀር ትራስ እየሆነ በሁሉ ይገባል። የጥያቄ አገባብ ኑ ሲንተራሰው ጥርጥር ያሳያል። መኑመ አንተ፣ ምንተኑመ ትርአዩ ወጻእክሙ፣ ዝኑመ፣ አይቱመ፣ እፎመ፣ እስኩመ፣ ውእቱመ፣ ካልእመ ይላል። በአንቀጽም መጽአመ ዘይመጽእ እያለ ይገባል። ከንዑሳን በቀር በሌሎቹ ማ ተብሎ ሲፈታ ያምርለታል። **ሚ** ምን፣ ምንድን፣ ምንኛ፣ ስንት ይሆናል። ምን፣ ምንድን ሲሆን በአናቅጽ ሁሉ ይገባል። ምስጢሩም ጥያቄና ምርመራ አንክሮ ነው። ሚ የአቢ እም ረንብ ወሚ የሐምም እም ቁር ሚ እግበሮ ለዝ ሕዝብ፣ ሚ ላእሌነ ብሎ ምን አለብን ይላል። ምንኛ፣ ስንት፣ ምን ሲሆን በኃላፊና በትንቢት በቅጽል ይገባል። ሚ በዝኑ እለ ይሳቅዩኒ፣ ሚ ይበዝኅ ኀዘነ እምየ፣ ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ይላል።

እፎ

እንዴት፣ ረግ፣ ምን፣ ምንኛ፣ በ ሲወድቅበት ስለምን ይሆናል። ኢ፣ ኬ፣ ኑ፣ መ፣ እንጋ እያጋነኑት ሳያጋንኑትም በኃላፊና በትንቢት በነባር በቅጽል ይገባል። ምስጢሩም ጥያቄና አንክሮ ድንጋጼ ነው። እንዴትና ረግ አንድ ወገን ናቸው። እፎ ወድቀ ኮከበ ጽባሕ እም ሰማይ፣ እፎ አግመርኪዮ ለዘኢይትገመር ይላል። ኢ፣ኬ ሲያጋንኑት እፎኢ እንዘ አይሁዳዊ አንተ ትስእል በኀቤየ ትስተይ ማየ እንዘ ሳምራዊት አነ ብሎ እንዴት ነዋ ረግና ይላል። በቀሩትም እፎኑ ንዜኑ፣ እፎኑመ ይኴንን ዓለመ፣ እፎ እንጋ ማኅጸነ ድንግል ጾሮ እያለ ይገባል። ምን፣ ምንኛ ሲሆን እፎ ትቤ፣ አ ሞት እፎ ዝክርክ መሪር እያለ ምንኛ ይሆናል። ስለምን ሲሆን በእፎ ትነውኅ ዕለት እም ዕለት ይላል። በደጊመ ቃልም ሲነገር በደጊመ ቃል ይፈታል። ይህም እፎ እፎ ወይም ምን ምን እንዴት እንዴት ረግ ረግ ይላል። እፎያዊ እንዴት ያለ እንደምን ያለኛል።

ሁ፣ ኑ

ጥያቄና አጋናኝ ናቸው። በነገር ሁሉ ትራስ እየሆኑ ይገባሉ። ጥያቄ ባለው ቃል ሲገቡ ን ይሆናሉ። ምስጢራቸው ጥያቄን መደብ አድርጎ ማድነቅና መናቅ መሰልቸት ያሳያል። ይትከሀልኑ ይጸእ ኄር እም ናዝሬት፣ መኑ ያኅድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ፣ ምንዳቤኑ፣ መጥባሕትኑ ይላል። አጋናኝ ሲሆኑ ከአይ እስከ እፎ ባሉት ይገባሉ። ዳግመኛም ቦሁ፣ ቦኑ እያሉ ሲገቡ በውኑ ተብለው ይፈታሉ። ቦኑ ረኣይ በዛቲ ሀገር በዚች ሀገር ነቢይ አለን ይላል።

ኦ

የጥሪ አገባብ ነው። ሆይ፣ ምን፣ ወዮ፣ ይብላኝ ይሆናል። በተለይም ለአራቱ ግብሮች የሰሚ አገባብ ነው። ምስጢሩ አክብሮ፣ አፍቅሮ፣ አራኅርኆ፣ ምክር፣ አፍርሆ እና አጎስሮ ወቀሳም ያሳያል። አክብሮ ሲሆን ኦ ኢየሱስ ወልደ ዳዊት ተሣሀለነ፣ አፍቅሮ ሲሆን ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ፣ አራኅርኆ ሲሆን ኦ መስተምሕርት አስተምሕሪ ኀበ ወልድኪ፣ ምክር

ሲሆን ኦ ወልድየ ስምዐኒ ዘእብለከ፣ አፍርሆ ሲሆን ኦ ሀገረ ሰዶም፣ አጎስሮ ሲሆን ኦ ይሁዳ፡ ኦ ሐናንያ እፎ መልአ ሰይጣን ውስተ ልብከ፣ ወቀሳ ሲሆን ኦ አዳም ምንትኑ ረሰይናከ ይላል። ኦ ምን ሲሆን ቃለ አንክሮ ነው ለክፉም ለበጎም ይነገራል። ኦ ዝንቱ ምስጢር፣ ኦ እሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሔር፣ ኦ ለዝ ዝንጋኤ ይላል። ወዮ፣ ይብላኝ ሲሆን ቃለ ሰቆቃው ነው እምና ለ ይስማሙታል። ኦ ሞት፣ ኦ ለዘሞተ ይሁዳ እስመ ሜጦ ለእግዚኡ ይላል። ሁለተኛም የሰሚ አገባብ ሲሆን ምስጢሩ ከጽዋኤነት አይወጣም ሰሚዎቹም አራት ናቸው። አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን። ኦ እየገባባቸው ሳይገባባቸውም ብቻቸውን እየተጠሩ ይሰማሉ። ኦ ሲገባ ኦ እግዚኦ፣ ኦ ብእሲቶ፣ ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን ይላል። ኦ ሲቀር ስምዐኒ እግዚኦ፣ ስምዒ ወለትየ፣ አጽምዑ ሕዝብየ እያለ ያሳያል። 3ኛ ኦኦ ተብሎ በደጊመቃል ሲነገር ኡኡ ይሆናል። የእሪታ ቃል ነው የሰው ያለህ ድረሱልኝ ማለት ይሰማበታል። ኦኦ ጉዩ እምሰሜን እንዲል።

አሌ፣ ወይ፣ ወይሌ፣ ሰይ

ሁሉም ቃለ ብካይ ናቸው። ወዮ፣ ወየው፣ ወዮታ፣ እዬዬ ይሆናሉ። አሌ ሎ፣ አሌ ላ፣ ወይ ሊተ፣ ሰይ ልየ፣ ወይሌ ለቅጥቃጤየ እያሰኙ በለ ሲገቡ ወዮልኝ፣ ወዮታ አለብኝ፣ ወዮታ ይገባታል ያሰኛሉ። ብቻቸውንም ወይ እጉየ፣ ወይ እግዚእየ እያሉ በቅርብ በቅርብ ይገባሉ።

አህ፣ አሀህ፣ ዬ፣ ሐዊሳ

አህ፣ አሀህ የአንክሮና የደስታ የኀዘንና ነቀፌታ ነው። የአንክሮና የደስታ ሲሆን አዬ አዬ ዋይ ዋይ ይሆናል። አህ አህ አንደደኒ ፍቅርከ፣ አህ አህ ለድምጸ ቅኔሆሙ ይላል። ኀዘንና ነቀፌታ ሲሆን ወዲያ ወዲያ ጎድግ ይሆናል። አህ አህ እም ዛቲ ኃፍረት፣ አህ አህ እም ዛቲ ሕሰም ይላል። **ዬ** የልቅሶና የደስታ ቃል ነው። የልቅሶ ሲሆን በቁሙ ወዮ፣ ወየው፣ እዬዬ ይሆናል። ዬ ዬ ዬ አውረድዎ እም ዕፅ ይላል። የደስታ ሲሆን እንሆ፣ እሰይ ይሆናል። ዬ መስቀል ጸገየ፣ አንፈርዐጹ ሰብአ ሰገል ረኪቦሙ ሕጻና ዘተወልደ ለነ ዬ ዬ ዬ ይላል። **ሐዊሳ** የደስታና የአንክሮ ቃል ይሆናል። ሐዊሳ ለምጽአትከ፣ ሐዊሳ ሐዊሳ ለዝንቱ ሐዋርያ ይላል። ምስጢሩ ደስ የሚያሰኝ ነገር ከማየት ከመስማት የተነሳ ራስን አንገትን በመነቅነቅና በማድነቅ መልካም መልካም ይበል ይበል ማለትን ያሳያል። **በሓ** በአድንኖተ ርእስ የሚነገር የሰላምታ ቃል ነው። በሓከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን እያለ በአራቱ ቅርቦች ይዘረዝራል።

እስኩ፣ ዮጊ፣ እንጋ፣ እንዳኢ

እስኩ እስኪ ይሆናል። ጥያቄ ባለው ቃል በግልሳይ አንቀጽ ቀድሞም ተከትሎም ይገባል። እስኩ ንግረኒ ምንትኑ ዝ ነገር ዘትሜህር፣ ንግረኒ እስኩ ሰብአ ሮሜኑ አንተ ይላል። **ዮጊ** እንሆ፣ አሁን፣ ወይ ምናልባት ይሆናል በኃላፊና በትንቢት ይገባል። ኢትፍቅድ ከዊነ መኮንን ዮጊ ኢትክል ተበቅሎቶ ለዘአበሰ ገሥጾ ለዐርክከ ዮጊ ኢገብረ። እም ትሡዒ ለአማልክት ወእም ዕጣነ ታዕርጊ ተመትሮተ ክሳድ አብደርኪ ወጎረይኪ ዮጊ ይላል። **እንጋ፣ እንዳኢ** ንዑስ ቅጽልና የጥያቄ አገባብ እየተከተሉ ሲገቡ እንጃ ይሆናሉ። ምስጢራቸው ምኞትና አንክሮ ጥርጥርን ያሳያል። አሐዩኑ እንጋ እስከ እማንቱ መዋእል፣ መኑ እንጋ ይክል ድኂነ፣ እንዳኢ እመቦ

ዘነለየ ልብከ ይላል። እንጋ ተለይቶ አለጥያቄ በኃላፊ አንቀጽ ሲገባ እነሆ ይሆናል። እንጋ በጽሐት ኀቤክሙ መንግሥተ እግዚአብሔር ይላል።

ክመ፣ ጽመ፣ ጽሚተ፣ ጓ፣ እንቋዕ፣ ጥቀ

ክመ ብቻ፣ መቼም፣ መች፣ ድንት ይሆናል። ሁሉም የጊዜ ነው። ብቻ ሲሆን ሕቀ ክመ ተርፎሙ ይላል ጥቂት ብቻ ማለት ነው። መቼም መች ሲሆን ሂ፣ ኒ ትራስ እየሆኑት ሳይሆኑትም ብቻውን ይገባል። ክመኒ ኢወረደ አይኅ ከመ አመ ኖኅ፣ ክመ ኢኮነ ዕረፍት ለእስራኤል ከመ አመ ነግሠ ሰሎሞን፣ አንተሰ አንተ ክመ ይላል። ድንት ሲሆን በጸጸት በምኞት ይገባል። ሶበ ኢዐለወ አው ሶበ ኢየዐሉ አዳም ትእዛዘ እግዚኡ ክመ እምነበረ ውስተ ገነት በከመ ይነብሩ። **ጽመ** ዝም ብሎ፣ ቀስ ብሎ፣ ዝግ ብሎ ይሆናል። መጽአ ጽመ፣ ይመጽእ ጽመ፣ ነዐ ጽመ፣ ሑር ጽመ፣ ብላዕ ጽመ እያለ በዘማች አንቀጽ ይገባል። **ጽሚተ** በዝምታ፣ በቀስታ፣ በስውር ይሆናል። ኢፈቀደ ይክሥታ አላ መከረ ጽሚተ ይኅድጋ። አልቦ ዘተናገርኩ ጽሚተ ብሎ ሰውሬ በስውር ይላል። ጓ እኮ፣ ቢያ፣ እንኳ ይሆናል። ትራስ እየሆነ በቃል መጨረሻ ይገባል። እኮ፣ ቢያ ሲሆን አገባቡ እንደ እስመ ነው። እስመ በደቂቅነቱ እኮ፣ ቢያ ይላልና። እንኳ ሲሆን በብትን ይገባል። ሕሡመ ይሜንኖ ኃጥእ ለጻድቅ ዝሰ ይትርፍ ቀቲሎቶ ጓ ይቅትሎ፡ ጓ ይትሜነዮ መግደሉን እንኳ ሊገድለው እንኳ ይመኛል ይላል። **እንቋዕ** የደስታ ቃል፣ እንኳን ይሆናል። እሠይ ማለት ነው። በኃላፊ በትንቢት ይገባል። እንቋዕ ተሰብረት ማዕጸ አሕዛብ እለ ይብሉኒ እንቋዕ እንቋዕ ይላል። **ጥቀ** ስንኳን ይሆናል። ወ፣ ሂ፣ ኒ ስንኳን ሲሆኑ ይስማሙታል። አብርሃም ጥቀ ኢሞተ ወነቢያትኒ ሞቱ። አልቦ ዘመድ ጊዜ ተዋርዶ ወይከውን ባዕደ ጊዜ ተዋርዶ ወይከውን ባዕደ ጊዜ ተዋርዶ ዘመድ። እመሰ ይትሌዓል በንብረተ ሥጋ ማዕድ ጥቀ ዘመዱ ወጥቀ ነገድ ባዕድ ይዘመድ ይላል።

እንከ፣ እምዮም፣ እምይእዜ

እንከ እንኪያ፣ እንግዲህ፣ ከእንግዲህ ወዲህ፣ ከዚያ ወዲያ፣ እንሆ ይሆናል። እንኪያ ሲሆን ይቤሎ ለዘይቤሎ አልብየ መፍቅድ ኀቤከ ለምንት እንከ መጻእከ ኀቤየ እንኪያ ወደ እኔ ለምን መጣህ ይላል። እንግዲህ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ሲሆን ትሬኢ እንከ ዘየዐቢ ኃጢአተ ይላል። እንግዲህስ ሲል እንከሰኬ ይብልዑ ፍሬ ምግባሮሙ፣ ግበሩ እንከሰ ይላል። እንሆ ሲሆን ሀለው እንከ ኀቤነ ክልኤቱ አኃው ይላል። እነሆ መሆኑ በናሁ ፈንታ ሲገባ ነው። እም ዮም እም ይእዜም እንከ በገባበት እየገቡ የእርሱን አፈታት ይወርሳሉ።

አ፣ ሶ፣ ኬ

አ ቃለመልእክት ነው። ትራስ እየሆነ በሁሉ ይገባል ምስጢሩም ቁልምጫና ከበሬታ ነው። በቅርብ ሲገባ ቃለ አጋኖ፣ ቃለ አስተብቁዖ፣ ቃለ ተጋንዮ ይሆናል። አስተብቁዖ ሲሆን ፍችው እባክህ ነው። ያንኑ በደጊመ ቃል ያናግራል። ተጋንዮ ሲሆን መድረሻውን ፊደል እንደ ኬ ራብዕ ያደርጋል። በትርፍ አማርኛም እኮ ይሆናል። መልእክት ሲሆን ፈነውኩአ ይዜንውዖአ ለእግዚእየአ ኤሳውአ ከመአ እርከብአ ሞገሰአ ይላል። አጋኖ ሲሆን አንተኑአ ውእቱ ግብጻዊ፣

አንተኑአ ዘይመጽእ ወሚመ ካልእ። አስተብቁዖ ሲሆን ኦ እግዚኦ አድኅንአ፡ አድኅነነአ እባክህ አድነን ወይም በደጊም እባክህ እባክህ አድነን አድነን ያሰኛል። ተጋንዮ ሲሆን እግዚእየአ እጉየአ እያለ ይህን በመሰለ ሲገባ ጌታየዋ፣ ወንድሜዋ ወይም ጌታየ ጌታየ፣ ወንድሜ ወንድሜ ይላል። ሀበኒአ ጎድገኒአ እያለም ሲገባ በደጊም ይፈታል ወይም ስጠኛ፣ ተወኛ፣ ስጠኝ እኮ፣ ተወኝ እኮ እያሰኘ ለክፉም ለበጎም ይሆናል። ሶ ከአ የበረታ የልመና ቃል ነው። ቁርጥ ባለው ነገር በሣልሳይ አንቀጽ እየገባ እባክህ ይሆናል። ወይም አንቀጽ ይዘረዝራል አምላክ ኃያላን ተመየጥሶ ብሎ ተመየጠነ ተመየጥ ለነ ይላል። አድኅንሶ ሠርኅሶ አድኅነነ ሠርሐነ ሠርሕ ለነ ይላል። ኬ እንደ አ ትራስ እየሆነ በሁሉ ሲገባ መድረሻውን ፊደል ራብዕ ያደርጋል። ምስጢሩም ማጋነንና ማስደነቅ ነው። አንዳንድ ጊዜም ራብዕ ሳያደርግ አጋኖ ይቀራል። ወይም ማ ይሆናል። ይምጽኡኬ ይርአዩ፣ ውእቱኬ ዘወረደ ይላል። ዝኬ እፎ ይህሳ ይላል። ማ ሲሆን ጽናሕኬ፡ ጽናሐኒኬ፣ አንተኬ ትሰመይ ኬፋ እያሰኘ ይህን በመሰለ ይገባል።

አል፣ ኢ

አል የኢ ፍች ነው። አሉታነቱም የአማርኛና የዕብራይስጥ እንጂ የግእዝ አይደለም። ይኸውም ሊታወቅ ከቦ በቀር በሌላ አንቀጽ ገብቶ አይገኝም ቦ አልቦ ይላል። ኢ በአናቅጽ ሁሉ እየገባ ጽድቁን አሉታ ያደርጋል። ሲፈታም ም ጽንዕ እየሆነው ሳይሆነውም በኃላፊ አል በትንቢትና በትእዛዝ አ በዘንድ እንዳ፣ ላ፣ ሳ ይሆናል። ይህም ኢበልዐ አልበላ፣ አልበላም ወይም እንደ ጎጃም አልበልቶም። ኢይበልዕ አይበላ፣ አይበላም። ኢይብላዕ እንዳይበላ፣ ላይበላ፣ ሳይበላ። ኢይብላዕ አይብላ ማለቱን ያሳያል። በቦዝም ሲገባ ኢነጊሦ ዳዊት፣ ኢተዘኪሮ አበሳነ ብሎ ሳይነግሥ ሳያስብ ያሰኛል። በሣልስ ቅጽልም ቃል ኢሐማሚ በባሕርየ ሥጋ ዘሐመ፣ ትውልድ ኢአማኒት እያለ ሲገባ ያላመነች የማታምን ተብሎ በዘ አማርኛ ይፈታል። በሳድስ ቅጽልም ኢርቱዕ ኢመፍትው ሲል ያልቀና ያልተገባ ያሰኛል። በዘ አማርኛ መፈታቱ ቅጽሉ በቂ ሲሆን ነው። አለዚያ ግን ኢ እንደ አንቀጽነቱ አይደለም ተብሎ ይፈታል። ማሰሪያውም አሉታ ሆኖ ወን እያስከተለ ሲደረድር አንቀጽ እንጂ አገባብ አይሆንም ፍችው ግን ሆኖ ሲባል ንዑስ አገባብ ነው። የሆኖም ምስጢር እንደ ወ ማጫፈር ነው። አልቦ በዝ መልአክ ኢነቢይ ወኢንጉሥ ኢቁርባን ወኢመሥዋእት። ነቢይ የለም ንጉሥም የለ ቁርባን የለም መሥዋእትም የለ እያሰኘ በየደጁ ያስራል። አገባብ ሲሆን ግን ነቢይ ሆኖ ንጉሡም ሆኖ ቀርባን ሆኖ እያለ በአልቦ ያስራል።

ደቂቅ አገባብም ሲሆን እንደ እንበለ ነው። አለ፣ ያለ ይሆናል። በብትን፣ በአርእስት፣ በጥሬ ይገባል። እንበለንም እየተከተለ ዘእንበለ ተምያጥ ወኢተውላጥ ኢቡዓዴ ወኢቱስሕት ብሎ ሲገባ አንቀጽና አገባብ እየሆነ በአንቀጽነቱ ሳይኖር በአገባብነቱ አለ፣ ያለ ያሰኛል። በ፣ ለ በጥሬ በአርእስት ዘ በቅጽል ይስማሙታል። ግብር ዘይትገበር በኢምክር ወበኢለብዎ እበድ ውእቱ፣ ማርያምሰ ፍኅርተ ብእሲ ከመ ዘኢፍኅርት ምኩራብ ማኅደሩ ለኢሩካቤ ወምእራፉ ለኢሰብሳብ፣ አብዳን ወጉንድያነ ልብ ለኢአሚን ይላል። ዘ ሲስማማው በቅጽል ይገባል። ምንት ብከ ዘኢነግእከ እም ካልእከ፣ ኢትንግእ ዘኢያንበርከ ይላል። በአርእስትም ብቻውን ሲገባ ኢበለዐ

ሥጋ ወኢሰትየ ወይን ብሎ አለመብላት አለመጠጣት ያሰኛል። ተውህቦ ለጴጥሮስ ጸጋ ኢብሂል ኢሞተ ክርሥቶስ በሥጋ ይላል።

አው፣ ሚመ

ወይ፣ ወይም፣ ወይስ ይሆናሉ። ምስጢራቸውም ማሻሻልና ማማረጥ ማነጻጸርና ማበላለጥ ነው። ዋዌነትም አለው። ሲገቡም አው ቀድሞ ሚመ ይከተላል። ኢትቁም አው ንበር ወሚመ ሐር። እየብቻቸውም ባሕርኑ አነ አው ቀላይ፣ እም ሰማይኑ ወሚመ እም ሰብእ ያሰኛሉ። አው ተለይቶ ዋዌ ይሆናል። አው ሐር ኀበ ንህብ አው ካልእት ሀገር። ተደጋግመውም ሲነገሩ አው ብቻውን ሚመ በወ ይደገማል። አው ሰምእ አው ዘይት፣ ሚመ ተፈጥሮ ወሚመ ኢተፈጥሮ ይላል።

ወ

ግራና ቀኙን የሚያያይዝና የሚያቆራኝ አያያዥ ማለት ነው። ወ በአገባብነቱ ም፣ ና፣ ዘተረስአ፣ ቸልታ፣ ውጥን ጨራሽ፣ ጠቅላይ፣ ከ፣ ጊዜ፣ ስንኪ፣ እንጂ፣ ግን፣ ል፣ ስ፣ አዳማቂ ይሆናል። ምንም የአማርኛው ስልት ቢበዛ ምስጢሩ ማያያዝና ማጫፈር ብቻ ነው። **ም** ሲሆን ተሳቢውን ከቶ በማጫፈር አንቀጽ ይገባል። ናሁ ትጸንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዩዮ ስሞ ኢየሱስ ይላል። ተሳቢ በሌላው በድርድር አንቀጽ ግን ጠቅላይ እንጂ ም አይሆንም። ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ይላል። ወተንስአ እመ-ታን አመ ሣልስት ዕለት ሲል ብቻ ስለተሳቢው ም ይሆናል። ና ሲሆን ዘተረስአ ነው በስምና በአንቀጽ እየገባ ባልወደቀበት ላይ የኂሊት ይፈታል። በስም ሚካኤል ወገብርኤል፣ ጴጥሮስ ወጳውሎስ በአንቀጽ ሖረ ወመጽአ፣ ሐመ ወሞተ ሄደና መጣ ወይም ሄዶ መጣ እያሰኘ ዘተረስዐነቱን ያሳያል። **ቸልታ** ሲሆን ወደፊት በወደቀበት ላይ ይፈታል ተንስአ ወነደገ ልብሶ፣ ተጠምቀ ወአጽነነ ርእሶ ብሎ ልብሱን ጥሎ ራሱን አዘንብሎ ይላል። **ውጥንም ሲጨርስ** በኂላ ሆኖ የፊቱን በፊት ሆኖ የኂላውን የወንዱን በሴት የአንዱን በብዙ የብዙውን በአንድ ያናግራል። በኂላ ሆኖ የፊቱን ሰማይ ወምድር የኀልፍ ሰማይ ያልፋል ምድርም ታልፋለች ይላል። በፊትም ሆኖ የኂላውን መጽአ ዝኩ ብእሲ ወብእሲቱኒ ይላል። በአሉታም ኢኮነ ደብረ ገብረ ወኢይከውን ወኢወግር አመተ ለብእሲት ይላል። የአንዱን ለብዙ አገብኣ ለኤልዛቤል ወለእለ ዘመው ምስሌሃ ይላል። ብዙውን በአንድ ተሰቅሉ ፈያት ወክርስቶስኒ ኀቡረ ምስሌሆሙ። **ስንኪ፣ እንጂ፣ ግን** ሲሆን ነቃፊ ነውና በአሉታና በአፍራሽ ይገባል። ኢወሀቦ ርስቶ ወኢመጠነ ምሥጋረ እግር ብሎ አንዲት እርምጃስ ስንኪ ይላል። እግር ቦሙ ወኢየሐውሩ ብሎ እንጂ ይላል። በልዐ ወኢሰትየ ብሎ አልጠጣም እንጂ ያሰኛል። አንነ ጴጥሮስ እድሜሁ ስብከተ ወይሁዳ አኀጸረ ዕለተ ብሎ ግን ይላል። **ል** ሲሆን ስምዐኒ ወእንግርከ፣ ቅረበኒ ወእግስስከ እያሰኘ በሣልሳይ አንቀጽ ይገባል። **ስ** ሲሆን በንዑስ ይገባል። አይቴኑ አሐውር ወአይቴ እኅይይ ብሎ ወዴትስ ይላል። ምንተ በልዐ ወምንተ ሰትየ ብሎ ምንስ ጠጣ ያሰኛል። **አዳማቂ** ሲሆን በጥንተ ነገር ይገባል። ወሀሎ አሐዱ ብእሲ። ወኮነ በሠላሳ ክረምት ይላል። ምስጢሩ ግን ከማቆራኘት አይወጣም የሚቀድመው መጽሐፍ አለና። ወንድና ሴትም ሲያጫፍር ተፈጥሩ አዳም ወሔዋን ይላል እንጂ ሔዋን ወአዳም አይልም።

ሂ፣ ኒ፣ ዓዲ

ስማቸው ማሰሪያ ከፋዮች፣ ማንጸሪያ ትርጓሜያቸው ም፣ ደግሞ ይሆናል። ሂ፣ ኒ በኋላ ዓዲ በፊትም በኋላም እየገቡ ይነገራሉ። ንትሜሰሎ በሕይወቱኒ፣ የጎድግ ለክሙኒ፣ ዓዲ ናቁርብ ለከ፣ ፈነውነ ምስሌሁ ዓዲ ይላል። ሁለተኛ ሂ፣ ኒ፣ ሰ፣ ባሕቱ ግን ሲሆኑ ወ ግን ሲሆን እንደገባው አግባ፡ ሦስተኛም ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ፣ ጓ በብትን ሲገቡ ስንኳ ይሆናሉ ወ ስንኳ ሲሆን እንደገባው አግባ።

ቅድመ

እም እያዳመቀው ሳያዳምቀውም ብቻውን በዘንድ አንቀጽ ገብቶ ሳ ይሆናል። እም ቅድመ ይትረበባ ሰማያት፣ በሰማይኒ ቅድመ ይትፈጠር ኪሩብ ሰማዮች ሳይዘረጉ ኪሩብ ሳይፈጠር ይላል። ደቂቅ አገባብም ሲሆን በፊት ይሆናል እም እና በ እየተስማሙት በቦታ በጊዜ ይገባል። በቦታ ዘሀሎ እም ቅድመ ሀገር በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር። በጊዜም ሲገባ እም ቅድመ ዳዊት፣ ቅድመ ዳዊት ነግሠ ሳኦል ያሰኛል።

ትካት፣ ዓለም

ድሮ፣ ጥንት፣ ቀድሞ ይሆናሉ። ትካት ብቻውን ሰብአ ትካት፣ ሕዝብ ዘኢተአምሪ ትካት እያለ ከአገባብም ጋራ እም ትካት ኀበ ዘትካት እያለ ይገባል። ዓለም ግን አገባብ ሳይዝ ብቻውን አይገባም። ነቢያት እለ እም ዓለም፣ ተዘከርኩ ፍትሐከ ዘእም ዓለም ይላል። ከዱሮ፡ ከጥንት፡ ከቀድሞ ጀምሮ ነበረ ይላል። ለ ሲወድቅበት ወትሮ፣ ዘወትር፣ ድንት ይሆናል። አንተሰ ትነብር ለዓለም። ዘ ሲጨመርበት አምላክ ዘለዓለም ብሎ ለድንት የሚኖር የማይጠፋ የማይለወጥ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ያሰኛል። ለዓለመ ዓለም ለዘላለም በጊዜው በዘመኑ ሁሉ ያለማቋረጥ። እምዓለም ወእስከ ለዓለም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ከፍጥረት እስከ ምጽአት ይላል።

ቅድም፣ ትማልም

ቅድም ብቻውን ሲነገር ፊት መጀመሪያ ይሆናል። ከትማልም ጋራ ሲናበብ ግን በስተያ፣ ወዲያ፣ ሐች ይሆናል። ትማልም ደግሞ ትላንት አምና ይሆናል። ዕለት እንተ ትማልም ኀለፈት። በተገናኝ ቅድመ ትማልም ብሎ ከትላንት በስትያ ወይም ወዲያ ሐች አምና የወዲያኛው ዓመት ያሰኛል።

ዮም፣ ይእዜ

ዛሬ፣ አሁን፣ ዘንድሮ ይሆናሉ። ዘትማልም ወዮም እም ይእዜ ወእስከ ለዓለም። ቅድምና ትማልም ዘመነ ብሉይ ሲባሉ ዮምና ይእዜ ዘመነ ሐዲስ ይባላሉ። ዳግመኛም በመምህራን ልማድ አሜር አስፈር ዓምና፣ ኀሪፍ ገሪፍ ዘንድሮ ይባላሉ። በመጻሕፍት ግን ከኀሪፍ በቀር የሦስቱ ምስክር አይገኝም።

ጌሠም፣ ሳኒታ

ነገ፣ ማግሥት፣ የዮም ተከታይ፣ ሁለተኛ ቀን ይላል። ዮምኬ ሰብእ ወጌሰመ መሬት ይላል። ወበሳኒታ እምድኅረ ዐርብ ይላል። በዘመን ሲገባም ከርሞ የዛሬ ኣመት ይሆናል። ኢትበሉኬ ለጌሠም እስመ ጌሠምሰ ትሄሊ ለርእሳ።

ዘልፍ፣ ወትር፣ ዘልፈ፣ ወትረ ወትሮ ዘወትር ያለማቋረጥ ይሆናሉ። ልማድ ዘዘልፍ ዘወትር ይሴብሑ ይላል። ለዝሉፉ፣ ለዝላፉ ለወትሮ ለዘወትር ለዘላለም ይሆናል።

ግሙራ ለግሙራ ከቶ፣ አካቶ ፈጽሞ ጭራሽ ይሆናሉ። በተገብሮም አንቀጽ ሲገባ ተካቶ ተጨርሶ ያሰኛሉ።

እምድሩ እንደ ግሙራ ነው አካቶ፣ ፈጽሞ፣ ጭራሽ ይሆናል።

ብዛትና ብልጫ የሚያሳዩ **ጥቀ፣ ፈድፋደ፣ በሕቁ** እጅግ በጣም ይሆናሉ። ጥቀ ተሰብሐ፣ ፈድፋደ ተለአለ፣ ለእመ ኢተሐጽቡ በሕቁ ይላል።

ቅጽልና በቂ እየሆኑ ሕጸጽ የሚያሳዩ **ጎዳጥ፣ ንስቲት፣ ሕቅ** ጥቂት ይሆናሉ። ዓዲ ጎዳጠ ኢትሬእዩኒ ይላል። መድረሻቸው ግእዝ እየሆነ ወይም በ ወድቆባቸው ንዑስ አገባብ የሚሆኑ ሳድስ ቅጽሎች በዐበይትና በንዑሳት በአናቅጽ ሁሉ እየገቡ እንደሚስማማቸው ይፈታሉ። ይህም እነግረክሙ ክሡተ አው በክሡት ብሎ ገልጩ ወይም በግልጥ ማለቱን ያሳያል። የቀሩትም ድሎትና መፍትው ብውሕ በለ ተዘርዝረው ሳይዘረዘሩም በዘንድ አንቀጽና በአርእስት በሳቢ ዘር ገብተው ሲነገሩ ማሰሪያቸው ነባር አንቀጽ ነው። አኮ ድሎት ሊተ አንቃዕዱ ወእርዓይ። መፍትው ትግበሩ ዘንተ ወዝክተሂ፣ አኮ ድሎት ወአኮ መፍትው አስተርእዮ በመንታ ፍናው፣ ብውሕ ሊተ አንብራሂ ወእሚማሂ።

ጽድቅና አሉታ አንቀጽ የሚያሰሙ ዮጊ፣ ዬ፣ ናሁ፣ ነዋ በሁሉ እየገቡ እንሆ ተብለው ይፈታሉ። ዮጊና ዬ በየቦታቸው ተነግረዋል። ናሁ ለወንድም ለሴትም ነዋ ለአንድ ወንድ ብቻ ይነገራል። ናሁ ኢመጽአ ለበዓል። ወናሁ ኤልሳቤጥኒ ነዋ ወልድኪ ይላል። ናሁ ተለይቶ ቃለ አንክሮ ይሆናል። ይኸውም መጽሐፍ መላኮች ዕብራይስጡ ሚ ሠናይ ወሚ አዳም ያለውን ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ብለው ስላገቡት ነው። ሁለተኛም በእስመ ፈንታ እየገባ ዐቢይ አገባብ ይሆናል። ወሥጋሁኒ እምድኅረ ትንሳኤሁ ኮነ ዘኢይማስን ወዘኢይመውት።ናሁ ኮነ አሐደ ምስለ እግዚአብሔር ቃል ዘእንበለ ፍልጠት ይላል። **ሀብ፣ ነዐ** ና ቶሎ በል ይሆናሉ። **ሕንክ** እንካ ይሆናል። አኢ፡ አኢ አዋጅ አዋጅ ስማ ስማ ይሆናል። በጽሐ ጊዜ ዘይትበሀል አኢ እንዲል ገድለ ተክለሃይማኖት።

ደቂቅ አገባቦች

ቤዛ፣ ተክለ

በብትን ገብተው ስለ ይሆናሉ። እሜጡ ነፍስየ ቤዛ አባግዒየ። ተወልደ ሴት ተክለ አቤል

ስለበጎቹ ቤዛ ስለ አቤል ምት ይላል። ቤዛ ለውጥነት ባለው ተክለ ምትክነት ባለው ይገባል።

ዲበ፣ ላእለ፣ መልእልተ

የቦታ አገባቦች ናቸው። ላይ፣ በላይ፣ ወደ፣ ላይ፣ በ፣ ለ፣ ስለ ይሆናሉ። ዘሐነጸ ቤቶ ዲበ ኰኩሕ፣ ዐርገ ዲበ ሰማላ፣ ከልብ ይገብእ ዲበ ቂያኡ፣ ዲበ ሀጕለ ውሉዶሙ ይግእሩ። በልጆቻቸው ጥፋት ስለ ልጆቻቸው ጥፋት ይላል። ላእለ መልእልተም እንደዚሁ ናቸው። አዕረፈት በረከት ላዕለ ያዕቆብ፣ ወመጽአ ቃል ላዕለ ዮሐንስ፣ ዐርጉ መልእልተ ወግር፣ ወጽልመት መልእልተ ቀላይ ይላል። ስለ ሲሆን ጸልዩ ላእሌየ ወላእለ ዝንቱ መሥዋእት እያሰኘ ይህን በመሰለ ይገባል። አንዳንድ ጊዜም ጥቅም ባለው ነገር ሲገባ ለ ይሆናል ግበሩ ምሕረተ ወምጽዋተ ላዕለ አኃዊክሙ ይላል። ሦስት አገባቦች በ፣ እም፣ እንተ ይስማሟቸዋል። ጸጋ በዲበ ጸጋ፣ ቀነጸ እም ዲበ ሐመር፣ አዝዘኒ እምጻእ ኀቤከ እንተ ዲበ ባሕር ይላል። ሁለተኛም በጥሬነታቸው ዘርፍ ይዘው ወይም ተዘርዝረው ቅጽል ይሆናሉ። ጠፈር ዲበ፡ ላዕለ፡ መልእልተ ምድር ዓለመ ብርሃናት ይላል።

ታሕተ፣ መትሕተ

ታች፣ በታች ወደታች ይሆናሉ። የቦታ አገባቦች በ፣ እም፣ ኀበ፣ መንገለ፣ ውስተ ወደ ሲሆኑ ይስማሟቸዋል። በታሕተ እም፣ ታሕተ ሰማይ፣ ኀበ መትሕት ይላል። በጥሬነቱም ሲነገር ተዘርዝሮና ዘርፍ ይዞ ቅጽል ይሆናል። በሰማይ በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ፣ ምድር ታሕተ ጠፈር ወመትሕተ ደመናት ዓለመ ሰብእ ወእንስሳት ይላል።

ውስተ፣ ውሳጤ፣ ማእከለ

ውስተ ውስጥ በውስጥ በማኽል፣ በ፣ ወደ ይሆናል። ዓሣ ዘውስተ ባሕር፣ ሠርዌ ዘውስተ ዓይንከ፣ ከመ አንበሳ ውስተ እንስሳ ኢሀሎ ወስተ መካኑ ብሎ በቦታው፣ ሖርከ ውስተ ሲኦል ብሎ ወደ ይላል ምስጢሩ ግን ውስጥን አይለቅም። የቦታ አገባብ ስለሆነ በ፣ እም፣ እንተ ይስማሙታል። ዘይወጽእ እም ውስተ አፍ፣ ወጽአት ሐጽ እንተ ውስተ ልቡ ብሎ በደረቱ ይላል። ውሳጤም ውስተ በገባበት እገባ ውስጥ በውስጥ ይሆናል። ይትነብዑ አራዊት ውሳጤ ግብ ይላል። በ፣ እም ይስማሙታል። ማእከለም ማኽል በማኽል ወደ ማኽል ይሆናል። ባእ ማእከለ ሀገር እንዲል። በ፣ እም፣ እንተ፣ ውስተ ይስማሙታል። በማእከለ ማኅበር እሴብሐከ እንዲል።

በ

በ በቁም ቀሪ፣ ም፣ ን፣ ለ፣ ጊዜ፣ ጋራ፣ እንደ፣ ቸልታ ይሆናል። በቁም ቀሪ ሲሆን በማሰሪያ ሁሉ እየገባ ማድረጊያ ይሆናል። አድነነነ በመለኮቱ ወቤዘወነ በትስብእቱ ይላል። ም ሲሆን ለእግዚአብሔር ምድር በምልኣ፣ እስመ ዚአየ ውእቱ ኩሉ ዓለም በምልኡ ይላል። ን ሲሆን የግእዝ ወራሽ ነው። ለምሁራነ ልብ በጥበብ፣ ኢቀባዕከኒ በዘይት ይላል ጥበበ ዘይተ ማለት ነው። ለ ሲሆን መንታነትና ተነጻጻሪነት ባላቸው በሕዋሳት ሁሉ ይገባል። አንቀጹም ተደራራጊና

አደራራጊ ነው። ተናጸሩ ገጸ በገጽ ብሎ ፊት ለፊት፣ ይትጓድኡ ክንፈ በክንፍ፣ አስተአኀዞሙ እደ በእድ ወእግረ በእግር፣ ወተናገሮ ቃለ በቃል ይላል። ጊዜ ሲሆን የአመ ወራሽ ነው ኢመፍትው አድልዎ በፍትሕ ብሎ በፍርድ ጊዜ ይላል። ጋራ ሲሆን የምስለ ወራሽ ነው ተዋሐደ ቃል በሥጋ እንዲል። እንደ ሲሆን የከመ ወራሽ ነው ጽድቅ በወልታ የዐውደከ እንዲል። ቸልታም ሲሆን የእንዘ ወራሽ ነው ጸለየ ወሰአለ ኀበ እግዚአብሔር በብካይ አልቅሶ ወይም እያስለቀሰ ያሰኛል። በቦታ ላይ ሲወድቅ አገባብነቱን ሳይለቅ አንቀጽ ይሆናል ኤልያስ በገነት፣ አቡነ ዘበሰማያት እንዲል። **በበ** በየ ይሆናል ከተጸውዖ ስም በቀር በብትን ሁሉ ይገባል። በበደወሉ ብሎ በየአውራጃው በበዕለት ብሎ በየዕለቱ፣ ይሠውዑ በበነግህ ወበበሠርክ ብሎ ጢት ጢት ማታ ማታ፣ በበአሐዱ ብሎ በእያንዳንዱ፣ አንዱም አንዱም፣ አንዳንድ ያሰኛል። በ በማይስማማው ግስ ገብቶ ሲገኝ በሚስማማው ግስ ይፈታል መጻእክሙ ተአኀዙኒ በአብትር በበትር መትታችሁ ትይዙኝ ዘንድ፣ ከልብኑ አነ ከመትምጻእ ኀቤየ በአዕባን ወበበትር ደንገያና በትር ይዘህ ይላል።

ለ

አቀባይ ወይም በቁም ቀሪ፣ አቀብሎ ሸሸ፣ አዳማቂ፣ የ፣ ን፣ ከ፣ ወደ፣ ላይ፣ ስለ፣ ጋራ ይሆናል። በቁም ቀሪ ሲሆን ሀቡ ዘቁሳር ለቁሳር ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር፣ ኢትበሉ ለጌሠም ይላል። በባለቤትና በቅጽልም እንደ በ እየተደረበ ይነገራል። ለካህናት ለደቂቀ አሮን፣ ለብእሲት ለመርዐተ በግዑ ይላል። በ እና ለ በአማርኛም እንደዚሁ ናቸው ተደራርበው ይነገራሉ። አቀብሎ ሸሸ ሲሆን ለይኩን ብርሃን፣ ለይትጋባእ ማይ እያሰኘ በትእዛዝ አንቀጽ ይገባል። አዳማቂም ሲሆን ለኀበ ሰማያት፣ ለመንገለ እግዚአብሔር፣ ለእመ ርኅበ ጸላኢከ እያለ በአገባብ ይወድቃል። የ ሲሆን ዘርፍ አያያዥና የዘርፍ ደፊ ነው። ን ሲሆን ተጠቃሽ ወይም የግእዝ ወራሽ ይባላል። ከ ሲሆን ተሠጠ ለክልኤ፣ ተከፍለ ለአርባእቱ እያለ በአኃዝ ገብቶ ይነገራል። ወደ ሲሆን ተመይጠ ለብሔሩ ግብጽ ይላል። ላይ ሲሆን ወአምጽአ ረኀበ ለብሔር ብሎ በምድር ላይ ይላል። ስለ ሲሆን ኢትጸሊ ለዝ ሕዝብ ይላል። ጋራ ሲሆን የምስለ ወራሽ ነው ትከውኑ ሱቱፋነ ለሐራ ሰመይ እንዲል። በዘ ፈንታ ገብቶ የ ሲሆን ውእቱን በቁም ቀሪ ሲሆን ደለወ፡ይደሉና ያመጣል። ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ፣ ለአብ ስብሐት ይላል። **ለለ** ለየ፣ እየ ደጊመ ቃል ይሆናል ከተጸውዖ ስም በቀር በብትን ሁሉ ይገባል። ለለርእሱ ለእየራሱ፣ እየራሱ፣ ራስ ራሱ ይላል። ለለአሐዱ ለእያንዳንዱ፣ እያንዳንዱ፣ አንዳንዱ፣ አንዱም አንዱም ይላል። ለለዕለቱ ለየዕለቱ፣ እየዕለቱ፣ ዕለት ዕለት እያሰኘ ሌላውን ሁሉ ያሳያል። ሁለተኛም በኃላፊና በትንቢት ሲገባ ዓቢይ አገባብ ይሆናል። ዐቢይነቱም አመንና ሶበን እንዘን ይመስላል። ፍችውም ጊዜና፣ የ፣ ሲ፣ ስ ደጊመ ቃል ነው። ወለለወለደ፣ ወለለይወልዳ ተባዕተ ቅትላሁ ወንድ ወንዱን ግደሉት፣ ለለተናገርኩ ተዘከርኩ በተናገርኩ በተናገርኩ ጊዜ የተናገርሁትን፣ ለለእትናገር ስናገር ስናገር በደጊመ ቃልም ፈንታ ቁጥር ይሆናል።

ምስለ

ጋራ፣ ከነ፣ እንደ፣ ከ፣ ና ይሆናል። ጋራ በሚሆንበት ኀቡረ ሲጨመር አብሮ በአንድነት ያሰኛል። ንዒ ኀቤ ምስለ ወልድኪ ብሎ ከልጅሽ ጋራ፣ ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስሌሆሙ ኀቡረ

ከእርሳቸው ጋራ ዐብረው ወይም በአንድነት፣ መጽአ ብእሲ ምስለ ብእሲቱ ብሎ ከነ ሚስቱ ወይንም ከሚስቱ ጋራ ማለቱን ያሳያል። እንደ ሲሆን የከመ ወራሽ ነው አበስነ ምስለ አበዊነ፣ ወኢተቀስፉ ምስለ ሰብእ ብሎ እንደሰው ይላል። ከ ሲሆን የእም ወራሽ ነው መለያየትን በሚያሳዩ ግሦች ይገባል። ወብእሲትኒ ኢትትነደግ ምስለ ምታ ብሎ ከባሏ አትፋታ ይላል። ና ሲሆን እንደ ወ አጫፋሪ ነው። በብዙ ወንድ አንቀጽ ይገባል ከንቶ ይትናገሩ አሐዱ ምስለ ካልዑ ብሎ አንዱና ሌላው ብሎ ያሳያል። ምስለ በማይመስለው ግስ ሲገባ ቦዝ ሆኖ ይፈታል። ሰረረ ንስር ምስለ መጽሐፍ ብሎ መጽሐፍ ይዞ ይላል።

አያተ፣ ጽላሎተ

አያተ በብትን ብቻ ጽላሎተ በተጸውዖ ስም እየገቡ እንደ ይሆናሉ። ተዋሐደ ሥጋ ወቃል አያተ ሐመልማል ወነበልባል፣ አስናኒከ አያተ አዕናቍ እለ ተሰክዐ፣ተሰቅለ ጴጥሮስ ቁልቁሊተ ጽላሎተ ዶርሆ ይላል። **አፍኣ** ውጭ፣ በውጭ ይሆናል አውጽእዎ አፍኣ፣ ይቀውም አፍኣ እንዲል። **ከዋላ** ኋላ፣ በኋላ ይላል ነአቅብ ፍጽመ ወከዋላ፣ የሐውሩ ከዋላ እንዲል። **ዝየ** በዚህ፣ ከዚህ፣ ወደዚህ ይላል ዝየ አኀድር፣ ምንት ብከ ዝየ፣ አምጽእዎ ሊተ ዝየ ይላል። **ህየ** በዚያ፣ ከዚያ፣ ወደዚያ ይላል ተከለ ገነተ ወሜሞ ህየ፣ በህየኒ ሰመዮ ወልደ ይላል። **ለፌ** ወዲህ ወደዚህ ይላል ትመጽእ ለፌ ኀበ አነ እቀውም፣ እለ ይብሉ ከመ ክርስቶስ ለፌ እማርያም ይላል። ተደጋግሞ ተጫፍሮ ሲነገር ወዲህና ወዲያ ቀኝና ግራ ይሆናል፣ ነጽር ለፌ ወለፌ፣ አንጌገየ ለፌ ወለፌ ይላል። **ከሣ** ወዲያ ይላል ዝርዎ ከሣ፣ ሑር ከሣ ይላል። **ኩለሄ** ቦታ፣ ሁሉ፣ መላው፣ ጠቅላላው አራቱ ማዕዘን ብቻውንም ከአገባብም ጋራ ይነገራል። ብቻውን ሖርኩ መትሕተ ሰማይ ኩለሄ፣ ከአገባብም ጋራ ምሉእ በኩለሄ፣ ተጋብኡ ኀቤሁ እምኩለሄ እለይነብሩ ውስተ ኩለሄ ይላል። ከደቂቅ አገባብ የሚጨመሩ የቦታና የጊዜ ጥሬዎች እነዚህም ተናበውና ተዘርዝረው ግእዝ ኃምስ ሆነው ይነገራሉ። ላዕል፣ ላዕሉ፣ መልእልት፣ ላዕሊት ወደ ላይ ይሆናሉ። ታሕት፣ ታሕቱ መትሕት፣ ታሕቲት ታች ይሆናሉ። ትርአስ፣ ትርጋጽ፣ ውስጥ፣ ውሳጢ፣ ውሳጢት፣ ቅድም፣ ፍጽም፣ ገጽ፣ ድኅር፣ ከዋላ፣ የማን፣ ይምን፣ ጸጋም፣ ጽግም የእነዚህም አዋጅ እንደነ ላእል ነው። ግድም በደጊም ብቻ ይነገራል። አንትሙ ተሐውሩ ግድመ ግድመ ይላል። ድኅሪት፣ ግንጽሊት፣ ግፍትዒት የኂሊት፣ የግርንግሪት ይላል።

እየተናበቡ የሚነገሩ የቦታ ጥሬዎች

ጽንፍ፣ ክንፍ፣ ከንፈር፣ ሐይቅ፣ ድንጋግ፣ ገበዝ፣ ወሰን ዳር፣ ዳርቻ ጫፍ ጠርዝ ይሆናሉ። ጽንፍ ለባሕር፣ ለየብስ፣ ለኀብስት፣ ለልብስ ይሆናል። ጽንፈ ባሕር የብሰ እንዲል። ክንፍ ለሁሉ ይሆናል። ክንፈ ምድር፣ ክንፈ ቤት። ከንፈር ሐይቅ ለባሕር ይሆናሉ። ድንጋግ ለወንዝ ለባሕር ለዘመን ይሆናል። ገበዝ ለወንዝ ብቻ። ወሰን ለሁሉ ይሆናል። ወበጽሐ ዮርዳኖስ እስከ ድንጋጊሁ፣ ኖጻ ዘድንጋገ ባሕር፣ ሞት ድንጋገ እድሜ ዘኢይበጽሖ መልአክ፣ ተቀበሎ ዲበ ገበዘ ተከዚ፣ ኢትትአደዊ እምወሰንኪ ይላል።

አድያም፣ ደወል፣ ብሔር

አውራጃ፣ ቀበሌ፣ ግዛት፣ አገር ይሆናሉ። አድያመ ዮርዳኖስ፣ ደወለ ጢሮስ፣ ብሔረ ግብጽ፣ ብሔረ አሕዛብ ይላል። ደወል ተለይቶ ወሰን ድንበር ይሆናል ኢታፍልስ ደወለ ገራህት እንዲል። **ጥቃ፣ ጎር፣ ሕጽን፣ ገቦ፣ ጉንድ** አጠገብ፣ ጎን፣ ወገብ ይሆናሉ። ይነብር ጥቃ ፍኖት፣ ወቤቱ ጎረ ምኩራብ፣ ሕጽነ ደብር፣ ጕንደ ደብር፣ ገቦ ደብር፣ ኢትጸውዕ ጎረከ፣ ይረፍቅ ውስተ ሕጽኑ፣ ይወድቁ በገቦከ፣ አጻብዒከ እም ጕንደ ክልኤ አእጋር ይላል። **ጽጕ፣ ጽጐጕ፣ ጽጐጓት** ጥግ፣ ወልወል ይሆናል። ጽጕ ቤት፣ ጽጕ ሀገር ወለእመ ሀለው ጽጐጓት ማእከለ አብያት ብሎ ወልወል ይላል። **ዐውድ፣ ዘውር** ዙሪያ ይሆናሉ። ክበብ ባለው ሁሉ ይገባሉ ዐውደ ቤት፣ ዘውረ አክሊል። ዐውድ ተለይቶ አደባባይ፣ ሸንጎ፣ አውድማ ይሆናል። ነበሩ ዓውደ ለኰንኖቱ፣ ዘቦቱ ያነጽሕ ዐውደ እክሉ እንዲል።

የጊዜ ጥሬዎች

ቅድም፣ መቅድም፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ

ቀድሞ፣ አስቀድሞ፣ ፊት፣ መጀመሪያ ይሆናሉ።ቅድምና መቅድም ግእዝ ሁነው የቀሩት ጉልት ሆነው ሳይፈልሱ ይነገራሉ። 5ቱ ሁሉ ለአንድና ለብዙ ለወንድና ለሴት ለሩቅና ለቅርብ እየሆኑ እንደ አንቀጻቸው ስልት ይፈታሉ። ቅድመ አሠኒ፣ መቅድመ ኅሡ፣ ቀዲሙ ዜነወነ፣ ዘነገሩክሙ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ ነገረ በኦሪት፣ ቀዳሚ ጸሐፍኩ ለከ ይላል። ተናበው የሚነገሩ ጥንት፣ መሰረት መጀመሪያ፣ ፍጻሜ፣ተፍጻሜት መጨረሻ ይሆናሉ ሲገቡም ጥንተ ሕይወት፣ ጥንተ ዕለት፣ መሰረተ ንጽሕ፣ መሠረተ ቃል፣ ፍጻሜ ዘመን፣ ተፍጻሜተ መዋዕል ያሰኛሉ።

የአካልና የባሕርይ ጥሬዎች

ኩለንታ ሁለንተና፣ ሁለመና ይሆናል ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር እንደ ማለት ነው። **ጠባይዕ** በቁሙ ጠባይ፣ ባሕርይ ይሆናል። **አካል፣ ሕዋስ፣ መንፈስ፣ ነፍስ፣ ነፍስት፣ መሌሊት** አካል፣ ብልት፣ ገላ ሰውነት ይሆናሉ። **አካል** በቁሙ፣ ቁመት፣ አቋቋም ለመያዝ የሚበቃ መጠን፡ ግዘፍ ይሆናል። **ህላዌ** ባሕርይ፣ አካል፣ አቋቋም አናዎር ነው። **ክዋኔ** አኳኋን፣ ሁነታ ማለት ነው።

ጸዋትወ ቅኔ

ሠምና ወርቅ

ሰምና ወርቅ ማለት እንደ ወንድማማች በምስጢር መንታ ሲሆኑ በንባብ ሳይጫፈሩ በ6 ነገር ተባብረው ተጣምረው አንድ ወጣት ቃል መስለው የሚነገሩ ተመሳሳዮች ማለት ነው። ሰምና ወርቅ ሲመሰሉ ሰም ተናቦ እየቀደመ ወርቅ ይከተላል። ወርቅም ቀድሞ ሰም ቢከተል ካልተናበበ ጸያፍ አይባልም። ቢናበብ ግን **ግንባር ጸያፍ** ይባላል። ርኑባን አሕዛብ በልዑ ኀብስተ ሃይማኖት ወይም ኀብስተ ሃይማኖተ በል። በልዑ ሃይማኖተ ኀብስተም ይላል። ሰም ተናቦ ለወርቅ 3

ፊደላት ያተርፍለታል። ፊደላቱም ግእዝ፣ ሳብዕ፣ ኃምስ ናቸው። ይህም ሰሎሞን አማኑኤል ሐነጸ መቅደሰ ደሞ ማሕየዊ ባለ ጊዜ ሳብዕና ኃምስ ማስቀረቱን ያሳያል ባይናበበው ግን ደሞ ማሕየዊ ባለ ነበር። ሰም ለወርቅ የሚያተርፍለት ይህ ብቻ አይደለም። ከዚህ ሌላ ደግሞ 6 ነገር ያተርፍለታል እነዚህም ማሰሪያ አንቀጽ፣ ተናባቢ፣ አፈታት፣ ቅጽል፣ ዝርዝር ናቸው። 6 ነገር ማትረፉም እንዲህ ነው። እመ ርኅራኄ ቤተ ክርስቲያን ትወግእ ጥዑመ ሥጋዌ ሐሊበ እግዚእነ ለደቂቃ ምእመናን በይነ ዘአእመረት በማለት አንቀጽን ለደቂቃ በማለት ዝርዝር ማትረፉን ያሳያል።

ባለቤትና ዘርፍ በሰምና በወርቅ አካሄድ ሲነገሩ ብዙ ስም አላቸው። የሰም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ የወርቅን ባለቤት ሲያመጣ **ውስጠ ወይራ** ያሰኛል። ይህም ነዳያን አሕዛብ በልዑ ኀብስተ ጼጥሮስ ባዕል ባለ ጊዜ ሃይማኖተ ጼጥሮስ ማለቱን ያሳያል። ስሙም ክብ ውስጠ ወይራ ይባላል። የሰሙ ዘርፍ ባዕል ሲቀር ግን ክብ አይባልም። ሁለተኛም የወርቅ ባለቤት እየቀደመ የሰም ባለቤት ተከትሎ ከወርቅ ዘርፍ ሲናበብ **ዝምድ** ያሰኛል። ይህም ተበልዐ ሃይማኖት ኀብስተ ጼጥሮስ ባዕል ማለቱን ያሳያል። ስሙም ድርብ ዝምድ ይባላል።ባዕል ሲቀር ግን ነጠላ ዝምድ ወይም ቅጽል ከምሳሌ ያሰኛል። ሦስተኛም የሰም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ እቀደመ የወርቅ ባለቤት ሲከተል **ፍላጻ** ይባላል። ይህም ተበልዐ ኀብስተ ጼጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ሲል ድርብ ፍላጻ የሰሙ ዘርፍ ባዕል ሲቀር ነጠላ ፍላጻ ይባላል። አራተኛም የሰም ባለቤት በወርቅ ባለቤት ላይ በሚናበብበት ጊዜ በወርቅ ባለቤት ሲጠብቅ **ጥምዝ** ይባላል። ይህም በልዐ ኀብስተ ዘጼጥሮስ ሃይማኖተ ባለ ጊዜ ጥምዝነቱን ያሳያል። አምስተኛም ዘርፍ በዘ እና በለ ሲደፋ ስሙ **ድፋት** ይባላል። ይህም በልዐ ዘጼጥሮስ ባዕል ሃይማኖተ ኀብስተ ቢል የዘ ድርብ ድፋት ባዕል ሲቀር ነጠላ ድፋት መሆኑን ያሳያል። ዳግመኛም በልዐ ለጼጥሮስ ባዕል ጥዑመ ሃይማኖተ ኀብስቶ ጊዮርጊስ ርኁብ ሲል የለ ድርብ ድፋት ባዕል ሲቀር ነጠላ ድፋት ይባላል። ስድስተኛም በልዐ ወይም ተበልዐ ሃይማኖተ ጼጥሮስ ኀብስተ ባዕል ተብሎ በየገንዘቡ ሲነገር ተቻቻይ ይባላል።

የምሳሌ አዋጅ

ሩቅና ቅርብ አንድና ብዙ ወንድና ሴት አይመሰሉም። ይኸውም በማሰሪያ በአንቀጽ በቅጽል ኀብረትና አንድነት የላቸውምና ስለዚህ ነው። ሁለተኛም ወ አንድ ያደረጋቸው ሁለት ስሞች ሰም ሆነው ወርቅም ሆነው ከስም ተዛምደው አይመሰሉም። ነባቢና ኢነባቢ ካህነ እብን ቀዳሲ፣ ስምና ስም ዳዊተ ሚካኤል፣ ስምና ግብር ሰሎሞነ ጥበብ፣ ኀዳሪና ማኅደር ወርቀ መዝገብ ወይም ኀብስተ መሶብ ብሎ አለመመሰል ነው። ምሳሌም ከአንቀጽ ወዲህ እንጂ ከአንቀጽ ወዲያ የለም። ዝናም መጽአ ሆሳእና ቢል **ፍርቅ** ይባላል።

ብትን ሰዋስው

ብትን ሰዋስው ማለት 7 ቅንጣት ጥሬ ወይም 7 ዓይነት ፍሬ ማለት ነው። ውጥንቅጥ እንደ ማለት ነው። እነዚህም ቦታና ጊዜ፣ ባሕርይ እና አካል፣ ስምና ግብር፣ ነገር ናቸው። ብትን ሰዋስውም ያሰኛቸውም አገባብ ሳይዙ ብቻ ብቻቸውን ተነግረው በአፈታታቸው አገባብ ማምጣት

ነው። መድረሻቸው በዝርዝርነት በነባርነት ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ሲሆን በ5 አገባብ አማርኛ ይፈታል። የ5ቱ አገባብ አማርኛ በ፣ ከ፣ ወደ፣ ጋራ፣ ለ ነው። ን ሲሆን ጼሐ ፍኖተ፣ ተከለ ደብተራ፣ ቀሠመ ጽጌ፣ አኀዘ መርኖ ይላል። በ ሲሆን በሁሉ ይገባል። ወደ ሲሆን በቦታ ብቻ ይገባል። ዐርገ ሐመረ፣ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ ማርያምሃ ብሎ ወደ ማርያም እያሰነ ኀበ በገባበት ይገባል።

ግብር፣ ነገር በዝርዝርነት በነባርነት ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ሲሆኑ በ ይሆናሉ። በ6 ግሦች ያሳስራሉ። ግሶችም ንእሰ፣ ዐብየ፣ ዐረየ፣ ቀደመ፣ ኀብረ፣ ስክረ ናቸው። ኢትስክሩ ወይነ ብሎ በወይን፣ ዐረይነ ሕማመ፡ ንዴሪ ክብረ ምስሌሁ በመከራ ብሎ በክብር፣ ቀደመ አሳሄል ሩጸተ እም አብያጺሁ ብሎ በሩጫ፣ ኀብሩ ምክረ ወሃይማኖተ ብሎ በምክር በሃይማኖት ያሰኛል። ጊዜም በ ሲሆን ለቦታ በሚስማሙ አናቅጽ ያሳስራል። ይህም ሌሊተ ቦኡ ወሌሊተ ወጽኡ፣ መዓልተ ወሌሊተ ዕቀበነ አንተ ይላል።

ግብር፣ ነባር፣ ባሕርይ፣ አካል ግእዝና ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ሁነው ሲነገሩ ከ ይሆናሉ። የሚስቧቸውም አናቅጽ ጸምአ፣ ርኅበ፣ ነድየ፣ ተዐርቀ፣ ጸመ፣ ዐብየ፣ ንእሰ እነዚህን የመሰሉ ናቸው። ተዐርቀ ልብሰ፣ ርኅበ ኀብስተ፣ ተከልዐ ውዴተ ወሐሜተ ብሎ ከሐሜት ማለቱን ያሳያል። ብትን ሰዋስው ሁሉ በዝርዝርነት በነባርነት ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ሲሆን ጋራ፣ እንደ ይሆናል። ተማከረ ሰብአ ብሎ ከሰው ጋራ ያሰኛል። ተቀስፈ እግዚእነ ሰራቂ፣ ወተሰቅለ እቡሰ እንደሌባ እንደ በደለኛ ይላል። ሁኖም ሲሆን አምላክ ሞተ ሰብአ ብሎ ሰው ሆኖ ይላል። አድርጎም ሲሆን አስተየ ማየ ወይነ ውሃውን ወይን አድርጎ ይላል። መስሎም ሲሆን አስተርአየ ሰይጣን ሰብአ፣ አስመስሎም ሲሆን ይውህብ ሰይጣን እብነ ወርቀ አው ኀብስተ ይላል። ተብሎም ሲሆን ተሰቅለ ክርስቶስ ኃጥአ ይላል።

ሙሻ ዘር

ተናቦ የሚስብና ደቂቅ አገባብ የሚያመጣ ተናባቢ ዘር ማለት ነው። ሳድስ ቅጽል ተናቦ 9ኙን አገባብ ሲያመጣ ክርስቶስ ምውተ አዳም ብሎ ለአዳም ስለ አዳም የሞተ፣ ስቁለ ፈያት ሲል ከወንበዶች ጋራ እንደ ወንበዶች ማለት ነው፣ ገብርኤል ፍንወ ማርያም እስከ ማርያም ወደ ማርያም ይላል፣ ሰሎሞን ንጉሠ ዳዊት ሲል የዳዊትን ያህል የነገሠ፣ አዳም ፍጡረ መራት ሲል ከመራት የተፈጠረ፣ ኢየሱስ ስቁለ ዕፅ ወቅንወ ሐጺን በእንጨት የተሰቀለ በብረት የተቸነከረ ይላል። ዳግመኛም የስድስቱ አዕማድ ሣልስ ቅጽል (6 ያለው 5ቱ አዕማድ አቅታሊ፣ ተቀታሊ... ወዘተ ያለውንና መስም ውስጠዘን ጨምሮ ነው) ከብትን እኒህን ዘጠኙን ሲያመጣ አገባቡ እንዲህ ነው። የገቢር ሣልስ ለንና በእንተን ሲያመጣ አብ መጣዌ ዓለም ወልደ ከመ ይኩን ቤዛ። ከመንና ምስለን ሲያመጣ ጲላጦስ ቀሣፌ ሰረቅት ወሰቃሌ ፈያት ክርስቶስሀ ይላል። ኀበንና እስከን ሲያመጣ አብ ፈናዌ ማርያም ገብርኤልሀ፣ መጠነን ሲያመጣ ሳሙኤል ቀባኤ ሳኦል ዳዊትሀ፣ እምንና በን ሲያመጣ ወልድ ፈናዌ ሰማይ መንፈሶ ወከዓዌ አርድእት ሞገሶ ያሰኛል።

አርእስትና ሳቢዘር የገቢር አርእስት 9 አገባብ ሲያመጣ ደለዎ ለክርስቶስ ለባሴ ክህነት ጸውዖተ ሐመር አርድእተ ወአንኖተ ደብር ስብከተ፣ መጥዎተ አዳም ነፍሶ ወአኀስሮተ ገብር ርእሶ (እም፣ በ፣ ለ፣ በእንተ፣ ከመ፣ መጠነ)። መዊተ ፈያት ስቁለ ወፈንዎ ቤቱ ገነት የማናየ ርግበ በእንተ መሓላሁ (ምስለ፣ ኀበ፣ እስከ) የቀሩትም ሳቢዘሮችና አርእስቶች እንዲህ ይገባሉ። ስቅለተ አዳም ተሰቅሎተ አዳም ፈቀደ እግዚአ (ለ፣ በእንተ)። አፍቀረ ወልድ ልደተ ማርያም ወይም ተወልዶተ ማርያም (ም)። ተክህሎ ለንስር አብጽሖተ ኤርምያስ ጦማረ (ኀበ፣ እስከ)።

ሠረዝ

ሠረዝ ማለት ፍጹም ቃልን ከቃል የሚለይ ማእከላዊ ነቁጥ ማለት ነው። በዚህ ክፍል ሠረዝ የምንለው በሠረዝ ተከፍሎ የሚነገር 7 መንታ ቃል ነው። ኀዳሪና ማኀደር፣ ወላጅና ተወላጅ፣ ገንዘብና ባለገንዘብ፣ ልዑልና ትሑት፣ ሩቅና ቅርብ፣ ለሚና አልሚ፣ አጥፊና ጠፊ ናቸው። 2ኛም ታጥፎ ተመላልሶ እየተዛወረ የሚነገር ስለሆነ ተዛዋሪ ይባላል። ዐቢይ አገባብ የሌላቸው የፍጹማን ቃላት አነጋገር በየአገባቡነና ሲጠቀለል ስልቱና ዓይነቱ 5 ነው። 1ኛው በአው፣ ወሚመ ማሻሻል ማማረጥ፣ 2ኛው በዋዌ መደርደር ተሠይጠ ዮሴፍ ወኮነ ገብረ ወሐማ እገሪሁ በመዋቅሕት እንደማለት ነው፣ 3ኛው በወ፣ ሂ፣ ኒ እና በሰ በባሕቱ መክፈል ነው፣ 4ኛው ነጥሎ ደርቦ መሠረዝ፣ 5ኛው ማነጻጸር ነው። በክፍልም ሆኖ በሠረዝም ሆኖ ሲነገሩ ለሁሉም የተለየ አገባብ አላቸው። የኀዳሪ ለ ነው። የማኀደር ኀበ፣ ዲበ፣ ላእለ፣ መልእልተ፣ ታሕተ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ ውስተ፣ ውስጠ፣ ማእከለ በ እየተሰማቸው ሁሉም በ ናቸው። የወላጅ እም ተወላጅ ለ ናቸው። የገንዘብና የባለገንዘብ ለ፣ በ፣ ኀበ ናቸው። የልዑልና የትሑት በ፣ ኀበ፣ ታሕተ፣ ቅድም፣ እም ናቸው። የለሚ ለ፣ ኀበ፣ ቅድመ የአልሚ በ ናቸው። የጠፊና የአጥፊ መንገድ በ፣ ኀበ፣ ቅድመ ናቸው። የሩቅ እም የቅርብ ኀበ፣ መንገለ፣ ለ ናቸው። በተገናኝ የሁሉም ማሰሪያ ውእቱ ነው።

ኀዳሪና ማኀደር በነጠላ ገብተው በክፍል ሲነገሩ ማርያም ለአማኑኤል መዝገብ ይእቲ፤ ወአማኑኤል በማርያም ወርቅ ውእቱ ይላል። ስትፈታም ማርያም ለአማኑኤል ሳጥን ናት። ዐማኑኤልም በማርያም ዘንድ ወርቅ ነው። በነጠላ ገብተው በሠረዝ ሲነገሩ መቃብር ወመዋቲ ለመዋቲ ወታሕተ መቃብር ገራህተ ዘርዕ ወዘርዐ ገራህት ይላል። ስትፈታም መቃብር ለሚች የዘርዕ እርሻ ናት። ሚችም በመቃብር ታች የእርሻ ዘር ነው። ሁለተኛም በሰምና በወርቅ ገብተው በክፍል ሲነገሩ። ማርያም መዝገብ ለአማኑኤል ወርቅ ሰማይ መዳይ ይእቲ፣ ወአማኑኤል ወርቅ በማርያም መዝገብ መንፈስ ቅዱስ ብሩር ውእቱ ይላል። ስትፈታም ማርያም ሳጥን ለአማኑኤል ወርቅ ሰማይ መዳይ ናት። አማኑኤል ወርቅም በማርያም ሳጥን መንፈስ ቅዱስ ብር ነው። በሠረዝም ሲነገሩ ማርያም መዝገብ ወአማኑኤል ወርቅ ለዐማኑኤል ወርቅ ወበማርያም መዝገብ ሰማይ መዳይ መንፈስ ቅዱስ ብሩር ይላል። እንደላይኛው ፍታ።

ወላጅና ተወላጅ በነጠላ ገብተው በሠረዝ ሲነገሩ ራሔል ወዮሴፍ ለዮሴፍ ወእም ራሔል ያዕቆብ ወብንያም ይላል። በሰምና ወርቅ ገብተው በክፍል ሲነገሩ ገቦ ኢየሱስ ከርሠ አንበሪ ለዮናስ ደም፣ ክሣደ ጊዮርጊስ እም ወዮናስ ደም እም ከርሰ አንበሪ ገቦ ኢየሱስ ማየ ሕይወት ዓሣ ውእቱ ይላል።

ገንዘብና ባለገንዘብም በነጠላ ገብተው በክፍል ሲነገሩ ዘመነ ሊቃውንት ለትምህርተ ሃይማኖት ዘመነ ሐዋርያት ውእቱ ወትምህርተ ሃይማኖት ለዘመነ ሊቃውንት መሥዋእተ ወንጌል ውእቱ ይላል። ይህ ቦታና ጊዜ ሲገቡ ነው። በነጠላ ገብተው በሠረገ ሲነገሩም ተክለ በለስ ወገነት ወለተክለ በለስ ተክለ ወይን ወደብር ውእቱ ይላል። ይህም ቦታና ግብር ሲገቡ ነው። በሦምና በወርቅ ገብተው በክፍል ሲነገሩ አካልም ገንዘብና ባለገንዘብ ሲሆን ዳዊት ወልድ ለሚካኤል ኢዮአብ ሰሎሞን አብ ውእቱ ወሚካኤል ኢዮአብ ለዳዊት ወልድ ገብርኤል አቢሳ ውእቱ ይላል። የሁሉም አገባብ ለ ነው። ዳግመኛም አካልና ነገር በሦምና በወርቅ ሲገቡ ንሥሓ ወርቅ ለአዳም ኪራም ብሩር ጌጋይ ውእቱ ወአዳም ኪራም ለንሥሓ ወርቅ ዳዊት ነዊ ውእቱ።

ልዑልና ትሑት በነጠላ ገብተው በክፍል ሲነገሩ ወርቅ እም ብሩር ዕንቁ ባሕርይ ውእቱ ወብሩር እም ወርቅ ኀጺን ውእቱ ይላል። በሦምና በወርቅ ገብተው በሠረገላ ሲነገሩ ጴጥሮስ ወርቅ ወይሁዳ ብሩር እም ይሁዳ ብሩር ወእም ጴጥሮስ ወርቅ ክርስቶስ ዕንቁ ባሕርይ ወመልአከ ዝንቱ ዓለም ኀጺን ውእቱ ይላል።

ለሚና አልሚ በነጠላ ገብተው በሠረገ ሲነገሩ ነፋስ ወእሳት ለእሳት ወበነፋስ ሕይወት አርዝ ውእቱ ይላል። በሦምና በወርቅ ገብተው በክፍል ሲነገሩ ንጽሕና ነፋስ ለሥጋ ማርያም እሳት ክብረ መላእክት ሕይወት ወሥጋ ማርያም እሳት በንጽሕና ነፋስ አካለ ኪሩብ አርዝ ውእቱ ይላል።

ጠፊና አጥፊ ደግሞ በነጠላ ገብተው በሠረገ ሲነገሩ ቤት ወነፋስ በኀበ ነፋስ ወቤት ደመና ንስር ውእቱ ይላል። በሦምና ወርቅ ገብተው በክፍል ሲነገሩ አበሳ አዳም ቤት በኀበ ደመ ኢየሱስ ነፋስ አበሳ ሔዋን ደመና ውእቱ ወደመ ኢየሱስ ነፋስ በኀበ አበሳ አዳም ቤት መስቀል ንስር ውእቱ ይላል።

ሩቅና ቅርብ በነጠላ ሲገቡ ሩቁ ፀሐይ እምነ ምድር ሰማይ ቅርቡም ኮከብ ለወርኀ ፀሐይ ይላል። በሦምና በወርቅ ሲገቡም ሩቁ ሥጋ ማርያም ፀሐይ እምነ ምድር አበሳ አካለ ሱራፊ ሰማይ ቅርቡም ሥጋ ማርያም ኮከብ ለወርኀ ንጽሕና አካለ ኪሩብ ፀሐይ ይላል። የሠረገ አፈታት ሲገለጥ ማርያም ለአማኑኤል ከመ መዝገብ ይእቲ ወአማኑኤል በማርያም ከመ ወርቅ ውእቱ ማለት ነው።

አንጻር

አንጻር የምንለው ፊት የተነገረው ፍጹም ቃል በደቂቅ ቅጽል ሲታጠፍ ፊተኛውን ለመግለጥና ለማስረዳት ከአጸፋ በኋላ የሚጨምር ቃል ነው። አስተጣጠፉም ትእምርተ ዝኒ ከመ ንርኣይ እንዳለው ነው። የአንጻር ጥሬዎች ንባብ፣ ዜና፣ ነገር፣ ጽድቅ፣ አማን እውነት፣ አምሳል፣ ምሳሌ፣ ጽላሎት አምሳያ፣ አርአያ አብነት፣ ተአምር፣ትእምርት ምልክት ሲሆኑ እነዚህንም የመሰሉ ተውላጥና ፍዳ፣ ጥንት፣ መሠረት፣ ፍጻሜ፣ ተፍጻሜት ተጨምረው ከደቂቅ ቅጽል እየተናበቡ በጥሬነታቸው የአጸፋ ባለቤት ሲሆኑ ወይም ከመ በኃላፊና በትንቢት በነገር ገብቶ

ሲጫናቸው ኂለኛውን ቃል ከፊተኛው ያነጻጽራሉ። ማሰሪያቸውም ኮነ፣ ረሰየ፣ ጸድቀ፣ ተሐሠወ፣ ተከሥተ፣ ነጸረ፣ ሰአለ፣ ለበወ፣ ዖቀ፣ ጠየቀ፣ ጽሕቀ እነዚህን የመሰለ ነው።

አመረ=አወቀ

አሚር፣ አሚሮት=ማወቅ፣ ዐዋቂነት

አሚሮቱ=ማወቁ፣ አሚሮቶ=ማወቁን

አሚሮተከ፣ ተክሙ፣ ተነ እያለ ማወቅህ ማወቃችሁ ማወቃችን እያለ ያሳያል።

ኢአመረ አላወቀም፣ ኢየአምር አያውቅም፣ ኢይእምር እንዳያውቅ ላያውቅ ሳያውቅ፣ ኢይእምር አይወቅ፣ ኢያእመረ አላሳወቀም ይላል አ በኢ ምክንያት ያ ይሆናል።

የቦዝ አንቀጽ ዝርዝር እስከ 80 ሲሄድ

አሚሮሁ=አውቆት፡ ለት፡ በት፣ አሚሮሆሙ፣ ክሙ፣ ሃ፣ ኪ፣ ሆን፣ ክን፣ የ፣ ነ ይላል

አሚረከሁ፣ ሆሙ፣ ሃ፣ ሆን እያለ በሌላውም ይሄዳል።

የጽንዕ አንቀጾች

የጽንዕ አንቀጾች ኮነና ሀሎ፣ ውእቱና ቦ፣ ሎ ናቸው። አሚሮ ሀለወ ብሎ አውቋል፣ አውቆ ነበር ይላል። የአምር ሀሎ ብሎ ያውቃል፣ ያውቅ ነበር ይላል። አሚሮ የሀሉ አውቆ ይኑር።

ግጥም

አፍ አለጆሮ ቢያዜም ቢያነብ

አይታነጽም ሸካራው ልብ

::

መራራው ጥዑም ስለተባለ

ማር የማይጥመው ብዙ ሰው አለ

“አ”

አንደኛ የመጀመሪያ ፊደል፣ የፊደል ሁሉ ራስ፣ በኩር ቀዳማይ ነው። አ የማብዛት ልማድ ፍችው ዎች ነው። ደብር፡ አድባር፣ ወግር፡ አውግር፣ ፈለግ፡ አፍላግ ይላል። ተራሮች፣ ኮረብቶች፣ ወንዞች ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም “ት” ምዕላድ እየሆነለት ከት ጋራ ያበዛል። ጥብ፡ አጥባት፣ ነቅዕ፡ አንቅዕት፣ ባሕር፡ አብሕርት። ዳግመኛም በአ ብቻ የሚበዛ ቃል “ት” ሲጨመርበት የብዙ ብዙ ይሆናል። አድባር፡ አድባራት፣ አውግር፡ አውግራት፣ አፍላግ፡


አፍላጋት፡፡ በአ እና በት የሚበዛም የብዙ ብዙ ለመሆኑ ሁለተኛ ት ይፈልጋል፡፡ ነቅዕ ብሎ አንቅዕት፡ አንቅዕታት ይላል፡፡ አ የማስደረግ ልማድ ፍችው አስ ነው፡፡ ቀተለ፡ አቅተለ፣ ክህለ፡ አክሀለ፣ ገብረ፡ አግበረ፡፡ ዳግመኛም ቆመ፣ ቦአ፣ ወጽአ ይህን በመሰለ በሐውልትና በአንጉል ግስ ላይ ሲጨመር የማድረግና የማስደረግ ልማድ እየሆነ አንዱን አንቀጽ በሁለት ጾታ ያስፈታል፡፡ አቀመ ብሎ አቆመ፡ አስቆመ፣ አብአ ብሎ አገባ፡ አስገባ፣ አውጽአ ብሎ አወጣ፡ አስወጣ፣ አምጽአ ብሎ አመጣ፡ አስመጣ ይላል፡፡ በካልዓይና በሣልሳይ ራሱን እየጎረደ የትንቢት መነሾች አሥራውን ሁሉ ራብዕ ያደርጋል፡፡ አቅተለ፡ ያቀትል፣ አግበረ፡ ያገብር ይላል፡፡ አእመረ፡ ያአምር፡ ያእምር ይላል፡፡ ሖርኩ፡ አሐውር፣ ዐረጉ፡ አዐርግ፣ ወረድኩ፡ እወርድ፡፡ በማስደረግ ጊዜ ሁለተኛ አ ስላለበት ራብዕ ይሆናል፡፡ አሖርኩ፡ ኣሐውር፣ አዕረጉ፡ ኣዐርግ፣ አውረድኩ፡ ኣወርድ አእመርኩ ብሎ ኣአምር ይላል፡፡ ኣ የቅጽል በር ከፋች ነው በዝረዝር ጊዜ ዚኣሁ፣ እንቲኣሁ፣ እሊኣሁ ይላል፡፡

አአትሪኮን፡ ዝርው ቃል፣ ድምጽ ሰብአዊ ፍሬ ነገር የሚሰማበት ነው፡፡ አብ(ጥ)፡ የዕብራውያን ወር ነሐሴ ወይም የሚያዝያ አምስተኛ ነው፡፡ በዘጠነኛው ቀን ያውም በጨረቃ ቁጥር ፊተኛውና ኋለኛው ሁለቱ መቅደሶች በዘመን ሩጫ ተከታትለው የፈረሱበት የተቃጠሉበት ስለሆነ ዕለቱን 24 ሰዓት ይጾሙታል፡፡ ወርኑንም ወርኀ ምዝባሬ ይሉታል፡፡ **አባ**፡ ወላጅ አባት፣ ወንድ ተባት፣ በዘር በሩካቤ የሚወልድና የሚያስወልድ ነው፡፡ አብ በጥሬነቱ ዘርፍ ይዞ ሲቀጸል ወይም በቂ ሆኖ እንደ ዘርፍ ሲፈታ ምስጢሩ ከአባትነት ከጌትነት ከባለቤትነት አይወጣም፡፡ አባም በአማርኛ ለሥጋዊ አርበኛ የፈረስ ስም ሆኖ ሲነገር እንደዚሁ ነው፡፡ አባ ጠቅል ብሎ የጠቅል ጌታ ወይም ባለቤት ያሰኛል፡፡ **አበጉንባሕ**፡ ርኩም፣ ጉንባሳ ዘዳ.19፣18 አበጉንባሕ ወከራድዮን እንዲል፡፡ **አበደም**፡ ደመኛ፣ ባለደም፣ ደም አፍሳሽ ወይም የሚች ወገን ደም ፈላጊ፡፡ አድኅነኒ እምአበ ደም እንዲል ደራሲ፡፡

አበምኔት፡ የገዳም አባት ባለገዳም፡፡ **አቤሜሌክ**፣ (ዕብ፣አቢሜሌኽ) አበ ንጉሥ የንጉሥ አባት ማለት ነው፡፡ **አቢሳ**፣ (ዕብ፣ አቢሻይ) አበጋዳ፣ በዓለ ጋዳ እጅ መንሻ የሚሰጥ ወይም የሚቀበል ማለት ነው፡፡ **አቤሴሎም**፣ (ዕብ፣ አብሻሎም) አበሰላም፣ በዓለ ሰላም፣ ሰላማዊ ማለት ነው፡፡ **አቢብ**(ዕብ)፡ መጸው ዘመነ መጸው ከክረምት ቀጥሎ የሚብት የጽጌ የፍሬ የልምላሜ ወራት፣ በዓለ ፋሲካ የሚውልበት ወርኀ ትፍሥሕት፣ ወርኀ ተሐድሶ ይኽውም ሚያዝያ ነው፡፡ **አባዊ፣ አበዋዊ** (ዊት፣ ውያን፣ያት) ወገን ቅጽል በጽሐ ጊዜ ተራኅርኖ ሣህል አባዊት እንዲል ያዕቆብ ዘእልበረዲ፣ ገድለ አዳም፡፡ **አቦ**(ኦሮምኛ) ትግረኞች አባ ጋብር አማሮች አቡየ የሚሏቸውን ጻድቅና ቅዱስ ኦሮሞዎች አቦ ይሏቸዋል፡፡ **አብጥሊስ** የመጽሐፍ ስም ነው፡፡ ሦስተኛው የሐዋርያት ሲኖዶስ ፍቸው ቀኖና ማለት ነው፡፡ **አቤል**፣ (ዕብ፣ሀቤል) የሰው ስም ወልደ አዳም፡፡ አቤል መስክ፣ ጨፌ፣ አልቃሽ፡፡ ሀቤል ከንቱ ብላሽ ማለት ነው፡፡ **አቦሊ** የገንዘብ ስም ታናሽ ገንዘብ፣ 5 ሳንቲም የዲድርክም ኻያኛ፣ በዕብራይስጥ ጌራ ይባላል፡፡ ኻያው ጌራ አንድ ሰቅል እንዲሆን ኻያው አቦሊ አንድ ዲድርክም ነው፡፡ **አቤኔዜር** የረድኤት ደንጊያ፡፡ **እብነ በረድ** ነጭ ደንጊያ በረድ የሚመስል፡፡ **አበቅ**፣ (ዕብ፣ አባቅ) በቁመ ጸበል፣ ትቢያ፣ አቧራ፣ ቅንቅን በነፋስ የሚበን ደቃቅ ነገር ሁሉ፡፡ **አበርጊላ** ገበጣ፣ የገበጣ ጨዋታ፡፡ **አብሲማዳኮስ** (ጽርእ) ከሁለት አንድ የሆነ አምላክ ወሰብእ አንድ አካል፡፡ **አግን** ቡሖ፣ ሊጥ፡፡ **አገን** ንፍጥ

የአፍንጫ እድፍ። **ማሕረጸ አድግ** የወፍጮ ግልገል ማለት ነው። አድግ ታችኛው እናቱ ተሸካሚው ማሕረጽ ላይኛው ልጁ መጁ። እበን፣ ዕፀው፣ ቍየጽ፣ እገር፣ እዘን እንደዚህ ያለው መድረሻው ሳድስ ሆኖ መካከሉ ግእዝ **ዘውግ** ይባላል። አዳም፣ ነቋር፣ ጸጓር፣ ጸዋግ፣ የዋሕ ይህንን የመሰለ ሁሉ ቅጽልነቱ **ፈናፍንታም** ነው። ለወንድም ለሴትም ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የሰው ስሞች ሁሉ ትርጉም ስላላቸው ይህንን የኪዳነ ወልድ ክፍሌን ግስ ማየት ጥሩ ነው። **እድሜ** ቀጠሮ። **አዶናይ** ለአንድ ለብዙ ይሆናል እግዚአየ አጋእዝትየ ማለት ነው። **አህያ፣ ሸርህያ** እሄሉ ዘእሄሉ ማለት ነው። **አውሎጊያ** (ጽር፣ ኤፍሎጊኣ) ቡሩክ ጎብስት ተረፈ መሥዋእት ከቁርባን በኋላ በቡራኬ ጊዜ የሚሰጥ። ሙሴ 40 ዘመን በሱዳን አገር ኖሮ ሱዳናዊትን ሴት እንዳገባ በኦሪቱ ያመለክታል (ዘኍ.12፣1)። **አዜብ** በምዕራብና በደቡብ መካከል ያለ የደቡብ ግራ የመስእ ትይዩና አንጻር ፊት ለፊት፣ እዝናዊ ጆሯም፣ ጆሯማ ነው።



አሐተኔ አንድነት፣ በአንድነት፣ አንድ ላይ። ነበርነ አሐተኔ፣ ተጋባእነ አሐተኔ። **አጥረስካ** ባለቅኔዎች ተዝካር ይሉታል። **ኢዮቤል** ከ49 ዓመት በኋላ በኃምሳኛው ዓመት ብዙ ጠቦት የሚሠዋበት ቀንደ መለከት የሚነፋበት። **ኢያዜር** ዘውድ፣ አክሊል ጋሜ፣ የብጽአት ጠጉር የማይላጭ ባለ ብሉዮች ግን ዘውድ አክሊል በማለት ፈንታ ልብሰ መንግሥት አርድ አንቀጥቅጥ ይሉታል። **ኤረር** ብሩህ ሰማይ ከጠፈር በላይ ከራማ በታች ያለ እሊህም ከጠፈር እስከ ጽርሐ አርያም ያሉት ጉልላት ሰገነት ደርብ ምድር ቤት እንደማለት ናቸው። አየራቸውም ትክክል ነው። የርሕቀቱና የምጥቀቱ መጠን ከአንዱ እስከ አንዱ ሺህ ዓመት ያስኬዳል ይባላል። ዙሪያ ቅጥራቸውም አፍኣው የሚፋጅ ውስጡ የማይፋጅ የእሳት ቅጥር ነው። **ኢየሩሳሌም** ኢ የግእዝ ተውሳክ ነው። የሩ ሀገር ሳሌም ሰላም በተገናኘ ሀገረ ሰላም ማለት ነው። ሳሌም ከመባል በፊት ሴዱ ስላቀናት ሳይዳ ቤተሳይዳ ትባል ነበር። ቤተ ጸጋ ወሣሕል ማለት ነው። ከሴዱ በኋላ ልጁ ሳሌም ስለነገሠባት ሳሌም ኢየሩሳሌም ተብላለች ከዚያ ወዲህ ስሟ አልተለወጠም። **መልከ ጼዴቅን** ዮሐንስ መደብር ከነገደ ካም ያደርገዋል ቀሌምንጦስ ዜና አይሁድና ጊዮርጊስ ወልደ ሐሚድ ደግሞ ከነገደ ሴም ያደርጉታል። **ኢየሱስ** መድኅን፣ መድኃኒ፣ መድኃኒት፣ ቤዛ፣ መቤዝው ማለት ነው። የሱስ ማለት ይበቃ ነበር ኢ እንዲያው በከንቱ ተጨምሯል ምስጢር

የለውም። ኢያሱ ኢዮስያስ እንደማለት ነው። ባለሐዲሶች ግን ኢን አኮ መድኃኒት ሲሉ አይሁድ ጨምረውታል ብለው ያወራሉ ውሸት ነው። **አክሊሮስ** ቁሰ ገበዝ የቤተክርስቲያን ሹም አስተንታኝ። **አክራጦን** ጥሩ የወይን ጠጅ። **አካፅ** ስመ አምላክ አምላክ ከሀሊ ማለት ነው። **አክሲጦስ** ያልታወቀ ጥሬ ትርፍ ቃል በጽርኡም በዕብራይስጡም የሌለ ባለብሉዮች ጉባኤ ነቢያት ጉባኤ ካህናት ይሉታል ወትቤ አክሲጦስ አይቱ ሖረ ወልድ እጉኪ እንዲል ማሕ.5፣17። **አኩስም**፣ (ዕብ፣ አ፣ ኩሽም) አ ጥንት ቀዳማዊ ርእስ፣ ኩሽም ኩሻውያን የኩሽ ልጆች ሕዝበ ኩሽ፣ ነገደ ኩሽ። አኩሽም ጥንታዊት ቀዳማዊት የነገደ ኩሽ መዲና። **አክሲማሮስ** ስድስት ቀን ማለት ነው። የስድስቱን ቀን ስነ ፍጥረት አምልቶ አስፍቶ የሚናገር 22 ብሎ የሚቆጥር የኤጲፋንዮስ መጽሐፍ። **እሉ፣ እሎንቱ** (ዝ፣ ንቱ) ባለቤት ሲኖር ጭብጥ ቅጽል ሲቀር አጸፋና በቂ ይሆናል። **ኤልዳ** ስመ ሀገር አዳምና ሔዋን የተፈጠሩበት ማዕከለ ምድር። **አላዶር** የቀኖት ስም የቀኝ እጅ። **ኤሎሄ** አምላኪየ፣ ፈጣሪየ፣ ለሐኩየ ማለት ነው። **ኤልያስ** ዕፀ ዘይት፣ ፍሬ ዘይት፣ ቅብዐ ዘይት። **ኤልያስ** ስመ ነቢይ ኃይለ እግዚአብሔር ማለት ነው። **ኤላም** (ጽር፣ ዕብ፡ ኡላም) በረንዳ፣ ደጀ ሰላም በታላቅ ቤት ደጃፍ ወይም በቅጥሩ በር የሚሠራ። **እልመክኑን** ጎበዕ ማለት ነው። **ኤልማስ** አምላኪየ ማለት ነው። **እልመስጦ**፣መስጦ እምነት ሃይማኖት ማለት ነው። **አሌፋት** ከአሌፍ እስከ ታው ያሉ መክብባቸው አሌፍ ስለሆነ በእርሱ ስም አሌፋት ተብለው ይጠራሉ። **አልፋ** ስመ አምላክ ቀዳማዊ። **አልፋ** ቅድስት ሥላሴ አ፡ አብ፣ ል፡ ወልድ፣ ፋ፡ መንፈስ ቅዱስ ምስጢሩ ግን ያው ቅድምና ነው አይለወጥም። **ኢሎፍሊ** ስመ ሀገር ይችውም ሜዲትራኒ በሚባለው በታላቁ ባሕር አጠገብ በዳር በድንበሩ በወደቡ ያለች የምድረ እስራኤል ጎረቤት ናት። **አሜክላ** ኮሸሸላ። **እመ አህጉር** መዲና፣ ታላቅ ከተማ። **እብኖዲ** አምላክ። **ኢን**፣ (ዕብ፣ ሂን) የልክ ስም ታናሽ ገንቦ የርጥብ መስፈሪያ መሣሪያ። 12 ሉግ የምትይዝ የአንዱ ሉግ መጠን ስድስት እንቁላል ይሆናል። **አንጌቤን** የወይዘሮ ልጅ በእናቱ ከቤተ መንግሥት የሚወለድ የነገሥታት ወገን፣ ተቀማጭ፣ ሥራ ፈት፣ ድልድል፣ ቅምጥል፣ ቂጣም፣ ዘፍጣጣ። **አናጉንስጢስ** አንባቢ የንፍቀ ዲያቆን ምክትል። **አንጢዲቁማርያጦስ** (ሮማይ) አጽራረ ማርያም። እሊህም በአራተኛው መቶ ዓመተ ሥጋዌ የተነሱ ናቸው። በማርያም ድንግልና ላይ እንደ አይሁድ ክፉ የሚያወሩ የሚናገሩ ናቸው። **አንቄ** ነጣቂ አሞራ፣ ጭልፊት። **አንቀጽ** በር፣ ደጅ አፍ። **እንቆራ** የንብ እንጀራ። **አሠረ ንጉሥ** የቅኔ ስም ለንጉሥ የሚሰጥ የዕጣነ ሞገር ተቀጥላ። **ኢፍ**፣ (ዕብ፣ ኤፋ) የመስፈሪያ ስም ታላቅ ቁና የሐሜር አስረኛ አንዱ ኢፍ ሦስት ስኣ ይይዛል። ስኣ እንደ መሸመቻ ያለች ትንሽ ቁና ነች። **ኤፉድ** ልብሰ ተክህኖ ካህናተ አሪት በተልእኮ ጊዜ የሚለብሱት የሚታጠቁት ቀሚስ ልብሰ እንግድኣ ሰደርያ አጭር ሱሪ ቁምጣ ቆራጣ የሥራ ልብስ ማናቸውም። **ኤፍራጥስ** ከአራቱ ዐበይት አፍላጋት ሁለቱ በአፍሪቃ ክፍል ሁለቱ በእስያ ክፍል ስለሆኑ ግዮን ካርቱም ሲደርስ ከኤፌሶን ገጥሞ አንድ ወንዝ ሆኖ ሜዴትራኒ እንዲገባ ኤፍራጥስም ባቢሎን ሲደርስ ከጤግሮስ ጋር ይገጥምና አንድ ወንዝ ሆኖ ወደ ባሕረ ፋርስ ይገባል። **ኤፌሶን** ስመ ፈለግ ነው። ከአራቱ አፍላጋት አንደኛው መጀመሪያው ወንዝ ጎጃምን የሚከብ ጥቁር ዓባይ ጥቁር መባሉም የውሃው መልክ ዓይነቱ ጎብሩ ጥቁር ኒል ስለመሰለ ነው። ኤ የመላሽ ተውሳክ ነው። **አቅሌስያ** ቤተክርስቲያን ጉባኤ ምእመናን ማለት ነው። **አራቦት** ሜዳ በረሃ። **አርጋኖን** (ጽር) የማሕሌት ዕቃ መዝሙር በገና መልካም ዜማ ለጆሮ ለልብ የሚጣፍጥ ደስ የሚያሰኝ ድምጥ። **አሮድዮን**

ያፈ ያሬድ በአምሳለ ያፍ ታይቶ ዜማ ያስተማረው ምስጢር ያናገረው መልአክ ወይም መንፈስቅዱስ ስንክሳር ግን ሦስት ወፎች ይላል። ያፍ ዘይብልዎ አሮድዮን ከመ ቃለ ጠቢባን ይትፌሣሕ ወይትሐሠይ ሶበ ይትፈለጥ እምኀበ የኀድሩ ሰብዓ ዓለም ወየሐውር ኀበ መካነ በድው ወይነብር ውስቴቱ ወተብህለ በእንተ ውእቱ ያፍ ዘእሙር በክልኤ ሐረታት ከመ ኩሉ ዘሰምዐ ቃናሁ ወንቃወ ዜማሁ ይትአሰር ድኅሬሁ በሐረቱ ውስተ ገዳም እስከ ውእቱኒ እምጣዕመ ቃናሁ ይረስዕ ሕይወቶ ወይደክም ወይመውት። **አርዳሚስ** የሰሎሞን ልጅ የምኒልክ ታናሽ የሮብዓም ታላቅ በነገሥትና በዜና መዋዕል ያልተጣፈ ባለሐዲሶች የሚተርኩት። **አሪት** በቁመ ሕግ ፍትሕ ትእዛዝ። **አረማዊ** የአራም የግሪክ ወገን አሕዛብ አረመኔ፣ ክፉ ጨካኝ፣ እምነት፣ ርኅራኄ የሌለው። **አርስጣላብ** የፀሐይና የጨረቃ የኮከብ መነጽር መልካቸውን አቅርቦ የሚያሳይ የሚያስመረምር ወይም መንገዳቸውን የሚናገርና የሚያስተምር የፍልስፍና መጽሐፍ። **አርቶዶክስ** (ጽርእ) ኦርቶ ርቱዕ ዶክስ ባሕል ሐሳብ በተገናኘ ርቱዐ ሃይማኖት ማለት ነው። **አስጣሮት** ጣዖታት የበግ መንጋ የሚመስሉ በበጎች አምሳል የተቀረጡና የተሳሉ የበግ ምስሎች። ባለብሉዮች ግን ከዋክብት ሦስቶ ስድስቶ ይሏቸዋል። **እስያ** ስመ ክፍለ ምድር የአውሮፓ ምስራቅ የቱርክ ሀገር ደግሞ ለብቻዋ ታናሽ እስያ ትባላለች። ዘየዐቅብ እስኪተ የዐቅብ ሕይወተ ይላል ፈላስፋ። **እስፍንቶፎኔሕ** የፍልስፍና ስም ፈርዖን ለዮሴፍ ያወጣለት ከሣቴ ኀቡእ ማእምረ ኀቡኣት ማለት ነው። **አሶር** ስመ ነገድ ስመ ሀገር ታችኛው ሶርያ ነነዌ። **አስራብ** ፈሰሾች። **አስቴር** ኅብእት ስውርት። **ኢትዮጵያ** የካም ልጅ የኩሽ ሌላ ስሙ ነው። መዲናውና መቃብሩ አኩስም ናት። በብሉይ በሐዲስ የተጣፈው ዋነኛውና መደበኛው ኢትዮጵያ ግን ታላቁን በረሓ ሰሐራን ጨምሮ የኖባ ክፍል ነው። **ኤታኒም** (ዕብ) የዕብራውያን ሰባተኛው ወር ጥቅምት ነው። ሰባተኛነቱ ለሚያዝያ ነው። በፀሐይ ቁጥር ግን የመስከረም ጫፍ ይሆናል። ዘሌ.23፣24 አመ ርእሰ ሳብዕ ወርኅ ግበሩ መጥቅዐ ባለው ይታወቃል። የግእዝና የቅብጥም ዓውደ ወርኅ በመስከረም ራስ መሆኑ መጥቅዕን መሠረት ይዞ ነው። ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ቀዳማይ ወርኅ ኤታኒም ነበረ። ኋላ ግን ከግብጽ የወጡበት ኔሳን ስለሆነ በሚያዝያ እንዲያከብሩ ነገራቸው። **አተርጋምን** (ጽርእ) ቃል፣ ድምጽ ቃለ መላእክት። **አትሮንስ**፣ (ጽር፣ ትሮኖስ) የንጉሥ ዙፋን የጳጳስ ወንበር ታላቅ ምጡቅ የሰባኪ የአንባቢ ስፍራ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰራ የመጽሐፍ ወንበር ታጥፎ የሚቀመጥበት ተዘርግቶ የሚነበብበት። **ኤጲፋንያ** (ጽር) አስተርእዮ፣ መታየት፣ መገለጽ ዕለተ ጥምቀት። **ኤጲስ ቆጶስ**፣ (ጽር፣ ሄፒስኮፖስ) ጠባቂ ምምህር የጳጳስ ሁለተኛ የሊቀጳጳስ ሦስተኛ ነው።

"በ"

ቦኣኔርጌስ (ጽር፣ ዕብ በኔይ ርጎሽ) ደቂቀ ነጎድጓድ። **ብእሲሁ** ሰውየው ሰውነቱ ይህ ሰው ያ ሰው። **ብእሲቶ** የቅርብ ሰሚ ተጠሪ አንች ሴት እሜቶ ወይዘሮ ብእሲና ብእሲት እንደወርቅና እንደ ሐራ ውስጠ ብዙዎች ስለሆኑ ግልጠ ብዙነት የላቸውም። **ቡባ(ጥ)** (ዕብ) አሻንጉሊት በወንድ ወይም በሴት ልጅ አምሳል የሚሰራ የልጅ የሕጻን መጫወቻ ልጅን ና ልዘልህ ሲሉ እንቡ እንቡቡ ማለት ከዚህ የወጣ ነው። **ባቢል** ስመ ያፍ የተረት ወፍ እንደ ፊንክስ ያለ በፍጥረታት ውስጥ የሌለ ያልነበረ ያልተፈጠረ መሐመዳውያን ሱር በሚባለው መጣፋቸው የሚያወሩት። **ባቤል** (ዕብ፣ ጽር፡ ባቢሎን) ስመ ሀገር ቱሣሔ፣ ጉሠት፣ ሠጠት፣ ድብልቅልቅ፣

ዝብርቅርቅ፣ ቅልቅል፣ ውጥንቅጥ፣ ቅይጥ፣ ምስቅልና ማለት ነው። ባለብሉዮች ግን ዝሩት፣ መካነ ዝርወት እንተ ባቲ ተዘርው አበው ቀደምት ወተሌለዩ ልሣናት ይሉታል ዘፍ.10፣10። **በግዕ**፣(ዕብ፣በግ) የክርስቶስና የእውነተኛ ክርስቲያን ምሳሌ በጎ ማለት ከዚህ ወጥቷል። **ባጎር** ጎበዝ፣ ጎልማሳ፣ ሰሎሞን። **ብድብድ** ሞተ ግብት፣ ቸነፈር፣ መቅሠፍት፣ ፈጥኖ የሚገድል፣ ክፉ፣ ጨካኝ ንጉሥ እንደ ሄሮድስ እንደ ቴዎድሮስ ያለ። **ባህል** በቁሙ ነገር፣ ክርክር፣ አባባል፣ አነጋገር፣ የነገር ስልት፣ ትርጓሜ ምስጢር፣ ድርሳን፣ ልማድ፣ ሕግ፣ ሥርዓት፣ የሃይማኖት ትምህርት ነው። **ብሄሞት** (ዕብ) ጉማሬ፣ የወንዝ አውሬ፣ የባሕር ፈረስ፣ ቆርበተ ወፍራም፣ አንገተ ደንዳና፣ የበረሓ ጎሽ፣ ጠባዩ የአውሬ መልኩ የበሬ ነው። **ቡኣት፣ በአት** መግባት አገባብ። **በአት** (ጥ) ዋሻ። **ቦዝ** ቸልታ አንቀጽ። **በዊሕ፣ ሖት**፣ (ቦሐ፡ ይበውሕ፡ ይባሕ፣ ዐረ፡ ባሐ) መታየት፣ መገለጥ፣ መጉላት፣ ብሩህ ጽዱል፣ ፀዐዳ መሆን። ቡሔ፣ ቢሓ፣ ብሓ ማለት ከዚህ የወጣ ነው። **በሐሱ** የበግ የፍየል ተባት። **ብሔር** ቦታ ሰፈር፣ ስፍራ በሀገር ውስጥ ያለ ታናናሽ ክፍል። **ባሕርይ** በቁሙ የነገር ሁሉ ሥር መሰረት ምንጭ፣ መውጫ፣ መፍለቂያ፣ መገኛ፣ ጠባይዕ፣ ህላዌ፣ ክዋኔ፣ ባሕርይ። በግእዝ ቋንቋ አካላዊ ፍጹመ አካል ቢባል እንጂ አካል አይባልም። አካልም ባሕርያዊ ሕያወ ባሕርይ ቢባል እንጂ ባሕርይ አይባልም።ከባሕርይ ለሚገኝ ባሕርያዊ ስራ ሠሪው አካል መሣሪያው ባሕርይ ነው። አካል ሠሪ እንዲባል ባሕርይ ደግሞ ሠሪ አይባልም። ማጭድ መጨፈጃ እንጂ ዐጫጅ እንዳይባል። አካልን ከባሕርይ ገባሪን ከግብር በየስሙና በየስልቱ ለይቶ የማያውቅ መምህር ግን አካል ሲሉት ባሕርይ ባሕርይ ሲሉት አካል እያለ የግእዝን ቋንቋ የመጻሕፍትን ቃል የሊቃውንትን ባህል ትርጓሜና ምስጢር ያበላሻል። **ባሕታዊ** ጳውሊ 80 ዘመን ሰው ሳያይ በበረሃ ኖሯል። ስለዚህ ሊቀ ባሕታውያን ይባላል። ባሕታዊ ብቻውን የሚኖር፣ ብቸኛ፣ ስደተኛ፣ መናኝ መነኩሴ፣ ዝጉሕ፣ ከዓለም ከሰው ተለይቶ ከአራዊት ጋራ በዱር በጣሻ በገደል የሚኖር ከቀድሞ ሰዎች እንደ ኤልያስ እንደ ዮሐንስ ከኋላ ሰዎች እንደጳውሊ እንደእንጦንስ ያለ። **ቤዝዎ፣ ዎት** መቤዠት፣ ማዳን፣ መታደግ፣ ከጭንቅ ከባርነት ማውጣት ነው። ለውጥ መስጠት፣ ገንዘብን ወይም ራስን እንደ ክርስቶስ። **ቤዛ** በቁሙ ዋጋ፣ ካሣ፣ ለውጥ፣ ምትክ፣ ዋቢ፣ ዋስ፣ መድን፣ ተያዥ። **ብሉይ** በቁሙ ያረጀ፣ ያፈጀ፣ አሮጌ፣ አንቲካ፣ ጥንታዊ፣ ቀዳማዊ፣ የዱሮ፣ የቀድሞ፣ የፊት ሕግ፣ ኪዳን፣ መዋዕል፣ ዘመን። **ብሌን** የኩል መኪያ ሣር የዓይን ማሚቶ ብረቲቱን ብሌን ማለት ከዚህ የወጣ ነው። **በልቀም** መሬታዊ ባሕርይ የሚዝል የሚደክም፣ የሚተኛ፣ የሚጋደም። **በለሶን** ዕፀ አእምሮ የገነት በለስ አዳምና ሔዋን ፍሬውን በልተው ቅጠሉን የለበሱት ኋላም የጌታ ልደት እለት በተአምራት መልአክ አምጥቶላት ዳግሚት ሔዋን ድንግል ማርያም ለልጇ ለዳግማይ አዳም ያለበሰችው ነው። ከደነቶ እሙ ቆጽለ በለሶን እንዲል ድጓ። **ብንት** የዓይን ማሚቶ ጥቁሩ ብረቱ ብሌኑ እንደ መስታዎት የሰው መልክ የሚታይበት። ብርሃን የሚሳልበት። **ብሥራትከ፣ ኪ** እያለ ይዘረዘራል። የምስራች ደስ ይበልህ ማለት ነው። **ባሦር**፣ (ዕብ፡ ባሣር፣ ሱር፡ ቤስራ) ሥጋ፣ የሥጋ ክፍል። **በዓል** በቁሙ የደስታ የዕረፍት ቀን ያለፈ ነገር የሚታሰብበት። ሕዝብ የበዓሉን ምስጢር እያሰበ ደስ ብሎትና ለብሶ አጊጦ የሚዘምርበት እልል የሚልበት ነው። **በዓለ አርብዓ** ዕርገት። **በዓለ ኀምሳ** ጰራቅሊጦስ። **በዓለ መርዓ** የሙሽሮች በዓል። **በቅል** በቅሎ አጋሠሥ። **በርበር** ያልተማረ ያልሠለጠነ ሕዝብ በቅሚያ የሚኖር አረመኔ ሸፍታ፣ ወያኔ። **ዕብሬት** ፈረቃ፣ ፈንታ፣ ተራ፣ ሰሞን፣ የጊዜ ክፍል። **ብርኒ**

ድመት፡፡ **ብርፎሪኮን** የትንቢትና የተግሣጽ የስብከት ቃል፡፡ ቤርሳቤሐ፣ (ብዔር ሻባዕ) አዘቅተ መሐላ፡፡ ባስልዮስ የሰው ስም ንጉሥ ንጉሣዊ ማለት ነው፡፡

"ገ"

ጌ፡ (ጽር፡ ጊ) ምድር፣ ሀገር፣ ርስት ማለት ነው ባለጌ፣ ሐጼጌ፣ እቴጌ እንዲሉ፡፡ ግእዝ፡ የቋንቋ ስም ሴማዊ አዳማዊ ቋንቋ ነው፡፡ **ገቦ**፡ ጎድን፣ ወገብ፣ ወገን፣ ማእዝን፣ ቅርብ፣ አጠገብ ይላል ግንቦት ማለት ከዚህ ወጥቷል ገቦ ክረምት ማለት ነው፡፡ **ጉባኤ ቃና**፡ የቅኔ ስም፣ መጀመሪያ ቅኔ ባለ ሁለት ቤት፡ የስሙ ንባብና ምስጢር ከወንጌል ወጥቷል ዮሐ.2፣11፡፡ **ገብላ**፡ ገንዳ፣ ከግንድ ከደንጊያ የሚሰራ ማቡኪያ፣ የከብቶች ውሃ ማጠጫ፡፡ **ግብጽ**፡ ስመ ነገድ፣ ስመ ሀገር የካም ዕፃ የእስያና የአፍሪቃ ወሰን ድንበር ማለት ነው፡፡ በግብጽ ፈንታ ቅብጥ ይላል ፍችው አንድ ነው፡፡ **ገበታ ሐዋርያ** (አማርኛ) የመጽሐፍ ስም ከያዕቆብ እስከ ይሁዳ ያሉት ሰባቱ የሐዋርያት መልእክታት ናቸው መጽሐፉን ገበታ ያሰኘው እንጨቱ ነው፡፡ **ተጋደለ**፡ በቁመ ታገለ፣ ተናነቀ፣ ተቋሠለ፣ ተጋ፣ ተዋጋ፣ ተሰለፈ፣ ተቃወመ፣ ተከራከረ፣ ተደባደበ በጉልበት በአንደበት በመሰለው ሁሉ፡፡ **ገድል**፡ በቁመ ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ ድል እና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም የሚሠሩት ሥራ የሚቀበሉት መከራ ነው፡፡ **ገሐድ**፡ በቁመ የልደት የጥምቀት ዋዜማ እንደ አርብና ረቡዕ የሚጾም፡፡ **ጉሕና**፡ በቁመ ዓቢይ ዜማ፣ስልት ያለው ጩኸት፣ ጉማ፣ ወፍራም ድምጽ፡፡ **ገሀነም**፡ የእሳት ጉድጓድ ዐዘቅት፣ መካነ ኃጥዓን፣ ኃጥዓን ከሞቱ በኋላ የሚኖሩበት የሥቃይ ቦታ፣ እሳቱ ትሉ የማይጠፋ የማያንቀላፋ **ጎሕ**፡ ወገግታ፣ ውጋገን፣ የንጋት ብርሃን፣ ከጽባሕ በፊት የሚታይ የአጥቢያ ኮከብ፡፡ **ጎል**፡ ግርግም፣ በዚያ በበረቱ ውስጥ ዙሪያውን ወይም በአንድ ወገን እንደ ገንዳ ሆኖ የሚሰራ የእንስሳት ማዕድ ገለባ ደፈጫ የሚቅመሰበት፡፡ **ጎልጎታ**፡ (ዕብ፡ ጎልጎልታ) መካነ ርእስ፣ መካነ ድማኅ፣ ይህችውም የአዳም የራስ ቅል የተቀበረባት ዳግማይ አዳም የተሰቀለባት ቀራንዮ ናት፡፡ ዮሐ.19፣17፡፡ **ጎር**፡ ጓሮ፣ የቤት ኋላ፡፡ **እግዚኦ**፡ የጩኸትና የአቤቱታ የምልጃ የልመና ቃል፣ በቅርብ ፊት ለፊት ላለ ለሚያይ ለሚሰማ የሚነገር ነው፡፡ **እግዚአብሔር**፡ (ዕብ፡ ይሆዋ፣ ሱር፡ ይያ፣ ዐረ፡ ረብ፣ ጽር፡ ወቅብ፡ ኪርያስ፣ ሮማይ፡ ዶሚኑስ) ስመ አምላክ እግዚእ ጌታ ብሔር ዓለም በተገናኝ የዓለም ገዢ፣ የዓለም ጌታ፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ፣ ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ ለእርሱ አስገኝና ጌታ የሌለው አበ ዓለም ንጉሠ ዓለም፡፡ **ጸባኦት**፡ ኃይላት፣ ሠራዊት፡፡ **እግዚአብሔርና** ብሎ እግዚአብሔርነት አምላክነት ይላል፡፡ **ግዝረት**፡ መግዘር፣ መገዘር፣ አገዛዘር፣ ገዘራ፣ ግዙርነት፣ ግዝራት፡፡ **ጉሕላዌ**፡ **ጉሕሉት**፡ መታለል፣ ማታለል፣ አታላይነት፣ ሽንገላ፣ ክዳት፣ ተንኮል፣ ሰይጣናዊ ባህል **ግሑስ**፡ የራቀ፣ የተለየ፣ ልዩ ፍጹም ባህታዊ በረኸኛ፡፡ **ግላ**፡ ጨለማ፡፡ **ጋሌ**፡ ፋሮ፣ መጠማጥ፣ የዱር ድመት፣ ሙጭ ሙጭላ፡፡ **ገልእ**፡ የሸክላ ስባሪ፡፡ **ጉፋ**፡ ነጣቂ ወፍ፣ አሞራ፣ ጭላት፡፡ **ግልባቤ**፡ ክንብንብ፣ ሰርመዲ፡፡ **ገሊላ**፡የምድረ እስራኤል ሰሜን፣ በዮርዳኖስና በጥብርያዶስ በዓቢይ ባሕር መካከል ያለ የይሳኮርና የዛብሎን ክፍል፡፡ **ጋዛ**፡ ስመ ሀገር፣ የይሁዳ ክፍል፣ የፍልስጥዔም ደቡብ፣ እንደ ዘጌ እንደ ቆራጣ በባሕር ጠረፍ ያለች፡፡ **ገላሜዎስ**፡ እስስት፡፡ **ገመል**፡ በቁመ ገመል፣ ቀጭኔ፡፡ **ግምዔ**፡ ምንቸት፣ ቶፋ፡፡ **ጌና**፡ ገና፣ ልደት፡፡ **ገነት**፡

ዓለመ ጻድቃን፣ አዳምና ሔዋን የነበሩበት እግዚአብሔር ያዘጋጀው የዕረፍትና የሕይወት የተድላ የደስታ ቦታ።

“ደ”

ድብ፡ በቁመ። **ድባብ**፡ በቁመ ጃንጥላ። ተድባብ፡ ጣራ፣ ባጥ፣ መክደኛ፣ ክዳን፣ ጥላ፣ ከለላ፣ ዳስ፣ ጎጆ። **ድብ**፡ የጅብ ወገን ጥላው የሚያፈዝ። **ደብር**፡ ተራራ፣ ጋራ፣ ከወግር የሚበልጥ። አንደበራ፡ ዲቃላ፣ በዝሙት የተወለደ፣ የአመንዝራ ልጅ፣ ያልተሰራ ያልተቀጣ ሕገ ወጥ ደፋር። **ዴዴ** ፡ደጅ። **ድድ**፡ መሠረት። **ዳዊት**፡ (ዕብ፡ ዳዊድ) የሰው ስም፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ ፍቁር መፍቀሪ ማለት ነው። **ዳኅና**፡ ደኅንነት፣ ጤና፣ ሰላም። **ዳን**፡ ስመ ነገድ፣ ስመ ሀገር ፈረደ ማለት ነው። **ዳንኤል**፡ ዳኛየ የሚፈርድልኝ ማለት ነው። **ድራሞ**፡ ደስክ የእንቅልፍ ጋኔን፣ የሚጫን የሚደብት ይልቁንም በጸሎትና በጉባኤ ጊዜ።

“ሀ”

ሀቢብ፡ ወዳጅ። **ሀገሪት**፡ ያቀኗት፣ የቆረቆሯት፣ የተወለዱባት ሀገር፣ ርስር፣ ጉልት። **ሀሀርኤል**፣ ምሥዋዕ የምሥዋዕ ስም ደብረ አምላክ ማለት ነው። **ሆባይ**፡ ሳቢሳ፣ አሞራ። **ሀውል**፡ ላበት ከሞቀ ገላ ከአፍ የሚወጣ። **ሀየል**፡ ዋልያ። **ሃይማኖት**፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ፣ የአምልኮት ባህል፣ በልብ በረቂቅ ሀሳብ የሚሳል። **ህላዌ**፡ መኖር፣ መሆን፣ አናዎር፣ ኑሮ። **ሆሣዕና**፡ (ሆሻዓህ-ናእ) አድኅነን እባክህ አድነን ማለት ነው።

“ወ”

ወገል፡ በቁመ እርፍን ከሞፈር ከድግር የሚያያይዝ። **ትውዝፍት**፡ ትእቢት፣ ኩራት ከልብስና ከጌጥ የተነሳ። **ተዋሕዶ**፡ ኦርቶዶክስ በኒቅያ ተዋሕዶ በኤፌሶን ነው። ትውክልት፡ በቁመ መታመን እምነት ጽኑ ተስፋ፣ አለኝታ፣ የማይታበል የማይጠረጠር የሃይማኖት ፍሬ ነው። **ልገት**፡ ጎጆ። **አዋልድ**፡ የሊቃውንት መጽሐፍ፣ ድርሳናት፣ ተግሣጻት፣ ንባባቸውና ምስጢራቸው እንደ አጽቅ ሆኖ ከብሉይ ከሐዲስ የወጣ። **ልደት**፡ ልጅነት፣ ልጅ መሆን፣ ልጅ መባል። **ሞፈር**፡ የእርሻ እቃ።

“ዘ”

ዝ የቅርብ ቅጽልና ዐጸፋ ይህ ቅጽል ሲሆን ጭብጥ ወይም እጅታ ይባላል። **ዝእብ**፡ ጅብ፣ ነጣቂ አውሬ፣ መልኩ ውሻ የሚመስል ሆዳም አህዮች ጠላት። **ዝግራ**፡በቁመ ኀርግራ።

“ሐ”

የሦስቱ ሀ፣ ሐ፣ ኀ ድምጽ እንደመልካቸው ልዩ ልዩ ሲሆን ከሰላማ ወዲህ ባለመለየት ይነገራል። ጥሩ መምህርና የተማሪ ቤት ከሌለ የፊደልን ጠባይ በጥፈትና በአጠራር ጠንቅቆ

ማወቅ አይቻልም። **ሕግ**፡ ሕግ የሚባለው አታድርግ አታድርግ የሚለው ነው። አድርግ አድርግ የሚለው ግን ትእዛዝ ይባላል። **ሕገ ጠባይዕ**፡ ባሕርያዊ ሕግ፣ ፍጡር ሁሉ በባሕርዩ አውቆ የሚሰራው መውለድ መዋለድ በየጥቂቱ ማደግ መራብ መጠማት ምግብን መሻት የመሰለው ሁሉ። **ሐጌ**፡ የሰው ስም ነቢይ፣ ከ12ቱ ደቂቀ ነቢያት አንዱ በዓላዊ ዘተወልደ በዕለተ በዓል ማለት ነው። **ሕዋር**፡ በረንዳ። ሔኖክ፡ (ዕብ፡ሐኖኽ) የሰው ስም ሐዲስ ቅዱስ ማለት ነው። **ሕጹጻን**፡ የመጽሐፍ ስም ዜና መዋዕል፣ ትራፋተ ነገሥት ማለት ነው። በነገሥት የሌሉ ከነገሥት የቀሩ ጥቃቅን ቃሎች ታናናሽ ታሪኮች ስላሉበት ስሙ ሕጹጻን ተብሏል። ይኸውም ሁለት ክፍል ነው። **ሐርገጽ**፡ ዐዞ፣ የባሕር አውሬ፣ እንቅልፋም። ትሕርምት፡ በቁሙ ጾም፣ ተአቅቦ፣ የትሩፋት ሕግ ምስጢሩ ያው መከልከል ነው። ሐሪስ፡ አውራሪስ። መሐስዕ፡ ጠቦት ጡት የተወ ዓመት የሆነው ጠቦት ወጠጤ።

“ኀ”

ኀዲር ኀዲሮት፡ ማደር፣ ከሠርክ እስከ ነግህ በአንድ ቦታ መኖር፣ ተኝቶ ተጋድሞ ሌሊትን በእንቅልፍ ማሳለፍ። ኀጣጥ፡ (ዕብ፡ አጣድ) በቁሙ ዐጣጥ፣ እሾኽ ታናናሽ እሾኻም እንጨት። ተኀመሰ፡ አምስት ተባለ፣ አምስት ሆነ። **ኀኒቅ ኀኒቆት**፡ ማነቅ፣ ማስጨነቅ፣ ጉረሮን አንገትን አጥብቆ ሰቅስቆ መያዝ ማሰር ለመግደል አፍንና አፍንጫን ማፈን መድፈን ትንፋሽ መከልከል። **ኀሚሥ ኀሚሦት**፡ መሻት፣ መፈለግ፣ መለመን ለማግኘት፤ መጠየቅ፣ መመርመር ለማወቅ፤ መውደድ፣ መፍቀድ፣ መከጀል ምስጢሩ ያው መፈለግ ነው ከመሻት አይወጣም።

“ጠ”

ጠቢብ ጠቢቦት፡ መጠበብ፣ መፈልሰፍ፣ መራቀቅ፣ ልባም፣ ጥበበኛ መሆን በግብር በነገር። **ጥብሕ**፡ እርድ፣ ፍሪዳ፣ መሥዋዕት። **መጥባሕት**፡ ማረጃ፣ መቁረጫ፣ ካራ፣ ቢላዎ፣ ሰንጢ፣ ስለታም ብረት፣ ጎራዴ ሰይፍ፣ ሾተል። **ጠበል**፡ በቁሙ፣ የጥምቀት ውሃ፣ የተባረከ፣የተጸለየበት ወይም በተአምራት የፈለቀ፣ ከደዌ የሚያድን የሚፈውስ። **ጠባይዕ**፡ የጠባይዕ ፍች እንደ ህላዌ ነው ለባሕርይ በሚመችበት ባሕርይ ለአካል በሚመችበት አካል ይባላል። ጠባይዕን በአካል ቦታና በአካል ፈንታ ባሕርይ ብሎ መፍታት ምስጢራትን ሁሉ ያፈርሳል። ህላዌም ለባሕርይና ለአካል ይነገራል። **ህሉና፡ ህልውና**፡ ነዋሪነት፣ አነዋወር፣ ኑሮ። **ጢጤን**፡ ዶቅማ። **ጠያር**፡ አውሮፕላን።

“የ”

ዬ የቅጽል ምእላድ፣በሴት አንቀጽ ለሚነገር ቃል ሐዳስዩ፣ ድንግልዩ፣ ብሊትዩ፣ ዕቤርዩ እያለ ይህን በመሰለ ይገባል ሲፈታም ዐዲሷ፣ ዐዲሲቱ፣ ባልቴቷ፣ ባላቴቲቱ ያሰኛል። **ይ** የቅጽል ምእላድ እንደ ዊ በጥሬና በስም እየገባ ወገን የሚያሳይ፣ ቀዳማይ፣ ፈያታይ፣ ላዕላይ፣ ታሕታይ ፊተኛ የፊት የወንበዶች ወገን ቀማኛ፣ ላይኛ፣ ታችኛ፣ የላይ፣ የታች፣ በላይ፣ በታች ያለ። ግብጻይ የግብጽ ሰው፣ ቀርናይ ቀንደኛ፣ ቀንዳም፣ ባለቀንድ፣ የቀንድ ከብት ተዋጊ እያሰኘ እንደ

ሙሻ ዘር እንደ ሣልስ ቅጽል በሚያምርለት ስልት ይፈታል። **ዮ፡ (ያ፡ ዮሙ፡ ዮን)**፡ ድርብ ዝርዝር የገቢር አጸፋ በአራት ሠራዊት በሩቅ በሩቆች የሚነገር ኪያሁ በሚለው ፈንታ እየገባ ያን፣ ያንን ያሰኛል ሀበኒዮ እም ውእቱ ማይ፣ ከመ የሀበኒያ ለይእቲ መጽሐፍ፣ ወሊተ ወሀብከኒዮሙ፣ አልቦ ዘየሀይደኒዮን ይላል **ይሁዳ** (ዕብ) የሰው ስም ምስጋና፣ እምነት ወይም አማኒ ምእመን ማለት ነው። **ይሆዋ**፡ (ዕብ፡ ይሆዋህ) ስመ አምላክ ከፍጡራን ስም የተለየ ከፈጣሪ በቀር ለማንም ፍጡር የማይሰጥ ፍጡራን የማይጠሩበት መጽሐፍ ግን በይሆዋ ፈንታ ይሆባ ይላል ፍችውም እግዚአ ኩሉ አምላከ ኩሉ ፈጣሬ ኩሉ ዓለም ንጉሠ ኩሉ ዓለም ያሰኛል። **ዮዳሄ**፡ (ጽር፡ ዕብ፡ ይሆያዳዕ) የሰው ስም፣ እግዚአብሔር ያውቃል ማለት ነው። **ያክንት**፡ የቀይ ዕንቊ በርበሬ የሚመስል። **ዮርዳኖስ** ስመ ፈለግ የከነዓን ወንዝ ከደብረ ሔርሞን የሚመነጭ። ያሬድ፡ (ዕብ) ወሪድ ርደት ማለት ነው። ጎጃማዊ ቅኔ ስለ ያሬድ እንዲህ ይላል።

“አእመርነሂ ከመሀሎ በቀራንዮ ገነት

ያሬድ ዘወለዶ ሔኖክ ማህሌት” ይላል።

“ከ”

ኪሄላ፡ የጠፍር ኪስ፣ ዕሩር፣ ጥንግ፣ የተኩስ። **ከዊን**፡ መሆን፣ መባል፣ ሳይለወጡ በሱታፌና በምሳሌ በግብር ሌላ ስም መቀበል። ቃል ሥጋ ኮነ፣ ውእቱ አምላክ ዘኮነ ሰብአ ወውእቱ ሰብእ ዘኮነ አምላከ በተዋሕዶተ መለኮት ምስለ ትስብእት። **ኩነት**፡ መሆን፣ አኳኋን፣ ሁነታ፣ አናዎር። **ኪዳን**፡ በቁመ ውል፣ ቁም ነገር፣ የፍቅርና የአንድነት መሐላ ሰላማዊ ሕግ፣ ሁለቱን ወገን አንድ የሚያደርግ ስለ ጥቅም በተስፋ የቆመ የተጣፈ ሥርዓት፣ ቢያፈርሱት ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ ጥቅም የሚያሳጣ **ከልብ**፡ ውሻ፣ የቤት አውሬ፣ የጅብ ወገን፣ የክፉ ሰዎች ምሳሌ። **ኩሊት**፡ በቁመ ኩላሊት፣ የሆድ ዕቃ፣ ንዋየ ውስጥ፣ ከጉበትና ከጣፊያ በታች በግራና በቀኝ በሁለት ወገን የሚገኝ ክብ እንክብል የባሕርይ ሚዛን፣ የፍትወት ምንጭ፣ የፈቃደ ሥጋ መነሻ። **ኩሉ**፡ ከተጸውዖ ስም በቀር ውስጠ ብዙነት ላለው ለብትን ሰዋስው ሁሉ ቅጽልና አጸፋ በቂ ይሆናል። ኩሉ ሕዝብ፣ ኩሉ ፍጥረት፣ ኩሉ ነፍስ ይሴብሑ ሲል ቅጽል። ኩልክሙ ተዐልውኒ፣ ወኩሎሙ ሰማእተ ኮኑ ሲል አጸፋ። ኩሉ ዐረየ፣ ወኩሉ ከመ ልብስ ይበሊ ሲል በቂ ነው። ኩሉ በማንም ቋንቋ ውስጠ ብዙነት ለሌለውና መከፈል ለማይስማማው ለአንድ ብቻ አይነገርም። **ኩልሄ** ለተገብሮ **ኩለሄ** ለገቢር ይስማማል። **ከለሜዳ**፡ አጭር ካባ የክብርና የማዕርግ ልብስ ከአንገት እስከ ወገብ ወይም እስከ ጉልበት የሚደርስ ነገሥታት መኳንንት ልጆቻቸውም የሚለብሱት። **ኩለንታ**፡ ሁለንተና። **ኬልቄዶን**፡ ነጭ ዕንቁ በንጣቱ ሰማያዊነት ያለበት። **ከመ**፡ ዐቢይና ደቂቅ አገባብ በአንጻር በውጥን ይገባል። ምስጢሩ መጠንና ልክ አምሳል። በከመ ፈነወኒ አቡየ ከማሁ አነሂ እፌንወክሙ። ዐጉቱኒ ከመ ንህበ መዓረ። **ምክንያት**፡ በቁመ፣ የቃል መከታ፣ ሰበብ፣ የነገር ማንሻ፣ መገኛ፣ ሥረ ነገር፣ ጥንት፣ መሠረት። **ክንፍ**፡ የአዕዋፍ ገላ፣ መብረሪያቸው። **ከንቱ**፡ በቁመ ብላሽ፣ የማይረባ፣ የማይጠቅም፣ ያለዋጋ ፈጥኖ የሚያልፍ። **ካዕሴ**፡ ፈርስ፣ እበት። **ኮራዚ**፡ (ዕብ፡ ኮራዚን) የከተማ ስም፣ በጌንሳሬጥ ባሕር አጠገብ የነበረች ከተማ። **ኪርያላይሶን**፡ (ጽር፡ ኪርዬ፡ ኤሌይሶን)፡ እግዚኦ ተማሃል፣ ኪሪዬ አቤቱ ጌታ ሆይ፣

ኤሌይሶን ይቅር በል፣ ኤሌይሶንሜ ተሣሀለኒ፣ ኤሌይሶን ኢማሰ ተሣሃለነ፡፡ **ከርከዬን**፡ ጥቁር ዕንቁ፣ ከሰልማ፡፡ ከርካዕ፡ ቀርቀሀ፣ ውስጠ ክፍት፡፡ **መንኮራኩር**፡ ሠረገላ፣ የሠረገላ እግር (ተሸከርካሪው/ጎማው) **መስከረም**፡ መስ ከመስየ ወጥቶ በከረም ላይ ወድቋል ስለዚህ መስየ ክረምት ተብሎ ይፈታል፡፡ ምስጢሩ ጸአት ነው፡፡ የክረምት ጫፍ መካተቻ ነው፡፡ **ከርሜል**፡ ባለቅኔዎች ችፍርግ ይሉታል ምስክር የለውም፡፡ **ክርስጵራስስ**፡ ቅጠልማ ዕንቁ፡፡

“ለ”

መልአክ፡ በቁሙ የእግዚአብሔር መልእክተኛ፣ ሰማያዊ፣ ረቂቅ፣ የእሑድ ፍጥረት፣ አለቃ፣ ተሸሞ ከንጉሥ የተላከ፡፡ **ልብ**፡ በቁሙ፣ የታወቀ ሕዋስ ከንዋያተ ውስጥ አንዱ በሕያው ፍጥረት ውስጥ በየደረቱ የሚገኝ የደም መሰብሰቢያ፣ ደም ከእርሱ እየመነቸ ወደገላ ሁሉ የሚናኝበት የሚሰራጭበት ውስጣዊ ገላ፡፡ **ለበወ**፡ ለበመ፣ ልባም ሆነ፣ ልብ አደረገ፣ አስተዋለ፣ አወቀ፣ ተረዳ፣ ጠነቀቀ **ልቡና**፡ በቁሙ እውቀት፣ ሀሳብ፣ ማስተዋል፡፡ **ልብን**፡ ነጭ ዕጣን፣ ከወተታም እንጨት የሚወጣ፡፡ **ሊባኖስ**፡ ደጋ፣ በሶርያና በእስራኤል መካከል ያለ ዛፋም እንጨታም ደናም የተራሮች ራስ፣ ሰማይ ጠቀስ ውርጭና በረዶ እንደ ሻሸ ሸፍኖት የሚኖር ነው፡፡ **ሌጌዎን**(ጽርእ) ሠራዊት፣ ጭፍራ፣ የጦር አበጋዝ፣ የጭፍራ አለቃ፣ ስድስቱ ሺህ ጭፍራ ከነአለቃው አንድ ሌጌዎን ይባላል፡፡ **ሊቅ**፡ በቁሙ፣ አለቃ፣ ታላቅ አባት፣ ጌታ፣ መምህር፣ ሹም፣ አሮጌ፣ ሽማግሌ፡፡ **ሉሲፈር**(ሮማይስጥ) የዲያብሎስ ስም ከሸፍትነት በፊት የነበረው ስም፣ ጸዋሬበርህ፣ ፍድፋደ በርህ፣ ቤዝ ብሩህ፣ ኮከበ ጽባሕ ማለት ነው፡፡ ልማድ፡ በቁሙ ልምድ፣ አመል፣ የተለመደ ግብር፡፡ **ላጽቂት**፡ እንሽላሊት፡፡ **ለቆ**፡ (ዕብ፡ ሌቂሽ) በቁሙ፣ ደኃራዊ ሣር፣ ዳግማይ ቡቃያ፣ ቅጥይ፣ ከቆረጣና ከአጨዳ በኋላ በገፍና በብላጊ ዝናም የሚበቅል ነው፡፡ ቋንቋው አማርኛ ነው፡፡ **ልሣነ ወርቅ**፡ ጽሩየ ቃል፣ አንደበተ ጥሩ ማለት ነው፡፡

“መ”

ምድራዊ፡ የምድር፣ ከምድር የተገኘ፣ በምድር የሚኖር፡፡ **ሞት**፡ የሥጋዊና የደማዊ ሕይወት ፍጻሜ፣ በአዳም ኃጢዓት የመጣ ጠባይዓዊ ዕዳ፣ ባሕርያዊ ፍዳ፡፡ **ማውታ**፡ ሳያርዱት ታሞ ወይም ገደል ገብቶ የሞተ፡፡ **ምሕላ**፡ ልመና፣ ምልጃ፣ የማህበር የሕዝብ ጸሎት፣ እግዚኦታ፡፡ **ምሑር ምሑሮት**፡ መማር፣ ይቅር ማለት፣ ዕዳን በደልን መተው፡፡ **መለኮት**፡ ግዛት፣ መንግሥት፣ ሥልጣን፣ መለኮት በቁሙ ልዩ ክቡር ስም ከፈጣሪ በቀር ማንም ፍጡር የማይጠራበት እንደ እግዚአብሔር ያለ፣ የባሕርይ አምላክ፣ ባሕርያዊ ንጉሥ፣ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው፣ ዘላለማዊ ገዥ፣ ገባሬ ኩሉ፣ መላኬ ኩሉ፣ ምሉእ ውስተ ኩሉ ማለት ነው፡፡ መለኮት ቅድስት ሥላሴን የሚያዋሕድ፣ የሚያስተባብር አንድ አምላክ የሚያሰኝ ነው፡፡ መፍጠርና ፈጥሮ መግዛት የሥላሴ የባሕሪያቸው ስለሆነ ባሕርያቸው በግብር ስሙ መለኮት ይባላል፡፡ መለኮትን ከአሐዱ በቀር ሠለስቱ አይነካውም፡፡ **ሞሎክ**፡ የደቂቀ አሞን ጣዖት፣ እስራኤል ያመልኩት የነበረ፣ ፊቱ የጥጃ እጁና ግንዱ የሰው እጆቹ ሕጻን ለመቀበል የተዘረጉ በስተፊቱና በአንጻሩ ወደ ምሥራቅ ወገን ሰባት ቅጥርና ደጃፍ ያለው፣ መላኪ ንጉሥ መሪ ጠባቂ ማለት ነው፡፡ የአምልኮቱም ሥርዓት ስንዳሌና ዘይት ለሚያቀርብ አንደኛው በር፣ ርግብና ዋኖስ ለሚያቀርብ

ሁለተኛው በር፣ በግ ለሚያቀርብ ሦስተኛው በር፣ ፍየል ለሚያቀርብ አራተኛው፣ ጥጃ ለሚያቀርብ አምስተኛው፣ በሬ ለሚያቀርብ ስድስተኛው፣ ልጁን ለሚያቀርብ ግን ሰባቱ ሁሉ ተከፍቶለት ለጣዖቱ እጅ በእጅ ይሰጣል። ከዚያ በኋላ ካህናቱ ሀጻኑን ከሞሎሕ እጆች ተቀብለው በሁለት ወገን እሳት ያነዱና ከማኻል አግብተው ተወከፍ ለነ እያሉ ያሳልፉታል። **ሜላት**፡ ጥሩ ጸምር፣ ጥሩ ሐር። **ምኔት**፡ ገዳም፣ ልዩ ክልክል የመነኮሳት ሀገርና መንደር ከነቤተ ክርስቲያኑ። **መነኮስ**፡ መነኩሴ፣ ለማኝ፣ መናኝ፣ ድኃ፣ ከዓለም ከዘመድ ከሕዝብ ከገንዘብ የተለየ **መንተሌ**፣ ጥንቸል። **ማዕነቅ**፡ ቡላል። **ማርታ**፡ እመቤት፣ እግዝእት ማለት ነው። **መርድ**፡ የከበሬታ ስም፣ ከራሶች በላይ፣ ከንጉሦች በታች፣ መካከለኛ የሸዋ ባለአልጋ። **ማርቲር**፡ ሰምዐ፣ መሰከረ፣ ሰማእት ሆነ። **ሜሮን**፡ በቁሙ፣ ቅብዐ ቅዱስ፣ የተባረከ ሽቱ፣ ጳጳሳት ከበለሳንና ከዕፀወ ዕጣን ከአስጸዳቶስ ከሌላም ከብዙ ዓይነት ሽቱ የሚያወጡት ነው።መደበኛው ግን በለሳን ነው።

“ነ”

ንቡረ እድ፡ በሹመትና በቡራኬ ጊዜ እጅ የተጫነበት። **ንብረት**፡ በቁሙ፣ መኖር፣ መቀመጥ፣ አቀማመጥ፣ ኗሪነት፣ አናዎር፣ ኃላፊ ውእቱ ንብረተ ዝ ዓለም። **ኑባሬ**፡ ዝኒ ከማሁ አናዎር፣ ኑሮ፣ አቀማመጥ። **ነፄ**፡ ንዋያም፣ ገንዘባም፣ ባለብዙ ገንዘብ፣ ዘወትር የሚያጌጥ የሚሸለም። **እንዚራ**፡ ንዋየ ማህሌት የሚመታ የሚነፋ ነው። **ናዝሬት**፡ ስመሀገር ታናሽ ከተማ፣ከገሊላ አውራጃ በዛብሎን ክፍል ከአንዲት ተራራ ላይ የተሰራች፣ ደብረ ታቦርና ቅፍርናሆም የሚያማክሏት፣ የቀድሞ ሰዎቿ እጅግ የተናቁ የተዋረዱ ኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸነሰባት፣ ያደገባትና የኖረባት፣ ዘይቤው ምንንት ኅሥርት ማለት ነው። ምእመናንም በናዝራዊው ኢየሱስ ስላመኑ ናዝራውያን ይባላሉ። **ናሆም**፡ የሰው ስም ነቢይ ከ12ቱ ደቂቀ ነቢያት አንዱ ነው፣ ናዛዚ፣ መናዝዝ፣ ወይም ኑዛዜ፣ ዕረፍት፣ ኅድአት ማለት ነው። **መንጪጥ**፡ ዋኖስ፣ ቡላል፣ ርግብ፣ አነጥናጭ ወፍ። **ናይናን**፡ (ቅብጥ፡ ናይ፡ ናን) መሐር ኪያነ፣ መሐረነ። **ኔስታሊ**፡ (ጽር፡ ኔስታን፣ ዕብ፡ ንሑሽታን) የነሐስ እባብ፣ ሙሴ በአርዌ ምድር አምሳል የሠራው። **አንኩዕ**፡ (ብ፡ አናኩዕ)፡ ደኅባ ኩብኩባ፣ ችግኝ፣ ፌንጣ፣ ግልገል አንበጣ፣ የሚዘል፣ የሚፈናጠር **ኒካዐ**፡ (ጽር፡ ኔካያ፣ ዕብ፡ ንኮ) ሰባራ፣ አንካሳ። **መንክራዊ**፡ ታምራታም፣ ባለ ታምራት። **ነነዌ**፡ (ዕብ፡ ኒንዌ)፡ ስመ ሀገር፣ የአሶር መዲና፣ ውቢቱ፣ ዉቢት፣ ዐባይ፣ ልእልት፣ ቀዳሚት ማለት ነው። **ነፍሥት**፡ ሰውነት፣ ሥጋ፣ ገላ፣ ሕዋስ፣ አካል፣ መልክ፣ ፊት። **መንፈሳዊ**፡ ረቂቅ፣ ንጹሕ፣ ቅዱስ፣ ለነፍሱ ያደረ የእግዚአብሔር ወገን። ስለ ዓውደ ዓመት በዓል እንግጫና አበባ ይዞ እንቁጣጣሽ ማለት ምስጢሩ የምስራች ነው። ኀለፈ ክረምት ቆመ በረከት ተሠርገወት ምድር በሥነ ጽጌያት እያሰኘ ርግበ ኖኅን ያሳስባል። **ንሥሓ**፡ በቁሙ፣ ሐዘን፣ ጸጸት፣ ቁጭት፣ ምላሽ፣ መቀጮ፣ ቅጣት፣ ቀኖና የኃጢአት ካሣ **ነሥሐ**፡ ንሥሓ ገባ፣ ዐዘነ፣ ተጸጸተ፣ ተመለሰ፣ ክፉ አመሉን ተወ፣ ጠባዩን ለወጠ። **ኖትያ**፡ መርከበኛ። ናታኒም፡ ንቱናን ውሁባን ለቤተመቅደስ ተሰጡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች፣ እስራኤል ያይደሉ አሕዛብ የገባያን ሰዎች።

“ሠ”

ሁለት ዓይነት ሰ፣ ሠ በግእዝ፣ በሱርስት፣ በዕብራይስጥ እንጂ በዐረብ የለም። **ትሥጉት**፡ ሥጋነት፣ ሰውነት፣ ሰው መሆን፣ ሥጋ መልበስ። **ሠግላ**፣ ሾላ። **ሣሃሊ**፡ ልበ ሰፊ፣ ነገር አላፊ፣ ይቅር ባይ፣ ዐዛኝ፣ ሩሩ። **ሡዕ**፡ ማቀጣጠያ፣ ጭራሮ፣ ገለባ፣ ኩበት፣ ጧፍ፣ ጋዝ፣ ክብሪት፣ የተልባ እግር፣ ፈትል። **ሠኔ**፡ የወር ስም፣ ሠናየ ዘርዕ፣ ወርኀ ዘርዕ ሠናይ ማለት ነው። **ሥን**፡ ውበት፣ መልክ፣ ደም ግባት። **መሥዕርት**፡ ሚዶ፣ የጸጉር ማበጠሪያ። **ሚራክ**፡ ሲር፣ ማዘቢያ፣ ቶታን። **ሡራሬ**፡ ሥራ፣ አሠራር፣ ወሡራሬሃ አዳም።

“ዐ”

ዕበይ፡ ልዕልና፣ ከፍታ፣ ብልጫ፣ ታላቅነት፣ ገናናነት፣ ብዛት፣ ጽናት። **ዕብራይስጥ**፡ የዔቦር ቋንቋ፣ እስራኤል የሚናገሩበት፣ ኦሪት ነቢያት መጀመሪያ የተጣፉበት የብሉይ ኪዳን ምንጭ። **ዕብሬት**፣ ፈረቃ፣ ተራ። **ዐጌ**፡ ተልባ፣ የተልባ እግር። **ዕጓለ እመሕያው**፡ ዕጓል ልጅ፣ መ መሬት፣ ሕያው ፈጣሪ፣ ይህ ሁሉ መላሾች ያበጁት ያቀጣጠሉት ነው ዕብራይስጡ አዳም ይላል እንጂ ዕጓል አይልም ስንኳን የዘርፍ ዘርፍ አንድ ዘርፍ የለውም። **ዕጉሥታር**፡ ሬት። **ማዕዶት**፡ ማዶ፣ አሻገር፣ ከወንዝ ወዲያ ወይም ወዲህ ያለ ቦታ ትይዩ አንጻር ፊት ለፊት አቅጣጫ፣ አፍዛጋር፣ የፋሲካ ሰኞ፣ ሐማሴኖች እናቴ ሲሉ አደይ ይላሉ። **ተዓደመ**፡ ተቃጠረ፣ ተቀጣጠረ። **ዕድሜ**፡ ቀጠሮ፣ የተወሰነ ጊዜ፣ ዘመን፣ ወራት። **ዔዴን**፡ (ዕብራ)፡ ምቹ ቦታ። **ዐዚዝ**፡ጥኑ፣ ብርቱ፣ ጠንካራ፣ ልባም። ዐዛውንት ማለት ከዚህ ወጥቷል። **ምዕዛር**፡ የብርሃን ወንፊት፣ ብርሃን የሚነዛበት ብሉ ነዳላው። የአቡሻህር፣የመርሐ ዕውር የቁጥር መምህራን ለፀሐይ 595 ለጨረቃ 105 ምዕዛር አላቸው ይላል። **ዐይግ**፡ ኩሬ፣ የውሃ መቋሚያ፣ መጠራቀሚያ፣ ጎድጓዳ ቦታ። ዐይን፡ ሰብዐ ዓይን፡ ሰላይ፣ ጉበኛ። **ትዕይንት**፡ ሰፈር፣ ከተማ፣ መንደር፣ ሠራዊት፣ ጭፍራ፣ ማኅበር። ታዕካ፡ የንጉሥ ቤት፣ ቤተ መንግሥት፣ አዳራሽ፣ ታላቅ ከፍተኛ ከፍ ካለ ቦታ የተሰራ ግቢ፣ ሰፈር፣ ከልካይ፣ አስከልካይ፣ ዘበኛ፣ አጋፋሪ ያለበት። **ዓለም**፡ ቦታ፣ ዘመን፣ ዓለመ ሥጋ፣ ሰው እስከ ሞትና እስከ ምጽአት የሚኖርበት። **ዓለም ዘይመጽእ**፡ ዓለመ ነፍስ፣ ከሞትና ከኅልፈት በኋላ የሚመጣው። **ለዓለም**፡ ፍጻሜ ላለው ሲነገር ምድርሰ ለዓለም ትቀውም፣ ፍጻሜ ለሌለው ሲነገር ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ይላል። **ዐለቅት**፡ (ዕብ፡ ዐሉቃህ፣ ሱር፡ ዓላቅታእ፣ ዐረ፡ ዐለቅት) ዐልቅት፣ የትል ዓይነት፣ ከውሃ ከረግረግ የሚገኝ፣ የሚነክስ፣ የሚጣበቅ፣ ከያዘ የማይለቅ ደም የሚመጥ የሚመጠምጥ። **ዐለስ**፡ አጃ፣ የስንዴ ዓይነት። **ዓመተ ዓለም**፡ ከጥንት ከአዳም ጀምሮ ያለው ዘመን። **ዐምሐራ**(ዐም፡ ሐራ)፡ አማራ፣ ጨዋ ሕዝብ፣ ነጻነት ያለው ባለነጻ ግዑዝ አግዓዚ ማለት ነው። **ዐማኑኤል**፡ (ጽር፡ ሄማኑኤል፣ ዕብ፡ ዒማኑኤል)፡ የሥግው ቃል ስም በኩነት በተዋሕዶ የተሰጠው፣ ዒማኑ ምስሌነ፣ ኤል አምላክ በተገናኘ አምላክ ምስሌነ ወይም ምሰሌነ አምላክ፣ ሊቃውንት ግን አምላክ ወሰብእ ብለው የምስጢር አፈታት ይፈቱታል። **ዕንቊ**፡ ክቡር ደንጊያ። **ዕንቆራ**፡ የማር ሰፈፍ። **ዐቃቤ ሥራይ**፡ ሐኪም፣ ባለመድኃኒት። **ዐቅራብ**፡ ጊንጥ፣ በኸርራቱ ጫፍ የሚነድፍ። **ዐረብ**፡ ምዕራብ። **ዐረቦን**፡ በቁመ፣ መያዣ፣ መጀመሪያ፣ የስጦታ ድራር። **ምዕራፍ**፡ ሴት እና ወንድ የሚለይበት

በሜትር 184 ይሆናል ይላሉ። 400 ክንድ የሚሉም አሉ። **ዕርፍ**፡ በቁመ፣ የማረሻ እጀታ። **ዐራቅይና**፡ አስታራቂነት። **ዐራት**፡ ዐልጋ፣ አርባዕቱን አራት ማለት የመጣ ከዚህ ነው።

"ፈ"

ፍግዕ፡ ፍግዓ፡ ትፍግዕት፡ ተድላ፣ ደስታ፣ ምቾት። **ፈጎር**፡ ሕገ ጣዖት፣ መካነ ጣዖት ፍችው ከሚት፣ ፈቲሕ፣ ከሚተ ዕርቃን ፈቲሐ አፍ፣ በዓለ ፈቲሕ ከሚት፣ የአምልኮው ሥርዓት በፊቱ ቆሞ ዕራቁት መጣል፣ አፍን እንደ አቁማዳ መክፈት መልቀቅ ማፋሸግ ማዛጋት ዋሻ ማስመሰል ነውና ይህንን ያሳያል። **ፊደል**፡ በቁመ፣ የድምጽና የቃል መልክ ሥዕል መግለጫ ማስታወቂያ። ቅኔ፡-

መምህራነ ኮኑ በበደወሉ።

ፊደላተ ዘኖለቁ ኩሉ።

ድመትን ብስ ማለት ከአንበሳ የተወሰደ ነው የአንበሳ ዝርያ አለባትና። **ፎንቃስ**፡ ጉራዛ፣ ጠጉራም ነጭና ጥቁር፣ ጭራው ፍጹም ነጭ፣ የጦጣ ወገን በዛፍ ላይ የሚኖር፣ ከዛፍ ወደዛፍ የሚዘል። **ፈጢር ፈጢሮት**፡ መፍጠር፣ ማስገኘት፣ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት፣ ግብር እምግብር መሥራት ማድረግ፣ ማዘጋጀት፣ ዐዲስ ነገር ማውጣት፣ መውለድ፣ ባለቅኔዎች ወደደ ብለው ምስክሩን ቅኔ ይጠቅሳሉ ከመጻሕፍት ውስጥ አልተገኘም። ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ። **ፍያል**፡ ፍንጃል፣ ኩባያ፣ ጽዋ። **ፊካትም**፡ ታላቅ ፈሳሽ ወንዝ፣ በባሕር ላይ የሚያልፍ የሚጎርፍ እንደ ዓባይና እንደ ጣና፣ የውሃ እናት፣ እንዝዝ፣ ጥቁር እንዝዝ የምትመስል። **ፊልክስዩስ (ጽርእ)**፡ የሰው ስም፣ የመጽሐፍ ስም፣ የመነኮሳት መጽሐፍ፣ መፍቀሬ ነግድ ተወካፊ ነግድ ማለት ነው ፊሎስ ወዳጅ፣ ክሲኖስ ነግድ። **ፍልፊል**፡ የአይጥ ወገን፣ ከአይጥ የሚበላልጥ። **ፈላስፋ**፡ መፍቀሬ ጥበብ ጥበበኛ፣ አዋቂ፣ ተራቃቂ። **ፍልስፍና**፡ በቁመ፣ ፈላስፋነት፣ ፈላስፋ መሆን፣ ጥበብ፣ እውቀት። **ፊንክስ**፡ (ጽር፡ ፊኒክስ)፡ የአሞራ ስም፣ የተረት አሞራ፣ የቀድሞ ሰዎች አረማውያን የሚያምኑበት የሚተርቱበት በተረቱ ትንሳኤ ሙታንን የሚያስረዳ። **አፍያት**፡ እፉኝት፣ እባብ፣ አጭር ኻርራት ጎንዳ ትንፋሹ እና መርዙ ቶሎ የሚናኝ የሚጎዳ። **ፈጸንት**፡ ንዳድ፣ ወባ፣ ትኩሳት፣ ተቅማጥ። **ፍቅር**፡ በቁመ ውዴታ፣ ይቅርታ፣ ዕርቅ፣ ሰላም፣ የልብ አንድነት፣ ስምምነት፣ ረቂቅ መጣበቅ፣ የሀሳብና የአእምሮ መጫ። **ፍሥሓ**፡ ደስታ፣ ኑዛዜ፣ ሰላም፣ ጤና፣ መልካም። **ፈረሳዊ**፡ ፈረሰኛ፣ ባለፈረስ፣ ጋላቢ። **ፈትል**፡ ዝሀ።

"ጸ"

መጽአሞ፡ የገደል ማሚቶ፣ ተራራ፣ ገደል፣ ዋሻ እያስተጋባ የሚጮኸው ጩኸት። **ጸበል**፡ ብናኝ፣ ትቢያ ደቃቅ አፈር። **ጸጋ**፡ በቁመ ሀብት፣ መልካም ስጦታ፣ ዕድል ፈንታ፣ ስርየት፣ ይቅርታ፣ ብዕል፣ ክብር፣ የቸርነት ሥራ፣ አለዋጋ የሚሰጥ የሚደረግ። **ጽግነት**፡ የሌት ወፍ። **ጸጉር**፡ ጠጉር፣ የገላ ሳር፣ የሚጋ ቡቃያ ማለት ነው። **ጸደይ**፡ በሐጋይና በክረምት መካከል ያለ

ክፍል ነው። **ጽድቅ**፡ በቁመ፣ እውነት፣ እርግጥ ቅንነት፣ የሚገባ ነገር ሕግ፣ ትእዛዝ፣ ባሕርያዊ መጽሐፋዊ ሥራ። **ጸማዕት**፡ ዋሻ፣ በአት፣ የመነኩሴ ቤት፣ የባሕታዊ ቦታ። **ምጽዋት**፡ በቁመ፣ ለድኻ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ገንዘብ፣ ስጦታ በብሉይ በሐዲስ የታዘዘ፣ ሌላውም የፍቅርና የርኅራኄ ሥራ ምክርን፣ ርዳታን የመሰለው ሁሉ። **መጽሔት**፡ መስታዮት፣ ንጹሕ፣ ብሩህ፣ ጽሩይ መልክ የሚያሳይ ማይ ሰማይ የሚመስል። **ጸሓይ**፡ ሊጣፍ የሚገባው በዚህ ጸ ነበር ስለ ልማድ ወደ ፀ ሄዷል። **መጽሐፍ**፡ በቁመ መጣፍ፣ በላዩ ቃል ነገር የተጣፈበት ብራና ወረቀት፣ ነዶው በአንድነት የታሰረ እና የታዘዘ የተሰፋ የተጠረዘ። **ጸጥ**፡ በቁመ፣ ዝም፣ ጫ ማለት፣ ዝምታ፣ እርጋታ፣ አለድምጽና አለሁከት መሆን። **ጼዴነት**፡ የዱር፣ የበረሀ ዛር፣ ጋኔን። **ጼው**፡ ጨው፣ ዐሸዐ፣ አሞሌ በቆላ በረሀ ከውሀማ መሬት የሚገኝ በውሃ የሚቀልጥ የሚማማ፣ መጣጣ፣ ሆምጣጣ፣ መባልዕትን ሁሉ የሚያጣፍጥ። **ጽዮን፡ (ዕብ፡ ጺዮን)**፡ ስመ ሀገር፣ ዳዊት የያዛት ሀገር፣ የኢያውሴዎን አንባ፣ ፍችው ጸወን ምልክት ማለት ነው። **ጼናታም**፡ ጤናዳም። **ጸያፍ**፡ በቁመ፣ አለስልቁ፣ አላገባቡ የተጣፈ፣ የተነገረ ቃል፣ ኮልታፋ "ረ" ሲሉት "ለ" የሚል። **ጸክ፡ ጸኩ**፡ ጭን ሹልዳ፣ ታፋ። **ጸልዮ ጸልዮት**፡ መጸለይ፣ መለመን፣ ማመስገን፣ ከአምላክ ጋራ መነጋገር። **ጽልመት**፡ መጨለም፣ መጥቆር፣ አጨላለም፣ ጨለማ፣ ሌሊት፣ የጨረቃ ጠፍ፣ ጥቁረት፣ ጥቁርነት፣ በምስጢር ኃጢአት፣ ክህደት፣ ድንቁርና፣ ሐዘን፣ መከራ ይሆናል። **ጸዊም ጸዊሞት**፡ መጾም፣ ጥሉላትን ፈጽሞ መተው፣ ሰውነትን ከመብል ከመጠጥ፣ ከሌላውም ሁሉ ከክፉ ነገር መከልከል መጠበቅ። **ጽማዌ**፡ መጨመት፣ ጭምትነት፣ ዝምታ፣ እርጋታ፣ ጸጥታ። **ጽሙና**፡ ጭምትነት፣ ድካም፣ ጸጥታ፣ የገዳም ሥርዓት፣ ጾም፣ ትሕርምት፣ ምናኔ፣ ብቸኝነት። **ጸምር**፡ የበግ የፍየል ጸጉር። **ጸኒሕ ጸኒሖት**፡ ደጅ መጥናት፣ መቆየት፣ መጠበቅ፣ መታገሥ፣ ተስፋ ማድረግ፣ ማድባት። **ጽንሐት**፡ መቆየት፣ መታገሥ፣ አቆያየት፣ ቆይታ፣ ደጅ ጥናት፣ ሽመቃ። ስለ ችግር ቅኔ፡-

ብዕልሰ እመ በጽድቅ ወበኃጢአት ተጽናስ።

አክአብ እንዘ ሀሎ እም ኢተጸነሰ ኤልያስ።

ጸቃውዕ፡ ወለላ ማር፣ የማር ወለላ። **ጽራግ ማሰሬ**፡ የንጉሥ አልባሽ፣ የአሽከሮች አለቃ፣ጃን ሸላሚ።

"ፀ"

ጎ የሐ ዲቃላ ስለሆነ ከሐ ቢደረብ እንጂ ለብቻው እንዳይቆጠር፣ ፀ ደግሞ የጸ ዲቃላ ስለሆነ ከጸ ቢደረብ እንጂ ለብቻው አይቆጠርም። እንደ 22ቱ ፊደላት አባትነት፣ መደበኝነት የለውም። **ፀበርት**፡ ዝንጣፊ። **ፂያት**፡ መስክ፣ ጨፌ፣ ክልክል፣ ሣራም፣ ቅጠላም፣ ሰፊ ቦታ የከብት መሰማሪያ።

"ቀ"

ቀበያውበጠ፡ ቀላወጠ፣ ምስክር ሳይኖረው እንዳው በልማድ ይገሰሳል። ቃቤላ፡ ማሽላ፣ የአገዳ

እህል። **ቅብዐት**፡ የሃይማኖት ስም፣ ዕውር ዘኢየሱስ በአጼ ፋሲል ዘመን ያመጣው፣ የቅባት ባሕል 3 ወገን ነው። መጀመሪያው የእነ ዕውር ዘኢየሱስ መጽሐፍ አንደየ ርእሶ ይላልና ቃል በተዋሕዶ ዜገ ከሥጋ ሲዋሐድ የባሕርይ ክብሩን አጣ ለቀቀ ሲቀባ ወደ ጥንተ ክብሩ ተመልሶ በሰውነቱም በአምላክነቱም አንድ ወገን የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል። ምስጢሩ እንደ በትረ ሙሴ ማለት ነው። ሚጠትንና ውላጤን በአንድነት ያሳያል። ሁለተኛው በአንደኛው ዮሐንስ የተነሱ እነ አካለ ክርስቶስ ዜገ ማለትን ነቅፈው አጸይፈው መጽሐፍ እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ ይላልና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነት ክብር አላገኘም ሲቀባ ግን ክብር ተላልፎለት በቅባት የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ብለዋል። ምስጢሩ መቀባትና መለወጥን ለሥጋ ብቻ መስጠት ነው። ሦስተኛ በቴዎድሮስ ዘመን የነበሩት እነ አለቃ ጎሹ በቅባት ብቻ ማለትን ነቅፈው መጽሐፍ በሁለቱም ሁሉ በተዋሕዶ ከበረ በቅባት ከበረ ይላልና ቅባት ያለተዋሕዶ ተዋሕዶም ያለቅባት ብቻ ብቻውን አያከብርም። በተዋሕዶ በቅባት በአንድነት የአምላክነት ክብር ከብሮ የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል። ሦስቱም ሁሉ ፍጹም ውላጤ ነው። ሥጋን ከፍጡርነት ቃልን ከመሲሕነት ያወጣል። ምድራዊ አንጥረኛ የሰራውን መስቀል ግብዞችና አታላዮች ከሰማይ ወርዷል እያሉ እንደሚያጭበረብሩበት ያለ ነው። **መቅድም**፡ በቁመ የመጽሐፍ መግቢያ በር፣ ደጃፍ፣ አስቀድሞ የመጽሐፉን ጠባይ የተጣፈበትን ምክንያት ገልጦ የሚነግር የሚያስረዳ። **ቁድሮስ**፡ የቦታ ስም፣ በደብረ ዘይትና በኢየሩሳሌም መካከል ያለ ቆላ፣ ሸለቆ፣ ዛፉም፣ ዘይታም፣ አታክልታም፣ ፀሐይ ቶሎ የማይደርሰው ቢደርሰውም ቶሎ የሚያልፈው፣ መካነ ጽልመት ወጽላሎት። **ቀድሶ ቀድሶት**፡ መቀደስ፣ መባረክ፣ ማመስገን፣ ማክበር፣ ማግነን፣ ማንጻት፣ ማጥራት፣ መለየት፣ ለእግዚአብሔር መስጠት፣ የእግዚአብሔር ገንዘብ ማድረግ። **ቃዬስ**፡ (ዕብ፡ ቃዬሽ) ሲና፣ የሲና በረሀ፣ ምድረ በዳ። **ተቅዋም**፡ መቅረዝ፣ ማብሪያ፣ የመብራት ዕቃ፣ የቀንዲል የፋና ማኖሪያ የሚቆም የሚተከል ወይም የሚሰቀል የሚንጠለጠል ባለብዙ አጽቅ። **ቋዕ**፡ ቁራ፣ ጥቁር አሞራ፣ ከእርኩም ይልቅ እንደ ዝኖን እድሜያም ነው ይባላል። ገላግልቱም ሲፈለፈሉ ነጫጮች ቀያዮች ሆነው ይወጡና በኋላ ሲያድጉ ይጠቁራሉ። እናታቸውም ስለንጣታቸው ፈርታ ደንግጣ እስኪጠቁሩ ድረስ ከዚያው ጥላቸው ወደሌላ ቦታ ትሄዳለች። የፍጥረቱ አባት እግዚአብሔር ግን ፈትፍቶ እንደማጉረስ ከተሐዋስያን ታናናሹን ዝንብና ትንኝ እስከ አፋቸው እያቀረበ ይመግባቸዋል። **ቆጵሮስ**፡ (ጽር፣ ኮፕሮስ)፡ ፍግ፣ ፋንድያ፣ ዐዛባ፣ እበት፣ ኩበት። **ቀሊል ቀሊሎት**፡ መቅለል ማነስ፣ ከሚዛን ቂል ማለት ከዚህ ወጥቷል። ኢታስተቃልሎ ለጸላኢከ ወበዝንቱ ትከውን ምውአ ሎቱ እንዲል ፈላስፋ። የተማሪ እናት ልጇን አጼ ቴዎድሮስ ስላቃጠለባት እንዲህ አለች ይባላል፡-

ይማርልኝ ብየ በጌምድር ሰድጄ።

ቀለም ገባው አሉ እሳት ሆነ ልጄ።

ቀኒእ ቀኒያት፡ በሌላው ዕድልና ሀብት መቅናት፣ መመቅኘት፣ ማዘን፣ መቆጣት፣ መበሳጨት፣ ወይም እንደእርሱ ለመሆን መንቃት፣ መትጋት፣ እርሱን አብነት ማድረግ። **ቅኑም**፡ (ሱር፡ ቅኑማ፣ ዐረ፡ አቅኑም)፡ አካል፣ ህላዌ፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ ያለው እኔ የሚል። **ቀኖና**፡ (ጽር፡ ካኖን)፡ ሥርዓት፣ ሕግ፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት። **ቅንፍዝ**፡ ጃርት፣ እሾኻም አውሬ፣

ጠጉሩ እንደ ጋሬጣ እንደ ምስማር ያለ፡፡ **ቋንቋ**፡ በቁመ፣ ልሳን፣ የነገር ስልት፡፡ **ቁንቁኔ**፡ ግንደ ቆርቁር፣ ነቀዝ፣ ብል፣ ትል፣ የዕጽና የእክል የልብስ፡፡ **ቀሡት**፡ ማድጋ፣ እንስራ፡፡

“ረ፣ፐ”

ረቢ፡ (ዕብ፡ ራቢ)፡ የከበሬታ ስም፣ ጌታየ፣ ጌታ፣ አለቃ፣ ሹም፣ መምር፣ ሊቅ፣ ሽማግሌ፡፡ **ርባኤ**፡ አራት መሆን አራትነት፡፡ **ረድኤት**፡ በቁመ፣ ርዳታ፣ መልካም ሥራ፡፡ **ሩፋኤል**፡ (ዕብ፡ ርፋኤል)፡ የመልአክ ስም፣ ፈውስ አምላክ፣ ፈዋሴ አምላክ ዘሥዩም ዲበ ፈውስ ማለት ነው፡፡ **ፔካ**፡ ነጭ ድንጋይ፣ ዕብነ በረድ፡፡

“ሰ”

ስኢል፡ ስኢሎት፡ መለመን፣ መፈለግ፣ መሻት፣ እባክህ ስጠኝ፣ አድርግልኝ ማለት፣ መማለድ፣ መጠየቅ፣ መመርመር፣ ለማወቅ፣ ለማግኘት፡፡ **ሰብእ**፡ ሰው፣ ሥጋ ብቻ ወይም ነፍስ ብቻ ያይደለ ፍጹመ ሥጋ ወነፍስ ፍጹመ ጸጋ ምሉአ ጸጋ፡፡ **ተሰብአ**፡ ሰው ሆነ፣ ሥጋ ለበሰ፣ ነፍስንና ሥጋን ነሳ፣ ተዋሐደ፣ ገንዘብ አደረገ፣ ሰው ተባለ፣ በሰው ስም ተጠራ፡፡ **ሰበድዓት**፡ ስመ ነገድ፣ የሰውና የአራዊት መልክ ያላቸው፡፡ **ሻዳይ**(ዕብ)፣ ስመ አምላክ፣ ኃያል ጽኑዕ፣ ከሃሌ ኩሉ፣ ልዑል፣ ላእለ ኩሉ፣ **ኤልሻዳይ**፡ አምላከ ተስፋ፣ ዘይሴፎ ኩሉ ኪያሁ ወዘያስተሴፉ፡፡ **ሶበርት**፡ ኮሶ፡፡ **ሰውጥ**፡ አለንጋ፣ ለበቅ፡፡ **ሶከር**፣ የሸንኮራ አገዳ ማር ማር ጥንቅሽ ጥንቅሽ የሚል፡፡ **ሱላማጢስ**፡ ፍጽምት፡፡ ከሰላማ በፊት መቶ ብሎ እልፍ እንጂ ሺህ አልነበረም፡፡ ሺሁን አምአት ወይም አሠርቱ ምእት ይሉት ነበር፡፡ ጥንታዊው ፊደል የአበደገ ሲፋለስ አጎዙም ተፋልሷል፡፡ **ሺዋ**፡ ስመ ሀገር፣ ምስጢሩ ብዛት፣ ብዙነት፣ ነውና ሺሖ አሸዋ ከማለት ይስማማል፡፡ ጥንታዊው የወሎ ባላባት ሴት ልጁን ለግሼው ባላባት ለወንድ ልጁ በሕግ አጋብቷት ስትኖር ከብዙ ዘመን በኋላ ልጆቿን ይዛ አባቷን ለማየት ወሎ ሄደች፡፡ አባቷም በልጆቿ ብዛት ተደንቆ፣ ልጄ ሺዋ ልጄ ሺዋ ቀድሞም ስድርሽ ሺ ሁኝ ሺ ያድርግሽ ብየ መርቄሽ ነበረ፡፡ አሁንም እንደ ምርቃቱ ሺ ስለሆንሽ ከእንግዲህ ወዲህ ስምሽ ሺዋ ይሁን፡፡ ሺዋ ብየሻለሁ አላት፡፡ ልጆቿም የአሁኑን ሸዋ አቀኑት፡፡ በእርሷ ስም ሺዋ ተብሏል፡፡ **ምስኪን**፡ (ዕብ፡ ሚስኬን፣ ሱር፡ ሜስኬና፣ ዐረ፡ መስኪን)፡ ደኃ፣ ጦም አዳሪ፣ ቤት ንብረት ገንዘብ ርስት መጠጊያ የሌለው ጥገኛ ለማኝ **ሰላም**፡ (ሱር፡ ሸላም፣ ዕብ፡ ሻሎም)፡ በቁመ፣ ፍጹም ጤና ዕረፍት፣ ዕርቅ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደኅንነት፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሰላምታ፣ የቡራኬ የምርቃት ቃል፡፡ **ሰምዕ**፡ ሰም፣ ጢፍ፡፡ **ሰንዱን**፡ ጥሩ ነጭ ልብስ፣ ሻሽ፣ በፍታ፣ መጎናጸፊያ፡፡ **ሲኖዶስ**(ጽር)፡ ጉባኤ፣ የጳጳሳትና የሊቃውንት ማኅበር፡፡ **ሰፍነግ**፡ ውሃ የሚመጥ፡፡

“ተ፣ጸ”

ታኦዶኮስ፡ (ጽር፡ ቴዎቶኮስ)፡ ወላዲተ አምላክ፣ እመ አምላክ፡፡ **ቴዎፍሎስ**፡ ፍቁረ አምላክ፡፡ **ታቦር**(ዕብ)፡ የተራራ ስም፣ ታላቅ፣ ረዣዥም ተራራ በናዝሬት አጠገብ በስተምሥራቅ ያለ፣ ጌታ ምስጢረ መንግሥቱን ለነቢያት ለሐዋርያት የገለጸበት፡፡ **ቲሃ**፡ ችቦ፣ ዳቦት፡፡ ተከዚ፡ ፈሳሽ፣

ጎርፍ፣ ወራጅ ውሃ። **ተቅዳ**፡ ድንብላል። **ተርጎመ**፡ ቃልን በቃል ለወጠ ገለበጠ፣ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ወይንም በዚያው በአንዱ ቋንቋ አንድም እያለ ፈታ፣ አፍታታ፣ ዘረዘረ፣ ለአንዱ ቅንጣት ቃል ብዙ ፍሬ ብዙ ፍካሬ ሰጠ። **ትርጓሜ**፡ ዘይቤ አወጣጥ፣ የንባብ ፍሬ፣ ምስጢሩ ስልቱ፣ ውስጡ ሐሳቡ። **ጳልቃን**፡ ርኩም።

ኖኅተ ቅኔ

አዘጋጅ መምህር ተክለማርያም አምላኩ

አእመረ በአሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል ይኽውመ አእመረ፣ አእመርከ፣ አእመርኩ፣ አእመርክሙ፣ አእመርነ፣ አእመረት፣ አእመርኪ፣ አእመራ፣ አእመርክን እና አእመርነ ናቸው። እንደገና ውእቱ ብእሲ አእመሮ አእመራሁ ለውእቱ ብእሱ እያለ ይረባል። ንዑስ አንቀጽ አእምሮት የሚለው በ10ሩ መራሕያን ይዘረዘራል። አእምሮቱ፣ አእምሮታ እያለ ማለት ነው። ቦዝ አንቀጽም እያንዳንዱ አእሚሮ አእሚራ እያለ ከዜደ በኋላ እንደገና አእሚሮሁ አእሚሮሃ እያለ ይረባል።

ውስጠ ዘ እና ባዕድ ቅጽል

እሙር፣ ማእምረ፣ መስተአምር ብሎ ያወቀ፣ የታወቀ፣ ያሳወቀ፣ የተዋወቀ፡ ያስተዋወቀ፣ የሚያውቅ፣ የሚያሳውቅ፣ የሚተዋወቅ፣ የሚያስተዋውቅ፣ አዋቂ፣ ታዋቂ፣ አሳዋቂ፣ ተዋዋቂ፣ አስተዋዋቂ፣ ያውቅ ነበር፣ አዋቂ ነው ይላል። እንዲህ እያለ ይዘረዘራል።

ሣልስ ውስጠ ዘ አእማሪ ብሎ አዋቂ፣ የሚያውቅ፣ ያውቅ የነበረ፣ አዋቂ ነው ተብሎ ይተረጎማል። እንደገና አእማሪሁ አእማሪሃ እያለ እስከመጨረሻው ይረባል።

የቦ ዝርዝር

ቦ፣ ሎ፣ ሀሎ ብሎ አለ፣ ኖረ፣ ነበረ፣ ይኖራል፣ ይኖር ነበር፣ ይኑር

ቦ፣ ሎ፣ ሀሎ ብሎ አለህ ኖርህ፣ ነበርህ፣ ትኖራለህ፣ ትኖር ነበር፣ ኑር እያለ በ10ሩ ይዘረዘራል።

ቦ፣ ቦቱ፣ ሎ፣ ሎቱ ብሎ አለው፣ ኖረው፣ ነበረው፣ አለለት፣ ኖረለት፣ ነበረለት፣ አለበት፣ ኖረበት፣ ነበረበት፣ ይኖረዋል፣ ይኖርለታል፣ ይኖርበታል፣ ይኑረው፣ ይኑርለት ይላል፡

ቦ፣ ብከ፣ ሎ፣ ለከ ብሎ አለህ፣ ኖረህ፣ ነበረህ እያለ እንደላይኛው እስከመጨረሻው ይረባል።

አንተ እጉ ቦ ቦቱ፣ ሎ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ ብሎ አንተ ወንድም ለዝያ ሰውየ አለኸው፣ ኖርከው፣ ነበርከው፣ አለህለት፣ ኖርህለት፣ ነበርህለት፣ አለህበት፣ ኖርህበት፣ ነበርክበር፣ ትኖረዋለህ፣ ትኖርለታለህ፣ ትኖርበታለህ፣ ኑረው፣ ኑርለት፣ ኑርበት እያለ በሌላውም እስከመጨረሻው ይሄዳል።

የውእቱ ዝርዝር

ውእቱ ውእቱ ብሎ እርሱ ነው፣ አለ፣ ሆነ፣ ኖረ፣ ነበረ፣ ተባለ፣ ይሆናል፣ ይኖራል፣ ይባላል፣ ይሁን፣ ይኑር፣ ይባል ይላል።እንዲህ እንዲህ እያለ በ10ሩ መራሕያን ይዘረዘራል።

አንተ ውእቱ ብሎ አንተ ነህ፣ አለህ፣ ሆንህ፣ ነበርህ፣ ተባልክ፣ ትሆናለህ፣ ትኖራለህ፣ ትባላለህ፣ ሁን ኑር ተባል ይላል። አንተ አንተም እንዲሁ ነው የሚተረጎም።

ውእቱ ብእሲ ዘመዱ ውእቱ ለውእቱ ብእሲ ብሎ ያ ሰውየ ለዚያ ሰውየ ዘመዱ ነው፣ አለው፣ ሆነው፣ ኖረው፣ ነበረው፣ ተባለው፣ አለለት፣ ሆነለት፣ ኖረለት፣ ነበረለት፣ ተባለለት፣ አለበት፣ ሆነበት፣ ኖረበት፣ ነበረበት፣ ተባለበት፣ ይሆነዋል፣ ይኖረዋል፣ ይባለዋል፣ ይሆንለታል፣ ይኖርለታል፣ ይባልለታል፣ ይሆንበታል፣ ይኖርበታል፣ ይባልበታል፣ ይሁነው፣ ይኑረው፣ ይባለው፣ ይሁንለት፣ ይኑርለት፣ ይባልለት፣ ይሁንበት፣ ይኑርበት፣ ይባልበት። እያለ በአሥሩ መራሕያን እስከመጨረሻው ይሄዳል።

ኢ፣ አኮ እና ሐሰ ሲረባ ይህንን የውእቱ እርባታ በአሉታ መፍታት ነው።

ዓዲ ገና ነው፣ ገና ይሆናል፣ ገና ይሁን

ዓዲ ገና ነህ፣ ገና ትሆናለህ፣ ገና ሁን ብሎ በአሥሩ መራሕያን ይዘልቃል።

እንደገና ዘርዝሮ ዓዲሁ ብሎ ገናው ነው፣ ገናው ይሆናል፣ ገናው ይሁን እያለ እንደ አእመረው እስከ መጨረሻው ይዘልቃል።

የቅኔ መንገድ

የውስጠዘ ድርብ

ሰማዕት ሶምሶን ቀታሌ ቀታሊ ኃይላተ

አኪያ ኢዮአብ አንበሳ መልአከ ሐሰት ሞተ

ኃይላትን የገደለ አንበሳ መልአከ ሐሰት ይህን የገደለ ሶምሶን ሰማዕት ሞተ። የውስጠዘ ድርብ ያሰኘው ቀታሌ ቀታሊ ያለው ነው።

ፍና ተሳልቆ

ለዋሕድ ወልድ እንተ አልቦቱ ዘቦቱ

እምባሕርየ አብ አብ ግዘፈ ሥጋ አልቦቱ።

የአብ የባሕርይ እናት ያለችው አብ የሌለው ልጅ የሥጋ ግዝፍና የለውም። ፍና ተሳልቆ ያሰኘው ያለውን የለውም የሌለውን አለ ስላለ ነው።

የቅጽል አወዳደቅ

ልሂቅ ጴጥሮስ ማእምረ ነሣኢ አዛበ

ገብረአብ ረድእ ንሥሓ ልቡና ጥበበ

ጴጥሮስ ሽማግሌ ጭራን ከያዘ ገብረ አብ ተማሪ የልብ ንሥሓ ጥበብን ያወቀ ነው።የቅጽል አወዳደቅ ያሰኘው ነሣኢ ያለውን ነው።

አገባብ ድርድር መንገድ

ተርፈ ሎጥ ቅድመ ቅድመ ይርዓይ ኩሎ

ኩነታ ለሰዶም እመእመሀሎ ኢሀሎ

አንድ ሎጥ ቢኖር ባይኖር ሁሉ የሰዶምን ሁኔታ ሳያይ ቀረ። አገባብ ድርድር ያሰኘው ቅድመ ቅድመ እመ እመ ናቸው። እመ እመ ኢሀሎ በቅኔ አይሆንም። እመ ሀሎ ወእመ ኢሀሎ ቢል ግን ይሆናል።

እርከን መንገድ

ኪሮስ እግር ዘተጋድሎ ኢያሱ

ዘወንጌል ከነዓን ጽንፈ ኢያሪኮ ያንሶሱ

የከነዓን ወንጌል ሰው የሆነ ኢያሱ ተጋድሎ የዚህ እግር ኪሮስ በኢያሪኮ ዳርቻ ይመላለስ ነበር።እርከን ያሰኘው ዘ በቂ የሆነውን አያያዥ የሆነውን ነው።

ባዕድ ዝርዝር/ ደላይ መንገድ

ረኀብ ኪራም ዘገብሮ ለቴዎድሮስ ሕንባበ

አእመሮ ለዮሴፍ ኬንያ ማርያምሃ ጥበበ

በቴዎድሮስ ጊዜ ፍሬን ያደረገ ረኀብ ኪራም ከዮሴፍ ጥበበኛ ማርያም ጥበብን አወቀ። ባዕድ ዘር ያሰኘው ዘገብሮ እና አእመሮ ናቸው። ዝርዝርና ደላይ አንድ ነው። ቀሪውን መንገድ ከአገባቡ ጋር ተመልከት።